# የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
# የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ።

## ማ ው ጫ ።

## አንደኛ ፡ መጽሐፍ ።

ገጽ

## ስለ ፡ ሰዎች ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ሰዎች ።


ምዕራፍ ፡ ፩ ። ስለ ፡ ሰውና ፡ ስለ ፡ መብቶቹ ። .... .... .... .... ፩
ክፍል ፡ ፩ ። ስለ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ አሰጣጥ ። ..... .... .... .... ፩
ክፍል ፡ ፪ ። ስለ ፡ ሰው ፡ መብቶች ። .... .... .... .... .... ፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ። ስለ ፡ ስም ። .... .... .... .... .... .... ፰
ምዕራፍ ፡ ፫ ። ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ማስረጃነት ። ..... .... .... ፲፩
ክፍል ፡ ፩ ። ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹማምቶች ። .... .... .... ፲፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹማምት ፡ ሥልጣን ፡ አሰጣጥ ። .... .... .... .... .... .... .... ፲፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ተግባር ። ፲፬
ክፍል ፡ ፪ ። ስለ ፡ ሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቦች ። .... .... .... ፲፯
ክፍል ፡ ፫ ። ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ። .... .... .... ፳፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ። በጠቅላላው ። ... .... .... .... .... ፳፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ። የመወለድ ፡ ጽሑፎች ። .... .... .... ፳፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ። የመሞት ፡ ጽሑፎች ። .... .... .... ፳፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ። የጋብቻ ፡ ጽሑፎች ። .... .... .... ፳፯
ክፍል ፡ ፬ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎችን ፡ ስለማቃናት ። .... .... ፳፯
ክፍል ፡ ፭ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ ግልባጮችና ፡ ቅጂዎች ። .... .... .... .... .... .... .... .... ፳፰
ክፍል ፡ ፮ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍን ፡ ደንብ ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ። ..... .... .... .... .... .... ፴
ክፍል ፡ ፯ ። ስለ ፡ ታወቁ ፡ ሰነዶች ። .... .... .... .... .... ፴፪
ምዕራፍ ፡ ፬ ። ስለ ፡ መጥፋት ፡ .... .... .... .... .... .... ፴፬
ክፍል ፡ ፩ ። የመጥፋት ፡ መግለጫ ። .... .... .... .... .... ፴፬
ክፍል ፡ ፪ ። የመጥፋቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። .... .... .... .... .... .... .... .... ፴፯

ገጽ ፡

ክፍል ፡ ፫ ፤ ጠፉ ፡ መባሉ ፡ የሚቀርበት ፡ ጊዜ ። ..... .... .... ፹፯
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታና ፡ ስለመደበኛ ፡ ቦታ ። ፹፰
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ። .... .... .... .... .... .... ፹፰
ክፍል ፡ ፪ ፤ መደበኛ ፡ ቦታ ። ........................ ፺

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦች ። ፺፩
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ሰዎች ። .... .... .... .... ፺፪
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ..... .... .... .... .... ፺፪
ክፍል ፡ ፪ ፤ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ ስለሚ
ጠብቁ ፡ ክፍሎች ። ..... .... .... .... .... .... .... ፺፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ አሳዳሪና ፡ ስለ ፡ ሞግዚት ። ፺፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ አባሎ
ችና ፡ ስለ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሞግዚት ። .... .... .... ፺፫
ክፍል ፡ ፫ ፤ የአሳዳሪውና ፡ የሞግዚቱ ፡ ሥልጣን ። .... .... .... ፺፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሰውነት ፡
አጠባበቅ ። .. .... .... .... .... .... .... .... ፺፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰን ፡ ልጅ ፡ ሀብቶች ፡
ስለ ፡ ማስተዳደር ። .... .... .... .... .... .... ፻፩
ክፍል ፡ ፬ ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ለመጠበቅ ፡ የተመለ
ከቱትን ፡ ደንቦች ፡ መጣስ ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ። ፻፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሥራዎች ። ፻፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የሞግዚቱ ፡ ሥራዎች ። .... .... .... ፻፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ ኀላፊነቶች ። ፻፱
ክፍል ፡ ፫ ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ስለ ፡
መቅረቱ ። .... .... .... .... .... .... ፻፲
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ መው
ጣት ። .... .... .... .... .... .... .... ፻፲
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የሞግዚትነት ፡ ሥራ ፡ ሒሳቦች ። ፻፲፪

ገጽ

ምዕራፍ ፫ ፤ አእምሮዋቸው ፡ ስለ ፡ ጉደለ ፡ ሰዎችና ፡ ስለ ፡ ድውዮች ። ፳፫
ክፍል ፡ ፩ ፤ ችሎታ ፡ ስላልተከለከሉት ፡ የአእምሮ ፡ ጉደ
ሎዎችና ፡ ድውዮች ። .. .... .... .... .... ፳፫
ክፍል ፡ ፪ ፡ በፍርድ ፡ ስለሚደረግ ፡ ክልከላ ፡ .... .... .... ፳፮
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ በሕግ ፡ ስለ ፤ ተከለከሉ ፡ ሰዎች ። .... .... .... ፴፩
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ። .................... ፴፫

አንቀጽ ፡ ፫ ።

በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡
ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ንብረቶች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅቶችና ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ። .... .... .... .... .... .... .... ፴፬
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ማኅበሮች ። .... .... .... .... .... ፴፯
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፎችና ፡
ስለ ፡ ውስጥ ፡ ደንቦች ። .... .... .... .... .... ፴፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ማኅበረተኞች ። .... .... .... .... ፴፰
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ሥራው ፡ አመራር ። ..................... ፵
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ። ... .... .... .... ... ፵፪
ክፍል ፡ ፭ ፤ የማኅበሩ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።.... .... ... ፵፬
ክፍል ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መፍረስና ፡ ሒሳብ ፡ መጣራት ። .... .... ፵፭
ክፍል ፡ ፯ ፤ ማኅበሮችን ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ። .... .... .... ፵፰
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ንብረቶች ። .... ፶፪
ክፍል ፡ ፩ ፤ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ።.... .... .... .... ፶፪
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ኮሚቴዎች ። ... .... .... .... .... ፶፫
ክፍል ፡ ፫ ፤ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚወጡ ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ። ፶፱
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡
ዜጋ ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ የውጭ ፡
አገር ፡ ዜጋ ፡ ንብረቶች ። .... .... .... .... .... ፷፭

ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።

ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድና ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ ( አወራረስ ) ።

አንቀጽ ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ በጠቅላላው ። .... .... ፷፯

ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ መተጫጨት ። .... .... .... .... .... ፩፻፷
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ አፈጻጸም ። .... .... .... .... ፪፻፷፫
ክፍል ፡ ፩ ፡ ለማንኛዎቹም ፡ ዐይነቶች ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚሆኑ ፡ አጠቃ ላይ ፡ ሁኔታዎች ። .... .... .... .... .... ፪፻፷፫
ክፍል ፡ ፪ ፤ ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ። .... .... .... .... ፪፻፷፬
ክፍል ፡ ፫ ፤ ሌሎች ፡ ዐይነቶች ፡ ጋብቻዎች ። .... .... ... ፪፻፷፰
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የጋብቻ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ ምክንያት ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ። .... .... .... .... ፪፻፷፰
ክፍል ፡ ፩ ፤ ለጋብቻ ፡ ሥርዐቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚሆን ፡ የወል ፡ ሁኔታ ። ፪፻፷፰
ክፍል ፡ ፪ ፤ ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ። .... .... .... .... ... ፪፻፸፪
ክፍል ፡ ፫ ፤ ሌሎች ፡ ጋብቻዎች ። . .... .... .... .... ፪፻፸፪
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ የጋብቻ ፡ ውጤት ። ... .... .... .... .... ፪፻፸፫
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ። .... .... .... .... ... ፪፻፸፫
ክፍል ፡ ፪ ፤ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ጋብቻው ፡ ያለው ፡ ውጤት ።.... .... ፪፻፸፭
ክፍል ፡ ፫ ፤ ጋብቻው ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ውጤት ። .... ... ፪፻፸፮
ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ .. .... .... .... .... ፪፻፹
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጋብቻ ፡ የሚፈርስበት ፡ ምክንያት ። .... .... .. ፪፻፹
ክፍል ፡ ፪ ፤ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ ስለማጣራት ። .... .... .... .... .... ፪፻፹፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ የአንዱ ፡ መሞት ። ፪፻፹፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የመፋታት ፡ ሁኔታ ። ... .... .... ፪፻፹፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ሌላ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ። .... .... ፪፻፹፰
ምዕራፍ ፡ ፯ ፤ የጋብቻ ፡ ማስረጃ ። .... .... .... .... .... ፪፻፹፰
ምዕራፍ ፡ ፰ ፤ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ መኖር ። ፪፻፺፩
ምዕራፍ ፡ ፱ ፤ በጋብቻና ፡ በፍቺ ፤ ከጋብቻው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚነሡ ፡ ክርክሮች ። ፪፻፺፫
ምዕራፍ ፡ ፲ ፤ ስለመወለድ ። .... .... .... .... .... .... ፪፻፺፮
ክፍል ፡ ፩ ፤ አባትና ፡ እናትን ፡ ስለ፡ማወቅ ። . .... .... .... ፪፻፺፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .. .... .... ፪፻፺፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ አባት ፡ ነው ፡ ስለሚያሰኝ ፡ ግምት ። ፪፻፺፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ አባትነትን ፡ ስለ ፡ ማወቅ ። .... .... ፪፻፺፰

| | ገጽ |
|---|---|


ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ በፍርድ ፡ ስለሚደረግ ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ። .. .... ..... .... .... .... .... ፮፳

ክፍል ፡ ፪ ፤ በአባትነት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚነሣ ፡ ክርክር ።.... .... ፮፳፩

ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ልጅነት ፡ ማስረጃ ። .... .... .... .... ፮፳፪

ክፍል ፡ ፬ ፤ በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ስለሚነሣው ፡ ክርክርና ፡ ስለመካድ ። ፮፳፬

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ክርክር ። ፮፳፬

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ መካድ ።.... .... .... .... ፮፳፭

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፤ ስለ ፡ ጉዲፈቻ ፡ ( የማር ፡ ) ልጅ ። .... .... .... ፮፳፯

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፤ ስለ ፡ ቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ።.. .... .... .... ፮፴

አንቀጽ ፡ ፫ ።

ስለ ፡ ውርስ ፡ ( ስለ ፡ አወራረስ ) ። ፮፴፬

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውርስ ፡ አስተላለፍ ። .... .... .... ፮፴፬

ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... ፮፴፬

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውርስ ፡ አከፋፈትና ፡ በውስጡ ፡ ስለ ሚገኝበት ። .... .... .... .... .... .... ፮፴፬

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ወራሽ ፡ ለመሆን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ችሎታ ። ፮፴፭

ክፍል ፡ ፪ ፡ ሳይናዘዝ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ .... .... ፮፴፮

ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ኑዛዜ ። .... .... .... .... .... ፮፵

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ የኑዛዜ ፡ ዋጋ ፡ መኖር ፡ ሁኔታዎች ፡ ፮፵

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ በኑዛዜዎቹ ፡ የሰፈረ ፡ ቃልና ፡ የኑዛዜ ፡ ትር ጓሜ ።.... .... .... .... .... .... .... ፮፶

ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ወራሽነትን ፡ ስለ ፡ ማጣራት ።.... .... .... .... ፮፶፫

ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውርሱ ፡ አጣሪ ። .... .... .... .... ፮፶፱

ክፍል ፡ ፪ ፤ መብት ፡ አለኝ ፡ ባዮችን ፡ ቁርጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ስለ ፡ መወሰን ። .... .... .... .... .... .... ፯፻፫

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ የወራሾቹን ፡ ሁኔታ ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡ ፯፻፫

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ወራሾችና ፡ ጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተ ሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ምርጫ ። ፯፻፭

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ለወራሹ ፡ ስለሚሰጡ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶ ችና ፡ የወራሽነት ፡ ጥያቄ ። .... .... .... ፯፻፲

ገጽ ፤

ክፍል ፤ ፫ ፤ ስለ ፤ ውርስ ፤ አስተዳደር ። .. .... .... .... ፱፻፲፩
ክፍል ፤ ፬ ፤ የውርሱን ፤ ዕዳ ፤ ስለ ፤ መክፈል ። .... .... .... ፱፻፲፬
ክፍል ፤ ፭ ፤ ከውርሱ ፤ ላይ ፤ ስለሚጠየቀው ፤ የቀለብ ፤ ገንዘብ ። ፱፻፲፭
ክፍል ፤ ፮ ፤ የኑዛዜ ፤ ስጦታዎችን ፤ ስለ ፤ መክፈል ። .... .... ፱፻፲፱
ክፍል ፤ ፯ ፤ ስለ ፤ ውርሱ ፤ መዘጋት ። .... .... .... .... ፱፻፳፪
ምዕራፍ ፤ ፫ ፤ ስለ ፤ ውርስ ፤ ክፍያ ። .... .... .... .... ፱፻፳፬
ክፍል ፤ ፩ ፤ ስለ ፤ ውርሱ ፤ አለመነጣጠልና ፤ ለውርስ ፤ ክፍያ ፤ ስለሚ
ቀርብ ፤ ጥያቄ ። .... .... .... .... .... ፱፻፳፬
ክፍል ፤ ፪ ፤ የጋራ ፤ ወራሾች ፤ ስለሚመልሱት ፤ ንብረቶች ። ፱፻፳፭
ክፍል ፤ ፫ ፤ የመከፋፈሉ ፤ አሠራር ። .... .... .... .... ፱፻፳፯
ክፍል ፤ ፬ ፤ መከፋፈሉ ፤ ከተፈጸመ ፤ በኋላ ፤ በወራሾቹ ፤ መካከል ፤ ስላ
ለው ፤ ግንኙነት ። .... .... .... .... .... ፱፻፴፪
ንኡስ ፤ ክፍል ፤ ፩ ፤ የጋራ ፤ ተካፋዮች ፤ ሊሰጡ ፤ ስለሚገባቸው ፤
ዋስትና ። .... .... .... .... .... .... ፱፻፴፪
ንኡስ ፤ ክፍል ፤ ፪ ፤ ክፍያውን ፤ ስለ ፤ ማፍረስ። .... .... ፱፻፴፫
ክፍል ፤ ፭ ፤ የውርሱ ፤ ሀብት ፤ ከተከፋፈለ ፤ በኋላ ፤ ገንዘብ ፤ ጠያቂ
ዎች ፤ ያላቸው ፤ መብት ። .... .... .... .... ፱፻፴፬
ምዕራፍ ፤ ፬ ፤ ውርስን ፤ ስለሚመለከቱ ፤ ስምምነቶች ። .... .... ፱፻፴፭
ክፍል ፤ ፩ ፤ ወደፊት ፤ በሚገኝ ፤ ውርስ ፤ ላይ ፤ ስለሚደረግ ፤ የውል ፤
ስምምነት ። .... .... .... .... .... .... ፱፻፴፭
ክፍል ፤ ፪ ፤ የተከፋፈሉ ፤ ስጦታዎች ። .... .... .... .... ፱፻፴፮
ክፍል ፤ ፫ ፤ የውርስ ፤ መብቶችን ፤ ስለ ፤ ማስተላለፍ ። .... .... ፱፻፴፯

## ሦስተኛ ፤ መጽሐፍ ።

### ስለ ፤ ንብረት ።

### አንቀጽ ፤ ፮ ።

### ስለ ፤ ንብረት ፤ በጠቅላላውና ፤ ስለ ፤ ይዞታ ።

ምዕራፍ ፤ ፩ ፤ ስለ ፤ ንብረት ፤ በጠቅላላው ። ... .... .... .... ፱፻፴፰
ምዕራፍ ፤ ፪ ፤ ስለ ፤ ይዞታ ። ... .... .... .... .... .... ፱፻፵

### አንቀጽ ፤ ፯ ።

### ስለ ፤ ግል ፤ ሀብት ።

ምዕራፍ ፤ ፩ ፤ ሀብት ፤ ስለሚገኝበት ፤ ሁኔታ ፤ ሀብትን ፤ ስለ ፤ ማስተላለፍ ፤
ሀብት ፤ ስለሚቀርበትና ፤ ስለ ፤ ባለሀብትነት ፤ ማስረጃ ። ፱፻፵፫

ገጽ ፡

ክፍል ፡ ፩ ፤ ሀብት ፡ ስለሚገኝበቅ ፡ ሁኔታ ። .... .... .... ፪፻፵፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለመያዝ ። .... .... .... .... ፪፻፵፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የቅን ፡ ልቡና ፡ ባለይዞታነት ። .... .... ፪፻፵፭
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ይዞታ ። ... .... .... ... ፪፻፵፮
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ የዋና ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር። .. .... ... ፪፻፵፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ባለሀብትነትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ። ... .... ... ፪፻፶፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ሀብትነት ፡ መቅረት ። .. .... .... ... ፪፻፶፪
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ሀብትነት ፡ ማስረጃ ። .. .... .... ... ፪፻፶፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ የባለሀብቱ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። ... .... .... ፪፻፶፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... ፪፻፶፭
ክፍል ፡ ፪ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሚመለከቱ ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ። ፪፻፶፮
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ውሃዎች ፡ ባለሀብትነትና ፡ በውሃዎች ፡ ስለ ፡ መገልገል ። ፪፻፷

## <u>አንቀጽ ፡ ፫ ።</u>

## <u>የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ በአላባ ፡ ስለ</u>

## <u>መጠቀምና ፡ ስለሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ።</u>

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ጋራ ፡ ባለ ፡ ሀብትነት ። .... .... .... ፪፻፷፯
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ። .... .... .... .... ፪፻፷፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። .. .... .... .... .... ፪፻፸፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ የአግካይ ፡ ወሰን ፡ አጥሮች ። .... .... ፪፻፸፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ያንድ ፡ ቤት ፡ ፎቅ ፡ ወይም ፡ ለመኖሪያ ፡ የተመደቡ ፡ ክፍሎች ፡ ባለሀብትነት። . .... .... .... ፪፻፸፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ በአላባ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ መብት ። .... .... ፪፻፸፯
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ። .... .... .... .... ፪፻፸፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ግዙፍ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሀብቶች ፡ የሚጸና ፡ (የሚፈጸም ፡) ልዩ ፡ ደንብ ። .. .... .... .... .... .... ፪፻፹፪
ክፍል ፡ ፫ ፤ የገንዘብና ፡ ሌሎች ፡ ግዙፎች ፡ ያልሆኑ ፡ ነገሮች ፡ በአላባ ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ። .... .... .... ፪፻፹፭
ክፍል ፡ ፬ ፤ በቤት ፡ ውስጥ ፡ የመኖር ፡ መብት ። .... .... ፪፻፹፯
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ። .... .... .... ፪፻፹፯
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ በቀዳሚነት ፡ ግዢ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ። ፪፻፺፬

ገጽ

ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ባለሀብቱ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ንብረቶች ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ እንዳያደርግ ፡ መብቱን ፡ ስለ ፡ ማጥበብ ። .... .... ፪፻፺፱
ክፍል ፡ ፩ ፤ የግዢን ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ የመግዛትን ፡ መብት ፡ ስለሚመለከት ፡ የውል ፡ ስምምነት ። .... .... .... ፪፻፺፱
ክፍል ፡ ፪ ፤ ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይያዝ ፡ የማድረግ ፡ ስምምነት ። ፫፻፰

## አንቀጽ ፡ ፱ ፤

## በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ (የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ፡ እና ፡) ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ። .. .... .... .... ፫፻፰
ክፍል ፡ ፩ ፤ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ። ... .... .... ፫፻፰
ክፍል ፡ ፪ ፤ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀሙትን ፡ ሀብቶች ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ። .. .... .... .... .... .... ፫፻፲፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ የኅብረት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ። .... .... ፫፻፲፰
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ። ፫፻፳፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ማኅበሮቹ ፡ መቋቋም ። .... .... .... ፫፻፳፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ የሥራ አካሄድ ። .... .... .... ፫፻፳፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ የግል ፡ ርስት ፡ የሚጠበቅበት ፡ ሁኔታ ። ፫፻፳፭
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ መሬቶቹ ፡ የኅብረት ፡ ሀብት ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ . .... .... .... .... .... .... ፫፻፳፯
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የከተማ ፤ ክልል ፡ የሆኑ ፡ ሰፍራዎች ፡.... .... .... ፫፻፳፰

## አንቀጽ ፡ ፲ ።

## ስለ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ መዝገቦቹ ፡ አያያዝና ፡ ግልጽ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ። ፫፻፵፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚጻፉ ፡ ነገሮች ። ፫፻፵፭
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ በመዝገቦቹ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጽሑፎች ፡ አመዘጋገብ ። .... .... ፫፻፶
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ አመዘጋገቡ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ። .... .... .... ፫፻፷
ክፍል ፡ ፪ ፤ ለአመዘጋገብ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ፎርሙሎች ። .... ... ፫፻፷፪
ክፍል ፡ ፫ ፤ የተመዘገቡትን ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ ማቃናትና ፡ ስለ ፡ መሠረዝ ። ፫፻፷፰
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ማስመዝገብ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። .... .... .... .... .... ፫፻፺፪

## አንቀጽ ፡ ፲፩ ።

ስለ ፡ ድርሰትና ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ባለሀብትነት ። ፫፻፺፱

ገጽ ፤

## ፬ኛ ፤ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ግዴታዎች ።

## አንቀጽ ፡ ፲፪ ፤

## ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውል ፡ አመሠራረት ። .... .... .... .... ፫፻፷፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ ፈቃዶ ፡ ስለ ፡ መዋዋል ። .... .... .... .... ፫፻፷፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ውለታን ፡ የመቀበል ፡ አቋሞች ። ፫፻፷፩
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የተዋዋዮቹ ፡ ፈቃድ ፡ ጕድለት ። ፫፻፷፬
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ውለታው ፡ ጕዳይ ። .... .... .... ፫፻፷፯
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ውል ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ። .... .... .... ፫፻፷፰
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ የውሎች ፡ ውጤት ። .... .... .... .... .... ፫፻፸
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውል ፡ ትርጕም ። .... .... .... .... ፫፻፸፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ አፈጻጸም ። .... .... .... .... ፫፻፸፪
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ውል ፡ መሻሻል። ... .... .... .... ... ፫፻፸፯
ክፍል ፡ ፬ ፤ ውልን ፡ ስላለመፈጸም ። .... .... .... .... ፫፻፸፰
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የግዴታዎች ፡ መቅረት ። .... .... .... .... ፫፻፹፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ውሎችን ፡ ስለመሠረዝና ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ። ... .... ፫፻፹፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ውልን ፡ ስለ ፡ ማስቀረትና ፡ ዕዳን ፡ ስለ ፡ መተው ። ፫፻፹፰
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ፡መተካት ፤ (ኖባሲዩን)። .... .... .... ፫፻፹፱
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ማቻቻል ። .... .... .... .... .... ፫፻፹፱
ክፍል ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ መብት ፡ መቀላቀል ። ... .... .... .. ፫፻፺፩
ክፍል ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ ይርጋ ። .... .... .... .... .... ፫፻፺፩
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የአንዳንድ ፡ ግዴታዎች ፡ ወይም ፡ የአንዳንድ ፡ ውሎች ፡ አኳኋን ። .. .... .... .... .... .... ... ፫፻፺፫
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጊዜ ። .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፫
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሁኔታ ።... .... .... .... .... .... ፫፻፺፬
ክፍል ፡ ፫ ፤ ማማረጫ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ።... .... .... ... ፫፻፺፭
ክፍል ፡ ፬ ፤ ቃብድ ። .... .... .... .... .... ፫፻፺፯
ክፍል ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ የተጻፈ ፡ የውል ፡ ቃል ። .... .... ፫፻፺፯
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ ባለዕዳዎች ፡ ወይም፡ ባለገንዘቦች ። ፫፻፺፱
ክፍል ፡ ፩ ፤ በባለዕዳዎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ የማይከፋፈል ፡ አንድነት ። .... .... .... .... .... .... .... ፫፻፺፱

ገጽ ፡

ክፍል ፡ ፪ ፤ በባለገንዘቦቹ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ አንድነት ። ፩፻፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለማይከፋፈሉ ፡ ግዴታዎች ። .... .... .... ፩፻፪
ክፍል ፡ ፬ ፤ ዋስትና ። ... .... .... .... .... .... ፩፻፫
ምዕራፍ ፡ ፯ ፤ ከውሉ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ስላላቸው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ። ፩፻፱
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የሚሰጥ ፡ ተስፋና ፡ የሚደረግ ፡ ውል ። ፩፻፱
ክፍል ፡ ፪ ፤ የገንዘብ ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ ስለመዳረግ ፡ ( ዳረጎት ። ) . .... .... .... .... .... ፩፻፲፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ የምትክ ፡ ውክልናና ፡ የዕዳ ፡ ማስተላለፍ ። .... ... ፩፻፲፬
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ወራሾች ፡ (የወገኖቹ ፡ ወራሾች ።) ፩፻፲፮
ክፍል ፡ ፭ ፤ ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ። ፩፻፲፯
ምዕራፍ ፡ ፰ ፤ የውልን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከት ፡ ማስረጃ ። . .... .. ፩፻፲፱
ክፍል ፡ ፩ ፤ የማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታና ፡ አቀባበሉ ። .... .. ፩፻፲፱
ክፍል ፡ ፪ ፤ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ። . .... .... .... .... ፩፻፳
ክፍል ፡ ፫ ፤ ገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ የሚያስቈጥሩ ፡ የሕሊና ፡ ግምቶች ። ፩፻፳፫

አንቀጽ ፡ ፲፫ ።

ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ። . .... .... ፩፻፳፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ በጥፋት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተመሠረተ ፡ አላፊነት ። ፩፻፳፭
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ። ... .... ... ፩፻፳፭
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። .... .... .... ፩፻፳፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ አጥፊ ፡ ሳይሆን ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ። .... .... ፩፻፴፫
ክፍል ፡ ፫ ፤ የካሣ ፡ አከፋፈልና ፡ ልክ ። . .... .... ... ፩፻፴፱
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ። .... ... ፩፻፴፱
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ስለ ፡ መካስ ። ፩፻፵፩
ክፍል ፡ ፬ ፤ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተግባር ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ። ... ... ፩፻፯
ክፍል ፡ ፭ ፤ ካሣ ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ክስ ። .... .... .... ፩፻፵፯
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ። .... .... .... .... ፩፻፶፫
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... ፩፻፶፫
ክፍል ፡ ፪ ፤ የማይገባውን ፡ ዕዳ ፡ መክፈል ። .... .... .... ፩፻፶፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ። .... .... .... .... ፩፻፶፭

ገጽ ፣

## አንቀጽ ፣ ፲፬ ።

## ስለ ፣ እንደራሴነት ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ፤ ጠቅላላ ፣ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... ፩፻፶፯
ምዕራፍ ፣ ፪ ፤ ስለ ፣ ወኪልነት ። .... .... .... .... .... ፩፻፷፪
ክፍል ፣ ፩ ፤ የወኪልነት ፣ ሥልጣን ፣ አጻጻምና ፣ የሥራው ፣ ግብ ። ፩፻፷፪
ክፍል ፣ ፪ ፤ የተወካዩ ፣ ግዴታዎች ። .... .... .... .... ፩፻፷፬
ክፍል ፣ ፫ ፤ ስለ ፣ ወካዩ ፣ ግዴታዎች ።.... .... .... .... ፩፻፷፯
ክፍል ፣ ፬ ፤ ስለ ፣ ውክልና ፣ መቅረት ።.... .... .... .... ፩፻፷፰
ክፍል ፣ ፭ ፤ለሦስተኛ ፣ ወገኖች ፣ የውክልናው ፣ ሥልጣን ፣ የሚያስከትለው ፣ ውጤት ። .... .... .... .... .... ፩፻፸
ምዕራፍ ፣ ፫ ፤ ስለ ፣ ኮሚሲዮን ። .... .... .... .... .... ፩፻፸
ክፍል ፣ ፩ ፤ ስለ ፣ ግዢ ፣ ወይም ፣ ስለ ፣ ሽያጭ ፣ ኮሚሲዮን ። ፩፻፸
ክፍል ፣ ፪ ፤ ስለ ፣ ማመላለሻ ፣ ኮሚሲዮን ። .... .... .... ፩፻፸፬
ምዕራፍ ፣ ፬ ፤ ዳኞች ፣ ስለሚሰጡት ፣ ውክልና ። .... .... .... ፩፻፸፭
ምዕራፍ ፣ ፭ ፤ ስለ ፣ ሥራ ፣ አመራር ። .... .... .... .... ፩፻፸፯

## ፭ኛ ፣ መጽሐፍ ።

## ስለ ፣ ልዩ ፣ ውሎች ።

## አንቀጽ ፣ ፲፭ ፣

## መብቶች ፣ ማስተላለፍን ፣ ስለሚመለከቱ ፣ ውሎች ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ፤ ስለ ፣ ሽያጭ ። .... .... .... .... .... ፩፻፸፰
ክፍል ፣ ፩ ፤ የውሉ ፣ አደራረግ ። .... .... .... .... ፩፻፸፱
ክፍል ፣ ፪ ፤ ስለ ፣ ውሉ ፣ መፈጸም ። .... .... .... .... ፩፻፸፱
ንኡስ ፣ ፩ ፤ ክፍል ፣ ጠቅላላ ፣ ድንጋጌዎች ።.. .... .... ፩፻፸፱
ንኡስ ፣ ክፍል ፣ ፪ ፤ የሻጉው ፣ ግዴታዎች ። .... ... ፩፻፹፯
ንኡስ ፣ ክፍል ፣ ፫ ፤ በሻጩና ፣ በገዢው ፣ ላይ ፣ ያሉ ፣ አጠቃላይ ፣ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... .... ፩፻፹፰
ክፍል ፣ ፫ ፤ ውልን ፣ ስላለመፈጸም ። .... .... .... ፩፻፺፩
ንኡስ ፣ ክፍል ፣ ፩ ፤ ውልን ፣ በግድ ፣ ስለ ፣ ማስፈጸም ። ፩፻፺፩
ንኡስ ፣ ክፍል ፣ ፪ ፤ የውል ፣ መፍረስ ። .... .... .... ፩፻፺፫
ንኡስ ፣ ክፍል ፣ ፫ ፤ የጉዳት ፣ ኪሣራ ። .... .... .... ፩፻፺፱
ክፍል ፣ ፬ ፤ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የሽያጭ ፣ አሠራር ። .... .... .... ፪፻፩

ገጽ

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ ዋጋው ፡ በየጊዜው ፡ ስለ ፡ ሚከፈልለት ፡ ሽያጭ ። .... .... .... .... .... ፭፻፭
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፭ ፤ ባለሀብትነቱን ፡ ለራሱ ፡ በማስጠበቅ ፡ የሚ ደረግ ፡ ሽያጭ ። .... .... .... .... .... ፭፻፮
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፮ ፤ የተሸጠውን ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ የሚ ደረግ ፡ ውል ። .... .... .... .... .... ፭፻፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፯ ፤ ዕቃውን ፡ ከመላክ ፡ ግዴታ ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ። .... .... .... .... .... ፭፻፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፰ ፤ በሐራጅ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሽያጭ ። .... ፭፻፲
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ የመሸጥ ፡ ውል ፡ መሰልነት ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ። ፭፻፲፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ የለውጥ ፡ ውል ። .... .... .... .... ፭፻፲፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ የባለሀብትነትን ፡ መብት ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎችን ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ። .... .... .... .... .... ፭፻፲፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ኪራይ ፡ ሽያጭ ። .... .... .... .... ፭፻፲፪
ክፍል ፡ ፬ ፤ የዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ ውል ። .... .... .... .... ፭፻፲፪
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ስጦታ ። .... .... .... .... .... ፭፻፲፭
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የሚያልቅ ፡ ነገር ፡ ብድር ። .... .... .... ፭፻፳፬
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ መጠሪያን ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ። .... .... .... .... ፭፻፳፯
ክፍል ፡ ፩ ፤ ለዘለዓለም ፡ ስለሚኖር ፡ መጠሪያ ። .... ፭፻፳፰
ክፍል ፡ ፪ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ስለሚቈይ ፡ መጠሪያ ። ፭፻፳፱

## <u>አንቀጽ ፡ ፲፮ ።</u>

## <u>የሥራዎች ፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሎች ።</u>

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ። .... .... .... ፭፻፴፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ። .... .... .... .... ፭፻፴፪
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሠራተኛው ፡ ሥራ ። .... .... .... .... ፭፻፴፫
ክፍል ፡ ፫ ፤ ለሠራተኛው ፡ ስለሚገባው ፡ ደሞዝ ። .... .... ፭፻፴፬
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ አሠሪው ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ግዴታ ። ፭፻፴፰
ክፍል ፡ ፭ ፤ ለሠራተኞች ፡ የሚገባ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ። .... .... ፭፻፵፩
ክፍል ፡ ፮ ፤ ውልን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ። .... .... .... .... ፭፻፵፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራዎች ፡ ውሎች ። ፭፻፵፰
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ዋያ ፡ ሥራ ፡ መልመጃ ፡ ውል ። .... .... ፭፻፵፰
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሥራ ፡ ማከራየት ፡ ውል ። .... .... .... ፭፻፵፱

ገጽ

ክፍል ፡ ፫ ፤ በቤተ ፡ ሰብ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ስለሚኖር ፡ አሽከር ፡ የሥራ ፡ ውል ። .... .... .... .... .... .... ፮፻፵፱
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ እርሻ ፡ ሥራ ፡ ውል ። ... .... .... ... ፮፻፶
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ እርሻ ፡ ውል ። .... .... .... ፮፻፶
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ። .... .... .... .... ...., ፮፻፶፩
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ዕውቀት ፡ ሥራ ፡ ማከራየት ፡ ውል ። ... .... .. ፮፻፶፪
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ ሕክምና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሆስፒታል ፡ ውል ። ... ... ፮፻፶፫
ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ ሆቴል ፡ ሥራ ፡ ውል ። .... .... .... .... ፮፻፷
ምዕራፍ ፡ ፯ ፤ አትሞ ፡ የማውጣት ፡ (ፒብሊሽንግ ፡) ውል ። .... .... ፮፻፷፩

<u>አንቀጽ ፡ ፲፯ ።</u>

<u>የዕቃ ፡ ጥበቃን ፡ በዕቃ ፡ መገልገልን ፡ ወይም ፡</u>

<u>በዕቃ ፡ መጠቀምን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሎች ።</u>

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .. .... .... .... .... ፮፻፷፱
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ዕቃ ፡ ማከራየት ። .... .... .... .... ፮፻፸፪
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .... .... .... .... ፮፻፸፪
ክፍል ፡ ፪ ፤ እንስሳን ፡ ስለ ፡ መከራየት ። .... .... .... ፮፻፸፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ በአንድ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ሥራ ፡ ኪራይ ፡ ውስጥ ፡ ከብትን ፡ ጭምር ፡ ስለ ፡ ማከራየት። .. .... .... ፮፻፸፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የከብቶቹ ፡ ኪራይ ፡ ዋና ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ። ፮፻፹
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ መገልገያ ፡ ብድር ፡ ወይም ፡ ትውስት ። ... .. ፮፻፹፫
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ አደራ ። .. .... .... .... .... .... .... ፮፻፹፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ አደራ ፡ በጠቅላላው ። .... .... .... ፮፻፹፭
ክፍል ፡ ፪ ፤ በትእዛዝ ፡ የተቀመጠ ፡ አደራ ። .... .... .... ፮፻፹፱
ክፍል ፡ ፫ ፤ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ አደራ ። .... .... .... . ፮፻፹፱
ክፍል ፡ ፬ ፤ ባለቤቱ ፡ ሳያውቅ ፡ የተገኙ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የተቀመጡ ፡ ዕቃዎች ። .... .... .... ፮፻፺
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ የዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ቦታ ። .... .... .... ፮፻፺
ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ መያዣ ፡ ውል ። .... .... .... .... ፮፻፺፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ መያዝ ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ። .... .... ፮፻፺፭
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ የሚጸናባቸው ፡ ሁኔታዎች ። ፮፻፺፮
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የመያዣ ፡ ሰጪው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ። ፮፻፺፯

ገጽ

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ዕቃውን ፡ የያዘው ፡ ባለገንዘብ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። .... .... .... .... .... ፲፭፻፺፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ የመያዣ ፡ ውል ፡ የሚቀርበት ። .. .... ፲፮፻
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፭ ፤ የመያዣ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ። .... ... ፲፮፻
ክፍል ፡ ፪ ፤ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ፡ ሰነዶችን ፡ ወይም ፡ ግዙፍ፡ ያልሆኑ፡ ሌሎች ፡ ሀብቶችን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ። .... .... ፲፮፻፪

<u>አንቀጽ ፡ ፲፰ ።</u>

<u>የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ስለ</u>
<u>ሚመለከቱ ፡ ውሎች ።</u>

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለየማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሺያጭ ። .... .... ፲፮፻፭
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ኪራይ ። .... .... .... .... .... .... ፲፮፻፱
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይ ፡ በጠቅላላው ። .... ፲፮፻፱
ክፍል ፡ ፪ ፤ የቤትን ፡ ኪራይ ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ። ፲፮፻፳፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ መሬት ፡ የተሰጡ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ። ... .... ፲፮፻፳፯
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሥራ ፡ ውል ። .... ፲፮፻፴፯
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣና ፡ ስለ፡ ወለድ ፡ አግድ ። .... .... .... .... .... .... .... ፲፮፻፵፪
ክፍል ፡ ፩ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ አቋቋም ። .... ፲፮፻፵፪
ክፍል ፡ ፪ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ውጤቶች ። ፲፮፻፵፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ቀደምትነት ፡ የብልጫ፡መብት ። ፲፮፻፵፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የመከታተል ፡ መብት ። .... .... ፲፮፻፶፪
ክፍል ፡ ፫ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ መቅረት ። ፲፮፻፶፰
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ (አንቲክሬዝ) ። .... .... ፲፮፻፷

<u>አንቀጽ ፡ ፲፱ ።</u>

<u>የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ (የአድሚኒስትራ</u>
<u>ሲዮኖች) ፡የሚያደርጉዋቸው ፡ ውሎች ።</u>

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .... .... .... ...... .. ፲፮፻፷፫
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ ሥርዐት ። . .... .... ፲፮፻፷፬
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ፈቃድን ፡ ስለ ፡ መስጠት ። .... .... ፲፮፻፷፬

ገጽ

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ የጨረታ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ። .... .... ፯፻፷፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ የውል ፡ ምክንያት ። ... .... .... ፯፻፸፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ ውል ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ። .... .... ፯፻፸፪
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ ደንበኛ ፡ አፈጻጸም ፡ ፯፻፸፪
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ ምርመራ ። .... .... ፯፻፸፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ ያለመፈጸም ። .... .... ፯፻፸፯
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ ውሎችን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መልቀቅና ።
ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ስለ ፡ ተስማማ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ። ፯፻፸፱
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ኮንሲሲዮን ። ፯፻፹
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ የመቋረጥ ፡ ውል ። .... .... ፯፻፹፱
ክፍል ፡ ፩ ፤ ውልን ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ። .... .... .... ፯፻፹፱
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ውል ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ አፈጻጸም ። .... .... ፯፻፺
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ሥራዎች ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂነት ። ፯፻፺
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ። .... .... ፯፻፺፫
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ሥራዎች ፡ ርክክብ ። .... .... ፯፻፺፬
ክፍል ፡ ፫ ፤ ውልን ፡ ስለ ፡ ማሻሻል ። .... .... .... .... ፯፻፺፭
ክፍል ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ውል ፡ አለመፈጸም ። .... .... .... .... ፰፻
ክፍል ፡ ፭ ፤ ውልን ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ መያዣነት ፡ ስለማስተላለፍ ። ፰፻፩
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ማቅረብ ፡ ውል ። .... .... .... ፰፻፩

## አንቀጽ ፡ ፳ ።

## ስለ ፡ ግልግልና ፡ ስለ ፡ ስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ ውል ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ግልግል ። .... .... .... .... .... ፰፻፬
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ግልግል ፡ በጠቅላላው ፡ .... .... .... ፰፻፬
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ዕርቅ ። .... .... .... .... .... ፰፻፭
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ የመጨረስ ፡ ስምምነት ። .... .... ፰፻፯

## አንቀጽ ፡ ፳፩ ።

## በቀድሞው ፡ ሕግና ፡ በዚህ ፡ በአሁኑ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ .. .... .... .... .... ፰፻፲፫
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ልዩ ፡ ድንጋጌ ። .... .... .... .... .... ፰፻፲፬

ገጽ

## አንቀጽ ፡ ፸፪ ።

### መሸጋገሪያ ፡ ሕግ ።


ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ሰዎችንና ፡ ውርስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፯፻፲፮

ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ንብረትና ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ማድረግን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ .... .... .... ፯፻፲፯

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

# የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ።

## ፲፱፻፶፪ ዓ. ም.

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍ ፡ ፪/ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ም ፡ በተለይ ፡ የወጣ ፡

አ ዲ ስ ፡ አ በ ባ ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮ
ጵያ ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመተ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓመተ ፡
ምሕረት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

# መ ቅ ድ ም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ኢትዮጵያ ፡ የደረሰችበትን ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ከሚለዋወጠው ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ለማራመድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችንን ፡ ማኅበራዊ ፡ አቋም ፡ የሚመለከተውን ፡ ሕግ ፡ በዘመናዊ ፡ አኳኋን ፡ ማሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አወጅን ። እስካሁን ፡ የተደረገውን ፡ እርምጃ ፡ ለማጠንከርና ፡ ወደፊትም ፡ የበለጠ ፡ መስፋፋትንና ፡ እድገትን ፡ ለማግኘት ፡ እያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጠቅላላው ፡ አገራችንን ፡ በሙሉ ፡ የሚያጋጥሙትን ፡ ጉዳዮች ፡ ለማከናወን ፡ እንዲቻል ፡ ትክክለኛና ፡ ዝርዝር ፡ የሆኑ ፡ ደንቦች ፡ ማዘጋጀት ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከጥንት ፡ ዘመናት ፡ ከወረስናቸው ፡ በጽኑ ፡ ከተመሠረቱት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ የሕግ ፡ ልምዶችና ፡ በጅጅኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓላችን ፡ በሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ጋር ፡ የሚስማሙ ፡ ናቸው ፤ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ ተሽለው ፡ የሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ ተጠንተዋል ።

ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ የሰዎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላቸው ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ለመግለጽ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ከወጣላቸው ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የሚደርስ ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ልምዳቸውን ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕን ፡ የሚጠብቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

እኛ ፡ ያቋቋምነው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ይህን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ በተከበረውና ፡ በጥንቱ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፍና ፡ ፍርድ ፡በመዝገብ ፡ መጻፍ ፡ ከተጀመረ ፡ ወዲህ ፡ የተገለጹትን ፡ ጥንታዊ ፡ የሆኑትን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን ፡ ታላቅ ፡ የሕግ ፡ ልምዶችና ፡ አቋሞች ፡ በመመልከትና ፡ በተለይም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንና ፡ ለተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ በማሰብ ፡ ነው ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ የሆኑትን ፡ መብቶቹንና ፡ ግዴታዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንዲገባው ፡ ለማድረግ ፡ ዐቅደን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ቃላቶች ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ እንዲዘጋጁ ፡ አድርገናል ።

እንደዚሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከትና ፡ የሚጠቀልል፡ሕግ ፡ ሁሉ አንድነትን ፡ ያለውና ፡ የተሟላ ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ዛሬ ፡ በዐዋጅ ፡ የምናወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይገኛል ።

የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ በጥንቃቄ ፡ ያዘጋጀውና ፡ ፓርላሜንታችን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትጋት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያየው ፡ በመሆኑ ፡ የታቀደበትን ፡ ዓላማ፡ እንደሚያስገኝ ፡ የሚያሳምን ፡ ነው ።

የፍርድ ፡ ምንጭ ፡ የጥበብና ፡ የሀብት ፡ ማግኛ ፡ በሆነ ፡ ሁሉን ፡ በሚችል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አሠሪነት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ላሁኑ ፡ ሕዝባችንና ፡ ለ መጭው ፡ ትውልድ ፡ ለሰላሙና ፡ ለደኅንነቱ ፡ እንደሚሆን ፡ እናምናለን ።

በነገሥን ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ዛሬ ፡ ሚያዝያ ፡ ሀያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አምሣ ፡ ሁለት ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ተጻፈ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ቍጥር ፡ ፩፻፷፭ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡

# ዐ ዋ ጅ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ በሚገባ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ አዲስ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ማወጅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ አገኘነው ፤

ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በኛ ፡ መሪነት ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አድርገን ፡ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ ስለ ፡ ተቀበሉት ፤

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በ፹፰ተኛውና ፡ በ፴፬ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፤

የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ የመከሩበትን ፡ አይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አውጀናል ።

፩ ፡ ይህ ፡ ዐዋጅ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ዘዋጅ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

፪ ፡ ይህ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ዐዋጅ ፡ በተለይ ፡ በቍጥር ፡ ፪/ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የታተመው ፡ ከመስከረም ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ።

ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አክሊሉ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡

ምክትል ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርና ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።

BACK

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ።

# አንደኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።
## ስለ ፡ ሰዎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ሰውና ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መብቶች ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።
#### የሰው ፡ መብት ፡ አሰጣጥ ።

**ቍጥር ፡ ፩ ። መሠረቱ ።**

ሰው ፡ ከተወለደበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሞተበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሕግ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍጥር ፡ ፪ ። የተፀነሱ ፡ ልጆች ።**

የተፀነሰ ፡ ልጅ ፡ በሕይወት ፡ ከተወለደና ፡ የሚኖር ፡ ከሆነ ፡ የራሱ ፡ ጥቅም ፡ በሚያሻበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ ይገመታል ።

**ቍጥር ፡ ፫ ። የተፀነሰበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) የልጅ ፡ መፀነስ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ ልጁ ፡ ከተወለደበት ፡ በፊት ፡ ካለው ፡ ከሦስት ፡ መቶኛው ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ነው ።

(፪) ይህንንም ፡ ግምት ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆን ፡ ማንኛውንም ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፫) የልጁ ፡ አባት ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መወሰንን ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ የተፀነሰበትን ፡ ቀን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍጥር ፡ ፬ ። የሚኖር ፡ ወይም ፡ የማይኖር ፡ ልጅ ።**

(፩) ይህን ፡ ተቃዋሚ ፡ የሚሆን ፡ ማናቸውም ፡ ማስረጃ ፡ ቢቀርብም ፡ እንኳ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ተወልዶ ፡ ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ በሕይወት ፡ ከቈየ ፡ በሕይወት ፡ እንደ ፡ ኖረ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) አንድ ፡ ልጅ ፡ ተወልዶ ፡ በሕይወት ፡ የቈየው ፡ ከ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሕይወት ፡ እንዳልኖረ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) የልጁን ፡ መሞት ፡ ያስከተለው ፤ በተፈጥሮው ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ያልሆነ ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተውን ፡ አገማመት ፡ ቀሪ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

**ቍጥር ፡ ፭ ። አንድ ፡ ሰው ፡ በሕይወት ፡ መኖሩን ፡ ወይም ፡ መሞቱን ፡ ስለ ፡ ማስረዳት ።**

(፩) ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ወገን ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሕይወቱ ፡ አለ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ

BACK



በሕይወቱ ፡ ነበረ ፤ ወይም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ሞቷል ፡ ብሎ ፡ ማስረዳት ፡ የሚገባው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ መብት ፡ ኖሮት፡ ሊጠቀምበት ፡ የሚ ጠይቀው ፡ ወገን ፡ ነው ።

(፪) አንድ ፡ ሰው፡በሕይወት ፡ አለ ፡ ወይም ፡ በሕይወት ፡ ነበረ ፡ ተብሎ ፡ ለማስ ረዳት ፡ የሚቻለው ፡ ይህንኑ ፡ በሕይወት ፡ አለ ፡ ወይም ፡ ነበረ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ በማቅረብ ፤ ወይም ፡ በቂ ፡ ምስክሮችን ፡ አቅርቦ ፡ በማስመስ ከር ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አቅርቦ ፡ በማስረዳት ፡ ነው ።

(፫) ያንድ ፡ ሰውን፡ መሞት ፡ ጉዳይ ፡ በማስረጃ፡ ማረጋገጥ ፡ የሚቻለውም፡ በዚሁ፡ አንቀጽ፡በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ በቍጥር ፡ ፵፯፡ በተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯ ። (፪) አብሮ ፡ ሟቾች ።

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አብረው ፡ በሞቱ ፡ ጊዜና ፡ ከነዚሁ ፡ ማንኛው ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ለማስረዳት ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፯ ። የመለያ ፡ ማስረጃ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚታወቀው ፡ የመታወቂያ ፡ ሰነድ ፡ ለመ ስጠት ፡ የተቋቋመው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ሰነድ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ ሰነድ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቂ ፡ ምስክሮች ፡ አቅርቦ ፡ በማስመስ ከር ፡ ነው ።

(፫) ምስክሮቹም ፡ የሰጡት ፡ መግለጫ ፡ ትክክለኛ ፡ ባለመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።
## ስለ ፡ ሰው ፡ መብቶች ።

ቍ ፡ ፰ ። ሰው ፡ መሆን ፡ የሚያስገኘው ፡ ውጤት ፤—

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ የመጠቀም ፡ መብትና ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተመለከተው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነፃ ነት ፡ የተረጋገጠለት ፡ ይሆናል ።

(፪) በዚህም ፡ አስተያየት ፡ ረገድ ፡ የዘርንም ፡ ልዩነት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የቀለምን ፡ የሃይማኖትንም ፡ ሆነ ፡ የፆታን፡ ልዩነት ፡ መከተል ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፱ ። የዚህ ፡ ውጤት ፡ ወሰን ።

(፩) የሰው ፡ ልጆች ፡ መብትና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተረጋገ ጡት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ነፃነቶች ፡ አይነገድባቸውም ።

(፪) ይህን ፡ መብቱን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በራስ ፡ ፈቃድ ፡ የተደረገ ፡ የመቀ

BACK



ነስ ፡ አወሳሰን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ተገቢ ፡ ለሆነ ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጥቅም ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ (የማይጸና) ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ አሠራርን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ አሠራር ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ በአድራጊው ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ የአላፊነት ፡ ጉዳይ ፡ ሳይቀር ፡ ተበዳዩ ፡ በደሉ ፡ እንዲቀርለት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፲፩ ። በነፃነት ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ መሰናክልና ፡ ስለ ፡ መበርበር ።**

በሕግ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ማንም፡ሰው ፡ የግል ፡ ነፃነቱን ፡ ማጣትም ፡ ሆነ ፡ ያላገባብ ፡ መበርበር ፡ ሊደርስበት ፡ አይገባም ።

**ቍ ፡ ፲፪ ። የመኖሪያ ፡ ስፍራን ፡ የመምረጥ ፡ ነፃነት ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የመኖሪያ ፡ ስፍራውን ፡ በሚስማማው ፡ ቦታ ፡ የመወሰንና ፡ እንደ፡ ፈለገም ፡ ይህን ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራውን ፡ የመለወጥ ፡ ነጻነት ፡ አለው ።

(፪) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የመኖሪያ ፡ ስፍራውን ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚገባው ፡ ግዴታ ፡በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አስተያየት ፡ በኩል ፡ እንዳችም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፫) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ አልኖርም ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ አልደርስም ፡ ብሎ ፡ የሚገባው ፡ ግዴታ ፡ ተገቢ ፡ ለሆነ ፡ ጥቅም ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ አይጸናበትም ።

**ቍ ፡ ፲፫ ። የመኖሪያ ፡ ቤት ፡ አለመደፈር ።**

(፩) ያንድ ፡ ሰው ፡ ማናቸውም ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የማይደፈር ፡ ነው ።

(፪) በሕግ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለቤቱ ፡ ሲቃወም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፤ የሌላውን ፡ ሰው፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ለመበርበር ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፬ ። የማሰብ ፡ ነፃነት ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የማሰብና ፡ አሳቡን ፡ የመግለጽ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

(፪) ይህንንም ፡ ነጻነቱን ፡ ሊቀንሱበት ፡ የሚችሉት ፡ የሌሎችን ፡ መብቶች ፡ የማክበር ፡ ግዴታዎች ፤ መልካም ፡ ባህልንና ፡ ሕጎችን ፡ አክብሮ ፡ የመጠበቅ ፡ ግዴታዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፭ ። ስለ ፡ ሃይማኖት ።**

የሕዝብን ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ወይም ፡ ጸጥታን ፡ ወይም ፡ በፖለቲካ፡ረገድ ፡ የሚያውክ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ሥርዐት ፡ አክብረው ፡ በነፃ ፡ ከመፈጸም ፡ አይከለከሉም ።

**ቍ ፡ ፲፮ ። የመሥራት ፡ ነፃነት ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ ወይም ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜዎቹን ፡ በሚ መለከተው ፡ ረገድ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በገዛ ፡ አሳቡ ፡ የመረጠውን ፡ ሥራ ፡ ለማካሄድ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

(፪) ይህንን ፡ ነፃነቱን ፡ ሊቀንሱበት ፡ የሚችሉት ፡ ምክንያቶች ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ መልካም ፡ ባህልንና ፡ ሕጎችን ፡ የማክበር ፡ ግዴታዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፫) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ የመሥራት ፡ ነፃነቱን ፡ በመቀነስ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ለማካሄድ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ላለመሥራት ፡ የገ ባው ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ሁሉ ፡ ተገቢ ፡ ጥቅም ፡ መኖሩን ፡ ካላረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ሊጸናበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፯ ። ስለ ፡ ማግባትና ፡ ስለ፡መፍታት ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ እንዳያገባ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዳ ያገባ ፡ ያደረገው ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አስተያ የት ፡ ረገድ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እፈታለሁ ፡ ወይም ፡ አልፈታም ፡ ብሎ ፡ የሚገ ባው ፡ ግዴታ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፲፰ ። የሰው ፡ አካል ፡ የማይደፈር ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ አካሉን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያደርገው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ግዴታ ፡ ሁሉ ፤ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚፈጸመው ፡ አካሉን ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በአካሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ከሆነ ፡ ስምም ነቱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አካሉን ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠቱ ፡ ጉዳይ ፡ በሕክምና ፡ ጥበብ ፡ በኩል ፡ ጉዳት ፡ የማያደርስ ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ የዚህ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ አይጸናበትም ።

**ቍ ፡ ፲፱ ። ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ ውሎች ፡ ተለዋጭ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሕይወት ፡ ሳለሁ ፡ ወይም ፡ ከሞትሁ ፡ በኋላ ፡ አካሌን ፡ በመላውም ፡ ሆነ ፡ በከፊሉ ፡ ሰጥቻለሁ ፡ ብሎ ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ በማንኛ ውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ አሠራር ፡ ሊጠቀም ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በተሰጠው ፡ ተስፋ ፡ መሠረት ፡ ላደረገው ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ኪሣራ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፳ ። የሐኪሞች ፡ ምርመራና ፡ ሕክምና ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የሐኪም ፡ ወይም ፡ የቀዳጅ ፡ ሐኪም ፡ ምርመራ ፡ ወይም ፡ ሕክምና ፡ እንዳይደረግለት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንቢ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ሰዎች ፡ የጤንነት ፡ ምርመራ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ክትባት ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ መሳሰለው ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ጉዳይ ፡ የወጡት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያዎችና ፡ ሕጋውያን ፡ ዐዋጆች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፫) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ችሎታ ፡ ለሌለው ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ በሥልጣኑ ፡ የሚተዳደረው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ጤንነቱ ፡ እንዲጠበቅ ፡ የሐኪም ፡ ምርመራ ፡ የሚያደርግበትና ፡ የሚያሳክምበት ፡ ሥልጣኑ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፳፩ ። (፪) አወሳሰን ።

ቢሆንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሐኪም ፡ እንዲመረመር ፡ ወይም ፡ እንዲታከም ፡ የሚጠይቅበት ፡ ምርመራ ፡ ማንኛውንም ፡ ያለመጠን ፡ የሆነ ፡ ጉዳትን ፡ የማያስከትል ፡ ሲሆን ፤ ሰውዬውም ፡ ይህንን ፡ የሐኪም ፡ ምርመራና ፡ ሕክምና ፡ ለማድረግ ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ሕክምናና ፡ ምርመራ ፡ ሊያግድለት ፡ ሊያስቀርለት ፡ ወይም ፡ ሊያሽለው ፡ ይችል ፡ በነበረው ፡ ሕመም ፡ ወይም ፡ ደዌ ፡ ክርክር ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፳፪ ። የሐኪም ፡ ምርመራ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በሰውነት ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ እርግጠኛ ፡ አደጋ ፡ ሊያስከትል ፡ በማይችል ፡ በሐኪም ፡ ምርመራ ፡ ለመመርመር ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ተመርምሮ ፡ ሊገኝበት ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ የተገመተው ፡ ነገር ፡ እንዳለበት ፡ ያህል ፡ ሊቈጥሩት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፳፫ ። የዝምታ ፡ መብት ።

የሰውን ፡ አካል ፡ በመድፈር ፡ (በሰውነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ) ፡ የተገኘ ፡ ማንኛውም ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የአሳብ ፡ መግለጫ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፳፬ ። የሞያ ፡ ሥራ ፡ ምስጢር ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፤ ሌላው ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ የሚያጐድል ፡ ወይም ፡ ለማጐደል ፡ የሚችል ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ ያወቃቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ እንዲገልጽ ፡ ለመገደድ ፡ አይችልም ።

(፪) እነዚህን ፡ ሁኔታዎች ፡ ለባለአደራው ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ እንዲያውቃቸው ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ እነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ በባለአደራው ፡ እንደበት ፡ እንዳይገለጹበት ፡ የመከልከል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፤ በሀገርና ፡ በእንቴርናሲዮናል ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፳፭ ። ስለ ፡ መቃብር ፡ ሥርዐት ። (፩) የሟቹ ፡ ፈቃድ ።

(፩) ማንኛውም ፡ ለመናዘዝ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የመቃብሩን ፡ ሥርዐት ፡ አስቀድሞ ፡ ለማደራጀት ፡ ይችላል ።

(፪) የዚህንም ፡ ድርጅት ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲጠብቁለት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) እነዚህም ፡ የሟቹን ፡ የመጨረሻ ፡ ፈቃድ ፡ ለማስፈጸም ፡ አደራ ፡ የተቀበሉት ፡ ሰዎች ፡ እንደሌሉም ፤ የግዙፍ ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ (የሞራል) ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤ ሰውዬው ፡ ለሞተበት ፡ ቦታ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆኑት ፡ ዳኞች ፡ የታሰበውን ፡ ድርጅት ፡ እንዲያስፈጽሙ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፳፮ ። (፪) ያልተገለጸ ፡ አሳብ ፡ (ፈቃድ) ።

(፩) ሟቹ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ አሳቡን ፡ (ፈቃዱን) ፡ ሳይገልጽ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመቃብሩን ፡ ሥርዐት ፡ ድርጅት ፡ የሚያከናውኑት ፡ የሟቹ ፡ ባለቤት ፡ ወይም ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶቹ ፡ ናቸው ።

(፪) በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤት ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶቹ፡ ባቅራቢያው ፡ ያልተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ያልታወቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ ሥርዐቱን ፡ ለማስፈጸም ፡ በጀመሩት ፡ ሰዎች ፡ አማካይነት ፡ ይከናወናል ።

(፫) በአፈጻጸሙም ፡ በኩል ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጉዳዩን ፡ በቅርብ ፡ በሚከታተሉት ፡ ሰዎች ፡ አማካይነት ፡ ሰውዬው ፡ በሞተበት ፡ ቦታ ፡ ያሉት ፡ ዳኞች ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲወስኑ ፡ ሊጠየቁ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፳፯ ። የሰው ፡ ሥዕል ። (፩) (መሠረቱ) ።

ባለፎቶግራፉ ፡ ወይም ፡ ባለሥዕሉ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ የማንም ፡ ሰው ፡ ፎቶግራፍ ፡ ወይም ፡ ሥዕል ፡ በሕዝብ ፡ አደባባይ ፡ ሊለጠፍም ፡ ሆነ ፡ ሊባዛ ፡ ወይም ፡ ሊሸጥ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፳፰ ፡ (፪) ልዩ ፡ አስተያየት ።

የፎቶግራፉ ፡ ወይም ፡ የሥዕሉ ፡ መባዛት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ባለፎቶግራፉ ፡

የታወቀ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ በሚያከናውነው ፡ ሕዝባዊ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፤ ወይም ፡ በፍርድና ፡ በፖሊስ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በኩል ፡ አስፈላጊነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ ለኪን ፡ ጥበብ ፡ (ሲያንስ) ፡ ለሥልጣኔ ፡ አስተዳደግ ፡ ወይም ፡ ለትምህርት ፡ መስጫ ፡ ጥቅም ፡ በመሆኑ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የፎቶግራፉ ፡ መባዛት ፡ የተፈጸመው ፡ በክብረ ፡ በዓል ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ከተፈጸመ ፡ ሥርዐት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ባለው ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ የባለፎቶግራፉ ፡ ፈቃድ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፳፱ ። (፫) ክልከላ ።

(፩) ባለሥዕሉ ፡ ሳይፈቅድ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ሥዕል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ቊጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ በአደባባይ ፡ የተለጠፈ ፡ ወይም ፡ ለሽያጭ ፡ የቀረበ ፡ (የተዘጋጀ) ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሥዕሉ ፡ ይህ ፡ አድራጎት ፡ እንዲወገድ ፡ ለመጠየቅ ፡ (ለማስገደድ) ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በርትዕ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ሥዕሉን ፡ በአደባባይ ፡ በመለጠፍና ፡ በመሸጥ ፡ የተጠቀመው ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ያገኘው ፡ ሀብት ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ ዳኞች ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊወስኑበት ፡ ይችላሉ ።

(፫) የሥዕሉ ፡ በአደባባይ ፡ መለጠፍና ፡ መሸጥ ፡ እንዲቋረጥ ፡ እንዲታገድ ፡ እንደ ፡ ተጠየቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ጥያቄው ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በስም ፡ ማጥፋት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚፈጽመው ፡ ዳኞች ፡ የሞራል ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ሊያሰጡት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፴ ። (፬) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መብት ።

(፩) ሥዕሉ ፡ በአደባባይ ፡ የወጣበት ፡ ወይም ፡ የተሸጠበት ፡ ሰው ፡ ሞቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ፈቃዱን ፡ ለመግለጽ ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሥዕሉ ፡ በአደባባይ ፡ መገለጽ ፡ ወይም ፡ መሸጥ ፡ የሟቹን ፡ ክብር ፡ የሚነካ ፡ ወይም ፡ ግምቱን ፡ የሚያጐድልበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቊጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ መብቶች ፡ የሟቹ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) በዚህም ፡ ቊጥር ፡ ለተጻፈው ፡ አፈጻጸም ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ የሟቹ፡ባለቤት፤ይህም ፡ ባይኖር ፡ የቅርብ ፡ ተወላጅ ፡ (ልጅ ፡ የልጅ፡ልጅ) ፡ ወይም ፡ ተወላጁ ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፡ ወደ፡ላይ ፡ የሚቈጠር ፡ የሟቹ ፡ የቅርብ ፡ ወላጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) የዝምድናው ፡ ደረጃ ፡ እኩል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ ከተወላጆቹ ፡ በዕድሜ ፡ የሚበልጠው ፡ ወይም ፡ ወደላይ ፡ ከሚቈጠሩት ፡ ወላጆቹ ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፴፩ ። ደብዳቤ ፡ የማይደፈር ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ለራሱ ፡ ብቻ ፡ የተጻፈለትን ፡ ደብዳቤ ፡ ተቀባይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ የተጻፈውን ፡ ላኪው ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለመግለጽ ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ተገቢ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍርድ ፡ በኩል ፡ ለሚያጋጥመው ፡ ጉዳይ ፡ ለፍርድ ፡ ችሎት ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ስም ።

**ቍ ፡ ፴፪ ። መሠረቱ ።**

(፩) እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ የግል ፡ ስሞችና ፡ የአባት ፡ ስም ፡ ይኖረዋል ።

(፪) በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ( በአድሚኒስትራሲዮን ) ፡ ጽሑፎች ፤ የግል ፡ ስሞቹንና ፡ የአባቱን ፡ ስም ፡ በሚያስከትል ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ይመለከታል ።

**ቍ ፡ ፴፫ ። የስም ፡ አሰጣጥ ።**

(፩) የልጁ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ የአባቱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ነው ።

(፪) የልጅ ፡ አባት ፡ ያልታወቀ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ልጁ ፡ ተክዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጁ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ የእናቱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ነው ።

(፫) እንዲሁም ፡ በእናቲቱ ፡ መጠለፍ ፡ ወይም ፡ መደፈር ፡ ምክንያት ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ አፈጻጸሙ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፴፬ ። የግል ፡ ስም ፡ ምርጫ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የአንድ ፡ ልጅን ፡ የግል ፡ ስም ፡ የሚመርጠው ፡ አባቱ ፤ ወይም ፡ አባቱ ፡ በሌለ፡ ጊዜ ፡ የእናቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ነው ።

(፪) ለልጁ ፡ ሁለተኛ ፡ የግል ፡ ስም ፡ እናቱ ፡ ወይም ፡ እርስዋ ፡ እንደሌለች ፡ የእናቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ መርጠው ፡ ሊያወጡለት ፡ ይችላሉ ።

(፫) የልጁ ፡ አባት ፡ ያልታወቀ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ ልጁ ፡ የአባቱ ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ የሌሉት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጁ ፡ እናት ፡ ወይም ፡ እርስዋ ፡ ባትኖር ፡ የእናቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ለልጁ ፡ ሁለት ፡ የግል ፡ ስም ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፴፭ ። (፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ።

(፩) ከዚሀ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ በሚውል በት፡ረገድ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ የሆነ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠር ፡ ወላጅ ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ በታጣ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ የሆነ ፡ የጐን ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) የዝምድናውም ፡ ደረጃ ፡ እኩል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ የልጁን ፡ የግል ፡ ስም ፡ የሚመርጠው ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠር ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ የጐን ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፴፮ ። የአባት ፡ ስም ።

(፩) ለልጁ ፡ ያባት ፡ ስም ፡ የሚሆነው ፡ የአባቱ ፡ የግል ፡ ስም ፡ ነው ።

(፪) አባቱ ፡ ባልታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዮው ፡ ያባት ፡ ስም ፡ አይኖረውም ።

(፫) በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ (በአድሚኒስትራሲዮን) ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ያባት ፡ ስም ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ያባት ፡ ስም ፡ አይጻፍም ።

ቍ ፡ ፴፯ ። ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚሰጥ ፡ መግለጫ ።

ልጁ ፡ በተወለደበት ፡ ቀበሌ ፡ (አጥቢያ)፡ ለሚገኘው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ የልጁን ፡ መወለድ ፡ መግለጫ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፤ ልጁ ፡ ከተወለደበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ባለው ፡ በተከታዩ ፡ ዘጠና ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለተወለደው ፡ ልጅ ፡ የተሰጠውን ፡ የግል ፡ ስም ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፴፰ ። የተከለከለ ፡ የግል ፡ ስም ።

(፩) ማንኛውም ፡ ልጅ ፤ ያባቱ ፡ ወይም ፡ የናቱ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በሕይወት ፡ ካሉት ፡ እኅቶቹና ፡ ወንድሞቹ ፡ ያንደኛው ፡ የግል ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ።

(፪) እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገርም ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሚለየው ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የግል ፡ ስም ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፴፱ ። ወላጆቹ ፡ ያልታወቀ ፡ ልጅ ።

(፩) አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ ለማወቅ ፡ ያልተቻለ ፡ ልጅ ፡ በመወለዱ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ውስጥ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ የሚሰጠው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ ሁለት ፡ የግል ፡ ስሞች ፡ ይኖሩታል ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስሞቹም ፡ የሚመረጡለት ፡ በተወለደበት ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ልማዳዊ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስሞች ፡ መካከል ፡ ነው ።

BACK



(፫) የግዙፍ ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ (የሞራል)፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤ የተባለው ፡ ልጅ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላው ፡ ድረስ ፡ የተሰጠው ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስም ፡ እንዲለወጥለት ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፵ ፡፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ስም ፡፡**

(፩) ያገባች ፡ ሴት ፡ የራስዋ ፡ የሆነውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ ትቈያለች ፡፡

(፪) ስለ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ጋብቻዋ ፡ ጸንቶ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በባልዋ ፡ ስም ፡ ልትጠራ ፡ ወይም ፡ ራስዋ ፡ እንድትጠራ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ፡፡

(፫) ጋብቻው ፡ የቀረው ፡ በመፋታቷ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሌላ ፡ ባል ፡ በማግባቷ ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው፡የስም፡መጠራት መብት ፡ ቢጠቅማትም ፡ ቢጐዳትም ፡ ከጋብቻው ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይቀራል ፡፡

**ቍ ፡ ፵፩ ፡፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስም ፡፡**

(፩) የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ የጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ይኖረዋል ፡፡

(፪) በጉዲፈቻው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የግል ፡ ስም ፡ ሊሰጠውና ፡ የጉዲፈቻ ፡ አድራጊውም ፡ መደበኛ ፡ የግል ፡ ስም ፡ እንደ ፡ አባት ፡ ስም ፡ ሊሆነው ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፵፪ ፡፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ መለወጥ ፡፡**

(፩) በቂ ፡ ምክንያት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰውዬው ፡ ጠያቂነት ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ እንዲለወጥ ፡ ዳኞች ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ፡፡

(፪) ዳኞቹም ፡ የቀረበላቸውን ፡ ጥያቄ ፡ ሲመረምሩ ፡ የስሙ ፡ መለወጥ ፡ ጕዳይ ፡ በሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ ጉዳት ፡ እንዳያስከትል ፡ ጥንቃቄ ፡ ያደርጋሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፵፫ ፡፡ የግል ፡ ስም ፡ መለወጥ ፡፡**

ከግል ፡ ስሞቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹ ፡ እንዲሠረዙ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የግል ፡ ስም ፡ እንዲጨመርለት ፡ ባለጥቅሙ ፡ ጥያቄ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሊፈቀድለት ፡ ይቻላል ፡፡

**ቍ ፡ ፵፬ ፡፡ ስምን ፡ የሚመለከቱት ፡ ውሎች ፡፡**

(፩) ስለ ፡ ስም ፡ የሚደረግ ፡ ማንኛውም ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡፡

(፪) የንግድ ፡ ስምን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ፡፡

**ቍ ፡ ፵፭ ፡፡ በራስ ፡ ስም ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡፡**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ በገዛ ፡

ስሙ ፡ የመገልገል ፡ ጕዳይ ፡ በይመስላል ፡ ከሚደርሰው ፡ መዘባረቅ ፡ የተነሣ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ክብርና ፡ ገናናነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ግብ ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ የሚያስከትል ፡ ነገር ፡ ሊኖረው ፡ አይገባም ።

(፪) አስፈላጊ ፡ መሆኑም ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፤ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ጕዳይ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የመወዳደርና ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ቍ ፡ ፵፯ ። በሌላው ፡ ስም ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ በመሰል ፡ ስሙ ፡ ምክንያት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ያላገባብ ፡ በመገልገሉ ፡ ግዙፍና ፡ የሕሊና ፡ (የሞራል) ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ ሁኔታ ፡ የሚያጋጥመው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሙን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ እንዳይገለገልበት ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) ባለስሙ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፤ ወይም ፡ ፈቃዱን ፡ ለመግለጽ ፡ ችሎታ ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ስም ፡ የማይጠራበት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የሚቴ ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ባልና ፡ ተወላጆቹ ፡ ይህ ፡ የመቃወም ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

(፫) ይህ ፡ በስም ፡ ያላገባብ ፡ የመገልገል ፡ ጕዳይ ፡ እንዲታገድ ፡ ተጠይቆ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሳይታገድ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ስም ፡ ማጥፋት ፡ ተቈጥሮ ፡ የሕሊና ፡ (የሞራል) ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ሊወሰን ፡ ይቻላል ።

# ምዕራፍ ፡ ፫ ።

# ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ አስረጅነት ።

## ቍ ፡ ፵፰ ። የአስረጅነቱ ፡ ዐይነት ።

(፩) ልደት ፤ ሞትና ፡ ጋብቻ ፡ ያጠራጠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ክርክር ፡ የተነሣባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚረጋገጡት ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ አስረጅነት ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅድበት ፡ ጊዜ ፡ በታወቀ ፡ ሰነድ ፡ አስረጅ ፡ አማካይነት ፡ ወይም ፡ በሁኔታ ፡ መኖር ፡ ሊረጋገጡ ፡ ይችላሉ ።

# ክፍል ፡ ፩ ።

# ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹማምቶች ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

## የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹማምት ፡ ሥልጣን ፡ አሰጣጥ ።

## ቍ ፡ ፵፱ ። በአገረ ፡ ገዢው ፡ ስለ ፡ መሾም ።

(፩) ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ የከተማና ፡ የባላገር ፡

BACK



ቀበሌ ፡ (አጥቢያ) ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ የሚሆነውን ፡ ሰው ፡ ይሾማል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በያንዳንዱ ፡ ቀበሌ ፡ (አጥቢያ) ፡ ለእነዚህ ፡ ሹማምቶች ፡ ምትክ ፡ ሆነው ፡ የሚሠሩ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሠራተኞችን ፡ ይሾማል ።

ቍ ፡ ፺፱ ። ሰፈር ፡ ወይም ፡ የቀበሌ ፡ ክፍል ።

(፩) አንድ ፡ የከተማ ፡ ቀበሌ ፡ በብዙ ፡ ሰፈሮች ፡ የተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ልዩ ፡ ሰፈር ፡ አንዳንድ ፡ የተለየ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹምን ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ ሊሾም ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ያንድ ፡ የባላገር ፡ ቀበሌ ፡ ክፍል ፡ ለብቻው ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ ቀበሌ ፡ የተራራቀ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ለዚሁ ፡ የተለየ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹምን ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ምትክ ፡ ይሾምላቸዋል ።

ቍ ፡ ፻ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ምትክ ።

(፩) ዋናው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ የሚያውከው ፡ በራሱ ፡ በኩል ፡ የደረሰ ፡ እክል ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ምትኮቹ ፡ ተተክተው ፡ ይሠራሉ ።

(፪) ምትክ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲያከናውኑ፡ በሚጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራቸውን ፡ የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ አልወሰነላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀዳሚነት ፡ የሚተካው ፡ በዕድሜ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነው ፡ ነው ።

(፫) ከምትኮች ፡ አንደኛው ፡ ያደራጀው ፡ ሰነድ ፡ የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ያህል ፡ የሚቈጠርና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አስረጅ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፩ ። የሥራቸው ፡ አጀማመር ።

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙ ፡ ሥራ ፡ የሚጀመረው ፤ ሥራውን ፡ ከተቀበለና ፤ ፊርማውም ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በክብር ፡ መዝገቡ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሥራዎች ፡ የሚጀመሩት ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ የሾመው ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ በማደራጀት ፤ ወይም ፡ ይኸው ፡ ሰነድ ፡ ሲደራጅ ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ስም ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፤ የዚሁኑ ፡ አሠራር ፡ በተግባሩ ፡ አከናውኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ወይም ፡ የዚሁኑ ፡ የሥራውን ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎችም ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙን ፡ ምትኮች ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፶፪ ፡ ሥራው ፡ የሚቀርበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሥራ ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ ሲሞት ፡ ወይም ፡ ከሥራው ፡ ሲነሣ ፤ ወይም ፡ ሲሻር ፡ ወይም ፡ ስንብት ፡ ጠይቆ ፡ ይህንኑ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ሲቀበለው ፡ ነው ።

(፪) የክብር ፡ መዝገብ፡ሹሙ ፡ ምትኮች ፡ ሥራ ፡ የሚቀረው ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፶፫ ። የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ምትኮች ፡ ሠራተኞች ፡ መሞትና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈይ ፡ እክል ።**

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ከምትኮቹ ፡ ያንዱን ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ ለዘወትር ፡ ከሥራ ፡ የሚለያቸው ፡ እክል ፡ የገጠማቸው ፡ መሆኑን ፡ ያለ ፡ መዘግየት ፡ ለግዛቱ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ያስታውቃል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ምትኮች ፡ የሆኑት ፡ የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ መሞቱን ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ እንዳያከናውን ፡ ለዘወትር ፡ የሚቈይ ፡ እክል ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑን ፡ ማንኛውንም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሁኔታ ፡ ለግዛቱ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ሳይዘገይ ፡ ያስታውቃል ።

**ቍ ፡ ፶፬ ። የቀበሌ ፡ (የአጥቢያ) ፡ ሹም ።**

(፩) አገረ ፡ ገዢው ፡ የሾመው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ምትክ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ለማከናወን ፡ በማይችሉበት ፡ ሁኔታ ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ የቀበሌው ፡ ሹም ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ቀበሌ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ይሆናል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገርም ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹምነት ፡ ሥራው ፤ በራሱ ፡ ኀላፊነት ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ረዳቶች ፡ እየተተካ ፡ ወይም ፡ እየተረዳ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላል ።

(፫) ይህንንም ፡ ሁኔታ ፡ ለአገረ ፡ ገዢው ፡ ሳይዘገይ ፡ ያስታውቃል ።

**ቍ ፡ ፶፭ ። የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።**

(፩) ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ ለያንዳንዱ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ከተማ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ሠራተኞችን ፡ መርጦ ፡ ያቋቁማል ።

(፪) እነዚህም ፡ ሠራተኞች ፡ በሥራው ፡ አቋቋምና ፡ አመራር ፡ በኩል ፡ አላፊ ፡ ከሚሆን ፡ የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ (ዲሬክተር) ፡ በቀር ፡ የጽሕፈት ፡ ቤቱን ፡ (የቢሮውን) ፡ ሥራ ፡ ለማካሄድ ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፤ ቍጥራቸው ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ የተወሰነ ፡ ሠራተኞች ፡ ይኖሩበታል ።

**ቍ ፡ ፶፮ ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሚመለከት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ።**

(፩) ግርማዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ቤተ ፡

BACK



ዘመድን ፡ በሚመለከተው ፡ የክብር ፡ አመዘጋገብ ፡ ጉዳይ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹምነትን ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽመው ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ቃል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ ረገድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ የሚባሉት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፶፯ ። የኢትዮጵያ ፡ ቆንሲሎች ።**

የኢትዮጵያ ፡ ቆንሲሎች ፡ በተሾሙበት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን፡የኢትዮጵያ፡ ዜጎች ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹማምቶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፶፰ ። የመርከብ ፡ አዛዦች ።**

የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ አዛዦች ፡ በመርከባቸው ፡ ውስጥ ፡ በሚደርሰው ፡ ልደት ፡ ሞትና ፡ ጋብቻ ፡ ረገድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሞች ፡ ናቸው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
## የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ተግባር ።

**ቍ ፡ ፶፱ ። መሠረቱ ።**

የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ተግባር ፡ በራሱ ፡ ክፍል፡ ውስጥ ፡ የሚደርሰው፡ልደት፡ ሞት ፤ ጋብቻ ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጻፍ ፡ መቈጣጠርና ፡ መጠባበቅ ፡ ነው ።

### ሀ ) የከተማ ፡ ቀበሌ ።

**ቍ ፡ ፷ ። የመዝገቦች ፡ አያያዝና ፡ አቀማመጥ ።**

(፩) ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ይህን ፡ ግዴታ ፡ እንዲያከናውን ፡ በግልጽ ፡ ያዘ ዘው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በዚሁ ፡ ቀበሌ ፡ የክብር ፡ መዝገቦችን ፡ ራሱ፤ መያዝ ፡ አለበት ።

(፪) የዚህንም ፡ መዝገብ ፡ ጥበቃና ፡ አቀማመጥ ፡ ራሱ ፡ አረጋግጦ ፡ ባለጉዳዮቹም ፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፡ የዚህን ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ ቅጅ ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ግል ባጭ ፡ ለባለጥቅሞቹ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፷፩ ። የሰነዶች ፡ አጻጻፍ ።**

(፩) በክብር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የሚጻፉትን ፡ ማስረጃዎች ፤ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ በእጁ ፡ እንደ ፡ ገቡለት ፤ በራሱ ፡ አሳቢ ነት ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

(፪) የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚያስ

BACK



ፈልጉትን ፡ ማስረጃዎች ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ አሟልቶ ፡ ለመጻፍ ፡ እንዲችል ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ ጥሪ ፡ ያደርግላቸዋል ።

**ቍ ፡ ፳፪ ። የጊዜ ፡ ውሳኔ ።**

የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ፡ ጽሑፎች፡ በሚከተሉት ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ፡

ሀ/ ስለ ፡ ልደት ፡ ጽሑፎች ፡ ሦስት ፡ ወር ።

ለ/ ስለ ፡ ሞት ፡ ጽሑፎች ፡ አንድ ፡ ወር ።

ሐ/ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ጽሑፎች ፡ አንድ ፡ ወር ።

**ቍ ፡ ፳፫ ። የጊዜው ፡ ውሳኔ ፡ አለመፈጸም ።**

(፩) የተወሰነው ፡ ሕጋዊ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሚጻፉ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ ዋጋቸው ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ አስረጂ ፡ ብቻ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ የተመዘገቡት ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ አይጸናም ።

(፫) ይህ ፡ ሲሆን ፡ ጽሑፉ ፡ ፍርዱን ፡ የሚጠቅስ ፡ ቃል ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ይኖርበታል።

## ለ) የገጠር ፡ ቀበሌዎች ።

**ቍ ፡ ፳፬ ። ማስታወቂያዎች ።**

(፩) ይህን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙ ፡ በአገረ ፡ ገዢው ፡ በግልጽ ፡ ባልታዘዘበት ፡ የገጠር ፡ ቀበሌዎች ፤ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙ ፡ ራሱ ፡ መዝገቦችን ፡ እንዲይዝ ፡ አይገደድም ።

(፪) በቀበሌው ፡ ውስጥ ፡ የደረሱትን ፡ ልደት ፡ መሞትና ፡ ጋብቻ ፡ የሚመለከቱትን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ ለመመዝገብ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙ ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ ብቻ ፡ አለበት ።

(፫) እነዚህን ፡ መረጃዎች ፡ እምነት ፡ በማድረግ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወዲያውኑ ፡ ይመዘግባሉ ።

**ቍ ፡ ፳፭ ። የአፈጻጸሙ ፡ ደንብ ።**

(፩) እያንዳንዱን ፡ ቀበሌ ፡ ስለሚመለከተው ፡ እነዚህ ፡ መረጃዎች ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ መሰብሰብ ፡ እንዳለባቸው ፡ ከአገረ ፡ ገዢው ፡ የሚሰጡት ፡ ትእዛዞች ፡ ይወስናሉ።

(፪) በተለይም ፡ እነዚህ ፡ ትእዛዞች ፡ በምን ፡ ስፍራና ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ መረጃዎቹ ፡ መሰጠት ፡ እንዳለባቸው ፡ ይወስናሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፳፮ ። መረጃዎቹ ፡ የሚቀርቡበት ፡ ስፍራ ።**

(፩) ትእዛዞቹም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ የሚመለከቱትን ፡ መረጃዎች ፡ ለመስጠት ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ወይም ፡ ለቀበሌው ፡ ቀረብ ፡ ባለው ፡ ባንድ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እንዲሄድ ፡ የክብር ፡ መዝገቡን ፡ ሹም ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፡ ትእዛዞቹ ፡ መዝገቦችን ፡ ማቋቋም ፡ ከሚያስፈልግበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ እነዚህን ፡ መረጃዎች ፡ መሰብሰብ ፡ እንዳለባቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ መዝገቦቹ ፡ በቀበሌው ፡ ወይም ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ክፍል ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ለመሆናቸው ፡ ትእዛዝን ፡ ለይተው ፡ ይወስናሉ ።

**ቍ ፡ ፳፯ ። መረጃዎቹ ፡ የሚቀርቡበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብን ፡ የሚመለከቱ ፡ መረጃዎች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ቀበሌ ፡ ቢያንስ ፡ በዓመት ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ መሰብሰብ ፡ አለባቸው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በ፩ኛ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ተመለከተው ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ የመሄድ ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፳፰ ። አማካይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መግለጫዎችን ፡ ማቅረብ ፡ ስለ ፡ መቻሉ ።**

(፩) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ከወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውጭ ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ የሚመለከቱ ፡ መረጃዎችን ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ቀበሌውን ፡ የሚመለከቱ ፡ መዝገቦች ፡ በዚሁ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ የሚገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህ ፡ መረጃዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፳፱ ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ የጽሑፎች ፡ አሠራር ።**

(፩) ትእዛዞቹ ፤ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙን ፡ ራሱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎችን ፡ እንዲጽፍ ፡ ሊፈቅዱለት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ የተጻፉትን ፡ ጽሑፎች ፡ የያንዳንዱን ፡ ጽሑፍ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲያጸድቃቸው ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) ይህም ፡ ማጽደቅ ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ የሚመለከት ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፴ ። የዘገዩ ፡ ማስታወቂያዎች ።**

(፩) ምክንያት ፡ የሆናቸው ፡ ነገር ፡ ከደረሰ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የተጻፉ ፡ ወይም ፡ የጸደቁ ፡ ጽሑፎች ፡ ዋጋቸው ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ አስረጂ ፡ ብቻ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቦች ፡ ላይ ፡ የተጻፉ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ አይጸናም ።

(፫) ይህም ፡ ሲሆን ፡ ጽሑፉ ፡ ፍርዱን ፡ የሚጠቅስ ፡ ቃል ፡ በላዩ ፡ ይኖርበታል ።

## ሐ) ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

**ቍ ፡ ፴፩ ። የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።**

(፩) ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትንና ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ዘመድን ፡ የሚመለከቱ ፡ የክብር ፡ መዝገቦችን ፡ የሚይዘው ፡ ራሱ ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ።

(፪) ሚኒስትሩም ፡ አጠባበቃቸውንና ፡ አቀማመጣቸውን ፡ ያረጋግጣል ። የነዚህንም ፡ መዝገቦች ፡ ግልባጭ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፴፪ ። ቆንሲሎች ።**

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቆንሲሎች ፡ በባለጕዳዮቹ ፡ ጥያቄ ፡ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ጽሑፎችን ፡ አይመዘግቡም ።

(፪) ቆንሲሎቹ ፡ ራሳቸው ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቦችን ፡ ይይዛሉ ።

(፫) ቆንሲሎቹ ፡ አጠባበቃቸውንና ፡ አቀማመጣቸውን ፡ እያረጋገጡ ፡ ለባለ ጕዳዮች ፡ የነዚሁኑ ፡ መዝገቦች ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ ቅጂዎች ፡ ይሰጣሉ ።

**ቍ ፡ ፴፫ ። የመርከብ ፡ አዛዦች ።**

የኢትዮጵያ ፡ መርከብ፡ አዛዦች ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ፡ ሊጻፉ ፡ የሚገባቸውን ፡ በመርከባቸው ፡ ላይ ፡ የደረሱባቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቆንሲል ፡ በሚኖርበት ፡ የመጀመሪያ ፡ ወደብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ያስታውቃሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቦች ።

**ቍ ፡ ፴፬ ። የመዝገቦቹ ፡ ዝርዝር ።**

በያንዳንዱ ፡ ቀበሌና ፡ በያንዳንዱ ፡ ቆንሲላ ፡ የልደት ፡ አንድ ፡ መዝገብ ፡ የሞት ፡ አንድ ፡ መዝገብና ፡ የጋብቻ ፡ አንድ ፡ መዝገብ ፡ ይኖራል ።

**ቍ ፡ ፴፭ ። የመዝገቦቹ ፡ አሰጣጥ ።**

(፩) ጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ መዝገቦችን ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተቀብሎ ፡ ለሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ በነፃ ፡ ይሰጣቸዋል ።

(፪) መዝገቦችን ፡ እንዲይዙ ፡ የተደረጉት ፡ ሰዎች ፡ መዝገቡ ፡ ያልቃል ፡ ተብሎ ፡ ከሚገመተው ፡ ከ፤ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ መዝገብ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ መጠየቅ ፡ አለባቸው ፡፡

(፫) የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲከበር ፡ ያደርጋል ፡፡

**ቍ ፡ ፻፯ ፡፡ የመዝገቦቹን ፡ ከቦታቸው ፡ መዛዋወር ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡፡**

ከተቋቋሙበት ፡ ስፍራ ፡ ወደሌላ ፡ የማዛወሩ ፡ ጕዳይ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ካልተመለከተ ፡ ወይም ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ መዝገቦቹ ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ ካሉበት ፡ ስፍራ ፡ መዛዋወር ፡ የለባቸውም ፡፡

**ቍ ፡ ፻፰ ፡፡ የግድ ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ጽሑፎች ፡ (፩) የቀበሌው ፡ መዝገቦች ፡፡**

(፩) እያንዳንዱ ፡ መዝገብ ፡ ቀበሌውንና ፡ ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰፈሩን ፡ ወይም ፡ የሚመለከተውን ፡ የቀበሌውን ፡ ክፍል ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ቀበሌ ፡ የሚገኝበትን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ያመለክታል ፡፡

(፪) እንደዚሁም ፡ መዝገቡ ፡ የማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ይሆናል ፡፡

(፫) እነዚህ ፡ ማመልከቻዎች ፡ በመዝገቡ ፡ ልባስና ፡ ክፈፍ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ሆነው ፡ በያንዳንዱ ፡ የመዝገቡ ፡ ቅጠል ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፻፱ ፡፡ (፪) ሌሎች ፡ መዝገቦች ፡፡**

(፩) ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብን ፡ የሚመለከቱ ፡ መዝገቦች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በ፩ኛ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ጽሑፍ ፡ ሳይሆን ፡ የንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ መዝገቦች ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ የያዙ ፡ ይሆናሉ ፡፡

(፪) በቆንሲላዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ መዝገቦች ፡ በተቋቋሙበት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የቆንሲላ ፡ ምልክት ፡ የያዙ ፡ ይሆናሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፻፲ ፡፡ የመዝገቦቹ ፡ ዐይነት ፡ (ፎርም) ፡፡**

(፩) መዝገቦቹ ፡ በብዙ ፡ ገጾች ፡ የሚጀምሩ ፡ ሆነው ፡ እነዚህን ፡ መዝገቦች ፡ እንዲይዙ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ እንዲጻፍባቸውና ፡ በስማቸው ፡ አቅጣጫ ፡ የነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ፡ ያሉባቸው ፡ ይሆናሉ ፡፡

(፪) ቀጥሎም ፡ መዝገቦቹ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ያላቸው ፤ ብዙ ፡ ቅጠሎች ፡ የያዙና ፡ እያንዳንዱም ፡ ቅጠል ፡ ለአንዳንድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያገለግል ፡ መሆን ፡ አለበት ፡፡

(፫) እንዲሁም ፡ የመዝገቦቹ ፡ ጽሑፎች ፡ የሚመለከቱዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ ማውጫ ፡ ለመመዝገብ ፡ የተመየጡ ፡ ገጾች ፡ በመጨረሻው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ይኖራቸዋል ፡፡

**ቍ ፡ ፹ ። የመዝገቦቹ ፡ ቅጠሎች ።**

(፩) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገቦች ፡ ቅጠሎች ፡ ከተያያዙበት ፡ ቀሪ ፡ ጋራ ፡ ትክ ክል ፡ የሆኑ ፡ ጽሑፎችን ፡ የያዙ ፡ በራሪዎች ፡ ያሉባቸው ፡ ናቸው ።

(፪) የመወለድና ፡ የጋብቻ ፡ መዝገቦች ፡ ሦስት ፡ በራሪዎች ፤ የሙታን ፡ መዝገቦች ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ በራሪዎች ፡ ብቻ ፡ ያሏቸው ፡ ናቸው ።

(፫) የቅጠሎቹ ፡ ጀርባ ፡ በእጅ ፡ እንዲጻፉ ፡ በሕግ ፡ ለተመለከቱት ፡ ግኚ ፡ ጽሑ ፎች ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፹፩ ። ሦስተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ።**

(፩) ከቀሪው ፡ በጣም ፡ የራቀው ፡ ሦስተኛ ፡ ቍጥር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ በራሪ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከቀሪው ፡ የሚለያይ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ በራሪ ፡ ስለ ፡ መወለድ ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለልጁ ፡ አሳዳሪ ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለባል ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ አማካይነት ፡ ይሰጣል ።

(፫) ባለጕዳዩም ፡ በራሪውን ፡ ያኖራል ።

**ቍ ፡ ፹፪ ። ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ።**

(፩) መዝገቡ ፡ በአለቀ ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ በራሪዎች ፡ ከቀሪው ፡ ተለይተው ፡ ተሰብስበው ፡ አንድነት ፡ ተያይዘው ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ባለው ፡ የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ በተወሰነው ፤ መጀመሪያዎቹ ፡ በራሪዎች ፡ ከተቀመጡበት ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይቀ መጣሉ ።

(፪) በጽሕፈት ፡ ሚኒስትርና ፡ በቆንሲሎቹ ፡ የሚገኘው ፡ መዝገብ ፡ ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ የሆኑት ፡ በራሪዎች ፡ ተቀማጭ ፡ እንዲ ፡ ሆኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይላካሉ ።

(፫) ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ የሆኑት ፡ በራሪዎች ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ በተመደበው ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ እንዲጠረዙ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፹፫ ። አንደኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ።**

ከቀሪው ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ አንደኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪዎች ፡ ከመዝገቡ ፡ ቀሪ ፡ ጋራ ፡ ተያይዘው ፡ መዝገቦቹ ፡ በነበሩበት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ በተወሰነው ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይኖራሉ ።

**ቍ ፡ ፹፬ ። ያልተሠራባቸው ፡ ቅጠሎች ፡ አለመኖር ።**

(፩) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ከማዘጋጀቱ ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ በመጨረሻ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኝበትን ፡ ቅጠል ፡ [illegible] ተቀ ቍጥር ፡ መመርመር ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ የመጨረሻ ፡ ጽሑፍ ፡ ከተደረገበት ፡ ቅጠል ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ ጽሑፍን ፡ ይመዘግባል ።

(፫) በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ያልተሠራበትን ፡ ቅጠል ፡ እን ዲተው ፡ አልተፈቀደለትም ።

<u>ቍ ፡ ፻፳፭ ። በስሕተት ፡ ያልተሠራበት ፡ ቅጠል ።</u>

(፩) ከአንድ ፡ ስሕተት ፡ የተነሣ ፡ አንዱ ፡ ቅጠል ፡ ሳይሠራበት ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ይህን ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ተመለከተ ፡ የተባለውን ፡ ቅጠል ፡ ይሠርዘዋል ።

(፪) ባልተሠራበትም ፡ በራሪ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መስቀልኛ ፡ የሆነ ፡ ሁለት ፡ መሥ መር ፡ አድርጎ ፡ በበራሪው ፡ ላይ ፡ ሳይሠራበት ፡ በስሕተት ፡ የቀረ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ይጽፍበታል ።

(፫) ያልተሠራበት ፡ ቅጠል ፡ በምንም ፡ አኳኋን ፡ ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ አገልጋይ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፻፳፮ ። ማውጫ ።</u>

(፩) አንድ ፡ መዝገብ ፡ በአለቀ ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በመዝገቡ ፡ ማስ ቂያ ፡ ገጾች ፡ ውስጥ ፡ የመዝገቡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ መሠረት ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ (ሊስት) ፡ ይመዘግባል ።

(፪) ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪዎችን ፡ አንድነት ፡ አያይዞ ፡ አስሮ ፡ እርሱ ፡ ካስ ናዳው ፡ የማውጫ ፡ ቅጂ ፡ ጋራ ፡ አድርጎ ፡ በደንቦቹ ፡ ወደ ፡ ተመለከተው ፡ ስፍራ ፡ ይህን ፡ የተያያዘ ፡ እስር ፡ ይልካል ።

<u>ቍ ፡ ፻፳፯ ። ስለ ፡ መዝገቦች ፡ መጥፋት ።</u>

(፩) በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ የተቀመጠ ፡ መዝገብ ፡ ፣ጠፉ ፡ ወይም ፡ የወደመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀበሌው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በሚያመለክተው ፡ በመዝገቡ ፡ ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪዎች ፡ ረዳትነት ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይቋቋማል ።

(፪) የአንድ ፡ መዝገብ ፡ ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪዎች ፡ የጠፉ ፡ ወይም ፡ የወደሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጠፉት ፡ ወይም ፡ የወደሙት ፡ በራሪዎች ፡ እስተማጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በሚያመለክተው ፡ በቀበሌው ፡ በተቀመጡት ፡ በራሪዎች ፡ ረዳትነት ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይቋቋማሉ ።

(፫) የጠፉት ፡ መዝገቦች ፡ በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ያሉት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ያሉት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ ኀይሉ ፡ ቃላት ፡ ውሳኔዎች ፡ በተመ ሳሳይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፻፳፰ ። የሚሠራባቸው ፡ መዝገቦች ፡ ስለ ፡ መጥፋታቸው ።</u>

(፩) ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪዎች ፡ የሆኑት ፡ ሳይቈረጡ ፡ የሚሠራበት ፡ አንድ ፡ መዝገብ ፡

የጠፋ ፡ ወይም ፡ የወደመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወዲያውኑ ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ያስታውቃል ።

(፪) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትም ፡ መዝገቡን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማቋቋም ፡ አስፈላጊውን ፡ ያደርጋል ።

(፫) የአንድ ፡ መዝገብ ፡ አንደኛና ፡ ሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪዎች ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ሁለቱም ፡ ቢጠፉ ፡ ወይም ፡ ቢወድሙ ፡ እንደዚሁ ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፹፱ ። የመዝገቡን ፡ አያያዝ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ።

(፩) የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በቀበሌዎቹ ፡ ውስጥ ፡ የክብር ፡ መዝገቦችን ፡ መልካም ፡ አያያዝ ፡ ይቈጣጠራል ።

(፪) የምርመራውን ፡ ሥራ ፡ አደራጅቶ ፡ ባገኛቸው ፡ በወንጀል ፡ ሥራዎች ፡ ለማስቀጣት ፡ ራሱ ፡ ይከታተላል ።

(፫) በቆንሲላዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙ ፡ መዝገቦችም ፡ እነዚሁኑ ፡ የመሰሉ ፡ ተግባሮች ፡ የሚፈጽመው ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ በጠቅላላው ።

ቍ ፡ ፺ ። የሚጻፉ ፡ ቃሎች ።

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ የቀሩትን ፡ ባዶ ፡ ቦታዎች ፡ በመሙላት ፡ ይጻፉሉ ።

(፪) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የተጻፉበት ፡ ቀን ፤ ወርና ፡ ዓመት ፤ የተቀበላቸው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊርማ ፡ ይኖርባቸዋል ።

ቍ ፡ ፺፩ ። የተከለከሉ ፡ ጽሑፎች ።

በሕጉ ፡ ከተመለከቱት ፡ ጽሑፎች ፡ በቀር ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፺፪ ። ያልታወቁ ፡ ወይም ፡ ያልተረጋገጡ ፡ መረጃዎች ።

(፩) በአንድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የቀረው ፡ ባዶው ፡ ቦታ ፡ እርግጠኛ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ መረጃ ፡ ባለማግኘት ፡ መዝገቦችን ፡ በሚይዘው ፡ ሰው ፡ ሊሞላ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይኸው ፡ ሰው ፡ "ያልታወቀ ፡" የሚል ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ በማግባት ፡ ባዶውን ፡ ቦታ ፡ ይሞላል ።

(፪) የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ የሚሰጠውን ፡ መልስ ፡ ያወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ በተገባው ፡ ቦታ ፡ "ምናልባት ፡" የሚል ፡ ቃል ፡ በመጨመር ፡ ይጽፋል ።

BACK



## ቍ ፡ ፺፫ ። የቃሎች ፡ ማሳጠር ፡ አለመኖር ።

በጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ የሚጠየቁት ፡ ማመልከቻዎች ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አኳኋንና ፡ ምንም ፡ ማሳጠር ፡ ሳይደረግ ፡ የሚጻፉ ፡ ይሆናሉ ።

## ቍ ፡ ፺፬ ። ሥርዝና ፡ እመጫት ፡ አለመኖር ።

የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ ምንም ፡ ስርዝ ፡ ወይም ፡ እመጫት ፤ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ቃል ፡ ሊጻፍባቸው ፡ አይገባም ።

## ቍ ፡ ፺፭ ፡ ፊርማ ።

በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ እንዲፈርሙ ፡ ከተጠየቁት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ለመፈረም ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ያላወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ በፊርማው ፡ ፈንታ ፡ የጣቱን ፡ አሻራ ፡ ምልክት ፡ ያደርጋል ።

## ቍ ፡ ፺፮ ። ያልተሠራባቸው ፡ ቅጠሎች ።

(፩) በሥርዝ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መሠራት ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ያልተሠራበት ፡ በራሪ ፡ ቅጠል ፡ በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ መስቀልኛ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሥርዞች ፡ ይደረጉበታል ።

(፪) በያንዳንዱ ፡ የጽሑፍ ፡ በራሪ ፡ ላይም ፡ ያልተሠራበት ፡ ቅጠል ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ያደርግበታል ።

(፫) የቅጠሉ ፡ ሦስተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይቀደዳል ።

## ቍ ፡ ፺፯ ። የጽሑፎች ፡ አስረጂነት ፡ ኀይል ።

(፩) ለያዙአቸው ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ደንበኛ ፡ ሆነው ፡ የተመዘገቡ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ የሚታመኑ ፡ ናቸው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ የዳኞችን ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፺፰ ። በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ያልተጻፉ ፡ ጽሑፎች ።

(፩) በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመዘገቡ ፡ ጽሑፎች ፤ በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተጻፉት ፡ ጽሑፎች ፡ ያለ ፡ አስረጂነት ፡ የላቸውም ።

(፪) እንደ ፡ ተራ ፡ ማስረጃዎች ፡ ብቻ ፡ ይቈጠራሉ ።

BACK



## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
## የመወለድ ፡ ጽሑፎች ።

**ቍ ፡ ፺፱ ። የጽሑፉ ፡ ቃል ።**

የመወለድ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያመለክተው ።

(ሀ) የተወለደበትን ፡ ቀን ፡ ወርና ፡ ዓመት ።

(ለ) የልጅን ፡ ፆታ ።

(ሐ) የተሰጡትን ፡ የግል ፡ ስሞች ።

(መ) የአባቱንና ፡ የእናቱን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የግል ፡ ስም ፤ የተወለዱበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤

(ሠ) ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያመልካቹን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የግል ፡ ስም ፤ የተወለደበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻ ። የጽሑፍ ፡ አስፈላጊነት ።**

ልጁ ፡ አርባ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ከኖረና ፤ የመወለድ ፡ ጽሑፍን ፡ ለማስመዝገብ ፡ ከተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ማለቅ ፡ በፊት ፡ ቢሞትም ፡ እንኳ ፤ መወለዱን ፡ ማስታወቅና ፡ የመወለዱን ፡ ጽሑፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈላጊዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፩ ። መወለድን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) የልጅ ፡ መወለድ ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ይህም ፡ መግለጫ ፡ የልጁ ፡ አባት ፤ አባቱ ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፡ የልጁ ፡ እናት ፡ ወይም ፡ የልጁ ፡ አሳዳጊ ፡ ( ሞግዚት ) ፡ እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ ልጁን ፡ አግኝቶ ፡ ያነሣው ፡ ሰው ፡ ሊገልጽ ፡ ይገባዋል ።

(፫) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹሙ ፡ የልጁን ፡ መወለድ ፡ ካወቀ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የልጁን ፡ መወለድ ፡ ለመመዝገብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፪ ። የልጁ ፡ የግል ፡ ስም ።**

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ መወለዱን ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ከመመዝገቡ ፡ በፊት ፡ ለልጁ ፡ የሚሰጠውን ፡ የግል ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ስሞች ፡ ዘመዶቹን ፤ ዘመዶችም ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጁን ፡ አሳዳሪ ፡ ይጠይቃል ።

(፪) መልስ ፡ ያልተሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የቀረቡት ፡ የግል ፡ ስሞች ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊቀበሏቸው ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክብር ፡ መዝገቡ ፡ ሹም ፡ ራሱ ፡ የልጁን ፡ የግል ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ስሞች ፡ ይመርጣል ።

**ቍ ፡ ፻፫ ። ወድቀው ፡ ስለሚገኙ ፡ ልጆች ።**

(፩) ወድቆ ፡ ለሚገኝ ፡ ማን ፡ መሆኑ ፡ ላልታወቀ ፡ ለአራስ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ የመወለዱ ፡ ጽሑፍ ፡ መደራጀት ፡ አለበት ።

BACK



(፪) ልጁ ፡ የተገኘበትን ፡ ቀንና ፡ ስፍራ ፤ ይኖረዋል ፡ የሚባለውን ፡ ዕድሜ ፤ ያታውን ፤ የተሰጡትን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስሞች ፡ በዝርዝር ፡ የሚያሳይ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ይደራጇል ።

(፫) ስለ ፡ ልጁ ፡ መወለድ ፡ በተጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ፕሮሴቬርባሉ ፡ የሚመራ ፡ ምልክት ፡ ይጠቀሳል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።
## የመሞት ፡ ጽሑፎች ።

**ቍ ፡ ፻፩ ። የጽሑፉ ፡ ቃል ።**

የመሞት ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያመለክተው ።

(ሀ) የሞተበትን ፡ ቀን ፡ ወርና ፡ ዓመት ።

(ለ) የሞተውን ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የግል ፡ ስም ፤ የተወለደበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ።

(ሐ) የአባቱን ፤ የእናቱን ፤ የቤተ ፡ ዘመድና፡የግል ፡ ስም ፡ የተወለደበትን ፡ አገርና ፡ ቀን ።

(መ) በሕይወት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስም ፤ የተወለደበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤ ጋብቻው ፡ የተደረገበትን ፡ ቀን ።

(ሠ) ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሞተውን ፡ ያስታወቀውን ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድና ፡ ስም ፡ የግል ፡ ስም ፤ የተወለደበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፪ ። የጽሑፍ ፡ አስፈላጊነት ።**

የሞተው ፡ ሰው ፡ የመወለድ ፡ ጽሑፍ ፡ ሊጻፍለት ፡ ይገባው፡የነበረ ፡ ሲሆን፡ መሞቱን ፡ ማስታወቅና ፡ የመሞቱንም ፡ ጽሑፍ፡ ማደራጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው።

**ቍ ፡ ፻፫ ። የሞተውን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሞቱን ፡ የማስታወቁ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(፪) እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማስታወቁ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ይኖሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዶቹ ፡ እነዚሀ ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቅርብ ፡ ጎረቤቶቹ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፬ ። በሌላ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መሞት ።**

ሟቹ ፡ ከመኖሪያ ፡ ስፍራው ፡ ውጭ፡ የሞተ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የማስታወቁ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሰውዬው ፡ የሞተበት ፡ ቤት ፡ ባለቤት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፭ ። ሆፒታሎች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፤ ሆቴሎችና ፡ ወህኒ ፡ ቤቶች ።**

(፩) የሞተው ፡ በአንድ ፡ ሆፒታል ፤ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ወይም ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሞቱን ፡ መግለጽ ፡ ያለበት ፡ ከዚሀ ፡ በላይ ፡ የተባለው ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ መሪ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ነው ።

BACK



(፪) በሠሩት ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ መሠረት ፡ የተገደሉትን ፡ ሰዎች ፡ ማስታወቅ ፡ ያለበት ፡ የቀፈረደበት ፡ ሰው ፡ በሚገደልበት ፡ ጊዜ ፡ የታሰረበት ፡ የወህኒ ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፱ ። በሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ወታደሮች ።**

ወታደሩ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ለዕረፍት ፡ በተፈቀደለት ፡ የስንብት ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ ክፍለ ፡ ጦሩ ፡ ከሰፈረበት ፡ ውጭ ፡ የሞተ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ በሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ያሉ፡ ወታደሮችን ፡ መሞት ፡ መግለጽ፡ ያለበት ፡ ክፍሉን ፡ የሚያዘው ፡ ሹም ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፲ ። ሬሳ ፡ ስለ ፡ ማግኘት ።**

(፩) የአንድ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ ከአንድ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ ማስታወቅ ፡ ያለበት ፡ ሬሳውን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) የሞተው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያልታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሬሳው ፡ የተገኘበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤ ሟቹ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለውን ፡ ዕድሜ ፡ ያታውንና ፡ በግምት ፡ የሞተበትን ፡ ቀን ፡ የሚዘረዝር ፡ ፕሮሴርቬባል ፡ ይደራጃል ።

(፫) ስለ ፡ መሞቱ ፡ የሚደረገው ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ ፕሮሴቬርባሉ ፡ የሚመራ ፡ ምልክት ፡ ይደረግበታል ።

**ቍ ፡ ፻፲፩ ። ያልተገኘ ፡ ሬሳ ፡ (፩) መሞቱን ፡ የሚያስታውቅ ፡ ፍርድ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የመጥፋቱ ፡ ምክንያት፡ መሞቱን ፡ የሚያረጋግጥ፡ ሆኖ ፡ ሬሳው፡ ያልተገኘ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ የሚያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) መሞቱን ፡ የሚያስታውቀው ፡ ፍርድ ፡ እንደ፡መሞት ፡ ጽሑፍ ፡ ይቈጠራል።

**ቍ ፡ ፻፲፪ ። (፪) ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ።**

(፩) ባለሥልጣን ፡ የሚሆኑት ፡ ዳኞች ፤ መሞቱ ፡ እንዲረጋገጥለት ፡ ጠያቂው ፡ የጠየቀለት ፡ የሟች ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ በሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ የሚገኙት ፡ ናቸው።

(፪) እነዚህም ፡ ዳኞች ፡ ሞትን ፡ ባስከተለው ፡ አጋጣሚ ፡ ቦታ ፡ ላሉ ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ላሉ ፡ ዳኞች፡ መብት ፡ ሥልጣናቸውን ፡ መተው ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚሁ ፡ የሆነው ፡ የሥልጣን ፡ ማስተላለፍ ፤ መብቱ ፡ የተላለፈላቸውን ፡ ዳኞች ፡ ያስገድዳል ።

**ቍ ፡ ፻፲፫ ። አደጋዎች ። (፩) የኅብረት ፡ ፍርድ ።**

(፩) መሞቱ ፡ ባንድ ፡ አደጋ ፡ ነገር ፤ እንደ ፡ መስጠም ፤ እንደ ፡ አየር ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ መናወጥ ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ መንሸራተት ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሞቱ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚያሳምን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡የነዚህን ፡ ሰዎች ፡ መሞት ፡ በኅብረት ፡ ፍርድ ፡ ለመገለጽ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ አደጋው ፡ በደረሰበት ፡ ቦታ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

BACK



(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ በራሪ ፡ ሲጠፋ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ መርከቡ ፡ ወይም ፡ በራሪው ፡ በሚነሣበትና ፡ በሚያርፍበት ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፲፬ ። (፪) እያንዳንዶቹ ፡ ቅጂዎች ።**

(፩) ከኀብረቱ፡ፍርድ ፡ የያንዳንዶቹን ፡ ቅጂዎች ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ ሊወስዱ ፡ ይችላሉ።

(፪) መሞቱን፡የሚያስታውቀው ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ መሞት ፡ ጽሑፍ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፻፲፭ ። የሞተበት ፡ ቀን ።**

(፩) መሞቱን፡የሚያስታውቀውን ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጡ ፡ ዳኞች ፡ ምክንያቱን ፡ በመከታተል ፡ ያደረጉትን ፡ ግምት ፡ በመመልከት ፡ በፍርዳቸው ፡ ውስጥ ፡ የሞተበትን ፡ ወይም ፡ የሞቱበትን ፡ ቀን ፡ በግምት ፡ የወሰኑትን ፡ ቀን ፡ ይገልጻሉ ።

(፪) የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በተንኰል ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ እንደ ዚህ ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ ሊለወጥ ፡ አይቻልም ።

(፫) ለማስለወጥም ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፤ ፍርዱ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀባይነት ፡ ማግኘቱ ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ፻፲፮ ። መሞትን ፡ የሚያስታውቀው ፡ ፍርድ ፡ መሻር ፤ መሠረዝ ።**

መሞቱ ፡ በፍርድ ፡ የተገለጸው ፡ ሰው ፤ ፍርዱ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ የመጣ ፡ እንደ ሆነ ፤ በራሱ ፡ ወይም ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጠያቂነት ፡ ፍርዱን፡የሰጡት ፡ ዳኞች ፡ ፍርዱን ፡ ይሽራሉ ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።
## የጋብቻ ፡ ጽሑፍ ።

**ቍ ፡ ፻፲፯ ። የጋብቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ቃል ።**

የጋብቻው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያመለክተው ።

(ሀ) የባልና ፡ የሚስትን ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የግል፡ስም ፤ የተወለዱበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤

(ለ) የባልና ፡ የሚስትን ፡ ምስክሮች ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የግል ፡ ስም ፡ የተወለዱበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤

(ሐ) በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት፡ ጋብቻው ፡ የተከበረ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻው ፡ የተከበረበትን ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፲፰ ። የጽሑፉ ፡ አስፈላጊነት ።**

ጋብቻው ፡ የተከበረው ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ ፎርም ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ የጋብቻ ፡ ማስታወቂያና ፡ የጋብቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ ማደራጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፲፱ ። ጋብቻውን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታ ።

(፩) ጋብቻውን ፡ የማስታወቁ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ጋብቻውን ፡ ያከበረው ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተጋቢዎቹ ፡ ይኸው ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፻፳ ። በሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ጽሑፍን ፡ ስለ ፡ ማደራጀት ።

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ጋብቻ ፡ መደረጉን ፡ ከዐወቀ ፤ የጋብቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ በሥልጣኑ ፡ ብቻ ፡ ያደራጃል ።

(፪) ይህ ፡ ሲሆን ፡ የጋብቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማስፈረም ፡ ባለጕዳዮቹን ፡ ይጠራል ።

ክፍል ፡ ፬ ።

የክብር ፡ መዝገብን ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ ማቃናት ።

ቍ ፡ ፻፳፩ ። መሠረቱ ።

ዳኞች ፡ በሚሰጡት ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለማቃናት ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፻፳፪ ። ስለ ፡ ማቃናት ፡ ጥያቄ ።

የክብር ፡ መዝገብን ፡ ጽሑፍ ፡ የማቃናት፡ ጥያቄን ፤ ዐቃቤ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፤ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ለዳኞች ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፳፫ ። አንድ ፡ ተጨማሪ ፡ የግል ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ማግባት ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ጋብቻን ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ጋብቻ ፡ በሚከተለው ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ተጨማሪ ፡ የግል ፡ ስም ፡ ለመጨመር ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የትእዛዝ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፳፬ ። ስለ፡አጻጻፍ ፡ ስሕተት ።

ጥያቄው ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ አጻጻፍ ፡ ውስጥ ፡ የተደረገን ፡ ስሕተት ፡ ለማቃናት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በዚሁ ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ የትእዛዝ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፳፭ ። ሌሎች ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ አኳኋን ፡ ጊዜ ፡ በጥያቄው ፡ ላይ ፡ ዳኞች ፡ የሚሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይሆናል ።

(፪) ዳኞች ፡ ከመደንገጋቸው ፡ በፊት ፡ ጽሑፉ ፡ የሚመለከታቸው ፡ሰዎች ፡ ወይም፡ ሰው ፡ ባለጕዳዮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲናገሩ ፡ ይፈቅዱላቸዋል ።

ቍ ፡ ፻፳፮ ። ጽሑፉ ፡ የሚቃናበት ፡ ዐይነት ።

(፩) እንዲቃኑ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠባቸው ፡ ቃሎች ፡ እንደሚነበቡ ፡ ሆነው ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ይሠረዛሉ ።

(፪) በተሠረዙት ፡ ምትክ ፡ የሚገቡ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ሆነው ፡ የሚገቡ ፡ ቃሎች፤ጽሑፉ ፡ እንዲቃና ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ያዘዘውን ፡ ፍርድ ፡ ከሚጠቅስ ፡ ማስገንዘቢያ ፡ ጋራ ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ።

(፫) እነዚህም ፡ መለዋወጫዎች ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፤ በተቃናው ፡ ጽሑፍ ፡ በራሪ ፡ ወረቀቶች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይደረጋሉ ።

ቊ ፡ ፻፳፯ ። አዲስ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።

(፩) የሚቃናው ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሠረዝ ፡ የሚል ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ ጽሑፉ ፡ እንዲሠረዝና ፡ በተባለው ፡ ጽሑፍ ፡ ፈንታ ፡ አዲስ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲደራጅ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) በዚህ፡ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ የፈተኛው ፡ ጽሑፍ ፡ በራሪ ፡ ወረቀት ፤ በመስቀልኛ፡ ቅርጽ ፡ ሆነው ፡ ከላይኛው ፡ ማዕዘን ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ማዕዘን ፡ መሐል ፡ ለመ ሐል ፡ በሚሸጋገሩት ፡ ሁለት ፡ መሥመሮች ፡ በመዝገቦቹ ፡ መካከል ፡ ተሰርዞ ፡ በቀድሞው ፡ ጽሑፍ ፡ ምትክ ፡ በገባው ፡ በአዲሱ ፡ ጽሑፍ ፡ በያንዳንዱ ፡ በራሪ ፡ ወረቀት ፡ ላይም ፡ የመምሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ይደረግበታል ።

(፫) በአዲስ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንዲጻፍ ፡ ወደ ፡ አደረገው ፡ ፍርድ ፡ የሚመራ ፡ ምል ክት ፡ ይደረግበታል ።

ቊ ፡ ፻፳፰ ። የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሥልጣን ።

የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲቃና፡ ትእዛዝን ፡ የሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ፡ በፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ የተቃናው ፡ የጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ በነበረው ፡ ሁኔታ ፡ በማንኛውም ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ክፍል ፡ ፭ ።

## የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ ግልባጮችና ፡ ቅጂዎች።

ቊ ፡ ፻፳፱ ። የመወለድ ፡ ጽሑፍ ።

(፩) በቀበሌዎች፡ወይም፡በቆንሲላዎች ፤ የክብር ፡ መዝገብ ፡ አስቀማጮች ፡ የሆኑ፡ ሠራተኞች ፡ ስለ ፡ ሕፃኑ ፡ መወለድ ፡ ከተደረገው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚመነጩትን ፡ የክብሩ ፡ መዝገብ ፡ የተዘጋጀበትን ፡ ጊዜ ፤ ሕፃኑ ፡ የተወለደበትን ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፤ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ መሆኑን ፤ የሕፃኑን ፡ አባት ፡ የቤተ፡ ዘመድና ፡ የግል ፡ ስም ፡ ለሚጠይቅ ፡ ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሌላ፡ሐተታ ፡ ሳይጨ ምሩ ፡ ቅጂዎቹን ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳሉ ።

(፪) ለልጁ፡ ወራሾች፡ ወይም ፡ ለመንግሥት፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ለፈቀዱለት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የመወለዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጮች ፡ ሊሰጡ ፡ አይ ችሉም ።

BACK



**ቍ ፡ ፺፩ ፡ የመሞት ፡ ጽሑፍ ።**

በቀበሌዎች ፡ ወይም ፡ በቆንሲላዎች ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ አስቀማጭ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፤ የመሞትን ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ ለሚጠይቅ ፡ ለማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፺፪ ። የጋብቻ ፡ ጽሑፍ ።**

እንደዚሁም ፤ የጋብቻን ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ ለሚጠይቅ ፡ ለማናቸውም ፡ ሰው ፤ ግልባጩን ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፺፫ ። ንጉሣዊ ፡ ቤተ፡ ዘመድን፡ ስለሚመለከቱት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች።**

ዳኞች፡ ሲጠይቁት ፡ ንጉሣዊ፡ ቤተ ፡ ዘመድን፡ በሚመለከቱ፡ መዝገቦች ፡ ውስጥ፡ ያሉትን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎችን ፡ ግልባጭ ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትሩ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፺፬ ። የሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ፡ ወረቀቶች ፡ አስቀማጮች ።**

ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጣሙ ፡ ጊዜ ፡ የሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ፡ ወረቀቶች ፡ አስቀማጮች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተነገሩት ፡ ግዴታዎች ፡ ዐይነት ፡ ይገደዳሉ ።

(ሀ) የክብር፡መዝገብ ፡ ጽሑፍን ፡ የያዘ ፡ የቀበሌው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ የወደመ ፡ ወይም ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) መዝገቡ፡በቀበሌው፡ተጠብቆ ፡ የተቀመጠ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በዚህ ፡ በተባለው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሁለተኛ ፡ ቍጥር ፡ በራሪ፡ወረቀቶች ፡ በተያያዙበት ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ የጐደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በቀበሌው፡ተጠብቆ ፡ በተቀመጠው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ፡ በሁለተኛው ፡ ቍጥር ፡ በራሪ ፡ ወረቀቶች ፡ ከተያያዙት ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ጽሑፉ፡የተደራጀው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቆንስላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) ይህ፡የተባለው ፡ ግዴታ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፤ በዳኞች ፡ የታዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፺፭ ። የተቃና ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ።**

(፩) በሕግ ፡ መሠረት ፤ አንድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ የተቃና ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለባለጕዳዮቹ፡ የሚሰጠው ፡ ቅጂ ፡ ወይም ፡ ግልባጭ ፡ ይህንኑ ፡ መቃናት ፡ በመከተል ፡ ነው ።

BACK



(፪) በቅጂው፡ ወይም ፡ በግልባጩ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ ከጽሑፉ ፡ መቃናት፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ማመልከት ፡ የለበትም ።

(፫) ጽሑፉን፡ እንዳለ ፡ የሚያሳዩና ፡ በጽሑፉ ፡ ሊደረግለት ፡ የተቻለውን ፡ መቃ ናት ፡ የሚገልጹ ፡ ትክክል ፡ የሆኑ ፡ ግልባጮች ፡ የሚሰጡት ፤ ዳኞቹ ፡ ራሳቸው፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፳ ። ፎርሙና ፡ ወጪው ፡ ገንዘብ ።**

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ ቅጂዎች ፡ ወይም ፡ ግልባጮች ፡ ታትመው ፡ በጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ አማካይነት ፡ ለቀበሌው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በተሰ ጡት ፡ ሞዴሎች ፡ ላይ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ይዘጋጃሉ ።

(፪) እነዚህን ፡ ቅጂዎች፡ወይም ፡ ግልባጮች ፡ እነርሱን ፡ መስጠት ፡ ያለበት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፈርሞባቸው ፡ እርሱ ፡ የሚሠራበት ፡መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ማኅተም ፡ ይታተምባቸዋል ።

(፫) ቅጂዎቹ፡ሲሰጡ ፤ ተቀባዮቻቸው ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብርና ፤ እንዲሁም ፡ ኮፒው ፡ ወይም ፡ ቅጂው ፡ በፖስታ ፡ የሚላክ ፡ ሲሆን ፤ የፖስታውን ፡ ዋጋ ፡ ይከ ፍላሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፳፩ ። የጽሑፎች ፡ አስረጂነት ፡ ኀይል ።**

የክብርን ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፎች ፡ አስቀማጮች ፡ የሚሰጧቸው ፡ ቅጂዎች ፡ ወይም ፡ ግልባጮች ፡ በመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ጽሑፎች ፡ የሚያስረዱትን ፡ ያህል ፡ ያስ ረጂነት ፡ ኀይል ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፱፻፳፪ ። ማስታያየት ።**

(፩) ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ ቅጂዎቹ ፡ ወይም ፡ ግልባጮቹ ፡ ከዋናው ፡ ጋራ ፡ እንዲተያዩ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፤ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ ፎቶግራፍ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለማ ዘዝ ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍን ፡ ደንብ ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያስከትለው ፡ ኪሣራ ።

**ቍ ፡ ፱፻፳፫ ። በሠራተኞቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ያለባቸው ፡ ኀላፊነት ።**

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ደንቦቹ ፡ አፈጻጸም ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ መዝገቦች ፡ አያያዝ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አጠባበቃ ቸው ፡ በታዘዙት ፡ ሠራተኞች ፡ በኩል ፡ የተደረገ ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሲኖር ፡ በዚህ፡ በተባለው ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ምክንያት ፡ጉዳት ፡ ለደረሰባቸው ፡ ሰዎች፡ ሁሉ ፡ ኀላፊነትን ፡ ያመጣባቸዋል ።

BACK



ቍ ፡ ፻፴፱ ። ጽሑፍን ፡ ለመጻፍ ፡ እንቢ ፡ ማለት ።

(፩) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ መዝገቦቹን ፡ ለመያዝ ፡ የተሾመው ፡ ሠራተኛ ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ የሚገባውን ፡ በተሰጠው ፡ ማስታወቂያ ፡ መሠረት ፡ በእንቢተኛነት ፡ አላገባም፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለጕዳዮቹ ፡ እንቢ ፡ አለን ፡ ሲሉ፡ ለዳኞች ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፤ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ እንዲጻፍ ፡ የሚያደርገውን ፡ ምክንያት ፡ የሚመለከቱትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርቡበት ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፤ የመዝገቦቹ ፡ አስቀማጭ ፡ (መዝገብ ፡ ያዥ) ፡ የመዝገቦቹን ፡ ጽሑፍ ፡ ቅጂ ፡ ወይም ፡ ግልባጭ ፡ አልሰጥም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊከሰስ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፵ ። የምስክሮቹና ፡ ያመልካቾቹ ፡ ኀላፊነት ።

(፩) በክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ ነገር ፤ አመልካቾቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ ለሚያረጋግጡዋቸውና ፡ ለሚያግፋዋቸው ፡ ነገሮች ፡ እርግጠኛነት ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ያስታወቁት ፡ ወይም ፡ ምስክር ፡ የሆኑበት ፡ ነገር ፡ ትክክለኛ ፡ ሆኖ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ምክንያት ፡ ጉዳት ፡ ለሚደርስባቸው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃሉ ።

ቍ ፡ ፻፵፩ ። የወንጀል ፡ ኀላፊነት ። (፩) በጽሑፍ ፡ ስላለማግባት ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት፡ቅጣቶች ፡ የሚያገኙዋቸው ፡ ሰዎች፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ግዴታ ፡ እያለበት ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳያዘጋጅ ፡ የቀረ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፤

(ለ) በክብር ፡ መዝገብ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሆነውን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ እያለበት ፡ በሕግ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፤

(ሐ) ጽሕፈቱን ፡ እንዲያገባ ፡ የተላለፉለት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በደረሱለት ፡ ጊዜ ፤ ወዲያውኑ ፡ በፍጥነት ፡ ጽሑፉን ፡ ያላዘጋጀ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፤

ቍ ፡ ፻፵፪ ። (፪) ያለ፡ማስታወቅ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ የሚወድቁባቸው ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ የሆነውን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ እያለባቸው ፡ በሕግ ፡ በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያላስታወቁና ፡ ይህ ፡ አለማስታወቃቸው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ መዝገብ ፡ እንዳይገባ ፡ መሆንን ፡ ያስከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ሳያስታውቁ ፡ የቀሩ ፡ ሰዎች ፤

(ለ) የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍን ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ ማግባት ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲሰጡ ፤ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ጠይቋቸው ፡ እነሱን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ሳይሰጡ ፡ የቀሩ ፡ ሰዎች ፡፡

ቍ ፡ ፻፵፫ ፡፡ (፫) ትክክል ፡ ያልሆኑ ፡ ማስታወቂያዎች ፡፡

(፩) በክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ መዝገብ ፡ ለማስገባት ፤ ለክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ትክክል ፡ አለመሆናቸውን ፡ እያወቁ ፡ ትክክል ፡ ያልሆኑትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የሚሰጡ ፡ ሰዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ፡፡

(፪) እንደዚሁም ፡ ሐሰት ፡ መሆናቸውን ፡ እያወቁ ፤ እነዚህን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በሚደግፉ ፡ ምስክሮች ፡ ላይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ፡፡

(፫) እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፤ ያልተረጋገጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ዐውቆ ፡ ሳለ ፤ እነዚህን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ እንዲታመኑ ፡ አድርጎ ፡ የክብር ፡ መዝገብን ፡ ጽሑፍ ፡ መዝገብ ፡ በሚያደራጅ ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነውን ፡ ቅጂ ፡ ወይም ፡ ግልባጭ ፡ በሚሰጥ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፤ ወይም ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ፡፡

ቍ ፡ ፻፵፬ ፡፡ (፬) የመዝገብ ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡፡

የክብር ፡ መዝገብን ፡ የሚያጠፋ ፡ ወይም ፡ የሚያበላሽ ፡ ሰው ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ፡፡

ቍ ፡ ፻፵፭ ፡፡ (፭) በተበላሸው ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መገልገል ፡፡

በተንኰል ፡ በተበላሸው ፤ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ በጽሑፉ ፡ ቅጂ ፡ ዐውቆ ፡ የተገለገለ ፡ ሰው ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ፡፡

## ክፍል ፡ ፯ ፡፡

## ስለ ፡ ታወቁ ፡ ሰነዶች ፡፡

ቍ ፡ ፻፵፮ ፡፡ መሠረቱ ፡፡

(፩) የታወቁ ፡ ሰነዶችን ፡ የሚያዘጋጁ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹማምቶች ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ውል ፡ እንዲያፈራርሙ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡፡

(፪) እነዚህንም ፡ ጽሑፎች ፡ ዳኞች ፡ እንዲፈቅዱዋቸውና ፡ እንዲያጸድቋቸው ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፻፺፯ ። መፍቀድ ።**

የታወቁ፡ ጽሑፎችን፡ ማስረጃ፡ እንዲሆኑ ፡ የሚፈቅዱ፡ ዳኞች፡ ብቻ ፡ ናቸው። ይኸውም ፡ የሚሆነው ፤

(ሀ) መዝገቦቹ ፡ በደንብ ፡ የተያዙ ፡ ላለመሆናቸው ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለባ ቸው ፡ ለመሆናቸው ፡ አስረጂ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) እነዚህ ፡ መዝገቦች ፡ የጠፉ ፡ የተቀደዱ ፡ ለመሆናቸው ፡ አስረጂ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የነዚህን ፡ መዝገቦች ፡ የጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ ለማግኘት ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ ለማግኘት ፡ እጅግ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ጽሑፉን ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰው ፤ ጽሑፉ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቦታ ፡ የማያ ውቅ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ላለማወቁም ፡ ይቅርታ ፡ ሊደረግለት ፡ የሚቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) በሌላም ፡ በሕግ ፡ በታወቁ ፡ ሁኔታዎች ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፺፰ ። ጽሑፉን ፡ የሚያዘጋጀው ።**

(፩) የታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሆን ፡ ዳኞች ፡ በፈቀዱ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የታ ወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረጅበትን ፡ ቦታ ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ዳኞቹ ፤ ለሚጠይቁት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፤ ወይም ፡ ውል ፡ እንዲያዋ ውል ፡ በሕግ ፡ ለተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ተቃዋሚዎችን ፡ ለመቀስቀስና ፤ የጽሑፉን፡ እውነተኛነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚረዱትን ፡ ትእዛዞች ፡ ሁሉ ፡ ይሰጣሉ ።

**ቍ ፡ ፻፺፱ ፡ የጽሑፉ ፡ ቃሎች ።**

ባልተገኙት፡ የክብር፡ መዝገብ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም፡ የነዚሁን ፡ ጕድለት ፡ እን ዲያቃኑ ፡ ሲባል ፡ የተደራጁት ፡ የታወቁ ፡ ጽሑፎች ፡ በእነዚያ ፡ ላይ ፡ ሊገኙባ ቸው ፡ ይገባ ፡ የነበረው ፡ ቃል ፡ ይኖርባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻ ። የተያያዘ ፡ ራፖር ።**

(፩) የታወቀውን ፡ ጽሑፍ ፡ ያደራጀው ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ውል ፡ እንዲያፈራርም ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ የታዘዘውን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ባቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚያስረዳ ፡ ራፖር ፡ ከጽሑፉ ፡ ጋራ ፡ እያይዞ ፡ ለዳኞቹ ፡ ያቀርባል ።

(፪) በተለይም ፡ የታወቀው ፡ ጽሑፍ ፡ አስቀድሞ ፡ መዝገብ ፡ ከገባው ፡ ከአንድ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ከአንድ ፡ ከታወቀ ፡ ጽሑፍ፡ ጋራ ፡ ተቃዋሚነት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ፡ (ያስታውቃል) ።

**ቍ ፡ ፻፶፩ ። የጽሑፉ ፡ አስረጅነት ፡ ኀይል ። (፩) ከመጽደቁ ፡ በፊት ።**

(፩) የተዘጋጁበትን፡ጊዜና ፡ የተሰናዱበትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመገመት ፡ የታወቁት ፡ ጽሑፎች ፡ የሚኖራቸውን ፡ የአስረጅነት ፡ ዋጋ ፡ እንደ፡መሰላቸው ፡ ዳኞች ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ዳኞቹ ፡ የጽሑፉን ፡ ቃል ፡ ለመመርመር ፤ የሚገባ ፡ መስለው ፡ የሚታዩዋቸውን ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፶፪ ። (፪) ከመጽደቁ ፡ በኋላ ።**

የታወቀውን ፡ ጽሑፍ ፡ ዳኞቹ ፡ ባጸደቁት ፡ ጊዜ ፤ እንደ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ፡ ልክ ፡ የአስረጅነት ፡ ኀይል ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፻፶፫ ። የምስክሮቹ ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በምስክርነት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ እገሌ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ የዚህኑ ፡ ሰው ፡ የክብር ፡ መዝገብን ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የክብር ፡ መዝገቡን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከተውን ፡ ጕዳይ ፡ አረጋግጦ ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ትክክለኛ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ሰውዬው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱን ፡ ባሳሳተው ፡ ሰው፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ መጥፋት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የመጥፋት ፡ መግለጫ ።

**ቍ ፡ ፻፶፬ ። ጥያቄ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የጠፋና ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ወሬውን ፡ ያልሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ቢሆን ፡ የሰውዬው ፡ መጥፋት ፡ በዳኞች ፡ እንዲነገር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ለዚህ ፡ ነገር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚሆኑት ፡ ዳኞች ፤ የጠፋው ፡ ሰው ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ አድርጎ ፡ ይቀመጥበት ፡ በነበረው ፡ ቦታ ፡ የሚገኙት ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፶፭ ። የጥያቄው ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ።**

ጥያቄው ፡ በማስታወቂያ ፡ የሚወጣው ፡ ዳኞች ፡ በሚወስኑት ፡ ሁኔታና ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ በመጨረሻ ፡ ዋና ፡ መኖሪያው ፡ በነበረበት ፡ ቦታና ፡ እንዲሁም ፡ ማስታወቂያው ፡ ይጠቅማል ፡ ብለው ፡ በገመቱት ፡ ቦታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፶፮ ። ምርመራ ።**

የሰውዬውን ፡ መጥፋት ፡ ለመረዳት ፤ ዳኞቹ ፤ ከዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ ጠቃሚ ፡ በሚመስላቸው ፡ በማናቸውም ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ የጠ

BACK



ፋው ፡ ሰው ፡ በመጨረሻ ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ አድርጎት ፡ በነበረው ፡ ቦታና ፤ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ መኖሩ ፡ በታየበት ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ጠፋው ፡ ሰው ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፶፯ ። የውሳኔ ፡ መሠረት ።**

(፩) ዳኞቹ ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ የሚመስል ፡ ሆኖ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ጠፍቷል ፡ ሲሉ ፡ ያስታውቃሉ ።

(፪) በዚህ ፡ ረገድ ፤ ዳኞቹ ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ጠባይ ፤ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ይይዛሉ ። በተለይም ፡ ይህ ፡ በመጥፋት ፡ የተገመተው ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ የሚያስተዳድርለት ፡ ወኪል ፡ ማድረጉንና ፡ አለማድረጉን ፤

(፫) ወሬውን ፡ ለማስታወቅ ፡ ሊከለከሉ ፡ የቻሉትን ፡ ምክንያቶች ፡ መመርመር ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፻፶፰ ። ነገሩን ፡ ለመወሰን ፡ የሚሰጠው ፡ የቀጠሮ ፡ ቀን ።**

ዳኞቹ፤ ስለ፡ሰውዬው፡ መጥፋት፡ የሚሰጡትን፡ ፍርድ፡እስከ፡ አንድ፡ ዓመት፡ ለማቈየት ፤ ወይም ፡ ስለ ፡ መጥፋቱ ፡ የሰጡት ፡ የማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ውጤት ፡ እንዳይኖረው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፶፱ ። መጥፋቱን ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

ጠያቂው ፡ ከአቀረበ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላና ፡ ጥያቄውም ፡ በቀረበበት ፡ ቀን ፡ ሰውዬው ፡ ከጠፋ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ አልፎት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ጥያቄውም ፡ በማስታወቂያ ፡ እንዲወጣ ፡ ዳኞች ፡ ከወሰኑ ፡ በኋላ ፡ ወሬውን ፡ ያልሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጥፋቱን ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፻፷ ። የመጨረሻዎቹ ፡ ወሬዎች ፡ የደረሱበት ፡ ቀን ።**

ዳኞቹ ፡ በሚሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፤ የጠፋው ፡ ሰው ፡ የመጨረሻ ፡ ወሬዎች ፡ የደረሱበትን ፡ ቀን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፷፩ ። የሞት ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ።**

ዳኞቹ ፡ ያገኙዋቸው ፡ አስረጂዎች ፤ የጠፋው ፡ ሰው ፤ የሞተ ፡ ለመሆኑ ፡ እንደ ፡ እርግጠኛ ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ ሊቈጠር ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለመጥፋቱ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጡ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ ዳኞች ፡ የጠፋውን ፡ ሰው ፡ የሞት ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣሉ ።

**ቍ ፡ ፻፷፪ ። የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ወጪ ።**

(፩) የተደረገው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሰውዬውን ፡ መጥፋት ፡ ማስታወቂያ ፡ ያስከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ የተደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ በጠፋው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይታሰባሉ ።

(፪) እንደተባለው ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፤ በጠያቂው ፡ ላይ ፡ ይታሰባል ።

## ክፍል ፡ ፯ ፡፡

## የመጥፋቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡፡

**ቍ ፡ ፻፳፫ ፡፡ ጋብቻ ፡፡**

(፩) የጠፋ ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፤ የመጥፋቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ፍርድ ፡ የመጨረሻ ፡ በሆነ በት ፡ ቀን ፡ ይፈርሳል ፡፡

(፪) የመጨረሻዎቹ ፡ ወሬዎች ፡ ከተሰሙበት ፡ በኋላ ፡ የተፈጸመውን ፡ የወንዱን ፡ ወይም ፡ የሴቲቱን ፡ ጋብቻ ፤ ጠፋ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ሊቃወ መው ፡ የሚችል ፡ የለም ፡፡

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ በተጀመረበት ፡ ቀን ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ በማያከራክር ፡ አኳኋን ፡ ፀቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻውን ፡ ሊቃወመው ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፻፳፬ ፡፡ ጠፋ ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ የሚሰጡት ፡ ውርሶች ፡፡**

(፩) የመጨረሻዎቹ ፡ ወሬዎች ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፤ ጠፋ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በሕይ ወቱ ፡ ቢገኝ ፡ ኖሮ ፡ እርሱ ፡ ወራሽ ፡ ለመሆን ፡ የሚችልበት ፡ ያወራረስ ፡ ሥር ዐት ፡ የተጀመረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለእርሱ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ ድርሻ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ሳይገባ ፡ ሥርዐቱ ፡ ይፈጸማል ፡፡

(፪) የወራሽነት ፡ ንብረቶች ፡ ይዞታ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሰዎች ፤ ጠፋ ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ መብቶቹ ፡ መድን ፡ የሚሆን ፡ ዋስ ፡ እንዲጠሩ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሰጡ ፡ ዳኞች ፡ ሊያስገድዷቸው ፡ ይችላሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፻፳፭ ፡፡ በጠፋው ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ የሚገኙ ፡ መብቶች ፡፡**

(፩) በጠፋው ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ የሚገኙት ፡ መብቶች ፡ ያሏቸው ፡ ሰዎች ፡ መጥፋ ቱን ፡ የሚወስነው ፡ ፍርድ ፡ የመጨረሻ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ተቈጥሮ ፤ በመብቶቻቸው ፡ ሊጠቀሙባቸው ፡ ይችላሉ ፡፡

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ባገኙዋቸው ፡ መብቶች ፡ ከመጠቀማቸው ፡ በፊት ፡ ሊመለሱ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነገሮች ፡ አስቀድመው ፡ ዋስ ፡ እንዲጠሩ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሰጡ ፡ ዳኞች ፡ ሊያስገድዷቸው ፡ ይችላሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፻፳፮ ፡፡ በጠፋው ፡ ሰው ፡ መኖር ፡ የሚሰጡ ፡ ግዴታዎች ፡፡**

(፩) ጠፋ ፡ ከተባለው ፡ ሰው ፡ መኖር ፡ የተነሣ ፡ ግዴታዎች ፡ ያሉባቸው ፡ ሰዎች ፡ እነዚህን ፡ ግዴታዎች ፡ መፈጸም ፡ ይቀርላቸዋል ፡፡

(፪) ስለሆነም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፤ የጠፋው ፡ ሰው ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማለት ፡ ዋስ ፡ እንዲጠሩ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነውን ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሰጡ ፡ በዳኞቹ ፡ በኩል ፡ ሊገደዱ ፡ ይችላሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፻፷፯ ። የጠፋው ፡ ሰው ፡ ንብረቶች ። (፩) ይዞታን ፡ ስለ፡መስጠት ።**

(፩) የጠፋው ፡ ሰው ፤ ኑዛዜ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ በሚያቀርቡዋቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ መሠረት ፡ ኑዛዜው ፡ ይፈሳል ፡ (ይነገራል) ።

(፪) የጠፋው፡ ሰው ፡ የመጨረሻ ፡ ወሬዎቹ ፡ በተሰሙበት ፡ ቀን ፡ የሞተ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ንብረቶቹን ፡ ለመውረስ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፤ የንብረቱ ፡ ይዞታ ፡ እንዲሰጣቸውና ፡ ንብረቶቹን ፡ እንዲካፈሉ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፷፰ ። (፪) ወራሽነቱ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ንብረቶቹን ፡ እጅ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፤ በንብረቶቹ፡ሲጠቀም ፤ እንደ ፡ መልካም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባት ፡ እንዲሆን ፡ ይገደዳል ።

(፪) በንብረቶቹ ፡ መጠቀምን፡ከመጀመሩ ፡ በፊት ፤ ሊመለሱ፡ ስለሚችሉ ፡ ነገሮች፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ወይም ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሰጥ ፡ ዳኞቹ ፡ ሊያስገድዱት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፷፱ ። (፫) ባለይዞታ ፡ እንዲሆን ፡ የተፈቀደለትን ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ ማጥበብ፤ (ል፡ለ፡መቀነስ) ።**

(፩) ገንዘቦቹን ፡ በተቀበለ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የተቀበላቸውን ፡ ገንዘቦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ይገደዳል ።

(፪) የጠፋውን ፡ ሰው፤ልጆች ፡ ለማቋቋም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ንብረቶቹን ፡ በስጦታ፡ ስም ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይችልም ።

ክፍል ፡ ፫ ።

**ጠፋ ፡ መባሉ ፡ የሚቀርበት ፡ ጊዜ ።**

**ቍ ፡ ፻፸ ። ምክንያቶች ፡ (፩) መሠረቱ ።**

ጠፍቷል ፡ የማለት ፡ ማስታወቅ ፡ ውጤት ፡ መስጠቱ ፡ የሚቀረው ።

(ሀ) ጠፋ ፡ የተባለው ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ጠፍቷል፡የሚለው ፡ የፍርድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በሕይወት ፡ ለመኖሩ ፡ አስረጂ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የመጨረሻ ፡ ወሬዎቹ ፡ የተሰሙበት ፡ ተብሎ፡ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ለመሞቱ ፡ አስረጂ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፸፩ ። (፪) ጠፋ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ መመለስ ።**

(፩) ጠፋ፡የተባለው፡ ሰው ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ንብረቶቹን ፡ በሚገኙበት ፡ አኳኋን፡ እንዲሁም ፡ የተሸጡትን ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋና ፡ እነዚህንም ፡ ዋና ፡ ገንዘቦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ የተገኙትን ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ መልሶ ፡ ይወስዳል ።

(፪) ጠፋ ፡ ከተባለው ፡ ሰው፡ንብረቶች ፡ የተገኙት ፡ ገቢዎች ፤ ንብረቶቹን ፡ በይዞታ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ እነዚህን ፡ ገቢዎች ፡ ላገኙ፡ ሰዎች ፡ ገቢ ፡ እንደ፡ሆኑ ፡ ይቀራሉ ።

(፫) ንብረቶቹን ፡ እጅ ፡ ለማድረግ ፡ የተላኩት ፡ ሰዎች፡በተንኰል ፡ ወይም ፡ በመጥፎ ፡ አስተዳደር ፡ ላጠፉት ፡ ነገር፤ ጠፋ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፸፪ ። ስለ ፡ ሞቱ ፡ የሚሰጥ ፡ ግምት ። (፩) ሁኔታዎች ።**

መጥፋቱን ፡ በሚወስነው፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ ከተወሰነው ፤ የመጨረሻ ፡ ወሬዎች፡ ከተሰሙበት ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መሞቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ወሬዎቹ ፡ በተሰሙበት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ጠፋ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መጥፋቱ ፡ የተሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ልዩ ፡ የሆነው ፡ ወኪል፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፸፫ ። (፪) ውጤቶች ።**

(፩) የጠፋውን ፡ ሰው ፡ ንብረቶች ፡ እጅ ፡ ለማድረግ ፡ የተላኩት ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ፡ በላይ ፡ ከተነገረው ፡ ቀን ፡ አንሥተው ፡ ለይዞታው ፡ ማስረጃ ፡ እንዳቀረበው ፡ ሰው ፡ ባለመብት ፡ ሆነው ፡ ይሠራሉ ።

(፪) ጠፋ፡የተባለው ፡ ሰው ፡ የተመለሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ የተሰጡት ፡ ዋሶች ፡ ወይም ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ነፃ ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታና ፡ ስለ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ።

**ቍ ፡ ፻፸፬ ። ትርጓሜ ።**

የአንድ ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ የሚባለው ፡ ለጊዜው ፡ የሚኖርበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፸፭ ። ድንገተኛ ፡ የመሰንበቻ ፡ ቦታ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፤ ለጊዜው ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ቢሰነብት ፡ ይህ ፡ የተባለው፡ ቦታ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ነው ፡ ለማሰኘት ፡ አይበቃም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ መሰንበቱ ፡ የሚቀጥል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ቈይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፻፹፮ ። የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ አለመኖር ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ከሌላ፡ ዘንድ ፡ ለመሆኑ ፡ አስረጂ ፡ ካልተገኘ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፻፹፯ ። ብዙ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታዎች ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፤ በነዚህ፡የመኖሪያ ፡ ቦታዎች ፡ አንዱ ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሌሎቹ ፡ ተጨማሪ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታዎች ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፹፰ ። ያገቡ ፡ ሴቶችና ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች ።**

(፩) ያገቡት ፡ ሴቶች ፡ የራሳቸው ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ሊኖራቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሱት ፡ ልጆችና ፤ ችሎታ ፡ የተከለከሉ ፡ ሰዎች ፡ የራሳቸው ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፹፱ ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ።**

የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሊኖራቸው ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፻፺ ። ነጋዴዎች ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ አንደኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፻፺፩ ። በውል ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ የሚጠቀስ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ። (፩) መሠረቱ ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ ከሌላ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፤ ወይም ፡ አንዱን፡ ጕዳይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተወሰነውን ፡ የሥራ ፡ ክንውን ፡ ስለሚመለከት ፡ ነገር ፤ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ሆኖ ፡ እንዲቈጠር ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለማግባት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፺፪ ። (፪) ውጤቶች ።**

(፩) ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር፡ ይህ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለእርሱ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፤ በዚህ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ አይገደድም ።

(፪) ይህ ፡ የውል፡ጥቅም፡ የተደረገለት፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ መረጠ ፤ የተዋዋዩን ፡ እውነተኛ ፡ የመሪኖያ፡ ቦታ ፤ ወይም ፡ በውሉ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱን፡ የተዋዋዩ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ አድርጎ ፡ ለመቍጠር ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## መደበኛ ፡ ቦታ ።

### ቍ ፡ ፻፹፫ ። ትርጓሜ ።

የአንድ ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ማለት ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በነዋሪነት ፡ ዐይነት ፡ እዚያው ፡ ቦታ ፡ በመኖር ፡ አሳብ ፤ የጕዳዮቹና ፡ የጥቅሞቹ ፡ ዋና ፡ ስፍራ ፡ ያደረገው ፡ ቦታ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፻፹፬ ። የሐሳብ ፡ ግምት ።

(፩) የአንድ፡ ሰው ፡ ደንበኛ ፡ የመኖሪያ ፡ ስፍራው ፡ አንድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ በነዋሪ ፡ አኳኋን ፡ ለመኖር ፡ አሳብ ፡ እንዳለው ፡ ይገመታል ።

(፪) ይህ ፡ የተባለው ፡ ሰው፡የገለጸው፡ተቃራኒ፡ አሳብ ፡ ቢኖር ፤ አሳቡ ፡ በቂ ፡ በሆነ፡ አነጋገር ፡ የተለየ ፡ ካልሆነና ፡ ውጤትም ፡ የሚኖረው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ደንበኛ ፡ ሁኔታ ፡ ወደፊት ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ የሚሆን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በደንበኛው ፡ የነገሮቹ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ደርሶ ፡ መታየት ፡ ያለበት ፡ ተቃራኒው ፡ አሳብ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አይቈጠርም ።

### ቍ ፡ ፻፹፭ ። የሞያ ፡ ሥራ ፡ መኖሪያና ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ የሚሠራቸው ፡ የሞያ ፡ ሥራዎች ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የማኅበራዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ የሆነ ፡ እን ሆነ ፤ ጥርጣሬ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የማኅበራዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ።

### ቍ ፡ ፻፹፮ ። መደበኛ ፡ ቦታው ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በአንድ፡ጊዜ ፡ ብዙ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

### ቍ ፡ ፻፹፯ ። መደበኛ ፡ ቦታን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ ቦታውን ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ እስካደረገ ፡ ድረስ ፡ መደበኛ ፡ አድርጎ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ ይቈያል ።

### ቍ ፡ ፻፹፰ ። ያልታወቀ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ።

(፩) የአንድ ፡ ሰው፡ የመጨረሻ፡ መደበኛ፡ ቦታው፡ የት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በደንብ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ቦታ ፡ መደበኛ ፡ ቦታው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በደንብ፡ የሚቀመጥበት፡ቦታ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በጣም ፡ ራቅ ፡ ካለ ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ ፡ ምክትል ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ያደረገው ፤ እንደ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ባለጕዳዩ ፡ የሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፻፹፱ ። ያገቡ ፡ ሰዎች ።**

(፩) ያገባች ፡ ሴት ፡ ጋብቻው ፡ እስከ ፡ ቈየበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ መደበኛ ፡ ቦታዋ ፡ የባልዋ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ነው ።

(፪) ጋብቻው ፡ የፈረሰ ፡ ወይም ፡ ባልዋ ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሴቲቱ ፡ የራሱዋ ፡ የሆነ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ለማቋቋም ፡ ትችላለች ።

**ቍ ፡ ፻፺ ። ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ ያልወጣ ፡ ልጅ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ።**

ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ ያልወጣ ፡ ልጅ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ የአሳዳሪው ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፺፩ ። ችሎታ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ።**

ችሎታ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ በተከለከለ ፡ ጊዜ ፡ የነበረበትን ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

## አንቀጽ ፡ ሁለት ።

## ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ፻፺፪ ። የችሎታ ፡ ደንብ ።**

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ ተወስኖ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮውን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ችሎታ ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፻፺፫ ። ጠቅላላ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።**

ጠቅላላ ፡ የችሎታ ፡ ማጣትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስከትሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ዕድሜ ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ የፍርድ ፡ ቅጣት ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፺፬ ። የተለየ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።**

(፩) የተለየ ፡ ችሎታ ፡ ማጣትን ፡ ለመወሰን ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ የሚቻለው ፡ የሰውዬውን ፡ ዜግነት ፡ በመመልከት ፡ ወይም ፡ የሚያከናውነውን ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ነው ።

(፪) ይኸውም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፭ ፡ ከ፫፻፹፱ ፡ እስከ ፡ ፫፻፺፫ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ሕግና ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ ይደነገጋል ።

**ቍ ፡ ፻፺፭ ። በፈቃድ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የሕዝባዊ ፡ መብቶቹን ፡ አልጠቀምባቸውም ፡ ወይም ፡ አልሠራባቸውም ፡ ብሎ ፡ በከፊልም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ለመተው ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ፡ማኅበራዊ ፡ ጥቅም ፡ ሕጋዊ ፡ ተገቢነት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ እነዚህን ፡ መብቶች ፡ አልሠራባቸውም ፡ ወይም ፡ አልጠቀምባቸውም ፡ ብሎ ፡ በፈቃዱ ፡ የሚወሰንበት ፡ ስምምነት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፻፺፮ ። ችሎታን ፡ የማጣት ፡ አስረጂ ።**

(፩) ሰው ፡ ሁሉ ፡ ችሎታ ፡ እንዳለው ፡ ይገመታል ።

(፪) ይህ ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማስረዳት ፡ የሚገባው ፤ ሰውዬው ፡ ችሎታ ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ የሚከራከረው ፡ ወገን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፺፯ ። የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ።**

የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ የሚረጋገጠው፡እንደ ፡ ዐይነታቸው ፡ ለነዚሁ ፡ የሰውነት ፡ መብት፡በሚሰጧቸው ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ሰዎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፻፺፰ ። ትርጓሜ ።**

አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ማለት ፤ በሁለቱም ፡ ፆታ ፡ (ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት) ፡ ዕድሜው ፡ ገና ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላው ፡ ሰው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፺፱ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሰውነቱ ፡ አስተዳደር ፡ በአንድ ፡ አሳዳሪ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እየተጠበቀ ፡ በመኖር ፡ ለዚህም ፡ ላሳዳሪው ፡ ሊታዘዝ ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) የገንዘብ ፡ ጥቅሞቹን ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይና ፡ ስለ ፡ ንብረቱም ፡ አስተዳደር ፡ ሞግዚቱ ፡ እንደራሴው ፡ ነው ።

(፫) በሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ጕዳዮች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ሰው ፡ የሕግ ፡ ተግባሮችን ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፻፲ ። የዕድሜ ፡ ማስረጃ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የአንድ፡ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ስንት ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ሊረጋገጥ ፡ የሚቻለው ፡ በተወለደበት ፡ ቀን ፡ በተጻፈው ፡ መዝገብ ፡ አስረጅነት ፡ ነው ።

(፪) የመወለድ ፡ ጽሑፍ፡የሌለ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ስንት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የሚረጋገጠው ፡ በቂ ፡ ምስክሮች ፡ በፈረሙበት ፡ በተረጋገጠ ፡ ጽሑፍ ፡ አማካይነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፲፩ ። (፪) የመወለድን ፡ ጽሑፍ ፡ ተቃዋሚ ፡ ስለሚሆን ፡ ማስረጃ ።**

(፩) የማስረጃውን ፡ አቀራረብና ፡ የአስረጅነቱን ፡ ዝርዝር ፡ የሚያጠራጥር ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ ያጋጠማቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ስንት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማስረዳት ፡ የመወለድን ፡ ጽሑፍ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ የተወለደበትን ፡ ዘመን ፡ ለማረጋገጥ ፡ በመወለድ ፡ ጽሑፍ ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ እንዳይቀርብ ፡ የሚከለክለው ፡ የዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ይግባኝ ፡ ሊቀርብበት ፡ ይችላል ።

(፫) በማናቸውም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ የታወቀውን ፡ ጽሑፍ ፡ በቂ ፡ ምስክሮች ፡ በማቅረብ ፡ ለመቃወም ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፻፲፪ ። (፫) በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስረጃ ።**

(፩) አንድ ፡ የታወቀ ፡ የዕድሜ ፡ ማረጋገጫ፡ጽሑፍ ፡ መቃወሚያ ፡ የቀረበበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመወለዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ የተፈቀደ ፡ ሲሆን ፡ ዳኞቹ ፤ የቀረበላቸውን ፡ ችግር ፡ ለማቃናት ፡ እንዲችሉ ፡ የሰውዬውን ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ስለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ ለመረጃ ፡ የሚሆናቸውን ፡ ውሳኔ ፡ ሁሉ ፡ ያዛሉ ።

**ቍ ፡ ፻፲፫ ። (፬) ስለ ፡ ይግባኝ ።**

(፩) በመጀመሪያ ፡ ደረጃ፡ችሎት ፡ ያደረጉት ፡ ዳኞች ፤ አንድ ፡ የምርመራ ፡ ጉዳይ ፡ ተደርጎ ፡ ነገሩ ፡ እንዲጣራ ፡ ወይም ፡ እንዳይጣራ ፡ የሰጡት ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ይግባኝ ፡ ያስከትላል ።

(፪) የሰውዬውንም፡የዕድሜ ፡ መጠን ፡ ስለሚወስኑትም ፡ ዳኞች ፡ ፍርድ ፤ አፈጻጸሙ ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## አካለ፡መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ ስለሚጠብቁ ፡ ክፍሎች ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ አሳዳሪና ፡ ስለ፡ሞግዚት ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፮ ። የወላጆች ፡ ሥልጣን ።**

አባትና ፡ እናት ፡ ጋብቻቸው ፡ ጸንቶ ፡ አብረው ፡ በሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱት ፡ ልጆቻቸው ፡ አሳዳሪነትና ፡ ሞግዚትነት ፡ በአንድነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፯ ። ከወላጆች ፡ የአንዱ ፡ አለመገኘት ።**

(፩) ከወላጆቹ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ችሎታ፡ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተገቢነት ፡ መብት ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ መብቱ ፡ የታገደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአስተዳዳሪነቱን ፡ ሥልጣን ፡ ይዞ ፡ የሚቈየው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ያልታወቀ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የዚህን ፡ ሥልጣን ፡ ሥራ ፡ የምትፈጽም ፡ እናት ፡ ብቻ ፡ ናት ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፰ ። የልጆቹ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ መፋታት ።**

(፩) አባትና ፡ እናት ፡ በተፋቱ ፡ ጊዜ፡ለልጁ፡ ሞግዚትና፡ አሳዳሪ ፡ የሚመርጡ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

(፪) ከተፋቱትም፡ ባልና፡ሚስት፡ አንደኛው፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ በሕይወቱ ፡ ያለው ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ለመያዝ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፱ ። በኑዛዜ ፡ ቃል ፡ የተመረጠ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በሕይወት ፡ ያለው ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት፡ ከጊዜ ፡ ሞቱ ፡ በኋላ ፡ ልጁን ፡ የሚያስተዳድር ፡ ወይም ፡ ለልጁ ፡ ሞግዚት ፡ የሚሆነውን ፡ ሰው ፡ በመጨረሻ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡የአሳዳሪውን ፡ ወይም ፡ የሞግዚቱን ፡ ሥልጣኖች ፡ ለመወሰንና ፡ ወይም ፡ የአሳዳጊነቱን ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ሥልጣን ፡ በተወሰነ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

BACK



(፫) እንዲሁም ፡ ደግሞ፡አንድ ፡ ወይም ፡ ቍጥራቸው ፡ የተወሰነ ፡ ሰዎች ፡ ለልጁ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪፻፰ ። (፪) አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ለመሾም ፡ የሚፈጸም ፡ ግዴታ ።

አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጁን ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ ሥራ ፡ ያካሂድ ፡ የነበረ ፡ ካልሆነና ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ሥልጣኑን ፡ ዐውቆ ፡ የተው ፡ ካልሆነ ፡ ባቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው፡ ቍጥር ፡ ለአባት ፡ ወይም ፡ ለእናት ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

ቍ ፡ ፪፻፱ ። (፫) ወደ ፡ ዳኞች ፡ አቤቱታን ፡ ስለ፡ ማቅረብ ።

አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገድድ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ስለ፡ሞግዚቱ ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ እናቱ፡ ያደረጓቸውን ፡ አወሳሰኖች ፡ ወይም ፡ ሁኔታዎች ፡ ዳኞች ፡ ሊያስቀሩት፡ ወይም፡ ሊለዋውጡት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፲ ። የልጅን ፡ አሳዳሪነት፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥልጣን ፡ ሊይዙ ፡ የሚገባቸው ፡ ዘመዶች ፤ (፩) ሊከተሉት ፡ የሚገባው ፡ ተራ ።

አንድ ፡ ልጅ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ከሁለቱ ፡ በመጨረሻ ፡ የሞተው ፡ ወላጁ ፡ በሚገባ ፡ ሁኔታ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ሳያደርግለት ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለልጁ ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሚመረጡና፡ይህ፡ሥልጣን፡የሚሰጣቸው፡ከዚህ፡ቀጥሎ፡ለተመለከቱት፡ሰዎች፡ነው ።

(ሀ) የልጁ ፡ የአባት፡ወገን፡አያት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ እንደሌለ ፡ የአባቱ ፡ ወገን ፡ ሴት ፡ አያት ።

(ለ) የልጁ ፡ የእናት፡ወገን ፡ ወንድ ፡ አያት ፡ ይህ ፡ እንደሌለ ፡ የእናቱ ፡ ወገን ፡ ሴት ፡ አያት ።

(ሐ) እነዚህ ፡ በሌሉ ፡ ጊዜ፡በዕድሜ ፡ ታላቅ ፡ የሆኑት ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ወገን ፡ አጎት ፡ ወይም ፡ የአባት ፡ ወገን ፡ አክስት ፤

(መ) እነዚህም ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕድሜ ፡ ታላቅ ፡ የሆኑት ፡ የልጁ ፡ የእናት ፡ ወገን ፡ አጎት ፡ ወይም ፡ የእናት ፡ ወገን ፡ አክስት ።

(ሠ) እነዚህም ፡ የሌሉ ፡ ሲሆን፡ በዕድሜ ፡ ታናሽ ፡ የሆኑ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ፡ አጎት ፡ ወይም ፡ አክስት ።

ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። (፪) ይህ ፡ ተራ ፡ ሊለወጥ ፡ የሚችልበት ፡ መንገድ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው፡ ቍጥር፡እንደተመለከተው ፤ ሥልጣን ፡ በሚሰጠው፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ለልጁ ፡ የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡

BACK



ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ የአሳዳሪነቱ ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠኝ ፡ ሲል ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ጥያቄ፡መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ባለጥቅሞቹ ፡ የተስማሙ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፤ ወይም ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ሳይስማሙ ፡ ሲቀሩ ፡ ለዳኞቹ ፡ ነው።ለጥያቄውም፡ ማቅረቢያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም፡ ሕጋዊ ፡ ሞግዚቱ ፡ የዚህን ፡ ሥልጣን ፡ መያዙ ፡ ከታወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ነው ።

(፫) የባለጉዳዮቹ ፡ አሳብ ፡ ከተመረመረ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ አሳብ ፡ ከተጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ላለመቀበል ፡ የሚገባው ፡ የልጁን ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ በመገመት ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። በሕግ ፡ የሚመረጡ ፡ ዘመዶች ፡ መታጣት ።

(፩) ከዚህ፡በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለማድረግ፡ ለልጁ ፡ አንድ ፡ አሳዳሪ ፤ ሞግዚት ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ይህ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፡ ዳኞች ፡ ለመረጡት ፡ ሰው ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ዳኞቹም ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ የልጁ ፡ ዘመድ ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ ባልሆነ ፡ ባለጉዳይ ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢነት ፡ ሊሠሩ ፡ ይችላሉ ።

(፫) በሕጉ ፡ መሠረትም ፡ ይህን ፡ ጉዳይ፡በሚመለከተው ፡ ባለሥልጣን ፡ ጥያቄ ፡ ጉዳዩ ፡ ሊቀርብላቸው ፡ ይገባል ።

## ቍ ፡ ፪፻፲፫ ። የዳኞች ፡ ምርጫ ። (፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዶች ።

ዳኞች፡ ለልጁ፡ አሳዳሪ፡ ወይም ፡ ሞግዚት፡ እንዲሆን፡ የሚመርጡትና፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጡት ፡ የልጁ ፡ የቅርብ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ያለውንና ፡ በተቻለም ፡ መጠን ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ችሎታና ፡ ፈቃደኛነት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪፻፲፬ ። (፪) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ።

(፩) የአሳዳሪነትን ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥልጣን ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ዳኞች ፡ ላንድ ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ከአባሎቹ ፡ አንዱ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ እንዲያከናውን ፡ ለመወከል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፭ ። ተመሳሳይ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ፡በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች፡እንዲፈጸሙ ፡ ለማድረግ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ የሚቈጠረው ፡ ከሕጋዊ፡ምክንያት ፡ ወይም ፡ ከሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ለልጁ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ሆነው ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ ባልቻሉ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ሕፃኑም ፡ ለማደጎ ፡ (ለጉዲፈቻ)፡ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጁ ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፮ ። የአሳዳሪው ፡ ወይም ፡ የሞግዚቱ ፡ መታወቂያ ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪ ፡ እንዲሆን ፡ ሥልጣን፡ ተሰጥቶት ፡ የልጁን ፡ ባለአደራነት ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ በጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ ሞግዚትም ፡ ነው ።

(፪) ከነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ካልተገኘ ፡ በሕይወት ፡ ያለው ፡ አባት፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ለልጁ ፡ የሚሾሙት ፡ ሞግዚት ፡ ወይም ፡ አሳዳሪ ፡ ሁለቱንም ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፯ ። ለአባትና ፡ ለእናት ፡ የተሰጠ ፡ መብት ።**

አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ጕዳዩ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጃቸውን ፡ አሳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ ራሳቸው ፡ ይዘው ፡ አንድ ፡ ሞግዚት ፡ ለመሾም ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፰ ። ለዳኞቹ ፡ የተሰጠ ፡ መብት ።**

ዳኞች ፡ የልጁን ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ የመሾም ፡ ሥልጣን ፡ የራሳቸው ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአሳዳሪው ፡ ሌላ፡ ለልጁ ፡ ሌላ ፡ ሞግዚት ፡ ለመሾም ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፱ ። ተጨማሪ ፡ ሞግዚት ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሀብት ፡ አስተዳደር ፡ ጕዳይ ፡ ዳኞች ፡ ለመረጡት ፡ ለአንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ሞግዚት ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ሀብቶች ፡ ተሰጥተውት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሀብት ፡ ተቀባዩ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ተጠቃሚው ፡ ልጅ ፡ አካለመጠን ፡ እስኪያደርስ ፡ ድረስ ፡ ንብረቱን ፡የሚጠብቅለት ፡ ተጨማሪ፡ ሞግዚት ፡ ሀብት ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ ተናዛዡ ፡ መርጦ ፡ ሊሾምለት ፡ ይችላል ።

(፫) የልጁ ፡ አባት፡ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላ

ጆች ፡ ትተውት ፡ ከሚሞቱት ፡ የውርስ ፡ ገንዘብ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ለሚደርሰው ፡ ንብረትም ፡ በዚሁ ፡ መብት ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፷ ። ምትክ ፡ ሞግዚት ። (፩) በሞግዚትና ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ ፡ ግጭት ።**

(፩) በሞግዚቱና ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ መካከል፡ ግጭት ፡ የተነሣ ፡ (ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ ያለ) ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞቹ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ምትክ ፡ ሞግዚት ፡ ይሾሙለታል ።

(፪) ምትክ ፡ ሞግዚት፡የሚመረጠው ፡ በሞግዚቱ ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ‚ባላ ፡ ከሆኑት ፡ በአንደኛው ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢነት ፡ ነው ።

(፫) ተጠባባቂ ፡ ሞግዚት፡አስቀድሞ ፡ ተሾሞም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚሁ ፡ ተጠባባቂ፡ ሞግዚት ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የምትክ ፡ ሞግዚትነት ፡ ሥልጣንና፡ሥራ፡ይኖረዋል።

**ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። (፪) አካለመጠን ፡ ባላደረሱ ፡ በብዙ ፡ሕፃናት ፡ ጥቅም ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ ፡ ግጭት ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ባላደረሱ፡በብዙ ፡ ሕፃናት ፡ ጥቅም ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ (ተቃዋሚ ፡ ጥቅም) ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የነዚህም ፡ ተጠሪ ፡ ወኪል ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ የጋራ ፡ ሞግዚት ፡ብቻ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠው፡ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) ግጭት ፡ የተነሣበት ፡ (ተቃዋሚ ፡ የሆነው) ፡ ጥቅም፡ የሚተካከለውም ፡ በሞግዚቱና ፡ በምትክ ፡ ግሞዚቱ ፡ መካከል ፡ በሚደረግ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። የሥራው ፡ አጀማመር ።**

(፩) የአሳዳሪነቱ ፡ ወይም፡ የሞግዚትነቱ፡ሥራ ፡ የሚጀመረው ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም፡ ሞግዚቱ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በዳኞች ፡ ትእዛዝ ፡ ተመርጠው ፡ እንደ ፡ ተሾሙ ፡ ወዲያውኑ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት፡ሥራ ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑን ፡ ከማወቁ ፡ በፊት ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ ይህን ፡ ሥራውን ፡ ሳይጀምር ፡ ለደረሰው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ሊደርስበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። ሥራው ፡ የግዴታ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

የአሳዳሪነትን ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነትን ፡ ሥራዎች ፡ እንዲያከናውን ፡ ተመርጦ ፡ የተሾመው ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ እንዲያከናውን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፺፬ ። ሥራው ፡ እንዲቀርለት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።**

(፩) አንድ፡ሰው፡ ለአንድ ፡ ሕፃን፡ ሞግዚት ፡ ወይም፡ አሳዳሪ፡ ቢሆን ፤ የዚህ ፡ ሥራ፡ አፈጻጸም ፡ በግል ፡ ጕዳዩ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ የሚያስከትል ፡ ወይም ፡ የማይስማማ ፡ ነገር ፡ የሚያደርስበት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ እንዲቀርለት ፡ ዳኞችን ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡አንድ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት፡ ከተሰጣቸው ፡ የአሳዳሪነትና፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራቸው ፡ እንዲሻሩ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፺፭ ። በሕግ ፡ አግባብ ፡ የሚሰጥ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት።**

እራሳቸው ፡ ጥያቄ ፡ ካቀረቡና ፡ ለራሳቸው ፡ ልጆች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡፤የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራ ፡ እንዳይዙ ፡ በሕግ ፡ የሚፈቀድላቸው ።

(ሀ) ሴቶች ፤

(ለ) ዕድሜው ፡ ስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ የሞላው ፡ ሰው ፤

(ሐ) አካለመጠን ፡ ያላደረሱ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ ሰው ፤

(መ) በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ወታደሮች ፤

(ሠ) በውጭ፡አገር ፡ እንዲኖሩ ፡ ሥራቸው ፡ የሚያስገድዳቸው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፺፮ ። ለጊዜው ፡ ሥራውን ፡ የማከናወን ፡ ግዴታ ።**

(፩) የልጅ ፡ አሳዳሪነት፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት፡ሥራ ፡ ችግር ፡ ያደርስብኛል ፡ ብሎ፡ ምክንያት ፡ በማቅረብ ፡ ይህ ፡ አላፊነት ፡ እንዲወገድለት ፡ የሚጠይቅ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ሌላ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ተተክቶ ፡ ሥልጣኑን ፡ እስኪረከበው ፡ ድረስ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ለጊዜው፡ የማከናወን፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም፡የአሳዳሪነቱ ፡ወይም ፡ የሞግዚትነቱ ፡ ሥራ ፡ በሹመት፡ የተሰጠው፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚትም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ግዴታ ፡ ይኖርበታል ።

**ቍ ፡ ፻፺፯ ። ስለ ፡ ሥራው ፡ መቅረት ።**

(፩) የአሳዳሪው ፡ ወይም፡የሞግዚቱ ፡ ሥራ ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ የሚጠበቀው፡ልጅ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ባደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከሞግዚት፡ ጥበቃ ፡ ነፃ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም፡ሞግዚቱ ፡ ሲሞት ፤ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ሲያጣ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ያለመሆኑ ፡ ሲገለጽ ፡ ወይም ፡ ከሥራው ፡ ሲሻር ፡ ቀሪ፡ይሆናል ።

BACK



(፫) በመጨረሻውም ፤ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ሰው ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞው ፡ ሞግዚት ፡ ሥራውን ፡ ይተዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፫ ። ችሎታ ፡ ማጣት ። (፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ።**

የራሱን ፡ ልጆች ፡ በሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራን ፡ ለማካሄድ ፡ ችሎታ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፬ ። (፪) በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የተከለከሉ ፡ ሰዎች ።**

(፩) ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የተከለከለ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራን ፡ ለማከናወን ፡ አይችልም ።

(፪) ይህን ፡ ሥራ ፡ ያከናውን ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፤ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ መሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ችሎታ ፡ የተከለከለውን ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ተረክቦ ፡ በምትክነት ፡ ለማካሄድ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ሞግዚቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የሌለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የታገደው ፡ ሰው ፡ ምትክ ፡ እንዲደረግለት ፡ ሞግዚቱ ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፭ ። ተገቢ ፡ ስላለመሆን ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራን ፡ ለማካሄድ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ዳኞች ፡ ለመወሰን ፡ የሚችሉት ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ በመፈጸሙ ፡ ከግል ፡ ነፃነት ፡ የሚከለክል ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ቅጣት ፡ የተፈረደበት ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ዳኞች ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ቅጣት ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ የገመቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ተገቢ ፡ አለመሆኑን ፡ ጭምር ፡ ለመበየን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፮ ። (፩) የአሳዳሪው ፡ መሻር ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ እንዲሆን ፡ የተሾመ ፡ ሰው ፡ ልጁ ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ጥበቃ ፡ ሳያገኝ ፡ ወይም ፡ ከግብረ ፡ ገብነት ፡ ጋራ ፡ የተመሳሰለ ፡ የአእምሮ ፡ አስተዳደግ ፡ ወይም ፡ ከችሎታው ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ እንዲያገኝ ፡ ሳያደርግለት ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አሳዳሪው ፡ እንዲሻር ፡ ዳኞች ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህንንም ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፤ አሳዳሪው ፡ የሚኖርበትን ፡ አካባቢ ፡ የስፍራ ፡ ሁኔታና ፡ የጊዜውንም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ መገመትና ፡ መሠረት ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

BACK



(፫) በተለይም ፡ ዳኞች ፡ አሳዳሪውን ፡ ለመሻር ፡ የሚችሉት ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ወንጀል ፡ መሥራቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲሆንና ፡ ይህም ፡ ቅጣት ፡ የደረሰበት ፡ በመጥፎ ፡ አስተዳደግ ፡ ወይም ፡ በአሳዳሪው ፡ ጕድለት ፡ ተገቢውን ፡ የግብረ ፡ ገብነት ፡ ሥልጣኔ፡ ለማግኘት ፡ ካለመቻሉ ፡ የተነሣ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። (፪) የሞግዚቱ ፡ መሻር ።**

አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሞግዚት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንዲሻር ፡ ዳኞች ፡ የሚወስኑት ፡ ሞግዚቱ ፡ የሕፃኑን ፡ ንብረትና ፡ ሀብት፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ያስተዳደረና፡ አጠባበቁም፡ በቂ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የልጁ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ ወይም፡ የቤተ ፡ ዘመድ ጉባኤ ፡ አማካሪዎች ፡ በሚገባ ፡ የሰጡትን ፡ ደንብና ፡ የንብረት ፡ አስተዳደር ፡ ሥርዐት ፡ ሳይጠብቅና ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዕዳ፡ ለመክፈል ፡ ያለመቻሉ ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። (፫) የወላጆች ፡ መሻር ።**

(፩) ዳኞች ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተጠብቀው ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ሌሎቹ ፡ ወላጆች ፡ ከልጃቸው ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ ሥራቸው ፡ እንዲሻሩ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ አይሰጡም ።

(፪) ዳኞች ፡ ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ ያደረጉት ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በተሻረው ፡ ወገን ፡ ጠያቂነት ፡ እንደ፡ገና ፡ ሊመረመር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። (፬) ሥነ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) አንድ ፡ አሳዳሪ፡ወይም ፡ አንድ ፡ ሞግዚት ፡ እንዲሻር ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ በአንድ ፡ የልጁ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ግንኙነት ፡ በአለው ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አስከባሪው ፡ በኩል ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ዳኞች፡ የአሳዳሪውን፡ወይም ፡ የሞግዚቱን ፡ መሻር ፡ በፍርድ ፡ ከመወሰናቸው ፡ በፊት ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሀብቱ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ አድርገው ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ የሚያመለክተውን ፡ ነገር ፡ ሊሰሙት ፡ ይገባል ።

(፫) ዳኞች ፡ አንድ፡አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት፡ እንዲሻር ፡ ውሳኔ ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ምትክ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊውን ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፭ ። የዳኞች ፡ ሥልጣንና ፡ ግዴታ ።**

(፩) ዳኞች ፡ አንዱን፡ ሰው ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ ለመሾም ፡ ሲመርጡ ፡ ወይም ፡ የተሾመውን ፡ ከሥራው ፡ ሲለውጡ ፡ (ሲሽሩ) ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡

BACK



ከልጁ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ አማካሪ ፡ ጋራ ፡ መመካከር ፡ ይገባቸዋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ አስፈላጊነቱን ፡ የገመቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለጕዳይ ፡ የሆነውን ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ ይሰማሉ ።

(፫) ዳኞች ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጡ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው፡ልጅ ፡ ጥቅም ፡ የማ ይጓደልበትን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ መከተል ፡ እንጂ ፡ በመመርመር ፡ ያገኙትን፡ አሳብ፡ የመቀበል ፡ ግዴታ ፡ የለባቸውም ።

ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። ሥራው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ በዋጋ ፡ የሚከናወን ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የአሳዳሪነትና ፡ የሞግዚትነት፡ሥራ ፡ የሚከናወነው ፡ ማናቸውም ፡ ዋጋ ፡ ሳይ ከፈልበት ፡ በነፃ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፤ አሳዳሪው ፡ ወይም፡ሞግዚቱ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚጠይቀው፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነና ፤ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ አካለ መጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ የሌለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድ፡የተወሰነ ፡ የዓመት ፡ አበል ፡ ሊቈረጥለት ፡ ይቻላል ።

(፫) ይህም ፡ የዓመት፡አበል ፡ አካለመጠን ፡ ካላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሀብት ፡ ገቢ፡ላይ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከሌላ ፡ ሀብት ፡ ሊወሰድ ፡ አይችልም ። የአበሉም ፡ ልክ ፡ ከጠ ቅላላው ፡ የሀብት ፡ ገቢ ፡ ከሦስት ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ሊያልፍ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። የሥራው ፡ አካሄድ ፡ የግል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የአሳዳሪነቱ ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነቱ ፡ ሥራ ፡ የግል ፡ ጠባይ ፡ የያዘ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውነው ፡ ያው ፡ ራሱ ፡ እንጂ ፡ ለአሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ለሞግዚቱ ፡ ወራሾች ፡ ለመተላለፍ ፡ አይችልም ።

(፪) ወራሾቹ፡ግን ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቁት ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ በፈ ጸመው ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ ጕድለት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በውርስ ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። የወራሾች ፡ ግዴታ ።

(፩) የአንድ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ሞግዚት ፡ ወራሾች ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ወዲያውኑ ፤ በቍጥር ፡ ፪፻፲ ፡ በተመለከተው ፡ በሕጉ፡ መሠረት ፡ ለሚቼ ፡ ምትክ፡ ሊሆን፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ማስታወቅ፡ ግዴታ፡ነው ። የዚህ፡ ዐይነት ፡ ሰው ፡ የሌለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚቼ ፡ ምትክ ፡ የሚመረጠውን ፡ ሰው ፡ እንዲያዝዙ ፡ ለዳኞች ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

(፫) የአሳዳሪው ፡ ወይም ፡ የሞግዚቱ፡ወራሾች ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባ፩እና፡ በ፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ የተጻፈውን ፡ ግዴታቸውን ፡ እስከሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ አላፊዎች ፡ ሆነው ፡ ይቈያሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፪፻፴፱ ። የሞግዚትነት ፡ ማስረጃ ።**

(፩) አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡አሳዳሪነቱን ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነቱን፡ የሚያስረዳለት ፡ ጽሑፍ ፡ ዳኞች ፡ እንዲሰጡት ፡ አሳዳሪው ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የውል ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ይህነኑ ፡ ጽሑፍ ፡ የውል ፡ ቤቱ ፡ ሹም፡ ለሞግዚቱ ፡ ወይም ፡ ለአሳዳሪው ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፵ ። ከሞግዚትነት ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ሁኔታ ።**

ሞግዚትነትን ፡ የሚመለከተው ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌ ፤ በተጨማሪ ፡ ሞግዚትና ፡ በምትክ ፡ ሞግዚትም ፡ ጕዳይ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ፡ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ አባሎችና ፡ ስለ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሞግዚት ።

### (ሀ) ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ የሚሆን ፡ አቋቋም ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፩ ። መሠረቱ ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው፡ልጅ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የሚሆኑት ፡ የልጁ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆችና ፡ አካለመጠን ፡ ያደረሱ ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡ ናቸው ።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ሰው ፡ የጉዲፈቻ፡(የማደጎ) ፡ ልጅነት ፡ ውል፡ ያለው፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ አባሎች ፡ የሚሆኑት ፡ የጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፪ ። የወላጆች ፡ አለመኖር ።**

አካለመጠን፡ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በአንድ ፡ የዝምድና ፡ መሥመር ፡ ውስጥ ፡ ወደ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ የሌሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አማካሪ ፡ አባሎች ፡ እንዲሆኑ ፡ የሚጠሩ ፡ ከአጎቶቹ ፡ ወይም ፡ ከአክስቶቹ ፡ በዕድሜ ፡ ታላቅ፡ የሆነው ፡ እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ ከዚሁ ፡ የዝምድና ፡ መሥመር ፡ ከተመራጮቹ ፡ እንደ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ የሆኑት ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፫ ። እናትና ፡ አባት ፡ በተፋቱ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሁኔታ ።**

አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ እናትና ፡ አባት ፡ ተፋትተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የሚሆኑት ፡ ከዚህ ፡ በላይ፡ ባሉት፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ዘመዶቹም ፡ በላይ ፡ የመፋታቱን ፡ ጕዳይ ፡ የወሰኑትም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጭምር ፡ ናቸው ።

BACK



**ቍ ፡ ፪፻፵፩ ። የአማካሪ ፡ አባሎች ፡ ተጨማሪነት ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ በመጨረሻ ፡ ኑዛዜው ፡ ላይ ፡ አንድ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የምክር ፡ አባሎች ፡ ሆነው ፡ በተጨማሪነት፡ እንዲሠሩ፡ ቃሉን ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) እናትም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ አላት ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፪ ። አባሎቹ ፡ ከምክር ፡ ውጭ ፡ ስለሚሆኑበት ፡ ጕዳይ።**

አባት ፡ ወይም፡ እናት፡ ከልጆቻቸው፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹ ፡ አካለመጠን፡ ላላደረሱት ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ወይም ፡ እኅቶቻቸው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ፡ አባል ፡ እንዳይሆኑ ፡ በመጨረሻ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃላቸው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፫ ። ተጨማሪ ፡ አባሎችን ፡ ስለ ፡ መምረጥ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አራት ፡ አባሎች ፡ ሳይኖሩት ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ አካለመጠን፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ፡ ጥቅም ፡ ከሚያስቡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ዘመዶች ፡ ወይም ፡ ባዕዶች ፡ ከሆኑት ፡ ውስጥ ፡ ተጨማሪ ፡ አባሎች ፡ ይመረጣሉ ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ አማካሪዎች ፡ ብዛታቸው ፡ ከሁለት ፡ ያላነሰ ፡ ከሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ አባሎችን ፡ ይመርጣሉ ።

(፫) ከሁለት ፡ ያነሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ሳይስማሙ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ አባሎችን ፡ የሚመርጠው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በሚኖርበት ፡ ቀበሌ ፡ ያለው ፡ የክፍል ፡ ሹም ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ቢሆን ፡ ጕዳዩ ፡ ይመለከተናል፡ የሚሉ ፡ ወገኖች ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ፡ የማቅረብ ፡ መብታቸው ፡ እንደ፡ተጠበቀ፡ ነው ።

## ለ) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ አባሎች ፡ ስብሰባ ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፬ ። በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሚደረግ ፡ ስብሰባ ።**

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ስብሰባ፡ የሚደረገው ፤ በሕጉ፡ መሠረት ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ አስቀድመው ፡ ካልተሰበሰቡ ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ካላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ በመጨረሻ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በአርባኛው ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፭ ። የአማካሪዎቹ ፡ ጥሪ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፤ ስብሰባ ፡ የሚያደርጉት ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ጥሪ ፡ ባደረጉላቸው ፡ ቍጥር ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም፡በተጨማሪው ፡ ሞግዚት ፡ ጠያቂነት ፡ ጥሪ ፡ ሊደረግላቸው ፡ ይቻላል ።

(፫) ተጨማሪ፡ሞግዚት፡ አልተሾመ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ማንኛውም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ አባል ፡ በሚያደርገው ፡ ጥያቄና ፡ ጥሪ ፡ አባሎቹ ፡ ሊሰበሰቡ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፱ ። የጊዜ ፡ ውሳኔ ።**

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ለመሰብሰብ ፡ እንዲችሉ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ ለስብሰባው ፡ አንድ ፡ ቀጠሮ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺ ። ጉባኤው ፡ የሚነጋገርበት ፡ ጉዳይ ።**

(፩) ለቤተ፡ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ከሚላከው ፡ መጥሪያ ፡ ጋራ ፡ የሚመከርበትና፡ ድምፅ ፡ የሚሰጥበት ፡ ጉዳይ ፡ ይላክላቸዋል ።

(፪) አካለመጠን፡ያላደሰረው ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የሚሰበሰበው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በጠቅላላው ፡ አደራረግ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ሁኔታ ፡ መርምሮና ፡ በሚከተሉትም ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ ተገቢዎች ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ በሥልጣኑ ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፩ ። የስብሰባው ፡ ቦታ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ስብሰባ ፡ የሚደረገው ፤ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በሚገኝበት ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) ዳኞች ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ጥያቄ ፤ አንድ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ያገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ፡ ስብሰባ ፡ ባንድ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እንዲሆን ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፪ ። ወጪ ።**

ለጥሪውና ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ በነዚሁ፡ የምክር ፡ አባሎች ፡ ኪሣራ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፫ ። በጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መመካከር ።**

ይህ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሞግዚቱ፡የቤተ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ስብሰባ ፡ ሳያደርግ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ የዚሁኑ ፡ ምክር ፡ አባሎች ፡ የየአንዳንዱን ፡ ሐሳብ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፵፱ ። ስለ ፡ አባሎች ፡ በስብሰባው ፡ መገኘት ፡ አለመቻል ፤ ወይም ፡ ወኪል ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ስብሰባ ፡ አባሎች፡ባንድ ፡ ስብሰባ ፡ ለመገኘት ፡ ያልቻሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ወይም ፡ የድምፃቸውን ፡ ብልጫ ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጽ ፡ ይችላሉ ።

(፪) በምክሩም ፡ ስብሰባ ፡ ሌላ ፡ ወኪል ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፪፻፶ ። አስፈላጊው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ብዛት ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ በስብሰባው ፡ ያሉት ፡ ወይም ፡ የሌሉት ፡ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ ድምፅ ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ብልጫ ፡ ተቈጥሮ ፡ ነው ።

(፪) ውሳኔዎቹም ፡ በአንድ ፡ ፕሮቴቬርባል ፡ ውስጥ ፡ ተጽፈው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ይፈርሙባቸዋል ።

(፫) አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ውሳኔውን ፡ ባጸደቁት ፡ በአብዛኞቹ ፡ አባሎች ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፩ ። የአሳዳሪውና ፡ የሞግዚቱ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ ምንም፡ አባሎች ፡ ባይሆኑም ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) አባሎች ፡ ባልሆኑም ፡ ጊዜ ፡ በምክሩ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ምክር ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ የውሳኔ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ አይኖራቸውም ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፪ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሁኔታ ።**

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ያላደሰረው ፡ ልጅ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፫ ። በምክር ፡ አባሎች ፡ ፈንታ ፤ ዳኞችን ፡ ስለ፡መተካት ። (፩) የድምፅ፡ብልጫ፡ ብዛት ፡ ስላለመኖሩ ።**

(፩) በአባሎቹ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ አለመስማማት ፡ ምክንያት ፡ አንድም፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ብዛት ፡ በምክሩ ፡ ስብሰባ ፡ ሊሰጥ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የምክሩ ፡ ስብሰባ ፡ ሊፈጽመው ፡ ያልቻለውን ፡ ውሳኔ ፡ ዳኞች ፡ ይወስናሉ ።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ፡ልጅ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ለዳኞች ፡ ነገሩን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንዲሁም ፡ ተጨማሪ፡ሞግዚት ፤ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ሞግዚት ፡ በሌለ ፡ ጊዜ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጕዳዩን ፡ ለዳኞች ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፱ ። (፪) አስቸኳይነት ።**

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤን ፡ ለመሰብሰብ ፡ አስቸጋሪ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ጥያቄ፡ በቤተ ፡ ዘመድ፡ ጉባኤ ፡ ፈንታ፡ ዳኞቹ ፡ ተተክተው ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ።

**ቍ ፡ ፯፻፷ ። አቤቱታ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር፡ጉባኤ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ በአንድ፡ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብ ፡ ይቻላል ።

(፪) አቤቱታውንም፡የልጁ፡ሞግዚት፡ወይም፡ተጨማሪ፡ሞግዚቱ፡ወይም፡ ማናቸውም፡የቤተ፡ዘመድ፡ምክር፡አባል፡የሆነ፡አንድ ፡ ሰው፡ ሊያቀርበው፡ይችላል።

## (ሐ) ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ሞግዚት ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፩ ። ምርጫ ።**

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ የተጨማሪ ፡ ሞግዚትን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ከአባሎቹ ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፪ ። የሞግዚቱ ፡ ተጠባባቂነት ።**

(፩) ተጨማሪውም ፡ ሞግዚት ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ፈንታ ፡ የሞግዚቱን ፡ ሒሳቦች ፡ ይቀበላል ።

(፪) በቤተ ፡ ዘመድ፡ጉባኤ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ተግባሮች ፡ አፈጻጸም ፡ ውስጥ ፡ ሞግዚቱን ፡ ይረዳል ።

(፫) ጠቃሚ ፡ መሆኑንም ፡ የገመተ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፫ ። ሞግዚትን ፡ ስለ ፡ መተካት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መርዳት ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ጥቅሞች፡ ተቃዋሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ጥቅሞች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሞግዚቱ ፡ ጥያቄ ፡ ተጨማሪው ፡ ሞግዚት ፡ ምትኩ ፡ ይሆናል ።

(፪) አካለ፡መጠን፡ ባላደረሱ ፡ በብዙ፡ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ መካከል ፡ ተቃራኒ፡ ጥቅም፡ ባለ ፡ ጊዜና ፡ ሞግዚቱም ፡ የእነዚሁ ፡ የኅብረት ፡ (የጋራ )፡ እንደራሴ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ጠያቂነት ፡ ተጨማሪው ፡ ሞግዚት ፡ ዋናውን ፡ ሞግዚት ፡ ይረዳዋል ።

## (መ) የወል ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፬ ። የሥራዎቹ ፡ አካሄድ ።**

(፩) ስለ ፡ ሞግዚት ፡ የሚሰጡት ፡ አስተያየቶች ፡ ለእነዚህም ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባልና ፡ የተጨማሪ ፡ ሞግዚት ፡ ሥራዎች ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ።

(፫) ለሞግዚትነት ፡ አለመቻልንና ፡ አለመገባትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ አባሎችና፡ በተጨማሪ ፡ ሞግዚት ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የአሳዳሪውና ፡ የሞግዚቱ ፡ ሥልጣን ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሰውነት ፡ አጠባበቅ ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፭ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ መኖሪያ ።**

(፩) አሳዳሪው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሚኖርበትን ፡ ቦታ ፡ ይወስናል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ያላሳዳሪው ፡ ፈቃድ ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ ለመተው ፡ አይችልም ።

(፫) ያለፈቃድ፡የራቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሳዳሪው ፡ እንዲመለስ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጤና ።**

(፩) አሳዳሪው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ጤና ፡ ይጠብቃል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የታመመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲድን ፡ አስፈላጊዎችን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ያደርግለታል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አስተዳደግ ።**

(፩) አሳዳሪው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ አስተዳደግ ፡ ይመራል ።

(፪) ያደረጋቸውን ፡ ጥፋቶች፡በማመዛዘንና ፡ አስተዳደጉንም ፡ በመጠበቅ ፡ አስተያየት ፡ ቀላል ፡ የሰውነት ፡ ቅጣቶችን ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። ግንኙነትና ፡ ደብዳቤ ፡ መጻጻፍ ።**

(፩) አሳዳሪው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ግንኙነቶች ፡ ይጠብቃል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሚላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፫) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሳዳሪው ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ወላጆቹን ፡ እንዳያይ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳይጻጻፍ ፡ መከልከል ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ጠቅላላ ፡ ትምህርትና ፡ የሞያ ፡ ትምህርት ።**

(፩) አሳዳሪው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ከችሎ

BACK



ታው ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይና ፡ ሙሉ ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ ትምህርትና ፡ የሞያ ፡ ትምህርትን ፡ እንዲያገኝ ፡ መትጋት ፡ አለበት ።

(፪) አሳዳሪውም ፡ ለዚሁ፡ትምህርት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ውሎች ፡ ጨርሶ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ፡የሞያ ፡ ትምህርትን ፡ እንዲያከናውን ፡ ይፈቅዳል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹ ። አካለመጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ። (፩) ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) አሳዳሪው፡አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ገቢ ፡ የሚሆነውን ፡ የግሉን ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ ለዚሁ ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ ያውለዋል ።

(፪) አሳዳሪውም፡ገንዘቡን ፡ ለምን ፡ አገልግሎት ፡ እንዳዋለው ፡ ለልጁ ፡ ማስታወቅ ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፩ ። (፪) ገቢ ፡ ስለሚሆን ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ።**

(፩) አካለመጠን፡ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ገቢ፡ገንዘብ፡ብዙ፡ የሆነ፡እንደ ፡ ሆነ ፡ አሳዳሪውም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ያልሆነ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተወሰነው ፡ ደንብ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ ምክር ፡ ቀሪ ፡ እንዲሆን ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ይህ ፡ ሲሆን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አካለመጠን ፡ ካላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ገቢዎች ፡ ላይ ፡ ለአጠባበቁና ፡ ለትምህርቱ ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ ወጪ ፡ በየዓመቱ ፡ ለአሳዳሪው ፡ የሚሰጥ ፡ አንድ ፡ የተቈረጠ ፡ ገንዘብ ፡ ይወስናል ።

(፫) አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ የገቢ ፡ ትርፎቹን ፡ ለዚሁ ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ ሞግዚቱ ፡ ተቀማጭ ፡ ያደርጋቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። (፫) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ሥራ ።**

አካለመጠን፡ያላደረሰው ፡ ልጅ፡ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ከሞላው ፡ በኋላ ፡ በሥራው ፡ ያገኛቸውን ፡ ገቢዎች ፡ ራሱ ፡ ይቀበላል ።
ለራሱ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ በነዚህ ፡ ገቢዎች ፡ ለማዘዝ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። (፬) በስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጡ ፡ ሀብቶች ።**

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሀብቶችን ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ የሚሰጥ ፡ ወይም ፡ የሚተው ፡ ሰው ፤ ልጁ ፡ አካለመጠን ፡ አደረሰ ፡ ድረስ ፡ የነዚሁ ፡ ገቢዎች ፡ ሀብቶች ፡ የማይነኩ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ለአሳዳሪው ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) በስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ውል ፡ እነዚህን ፡ የሀብት ፡ ገቢዎች ፡ ስለ ፡ ማስተዳደርና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ የተጻፉት ፡ ትእዛዞች ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

BACK



ቍ፡ ፪፻፷፬ ። (፭) ገቢዎቹን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መያዝ ።

(፩) አካለመጠን፡ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ የሀብት ፡ ገቢዎች ፡ አሳዳሪው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሊያስተላልፍ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ውል ፡ ሊገባባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) ከአሳዳሪውም ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ሊይዙት ፡ አይችሉም ።

ቍ፡ ፪፻፷፭ ። አባትነትን ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።

(፩) ዲቃላ ፡ ልጅን፡ለማወቅ ፡ ለመቀበል ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ፈቃድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) አካለመጠን፡ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በአሳዳሪው ፡ ፈቃድ ፡ ያደረገው ፡ ካልሆነ፡ በቀር ፡ ችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ እስከ ፡ ቈየበትና ፡ ችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ በቀረበት ፡ በተከታዩ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ የዲቃላ ፡ ማወቅ ፡ ቃል ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፫) ይህ፡የመሻር፡ መብት ፡ የግሉ ፡ ስለ ፡ ሆነ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ፡ ሊፈጽሙት ፡ አይችሉም ።

ቍ፡ ፪፻፷፮ ። የአባትና ፡ የእናት ፡ ሥልጣን ፡ ሥራ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) የልጅ፡ አባትና፡እናት ፡ የአሳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ ሁለቱም ፡ በተሰጣቸው ፡ ጊዜ ፤ ሥራውን ፡ የሚያከናውነው ፡ አባት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) አባትዬው፡በመራቁ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሐሳቡን ፡ ለመግለጽ ፡ በማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በእሱ ፡ ምትክ፡ ሥራውን፡ የምታከናውነው ፡ የልጁ ፡ እናት ፡ ናት ።

ቍ፡ ፪፻፷፯። (፪) ክርክር ።

(፩) የልጁን ፡ ሰውነት፡አጠባበቅ ፡ በሚነካ፡ጕዳይ ፡ በአባትና ፡ በእናት ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጁ ፡ እናት ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ዳኞች፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ትችላለች ።

(፪) እናት ፡ ካልሆነች ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ክርክር ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለቤተ፡ ዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

ቍ፡ ፪፻፷፰ ። ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ፡ማቅረብ።(፩) መሠረቱ ።

(፩) የልጁ ፡ አሳዳሪ ፡ ያደረጋቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ የልጁ ፡ ወላጅ ፡ በሆነ ፡ ወገን ፡ ጥያቄ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብባቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) ወላጅ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ማናቸውም ፡ አንድ ፡ አባል ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

ቍ፡ ፪፻፷፱ ። (፪) ስለ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እናት ፡ አሳዳሪነት ።

የልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ አሳዳሪ፡ሆኖ ፡ በሚያደርገው ፡ ውሳኔ ፡ ተቃዋሚ ፡ በመሆን ፡ አንዳችም ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብበት ፡ አይችልም ፤ አቤቱታ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ ግን ፡—

BACK



(ሀ) የልጁ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የተፋቱ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በልጁ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ አባትና ፡ እናት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሌላ ፡ ያገቡ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ግንኙነት ፡ አብረው፡ የኖሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰን ፡ ልጅ ፡ ሀብቶች ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ።

**ቍ ፡ ፪፻፶ ። መሠረቱ ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ በብሔራዊ ፡ ኑሮው፡ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ አካለ ፡ መጠንን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ እንደራሴ ፡ ነው ።

(፪) ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን፡ያላደረሰን ፡ ልጅ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅሞችንና ፡ ሀብቶቹን ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ መልካም፡ አባት ፡ በመሆን ፡ ሀብቶቹን ፡ ያስተዳድራል።

**ቍ ፡ ፪፻፶፩ ። የሀብት ፡ ዝርዝርና ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ መግለጫ ፡ መዝገብ ፡(እንቫንቴር) ።**

**(፩) ሞግዚቱ ፡ ሥራ ፡ ከጀመረ ፡ በኋላ ፡ ስለሚሆን ፡ ነገር ።**

(፩) ሥራ፡ከጀመረበት፡ ቀን፡ ቀጥለው ፡ በአሉት ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ሞግዚቱ ፡ ቢቻል ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ፡ ምክር ፡ ጉባኤ፡ መካከል ፡ የተመረጡ ፡ በቂ ፡ ምስክሮች፡በአሉበት ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰን ፡ ልጅ ፡ የሀብት ፡ ዝርዝርና ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ መግለጫ ፡ መዝገብ ፡ ያዘጋጃል ።

(፪) ሞግዚቱ፡ አካለመጠን፡ካላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ እንዳለው፡ በሀብቱ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገለጽ ፡ ካላደረገ ፡ ይቀርበታል ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፪ ። (፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ የደረሰ ፡ ውርስ ፡ (አወራረስ) ።**

(፩) አካለመጠን፡ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የደረሰውን ፡ ውርስ ፡ ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን፡ ስላላደረሰው፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ውርሱን፡ ከመቀበሉ፡ በፊት ፡ ቢቻል ፡ ከቤተ፡ ዘመድ፡ ምክር፡ አባሎች፡ መካከል፡ የሆኑ ፡ በቂ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ የሚወርሰውን ፡ የሀብት ፡ ዝርዝርና ፡ የዋጋ ፡ ግምት፡ መግለጫ ፡ (እንቫንቴር)፡ መዝገብ፡ አስቀድሞ ፡ ያዘጋጃል ።

(፪) ሞግዚቱ ፡ የመጠየቅ ፡ ሥልጣን ፡ መሻር ፡ እንዳይደርስበት ፡ ከዚህ ፡ ውርስ ፡ ውስጥ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ እንዳለው ፡ ሀብቱ፡ በተቈጠረበት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ፡ እንዲገለጽ ፡ ካላደረገ ፡ ይቀርበታል ።

(፫) የሀብቱ ፡ ዝርዝር ፡ ቍጥር፡ መዝገብ ፡ ጒድለት፡ ተገኝቶበት፡ አካለመጠን፡ ባላደረሰው ፡ልጅ ፡ ላይ ፡ ሊያደርስበት ፡ ለሚችለው ፡ ጉዳት ፡ ሞግዚቱ ፡ አላፊ ፡ ነው።

**ቍ ፡ ፪፻፹፫። የሞግዚቱና ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሀብቶች ፡ ስለ ፡ መደባለቅ ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው፣ልጅ ፡ ሀብቶች ፡ ከራሱ ፡ የግል ፡ ሀብቶች ፡ ጋራ ፡ እንዳይደባለቁ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) በተለይም ፡ አካለመጠን፡ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ገንዘብ ፡ ሞግዚቱ ፡ በራሱ ፡ በግል ፡ ሒሳብ ፡ እባንክ ፡ ማግባት ፡ ወይም ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ የተከለከለ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። እርግጠኛ ፡ በሆነ፡ በታመነ፡ ቦታ ፡ ሰነዶችንና ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን፡ ዕቃዎች፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።**

አካለመጠን፡ ላላደረሰ፡ ልጅ፡ ሀብቶች፡ አስተዳደር ፡ ችግር ፡ የማያመጣ ፡ ከሆነ፡ ሞግዚቱ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችን፤ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ዕቃዎችን ፤ ዋና ፡ ዋና ፡ ጽሑፎችን ፤ እነዚህንም ፡ የሚመሳሰሉ፡ ሌሎች ፡ ነገሮችን፡ እርግጠኛ ፡ በሆነ ፡ በታመነ፡ ቦታ ፡ ያስቀምጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፭። ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ።**

(፩) አባት፡ወይም ፡ እናት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ ሞግዚቱ፡ ሥራውን፡ ሲጀምር፡ ለቤተ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ አድርጎ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ፡ ሀብት ፡ ሁኔታ ፡ ያመለክታቸዋል ።

(፪) እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ሞግዚቱ ፡ የአስቸኳይነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸውን ፡ የአሳዳሪነት ፡ ሥራዎቹን ፡ ብቻ ፡ በመሥራት ፡ ተወስኖ ፡ ይቈያል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፮ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ የሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ፡ምክር፡ጉባኤ፡ከአባት ፡ ወይም ፡ ከእናት ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ሀብት ፡ አስተዳደር ፡ የሚመለከቱ ፡ ትእዛዞች ፡ ለሞግዚቱ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ሞግዚቱ፡አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ እንዳያደርግ፡ አንዳንዶችንም ፡ ነገሮች ፡ የሚፈጽመው ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ አስፈቅዶ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሊከለክለው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፯ ። አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ በስጦታ ፡ በኑዛዜ ፡ ወይም ፡ በውርስ፡ ክፍያ ፡ የሚደርሱት ፡ ሀብቶች ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ላላደረሰ፡ልጅ ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ሀብቶችን ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በውርስ ፡ ከእርሱ ፡ ለሚያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ እነዚሁን ፡ ሀብቶች ፡ ሲያስተዳድር ፡ ሞግዚቱ ፡ በአንዳንድ ፡ ደንቦች ፡ ተመርቶ ፡ እንዲሠራ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሊጽፍ ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ተከትሎ ፡ መሠራት ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡

BACK



ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ መስሎ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞቹ ፡ እንዲያሻሽሏቸው ፡ ሞግዚቱ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። የንግድ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ።**

(፩) በልጁ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት፡ላይ ፡ ካልሆነ፡ በቀር፡ አካለመጠን፡ ካላደረሰው፡ ልጅ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ፡ የንግድ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሥራ፡ ዎች ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ለሞግዚቱ፡ የእነ ዚህን ፡ ሥራዎች ፡ ሒሳብ ፡ የሚያጣራ ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ የሚቀጥል ፡ ለመ ሆኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ሞግዚትነቱ፡የሚቈይበትን ፡ ጊዜና ፡ የሞግዚቱን ፡ ችሎታ ዎችና ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለውን ፡ እንዲሁም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ጥቅሞች ፡ በሚገባ ፡ ይመለከታል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ሀብቶች ፡ ሽያጭ ።**

(፩) ሞግዚቱ፡አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሆኑትን ፡ ግዙፍ ፡ የሆኑ ፡ ተን ቀሳቃሽ ፡ ንብረቶችን ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ሰነድ ፡ መሸጥ ፡ ይች ላል ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ፡ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ላይ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፤ ይኸንኑ ፡ የሽያጭ ፡ አሠራር ፤ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ እን ዲያውም ፡ ሽያጩን ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸ ። ለአምጪው ፡ የሚል ፡ ሰነድ ።**

(፩) በልጁ ፡ አባት፡ወይም ፡ እናት ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረ ሰው ፡ ልጅ ፡ ገንዘብ ፡ ከሆኑ፡በኋላ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ ለአምጪው፡ የሚሉ ፡ ሰነዶችን ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ ስም ፡ በተጻፈባቸው ፡ ሰነዶች ፡ እንዲለ ወጡ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር፡ጉባኤ ፡ ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ነፃ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፩ ። ዕዳዎችና ፡ ገቢ ፡ ገንዘቦች ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን፡ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ዕዳዎች ፡ ይከፍላል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሚገቡትን፡ካፒታሎችና ፡ ሌሎች ፡ ገቢ ዎችን ፡ ተቀብሎ ፡ ለሚከፍለው ፡ ሰው ፡ የደረሰኝ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፪ ። ዋናውን ፡ (ካፒታሉን) ፡ ገንዘብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ።**

**(፩) የሞግዚቱ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ዋናዎቹ ፡ ገንዘቦች፡(ካፒታሎቹ) ፡ ከአምስት ፡ መቶ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የበ ለጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ካፒታሎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውላቸው ፡ ይገባል ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር፡ጉባኤ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተውን ፡ ለማሻሻል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፫ ። (፪) የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ካፒታሎቹ ፡ በሞግዚቱ ፡ እጅ ፡ ከገቡበት ፡ ጀምሮ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ሊያሻሽለው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፬ ። (፫) የሚገዙ ፡ ሀብቶች ፡ ዐይነት ።**

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሞግዚቱ ፡ የሚገዛውን ፡ ሀብቶች ፡ ዐይነት ፡ አስቀድሞ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፭ ።(፬) ቅጣት ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ በሥራ፡ ላይ ፡ ሳያውል ፡ የተዋቸውን፡ ገንዘቦች ፡ ደንበኛ፡ ወለድ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ተጨማሪ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፮ ። ገቢዎች ።**

(፩) ለአጠባበቁና፡ለአስተዳደጉ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውሉ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ገቢዎች ፡ ሞግዚቱ ፡ ላሳዳሪው ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) ይህ ፡ የሚሰጠውም፡በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በተወሰኑት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ጊዜዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) ይህን ፡ የመሰለ፡ውሳኔ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በየስድስቱ ፡ ወር ፡ በአሳዳሪው ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፯ ። የኪራይ ፡ ውሎች ።**

በቤተ ፡ ዘመድ፡ ምክር፡ ጉባኤ፡ ተፈቅደው፡ የተፈጸሙ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር፡ሞግዚቱ ፡ ያደረጋቸው ፡ የኪራይ ፡ ውሎች ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ አካለመጠን ፡ ካደረሰ ፡ በኋላ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አያስገድዱትም ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፰ ። ውርስ ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን፡ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በውርስ ፡ የደረሱትን ፡ ሀብቶች ፡ በዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ አስገብቶ ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ ሆኖ ፡ ይቀበላል ።

(፪) ይህ ፡ ውርስ ፡ በታወቀ ፡ አኳኋን፡ለአውራሹ ፡ ዕዳ ፡ የሚበቃ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡

BACK



አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በውርስ ፡ የደረሰውን ፡ ሀብት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ካልተፈቀደለት ፡ ሞግዚት ፡ ለመተው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። ስጦታ ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን፡ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ የተሰጠውን ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ስጦታ ፡ በቤተ፡ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ፡ ካልተፈቀደለት ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፪) ልማድ ፡ ለማስገደድ፡ ከሚችለው ፡ አነስተኛ ፡ ከሆኑ ፡ ስጦታዎች ፡ በቀር፡ ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ምንም ፡ ስጦታ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻ ። የዋስትና ፡ ውለታ ።**

ሞግዚቱ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ ዋስ ፡ መሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፩ ። ግልግል ።**

ሞግዚቱ ፡ ክርክር ፡ የሚደረግበት ፡ ጥቅም ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ጥቅሞች፡ በሚመለከት፡ ነገር ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ካልተፈቀደለት ፡ ምንም ፡ ግልግል ፡ ለመ ፈጸም ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፪ ። ሞግዚቱ፡ አካለመጠን ፡ ካላደረሰው ፡ ልጅ፡ ጋራ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ውሎች ።**

(፩) ሞግዚቱ፡በቤተ፡ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ካልተፈቀደለት ፡ በቀር፤ አካለመ ጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ሀብቶች ፡ ለመግዛት ፤ በኪራይ ፡ ውል ፡ ለመውሰድ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ካደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ ሌላ ፡ ውል ፡ ለመዋዋልም ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሞግዚቱ፡በቤተ፡ዘመድ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ካልተፈቀደለት ፡ በቀር ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ፡ የሚጠይቅበትን ፡ መብት ፡ ለመቀበል ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፫ ። ብድር ።**

ሞግዚቱ ፡ በቤተ፡ዘመድ፡ምክር፡ ጉባኤ፡ ካልተፈቀደለት ፡ በቀር ፡ አካለመጠን፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ የብድርን ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፬ ። አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ማማከር ።**

(፩) ጥፋትንና፡ልማትን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የቻለና ፡ ቢያንስ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱን ፡ በሚመለከቱት ፡ ዋና ፡

ዋና ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ማማከር ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) አካለመጠን ፡ ካላደረሰው፡ ልጅ ፡ ፈቃድ ፡ መቀበል ፡ ሞግዚቱን ፡ ከኀላፊነት፡ ነጻ ፡ አያደርገውም ።

**ቍ ፡ ፫፻፫ ። አካለመጠን፡ያላደረሰው፡ልጅ፡እንዲሠራ፡የተሰጠው ፡ ፈቃድ ። (፩)መሠረቱ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ዕድሜና፡የሀብቱን ፡ ልክ ፡ ተመልክቶ ፡ ለዕለት ፡ ጒዳይ ፡ በሚሆን ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ልጁ ፡ ብቻውን ፡ ውሎችን ፡ እንዲያደርግ ፡ ሞግዚቱ ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

(፪) ይኸውም ፡ ፈቃድ ፡ በዝምታም ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፬ ። (፪) የዕለት ፡ ጒዳይ ፡ ሥራዎች ።**

(፩) አንድ ፡ ሥራ ፡ በማናቸውም፡አኳኋን ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር፡ጉባኤ ፡ እንዲታይ ፡ ሕግ ፡ ሲያዝ ፡ የዕለት ፡ ጒዳይ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ ሊታይ ፡ አይቻልም ።

(፪) አንድ፡ሥራ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፤ ዋጋው ፡ ከመቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የሚበልጥ ፡ ወጪን ፡ ወይም ፡ ግዴታዎችን ፡ እንዲያደርግ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ የሚያስገድደው ፡ ሲሆን ፡ የዕለት ፡ ጒዳይ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ ሊታይ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፭ ። (፫) በሞግዚቱ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ውጤት ።**

በሞግዚቱ ፡ ፈቃድ ፤ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ላደረጋቸው ፡ የግዴታ ፡ ውሎች ፡ ሞግዚቱ ፡ ሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ ሰዎች ፡ ለሚጠይቁት ፡ ዋስ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፮ ። ኑዛዜ ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን፡ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ኑዛዜ ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ።

(፪) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው፡ ልጅ ፡ ዐሥራ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ከሞላው ፤ ኑዛዜ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

(፫) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ፡ ልጅ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላው ፡ ያደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ቢኖር ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ከሞላው ፡ በኋላ ፡ ኑዛዜውን፡ ባይሽረውም ፡ እንኳ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፯ ፤ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ሰዎች ፡ ጋብቻ ።**

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በጋብቻው ፡ ሲስማማ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በጋብቻ ፡ አንቀጽ ፡ ቍ ፡ ፭፻፹፪ ፡ የተመለከተው ፡ ሰው ፡ አብሮ ፡ መስማማት ፡ (ፈቃድ ፡ መስጠት) ፡ ይገባዋል ።

(፪) ለጋብቻ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ በእንደራሴ ፡ አማካይነት ፡ ለመስጠት፡ ይችላል ።

(፫) አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጋብቻ ፡ ፈቃጅነትን ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው፡

BACK



በዚህ ፡ ሕግ ፡ በጋብቻ ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፸፪ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ አንዳችም ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ፪፻፲ ። የሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ ወጪዎች ።**

ሞግዚቱ ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ጥቅሞች ፡ ለሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ወጪ ፡ ያደረገው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። የሥራው ፡ አካሄድ ፡ ማስረጃዎች ።**

(፩) ሞግዚቱ ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በወሰነው ፡ ሁኔታዎችና ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፡ በሞግዚትነቱ ፡ የሠራውን ፡ ማስረጃና ፡ ሒሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ የሞግዚትነትን ፡ ሥራዎች ፡ የሠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ነፃ ፡ ናቸው ።

(፫) እነርሱም ፡ የመረጡትን ፡ ሞግዚት ፡ ነፃ ፡ ሊያደርጉት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። መምራት ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፸፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፹ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሞግዚትነትና ፡ በሞግዚቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ በሚደረገው ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ለመጠበቅ ፡ የተመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ መጣስ ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሥራዎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፫ ። መሠረቱ ።**

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፬ ። እንዲፈርስ ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።**

(፩) እነዚህ ፡ ተግባሮች ፡ እንዲፈርሱ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ናቸው ።

(፪) በሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ከሚሻሻሉት ፡ በቀር ፤ በስሕተት ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፈቃድ ፡ ውል ፡ ፈራሽነት ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፭ ። የተዋዋዩ ፡ ቅን ፡ ልቡና ።**

አካለመጠን ፡ ካላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለ ፡ ሰው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ይህን ፡ እንዲያደርግ ፡ ፈቃድ ፡ የተቀበለ ፡ መሆኑን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ አምኖ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውም ፡ ልጅ ፡ የልማድ ፡ ዕውቀት ፡ ስለ

BACK



ሌለው፡ ተዋዋዩ ፡ የልጁን፡ ጥቅም ፡ በማስቀረት ፡ ያልተጠቀመበት፡ ከሆነ ፡ አካለ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ያደረጋቸው ፡ ውሎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፮ ። መክፈል ።**

(፩) አካለ፡መጠን፡ ያላደረሰውን፡ ልጅ ፡ የጠቀሙት ፡ ለመሆናቸው ፡ ማስረጃ ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ሥራው ፡ እንዲፈርስ ፡ ክስ ፡ እስከ ፡ ቀረበበት ፡ ቀን ፡ ድረስ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ ብልጽግና ፡ መጠን ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የሚደረጉ ፡ የገንዘብ ፡ መክፈሎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

(፪) ከዚህ ፡ ሁኔታ፡ ውጭ ፡ አካለ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው፡ልጅ ፡ መመለስ ፡ የለበትም።

**ቍ ፡ ፫፻፲፯ ። ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ።**

**(፩) መሠረቱ ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ፡መበልጸግ ፡ በተመለከተው ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡መሠረት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ብልጽግናን ፡ በመመልከት ፡ የተጠቀመ ፡ ሲሆን ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ኀላፊነት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፰ ። (፪) አካለመጠን ፡ ሳያደርስ ፡ አድርሻለሁ ፡ ማለት ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው፡ልጅ ፡ አካለመጠን ፡ አድርሻለሁ ፡ ብሎ፡ ቢናገርም፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ መናገሩ ፡ አካለመጠን ፡ ባለማድረሱ ፡ የሚጠቀምበትን ፡ መብት ፡ አያሳጣውም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆነ፡ኀላፊነትን ፡ የሚያመጣ ፡ ጥፋት ፡ ሆኖ ፡ አይቈጠርበትም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ። የሞግዚቱ ፡ ሥራዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፱ ። በደንብ ፡ የተፈጸሙ ፡ ሥራዎች ።**

(፩) ሥልጣኑ ፡ እስከሚፈቅድለት ፡ ወይም፡ፈቃድ ፡ ተቀብሎ ፡ ሞግዚቱ ፡ የፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ሊጣሉ ፡ አይቻልም ።

(፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰው፡ልጅ ፡ ሞግዚቱ ፡ የሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ልጁ፡ አካለመጠን ፡ በአደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ተቈጥረው፡ በኀላፊነት ፡ ያስጠይቁታል ።

(፫) ሞግዚቱ ፡ በተገለጸ፡አኳኋን ፡ በኀላፊነት ፡ እጠየቅበታለሁ ፡ ሲል ፡ ተስፋ ፡ የሰጠበትና ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ልጁ ፡ አካለመጠን ፡ ከአደረሰ ፡ በኋላም ፡ ሞግዚቱን ፡ ያስጠይቁታል ፡ ተብሎ ፡ የተደነገገ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሞግዚቱን ፡ ኀላፊ ፡ አያደርገውም ።

**ቍ ፡ ፫፻፳ ። ሕጋውያን ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።**

(፩) የሕግ ፡ ድንጋጌዎችን፡በመተላለፍ ፡ ሞግዚት ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ሥራዎች ፤ እንደራሴ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ እንደራሴነት ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ፈቃድን ፡ መቀበል ፡ በሕግ ፡ ግዴታ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ሳይፈቅድ ፡ ሞግዚቱ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ሥራዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ይሆናሉ ።

(፫) እንደዚሁም፡ደግሞ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር፡ ጉባኤ ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ፡ ሞግዚቱ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ሥራዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፩ ። ሕጋውያን ፡ ያልሆኑትን ፡ ትእዛዞች ፡ ስለ ፡ መተላለፍ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ለሞግዚቱ ፡ የሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፤ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ባስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ ካላወቁት ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ይገባቸው፡ ካልነበረ ፡ በቀር ፤ ሞግዚቱ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፍ ፡ የሠራው ፡ ነገር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) አካለመጠን ፡ ላላደረሰ፡ልጅ ፡ ንብረቶቹን ፡ የሰጠ ፡ የተናዘዘ ፡ ወይም ፡ የተወ ፡ ሰው ፡ ለሞግዚቱ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ባደረገለትም ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

(፫) ሞግዚቱ፡ያደረገው ፡ ሥራ ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሰው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ የሠራው ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፪ ። ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ሞግዚትና ፡ ስለ ፡ ምትክ ፡ ሞግዚት ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ በተጨማሪ ፡ ሞግዚትና ፡ በምትክ ፡ ሞግዚትም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

ሊያሲዙ ፡ የሚችሉ ፡ ኀላፊነቶች ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፫ ። ስለ ፡ ሞግዚት ።**

(፩) ሞግዚቱ ፤ በሠራው፡መጥፎ ፡ አመራር ፡ በመጽናቱ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የቤተ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ለሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ባለመታዘዙ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የእርሱ ፡ ጥቅም ፡ አካለመጠን፡ ካላደረሰ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ [illegible] በመሥራቱ ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳቶች ፡ ሁሉ ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

(፪) ሞግዚቱ ፡ በቤተ፡ዘመድ ፡ ጉባኤ ፡ በተሰጡት ፡ ትእዛዞች ፡ መሠረት ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፣ ተንኰል ፡ ካልተገኘበት ፡ በቀር ፡ በኀላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተጨማሪ ፡ ሞግዚትና ፡ በምትኩ ፡ ሞግዚትም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፳፬ ። ስለ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሞግዚት ።

ተጠባባቂው ፡ ሞግዚት ፣ አንዳች ፡ ጥፋት ፡ አለመሥራቱን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር፣ በሞግዚቱ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈረደው ፡ ነገር ፣ በአንድነት ፡ ኀላፊነት ፡ ዋስ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፳፭ ። የሁኔታ ፡ ሞግዚት ።

(፩) ሞግዚት፡ሳይሆን ፣ የሞግዚትነትን ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፣ በሥራ ፡ አካሄድ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፣ ስለሚያካሂደው ፡ ሥራ ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃል ፡—

(፪) ሞግዚት ፡ ሳይሆን፡በሠራው ፡ ሰው ፡ በሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ሞግዚቱ ፡ ባንድነት ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፳፮ ። ስለ፡ሞግዚቲቱ ፡ ባል ።

ሞግዚቱ ፡ ሆና ፣ ከሞግዚትነቷ ፡ ጋራ ፡ በተያያዘ ፡ ሥራ ፡ የተደረገውም ፡ ተጋብተው ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፣ የሞግዚቲቱ ፡ ባል ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ በሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ባንድነት ፡ ኀላፊነት ፡ ዋስ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፳፯ ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ።

(፩) የማታለል ፡ ነገር ፡ ካልተገኘባቸው ፡ በቀር ፣ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ በሚሠሩዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ አንዳች ፡ ኀላፊነት ፡ የለባቸውም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፣ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፣ ቃለ ፡ ጉባኤውን ፡ (ፕሮሴቬርባልን) ፡ ሲፈርሙ ፣ አባሎቹ ፣ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የተጠሩ ፡ ለመሆኑና ፡ ውሳኔውንም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሰጡ ፡ መሆናቸውን ፡ በኀላፊነት ፡ ያረጋግጣሉ ።

ክፍል ። ፰ ።

አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ስለ ፡ መቅረቱ ።

ቍ ፡ ፫፻፳፰ ። ምክንያቶች ።

አካለመጠንን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አካለመጠን ፡ ሲያደርስ ፡ ወይም ፡ ከሞግዚት፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ ይውጣ ፡ ሲባል ፣ ችሎታ ፡ የለውም ፡ መባሉ ፡ ይቀራል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ ስለ፡መውጣት ።

ቍ ፡ ፫፻፳፱ ። ጋብቻ ።

አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በጋብቻው ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ በሞግዚት ፡ ከመተዳደር ፡ ነፃ ፡ ይወጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፫፻፴ ። በተለይ ፡ በሞግዚት ፡ ከመተዳደር ፡ ነፃ ፡ ማውጣት ፡ (፩) ምክንያቶች።**

(፩) አካለመጠን፡ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሲሞላው ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ ይቻላል ።

(፪) ለዚሁም፤የቤተ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥበት ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፩ ። ጥያቄ ።**

ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ የቤተ፡ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፤ ወይም ፡ አሳዳሪው ፤ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡ ባቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፪ ። ጥያቄውን ፡ ስላለመቀበል ።**

አካለመጠንን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ አባትና ፡ እናት፡ ያሉት ፡ እንደ፡ሆነና ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፤ ልጁ ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ለመውጣት ፡ በቅቷል ፡ ብሎ ፡ ፈቃዱ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ካልተናገረ ፡ በቀር ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ልጁ ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ይውጣ ፡ ሲል ፡ ለመወሰን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፫ ። ውጤቶች ።**

ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ይውጣ ፡ ተብሎ ፡ የቀበየነለት ፡ ልጅ ፡ ሰውነቱን ፡ ለማስተዳደርና ፡ ገንዘቡን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጥቅሞች ፡ ለማስተዳደር ፡ ስለሚመለከተው፡ ስለ፡ማናቸውም፡ ነገር ፡ ሁሉ ፤ በሕግ ፡ አካለመጠን ፡ እንዳደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። የማይሻር ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ከሞግዚት፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ይውጣ ፡ ተብሎ ፡ የተበየነው ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ።

(፪) ከጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ የተገኘው፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ መውጣት ፡ ጋብቻው ፡ ቢፈርስም ፡ እንኳ ፤ ውጤቱን ፡ እንደ፡ጠበቀ ፡ ይቀራል ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፤ ከተጋቡት ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ ለጋብቻ ፡ የተወሰነው ፡ ሕጋዊ ፡ ዕድሜ ፡ ባለመድረሱ ፡ ምክንያት ፤ ዳኞች ፡ ጋብቻው ፡ ይፈርሳል ፡ ሲሉ ፡ የፈረዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለተባለው ፡ ነገር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## የሞግዚትነት ፡ ሥራ ፡ ሒሳቦች ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፫ ። መሠረቱ ።**

(፩) የሞግዚትነቱ፡ሥራ ፡ ሲፈጸም ፤ ሞግዚት ፡ ሆኖ ፡ ለአስተዳደረው፡ልጅ፡ወይም፡ ለወራሾቹ ፡ የአስተዳደረበትን ፡ የሥራ ፡ ሒሳብ ፡ ማስረጃዎች ፡ ሞግዚቱ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) የልጁን ፡ ንብረት፡ሁሉ ፡ ይመልስለታል ። ሞግዚት ፡ የሆነበትን ፡ የልጁን ፡ መብትና ፡ ሁኔታ ፡ የሚገደድባቸውንም ፡ ዕዳዎች ፡ ያስታውቀዋል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። የንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ አለመግባት ።**

(፩) ሞግዚቱ ፤ ሥራዎቹን ፡ በያዘ፡ጊዜ ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ በውርስ ፡ ሀብት ፡ በተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ የንብረቶቹን ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ከማግባት ፡ ቸል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የልጁን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ልጁ ፡ በውርስ ፡ ያገኘውን ፡ ሀብት ፡ በማናቸውም ፡ አደራረግ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን፡አስረጂ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ በቂ ፡ ምስክሮች ፡ በሚያረጋግጡት ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ንብረት ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ገንዘብ ፡ በመሆን ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፭ ። ሒሳቦችን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ።**

(፩) በሞግዚት፡የሚተዳደረው ፡ ልጅ ፡ የሞግዚትነቱን ፡ ሥራ ፡ ሒሳቦች ፡ ያጸደቀ፡ እንደ፡ ሆን፡ሒሳቦቹን ፡ ካጸደቀ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፤ አጽድቆት ፡የነበረውን ፡ ሒሳብ ፡ ራሱ ፡ ሊያፈርሰው ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የሚቻለው ፡ ልጁ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላው ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

(፪) በሞግዚት፡የሚተዳደረው ፡ ልጅ ፡ ሒሳብ ፡ እንዳይቀርብ ፡ ለሞግዚት ፡ ፈቃድ፡ ቢሰጠውም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን፡ልጅ ፡ አካለመጠን ፡ ያደረሱት ፡ ሲወርሱት ፤ እነዚህ ፡ አካለመጠን ፡ ያደረሱት ፡ ወራሾች ፡ የልጁ ፡ ሞግዚት ፡ ያደረገውን፡ሒሳብ፡ ያጸደቁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱን ፡ ከመተሳሰብ ፡ ነፃ ፡ አውጥተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሁለቱ ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች፡ ለመጠቀስ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፮ ። ስለ ፡ ይርጋ ።**

(፩) አካለመጠን ፡ ያላደረሰው፡ልጅ ፤ ወኪሎቹ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ በሞግዚትነቱ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ በሞግዚቱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚያቀርቧቸው ፡

ማንኛዎችም ፡ ክሶች ፤ ሞግዚቱ ፡ የሞግዚትነቱን ፡ ሥራ ፡ ከተወበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ፡እስከ፡አምስት፡ ዓመት፡ ሳያቀርቡ፡ የቀሩ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በይርጋ ፡ይታገዳሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ንብረቶች ፡ እንዲመለሱለት ፡ የመጠየቅ ፤ ወይም ፡ በማይገባ ፡ በተደ ረገው ፡ (በተገኘው)፡ ብልጽግና ፡ ላይ፡ የሚሆነው ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ አይከለከልበትም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## አእምሮዋቸው ፡ ስለ ፡ ጐደለ ፡ ሰዎችና ፡ ስለ ፡ ድውዮች ።

### ቍ ፡ ፫፻፴፱ ። ትርጓሜ ።

(፩) አእምሮው፡ጐደሎ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ በተፈጥሮ፡ዕውቀቱ፡ያልተስተካከለ ፡ በመሆኑ ፤ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ መናወጥ ፡ ወይም ፡ በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ የሚ ሠራው ፡ ሥራ ፡ የሚያደርሰውን ፡ ለማወቅ ፡ የማይችል ፡ ነው ።

(፪) የአእምሮ፡ ደካሞች፡ ሰካራም፡ ወይም፡ በመጠጥ ፤ አፍዛዥ ፡ በሆኑ ነገሮች ፡ ልማድ ፡ የተመረዙና ፡ ገንዘብን ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ የሚያባክኑ ፡ ሰዎች ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አእምሮዋቸው ፡ እንደ፡ጐደለ ፡ ሰዎች ፡ ይቈጠራሉ ።

### ቍ ፡ ፫፻፵ ። ድውዮች ።

ድዳ ፤ደንቆሮ ፤ ዕውር ፤ የሆኑና ፡ ነዋሪ ፡ በሆነ ፡ ደዌ ፡ ምክንያት ፤ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ለመተዳደር ፡ ወይም ፡ ንብረታቸውን፡ ለማስተዳደር፡ ችሎታ፡ ለሌላቸው ፡ ሰዎች፤ ስለ፡አእምሮ ፡ ጐደሎዎች፡ የተነገሩትን፡ እርዳታዎች፡ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ችሎታ ፡ ስላልተከለከሉት ፡ የአእምሮ ፡ ጐደሎዎችና ፡ ድውዮች ።

### ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። በግልጽ ፡ ስለ፡ ታወቀ ፡ የአእምሮ ፡ ጕድለት ፤ (፩) የተዘጋበት ፡ ዕብድ ።

ዕብደቱ ፡ በግልጽ፡ እንደ፡ታወቀ፡ ሆኖ ፡ ሕግ ፡ የሚቈጥረው ፡ ይህ ፡ የተባለው፡ ሰው ፡ በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ የዕብዶች ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ፡ ወይም፡ በአእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በአንድ ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተዘግቶበት ፤ በዚህ ፡ በተዘጋበት ፡ ቦታ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። (፪) ስለ፡ ገጠር ፡ የቀበሌ ፡ ግዞቶች ።

እንዲሁም ፡ ከሁለት ፡ ሺህ ፡ የማያንሱ ፡ ነዋሪዎች ፡ በሚገኙባቸው ፡ የቀበሌ ፡ ግዞቶች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ አብሮዋቸው ፡ በሚኖር ፡ ሰዎች ፡ በኩል ፤ በአእምሮው ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ የግድ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ተጠ

BACK



ባባቂነት ፡ የሚደረግለት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝና ፡ ከእርሱ፡ጋራ ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ በተ ባለው ፡ ሁኔታው ፡ ምክንያት ፡ ለመዛወሩ ፡ ፈቃድ ፡ ወሰን ፡ ሰጥተውት ፡ ሲገኙ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ዕብደቱ ፡ በግልጽ ፡ እንደ፡ታወቀ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ዕብድ ፡ ስለሚሠራቸው ፡ ሥራዎች ። (፩) መሠረቱ።

(፩) ዕብደቱ ፡ ግልጽ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሠራቸውን ፡ ሥራዎች ፡ እርሱ ፡ ወይም ፡ ወኪሎቹ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ ሊቃወሟቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፡ አንድ፡ሰው ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ለመተዳደር ፡ ወይም ፡ ንብረቶቹን ፡ ለማስተዳደር ፡ ችሎታ ፡ የሚያሳጣው ፡ ድውይነቱ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተጻፈው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፬ ። (፪) በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሚሆን፡አስረጂ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሥራና፡ፈቃድ፡ የውለታን ፡ ፈራሽነት ፡ የሚያስከትል ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚ ገመት ፡ ነው ።

(፪) በስሕተት ፡ መገኘት ፡ ምክንያት ፡ የሥራዎችንና ፡ የውሎችን ፡ መፍረስ ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፵፭ ። ስለሚመጣው ፡ ኀላፊነት ። (፩) የሥረ ፡ ነገሩ ፡ ደንቦች ።

ዕብድ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከእርሱ፡ጋራ ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ በመፍረሳቸው ፡ ምክ ንያት ፤ በቅን ፡ ልቡና ፡ በተዋዋዮች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፮ ። (፪) ስለ ፡ ማስረጃ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ አለ ፡ በመባል ፡ ይገመታል ።

(፪) ስለሆነም፡ ሦስተኛ፡ወገኖች ፡ ማናቸውንም፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ቢያቀርቡም፡ እንኳ፡ ዕብድ ፡ የሆነው፡ ሰው ፡ ባለበት ፡ አንድ፡ ቀበሌ፡ ውስጥ ፤ ወይም ፡ በዚሁ፡ ቀበሌ ፡ አዋሳኝ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ለመሆናቸው ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፵፪ ፡ የተመለከተው ፡ ነገር ፡ ሲያጋጥም ፤ በክፉ፡ ልቡና ፡ ያደረጉት ፡ ለመሆናቸው ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፵፯ ። ዕብደቱ ፡ በግልጽ ፡ ስላልታወቀ ፡ ሰው ።

(፩) የዕብደቱ፡ ሁኔታ፤ በግልጽ ፡ ያልታወቀ፡ ሰው፡ የፈጸማቸው ፡ የሕግ ፡ ሥራ ዎች ፡ ውሎች ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ የአእምሮ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ሊሻሩ ፡ አይ ችሉም ።

BACK



(፪) ዕብድ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ እነዚህን ፡ ውሎች ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፤ ጉድለት ፡ የሌለበትን ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠት፡ በማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ እንደ፡ነበረ ፡ ለማስረዳት፡ ከቻለ ፡ ውሎቹን ፡ ለማስፈረስ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፰ ። ስለ ፡ ወራሾችና ፡ ስለባለገንዘቦች ። (፩) መሠረቱ ።**

ዕብደቱ ፡ በግልጽ፡ያልታወቀው ፡ ሰው፡ ወራሾች ፡ ወይም፡ ባለገንዘቦች ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ለፈጸመው ፡ ውል ፡ ጉድለት ፡ የሌለበት ፡ ፈቃድ ፡ ቃል ፡ አልሰጠበትምና ፤ ውሉ ፡ ሊፈርስ ፡ ይገባዋል ፡ ሲሉ ፡ ዕብደቱን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፤ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፱ ። (፪) ልዩነት ።**

(፩) ስለ፡ሆነም ፤ የዚህ፡የውል ፡ አድራጊው ፡ የአእምሮ ፡ ጉድለት ፡ ከተደረገው፡ የውል ፡ ቃል ፡ የተነሣ፡ የሚታወቅ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር፡ የተነገረው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ውል፡አድራጊው ፡ ውል ፡ እንዳይፈጽም ፡ የክልከላ ፡ ጥያቄ ፡ ቀርቦበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥያቄው ፡ የቀረበው ፤ የተባለው ፡ ውል ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ዳኞቹ ፡ ስለ፡ክልከላው፡ በቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት፡ ከመቻላቸው ፡ በፊት፡ ውል ፡ እንዳያደርግ ፡ ይከልከል ፡ ተብሎ ፡ ጥያቄ፡ የቀረበበት ፡ ሰው ፡ ቀደሞ ፡ ካልሞተ ፡ በቀር ፡ የተባለው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

**ቍ. ፫፻፶ ። ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) ዕብደቱ ፡ በግልጽ ፡ ለታወቀው ፡ ሰው ፡ ያለበት ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ኀላፊነት ፡ ለጤናማ ፡ ሰው ፡ እንዳለው ፡ ኀላፊነት ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ይህ፡ዕብድ፡ ያለ፡አግባብ ፡ ካገኘው ፡ ብልጽግና ፡ የተነሣ ፡ ላሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ጤናማ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ያሉበት ፡ ግዴታዎች ፡ ይኖሩበታል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በፍርድ ፡ ስለሚደረግ ፡ ክልከላ ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። ስለ፡ክልከላ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ።**

(፩) መከልከሉ፡ለጤናውና ፡ ለጥቅሙ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ዕብድ ፡ ሰው፡ እንዲከለከል ፡ ( እንዲጠበቅ ) ፡ ዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፤ ስለ፡ ዕብዱ፡ሰው ፡ ወራሾች ፡ ጥቅም ፡ ዳኞች ፡ የዕብዱን ፡ መከልከል ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፤ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፵ ፡ በተመለከቱት ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ የመከልከል ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፪ ። ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ዕብድነትን ፡ ስለማስታወቅ ።**

(፩) ዳኞቹ ፡ ስለ፡አንዳንድ፡ሰው ፡ መከልከል ፡ ፍርዳቸውን ፡ ሲሰጡ ፤ በሚሰጡት፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ ጊዜውን ፡ በመወሰን ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ዕብደት ፡ የጀመረው፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው፡ኀይለ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ ስለ፡ክልከላው ፡ ከተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በኋላ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

(፫) በተሰጠው ፡ ውሳኔ፡ውስጥ ፡ የተቈረጠው ፡ ቀን ፡ ስለ፡ክልከላው፡ ከቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በፊት ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፫ ፡ ለክልከላው ፡ ስለሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።**

(፩) ስለ፡ክልከላው፡ውሳኔ፡ እንዲሰጥ ፤ ዕብድ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ ድውዩ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፤ ወይም ፡ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከሥጋ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የክልከላው ፡ ፍርድ ፡ የሚከለከለው ፡ ሰው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ከማድረሱ ፡ በፊት ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

(፫) ስለሆነም ፡ እንዲከለከል፡ጥያቄ ፡ የቀረበበት ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የክልከላ ፡ ፍርድ ፡ አይሰጥም ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፬ ። ስለ ፡ ክልከላው ፡ አደራረግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) ዳኞቹ ፡ የአንዱን፡ሰው ፡ መከልከል ፡ ከመፍረዳቸው ፡ በፊት ፤ ይህን ፡ ክልከላ ፡ ለማድረግ ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ መረዳት ፡ አለባቸው ።

(፪) እንዲከለከል ፡ ጥያቄ፡የቀረበበትን ፡ ሰው ፡ እነርሱ ፡ ራሳቸው ፡ ሳያዩት ፡ እንዲከለከል ፡ አስቀድመው ፡ ለመፍረድ ፡ አይችሉም ።

(፫) ይከልከል ፡ የሚባለው፡ሰው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ለመቅረብ ፡ የማይቻለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞቹ ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱን ፡ በመላክ ፤ ወይም ፡ አንዱን ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ በመላክ ፡ ነገሩን ፡ ይመራመራሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፭ ። አቤቱታ ።**

አእምሮው ፡ ጐደሎ፡ ወይም፡ድውይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፤ ከባልና ፡ ሚስት፡ ደኅነኛው ፤ ከሥጋ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ፡ ዘመዶቹ፡ አንዱ ፤ ወይም ፡ ዐቃቤ፡ ሕግ ፤ ዳኞቹ ፡ ስለ፡ክልከላ ፡ በሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፮ ። በፍርድ ፡ የተከለከሉ ፡ ሰዎች ፡ መዝገብ ።**

(፩) በፍርድ፡ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ የክልከላ ፡ ፍርድ ፡ የተፈረደባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ የያዘ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ መዝገብ ፤ በያንዳንዱ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ መኖር ፡ አለበት ።

(፪) መዝገቡም፡ሰዎቹ ፡ የሚለዩባቸውን ፡ ማስታወቂያዎችና ፡ ክልከላውን ፡ ስለ ሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የተሰጡትን ፡ ፍርዶች ፡ የሚገልጹ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ብቻ ፡ ይጻፉበታል ።

(፫) መዝገቡን ፡ ባለጕዳይ፡የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሊመለከተው ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፶፪ ። ፍርዱን ፡ ስለ፡ማስታወቅ ።</u>

(፩) የተከለከለው ፡ ሰው፡በሚኖርበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በሚኖር ባቸው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፤ ወይም ፡ ተቀማጭ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖርበት፡በተጠራ በት ፡ ስፍራ ፡ ለሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፤ አሳሳቢ ፡ በመሆን ፡ የሚሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ የሚያስታውቅ ፤ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ ነው ።

(፪) ደግሞ ፡ የክልከላውን ፡ ውጤቶች፡ ስለ፡መለዋወጥ፡የሚሰጠውን ፡ ማናቸው ንም ፡ ፍርድ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ፡ተነገረው ፡ የሚያስታውቅ፡ አሳዳሪው ፡ ነው።

<u>ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስለሚደረገው ፡ ጥበቃ ።</u>

ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ ለተከለከ ለው ፡ ሰው ፡ የሚደረገው ፡ ጥበቃ ፡ አካለመጠን ፡ ስላላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ሰውነትና ፡ ንብረቶች ፡ አጠባበቅ ፡ በተሰጠው ፡ ደንብ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፶፬ ። ስለ ፡ አሳዳሪና ፡ ስለ ፡ ሞግዚት ።</u>

(፩) ለተከለከለው፡ሰው፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት፡ የሚሆኑትን ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ የሚሾሟቸው ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

(፪) ከባል ፡ ወይም፡ከሚስት ፡ ወደ፡ ላይ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ወላጆቹ ፡ ወይም ፡ ከተወ ላጆቹ ፡ ልጆች ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ የዕብዱን ፡ ሰው ፡ የአሳዳሪነትን ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነትን ፡ ሥራ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ይዞ ፡ ለመኖር ፡ አይገደድም ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፶፭ ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ። (፩) ስለ፡አቋቋሙ ።</u>

(፩) አካለመጠን፡ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ የቤተ ፡ ዘመድን ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ስለሚ መለከት ፡ ጕዳይ ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ ተከለከ ለው ፡ ሰው ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

(፪) በተከለከለው፡ሰው ፡ ምክር ፡ ጉባኤ፡ የሚገኙት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላ ጆቹ ፡ አካለመጠን ፡ ያደረሱ ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፤ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስትና ፡ አካለመጠን ፡ ያደረሱት ፡ ተወላጆቹ ፡ ናቸው ።

(፫) በዚህ ፡ አኳኋን፡የተቋቋመው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አራት ፡ አባ ሎች ፡ ያልተገኙበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞቹ ፡ ለዚህ ፡ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ ዕድል፡ አሳቢ ፡ ከሆኑት ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወይም ፡ ዘመዶቹ ፡ ካልሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ጠርተው ፡

የጐደለውን ፡ የአባሎቹን ፡ ቍጥር ፡ ይሞላሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፭ ። (፪) የስብሰባው ፡ ቦታ ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ መሰብሰቢያ ፤ ዳኞቹ ፡ በወሰኑት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ቦታ ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ለምክር ፡ የሚሰበሰብበት ፤ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ የክልከላው ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ በሚገኝበት ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ላይ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፮ ። የተከለከለው ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ።**

(፩) የተከለከለው ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፤ ይህ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፤ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ለመሆኑ ፡ በሕግ ፡ መሠረት፡ ማስታወቂያ ፡ በወጣበት፡ ቦታ ፡ ተቀማጭ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ መጠባበቅ ፡ አለበት ።

(፪) የተከለከለው ፡ ሰው ፡ መኖሪያ ፡ ቦታውን ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አሳዳሪው ፤ እንዲደረግ ፡ የሚጠይቀው ፡ ማስታወቂያ ፡ በአዲሱ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ እንዲነገር ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፯ ። ስለ፡ተከለከለው ፡ ሰው ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ።**

(፩) የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፤ የአሳዳሪው ፡ ሀብት ፡ አይሆንም ።
(፪) ከእነዚህ ፡ ገቢ ፡ ገንዘቦች ፡ ስለ ፡ ተከለከለው ፡ ሰው ፡ አኗኗር ፡ በተለይ ፡ ለሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ ለመዳኛው ፡ መዋል ፡ አለባቸው ።
(፫) አሳዳሪው ፡ ገንዘቡ ፡ የዋለበትን ፡ ሒሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፰ ። አሳዳሪው ፡ ባደረጋቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ ባደረጋቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ አቤቱታ ፡ ሊያቀርብላቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። የተከለከለው ፡ ሰው ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ።**

አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ሞግዚት ፤ አባቱ ፡ ወይም ፡ እናቱ ፡ ሲሆኑ ፡ ስለእነሱ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ የሚሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ ሞግዚት ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

**ቍ ፡ ፫፻፸ ። የኪራይ ፡ ውል ።**

ሞግዚት ፡ ያደረጋቸው ፡ የኪራይ ፡ ውሎች ፤ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ ፈቃድ ፡ ካልተደረጉ ፡ በቀር ፤ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ የችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ ሁኔታ ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ የሚያስገድዱት ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፯ ። ስጦታዎች ።**

(፩) የተከለከለው፣ ሰው፡ ሞግዚት ፤ በዚህ ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስም ፤ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ ተወላጆች ፡ ልጆች ፡ ስጦታ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚህ ፡ ስጦታዎች ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ፡ የተፈቀዱ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፰ ፡ ኑዛዜ ።**

(፩) የተከለከለ፡ ሰው፡ ክልከላው ፡ በፍርድ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ ኑዛዜ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

(፪) ከተከለከለበት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ የተናዘዘው ፡ ኑዛዜ ፡ ይጸናል ።

(፫) ነገር፡ ግን፡ የኑዛዜው ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለርትዕ ፡ ነገር ፡ ተቃራኒ ፡ መስለው ፡ ለዳኞቹ ፡ የታዩዋቸው ፡ እንደ፡ሆነና፡ የተናዘዘውም ፡ የጤናው ፡ ሁኔታ ፡ ያስደረገው፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ዳኞቹ፡ ኑዛዜውን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ፈራሽ ፡ ሊያደርጉት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። ጋብቻ ።**

(፩) በፍርድ ፡ የተከለከለ፡ ሰው፡ ዳኞች ፡ ካልፈቀዱለት ፡ በቀር ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ አይችልም ።

(፪) ስለዚህ፡ ጉዳይ ፡ የሚቀርበውን፡ ጥያቄ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ አሳዳሪው ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

(፫) ማንኛውም፡ ባለጥቅም፡ ሁሉ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ከዳኞች ፡ ሳያስፈቅድ ፡ ያደረገው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፸ ። ስለ ፡ ፍችና ፡ ልጅን ፡ ስለ፡መካድ ።**

(፩) ፍቺ ፡ ወይም፡ ከሕግ፡ ውጭ ፡ የሚደረገው ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ እንዲቀር ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፤ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያሳዳሪውም ፡ ፈቃድ ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) የተከለከለ፡ ሰው፡ ልጅን፡ የሚክድበት፡ ሁኔታ፡ በዚህ፡ ሕግ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጾ ፡ ተመልክቷል ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፩ ። የክልከላን ፡ ውጤቶች ፡ ስለ፡ማጥበብ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ዳኞች ፡ የክልከላን፡ ፍርድ ፡ ሲሰጡ ፤ ወይም፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ የክልከላውን ፡ ውጤቶች ፡ ለማጥበብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ለተከለከለው፡ ሰው፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ውሎች ፡ እንዲያደርግ ፡ ሊፈቅዱለት ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚሁም ፤ ከተከለከለው፡ሰው ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አንዳንዶችን ፡ ውሎች ፡ ሞግዚቱ ፡ ለብቻው ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ፡ ሲሉ ፡ ዳኞቹ ፡ ለመከልከል ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፹፪ ። (፪) የማጥበቡ ፡ ውጤቶች ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ፡በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ ሞግዚት፡ የተደረገው ፡ የሥልጣን ፡ ማጥበብ ፤ ከሞግዚቱ ፡ ጋራ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለተዋዋሉ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን፡አስረጂ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እንደ፡ ተዋዋሉ ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ፫፻፹፫ ። የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስላደረጋቸው ፡ ውሎች ፡ ፈራሽነት ።

(፩) የተከለከለው፡ሰው ፡ የፈጸማቸውንና ፡ ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ያደረጋቸውን፡ ሥራዎች ፡ ለመቃወም፡ በሚቻልበት ፡ አኳኋን ፡ ለመቃወም ፡ ይቻላል ።

(፪) አእምሮው ፡ የጐደለ፡ሰው ፤ አእምሮው ፡ መለስ ፡ ባለለት ፡ ጊዜ ፡ የፈጸማቸው ፡ ውሎች፤ናቸው ፡ በማለት ፤ ዳኞቹ ፡ የእነዚህን ፡ ውሎች ፡ ውጤት ፡ ለማጽደቅ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፫፻፹፬ ። የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ሞግዚት ፡ ስላለበት ፡ ኀላፊነት ፡ (፩) መሠረቱ ።

የተከለከለው ፡ ሰው ፤ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ከማያውቅ ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ውል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ በመፍረሱ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ በቅን ፡ልቡና ፡ በተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ የተከለከለው ፡ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

ቍ ፡ ፫፻፹፭ ። (፪) ቅን ፡ ልቡና ።

ከተከለከለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ ውል ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ክልከላው ፡ በተገለጸበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ የሚፈርመው ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እንዳደረገው ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፫፻፹፮ ። ስለ፡መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ኀላፊነት ።

(፩) የፍርድ ፡ ቤቱ፡ የመዝገብ፡ ቤት፡ ሹም ፡ ስለ፡ክልከላ ፡ የተሰጠውን ፡ የፍርድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፤ የተከለከለውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በተለይ ፡ ስለዚሁ ፡

BACK



ጉዳይ ፡ በተዘጋጀው ፡ መዝገብ፡ ውስጥ ፡ ሳያገባ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ፡ ኀላ ፊነት፡ የተከለከለው፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም፡ ይሆናል ።

(፪) ከተከለከለው፡ ሰው፡ ጋራ፡ የተዋዋለውን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መዝገብን ፡ እን ዳያይ ፡ የከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ እንደዚሁ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፸፯ ። ስለ ፡ ክልከላው ፡ መቅረት ፡ (መነሣት) ። (፩) ስለሚቀርበው ፡ ጥያቄ ።

(፩) ስለ፡ክልከላ፡ የተሰጠው፡ ፍርድ ፡ ሲሻር ፡ የችሎታ ፡ ማጣት፡ፍጻሜ ፡ ይሆናል።

(፪) አእምሮው ፡ ከጐደለው፡ ሰው፡ በቀር ፡ ስለ፡ክልከላው፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ለመ ጠየቅ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የክልከላው ፡ ውሳኔ ፡ እንዲቀር ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚሁም፡ የተከለከለው፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፤ የክልከላው ፡ ውሳኔ ፡ እንዲቀር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፸፰ ። (፪) ውሳኔ ።

ክልከላው ፡ እንዲወሰን ፡ ያስደረጉት ፡ ምክንያቶች ፡ በቀሩ ፡ ጊዜና ፡ የተከለከለ ውም ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ ለመምራትና ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የክልከላውን ፡ ውሳኔ ፡ ማስቀረት ፡ ማንሣት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፸፱ ። (፫) ውጤቶች ።

የክልከላው ፡ ውሳኔ ፡ መቅረት ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ መውጣት ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## በሕግ ፡ ስለ ፡ ተከለከሉ ፡ ሰዎች ።

ቍ ፡ ፫፻፹ ። ትርጓሜ ።

(፩) በሕግ፡ የተከለከለ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ የተቀጣ ፡ ሰው ፡ በመቀጣቱ ፡ ምክ ንያት ፡ ንብረቶቹን ፡ እንዳያስተዳድር ፡ ሕግ ፡ የከለከለው ፡ ነው ።

(፪) አንድ፡ ሰው ፡ በሕግ፡ እንደ፡ተከለከለ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠርባቸው፡ ሁኔታዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ተወስነዋል ።

ቍ ፡ ፫፻፹፩ ። በሕግ ፡ ስለሚወሰነው ፡ ክልከላ ፡ አስተዳደር ።

ከዚህ ፡ ቀጥለው፡ ባሉት፡ ድንጋጌዎች ፡ ከተወሰኑት ፡ መለያየቶች፡ በቀር ፡ በሕግ፡ የሚደረገው፡የክልከላ ፡ አስተዳደር ፡ በፍርድ ፡ ከሚሰጠው፡ የክልከላ ፡ አስተዳደር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፹፪። አሳዳሪ ፡ ስላለመኖሩ ።

በሕግ ፡ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፫፻፹፫። ስለ ፡ ሞግዚት ። (፩) ስለ ፡ መመረጡ ።

(፩) በሕግ ፡ የተከለከለው፡ሰው ፡ የንብረቶቹ ፡ አስተዳደር ፡ ዳኞች ፡ ለመረጡት ፡ ሞግዚት ፡ ይሰጣል ።

(፪) ዳኞች፡ የመረጡት፡ ሞግዚት ፡ ወይም ፡ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከተከለከለው ፡ ሰው ፡ ዘመዶች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በሚያቀርቡት፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ በሞግዚቱ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ሞግዚት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፫፻፹፬ ። ሥራዎቹን ፡ መቀበል ፡ በፈቃድ፡ ስለ፡መሆኑ ።

(፩) በሕግ፡ የተከለከለውን፡ ሰው ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራዎች ፡ መቀበል ፡ የፈቃድ ፡ ነው ።

(፪) እነዚህን፡ ሥራዎች፡ ፈቅዶ ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፤ ዳኞቹ ፡ በሚያመዛዝኑት ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ በእርሱ ፡ ምትክ፡ሌላ ፡ ሞግዚት ፡ እንዲተካለት ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፫) ሥራዎቹን፡አምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ አካሂዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሞግዚቱ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ መቀበል ፡ ያስፈልጋል።

ቍ ፡ ፫፻፹፭ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ።

በፍርድ ፡ ክልከላ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ የተሰጠው፡ ሥልጣን ፡ በሕግ ፡ ሲደረግ ፡ ዳኞች ፡ ይሠሩበታል ።

ቍ ፡ ፫፻፹፮ ። በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ስላሉት ፡ ሥራዎች ።

(፩) በሕግ፡ ክልከላ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ጋብቻን ፡ ለማድረግ ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ ዲቃላ ፡ ልጅን ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ለማወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚሁም፡ ፍቺን፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ልጅን ፡ ለመካድ ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፤ ክስን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፫) ሞግዚቱ፡ በሕግ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫፻፹፯። የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ሥራዎች ፡ ፈራሾች ፡ ስለ፡ መሆናቸው ።

(፩) በሕግ፡ የተከለከለው፡ ሰው ፡ ያደረጋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ውሎች ፡ ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

(፪) እነዚህ፡ ሥራዎች፡ እንዲፈርሱ ፡ ሥራው ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሚደረገው ፡ አኳኋን ፡ በሕግ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፤ ከእርሱ፡ጋራ ፡ የተዋዋለው ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፫፻፹፰ ። ስለ ፡ ክልከላው ፡ ፍጻሜ ።**

በሕግ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ ማጣትን ፡ ያስከተለበትን ፡ ቅጣት ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነበት ፡ ክልከላ ፡ ቀሪ ፡ ይሆንለታል ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## ስለ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፱ ። እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ መቈጠር ።**

(፩) በፍትሐ፡ ብሔር ፡ መብቶች፡ የመሥራትንና ፡ የመጠቀም ፡ ችሎታን ፡ በሚመለከት ፡ ረገድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል።

(፪) እንደ፡ ፍትሐ፡ ብሔር ፡ መብቶች ፡ የሚቈጠሩትም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ወይም ፡ ከአገሩ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ተካፋይ ፡ መሆንን ፡ የማይመለከቱ ፡ ማናቸውም ፡ መብቶች ፡ ናቸው ።

(፫) የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፺ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ባለሀብትነትን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ የተጠበቁ ፡ ሁኔታዎች ፡ (፩) መሠረቱ ።**

ማንኛውም፡ የውጭ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ከንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ በሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፩ ። (፪) እንዲሸጥ ፡ ስለ ፡ ማስገደድ ።**

ማንኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፺ ፡ በተመለከተው ፤ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው፡ ባለሥልጣኖች ፡ በ፮ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ርስቱን ፡ ለኢትዮጵያዊ ፡ እንዲያስተላልፍ ፡ ሊያስገድዱ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፪ ። (፫) ቅጣት ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተወሰነው ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የውጭ ፡ አገሩ ፡ ዜጋ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለአንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሳያስተላልፍ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱ ፡ በመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጠያቂነት ፡ ተይዞ ፡ ይሸጣል ።

(፪) ስለማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መሸጫ ፡ ለተደረገው፡ ወጪና ፡ ደንብን ፡ በመተላለፍ ፡ ለተደረገው ፡ ሥራ ፡ መቀጫ ፡ የሚሆን ፡ ከመቶ ፡ ሐያ ፡ ተቀንሶ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ለውጭ ፡ አገሩ ፡ ሰው ፡ ይመለስለታል።

(፫) የውጭ፡ አገሩ፡ ሰው፡ የማይንቀሳቀሰውን፡ ንብረት ፡ ባለሀብትነት ፡ ያገኘው ፡ በወራሽነት፡ ምክንያት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተቀናሹ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ብቻ ፡ ነው።

**ቊ ፡ ፫፻፺፫ ። ከባለሀብትነት ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ መብቶች ።**

አንድ ፡ የው ጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከኀምሳ ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰው ፡ በዕ ድሜ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የመገልገል ፡ ወይም ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ የሚያገኝባቸው ፡ ወ ሎች ፡ ሁሉ ፡ የማ ይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ባለሀብትነት ፡ እንደሚያስተላልፉ ፡ ወ ሎች ፡ ይቈጠ ራሉ ።

## አንቀጽ ፡ ሦስት ።

## በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ንብረቶች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅቶችና ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

**ቊ ፡ ፫፻፺፬ ። መንግሥት ።**

(፩) መንግሥት ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁ፡እንደ ፡ መሆኑ ፡ መንግሥቱ ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቶቹ ፡ አማካይነት ፡ ከተ ፈጥሮው ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊያገኝና ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፫፻፺፭ ። የመንግሥቱ ፡ ግዛት ፡ ክፍሎች ።**

(፩) ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፤ አውራጃዎች ፤ ወረዳዎች ፤ ምክትል ፡ ወረዳዎች ፡ የከተ ማና ፡ የገጠር ፡ ቀበሌዎች ፡ እንዲሁ ፡ በሕግ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸውና ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁ ፡ እንደ፡መሆናቸው ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቶቻቸው ፡ አማካይነት ፡ በአስተ ተዳደር ፡ ሕጎች ፡ የተፈቀዱትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊያገኙና ፡ ሊሠሩባቸው ፡ ይችላሉ ።

**ቊ ፡ ፫፻፺፮ ። ሚኒስቴሮች ።**

(፩) የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ፡ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በሕግ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸውና ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁ ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቶቻቸው ፡ አማካይነት ፡ በአስተ ዳደር ፡ ሕጎች ፡ የተፈቀዱትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊያገኙና ፡ ሊሠሩባቸው ፡ ይች ላሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፯ ። የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ።**

እንዲሁም ፡ ማንኛዎቹም ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ በአስተዳደር ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተለይ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸውና ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፰ ። የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።**

(፩) የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ በሕግ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ አንድ፡ ሰው ፡ የምትቈጠር ፡ ናት ።

(፪) እንዲህ፡ እንደ ፡ መሆኗ ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቶቿ ፡ አማካይነት ፡ በአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ የተፈቀዱትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ልታገኝና ፡ ልትሠራባቸው ፡ ትችላለች ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፱ ። የጳጳስ ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ።**

በአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ ሁኔታዎችና ፡ ወሰኖች ፡ በተሰጡ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት፡ የኦርቶዶክሳዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክፍል ፡ የሆኑ ፡ የጳጳስ ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፤ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸውና ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፬፻ ። የሥራጮና ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶቹ ፡ ተግባር ፡ ሥልጣን ፡ የሚደርስበት ።**

(፩) የአስተዳደር፡ ሕጎች፤ ከዚህ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱትን ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጧቸውን ፡ ድርጅቶች ፡ የያንዳንዱ ፡ ተግባር ፡ ሥልጣን ፡ የሚደርስበትን ፤ እንዲሁም ፡ ከነዚሁ ፡ ድርጅቶች ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የተመረጡትን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ሕጎቹም ፡ አንዳንድ፡ ሥራዎችን፡ ለማስፈጸም ፡ እነዚህን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች፤ የሁኔታዎችን ፡ ወይም ፡ የተወሰኑትን ፡ ፎርሞች ፡ አፈጻጸም ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፩ ። ሕጋዊ ፡ ትእዛዞችን ፡ ስላለመፈጸም ።**

(፩) በሕግ ፡ የታወቀላቸው፡ የተግባር፡ ሥልጣን ፡ ከሚዘረጋበት ፡ ውጭ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ የተገደዱትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ ፎርም ፡ ባለመፈጸም ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከቱት ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ የሚፈጽሟቸው ፡ ሥራዎች ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

(፪) እንደዚሁ፡ ሕጉ፡ በነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ሥራዎቹ ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ ባይናገርም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፪ ፡፡ ፈራሽነት ፡፡**

(፩) ከዚህ፡በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር፡ የተመለከተውን ፡ ፈራሽነት ፡ ማንኛውም ፡ ባለ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ፡፡

(፪) ሥራው ፡ ከተፈጸመበት፡ ጊዜ፡ ጀምሮ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፈራሽነቱ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ፬፻፫ ፡፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡፡**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ፡ የተጠቀሱት፡ ድርጅቶች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለ ሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ በተ ወሰኑት፡ ሕጋውያን፡ ደንቦች፡ መሠረት፤ በመሥሪያ ፡ ቤቶቻቸው፡ ወይም ፡ በሠራ ተኞቻቸው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ተግባር ፤ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ፡፡

(፪) እንደዚሁ ፡ ድርጅቶቹ ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ ሕጋውያን ፡ ደንቦች ፡ መሠ ረት ፡ ያላግባብ ፡ ያገኙትን ፡ ብልጽግና ፡ መመለስ ፡ አለባቸው ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፡፡

## ስለ ፡ ማኅበሮች ፡፡

**ቍ ፡ ፬፻፬ ፡፡ ትርጓሜ ፡፡**

ማኅበር ፡ ማለት ፡ ትርፎችን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም፡ ለመከፋፈል ፡ ሳይሆን ፤ አንድ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት፡ በሁለት፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች፡ መካከል ፡ የሚቋቋም ፡ ስብ ሰባ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፬፻፭ ፡፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡፡**

(፩) ትርፎችን፡ ለማግኘት፡ ወይም ፡ ለመካፈል፡ የተቋቋሙ ፡ ስብሰባዎች ፤ በንግድ ፡ ሕግ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚመሩ ፡ ናቸው ፡፡

(፪) የአባሎቻቸውን፡ የገንዘብ፡ ጥቅም ፡ ለማበርከት ፡ ቁጠባ ፡ (ኤኰኖሚ) ፡ እንዲ ያደርጉ ፡ በመፍቀድ ፡ በመተባበር ፡ አብሮ ፡ መሥራት ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ስብሰ ባዎች ፡ በግልጽ ፡ ማኅበር ፡ ደንቦች ፡ ይመራሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፬፻፮ ፡፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ (ሰንዲካ) ፡፡**

(፩) የአባሎቻቸውን ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ለመከላከል ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የተቋቋሙ ፡ ስብሰባዎች ፤ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮችን ፡ (ሰንዲኮችን) ፡ በሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ የሚመሩ ፡ ናቸው ፡፡

(፪) እነርሱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ፡ ሕጎች ፡ ባይኖሩም ፡ እነዚህ ፡ ስብሰባዎች ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ማኅበሮች ፡ ተገምተው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ሕጋውያን ፡ ደንቦች ፡ የሚመሩ ፡ ይሆናሉ ፡፡

BACK



ቍ ፡ ፬፻፯ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ስብሰባዎች ፡

(፩) ከኢትዮጵያ ፡ አርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፤ ሃይማኖቶችና ፡ ማኅበሮች ፡ የሚተዳደሩት ፡ እነዚሁኑ ፡ በሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ነው ፡፡

(፪) እነርሱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ እንደሌሉ ፡ እነዚህ ፡ ስብሰባዎች ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ማኅበሮች፡ ተገምተው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች፡ የሚመሩ፡ ይሆናሉ ፡፡

ክፍል ፡ ፩ ፡፡

ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፎችና ፡ ስለ ፡ ውስጥ ፡ ደንቦች ፡፡

ቍ ፡ ፬፻፰ ፡ የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡፡

(፩) ማኅበሩ ፡ በመሥራቾቹ ፡ መካከል፡በሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ በአንድ ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚመራ ፡ ነው ፡፡

(፪) የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ የማያመለክት ፡ ወይም ፡ ከደንቦቹ፡ አንዱ ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚሟሉ ፡ ወይም ፡ የሚተኩ ፡ ይሆናሉ ፡፡

ቍ ፡ ፬፻፱ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ እንዲኖር ፡ የመስማማት ፡ ግዴታ ፡፡

(፩) ከማኅበረተኞቹ፡ አንዱ፡ ጥያቄ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ እንዲኖሩት ፡ ያስፈልጋል ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ ማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ይኑረው ፡ ተብሎ ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፤ ማኅበሩ ፡ ሥራውን ፡ በሚያካሂድበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሊያቀርበው ፡ ይቻላል ፡፡

(፫) ጥያቄው ፡ ከተደረገ፡ በኋላ፡ በሦስት ፡ ወር፡ ውስጥ ፡ ማኅበሩ ፡ የውስጥ፡ ደንቦችን ፡ ሳያዘጋጅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይቻላል ፡፡

ቍ ፡ ፬፻፲ ፡ የውስጡ ፡ ደንብ ፡ መኖር ፡ ውጤት ፡፡

(፩) ማኅበሩ፡ የውስጥ፡ ደንብ ፡ ሲኖረው ፡ የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ፡፡

(፪) ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ማኅበሩ ፡ የሚመራው ፡ በውስጡ ፡ ደንብ ፡ ይሆናል ፡፡

(፫) የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ የማያመለክት ፡ ወይም ፡ ከደንቦቹ ፡ አንዱ ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የውስጥ ፡ ደንቡ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚሟላ፡ ወይም ፡ የሚተካ ፡ ይሆናል ፡፡

· ፡ **፩፻፲፩ ። የደንቦቹ ፡ ፎርምና ፡ የሚጸፉባቸው ፡ ነገሮች ።**

(፩) የማኅበሩ፡ የውስጥ፡ ደንብ ፡ ፈራሽነትን ፡ እንዳያስከትል ፤ የማኅበሩን ፡ ስም ፤ ዓላማውን ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚገኝበትን ፡ ቦታና ፡ የተቋቋመበትን ፡ ቀን ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መሥራቾች፡ ተብለው፡ የተመረጡ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ማኅበረተኞች ፡ ይፈርሙበታል ።

· ፡ **፩፻፲፪ ። ዐይነተኛ ፡ የሆኑትን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መቀበል ።**

(፩) የውስጥ፡ ደንቦቹ፡ በአገር፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የተፈቀደውን ፡ የውስጥ ፡ ደንብ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ መፈረሙ ፡ አስ ፈላጊ ፡ አይደለም ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ በመጥቀስና ፡ ሁለት ፡ ማኅበረተኞች ፡ የፈ ረሙበት ፡ ልዩ ፡ ጽሑፍ ፡ ካለ ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፫) ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ፈራሽነትን ፡ እንዳያስከትል ፤ የማኅበሩን ፡ ስም ፤ ዓላማውን ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚገኝበትን ፡ ቦታና ፡ የተቋቋመበትን ፡ ቀን፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

ነ ፡ **፩፻፲፫ ። የውስጡን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።**

የማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የሚጠቅሰው ፡ ልዩ ፡ ጽሑፍ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ በጠ ቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ።

ነ ፡ **፩፻፲፬ ። የውስጥ ፡ ደንቦችን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

(፩) ለማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጥያቄ ፡ በማቅረብ ፡ የማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ለባለጉዳዩ ፡ ሁሉ ፡ ሳይዘገዩ ፡ እንዲተላለፉ ፡ መደረግ ፡ አለባቸው ።

(፪) የውስጥ፡ ደንቦቹ፡ የተላለፉበት፡ ቀን፡ በተላለፈው ፡ ግልባጭ ፡ ላይ ፡ ይጻፋል ።

(፫) አስፈላጊ ፡ ከሆነ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹን ፡ በፖስታ ፡ ለመላክ ፡ ስለሚደርሰው ፡ ወጪ ፡ በተወሰነው ፡ ታሪፍ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ ለማስከፈል ፡ ይችላል።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ማኅበረተኞች ።

ኍ ፡ **፩፻፲፭ ። ማኅበረተኛነት ።**

ማኅበሩ ፡ መሥራቾቹና ፡ በዚሁ ፡ ማኅበር ፡ የገቡ ፡ አባሎች ፡ ያሉበት፡ይሆናል ።

ኍ ፡ **፩፻፲፮ ። አዲስ ፡ አባሎች ።**

ተቃራኒ ፡ ደንብ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ማኅበሩ ፡ አዲስ ፡ አባሎች ፡ ለማስገባት ፡ ይች ላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፩፻፲፯ ። ለመግባት ፡ ተስፋ ፡ መስጠት ።**

በአንድ ፡ ማኅበር ፡ ለመግባት ፡ ተስፋ ፡ መስጠት ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፲፰ ። የማኅበረተኞቹ ፡ ትክክለኛነት ።**

በማኅበሩ፡ መመሥረቻ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፩፻፲፱ ። ማኅበረተኛነቱ ፡ የግል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ማኅበረተኛነት ፡ ተላልፎ ፡ የማይሰጥ ፡ ነው ።

(፪) ለማኅበረተኛውም ፡ ወራሾች ፡ አያልፍም ።

(፫) የመመሥረቻው፡ ጽሑፍ፡ ወይም ፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ እነዚህን ፡ ውሳኔዎች ፡ ሊያፈርሱ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፩፻፳ ። በማኅበረተኛነት ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ መሥራት ። (፩) ስለ ፡ መወከል ።**

የመመሥረቻው፡ ጽሑፍ፡ ወይም ፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌላቸው ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የማኅበረተኛነቱን ፡ መብቶች ፡ ባንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፩፻፳፩ ። (፪) የመዋጮ ፡ አከፋፈል ፤ ማኅበረተኞቹ ፡ በየጊዜው ፡ ስለሚከፍሉት ፡ ድርሻ ።**

ማኅበረተኛው ፡ አስቀድሞ ፡ ለመክፈል ፡ የሚገባውን ፡ መዋጮ ፡ ለማኅበሩ ፡ ካልከፈለ ፡ በቀር ፡ ማናቸውንም ፡ የማኅበረተኛነቱን ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፩፻፳፪ ። (፫) አከፋፈል ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ውሳኔ፡ ከሌለ፡ በቀር ፡ የሚከፈለው ፡ ድርሻ ፡ በየዓመቱ፡ መጀመሪያ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ስለ ፡ ድርሻው ፡ ገንዘብ፡ አከፋፈል፡ ስላለፈው ፡ ዓመትና ፡ ስላለበት፡ ዓመት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፩፻፳፫ ። ከማኅበረተኛነት ፡ የመውጣት ፡ መብት ።**

(፩) ማናቸውም፡ ማኅበረተኛ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩ ፡ ለአንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜም ፡ የተቋቋመና ፡ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ በነፃ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

(፪) ከማኅበሩ፡ የሚወጣው፡ ማኅበረተኛ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ያለፉትን ፡ መዋጮዎችና ፡ ያለበትንም ፡ ዓመት ፡ ድርሻ ፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፬፻፷፬ ። ማኅበረተኛውን ፡ ስለ ፡ ማስወጣት ።

(፩) ማኅበረተኛው፡ በመመሥረቻው፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ከማኅበሩ ፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ።

(፪) ከነዚህ፡ ሁኔታዎች፡ ውጭ ፡ ለማስወገድ ፡ ትልቅ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኛውን ፡ ዋናው ፡ ጉባኤ ፡ ከማኅበሩ ፡ ሊያስወግደው ፡ ይችላል ።

(፫) የተወገደው ፡ ማኅበረተኛ ፡ መወገዱ ፡ ከተነገረው ፡ በኋላ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መወገዱ ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፷፭ ። ማኅበረተኞቹ ፡ በማኅበሩ ፡ ሊወከሉ ፡ ስላለመቻሉ ።

ማኅበሩ ፡ ስላከናወናቸው ፡ ነገሮች ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ የግዴታ ፡ ኀላፊነት ፡ አያገኛቸውም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሥራው ፡ አመራር ።

ቍ ፡ ፬፻፷፮ ። ዲሬክተሮችን ፡ ስለ ፡ መሾም ።

(፩) ማኅበሩ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በተቋቋመበት ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በተሾሙ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ዲሬክተሮች ፡ ይመራል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዲሬክተሮችን ፡ የሚሾማቸው ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። አባልነት ።

ተቃራኒ፡ ውሳኔ፡ ከሌለ፡ በቀር ፡ ዲሬክተሮች ፡ የሚመረጡት ፡ ከማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፷፰ ። የሥራ ፡ አመራር ፡ ምክር ፡ ቤት ።

(፩) ብዙ፡ ዲሬክተሮች፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በሚገኙት ፡ በአሉት ፡ ወይም ፡ በተወከሉት ፡ አባሎች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ማኅበሩን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚወስነው ፡ ይህ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፫) በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ በተደረገው ፡ ውሳኔ ፡ የማይስማሙት ፡ ማኅበረተኞች ፡ አለመስማማታቸውን ፡ በአንድ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ውስጥ ፡ ለማጻፍ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፬፻፳፱ ። የዲሬክተሮቹ ፡ ሥልጣን ። (፩) ሕግ ።**

(፩) የማኅበሩ፡ ዲሬክተሮች፡ ለማኅበሩ ፡ አመራር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማሉ ።

(፪) ዲሬክተሮቹ፡ ከፍርድ ፡ ሥራ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ ግንኙነትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ሥራ ፡ ውጭ ፡ የማኅበሩ ፡ እንደራሴዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፬፻፴ ። (፪) የውስጥ ፡ ደንቦች ።**

(፩) የውስጥ፡ ደንቦቹ፡ የዲሬክተሮችን ፡ ሥልጣኖች ፡ ለመወሰን ፡ ወይም ፡ እነዚሀ ፡ ሥልጣኖች ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራባቸው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ደንቦቹ፡ በማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ያወቁ ፡ መሆናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደንቦቻቸው ፡ ለሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ መከራከሪያ ፡ ሊሆኑባቸው ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፩ ። (፫) የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ።**

(፩) የማኅበሩ፡ መመሥረቻ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡የማኅበሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ፡ የዲሬክተሮችን ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስኑባቸው ፡ ወይም ፡ እነዚህ ፡ ሥልጣኖች ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራባቸው ፡ ሁኔታውን ፡ የሚቈርጡባቸው ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያወቁ ፡ መሆናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለሦስተኛ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑባቸው ፡ አይችሉም ።

(፪) ደንቦቹን ፡ መተላለፍ ፤ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ፡ ለማኅበሩ ፡ የዲሬክተሩን ፡ ወይም ፡ የዲሬክተሮቹን ፡ ኀላፊነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፪ ። ለጊዜው ፡ የሚሠራ ፡ ዲሬክተር ።**

ለማኅበሩ ፡ እንዲሠሩ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሌሉ ፡ ወይም ፡ መሰናክል ፡ ያገኛቸው ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ባለጕዳይ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ለጊዜው፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ ዲሬክተር ፡ ዳኞች ፡ ይመርጣሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፫ ። ችሎታን ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ።**

(፩) በማኅበሩ፡ ስም፡ እንዲሀ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ችሎታቸውንና ፡ ሥልጣናቸውን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጽሑፍ ፡ ከማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህም፡ ጽሑፍ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ተግባሮቹ ፡ ለስንት ፡ ጊዜ ፡ እንዲቈዩ ፡ እንደ ፡ ተሰጣቸው ፡ ለይቶ ፡ ያመለክታል ።

BACK



ቊ ፡ ፬፻፴፬ ፡ የዲሬክተሮች ፡ ኀላፊነት ።

የማኅበሩ ፡ ዲሬክተሮች ፡ በውክልና ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በዚህ ፡ ማኅበር ፡ በኩል ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

ቊ ፡ ፬፻፴፭ ። የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብትን ፡ ስለ፡ማስወገድ ።

ተቃራኒ፡የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ሒሳባቸውን ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ በዲሬክተሮች ፡ ኀላፊነት ፡ የተደረገውን ፡ ለመደንገግ ፡ በሚደረገው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ዲሬክተሮች ፡ በዚሁ ፡ ጉባኤ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብቶቻቸውን ፡ ሊሠሩባቸው ፡ አይችሉም ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ።

ቊ ፡ ፬፻፴፮ ፡ የመጨረሻ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የማኅበረተኞቹ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ለማኅበሩ ፡ የበላይ ፡ የመጨረሻ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው ።

(፪) በሌላው ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ያልሆኑትን ፡ የማኅበሩን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ይወስናል ።

ቊ ፡ ፬፻፴፯ ። ዲሬክተሮችን ፡ ስለ ፡ መሾምና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል፡ ቃል፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ዲሬክተሮችን ፡ ይሾማል ፤ ሥራቸውን ፡ ይቈጣጠራል ፤ ሒሳባቸውንም ፡ ያጸድቃል ።

(፪) ስለ፡ማኅበሩም፡ አመራር፡ የሚመለከቱትን፡ ትእዛዞች፡ ሊሰጣቸው ፡ ይችላል።

ቊ ፡ ፬፻፴፰ ። ዲሬክተሮችን ፡ ስለ፡መሻር ።

(፩) እንደ ፡ ስምምነቱ ፤ የሥራ ፡ ድካም ፡ ዋጋ ፡ መብታቸው ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ዲሬክተሮችን ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፪) ዲሬክተሮች፡ ግዴታዎቻቸውን፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ሕገ ፡ ወጥነት ፡ እንደ፡ማፍረስ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ ነገሮች ፡ በደንበኛው ፡ ለመምራት ፡ ችሎታ ፡ እንደ ማጣት ፡ የሆኑ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ የመሻር ፡ መብት ፡ ለማስወገድም ፡ ሆነ ፡ ለመቀነስ ፡ አይፈቀድም ።

ቊ ፡ ፬፻፴፱ ። አባሎችን ፡ ስለ፡ማስገባትና ፡ ስለ፡ማስወገድ ።

(፩) ጠቅላላው፡ ጉባኤ፡ አዲስ ፡ አባሎችን ፡ ስለ፡ማስገባት ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን፡ አባሎች ፡ ስለ፡ ማስወገድ ፡ ይወስናል ።

(፪) አባሎችን፡ የማስገባት፡ ወይም፡ የማስወገድ፡ ሥልጣን ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ መጽደቁ ፡ የተጠበቀ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለሥራ ፡ መምሪያ ፡ ክፍሎች ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፶ ። የውስጥ ፡ ደንቦቹን ፡ ስለ፡መለዋወጥ ፡ (፩)መሠረቱ ።**

(፩) ተቃራኒ፡ ድንጋጌ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የመመሥረቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ለመለዋወጥ ፡ ይችላል ።

(፪) የመመሥረቻውን፡ ጽሑፍ፡ ወይም ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ የመለዋወጡ ፡ ሥልጣን ፡ ለማንም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ክፍል ፡ ሊፈቀድ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፩ ። (፪) ወሰን ።**

(፩) የሚደረገው ፡ ውሳኔ ፡ የማኅበሩን፡ ዓላማ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ ትክክል ፡ ያልሆኑ ፡ መብቶችን ፡ ለመፍቀድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ፈቃድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) ማኅበረተኞቹ፡ ካልፈቀዱ፡ በቀር ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ የተሰጡት ፡ እነዚህ ፡ ልዩ መብቶች ፡ ሊወሰዱባቸው ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፪ ። ስለ ፡ ጥሪ ። (፩) መሠረቱ ።**

በመመሥረቻው፡ ጽሑፍ፡ ወይም ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች፡ እንደ፡ ተመለከቱትና ፡ አስቸኳይ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜና ፡ የማኅበሩ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊነቱን ፡ በሚያስገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ዲሬክተሮች ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ እንዲላክለት ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፫ ። (፪) የማኅበረተኞቹ ፡ መብት።**

(፩) በውስጡ፡ ደንብ፡ የተወሰነው ፡ የማኅበረተኞች ፡ ብዛት ፡ ጥሪ ፡ እንዲደረግ ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ ሊደረግለት ፡ ይገባል ።

(፪) ስለዚሀ ፡ ጕዳይ፡ ደንቦቹ፡ ምንም ፡ የማያመለክቱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሚነጋገሩባቸውን ፡ ነገሮች ፡ በማመልከት ፡ በጽሑፍ ፡ ጥያቄ ፡ ያደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንድ ፡ አምስተኛው ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪው ፡ እንዲደረግ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፬ ። (፫) ዳኞች ፡ የሚያደርጉት ፡ ጥሪ ።**

(፩) ጥሪ ፡ እንዲያደርግ ፡ በሚገደድበት ፡ ጊዜ ፡ የሥራው ፡ አመራር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ ያላደረገ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ጥያቄ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ። ዳኞች ፡ ጥሪ ፡ ይልኩለታል ።

(፪) እንዲሀ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ ዳኞች፡ ስለ ፡ ጉባኤው ፡ ፕሬዚዳንትነት ፡ የሚመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፭ ። (፩) አደራረግና ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) የጠቅላላው፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ አደራረግና ፡ ጊዜው ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለሕሊና ፡ ተስማሚ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ ዲሬክተሮች ፡ ይወስኗቸዋል ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፮ ። በጉባኤው ፡ የሚደረግ ፡ የድምፅ ፡ አሰጣጥ ።**

(፩) የጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ በሚገኙት ፡ ወይም ፡ በተወከሉት ፡ አባሎች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የሚሆን ፡ ነው ።

(፪) ሊነጋገሩበት ፡ ከቀረበው ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ውሳኔ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፯ ። ትክክልነት ።**

ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ በጽሑፍ ፡ የተቀበሉት ፡ ሐሳብ ፡ እንደ ፡ ዋናው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ የሚተካከል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፰ ። የጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔዎች ፡ ፈራሽነት ። (፩) ክስ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ምንም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ እርሱ ፡ ባልተቀበላቸውና ፡ የሕጉን ፡ ወሳኔዎች ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹን ፡ በሚጥሱት ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ ለዳኞች ፡ ክስ ፤ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ ክስ ፤ ውሳኔ ፡ መደረጉን ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በያዘው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ካላቀረበ ፡ ተቀባይነትን ፡ አያገኝም ።

(፫) በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ እንደተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ዋናው ፡ ጉባኤ ፡ ተንኰል ፡ ሳይኖርበት ፡ ጥሪ ፡ የተደረገለት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የተደረጉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ማኅበረተኛው ፡ እንዳወቃቸው ፡ ይገመታሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፱ ። (፪) የፍርዱ ፡ ሥልጣን ።**

የጠቅላላውን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ለመሻር ፡ የሚነገረው ፡ ፍርድ ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፬፻፶ ። ውሳኔዎች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ፤ (ስለ ፡ ማገድ) ።**

ከማኅበሩ ፡ ዲሬክተሮች ፡ በአንዱ ፡ ወይም ፡ በማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈራሽነቱ ፡ የተጠየቀውን ፡ ውሳኔ ፡ አፈጻጸም ፡ ለመከልከል ፡ (ለማገድ ፡ )ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

## የማኅበሩ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፩ ። መሠረቱ ።**

(፩) ማኅበሩ ፡ በውስጡ ፡ ከአሉት ፡ ሰዎች ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ነው ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የአባሎቹ ፡ ግዴታዎችና ፡ መብቶች ፡ አይደሉም ።

(፫) እንዲሁም ፡ የማኅበሩ፡ አባሎች፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የማኅበሩ ፡ መብ ቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ አይደሉም ።

ቊ ፡ ፬፻፶፪ ። ስም ።

(፩) የማኅበሩ ፡ ስም ፡ እንደ፡ ሰዎች፡ ስም ፡ ዐይነት ፡ ልክ ፡ የሚጠበቅ ፡ ነው ።

(፪) የሆነ፡ ሆኖ፡ ይህ ፡ ጥበቃ ፡ በሕግ ፡ የሚደረገው ፤ የማኅበሩ ፡ የውስጥ፡ ደንቦች፡ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተቀመጡ ፡ ሲሆኑ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መብ ቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ ጕዳዩን ፡ በማወቅና ፡ በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ የሆነ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፬፻፶፫ ። መኖሪያ ፡ ቦታ ።

(፩) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መኖሪያ፡ ቦታ፡ የሚባለው ፡ በመመሥረቻው፡ጽሑፍ፡ወይም፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ መሠረት ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በተቋቋመበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ነው ።

(፪) ማኅበሩ ፡ በኑዋሪ ፡ አኳኋን፡ ያሉት፡ የያዛቸው ፡ ሌሎች ፡ ቦታዎች ፡ ሁሉ ፡ ምክ ትል ፡ መኖሪያ ፡ ቦታዎች ፡ ይባላሉ ።

ቊ ፡ ፬፻፶፬ ። ችሎታ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) ማኅበሩ ፡ ከዐይነቱ ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙትን ፡ የብሔራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተግባሮችን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይችላል ።

(፪) ማኅበሩም ፡ እነዚህን፡ ተግባሮች፡ በሥራ ፡ መምሪያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶቹ ፡ አማ ካይነት ፡ ይፈጽማል ።

ቊ ፡ ፬፻፶፭ ። (፪) የፍርድ ፡ ጕዳዮች ።

(፩) ማኅበሩ ፡ በጠያቂነት፡ ወይም ፡ በተከላካይነት፡ በዳኝነት ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ነገር፡ ማኅበሩ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚወከል ፡ ይሆናል ።

(፫) የመልእክትን፡ ደብዳቤ፡ ወይም፡ አንድ ፡ ጽሑፍን ፡ ለማድረስ ፡ የሚላከውን ፡ ማስታወቂያ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ሊቀበል ፡ የሚችለው ፡ አባል ፡ የትኛው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለይቶ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ በማኅበሩ ፡ ወይም ፡ በዲሬ ክተሩ ፡ አድራሻ ፡ ለማኅበሩ ፡ ቢላክለት ፡ የተላከው ፡ ደብዳቤ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጽሑፍን ፡ ለማድረስ ፡ የተጻፈው ፡ ማስታወቂያ ፡ በሚገባ ፡ የተላከ ፡ ሆኖ ፡ ይቈ ጠራል ።

BACK

**ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። (፫) ስጦታዎችና ፡ ውርስ ።**

(፩) አንድ ፡ ማኅበር፡ በስጦታ ፡ ወይም፡ በውርስ ፡ ያገኛቸው ፡ ሀብቶች ፡ ከአንድ ፡ ከተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ የሚያልፉ ፡ ሲሆኑ ፡ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እነዚህ ፡ በቋም ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡ ለአንድ ፡ ማኅበር ፡ የተሰጡ ፡ ሀብ ቶች ፡ እንዲገለጹለት ፡ ማኅበሮችን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) በእንደዚህ፡ ያለው፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ተጠቃሚው ፡ ማኅበር ፡ የቋም ፡ ስጦታ ዎችን ፡ ወይም ፡ የውርሶችን ፡ ሀብቶች ፡ ከተቀበለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የተቀበለውን ፡ የቋም ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ ያገኘውን ፡ ውርስ ፡ ለማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ፡አለበት ። ሳያስታውቅ፡ቢቀር፡ ግን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ በ፬፻፳፰ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ያገኘዋል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ የማኅበሩ ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) ዲሬክተሮቹና ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሳይፈጽሟቸው ፡ የቀሩትና ፡ የሠሯቸው ፡ ተግባ ሮች ፡ ግዴታ ፡ ባለባቸውና ፡ አላፊነትን ፡ የሚያመጡ ፡ ተግባሮችን ፡ በሚፈጸ ሙበት ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ኀላፊነትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ሲሆን ፡ ማኅበሩ ፡ ዲሬክተሮቹና ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሳይፈጽሟቸው ፡ በቀሩት ፡ በሠሯቸው ፡ በአላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

(፪) እንዲሁም፡ ማኅበሩ፡ በማይገባ ፡ የበለጸገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአላፊነት ፡ ይጠየ ቃል ።

(፫) ለዚህ ፡ ነገር፡ ከውል፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላግባብ ፡ ስለ ፡ መበ ልጸግ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የተነገሩት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፫ ። ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ ዋስትና ።**

በማኅበሩ፡ ስም፡ የሠራው ፡ ዲሬክተር ፤ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በተቀ መጡት ፡ በውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ ያልተከናወነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለማኅበሩ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የአንድነት ፡ ዋስ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

## ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መፍረስና ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፬ ። መፍረስ ። (፩) የውስጥ ፡ ደንቦች ።**

ማኅበሩ ፡ የሚፈርሰው ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በውስጥ ፡ ደንቡ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፭ ። (፪) ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ።**

ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ የማኅበሩን ፡ መፍረስ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፷፩ ። (፫) ዳኞች ።</u>

በሥራ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በአንድ ፡ አምስተኛ ፡ ወይም ፡ በማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚወስኑት ፤

(ሀ) በማኅበረተኞቹ፡ ብዛት፡ ማነስ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤትን ፡ አባሎች ፡ ለመምረጥ ፡ ወይም ፡ ማኅበሩን ፡ ለማካሄድ ፡ ያልተቻለ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) የማኅበሩ ፡ ዓላማ፡ የተደረሰበት፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ ሊደረስበት ፡ ያልተቻለ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ረጅም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ባለመከናወኑ ፡ ማኅበሩ ፡ ይህን ፡ ዓላማ፡ መከተል ፡ ያቋረጠ ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ፡ ወይም፡ በውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ከተወሰነው ፡ የተለየ ፡ ዓላማ ፡ ማኅበሩ ፡ የሚከተል ፡ ሲሆን ፤

(መ) ማኅበሩ ፡ ዕዳውን ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፷፪ ። (፬) የአስተዳደር ፡ ውሳኔ ።</u>

(፩) ዓላማውና፡ ክንውኑ፡ ሕገ ፡ ወጥ፡ ወይም፡ ለመልካም፡ ጠባይ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የማኅበሩን ፡ መፍረስ ፡ ይናገራል ፡ ( ይወስናል ) ።

(፪) ከማኅበሩ ፡ ዲሬክተሮች ፡ አንዱ ፤ ውሳኔው ፡ ለማኅበሩ ፡ ከተነገረ ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ወር፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ በዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ለአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የይግባኝ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ፡ በዚህ ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ውሳኔ ፡ እስኪሰጥ ፡ ማኅበሩን ፡ የሚሽረው ፡ ውሳኔ ፡ አፈጻጸሙ ፡ እንዲዘገይ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፷፫ ። የሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) ማኅበሩ፡ በሒሳብ፡ ማጣራት፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ማኅበሩም፡ ለዚህ ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ አስፈላጊ፡ ለሆኑ ፡ ነገሮች ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ይቈጠራል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፷፬ ። ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ። (፩) ምርጫ ።</u>

(፩) በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ ተቃራኒ ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፤ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ካልወሰኑ ፡ በቀር ፡ ማኅበሩን ፡ ይመሩ ፡ በነበሩ ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩ ፡ ሒሳብ ፡ ይጣራል ።

BACK



(፪) እነዚህ ፡ ሰዎች፡ የሌሉ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ የመረጧቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ የማኅበሩን ፡ ሒሳብ ፡ ያጣራሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፷፭ ። (፪) ሥልጣን ።

(፩) ሒሳብ፡ አጣሪው፡ ለሥራ፡ መምሪያ፡ ምክር፡ ቤት፡ የነበረው፡ ሥልጣን፡ አለው።

(፪) ለሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለው ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

(፫) አዲስ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ሊጀምር ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፬፻፷፮ ። (፫) ኀላፊነት ።

(፩) ሒሳብ፡ አጣሪው፡ በማኅበሩ፡ ላይና፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሆኑት ፡ ላይ ፡ ሥራዎችን ፡ በማከናወን ፡ በሚያደርገው ፡ ጥፋት ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

(፪) ከክሱ፡ መቅረብ፡ በፊት ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ የዲሬክተርነትን ፡ ሥራዎች ፡ የሠራ ፡ ማናቸውም ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንድ ፡ ሰው ፤ በማኅበሩ ፡ በኩል ፡ የሒሳብ ፡ አጣሪውን ፡ በአላፊነት ፡ ሊያስጠይቀው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። የፈረሰው ፡ ማኅበር ፡ ንብረት ።

(፩) የፈረሰው ፡ ማኅበር፡ ንብረት፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ሊከፋፈል ፡ አይቻልም ።

(፪) በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ፡ ወይም፡ በውስጥ፡ ደንቦቹ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ የሌለ፡ ሆኖና ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤም፡ በሚገባ ፡ ለሌላ ፡ ሥራ፡ ያላዋላቸው ፡ እንደ፡ሆነ ፡ እነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ማኅበሩን ፡ ያፈረሰው ፡ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ሀብቶችን ፡ በሌላ፡ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ለመወሰን ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## ማኅበሮችን ፡ ስለ፡መቈጣጠር ።

ቍ ፡ ፬፻፷፰ ። የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።

(፩) በያንዳንዱ፡ የጠቅላይ፡ ግዛት፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ከጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ (የተሳሰረ ፡) አንድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይኖራል ።

(፪) የተባለው ም፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ማኅበሮች ፡ ይቈጣጠራል ።

ቍ ፡ ፬፻፷፱ ። የማኅበር ፡ የውስጥ ፡ ደንቦችን ፡ ማስቀመጥ ።

የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፤ የማኅበሮች፡ ጽሕፈት ፡ ቤት፡ የማኅበሩን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ እንዲያዘጋጁና ፡ እነዚህኑም ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያስቀምጡ ፡ መሥራቾቹን ፡ ወይም ፡ መሪዎቹን ፡ ያስጠነቅቃቸዋል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸ ። የታወቁ ፡ ማኅበሮች ፡ መዝገብ ።**

(፩) የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትንና ፡ አሉ ፡ ተብለው ፡ የተነገሩትን ፡ ማኅበሮች ፡ መዝገብ ፤ በፊደል ፡ ተራ ፡ ይይዛል ፡ (ያስቀምጣል) ።

(፪) የአንድ፡ ማኅበር፡ ዲሬክተሮች፤ በመዝገብ፡ እንዳይጻፍ፡ የማኅበሮቹ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት፤ በተቃወመበት፡ እንቢታ፡ ላይ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፩ ። የተራ ፡ ቍጥር ።**

(፩) በመዝገብ ፡ የተጻፈው፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበር ፡ ጽሕፈት፡ቤቱ ፡ ስለ፡ማኅበሩ ፡ ያዘጋጀውን፡ ዶሴ ፡ ቍጥር ፡ የሚያመለክት ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ይቀበላል ።

(፪) ይህ ፡ የተባለው ፡ ተራ፡ ቍጥር፡ በማኅበሮቹ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ውስጥና ፡ ማኅበሮቹን ፡ ከሦስተኛ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ በሚያገናኙት ፡ የደብዳቤ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ መግባት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፪ ። የማኅበሩ ፡ ዶሴ ።**

በመዝገብ ፡ የተጻፈው ፡ የያንዳንዱ ፡ ማኅበር ፡ ዶሴ ፡ የሚያመለክተው ።

(ሀ) የማኅበሩን ፡ ስም ፡ ከነተራ ፡ ቍጥሩ ፤

(ለ) የማኅበሩን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦችና ፡ በነዚህ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ የተደረጉትን ፡ መለዋወጥ ፡ እነዚህ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ መለዋወጦች ፡ የተደረጉበትን ፡ ጊዜ ፡ ቍጥር ፤

(ሐ) የማኅበሩ ፡ ዲሬክተሮችን ፤ ወይም፡ ለማኅበሩ ፡ ወኪልነት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፤

(መ) ለማኅበሩ ፡ ሊኖሩት ፡ የሚችሉትን፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የተቀማጭነትን ፡ ቦታዎች ፡ መግለጫ ፤

(ሠ) ስለ፡ ማኅበሩ፡ መፍረስ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔና፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ የመጨረሻ ፡ አስተሳሳቢዎቹን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፫ ። ጠቅላላ ፡ ስብሰባዎች ። (፩) የስብሰባ ፡ ጥሪ ።**

(፩) ጠቅላላ፡ የሆነው፡ ስብሰባ፡ በሚቀመጥበት፡ ጊዜ፡ ሁሉ ፡ ለማኅበሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በአስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያ ፡ ይላክለታል ።

(፪) ጽሕፈት፡ ቤቱ ፡ በነዚህ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባዎች ፡ ውስጥ፡አንድ፡ታዛቢ፡ወኪል ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) በተለይ፡ የስብሰባውን፡ ጥሪ ፡ አደራረግና ፡ የጥሪውን ፡ ጊዜ ፤ ስብሰባው ፡ የሚነጋገርበትን ፡ ጕዳይና ፡ የስብሰባውን ፡ አያያዝ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ነገር ፤ የጠቅላላውን ፡ ስብሰባ ፡ የሥራውን ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ ለማረጋገጥ ፡ ጠቃሚዎች ፡ የሚመስሉትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፩ ። (፪) ውሳኔዎች ።**

በማኅበሮቹ፡ ጽሕፈት፡ ቤት ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ የተደረገበትን ፡ ቀን ፡ በሚከተለው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ በሚይዘው ፡ መዝገብ ፡ ዶሴ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ ያለባቸው ፤ በተባለው ፡ ስብሰባ ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ፡ በማስታወቂያ ፡ ይላኩለታል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፪ ። (፫) የውሳኔዎቹ ፡ ፈራሽነት ።**

(፩) የማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጠቅላላው ፡ ስብሰባ ፡ የሰጣቸውን ፡ የሕግ ፡ ወይም፡ የማኅበር ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች፡ ተቃራኒ፡ የሆኑትን ፡ ውሳኔዎች ፡ በዳኞች ፡ ፊት ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) ክሱም ፡ እንዳይፈርስ ፤ የተደረገው ፡ የውሳኔው ፡ ግልባጭ ፡ ከተላከለት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፫ ። የማኅበር ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መለዋወጥ ።**

(፩) በማኅበሮቹ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች፡ ላይ ፡ መለዋወጥ፡ የተደረገ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ጠቅላላው፡ስብሰባ ፡ መለዋወጡን ፡ የተቀበለበትን ፡ ቀን ፡ በሚከተለው ፡ ወር ፡ ውስጥ፡ የተባለውን ፡ መለዋወጥ ፡ የያዘው ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የደንቦቹ ፡ ግልባጭ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይሰጣል ።

(፪) ይኸው፡ ግልባጭ፡ በገበሩ ፡ ላይ ፡ ቢ.. .... ....ቀን ፡ የተሻሻለ ፡ ጽሑፍ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ ይኖረዋል ።

(፫) ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መለዋወጣቸውን ፡ ማወቃቸው ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ለማኅበሮቹ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ የተደረጉት ፡ መለዋወጦች ፡ በማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ተነገረ ፡ ድረስ፡ በሦስተኛ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑባቸው ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፬ ። የማኅበር፡ ዲሬክተሮች ።**

(፩) የሥራው ፡ አመራር ፡ (ዲሬክሲዮን) ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ስም ፡ እንዲሁም ፡ ለማኅበሩ ፡ ወኪል ፡ የመሆን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስም፡እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከተመረጡበት ፡ ቀን ፡ በሚከተለው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይነገራል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ለተጻፈበት ፡ ሊስት ፡ የተደረገውም ፡ ማናቸውም ፡ መለዋወጥ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይነገራል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፭ ። የሒሳብ ፡ ሚዛን ።**

(፩) ማኅበሩ ፡ በየመቱ ፡ ጠቅላላው ፡ ስብሰባ፡ ያጸደቀውን፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ለማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ያስታውቃል ።

(፪) ያገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር ፡ የዚህን ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ መልካም ፡ አቀራረብና ፡ እውነተኛነትን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚስማሙ ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ ደንቦች ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፬፻፹፱ ። የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ።

(፩) ያገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፤ የማኅበሮቹ፡ ጽሕፈት፡ ቤቶች፡ በማኅበሮች፡ ላይ፡ ግጠኛ፡የሆነውን ፡ የመቈጣጠር፡ ሥራ፡ እንዲሠሩ፡ ለማድረግ፡ ሌሎችንም ፡ በ ሚነት ፡ ያላቸውን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ በሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ለ ዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚህ ፡ ጥንቃቄዎች፡ እንደ፡ ማኅበሩ፡ ግብ ፡ ትልቅነትና ፡ እንደሚቈይበ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤታቸው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ለሆኑ፡ማኅበሮ ወይም፡በውጭ ፡ አገር ፡ የማኅበርን ፡ ሥራ ፡ ክንውን ፡ ለያዙ ፡ ወይም ፡ አብዛኛ አባሎቹ፡ የውጭ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ለሆኑ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ አመራሩ ፡ (ዲሬ የን) ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎ ለሚገኙባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ልዩ ፡ የሆኑት ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሊታዘዙ ፡ ይችላ

ቍ ፡ ፬፻፺ ። የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡(፩) ለጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚደረጉ ፡ ማስታወቂያዎ

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ የሚቀጡት ፤

(ሀ) የማኅበርን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ በሕግ ፡ በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ውስ ለማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ያልሰጡት ፡ የማኅበር ፡ መሥራቾች ።

(ለ) ለማኅበሮች፡ ጽሕፈት፡ቤት፡ ስለሚደረጉት፡ ማስታወቂያዎች፡ወይም ፡ ሚሰጡት ፡ ጽሑፎች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ የ ለፉ ፡ የማኅበሩ ፡ መሪዎች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። (፪) የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕጋውያን ፡ ትእዛዞች ፡ መጣስ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ የሚቀጡት ።

(ሀ) ተራ፡ ቍጥሩን፡ በማኅበር ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋ በሚያደርገው ፡ በደብዳቤ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ያላመለከተ ፡ ማኅበር ፤

(ለ) ባለጕዳዩ፡ ባቀረበው፡ ጥያቄ ፡ የማኅበሩን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ለተባለ ባለጕዳይ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ያላስታወቀ ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። (፫) ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ ማኅበር ።

(፩) የማኅበሮች፡ ጽሕፈት፡ ቤት ፡ ለአፈረሰው ፡ ማኅበር ፡ በሥራ ፡ አስኪያጅን የአንድ፡ የሥራ፡ ክንውን ፡ የቀጠሉ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የማኅበሩን ፡ ሕገ ፡ ወጥነት ፡ እያወቁ ፡ የሥራውን ፡ መካሂ ተካፋዮች ፡ በመሆን ፡ የቀጠሉ ፡ የተባለው ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ በወንጀ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበ ፡ ንብረት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፫ ። ትርጓሜ ።**

የበጎ ፡ አድራጎት፡ ድርጅት ፡ ተግባር ፡ ማለት ፡ አንድ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሀብቶች ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሳይሆን ፡ በማይመለስ ፡ አኳኋንና ፡ ለዘለዓለም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ የጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ ግብ ፡ ላለው ፡ የሚያውልበት ፡ ሥራ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፬ ። ፎርሞች ።**

(፩) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ በቁም ፡ ስጦታ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

(፪) የዚህም ፡ ነገር፡ መቋቋም ፡ በዐይነቱና፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ስጦታዎችን ፡ ወይም፡ ኑዛዜዎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ የሚመራ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ነገሩን ፡ ማጽደቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትን ፡ ተግባር ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ካላጸደቀው ፡ በቀር ፡ አይቋቋምም ።

(፪) የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን፡ ይህ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የሚመለከታቸውን ፡ የሌሎች ፡ ሚኒስቴሮችን ፡ ሐሳብ ፡ ይጠይቃል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። ነገሩ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ። (፩) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መሥራቹ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ።**

የበጎ ፡ አድራጎቱ፡ ድርጅት፡ ተግባር፡ እንዲጸድቅ ፡ ለማድረግ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ መሥራቹ ፡ በሕይወት ፡ ካለ ፡ መሥራቹ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። (፪) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መሥራቹ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ።**

(፩) መሥራቹ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የተባለውን ፡ ጥያቄ ፤ መሥራቹ ፤ ሥራውን ፡ ሰጥቶት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ ሊጠይቅ ፡ ይገባል ።

(፪) እንደተባለው ፡ ጠያቂ ፡ የሌለ፡ ሲሆን፡ የበጎ ፡ አድራጎትን ፡ ድርጅት ፡ ጽሑፍ፡ ያዘጋጁ ፡ ሰዎች ፤ ወይም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ ምስክር ፡ የሆኑት ፡ ወይም ፡ የዚህን ፡ ተግባር ፡ አደራ ፡ ያስቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ ሊጠይቁ ፡ ይገባል ።

(፫) የዚህን ፡ ተግባር ፡ ፈቃድ ፡ የመጠየቅ ፡ ግዴታ ፡ የሚወድቅባቸው ፡ ሰዎች ፡ ፈቃዱን ፡ ሳይጠይቁ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለውን ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድር

ጅት ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲጸድቅ ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ መሥራቹ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ፡ በሦስት ፡ ወሩ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ሊያቀርበው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፰ ። የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትን ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መሻር ።**

(፩) የበጎ ፡ አድርጎት ፡ ድርጅትን ፡ ተግባር ፡ መሥራች ፡ ይህን ፡ ተግባሩን ፡ እንዲያጸድቅለት ፡ ለአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ከመፍቀዱ ፡ በፊት ፡ ያቆመውን ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ በነፃ ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፪) የመሥራቹ ፡ ወራሾች ፡ በዚህ ፡ በመሻር ፡ መብታቸው ፡ ሊሠሩ ፡ የሚችሉት ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱን ፡ ሥራ ፡ ፈቃድ ፡ የመቀበል ፡ ግብ ፡ ያለው ፡ ጥያቄ ፡ ለአገር፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት፡ ድርጅቱን ፡ ተግባር ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ሳያጸድቀው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፱ ። የማጽደቁ ፡ ተግባር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ስለ ፡ መሥራቱ ።**

(፩) የበጎ፡ አድራጎት፡ ድርጅት ፡ ፈቃድ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበው ፡ በመሥራቹ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ድርጅቱን ፡ የሚያጸድቀው ፡ የአስተዳደር ፡ ውሳኔ ፡ የፈቃዱ ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የሚጸና ፡ ይሆናል ።

(፪) የፈቃድ፡ ጥያቄ፡ የቀረበው ፤ መሥራቹ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ፡እንደ፡ሆነ ፤ ውሳኔው፡ መሥራቹ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የሚጸና ፡ ይሆናል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ መሥራት ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ከመፈቀዱ ፡ በፊት ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ባለመብቶች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፺ ። ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የሚደረገው ፡ ጥበቃና ፡ ተጠባባቂነት።**

(፩) የበጎ ፡ አድራጎት፡ ድርጅት ፡ ተግባር ፡ የተፈቀደበት ፡ ጽሑፍ ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቱ ፡ ተግባር ፡ የሚደረገውን ፡ ጥበቃና ፡ ተጠባባቂነት፡ የታዘዘውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለይቶ ፡ ያስታውቃል ።

(፪) በተባለው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ማናቸውም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያልተመረጠበት ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ተግባር ፡ የሚደረገውን ፡ ጥበቃና ፡ ተጠባባቂነት ፡ የሚያከናውነው ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱ ፡ ድርጅት ፡ ተግባር ፡ ባለበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሚገኘው ፡ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት፡ ቤት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፤ (፩) ግብ ።**

የበጎ፡ አድራጎት፡ ድርጅት ፡ በተቋቋመባቸውና፡ በሚተዳደርባቸው ፡ የውስጥ፡ ደንቦች ፡ የሚመራ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፪ ። (፪) በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፈው ።**

የውስጥ፡ ደንቦቹ፡ በተለይ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቱን ፡ ስም ፡ ግቡንና ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ ያመለክታሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፫ ። የውስጥ ፡ ደንቦቹን ፡ የሚያሰናዳው ።**

(፩) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትን ፡ የውስጥ፡ ደንቦች ፡ የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መሥራች ፡ ሊያሰናዳቸው ፡ ይችላል ።

(፪) እርሱ ፡ ያላሰናዳቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ለጠባቂነትና ፡ ለተጠባባቂነት፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በተሰጠው ፡ መሥሪያ፡ ቤት ፡ ይደራጃሉ ።

(፫) የውስጥ፡ ደንቦቹ፡ ለበጎ ፡ ተግባር ፡ ድርጅት ፡ ተቃራኒዎች ፡ ሆነው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ የተባሉትን ፡ ደንቦች ፡ ለማውጣልን ፡ ሲል ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፬ ፡ አመራሩ ።**

(፩) የበጎ ፡ አድራጎቱ ፡ ድርጅት ፡ የሚመራው ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ መሠረት ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ዲሬክተሮች ፡ ነው ።

(፪) የማኅበርችን፡ ዲሬክተሮች ፡ የሚመለከቱት፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለድርጅት ፡ ዲሬክተሮችም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፭ ። የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ።**

(፩) በበጎ፡ አድራጎት፡ ድርጅት ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመው ፡ የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የመጨረሻው ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው ።

(፪) ለበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት፡ የተደረገው፡ የጠባቂነትና ፡ የተጠባባቂነት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ወኪል ፡ ይኖረዋል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፮ ። የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሥራ ።**

(፩) የአስተዳደሩ፡ ምክር፡ ቤት ፡ የሌላው ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ ባልሆነት ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ምክር፡ ቤቱ፡ በተለይ ፡ ዲሬክተሮቹን ፡ ይሾማል ፡ ይሽራል ፡ የሥራቸውን ፡ መካሄድ ፡ ይቆጣጠራል ፡ ሒሳባቸውንም ፡ ያጸድቃል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፯ ። የውስጥ ፡ ደንቦቹን ፡ ስለ፡ መለዋወጥ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

የአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ያወሰነው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ መለዋወጥ ፡ የድርጅቱ ፡ ጠባቂና ፡ ተጠባባቂው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ካላጸደቀው ፡ በቀር ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፰ ። (፪) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቱ ፡ መሥራች ፡ የሚያደርገው ፡ ክልከላ ።**

(፩) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቱ ፡ ሥራ፡ መሥራች ፡ አንዳንዶቹ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ደንቦች ፡ እንዳይለዋወጡ፡ ግልጽ፡ በሆነ ፡ ውሳኔ፡ ለመከልከል፡ ይችላል ።

(፪) የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መሥራች ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ የገለጸውን ፡ ፈቃድ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦቹ፡ የተለዋወጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መሥራቹ ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፤ ወይም፡ የመሥራቹ፡ ወራሾች ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱ ፡ ድርጅት ፡ ተግባር ፡ ፈርሷል ፡ ብለው ፡ እንዲያስታውቁላቸው ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፫) የውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ መለዋወጥ፡ ከተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ መሥራቹ ፡ ከሞተ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተነገረው ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፱ ። የምክር ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባ ።**

(፩) የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ይሰበሰባል ።

(፪) በሚያስቸግል ፡ ጊዜ ፤ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኖ ፡ በሚያሳይበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ዲሬክተሮቹ ፡ ስብሰባው ፡ እንዲደረግ ፡ ጥሪውን ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻ ። የምክር ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔዎች ።**

(፩) የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚፈጸሙት ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሲኖር ፡ ነው ።

(፪) ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የተደረገው ፡ የጠባቂነትና ፡ የተጠባባቂነት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፤ የውሳኔዎቹን ፡ ፈራሽነት ፡ ወይም ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ መታገዳቸውን ፡ እንዲያስታውቁለት ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፩ ። የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) የማኅበሮችን ፡ ስም ፤ የመኖሪያ ፡ ስፍራንና ፡ ችሎታን ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎች ፡ በድርጅቶችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ድርጅቱ ፡ የጠባቂውንና ፡ የተጠባባቂውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አስፈቅዶ ፡ የቁም ፡ ስጦታዎችንና ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታዎችን ፡ መቀበል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፪ ። የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ተጠቃሚዎች ፡ መብቶች ።**

(፩) ለጥቅማቸው ፡ ተብሎ ፡ የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የተቋቋመላቸው ፡ ሰዎች ፡ መብታቸው ፡ እንዲከበርላቸው ፡ ሲሉ ፡ በበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

BACK



(፪) ተጠቃሚዎቹ፡ በደንቦቹ፡ በሚበቃ፡ (በሚገባ፡) ተለይተው ፡ ያልታወቁ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ዲሬክተሮች ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በሚታያ ቸው ፡ ግምት ፡ ይወስኗቸዋል ።

**ቍ ፡ ፭፻፫ ። የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መቅረት ። (፩) የውስጥ ፡ ደንቦቹ ።**

የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ በተወሰኑት ፡ ምክንያ ቶች ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፭፻፬ ። (፪) ሌሎች ፡ ሁኔታዎች ፡ ( ምክንያቶች ) ።**

የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ለጠባቂነት ፡ በተደረገለት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በኩል ፡ በሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ የበጎው ፡ አድራ ጎት ፡ ድርጅት ፡ ቀሪ ፡ ሁኗል ፡ ብለው ፡ የሚወስኑት ፡—

(ሀ) ግቡ ፡ (ዓላማው፡) የተፈጸመ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ወደ ፡ ግቡ ፡ ለመድረስ፡ የማይችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የተባለው ፡ ግብ፡ ሕገ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ በደንቦቹ ፡ ከተመለከተው ፡ ግብ ፡ ሌላ ፡ የተ ከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) የበጎው ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፭ ። የብዙዎች ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ መቀላቀል ።**

(፩) የሁለት ፡ ወይም ፡ የብዙዎች፡ የበጎ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ መቀላቀል ፡ ለጠ ቅላላ ፡ ጥቅም ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የነዚህን ፡ የበጎ ፡ አድራ ጎት ፡ ድርጅት ፡ የሥራ ፡ መካሄድ ፡ መከናወን ፡ አንድነት ፡ ለማያያዝ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞቹ ፡ የነዚህኑ ፡ መቀላቀል ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ።

(፪) ለጠባቂነትና ፡ ለተጠባባቂነት ፡ የተደረገው ፡ መሥሪያ፡ ቤት ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ ለሆኑት ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ የጋራቸው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ተባለው ፡ ጕዳይ ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ የተባለው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሊያቀ ርበው ፡ ይችላል ።

(፫) በዚህ፡ ዐይነት ፡ ለተቋቋመው፡ ድርጅት ፡ አዲስ ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ ይኖሩ ታል ።

**ቍ ፡ ፭፻፮ ። የሒሳብ ፡ መጣራትና ፡ መቈጣጠር ።**

(፩) ስለ፡ማኅበሮች፡ ሒሳብ፡ ማጣራት፡ የተነገሩት ፡ የዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራትም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆ ናሉ ።

(፪) ስለ፡ ማኅበሮች፡ የሒሳብ፡ መቈጣጠር ፡ የተነገሩት ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎች፡ ስለ፡በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ የሒሳብ፡ መቈጣጠር ፡ ነገር ፡ ተፈጻሚዎች፡ ይሆናሉ ።

(፫) ለድርጅቶች፡ ጠባቂነትና ፡ ተጠባባቂነት ፡ የተቋቋመ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማኅበሮቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተሰጠው ፡ ሥራ ፡ ለድርጅቶች ፡ ጠባቂና ፡ ተጠባባቂ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ይሰጣል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ፡ኮሚቴዎች ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፭ ። ፈቃድን ፡ የማግኘት ፡ ግዴታ ።

(፩) ስለ፡አንድ፡ የተወሰነ፡ ሥራ፡ ጥቅም ፤ ስለ፡ሰው ፡ ፍቅር፡ ወይም፡ ስለ፡ጠቅላላ ፡ ጥቅም፡ በይፋ ፡ በሚደረጉት ፡ ልመናዎች ፡ በታላላቅ፡ የሕዝብ ፡ በዓላት ፡ ቀኖች፤ ወይም ፡ በዚህ ፡ ተራ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ አደራረጎች ፡ ረዳትነት ፤ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ ሌሎችን ፡ ንብረቶች ፡ የመሰብሰብ ፡ ዓላማ ፡ ያላቸው ፡ ኮሚቴዎች ፡ የተቋቋሙትና ፡ የሚሠሩት ፡ በመንግሥቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውሳኔ ፤ በአንድ ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ክፍሉን ፡ በሚመለከተው ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ ካልተፈቀደላቸው ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ሥራቸውን ፡ ለማከናወን ፡ አይችሉም ።

(፪) ሳይፈቀድላቸው ፡ በይፋ፡ የሚደረገውን፡ ልመና ፡ የሚያደራጁ ፡ ወይም ፡ ከሕዝብ ፡ ስጦታዎችን ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ የሚለምኑ ፡ ኮሚቴዎች ፡ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይቀጣሉ ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፮ ። የኮሚቴዎች ፡ ድርጅት ።

(፩) ውሳኔው ፡ በኮሚቴ ፡ የሚሰበሰቡትን ፡ ሰዎች ፡ ያስታውቃል ።

(፪) የተባለው፡ የጊዜ፡ ውሳኔ ፡ የኮሚቴውን ፡ ሥራና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲሁም ፡ ሥራውን ፡ ሊፈጽምበት ፡ የሚገባውን ፡ ጊዜ ፡ ለይቶ ፡ ያስታውቃል ።

(፫) አስፈላጊ ፡ ሲሆን፡ የኮሚቴው ፡ ሥራ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻልበትን ፡ የአደራረጉን፡ ዐይነት ፡ ይወስናል ፤ በኮሚቴው ፡ የተሰበሰበውን ፡ መላውን ፡ ገንዘብና ፡ በሥራ፡ ላይ ፡ የመዋሉን ፡ ለመቈጣጠርም ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ ያዛል ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። ስጦታዎችና ፡ የእንሰጣለን ፡ ባዮች ፡ ፊርማ ።

(፩) ኮሚቴው፡ ስጦታዎችንና፡ የእንሰጣለን፡ ባዮችን ፡ ፊርማ ፡ ለመቀበል፡ ይችላል።

(፪) የኮሚቴው፡ ፕሬዚዳንት፤ ፈራሚዎች ፡ የሰጡትን ፡ ቃል ፡ ለማስፈጸም ፡ በፈራሚዎቹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

BACK



**ቍ ፡ ፫፻፲ ። የአባሎቹ ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) የኮሚቴው ፡ አባሎች ፡ ስለ፡ሥራው ፡ መካሄድና ፡ ስለ፡አስተዳደሩ ፡ በየራሳቸውና ፡ በአንድነት ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ማናቸውም ፡ ሰጪ ፡ ወይም ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ የፈረመ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የኮሚቴውን ፡ አባሎች ፡ ባለባቸው ፡ ኀላፊነት ፡ ሊጠይቃቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፩ ። የኮሚቴው ፡ መቅረት ።**

ኮሚቴው ፡ የተወሰነው፡ ጊዜ፡ ሲያልቅ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፪ ። የኮሚቴው ፡ መፍረስ ።**

ኮሚቴው ፡ በአገር ፡ አገዛዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ለመፍረስ ፡ የሚቻለው ፡—

(ሀ) ከዓላማው ፡ የተለየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የዓላማው ፡ አፈጻጸም ፡ የማይቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የተተወ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፫ ። የሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ (፩) ንብረቱ ፡ የማይበቃ ፡ ሲሆን ።**

(፩) በኮሚቴው፡ የተጠራቀሙት፡ ንብረቶች ፡ ኮሚቴው ፡ ያሰበውን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ ያልተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የተባለው ፡ ሥራ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ለኮሚቴው ፡ ፈቃድ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፤ ለተመለከተው ፡ ዓላማ ፡ ይውላሉ ።

(፪) ስለዚህ፡ ነገር፡ በውሳኔው ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአስተዳደሩ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲያዝባቸው ፡ ተደርጎ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለአንድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሥራ ፡ ያውላቸዋል ።

(፫) ለኮሚቴው፡ ንብረትን፡ የሰጡ ፡ ሰዎች ፤ መልሰው ፡ የመውሰድን ፡ መብት ፡ በውል ፡ በግልጽ ፡ አግብተው ፡ ካልተገኙ ፡ በቀር ፡ መልሰው ፡ ለመውሰድ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፬ ። (፪) ቀሪ ፡ ንብረት ።**

(፩) ኮሚቴው ፡ የተሰበሰበው ፡ ንብረት ፡ ለተወሰነው ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነው ፡ በላይ ፡ ትርፍ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተወሰነው ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ትርፍ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ኮሚቴው ፡ በፈቀደው ፡ ውሳኔ ፡ ለተመለከተው ፡ ዓላማ ፡ ይውላል ።

(፪) ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በውል ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲያዝበት ፡ ተደርጎ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለአንድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሥራ ፡ ያውለዋል ።

(፫) ለኮሚቴው ፡ ገንዘብ ፡ የሰጡት ፡ ሰዎች ፡ ገንዘቡን ፡ መልሰው ፡ ለመውሰድ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፬፻፹፪ ። ወደ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መለወጥ ።

(፩) ኮሚቴው፡ የሰበሰበው፡ ንብረት ፡ በውስጥ ፡ ደንቦቹ ፡ መሠረት ፡ ቀዋሚ ፡ እንዲሆን ፡ ለተወሰነ ፡ ዓላማ፡እንዲውል ፡ የታሰበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ አንድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ማቋቋም ፡ ይገባል ።

(፪) የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

<u>ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውሉ ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ፡ (ፊደ.ይኮሚስ) ።</u>

ቍ ፡ ፬፻፹፫ ። ትርጓሜ ።

ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት፡ የሚውል ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ማለት ፡— የአደራ ፡ ንብረት ፡ አቋቋሚው ፡ በሰጠው ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የአደራ ፡ ጠባቂ ፡ የሚያስተዳድራቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ንብረቶች ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ የተቋቋሙበት ፡ ድርጅት ፡ (ስሪት ፡) ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፹፬ ። አቋቋሙ ፡ (ፎርሙ ) ።

(፩) ይህ ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውል ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ በሕይወት ፡ ባሉ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በሚደረግ ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

(፪) የዚህ ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ መቋቋም ፡ ስለ ፡ አቋቋሙም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሥረ ፡ ነገሩ ፡ ስጦታዎችን ፡ ወይም ፡ ኑዛዜዎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ይመራል ።

(፫) አንድ ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሆነውን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ለማቋቋም ፡ በስጦታው ፡ ወይም ፡ በኑዛዜው ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ መጻፍ ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። በልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ንብረት ፡ ተጠቃሚ ።

በልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ተጠቃሚ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ባይሆን ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ በተቋቋመበት ፡ ጊዜ ፡ የተፀነሰ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ብዛት ።

(፩) የልዩ፡ በጎ፡ አድራጎት ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ከአራት ፡ በላይ፡ ሊሆን ፡ ሳይችል ፤ ባንድ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ለመተዳደር፡ ይችላል ።

(፪) ቍጥራቸው ፡ ከአራት፡ በላይ፡ የሆነ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ተመርጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተመረጡት ፡ ፬ቱ ፡ ብቻ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ያካሂዳሉ ።

(፫) የተመረጡት ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ሥራውን ፡ አንቀበልም ፡ ያሉ ፤ የሞቱ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ያጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌሎች ፡ የተመረጡት ፡ ሰዎች ፡ በምርጫቸው ፡ ተራ ፡ ገብተው ፡ በፊተኞቹ ፡ እግር ፡ ይተካሉ ።

ቍ ፡ ፭፻፵ ። የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ።

(፩) የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪን ፡ የሚመርጠው ፤ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለውን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ያቋቋመው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፤ እርሱ ፡ የመረጠው ፡ ባይኖር ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ የተመረጠው ፡ አስተዳዳሪ ፡ የተሰጡትን ፡ ሥራዎች ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ የሞተ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአደራውን ፡ ንብረት ፡ ያቋቋመው ፡ ሰው ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ የመምረጥን ፡ ሥልጣን፡ የሰጠው ፡ ወይም ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞቹ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ይመርጣሉ ።

ቍ ፡ ፭፻፵፩ ። የአስተዳዳሪዎቹ ፡ ሥራ ፡ መልቀቅ ።

(፩) አስተዳዳሪው ፡ (ፊዴይኮሚሴሩ ፡) የሚገባ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የተሰጡትን ፡ ሥራዎች ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ አካሂዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራውን ፡ ለመተው ፡ ይችላል ።

(፪) የአስተዳዳሪነቱ፡ ኀላፊነት ፡ እርሱ ፡ የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ስንብቱን ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ በተመረጠው ፡ ሌላ ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ላይ ፡ እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፤ የተባለው ፡ የአስተዳዳሪነት ፡ ኀላፊነት ፡ በሱው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቈያል ።

ቍ ፡ ፭፻፵፪ ። የአዲሱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ መሻር ።

የሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለውን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ያቋቋመው ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ከአስተዳዳሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ በአደራው ፡ ንብረት ፡ ተጠቃሚ ፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ባቀረበው፡ ጥያቄ፡ ዳኞች ፡ ያንድ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲቀር ፡ አድርገው፡ በርሱ ፡ ቦታ ፡ እነርሱ ፡ የመረጡትን ፡ አዲስ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ለማድረግ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፭፻፵፫ ። የአደራ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሹመት ፡ ማስረጃ ።

(፩) አስተዳዳሪው ፡ የአስተዳዳሪነቱንና ፡ የሥልጣኑን ፡ ማስረጃ ፡ ዳኞች ፡ እንዲሰጡት ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህ፡ ማስረጃ፡ አስፈላጊ፡ ሲሆን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ፡ ለይቶ ፡ ያስታውቃል ።

**ቍ ፡ ፭፻፳፬ ። ስለብዙ ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ።**

(፩) ብዙዎች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በመካከላቸው ፡ በሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳደርን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ይሰጣሉ ።

(፪) ሳይስማሙ ፡ በሚቀሩበት ፡ ጊዜ ፤ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይወሰናል ።

(፫) በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ያልተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ በውሳኔው ፡ ያለ ፡ መስማማታቸውን ፡ በፕሮሴቬርባል ፡ ውስጥ ፡ እንዲጸፍላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፭፻፳፭ ። ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳደር ።**

(፩) አስተዳዳሪው ፡ (ፊዴይኮሚሴሩ) ፡ ጠንቃቃና ፡ እንደ ፡ አስተዋይ ፡ የሥራ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ይህን ፡ የተባለውን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ያስተዳድራል ።

(፪) ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውሉት ፡ እነዚህ ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ፡ የሚባሉትና ፡ የራሱ ፡ ንብረቶች ፡ እንዳይቀላቀሉ ፡ ይጠነቀቃል ።

(፫) ለዚሁ ፡ ነገር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲያደርግ ፡ ይገደዳል ።

**ቍ ፡ ፭፻፳፮ ። በፍርድ ፡ በኩል ፡ የንብረቱ ፡ ወኪል ።**

(፩) አስተዳዳሪው ፡ በፍርድ ፡ ረገድ ፡ ለተባለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ እንደራሴ ፡ ነው ።

(፪) በአስተዳዳሪነቱም ፡ በተቋቋሙ ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ፡ ተጠቃሚዎች ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊከሱት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፳፯ ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሥልጣን ።**

(፩) የአደራ ፡ በሚባሉት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የአስተዳዳሪው ፡ ሥልጣን ፡ የአንድ ፡ ባለሀብት ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለው ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ በተቋቋመበት ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አስተዳዳሪው ፡ የማይንቀሳቀሱትን ፡ ንብረቶች ፡ ዳኞች ፡ ካልፈቀዱለት ፡ በቀር ፡ ለመሸጥ ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ።

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ አስተዳዳሪው ፡ ንብረቶቹን ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለመልቀቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፳፰ ። የአቋቋሚው ፡ መሪ ፡ ትእዛዞች ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ንብረቶቹን ፡ ካቋቋመው ፡ ሰው ፡ የተቀበላቸውን ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ መሪ ፡ ትእዛዞች ፡ መከተል ፡ አለበት ።

(፪) ስለሆነም ፡ በንብረቱ ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተባሉት ፡ መሪ ፡ ትእዛዞች ፡ ውጭ ፡ እንዲሠራ ፡ ከዳኞች ፡ ማስፈቀድ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፳፻፳፱ ። (፪) ቅጣት ።</u>

(፩) ለአደራ ፡ ንብረት፡ አስተዳዳሪው ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን፡ የሚሰጥባቸው፡ ወይም፡ በሥልጣኑ ፡ የሚሠራበትን ፡ ዐይነት ፡ የሚደነባባቸው ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ የተቋቋመበት ፡ ውል ፡ ውሳኔዎች ፡ መኖራቸውን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማወቃቸው ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ እንደ ፡ ነበረባቸው ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ውሳኔዎቹ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ።

(፪) እነዚህን ፡ ውሳኔዎች ፡ አለመከተል ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ፡ አስተዳዳሪውን ፡ በኀላፊነት ፡ ተጠያቂ ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ለሚውለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሠራው ፡ ወይም ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሠራ ፡ መስሎት ፡ ያደረገው ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ መልካም ፡ አሳቡን ፡ እውነተኛ ፡ ለመሆኑ ፡ አእምሮ ፡ የሚቀበለው ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ለአስተዳዳሪው ፡ ከሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ነፃ ፡ ሊያደርጉት ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፳፻፴ ። የንብረት ፡ መተካት ።</u>

የአደራ ፡ አስተዳዳሪው ፡ ባደረገው ፡ መሸጥ ፡ መለወጥ ፡ በተተኩት ፡ ንብረቶች ፡ የተገኙት ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውሉት ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ፡ ያፈሩዋቸው ፡ ገቢዎች ፡ በተባሉት ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፳፻፴፩ ። የግል ፡ ጥቅም ፡ ያለ ፡ መኖር ።</u>

የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ለልዩ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ በተቋቋመበት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተነግረው ፡ ከተፈቀዱለት ፡ ጥቅሞች ፡ በቀር ፡ ከተባለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ መውሰድ ፡ አይገባውም ።

<u>ቍ ፡ ፳፻፴፪ ። የጉዳት ፡ ካሣ ።</u>

የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ በተባለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳደር ፡ ምክንያት ፡ ስላደረገው ፡ ወጪ ፡ ገንዘብና ፡ ስለ ፡ ደረሱበት ፡ ግዴታዎች ፡ የጉዳትን ፡ ካሣ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፭፻፴፫ ። የአስተዳዳሪው ፡ ኃላፊነት ።

የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ውክልናን ፡ በሚመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ በልዩ ፡ አድራጎት ፡ በአደራው ፡ ንብረቶች ፡ በሚጠቀሙት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድና ፡ የተባለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ በሚጸረጥበት ፡ ጊዜ ፡ ንብረቶችን ፡ መቀበል ፡ ለሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ለአደራ ፡ ንብረቱ ፡ መልካም ፡ አስተዳደር ፡ ኃላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፭፻፴፬ ። ሒሳቦቹን ፡ ማቅረብ ። (፩) ለማን ፡ እንደሚደረግ ።

(፩) አስተዳዳሪው ፡ አስተዳደሩን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ሒሳቦችና ፡ የአደራውን ፡ ንብረት ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከተውን ፡ መግለጫ ፡ በአደራው ፡ ንብረት ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለተመረጠው ፡ ሰው ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) የተመረጠ፡ ሰው ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአደራው ፡ ንብረት ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ፡ መሠረት ፡ ጥቅም ፡ ላለው ፡ ለማናቸውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በአስተዳደሩ፡ ሥራ ፡ ምትክ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፭፻፴፭ ። (፪) በምን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚቀርብ ።

(፩) የልዩ፡ በጎ፡ አድራጎት፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ፡ ሒሳብ ፡ የሚቀርብበትን ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ያልወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተባለው ፡ ሒሳብ ፡ በዓመት ፡ በዓመት ፡ አስተዳዳሪው ፡ አስተዳደሩን ፡ ሲጀምር ፡ በተወሰነው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ለአእምሮ ፡ ተገቢ፡ መስሎ፡ የሚታይ ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ አንድ ፡ ባለ ጕዳይ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች፡ ሒሳቦቹ ፡ በመካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ እንዲቀርቡ ፡ ለመፍቀድ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪው ፡ ሒሳቦቹን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ እንዲያዘገይ ፡ ወይም ፡ እንዲለወጥ ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፭፻፴፮ ። ከአስተዳዳሪው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

ከአስተዳዳሪው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ በሆኑት ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

ቍ ፡ ፭፻፴፯ ። ከአደራ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

(፩) አስተዳዳሪው ፡ በአደራው ፡ ንብረት ፡ ረገድ ፡ የተዋዋሉትን ፡ [ሀብቶች ፡ በሚመለከት ፡ ውል ፡ የተዋዋላቸው ፡ ሰዎች ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ በሆኑት ፡ ሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ መብታቸውን ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

(፪) የአደራ ፡ ንብረት፡ አስተዳዳሪው ፡ በግልጽ ፡ ራሱ ፡ የገባበት ፡ ግዴታ ፡ ከሌለ ፡ ወይም፡ ስለ ፡ እንደራሴነት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከአደራው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ራሱ ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ አይያዝም ።

**ቍ ፡ ፭፻፴፰ ። የባለጥቅሞቹ ፡ መብቶች ። (፩) በአስተዳዳሪው፡ ዘንድ ።**

(፩) የአደራው፡ ንብረት፡ ባለጥቅም ፤ በአደራው ፡ ንብረት ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ ለእርሱ ፡ የሚገባው ፡ ትርፍ ፡ እንዲሰጠው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ባለጥቅሙ ፡ መብቶቹ፡ በሚያሠጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆን ፡ አስተዳዳሪው ፡ እንዲሻር ፡ ወይም ፡ የተገቡ ፡ ተያዦችን ፡ እንዲሰጥ ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፴፱ ። (፪) በአደራ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ።**

(፩) የአደራ፡ ንብረቶች፡ ባለጥቅም፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ በሚባሉት፡ ሀብቶች፡ ላይ ፡ የማዘዝ ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ ንብረቶች ፡ በሚመለከተው ፡ ነገር ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ እንዲቋረጥ ፡ ማድረግን ፡ በመሳሰለው ፡ ሥራ ፡ መብቶቹን ፡ የመጠበቅ ፡ ተግባሮችን ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

(፫) እንደዚሁም፡ ደግሞ፡ ለሦስተኞች፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ለአንዳንድ ፡ ሦስተኞች፡ ወገኖች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ንብረቶች ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ (ሀብቶች) ፤ ንብረቶች ፡ መሆናቸውን ፡ በማስታወቂያ ፡ ለመግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፵ ። ከተጠቃሚው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለውን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ያቋቋመው ፡ ሰው ፤ የዚህን ፡ የአደራውን ፡ ንብረት ፡ ገቢ ፡ ከአስተዳዳሪው ፡ እጅ ፡ ላይ ፤ በአደራው ፡ ንብረት ፡ ተጠቃሚ ፡ ከሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሊያዙት ፡ አይችሉም ፡ ብሎ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) ገቢዎቹ ፡ የማይያዙ፡ ናቸው ፡ ተብሎ፡ በዚህ ፡ በተባለው ፡ ዐይነት ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ ተነግሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የንብረቱ ፡ ተጠቃሚ ፡ ሊያስተላልፋቸው ፡ ወይም ፡ በዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ሊያገባቸው ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፵፩ ። (፪) የዳኞች ፡ ሥልጣን ።**

ስለ ፡ ሆነም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ሁኔታ፡ ሲያጋጥምና ፡ በአደራው ፡ ንብረት ፡ ተጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ወይም ፡ የተጠየቀው ፡

ገንዘብ ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ ተጠቃሚ ፡ ከሠራው ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ አታላይነት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ ባለጥቅም ፡ ወይም ፡ ከገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አንዱ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ ገቢ ፡ ገንዘቦች ፡ እንዲያዙ ፡ ወይም ፡ እንዲተላለፉ ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለውን ፡ የአደራውን ፡ ንብረት ፡ የሚያቋቁመው ፡ ውለታ ፡ መቅረት ። (፩) መደበኛ ፡ ሁኔታ ።**

ለልዩ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ውል ፡ የአደራውን፡ ንብረት ፡ ያቋቋመው ፡ ሰው ፡ የወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፫ ። (፪) የዳኞች ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ዳኞች ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ ባለጥቅም ፤ ለሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቀረበላቸው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የተባለው ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ ውል ፡ እንዲቀር ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) የአደራው ፡ አስተዳዳሪ ፡ በዳኝነቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ጊዜ ፡ መሰማት ፡ አለበት ።

(፫) ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውለውን ፡ ንብረት ፡ ያቋቋመው ፡ ሰው ፤ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ በተባለው ፡ መብት ፡ ዳኞች ፡ እንዳይሠሩበት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፬ ። የአደራው ፡ ንብረት ፡ የሒሳብ ፡ መጣራት ።**

የአደራው ፡ ንብረት ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ አስተዳዳሪው ፡ የነዚህን ፡ ንብረቶች ፡ ባለሀብትነትና ፡ የአስተዳዳሪውን ፡ ሥራ ፡ ለማስረዳት ፡ ጠቃሚዎች ፡ ከሆኑት ፡ ጽሑፎች ፡ ጋራ ፡ በንብረቱ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ የተባሉትን ፡ ንብረቶች ፡ ማስረከብ፡አለበት።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

**በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ፡ ተሰጣቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ንብረቶች ።**

**ቍ ፡ ፬፻፺፭ ። የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ።**

(፩) የማኅበሩ፡ ዋና ፡ መኖሪያ፡ ስፍራ፡ በውጭ፡ አገር ፡ ሆኖ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ለማካሄድ ፡ የሚፈቅድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ማኅበር ፡

BACK



አዲስ ፡ አበባ ፡ ለሚገኘው ፡ ለማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ግመልከቻውን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፤ ከግመልከቻውም ፡ ጋራ ፡ የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተያይዞ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ለማቋቋም ፡ የተጠየቀው ፡ ሥራ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ከመልካም ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተጠየቀውን ፡ ፈቃድ ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ፤ የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለነገሩ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ እንዲቋቋሙ ፡ በተጠየቁት ፡ ማኅበሮች ፡ ጒዳይ ፡ የሚያገባቸውን ፡ ሚኒስቴሮች ፡ አሳብ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

(፫) አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ይህን ፡ ፈቃድ ፡ ከማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከማግኘቱ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ለመጀመርም ፡ ሆነ ፡ አባሎችን ፡ ለመሰብሰብ ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፵፮ ። ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ንብረቶች ።</u>

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበ ፡ ንብረት ፡ ድርጅቶች ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ለአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ግመልከቻቸውን ፡ ካላቀረቡ ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራቸውን ፡ ለመጀመር ፡ አይችሉም ።

(፪) ይህ ፡ ሥራ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ባህል ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ፈቃድን ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ። የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርም ፡ በጒዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ ጒዳይ ፡ የሚያገባቸውን ፡ ሚኒስቴሮች ፡ አሳብ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፵፯ ። ፈቃዱን ፡ ወይም ፡ ጥያቄውን ፡ የመቀበሉ ፡ ውጤት ።</u>

(፩) በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ንብረት ፡ ድርጅቶችን ፡ ይህን ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፵፭ ፡ የተመለከተውን ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፵፮ ፡ የተመለከተውን ፡ የማጽደቅ ፡ ፈቃድ ፡ እንዳገኙ ፡ ወዲያውኑ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መብታቸው ፡ በሚጠቀሙበትና ፡ በሚሠሩበት ፡ ረገድ ፡ ልክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ተቋቋሙ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተሰጣቸው ፡ ኢትዮጵያው

ያን ፡ ማኅበሮችና፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት፡ እንደ ፡ ተመደቡ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንብረቶች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ በተቋቋሙበት፡ አገር ፡ የታወቀላቸው ፡ ዜግነት ፡ በኢትዮጵያም ፡ የታወቀላቸው ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፬፻፺፯ ፡ የተጠበቁ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ የተሰጣቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ማኅበሮች፡ወይም፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የሆኑት ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ የሚያካሂዱትና ፡ የሚያከናወኑት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ልዩ ፡ ውሳኔ ፡ ሊከለከል ፡ ወይም ፡ ሊፈቀድ ፡ ይችላል ።

(፪) የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆኑ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ንብረቶች ፡ ድርጅቶች፡በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት፡የመሆን፡ ችሎታቸው ፡ የሚቀነስባቸው ፤ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ለባ ጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በተወ ራው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፺፰ ፡ የፈቃዱን ፡ ወይም ፡ የማጽደቅ ፡ ፈቃዱን ፡ ጥያቄ ፡ ስለ ፡ መሻር ።

(፩) በቍጥር ፡ ፬፻፺፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድና ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፺፮ ፡ መሠረት ፡ የማጽደቅ ፡ ፈቃድ ፡ ያገኘው ፡ ጥያቄ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሊሻር ፡ ይቻላል ።

(፪) ይህም ፡ የፈቃድ ፡ መሻር ፡ ውሳኔ ፡ ለማኅበሩ ፡ ወይም ፡ ለንብረቱ ፡ ድርጅት ፡ በተገለጸበት ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት፡የተሰጠው፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ ዲሬክተር ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበው ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ለዳኞች ፡ የይግባኝ ፡ አቤቱታ፡ ለማቅረብ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱም ፤ ይህ ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ የማጽደቅ ፡ ፈቃድ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚሻር ፡ ወይም ፡ የማይሻር ፡ መሆኑን ፡ እስኪወስን ፡ ድረስ ፡ የፈቃዱን ፡ መሻር ፡ ውሳኔ ፡ አግዶ ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ።

# ሁለተኛ መጽሐፍ ፡፡

## ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድና ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ (አወራረስ) ።

### አንቀጽ ፡ ፬ ።

### ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡

### በጠቅላላው ።

**ቍ ፡ ፭፻፶ ። የሥጋ ፡ ዝምድና ።**

(፩) በዝምድና ፡ መተሳሰር ፡ የሚገኘው ፡ ከሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ነው ።

(፪) በወላጆችና፡ በተወላጆች ፡(ተወላድያን) ፡ መካከል ፡ በቀጥታ ፡ መሥመር፡ የሚቈጠር ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰር ፡ አለ ።

(፫) ካንድ፡ አባት፡ እናት ፡ በተወለደ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ወላጅ ፡ ብቻ ፡ በሚገናኙ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ የሚቈጠር ፡ የትውልድ ፡ መሥመር ፡ አለ ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፩ ። የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ደረጃ ።**

(፩) የሥጋ ፡ ዝምድና፡ አቈጣጠር ፡ የጋራ ፡ ከሆነው ፡ የግንድ ፡ ወላጅ ፡የዝምድና ፡ ደረጃ ፡ ጀምሮ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ካለው ፡ ትውልድ ፡ መሥመር ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

(፪) የሥጋ ፡ ዝምድና፡ ከሰባተኛው ፡ የትውልድ ፡ ደረጃ ፡ ወዲያ፡ ምንም ፡ ውጤት፡ አይሰጥም ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፪ ። ጋብቻ ።**

(፩) የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ከጋብቻ ፡ ይገኛል ።

(፪) ባል ፡ ከሚስት፡ ወደ፡ላይ፡ ከሚቈጠሩ፡ ወላጆች ፡ ወይም፡ወደ፡ታች፡የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ጋራ ፤ ሚስት ፡ ከባሏ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ወደ፡ ታች ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ (ተወላድያን) ፡ ጋራ ፡ ቀጥታ ፡ የሆነ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ አላቸው ።

(፫) ባል ፡ ከሚስቱ ፡ የጐን ፡ ዘመዶች ፡ ሚስት ፡ ከባሏ፡ የጐን ፡ ዘመዶች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ የሚቈጠር ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፫ ። የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ በ፫ኛ ፡ ደረጃ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

የጋብቻ፡ ዝምድና፡ ወደ ፡ ጐን ፡ በሚቈጠር ፡ ዝምድና ፡ ላይ ፡ ከሦስተኛ ፡ የዝምድና ፡ ደረጃ ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፬ ። በሁለት ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ።**

(፩) ባል፡ ከሚስቱ ፡ ወንድም፡ ሚስት ፤ ወይም ፡ ከሚስቱ ፡ እኅት ፡ ባል ፤ ሚስት ፡ ከባሏ ፡ ወንድም ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ከባሏ ፡ እኅት ፡ ባል ፡ ጋራ ፡ ዕጥፍ ፡ የሆነ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ አላቸው ።

(፪) ይኸው ፡ ዕጥፍ ፡ የሆነ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ተራ ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ውጤቶች ፡ አሉት ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፭ ። የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ መጨረሻ ።**

ዝምድናውን፡ ያስገኘው፡ ጋብቻ፡ ቢፈርስም ፡ በጋብቻ ፡ የተገኘው ፡ የቀጥታ ፡ ዝምድናና ፡ የጐን ፡ ዝምድና ፡ መተሳሰር ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይኖራል ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፮ ። የጉዲፈቻ ፡ ዝምድና ፡ (፩) መሠረቱ ።**

በአንድ፡ የጉዲፈቻ፡ ውል፡ የሥጋ፡ ዝምድናና፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ በተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፯ ። (፪) ውጤት ።**

በቍጥር ፡ ፭፻፶፰ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ አስተያየት ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ ልጅ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፰ ። (፫) የተጠበቀ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የጉዲፈቻ፡ አድራጊው፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ወይም፡ ወደ፡ጐን፡ የሚቈጠሩ ፡ ዘመዶች ፡ ጉዲፈቻውን፡ በግልጽ ፡ የሚቃወሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ካስታወቁ ፡ ጉዲፈቻው ፡ በነርሱ ፡ በኩል ፡ አንዳችም ፡ ውጤት ፡ አያስከትልም ።

(፪) ከዚህ፡ በላይ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ የጉዲፈቻ፡ አድራጊው፡ ዘመዶች ፡ መቃወሚያ ፡ የጉዲፈቻው ፡ ውል ፡ ከጸደቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ እስከ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በአንድ ፡ ውል ፡ አዋዋይ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ካልተመዘገበ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ (አይጸናም) ።

(፫) ጉዲፈቻ፡ በጉዲፈቻ፡ አድራጊው፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ በተወላጆቹም ፡ ላይ፡ ውጤት ፡ አለው ፡ (ይጸናል) ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፱ ። የጉዲፈቻው ፡ ልጅ ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ።**

(፩) የጉዲፈቻው ፡ ልጅ ፡ ከጥንት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰር ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይኖራል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የጉዲፈቻ፡ ልጅ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስትና ፡ ተወላጆች ፡ ላይ ፡ የዝምድናው ፡ መተሳሰር ፡ ይጸናል ።

(፫) በማንኛዎቹም ፡ ሁኔታዎች ፤ ከጉዲፈቻው ፡ ቤተ ፡ ዘመድና ፡ ከጥንት ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ መካከል ፡ ምርጫ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጉዲፈቻው ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ቅድሚያ ፡ ያገኛል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ መተጫጨት ።

**ቍ ፡ ፭፻፷ ። ትርጓሜ ።**

(፩) መተጫጨት ፡ ማለት ፡ የእጮኛውና ፡ የእጮኛዪቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ በልጆቻቸው ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ይኖራል ፡ ብለው ፡ የእነዚሁ ፡ የሁለቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ የሚያደርጉት ፡ ውል ፡ ነው ።

(፪) ወደፊት ፡ ተጋቢዎች ፡ የሆኑት ፡ የእጮኛዎቹ ፡ የየአንዳንዳቸው ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ፈቃድ ፡ ካልሰጡ ፡ በቀር ፡ መተጫጨት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ አይኖረውም ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፩ ። ለማግባት ፡ የቃል ፡ መስጠት ።**

(፩) በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የማግባት ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ መለዋወጥ ፡ መተጫጨት ፡ አይደለም ።

(፪) ይህ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ በጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ቢፈርስ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኀላፊነትና ፡ ያላግባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ማስከፈልን ፡ ያስከትላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፪ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ። (፩) የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ እንደራሴ ።**

የመጀመሪያ ፡ ጋብቻ ፡ ለሚያደርገው ፡ ዕጮኛ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ —

(ሀ) የዚሁ ፡ የአግቢው ፡ አባት ፤

(ለ) አባት ፡ የሌለ ፡ ወይም ፡ ፈቃዱን ፡ ለመስጠት ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እናት ፤

(ሐ) እናት ፡ የሌለች ፤ ወይም ፡ ፈቃድዋን ፡ ለመስጠት ፡ የማትችል ፡ የሆነች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከአያቶቹ ፡ ወይም ፡ ከቅድም ፡ አያቶቹ ፡ አንዱ ።

(መ) ወላጆች ፡ የሌሉ ፤ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ ማናቸውም ፡ ፈቃዱን ፡ ለመስጠት ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ወይም ፡ ያባት ፡ ወይም ፡ የእናት ፡ ወንድም ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፫ ። (፪) ተከታይ ፡ ጋብቻ ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ከተጠቀሱት ፡ ማንኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፤ አስቀድሞ ፡ አግብቶ ፡ ለነበረ ፡ ሰው ፡ መተጫጨቱ ፡ የሚደረግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ መተጫጨቱን ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፬ ። (፫) ሕጋዊ ፡ እንደራሴ ፡ ስለ ፡ ማጣት ።**

(፩) ወደፊት ፡ ከሚጋቡት ፡ አንዱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ የሚሆነው ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ እኅት ፤ ያባት ፡ ወይም ፡ የናት ፡ ወንድም ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመተጫጨቱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ የሚሆነውን ፡ ሰው ፡ በነጻ ፡ ይመርጣል ።

(፪) ወደፊት ፡ ከሚጋቡት ፡ አንዱ ፡ ዕጮኛ ፤ ዕድሜው ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዕጮኛዪቱ ፡ ዕድሜዋ ፡ ሓያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡

የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመተጫጨቱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ የሚሆነውን ፡ ሰው ፡ በነፃ ፡ ይመርጣል ።

ቍ ፡ ፭፻፷፫ ። የዕጮኛዎቹ ፡ ፈቃድ ።

ዕጮኛውና ፡ ዕጮኛዪቱ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ካልሰጡ ፡ በቀር ፡ መተጫጨቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፭፻፷፬ ። ጋብቻን ፡ የሚከለክል ፡ ምክንያት ።

(፩) የዕጮኛዎቹን ፡ ጋብቻ ፡ የሚከለክል ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መተጫጨቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፪) በተለይም ፡ ዕጮኛው ፡ ወይም ፡ ዕጮኛዪቱ ፡ ለጋብቻ ፡ በሕግ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕድሜ ፡ ካላደረሰ ፡ መተጫጨቱ ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፭፻፷፭ ። የመተጫጨቱ ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም) ።

የመተጫጨት ፡ ሥርዐት ፡ መተጫጨቱ ፡ በሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፭፻፷፮ ። ምስክሮች ።

(፩) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ለተጋቢዎቹ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ከሌሏቸው ፡ የመተጫጨቱ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ከባል ፡ ምስክሮች ፡ አንዱ ፤ ከሚስቲቱ ፡ ምስክሮች ፡ አንዱ ፤ የመጀመሪያ ፡ ምስ ክሮች ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፭፻፷፯ ። የመተጫጨት ፡ ማስረጃ ።

(፩) መተጫጨት ፡ በማናቸውም ፡ በሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ መዝገቦች ፡ (የክብር ፡ መዝ ገብ) ፡ መጻፍ ፡ የለበትም ።

(፪) መተጫጨትን ፡ በማናቸውም ፡ ማስረጃ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፭፻፷፰ ። መተጫጨቱ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

መተጫጨቱ ፡ ሲደረግ ፡ የሠርጉን ፡ በዓል ፡ ለማድረግ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ያል ተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕጮኛው ፡ ወይም ፡ ዕጮኛዪቱ ፡ ወይም ፡ ከቤተ ፡ ዘመዶ ቻቸው ፡ የተፈቀደለት ፡ እንደራሴ ፡ የሰርጉ ፡ በዓል ፡ እንዲደረግ ፡ ፈቃድን ፡ ከገ ለጸበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፭፻፷፱ ። የመተጫጨት ፡ መፍረስ ።

(፩) ዕጮኛው ፡ ወይም ፡ ዕጮኛዪቱ ፡ ወይም ፡ ለመተጫጨቱ ፡ ፈቃድ ፡ የሰጠው ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ መዘግየታቸውን ፡ ወይም ፡ እንቢተኛነታቸውን ፡ የሚያስረዳ ፡ ሕጋዊ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ ጋብቻውን ፡ እንቢ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መተጫጨት ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) እንዲሁም፡ ዕጮኛው፡ ወይም ፡ ዕጮኛዪቱ ፡ ወይም ፡ ለመተጫጨቱ፡ ፈቃድ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ በሁኔታ ፡ ወይም ፡ በጠባይ ፡ (በምራል) ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያደርግ ፡ ሁኔታ ፡ ያሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መተጫጨቱ ፡ ፈራሽ፡ይሆናል።

<u>ቍ ፡ ፭፻፷፪ ። የመተጫጨት ፡ መፍረስ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት</u> ። (፩) ወጪና ፡

<u>የተቀበሉትን ፡ ማጫ ፡ ስለ ፡ መመለስ ።</u>

(፩) ለመተጫጨቱ ፡ መፍረስ ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በመተጫጨት ፡ ምክንያት ፡ የተደረጉትን ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳል ።

(፪) በመተጫጨት፡ ምክንያት፡ የተቀበለውን ፡ ስጦታ ፡ ለመተጫጨቱ ፡ መፍረስ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ሰውና ፡ እንዲሁም ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ወገኖች ፡ መመለስ ፡ አለባቸው ።

<u>ቍ፡ ፭፻፷፫።(፪)የሕሊና፡ጉዳት ።</u>

(፩) የመተጫጨቱ ፡ መፍረስ ፡ ስለሚያስከትለው፡ የሕሊና ፡ ጉዳት ፤ ለመፍረሱ ፡ አላፊ ፡ ላልሆነው ፡ ዕጮኛ ፡ ወይም ፡ ለዕጮኛዪቱ ፡ ወይም ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ በሕሊና ፡ ግምት ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ካሣ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

(፪) የዚህን ፡ ካሣ፡ ልክ ፡ ለመወሰንና ፡ ካሣውንም ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለውን ፡ ባለመብት ፡ ዳኞች ፡ የአገሩን ፡ ልማድ ፡ መሠረት፡ አድርገው ፡ ይከተላሉ ።

(፫) ስለ ፡ ሕሊና ፡ ጉዳት ፡ እንዲከፈል ፡ የሚደረገው ፡ ኪሣራ፡ ከአንድ ፡ ሺሕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፷፬ ። (፫) የመቀጫ ፡ የውል ፡ ቃል ።</u>

(፩) በመተጫጨት፡ ውል፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የመቀጫ ፡ ውል ፡ ቃል ፡ ተጽፎበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መተጫጨቱ ፡ እንዲፈርስ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፤ በውሉ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ሁኔታው ፡ የሚያስከትላቸውን ፡ ሁሉ ፡ በመገመት ፡ በውሉ ፡ የተጠቀሰውን፡ ገንዘብ ፡ ዳኞች ፡ ሊቀንሱት ፡ ይቻላል ።

(፫) ገንዘቡ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቀነስ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፷፭ ። የወላጅ ፡ መቃወም ።</u>

(፩) በግልጽ ፡ ፈቃዱን ፡ ያልሰጠ ፡ ከዕጮኛዎቹ ፡ ያንደኛው ፡ ወላጅ ፡ ለጋብቻው ፡ ተቃዋሚነቱን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመተጫጨቱ ፡ መፍረስ ፡ ምንም ፡ አላፊነትን ፡ አያስከትልም ።

(፪) እንዲህ፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የተቀበሏቸውን ፡ ስጦታዎች ፡ ብቻ፡ መመለስ ፡ አለባቸው ።

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፸፮ ። ይርጋ ።**

በመተጫጨት ፡ መፍረስ፡ ላይ ፡ ተመሥርተው ፡ የሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ መተጫጨቱ ፡ ከፈረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ካልቀረቡ ፡ በይርጋ ፡ የሚታገዱ ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ጋብቻ ፡ አፈጻጸም ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፯ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጋብቻ ።**

(፩) ጋብቻ፡ ባንድ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ ሕጉ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ባገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ የሚደረጉትን ፡ ጋብቻዎች ፡ ያውቃል ፡ (ይቀበላል) ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፰ ። ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ።**

ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አንድ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም፡ ፊት ፡ ሲቀርቡና ፡ የሕዝብ ፡ የክብር፡ መዝገብ ፡ ሹምም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ሲቀበለው፡ ጋብቻ ፡ ተፈጸመ ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፱ ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ።**

አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ውሳኔዎችን ፡ ወይም ፡ ሥርዐቶችን ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንደኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ሲፈጽሙ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የሚጸና ፡ ጋብቻ ፡ እንዳቋቋሙ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፭፻፹ ። የልማድ ፡ ጋብቻ ።**

አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት፡ ሴት፡ በጐሣቸው ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ በአንኛው ፡ ጐሣ ፡ ልማድ ፡ ከሁለቱ ፡ መካከል ፡ ነዋሪ ፡ የሆነውን ፡ ግንኙነት ፡ የሚያስከትል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ ፈጽመዋል ፡ የሚያሰኘውን ፡ ካደረጉ ፡ በመካከላቸው ፡ ጋብቻ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ለማንኛዎቹም ፡ ዐይነቶች ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚሆኑ ፡ አጠቃላይ ፡ ሁኔታዎች ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፩ ። ዕድሜ ።**

(፩) ወንድ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፤ ሴቲቱ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላቸው ፡ ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም ።

(፪) ስለ፡ ከባድ፡ ምክንያት ፡ በከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ለመቀነስ ፡ እንዲቻል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተለይ ፡ የሚሾሙት ፡ ሰው ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፹፱ ። የሥጋ ፡ ዝምድና ።**

ጋብቻ ፡ የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፺ ። የጋብቻ ፡ ዝምድና ።**

ጋብቻ፡ የጋብቻ፡ ዝምድና ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፩ ። በሕግ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ልጅነት ።**

የዲቃላ ፡ ልጅነት ፡ ተወላጅነቱ ፡ በሕግ ፡ የታወቀለት ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ፡ ከዚህ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ሁለት ፡ ቍጥሮች ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ጋብቻን ፡ ለማስከልከል፡ በቂ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፪ ። በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰረ ፡ ከሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ሁለተኛ ፡ ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፫ ። ጋብቻን ፡ በእንደራሴ ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) እያንዳንዳቸው፡ ተጋቢዎች ፤ ጋብቻ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸው ፡ መፍቀድ ፡ አለባቸው ።

(፪) ስለ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ የመንግሥቱ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ በእንደራሴነት ፡ ጋብቻን ፡ መፈጸም ፡ አይፈቀድም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፬ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ጋብቻ ።**

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ጋብቻ ፤ ሊፈጸም ፡ የሚቻልበት ፤ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቷል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፭ ። በፍርድ ፡ የተከለከለ ።**

(፩) በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ዳኞች ፡ ካልፈቀዱለት ፡ በቀር ፡ ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

(፪) ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ ለዳኞቹ ፡ የሚደርሳቸውን ፡ ጥያቄ ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ አሳዳሪው ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፫) በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ሊፈጽም ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቷል ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፱ ። ኀይል ።**

(፩) መፍቀዱ ፡ የተደረገው ፡ በኀይል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) በኀይል ፡ ተደረገ ፡ የሚባለው ፡ ከባድ ፡ ከሆነ ፡ ጉዳትና ፡ ከቀረበ ፡ ዛቻ ፡ የተነሣ ፡ ፈቃዱን ፡ የሰጠውን ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ ከተወላጆቹ ፡ አንዱን ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ፈቃዱን ፡ የሰጠው ፤ አንዱን ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አክብሮ ፡ በመፍራት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺ ። ዋና ፡ መሳሳት ። (፩) መሠረቱ ።**

አንደኛው ፡ ተጋቢ ፡ በአንደኛው ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ መሳሳት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈቃዱ ፡ የተጓደለ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፩ ። (፪) የተወሰኑ ፡ ምክንያቶች ።**

ማንኛውም ፡ መሳሳት ፡ የማይሆን ፡ ሆኖ ፤ ዋና ፡ መሳሳት ፡ የሚባሉት ፡—

(ሀ) በሚያገቡት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መሳሳት ፤ ይኸውም ፡ አገባዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ያላሰበውን ፡ አግብቶ ፡ ሲገኝ ፤

(ለ) በሚያገቡት ፡ ሰው ፡ ሃይማኖት ፡ መሳሳት ፤ ይኸውም ፡ ያገባው ፡ ሰው ፡ ሃይማኖት ፡ የርሱን ፡ ሃይማኖት ፡ ያልመሰለ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) በሚያገቡት ፡ ሰው ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ ሰውነት ፡ መሳሳት ፤ ይኸውም ፡ ያገቡት ፡ ሰው ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ የያዘው ፡ ወይም ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፪ ። መቃወሚያ ። (፩) ማን ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚችል ።**

(፩) ጋብቻውን ፡ ለመቃወም ፡ የሚቻለው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በጋብቻ ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፷፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ እንደራሴ ፡ የሚባለው ፡ ወይም ፡ አካለ፡መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ አግቢ ፡ አሳዳሪው ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ በዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፫) ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፫ ። (፪) የሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ዐይነት ።**

(፩) እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ መቃወሙ ፡ የጋብቻው ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ጊዜ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ለመቃወሙ ፡ ማናቸውም ፡ ልዩ ፡ አሠራር ፡ አያስፈልገውም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፩ ። (፫) መቃወምን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

(፩) በጋብቻው፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ መቃወም ፡ እንዲቀር ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰም ፡ ቢሆን ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ መቃወም ፡ የተደረገበት ፡ ሰው ፡ ዕድሜው ፡ ከሐያ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደፊት ፡ ከሚጋቡት ፡ ዕጮኞች ፡ ያንደኛው ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ባደረገው ፡ መቃወም ፡ ላይ፡ ማንኛቸውንም፡ አቤቱታ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፪ ። (፬) ለመቃወም ፡ ስላለመቻሉ ።**

(፩) በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን፡ የመጀመሪያውን ፡ መቃወም ፡ ያልተቀበሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጋብቻው ፡ ሌላ ፡ መቃወሚያ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፪) ዐቃቤ፡ ሕግ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አስቀድሞ ፡ አግብቶ ፡ በነበረ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፫ ። በብቸኛነት ፡ ለመኖር ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ሴቲቱ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበራት ፡ ጋብቻ ፡ ከቀረበት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ መቶ ፡ ንያ ፡ ቀን ፡ ካላለፈ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማግባት ፡ አትችልም ።

(፪) ሴቲቱ ፡ ይህ ፡ አብሮ ፡ መኖር ፡ ከተቋረጠ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ እንደ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ውሳኔ ፡ የጸና ፡ አይሆንም ።

(፫) በብቸኝነት፡ ለመኖር ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ እንዳትጠብቅ፡ ዳኞች ፡ ሊፈቅዱላት ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፬ ። ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ።**

ከእጮኞዎቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወይም ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ ከጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሳያቋርጥ ፡ በሚኖርበት ፡ ቦታ ፡ ጋብቻው ፡ በቀበሌው ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ ይፈጸማል ።

**ቍ ፡ ፭፻፺፭ ። ያለ፡ማግባት ፡ ግዴታዎች ፡ (ውለታዎች) ።**

(፩) አንድ፡ ሰው፡ አላገባም ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደ፡ ገና፡ አላገባም ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ ቢሰጥ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፪) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹምም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አይመለከትም

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፺፱ ። ጋብቻን ፡ ለማድረግ ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።**

ወደ፡ ፊት ፡ የሚጋቡት ፡ ዕጮኛዎች ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ ማሰባቸውን፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ካንድ ፡ ሳምንት ፡ አስቀድመው ፡ ለሕዝብ ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ያስታውቃሉ ።

**ቍ ፡ ፮፻ ። ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

(፩) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ፡ ሹምም ፡ የጋብቻው ፡ ሁኔታዎች ፡ ተከናውነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያረጋግጣል ።

(፪) ጋብቻውን፡ የሚከለክል፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ የተወሰነ ፡ ወይም ፡ እርግጠኛ ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ የተረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ ይከለክላል ።

(፫) እንዲህ፡ ሲሆን፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚጋቡት፡ ዕጮኛዎች ፡ የከለከለበትን ፡ ምክንያት ፡ ያስታውቃል ።

**ቍ ፡ ፮፻፩ ። በመከልከሉ ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

(፩) የሕዝብ ፡ የክብር፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ባደረገው ፡ ክልከላ ፡ ላይ ፡ ከዕጮኛዎቹ ፡ አንዱ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ፤ ዳኞቹም ፡ ስለዚሁ ፡ ክልከላ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣሉ ።

(፪) ክልከላው፡ ያላግባብ ፡ መሆኑን ፡ ዳኞቹ ፡ የበየኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማናቸውም፡ ምክንያት ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሊከለክል ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፪ ። የጋብቻን ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

ጋብቻው ፡ የሚፈጸምበት ፡ ( የሚከበርበት) ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚጋቡት ፡ ዕጮኛዎችና ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ መካከል ፡ በስምምነት ፡ ይወሰናል ።

**ቍ ፡ ፮፻፫ ። የጋብቻን ፡ ሥርዐት ፡ አፈጻጸም ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) ጋብቻው፡ ወደ፡ ፊት፡ የሚጋቡት፡ ዕጮኛዎችና ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ዕጮኛዎች፡ ሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ በግልጽ ፡ ይፈጸማል ።

(፪) ምስክሮቹም፡ የባልና፡ የሚስቱ ፡ ዘመዶች ፡ ወይም ፡ ባዕዶች ፡ ሊሆኑ፡ይችላሉ።

**ቍ ፡ ፮፻፬ ። የጋብቻ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዐት ።**

(፩) ወደ ፡ ፊት ፡ የሚጋቡት ፡ ዕጮኛዎች፡ ምስክሮች ፡ ጋብቻውን ፡ የሚከለክል ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ አናውቅም ፡ ሲሉ ፡ በመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ ይሰጣሉ ።

(፪) የሕዝብ ፡ የክብር፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከሚጋቡት ፡ ዕጮኛዎች ፡ ከያንዳንዳቸው ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ለመሆን ፡ የመፍቀዳቸውን ፡ ቃል፡ ይቀበላል ።

BACK



(፫) የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በሥልጣኑ ፡ ውስጥ ፡ ለሆነ ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ ስም ፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰሩ ፡ መሆናቸውን ፡ አስታውቆ ፡ ወዲያውኑ ፡ የጋብቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ ያዘጋጃል ።

ክፍል ፡ ፫ ።

ሌሎች ፡ ዐይነቶች ፡ ጋብቻዎች ።

ቍ ፡ ፭፻፭ ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ።

(፩) የሃይማኖት፡ ጋብቻ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታና ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ይወሰናል ።

(፪) በዚህ፡ ሕግ፡ ስለ ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም) ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ፡ ስለ፡ ሰዎች ፡ በሚለው፡ አንቀጽ፡ በተመለከተው፡ መሠረት፡ አንድ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መጻፍ ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፮ ። የልማድ ፡ ጋብቻ ።

(፩) የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻልበት፡ ሁኔታና ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ዐይነት ፡ በአገሩ ፡ ልማድ ፡ ይወሰናል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ፡ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ የተመለከቱት፡ ሁኔታዎች ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መጻፍ ፡ ይገባዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

የጋብቻ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ ምክንያት ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ለጋብቻ ፡ ሥርዐቶች፡ ሁሉ ፡ የሚሆን ፡ የወል ፡ ሁኔታ ።

ቍ ፡ ፭፻፯ ። የዕድሜ ፡ ሁኔታ ። (፩) የወንጀል ፡ ቅጣት ።

(፩) ዕድሜው፡ ከዐሥራ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ወይም፡ ዕድሜዋ ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነችውን፡ሴት ፡ እያወቀ፡ወይም፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ የጋብቻን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ያስፈጸመ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተጻፈው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ከሁለቱ፡ ተጋቢዎች፡ ዕድሜው፡ ከዐሥራ፡ ስምንት ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ወንድ ፡ ከ፲፭ ፡ በታች ፡ የሆነችውን ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ከ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆናት፡ሴት፡ ከ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነውን ፡ ወንድ ፡ ያገባችና ፡ እንዲሁም፡ ጋብቻቸውን፡ የፈቀዱ ፡ ሰዎች ፤ ለጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምስክሮች ፡ የሆኑት ፡ በወንጀ ለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣሉ ።

**ቍ ፡ ፮፻፰ ። የጋብቻው ፡ መፍረስ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ በማናቸ ውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ፡ ይወሰናል ።

(፪) በሕጉ፡ በሚያስገድደው፡ መሠረት ፡ ለጋብቻ ፡ የተወሰነው ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ተሟልቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ጥያቄ ፡ ሊቀርብ ፡ አይ ችልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፱ ። የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፤ (፩) የጋብቻ ፡ መፍረስ ።**

በሥጋ ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ምክንያት ፡ ያለውን ፡ ክልከላ ፡ በመጣስ ፡ ጋብቻ ፡ ተደርጎ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ይደረጋል ። (ይወሰናል) ።

**ቍ ፡ ፮፻፲ ። (፪) የወንጀል ፡ ቅጣት ።**

(፩) በሥጋ፡ ወይም፡ በጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ምክንያት ፡ የሚከለከል ፡ ነገር፡ መኖሩን፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ በሁለት ፡ ተጋቢዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻን ፡ የሚያስፈጽም ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸ ሙበታል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የዝምድና ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ መተሳሰር ፡ መኖሩን ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ጋብቻ ፡ እንዲደረግ ፡ የፈቀዱ ፡ ተጋቢዎች ፡ ራሳቸው ፡ ጋብቻ ውን፡ የፈቀዱና ፡ ለጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምስክሮች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች፡ በወን ጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ የተጻፉት ፡ ቅጣቶች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ዳኞች ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ የወሰኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፲፩ ። በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ጋብቻ ። (፩) የወንጀል ፡ ቅጣት ።**

(፩) ከዚህ፡ በፊት፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰረ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ሁኔታ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ የአንድ ፡ ሰውን ፡ ጋብቻ ፡ ያስፈጸመ ፡ ባለሥልጣን፡ ወይም ፡

የሕዝብ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም፡ ይህን፡ ሁኔታ ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ጋብቻ ፡ እንዲደረግ ፡ የፈቀዱ ፡ ተጋቢዎቹ ፡ ራሳቸው ፡ ጋብቻውን ፡ የፈቀዱና ፡ ለጋብቻው ፡ ሥን ፡ ሥርዐት ፡ ምስክር ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይቀጣሉ ።

**ቊ ፡ ፮፻፲፪ ። (፪) የጋብቻ ፡ መፍረስ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ ቢጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ፡ ያደረገው ፡ ሰው፡ (ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት)፡ አንደኛው ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ ይፈርሳል ።

(፪) ዳኞች፡ ጋብቻው፡ እንዲፈርስ፡ የሚያደርጉት ፡ በማይጠረጠር ፡ አኳኋን ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ ባለቤት ፡ ጋብቻው ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ፡ በሕይወት ፡ መኖሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፮፻፲፫ ። (፫) ስለ ፡ ማጽናት ።**

የመጀመሪያዪቱ ፡ ሚስት ፡ ለመኖርዋ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ያለበት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ተደርጓል ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፮፻፲፬ ። ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፤ (፩) የወንጀል ፡ ቅጣት ።**

(፩) በአእምሮው ፡ መናወጽ ፡ የተከለከለ ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ በአእምሮው ፡ መናወጽ ፡ የተከለከለውን ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖር ፡ ጋብቻውን ፡ ያስፈጸመው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፤ ወይም ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለውን ፡ ሰው ፡ ያጋባና ፡ ለዚሁ ፡ ጋብቻ ፡ ምስክሮች ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

**ቊ ፡ ፮፻፲፭ ። (፪) የጋብቻው ፡ መፍረስ ።**

(፩) ጋብቻው፡ እንዲፈርስ፡ አካለመጠን፡ ያላደረሰው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በአእምሮው፡ መናወጽ ፡ ምክንያት ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፡ መፍቀድ ፡ ይገባው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ ዳኞችን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ችሎታ ፡ ያጣው ፡ ሰው ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ ከቀረ ፡ ከ፮ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ለመቅረብ ፡ አይችልም ።

(፫) ለዚሁ፡ ጕዳይ ፡ ሌሎች፡ ሰዎች ፡ የሚያቀርቡት ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ መኖሩን፡ ካወቁ ፡ ከ፮ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ወይም ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ሊቀርብ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፮፻፲፮ ። ከኀይል ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ የተደረገ ፡ ጕድለት ፤ (፩) የወንጀል ፡ ቅጣት ።

(፩) በኀይል፡ ጋብቻን፡ እንዲፈቅድ ፡ ያደረጉት፡ ሰዎችና ፡ ለዚሁ፡ ጋብቻ፡ ምስክሮች፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በወንጀል ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ ይህን ፡ ሁኔታ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ይህን ፡ ጋብቻ፡ ያስፈጸመ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፮፻፲፯ ። (፪) የጋብቻ ፡ መፍረስ ።

(፩) ማናቸውም፡ ሰው ፡ በኀይል፡ ጋብቻ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለዚሁ፡ ጕዳይ፡ የሚሆነው ፡ ጥያቄ ፤ የኀይል ፡ ሥራው ፡ ከተቋረጠ፡ ከስድስት፡ ወር ፡ በኋላና ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻው ፡ ከተፈጸመ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት፡ በኋላ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፮፻፲፰ ። ስሕተት ።

(፩) ማንም፡ ሰው፡ ከዋና ፡ ስሕተት ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስለት ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ የሚሆነው ፡ ጥያቄ፡ ስሕተቱን፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ በሚቀጥለው ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ውስጥና ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻው ፡ ከተፈጸመበት ፡ በሚከተሉት ፡ ፪ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ካልቀረበ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፮፻፲፱ ። መቃወም ።

(፩) በጋብቻው፡ ላይ፡ የተደረገውን ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ መቃወም ፡ በማቃለል ፤ ጋብቻውን ፡ የሚያስፈጽም ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም፡ ለጋብቻው፡ ፈቃደኛ ፡ የሆኑ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ተጋቢዎች ፤ ጋብቻውን ፡ የፈቀዱ ፡ ሰዎችና ፡ ምስክሮች፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።

(፫) በጋብቻው ፡ ላይ ፡ ለቀረበው ፡ መቃወሚያ ፡ ዋጋ ፡ አልተሰጠውም ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፮፻፳ ። በብቸኝነት ፡ ለመኖር ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) በብቸኝነት፡ ለመኖር፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ያንዲቱን ፡ ሴት ፡ ጋብቻ ፡ የሚያስፈጽም ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም፡ ለጋብቻው፡ ፈቃደኛ ፡ የሆኑ ፡ ተጋቢዎች ፤ ጋብቻውን ፡ የፈቀዱ ፡ ሰዎችና፡ ምስክሮች፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ በተመለከቱት፡ቅጣቶች፡ይቀጣሉ።
(፫) በብቸኘነት ፡ ለመኖር ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አልተከበረም ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ጋብቻ ፡ እንዲፈርስ ፡ ሊታዘዝ ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ።

### ቍ ፡ ፮፻፷፩ ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሥልጣን ፡ አለመኖር ።

(፩) ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተደነገገውን ፡ ሳይፈጽም ፡ ዐውቆ ፡ ወይም፡ ይህን፡ ሁኔታ፡ ማወቅ፡ ሲገባው፡ ጋብቻውን፡ ያስፈጸመ፡ የሕዝብ፡የክብር ፡ መዝገብ፡ ሹም፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል።
(፪) እንዲሁም፡ ተጋቢዎቹና ፡ ለዚሁ ፡ ጋብቻ ፡ ምስክሮች ፡ የሆኑት ፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣሉ ።
(፫) የሕዝብ፡ የክብር፡ መዝገብ ፡ ሹም፡ ሥልጣን፡ የለውም ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ብቻ፡ ጋብቻ ፡ እንዲፈርስ ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

### ቍ ፡ ፮፻፷፪ ። ሥርዐቶችን ፡ አለመጠበቅ ።

(፩) የጋብቻን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ (ደንቦች)፡ ያልጠበቀ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ይቀጣል ።
(፪) በእንደዚህ ፡ ያሉት፡ ምክንያቶች ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ሌሎች ፡ ጋብቻዎች ።

### ቍ ፡ ፮፻፷፫ ። ፈራሽነት ።

(፩) በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ግዴታዎች፡ ወይም፡ ሥርዐቶች፡ ባለመፈጸማቸው፡ ምክንያት፡ ጋብቻውን፡ ዳኞች፡ ሊያፈርሱት፡ አይችሉም።
(፪) በሃይማኖት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተነገረ ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ መሻር ፡ ለፍቺው ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።
(፫) በልማድ፡ ጋብቻ፡ ባለሥልጣኖች፡ የተነገረ ፡ የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ መሻር ፡ በሕግ፡ ፊት ፡ ተቀባይነትን ፡ አያገኝም ።

### ቍ ፡ ፮፻፷፬። የገንዘብ ፡ መቀጫና ፡ የጉዳት ፡ ካሣዎች ።

(፩) የሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ለልማድ፡ ጋብቻ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ሥርዐቶች፤ በሃይማኖት፡ ወይም፡ በተከተሉት፡ ልማድ፡ መሠረት ፡ ጉዳት ፡ ለደረሰበት፡ ወገን፡ ጥቅም፤ የጉዳት፡ ካሣ፡ እንዲሰጥ፡ እንዲከፍል፡ ሊወሰን ፡ ይቻላል ።

(፪) ይሆን ፡ ተቃዋሚ ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ የተሰጡት ፡ የጉዳት ፡ ካሣዎች ፡ አለመጠን ፡ የበዛ ፡ መስሎ ፡ ከታያቸው ፡ ዳኞች ፡ መቀነስ ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ለርትዕ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ተግባር ፤ አእምሮ ፡ የማይቀበለው ፡ ወይም ፡ ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ልማዱ ፡ ውጤት ፡ እንዳይኖረው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የጋብቻ ፡ ውጤት ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።

### ቍ ፡ ፮፻፴፭ ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጋብቻ ፡ ትክክለኛነት ።

(፩) በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ቢሆን ፡ ጋብቻ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ትክክል ፡ የሆኑ ፡ ውጤቶችን ፡ ይሰጣል ።

(፪) በዚህ ፡ ረገድ ፡ ጋብቻ ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ በታዘዙት ፡ ሥርዐቶች ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመም ቢሆን ፡ ልዩነት ፡ አይደረግለትም ።

### ቍ ፡ ፮፻፴፮ ። የሩካቤ ፡ ሥጋው ፡ ግንኙነት ፡ መፈጸም ።

ጋብቻው ፡ ለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋው ፡ ግንኙነት ፡ በውነ[ት] መፈጸሙ ፡ ወይም ፡ በግምት ፡ ተፈጽሟል ፡ መባሉ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

### ቍ ፡ ፮፻፴፯ ። የጋብቻው ፡ ውል ።

(፩) ተጋቢዎቹ ፡ በገንዘባቸው ፡ በኩል ፡ ጋብቻቸው ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤ[ት] ጋብቻቸውን ፡ ከማድረጋቸው ፡ በፊት ፡ በውል ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በመካከላቸው ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ አን[ዱ] ላንዱ ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎችና ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ሊያረጋግጡ ፡ ይችላለ[ሉ]

(፫) ልዩነት ፡ እንዳይደረግባቸው ፡ ሕግ ፡ የማይፈቅዳቸው ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁለ[ቱ] እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

### ቍ ፡ ፮፻፴፰ ፡ ከባልና ፡ ሚስት ፡ የአንደኛው ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።

(፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ የሚያደርገውን ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ እንዲፈቅድ ፡ አስፈላጊ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ የሞግዚቱም ፡ ፈቃ[ድ] አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ የሚያደርገውን ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እርሱ[ው] ራሱ ፡ ሊፈጽም ፡ ይገባዋል ። ዳኞች ፡ ካላጸደቁት ፡ ግን ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

BACK



(፫) በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መዋዋልን ፡ ስለሚያስከትል ፡ ጉዳይ ፡ የችሎታ ፡ ማጣት ፡ ደንብ ፡ አይጸናበትም ።

ቍ ፡ ፯፻፳፱ ። የውሉ ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም) ።

የጋብቻው ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ ካልሆነና ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ሁለቱ፡ በባልየው፡ ወገን ፡ ሁለቱ ፡ በሚስቲቱ ፡ ወገን ፡ የፈረሙበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፴ ። የውሉ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ቦታ ።

(፩) የውሉ ፡ አንድ ፡ ግልባጭ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ውል ፡ ለማፈራረም ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የሚቀመጥ ፡ ይሆናል ።

(፪) ተጋቢዎቹ፡ ለማየት፡ ሲፈቅዱ ፡ እንዲሁም ፡ ዳኛው ፡ ወይም ፡ ተጋቢዎቹ ፡ የፈቀዱላቸው ፡ ሰዎች ፡ የውሉን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማየት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፯፻፴፩ ። ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ስላለው ፡ ነፃነት ፡ ወሰን ።

(፩) የጋብቻ፡ ውል፡ በሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ማንኛውንም ፡ ግዴታ ፡ ሊያስከትል ፡ ወይም ፡ አዛዥነት ፡ ባላቸው ፡ በሌሎች ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡— ላይ ፡ የመቃወምን ፡ ሁኔታ ፡ ለማምጣት ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የጋብቻው ፡ ውል ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ሐተታ ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ ተጋብተናል ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ለመመራት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፯፻፴፪ ። የጋብቻን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) የጋብቻው ፡ ውል ፡ እንዲለዋወጥ ፡ ሁለቱ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በሚያቀርቡት ፡ ጥያቄ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ሊለዋወጥ ፡ ይችላል ።

(፪) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጥቅም ፡ የሚጠይቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ ከሁለቱ ፡ ባንደኛው ፡ ጠያቂነት ፡ ውሉ ፡ ሊለዋወጥ ፡ ይችላል ።

(፫) የውሉን፡ መለዋወጥ፡ የሚያመለክተው ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ውል ፡ ለማፈራረም ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የሚቀመጥ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፯፻፴፫ ። በባልና ፡ ሚስት ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ውል ።

(፩) ባልና ፡ ሚስት ፡ ተጋብተው ፡ በሚኖሩበት ፡ ጊዜ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ የሚደረገውን ፡ ውል ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ የፍርድ፡ ቤት፡ ዳኞች ፡ ካላጸደቁት ፡ በቀር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፪) በዚህ፡ ሕግ፡ በግልጽ ፡ ተለይተው ፡ የተነገሩት ፡ ውሎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው።

ቍ ፡ ፯፻፴፬ ፡ ሕጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ (ሥርዐት) ።

የጋብቻ ፡ ውል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የጋብቻው ፡ ውል ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ በባልና ፡ ሚስት ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ሳይጸና ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይሠራል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፪ ።

## በሰዎች ፡ ላይ ፡ ጋብቻው ፡ ያለው ፡ ውጤት ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፭ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሹም ።**

(፩) ባል ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሹም ፡ ነው ።

(፪) በዚህ፡ ሕግ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ እንዲሁም፡ ባል ፡ ለሚያዛት፡ ሕጋውያን፡ ለሆኑ፡ ነገሮች፡ ሚስት፡ መታዘዝ፡ አለባት።

**ቍ ፡ ፮፻፴፮ ። መከባበር ፡ መረዳዳትና ፡ መተጋገዝ ።**

(፩) ባልና ፡ ሚስት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መረዳዳትና ፡ መተጋገዝ ፡ አለባቸው ።

(፪) በጋብቻው፡ ውል፡ ውስጥ፡ ለዚህ፡ ተቃራኒ፡ የሆነ፡ ደንብ፡ ሊጻፍበት፡ አይቻልም።

**ቍ ፡ ፮፻፴፯ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሪነት ፡ (፩) ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) በባልዮው፡ መሪነት፡ ለቤተ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ጥቅም ፡ ሲሉ ፤ ባልና፡ ሚስቲቱ፡ የልጆቻቸውን ፡ የግብረ፡ ገብነትና ፡ የተፈጥሮ ፡ እድገት ፡ ማረጋገጥና ፡ እንዲሁም ፡ ወደፊት ፡ ልጆቻቸውን ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ለማሳደግና ፡ የኑሮዋቸውን ፡ ድርጅት ፡ ለማረጋገጥ ፡ መረዳዳት ፡ አለባቸው ።

(፪) በጋብቻቸው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ የገቡበት ፡ ግዴታ ፡ ተከብሮ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፰ ። (፪) ከባልና፡ ሚስት፡ የአንዱ፡ መታወክ ።**

(፩) ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንደኛው ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በስፍራው ፡ የማይገኝ ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ዘመዱን ፡ በመተው ፡ ምክንያት፡ የተፈረደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቍጥር ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ አንደኛው ፡ ብቻውን ፡ ይፈጽማል ።

(፪) ከሁለቱ ፡ አንዳቸው ፡ የአንድነት ፡ ኑሮውን ፡ በፈቃዱ ፡ ትቶ ፡ የሄደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከመኖሪያ ፡ ስፍራው ፡ በመራቁም ፡ ሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የፈቃደኛነት ፡ አሣቡን ፡ ለመግለጽ ፡ በማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜም ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) የጋብቻው ፡ ውል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያሉትን ፡ ሥርዐቶች ፡ አፍራሽ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፴፱ ። ከጋብቻ ፡ በፊት ፡ ከሌላ ፡ ስለ፡ተወለደ ፡ ልጅ ።**

(፩) ከባልና ፡ ሚስቲቱ ፡ አንዱ ፡ ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ከሌላ ፡ ስለ ፡ ወለዳቸው ፡ ልጆች ፡ ማሳደግን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ብራሱ ፡ አሳብና ፡ መሪነት ፡ የፈቀደውን ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ይህን ፡ ሥርዐት ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፵ ። አብሮ ፡ መኖር ።**

(፩) ባልና ፡ ሚስት ፡ አብረው ፡ እንዲኖሩ ፡ ይገደዳሉ ።

(፪) ይህ ፡ አድራጎት ፡ ጤንነታቸውን ፡ በብርቱ ፡ የሚቃወም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከጋብቻቸው ፡ ውል ፡ በተገኘው ፡ ግዴታ፡ መሠረት ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ፡ ጋራ ፡ ደንበኛውን ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

(፫) ይህን ፡ ሥርዐት ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፩ ። የመኖሪያ ፡ ስፍራን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) አብረው ፡ የሚኖሩበትን ፡ ስፍራ ፡ የሚወስነው ፡ ባልየው ፡ ነው ።

(፪) የመኖሪያቸውን፡ ቦታ፡ ባልየው ፡ የወሰነው ፡ ያለ፡ አገባብ ፡ ወይም ፡ የጋብቻውን ፡ ውል ፡ ድንጋጌዎች ፡ በግልጽ ፡ ተቃራኒ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ፡ ሚስቲቱ ፡ ለቤተ፡ዛመድ ፡ ዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ትችላለች ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፪ ። በስምምነት ፡ ስለ ፡ መለያየት ።**

(፩) ባልና ፡ ሚስት ፡ ላንድ፡ ለተወሰነ ፡ ወይም፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተለያይተው ፡ ለመኖር ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪ ስለዚህ፡ ጉዳይ፡ የተደረገውንም ፡ ስምምነት ፡ የመለወጡ ፡ ጉዳይ ፡ የማይገባ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ አስቦ ፡ ሊለውጠው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፫ ። የመተማመን ፡ ግዴታ ።**

(፩) ሚስት ፡ ለባሉዋ ፡ ታማኝ ፡ መሆን ፡ ይገባታል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ባል ፡ ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፬ ። የባልየው ፡ የጥበቃ ፡ ተግባር ።**

(፩) ባል ፡ ሚስቱን ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) ምክንያት ፡ የሌለው ፡ የማይበድል ፡ ከመጠንም ፡ ያላለፈ ፡ ከሆነ ፡ ለኑሮዋቸውም ፡ መልካም ፡ ጥቅም ፡ ከሆነ ፤ ባል ፤ ሚስቱ ፡ የምታደርጋቸውን ፡ ግንኙነቶች ፡ ለመቈጣጠርና ፡ የጠባይዋንም ፡ አመራር ፡ ለመጠበቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፵፭ ። የባልና ፡ የሚስት ፡ የሞያ ፡ ሥራ ።**

(፩) ከተጋቢዎቹ ፡ እያንዳንዱ ፡ የመረጠውን ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የጥበብ ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ይችላል ።

(፪) ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ግን ፡ ለትዳራቸው ፡ ለቤተ ፡ ዘመዳቸው ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ የማይጠቅም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያንደኛውን ፡ የተወሰነ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ሞያ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፮ ። የቤት ፡ አያያዝ ።**

ባል፡ አሽከር፡ ለመቅጠር ፡ ችሎታ፡ የሌለው ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ሚስቲቱ ፡ የቤት ፡ አያያዝን ፡ ሥራ ፡ እንድታከናውን ፡ ግዴታ ፡ አለባት ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ጋብቻው ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ውጤት ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፯ ። የባልና ፡ ሚስት ፡ የግል ፡ ሀብት ። (፩) ያለገንዘብ ፡ የተገኙ ፡ ሀብቶች ።**

በጋብቻቸው ፡ ጊዜ ፡ የነበሯቸው ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ሀብቶች ፡ ወይም ፡ ከጋብቻቸው ፡ በኋላ ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ ያገኙዋቸው ፡ ሀብቶች፡ ለየራሳቸው፡ የግል ፡ ሀብቶቻቸው ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፰ ። (፪) በገንዘብ ፡ የተገኙ፡ ሀብቶች ።**

(፩) እንዲሁም ፡ ከተጋቡ፡ በኋላ ፡ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ በገንዘቡ ፡ የገዛቸው ፡ ሀብቶች ፡ የግል ፡ ሀብቶቹ ፡ ናቸው ፤ ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ ሀብቱ ፡ የተገኘው፡ በግል ፡ ገንዘቡ ፡ የገዛው ፡ ሲሆንና ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ገንዘቡ ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ልውጫ ፡ ያገኘው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ ገንዘቡ ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ ደግሞ፡ በራሱ ፡ ሀብት ፡ ልውጫ ፡ ያገኘው ፡ ሀብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በመጨረሻው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ግን ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተገዛው ፡ የተገኘው ፡ ሀብት ፡ የግል ፡ ይሁንልኝ፡ ብሎ፡ አንደኛው ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛ ፡ ካላጸደቀው ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፱ ። የግል ፡ ሀብትን ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ከተጋቢዎቹ፡ አንዱ፡ የግል ፡ ንብረቱን ፡ ለማስተዳደርና ፡ ገቢውንም፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፪) የዚህንም ፡ የሀብቱን ፡ ገቢ ፡ ራሱ ፡ ሊያዝዝበት ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፮፻፷ ። (፪) የጋብቻ ፡ ውል ።**

(፩) በጋብቻው፡ ውል፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንደኛው ፡ የሀብቱ ፡ መሪና፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ ከሀብታቸው ፡ ውስጥ ፡ የተወሰነውን፡ ክፍል ፡ ያስተዳድራል ፤ እንዲያውም ፡ ይህን ፡ ሀብት ፡ ያዝዝበታል ፡ የሚል ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ ሊኖርበት ፡ ይችላል ።

(፪) በእንደዚህ፡ ያለው፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንብረቱ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ባልሆነው ፡ ወገን ፡ ጥያቄ ፡ በየዓመቱ፡ አንድ ፡ የሀብት ፡ ማስተዳደር ፡ መግለጫ ፡ እንዲቀርብ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፩ ። (፫) የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ።**

ከባልና ፡ ከሚስት ፡ አንዱ ፡ ላንደኛው ፡ የንብረቱን ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ከግል ፡ ሀብቱ ፡ ያንዱን ፡ ንብረት ፡ ጠባቂነትና ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ሥልጣን፡ ለመስጠት ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፪ ። የጋራ ፡ ሀብት ።**

(፩) የባልና ፡ ሚስት ፡ ደመወዝና ፡ ገቢዎች ፡ የጋራ ፡ ሀብቶቻቸው ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም፡ ባልና፡ ሚስቱ ፡ ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ በገንዘብ ፡ የገዟቸው፡ ሀብቶችና፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ የአንዱ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ይሁኑ ፡ ያል ተባሉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሁለቱ ፡ የጋራ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

(፫) እንዲሁም፡ በስጦታው፡ ውል ፡ ወይም ፡ በኑዛዜው ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ፡ ከሌለ፡ በቀር ፡ ለሁለቱ ፡ ተጋቢዎች ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጡት ፡ ንብረቶች ፡ የጋራ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፫ ። የሕሊና ፡ ግምት ።**

(፩) ከባልና፡ ሚስት፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር፡ ማንኛውም ፡ ሀብታቸው፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጋራ ፡ ንብረታቸው ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የግል፡ ሀብት፡ መሆኑን ፡ ሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሚያውቁት ፡ ወይም ፡ ሊያውቁት ፡ የሚገባው ፡ ካልነበረ ፡ በቀር ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በሦስተኛው ፡ ወገን፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርጉበት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፬ ። ደመወዝና ፡ ገቢ ፡ (፩) ደንበኛ ፡ አመራር ።**

(፩) ተጋቢዎቹ ፡ እያንዳንዱ ፡ ደመወዙንና ፡ ገቢውን ፡ ይቀበላል ።

(፪) ባልና፡ ሚስትም፤ ለየራሱ ፡ የሚያገኘውን ፡ ደመወዝና ፡ ገንዘብ፡ እንዲሁም ፡ ከግል ፡ ንብረቱ ፡ የሚያገኘውን ፡ ለማስቀመጥ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ የባንክ ፡ ሒሳብ ፡ ለመክፈት ፡ ይችላል ።

(፫) ከሁለቱ፡ በአንደኛው፡ ጠያቂነት፡ ከደመወዝና፡ ከንብረት ፡ ገቢ ፡ ያገኘውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፭ ። (፪)የባልና ፡ የሚስት ፡ መብት ።**

(፩) ከባልና፡ ከሚስት፡ አንዱ ፡ የሚገባውን ፡ ደመወዝ ፡ ገቢ ፤ አንደኛው ፡ እንዲቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

(፪) የዘመድ፡ የሽምግልና፡ ዳኞች፡ ከባልና፡ ከሚስቱ ፡ በአንደኛው ፡ ጠያቂነት ፡ ከሁለቱ ፡ የአንደኛውን ፡ ደመወዝ ፡ አንዱ ፡ እንዲቀበልና ፡ ለመቀበሉም፡ ደረሰኝ ፡ እንዲሰጥ ፡ በስምምነት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንዲሁም፡ የቤተ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ከባልና ፡ ሚስት፡ደመወዝ፡ ወይም ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ አንደኛው ፡ እንዲይዝና ፡ በመላው ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ተቀባይ ፡ እንዲሆን ፤ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፶፮ ። የጋራ ፡ ሀብትን ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ።</u>

(፩) ሚስትዮዋ፡ ከምታገኘው፡ ጥቅም ፡ ደመወዝና ፡ ገቢ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ፡ የተገኘውን ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሚያስተዳድረው ፡ ባልዮው ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር፡፮፻፵፭፡ የተመለከቱት፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ፡ናቸው ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሴቷ ፡ በምታቀርበው፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ጥቅም ፡ ሲሆን ፡ የጋራ ፡ ሀብታቸውን ፡ ወይም ፡ ከጋራ ፡ ሀብታቸው ፡ አንዳንዱን ፡ ሚስትዮዋ ፡ እንድታስተዳድር ፡ ሊፈቅዱ ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፶፯ ። የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።</u>

ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ በጋራ ፡ ሀብቶቹ ፡ ላይ ፡ ያስተዳደር ፡ ተግባር ፡ ሲፈጽም፡ ባለመዘግየት ፡ ለአንደኛው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፶፰ ። የሥልጣኑ ፡ መቀነስ ።</u>

የሁለቱን ፡ ተጋቢዎች ፡ ስምምነት ፡ የሚያስፈልገው ።

(ሀ) የጋራ ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ።

(ለ) ዋጋው ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ ወይም ፡ በባልዮውና ፡ በሚስቲቱ ፡ ስም ፡ የተጻፈውን ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ፡ ለመሸጥ ።

(ሐ) ከመቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ለመበደር ፤

(መ) ከመቶ፡ ብር፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ስጦታ ፡ ለማድረግ ፤ ወይም ፡ ከመቶ ፡ ብር፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፶፱ ። የባልና ፡ የሚስት ፡ ዕዳ ።</u>

(፩) ከባልና፡ ከሚስቱ፡ ከአንደኛው ፡ የሚጠየቀው ፡ ዕዳ ፡ ከግል ፡ ሀብቱ ፡ ላይ፡ ወይም ፡ ከጋራ ፡ ንብረታቸው ፡ ላይ ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) ዕዳው፡ የመጣው፡ ለጋራ ፡ ንብረታቸው ፡ ጥቅም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አንድነት ፡ ዕዳ፡ ተቈጥሮ ፡ ከባልና ፡ ከሚስቱ ፡ በአንደኛው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ላይ፡ ወይም ፡ በጋራ ፡ ሀብታቸው ፡ ላይ ፡ ሊጠየቅ ፡ የሚችል ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፮፻፷ ። ለትዳር ፡ ጥቅም ፡ እንደ፡ተደረገ ፡ ስለሚቈጠር ፡ ዕዳ ።</u>

ለትዳር፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የሚቈጠረው ፡ ዕዳ ፡—

(ሀ) የባልና ፡ ሚስትን ፡ ወይም ፡ የልጆቻቸውን ፡ ምግብና ፡ መኖሪያ ፡ ለማዘጋጀት ፡ የተደረጉ ፡ ዕዳዎች ፤

(ለ) ባልዮው ፡ ወይም፡ ሚስትዮዋ፡ ምግብ ፡ ለመስጠት ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ፡ ለመ ክፈል ፡ የደረሱ ፡ ዕዳዎች ፤

(ሐ) ከባልና፡ ከሚስቱ፡ በአንደኛው፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ አመልካች ነት ፡ ዕዳው ፡ የደረሰው ፡ ለትዳር ፡ ጥቅም ፡ መሆኑን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ፡ ሽም ግልና ፡ ዳኞች ፡ ዐውቀው ፡ የተቀበሉት ፡ ሌላ ፡ ዕዳ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡፡

ቍ ፡ ፮፻፷፩ ፡፡ ለትዳራቸው ፡ ወጪ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ስለሚያደርጉት ፡ መረዳዳት ፡፡

ባልና ፡ ሚስት ፡ የትዳራቸውን ፡ ወጪ ፡ ለማደራጀት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባላቸው፡ ችሎታና ፡ ዐቅም ፡ መጠን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መረዳዳት ፡ አለባቸው ፡፡

ምዕራፍ ፡ ፯ ፡፡

ስለጋብቻ ፡ መፍረስ ፡፡

ቍ ፡ ፮፻፷፪ ፡፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐቶች ፡ ትክክል ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ፡፡

(፩) የጋብቻው ፡ ሥርዐት ፡ የተፈጸመበት ፡ ሥርዐት ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስና ፡ ይህ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ አንድ ፡ ዐይ ነት ፡ ነው ፡፡

(፪) ጋብቻው፡ የተፈጸመው፡ በአንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ባለ ሥልጣን፡ ፊት፡ ወይም፡ በሃይማኖት ፡ ሥርዐት ፡ ወይም ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ መሠ ረት ፡ ቢሆን ፡ በጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ረገድ ፡ ማናቸውም ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ አይ ደረገም ፡፡

ክፍል ፡ ፩ ፡፡

ጋብቻ ፡ የሚፈርስበት ፡ ምክንያት ፡፡

ቍ ፡ ፮፻፷፫ ፡፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡፡

(፩) ጋብቻው ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንደኛው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡—

(፪) እንዲሁም፡ ጋብቻው፡ ሕግ ፡ አንደኛው ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ ዳኞቹ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በሰጡ ፡ ጊዜ ፤

(፫) በጋብቻው ፡ ፍቺ ፡ ሲኖር ፡ ነው ፡፡

ቍ ፡ ፮፻፷፬ ፡፡ አልፈልግም ፡ ስለ ፡ ማለት ፡፡

ሚስት ፡ ባሉዋን ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ሚስቱን ፡ አልፈልግም ፡ ማለትን ፡ ሕግ ፡ አይ ፈቅድም ፡፡

ቍ ፡ ፮፻፷፭ ፡፡ በስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ መፋታት ፡፡

(፩) በባልና ፡ በሚስት ፡ ስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ መፋታት ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ካልተፈጸመ ፡ በቀር ፡ አይፈቀድም ፡፡

(፪) በዚህ፡ ሕግ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አፈጻጸም ፡ መፋ ታትን ፡ ለመወሰን ፡ አይቻልም ፡፡

BACK

**ቍ ፡ ፮፻፷፮ ። ለመፋታት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።**

(፩) ለመፋታት ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንደኛው ፡ ወይም ፡ ሁለቱ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የመፋታቱን ፡ ጥያቄ ፡ ሊያቀርቡ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የመፋታትን ፡ ጥያቄ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

(፫) የመፋታቱ ፡ ውሳኔ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ከባልና ፡ ከሚስቱ ፡ የአንደኛው ፡ መሞት ፡ ስለ ፡ መፋታት ፡ የቀረበውን ፡ አሠራር ፡ ያስቀረዋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፷፯ ። ከባድ ፡ ምክንያቶችና ፡ ሌሎች ፡ ምክንያቶች ።**

መፋታቱ ፡ የሚወሰንባቸው ፡ ሁኔታዎችና ፡ መፋታቱም ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ፤ መፋታቱን ፡ የሚጠይቀው ፡ ተጋቢ ፡ ለእርሱ ፡ የሚጠቅመው ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ በሚችለው ፡ ወይም ፡ በማይችለው ፡ መጠን ፡ ልዩ ፡ የሚሆኑ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፮፻፷፰ ። በከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ የሚደረግ ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ።**

መፋታትን ፡ የሚጠይቀው ፡ ወገን ፡ የጋብቻውን ፡ መጽናት ፡ ሊያፈርስ ፡ የሚችል ፡ ከፍተኛ ፡ ምክንያት ፡ ካቀረበ ፤ የመፋታቱ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ጥያቄው ፡ ከቀረበላቸው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ የመፋታትን ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፮፻፷፱ ። መፋታትን ፡ ሊያስከትሉ ፡ የሚችሉ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ። (፩) ከባልና ፡ ሚስት ፡ የአንደኛው ፡ ጥፋት ።**

(፩) ከባልና ፡ ከሚስት ፡ በአንደኛው ፡ ጥፋት ፡ መፋታትን ፡ ለማስከተል ፡ የሚችሉ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የዝሙት ፡ ተግባር ፡ የፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ከባልና ፡ ከሚስት ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቤት ፡ ጠፍቶ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያለበትን ፡ ስፍራ ፡ አንደኛው ፡ ሳያውቅ ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፸ ። (፪) ከባልና ፡ ከሚስት ፡ በአንዱ ፡ ጥፋት ፡ ያልሆነ ፡ መፋታትን ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ።**

እንዲሁም ፡ መፋታትን ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ የሚያሰኘው ፡

(ሀ) ከባልና ፡ ከሚስት ፡ አንዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ አእምሮው ፡ የተናወጸና ፡ የዕብድ ፡ መጠበቂያ ፡ በሆነ ፡ ስፍራ ፡ ተዘግቶበት ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) ከባልና፡ ከሚስት፡ ያንደኛው ፡ ከአገር፡ መጥፋት ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ተገልጾ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፷፭ ። (፫) የሃይማኖት ፡ ሥርዐት ፡ ጋብቻ ፡ የሚፈርስበት ፡ ሁኔታ ።**

እንዲሁም ፡ በሃይማኖት፡ ሥርዐት ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ ፡ በሃይማኖት፡ ባለሥልጣኖች ፡ የማይጸና ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ የዚሁኑ ፡ ጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፩፻፷፮ ። መፋታትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የሚቀሩበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) መፋታትን ፡ ሊያስከትል ፡ የቻለው ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ በአንደኛው ፡ ላይ፡ የሚመካኝ ፡ ጥፋት ፡ መታሰቡ ፡ የሚቀረው ፡ አንደኛው ፡ ይቅርታ ፡ ያደረገለት፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ቢቀርብ ፡ ይቅርታ ፡ ተደርጓል ፡ ተብሎ ፡ የሚታሰበው ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው፡ በአጥፊነቱ ፡ ከተፈረደበት ፡ ወይም ፡ የአጥፊነቱን ፡ ጠባይ ፡ ከተወበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) በሃይማኖት ፡ ሥርዐት ፡ የተፈጸመ ፡ የጋብቻ፡ መሠረዝ ፡ ጕዳይ ፡ መፋታትን፡ የሚያስከትለው ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ቀርቷል ፡ የሚያሰኘው ፡ የጋብቻውን ። ሥርዐት ፡ መፍረስ፡ የሚወስነው፡ ብይን ፡ ከተሰጣቸው ፡ በኋላ፡ ባልና ፡ ሚስቱ፡ ሳይለያዩ ፡ አብረው ፡ መኖራቸውን ፡ ያላቋረጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፷፯ ። ሌሎች ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) ከባልና ፡ ከሚስት ፡ በአንደኛው፡ የተጠየቁት ፡ ሌሎቹ ፡ የመፋታት ፡ ምክንያቶች ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ የመፋታት ፡ ምክንያቶች ፡ አይቈጠሩም ።

(፪) ስለሆነም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተወሰኑት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ጊዜዎች ፡ መሠረት፡ መፋታቱ ፡ እንዲወሰን ፡ የሚያበቁ ፡ ምክንያቶች፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፩፻፷፰ ። ለጊዜው ፡ የሚሰጡ ፡ ውሳኔዎች ።**

(፩) የሽምግልና፡ ዳኞች ፡ የዚህ ፡ ዐይነት፡ ጥያቄ ፡ እንደ፡ቀረበላቸው ፡ ወዲያውኑ፡ በተለይም ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ልጆቻቸውም ፡ የሚኖሩበትን ፡ መተዳደሪያ ፡ ወይም ፡ የባልንና ፡ ወይም፡ የሚስትን ፡ ወይም፡ የጋራ ፡ ንብረትን ፡ አጠባብቅ፡ ስለሚመከተለው ፡ ጕዳይ ፡ ሊይዝ ፡ የሚገባውን ፡ ያጠባበቅ ፡ ሥርዐት ፡ እንደ፡ ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ለጊዜው ፡ የሚጸና ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣሉ ።

(፪) የባልዮውን ፡ ወይም ፡ የሚስቲቱን ፡ መኖሪያ ፡ ወይም ፡ እንዳይደርሱበት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ስፍራ ፡ ለይተው ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፮፻፸፬ ። የማሻሻል ፡ ችሎታ ።

የሽምግልና፡ ዳኞች ፡ የሰጡትን ፡ ለጊዜው ፡ የተደረገውን ፡ ውሳኔ ፡ ከባለጥቅሞቹ ፡ በአንደኛው ፡ ጥያቄ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሊለዋወጡትና ፡ እንዲያውም ፡ በፍጹም ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፮፻፸፭ ። ስለ ፡ ማስታረቅ ፡ የሚደረግ ፡ ሙከራ ።

(፩) መፋታትን ፡ የሚያስከትል ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ እንዲታረቁና ፡ የመፋታት ፡ አሳባቸውን ፡ እንዲተዉ ፡ መጣጣርና ፡ መድከም ፡ አለባቸው ።

(፪) ስለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ የሚታያቸውን ፡ ገደብ ፡ በባልና ሚስቱ ፡ ይወስኑባቸዋል ።

ቍ ፡ ፮፻፸፮ ፡ በመፋታቱ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ የመፋታት ፡ አሳባቸው ን ፡ የማይለውጡ ፡ መሆናቸውን ፡ የተረዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመፋታታቸው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ስምምነት ፡ እንደሚያደርጉ ፡ መድከም ፡ አለባቸው ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ስለ፡መፋታታቸው ፡ ባደረጉት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ውሳኔያቸውን ፡ ይሰጣሉ ።

ቍ ፡ ፮፻፸፯ ። የመፋታታቸውን፡ብይን፡ለመስጠት፡ የሚደረግ፡የጊዜ፡ውሳኔ።(፩)፡መሠረቱ።

(፩) ተጋቢዎቹ ፡ ሳይስማሙ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የመፋታቱ ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ የመፋታትን ፡ ብይን ፡ ይሰጣሉ ።

(፪) ከዚህ፡ በላይ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተውን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ፡ ጋብቻው ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ጋብቻው ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በሚያደርጉት ፡ ስምምነት ፡ እስከ ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ሊያረዝሙት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፮፻፸፰ ። በመፋታቱ ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፡ ቃል ።

(፩) የመፋታቱን ፡ ብይን ፡ የሚወስነው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ብይን ፡ የመፋታታቸውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያስከትለውንም ፡ ውጤት ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ይህም፡ ብይን፡ በተለይ ፡ የሚገልጸው ፡ ከጋብቻው ፡ የተወለዱትን ፡ ሕፃናት ፡ አጠባበቅና ፡ አስተዳደግ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሁም ፡ ስለባልና ፡ ሚስቱ፡ ሀብት፡ መከፈል ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይወስናል።

**ቍ ፡ ፮፻፹ ። ተጨማሪ ፡ ብይን ።**

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፤ የመፋታቱን ፡ ብይን ፡ ብቻ ፡ በመስጠት ፡ ይወስናሉ ፤ ቀጥሎም ፡ የመፋታቱ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ሌላ ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክርክሮች ፡ በተጨማሪነት ፡ ለመበየን ፡ በቀጠሮ ፡ አውለው ፡ ሊያሳድሩ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የዚህም ፡ ተጨማሪ ፡ ብይን ፡ መስጠት ፡ የመፋታቱ ፡ ብይን ፡ ከተወሰነበት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፩ ። የሕፃናት ፡ አጠባበቅ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ከጋብቻው ፡ ስለ ፡ ተወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ አጠባበቅና ፡ አያያዝ ፡ ጉዳይ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በተለይ ፡ ለሕፃናቶቹ ፡ ምቾትና ፡ ጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ ጉዳይ ፡ በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያሰጥ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላቸው ፡ ድረስ ፡ ልጆቹ ፡ በናቲቱ ፡ እጅ ፡ እንዲቈዩ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፪ ። (፪) ለማሻሻል ፡ የሚቻልበት ፡ ዘዴ ።**

ስለ ፡ ሕፃናቱ ፡ አጠባበቅና ፡ አስተዳደግ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በአባት ፤ በእናት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በሚቈጠር ፡ ወላጅ ፡ በሆነው ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢነት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሊያሻሽሉት ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ማጣራት ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ከባልና ፡ ከሚስት ፡ የአንዱ ፡ መሞት ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፫ ። የፈቃድ ፡ ነፃነት ።**

(፩) ከተጋቢዎቹ ፡ አንደኛው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የሀብታቸው ፡ ክፍያ ፡ ጉዳይ ፡ የሚጣራው ፡ በጋብቻቸው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ስምምነት ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ሳይደረግ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተጋቢዎቹ ፡ ሀብት ፡ ክፍያ ፡ ሥርዐት ፡ የሚፈጸመው ፡ በዚሁ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ በተደነገገው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፮ ። የግል ፡ ሀብቱን ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።**

ከተጋቢዎቹ ፡ እያንዳንዱ ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳቸው ፡ የራሱን ፡ የግል ፡ ድርሻ ፡ ሀብት ፡ በዐይነቱ ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፯ ። የጋራ ፡ ሀብቱን ፡ በየድርሻው ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።**

(፩) ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ንብረቱ ፡ የነበረው ፡ ከጋር ፡ ተሸጦ ፡ ዋጋው ፡ ወደ ፡ ጋራ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ የተደባለቀ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከጋራ ፡ ሀብቱ ፡ ውስጥ ፡ ለዚሁ ፡ የግል ፡ ገንዘቡ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆነው ፡ መጠን ፡ ቀንሶ ፡ ዋጋውን ፡ ለራሱ ፡ ድርሻ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

(፪) ሚስት ፡ የግል ፡ ሀብቷን ፡ ከባሏ ፡ አስቀድማ ፡ መውሰድ ፡ ይገባታል ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፰ ። ስለ ፡ ካሣ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ማስተካከል ፡ መተማመኛ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፤ በሠራቸው ፡ ሥራዎችና ፡ የጋራ ፡ ሀብቶችን ፡ ወይም ፡ ያንደኛውን ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ በጎዱት ፡ ሥራዎቹ ፡ ምክንያት ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ ላንደኛው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍለው ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ።

(ሀ) ሥራውን ፡ የፈጸመው ፡ ጉዳቱን ፡ ለማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ ያልነበረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የሀብቱ ፡ ጠባቂነቱ ፡ ተግባር ፡ መጥፎ ፡ ዐይነት ፡ አስተዳደር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በከሳሹ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የማጭበርበርን ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፱ ። (፪) ጥያቄን ፡ ስለ ፡ አለመቀበል ።**

ጋብቻው ፡ ከመፍረሱ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ የኪሣራ ፡ ጥያቄ ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺ ። ያለ ፡ አግባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ።**

ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ያንደኛው ፡ ወገን ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ባንደኛው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ በጋራ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ መበልጸጉን ፡ ማረጋገጥ ፡ የሚችለው ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ ይደረጋል ።

BACK



**ቍ ፡ ፮፻፹፱ ። የጋራ ፡ ሀብት ፡ ክፍያ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ፡ ባለፉት፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎችና፡በጋብቻቸው፡ ውል ፡ ወይም ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ የተፈራረሙት ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የተጋቢዎቹ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ክፍያ ፡ የሚፈጸመው ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ ነው ።

(፪) የክፍያን ፡ ሥርዐት ፤ ክፍያ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በጋራ ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነትና ፡ ክፍያ ፡ ከተደገረ ፡ በኋላ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ ጕዳይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በውርስ ፡ አንቀጽ ፡ በተነገረው፡ ድንጋጌ ፡ የባልና ፡ የሚስትን ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ በማካፈልም ፡ ጊዜ ፡ በተመሳሳ ይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## የመፋታት ፡ ሁኔታ ።

**ቍ ፡ ፮፻፺ ። ጠቅላላ ፡ ደንብ ።**

(፩) ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ በተመለከቱት፡ ቍጥሮች፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች፡ እንደ፡ ተጠበቁ፡ ሆነው ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በተፋቱ ፡ ጊዜ ፡ የገንዘባቸው ፡ ግንኙነት ፡ የሚጣራው ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ለሚደረገው ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ በተሰጠው ፡ ደንብ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፪) በነዚህም፡ ቍጥሮች፡ ውስጥ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፤ በጋብቻም፡ ውል፡ ሆነ ፤ የጋብቻቸውን ፡ ውል ፡ ከማፍረሳቸው ፡ በፊት፡ ተጋቢዎቹ፡ በሚያደርጉት፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ስምምነት ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፩ ። ስጦታዎችና ፡ የጋብቻ ፡ ጥቅሞች ።**

(፩) ስጦታ ፡ የሰጡ ፡ ወይም ፡ ወራሾቻቸው ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜና ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑም ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ተጋቢዎቹ፡ የጋብቻቸውን ፡ ሥርዐት፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጋብቻቸው ፡ በመኖሩ፡ ምክንያት ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ የሰጠውን ፡ ስጦታ ፤ ወይም ፡ ከሁለቱ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያገኙትን ፡ ስጦታ ፡ እንዲመልሱ ፡ ያዛሉ ።

(፪) በጋብቻው፡ ጊዜ፡ ወይም፡ በጋብቻው ፡ ምክንያት ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ ለአንደኛው፡ ወይም ፡ ለሁለቱ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረውን ፡ ስጦታ ፡ ወይም ፡

BACK



ተደርጎ ፡ የነበረውን ፡ የስጦታ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ባልዮው ፡ ለሚስቱ ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ለባልዋ ፡ የተሰጣጡትን ፡ ወይም ፡ ለመስጠት ፡ የገቡበትን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ መሠረዝ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የቤት ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሊያስቀሩት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። ባልና ፡ ሚስቱን ፡ ስለ ፡ አለማስተካከል ።

(፩) የቤት ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ውስጥ ፡ በርከት ፡ ያለውን ፡ ድርሻ፡ ወይም ፡ ጠቅላላውን ፡ ላንደኛው ፡ ብቻ ፡ ደልድለው ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ የቤት፡ ዘመድ፡ የሽምግልና፡ ዳኞች፡ ከተጋቢዎቹ ፡ የአንደኛውን ፡ የግል፡ ንብረት፡ ለአንደኛው ፡ ድርሻ ፡ እንዲሆን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ። ይሁን፡ እንጂ ፤ ይህ፡ ለአንደኛው፡ እንዲሰጥ ፡ የሚወሰኑት ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ከባልዮው ፡ ወይም ፡ ከሚስትዮዋ ፡ ከሚወስደው ፡ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ ሢሶ ፡ በላይ ፡ መብለጥ ፡ አይገባውም ።

ቍ ፡ ፯፻፺፫ ። የመፋታቱ ፡ አላፊነት ፡ (፩) ከባድ ፡ ምክንያት ።

(፩) መፋታቱ ፡ የተወሰነው፡ የአንደኛው፡ ወገን፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ፪ ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ በተባለው ፡ ጥፋተኛ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) አጥፊ፡ ባልሆነው ፡ በአንደኛው ፡ ተጋቢ ፡ ላይ ፡ እነዚህ ፡ ቅጣቶች ፡ ተፈጻሚ ዎች ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

(፫) መፋታቱ ፡ የተወሰነው ፡ የሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ጥፋት ፡ ባልሆነ ፡ ከባድ፡ ምክ ንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባሉት ፡ ቅጣቶች ፡ በሁለቱም ፡ ላይ ፡ አይፈጸሙ ባቸውም ።

ቍ ፡ ፯፻፺፬ ። (፪) ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ስላለመኖሩ ።

(፩) መፋታቱ ፡ የተወሰነው ፡ ከባድ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ቅጣቶች ፡ ፍቺውን ፡ በጠየ ቀው ፡ ተጋቢ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ፍቺውን፡ ባልጠየቀው፡ ተጋቢ ፡ ላይ ፡ እነዚህን ፡ ቅጣቶች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለማ ድረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፫ ። መሪ ፡ የሆኑ ፡ ሐሳቦች ።**

(፩) በመሠረቱ ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች፡ የሚወስኗቸው፡ ቅጣቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ ፡ እነዚሁኑ፡ ለመወሰን ፡ ወይም፡ ላለመወሰን፡ እንዲሁም ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑበትን ፡ መጠን ፡ ለመወሰን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(፫) ለጕዳዩ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ ለጕዳዩ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ነገር፡ በተለይም ፡ መፋታትን ፡ ያስከተለውን ፡ የተጋቢዎቹን ፡ ጥፋት ፡ ክባድነትና ፡ በሕሊናም ፡ በኩል ፡ (በሞራል) ፡ የፍቺው ፡ ጥያቄ ፡ የሚያስወቅስበትን ፡ መጠን፡ መመርመር ፡ አለባቸው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

**ሌላ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ።**

**ቍ ፡ ፮፻፺፬ ። መሪ ፡ ደንቦች ።**

(፩) የጋብቻን ፡ ሁኔታዎች ፡ ከማጓደል ፡ የተነሣ፡ የጋብቻውን፡ መፍረስ ፡ ዳኞች፡ በሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ መፍረሱ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ በርትዕ ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ፍቺ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙነት ፡ ለማጣራት ፡ በተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ዳኞቹ ፡ ይመራሉ ።

(፫) በተለይም፡ ዳኞቹ፡ የሚመለከቱት ፡ የተጋቢዎቹን ፡ በቅን ፡ ወይም ፡ በመጥፎ፡ ልቡና ፡ መሆን ፤ ሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ መፈጸሙን ፡ ወይም ፡ አለመፈጸሙን ፡ ያሉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከፈረሰው ፡ ጋብቻ ፡ የተወለዱትን ፡ ልጆች ፡ጥቅምና ፡ በቅን፡ልቡና፡ የሆኑትን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ጥቅም ፡ ነው ።

**ምዕራፍ ፡ ፯ ።**

**የጋብቻ ፡ ማስረጃ ።**

**ቍ ፡ ፮፻፺፭ ። የሕጋዊ ፡ ማስረጃ ፡ አቋቋም ፡ ሥርዐት ።**

ጋብቻ ፡ መኖሩን፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ በዚህ፡ ምዕራፍ፡ በተመለከቱት ፡ ማስረጃዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፮ ። የጋብቻ ፡ ጽሑፍ ።**

ጋብቻ፡ ለመኖሩ ፡ ማስረጃ፡ የሚሆነው፡ ጋብቻው ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ፡ ወይም፡ ጋብቻው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የተደረገውን ፡ በጽሑፍ ፡ የተቋቋመውን ፡ የጋብቻ ፡ ጽሑፍ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፭ ፡፡ የባልና ፡ የሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ (፩) ትርጓሜ ፡፡**

(፩) የጋብቻ፡ ጽሑፍ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ጋብቻ ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ የባልና ፡ ሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ በማስረዳት ፡ ነው ፡፡

(፪) ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የባልና፡ ሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ አላቸው ፡ የሚባለው ፤ ባልና ፡ ሚስት ፡ ነን ፡ እየተባባሉ ፡ አብረው ፡ የሚኖሩ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ቤተ፡ ዘመዶቻቸውና ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ መኖራቸውን ፡ ሲያረጋግጡላቸው ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፮፻፺፮ ፡፡ (፪) ማስረጃና ፡ ክርክር ፡፡**

(፩) የባልና ፡ ሚስትነት ፡ ሁኔታ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት፡ የሚቻለው ፡ የተጋቢዎቹ፡ ዘመዶች ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ያልሆኑ ፡ አራት ፡ ምስክሮችን ፡ በማስመስከር ፡ ነው ፡፡

(፪) የባልና ፡ ሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ አለመኖሩን ፡ ለመከራከር ፡ የሚቻለው ፡ የተከራካሪዎቹ ፡ ዘመዶች ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ያልሆኑ ፡ አራት ፡ የመከላከያ ፡ ምስክሮችን ፡ በማስመስከር ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፮፻፺፯ ፡፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡፡**

የጋብቻ ፡ ሁኔታ፡ መኖሩን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ቀሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ ለመኖሩ ፡ የሚያከራክር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻ ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ ዳኞች ፡ ባጸደቁት ፡ በግልጽ ፡ በታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፮፻፺፰ ፡፡ ፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡፡**

(፩) የዚህን፡ ዐይነት ፡ ጽሑፍ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ፡ ብለው ፡ ዳኞች ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ ጋብቻ ፡ መኖሩ ፡ በዚህ ፡ በግልጽ ፡ በታወቀ ፡ ጽሑፍ፡ ሊረጋገጥ ፡ አይችልም ፡፡

(፪) ይህ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲፈጸም፡ የሚቀርበውን፡ ማመልከቻ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ ሊያቀርበው ፡ ይችላል ፡፡

(፫) ከዐቅም፡ በላይ ፡ የሆነ፡ ኀይል ፡ ካላጋጠመ ፡ በቀር ፡ የተጋቢዎቹ ፡ ወይም ፡ የወራሾቻቸው ፡ ቃል ፡ መሰማት ፡ አለበት ፡፡

**ቍ ፡ ፮፻፺፱ ፡፡ ይህ ፡ አድራጎት ፡ ሊፈቀድ ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡፡**

ዳኞች ፡ በታወቀ፡ ግልጽ ፡ በሆነ፡ ጽሑፍ፡ አማካይነት ፡ የጋብቻ፡ ጉዳይ፡ ለመኖሩ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሆን ፡ የሚፈቅዱት ፡—

(ሀ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፺፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፤

(ለ) በሃይማኖት፡ ባለሥልጣኖች፡ የተሠራ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ በጠያቂው ፡ አቅራቢነት ፡ አስረጂ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) አንድ፡ የጋብቻ፡ ውል ፡ በጠያቂው ፡ አማካይነት ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(መ) ተከሳሽ፡ የሆነው፡ ወገን ፡ ጋብቻ ፡ መኖሩን ፡ ያመነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም፡ ጋብቻው ፡ አለ ፡ የሚያሰኝ ፡ ግምትና ፡ ምልክት ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፤ ይህም ፡ ግምትና ፡ ምልክት ፡ ዳኞቹ ፡ ጉዳዩን ፡ ዐውቀው ፡ እንዲቀበሉት ፡ የሚያደርጋ ቸው ፡ ግልጽና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ያጋጠመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፬ ። በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ግዴታዎች ።

(፩) የጋብቻውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በከብር ፡ መዝገብ ፡ እንዲያገባና ፡ ጋብቻው ፡ በግልጽ ፡ እንዲታወቅ ፡ አስፈላጊውን ፡ ደንብ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ጥያቄ ፡ የሚ ቀርብለት ፡ የጋብቻውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በግልጽ ፡ በታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲ ያዘጋጅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፤ ዳኞች ፡ በሰጡት ፡ ትእዛዝና ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ የማስታወቅ ፡ ሥርዐት ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ ማስታወቂያ፡ ከተሰጠበት፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር፡ ድረስ፡ ጋብቻው፡ እንዳይፈጸም፡ የሚቃወሙ፡ ሌሎች፡ ወገኖች ፡ እንዳሉ ፡ የመቃወሚያ ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲያስመዘግቡ ፡ ያስታውቃል ።

ቍ ፡ ፯፻፭ ። ውሉን ፡ የማጽናት ፡ ጉዳይና ፡ ሥርዐቱ ፡ (ፎርሙ) ።

(፩) የጋብቻ፡ ጉዳይ፡ መኖሩን ፡ ስለ፡ማረጋገጥ ፡ የሚቀርበው፡በግልጽ ፡የታወቀው፡ ጽሑፍ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ጋብቻው ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕ ረት ፤ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ ጋብቻው ፡ የቀረበበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት፡ ያመለክታል ።

(፪) ይኸውም ፡ አራት ፡ ምስክሮች፡ ካላረጋገጡለትና፡ ዳኞች ፡ ካላጸደቁት፡ ፈራሽ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፯፻፮ ። የማስረጃው ፡ ባለዋጋነት ።

(፩) የጋብቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ያጸደቁት ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ የጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ መኖሩን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሰነድ ፡ በማንኛውም ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ያለ ፡ ነው ።

(፪) የጋብቻው፡ ሥርዐት፡ አልተፈጸመም ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ጋብቻው ፡ የተፈጸ መው ፡ በነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ፡ ከተጻፈው ፡ ቀን ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ በማለትም፡ ቢሆን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ያለበት ፡ የነዚህን ፡ ሰነዶች ፡ ትክክለኛ፡ አለመሆን፡ የሚከራከረው ፡ ወገን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፯ ። የጋብቻው ፡ አለመጽናት ፡ ወይም ፡ መፍረስ ።

ጋብቻው ፡ አይጸናም ፡ ወይም ፡ ፈርሷል ፡ የሚለው ፡ ተከራካሪ ፡ ይሆን ፡ ጉዳይ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ መኖር ።

**ቍ፡ ፯፻፰ ። ትርጓሜ ።**

ከጋብቻ፡ ውጭ፡ በግብረ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በሕግ ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻ ፡ ሳያደርጉ ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ በመኖር ፡ አድርገውት ፡ የሚገኘው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፱ ። ማጠናቀቂያ ።**

(፩) ከጋብቻ፡ ውጭ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ሰውዬውና ፡ ሴትዮዋ ፡ የሚያሳዩት ፡ ሁኔታ ፡ በደንብ ፡ እንደ ፡ ተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ዐይነት ፡ መሆኑ ፡ አስፈላጊና ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፪) ለሦስተኛ፡ ወገኖች፡ እንደ ፡ ተጋቡ ፡ ሆነው ፡ መቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

(፫) በታወቀ፡ በተደጋገመ፡ አኳኋን፡ ቢሆንም፡ እንኳ፡ ከአንድ፡ ሰውና ፡ ከአንዲት ፡ ሴት ፡ መካከል ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ብቻ ፡ በሁለቱ ፡ መካከል፡ ከጋብቻ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ይኖራሉ ፡ ለማለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፯፻፲ ። የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ ስላለማስከተሉ ።**

(፩) ከጋብቻ፡ ውጭ ፡ በግብረ፡ ሥጋ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በወንድዬውና ፡ በሴቲቱ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ እንዲሁም ፡ በሴቲቱና ፡ በወንድየው ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ አንዳችም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ግንኙነትን ፡ አያስከትልም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ጋብቻን ፡ የሚከለክሉ ፡ ድንጋጌዎች፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ባለም ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚዎች፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፩ ። የጡረታ ፡ ግዴታን ፡ ስላለማስከተሉ ።**

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በሚኖሩት ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ መካከል ፡ አንዳችም ፡ የጡረታ ፡ ግዴታ ፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፪ ። የጋራ ፡ ሀብት ፡ እንዲኖር ፡ ስላለመደረጉ ።**

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በሚኖሩት ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ መካከል ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ እንዳላቸው ፡ አያስቈጥራቸውም።

**ቍ ፡ ፯፻፲፫ ። የመውረስን ፡ መብት ፡ ስለአለማስከተሉ ።**

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ በሚኖሩት፡ ሴትና፡ ወንድ፡ መካከል፡ ማንኛውንም፡ የመውረስ፡ መብትን፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፩ ። ሴትዮዋ ፡ ለምትገባባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ወንድዮው ፡ ዋስ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ሁኔታ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ለእርሱ ፡ ወይም ፡ ለርሱዋ ፡ ወይም ፡ ከግንኙነቱ ፡ ለተወለዱት ፡ ልጆች ፡ መኖሪያ ፡ ስትል ፡ ሴቲቱ ፡ ለፈረመቻቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑት ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ባለአንድነት ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፪ ። የልጆች ፡ መወለድ ።**

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ መወለዳቸው ፡ የሚረጋገጠው ፡ ስለ ፡ መወለድ ፡ በተባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፫ ። የግንኙነቱ ፡ ማለቅ ፤ (፩) እንዲያልቅ ፡ የምታደርገው ፡ ሴትዮዋ ፡ ስትሆን ።**

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የምትኖር ፡ ሴት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ግንኙነትን ፡ እንዲያልቅ ፡ ለማድረግ ፡ ትችላለች ።

(፪) እንዲህም ፡ በማድረጓ ፡ አንዳችም ፡ ኪሣራ ፡ እንድትከፍል ፡ ወይም ፡ የተሰጣትን ፡ እንድትመልስ ፡ አትገደድም ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፬ ። (፪) እንዲያልቅ ፡ የሚያደርገው ፡ ወንድዮው ፡ ሲሆን ።**

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ግንኙነቱን ፡ እንዲያልቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ርትዕ ፡ ሲያስገድድ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ለሴትዮዋ ፡ ኑሮ ፡ የሚበቃ ፡ ኪሣራ ፡ ዳኞች ፡ እንዲከፍላት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፭ ። የግንኙነት ፡ ማስረጃ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩን ፡ የግንኙነቱ ፡ ሁኔታ ፡ በመኖሩ ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላል ።

(፪) አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የመኖር ፡ ሁኔታ ፡ አላቸው ፡ የሚባለው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በደንብ ፡ የተጋቡ ፡ ባይሆን ፤ የተጋቡ ፡ ሰዎችን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያሳዩና ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቻቸውና ፡ ጎረቤቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ሲገምቷቸው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፲፮ ። (፪) ማስረጃና ፡ መከራከሪያ ።**

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ በቂ ፡ ምስክሮችን ፡ በማስመስከር ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ግንኙነት ፡ ያለመኖሩን ፡ በመቃወም ፡ ለመከራከር ፡ የሚቻለው ፡ የባለጕዳዮቹ ፡ ዘመዶች ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ያልሆኑ ፡ በቂ ፡ ምስክሮችን ፡ በማስመስከር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፹ ። (፫) በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ጽሑፍ ።**

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩ ፡ የተካደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ ዳኞች ፡ ያጸደቁትን ፡ በግልጽ ፡ የታወቀውን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ጋብቻ ፡ መኖር ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነድ ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፸፪ ፡ እስከ ፡ ፯፻፸፯ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ ደንብ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩንም ፡ ስለ ፡ ማስረዳት ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ግንኙነቶች ።**

(፩) ከጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በአንድ ፡ ወንድና ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡ መካከል ፡ የተደረጉ ፡ ሌሎች ፡ ግንኙነቶች ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ የላቸውም ።

(፪) ባለጉዳዩ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ መከራከሪያ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ አይችልም ።

(፫) ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ግንኙነት ፡ የተወለዱትም ፡ ልጆች ፡ ከእናታቸው ፡ ጋራ ፡ በቀር ፡ ከሌላ ፡ ጋራ ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ የላቸውም ። ስለ ፡ ሆነም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የጉድፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ልጂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመቀበል ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## በጋብቻና ፡ በፍቺ ፡ ከጋብቻው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚነሡ ፡ ክርክሮች ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። የሚጸና ፡ መተጫጨት ፡ ስለ ፡ መኖሩ ።**

የመተጫጨት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ተፈጽሟል ፡ ወይም ፡ አልተፈጸመም ፡ ለማለትና ፡ ይህ ፡ መተጫጨት ፡ ይጸናል ፡ ወይም ፡ አይጸናም ፡ ብሎ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። በመተጫጨት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ክርክሮች ።**

(፩) በመተጫጨት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በመተጫጨት ፡ ውል ፡ መፍረስ ፡ ላይ ፡ የሚነሡትን ፡ ክርክሮች ፡ መርምረው ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጡ ፡ በዚሁ ፡ በመተጫጨቱ ፡ ሥርዐት ፡ ምስክሮች ፡ የነበሩት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

(፪) እንደ ፡ መጀመሪያ፡ ምስክሮች፡ ሆነው ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ፡ክርክሩ፡ እንዲመረመር ፡ የሚቀርበው ፡ ለነዚሁ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ነው ።

(፫) ባለጉዳዮቹ፡ የመተጫጨታቸው፡ ሥርዐት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ክርክራቸውን ፡ ሌሎች ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዲመረምሩ፡ ለመምረጥ፡ (ለመስማማት) ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፳፩ ። የሚጸና ፡ ጋብቻ ፡ ስለ ፡ መኖሩ ።

የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ውል ፡ የተፈጸመ ፡ ለመሆኑና ፡ ይህም ፡ ጋብቻ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፯፻፳፪ ። ከጋብቻ ፡ ጕዳይ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ችግሮች ።

(፩) በጋብቻው፡ ጊዜ፡ በባልና ፡ ሚስት ፡ መካከል ፡ የሚነሡትን ፡ ችግሮች ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ መርምረው ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጡት ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ።

(፪) እንደ ፡ መጀመሪያ፡ ምስክሮች፡ ሆነው ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ ፡ እንዲመረመር ፡ ክርክሩ ፡ የሚቀርበው ፡ ለነዚሁ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ነው ።

(፫) ባለጉዳዮቹ፡ የጋብቻው፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በመካከላቸው ፡ የተነሣውን ፡ ችግር ፡ ሌሎች ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዲመረምሩ ፡ ለመስማማት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፳፫ ። በሞት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈርስ፡ ጋብቻ ።

የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ ያስከተለው ፡ ምክንያት ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ የአንደኛው ፡ መሞት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ የሚያመጣው ፡ ክርክር ፡ እንዲወሰን ፡ የሚቀርበው ፡ ለነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፳፬ ። የመፋታት ፡ ጥያቄ ።

ከባልና ፡ ከሚስት ፡ ወይም ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የሚያቀርበው ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ እንዲወሰን ፡ የሚቀርበው ፡ ለነዚሁ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፳፭ ። በመፋታት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠሩ፡ክርክሮች ።

(፩) ከመፋታት፡ ጕዳይ፡ ውስጥ ፡ የሚነሣው ፡ ክርክር ፡ ለምርመራ ፡ የሚቀርበው፡ የመፋታቱን ፡ ውሳኔ ፡ ለሰጡት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ነው ።

(፪) ባለጉዳዮቹ፡ በሚፋቱበት፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከተፋቱ ፡ በኋላ ፡ ክርክራቸውን ፡ ለሚመረምሩ ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንዲቀርብ ፡ ለመስማማት ፡ ይችላሉ ።

BACK



ቍ ፡ ፯፻፳፱ ። የመፋታት ፡ ጒዳይ ፡ ስለ ፡ መኖሩ ።

የመፋታት፡ ውሳኔ፡ የተሰጠ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፯፻፴ ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ መኖሩ ።

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም፡ በዚህ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ በሚነሡት፡ ክርክሮች ፡ ላይ፡ውሳኔ፡ ለመስጠት ፡ የሚችሉት ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፯፻፴፩ ። ሽማግሌ ፡ ባልተመረጠበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሆን ፡ አሠራር ።

ክዚህ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች፡ በተነገሩት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ለሽምግልና ፡ መቅረብ ፡ ያለበትን ፡ ክርክር ፡ የሚቈርጥ ፡ ምንም ፡ ሽማግሌ ፡ ሳይመረጥ ፡ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተጋቢዎቹ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ይመርጣሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፴፪ ። ተጨማሪ ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ስለ ፡ መምረጥ ።

ማናቸውም፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን፡ የውል፡ ቃል፡ ቢኖርም ፡ እንኳ፡ የቤተ፡ዘመድ፡ ሽማግሎች ፡ ሽምግልናቸውን ፡ የተሟላ ፡ ለማድረግ ፡ በመካከላቸው ፡ በሚሰጥ ፡ የድምፅ ፡ ብዛት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ተጨማሪ ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ስለ ፡ መምረጥ ፡ ለመስማማት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፴፫ ። ሽማግሌን ፡ ስለ ፡ መተካት ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) ውሳኔ ፡ እንዲሰጥ ፡ የተመረጠው ፡ ሽማግሌ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ወይም ፡ የተነሣውን ፡ክርክር ፡ ያለ፡መዘግየት ፡ ለመቍረጥ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእርሱ ፡ ምትክ ፡ እርሱ፡ በተመረጠበት ዐይነት ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ ሊተካ ፡ ይቻላል ።

(፪) ይኸው ፡ የተመረጠው ፡ ሰው ፡ የሽምግልናውን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ዳኞቹ ፡ ያስወገዱት ፡ እንደ ፡ ሆነ ዳኞቹ ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ ይመርጣሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፴፬ ። (፪) ሽማግሌን ፡ በመምረጥ ፡ ስላለመስማማት ።

ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በመስማማት ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ መምረጥ ፡ ያለባቸው ፡ ሲሆንና ፡ በተባለው ፡ ምርጫ ፡ ያልተስማሙ ፡ ሲሆን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በሚቀርቡት ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞቹ ፡ ሽማግሌውን ፡ ይመርጣሉ ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፭ ። (፫) አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሽማግሌን ፡ ስላለመምረጡ ።**

ሽማግሌ ፡ መምረጥ ፡ ያለበት ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ እንዲመርጥ ፡ ከታዘዘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በዐሥራ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሽማግሌውን፡ ሳይመርጥ ፡ የቀረ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይፈቅደውን ፡ ሽማግሌ ፡ የመረጠ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ ባለመዘግየት ፡ ለመፈጸም፡ የማይችለውን ፡ ሽማግሌ ፡ የመረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሌላው ፡ ወገን ፡ በሚያቀርበው፡ ጥያቄ ፡ ሽማግሌ ፡ እንዲመርጥ ፡ ስለታዘዘው ፡ ወገን ፡ ዳኞቹ ፡ ሽማግሌውን ፡ ይመርጡለታል ።

**ቍ፡ ፯፻፴፮ ። ሽማግሌዎች፡ በቈረጡት፡ ነገር፡ ላይ፡ ለፍርድ፡ቤት፡ስለሚቀርበው፡ አቤቱታ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሰጡቸው ፡ ውሳኔዎች፡ ሽማግሌዎቹ፡ በጉቦ፡ መሥራታቸውን፡ ወይም፡ በሦስተኛ ፡ ሰዎች ፡ ላይ፡ ተንኰል ፡ በመሥራት ፡ የተደረጉ ፡ ወይም ፡ ለሕግ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ወይም፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ በግልጽ ፡ ከአእምሮ ፡ ሚዛን፡ ውጭ ፡ መሆናቸውን ፡ በማስረዳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዳኞች፡ፊት፡ክስ ፡ ሊቀርብባቸው ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፯ ። ሽማግሌ ፡ ነገሩን ፡ ሳይቈርጥ ፡ ስለ ፡ መቅረቱ ።**

እንዲሁም ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ፡ ሳይሰጡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞቹ ፡ ነገሩን ፡ ሊመረምሩ ፡ ይችላሉ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

## ስለ ፡ መወለድ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### አባትንና ፡ እናትን ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።

#### ንኡስ ፡ ክፍል ። ፩

#### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፰ ። በሕግ ፡ የተወሰኑት ፡ ደንቦች ፡ የማይጣሱ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ስምምነቶችን ፡ ካልፈቀዳቸው ፡ በቀር ፡ አባትንና ፡ እናትን ፡ ስለ ማወቅ ፡ የተሰጡት ፡ ደንቦች ፡ በስምምነት ፡ ሊለወጡ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፱ ። እናትነትን ፡ ስለ ፡ ማስረዳት ።**

በመወለድ ፡ ብቻ ፡ እናትነትን ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፵ ። አባትነትን ፡ ስለ ፡ ማስረዳት ።**

(፩) ልጁ ፡ በተፀነሰበት ፡ ወይም ፡ በተወለደበት ፡ ጊዜ ፡ በእናትና ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መቀበል ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ ግንኙነት ፡ የኖረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በመወሰዱ ፡ አባትነትን ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ አባት ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አባትነት ፡ ይገለጻል ።

(፫) በመጨረሻም ፡ እናት ፡ በመጠለፍ ፡ ወይም ፡ በመደፈር ፡ ተገድዳ ፡ ስትገኝ ፡ ዳኛ ፡ ልጅህ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ አባትነት ፡ ይገለጻል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

**አባት ፡ ነው ፡ ስለሚያሰኝ ፡ ግምት ።**

**ቍ ፡ ፯፻፵፩ ። ባልየው ፡ ወላጅ ፡ አባት ፡ ነው ፡ ስለሚያሰኝ ፡ ግምት ።**

በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ የተፀነሰው ፡ ወይም ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ያው ፡ የእናቱ ፡ ባል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፵፪ ። የዚህ ፡ ግምት ፡ ጠቅላላነት ።**

(፩) ከእናት ፡ የሚገኘው ፡ የልጁ ፡ ተወላጅነት ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የተረጋገጠ ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ቍጥር ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የልጁ ፡ የመወለዱ ፡ የምስክር ፡ ጽሑፍ ፡ የእናቱ ፡ ባል ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ መሆኑን ፡ ባያመለክት ፡ እንኳ ፡ ወይም ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ መሆኑን ፡ ቢያመለክትም ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ የመወለዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ተቃንቶ ፡ በባልየው ፡ ስም ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፯፻፵፫ ። እርግዝናው ፡ ስለሚቈይበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) ልጁ ፡ የጋብቻው ፡ ሥርዐት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከ፻፹ ፡ ቀን ፡ በላይና ፡ ከመፋታቱም ፡ በኋላ ፡ ፫፻ ፡ ቀን ፡ ሳይሞላ ፡ የተወለደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ ተጋብተው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተፀነሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

(፪) ለዚሁ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ አይፈቀድም ።

**ቍ ፡ ፯፻፵፬ ። የባል ፡ በአገር ፡ አለመኖር ።**

የልጁ ፡ መወለድ ፡ ባልየው ፡ በአገር ፡ የለም ፡ ተብሎ ፡ በፍርድ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ ባል ፡ አባቱ ፡ አይደለም ።

BACK



ቍ ፡ ፯፻፵፫ ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የሚኖር ፡ ወንድ ፡ አባትነትን ፡ ስለመገመት ።

(፩) ከጋብቻ፡ ውጭ፡ በሆነ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ጊዜ ፡ የተፀነሰው፡ወይም ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ እናቲቱን ፡ ይዞ ፡ የተቀመጠው ፡ ነው ።

(፪) የሕሊና፡ ግምትን፡ ጠቅላላ፡ ጕዳይና ፡ በርግዝና፡ የመቈየትን ፡ የሕሊና ፡ ግምት፡ የሚመለከቱት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ ለዚሁ፡ ግምት ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

አባትነትን ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።

ቍ ፡ ፯፻፵፬ ። መሠረቱ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉትን ፡ ቍጥሮች ፡ ተፈጻሚ ፡ በማድረግ ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ እገሌ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ያልታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአባት ፡ የሚገኘው ፡ የልጁ ፡ መወለድ ፤ አባት ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ሲል፡ ከማወቁ ፡ የተነሣ ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ መሆኑ፡ ሊረጋገጥ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፯፻፵፭ ። የማወቂ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚጻፍበት ።

(፩) አባትነትን፡ ማወቅ፡ የተፀነሰው ፡ ወይም ፡ የተወለደው ፡ ለልጁ ፡ አባት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሚሰጠው ፡ ቃል ፡ ይታወቃል ።

(፪) ይህ ፡ የሚሰጠው ፡ ቃል ፡ አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ እንዲኖረው ፡ ሲል ፡ የተናገረ ፡ መሆኑ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፯፻፵፮ ። የማወቂ ፡ አሠራር ፡ ፎርምና ፡ ማስረጃ ።

(፩) አባትነትን፡ ማወቅ፡ በጽሑፍ፡ ካልሆነ፡ ምንም፡ ውጤት፡ የለውም፡ (አይጸናም)።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በ፯፻፵፯ ፡ ቍጥር ፡ ከተደነገጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ አባትነትን፡ ለማወቂ ፡ በምስክር ፡ ለማረጋገጥ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፯፻፵፱ ። በውክልና ፡ ስለሚነገረው ፡ ቃል ።

(፩) የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የሚሰጠውን፡ ቃል ፡ የሚገልጸው ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰም ፡ ቢሆን ፡ ራሱ ፡የልጁ ፡ አባት፡ነው ።

(፪) አባትነትን፡ ለማስታወቅ፡ የሚደረገው ፡ ወኪልነት ፤ በጽሑፉ ፡ ሆኖ ፡ ዳኞቹ፡ ባጸደቁት ፡ ልዩ ፡ ውክልና ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ።

(፫) የመግለጫውንም ፡ ቃል ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለው ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ስም ፡ አሳዳሪው ፡ በዳኞች ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፶ ። ስለ ፡ አባት ፡ መሞት ።

(፩) የልጁ ፡ አባት ፡ የሞተ፡ ወይም ፡ ፈቃዱን፡ (ሐሳቡን) ፡ ለመግለጽ ፡ በማይችል በት ፡ ሁኔታ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአባትነቱን ፡ ማስታወቅ ፤ በእርሱ ፡ ስም ፡

ሆኖ ፡ በአባት ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ወንድ ፡ አያት ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ አያት ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚህ ፡ ሲታጡ ፡ በአባት ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ሊፈጽሙ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፩ ። ስለ ፡ እናቱ ፡ ማመን ።**

(፩) የአባት ፡ ልጁን ፡ መቀበል ፡ ውጤት ፡ የሚያገኘው ፡ የልጁ ፡ እናት ፡ ያረጋገጠችለት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) የልጁ ፡ እናት ፡ የሞተች ፡ ወይም ፡ አሳቧን ፡ ለመግለጽ ፡ በማትችልበት ፡ ሁኔታ ፡ የተገኘች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አባት ፡ የሚያደርገውን ፡ የልጅነቱን ፡ መቀበል ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ወንድ ፡ አያት ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ አያት ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) በእናት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ አያቶች ፡ ሲታጡ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ለተከለከለው ፡ አሳዳሪ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፪ ። ስለ ፡ ልጁ ፡ አካለመጠን ፡ ማድረስ ።**

የአባት ፡ ልጁን ፡ መቀበል ፡ የተደረገው ፤ ልጁ ፡ አካለመጠን ፡ ካደረሰ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልጁን ፡ መቀበሉ ፡ ውጤት ፡ የሚያገኘው ፡ ልጁ ፡ ራሱ ፡ አባትነቱን ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፫ ። የመቀበሉ ፡ ፎርም ።**

የአባትነትን ፡ ማወቅ ፡ የሚቀበለው ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ፩ ፡ ወር ፡ ክርክር ፡ ካላነሣ ፡ የአባትነትን ፡ ማወቅ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፬ ። ስለ ፡ ልጁ ፡ መሞት ።**

ልጅዮው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ተከቶ ፡ ካልሞተ ፡ በቀር ፡ በአባት ፡ በኩል ፡ የሚነገረው ፡ የልጁ ፡ መታወቅ ፡ ከልጁ ፡ መሞት ፡ በኋላ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፭ ። ቃልን ፡ ስመለወጥ ፡ (ስለማፍረስ) ።**

(፩) ልጄ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አባት ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ።

(፪) ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተቀበለ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ቃሉን ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰበት ፡ ዘመን ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ አካለመጠንን ፡ ካደረሰ ፡ በኋላ ፡ አካለመጠን ፡ ባደረሰበት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ማድረግ ፡ የሚችለው ፤ ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ የተቀበለው ፡ አሳዳሪው ፡ ፈቅዶለት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተቀበለበትን ፡ ቃሉን ፡ የሚሽረው ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፮ ። ስለ ፡ መሠረዝ ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ በተሰጡት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊፈርስ ፡ ይቻላል ።

(፪) በዚሁ ፡ አንቀጽ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ልጁ ፡ ልጁ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከተቀበለው፡ ሰው ፡ አልተፀነሰም ፡ ተብሎ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት፡ለማስረዳት፡ካልተቻለ ፡ በቀር ፡ ልጁ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ በስሕተት ፡ ወይም ፡ በማታለል ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፯ ።** **ለአንድ ፡ ልጅ ፡ የብዙ ፡ ሰውን ፡ አባትነት ፡ ማወቅ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

ስለ ፡ ልጁ ፡ ጥቅም ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ አንድ፡ሰው፡አባትነቱን፡ካወቀለትና ፡ ይህንንም ፡ ማወቅ ፡ በሚገባ ፡ ከተቀበሉት ፡ በኋላ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተሰጠው ፡ የማወቅ፡ቃል ፡ ፈርሶ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የሚያ ደርገውን ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ሊቀበሉት ፡ አይቻልም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

## በፍርድ ፡ ስለሚደረግ ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፰ ።** **ስለ ፡ መጥለፍና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መድፈር ፡ ሥራ ።**

ከዚህ ፡ በላይ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመፈጸም ፡ ልጁ ፡ አባት ፡ የሌ ለው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ልጅነቱ ፡ የተካደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የልጁ ፡ እናት ፡ ልጁ ፡ በተፀነሰበት ፡ ወራት ፡ የመጠለፍ ፡ ወይም ፡ የመደፈር ፡ ሥራ ፡ ደርሶባት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአባትነት ፡ መታወቅ ፤ በፍርድ ፡ ሊነገር ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፶፱ ።** **በፍርድ ፡ ለመጠየቅ ፡ ስለሚያስፈልጉ ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) አባትነቱ ፡ በፍርድ ፡ እንዲገለጽ ፡ የሚደረገው ፡ ክስ፡ በልጁ ፡ እናት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ እናቱ ፡ የሞተች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አሳቧን ፡ ለመግለጽ ፡ በማትችል በት ፡ ሁኔታ ፡ የተገኘች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በልጁ ፡ አሳዳሪ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ልጁ፡ ከተወለደ፡ ወይም ፡ መጠለፉን ፡ ወይም ፡ መደፈሩን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀል ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ክስ ፡ ለማ ቅረብ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፷ ።** **ስለ፡ክሱ ፡ መከናወን ።**

በፍርድ ፡ (በዳኝነት) ፡ የሚደረገው ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፡ እናቲቱን ፡ ከጠለፈው፡ ወይም ፡ በኀይል፡ ከተገናኘው፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ልጁ ፡ ያልተፀነሰ ፡ ለመሆኑ፡ማፍረሻ ፡ በማይገኝለት ፡ አኳኋን ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፤ ለመጠለፉ ፡ ወይም ፡ ለመደ ፈሩ ፡ አቋም ፡ የሆኑት ነገሮች ፡ እንደ ፡ ተረጋገጡ ፡ ወዲያውኑ ፡ በፍርድ ፡ የሚነ ገረው ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፡ ወዲያውኑ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፩ ።** **የሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ስላለመኖር ።**

በፍርድ ፡ ስለሚደረገው ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፡ በመጠለፍ ፡ ወይም ፡ በመደፈር፡ ካልሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ሊጠየቅ ፡ ወይም ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

## በአባትነት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚነሣው ፡ ክርክር ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፪ ። አባትነትን ፡ ስለ ፡ መወሰን ። (፩) መሠረቱ ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ቍጥሮች ፡ ተፈጻሚ ፡ በማድረግ ፡ አንድ ፡ ልጅ፡ ብዙ ፡ አባቶች ፡ አሉት ፡ የተባለ ፡ ሲሆን ፤ ለልጁ ፡ አባትነት ፡ በሕግ ፡ በሚሰ ሰጣቸው ፡ አባቶች ፡ መካከል ፡ በሚደረግ ፡ ውል ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፫ ። (፪) ሥርዐት፡ (ፎርም) ።**

(፩) የአባትነትን፡ ውሳኔ፡ የሚያሰጠውን ፡ ውል፤ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ሊያረጋግጡትና ፡ ዳኞች ፡ ሊያጸድቁት ፡ ይገባል ።

(፪) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ካልገጠመ ፡ በቀር ፡ የልጁን ፡ እናት ፡ ቃል፡ መስማት ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፬ ። ስለ ፡ ሕጋዊ ፡ ግምት ።**

ስለ ፡ አባትነት ፡ በሚደረገው ፡ ክርክር ፡ ስምምነት ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉትን ፡ ሁለት ፡ ግምቶች ፡ በመከተል ፡ ይፈጸማሉ ።

(ሀ) ከጋብቻ፡ ውጭ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከያዛት ፡ ሰው ፡ ይልቅ፡ ባልዋ፡ ይመረጣል ።

(ለ) እናቲቱ ፡ ልጁን፡ በወለደችበት፡ ጊዜ ፡ ላላት ፡ ባል ፡ ልጁ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ይልቅ፡ ልጁ፡ በተፀነሰበት፡ ጊዜ፡ ለነበራት፡ ባል፡ ልጁ፡ ነው፡ ማለት፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፭ ። ያባትነትን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ (፩) የተፈቀዱ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ልጁ ፡ የተወለደው ፡ ጋብቻው ፡ ከፈረሰ ፡ ወይም ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ከ፪፻፲ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ቈይቶ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባልዮው፡ወይም፡ ከሴትዮዋ ፡ ጋራ ፡ የግብረ ፡ ሥራ ፡ ግንኙነት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ እኔ፡ ነኝ፡ ለሚለው፡ ለሌላው፡ ሰው፡ በውል፡ ልጅነቱን፡ ሊያውቅለት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ልጁ ፡ ከጋብቻው ፡ መፈረስ ፡ ወይም ፡ የግብረ ፡ ሥጋው ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ ከቀረበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ቀኖችን ፡ አሳልፎ ፡ ተወልዶ ፡ እንደሆነ ፡ ለባልዮው ፡ ወይም ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፮ ። (፪) ሥርዐት ። (ፎርም) ።**

(፩) በውል ፡ የሚደረግ ፡ የአባትነት ፡ ማስተላለፍ ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ያረጋገጡትና ፡ ዳኞች ፡ ያጸደቁት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል፡ ካልተከለከለች፡ በቀር ፤ የልጁ ፡ እናት ፡ ቃሏ ፡ መሰማት ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፯፻፷፯ ። ስለ ፡ እንደራሴነት ።**

(፩) በዚህ ፡ ክፍል፡ የተመለከቱትን፡ ውሎች ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሱና፡ በፍርድ፡ ያልተከለከሉ ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ ራሳቸው ፡ መጨረስ ፡ አለባቸው ።

(፪) ውሎቹን ፡ ሕጋዊው ፡ እንደራሴ፡ (ወኪል)፡ በባለጕዳዮቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ሊጨ ርሳቸው ፡ አይችልም ።

(፫) ውሎቹን ፡ የመጨረስ ፡ ወኪልነት ፤ በጽሑፍ ፡ ተደርጎ ፤ ይህንኑም ፡ ዳኞቹ ፡ አጽድቀውት ፡ በልዩ ፡ ውክልና ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፰ ። ቃልን ፡ ስለ ፡ ማፍረስና ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) በዚህ ፡ ክፍል ፡ የተመለከቱት ፡ ውሎች ፡ ሊፈርሱ ፡ አይችሉም ።

(፪) በዚህ፡ ሕግ፡ «ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ » በሚል ፡ አንቀጽ ፡ የተሰጡትን፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በኀይል ፡ በሚደረግ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ሊፈ ርሱ ፡ ይችላሉ ።

(፫) በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ደንቦች፡ መሠረት፡ ልጁ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከተቀበለው፡ ሰው ፡ አልተፀነሰም ፡ ብሎ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ለማስረዳት ፡ ካልተቻለ ፡ በቀር ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ በስሕተት ፡ ወይም ፡ በማታለል ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ልጅነት ፡ ማስረጃ ።

**ቍ ፡ ፯፻፷፱ ። የመወለድ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ።**

በአባትነት ፡ ወይም ፡ በእናትነት ፡ በኩል ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ልጅነት ፡ የእገሌ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ በመወለድ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይረጋገጣል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸ ። የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ። (፩) ትርጓሜ ።**

(፩) የመወለድ፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ በመ ኖሩ ፡ ልጅነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ይሆናል ።

(፪) አንድ፡ ሰው፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ አለው ፡ የሚባለው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የዚያ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዚያች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ የሚገምቱት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፩ ። (፪) ስለ ፡ ማስረጃና ፡ ስለ ፡ ክርክር ።**

(፩) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ የባለጕዳዩ ፡ ዘመዶች ፡ ቢሆኑም ፡ ባይሆኑም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱ ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

(፪) የባለጕዳዮቹ፡ ዘመዶች፡ ቢሆኑም፡ ባይሆኑም ፡ አራት ፡ ምስክሮችን ፡ በማቅረብ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ ክርክር ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል።

**ቍ ፡ ፯፻፸፪ ። የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ በመጠየቅ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።**

የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ የተነሣበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ በመወለድ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የልጅነቱን ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ለመጠየቅ ፡ በሚቀርበው ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በባለሥልጣን ፡ በተሰጠና ፡ ዳኞች ፡ ባጸደቁት ፡ ጽሑፍ ፡ ልጅነቱ ፡ ይወሰናል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፫ ። ክሱን ፡ ስለ ፡ መቀበል ።**

(፩) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ዳኞች ፡ ካልፈቀዱት ፡ በቀር ፡ ሊቀርብ ፡ አይቻልም ።

(፪) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ፡ ክስን ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ ዳኞቹ ፡ ክሱን ፡ እንዲቀበሉ ፡ ከሚያደርጉ ፡ በቂ ፡ ከሆኑ ፡ ከባድነት ፡ ካላቸው ፡ ተግባሮች ፡ የሚመነጩ ፡ ግምቶች ፡ ወይም ፡ ምልክቶች ፡ ሲኖሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፬ ። ክስን ፡ ስላለመቀበል ።**

ልጅነቱን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መወለዱ ፡ ከተሰጠው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ሌላ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስን ፡ ለማቅረብ ፡ አይፈቀድለትም ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፭ ። ስለ ፡ ከሳሽ ።**

(፩) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችሉት ፡ ልጁ ፡ ወይም ፡ አዳሳጊው ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የልጅ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ሰዎች ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ክሱ ፡ የተከናወነ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አባት ፡ መሆን ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለው ፡ ሰው ፡ አባትነቱን ፡ ለመካድ ፡ ሲል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፮ ። ክስ ፡ ስለሚቀርበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) ልጅ ፡ በሕይወት ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) የልጁ ፡ አሳዳሪና ፡ በላይኛው ፡ ቍጥር ፡ በ፪ኛውና ፡ በ፫ኛው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ ልጁ ፡ አካለመጠን ፡ ባላደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችሉም ።

(፫) ልጁ ፡ ሐያ ፡ ዓመት፡ ሳይሞላው፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወራሾቹ ፡ ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፯፻፸፯ ። ስለ ፡ ተከሳሽ ።

(፩) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስ ፡ ያቀረበችው ፡ እናት ፡ ነኝ ፡ የምትለዋ ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክሱን ፡ ያቀረበችው ፡ እናት ፡ ባል ሆነች ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ እናት ፡ ነች ፡ በተባለችዋ ፡ ወይም ፡ በወራሾቿ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፫) የልጅነት፡ ሁኔታ፡ መኖሩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስ ፡ የቀረበው፡በማናቸውም፡ሲሆን፡ ክሱ ፡ የተከናወነ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፤ የልጁ ፡ እናት ፡ ነች ፡ የተባለችውና ፡ ልጁ ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ስለሚነሣው ፡ ክርክርና ፡ ስለ ፡ መካድ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ክርክር ።

ቍ ፡ ፯፻፸፰ ። መሠረቱ ።

በእናት ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ መወለድ ፡ (ልጅነት) ፡ በማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፤ በምን ፡ ጊዜም ፡ ሁሉ ፡ ክርክር ፡ ሊደረግበት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፯፻፸፱ ። ክስን ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ ክርክር ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ዳኞች ፡ ካል ፈቀዱ ፡ በቀር ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

(፪) በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ክርክር፡ ለማድረግ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ ዳኞቹ ፡ ክሱን ፡ እንዲቀበሉ ፡ ከሚያደርጉ ፡ እርግጠኛ ፡ ከሆኑና ፡ በቂ ፡ ከባድነት ፡ ካላቸው ፡ ተግባሮች ፡ የሚመነጩ ፡ ግምቶች ፡ ወይም ፡ ምልክቶች ፡ ሲኖሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፹ ። ክስን ፡ ስላለመቀበል ።

ከሳሹ ፡ እከራከርበታለሁ፡ የሚለው፡ ልጅነት፡ ለባለጉዳዩ ፡ ካለው ፡ የመወለድ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የመነጨና ፡ ከዚህ ፡ ከመወለድ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጋራ ፡

የሚስማማ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሁኔታው ፡ ለመከራከር ፡ ሲል ፡ ከሳሹ ፡ የሚጠይቀው ፡ ፈቃድ ፡ አይሰጥም ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። ስለ ፡ ተከሳሽ ።**

(፩) በሁኔታው፡ ላይ ፡ የሚቀርበው፡ ክስ ፤ በልጅነቱ ፡ (በመወለዱ) ፡ ላይ ፡ ክርክር፡ በተነሣበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በወራሾቹ ፡ ላይ ፡ ይደረጋል ።

(፪) የልጁን ፡ እናት፡ አስፈላጊም፡ ሲሆን ፡ አባትዮውን ፡ በነገሩ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

ስለ ፡ መካድ ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። መሠረቱ ።**

ከአባት ፡ የሚመጣው ፡ ለልጁ ፡ አባት ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ በማለት ፡ የሚቀርበው ፡ ክርክር ፡ የሚፈጸመው ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። ከልጁ ፡ እናት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ስላለመኖር ፡ (፩) መሠረቱ ።**

የልጁ፡ አባት፡ ነህ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ አባትነት ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ልጁ ፡ ከመወለዱ ፡ በፊት ፡ በ፻፹ኛውና ፡ በ፫፻ኛው ፡ ቀን ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ ከልጁ ፡ እናት ፡ ጋራ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ላለመገናኘቱ ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ በማይገኝበት ፡ አኳኋን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቱባለውን ፡ ልጅ ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፬ ። (፪) ስለ ፡ ሕሊና ፡ ግምት ።**

(፩) ከሁለቱ ፡ አንዱ፡ ባቀረበው፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሁለቱ፡ መካከል ፡ በጽሑፍ ፡ በተደረገው ፡ የመለያየት ፡ ስምምነት ፡ ምክንያት ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በእውነት ፡ ተለያይተው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ በመካከላቸው ፡ የሥጋ ፡ ግብር ፡ ግንኙነት ፡ እንዳልተደረገ ፡ ይገመታል ።

(፪) ለዚህ ፡ ተቃራኒ፡ ሆኖ ፡ የሚቀርበው፡ ማስረጃ ፡ በማንኛዎቹም ፡ ምክንያቶች፡ ቢሆን ፡ ይሰማል ፤ ይኸውም ፡ ማስረጃ ፡ በተለየ ፡ ቀላሎች ፡ ከሆኑ ፡ ግምቶች ፡ ሊመነጭ ፡ (ሊገኝ) ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፭ ። አባት ፡ ነህ ፡ ለማለት ፡ ስላለመቻሉ ። (፩) መሠረቱ ።**

የልጁ ፡ አባት ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ አባትነቱ ፡ በሕግ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፤ ልጁ ፡ ከዚህ፡ ከተባለው ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ተወልዷል ፡ ለማለት ፤ በዐይነቱ ፡ በጥራሽ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ በማይገኝበት ፡ አኳኋን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልጁ ፡ የኔ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፮ ። በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ።

(፩) ዳኞችን ፡ አስፈቅዶ ፡ የልጅ ፡ መካድን ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ ይህንኑ ፡ ፈቃድ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፹፯ ። (፪) ክስን ፡ ለመቀበል ፡ ስለ ፡ መቻል ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ የሚቀርበው ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ ዳኞቹ ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

(፪) የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ለሚቀርበው ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ ዳኞቹ ፡ ክሱን ፡ እንዲቀበሉ ፡ ከሚያደርጋቸው ፤ እርግጠኛ ፡ ከሆኑና ፡ በቂ ፡ ከባድነት ፡ ካላቸው ፡ ተግባሮች ፡ የመነጩ ፡ ግምቶች ፡ ወይም ፡ ምልክቶች ፡ ሲኖሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፹፰ ። (፫) ስለ ፡ ሕሊና ፡ ግምቶችና ፡ ስለ ፡ ከባድ ፡ ምልክቶች ።

(፩) የሕሊና ፡ ግምቶችና ፡ ከባድ ፡ (ትልቅ) ፡ ምልክቶች ፡ የሚባሉት ፤ ልጅህ ፡ ነው ፡ ከተባለው ፡ ሰው ፡ አባትነት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ (የማይገናኙ) ፡ ለመሆናቸው ፡ በሲያንስ ፡ ዕውቀት ፡ ተለይተው ፡ የሚታዩ ፡ ግዙፍ ፡ ሁኔታዎች ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፤ ሴቲቱ ፡ በሰውዬው ፡ አባትነት ፡ ጥርጣሬ ፡ ለማግባት ፡ በሚችል ፡ አኳኋን ፡ የልጅን ፡ መወለድ ፤ ወይም ፡ እንዲያውም ፡ እርግዝናዋን ፡ ለባልዋ ፡ ከደበቀችበት ፡ ምክንያት ፡ ሊመነጩ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፹፱ ። (፬) ስለ ፡ ሴሰኝነት ፡ (በባል ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ዝሙት) ፡ ወይም ፡ ስለ ሴቲቱ ፡ ማመን ።

ሴቲቱ ፡ በባልዋ ፡ ላይ ፡ ያደረገችው ፡ የሴሰኝነት ፡ (የዝሙት) ፡ ሥራ ፤ ወይም ፡ ልጁ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ለመሆኑ ፡ የምትሰጠው ፡ የእምነት ፡ ቃል ፤ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ትልቅ ፡ ምልክት ፡ ሊቈጠሩ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፯፻፺ ። የማይመስል ፡ አባትነት ።

የልጅነት ፡ ሁኔታው ፡ እንዲገለጽለት ፡ በመጠየቅ ፡ ልጁ ፡ ከእናቲቱ ፡ ለመወለዱ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አባትነቱ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ላለመሆኑ ፡ የሚያቀርባቸውን ፡ ምክንያቶች ፡ በማስረዳት ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ለመካድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፺፩ ። ስለ ፡ ከሳሽ ።

የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡—

(፩) የልጁ ፡ አባት ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ በሕጋውያን ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የልጁ ፡ አባትነት ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ጕዳይ፡ በተለይ፡ እናቲቱ ፡ ወይም ፡ አባት፡ ነኝ ፡ ባዩ ፤ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ልጁ ፡ ራሱ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። ክስ ፡ የሚቀርብበት ፡ ጊዜ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ የመካድ ፡ ክስ ፤ ልጁ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ በሚከተሉት ፡ ፻፹ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩ ፡ እንዲገለጽ ፡ ለመጠየቅ ፡ በቀረበው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ ልጁ ፡ ከእናቲቱ ፡ ለመወለዱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፤ የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩ ፡ እንዲገለጽ ፡ ለመጠየቅ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ የሚወስን ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፤ በ፻፹ ፡ ቀኖች ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፫ ። (፪) ስለ ፡ ልዩ ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያት ።**

(፩) ልጅህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አባትነቱ ፡ በሕግ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ በተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፡ ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የመካድን ፡ ክስ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ተወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ተወላጆቹ ፡ (ተወላድያን) ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፡ እነዚህም ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ ይቻላል ።

(፫) ወደ ፡ ላይ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለውን ፡ መብት ፤ ማናቸውም ፡ ሌላው ፡ ወራሽ ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፤ ከወንድሞቹ ፡ ወይም ፡ ከእኅቶቹ ፡ አንዱ ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፬ ። ክስን ፡ ስላለመቀበል ።**

ባልየው ፡ በጽሑፍ ፡ ፈቃዱ ፡ በጥበባዊ ፡ (በአርቲፊሲየል) ፡ መንገድ ፡ ልጁ ፡ የተፀነሰ ፡ ለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፡ የማለትን ፡ የክስ ፡ ጥያቄ ፡ ሊቀበሉት ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፭ ። ስለ ፡ ተከሳሽ ።**

(፩) ልጄ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ በልጁ ፡ ላይ ፤ እርሱም ፡ ሞቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በወራሾቹ ፡ ላይ ፡ ይቀርባል ።

(፪) የልጁን ፡ እናት ፡ በሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ እንድትገባ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) ልጁ ፡ አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ በተለይ ፡ የመረጡት ፡ ተጠባባቂ ፡ ሞግዚት ፡ ወኪል ፡ ይሆነዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

## ስለ ፡ ጉዲፈቻ ፡ የማር ፡ ልጅ ።

### ቍ ፡ ፯፻፺፮ ። በጉዲፈቻ ፡ ስለሚገኝ ፡ ልጅነት ።

(፩) በጉዲፈቻ፡ አባትና፡ በጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ በሚደረገው ፡ ውል ፡ ምክን ያት ፡ አንድ ፡ የሚያስተሳስር ፡ የልጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ሊፈጠር ፡ ይቻላል ።

(፪) በጉዲፈቻ፡ ልጅና፡ በጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ መካከል ፡ ከአሠራሩ ፡ የተነሣ ፡ የሚገኙት ፡ የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ መተሳሰር ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በመጀመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ ተገልጸዋል ።

### ቍ ፡ ፯፻፺፯ ። ስለ ፡ ጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ ዕድሜ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ሰው ፤ አካለ መጠን ፡ ካደረሰ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ባልና ፡ ሚስት ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ፡ በሚወልዱበት ፡ ጊዜ ፤ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ የአርባ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ ይበቃል ።

### ቍ ፡ ፯፻፺፰ ። ያገባ ፡ ሰው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ማበጀቱ ።

(፩) ጉዲፈቻ፡ አድራጊው ፡ ያገባ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ባንድነት ፡ ሆነው ፡ የጉዲፈቻውን ፡ ልጅ ፡ ለመቀበል ፡ ውል ፡ ካላደረጉ ፡ የጉዲፈቻው ፡ ሥር ዐት ፡ ሊፈጸም ፡ አይቻልም ።

(፪) ባል ፡ የሚስቱን ፤ ሚስት ፡ የባልዋን፡ ልጅ ፡ የጉዲፈቻ፡ ልጅ ፡ ያደረጉት፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ፡ አይሆንም ።

(፫) እንዲሁም ፤ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ አሳቡን ፡ ለመግለጽ ፡ በማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ሲገኝ ፡ ድንጋጌው ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

### ቍ ፡ ፯፻፺፱ ። የተፀነሰውን ፡ ልጅ ፡ በጉዲፈቻ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።

(፩) የተፀነሰውን ፡ ልጅ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅነት ፡ ልጁ ፡ ከመወለዱ ፡ በፊት ፡ ወይም፡ ልጁ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ በሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ በሚደረገው ፡ ማስታወቅ ፡ ብቻ ፡ ሊቀር ፡ ይቻላል ።

### ቍ ፡ ፰፻ ። ጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ ልጅ ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ጉዲፈቻ፡ አድራጊው፡ ልጅም፡ ቢኖረው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅን ፡ መውሰድ ፡ አይከለከልም ።

**ቍ ፡ ፰፻፩ ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ማድረግ ፡ የማይገባቸው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ባልና ፡ ሚስት ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጉዲፈቻ፡ ልጅ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ፡ ሆነም ፤ ጉዲፈቻ፡ አድራጊው፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ፡ገና፡ለሌላ፡ሰው፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ።

(፫) የጉዲፈቻው፡ ልጅ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በጉዲፈቻ ፡ የወሰዱት ፡ ሲሆን ፤ ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዳቸው ፡ በሞት ፡ የጉዲፈቻው ፡ ልጅ ፡ በሕይወት ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ የሚጋባው ፡ አዲሱ ፡ ተጋቢ ፡ ጉዲፈቻ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፪ ። ውሉን ፡ ስለሚያደርጉ ፡ ወገኖች ።**

(፩) ስለ ፡ ጉዲፈቻ ፡ የሚደረገው ፡ ውል ፤ በጉዲፈቻ ፡ የሚወለደው ፡ ልጅ ፡ ዕድሜው ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጉዲፈቻ ፡ አድራጊውና ፡ በጉዲፈቻው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ ይፈጸማል ።

(፪) ጉዲፈቻ፡ የሚደረገው፡ ልጅ፡ ዕድሜው፡ ከ፲፰፡ ዓመት፡ በታች፡ የሆነ፡እንደ፡ሆነ፡ ውሉን፡ ጉዲፈቻ ፡ አድራጊውና ፡ የጉዲፈቻው ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪ ፡ ይፈጽሙታል ።

**ቍ፡ ፰፻፫ ። የጉዲፈቻው ፡ ልጅ ፡ ወላጆች ፡ ፈቃድ።**

(፩) የጉዲፈቻው፡ ልጅ፡ አባትና፡ እናት፡ በሕይወት ፡ ያሉና ፡ የታወቁ ፡ ከሆኑ ፡ ሁለቱም፡ ልጃቸው፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ እንዲሆን ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) አባትና፡ እናቱ፡ ሞተው ፡ የሌሉ ፡ ወይም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ የማይችሉ፡እንደ፡ሆነና፡የማይቻል፡ ሲሆን፡ ጉዲፈቻውን፡ ለመፍቀድ፡ ወደ፡ላይ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆቻቸው ፡ በእነርሱ ፡ ምትክ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ልጁ ፡ ጉዲፈቻ ፡ እንዲሆን ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ ወደ፡ላይ ፡ የሚቈጠር፡ ወላጅ፡ የሌለው ፡ እንደ፡ሆነ፡ ፈቃድ፡ የሚሰጠው ፡ የቤተ፡ዘመድ ፡ ምክር፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፬ ። ስለ ፡ ጉዲፈቻው ፡ ውል ፡ መጽናት ።**

(፩) የጉዲፈቻው ፡ ውል፡ ዳኞች፡ ካላጸኑት ፡ በቀር ፡ ውጤት፡የለውም ፡(አይጸናም)።

(፪) ዳኞቹ ፡ ውሳኔ፡ ከመስጠታቸው፡ በፊት ፡ ጉዲፈቻ ፡ የሚሆነው ፡ ልጅ፡ ከዐሥር፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱ ፡ የሚለውንና ፡ ይህን ፡ የጉዲፈቻውን ፡ ውል ፡ አስቀድሞ ፡ አሳዳጊው ፡ ያልፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ የአሳዳጊውን ፡ ቃል ፡ መስማት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፭ ። የጉዲፈቻውን ፡ ውል ፡ ለማጽደቅ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ምክንያቶች ።**

የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለመሆን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖርና ፡ ጉዲፈቻ ፡ ለሚሆነው፡ልጅ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ሲታይ ፡ ብቻ ፡ ነው።

**ቍ ፡ ፰፻፮ ። የጉዲፈቻን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

የጉዲፈቻ ፡ ውል ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ሊፈ ርስ ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

## ስለ ፡ ቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ።

**ቍ ፡ ፰፻፯ ። ስለ ፡ ግዴታው ፡ ዓላማ ።**

የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ለባለጕዳዮች ፡ ሁኔታና ፡ ለአገሩ ፡ ልማድ ፡ የሚስማሙትን ፡ በመከተል ፡ እንደሚገባ ፡ ዐይነት ፡ ተጠዋሪው ፡ የሚ መገባቸውን ፡ የሚኖርባቸውን ፤ የሚለብሳቸውንና ፡ ጤናውን ፡ የሚጠብቅባቸ ውን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፰፻፰ ። ግዴታው ፡ በእነማን ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ስለመሆኑ ።**

(፩) የቀለብ፡ መስጠት፡ ግዴታ ፡ ያለው ፡ በቀጥታ ፡ ወላጆችና ፡ ተወላጆች፡ ወይም፡ በቀጥታ ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም፡ ከአንድ፡ አባትና ፡ ከአንድ ፡ እናት ፡ በተወለዱት ፡ ወይም፡በአባት፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ ወንድማማችና ፡ እትማማች ፡ በሆኑ ትም ፡ መካከል ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለ ።

**ቍ ፡ ፰፻፱ ። (፩) ግዴታው ፡ የሚወገድበት ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያት ።**

በጋብቻው ፡ ምክንያት ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰር ፡ በመፋታት ፡ ምክንያት ፡ የቀረ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፰፻፲ ። (፪) በዳኝነት ፡ በኩል ፡ ስለሚነገር ፡ አባትነት ።**

ሴትዮዋ ፡ በተጠለፈች ፡ ወይም ፡ በተደፈረች ፡ ጊዜ ፡ ልጅህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በዳ ኝነት ፡ ለተነገረበት ፡ ሰው ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ አይገባቸውም ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፩ ። (፫) ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ቀለብ ፡ ለመቀበል ፡ የማይገባው ፡ ስለ ፡ መሆኑ።**

እንዲሁም ፡ ቀለብ ፡ ተቀባዩ ፡ በቀለብ ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ላይና ፡ ወደ ፡ ታች ፡ በሚቈጠሩ ፡ ወላጆችና ፡ ተወላጆች ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ሙከራ ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀለብ ፡ መቀበሉ ፡ ይቀርበታል ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፪ ። ግዴታ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሁኔታዎች ።**

የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፤ ግዴታው ፡ እንዲ

ፈጸምለት ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰው ፤ ሠርቶ ፡ ለመብላት ፡ የማይችል ፡ ሲሆንና ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፫ ። ስለ ፡ ግዴታ ፡ አፈጻጸም ፡ ዐይነት ።**

(፩) በመደቡ ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ የሚፈጸመው ፡ ጧሪው ፡ ለተጠዋሪው፡ የቀለቡን ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

(፪) የዚህ ፡ የጡረታ ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ የሚወሰነው ፡ (የሚቈጠረው) ፡ የጡረታውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰው ፡ ያለበትን ፡ ችግርና ፡ የከፋዩን ፡ ሀብት ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፬ ። ሁኔታውን ፡ ለማሻሻል ፡ ስለ ፡ መቻል ።**

ቀለብ ፡ ሰጪው ፡ ወይም፡ ተቀባዩ ፡ በሚያቀርቡት ፡ ጥያቄ፡መሠረት ፡ ለጡረታ፡ ገንዘብ፡ ልክ፡ የተሰጠውን፡ ውሳኔ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ፡ ሁሉ፡ ለማሻሻል ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፭ ። የጡረታው ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈልበት ፡ ቦታ ።**

ዳኞቹ ፡ የሰጡት ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የጡረታ ፡ ገንዘቦች ፡ የሚከፈሉት ፡ በተጠዋሪው ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፮ ። የሚከፈል ፡ የጡረታ ፡ ገንዘብ ። (፩) ሊተላለፍና ፡ ሊያዝ ፡ ስላለመቻሉ ።**

(፩) ለጡረታ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ሊተላለፍና ፡ ሊያዝ ፡ አይቻልም ።

(፪) እንዲሁም፡ ስለ፡ ተባለ ፡ ለጡረታ ፡ የሚከፈሉ ፡ ገንዘቦች ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ አስቀድሞ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ በጡረታው ፡ ምግብ ፡ የሚጠቀመው ፡ ሰው ፡ ላለበት ፡ ችግር ፡ አሳቢ ፡ ለሚሆኑ ፡ ስለ ፡ እርዳታ ፡ ለተቋቋሙ ፡ ድርጅቶች ፡ ሊተላለፉ ፡ ይቻላል ።

(፫) እንዲሁም ፤ ውዝፎችን ፡ በጡረታው ፡ ለሚጠቀመው ፡ ሰው ፡ ለሕይወቱ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የሰጡት ፡ ሰዎች ፡ ሊቀበሉት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፯ ። (፪) የሚጠራቀም ፡ ስላለመሆኑ ።**

ቀለብ ፡ ተቀባዩ ፡ ውዝፉ ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ካላረጋገጠ፡በቀር ፤ ማናቸውም ፡ ውዝፍ ፡ ቢሆን ፡ ለመከፈሉ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ በሚከተሉ ፡ ሦስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ የተባለውን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይቀበለው ፡ ወይም ፡ ሳይጠይቀው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀሪ ፡ ይሆንበታል ።

**ቍ ፡ ፰፻፲፰ ። ቀለብ ፡ ተቀባዩን ፡ ከቤት ፡ ለማኖር ፡ ስለ ፡ መቻል ።**

(፩) ቀለብ፡ ሰጪው፡ ቀለብ ፡ ተቀባዩን ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ተቀብሎ፡በማስቀመጥ፡ ግዴታውን ፡ ልፈጽም ፡ ሲል ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ዳኞች፤ ይህን ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ የሚቀበሉት ፡ ወይም ፡ የማይቀበሉት ፡ ለመሆኑ ፡ አካባቢዎቹን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ተመልክተው ፡ ይወስናሉ ።

(፫) ቀለብ ፡ ሰጪው፡ ቀለብ ፡ ተቀባዩን፡ በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ምን፣ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ለመገደድ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፰፻፲፱ ። ስለ ፡ ቀለብ ፡ ሰጪዎች ፡ ብዛት ። (፩) መሠረቱ ።

ለቀለብ ፡ ተቀባዩ ፡ ቀለብ ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱን ፡ ለጠኝ ፡ ሲል ፡ ጥያቄውን ፡ ሊያቀርብለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፳ ። (፪) ስለ ፡ አቤቱታ ።

(፩) ቀለብ፡ እንዲከፍሉ፡ የተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሳይከፍሉ ፡ የቀሩትን ፡ ባለዕዳ ዎች ፡ ለመክሰስ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ዳኞቹ ፡ ተከሳሾቹ፡ ባለዕዳዎች፡ ያላቸውን ፡ ሀብትና ፡ ከከሳሹ ፡ ጋራ ፡ ያላቸ ቸውን ፡ የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ደረጃ ፡ በማመዛዘን ፡ እነዚህ ፡ የተከሰሱት ፡ ባለዕዳዎች ፡ የቀለቡን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከ ፊል ፡ እንዲከፍሉ ፡ ሊፈርዱባቸው ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፳፩ ። (፫) ለቀለብ ፡ ሰጪዎች ፡ የሚሰጥ ፡ የከፋይነት ፡ ተራ ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑትም ፡ ቀለብ ፡ ሰጪዎች ፡ ባለባቸው ፡ ግዴታ ፡ ምክንያት ፡ በቍጥር ፡ የዚህን ፡ የቀለብ ፡ ሰጪነት ፡ ዕዳ ፡ የሚችሉበት ፡ የከፋይነት ፡ ተራ ።

(ሀ) በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፤

(ለ) በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተወላጆቹ ፡ እንደየደረጃቸው ፤

(ሐ) በሦስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆቹ ፡ እንደየደረጃቸው ፤

(መ) በአራተኛው፡ ደረጃ፡ ከአንድ፡ አባትና ፡ ከአንድ ፡ እናት ፡ የተወለዱ ፡ ወን ድማማችና ፡ እኅትማማቾች ፤

(ሠ) በአምስተኛው ፡ ደረጃ ፡ ከአባት ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ ከእናት ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ ወንድማማችና ፡ እኅትማማች ፤

(ረ) በስድስተኛው ፡ ደረጃ ፡ የጋብቻ ፡ ተወላጆቹ ፡ እንደየደረጃቸው ፤

(ሰ) በሰባተኛው ፡ ደረጃ ፡ የጋብቻ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ እንደየ ደረጃቸው ፤

**ቍ ፡ ፫፻፳፪ ። (፬) በጋራ ፡ ቀለብ ፡ ሰጪዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።**

(፩) የጋራ፡ ቀለብ፡ ሰጪዎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ስለአላቸው ፡ ግንኙነት ፡ ለጋራ ፡ ቀለብ ፡ ተቀባያቸው ፡ ከእነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ቀለቡን ፡ እንዲሰጠው ፡ በማለት ፡ የሚጸና ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

፪) ቀለብ ፡ ተቀባዩ ፡ ስምምነቱን ፡ ይሁን ፡ ሲል ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን፡ ስምምነት ፡ የማያከብርበት ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ካልተገኘለት ፡ በቀር ፤ ቀለቡን፡ ለመቀበል ፡ ሌሎቹን ፡ ቀለብ ፡ ሰጪዎች ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፫ ። ስለ ፡ ጉዲፈቻ ፡ ልጅነት ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የጉዲፈቻ፡ ልጅ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስትና ፡ የቀጥታ ፡ መሥመር ፡ ተወላጆቹ ፡ የጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ቀለቡን ፡ ለመስጠት ፡ በማይችሉበት፡ ሁኔታ ፡ ካልተገኙ ፡ በቀር ፡ የሥር ፡ ወላጆቹን ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ቀለብ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) የሥር፡ ወላጆቹ ፡ ቀለብ ፡ ለማግኘት ፡ ሌላውን ፡ ከዝርያቸው ፡ አንዱን ፡ ለመጠየቅ ፡ የማይችሉ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፤ በጉዲፈቻ ፡ የሰጡትን ፡ ልጅ ፡ ቀለብ ፤ ሊጠይቁት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፬ ። ስለ ፡ ሥርዐተ ፡ ቀብር ፡ ኪሣራ ።**

(፩) የቀለብ፡ መስጠት፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ለዚህ ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ ሥርዐት ፡ ቀብር ፡ የወጣውንም ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ ተገዳጅ ፡ ይሆናል ።

(፪) የዚህን ፡ ኪሣራ ፡ ወጪ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፤ የሥራ ፡ አካሄድን ፡ በሚመለከቱት፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ገዘንቡን ፡ እንዲያገባለት ፡ ቀለብ ፡ ሰጪውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፭ ። ልዩ ፡ ስምምነቶች ።**

ልዩ ፡ ስምምነቶችን ፡ በማድረግ ፤ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለመለወጥ ፡ አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፡ አምስት ።

## ስለ ፡ ውርስ ፡ (ስለ ፡ አወራረስ) ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ውርስ ፡ አስተላለፍ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

#### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

#### ስለ ፡ ውርስ ፡ አከፋፈትና ፡ በውስጡ ፡ ስለሚገኝበት ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፮ ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ መከፈት ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሞተበት ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ መኖሪያው ፡ ስፍራ ፡ በሆነበት ፡ ቦታ ፡ የዚህ ፡ ሟች ፡ ውርስ ፡ ይከፈታል ።

(፪) በሟቹ፡ መሞት፡ ምክንያት ፡ የሚቈጠሩ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የሟቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታ ዎች ፡ ለወራሾቹና ፡ የኑዛዜ ፡ ባለስጦታዎች ፡ ይተላለፋሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፯ ። በውርስ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፤ (፩) ስለ ፡ ሕይወት ፡ የሚደረግ ፡ አሹራንስ ።**

(፩) ሟቹ፡ ተጠቃሚውን፡ ፡ያልወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ አሹራንሱ ፡ ለሟቹ፡ ወራሾች ፡ ጥቅም ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሟቹ ፡ በፈረመው ፡ ስለ ፡ ሕይወት ፡ አሹራንስ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ የሚከፈሉ ፡ ገንዘቦች ፡ የውርስ ፡ ንብረት ፡ ክፍል ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ሁኔታ ፡ ሲኖር ፡ የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ አይሆኑም ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፰ ፡ ፪ ፡ ጡረታና፡ ካሣ።**

በሞት ፡ ምክንያት ፡ ለሟቹ ፡ ዘመዶች ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የሚ ሰጡ ፡ ጡረታዎች ፡ ወይም ፡ ካሣዎች ፡ የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ አይሆኑም ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፱ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ውርስ ።**

(፩) የሟች ፡ ውርስ ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) ውርሱም ፡ በከፊል ፡ ያለ ፡ ኑዛዜና ፡ በከፊል ፡ በኑዛዜ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፫) ሟቹ፡ በኑዛዜ፡ ያላደላደላቸው ፡ ሀብቶች ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ለሚወርሱት፡ ይሰጣሉ።

BACK



## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ወራሽ ፡ ለመሆን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ችሎታ ።

**ቍ ፡ ፰፻፴ ።  ወራሽ ፡ ለመሆን ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ምክንያቶች ።**

ለሟቹ፡ ሀብት፡ ወራሽ፡ መሆን ፡ ለመቻል ፤ በሕይወት ፡ ያለ ፡ መሆንና ፡ ለወራሽነት ፡ የማይገባ ፡ አለመሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፩ ። የሟቹ ፡ ወራሽ ፡ በሕይወት ፡ ስለመኖር ።**

(፩) ሟቹ ፡ በሞተበት፡ ቀን ፡ አንድ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ አለ ፡ የማለት ፡ ማስረጃ ፡ የሚደረገው ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የዚሁ፡ አንቀጽ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከአገር ፡ መጥፋት ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ምክንያቶች ፡ ይወስናሉ ።

(፫) ምትክ ፡ ሆኖ ፡ መውረስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፪ ። ስለ ፡ አብሮ ፡ ሟቾች ፡ ሰዎች ።**

ሁለት፡ ወይም፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሞቱ ፡ ሲሆንና ፡ ከነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በኋላ ፡ የሞተው፡ የትኛው፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከአብሮ ፡ ሟቾች ፡ ሰዎች ፡ ሀብት ፡ ወራሽነት ፡ ምንም ፡ ሳያገኝ ፡ የነዚሁ፡ ሰዎች ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ውርስ ፡ በመጨረሻ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ዐይነት ፡ ተቈጥሮ ፡ ይወሰናል ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፫ ። ስለ ፡ ወራሹ ፡ መሞት ።**

ለአንድ፡ ውርስ፡ ወራሽ፡ የሆነ፡ አንድ ፡ ሰው፡ ውርሱ ፡ ከተከፈተ፡በኋላ ፡ የሞተ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የወራሽነቱ ፡ መብቶች ፡ ለርሱ ፡ ወራሾች ፡ ይተላለፋሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፬ ። ስለ ፡ ተፀነሰ ፡ ልጅ ።**

የተፀነሰ፡ ልጅ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ፡ በተመለከቱት፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ወራሽ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፭ ። በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ።**

በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶችና ፡ በተለይ ፡ ለአንድ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ የኑዛዜን ፡ ስጦታ ፡ ለመቀበል ፡ ያላቸው ፡ ችሎታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ድርጅቶችና ፡ በተለይ ፡ ለአንድ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ተወስኗል ።

<u>ቍ ፡ ፰፻፴፮ ። ስለ ፡ ሕጋዊ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ዲቃላ ፡ ወይም ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ።</u>

(፩) የሟቹ ፡ ወይም ፡ የወራሹ ፡ የሕግ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የዲቃላ ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ ወራሾችን ፡ ወይም ፡ የያንዳንዳቸውን ፡ ድርሻ ፡ ልክ ፡ ለመወሰን ፡ በሚመለከተው ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) እንደዚሁ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ፡ጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፶፯፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ እንደ፡ተጠበቁ፡ ሆነው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጆችም ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ልጆች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ፰፻፴፯ ። ስለ ፡ ወራሹ ፡ ጾታ ፡ ዕድሜና ፡ ዜግነት ።</u>

የወራሹ፡ ጾታ ፡ ዕድሜና ፡ ዜግነት ፡ በወራሽነት ፡ መብቶቹ ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ልዩነትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ አይደሉም ።

<u>ቍ ፡ ፰፻፴፰ ። ያልተገባ ፡ ስለ ፡ መሆን ። (፩) ወንጀሎች ፡ ወይም ፡ ቅጣቶች ።</u>

ሟቹን፡ ለመውረስ፡ የማይገባ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የወራሽነትን ፡ መብት፡ የሚያጣ፡

(ሀ) ሟቹን፡ ወይም፡ የሟቹን ፡ ወደ፡ታች፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጅ ፡ ወይም ፡ ወደ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ የሟቹን ፡ ባል ፡ ወይም፡ሚስት፡ አስቦ ፡ በመግደል ፡ የተፈረደበት ።

(ለ) ከነዚሁ ፡ ሰዎች፡ መካከል፡ አንደኛውን፡ ለመግደል ፡ በመሞከር ፡ የተቀጣ ፤

(ሐ) በሐሰት፡ በመወንጀል፡ ወይም፡ በሐሰት ፡ ምስክርነት ፡ ይህ ፡ በሐሰት፡መወንጀል ፡ በሐሰት ፡ መመስከር ፡ ከነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በአንደኛው፡ላይ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ የጽኑ ፡ እስራት፡ቅጣትን፡ ለማስከተል ፡ የሚያሠጋ ፡ ሁኖ ፡ የተቀጣ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፰፻፴፱ ። (፪) ስለ ፡ ማጣራት ።</u>

ወራሽ፡ የሆነው፡ ሰው፡ ወንጀሉን ፡ ወይም ፡ የወንጀሉን ፡ ሙከራ ፡ ያደረገው፡ አውራሹ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ወደ፡ታች ፡ በሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ ወይም ፡ ወደ፡ላይ፡ በሚቈጠር ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባለው ፡ የወራሽነት ፡ መብት ፡ ማጣት ፡ አይፈጸምበትም ።

<u>ቍ ፡ ፰፻፵ ። (፫) ሌሎች ፡ ምክንያቶች ።</u>

በተለይ ፡ ሟቹን ፡ ለመውረስ ፡ የማይገባ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡—

(ሀ) የሟቹን፡ ሰውነት፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ አውራሹ ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ በአሉት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ኑዛዜ ፡ እንዲያደርግ ፡ እንዳይለውጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይሽር ፡ የከለከለ ፤

(ለ) አስቦ፡ ያለሟቹ፡ ፈቃድ ፡ የሟቹን ፡ የመጨረሻ ፡ ኑዛዜ ፡ ያበላሸ ፡ እንዳይገኝ ፡ ያደረገ ፡ ያጠፋ ፡ ወይም፡ ጕዳዩን ፡ በማወቅ፡ በሐሰት ፡ ኑዛዜ ፡ የተጠቀመ የወራሽነት ፡ መብት ፡ ያጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፰፻፵፩ ። (፬) ይቅርታ ።**

(፩) ከዚህ፡ በፊት፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች፡ የተመለከተው፡ የመውረስ ፡ መብት ፡ማጣት፡ ሟቹ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ወራሹን ፡ ይቅርታ ፡ ያደረገለት ፡ መሆኑን ፡ አስታውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፪) በኑዛዜ ፡ ስለሚደረግ ፡ ስጦታ ፡ ሲሆን ፤ ሟቹ ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታውን ፡ ያደረገው ፡ ወራሽ ፡ መሆን ፡ እንዳይገባው ፡ የሚያደርገው ፡ ነገር ፡ከተፈጸመ ፡ በኋላና፡ ጕዳዩንም ፡ ዐውቆት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ የመውረስ ፡ መብት ፡ ማጣት ፡ አይኖርም ።

## ክፍል ፡ ሁለት ።

## ሳይናዘዝ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ውርስ ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፪ ። የመጀመሪያ ፡ ዝምድና ፡ ደረጃ ።**

(፩) የሟቹ ፡ ልጆች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሟች ፡ ወራሾች ፡ ናቸው ።

(፪) ከውርሱም ፡ እያንዳንዱ ፡ ትክክል ፡ ድርሻ ፡ ይቀበላሉ ።

(፫) የሟቹ ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ ከልጆቹ ፡ አንዱ ፡ ሞተው ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ትተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በነሱ ፡ ምትክ ፡ ሆነው ፡ ይወርሳሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፫ ። ሁለተኛ ፡ የዝምድና ፡ ደረጃ ። (፩) መሠረቱ ።**

ሟቹ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ያልተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ ወራሾቹ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፬ ። (፪) አፈጻጸሙ ።**

(፩) የሟች ፡ አባትና፡ እናት፡ የውርሱን ፡ ንብረት ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ ይካፈላሉ ።

(፪) ከአባት፡ ከእናት፡ አስቀድሞ ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ የሱን ፡ ፈንታ ፡ ልጆቹ፡ወይም፡ ሌሎች ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆቹ ፡ በሱ ፡ ተተክተው ፡ ይወርሳሉ ።

(፫) ከነዚህ፡ መሥመሮች፡ በአንዱ፡ መሥመር፡ ያለው ፡ ወራሽ ፡ ቢታጣ ፡ ውርሱ፡ በሙሉ ፡ በሌላው ፡ መሥመር ፡ ላለው ፡ ወራሽ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፭ ። ሦስተኛ ፡ ዝምድና ፡ ደረጃ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ሟቹ፤ ወደ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ወይም ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፤ ወይም ፡ የነርሱ ፡ ወደ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ፡ ተወላጆች ፡ የሌለው ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ አያ [illegible] ራሾቹ ፡ ይሆናሉ ።

BACK



(፪) የውርሱ፡ እኩሌታው፡ ፀአባት፡ መሥመር ፡ ላሉ፡ አያቶች፡ ወይም ፡ ወደ፡ ታች፡ ለሚቈጠሩ ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ይሆናል ። የቀረው ፡ የውርሱ ፡ እኩሌታ ፡ በእናት፡ መሥመር ፡ ላሉ ፡ አያቶች ፡ ወይም ፡ ወደ፡ ታች ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፪ ። (፪) ለሌላ ፡ የዝምድና ፡ መሥመር ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

(፩) በአባት፡ ወይም፡ በእናት፡ የትውልድ ፡ መሥመር፡ የዘር ፡ ተከታይ፡ ሳይኖረው፡ የሞተ ፡ አያት ፡ ድርሻው ፡ ለዚሁ ፡ መሥመር ፡ ወራሾች ፡ ይተላለፋል ።

(፪) አንድ ፡ የትውልድ ፡ መሥመር ፡ የዘር ፡ ተከታይ ፡ ሳይኖራቸው ፡ የሞቱ፡ አያ ቶች ፤ ማናቸውም ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ የዝምድና፡ መሥ መር ፡ ወራሾች ፡ ይተላለፋል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፫ ። አራተኛ ፡ የዝምድና ፡ ደረጃ ። (፩) መሠረቱ ።**

የሦስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ዘመድ ፡ ወራሾች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሟቹ፡ ቅድመ ፡ አያቶች ፡ ወራሾቹ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፬ ። አፈጻጸም ።**

(፩) የውርሱ፡ እኩሌታ፡ የአባት ፡ መሥመር ፡ ለሆኑ ፡ ቅድመ ፡ አያቶች ፡ ወይም ፡ ለተወላጆቻቸው ፡ እኩሌታው ፡ የእናት ፡ መሥመር ፡ ለሆኑ ፡ ቅድመ ፡ አያቶች፡ ወይም ፡ ለተወላጆቻቸው ፡ ይሰጣል ።

(፪) በላይኛው ፡ ኀይለ፡ ቃል ፡ የተነገረው፡ ውሳኔ ፡ እንደ፡ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ከሟቹ፡ በኋላ ፡ በሕይወት ፡ የሚገኘው ፡ የዚሁ ፡ ምትክ ፡ ለመሆን ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ቅድመ፡ አያት ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ተወላጅ ፡ የውርሱን ፡ ሀብት ፡ እኩል ፡ ይካፈ ላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፭ ። የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ የእናትን ፡ ለእናት፡ ወገን ፡ መስጠት ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፤ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ሟቹ፡ ሳይናዘዝ፡ በሞተ ፡ ጊዜ፡ ከዚህ፡በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተጻፈው ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ለሟቹ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ ከአባቱ ፡ መሥመር ፡ ወገን ፡ የመጣለትን፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የእናት ፡ መሥመር ፡ ወገን ፡ ለሆኑ ፡ ወራሾች ፡ በርስትነት፡ መስጠት ፡ አይቻልም ።

(፪) እንደዚሁም፡ ለሟቹ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ ከእናቱ ፡ መሥመር፡ ወገን፡ የመጣለትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የአባት ፡ ወገን ፡ ለሆኑ ፡ ወራሾች ፡ በር ስትነት ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ።

(፫) ከአባት፡ ወገን ፡ አያት፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡ የተገኘው ፡ የማይንቀሳ ቀስ ፡ ንብረት ፡ የእናት ፡ ወገን ፡ ለሆነ ፡ ተወላጅ ፡ እንዳይተላለፍ ፡ እንዲሁም ፡

BACK



ከእናት ፡ ወገን ፡ አያት ፡ የተገኘው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለአባት ፡ ወገን ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ሁለት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ የተ ነገረው ፡ ደንብ ፡ ለሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትውልድም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፰፻፶ ። (፪) አፈጻጸም ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው፡ ቍጥር፡ ደንብ ፡ ምክንያት ፡ በውርስ ፡ ለአንድ ፡ ወራሽ፡ ከአንድ ፡ ውርስ ፡ የመጣለትን ፡ ድርሻ ፡ ሊሰጠው ፡ የማይቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በርስትነት ፡ ሊሰጠው ፡ ከማይቻለው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሪም ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) በዚህም፡ የተነሣ፡ ከመብቶቹ ፡ ለተቀነሱበት ፡ ወራሽ ፡ የሚከፈለው ፡ ምንም ፡ ኪሣራ ፡ የለም ።

ቍ ፡ ፰፻፶፩ ። (፫) ስለ ፡ መወሰን ።

በአባት ፡ መሥመር ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ በእናት ፡ መሥመር ፡ ወገን ፡ ወራሾች ፡ ከሌሉ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ በሁለቱ ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፰፻፶፪ ። ለመንግሥት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

ዘመዶች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሟቹ ፡ ሀብት ፡ ወራሽነት ፡ ለመንግሥት ፡ ይተላለፋል ።

ቍ ፡ ፰፻፶፫ ። ምትክነት ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) ምትክ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ክፍያ ፡ በትውልድ ፡ አወራረድ ፡ ይፈጸማል ።

(፪) ተተኪ፡ የሆኑት ፡ ልጆች፡ ምትክ ፡ በሆኑበት ፡ ሰው ፡ እግር ፡ ገብተው ፡ በወ ራሽነት ፡ መብቱ ፡ ይሰሩበታል ።

(፫) እነዚህም ፡ ሲሞቱ፡ በዚሁ ፡ ሐሳብ፡ መሠረት ፡ ልጆቻቸው ፡ ምትክ ፡ ሁነው፡ ይገባሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፶፬ ። (፪) ወራሽነትን ፡ የመተው ፡ ሁኔታ ።

(፩) ወራሽ ፡ ሁኖ ፡ ወራሽነትን ፡ አልፈልግም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእርሱ ፡ ተተኪ ፡ ሊገባበት ፡ አይችልም ።

(፪) ነገር፡ ግን፡ ውርሱን ፡ አልፈልገውም ፡ በተባለው ፡ ሰው ፡ ምትክ ፡ ለመግባት፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፶፭ ። ለመውረስ ፡ የማይገባ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

ሟችን፡ መውረስ፡ የማይገባው፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ በእሱ ፡ ተተኪ ፡ ሆነው ፡ የሟች ፡ ወራሽ ፡ መሆን ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፮ ። ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የዝምድና ፡ መተሰሳር ፡ አስፈላጊነት ።**

ምትክ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ከሟቹ ፡ ጋራ ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰር ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምትክ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ኑዛዜ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### የኑዛዜ ፡ ዋጋ ፡ መኖር ፡ ሁኔታዎች ።

### (ሀ) የሥሪ ፡ ነገር ፡ ሁኔታዎች ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፯ ። ኑዛዜው ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ የግል ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ኑዛዜው ፡ የሟቹ ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ ራሱ ፡ የሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ ነው ።

(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በስሙ ፡ አንድ ፡ ኑዛዜ ፡ እንዲያደርግ ፡ እንዲለወጥ ፡ ወይም ፡ እንዲሻር ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ።

(፫) አንድ ፡ ሰው ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ወራሹን ፡ እንዲሁት ፡ እንደሚወስን ፡ ወይም ፡ ለማን ፡ እንደሚተላለፍ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፰ ። የጋራ ፡ ኑዛዜ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ የተናዘዙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኑዛዜው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፱ ። ኑዛዜን ፡ ስለሚመለከት ፡ ቃል ፡ መግባት ።**

(፩) ኑዛዜን ፡ ለማድረግ ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ባንዱ ፡ ሰው ፡ የተደረገ ፡ ቃል ፡ መግባት ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ተናዛዡ ፡ ኑዛዜውን ፡ ሊለውጥ ፡ ወይም ፡ ሊሽር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፷ ። ችሎታ ። (፩) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ኑዛዜ ።**

አካለመጠን ፡ ስላላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ኑዛዜ ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቷል ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፩ ። (፪) በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ።**

በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በ . . . . . . ቍጥር ፡ ተመልክቷል ።

BACK



**ቍ ፡ ፰፻፷፪ ። (፫) የዳኞች ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ስለሆነም ፡ ዳኞች፡ ከእንደዚህ፡ ያለው ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃሎች ፡ ተናዛዡ ፡ በጤናው ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ያላደረጋቸው ፡ የመሰላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ውጤት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያደርጋሉ ።

(፪) ነገር፡ ግን፡ ዋጋው ፡ ከአምስት ፡ ሺሕ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ሊያጸድቁት ፡ አይችሉም ።

(፫) እንዲሁም፡ ደግሞ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወራሽ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ፡ ከውርሱ ፡ ሀብት ፡ ሦስቱን ፡ ሩብ ፡ ማግኘት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፫ ። (፬) የአእምሮ ፡ መጉደል ።**

ከዚህ ፡ እንደሚከተሉት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተናዛዡ ፡ አእምሮ ፡ ጐደሎ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ ኑዛዜው ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ። ይኸውም ተናዛዡ፡ ኑዛዜውን ፡ ባደረገበት ፡ ጊዜ ፡ የታወቀ ፡ ዕብድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፬ ። (፭) በሕግ ፡ የተከለከለ ።**

በሕግ ፡ የተከለከለው ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ፡ ማድረግን ፡ ስለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ሙሉ ፡ ችሎታ ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፭ ። የማይቻል ፡ አፈጻጸም ።**

(፩) አንድ፡ የኑዛዜ፡ ቃል ፡ በሚቢቃ ፡ አኳኋን ፡ ተጠቃሚውን ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡ ካላመለከተ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) አፈጻጸሙም ፡ የማይቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደዚሁ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፮ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆኑ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃላት ።**

አንድ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለሕግ ፡ ወይም ፡ ለመልካም፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፯ ። ኀይል ።**

(፩) በአንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ሟቹ ፡ ያደረገው ፡ በተገዳጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ በኀይል ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፷፰ ። የመንፈስ ፡ መጫን ። (፩) መሠረቱ ።

በአንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በተናዛዡ ፡ ላይ ፡ በአለው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ የመንፈስ ፡ መጫንን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ፈራሽ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፰፻፷፱ ። (፪) ለአስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ለሞግዚት ፡ ጥቅም ፡ የሚደረግ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ።

(፩) ስለሆነም ፡ ለአስተዳዳሪው ፡ ወይም ፡ ለሞግዚቱ ፡ ጥቅም ፡ ሟቹ ፡ ያደረገውን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ዳኞች ፡ እንዲቀንሱ ፡ ወይም ፡ እንዲሽሩ ፡ ተፈቅዷል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ደንብ ፡ ሟቹ ፡ ከሐያ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በፊት ፡ የሞተ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፫) በኑዛዜው ፡ ቃል ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠር ፡ የሟቹ ፡ ወላጅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፰፻፸ ። (፫) ሐኪሞች ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰው ።

(፩) ዳኞች ፡ ሟቹ ፡ ከመሞቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ባሉት ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሕክምና ፡ ወይም ፡ ርዳታ ፡ ላደረጉለት ፡ ሐኪም ፤ ቀዳጅ ፤ አስታማሚ ፤ በሽተኛ ፡ ጠባቂ ፤ ጥቅም ፡ ወይም ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ የሕክምና ፡ ርዳታና ፡ የመንፈስ ፡ ርዳታ ፡ ላደረገ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ያደረገውን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላሉ ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ሐኪም ፡ ማለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታም ፡ ሆነ ፡ ለሟቹ ፡ አንድ ፡ የሕክምና ፡ ርዳታ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ያዘዘ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፫) በኑዛዜው ፡ ቃል ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የሟቹ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፰፻፸፩ ። (፬) ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ምስክሮች ።

ዳኞች ፡ ሟቹ ፡ ለኑዛዜው ፡ አደራረግ ፡ ተሳታፊ ፡ ለሆነ ፡ ለአንድ ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ለተሰጠው ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ለ፩ ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ አስተርጓሚ ፡ ያደረገውን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፸፪ ። (፭) የተናዛዡ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ።

ዳኞች ፡ ሟቹ ፡ በፊት ፡ ካደረገው ፡ ጋብቻ ፡ የተገኙ ፡ ተወላጆች ፡ ያሉት ፡ እንደሆነ ፤ ለኋለኛው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ጥቅም ፡ ያደረገውን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፫ ። (፮) ስለ ፡ ሰዎች ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ።**

ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ ለአንዱ ፡ ተወላጅ ፡ ወይም ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ጥቅም ፡ የተደረገ፡ የኑዛዜን ፡ ቃል ፡ ዳኞች ፡ ሊቀንሱት ፡ ወይም ፡ ሊሽሩት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፬ ። (፯) ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥያቄ ።**

(፩) የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ ሟቹ ፡ ለባል ፡ ወይም ፡ ለሚስት ፡ ጥቅም ፡ ያደረገው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ እንዲቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዲሻር ፡ የማድረጉን ፡ ጥያቄ ፡ የሟቹ ፡ ተወላጆች ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ለዳኞች ፡ ሌሎች ፡ ሊያቀርቡት ፡ አይቻልም ።

(፪) በሌላው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከሌሎቹ ፡ ማናቸውም ፡ ወራሾች ፡ በቀር ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ።

የሟቹ ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ለዳኞች ፡ ሊያቀርቡ ፡ ይችላሉ ።

(፫) በኑዛዜው ፡ ቃል ፡ ተጠቃሚ ፡ የሚሆነው ፡ ሰው ፡ ኑዛዜው ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ጥያቄውን ፡ ካቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በ፫ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ እንዲቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዲሻር ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ካላቀረበ ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፭ ። (፰) ዳኞች ፡ ምክንያቱን ፡ ማስታወቅ ፡ ያለባቸው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ሟቹ ፡ የተናዘዘውን ፡ ቃል ፡ ማፍረስ ፡ ወይም ፡ መቀነስ ፡ ከልቡና ፡ ፍርድ ፡ ከር ትዕ ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ነው ፡ የሚሉበትን ፡ ምክንያት ፡ ዳኞች ፡ በፍርዳቸው ፡ ውስጥ ፡ መግለጽ ፡ ይገባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፮ ፡ ተንኰል ።**

በአንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ቃላት ፡ ተናዛዡ ፡ በተንኰል ፡ ምክንያት ፡ ያደረጋቸው ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ሊሻሩ ፡ አይቻሉም ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፯ ። ስሕተት ።**

(፩) ስሕተት ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ውሎችን ፡ ስለ ፡ መሻር ፡ የተመለከቱት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በአንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ በተናዛዡ ፡ ስሕተት ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊሻር ፡ የሚችለው ፡ ይህ ፡ የተናዛዡ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲያዘነብል ፡ ያደረገው ፡ ስሕተት ፡ በኑዛዜው ፡ አነጋገር ፡ ወይም ፡ ኑዛዜውን ፡ በሚመለከት ፡ በአንድ ፡ የተጻፈ ፡ ሰነድ ፡ ግልጽ ፡ ሁኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፸፰ ። የአንድ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ መሻር ፡ የሚያስከትለው ፡ ነገር ።**

በእርግጠኛ፡ አኳኋን፡ በተናዛዡ፡ መንፈስ፡ ውስጥ ፡ ፈራሽ ፡ በሚሆነው ፡ ቃል፡ አፈጻጸምና ፡ በሌሎቹ ፡ ቃላት ፡ አፈጻጸም ፡ መካከል ፡ አስፈላጊ ፡ የሚያስተሳስር ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ በአንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ መሻር ፡ በዚሁ ፡ ያሉትን ፡ ሌሎች ፡ ቃላት ፡ መሻር ፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፰፻፸፱ ። ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ የውለታ ፡ ቃላትና ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ተናዛዡ ፡ አንድ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታን ፡ በአንድ ፡ ውለታ ፡ የሰጠ ፤ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ግዴታ ፡ ጋራ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ውለታ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ ለሕግ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ይህ፡ ሲሆን፡ ምንም ፡ የውለታው ፡ ወይም ፡ የግዴታው ፡ መፈጸም ፡ ተናዛዡ ፡ ኑዛዜውን ፡ ያደረገበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የኑዛዜው ፡ ስጦታ፡ ፈራሽ ፡ አይሆንም ።

## ለ/ የኑዛዜዎች ፡ ፎርምና ፡ ማስረጃ ።

**ቍ ፡ ፰፻፹ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀይነት ፡ ኑዛዜዎች ።**

ሦስት ፡ ዐይነት ፡ የኑዛዜ ፡ ፎርሞች ፡ አሉ ፤ እነዚሁም ።

(ሀ) በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፤

(ለ) በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፤

(ሐ) በቃል ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፩ ። በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ (፩) ፎርም ።**

(፩) በግልጽ፡ የሚደረገው፡ ኑዛዜ ፡ ተናዛዡ ፡ እየተናገረ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው፡ ወይም ፡ ተናዛዡ ፡ ራሱ ፡ የሚጽፈው ፡ ነው ።

(፪) ኑዛዜው፡ በተናዛዡና ፡ በአራት፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ካልተነበበና ፡ ይኸም ፡ ሥርዐት ፡ ( ፎርማሊቴ ፡ መፈጸሙንና ፡ የተጻፈበትንም ፡ ቀን ፡ የሚያመለክት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) ተናዛዡና፡ ምስክሮቹ፡ በኑዛዜው ፡ ላይ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፊርማቸውን ፡ ወይም ፡ ያውራ ፡ ጣት ፡ ምልክታቸውን ፡ ካላደረጉበት ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፪ ። (፪) ፡ የምስክሮቹ ፡ ብዛት ።**

በግልጽ ፡ ለሚደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ከምስክሮቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ዳኛ ፡ ወይም፡ ውል ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ኑዛዜውም ፡ የተደረገው ፡ ይህ ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ሥራ

BACK



ቸውን ፡ በሚያካሂዱበት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኑዛዜው ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ ሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳፫ ። (፫) የምስክሮቹ ፡ ችሎታ ።

(፩) በግልጽ፡ የሚደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ምስክሮች ፡ አካለመጠንን ፡ ያደረሱና ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ያልተከለከሉ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፪) ምስክሮቹ፡ ኑዛዜው ፡ የተጻፈበትን ፡ ቋንቋ ፡ ለማወቅና ፡ የተጻፈውን ፡ ለመስማት ፡ ወይም ፡ ለማንበብ ፡ ራሳቸው ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፫) እነዚህ ፡ ትእዛዞች ፡ ያልተፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኑዛዜው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳፬ ። በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፤ (፩) ፎርም ።

(፩) በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ተናዛዡ ፡ ራሱ ፡ በሙሉ ፡ ካልጻፈው ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ኑዛዜ ፡ መሆኑ፡ በግልጽ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፫) ኑዛዜው፡ የተደረገባቸው፡ ወረቀቶች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ተናዛዡ ፡ ካልፈረመባቸውና ፡ ቀን ፡ ካልጻፈባቸው ፡ ፈራሾች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳፭ ። (፪) በመኪና ፡ የተጻፈ ፡ ኑዛዜ ።

ተናዛዡ ፡ ያደረገውን ፡ ኑዛዜ ፡ ራሱ ፡ በመኪና ፡ ጽፎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በያንዳንዱ ፡ ቅጠል ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ በእጁ ፡ ጽሕፈት ፡ ካላመለከተው ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳፮ ። (፫)የኑዛዜውን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማወቅ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ተናዛዥ ።

በተናዛዡ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነውን ፡ ኑዛዜ ፡ ተናዛዡ ፡ ያልተማረ ፡ መሐይምን ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ ኑዛዜው ፡ የተጻፈበትን ፡ ቋንቋ ፡ ባለማወቁ ፡ ፍቺውን ፡ በማያውቃቸው ፡ ፊደሎች ፡ የጻፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳፯ ። ኑዛዜው ፡ የተደረገበት ፡ ቀን ።

(፩) በግልጽ፡ ወይም፡ በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ቀኑን ፡ ወሩንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ መግለጫዎች ፡ ከሌሉበት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም፡ በሐሰት ፡ የተጻፈበት፡ ምክንያት ፡ በዝንጋታ ፡ የተደረገ ፡ መሆኑና ፡ ኑዛዜው ፡ የተደረገበት ፡ እውነተኛ ፡ ቀን ፡ በኑዛዜው ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ከሚቹ ፡ በሚገኙት ፡ ሌሎች ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ ረዳትነት ፡ በትክክል ፡ ሊረጋገጥ ፡ የተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኑዛዜ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ፡ የተመለከተው ፡ የቀን ፡ መሳሳት ፡ የኑዛዜውን ፡ መፍረስ ፡ አያስከትልም ።

BACK



**ቍ ፡ ፰፻፹፰ ። ማስረጃ ፡ በመጥቀስ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ።**

ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ኑዛዜና ፡ በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ የኑዛዜውን ፡ ቃል ፡ ለመረዳት ፡ ሚቹ ፡ ያልጻፈውንና ፡ ያልፈረመውን ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ መጥቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፱ ። መፋቅ ፡ መሰረዝና ፡ መደለዝ ።**

(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ኑዛዜና ፡ በተናዛዥ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ የተናዛዡን ፡ ፈቃድ ፡ ለመለወጥ ፡ የሚችል ፡ ፍቀት ፡ ስርዝ ፡ ወይም ፡ ድልዝ ፡ ያለባቸው ፡ ሲሆን ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

(፪) ስለ፡ሆነም፡ የተናዛዡን፡ ሐሳብና ፡ ማንኛዎችንም ፡ ሌሎች፡ አካባቢ፡ነገሮችን፡ በመገመት ፡ ከቀረው ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ የተለየ ፡ ቃል ፡ ለመሆን ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ፍቀት ፡ ስርዝ ፡ ወይም ፡ ድልዝ ፡ የያዘ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) በተናዛዥ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ ሲሆን ፡ ፍቀቱን ፡ ስርዙን ፡ ወይም ፡ ድልዙን ፡ ተናዛዡ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በፊርማው ፡ ያጸደቃቸው ፡ መሆናቸው ፡ ከታወቀ ፡ እንዲሁም ፡ የግልጽ ፡ ኑዛዜ ፡ ሲሆን ፡ ምስክሮቹ ፡ በፊርማቸው ፡ ያጸደቁት ፡ ከሆኑ ፡ ኑዛዜው ፡ ፈራሽነትን ፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፰፻፺ ። ተጨማሪ ፡ ነገሮች ።**

(፩) አንድ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ኑዛዜ፡ በጽሑፍ ፡ ኅዳግ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመሥመሮቹ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ ከምስክሮቹ ፡ ፊርማ ፡ በኋላ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገሮች ፡ ያሉበት ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ኑዛዜ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገሮች ፡ ፈራሽ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፰፻፺፩ ። ኑዛዜን ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።**

(፩) ግልጽ፡ ወይም፡ በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ዘንድ፡ በተለይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በአንድ፡ የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ሊቀመጥ ፡ ይቻላል ።

(፪) ለማዋዋል፡ ሥልጣን፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ኑዛዜው ፡ የተቀመጠላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በየአንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ የያዘ ፡ መዝገብ ፡ ይኖራል ።

(፫) ይኸው ፡ መዝገብ፡ ኑዛዜው ፡ የተሰጠበትን ፡ ቀን ፡ የሚያመለክት ፡ ይሆናል ።

BACK



<u>ቍ ፡ ፲፻፶፱ ። የቃል ፡ ኑዛዜ ፡ (፩) ፎርም ።</u>

(፩) የቃል፡ ኑዛዜ፡ ማለት ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ የሞቱ ፡ መቃረብ ፡ ተሰምቶት ፡ የመጨረሻ ፡ ፈቃድ ፡ ቃሎቹን ፡ ለሁለት ፡ ምስክሮች ፡ የሰጠበት ፡ ነው ።

(፪) የቃል፡ ኑዛዜ፡ ምስክሮች ፡ አካለመጠንን ፡ ያደረሱና ፡ በፍርድ ፡ ወይም፡በሕግ፡ ያልተከለከሉ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷ ። (፪) በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቃል ።</u>

ተናዛዡ ፡ በተለይ ፡ በአንድ ፡ የቃል ፡ ኑዛዜ ።

(ሀ) ለቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚመለከቱትን ፡ ትእዛዞች ፡ ለመስጠት ፤

(ለ) እያንዳንዱ፡ ውርስ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ለመብለጥ ፡ የማይችል ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ለማድረግ ፤

(ሐ) አካለመጠንን፡ ላላደረሱ ፡ ልጆች ፡ አስተዳዳሪን ፡ ወይም ፡ ሞግዚትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፩ ። (፫) ቅጣት ።</u>

(፩) በቃል ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) በአንድ ፡ የቃል ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከ፭፻ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ስጦታ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፪ ። ብዙ ፡ ኑዛዜዎች ።</u>

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ያደረጋቸው ፡ የኑዛዜ ፡ ውሳኔዎች ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ የኑዛዜ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ።

(፪) አብሮ፡ ተፈጻሚዎች፡ ለመሆን ፡ በሚችሉበት ፡ መጠን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ኑዛዜዎች ፡ አብረው ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) የሁለት ፡ ኑዛዜዎችም፡ ቃላት፡ ሁለቱም ፡ ሊፈጸሙ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኋላ ፡ በተደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ቃል ፡ ምርጫ ፡ ይሰጠዋል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፫ ። የኑዛዜው ፡ አስረጂ ። (፩) ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ሰው ።</u>

በኑዛዜው ፡ የሰፈረውን ፡ ቃልና ፡ ኑዛዜው ፡ መኖሩን ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ በዚሁ ፡ ኑዛዜ ፡ ተጠቃሚ ፡ ነኝ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፬ ። (፪) የአስረጂው ፡ ዐይነት ።</u>

(፩) በግልጽ፡ ወይም፡ በተናዛዥ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ የኑዛዜ ፡ መኖር ፡ የሚረጋገጠው ፡ የኑዛዜውን ፡ ጽሑፍ ፡ ዋናውን ፡ በማቅረብ ፡ ወይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥል

ጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ትክ ክለኛ ፡ ሆኖ ፡ በተመሰከረ ፡ አንድ ፡ ግልባጭ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

(፪) ኑዛዜዎቹን፡ ለማስፈጸም፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ለማስረዳት ፡ አይ ቻልም ።

(፫) በጥፋት ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ኑዛዜው ፡ እንዲጠፋ ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሆን ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ኑዛዜ ዎቹን ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

## (ሐ) ስለ ፡ ኑዛዜዎች ፡ መሻርና ፡ ውድቅ ፡ መሆን ።

### ቍ ፡ ፰፻፺፰ ። ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መሻር ።

(፩) ተናዛዡ፡ ኑዛዜዎቹ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ በሚያስፈልገው ፡ ፎርም ፡ ዐይነት ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ በማስታወቅ ፡ ኑዛዜውን ፡ የሻረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኑዛ ዜው ፡ በጠቅላላው ፡ አኳኋን ፡ የሚሻር ፡ ይሆናል ።

(፪) ተናዛዡ፡ እንዲሁ፡ በሆነ ፡ ፎርም ፡ ከአንድ ፡ የኑዛዜ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኑዛዜው፡ በከፊል ፡ የሚሻር ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፰፻፺፱ ። ማጥፋት ፡ ወይም ፡ መሰረዝ ።

(፩) እንደዚሁ፡ ተናዛዡ፡ ኑዛዜውን ፡ ለመሻር ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ በቂ ፡ አድርጎ ፡ በመግለጽ ፡ ዐይነት ፡ ኑዛዜውን ፡ ራሱን ፡ በማጥፋት ፡ ወይም ፡ በመቅደድ ፡ ወይም ፡ የኑዛዜውን ፡ አነጋገር ፡ በመሰረዝ ፡ ኑዛዜውን ፡ ወይም ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ለመሻር ፡ ይች ላል ።

(፪) ተቃራኒ፡ አስረጂ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተናዛዡ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ተግባሮች ፡ አንዱን ፡ የፈጸመ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ኑዛዜውን ፡ ለመሻር ፡ ፍላጎት፡ ያለው፡ መሆኑ ፡ ይገመታል ።

(፫) ተቃራኒ፡ አስረጂ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የኑዛዜው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መሰረዝ ፡ የተናዛዡ ፡ ተግባር ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

### ቍ ፡ ፱፻ ። በኑዛዜ ፡ የተሰጠን ፡ ነገር ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) በኑዛዜ፡ የተሰጠን፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ ከከፊል ፡ ተናዛዡ፡ ፈቅዶ፡ለሌላ፡ ማስተላለፍ ፡ የተደረገውን ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ፈራሽ ፡ ያደርገዋል ።

(፪) ይህ፡ የተላለፈው፡ ነገር ፡ ተመልሶ ፡ ከባለቤቱ ፡ እጅ ፡ ቢገባም ፡ እንኳ ፡ ኑዛ ዜው ፡ በከፊል ፡ እንደ ፡ ተሻረ ፡ ይቀራል ።

<u>ቊ ፡ ፱፻፩ ። የመሻር ፡ ውጤት ።</u>

(፩) ተቃራኒ፡ ቃል፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ያንዱ ፡ ኑዛዜ ፡ መሻር ፡ አስቀድሞ ፡ ተደርጎ ፡ የነበረውን ፡ የኑዛዜውን ፡ ቃል ፡ አያጸድቀውም ።

(፪) በተሻሩት፡ የኑዛዜዎች፡ ቃላት ፡ ምትክ ፡ የገቡት ፡ አዳዲስ ፡ ቃላት ፡ ኑዛዜ ፡ በተደረገለት ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ወይም ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ አልፈልግም፡ በማለት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ፍጻሜ ፡ ለማግኘት ፡ ባይችሉም ፡ እንኳ ፡ የተሻሩት ፡ የኑዛዜ ፡ ቃላት ፡ ተፈጻሚነት ፡ ለማግኘት ፡ አይገባቸውም ።

<u>ቊ ፡ ፱፻፪ ። በቃል ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ ውድቅ ፡ መሆን ።</u>

በቃል ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ ከተደረገበት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ተናዛዡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ ከሆነ ፡ ውድቅ ፡ ነው ።

<u>ቊ ፡ ፱፻፫ ። በተናዛዡ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ ውድቅ ፡ መሆን ።</u>

በተናዛዥ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ ፈራሽ ፡ የሚሆነው ፡ ኑዛዜው ፡ በተደረገ ፡ በሰባት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም፡ፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ያልተቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቊ ፡ ፱፻፬ ። ስለ ፡ ልጅ ፡ መወለድ ። (፩) መሠረቱ ።</u>

(፩) በአንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ስጦታዎች ፡ ምንም ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ ከኑዛዜው ፡ በኋላ ፡ ተናዛዡ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ቢወልድና ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ውርሱን ፡ ለመቀበል ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታዎቹ ፡ ፈራሾች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ከኑዛዜው፡ ቀን፡ በኋላ ፡ የተናዛዡ ፡ ወደ፡ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ የተወለደ ፡ ሆኖ ፡ በምትክነት ፡ ለወራሽነት ፡ ቀርቦ ፡ ይኸንኑ ፡ ውርስ ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ዐይነት ፡ ይፈጸማል ።

<u>ቊ ፡ ፱፻፭ ። (፪) ልዩ ፡ አስተያየት ።</u>

(፩) ስለሆነም፡ ከዚህ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡እንደ፡ ተጠቀሰው ፡ ተናዛዡ ፡ ጉዳዩን ፡ ቢያውቅ ፡ ኑሮ ፡ ስጦታውን ፡ አያስቀርም ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ዳኞች ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጡትን ፡ ኑዛዜ፡ ስጦታዎች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዳሉ ፡ እንዲጸኑ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ ተናዛዡ፡ የወለደው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ወደ፡ታች ፡ የሚቈጠር፡ ተወላጅ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ሦስት ፡ እሩብ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ማግኘት ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፱፻፺ ። ለባል ፡ ወይም ፡ ለሚስት ፡ ተብሎ ፡ የሚደረግ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ።

ሟች፡ ለባል፡ ወይም፡ ለሚስት ፡ ብሎ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ያደረገው ፡ ቃል ፡ ውድቅ ፡ የሚሆነው ፡ ሟቹ ፡ ከባል ፡ ወይም ፡ ከሚስት ፡ ጋር ፡ ያደረገው፡ጋብቻ፡ በመሞት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ የፈረሰ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፺፩ ። የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ (፩) መሠረቱ ።

ለአንድ፡ ሰው ፡ የተደረገ፡ የኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ ውድቅ ፡ የሚሆነው ፡ ኑዛዜ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ከተናዛዡ ፡ በፊት ፡ የሞተ ፡ ወይም ፡ የተደረገለትን፡የኑዛዜ፡ስጦታ፡ ለመቀበል ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ያልፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፺፪ ። (፪) ምትክነት ።

የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ከተናዛዡ ፡ በፊት ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምትክ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) የኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ የሟቹን ፡ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ልዩ፡ ስጦታ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተቀባዩ ፡ ባለመኖሩ ፡ ሀብቱ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚተላለፍ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

በኑዛዜዎቹ ፡ የሰፈረ ፡ ቃልና ፡ የኑዛዜ ፡ ትርጓሜ ።

ቍ ፡ ፱፻፺፬ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የኑዛዜ ፡ ቃላት ።

ተናዛዡ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡—

(ሀ) አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ የጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ ወራሾች ፡ ማድረግ ፤

(ለ) ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ማድረግ ፤

(ሐ) አንድ፡ ወይም፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ወራሾቹን ፡ ከወራሽነት ፡ መንቀል ፡ ወይም፡ አንድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ድርጅት ፡ ማቆም ።

(መ) የቀብሩን፡ ሥነ፡ ሥርዐት ፡ የሚመለከቱ ፡ ትእዛዞችን ፡ መናገር ፡ መጻፍ ፤

(ሠ) ከሞተ፡ በኋላ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ሕጎች ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት፡ ይኖራቸዋል ፡ የሚለውን ፡ የሐሳቡን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፺፲ ። ትርጓሜ ።

(፩) ጥርጣሬ፡ በሚፈጥርበት፡ ጊዜ ፡ በራሱ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በሌሎች፡ አካባቢ ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የተናዛዡ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በተገመተው ፡ መሠረት ፡ ኑዛዜው ፡ መተርጐም ፡ አለበት ።

(፪) ስለ፡ሆነም፡ የኑዛዜው ፡ ቃላት ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተናዛዡ ፡ እውነተኛ ፡ ትክክለኛ ፡ ፈቃድ ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ትርጓሜ ፡ በመስጠት ፡ ከኑዛዜው ፡ ቃል ፡ መራቅ ፡ አይፈቀድም ።

**ቍ ፡ ፱፻፲፩ ። የሕሊና ፡ ግምት ።**

(፩) ተናዛዡ፡ የኔ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ የኔ ፡ ሀብቶች ፡ ወይም ፡ የኔ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሚል ፡ ቃል ፡ ዐይነት ፡ አገላለጽ ፡ ተናዞ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ለነዚህ ፡ ቃላቶች ፡ ተናዛዡ ፡ በሞተበት ፡ ቀን ፡ የነበራቸውን ፡ ፍች ፡ በመመልከት ፡ እንደ ፡ ተናገራቸው ፡ ይገመታል ።

(፪) ስለዚህ ፡ የሕሊና ፡ ግምት ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፱፻፲፪ ። ጠቅላላና ፡ ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ።**

(፩) ጠቅላላ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ፡ ማለት ፡ ተናዛዡ ፡ ሀብቱን ፡ በጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ከመላ ፡ ንብረቱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ በሙሉ፡ ሀብትነት ፡ ወይም ፡ በሌጣ ፡ ርስትነት፡ ለአንድ ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚያወርስበት ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ነው ።

(፪) ማንኛውም፡ ሌላ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፱፻፲፫ ። የኑዛዜ ፡ ስጦታና ፡ የክፍያ ፡ ደንብ ።**

የኑዛዜው፡ ቃል፡ የተናዛዡን፡ ተቃራኒ ፡ ሐሳብ ፡ የሚገልጽ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከውርስ ፡ ሀብት ፡ አንድ ፡ ድርሻን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ንብረትን ፡ ሟቹ ፡ ለወራሾቹ ፡ መስጠቱ ፡ ተራ ፡ የሆነ ፡ የክፍያ ፡ ደንብ ፡ እንጂ ፡ እንደ፡ኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይቈጠርም ።

**ቍ ፡ ፱፻፲፬ ። ስለ ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ ወራሽ ፡ መመረጥ ። (፩) ፎርም ።**

የአንድ ፡ የጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ ተቀባይን ፡ አመራረጥ ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡ ፎርም ፡ መከተል ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፱፻፲፭ ። (፪) ውጤት ።**

(፩) የኑዛዜው፡ ግልጽ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወራሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በኑዛዜ፡ ስጦታ፡ የተደረገላቸው ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችና ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወራሾች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠቅላላውን ፡ ውርስ ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ስለ፡ሆነም ፡ ተናዛዡ፡ ግልጽ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ከውርሱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ በላይ ፡ አያገኝም ፡ ብሎ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ለመግለጽ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፱፻፲፯ ። ገደብ ፡ ያለበት ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ። (፩) መሠረቱ ።</u>

በጠቅላላው፡ ወይም፡ በተለይ ፡ የሚደረጉ፡ የኑዛዜ፡ ስጦታዎች ፡ አንድ ፡ ሁኔታ፡ ሲደርስ ፡ የሚጸኑ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ ሲደርስ ፡ የሚቀሩ ፡ ሁነው ፡ ሊደረጉ ፡ ይቻላል ።

<u>ቍ ፡ ፱፻፲፰ ። (፪) የማግባት ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ማግባት ፡ ገደብ ።</u>

(፩) የኑዛዜ ፡ ስጦታ፡ የተሰጠው ፡ ሰው፡ በተለይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያግባ ፡ ወይም ፡ አያግባ ፡ ተብሎ ፡ የሚደረግ ፡ የኑዛዜ ፡ ገደብ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ።

(፪) በጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ ወራሹ ፡ እንዳያገባ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዳያገባ ፡ የሚያስገድደው ፡ የኑዛዜው ፡ ገደብ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) ስለ፡ሆነም፡ ወራሹ፡ እስከ፡አገባ፡ ወይም፡እንደ፡ገና፡ እስከ፡አገባ፡ ድረስ፡የአንድ፡ የተወሰነ ፡ ሀብትን ፡ ሪም ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ቀለብ ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ፡ የተደረገለት ፡ ያገኛል ፡ ብሎ ፡ ተናዛዡ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፱፻፲፱ ። (፫) የሕሊና ፡ ግምት ።</u>

(፩) የተናዛዡ፡ ግልጽ ፡ የሆነ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የተወሰነውን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳያደርግ ፡ በማለት ፡ በውለታ ፡ የተሰጠ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታውን ፡ በሚያስቀር ፡ ገደብ ፡ ዐይነት ፡ እንደ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ወራሹ፡ የተወሰነውን፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲያደርግ ፡ በማለት ፡ በውለታ ፡ የተሰጠ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ዐይነት ፡ ይቈጠራል ።

<u>ቍ ፡ ፱፻፳ ። (፬) ማረጋገጫዎች ።</u>

(፩) ሟቹ፡ ያደረገው ፡ ኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ ሲደርስ ፡ ስጦታው ፡ ይቀራል ፡ በሚል ፡ ገደብ ፡ አድርጎት ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ይህ ፡ ስጦታውን ፡ የሚያስቀረው፡ ሁኔታ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተሰጠውን ፡ ሀብት ፡ ሊመልስ ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚሆን ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ባለጥቅም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ዳኞች ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለትን ፡ ሰው ፡ ሊያስገድዱት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሟቹ ፡ ያደረገው ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ አንድ፡ሁኔታ፡ሲደርስ ፡ ስጦታው ፡ የሚጸና፡ ይሆናል፡ በሚል፡ ገደብ፡ አድርጎት ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ይህ ፡ ስጦታውን፡ የሚያጸናው ፡ ሁኔታ ፡ የደረሰ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ ሀብት ፡ በእጁ ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ለተደረገለት ፡ ሰውም ፡ ሊያስረክብ ፡ በዚሁ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ በተደረገለት ፡ ሰው ፡ ጥያቄ ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዋስትና፡ እንዲሰጥ ፡ እንዲሁም ፡ ዳኞች ፡ ሊያስገድዱት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፳ ። ግዴታ ። (፩) መሠረቱ ።

ተናዛዡ ፡ ወራሾቹን ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሰዎች ፡ ከሚደርሳቸው ፡ ሀብት ፡ ላይ፡ በተለየ ፡ ለአንድ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲሰጡ፡ ግድ ፡ እንዲሆንባቸው ፡ በኑዛዜው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፳፩ ። (፪) የግዴታው ፡ ወሰን ።

አንድ ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ወራሽ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ስለዚሁ ፡ ግዴታ ፡ አፈጻጸም ፡ በደረሰው ፡ ውርስ ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊገደድ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፱፻፳፪ ። (፫) ስለ ፡ ግዴታው ፡ አፈጻጸም ።

(፩) በግዴታው፡ ተጠቃሚ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የታዘዘለት ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡ በአካባቢው፡ ነገሮች ፡ ምክንያት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ስለ ግዴታው ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሰጠው ፡ ወራሹን ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለትን ፡ ሰው ፡ ተጠቃሚው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) እንደዚሁም፡ ተናዛዡ ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የተመረጠ ፡ ሰው ፡ ባይኖር ፡ ለያንዳንዱ ፡ የሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

ቍ ፡ ፱፻፳፫ ። (፬) ስለ ፡ ኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ መፍረስ ።

(፩) ተናዛዡ፡ ይህንኑ ፡ በግልጽ ፡ ካላመለከተ፡ በቀር ፡ በኑዛዜው ፡ የተወሰነውን፡ ግዴታ ፡ አለመፈጸም ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ አያፈርሰውም ።

(፪) በኑዛዜው ፡ የተሰጠውን፡ ንብረት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያገኙ ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፳፬ ። በኑዛዜው ስጦታ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ስለ፡ መወሰን ።

(፩) በኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ ተጠቃሚው ፡ በሚቃ ፡ አኳኋን ፡ ተወስኗል ፡ የሚለው ፡ ለው ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ ሰው ፡ ወራሹን ፡ ወይም ፡ የጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጠውን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲመረጥ ፡ ኑዛዜው ፡ የሚስገድድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በጉዳዩ ፡ ጥቅም ፡ ባለው ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ጥያቄ ፡ በኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ለሚያስታቀው ፡ ሰው ፡ ምርጫውን ፡ የሚያከናውን በት ፡ ጊዜ ፡ ሊወስኑለት ፡ ይችላሉ ።

(፫) ይህን ፡ ማስታወቅ ፡ ሳያደርግ ፡ የቀረ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ወይም ፡ ለማስታወቅ ፡ እንቢ ፡ ያለ፡እንደ፡ሆነ፡ ዳኞች ፡ የተናዛዡ ፡ ፈቃድ፡ በተሻለ ፡ መጠን ፡ የሚፈጸም፡

በት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በሚገምቱበት ፡ መንገድ ፡ ተጠቃሚውን ፡ የሚመርጥ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፭ ። ለድኾች ፡ የሚደረግ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ።**

(፩) ሌላ ፡ ዝርዝር ፡ ሳይኖርበት ፡ ለድኾች ፡ ጥቅም ፡ የተሰጠ፡ የኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ ዋጋ ያለው ፡ ነው ።

(፪) የኑዛዜውም ፡ ስጦታ፡ ተቃራኒ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተናዛዡ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ በነበረበት ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ በሚገኘው ፡ ቦታ ፡ ላሉት ፡ ደኾች ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይገመታል ።

(፫) በርሱ፡ ጠባቂነት፡ የተናዛዡን ፡ ፈቃድ ፡ ለማስፈጸም ፡ ይህን ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ ለመቀበል ፡ ችሎታ ፡ ያለውን ፡ ባለሥልጣን ፡ ያስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ ይወስናሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፮ ። ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚደረግ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ።**

(፩) ተናዛዡ፡ የያንዳንዱን፡ ድርሻ፡ ምን ፡ እንደ፡ሆን ፡ ሳይለይ ፡ ለሁለት ፡ ወይም፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጠቅላላ ፡ የኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ አድርጎላቸው ፡ እንደ፡ሆን ፡ ወይም፡ አንዱን ፡ ሀብት ፡ ለሁለት ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ አድርጎ ፡ እንደ፡ሆን ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ፡ የተደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ፡ ስጦታ፡ በተሰጠው፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ትክክል፡ የሆነ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) ከነዚህ፡ የኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ ከተደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ለርሱ ፡ የተደረገ ለትን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለመቀበል፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ያልፈቀደ ፡ እንደ፡ሆን ፡ ድርሻው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ለተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ይተላለፋል ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፯ ። በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረት ፡ ስለ፡ መለየት ።**

(፩) በኑዛዜ ፡ የተሰጠ ፡ ስጦታ፡ በሚበቃ ፡ ተለይቷል፡ የሚባለው፡ ወራሹ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ከብዙ ፡ ዕቃዎች ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ግምት ፡ ዋጋ ፡ ካላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ውስጥ ፡ እንዲመርጥ ፡ ኑዛዜው ፡ የወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) የኑዛዜ፡ ወርስ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ምርጫ ፡ የሚያደርገው ፡ ሟቹ ፡ የሚ መርጠውን ፡ ሰው ፡ ባልለየ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ምርጫውን ፡ እንዲያደርግ ፡ የተመ ረጠው ፡ ሰው ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ በወሰነለት ፡ ተገቢ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያላደረገ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፰ ። ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ስለ፡ መተካት ።**

(፩) በጠቅላላ፡ ወይም ፡ በልዩ፡ ሀብት ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ባይ ኖር ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊቀበል ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ተና ዛዡ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

BACK



(፪) ተቃራኒ፡ የኑዛዜ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ለተደረገለት ፡ ሰው ፡ የሚጠቅመው ፡ በማናቸው ም ፡ ሁኔታ ፡ የተመረጠው ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ቀዳሚ፡ የተደረገለት ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ ለመቀበል ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ያልፈቀደ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፳፱ ። ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንደሚተላለፍ ፡ አድርጎ ፡ መተካት ፤ (፩) መሠረቱ ።

(፩) ተናዛዡ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ፡ ጊዜ፡ አልፎ ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ሁኔታ ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፡ ወራሹ ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የውርሱን ፡ ሀብቶች ፡ ወይም ፡ የተወሰኑትን ፡ ሀብቶች ፡ በርሱ ፡ ምትክ፡ ለሚሆኑት ፡ ለአንዱ ፡ ወይም፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ማስተላለፍ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ኑዛዜ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ሀብቱን ፡ በመጀመሪያ፡ የሚቀበል ፡ ወራሽ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ተቀባይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ባለግዴታ ፡ ይባላል ።

(፫) የምትክነቱ፡ ሥራ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ከወራሹ ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ከተደረገለት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ንብረቱን ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ ዋና ፡ ወራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፴ ። (፪) የሚተካው ፡ ሰው ።

(፩) ዋናው ፡ ወራሽ ፡ ሟቹ፡ በሚሞትበት፡ ቀን ፡ ለመቀበል ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

(፪) ለውርስ ፡ መተካቱ፡ ውጤት፡ በሚያገኝበት ፡ ቀን ፡ ለመለየትና ፡ ለመቀበል ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፫) ስለዚህ፡ ወደ፡ ታች ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ለተጣለበት ፡ ሰው ፡ ወራሾች ፡ ለሆኑት ፡ ጥቅም ፡ የተደረገ ፡ የውርስ ፡ መተካት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፴፩ ። (፫) ውጤት ።

(፩) ከዚህ፡ በላይ ፡ ባለው፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሰው ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ በሚመለከተው፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይተላለፍ ፡ እንዳይያዝ ፡ ተብሎ ፡ የሚደረገው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ስምምነት ፡ ዐይነት ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ከዚህ፡ የሚቀጥሉት፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ የዚህን ፡ የኑዛዜ፡ ቃል፡ ውጤት ፡ ለመወሰን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ የጋራ ፡ ሀብትነት ፡ ስለ፡ ሪምና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ በሚመለከተው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች፡ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፴፪ ። (፬) የዳኞችን ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

ግዴታ፡ በተጣለበት፡ ሰው ፡ ወይም፡ ከሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ በሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ጥያቄ ፡ በሚገኘውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ ዳኞች ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ወይም ፡ እንዲያዝ ፡ ለማዘዝ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፱፻፴፫ ። (፭) ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ዋናው፡ ተጠቃሚ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ወይም ፡ ተናዛዡ ፡ የመተካቱን ፡ ሥር ዐት ፡ ለማስፈጸም ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፡ በማይገባ ፡ የተደረገን ፡ መሸጥ፡ መለወጥ፡ ወይም ፡ መያዝ ፡ እንዲፈርስ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የመተካቱ፡ ሥርዐት፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በሚከተለው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ክሳቸውን ፡ ቢያቀርቡ ፡ በቂ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፱፻፴፬ ። (፮) በመተካት ፡ ጕዳይ ፡ በአንድ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) ተናዛዡ፡ ዋና፡ ወራሽ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ሀብቶቹ ፡ ወይም ፡ መብቶቹ ፡ ከተላ ለፉ ፡ በኋላ ፡ የማይሸጡ ፡ የማይተላለፉ ፡ ወይም ፡ የማይያዙ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ የሚያገባው ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም፡ ዋና፡ ወራሽ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ሀብቶቹ ፡ ወይም ፡ መብቶቹ ፡ከተ ላለፉ ፡ በኋላ ፡ የነዚሁ ፡ ሀብቶች ፡ ወይም ፡ መብቶች ፡ ሁኔታ ፡ የሚወሰንበት ፡ ኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፱፻ ፡ ። (፯) በኑዛዜ ፡ ግዴታ ፡ የተጣልበት ፡ ሰው ፡ እንቢታ ።**

የኑዛዜው፡ ተቃራኒ፡ ቃል፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ሲሰጠው ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ሰው ፡ ስጦታውን ፡ ለመቀበል ፡ ያልቻለ፡ወይም፡ያልፈለገ ፡ ሲሆን ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ የኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ የሚደርሰውን ፡ ሰው ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲ ቀርብ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፱፻፴፮ ። (፰) በምትክ ፡ እንዲቀርብ ፡ የተጠራው ፡ ሰው ፡ አለመቅረብ ።**

(፩) ባለግዴታው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲያስተላልፍ ፡ ተደርጎ ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ የሚ ጸናባቸውን ፡ ንብረቶችና ፡ መብቶች ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ከሱ ፡ በምትክ ፡ የሚቀበለው ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ምክ ንያት ፡ በምትክነቱ ፡ ሥርዐት ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በነዚሁ ፡ ሀብቶችና ፡ መብቶች ፡ በኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ፈለገው ፡ ሊያዝባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) የሚተካው ፡ ሰው ፡ በአለመቅረብ፡ ወይም ፡ እንቢ ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ በማ ናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ተናዛዡ ፡ አስቦት ፡ የነበረው ፡ መተካት ፡ ሊፈ

ጸም ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምትክ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ እንዲያውተላለፍ ፡ የተ
ሰጡት ፡ ንብረቶች ፡ በዋናው ፡ ወራሽ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ወራሾች ፡ ይተላለፋሉ ።

(፫) በኑዛዜው ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የተናዛዡ ፡ ወራሾች ፡ በነዚህ ፡ ንብ
ረቶች ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ መብት ፡ አይኖራቸውም ።

ቍ ፡ ፱፻፴፪ ። ከወራሽነት ፡ መንቀል ። (፩) ግልጽ ፡ ኑዛዜ ።

(፩) ተናዛዡ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ የውርስ ፡ ስጦታ ፡ የሚያደርግለትን ፡
ሳይጠቅስ ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ የሚወርሱትን ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ አንዱን ፡ ግልጽ ፡
በሆነ ፡ ቃል ፡ ከወራሽነት ፡ ለመንቀል ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ ሲሆን ፡ የተነቀሉት ፡ ወራሽ ፡ ወይም ፡ ወራሾች ፡ ከተናዛዡ ፡ በፊት ፡
እንደ ፡ ሞቱ ፡ ተቈጥረው ፡ የውርሱ ፡ ሥርዐት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፱፻፴፫ ። (፪) ወደ ፡ ታች ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ።

(፩) ተናዛዡ ፡ ከርስት ፡ ከውርስ ፡ ለመንቀል ፡ የደረሰበትን ፡ ምክንያት ፡ በኑዛዜው ፡
ውስጥ ፡ ካልገለጸ ፡ በቀር ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጁን ፡
ከውርስ ፡ ቢነቅል ፡ አይጸናም ።

(፪) ተናዛዡ ፡ ወራሹን ፡ ከውርስ ፡ ለመንቀል ፡ የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ትክክል ፡
(እውነት) ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቈጥሮ ፡ ዳኞች ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ከውርስ ፡(ከርስት) ፡
ለመንቀል ፡ የሚያበቃ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ይመረምራሉ ።

(፫) ዳኞች ፡ ተናዛዡ ፡ በኑዛዜው ፡ ያስታወቀው ፡ ምክንያት ፡ ትክክል ፡ (እውነት) ፡
መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ መመርመር ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፱፻፴፬ ። (፫) በዝምታ ፡ ከውርስ ፡ መንቀል ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ዘመዶቹ ፡ የሁለተኛ ፡ የ፫ኛ ፡ ወይም ፡
የአራተኛ ፡ ደረጃ ፡ ዝምድና ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ ተቃራኒ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡
በቀር ፡ የጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ማድረግ ፡ የሟቹን ፡ ዘመዶች ፡ ወራሽነት ፡
መንቀሉን ፡ ያስከትላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የሟቹን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ የተወላጆች ፡ ከወራሽነት ፡
መንቀልን ፡ አያስከትልም ።

(፫) ሟቹ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ኖሮትና ፡ ከወራሽነት ፡ በግልጽ ፡
ያልነቀላቸው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኑዛዜ ፡ የጠቅላላ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡
ሰው ፡ እንደ ፡ ሟቹ ፡ ልጅ ፡ ተቈጥሮ ፡ ከነዚሁ ፡ ከተባሉት ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ከሚ
ቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ጋራ ፡ በውርሱ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵ ። (፬) አንዳንድ ፡ የውል ፡ ቃላትን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

የኑዛዜውን ፡ ወይም ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የአንድ ፡ ቃል ፡ መጽደቅ፡ የተቃወሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወራሾቹን ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱን ፡ በሙሉ፡ወይም ፡ በከፊል ፡ ከወራሽነት ፡ ነቅየዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናዛዡ ፡ የሚያስታውቅበት ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፩ ። የግልግል ፡ ቃል ።**

የውርስ ፡ ሀብት ፡ ስለ ፡ ማጣራት፡ (ማስላት)፡ ወይም ፡ ስለ፡ ማካፈል ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ከወራሾቹ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ በተደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል፡ የሚደረገው ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ ኑዛዜው ፡ እንደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኞች ፡ አድርጎ ፡ በሚመርጣቸው ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚወሰን ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ሟቹ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ቃል ፡ ለማግባት ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ወራሽነትን ፡ ስለ ፡ ማጣራት ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፪ ። መሪ ፡ ሐሳብ ።**

ውርሱም ፡ እስከ ፡ ተጣራ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ተለየ ፡ ንብረት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፫ ። ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚሆን ፡ መያዣ ፡ (ዋስትና) ።**

(፩) ከውርሱ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የገንዘብ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለገንዘባቸው ፡ ዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሚሆናቸው ፡ በመጣራት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ንብረት ፡ ነው ።

(፪) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በወራሾቹ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

(፫) ከወራሾቹ ፡ ከራሳቸው፡ ላይ ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ የውርሱ ፡ ሀብት ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ በውርሱ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፬ ። በማጣራቱ ፡ ሥራ ፡ ስለሚፈጸመው ።**

ውርሱን ፡ ማጣራት ፡ ማለት ፡—

(ሀ) የውርሱን ፡ ተቀባይ ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ መወሰን ።

(ለ) የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ መወሰን ፤

(ሐ) ለውርሱ፡ የሚከፈለውን፡ ገንዘብ ፡ መቀበል ፡ ለመክፈል ፡ አስገዳጅ ፡ የሆነውን ፡ ዕዳ ፡ መክፈል ፤

(መ) ሟቹ ፡ በኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ ላደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሰጣቸውን ፡ መክፈል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፭ ። የግልግል ፡ ቃል ።**

ወራሾችና ፡ በኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ የተደረገላቸው፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ውርሱ፡ ማጣራት፡ ወይም ፡ መካፈል ፡ ጕዳይ ፡ በመካከላቸው፡ በሚደረገው ፡(በሚሆነው)፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ የዘመድ ፡ አስታራቂ ፡ ዳኞች ፡ እንዲያዩት ፡ ስም ምነት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ውርሱ ፡ አጣሪ ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፮ ። መሠረቱ ።**

ያለ ፡ ኑዛዜ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ፡ የሆነ ፡ ውርስ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ አጣሪ ፡ ተብሎ፡ በተመረጡ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚጣራ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፯ ። በሕግ ፡ ስለ ፡ መመረጥ ።**

ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወራሾች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሰውዮው ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ አን ሥቶ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ፎርማሊቴ ፡ የአጣሪነት ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፰ ። በኑዛዜ ፡ ስለ ፡ መመረጥ ።**

(፩) ሟቹ ፡ አንድ ፡ ኑዛዜ፡ የተወ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሟቹ ፡ በዚሁ ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ የኑዛዜው ፡ አስፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፡ የአጣሪነት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) አንድ ፡ ግልጽ፡ የሆነ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተ ደረገለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሰዎች ፡ ያላንዳች ፡ ፎርማሊቴ ፡ የአጣሪነት ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

(፫) አንድ፡ የኑዛዜ፡ አስፈጻሚን ፡ የሚመርጥ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የሚደረግለትን ፡ ሰው ፡ የሚያመለክት ፡ ኑዛዜ ፡ መገኘት ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወራሽ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ የአጣሪነት ፡ ሥራ ፡ የሚያስቀረው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፱ ። አካለመጠንን ፡ ያላደረሰ ፡ ወይም ፡ የተከለከለ ፡ አጣሪ ።**

አንድ ፡ አካለመጠንን ፡ ያላደረሰ፡ ልጅ ፡ ወይም፡ አንድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ቃላት ፡ መሠረት ፡ የውርሱ ፡ አጣሪ፡ የሆነ፡እን ደሆነ ፡ ስለ፡ሥራው ፡ አካሄድ ፡ ሞግዚቱ ፡ ወኪሉ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፱፻፶ ። በፍርድ ፡ የሚጣራ ፡ ውርስ ። (፩) ይገባኛል ፡ ባይ ፡ የሌለው ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ጠያቂ ፡ የሌለው፡ ውርስ ።**

(፩) ወራሾቹ፡ የማይታወቁ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ ወራሽ ፡ የሚ ሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ ውርሱን ፡ ለማጣራት ፡ የማይፈቅዱ ፡ መሆናቸውን ፡

ገልጸው ፡ ያስታወቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ አንድ ፡ አጣሪ ፡ ይሾማሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ ተናዛዡ፡ ወራሾቹ ፡ ያልተዉና ፡ ውርሱም ፡ መንግሥት ፡ የሚወርሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ አንድ ፡ አጣሪ ፡ ይሾማሉ ።

(፫) እንዲህ፡ ሲሆን፡ የአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ ደንቦች ፡ በዳኞች ፡ አጣሪ ፡ ሆኖ፡ የሚመረጠውን፡ ሰው ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ማን ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ይወስናሉ ።

## ቍ ፡ ፱፻፷፩ ። (፪) ሌሎች ፡ ሁኔታዎች ።

ዳኞች ፡ በማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ጥያቄ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተውን ፡ አጣሪ ፡ ለመተካት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለመምረጥ ፡ የሚችሉት ፤

(ሀ) ሒሳብ፡ አጣሪውን፡ የመረጠው፡ ኑዛዜ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ የሚያከራክር ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪውን፡ በመለየት ፡ ላይ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነገር ፡ ሲኖር ፤

(ለ) ብዙ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ኖረው ፡ ውርሱን፡ ለማስተዳደርና ፡ ሒሳቡን ፡ ለማጣራት ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በወራሾቹ፡ መካከል ፡ አንዱ፡ አካለመጠን፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ፡ወይም ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ጥቅሙን ፡ ለመከላከል ፡ የማይችል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፤

(መ) የወርሱ፡ አስተዳደር፡ ወይም ፡ ማጣራቱ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ችግር ፡ ያስነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) አጣሪው፡ ትጉህ ፡ ያልሆነ፡ ወይም ፡ ሐቀኛ ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ፡ ለመፈጸም፡ ችሎታ፡ የሌለው፡ መሆኑ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፱፻፷፪ ። ዋስ ።

ዳኞች ፡ በማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ጥያቄ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሥራው፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ፡ መያዣ ፡ እንዲሰጥ ፡ አጣሪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

## ቍ ፡ ፱፻፷፫ ። ሥራው ፡ የፈቃድ ፡ ሥራ ፡ ስለ፡መሆኑ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ የአጣሪነት ፡ ሥራዎችን ፡ እንዲቀበል ፡ አይገደድም ።

## ቍ ፡ ፱፻፷፬ ። ከሥራው ፡ ስንብት ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።

(፩) አጣሪው፡ ሥራውን፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ወይም ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ለመሥ

ራት ፡ በግልጽ ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን፡ ለመተው ፡ ይችላል ።

(፪) የሥራው ፡ መተው፡ በማይገባ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የአጣሪውን፡ ኣላፊነት ፡ ያስከትላል ።

(፫) በማናቸው ም ፡ ሁኔታ ፡ ሌሎች ፡ አጣሪዎች ፡ ካልተነገረ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ አጣሪ ፡ ካልተመረጠ ፡ የአጣሪው ፡ ሥራዩን ፡ ትቻለሁ ፡ ማለት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፱፻፶፩ ። የሥራው ፡ መቅረት ።

(፩) የአጣሪው፡ ሥራ፡ የሚቀረው ፡ አጣሪው ፡ በሕጉ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ወይም ፡ በዳኞች፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ በአንድ ፡ አዲስ፡ አጣሪ ፡ የተተካ ፡ እንደ፡ሆነ፡ ነው።

(፪) እንዲሁም፡ የአጣሪው፡ ሥራ ፡ የሚቀረው ፡ አጣሪው ፡ ሥራውን ፡ ፈጽሞ ፡ አሠራሩን ፡ የሚያመለክት ፡ ሒሳብ ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፶፪ ፡ የአጣሪው ፡ ሥራ ።

(ሀ) ሟቹ ፡ አንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ትቶ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ መፈለግና ፡ በመጨረሻው ፡ ውርሱ ፡ የሚደርሳቸው ፡ ሰዎች ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ ማረጋገጥ ።

(ለ) የውርሱን ፡ ሀብት ፡ ማስተዳደር ፤

(ሐ) መክፈያቸው ፡ የደረሰውን ፡ የውርስ ፡ ዕዳዎች ፡ መክፈል ።

(መ) ማቹ ፡ በኑዛዜ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ስጦታዎች ፡ መክፈልና ፡ የኑዛዜውን ፤ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ ማንኛቸውም ፡ ሌሎች ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፱፻፶፫ ። የሥልጣን ፡ ወሰን ።

(፩) ሟቹ፡ ወይም፡ ዳኞች ፡ የአጣሪውን ፡ ሥልጣን ፡ ለመወሰን ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ እንዴት ፡ እንደሚፈጽም ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ዳኞች፡ ልዩ፡ ምክንያት ፡ ካገኙ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃለ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለመለወጥ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ማናቸው ም፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ተቃራኒ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባሉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ አለመተላለፍ ፡ የሚያስከትለው ፡ የአጣሪውም ፡ ኋላፊነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፶፬ ። ብዙ ፡ አጣሪዎች ።

(፩) ብዙ፡ አጣሪዎች፡ ያሉ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከሟቹ ፡ ወይም፡ ከዳኞች ፡ የተሰጠ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ ብዙ ፡ አጣሪዎች ፡ ያሉ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እነዚሁ ፡ በመተባበር፡ መሥራት ፡ አለባቸው ።

(፪) አጣሪዎቹ፡ በማጣራት፡ ያሉትን ፡ ሥራዎች ፡ መከፋፈል ፡ ወይም፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በመወከል ፡ ይህን ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ እንዲሠራ ፡ ሊያደርጉ ፡ ይችላሉ ።

(፫) የነዚህ፡ ዐይነት፡ ቃላት ፡ ወይም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ውክልና ፡ የሌለ ፡ ሁኖ ፡ እንደ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ ብቻውን፡ የማጣራቱን ፡ አንዱን፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የተሰጡት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፶፱ ። የአጣሪው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ።**

አጣሪው ፡ በሟቹ፡ በተወሰኑት፡ ሁኔታዎች ፡ (ውለታዎች) ፡ መሠረት ፡ ወይም፡ በወራሾቹ ፡ ወይም፡ በዳኞቹ ፡ መካከል ፡ በተደረገ ፡ ስምምነት ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የሚያረጋግጥለት ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፱፻፷ ። የሥራውን ፡ ክንውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያመለክት ፡ ራፖር ።**

(፩) ሒሳብ፡ አጣሪው፡ ሥራውን ፡ ሲጨርስ ፡ ወራሾች ፡ ለሆኑት ፡ የሥራውን፡ ክንውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያመለክት ፡ ራፖር ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም፡ በማናቸውም፡ ዐይነት ፡ ሟቹ ፡ ከሞተ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከወራሾቹ ፡ ጋራ ፡ በስምምነት ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ በወሰኑት ፡ ቀን ፡ የሥራውን ፡ ክንውን ፡ በራፖር ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፩ ። አላፊነት ።**

(፩) ሒሳብ፡ አጣሪው ፡ በጥፋቱ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነቱ ፡ ለሚያደርጋቸው ፡ ጉዳዮች ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ማናቸውም፡ ለሕጉ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ ለኑዛዜው ፡ ወይም ፡ በዳኞች ፡ለሱ፡ የተሰጡትን ፡ ትእዛዞች ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጥፋት ፡ ይቈጠራል ።

(፫) ዳኞች፡ አጣሪው ፡ ከወራሾቹና ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፡ በሚደረስበት ፡ አላፊነት ፡ ሥራዎቹን ፡ ለመፈጸም ፡ በማሰብ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያደረገ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ አላፊነት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ነጻ ፡ ሊያደርጉት ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## መብት ፡ አለኝ ፡ ባዮችን ፡ ቍርጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### የወራሾቹን ፡ ሁኔታ ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፪ ። ኑዛዜውን ፡ ስለ ፡ መፈለግ ።**

(፩) ሒሳብ፡ አጣሪው፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ሟቹ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ትቶ ፡ እንደ፡ሆነ፡ መፈለግ ፡ አለበት ።

(፪) ሒሳብ፡ አጣሪውም፡ ይህን ፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሟቹን ፡ ጽሑፎች ፡ ይመረምራል ፡ እንዲሁም ፡ ሟቹ ፡ በኖረበት ፡ ቦታ ፡ በሚገኙት ፡ በሕግ ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ከተሰጣቸው ፡ ዘንድና ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ ፍለጋዎችን ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፫ ። ኑዛዜውን ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ሟቹ ፡ ያደረገውን ፡ አንድ ፡ ኑዛዜ፡ በእጅ ፡ የያዘ ፡ ያገኘ ፡ ወይም ፡ ምስክር ፡ በመሆን ፡ ያወቀ ፡ ሰው ፡ ወዲያው ፡ የሟቹን ፡ መሞት ፡ እንዳወቀ ፡ ለሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) ኑዛዜውን፡ የሚያፈርስ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ መስሎ ፡ ቢታየውም ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፬ ። ኑዛዜወን ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።**

(፩) በግልጽ ፡ወይም፡ በሟቹ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ኑዛዜ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ ወይም፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ባለጕዳይ ፡ ጥያቄ ፡ ያደረገ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ኑዛዜው፡ በተገኘበት፡ ወይም ፡ በኖረበት ፡ ቦታ ፡ ባለው ፡ በሕግ ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ወዲያውኑ ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ።

(፪) በቃል፡ የሆነ ፡ ኑዛዜ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የኑዛዜ ፡ ምስክር ፡ በሆኑ፡ ሰዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፭ ። ስለ ፡ ኑዛዜ ፡ መከፈት ፡ (፩) ቀን ።**

(፩) ሟቹ፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ በአርባው፡ ቀን፡ አጣሪው፡ የሟቹን ፡ ኑዛዜ ፡ ይናገራል ።

(፪) ከዚህ፡ ጊዜ፡ በኋላ፡ ኑዛዜ ፡ የተገኘ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የተገኘበትን ፡ ቀን ፡ በሚከተለው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ይነበባል ።

(፫) እንዲሀ፡ ሲሆን፡ ከዚህ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ አስቀድሞ ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ይቀመጣል ።

BACK



ቍ ፡ ፱፻፷፯ ። (፪) አስቀድሞ ፡ የሚደረግ ፡ የኑዛዜ ፡ መከፈት ።

(፩) ሟቹ፡ ከዚዘ፡ ወይም ፡ ለቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ዝግጅት ፡ ጕዳይ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ መጀመሪያ ፡ ወራሾች ፡ የሆኑት ፡ ኑዛዜው፡ የሚነገርበትን ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ለማድረግ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የተስማሙበት ፡ እንደሆነ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በ፩ኛው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ከተመለከተው ፡ ቀን ፡ ቀደም ፡ ሊል ፡ ይችላል ።

(፪) መጀመሪያ፡ ወራሾች፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለሚነገረው ፡ ኑዛዜ ፡ ለመገኘትና ፡ እንደራሴ፡ ለማድረግ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የኑዛዜው ፡ ጽሑፍ ፡ አስቀድሞ ፡ ከመነገሩ ፡ በፊት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ባለው ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፱፻፷፯ ። (፫) ቦታ ።

(፩) ሟቹ፡ በሕይወት፡ ሳለ ፡ ወይም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ኑዛዜው ፡ በተቀመጠበት ፡ ቦታ ፡ ባለው ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ኑዛዜው ፡ ይከፈታል ።

(፪) ይህ ፡ ማስቀመጥ፡ አልተደረገ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኑዛዜው ፡ የሚከፈተው ፡ ሟቹ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፷፰ ። (፩) ማስታወቂያ ።

(፩) ስለ፡ ሟቹ ፡ ውርስ፡ ያለ፡ኑዛዜ፡ ወራሽ፡ የሆኑትና ፡ በመጀመሪያ፡ ሕጉ ፡ የሟቹ፡ ወራሾች ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ኑዛዜው ፡ ሲነበብ ፡ እንዲገኙ ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ እንዲልኩ ፡ ይጠራሉ ።

(፪) በማናቸው ም፡ አኳኋን፡ ኑዛዜው ፡ ሲፈስ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ አራት ፡ አካለመጠንን ፡ ያደረሱና ፡ ያልተከለከሉ ፡ ሰዎች ፡ መገኘት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፱፻፷፱ ። (፭) የዕለት ፡ ሥራ ፡ ተግባር ።

(፩) ኑዛዜው ፡ በሚፈስበት፡ ጊዜ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ና ፡ ቀርበው ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች፡ ሁሉ ፡ የኑዛዜውን ፡ ፎርምና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ይመረምራሉ ።

(፪) የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ ይነበባል ።

(፫) ኑዛዜውን ፡ ለማስቀመጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ዝግጅቶች ፡ ይደረጋሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፸ ። (፮) ብዙ ፡ ኑዛዜዎች ።

ሟቹ ፡ አንድ ፡ ኑዛዜ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ኑዛዜዎች ፡ ቢተውም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፱፻፸፩ ። የክፍያ ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ፤ (፩) የኑዛዜ ፡ ውርስ ።**

(፩) ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ወዲያውኑ ፡ የሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ በኑዛዜው ፡ በውርስ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ሆኑና ፡ የያንዳንዱም ፡ የወርስ ፡ መብት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያስታውቃል ።

(፪) ሒሳብ ፡ አጣሪውም ፡ ወዲያውኑ ፡ ወርሱ ፡ እንዴት ፡ እንደሚከፋፈል ፡ ለባለ ጕዳዮቹ ፡ ያስታውቃል ።

(፫) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ባለጕዳዮች ፡ ማለት ፤ የሟቹን ፡ ሀብቶች ፡ እንዲቀበሉ ፡ የተጠሩ ፡ ሰዎችና ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ባይኖር ፡ ኑሮ ፡ ሀብቶችን ፡ እንዲወስዱ ፡ ይጠሩ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፸፪ ። (፪) ሳይናዘዝ ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ውርስ ።**

(፩) እንዲሁም ፡ ሟቹ ፡ የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ አለመተው ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ የወርሱ ፡ አደራረግ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ያቀደውን ፡ የአከፋፈል ፡ ዐይነት ፡ ለባለጕዳዮቹ ፡ ያስታውቃል ።

(፪) ይህም ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚነገረው ፡ የኑዛዜው ፡ አለመኖር ፡ እርግጥ ፡ መስሎ ፡ እንደ ፡ ታየ ፡ ወዲያውኑና ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ ሟቹ ፡ ካረፈ ፡ ከአርባ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፸፫ ። ኑዛዜው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ክስ ፤ (፩) ኑዛዜው ፡ ሲነገር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ።**

(፩) ኑዛዜው ፡ ሲነበብ ፡ የነበሩ ፡ ወይም ፡ የተወከሉ ፡ ሰዎች ፡ ኑዛዜው ፡ አይጸናም ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ በኑዛዜው ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ አይጸናም ፡ በማለት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ያሳቸውን ፡ ሐሳብ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ክፍያው ፡ በሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ የቀረበወን ፡ የድልድልን ፡ አመዳደብ ፡ አሳብ ፡ ለመቃወም ፤ ኑዛዜው ፡ ከተነበበበት ፡ እንሥቶ ፡ የሚቈጠር ፡ የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ አላቸው ።

(፪) ይህ ፡ መግለጫ ፡ በጽሑፍ ፡ ካልሆነና ፡ ለአጣሪው ፡ ወይም ፡ ለዳኞች ፡ ወይም ፡ በወርሱ ፡ ላይ ፡ የተነሣውን ፡ ነገር ፡ ለመጨረስ ፡ ለተመረጡት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዲደርስ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ አይጸናም ።

(፫) ይህ ፡ መግለጫ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ጥያቄውን ፡ (ክሱን) ፡ ለዳኞች ፡ ወይም ፡ ለሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

**ቍ ፡ ፱፻፸፬ ። (፩) ኑዛዜው ፡ ሲነበብ ፡ ያልነበሩ ፡ ሰዎች ።**

(፩) በኑዛዜው ፡ ንባብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሳልነበሩ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜው ፡ ንባብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በወኪልነት ፡ ሳልሰሙ ፡ ሰዎችና ፤ እንዲሁም ፤ ኑዛዜው ፡ በሌሉበት ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠርበት ፡ መነሻ ፡ አጣሪው ፡ ስለ ፡ ክፍያው ፡ የድልድል ፡ አመዳደብ ፡ አሳቡን ፡ ከነገራቸው ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) ኑዛዜ፡ ከፈሰሰበት፡ ጊዜ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፤ ወይም ፡ ኑዛዜ ፡ የሌለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ሟቹ ፡ ከሞተ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት፡ በኋላ ፡ ስለኑዛዜው ፡ መጽናትና ፡ ስለ ፡ ከፍያው ፡ አመዳደብ ፡ አጣሪው ፡ ያቀረበው ፡ የድልድል ፡ አሳብ ፡ በማናቸውም ፡ አስተያየት ፡ ቢሆን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊቀርብበት ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፸፫ ። (፫) ለጊዜው ፡ የሚደረጉ ፡ ጥንቃቄዎች ።</u>

ዳኞቹ ፡ አንድ ፡ ባለጕዳይ ፡ ሲጠይቅና ፤ በቀዳሚዎቹ ፡ ቍጥሮች ፡ ለተመለከቱት ፡ ጥያቄዎች ፡ ፍርድ ፡ እስኪሰጣቸው ፡ ድረስ ፡ የወራሽነቱ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዳይዘገይ ፤ አስፈላጊዎች ፡ መስለው ፡ የታዩዋቸውን ፡ ለጊዜው ፡ የሚሆኑ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

<u>ስለ ፡ ወራሾችና ፡ ጠቅላላ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡</u>

<u>ስለ ፡ ሚያደርጉት ፡ ምርጫ ።</u>

<u>ቍ ፡ ፲፻፸፬ ። የአስፈላጊዎቹ ፡ ወራሾች ፡ አለመኖር ።</u>

ማናቸውም ፡ ወራሽ ፡ እንዲወርስ ፡ የተጠራበትን ፡ ውርስ ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለትን ፡ ለመቀበል ፡ አይገደድም ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፸፭ ። ምርጫው ፡ የግል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።</u>

(፩) ወራሽነትን፡ የመቀበል፡ ወይም ፡ አልቀበልም ፡ የማለቱ ፡ ፈቃድ ፡ የወራሹ ፡ የራሱ ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ በተባለው ፡ መብት፡ ከወራሹ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ሊሠሩበት ፡ አይችሉም ።

(፫) ከወርሱ፡ ላይ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁትን ፡ ሰዎች፡ መብት፡ለማጭበርበር፡ወራሹ፡ ወርሱን ፡ አልቀበልም ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፸፮ ። ወርስን ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ።</u>

(፩) ወራሹ ፡ ወርሱን ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ የተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ወራሽ ፡ መሆኑን ፡ አጣሪው ፡ ካስታወቀው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ነው ።

(፪) ዳኞቹ ፤ ወራሹ፡ ባቀረበው፡ ጥያቄ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፤ የተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ሊያረዝሙት፡ ይችላሉ ።

BACK



ቍ ፡ ፱፻፸፱ ። የአልቀበልም ፡ ባይነት ፡ አደራረግ ።

(፩) በኑዛዜው ፡ አልስማማም፡ ባይነት ፡ በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፤ አልቀበልም፡ ባይነቱ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተወሰ ነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ ለአጣሪው ፡ ካልተነገረ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፹ ። የመቀበሉ ፡ አደራረግ ።

ወራሽነትን ፡ መቀበል ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፩ ። በግልጽ ፡ የሚሆን ፡ ተቀባይነት ።

በወራሹ ፡ በኩል ፡ በግልጽ ፡ የሚሆን ፡ የወራሽነት ፡ መቀበል ፡ ወራሹ ፡ ወራ ሽነቱን ፡ በጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ ሲቀበል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፹፪ ። በዝምታ ፡ የሚሆን ፡ ተቀባይነት ።

(፩) በዝምታ፡ ወራሽነትን፡ ተቀብሏል ፡ የሚባለው ፡ ወራሹ ፡ በማያሻማ ፡ ዐይነት ፡ ወራሽነቱን ፡ የመቀበል ፡ አሳብ ፡ የሚገልጽ፡ ተግባር፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ነው።

(፪) እንዲሁም፤ ወራሹ፡ በሕግ ፡ በተፈቀደለት ፡ ጊዜ ፡ ው ስጥ ፡ ወራሽነቱን ፡ አል ቀበልም ፡ ያላለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውርሱን ፡ በዝምታ ፡ ተቀብሏል ፡ ይባላል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፫ ። ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ወራሽነቱን ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።

(፩) ተለይተው ፡ለተነገሩ፡ ለአንድ ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ተብሎ ፡ ወራሽነቱን ፡ መልቀቅ ፡ ማለት ፡ የወራሽነትን ፡ መብት ፡ እንደ፡መተው፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በዚህ፡ ዐይነት፡ ወራሽነቱን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ የለቀቀ ፡ ወራሽ ፡ ወራሽ ነቱን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) ወራሹ፡ ለእገሌ፡ ብሎ ፡ ሳይለይ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወራሾች ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ድርሻውን ፡ የለቀቀ ፡ እንደ፡ሆነና ፡ ለዚሁም ፡ መቻቻያ ፡ ገንዘብ ፡ ያልተ ቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውርሱን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፱፻፹፬ ። የአጠባበቅ ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ ተግባሮች ።

ወራሹ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ፡ ስለሚገኙ ፡ ንብረቶች፡ የፈጸማቸው ፡ እንደ፡ ጥበቃ ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ማደራጀትን ፡ የመሰሉ ፡ የአጠባበቅ ፡ ተግ ባሮች ፡ እና ፡ አስቸኳዮች ፡ የሆኑ ፡ የአስተዳደር ፡ ተግባሮች ፡ ወራሹን ፡ ውር ሱን ፡ በዝምታ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ አያስቈጥሩትም ።

ቍ ፡ ፱፻፹፭ ። በውርሱ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መደበቅ ።

ወራሹ ፡ በውርሱ ፡ ው ስጥ ፡ ባለ ፡ ንብረት ፡ መጠቀም ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ መደበቅ ፤ ወራሽነትን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ያስቈጥረዋል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፩ ። ምርጫውን ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሚያደርገው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ወራሾቹ ፡ ብዙ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ውርሱን ፤ አንዳንዶቹ ፡ ሲቀበሉ ፡ ሌሎቹ ፡ አንቀበልም ፡ ሊሉ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፹፪ ። ከመምረጡ ፡ በፊት ፡ የወራሽ ፡ መሞት ።

(፩) ወራሽ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ወራሽነቱን ፡ ከመቀበሉ ፡ ወይም ፡ አልቀበልም ፡ ከማለቱ ፡ አስቀድሞ ፡ የሞተ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ተቀባይነቱ ፡ ወይም፡ የአልቀበልም፡ ባይነቱ ፡ መብት ፡ ለርሱ ፡ ወራሾች ፡ ይተላለፋል ።

(፪) ከነዚሁም፡ ወራሾች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ወራሽነቱን፡ እንዲቀበሉ ፤ ሌሎቹ ፡ ግን ፡ አንቀበልም ፡ እንዲሉ ፡ ይፈቀድላቸዋል ።

(፫) የወራሹን፡ ውርስ ፡ አንቀበልም ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ አድራጎታቸው ፡ መጀመሪያ ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ አንቀበልም ፡ እንዳሉ ፡ ይቈጠራሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፹፫ ። ምርጫው ፡ ቍርጠኛ ፡ ቃል ፡ መሆን ፡ ስለሚገባው ።

(፩) የውርሱን፡ የመቀበል፡ ወይም ፡ የአለመቀበል ፡ ቃል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም፡ ውለታ ፡ ሊኖርበት ፡ አይችልም ።

(፪) ወራሹ ፡ ውርሱን፡ መቀበሉን ፡ ወይም፡ የአለመቀበሉን፡ ቃል ፡ ሲሰጥ ፡ በዚሁ፡ ውስጥ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በውለታ ፡ ቃል ፡ ጨምሮበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምርጫ ፡ እንዳላደረገ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፬ ። ወራሽነትን ፡ በከፊል ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ።

(፩) ውርሱን፡ በከፊል ፡ ለመቀበል፡ ወይም ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

(፪) ስለ፡ሆነም ፡ ውርሱን፡ አልቀበልም፡ ያለ ፤ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት፡ሰው ፡ ያለኑዛዜ ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ወራሽ ፡ በመሆን ፡ ወራሽነቱን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፫) እንደዚሁም፡ ልዩ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጠው ፡ ወራሽ ፡ ውርሱን ፡ አልቀበልም ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ እቀበላለሁ ፡ ወይም ፡ ውርሱን ፡ እቀበላለሁ ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ ለማማረጥ ፡ ይፈቀድለታል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፭ ። መቀበል ፡ የማይሻር ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ወራሹ ፡ ውርሱን ፡ እቀበላለሁ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ የመቀበሉ ፡ ቃል ፡ ሊፈርስ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፱፻፹፮ ። ውርሱን ፡ ለቅቄአለሁ ፡ የማለት ፡ ቃል ፡ መሻር ፤ (፩) ምክንያት ።

(፩) ውርሱን ፡ አልፈልግም፡ ያለውን፡ ቃል ፡ ወራሹ ፡ ተገድዶ ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፤ ይህን፡ ወራሽነቱን፡ ለቅቄአለሁ ፡ የማለቱን ፡ ቃል ፤ ለወራሽነት ፡ የተጠራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ወደ፡ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ ወይም፡

BACK



ወደ፡ላይ ፡ የሚቈጠር ፡ ወላጅ ፡ ወይም ፡ ወንድም ፡ ወይም ፡ እኅት ፡ ወይም፡ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ በማታለል ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ።

(፪) በሌላ፡ ምክንያት፡ ግን ፡ ውርሱን ፡ ለቅቄአለሁ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ሊሽር ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፱፻፺፪ ። (፪) አደራረጉና፡ ውጤቶቹ ።

(፩) ወራሽነቱን፡ ለቅቄአለሁ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ መሻር ፡ የሚፈልግ ፡ ወራሽ ፤ ለቅቄአለሁ ፤ የማለት ፡ ቃሉን፡ ለመስጠት ፡ ያስገደደው ፡ ኀይል ፡ ከቀረለት ፤ ወይም፡ የተታለለበት ፡ ተንኰል ፡ ከተገለጸ ፡ በኋላ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ ክሱ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

(፪) በማናቸውም ፡ ምክንያት፡ ቢሆን ፡ ለቅቄአለሁ፡ የማለት ፡ ቃል ፤ ከተነገረ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ።

(፫) ወራሽነቱን፡ ለቀቅሁ፡ የማለትን ፡ ውጤቶች ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ መሰረዝና ፡ መፍረስ ፡ በሚለው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉትን ፡ መሠረቶች ፡ በመከተል ፡ ዳኞቹ ፡ ይወስናሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፺፫ ። በወራሹ ፡ ምትክ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ መክሰስ ።

(፩) ውርሱን፡ አልፈልግም፡ መባሉ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስባቸው ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ፡ ውርሱን ፡ አልፈልግም ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አልፈልግም ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ከተነገረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በ፪ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ዳኞች ፡ አልፈልግም ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ እንዲያፈርሱት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ለገንዘብ፡ ጠያቂዎች፡ ጥቅም ፡ ሲባልና ፡ በሚጠይቁትም ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዳኞቹ ፡ ውርሱን ፡ አልፈልግም ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ሊሽሩት ፡ አይችሉም ።

(፫) ወራሽነቱን፡ ለቀቅሁ፡ ብሎ ፡ ለተወው ፡ ወራሽ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ውርሱን ፡ አልፈልግም ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ አይሻርም ።

ቍ ፡ ፱፻፺፬ ። የውርስ ፡ መቀበል ፡ ውጤት ።

ውርሱን፡ መቀበል፡ ሟቹ ፡ ከሞተበት፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል።

ቍ ፡ ፱፻፺፭ ። ወራሽነቱን ፡ የመልቀቅ ፡ ውጤት ።

(፩) ወራሽነቱን፡ ትቻለሁ፡ የሚል ፡ ወራሽ ፡ መቼውንም ፡ ወራሽ ፡ እንዳልሆነ ፡ ይገመታል ።

(፪) ወራሹ፡ አልፈልግም፡ ሲል ፡ የተወውን ፡ ድርሻ ፡ ወራሽነቱን ፡ ለተቀበሉት ፡ ለአብሮ ፡ ወራሾች ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ለተከታይ ፡ ወራሾች ፡ የሚተላለፍላቸው ፡ ይሆናል ።

(፫) ከነሱ፡ ጋራ፡ አብሮ ፡ ወራሽ ፡ የሆነው ፡ ውርሱን ፡ አልፈልግም ፡ ብሎ ፡ መልቀቁን ፡ ከአስታወቃቸው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወራሽነትን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተቀበሉትን ፡ ወራሾች ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፤ አብሮ ፡ ወራሽ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የተወውን ፡ ውርስ ፡ እንቀበላለን ፡ ወይም ፡ አንቀበልም ፡ ለማለት ፡ ይችላሉ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

<u>ለወራሹ ፡ ስለሚሰጡ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶችና ፡ የወራሽነት ፡ ጥያቄ ።</u>

<u>ቍ ፡ ፱፻፺፮ ። ለወራሹ ፡ የሚሰጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ። (፩) የምስክርነቱ ፡ ወረቀት ፡ መስጠት ።</u>

(፩) ወራሽ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ ለሟቹ ፡ ወራሽ ፡ መሆኑና ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ የሚያገኘውን ፡ ድርሻ ፡ የሚያመለክት ፡ የወራሽነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጡት ፡ ዳኞቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ዳኞቹም ፤ እንደዚህ፡ ያለውን፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበውን ፡ ወራሽ ፤ ማስረጃዎቹን ፡ ሁሉ ፡ እንዲያቀርብና ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታያቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ሊያስገድዱት ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፱፻፺፯ ። (፪) ውጤቶቹ ።</u>

(፩) የምስክር፡ ወረቀቱ፡ እስከ፡ ተሰረዘ ፡ ድረስ ፤ ወራሹ ፡ በተባለው ፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ እንደ ፡ ተገለጠው ፡ ወራሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ።

(፪) በወራሽነት ፡ ስም፤ በወራሹ፡ የተፈጸሙ ፡ ተግባሮች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተግባሮቹ ፡ በተፈጸሙበት ፡ ጊዜ ፤ የተባለው ፡ ወራሽ ፡ የወራሽነት ፡ መብት ፡ እንዳልነበረው ፡ በግልጽ ፡ ማወቁ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ እነዚህን ፡ ተግባሮች ፡ ለመቃወም ፡ አይቻልም ።

<u>ቍ ፡ ፱፻፺፰ ። (፫) ስለ ፡ መሰረዝ።</u>

(፩) የወራሽነቱ፡ ጥያቄ፡ በቀረበላቸው ፡ ጊዜ ፡ ዳኞቹ ፤ እነርሱ ፡ የሰጡትን ፡ የወራሽ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ለመሰረዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁ፡ ሲሆን ፤ ወራሹ፡ የተሰጠውን፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፫) ወራሹ ፤ የምስክሩ፡ ወረቀት፡ ጠፍቶብኛል ፡ ሲል ፡ ያመካኘ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ወረቀቱን ፡ ለመመለስ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለወደፊቱ ፡ በዚህ ፡ በተባለው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዳይገለገልበት ፤ የሚያረጋግጥ ፡ ለዚሁ ፡ የሚገባውን ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ይፈረድበታል ።

BACK



**ቍ ፡ ፱፻፺፱ ። የወራሽነት ፡ ጥያቄ ፤ (፩) መሠረቱ ።**

አንድ ፡ ሰው ፤ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የወራሽነት ፡ ማስረጃ ፡ ሳይኖረው ፤ ውርሱን ፡ ወይም ፡ ከውርሱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ በእጁ ፡ ያደረገ፡እንደ፡ሆነ ፤ እውነተኛው፡ ወራሽ ፡ ወራሽነቱ ፡ እንዲታወቅለትና ፤ የተወሰዱበት ፡ የውርስ ፡ ንብረቶች ፡ እንዲመለሱለት ፤ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የወራሽነት ፡ ጥያቄ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲ ። (፪) ጥያቄውን ፡ ለማቅረብ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ከሳሹ፡ መብቱንና ፡ የውርሱ፡ ንብረቶች ፡ በተከሳሹ ፡ መያዛቸውን ፡ ካወቀ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፤ ስለ፡ወራሽነት ፡ ጥያቄ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ፡ተቀባይነት ፡ ለማግኘት ፡ አይችልም ።

(፪) እንደዚሁም፡ ሟቹ፡ ከሞተበት ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ በመብቱ ፡ ለመሥራት ፡ ከቻለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፤ ከዘር፡ የወረደ፡ ርስት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የተባለው ፡ የውርስ ፡ ጥያቄ ፡ ክስ ፡ በማናቸውም ፡ አስተያየት ፡ ቢሆን ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም ።

**ቍ ፡ ፲፩ ። (፫) ውጤቶች ።**

(፩) ከሳሹ፡ ባቀረበው ፡ የወራሽነት ፡ ጥያቄ፡ ተከሳሹ ፡ ተረታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እጁ፡ ያደረጋቸውን ፡ የወራሽነትን ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ለከሳሹ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) በቅን፡ ልቡና ፡ ባለሀብት፡ ሁኛለሁ ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ ሊከራከር ፡ አይችልም ።

(፫) ለቀረው፡ ጒዳይ፡ ሁሉ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉት ፡ አላገባብ ፡ መበልጸግን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸማሉ ።

**ቍ ፡ ፲፪ ። (፬) ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገላቸው ፡ ሰዎች ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ለተደረገላቸው ፡ ሰዎችም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ውርስ ፡ አስተዳደር ።

**ቍ ፡ ፲፫ ። መሠረቱ ።**

አጣሪው ፡ ከተመረጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የወራሽነት ፡ ባለመብቶች ፡ ድርሻቸውን ፡ ወይም ፡ የሚደርሱዋቸውን ፡ ንብረቶች ፡ እስከ ፡ ተቀበሉ ፡ ድረስ ፡ የሟቹን ፡ ንብረት ፡ ማስተዳደር ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፰፻፱ ። እሽግ ።

(፩) በውርስ፡ ንብረት፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በአንዳንዱ ፡ የወራሽነት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ በማናቸውም ፡ ባለጕዳይ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች፡ ሟቹ ፡ እንደ፡ሞተ ፡ ወዲያውኑ፡ እሽግ፡ እንዲደረግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የማሸጉና ፡ እሽጉን ፡ የማንሣት፡ ኪሣራ፡ የሚታሰበው ፡ እንዲታሸግልኝ፡ሲል፡ ጥያቄ ፡ ባቀረበው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፰፻፲ ። የዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ፡ (፩) በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ንብረት ።

(፩) አጣሪው፡ የሟቹን ፡ መሞት፡ በሚከተሉ ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ በውርሱ፡ የሚገኙትን ፡ ንብረቶች ፡ በአንድ ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

(፪) አስፈላጊም ፡ ከሆነ ፡ አዳዲስ ፡ ንብረቶች ፡ ከተገኙበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ፡ በተጨማሪ፡ በዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ።

ቍ ፡ ፰፻፲፩ ። (፪) የንብረቶቹ ፡ ግምት ።

(፩) በውርስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ለውርስ ፡ ዕዳ፡ ለሆኑት ፡ እያንዳንዱ ፡ ጕዳዮች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፤ አጣሪው ፡ ለጊዜው ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ ይሰጣቸዋል ።

(፪) አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ግምቱ ፡ በልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ረዳትነት ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፰፻፲፪ ። (፫) ወራሾቹ ፡ ያለባቸው ፡ ግዴታዎች ።

(፩) በሟቹ፡ ሞት፡ ምክንያት ፡ የሚጠፉት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ወራሾቹ ፡ በውርሱ ፡ ባላቸው ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፡ በዚህ ፡ በሟቹ ፡ ላይ ፡ የነበራቸውን ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይቈያሉ ።

(፪) እነዚህ፡ ወራሾች ፡ ስለ ፡ ተባሉት፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ በዕቃ ፡ ዝርዝሩ ፡ መዝገብ ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ አስረጂዎች ፡ ለአጣሪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፰፻፲፫ ። (፬) ለባለጕዳዮቹ ፡ የሚደረግ ፡ ማስታወቂያ ።

(፩) ከውርሱ፡ አንድ፡ ድርሻ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በኪሣራቸው ፡ የዕቃው ፡ መዝገብ ፡ ዝርዝር ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለመጠየቅ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህን ፡ የተባለውን ፡ መብት፡ ከሟቹ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ዳኞች ፡ ሊሰጧቸው ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፱ ፡፡ (፩) ግምቱን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ ማየት ፡፡**

(፩) ከዚህ፡ በላይ፡ ባለው፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ የወርሱ ፡ ሀብት ፡ የመጨረሻ ፡ ክፍያ ፡ እስከሚደረግ ፡ ድረስ ፡ ለጊዜው ፡ አጣሪው ፡ ያደረገው ፡ የንብረቶቹ ፡ ግምት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲታይ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ፡፡

(፪) ይህ፡ ለጊዜው፡ የተደረገው ፡ ግምት ፡ ትክክለኛ ፡ አለመሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ፡ የሚታሰበው ፡ በውርሱ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡

(፫) እንደ ፡ ገና፡ መታየቱን፡ ወራሾቹ ፡ ያልጠየቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ወጪውን ፡ የሚችለው ፡ ግምቱን ፡ እንደገና ፡ ይታይልኝ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፲ ፡ የአጣሪው ፡ ጠቅላላ ፡ ሥልጣን ፡፡**

(፩) አጣሪው ፡ እንደ፡ መልካም፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባት ፡ ሆኖ ፡ የውርሱን ፡ ንብረቶች፡ በጥንቃቄ ፡ በትጋት ፡ ያስተዳድራል ፡፡

(፪) ወራሾቹ፡ በስምምነት፤ ወይም ፡ ዳኞች ፤ ማንኛውም ፡ ባለጕዳይ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ስለዚሁ ፡ ስለ ፡ አስተዳደሩ ፡ ጕዳይ ፡ ለአጣሪው ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፲፩ ፡፡ የጥበቃ ፡ ተግባሮች ፡፡**

አጣሪው ፡ በተለይ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ፡፡

(ሀ) የውርሱን፡ ንብረቶች፡ ሁሉ ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ማከናወንና ፡ ክሶችን ፡ ማቅረብ ፡፡

(ለ) በውርስ፡ ንብረቶች፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ክስ ፡ መከላከል ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፲፪ ፡፡ የውርሱ ፡ የገንዘብ ፡ መብቶች ፡፡**

(፩) አጣሪው፡ የመከፈያቸው፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የውርሱ ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ ሁሉ ፡ እንዲከፈሉ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ፡፡

(፪) እነዚህንም፡ እየተቀበለ፡ የደረሰኝ ፡ ወረቀት ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፲፫ ፡፡ የውርሱን ፡ ንብረቶች ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡፡**

(፩) በቶሎ፡ የሚበላሹ፡ ወይም ፡ በጥበቃቸው ፡ ወይም ፡ ለማስቀመጣቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ ወጪ፡ ገንዘብ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚጠይቁትን ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ፡ የሚገኙትን ፡ ፍሬዎች ፡ ሰብሎች ፡ እንዲሁም ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ፡፡

(፪) አጣሪው ፡ የውርሱን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌሎቹን ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ንብረቶች ፡ ለመሸጥ፡አይች ልም ።

(፫) በወራሾቹ፡ ሁሉ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ በዳኞች ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማይ ንቀሳቀሱትን ፡ ንብረቶች ፡ ለመሸጥ ፡ አይችልም ።

ክፍል ፡ ፩ ።

## የውርሱን ፡ ዕዳ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

### ቍ ፡ ሺ፲፩ ፡ የአከፋፈሉ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ።

የውርሱ ፡ ዕዳዎች ፡ እንደሚከተለው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራ ፡ ይከፈላሉ ።

(ሀ) በመጀመሪያ ፡ የሚከፈለው ፡ ለሥርዐተ ፡ ቀብሩ ፡ ወጪ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፤

(ለ) ቀጥሎ፡ የሚከፈለው፡ ስለ ፡ ውርሱ፡ አስተዳደርና ፡ ውርሱን ፡ ለማጣራት ፡ የተደ ረገው ፡ ወጪ ፤

(ሐ) ሦስተኛ ፡ የሟቹን ፡ ዕዳዎች ፤

(መ) አራተኛ ፡ የጡረታን ፡ ዕዳ ፤

(ሠ) አምስተኛ ፡ ሟቹ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታዎች ።

### ቍ ፡ ሺ፲፪ ፡ ለሥርዐተ ፡ ቀብር ፡ ወጪ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ።

(፩) ሟቹ ፡ ይዞት ፡ የነበረው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በሚታየው ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሥርዐተ ፡ ቀብሩ ፡ ወጪ ፡ ከሌሎቹ ፡ ዕዳዎች ፡ ቀደ ምትነት ፡ አይሰጠውም ።

(፪) ለሟቹ ፡ መታሰቢያ፡ የሚደረገው፡ ወጪ ፡ የተስካር ፡ ወጪ፡ለሥርዐተ ፡ ቀብሩ፡ በወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ አይታሰብም ።

(፫) ለሟቹ ፡ መታሰቢያ ፡ ማድረግ ፡ ለሚስቱ፡ ወይም፡ ለባል ፡ ወይም ፡ ለዘመዶቹ ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ አይሆንባቸውም ።

### ቍ ፡ ሺ፲፫ ። ለወራሽነቱ ፡ አስተዳደር ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ።

ውርሱን ፡ ለማስተዳደር ፡ ለማጣራት ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪ ፡ ገንዘቦች ፡ እነ ዚሀ ፡ ናቸው ።

(ሀ) ለማሸግ ፤ የዕቃ፡ ዝርዝር፡ ለመጻፍና ፤ ስለ ፡ ማጣራቱ ፡ ሒሳብ ፡ የወጣው ፡ ገንዘብ ፤

(ለ) ስለ፡ ውርሱ፡ ንብረቶች፡ ደንበኛ፡ ጥበቃ ፡ አጠባበቅ ፤ መልካም ፡ አያያዝና፡ አስተዳደር ፡ አጣሪው ፡ ያደረገው ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፤

(ሐ) ለክፍያ፡ የተደረገው ፡ ወጪና ፡ የውርሱን ፡ ንብረቶች ፡ ለወራሾቹ ፡ ለማስተላለፍ ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ፤

(መ) ለመንግሥት ፡ የሚከፈለውን ፡ የውርስ ፡ ማዛወሪያ ፡ ገንዘብ ፤

**ቍ ፡ ፲፻፲፯ ። የሟቹ ፡ ዕዳዎች ፤ (፩) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ስለ ፡ መፈለግ ።**

(፩) በውርሱ፡ ላይ ፡ የገንዘብ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ ፡ ለማወቅ ፡ አጣሪው ፡ የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል ።

(፪) ስለዚህም፡ ነገር ፤ የሟቹን፡ መዝገቦችና ፡ ወረቀቶች ፡ ይመረምራል ። እንዲሁም ፡ ሟቹ ፡ በኖረባቸው ፡ ስፍራዎች ፡ በሚገኙት ፡ የመንግሥት ፡ መዝገቦችና ፡ የሟቹም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለበት ፡ ቦታዎች ፡ በሚገኙት ፡ መዝገቦች ፡ አስፈላጊውን ፡ ፍለጋ ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፰ ። (፪) ማስታወቂያ ።**

(፩) እነዚህ ፡ ፍለጋዎች፡ ያልገለጹዋቸው፡ ከሟቹ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ እንዳሉ ፡ የሚያስገምት ፡ ነገር ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጣሪው ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ በሚታየው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ባለዕዳቸው ፡ መሞቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያወጣል ።

(፪) እነዚህም፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤ ለርሱ፡ እንዲያመለክቱ ፡ ያስታውቋቸዋል ። ስለዚህም ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ይወስንላቸዋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፱ ። የመከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ ዕዳዎች ።**

(፩) ዕዳው ፡ እንዳይከፈል፡ መቃወሚያ ፡ ካልቀረበ፡ ወይም ፡ የውርሱ ፡ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ ለባለዕዳዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተከፍሎ ፡ ሊደርስ ፡ ያለመቻሉ ፡ ፀግልጽ ፡ ካልታወቀ ፡ በቀር ፡ የውርስ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ የሚጠየቁትን ፡ የመከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ ዕዳዎች ፡ ሁሉ ፡ ይከፍላል ።

(፪) እነዚህ፡ ሁለቱ ፡ ሁኔታዎች፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ የባለዕዳዎች ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ደንቦች ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፳ ። ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ሰነድ ።**

(፩) በሟቹ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያላቸው ፡ ሰነዶች ፡ በአጣሪው ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) አጣሪው፡ የውርሱን፡ የንብረት ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ እስከሚያዘጋጅበት፡ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የነዚህን ፡ ዕዳዎች ፡ መክፈል ፡ ለማዘግየት ፡ ይችላል ።

(፫) ውርሱ፡ እነዚህን፡ ዕዳዎች ፡ ለመክፈል ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ የውርሱን ፡ ዕዳዎች ፡ ወይም ፡ አንዳንዶቹን ፡ ዕዳዎች ፡ እንዲከፍል ፡ አጣሪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፩ ። የመከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሱ ፡ ዕዳዎች ።**

(፩) ከውርሱ ፡ ሀብት፡ ላይ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸውና፡የመከፈያው፡ ጊዜ ፡ ያልደረሰ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ የገንዘቡ ፡ መከፈያ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፈላቸው ፡ እንዲችል ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ ከዚህ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ የውለታ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ሰዎችም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፪ ። ለዕዳው ፡ መከፈያ ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶች ፤ (፩) ጥሬ ፡ ገንዘብ ።**

አጣሪው ፤ የውርሱን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ አስቀድሞ ፤ በውርሱ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ፡ የሚገኘውን ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ያወጣል ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፫ ። (፪) በኑዛዜ ፡ ያልተሰጡ ፡ ንብረቶች ።**

(፩) ዕዳዎቹን፡ ለመክፈል፡ ንብረቶቹን ፡ ለመሸጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህን ፡ ንብረቶች ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ከመሸጡ ፡ በፊት ፡ አጣሪው ፡ ወራሾቹ ፡ ለመግዛት ፡ የሚፈልጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

(፪) አንዱ ፡ ወራሽ ፡ በገበያው ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ በበለጠ ፡ ዋጋ ፡ እገዛለሁ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጣሪው ፡ ለዚሁ ፡ ወራሽ ፡ ንብረቶቹን ፡ መሸጥ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፬ ። (፫) በኑዛዜ ፡ የተሰጡ ፡ ንብረቶች ።**

ሌሎችን ፡ ንብረቶች ፡ በመሸጥ ፡ ዕዳዎቹን ፡ ለመክፈል ፡ የሚቻል፡የሆነ፡እንደ፡ ሆነ ፡ ሟቹ ፡ በኑዛዜ ፡ የሰጣቸውን ፡ ንብረቶች ፡ ለመሸጥ ፡ አይቻልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ከውርሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚጠየቀው ፡ የቀለብ ፡ ገንዘብ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፭ ። መሠረቱ ።**

የውርሱ ፡ አጣሪ ፤ በኑዛዜ ፡ የተሰጡትን ፡ ስጦታዎች ፡ ከመክፈሉ ፡ አስቀድሞ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ይገባናል ፡ ሲሉ ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚችሉትን ፡ የቀለብ ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፮ ። የቀለብ ፡ ገንዘብ ፡ (ጡረታ) ፡ ጠያቂዎችን ፡ መወሰን ።**

(፩) ከዚህ ፡ በታች፣ በሚከተሉት፣ ቍጥሮች ፡ በተወሰኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ የቀለብ፣ ገንዘብ፣ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፤ የሟቹ ፡ ባል፣ ወይም ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ወደ፣ ታች፣ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡ ናቸው ።

(፪) የውርሱ፣ ንብረት፣ ለመንግሥት ፡ የሚገባ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሟቹ ፡ በሞተበት ፡ ጊዜ ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ያኖራቸው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተወሰኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ እንደዚሁ ፡ ቀለብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፯ ። ለቀለብ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለመኖር ።**

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር፣ የተነገሩት ፡ ሰዎች ፤ በችግር ፡ ላይ ፡ ካልተገኙና ፡ ሠርተው ፡ ኑሩዋቸውን ፡ ለማሸነፍ ፡ የማይችሉ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፤ የጡረታ ፡ ቀለብ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፰። የጡረታ ፡ ቀለብ ፡ ጠያቂው ፡ ያለ፡ኑዛዜ ፡ ወራሽነት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ።**

(፩) ለሟቹ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች፣ ወይም፣ ወደ ፡ ላይ ፡ ለሚቈጠሩ፣ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ለወንድሞችና ፡ ለእኅቶች ፡ የጡረታ ፡ ቀለብ ፡ የሚሰጣቸው ፡ የሟቹን ፡ ውርስ ፡ ወይም፣ ከውርሱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚወርሱ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እነዚህ፣ ሰዎች፣ ሟቹን ፡ ለመውረስ ፡ የማይገባቸው ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ ከውርሱ ፡ ተከልክለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጡረታ ፡ ቀለብ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አይኖራቸውም ።

(፫) እንደዚሁም፣ በሕግ፣ መሠረት ፡ ከነሱ ፡ ቅድሚያ ፡ በሚያገኙ ፡ ወራሾች ፡ ምክንያት ፡ ወራሽ ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀለብ ፡ ማግኘት ፡ መብት ፡ አይኖራቸውም ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፱ ። ከፍተኛ ፡ የጡረታ ፡ ቀለብ ።**

(፩) ወደታች፣ የሚቈጠሩ፣ ተወላጆች ፡ ወይም ፡ ወደ፡ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች፣ ወይም ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡ ያላቸው ፡ የጡረታ ፡ ቀለብ ፡ የመጠየቅ፣ መብት፣ ሟቹ ፡ እነሱን ፡ የሚጎዳ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ባያደርግ ፡ ኑሮ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ከውርሱ ፡ ለማግኘት ፡ በሚችሉት ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ለማግኘት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ነው ።

(፪) ሟቹ፣ ከመሞቱ፣ በፊት ፡ ባለፉት ፡ ፲ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ያደረጋቸው ፡ ችሮታዎች ፡ በኑዛዜ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተሰጡ ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፴ ። ለባልና ፡ ሚስቱ ፡ የሚከፈል ፡ የጡረታ ፡ ገንዘብ ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በተጻፈው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ቀለብ ፡ መኖ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ፡ በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተሠራው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ከውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ቀለብ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፩ ። የቀለብ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ።**

(፩) የቀለብ፡ ገንዘብ፡ ለማግኘት ፡ የሚደረገው ፡ ጥያቄ ፤ የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ከመከፋፈሉ ፡ በፊት ፡ ለአጣሪው ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።
(፪) አስቸኳይ፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ አጣሪው ፡ ለባለጕዳዮቹ ፡ ለጊዜው ፡ የቀለብ ፡ ገንዘብ፡ ሊሰጣቸው ፡ ይችላል ።
(፫) አጣሪው ፡ የቀለብ፡ ገንዘብን፡ ጥያቄ ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፤ ውሳኔው ፡ ወዲያውኑ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፪ ። የቀለብ ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ።**

(፩) ቀለብ፡ ተቀባይ፡ የሟቹ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ተቀባዩ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሰልሳ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የቀለቡ ፡ አከፋፈል ፡ እስከ ፡ ዕድሜው ፡ ልክ ፡ ድረስ ፡ ቀለብ ፡ በመስጠት ፡ ነው።
(፪) በሌሎች፡ ሁኔታዎች፡ ጊዜ ፡ ቀለብ ፡ መከፈሉ ፡ የሚፈጸመው ፡ ለቀለብ ፡ ተቀባዩ ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፫ ። ጡረታ ፤ (፩) የጡረታውን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈልና ፡ ለዚሁ፡የሚሰጥ፡ዋስትና።**

(፩) ጡረታ፡ የተፈቀደ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ሟቹ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ የሚከፈል፡ ይሆናል ።
(፪) የጡረታውም ፡ ተከፋይ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በተጠዋሪው ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።
(፫) አስፈላጊ፡ ሲሆን፡ ዳኞች ፡ ስለ ፡ ጡረታው ፡ መክፈል ፡ ከፋዩ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጠው ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፴፬ ። (፪) ማሻሻል ።**

(፩) የጡረታው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የመጨረሻ ፡ በሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ይቈረጣል ።
(፪) በውርሱ ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ንብረት ፡ በተገመገመ ፡ ጊዜ ፡ በስሕተት ፡ የተደረገ፡ ሆኖ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ የጡረታው ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሊሻሻል ፡ አይቻልም ።
(፫) በሕይወት ፡ ላለው ፡ የሟቹ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የተሰጠው ፡ የጡረታ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፭ ። (፫) ለጡረታ ፡ ተከፋይ ፡ የሆኑ ፡ ገንዘቦች ።**

(፩) ለጡረታ ፡ ተከፋይ ፡ የሆኑ ፡ ገንዘቦች ፡ የማይተላለፉና ፡ የማይያዙ ፡ ናቸው ።

(፪) ይህም፡ ስለ፡ተባለ፤ እነዚሁ ፡ ለጡረታ ፡ ተከፋይ ፡ የሆኑ ፡ ገንዘቦች፡ የመከፈያ ቸው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በጡረታው ፡ ተጠቃሚ ዎች ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ችግር ፡ አስፈላጊውን ፡ ለሚሰጡ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበር ፡ ድርጅቶች ፡ እንዲተላለፉ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) እንዲሁም ፡ በጡረታው ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የከፈሉት ፡ ሰዎች ፡ ለጡረታ ፡ ተከፋይ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ ለመ ያዝ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፮ ፡ የቀለብ ፡ ገንዘብ ፡ የሚመለከት ፡ ስምምነት ።**

(፩) ሟቹ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ከርሱ ፡ ውርስ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ፡ ተብለው ፡ በታሰ ቡት ፡ የጡረታ ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፡ የሚደረጉት ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ጽሑፎች ፡ ፍርስ ፡ ናቸው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ የተጻፉትን ፡ ደንቦች ፡ ለማስቀረት ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ በማሰብ ፡ የተደረጉ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ አይጸኑም ።

ክፍል ፡ ፯ ።

**የኑዛዜ ፡ ስጦታዎችን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

**ቍ ፡ ፲፻፹፯ ፡ መሠረቱ ።**

ሟቹ ፡ በኑዛዜ ፡ የሰጣቸውን ፡ ስጦታዎች፡ በኑዛዜው፡ ከወራሾቹ ፡ አንዱ ፡ እን ዲከፍል ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ አጣሪው ፡ ሟቹ ፡ በኑዛዜው ፡ የሰጣቸውን ፡ ስጦታ ዎች ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፰ ፡ በኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ምርጫ ።**

ከዚህ፡ከጥሎ ፡ ያሉት ፡ ሁለት ፡ ቍጥሮች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ፡ ሆነው፡ስለወራሾች፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ የኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ ለተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ምርጫ ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉ ፡ ውሳኔዎች ፡ ልዩ ፡ የኑዛዜውን ፡ ስጦታ ፡ የተደረገላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ ይህንኑ ፡ ስጦታ ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ አልፈልግም ፡ ለማለ ትም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፱ ፡ ብዙ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታዎች ።**

ለአንድ ፡ ሰው ፡ በኑዛዜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ስጦታ ፡ እንዲቀበል ፡ የታዘ ዘለት ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ከነዚሁ ፡ ከኑዛዜ ፡ ስጦታዎች ፡ አንዱን ፡ ለመቀበል ፡ ሌላ ውን ፡ አልፈልግም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፱፻፲ ። የአልፈልግም ፡ የማለቱ ፡ ውጤቶች ።

የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ስጦታውን ፡ አልፈልግም፡ ያለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በኑዛዜው ፡ የታዘዘውን ፡ ነገር ፡ እንዲያስፈጽም ፡ በአደራ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ተጥሎበት ፡ ለነበረ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፱፻፲፩ ። የመክፈያው ፡ ጊዜ ።

በኑዛዜው፡ የተሰጡትን፡ ስጦታዎች ፡ ወራሱ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ እንደ፡ ታየ ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፱፻፲፪ ። በኑዛዜው ፡ የተሰጡትን ፡ ስጦታዎች ፡ መቀነስ ።

(፩) ወራሱ፡ በኑዛዜው፡ የተሰጡትን ፡ ስጦታዎች ፡ ሁሉ ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ያል ሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአከፋፈሉ ፡ ሟቹ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ የገለጸው ፡ ተራ ፡ ይጠበቃል ።

(፪) በኑዛዜው ፡ ውስጥ፡ በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደሆነ ፤ በኑዛዜው ፡ ወይም ፡ ሟቹ ፡ በጻፈው ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት፡ ሰው ፡ ላደረገው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ የተሰጡ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ የተመለከቱት ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታዎች ፡ በቅድሚያ ፡ ይከፈላሉ ።

(፫) ሌሎቹ፡ በኑዛዜው ፡ የተደረጉ ፡ ስጦታዎች ፡ ባላቸው ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ የሚቀነሱ ፡ ይሆናሉ ።

## ቍ ፡ ፱፻፲፫ ። በኑዛዜ ፡ የተሰጠ ፡ የተለየ ፡ ነገር ።

(፩) የኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የተሰጠውን ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ሁኔታ ፡ እንዳለ ፡ የዚሁ ፡ ንብረት ፡ ተጨማሪ ፡ ከሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ አጣሪው ፡ ያስረክባል ።

(፪) የኑዛዜ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ በመልካም፡ ሁኔታ ፡ ሆኖ ፡ ይሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፱፻፲፬ ። በዐይነት ፡ ብቻ ፡ የተነገረ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ።

(፩) ዐይነቱ ፡ ብቻ ፡ የተነገረ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተናዛዡ ፡ ገንዘብ ፡ ከሆኑት ፡ ያንኑ ፡ ዐይነት ፡ ንብረቶች ፡ ውስጥ ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የመረጠውን ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

(፪) የኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ የተነገረላቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ከሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ በኑዛዜ ፡ የታዘዘላቸውን ፡ ለመምረጥ ፡ የተጠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ስለሚያደርጉት ፡ የምርጫ ፡ ቀዳሚነት ፡ ዕጣ ፡ ይጣላል ።

(፫) በወራሱ፡ ውስጥ ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት ፡ ዐይነት ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ኑዛዜ ፡ የተነገረለት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፤ የኑዛዜ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡

በዐይነት፣ መካከለኛ፣ የሆነውን፣ ንብረት ፡ እንዲሰጠው ፡ ወይም ፡ የእንደዚህ፣ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ግምት ፡ እንዲከፍለው ፡ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚውን ፡ ለመጠየቅ፣ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፲፻፺፫ ። በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ በኑዛዜ ፡ መስጠት ።

(፩) በኑዛዜ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት ፡ ሟቹ፣ በሚንቀሳቀስ፣ ንብረት ፡ በመያዣ ፡ ወይም፣በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የአስያዘው ፡ ንብረት ፡ የሆነ ፡ እንደ፣ ሆነ ፡ የዕዳው ፡ መከፈያ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ የተሰጠውን ፡ ስጦታ ፡ እንዲያገኝ ፡ መድን ፡ የሚሆን ፡ ማረጋገጫ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) በመያዣ ፡ ወይም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠበትን ፡ ዕዳ ፡ የመከፈያው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ተተክቶ ፡ በሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የነበረው ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

## ቍ ፡ ፲፻፺፬ ። የሌላ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ በኑዛዜ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፤ (፩) የዐይነት ፡ ነገሮች ።

ሟቹ፣ በዐይነት ፡ የሚሰጥ ፡ ዕቃ ፡ ተናዞ ፡ በሞተበት ፡ ጊዜ ፡ የዚሁ ፡ ዕቃ ፡ ዐይነት ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጣሪው ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ለተደረገለት ፡ ሰው ፤ ግምቱን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፲፻፺፭ ። (፪) የተለዩ ፡ ነገሮች ።

(፩) በኑዛዜው ፡ የተደረገው ፡ ስጦታ ፡ በተለየ ፡ ነገር ፡ እንደ፣ ሆነና ፡ ሟቹ ፡ በሞተበት ፡ ቀን ፡ በዚሁ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንዳችም ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ፣ የኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

(፪) ስለሆነም ፤ ሟቹ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ እያወቀ ፡ በኑዛዜው ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስጦታው ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

(፫) እንደዚህ፣ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ አጣሪው ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፲፻፺፮ ። የገንዘብ ፡ መብትን ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) የገንዘብ፣ መብት፣ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሟቹ ፡ በሞተበት፣ ቀን ፡ ባለው ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ መጠን ፡ ስጦታው ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) አጣሪው ፡ በኑዛዜ ፡ የተነገረውን ፡ ግዴታ፣ የኑዛዜው ፡ ስጦታ ፡ ለተደረገለት ፡ ሰው ፡ ስጦታው ፡ የሚገኝበትን ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ ማስረጃ ፡ በመስጠት ፡ ግዴታውን ፡ ይፈጽማል ።

(፫) ውርሱ ፡ የገንዘቡ ፡ መብት ፡ ለመከፈሉ ፡ መድንነት ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ በኑዛዜ ፡ የተደረገ ፡ ስጦታ (ጡረታ) ።**

ሟቹ ፡ ካንድ፡ ነገር፡ የሚገኘውን፡ ገንዘብ ፡ በኑዛዜ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚታሰበው፤ ተናዛዡ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፺ ። ፍሬዎችና ፡ ወለዶች ።**

(፩) አንድ ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ በኑዛዜ፡ የተሰጠ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚያፈራው ፡ ፍሬ ፡ የሚታሰበው ፡ ተናዛዡ ፡ ከሞተበት ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) በኑዛዜ፡ የተሰጠው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ የገንዘብ ፡ ወለድ ፡ በሕጋዊው ፡ ወለድ ፡ ልክ ፡ የሚታሰበው ፡ አጣሪው ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከደረሰው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፩ ። የማስረከቢያ ፡ ወጪ ።**

በኑዛዜ ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ ለማስረከብ ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ የሚታሰበው ፡ በውርሱ ፡ ላይ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

## ስለ፡ውርሱ ፡ መዘጋት ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፪ ። የውርሱ ፡ መዝጊያ ፡ ጊዜ ።**

(፩) የውርሱ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራት፡ ሥራ ፡ ሟቹ ፡ ከሞተ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ይዘጋል ።

(፪) የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስገድድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ ወይም ፡ ከባለጕዳዮቹ ፡ አንዱ ፡ ጥያቄ ፡ ሲያቀርብ ፡ ዳኞች ፡ ይህን ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሊያራዝሙት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፫ ። የንብረቶች ፡ መቀላቀል ።**

(፩) የውርሱ፡ ሒሳብ፡ ማጣራት ፡ በተዘጋ ፡ ጊዜ ፡ ከውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ ንብረት ፡ ከሌላው ፡ ከወራሹ ፡ ንብረት ፡ ጋራ ፡ ይቀላቀላል ።

(፪) የጋራ፡ ወራሾችም፡ እንዳሉ ፡ የውርሱ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ወራሾች ፡ ንብረት ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፬ ። አዲስ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስለ ፡ መቅረባቸው ።**

(፩) የውርሱ፡ ሒሳብ፡ ማጣራት ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ወራሹ ፡ እንዲከፍላቸው ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስለ፡ሆነም፡ ከውርሱ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁት ፡ ሰዎች ፡ የወራሹ ፡ የራሱ፡ ባለዕዳዎች ፡ ከሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ ወራሹ ፡ ከውርሱ ፡ ባገኘው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የቀደምትነት ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

(፫) ወራሹ፡ በውርስ፡ ካገኘው ፡ ሀብት ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዲከፍል ፡ አይገደድም ።

__ቍ ፡ ሺ፶፭ ። በግምት ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ፡ የድርሻ ፡ ዋጋ ።__

(፩) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ካላቀረቡ ፡ በቀር ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሀብቶችና ፡ የነዚህም ፡ ሀብቶች ፡ ዋጋ ፡ በዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብና ፡ በመከፋፈያው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደ፡ ተመለከተው ፡ ነው፡ተብሎ፡ ይገመታል ።

(፪) የዕቃ፡ ዝርዝር፡ መዝገብ ፡ አልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህነኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ለማቅረብ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንብረቶቹን ፡ ብዛትና ፡ ግምት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በማናቸውም ፡ ማስረጃ ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላሉ ።

__ቍ ፡ ሺ፶፮ ። የመደበቅ ፡ ሁኔታ ።__

(፩) የአንድ ፡ ንብረትን፡ ግምት፡ ስለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ ለመሆኑ ፡ በወራሾቹ ፡ ለማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱ ፡ የሚለው ፡ ግምት ፡ የታመነ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህም፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ያቀረበው ፡ ግምት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለመሆኑ ፡ እንደሚል ፡ ወራሾቹ ፡ የጠየቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መማል ፡ አለበት ።

__ቍ ፡ ሺ፶፯ ። የዕቃው ፡ መጥፋት ።__

የውርሱ ፡ መጣራት ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡ ደርሷል ፡ በሚለው ፡ ምክንያቶች ፡ የደረሰው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ተቀንሷል ፡ ወይም ፡ ጠፍቷል ፡ በማለት ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

__ቍ ፡ ሺ፶፰ ። ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ግዴታ ።__

(፩) የውርሱ ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ሥራ ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፤ ልዩ ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሰዎች ፤ ከውርሱ ፡ በስጦታ ፡ በደረሳቸው ፡ ንብረት ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ሊጠይቋቸው ፡ አይችሉም ።

(፪) ወራሹ፡ የማይከፍል፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ከውርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ሰጡ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

BACK



(፫) በዚህ ፡ ሕግ፡ ስለ፡ውሎች ፡ በጠቅላላው፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ዋስ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሚከራከርባቸውም ፡ መብቶች ፡ በኑዛዜ፡ ስጦታ፡የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የከሰሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ሊከራከርባቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፱ ። በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ክስ ።**

(፩) የውርሱን፡ ዕዳ፡ የከፈለ ፡ ልዩ ፡ ኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ተቀባይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ስለ፡ ከፈለው ፡ ዕዳ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ መብት ፡ ተተክቶ ፡ ወራሾቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከሌሎቹ፡ ልዩ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ተቀባዮች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ውርስ ፡ ክፍያ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ውርሱ ፡ አለመነጣጠልና ፡ ለውርስ ፡ ክፍያ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።

**ቍ ፡ ፰፻፷ ። ስለ ፡ ውርሱ ፡ አለመነጣጠል ።**

(፩) የውርሱ፡ አከፋፈል፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ውርሱ ፡ ሳይነጣጠል ፡ ይቈያል ።

(፪) የጋራ ፡ ወራሾች፡ የሆኑ፡ ሰዎች ፡ ባልተከፋፈሉት ፡ የውርስ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ስለ፡ሪምና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

(፫) የውርስ ፡ ሀብት፡ አጣሪነትን፡ የሚመለከቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እና ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፩ ። የልዩ ፡ ንብረቶች ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ ክፍያ ።**

የማይነጣጠለው፡ የጋራ፡ ወራሾች፡ ንብረት ፡ ክፍል ፡ የሆነውን ፡ ልዩ ፡ ንብረት ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ወይም ፡ እንዲከፋፈሉት ፡ ለማስገደድ፡አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፪ ። የክፍያው ፡ ጊዜ ።**

ውርሱ ፡ በተጣራ ፡ ጊዜ ፤ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ወራሾች ፡ ውርሱን ፡ እንከፋፈል ፡ ብለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፲፻፸፫ ። ውርሱን ፡ ለመከፋፈል ፡ የታዘዘ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ውርሱን፡ ለመከፋፈል፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ የተደረገው ፡ በማይስማማ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ሊበልጥ ፡ እስከማይችል ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ውርሱ ፡ ሳይነጣጠል ፡ እንዲቈይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የውርሱ፡ መከፋፈል ፡ የተፀነሰው ፡ ልጅ ፡ መወለድን ፡ ሁኔታ ፡ የሚጠብቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞቹ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ ውርሱ ፡ ሳይነጣጠል፡ መቈየት፡ አለበት ።

(፫) እንዲህ፡ ያለው፡ ነገር ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፤ ዳኞቹ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፤ የውርሱን፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ንብረቶችን ፡ የሚያስተዳድር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይመርጣሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፸፬ ። ውርሱን ፡ ስለ ፡ አለመነጣጠል ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።**

(፩) የውርሱ ፡ መከፋፈል፡ እንዲፈጸም ፡ ለመጠየቅ ፡ የጋራ ፡ ወራሾች ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ ሟቹ ፡ በኑዛዜው ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ወራሾቹ ፡ በመካከላቸው ፡ በሚያደርጉት ፡ ውል ፡ ሊወገድ ፡ ይቻላል ።

(፪) ከዚህ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል፡ የተመለከተው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ በተባለው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፫) የኑዛዜው ፡ ወይም፡ የውሉ ፡ ቃል ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ያላመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአምስቱ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ወዳቂ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የጋራ ፡ ወራሾች ፡ ስለሚመልሱት ፡ ንብረቶች ።

**ቍ ፡ ፲፻፸፭ ። የተመላሽነቱ ፡ መሠረት ።**

ውርሱን፡ የሚቀበለው ፡ የሟቹ ፡ ወደ፡ ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መመለስ ፡ የለብህም ፡ ተብሎ ፡ ከሟቹ ፡ ያገኘው ፡ ችሮታ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተቀብሎት ፡ የነበረውን ፡ ዋጋውን ፡ ከውርሱ ፡ ውስጥ ፡ መልሶ ፡ ማግባት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፸፮ ። የሚመለሱትን ፡ ስጦታዎች፡ መለየት ።**

(፩) በውርሱ፡ ውስጥ ፡ ተመልሶ፡ መግባት ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ ከጋራ ፡ ወራሾቹ ፡ የአንዱን ፡ ለትዳሩ ፡ ማቋቋሚያ ፡ ወይም ፡ የዚህኑ ፡ የጋራ ፡ ወራሽ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ መክፈያ ፡ እንዲሆነው ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ ነው ።

BACK



(፪) ከጋራ፡ ወራሾቹ ፡ ለአንዱ ፡ አስቀድሞ፡ የተሰጠው ፡ የማጫ ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ መመለስ ፡ አለበት ። (ይቈጠርበታል) ።

(፫) ከጋራ፡ ወራሾቹ፡ ለአንዱ፡ ለመማሪያው ፡ ሟቹ ፡ ያደረገው ፡ ወጪ ፡ መመለስ፡ የለበትም ፡ (አይቈጠርበትም) ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፯ ። ከመመለሱ ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ መሆን ።**

(፩) ሟቹ፡ ለወራሽ፡ ያደረገለት ፡ ችሮታዎች ፡ በእልቅናና ፡ ከሚደርሰው ፡ ወጭ ፡ በማድረግ ፡ ወይም፡ የተቀበለውን፡ እንዳይመልስ፡ (እንዳይቈጠርበት) ፡ ነጻ ፡ በማድረግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተባለው ፡ ወራሽ ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰደውን ፡ ንብረት ፡ መመለስ ፡ የለበትም ።

(፪) የቁም ፡ ስጦታ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ ይህን ፤ አሳብ፡ለማረጋገጥ፡ አንድ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ፡ የውል ፡ ቃል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፫) የኑዛዜ፡ ስጦታ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሟቹ ፡ ለወራሹ ፡ የሰጠውን ፡ ነገር ፡ እንዳይመልስ ፡ ነጻ ፡ በማድረግ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማረጋገጥ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ማስረጃ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፰ ። ከአንድ ፡ ነገር ፡ የሚገኝ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ የአሱራንስ ፡ ገንዘብ ።**

(፩) ሟቹ ፡ ለወራሹ፡ ካንድ፡ ነገር ፡ ከሚያገኘው ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ችሮታ ፡ ያደረገለት፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መመለስ ፡ የለበትም ።

(፪) እንዲሁም፡ ሟቹ፡ ለወራሹ ፡ ጥቅም ፡ የከፈለውን ፡ የአሱራንስ ፡ ዋጋ ፡ መመለስ ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፱ ። ቀጥታ ፡ ያልሆነ ፡ ጥቅም ።**

ወራሹ ፡ ከሟቹ ፡ ጋራ ፡ ባደረጋቸው ፡ ስምምነቶች ፡ ወይም ፡ የማኅበረተኛነት ፡ ውል ፡ ያገኛቸውን ፡ ትርፎች ፡ ወደ፡ ውርሱ ፡ መልሶ ፡ ማግባት ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፲፻ ። ገንዘቡን ፡ መልሶ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ ያለበት ፡ ሰው ።**

(፩) አስቀድሞ፡ የተወሰደውን፡ ንብረት፡ ሊመልስ፡ የሚገባው ፡ ወደ፡ታች ፡ የሚቈጠር ፡ የሟች ፡ ተወላጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም፡ ሌሎቹ፡ ወራሾች ፡ የወሰዱትን፡ እንዲመልሱ ፡ ሟቹ፡ ግዴታ ፡ ሊያደርግባቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፩ ። ወራሽ ፡ የሆነው ፡ ሰው ።**

ችሮታው ፡ በተደረገለት ፡ ቀን ፡ የሟቹ ፡ ወራሽ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የማይገመት ፡ የሆነ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ወራሹ ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰደውን ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፻፹፪ ፡ ምትክነት ፡

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ለሌላ፡ ሰው ፡ ምትክ፡ በመሆን ፡ ለወራሽነት ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ እርሱ ፡ ራሱ ፡ የተቀበላቸውን ፡ ስጦታዎች ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ ምትክ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የተተካለት ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ከሟቹ ፡ የተቀበላቸውን ፡ ችሮታዎች ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፻፹፫ ፡ ወራሽነትን ፡ አልቀበልም ፡ ባይ ፡

ወ ርሱን ፡ አልቀበልም፡ ያለ ፡ ወራሽ ፡ ከሟቹ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰደውን ፡ ነገር፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ መልሶ ፡ ማግባት ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፲፻፹፬ ፡ መመለሱ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡

(፩) የጋራ፡ ወራሾች ፡ የሚከፋፈሉትን፡ ጠቅላላውን ፡ የሟቹን ፡ ንብረት ፡ ለመመደብ ፤ ሟቹ ፡ በተዋቸው ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፤ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ መመለስ ፡ ያለባቸውን ፡ ሟቹ ፡ በቁም ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ የሰጣቸው ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ የሚጨመር ፡ ይሆናል ።

(፪) አንድ፡ የጋራ፡ ወራሽ ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰደውን ፡ ንብረት ፡ መመለስ ፡ ያለበት፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሊመልሰው ፡ እስከሚገባው ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ግምት፡ አስቀድሞ፡ ከድርሻው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፲፻፹፭ ፡ በጋራ ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ የገንዘብ ፡ መመለስ ፡ ስላለጡ ፡ ወሰን ፡

(፩) አስቀድሞ፡ የተወሰደውን፡ ንብረት ፡ መመለስ ፤ የወራሽነቱን ፡ ሀብት ፡ ከፍ ያና ፤ ስለዚህም ፡ ጕዳይ ፡ በጋራ ፡ ወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አንዳችም ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፪) ከውርሱ፡ ላይ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተነገረላቸው፡ ሰዎች ፡ ወራሹ ፡ አስቀድሞ ፡ የተቀበለውን ፡ መመለስ ፡ አለበት ፡ ብለው ፡ ሊከራከሩ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፲፻፹፮ ፡ የገንዘብ ፡ መመለሱ ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በመውሰድ ፡ ስለሚፈጸም ፡

(፩) አስቀድሞ፡ የተወሰደው፡ ነገር ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ፡ የሚመለሰው ፡ ከድርሻው፡ ላይ ፡ በመቀነስ ፡ ነው ።

(፪) ወራሽ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ በውርሱ፡ ውስጥ ፡ ከሚደርሰው ፡ ድርሻ ፡ ግምት ፡ በላይ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰደውን ፡ ንብረት ፡ ለመመለስ፡አይገደድም ።

(፫) አስቀድሞ፡ የተወሰዱት፡ ንብረቶች ፡ በዐይነታቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ተብሎ ፡ ሟቹ ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለማግባት ፡ አይፈቀድም ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፯ ። የሚመለሰው ፡ ንብረት ፡ ግምት ።**

(፩) ሊመለስ ፡ የሚገባው ፡ አስቀድሞ ፡ የተወሰደው ፡ ንብረት ፡ ግምት ፤ በነድ ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ ግምት ፡ ነው ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ግምት ፡ አልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታው ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ መመለስ ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፰ ። አስቀድሞ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት ፡ መጥፋት ።**

ወራሹ ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰዳቸው ፡ ንብረቶች ፡ ቢጠፉና ፡ በተደረገለትም ፡ ስጦታ ፡ መበልጸጉ ፡ ያቋረጠ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ንብረቶቹን ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ መልሶ ፡ ማግባት ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፱ ።

## የመከፋፈሉ ፡ አሠራር ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። ክፍያው ፡ በማን ፡ እንደሚደረግ ።**

(፩) የክፍያው ፡ ሥራ ፡ የሚፈጸመው ፤ በወራሾቹ ፡ መካከል ፡ በሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

(፪) ወራሾቹ ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ተግቶ ፡ ያሰናዳው ፡ የክፍያ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ለዳኞች ፡ ይቀርባል ።

**ቍ ፡ ፲፻፺ ። ዳኞቹ ፡ የሚያደርጉት ፡ ማጽደቅ ። (፩) ለአንድ ፡ ወራሽ ፡ የሚደረገው ፡ ጥበቃ ።**

(፩) ከወራሾቹ ፡ አንዱ ፡ ሳይኖር ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ ወኪል ፡ ያላደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ክፍያውን ፡ ዳኞች ፡ ካላጸደቁት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የክፍያውን ፡ ፈራሽነት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ እርሱ ፡ ሳይኖር ፡ ክፍያው ፡ የተፈጸመበት ፡ ወራሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ይኸውም ፡ የክፍያው ፡ ፈራሽነት ፤ ጠያቂው ፡ ክፍያውን ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ በማናቸውም ፡ አሳብ ፡ ሲሆን ፡ ሟቹ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚቈጠር ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ጥያቄው ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፺፩ ። (፪) ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚደረግ ፡ ጥበቃ ።**

(፩) እንዲሁም ፤ በጋራ ፡ ወራሾቹ ፡ መካከል ፡ የሚደረገው ፡ የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ክፍያ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ከጋራ ፡ ወራሾቹ ፡ ከአንዱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የውርሱን ፡ ክፍያ ፡ ዳኞቹ ፡ እንዲያጸድቁት ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) ይህን፡ ጥያቄ፡ የሚያቀርበው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የከፍያው ፡ ምን ፡ ሥርዐት ፡ ማጽደቅ ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያመለክተው ፡ ነገር ፡ መሰማት፡ አለበት።

(፫) የጋራ ፡ ወራሾች ፡ ባደረጉት ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ዳኞቹ ፡ ጥያቄውን ፡ አናጸድቅም ፡ ሲሉ ፡ እንቢ ፡ ካላሉ ፡ በቀር ፤ ስለ ፡ ሥርዐት፡ የሚወጣው ፡ ገንዘብ ፡ የሚታሰበው ፡ ጥያቄውን ፡ ባቀረበው ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂው ፡ ላይ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። የመከፋፈሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ።

(፩) ክፍያው፡ የሚ ፈጸመው ፤ ሟቹ፡ በጻፈው ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ መሠረት፡ ነው ።

(፪) ስለ፡ ክፍያው፡ አፈጻጸም ፡ የተጻፈ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፲፻፺ ። የንብረቶቹ ፡ ግምት ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) በወራሾቹ ፡ ድርሻ ፡ የተመደቡት ፡ ንብረቶች ፤ ክፍያው ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ይገመታሉ ።

(፪) የንብረቶቹን ፡ ግምት ፡ የሚያደርጉት ፡ ራሳቸው ፡ ወራሾቹ፡ ናቸው ።

(፫) ወራሾቹ፡ በግምቱ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግምቱ፡እነሱ ፡ በመረጧቸው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በመምረጥ ፡ ባይስማሙ ፡ ዳኞች ፡ በመረጧቸው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ግምቱ ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፲፻፺፩ ። (፪) ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሚያደርጉት ፡ ግምት ።

(፩) ስለ ፡ ማይንቀሳቀሱ፡ ንብረቶች፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሚያቀርቡት ፡ ቃለ፡ጉባኤ፡ (ፕሮሴቬርባል)፡ ግምቱ፡ የተደረገበትን፡ መሠረት፡ የሚያሳይ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ፕሮሴቬርባሉ ፤ የተገመተው፡ ንብረት፡ በሚመች ፡ አኳኋን ፡ ለመከፋፈል ፡ መቻሉንና ፡ የሚከፈልበትንም ፡ አኳኋን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፫) እንዲሁም ፡ ንብረቱ፡ የሚከፋፈል ፡ ሲሆን ፤ የሚደለደለውን ፡ የያንዳንዱን ፡ ድርሻና ፡ የድርሻውን ፡ ግምት ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፻፺፪ ። ዕጣ ፡ ድልድል ።

(፩) የክፍያዎቹን ፡ ድርሻ፡ የሚያደላድለው ፤ የጋራ ፡ ወራሾች ፡ በስምምነት፡የመረጡት ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) ወራሾቹ ፡ ያልተስማሙ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የመረጡት ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ፡ ድልድሉን ፡ ያደረጋል ።

ቍ ፡ ፲፻፺፫ ። የውርሱ ፡ ንብረት ፡ በመሠረቱ ፡ በዐይነታው ፡ የሚከፋፈል ፡ ስለ ፡ መሆኑ።

(፩) ክፍያው፡ በመሠረቱ፡ የሚደረገው ፡ እያንዳንዱ ፡ ወራሽ ፡ ከውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ንብረት ፡ እየተሰጠው ፡ በዐይነታው ፡ ነው ።

BACK



(፪) በዐይነታው ፡ የተመደቡት ፡ ድርሻዎች ፡ ትክክል ፡ ያልሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ይስተካከላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፹፯ ። የድርሻዎቹ ፡ አመዳደብ ።</u>

(፩) ከዚህ፡ በታች፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ወራሾቹ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ አመዳደብ ፡ ያላቸውን ፡ ድርሻ ፡ ይቀበላሉ ።

(፪) በተቻለ፡ መጠን፡ ለያንዳንዱ ፡ ወራሽ ፡ በበለጠ ፡ የሚያገለግሉት ፡ ንብረቶች ፡ ይሰጡታል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፹፰ ። የንብረቶቹ ፡ አመጣጥ ።</u>

በክፍያው ፡ ውስጥ ፤ ክፍያው ፡ እንደሚከተለው ፡ ይደለደላል ።

(ሀ) የአባት፡ መሥመር፡ ወራሽ ፡ ለሆኑት ፡ ለሚቹ ፡ የዚሁ ፡ መሥመር ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ያስተላለፉትን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፤

(ለ) የእናት ፡ መሥመር ፡ ወራሽ ፡ ለሆኑት ፤ ለሚችቱ፡ የዚሁ ፡ መሥመር ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ያስተላለፉትን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። ኢትዮጵያውያን ፡ ያልሆኑ ፡ ወራሾች ።</u>

ከወራሾቹ፡ መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ደግሞ ፡ አንዳንዶቹ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ያላቸው ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሉት ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለሆኑት ፡ ወራሾች ፡ በቅድሚያ ፡ ይሰጣሉ ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፺ ። የወራሾቹ ፡ ዕዳ ።</u>

ከወራሾቹ፡ አንዱ ፡ ለውርሱ፡ የሚከፍለው፡ ዕዳ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕዳው ፡ በድርሻው ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፺፩ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠባቸው ፡ ዕዳዎች ።</u>

ለአንድ፡ ወራሽ፡ ስለ፡ ሟቹ፡ ዕዳ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣ፡ ወይም ፡ በመያዣ፡ የተሰጡባቸው ፡ ንብረቶች፡ የደረሱት፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ለዕዳዎቹ፡ አላፊ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፺፪ ። በማያስቸግር ፡ ሁኔታ ፡ የማይከፋፈሉ ፡ ሀብቶች ፡ (፩) መሠረቱ ።</u>

በውርሱ ፡ ሀብት ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ሳይደርባቸው ፡ ሊከፈሉ ፡ የማይችሉ ፡ ንብረቶች ፡ ያሉ ፡ እንደ፡ሆነና ፡ ከወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ይህን ፡ የማይከፈል ፡ ሀብት ፡ ሊወስድ ፡ የሚገባው ፡ የትኛው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በስምምነት ፡ ለመወሰን ፡ ያልቻሉ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ ተሸጦ ፡ ገንዘቡ ፡ በወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ።

ቍ ፡ ፲፻፹፫ ። (፪) በሐራጅ ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

(፩) ከወራሾቹ፡ መካከል፡ አንደኛው ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሽያጩ ፡ የሚደረገው ፡ በሐራጅ ፡ ነው ።

(፪) በወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ የታጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ በሐራጅ ፡ ጨረታ ፡ ውስጥ ፡ ባዕድ ፡ ሰዎች ፡ እንዲገቡ ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፲፻፹፬ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መታሰቢያ ፡ ዕቃዎች ።

(፩) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጽሑፎችና ፡ የመታሰቢያ ፡ እምነት ፡ ያላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ እንዳይሸጡ ፡ ከወራሾቹ ፡ አንዱ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) በወራሾቹ፡ መካከል፡ ስምምነት ፡ የታጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ እንዲሸጡ ፡ ወይም ፡ ከወራሾቹ ፡ለአንደኛው ፡ እንዲሰጡ ፡ የሚወስኑት፡ዳኞች ፡ ናቸው ።

(፫) እንደዚህ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ ይህ ፡ የመታሰቢያ ፡ ዕቃ ፡ ከቤተ ፡ ዘመድ ፡ መካከል፡ እንዳይወጣ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፲፻፹፭ ። በክፍያ ፡ ው ስጥ ፡ የሚገቡ ፡ መብቶች ፡ ዐይነት ።

(፩) በውርሱ፡ ው ስጥ፡ ለተገኙት ፡ ንብረቶች ፡ ሚች ፡ ባለሀብት ፡ ወይም፡ ተከራዩ፡ ወይም ፡ ተጋዥ ፡ ወይም ፡ በእነዚህ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ መብት ፡ ነበረው፡ ሳይባል ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እነዚህን ፡ ድንጋጌዎች፡ ተፈጻሚዎች ፡ ለማድረግ፡ በንብረቱ ፡ አከፋፈል ፡ ዐይነትና ፡ ሁኔታ ፡ የክፍያውን ፡ ሥርዐት ፡ ለመፈጸም ፡ የሚቻል ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ ይበቃል ።

ቍ ፡ ፲፻፹፮ ። በብዙ ፡ የጋራ ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ ንብረቱ ፡ ሳይከፋፈል ፡ ስለ፡ማቈየት ።

(፩) ለአንድ ፡ ወራሽ ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ መብቶች ፡ የሚሰጠውን ፡ የዚህን ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌ ፡ ሌሎቹ ፡ ወራሾች ፡ በነዚህ ፡ መብቶች ፡ በአንድነት ፡ እንዲሠሩበት ፡ ተስማምተውበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ እነሱም ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ብዙዎቹ፡ ወራሾች፡ አንዱን ፡ ሀብት ፡ አብረን ፡ እንወርሳለን ፡ ሲሉ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ሀብት ፡ ለብዙ ፡ ወራሾች ፡ በአንድነት ፡ ሊሰጣቸው ፡ አይችልም ።

BACK



## ክፍል ። ፬ ።

## መከፋፈሉ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### የጋራ ፡ ተካፋዮች ፡ ሊሰጡ ፡ ስለሚገባቸው ፡ ዋስትና ።

**ቍ ፡ ሺ፺፯ ። ሕግን ፡ ስለ ፡ መጥቀስ ።**

(፩) በየድርሻቸው፡ ውስጥ፡ የተደለደለውን ፡ ግዙፍ ፡ ሀብት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፤ ሻጭ ፡ ለገዥ ፡ መድን ፡ በሚሆነው ፡ ዐይነት ፡ ወራሾችም ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ መድን ፡ ናቸው ።

(፪) በየድርሻው፡ ውስጥ፡ የተመደቡትን ፡ መብቶችና ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂነት ፡ መብቶች ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይም ፡ እንዲሁ ፡ በዋጋ ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ በሚተላለፍበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠውን ፡ መድን ፡ ዐይነት ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፺፰ ። የኪሣራው ፡ ልክ ።**

ሊከፈል ፡ የሚገባው ፡ የኪሣራ ፡ ልክ ፡ የሚወሰነው ፡ ክፍያው ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ሀብቱ ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፺፱ ። ኪሣራውን ፡ የሚከፍለው ፡ ሰው ።**

(፩) እያንዳንዱ፡ ወራሽ፡ ኪሣራውን ፡ የሚከፍለው ፡ ከውርሱ ፡ በደረሰው ፡ ድርሻ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ ነው ።

(፪) ከወራሾቹ ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወራሽ ፡ ከደረሰው ፡ ዕጣ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆን ፡ መጠን ፡ ዕዳው ፡ መድን ፡ በተሰጠው ፡ ወራሽና ፡ ዕዳ ፡ ሊከፍሉ ፡ በሚችሉት ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ የሚከፋፈል ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ሺ፻ ። የማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ የማግኘት ፡ መብት ።**

ከወራሾቹ ፡ አንደኛው ፤ በብልጫ ፡ ድርሻ ፡ ምክንያት ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባ ፡ ሒሳብ፡ እንዳለው ፡ ወይም ፡ በድርሻው ፡ ውስጥ ፡ የተደለደለው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ መከፈሉ ፡ የሚያጠራጥር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መከፋፈሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ይህ ፡ የጋራ ፡ ወራሽ ፡ መብቱን ፡ የሚያረጋግጡለት ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፩ ። ዋስትና ፡ የማይሰጥበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ውርሱን ፡ በጋራ ፡ ተካፋይ ፡ ከሆኑት ፡ አንደኛው ፡ የሚጠይቀው ፡ ዋስትና ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ በደረሰበት ፡ የመብት ፡ ማጣት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡

BACK



የተገኘው ፡ ሀብት ፡ ከተከፋፈለ ፡ በኋላ ፡ ለደረሰ ፡ ነገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋስ ትና ፡ ሊሰጠው ፡ አይገባውም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የውርሱ ፡ መከፋፈል ፡ በተደገረበት ፡ ጊዜ ፡ ከተካፋዮቹ ፡ ላንደ ኛው ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ዕጣ ፡ ያለ፡መድን ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑ ፡ በመከፋፈያው፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጾ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋስትና ፡ አይሰጥም ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ክፍያውን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

**ቍ ፡ ፲፻፪ ። ክፍያው ፡ የሚፈርስበት ፡ ምክንያት ።**

ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ የተመለከቱት፡ ቍጥሮች፡ ድንጋጌ፤ እንደ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ፡ የክፍ ያው ፡ ጕዳይ ፡ ሌሎች ፡ ውሎች ፡ በሚፈርሱበት ፡ አኳኋን ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፫ ። የተረሱ ፡ ንብረቶች ።**

(፩) ክፍያው፡ ከተደረገ፡ በኋላ ፡ በክፍያ ፡ ውስጥ ፡ ያልገቡ ፡ በውርሱ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ የሚቈጠሩ ፡ አዲስ ፡ ሀብቶች ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ በነዚሁ፡ አዲስ ፡ ንብረቶች ፡ መጠን ፡ አዲስ ፡ የክፍያ ፡ ሥርዐት ፡ መፈጸም ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) አስቀድሞ ፡ የተደረገው ፡ መከፋፈል ፡ እንዳለ ፡ ይረጋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፬ ። ንብረት ፡ ስለ ፡ መደበቅ ።**

ይህ ፡ በክፍያ ፡ ውስጥ ፡ ሳይገባ ፡ ቀርቶ ፡ የተገኘው ፡ አዲስ ፡ ንብረት ፡ ከወራ ሾቹ ፡ በአንዱ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ ይህንኑ ፡ ደብቆት ፡ የነበረው ፡ በመጥፎ ልቡና ፡ ከሆነ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ከደበቀው ፡ ንብረት ፡ የሚደርሰውን ፡ ድርሻ ፡ ያጣል ።

**ቍ ፡ ፲፻፭ ። ክፍያውን ፡ ስለ ፡ ማቃናት ። (፩) ማቃናት ፡ ስለሚደረግበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) የአንዳንድ፡ ንብረቶች፡ ዋጋ ፡ በተሳሳተ ፡ ሁኔታ ፡ በመገመቱ ፡ ምክንያት ፡ የክ ፍያው ፡ ተጠቃሚ ፡ ከሆነው፡ ወራሽ ፡ አንዱ ፡ ሊደርሰው ፡ ከሚገባው ፡ ከሦስት፡ ሩብ ፡ በታች ፡ ደርሶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ባለመብት ፡ በሆነው ፡ ወራሽ ፡ ጠያ ቂነት ፡ የክፍያውን ፡ ሥርዐት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲቃና ፡ ያደርጋል ።

(፪) እንዲሁም፡ አስቀድሞ፡ ተቀብሎት ፡ የነበረውን ፡ ስጦታ ፡ መልሶ ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ ያለበት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ ለሌሎች ፡ ወራሾች ፡ ሳይገልጽ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተደረገው ፡ ክፍያ ፡ እንዲቃና ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፮ ። (፪) ጥያቄው ፡ የሚቀርብበት ፡ ጊዜ ።**

ክፍያው፡ እንዲቃና፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ፡ ውርሱ፡ በተከፋፈለ ፡ በ፫ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣል ።

**ቍ ፡ ሺ፺፫ ። (፫) የክፍያው ፡ መቃናት ፡ ውጤት ።**

(፩) ክፍያው ፡ እንዲቃና፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ የተቀበሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጠያቂው ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ የኪሣራ ፡ ልክና ፡ ይህን ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፍለው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በምን ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚከፈል ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ክፍያው ፡ እንዲቃና ፡ የተደረገው ፡ በውርሱ ፡ ውስጥ ፡ ተመልሶ ፡ የሚገባ ፡ ስጦታ ፡ ባለመነገሩ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ስጦታ ፡ የተቀበለው ፡ የጋራ ፡ ወራሽ ፡ መልሶ ፡ ማግባት ፡ በነበረበት ፡ ዋጋ ፡ (ግምት) ፡ መጠን ፡ በተቃናው ፡ መከፋፈል ፡ ውስጥ ፡ ድርሻውን ፡ ያጣል ።

(፫) ይህነኑ ፡ ንብረት ፡ በክፍያ ፡ ውስጥ ፡ ሳያገባ ፡ የቀረው ፡ በቅን፡ ልቡና ፡ መሆኑን ፡ ወራሹ ፡ ለማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዳይሆን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፺፬ ። (፬) የኪሣራው ፡ አከፋፈል ።**

(፩) ሊከፈል፡ የሚገባው፡ ኪሣራ ፡ የሚወሰነው፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

(፪) አከፋፈሉን፡ ለመጠየቅ፡ የሚቻለው ፡ የኪሣራ ፡ ጠያቂው ፡ አብሮ ፡ ወራሽ ፡ ከሆኑት ፡ ወይም ፡ ከወራሾቻቸው ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፺፭ ። የመካፈሉን ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ መቃወም ።**

ከጋራ ፡ ወራሾቹ ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ክፍያው ፡ የተደረገው ፡ በመብታችን ፡ ላይ ፡ ማጭበርበር ፡ ተደርጓል ፡ ብለው ፡ ክፍያውን ፡ ለመቃወም ፡ የሚችሉት ፡ ያደረጉት ፡ መቃወሚያ፡ ሳይሰማ፡ እነሱ ፡ በሌሉበት ፡ መከፋፈሉ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

## የውርሱ ፡ ሀብት ፡ ከተከፋፈለ ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ያላቸው ፡ መብት ።

**ቍ ፡ ሺ፺፮ ። የክሶች ፡ መከፋፈል ።**

(፩) ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፤ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቱ፡ የማይከፋፈል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በወራሾቹ፡ ላይ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወራሽ ፡ በደረሰው ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ ጥያቄውንም፡ አከፋፍሎ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ስለ፡ ሆነም ፡ ወራሾቹ፡ ውርሱን ፡ ሲከፋፈሉ ፡ ባደረጉት ፡ ስምምነት ፡ ዕዳውን፡ በሞላው፡ ወይም ፡ አብዛኛውን ፡ አንዱ ፡ ወራሽ፡ ወይም ፡ ብዙ፡ ወራሾች ፡ እንዲከፍሉ ፡ ተስማምተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ በዚህ ፡ ስምምነት ፡ ለመጠቀም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፻፲፰ ። ከወራሾቹ ፡ አንዱ ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ ስላለመቻሉ ።

ከወራሾቹ ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዕዳው ፡ በሌሎቹ ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ በትክክል ፡ ይከፈላል ።

ቍ ፡ ሺ፻፲፱ ። በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ዎች፡ በሚሆኑበት ፡ ጕዳይ፤ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ከወ ርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ እንደ ፡ ሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ሺ፻፳ ። በወራሾች ፡ መካከል ፡ ስላለ ፡ ግንኙነት ።

(፩) ወ ርሱ፡ ከተከፋፈለ፡ በኋላ ፤ መክፈል ፡ ከሚገባው ፡ የበለጠ ፡ የዕዳ ፡ ድርሻ ፡ የከፈለው ፡ ወራሽ ፡ በብልጫ ፡ የከፈለውን ፡ ሒሳብ ፡ እንዲያገቡለት ፡ ሌሎቹን ፡ የጋራ ፡ ወራሾችን ፡ ሊጠይቃቸው ፡ ይችላል ።

(፪) የዋስትናን፡ አሰጣጥ ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ሚሆንበት ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ፡ የሚለው፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## ውርስን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ስምምነቶች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ወደፊት ፡ በሚገኝ ፡ ውርስ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ የውል ፡ ስምምነት ።

ቍ ፡ ሺ፻፳፩ ። ወደፊት ፡ በሚገኝ ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የውል ፡ ስምምነት፡ ማድረግ ፡ የተከለከለ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በሕግ ፡ ተገልጸው ፡ ከተፈቀዱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ ገና ፡ በሕይወቱ ፡ ባለው ሰው ፡ ወ ርስ ፡ ላይ ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎችና ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ሺ፻፳፪ ። ወደ፡ ፊት ፡ የሚገኝን ፡ ውርስ ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መንቀፍ ።

(፩) ገና ፡ ለወደፊት ፡ ይሰጣል፡ ተብሎ፡ ተስፋ ፡ የሚደረግበትን ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡

መቀበል ፡ ወይም ፡ ያለመቀበል ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ውርስ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ማስተላለፍ ፡ አይቻልም ።

(፪) ባለንብረት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የፈቀዳቸው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከቱት ፡ የውል ፡ ስምምነቶች ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፲፯ ። ለማውረስ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ መግባት ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ ውርሴን ፡ አሰጥሃለሁ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ አደርግልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ወይም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የተከፋፈሉ ፡ ስጦታዎች ።

**ቍ ፡ ሺ፻፲፰ ። መሠረቱ ።**

አባትና ፡ እናት ፡ ሌሎች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ለልጆቻቸውና ፡ ለሌሎች ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ሀብታቸውን ፡ ለመስጠትና ፡ ለማከፋፈል ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፲፱ ። የአፈጻጸሙ ፡ ፎርም ።**

በቁም ፡ ስለሚደረጉ ፡ ስጦታዎች ፡ በሕግ ፡ በተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ የስጦታ ፡ አከፋፈል ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳ ። ግቡ ።**

ይህ ፡ የስጦታ ፡ ማከፋፈል ፡ ጕዳይ ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠረው ፡ ወላጅ ፡ ባሉት ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፩ ። የተረሳ ፡ ንብረት ።**

ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠረው ፡ ወላጅ ፡ በሞተበት ፡ ቀን ፡ ትቷቸው ፡ የሚሞተው ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ በስጦታ ፡ መከፋፈሉ ፡ ውስጥ ፡ ሳይገቡ ፡ ቀርተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በስጦታ ፡ መከፋፈል ፡ ውስጥ ፡ ያልገቡት ፡ ንብረቶች ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ይከፋፈላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፩ ። የተረሳ ፡ ልጅ ። (፩) ስጦታው ፡ ፈራሽ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ስጦታ ፡ አድራጊው ፡ የስጦታ ፡ ማከፋፈል ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ከልጆቹ ፡ አንዱን ፡ የረሳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ስጦታው ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ የወለደ ፡ እንደሆነ ፡ ሰጪው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የተተወው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቹ ፡ የስጦታ ፡ አከፋፈሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፲፻፹፪ ። ልዩ ፡ አስተያየት ።**

(፩) ስለ፡ሆነም፡ ሚቹ ፡ ይህን፡ የተዘነጋውን ፡ ልጅ ፡ ከውርስ ፡ መንቀሉን፡ የሚገልጽ ፡ የሚጸና ፡ ኑዛዜ ፡ ትቶ ፡ ሞቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የስጦታ ፡ ክፍያው ፡ እንዲፈርስ ፡ መጠየቅ ፡ አይቻልም ።

(፪) እንደዚህም፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ ከውርስ ፡ የተነቀለው ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቹ ፡ በውርሱ ፡ ላይ ፡ ሊኖራቸው ፡ የሚችለው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

(፫) እንዲሁም፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሚቹ፡በስጦታ ፡ ማከፋፈል ፡ ውስጥ ፡ ከሰጣቸው ፡ ንብረቶች ፡ ለተረሳው ፡ ልጅ ፡ ድርሻ ፡ በቂ ፡ የሚሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ንብረቶች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተደረገው ፡ ማከፋፈል ፡ ድልድል ፡ እንዲፈርስ ፡ መጠየቅ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፫ ። ጉዳት ።**

(፩) በስጦታው፡ አከፋፈል፡ ውስጥ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ አንዱ ፡ ከሚደርሰው ፡ ከሩብ ፡ የበለጠ ፡ ጉዳት ፡ ደርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የስጦታ ፡ አከፋፈሉ ፡ እንዲቀር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ጉዳት፡ መኖሩ፡ የሚገመተው ፡ የስጦታው ፡ ክፍያ ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ ንብረቱ ፡ የነበረውን ፡ ዋጋ ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

(፫) ይህ ፡ የስጦታ፡ ክፍያ ፡ እንዲቀር ፡ የሚደረገው ፡ ከስ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠረው ፡ ስጦታ ፡ አድራጊው ፡ ወላጅ ፡ በሞተ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥና ፡ የስጦታው ፡ መከፋፈል ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በ፲ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የውርስ ፡ መብቶችን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፬ ። የወራሹ ፡ መብት ።**

፩) ውርሱ፡ ከተከፈተ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ወራሽ ፡ በውርስ ፡ የሚያገኘውን ፡ መብት ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ፡ ሆነም፡ በውርሱ ፡ ውስጥ፡ ካለው፡ ንብረት ፡ በተለይ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ በእርሱ ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

BACK



**ቍ ፡ ሺ፻፳፭ ። አሳልፎ ፡ የተሰጠውን ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡ የማስቀረት ፡ (የማስመለስ) ፡ መብት ።**

(፩) መብቱ ፡ የተላለፈው ፡ ከወራሾቹ ፡ ላንዱ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የወ ርስ ፡ መብት ፡ ከተላለፈለት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሌሎቹ ፡ የጋራ ፡ ወራሾች ፡ ግምቱን ፡ ከፍለው ለማስቀረት ፡ በሕግ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ ተሰጥቷቸዋል ።

(፪) ይህን ፡ የማስመለስን ፡ መብት ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ባለሀብትነት ፤ ስለ ፡ አላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነት ፡ ስለ ፡ ሌሎቹ ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ በሚመለከተው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

# ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ንብረቶች ።

## አንቀጽ ፡ ስድስት ።

## ስለ ፡ ንብረት ፡ በጠቅላላው ፡ ና ፡ ስለ ፡ ይዞታ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ንብረቶች ፡ በጠቅላላው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፮ ። ስለ ፡ ንብረቶች ፡ አከፋፈል ።**

ግዙፍነት ፡ ያላቸው ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ የሆኑና ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፯ ። ግዙፍነት ፡ ስላላቸው ፡ ንብረቶች ፤ (፩) መሠረቱ ።**

ግዙፍነት ፡ ያላቸው ፡ ንብረቶች ፡ ግዙፋዊ ፡ ሀልዎት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ሆነው ፡ የማይለያይ ፡ ሁኔታቸውን ፡ ሳያጡ ፡ በራሳቸውም ፡ ሆነ ፡ በሰው ፡ ካንዱ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሊዘዋወሩ ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፰ ። (፪) ላምጪው ፡ የሚሰጡ ፡ ሰነዶች ።**

ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የገንዘብና ፡ ሌሎቹም ፡ ግዙፍነት ፡ የሌላቸው ፡ ነገሮች ፡ መብቶች ፡ ላምጪው ፡ በተሰጠው ፡ ሰነድ ፡ ውስጥ ፡ ሲገኙ ፡ እንደ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ነገሮች ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፱ ። (፫) ስለ ፡ ተፈጥሮ ፡ ኀይል ።**

እንዲሁም ፡ እንደ ፡ ኤሌክትሪሲቴ ፡ ያሉት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የተፈጥሮ ፡ ኀይል ፡ ነገሮች ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በሰው ፡

BACK



ገዢነት ፡ ው ስጥ ፡ ያሉና ፡ ለሰው ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ የተደረጉ ፡ ከሆኑ ፡ እንደ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ነገሮች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፴ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የመሬት ፡ ርስቶችና ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፴፩ ። ያንድ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍሎች ፤ (፩) መሠረቱ ።**

ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ የሚመለከ ቱት ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ ተግባሮች ፡ የዚህ ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍል ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ይጠቀልላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፴፪ ። (፪) ትርጓሜ ።**

(፩) የአንዱ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍል ፡ የሚባለው ፡ በልማድ ፡ እንደሚታየው ፡ ለዚሁ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፤ ከተባለው ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ በግዙፍነት ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ሳይጠፉና ፡ አጕል ፡ ሳይሆን ፡ ለመለያየት ፡ የማይችል ፡ ነገር፡ ሲኖር ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ የዚያ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍል ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፴፫ ። (፫) ዛፎችና ፡ ሰብሎች ።**

(፩) ዛፎችና፡ ሰብሎች ፡ ከመሬት ፡ ሳይለያዩ ፡ በሚቈዩበት፡ ጊዜ ፡ ከመሬቱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ከመሬቱ ፡ ጋራ ፡ መለያየት ፡ ያለባቸው ፡ ወይም ፡ መለያየታቸውን፡ በሚያስከትል ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ከሆነ ፤ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ግዙፍነት ፡ ያለው ና ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፴፬ ። (፬) የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ።**

(፩) አንድ ፡ ነገር፡ ያንድ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አካል፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ሀብት ፡ ነው ፡ መባሉ ፡ ይቀራል ።

(፪) ከዚህም ፡ ጊዜ፡ አስቀድሞ፡ በዚሁ ፡ ነገር፡ ላይ ፡ የሌላ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መብ ቶች ፡ ናቸው ፡ ይባሉ ፡ የነበሩት ፡ ቀሪዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በዚያን፡ ጊዜ፡ ከአላፊነት ፡ የተነሣ ፡ ወይም፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ያለአገባብ፡ እን ዲበለጽግ ፡ ከመደረጉ ፡ የተነሣ ፡ የተባሉት ፡ ሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፴፭ ። ደባሎች ፡ ነገሮች ፤ (፩) መሠረቱ ።**

የሚያጠራጥር ፡ ጕዳይ ፡ ያለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ነገርን ፡ የሚመለከቱ ፡ መብ ቶች ፡ ወይም ፡ ተግባሮች ፡ ከዚሁ ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ ተያይዘው ፡ የሚገኙትን ፡ ተጨ ማሪዎችን ፡ ነገሮች ፡ የሚጠቀልሉ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፻፴፮ ። (፪) ትርጓሜ ።**

የአንድ ፡ ነገር ፡ ተጨማሪ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በባለሀብትነት ፡ ወይም ፡ በባለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነት ፡ ይዞ ፡ በሚጠቀምበት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለሚያገለግልበት ፡ ጉዳይ ፡ በነዋሪ ፡ ዐይነት ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፴፯ ። (፫) ደባል ፡ (ተጨማሪ) ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ መለያየቱ ።**

ተጨማሪዎች ፡ ነገሮች ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ ከዋናው ፡ ነገር ፡ የተለያዩ ፡ ሲሆኑ ፡ ተጨማሪ ፡ መሆናቸውን ፡ አያጡም ።

**ቍ ፡ ፲፻፴፰ ። (፬) የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ።**

(፩) አንድ ፡ ተጨሪማ ፡ ነገር ፡ ከአንድ ፡ ከሚንቀሳቀስ ፡ ወይም ፡ ከማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ የመያያዙ ፡ ጉዳይ ፤ ይህ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ከመያያዙ ፡ በፊት ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ የነበራቸውን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ባለመብትነት ፡ አያስቀርባቸውም ።

(፪) ቢሆንም ፡ ነገሩ ፡ ካንድ ፡ ንብረት ፡ ጋራ ፡ ከመያያዙ ፡ በፊት ፡ በጽሑፍ ፡ በተደረጉ ፡ ቀናቸው ፡ በተረጋገጠ ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ የተመለከተ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እነዚህን ፡ መብቶች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ባገኛቸው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑበት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፲፻፴፱ ። (፭) የተጨማሪነት ፡ ሁኔታ ፡ የሚቀርበት ፡ ጊዜ።**

(፩) ያንድ ፡ ነገር ፡ ባለሀብት ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘውን ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ደባልነቱን ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

(፪) ተጨማሪው ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ መሆኑን ፡ በማመን ፡ ከባለሀብቱ ፡ ጋራ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የተዋዋሉት ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ይዞታ ።

**ቍ ፡ ፲፻፵ ። ትርጓሜ ።**

ይዞታ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ በእጁ ፡ አድርጎ ፡ በእውነት ፡ የሚያዝበት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፩ ። በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በጠባቂ ፡ የሆነ ፡ ይዞታ ።**

በቀጥታ ፡ ወይም ፡ እንዲያው ፡ ነገሩን ፡ ይዞ ፡ ብቻ ፡ በሚቈይ ፡ በአንድ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ባለይዞታ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፪ ። የሚያልፍ ፡ መሰናከል ።**

በይዞታው ፡ መብት ፡ መገልገሉ ፡ በሚያልፉ ፡ ነገሮች ፡ የተከለከለ ፡ ወይም ፡ የተቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይዞታው ፡ የሚቀር ፡ አይሆንም ።

BACK



**ቍ ፡ ሺ፻፵፫ ። ይዞታን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

በውል ፡ ምክንያት ፡ ይዞታን ፡ የማስተላለፍ ፡ ነገር ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይዞታው ፡ የሚተላለፈው ፡ ነገሩን ፡ በሚያስረክብበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፵፬ ። ነገሩን ፡ የሚያሳዩ ፡ አስረጂዎች ።**

(፩) የሚተላለፈውን፡ ነገር፡ አዲስ፡ ባለይዞታ፡ ለሚሆነው፡ ሰው፡ የሚያሳዩና፡ይዞታውን፡ የሚፈቅዱ፡ አስረጂዎችን፡ በማስረከብ፡ ይዞታን፡ ማስተላለፍ ፡ ይቻላል ።

(፪) ሰነዶችን ፡ ባቀረበና ፡ እውነተኛ ፡ ይዞታ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ክፉ ፡ ልቡና ፡ (ተንኰል) ፡ እንዳለበት ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር፡ ለባለይዞታው ፡ ብልጫ ፡ ይሰጠዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፵፭ ። የይዞታ ፡ ማስታወቂያ ።**

(፩) ዕቃዎቹ፡ መኖራቸው፡ የተረጋገጠና ፡ በዐይነት ፡ የሚሰጡ ፤ በመለየት ፡ የታወቁ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ የዕቃው ፡ ይዞታ ፡ አዲስ ፡ ባለይዞታ ፡ ለሚሆነው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ተላለፈ ፡ የሚቈጠረው ፡ በዕቃው ፡ የሚያዝበት ፡ ሰው ፡ ዕቃውን ፡ ወደ ፊት ፡ አዲስ ፡ ይዞታ ፡ ለተሰጠው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የያዝሁት ፡ ብሎ ፡ ዋጋ ፡ ባለው ፡ (በሚጸና ፡) አኳኋን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በዕቃው ፡ በእውነት ፡ የሚያዝዝበት ፡ ሰው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከእርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ፡ናቸው።

**ቍ ፡ ሺ፻፵፮ ። በስውር ፡ ወይም ፡ በሚያሻማ ፡ አኳኋን ፡ የተደረገ ፡ ይዞታ ።**

(፩) በስውር ፡ ወይም፡ በሚያሻማ፡ አኳኋን ፡ የተደረገው ፡ ይዞታ ፡ ማናቸውንም ፡ መብት ፡ አይሰጥም ።

(፪) በስውር ፡ የተደረገ ፡ ይዞታ ፡ የሚባለው ፡ ነገሩን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ሰው ፡ በያዘው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ለማሳሰብ ፡ በሚችል ፡ አኳኋን ፡ ባለይዞታነቱን ፡ የደበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) በሚያሻማ፡ ዐይነት፡ የተደረገ ፡ ይዞታ ፡ የሚባለው ፡ በነገሩ ፡ የሚጠቀመው ፡ ሰው ፡ የራሱ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሆኑ ፡ በአካባቢዎቹ ፡ ነገሮች ፡ ሁኔታ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ ነገሩን ፡ በእጁ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የያዘው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፵፯ ። የባለይዞታውን ፡ ስም ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ስለ፡ ሌላ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ባለይዞታ ፡ መሆንን ፡ የጀመረ ፡ ሰው ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በጠባቂነት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

(፪) ለዚህ፡ ተቃራኒ፡ የሚሆን፡ ማስረጃ፡ በማናቸውም፡ መንገድ፡ ሊቀርብ፡ ይችላል።

(፫) ስለ፡ ሆነም፡ በጠባቂነት ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ አሳቡን ፡ በመለወጡ ፡ ብቻ ፡ ለይዞታው ፡ ማስረጃ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፻፹፰ ። የይዞታ ፡ መድን ፤ (፩) በኀይል ፡ መከላከል ።

(፩) ባለይዞታ፣ የሆነ፣ ሰው ፡ እንዲሁም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የያዘ ፡ ቢሆንም ፡ ይዞታውን ፡ ለመንጠቅ ፡ ወይም ፡ በይዞታው ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ለማንሣት ፡ የሚያደርገውን ፡ ማንኛውንም ፡ ኀይል ፡ በመከላከል ፡ ለመመለስ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እንዲሁም ፡ እጅ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ በንጥቂያ ፡ ወይም ፡ በስውር ፡ የተወሰደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነጣቂውን ፡ በማስወጣት ፡ ወይም ፡ ነገሩን ፡ በግፍ ፡ ሲወስድ ፡ ከተገኘው ፡ ወይም ፡ ይዞ ፡ ሲሸሽ ፡ ከተያዘው ፡ ነጣቂ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ወዲያውኑ ፡ በኍልበት ፡ በማስለቀቅ ፡ የተወሰደበትን ፡ ነገር ፡ ለመመለስ ፡ ይችላል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ የጊዜው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ካላስገደደ ፡ በቀር ፡ ከእጅ ፡ እልፊት ፡ መታገሥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። (፪) በዳኝነት ፡ የመጠየቅ ፡ ሥራ ።

(፩) ይዞታው ፡ የተወሰደበት ፡ ወይም ፡ በይዞታው ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ የተነሣበት፡ሰው፡ የተወሰደበት ፡ ነገር ፡ እንዲመለስለት ፡ ወይም ፡ የተነሣው ፡ ሁከት ፡ እንዲወገድለት ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የያዘው ፡ ነገር ፡ ከተነጠቀበት ፡ ወይም ፡ በይዞታው ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ከተነሣበት፣ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በፍርድ ፡ ካልጠየቀ ፡ እጅ፣ ይዛወርልኝ ፡ የማለት ፡ ክስ ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

(፫) ተከሳሹ ፡ የሥራውን ፡ አደራረግ ፡ የሚፈቅድ ፡ ለርሱ ፡ የሚናገርለት ፡ መብት፣ መኖሩን ፡ በፍጥነትና ፡ በማይታበል ፡ ዐይነት ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ዳኞቹ ፡ የተወሰደው ፡ ነገር ፡ እንዲመለስ ፡ ወይም ፡ የተነሣው ፡ ሁከት ፡ እንዲወገድ ፡ ያዛሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፺ ። የይዞታ ፡ መደረብ ።

(፩) የራሱ ፡ ሀብት ፡ ለማድረግ ፡ የሚገባ ፡ የይዞታ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከራሱ ፡ የይዞታ ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ንብረቱን ፡ ያስተላለፈለትን ፡ ሰው ፡ የይዞታ ፡ ጊዜ ፡ ለመደረብ ፡ የሚችለው ፤ የንብረቱን ፡ ይዞታ ፡ ያስተላለፈለት ፡ ሰው ፡ በይርጋ ፡ የራሱ ፡ ይዞታ ፡ ለማድረግ ፡ የሚፈቅድ ፡ መብት ፡ ኖሮት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ባለዐፅመርስቱ ፤ የአላባ፣ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ የከፈለውን ፡ ግብር ፡ መከራከሪያ፣ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

# አንቀጽ ፡ ፯ ።

## ስለ ፡ ግል ፡ ሀብት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ሀብት ፡ ስለሚገኝበት ፡ ሁኔታ ፤ ሀብትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

### ሀብት ፡ ስለሚቀርበትና ፡ ስለ ፡ ሀብትነት ፡ ማስረጃ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ሀብት ፡ ስለሚገኝበት ፡ ሁኔታ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ መያዝ ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፶፩ ። መሠረቱ ።**

ባለቤት ፡ የሌለውን ፡ አንድ ፡ ግዙፍነት ፡ ያለውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ ባለ ሀብት ፡ ለመሆን ፡ በማሰብ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሀብትነቱን ፡ ያገኛል ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፶፪ ። እንስሳት ።**

(፩) ለማዳ ፡ የሆኑ፡ ወይም፡ የተያዙ ፡ እንስሶች ፡ ከባለሀብቱ ፡ ሰው ፡ ቢያመልጡና፡ ቢጠፉ ፡ እርሱም ፡ በሚከተለው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሳይፈልጋቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ መፈለጉን ፡ ቢተው ፡ ባለቤት ፡ የሌላቸው ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ ለቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ለጋማ ፡ ከብቶች ፡ ለግመሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፶፫ ። ንቦች ።**

(፩) ቀፎዋቸውን ፡ ትተው ፡ የሄዱ ፡ ንቦች ፡ ባለቤት ፡ እንደሌለው ፡ ሀብት ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) በሌላ ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ የገቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀፎው ፡ የገቡለት ፡ ሰው ፡ በአግኚ ፡ ባለመብትነት ፡ የንቦቹ ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ የቀድሞው፡ የንቦቹ፡ ባለሀብት ፡ የሄዱበትን ፡ ሲከታተል ፡ ደርሶ ባቸው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ ከተገኘ ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

BACK



ቊ ፡ ፲፻፶፩ ። ስለ ፡ ተገኙ ፡ ዕቃዎች ። (፩) የአግኚው ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ግዙፍነት፡ ያለውን፡ አንድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ ያገኘና ፡ እጅ፡ ያደረገ ፡ ሰው፡ ያገኘውን ፡ ነገር ፡ እንዲያስታውቅ ፡ የሚያዝዘውን ፡ የአስተዳደር ፡ ደንብ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) እንደዚህ፡ ያለ፡ ደንብ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተገኘው ፡ ነገር ፡ ግልጽ ፡ እንዲወጣ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መፈጸምና ፡ ያገኘውን ፡ ነገር ፡ ባለ ሀብት ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ለማስታወቅ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁናቴ ፡ የታዘዘውን ፡ ምርመራ ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፲፻፶፪ ። (፪) የተገኘውን ፡ ነገር ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) ከዚህ፡ በላይ ፡ በተጻፈው፡ ቊጥር ፡ የተነገሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ የፈጸመ፡ አግኚ ፡ ያገኛቸውን ፡ ነገሮች ፡ በእጁ ፡ አድርጎ ፡ ለማስቀመጥ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በዚህ፡ ጊዜ ፡ ለዕቃው፡ አጠባበቅ ፡ በአእምሮ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፲፻፶፫ ። (፫) የተገኘውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

(፩) የጠፋ ፡ ዕቃ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ዕቃው ፡ በቶሎ ፡ የሚበላሽ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ወይም ፡ ጥበቃው ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ የሚያስፈልገው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያገኘውን ፡ ዕቃ ፡ በአደባባይ ፡ በሐራጅ ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ የዕቃው ፡ ምትክ ፡ ይሆናል ።

ቊ ፡ ፲፻፶፬ ። (፬) የተገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ባለሀብቱ ፡ መልሶ ፡ ስለሚወስድበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የዚህ ፡ ዕቃ ፡ የባለሀብትነቱ ፡ መብት ፡ እስከሚቀርበት ፡ ድረስ ፡ ባለሀብቱ ፡ ዕቃው ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ፡ ጊዜ፡ ዕቃውን ፡ ላገኙና ፡ እንዲጠበቅ ፡ ላደረጉ ፡ ሰዎች ፡ ኪሣራቸውን፡ ሁሉ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፲፻፶፭ ። (፭) ዕቃውን ፡ ላገኘ ፡ ሰው ፡ የሚሰጠው ፡ ኪሣራ ።

(፩) አስፈላጊ፡ ሲሆን ፡ ዳኞች ፡ የጠፋውን ፡ ዕቃ ፡ ላገኘ ፡ ሰው ፡ ካገኘው ፡ ዕቃ ፡ ግምት ፡ ከአራት ፡ አንድ ፡ ጉርሻ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ዳኞቹ ፡ ጉርሻ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑንና ፡ የገንዘቡንም ፡ ልክ ፡ የሚወስኑት ፡ የሁለቱን ፡ ባለጉዳዮች ፡ ሀብትና ፡ የጠፋበትን ፡ ነገር ፡ ባለሀብቱ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ለማግኘት ፡ የነበረውን ፡ ዕድል ፡ በመገመት ፡ ነው ።

(፫) የጠፋውን፡ ነገር፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ከመለሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ያልጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

BACK



ቍ ፡ ፲፻፶፱ ። የተቀበረ ፡ ገንዘብ ።

(፩) ተቀብሮ ፡ የተገኘ ፡ ገንዘብ፤ ገንዘቡ፡ የተገኘበት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ወይም ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ይሆናል ።

(፪) የተባለውን፡ ገንዘብ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ግምት ፡ አጋማሽ ፡ በጕርሻ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) የተቀበሩ፡ ገንዘቦች፡ ተብለው፡ የሚቈጠሩት፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ የእኔ ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ የማይረታባቸው ፡ ና ፡ ሲገኙም ፡ ከአምሳ ፡ ዓመት ፡ ከማያንስ ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ በእርግጥ ፡ ተቀብረው ፡ ወይም ፡ ተደብቀው ፡ የቈዩ፡መስለው፡ የሚታዩ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፻፷ ። ጥንታዊ ፡ ዕቃ ፡ (አንቲካ) ።

የጥንታዊ ፡ ነገርን፡ ምርመራ፡ አርኬዎሎዢንና ፡ ጥንታዊ፡ ዕቃዎችን፡ አንቲካዎችን ፡ የነዚህም ፡ ዘርፍ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ጕዳዮች ፡ የወጡት ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

የቅን ፡ ልቡና ፡ ባለይዞታነት ።

ቍ ፡ ፲፻፷፩ ። መሠረቱ ።

(፩) ግዙፍነት፡ ያለው፡ የተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ ባለሀብት ፡ ለመሆን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ዋጋ ፡ ሰጥቶ ፡ ውል ፡ የተዋዋለ ፡ ሰው ፡ የተባለውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ እጅ ፡ ሲያደርግ ፡ በቅን ፡ ልቡናው ፡ ምክንያት ፡ የዚህ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል።

(፪) ከርሱ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለው ፡ ሰው፡ በዕቃው ፡ ላይ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፻፷፪ ። የቅን ፡ ልቡና ፡ ትርጓሜና ፡ ማስረጃ ።

(፩) ግዙፍነት ፡ ያለውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ የሚገዛ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ እንዲያስተላልፍለት ፡ የተዋዋለውን ፡ ሰው ፡ ባለመብት ፡ ነው ፡ በማለት፡አምኖ፡ ከተዋዋለ ፤ በቅን ፡ ልቡና ፡ ተዋውሏል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

(፪) ተቃራኒ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፤ የገዛው ፡ እጅ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ በቅን፡ ልቡናው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ፲፻፷፫ ። ቅን ፡ ልቡና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ መኖር ፡ እንደሚገባው ።

(፩) ቅን ፡ ልቡና ፡ ንብረቱ ፡ እጅ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ መኖር ፡ አለበት ።

(፪) እጅ፡ አድራጊው፡ እጅ ፡ ያደረገውን ፡ ንብረት ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ የዚህን ፡ ንብረት ፡ ባለመብትነት ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ ያልነበረው ፡ መሆኑን ፡ ንብረቱን ፡ እጅ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ቢያውቅ ፡ ይህ ፡ ማወቁ ፡ ጉዳት ፡ አያደርስበትም ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፬ ። ለመጠየቅ ፡ አለመቻል ።**

(፩) ግዙፍነት፡ ያለውን፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ በፈቃዱ ፡ ከእጁ ፡ ያወጣ ፡ ሰው ፡ በቅን ፡ ልቡናው ፡ እጅ ፡ በማድረግ ፡ ባለሀብት ፡ ከሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መልስ ልኝ ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፪) ዕቃውን ፡ ከእጁ፡ ያወጣው፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ቢያገኘ ውም ፡ እንኳ ፡ ቀድሞ ፡ የለቀቅሁለት ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ያስለቀቀኝ ፡ በማታ ለል ፡ ነውና ፡ ዕቃዬን ፡ መልስልኝ ፡ ብሎ ፡ ዕቃው ፡ በእጁ ፡ የተገኘውን ፡ ሰው ፡ ሊጠይቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፭ ። የተሰረቀውን ፡ ነገር ፡ ለመጠየቅ ፡ ስለ ፡ መቻል ።**

(፩) አንድ ፡ ግዙፍነት፡ ያለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ የተሰረቀበት ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ባለሀብት ፡ ከሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመ ጠየቅ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ዕቃው ፡ ከተሰረቀበት፡ አንሥቶ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ክስ ፡ ካላቀረበ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፮ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለባለይዞታው ፡ ስለሚከፈለው ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ፈለግ ፡ የተደረገበትን ፡ ዕቃ ፡ ተጠያቂው፡ የገዛው ፡ ይህንኑ ፡ ዕቃ ፡ የመሳሰ ሉትን ፡ ነገሮች ፡ በሚሸጥ ፡ ነጋዴ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ገበያ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ በሐራጅ ፡ በሚሸጥበት ፡ በአደባባይ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ ባዩ ፡ (ተፋላሚው) ፡ ባስያዘው ፡ ነገር ፤ ገዢው ፤ ለዚህ ፡ ነገር ፡ የወ ጣሁትን ፡ ገንዘብ ፡ አግባልኝ ፡ ብሎ ፡ ሻጩን ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ ላገኙና ፡ በደንብ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ላደረጉ ፡ ሰዎች ፡ ኪሣራቸው ፡ ሁሉ ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፯ ። ጥሬ ፡ ገንዘብና ፡ ላምጪው ፡ የሚከፈል ፡ ሰነድ ።**

(፩) ጥሬ፡ ገንዘብን፡ ወይም ፡ ለአምጪው ፡ የሚከፈል ፡ ሰነድን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ካገኘ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ልቀቅልኝ ፡ ለማለት ፡ በማ ንኛቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም፡ በቅን፡ ልቡና፡ እነዚሁኑ ፡ ነገሮች ፡ በገዛው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መከራከሪያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

**ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ ስለ ፡ ይዞታ ።**

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፰ ። መሠረቱ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ባለእጅ ፡(ባለይዞታ)፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የዚሁኑ፡ንብረት ፡ ግብር ፡ ባለማቋረጥ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በስሙ ፡ ከከፈለ ፡ የዚሁ ፡ ሀብት ፡ ባለቤት ፡ ይሆናል ።

BACK



ስለ ፡ ሆነም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፤ መሬት፡ ሲሆንና ፡ በአገሩ ፡ ሥሪት ፡ መሠረት ፡ የመሬቱ ፡ ርስትነት ፡ የግል ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ሳይሆን፡ ተወላጆች ፡ የሚካፈሉት ፡ በሆነበት ፡ ስፍራ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የትውልድ ፡ ሐረጉን ፡ መዝዞ ፡ ርስቱ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይህ ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ አያግደውም ።

(፪) በዚህ፡ ሕግ፡ በአንቀጽ ፡ ስድስት ፡ በምዕራፍ ፡ ሁለት ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፻፷፱ ። ስለ ፡ መምራት ።

(፩) ስለ ፡ ወሎች፡ በጠቅላላው፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ይርጋ ፡ መቋረጥ ፡ የተነገሩት ፡ ውሳኔዎች ፡ ስለ ፡ ይዞታም ፡ ነገር ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ በይርጋ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ መከራከርና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፡ በይርጋ ፡ መከራከርንም ፡ ስለ ፡ መተው ፡ የተነገሩት ፡ የዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

## የዋና ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ።

ቍ ፡ ፲፻፸ ። የንብረቱ ፡ ፍሬ ።

(፩) ያንድ ፡ ነገር ፡ ባለሀብት፡ የሆነ ፡ ሰው፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ የሚሰጠው ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍሬ ፡ ባለሀብት ፡ ነው ።

(፪) ፍሬ ፡ ሲባልም ፡ ሀብቱ ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰጠው ፡ አበልና ፡ ነገሩም ፡ እንደ ፡ ተመደበበት ፡ ጕዳይ ፡ ከዚሁ ፡ ላይ ፡ ለመውሰድ ፡ ልማድ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የሚገኘው ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፸፩ ። የእንስሳት ፡ ውላጆች ።

(፩) የእንስሳትን ፡ ወላጅ፡ ባለሀብትነት፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ባለሀብትነቱ፡ የሚከተለው ፡ እንስቲቱን ፡ (እናቲቱን) ፡ ነው ።

(፪) ስለዚህም ፡ የእንስቲቱ ፡ ባለሀብት ፡ የወላጁ ፡ ባለሀብት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፸፪ ። ስለ ፡ ሰብል ፡ (፩) ባለመሬቱ ፡ ሲቃወመው ።

(፩) ባለመሬቱ ፡ ሲቃወመው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የዘራ ፡ ሰው ፡ የጀመረውን፡ ሥራ ፡ ለመቀጠል ፡ ወይም ፡ የዘራውን፡ ሰብል ፡ ለመሰብሰብ ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ሰብሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ የባለመሬቱ ፡ ይሆናል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሁለቱ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ ባለመሬቱ ፡ መቃወሙን ፡ ለመግለጽ ፡ ባልቻለበትም ፡ ጊዜ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ሺ፻፷፫ ።(፪) ባለመሬቱ ፡ ሳይቃወም ።

(፩) ባለመሬት ፡ ሳይቃወመው ፡ በሌላ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ዘር ፡ የዘራ ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስና ፡ የዘራውን ፡ ሰብል ፡ ለመሰብሰብ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ዘሩን ፡ የዘራው ፡ መሬቱ ፡ የራሱ፡ ሀብት ፡ መስሎት፡ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ሊዘራ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መስሎት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሰብሉ ፡ ከአራት ፡ እጅ ፡ ሦስቱን ፡ እጅ ፡ ለባለመሬቱ ፡ ለቆና ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ ሰብል ፡ ወስዶ ፡ መሬቱንም ለቆ ፡ ይሄዳል ።

(፫) ዘሩን ፡ የዘራው ፡ መሬቱ ፡ የራሱ ፡ አለመሆኑን ፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ሊዘራ ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰብሉን ፡ በሙሉ ፡ ለባለመሬቱ ፡ ለቆ ፡ ይሄዳል ።

(፬) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በሦስት ፡ ንኡስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ባለመሬቱ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ መዝራቱን ፡ እያወቀ ፡ ባይቃወምም ፡ የጸኑ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ሺ፻፷፬ ። (፫) ይህ ፡ መብት ፡ የሚሠራበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ከዚህ፡ በላይ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ለባለመሬቱ ፡ የታወቀለትን ፡ መብት ፤ መሬቱ፡ ቀድሞ ፡ የታረሰ ፡ ወይም ፡ ያልታረሰ ፡ ቢሆንም፡ ባለ ፡ መሬቱ ፡ ማግኘት ፡ ይገባዋል።

(፪) ሰብሉ ፡ ተሽጦ ፡ ወይም ፡ ተሰጥቶ ፡ ወይም ፡ ተበልቶ ፡ አልቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመሬቱ ፡ ለርሱ ፡ የሚገባውን ፡ ሰብል ፡ በጠየቀበት ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ ግምቱን፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ባለመሬቱ፡ ሰብሉ፡ በተሰበሰበ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ መብቱን ፡ ለማግኘት፡ የሚገባውን ፡ ሳያደርግ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

ቍ ፡ ሺ፻፷፭ ። ስለ ፡ አትክልቶች ፤ (፩) የባለመሬቱን ፡ ፈቃድ ፡ በመጣስ ፡ የተተከለ ።

(፩) ባለመሬቱ ፡ ሳይፈቅድ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ዛፍ ፡ የተከለ ፡ ሰው ፡ ከተከላቸው ፡ ዛፎች ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

(፪) አትክልቱ ፡ ለባለርስቱ፡ ስላስገኘው ፡ የሀብት ፡ ጥቅም ፡ አንዳችም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

(፫) ዛፉ ፡ ከመሬቱ፡ ላይ፡ ይነሣልኝ ፡ ብሎ ፡ ባለርስቱ ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማንሻው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጪ ፡ የሚችለው ፡ ተካዩ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፻፷፮ ። (፪) በባለመሬቱ ፡ ፈቃድ ፡ የተተከለ ።

(፩) ዛፉን ፡ የተከለው ፡ ሰው ፤ ባለርስቱ ፡ ፈቅዶለት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባላትክልቱን ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለማስለቀቅ ፡ ቢፈልግ ፤ ሊከፍለው ፡ የሚገባው ፡ ኪሣራ ፡ የሚወሰነው ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ባደረጉት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ሁለቱ ፡ ወገኖች፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ባይችሉ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቍጥር ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

__ቍ ፡ ፲፩፻፸፪ ። (፫) ስለ ፡ ኪሣራ ።__

(፩) በላይኛው፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው፡ ኪሣራ ፡ የሚከፈለው ፡ የተተከሉት፡ዛፎች፡ የሚሰጡት ፡ መደበኛ ፡ ጥቅም ፡ በሰብል ፡ አሰጣጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዛፎቹ ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይሰጣሉ ፡ ተብሎ ፡ ከሚታሰበው ፡ ሰብል ፡ እኩሌታው ፡ ነው ።

(፪) የተተከሉት፡ ዛፎች፡ የሚሰጡት ፡ መደበኛ ፡ ጥቅም ፡ በሰብል ፡ አሰጣጥ ፡ ያል ሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኪሣራው ፡ አከፋፈል ፡ የሚታሰበው ፤ ዛፎቹ ፡ በ፲ ፡ ዓመት፡ ከሚያወጡት ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ እኩሌታው ፡ ነው ።

(፫) በሁለቱም ፡ ሁኔታዎች፡ ቢሆን ፡ የዐሥር፡ ዓመቱ ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ባለመሬቱ ፡ የዛፉ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ሲል ፡ አሳቡን ፡ ከገለጸበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

__ቍ ፡ ፲፩፻፸፫ ። በሌላው ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሕንፃ ፡ ስለመሥራት ፡ ፩/ባለመሬቱ ፡__ ሲቃወም ።

(፩) ባለመሬቱ ፡ በግልጽ ፡ እየተቃወመው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሕንፃ፡የሠራ፡እንደ፡ሆነ፡በዚሁ፡ ሕንፃ ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ መብት፡ አይኖረውም ።

(፪) ባለመሬቱ፡ እንደ ፡ መረጠ ፡ ሕንጻ ፡ የሠራውን ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ኪሣራ ፡ ለቆ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ባለሕንጻው ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ አፍርሶ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በሁለቱ፡ ንኡስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ባለመሬቱ ፡ መቃወሙን ፡ ባልቻለበትም ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

__ቍ ፡ ፲፩፻፸፬ ፡ ፪/ ባለመሬቱ ፡ ሳይቃወም ።__

(፩) ባለመሬቱ ፡ ሳይቃወም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ሕንፃ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ የዚሁ ፡ ሕንጻ ፡ ባለሀብት ፡ ነው ።

(፪) ባለመሬቱ ፡ ከባለ ፡ ሕንጻው ፡ ጋራ ፡ የተስማሙበትን ፡ ግምት ፡ በመክፈል፡ ወይም ፡ በግምቱ ፡ ያልተስማማ፡እንደ፡ሆነ፡ከዚህ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ በቍጥር ፡ ፲፩፻፹ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሕንፃውን ፡ ግምት ፡ በመክፈል ፡ ሕንፃውን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ይችላል ።

ስለሆነም ፡ የሕንጻው ፡ ባለሀብት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ሕንጻውን ፡ አፍርሶ ፡ ለመሄድ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በሁለቱ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ባለመሬቱ ፡ የሕንፃውን ፡ መሥራት ፡ እያወቀ ፡ ሳይቃወም ፡ በቀረበትም ፡ ጊዜ ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፻፸ ። ስለ ፡ ግምት ፡ አወሳሰን ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፷፱ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለባለ ፡ ሕንጻው ፡የሚከፍለው ፡ ግምት፡ ፤ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ግልግልና ፡ ስለስምምነት ፡ በሚለው ፡ በ፳፫ኛው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ይሆናል ።

(፪) ሕንጻውን ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ መሬቱ ፡ የእርሱ ፡ አለመሆኑን ፡ አውቆ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው፡ወይም ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ፡የሆነ እንደሆነ ፡ ባለመሬቱም ፡ የሕንፃውን ፡ መሠራት ፡ እያወቀ ፡ ሳይቃወመው ፡ ሠርቶ ፡ እንደሆነ ፡ሕንጻውን ፡ ባለመሬቱ ፡ በዋጋ ፡ እንዲያስቀረው ፡ የሚስማማ ፡ ሲሆን ፡ ለሕንጻው ፡ ዋጋ ፡ ሊከፈል ፡ ከሚገባው ፡ ግምት ፡ ከአራት ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ ባለመሬቱ ፡ ከፍሎ ፡ ሕንፃውን ፡ ያስቀረዋል ።

ቍ ፡ ፲፻፸፩ ። የሌላ ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ መሥሪያ ፡ (ማቴሪያል) ፡ ሕንፃ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

(፩) የራሱ ፡ ባልሆኑ ፡ መሥሪያዎች፡ ሕንጻ፡ የሠራ ፤ የአትክልት ፡ ድርጅቶችን ፡ ያቋቋመና፡ ሌሎችንም ፡ ሥራዎች ፡ የፈጸመ ፡ ባለመሬት ፡ ለሠራባቸው ፡ መሥሪያዎች ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ።

(፪) የዕቃዎቹን ፡ ዋጋ፡ መክፈልና፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ኪሣራና ፡ ካሣ ፡ እንዲከፈል ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ።

(፫) የመሥሪያዎቹ፡ ባለሀብት፡ ዕቃውን ፡ ነቅሎ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፲፻፸፪ ። ዐይነቱን ፡ መስጠት ።

(፩) አንድ፡ ሰው፡ የራሱ ፡ ገንዘብ ፡ ያልነበረውን ፡ ነገር ፡ ያበጀ ፡ ወይም ፡ የለወጠ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ከታደሰው ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ የሥራው ፡ ግምት ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ የሠራተኛው ፡ ሀብት ፡ ይሆናል ።

(፪) በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያዋለው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የበለጠ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ሠራተኛው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያላደረገው ፡ ሲሆን ፤ ዳኞች ፡ የአዲሱ ፡ ዕቃ ፡ ባለሀብትነት ፡ ለዕቃው ፡ ባለሀብት ፡ እንዲሰጥ ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ከውል፡ ውጭ፡ ስለሚደርሱ ፡ አላፊነቶችና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የተነገሩት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፹፫ ። ቅልቅል ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ።**

(፩) በጣም፥ ሳይበላሹ፥ ወይም ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ወይም፥ በብዙ ፡ ኪሣራ ፡ ካልሆነ፥ ሊለያዩ ፡ ወይም ፡ ሊላቀቁ ፡ የማይችሉ ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ የተቀላቀሉ ፡ ወይም ፡ የተጣበቁ ፡ የብዙዎች ፡ ሀብቶች ፡ የሆኑ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ነገሮች ፡ ሲያጋጥሙ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በነገሩ ፡ መቀላቀል ፡ ጊዜ ፡ የየራሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ በነበረው ፡ ግምት፥ ምክንያትና ፡ መጠን ፡ በመቀላቀል ፡ አዲስ ፡ ለሆነው ፡ ነገር ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ነገሮች ፡ ሲቀላቀሉ ፡ ወይም ፡ ሲዋሐዱ ፡ አንዱ ፡ የሌላው ፡ ተጨማሪ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመት ፡ የሚገባው ፡ ሲሆን ፡ በመቀላቀል ፡ አዲስ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ የዋናው ፡ ነገር ፡ ባለሀብት ፡ ይወስደዋል ።

(፫) ከውል፥ ውጭ፥ ስለሚደርሱ ፡ አላፊነቶችና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የተነገሩት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ባለሀብትነትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፹፬ ። የማስተላለፉ ፡ ምክንያቶች ።**

ባለሀብትነት፥ የሚተላለፈው፥ በሕግ ፡ ወይም ፡ የግል፥ ባለጉዳዮች ፡ በሚያደርጉዋቸው ፡ ሕጋውያን ፡ ተግባሮች ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፹፭ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ባለሀብትነት ፡ (ባለርስትነት) ፡ በውል ፡ ወይም፥ በኑዛዜ ፡ ለማስተላለፍ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ማስመዝገብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፹፮ ። ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ።**

(፩) ግዙፍነት፥ ያላቸው፥ የተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ ባለሀብነት ፡ ንብረቱን ፡ በመግዛት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ያገኘው ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ እጅ ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ፡ የተላለፈ ፡ ይሆናል ።

(፪) ልዩ ፡ የሆኑ፥ አንዳንድ፥ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ የሚመለከቱት፥ የሕጎች፥ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፹፯ ። ሀብትነትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።**

የአንድ ፡ ንብረት ፡ ሀብትነቱ ፡ የሚተላለፍበት ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ ይሁን ፡ በማለት፥ የተደረጉ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ባንድ ፡ የመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ የተጻፉ ፡ ሆነው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በግልጽ ፡ የተቀበሏቸው ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ የተጻፉ ፡ ሆነው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲያውቋቸው ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑባቸው ፡ አይቻልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

### ስለ ፡ ሀብትነት ፡ መቅረት ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፰ ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መጥፋት ።**

ሀብትነቱ ፡ የዋለበት፡ ዕቃ ፡ የተበላሸ ፡ ወይም ፡ ሀልዎቱ ፡ (መኖሩ) ፡ የጠፋ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ሀብትነቱ ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፱ ። ሀብትነቱ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

እንደዚሁም ፡ ሀብትነቱ ፡ የሚቀረው ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ሀብትነቱ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፶ ። ከርስት ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ።**

በርስት ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገቡ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሀብትነት ፡ በርስትነት ፡ ከዚሁ ፡ መዝገብ ፡ ሲሰረዝ ፡ ሀብትነቱ ፡ (ርስትነቱ) ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፩ ። የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መብቱን ፡ ስለ ፡ መተው ።**

ግዙፍነት ፡ ያላቸው ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ባለሀብትነት ፡ ባለሀብቱ ፡ በማያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ መብቱን ፡ የመተውን ፡ ሐሳብ ፡ ካስታወቀ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፪ ። ሀብትነትን ፡ የሚያስቀር ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ።**

ግዙፍነት ፡ ያለው ፡ ያንድ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ሀብቱ ፡ የሚገኝበትን ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሀብቱ ፡ መሆኑን ፡ ባለማወቅ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያልተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መብቱን ፡ ያጣ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

### ስለ ፡ ሀብትነት ፡ ማስረጃ ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፫ ። የሚንቀሳቀሱ ፡ ግዙፍ ፡ ሀብቶች ።**

(፩) የሚንቀሳቀስ ፡ ግዙፍ ፡ ነገር ፡ ባለይዞታ ፡ ( ባለእጅ ) ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ያዘውና ፡ የዚሁ ፡ ነገር ፡ ባለሀብት ፡ (ባለቤት) ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ።

(፪) ይህ፡ ግምት፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ልክ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የሚከራከረው ፡ ሰው ፡ ትክክል ፡ ግምት ፡ ላለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፶፬ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፤ ጠፍ ፡ የሆኑና ፡ ባለቤት ፡ (ጌታ) ፡ የሌላቸው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ጠፍ ፡ የሆኑና ፡ ባለቤት ፡ የሌላቸው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፶፭ ። የባለሀብትነት ፡ የርስት ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ባለሀብትነትን ፡ በማወቅ ፡ በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይህ ፡ ማስረጃ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ የዚሁ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያስቈጥረዋል ።

(፪) የዚህ፡ ዐይነት፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የሚሰጥበት ፡ ደንብና ፡ ሥርዐት ፡ እንዲሁም ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ ሊታደስ ፡ እንደሚገባው ፡ በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ደንብ ፡ ይወሰናል ።

(፫) እንዲሁም ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ፡ ለመተካትና ፡ በዚህም፡ ምክንያት ፡ በአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ አላፊነት ፡ ዋስትና ፡ ለማግኘት ፡ መጠባበቂያ ፡ እንዲሆን ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የመሰጠቱ ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈለው ፡ ታክስ ፡ ልክ ፡ በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ደንብ ፡ ይወሰናል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፶፮ ። (፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ።**

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች፡ ለማስረዳት፡ የተቻለ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሀ) የባለርስትነት፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ የተሰጠው ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ በሌለው ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተሰጠው ፡ በማይረጋ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለከሳሹ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ በማይችል ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ከሳሹ፡ የማይንቀሳቀሰውን፡ ንብረት ፡ ያገኘው ፤ የገዛው ፡ የእርስት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ የሕሊና ፡ ግምት ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፶፯ ። (፪) የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) አንድ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረትን ፡ ለሚመለከት ፡ ነገር ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፤ ለዚሁ ፡ ለማይንቀ

BACK



ሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሰጥቶ ፡ የነበረው ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ፡ የርስት ፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ ጠፍቷል ፡ የሚያሰኝ ፡ ምክንያት ፡ የቀረበለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት፡ይሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ የቀድሞው ፡ ወረቀት ፡ ያለ ፡ መስረዙ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ለማስወገድ ፡ እንዲቻል ፡ አዲስ ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጠያቂው ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፫ ። (፫) የመንግሥት ፡ አላፊነት ።

(፩) አንድ፡ ሰው ፤ ለአንድ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከደንብ፡ውጭ ፡ የተሰጠውን ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ በሌለው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተሰጠውን ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በማመን ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ትክክለኛ ፡ ባለመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ መንግሥት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ሳይሰርዘው ፡ የቀረውን ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በማመን ፡ በአንድ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ፡አንድ ፡ መብት ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ለሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ አላፊው ፡ መንግሥት ፡ነው ።

(፫) በአስተዳደር፡ ክፍል፡ ሹማምቶችና ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በአላፊነት ፡ በሚጠየቁት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መንግሥት ፡ ኪሣራውን ፡ የሚጠይቅበት ፡ መብቱ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ። ፲፻፶፬ ። የርስት ፡ ወሰን ።

(፩) የመሬቱ፡ ርስት፡ ወሰን ፡ የሚታወቀው ፡ በርስት ፡ ክፍል ፡ ፕላንና ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ በሚደረግ ፡ የወሰን ፡ ምልክት ፡ ነው ።

(፪) በፕላኑ ፡ ላይ፡ ባለው፡ ወሰንና፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ወሰን ፡ መካከል፡ ልዩነት ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፕላኑ ፡ ወሰን ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፭ ። ስለ ፡ ግንብ ፡ ሥራዎች ፤ ስለ ፡ ተክሎችና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ።

(፩) ባንድ፡ ቦታ ፡ ላይ፡ የሚደረጉ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ሥራዎች ፡ ተክሎችና ፡ ሌሎች፡ ሥራዎች ፡ ከዚህ፡ የሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ሆነው ፡ በባለሀብቱ ፡ (በባለርስቱ)፡ ኪሣራ ፡ የተሠሩና ፡ የራሱ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ይገመታሉ ።

(፪) ተቃራኒ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፮ ። ስለ ፡ አጥር ።**

ሁለት ፡ ርስትን ፡ የሚለይ ፡ ማናቸውም ፡ አጥር ፡ የሁለቱ ፡ ርስት ፡ ባለሀብቶች፡ የጋራ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። ይኸውም ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለና ፡ ከነ ዚሁ ፡ ሁለት ፡ ቦታዎች ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ አጥር ፡ ያለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፯ ። ስለ ፡ ቦይ ።**

(፩) ስለ ፡ ቦይ፡ የአፈሩ፡ አወጣጥ ፡ ወይም ፡ አጣጣል ፡ ከቦዩ ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጋራ ፡ አለመሆኑን ፡ ያመለክታል ።

(፪) ቦዩ ፡ አፈሩ፡ ወደ፡ ተጣለበት ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገ መታል ።

(፫) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፰ ። ስለ ፡ ውሃ ፡ ቧንቧዎች ፡ ስለጋዝና ፡ ኤሌትሪክ ፡ ማደያ ፡ መሥመሮች ።**

የውሃ፡ ቧንቧዎች ፡ የጋዝና፡ የኤሌክትሪክ፡ ማደያ፡ መሥመሮችና ፡ ሌሎችም፡ እንደዚሁ ፡ ከተዘጋጁበት ፡ መሬት ፡ ውጭ፡ ቢገኙም፡ እንኳ፡ የሚነሡበት ፡ የዋናው ፡ ድርጅት ፡ ተጨማሪዎች ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱና ፡ የዋናው ፡ ክፍል ፡ ባለቤት ፡ ንብረት ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የባለሀብቱ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፱ ። ትርጓሜ ።**

(፩) ሀብትነት፡ ማለት፡ በአንዱ ፡ ግዙፍ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ የሰፋ ፡ መብ ትን ፡ የያዘ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ይህ፡ መብት፡ በሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ሥርዐቶች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ ሊከፋፈል፡ ወይም ፡ ሊቀነስ ፡ ወይም ፡ ሊወሰን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፲ ። በመብቱ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ነገር፡በንብረቱ፡ስለ፡መገልገልና፡ስለ፡መጠቀም።**

(፩) በሕጎችና፡ በደንቦች ፡ ከሚደረገው ፡ የመብት ፡ መቀነስ ፡ በቀር ፡ ባለሀብቱ ፡ በመሰለው ፡ መንገድ ፡ ሀብቱን ፡ ሊገለገልበትና ፡ ሊጠቀምበት ፡ ይችላል ።

(፪) ባለሀብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ወይም ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ ተቀብሎ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ሳይቀበል ፡ በንብረቱ ፡ ሊያዝዝበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፯ ። የመፋለም ፡ መብት ።**

ባለሀብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ እጁ ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ከያዘው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሀብቱ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ ለመፋለምና ፡ ማናቸውንም ፡ የኀይል ፡ ተግባር ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሚመለከቱ ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፰ ። ቦታውን ፡ ስለ ፡ ማጠር ።**

ባለሀብቱ ፡ ቦታውን ፡ ማጠር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፱ ። ወሰን ።**

ወሰኖቹ፡ የሚያጠራጥሩ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ጎረቤቱ ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባለሀብት ፡ (ባለርስት) ፡ ወሰኖቹን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ርዳታ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፲ ። የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሀብትነት ።**

የመሬት ፡ ሀብትነት ፡ (የመሬት፡ ርስትነት)፡ ማለት ፡ መሬቱን ፡ ሥራ ፡ ለማስያዝ ፡ ጠቃሚ ፡ እስከ ፡ ሆነው ፡ ጥልቀት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የውስጥ፡ሀብትነትን፡ ጭምር ፡ የያዘ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፲፩ ። የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ቍፈራ ፡ ወይም ፡ ሥራ ።**

በራሱ፡ መሬት ፡ ውስጥ፡ ሥራዎችን ፡ የሚያደራጅ ፡ ወይም ፡ የሚቆፍር ፡ ባለሀብት ፡ (ባለርስት) ፡ የጎረቤቶቹን ፡ መሬት ፡ ማናጋት ፡ አይገባውም ፤ እንደዚሁም ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ የሥራዎቹን ፡ ጥንካሬ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ እንዳያገኛቸው ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፲፪ ። የመሬት ፡ በላይ ፡ ሀብትነት ።**

የመሬት ፡ ሀብትነት ፡ ማለት ፡ መሬቱን ፡ ሥራ ፡ ለማስያዝ ፡ ጠቃሚ ፡ እስከ ፡ ሆነውም ፡ ጥልቀት ፡ ድረስ ፡ ያለውንና ፡ የወደ ፡ ላይ ፡ ሀብትነትን ፡ የያዘ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፲፫ ። ስለ ፡ ቅርንጫፎችና ፡ ስለ ፡ ዛፍ ፡ ሥሮች ።**

(፩) ማናቸውም፡ ሰው ፡ ወደ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ተዘርግተው ፡ የገቡትን ፡ የጎረቤቱን ፡ የዛፎች፡ቅርንጫፎች፡በአንድ፡ወር፡ውስጥ፡እንዲቈርጥ፡በዳኛ፡ማስገደድ፡ይችላል።

(፪) ያንድ፡ መሬት ፡ባለሀብት ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ ሳይኖርበት ፡ ከወሰኑ ፡ መሥመር ፡ አልፎ ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ በውስጥ ፡ የሚሄዱትን ፡ ሥሮች ፡ ሊቈርጣቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፫ ። ስለ ፡ መሥራትና ፡ ተክል ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ።**

ባለሀብቱ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ለርሱ ፡ መልካም ፡ መስለው ፡ የታዩትን ፡ ሥራ ዎችና ፡ ተክሎች ፡ ለመሥራትና ፡ ለማቋቋም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፬ ። በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መብት ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ባንድ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ውስጥ ፡ የተቋቋሙ ፡ ሥራዎችና ፡ ሌሎች ፡ የጥ በብ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ከመሬቱ ፡ ጋራ ፡ ነዋሪነት ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የተያያዙ ፡ ሁሉ ፡ ሌላ ፡ ባለሀብት ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) የዚሁ ፡ ባለሀብት ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ንብረት ፡ የአገልግሎት ፡ ግዴታ ፡ ባለቤቶች ፡ ንብረቶች ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፭ ። (፪) የተጠበቁ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ያንድ ፡ ቤት ፡ ፎቆችን ፡ ወይም ፡ ክፍሎችን ፡ የጋራ ፡ ሀብትነት ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ስለ ፡ ተሠሩት ፡ ሕንጻዎች ፡ ጕዳይ ፡ የተነገ ረው ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የተ ጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፮ ። በመሬቱ ፡ ላይ ፡ መግባትን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

ባለሀብቱ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ማንም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፯ ። አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ መግባት ። (፩) ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ጕዳት ፡ ወይም ፡ አደጋ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ካልገባ ፡ በቀር ፡ ሊደርስ ፡ ከሚ ችል ፡ ጕዳት ፡ ወይም ፡ ከተቃረበ ፡ አደጋ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ሊጠብቀው ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህ ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ እንደ ዚህ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ የሚደረገውን ፡ እቦታው ፡ ላይ ፡ መግባት ፡ መቻል ፡ አለበት ፤ (መፍቀድ ፡ አለበት) ።

(፪) ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጕዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሀብቱ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፰ ። (፪) አጥር ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማደስ ።**

(፩) በአንድ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የተሠራውን ፡ አጥር ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ለማደስ ፡ በጎረ ቤት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ማለፍ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ጎረቤት ፡ የሆነው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ መተላለፍን ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

(፪) በዚህ ፡ የተነሣ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሀብቱ ፡ ኪሣራ ፡ ለመ ጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፱ ። (፫) የጠፉ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ እንስሶች ።**

(፩) በተፈጥሮ ፡ ኀይል፡ ወይም፡ በድንገተኛ፡ ሁኔታ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ዕቃዎች፡በሌላ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ከብ ቶች ፡ እንደ ፡ ንብ ፡ መንጋ ፤ እንደ ፡ ዶሮ ፡ የመሰሉ ፡ እንስሶች ፡ ተላልፈው ፡ እን ዲሁ ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመብት ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እንዲፈልጓቸውና ፡ እንዲወስዷቸው ፡ የመሬቱ ፡ ባለሀብት ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ መግባትን ፡ መፍ ቀድ ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመሬቱ ፡ ባለሀብት ፡ ከዚሁ ፡ ባለመብት ፡ ላይ ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅና ፡ ኪሣራው ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ ዕቃውን ፡ ወይም ፡ እንስሳውን ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፫) ባለመሬቱ ፡ ራሱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፈልጎ ፡ የጠፋውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡ ባለመብት ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ እንዳይገባ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፳ ። ስለ ፡ መተላለፊያ ፡ ቦዮችና ፡ ቧንቧዎች ።**

(፩) ባለርስቱ ፡ የሚደርስበትን ፡ ኪሣራ ፡ በሙሉና ፡ አስቀድሞ ፡ካገኘ ፡ በራሱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለሌሎች ፡ መሬቶች ፡ ጥቅም ፡ የሚሆኑ ፡ የውሃ ፡ ቧንቧዎች፡የጋዝ፡ መተላለፊያዎች ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መሥመሮችና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ እንዲተላለፉ ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

(፪) አሠራሩም፡ ሌላ ፡ መሬት፡ የአገልግሎት ፡ ግዴታ ፡ ላለበት ፡ መሬት ፡ የበለጠ፡ በሚመች ፡ አኳኋንና ፡ ከሁሉ ፡ ያነሰ ፡ ኪሣራ ፡ በሚያስከትል ፡ ዐይነት ፡ መፈ ጸም ፡ አለበት ።

(፫) የዚህም፡ መሬት፡ ባለቤት ፡ የተቋቋመው ፡ ሥራ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ እንዲዘዋወርና ፡ እንዲቋቋም ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፳፩ ። የመተላለፍ ፡ መብት ፡ (፩) መሠረቱ ።**

መሬቱ ፡ የተዘጋበት ፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ለመጠቀም ፡ ለሕዝብ ፡ በሚያገለግ ለው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በቂ ፡ ያልሆነ ፡ መ[illegible]ጫ ፡ ያለ[illegible] ፡ ባለሀብት ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችለው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ ግምቱን ፡ ከከፈለ ፡ አስፈላጊ[illegible]ን ፡ መተላለ ፊያ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጎረቤቱን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፳፪ ። (፪) በእጅ ፡ ያለ ፡ መሬት ።

(፩) የመተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ መብት ፤ የመተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ እንዲወጣ ፡ በመሬቱ ፡ ተፈጥሮ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ ሊጠየቅ ፡ በሚችለው ፡ ጎረቤት ፡ ላይ ፡ ይፈጸማል ።

(፪) ለዚህም ፡ ነገር ፡ የመሬቶቹና ፡ የመተላለፊያዎቹ ፡ ሁኔታ ፡ መተላለፊያ ፡ የታጠረበት ፡ ( የተከለለው ) ፡ ጠቃሚነትና ፡ መተላለፊያ ፡ እንዲወጣበት ፡ የተጠየቀው ፡ መሬት ፡ በመተላለፊያው ፡ መንገድ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስበትን ፡ ጉዳት ፡ ማመዛዘን ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፳፫ ። (፫) የመሬት ፡ ክፍያ ፡ ሲሆን ።

መሬቱ ፡ መተላለፊያ ፡ ያጣበት ፡ ምክንያት ፡ መሬቱ ፡ ተከፍሎ ፡ በመሸጡ ፡ በልዋጭ ፡ በክፍያ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመተላለፊያው ፡ መንገድ ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ በተፈጸሙባቸው ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይጠየቅ ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፲፪፻፳፬ ። (፬) አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ።

የመተላለፊያ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ባለጥቅም ፡ በዚሁ ፡ መብቱ ፡ ቢገለገል ፡ መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ ለወጣበት ፡ መሬት ፡ የሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ አነስተኛ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ እንዲሠራና ፡ እንዲጠብቅ ፡ ሊገደድ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፳፭ ። በባለሀብትነት ፡ መብት ፡ አለመጠን ፡ ስለ ፡ መገልገል ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) ባለሀብቱ ፡ በመብቱ ፡ በሚገለገልበት ፡ ጊዜ ፡ የጎረቤቱ ፡ ርስት ፡ ጥቅም ፡ የሚቀነስበትን ፡ ወይም ፡ የሚጎዳበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ነገር ፡ ከመሥራት ፡ መጠበቅ ፡ ይገባዋል ።

(፪) በተለይም ፡ ጢስን ፡ ወይም ፡ ጠለሸትን ፡ ወይም ፡ በጉርብትና ፡ አኗኗር ፡ ሊታገሡት ፡ ከሚቻለው ፡ በላይ ፡ የሆኑትን ፡ ሽታዎች ፤ ጩኸቶች ፡ ወይም ፡ ንውጽውጽታዎች ፡ ወደ ፡ ጎረቤት ፡ እንዲሄድ ፡ ማድረግ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

(፫) እነዚህም ፡ የሚወሰኑት ፡ የአገሩን ፡ ልማድ ፡ በመከተልና ፡ እንዲሁም ፡ የመሬቱን ፡ አቀማመጥና ፡ የተፈጥሮውን ፡ ዐይነት ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፪፻፳፮ ። (፪) ስለ ፡ ቅጣት ።

አንድ ፡ ባለሀብት ፡ በመብቱ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመገልገሉ ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ ጉዳት ፡ እንደሚደርስበት ፡ የሚያሠጋው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ የኪሣራ ፡ መጠየቁ ፡ መብት ፡ ሳይነካበት ፡ የተባለው ፡ ባለሀብት ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰበትን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲያደርግ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ያደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የተሠጋበት ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲፈጽም ፡ ሊከሰው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፶፭ ። በባለሀብትነት ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የተሰጡት ፡ የመብት ፡ ወሰኖች ፡ የማይ ታለፉ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

(፩) የባለሀብቶች ፡ ልዩ ፡ መብቶችን ፡ የሚቀንሱት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገሩት ፡ በርስት ፡ መዝገብ ፡ ባይጻፉም ፡ እንዳሉ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

(፪) በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነት ፡ ሊሰረዙ ፡ ወይም ፡ ሊለዋወጡ ፡ ሊሻሻሉ ፡ አይቻልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ውሃዎች ፡ ባለሀብትና ፡ በውሃዎች ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፶፮ ። ለኅብረት ፡ ኑሮ ፡ ጥቅም ፡ በቀደምትነት ፡ አስፈላጊዎች ፡ ስለ ፡ መሆቸው ።**

(፩) ፈሳሾችም ፡ ቢሆኑ ፡ ወይም ፡ ባይሆኑ ፡ ውሃዎች ፡ ለኅብረት ፡ ኑሮ ፡ ጥቅም ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የተመደቡ ፡ ናቸው ።

(፪) ለኅብረት ፡ ኑሮ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊዎች ፡ እንደ ፡ መሆናቸውም ፡ መጠን ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚጠባበቋቸውና ፡ የሚጠብቋቸው ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፶፯ ። የውሃ ፡ ባለሀብት ፡ ስለ ፡ መሆን ።**

ውሃ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ በተሠራው ፡ በውሃ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ በኵሬ ፡ ወይም ፡ ለውሃ ፡ በተበጀ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ሁኖ ፡ ዐውቆ ፡ የማይፈስ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፶፰ ። የውሃ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ውሃው ፡ የወል ፡ የጋርዮሽ ፡ ሀብት ፡ እንዲሆን ፡ ወይም ፡ ለጥቅም ፡ እንዲውል ፡ የሚያደርጉ ፡ ሁኔታዎችና ፡ እንዲሁም ፡ የውሃው ፡ የንብረት ፡ ግዴታና ፡ የመገልገል ፡ መብቶች ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ።

(፪) የውሃ ፡ መገደቢያ ፡ ወይም ፡ ማድረጊያ ፡ የሆኑትን ፡ የኅብረት ፡ ሀብቶችን ፡ ባለሀብትነት ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፫) እንደዚሁም ፡ የልዩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎችና ፡ በጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ለአንድ ፡ ክፍል ፡ በተሰጡት ፡ የአስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፶፱ ። ስለ ፡ ዳኞች ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ውሃው ፡ ሊጠቅማቸው ፡ በሚችል ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ፍርዳቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ለሀብትነት ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ በመስ

ጠት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑት ፡ ጥቅሞች ፡ የሚስማሙበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው ።

(፪) ዳኞቹ፡ በሚሰጡት፡ ውሳኔ ፡ ምናልባት ፡ ከባለሀብትነት ፡ መብቶች ፡ ላይ፡ የደ ረሱ ፡ ጕዳቶች ፡ ቢኖሩ ፡ በሕግ ፡ የተደነገገ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ የጉዳት ፡ ኪሣራን ፡ የሚያሰጡ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፷፪ ። ውሃውን ፡ ለቤት ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ፤ (፩) የባለሀብቱ ፡ መብቶች ።**

የአንድ ፡ መሬት፡ ባለሀብት ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገ ኘውን ፡ ውሃና ፡ በመሬቱ ፡ አቋርጦ ፡ የሚያልፈውን ፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ወሰን ፡ የሚሄደውን ፡ ውሃ ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፤ ለቤቱ ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ለማዋልና ፡ መንጋ ውን ፡ ሊያጠጣበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፷፫ ። (፪) የጎረቤቶች ፡ መብት ።**

ጎረቤቶች ፡ ከውሃው ፡ ዋጋ ፡ አጅግ ፡ የበዛ ፡ የሆነውን ፡ የማይመዛዘን ፡ ገንዘብ ፡ ካልከፈሉ ፡ በቀር ፡ ውሃ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ የማያገኙ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜና ፡ የውሃው ፡ ባለ ሀብትም ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የውሃው ፡ ብዛት ፡ ለራሱ ፡ ቤት ፡ አስፈላጊ፡ ከመሆን ፡ አልፎ ፡ የሚተርፍ ፡ በሆነ፡ጊዜ ፡ ለጎረቤቶቹ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውንና ፡ ከብ ቶቻቸውን ፡ የሚያጠጡበትን ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ውሃ ፡ መስጠት ፡ አለበት፡

**ቍ ፡ ሺ፪፻፷፬ ። (፫) በጎረቤቶቹ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ደንብ ።**

(፩) ጎረቤቶቹ ፡ በዚህ ፡ ባላቸው ፡ መብት ፡ የሚገለገሉበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለ ክት፡ ደንብ፡ ለአእምሮ፡ ተስማሚ፡ በሆነ፡ ዐይነት፡ ባለሀብቱ፡ መወሰን፡ ይችላል ።

(፪) ለጎረቤቶቹ ፡ በታወቀላቸው ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ በመገልገላቸው ፡ ምክንያት ፡ የመሬት ፡ ባለሀብት ፡ በመሬቱ ፡ የሚገለገልበት ፡ ወይም ፡ የሚጠቀምበት ፡ ነገር፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ዐይነት ፡ የተቀነሰ ፡ ወይም ፡ የታወከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ጎረ ቤቶቹ ፡ የሚገባውን ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጡት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፷፭ ። ስለ ፡ ተከለከሉ ፡ ሥራዎች ።**

(፩) በጕድጓድ፡ ወሃ፡ በምንጭ ፡ ውሃ ፡ ወይም ፡ በፈሳሽም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማይ ፈስ ፡ በሌላ ፡ ውሃ ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፤ ይህን ፡ የሚገለገሉ በትን ፡ ውሃ ፡ ለማበላሸት ፡ የሚችል ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚደረግ ፡ የእ ድፍ ፡ ውሃ ፡ መሄጃ ፡ እንደ ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ እንዳ ይሠራ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህ፡ የተጠቀሰው፡ ሥራ ፡ የባለጥቅሞቹን ፡ መብት ፡ በመናቅ ፡ ተሠርቶ፡እንደ ፡ ሆነም ፤ የተባሉት፡ ባለጥቅሞች ፡ ሥራው ፡ እንዲፈርስ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፯ ። ስለ ፡ መስኖ ፡ ውሃ ፡ (፩) የባለሀብቱ ፡ መብት ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ አቋርጦ ፡ የሚያልፈውን ፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ የሚወርደውን ፡ ውሃ ፡ መሬቱን ፡ ለማጠጣት ፡ ሊገለገልበት ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ መብቱ ፡ ለቤት ፡ አገልግሎት ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ወይም ፡ መንጋቸውን ፡ ለማጠጣት ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ወይም ፡ መሬቱን ፡ አልፎ ፡ ከመሬቱ ፡ በታች ፡ በሚወርደው ፡ ውሃ ፡ የሚጠቀሙትን ፡ (የሚገለገሉትን ፡) ሰዎች ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፰ ። (፪) ለቤት ፡ አገልግሎት ፡ የሚሆን ፡ ውሃ ፡ ቀደምትነት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) መሬትን ፡ በመስኖ ፡ በማጣጣት ፡ የሚደረገው ፡ የውሃ ፡ መገልገል ፡ ይህንኑ ፡ ውሃ ፡ ለቤት ፡ አገልግሎት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ የሚገለገሉበትን ፡ ሰዎች ፡ የሚጎዳ ፡ ወይም ፡ ይጎዳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ በውሃው ፡ ለመገልገል ፡ መብት ፡ አለን ፡ የሚሉበትን ፡ ለማስረዳት ፡ በቻሉ ፡ ጊዜ ፡ የተባለውን ፡ አዲሱን ፡ የውሃ ፡ መገልገል ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ።

(፪) በዚሁ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በውሃው ፡ ለመጠቀሚያ ፡ የሚሆኑ ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ የታወቁ ፡ ትልልቅ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ የማቋቋም ፡ ሥራዎች ፡ ተፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመብቶቹ ፡ ለቤት ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ውሃውን ፡ ለሌላ ፡ ጥቅም ፡ ለማዋል ፡ በወሃው ፡ ለመጠቀም ፡ ያገኙት ፡ መብት ፡ አላቸው ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፱ ። (፫) ቅሬት ።**

ዳኞች ፡ ከወደ ፡ ታች ፡ የሚገኙት ፡ ባለመሬቶች ፡ በወሃው ፡ ለመጠቀም ፡ ያገኙት ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ ያወቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ያገኙትን ፡ መብታቸውን ፡ በሚጎዳው ፡ መጠን ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የተጀመሩት ፡ ወይም ፡ የተፈጸሙት ፡ ሥራዎችና ፡ የተቋቋሙት ፡ ነገሮች ፡ እንዲቋረጡ ፡ ወይም ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያዝዛሉ ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷ ። (፬) ለባለሀብቱ ፡ ስለሚገባው ፡ ኪሣራ ።**

ከወደ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ በላዩ ፡ አቋርጦ ፡ በሚያልፈው ፡ ወይም ፡ በወሰኑ ፡ ላይ ፡ በሚሄደው ፡ ውሃ ፡ እንዳይገለገል ፡ በሚወሰነው ፡ ክልከላ ፡ ምክንያት ፡ መሬቱን ፡ ለማልማት ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ በልማቱ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ላለው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ኪሣራ ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶ ። (፫) የኪሣራው ፡ ልክ ።**

(፩) የዚህን ፡ የኪሣራውን ፡ ልክ ፡ ዳኞች ፡ በርትዕ ፡ መሠረት ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ዳኞች ፡ ስለ ፡ ኪሣራው ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጡት ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ በተለይም ፡ በውሃው ፡ እንዳይገለገል ፡ በመከልከሉ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከሚገኘው ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ የተቀነሰውን ፡ ወደ፡ታች ፡ ያሉት ፡ ሰዎችም ፡ በውሃው ፡ ከመገልገላቸው ፡ የተነሣ ፡ የሚያገኙትን ፡ ጥቅም ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ኪሣራው ፡ በቅን ፡ ልቡናና ፡ ከመሬቱ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ያሉት ፡ በውሃው ፡ የሚገለገሉት ፡ ሳይቃወሙዋቸው ፡ የተሠሩትንና ፡ ዳኞች ፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ያደረጉዋቸውን ፡ ሥራዎችና ፡ የተቋቋሙትን ፡ ነገሮች ፡ ዋጋ ፡ የሚጨምር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፩ ። (፬) ባለሥልጣን ፡ ዳኞች ።**

ከዚህ፡ በላይ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች፡ የተመለከቱትን፡ ክርክሮች ፡ ለመወሰን፡ ሥልጣን፡ያላቸው፡ ዳኞች፡ እነዚህ፡ ከዚህ፡ በላይ፡ የተነገሩት፡ ሥራዎች፡ በተደቀኑበት፡ ወይም ፡ በተፈጸሙበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስፍራ ፡ የሚዳኙት ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፪ ። ውሃውን ፡ ለእንዱስትሪ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ማዋል ። (፩) የባለሀብቱ ፡ መብት ።**

(፩) የመሬቱ ፡ ባለሀብት ፡ መሬቱን ፡ አቋርጦ ፡ በሚያልፈው፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ በሚሄደው ፡ ውሃ ፡ ወፍጮን ፡ ለመትከል ፡ የልብስ ፡ ማጠቢያን ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ መታጠቢያን ፡ የመሳሰለ ፡ የእንዱስትሪን ፡ ወይም ፡ የንግድን ፡ ድርጅት ፡ በማቋቋም ፡ ሊገለገልበት ፡ ይችላል ።

(፪) እርሱም ፡ ውሃው ፡ ከመሬቱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ውሃውን ፡ ያልተበላሸና ፡ ወሃው ፡ ለሚሄድላቸው ፡ ሰዎች ፡ አገልግሎት ፡ ለመሆን ፡ እንዲችል ፡ አድርጎ ፡ መልቀቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፫ ። (፪) የነዚህ ፡ መብቶች ፡ አወሳሰን ።**

(፩) ባለሀብቱ ፡ ውሃው ፡ ከመሬቱ ፡ ወደ ፡ ውጭ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ውሃውን ፡ ያልለቀቀው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ወይም ፡ አበላሽቶ፡ ወይም፡ ለአንድ ፡ አገልግሎት ፡ የማይሆን ፡ አድርጎ፡ የለቀቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ስለ ፡ መስኖ ፡ ውሃ ፡ አገልግሎት ፡ በሚናገሩት፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች፡ይሆናሉ ።

(፪) ይህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ለሚገኘው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ከወደ፡ታች ፡ ያሉት ፡ ባለመብቶች ፡ ሳይቃወሙ ፡ ለተፈጸሙትና፡ ዳኞች፡ ከአገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ለአደረጓቸው ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ለተቋቋሙት ፡ ድርጅቶች ፡ ዋጋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እንዳች ፡ ኪሣራ ፡ አይከፈለውም ።

BACK



**ቍ ፡ ሺ፪፻፴፱ ፡፡ ከውሃ ፡ ስለሚገኝ ፡ ኀይል ፡፡**

የውሃውን ፡ ኀይል ፡ በማከፋፈል ፡ በማመላለስ ፡ ወይም ፡ በመሸጥ ፡ ወራጆች ፡ የሆኑትን ፡ ውሃዎች ፡ ለማከናወን ፡ የሚችሉት ፡ ከመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ኮንሴሲዮን ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፪፻፵ ፡፡ ስለ ፡ ዝናም ፡ ውሃ ፡፡**

(፩) የአንድ ፡ ቤት ፡ ባለሀብት ፡ (የቤት ፡ ጌታ)፡ የጣራውን ፡ የዝናም ፡ ውሃ ፡ በራሱ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እንዲወርድ ፡ ዐይነት ፡ እንጂ ፡ በጎረቤት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በማይወርድበት ፡ ዐይነት ፡ አድርጎ ፡ ለመሥራት ፡ ይገደዳል ፡፡

(፪) የሚያስፈልግም፡ ሲሆን፡ የዝናሙ ፡ ውሃ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ተበጀው ፡ የሕዝብ ፡ የወሃ ፡ መሄጃ ፡ በአሸንዳ ፡ ወይም ፡ በቧምቧ ፡ እንዲያመራ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፪፻፵፩ ፡፡ ከወደ ፡ ታች ፡ የሚገኘው ፡ መሬት ፡ ግዴታዎች ፡፡**

(፩) ከወደ፡ ታች፡ የሚገኙ ፡ መሬቶች፡ የሰው ፡ እጅ፡ ሳያግዘው ፡ በተፈጥሮው፡ ከወደላይ ፡ ከሚገኙት፡ መሬቶች፡ የሚወርደውን ፡ ውሃ፡ በግድ ፡ የሚቀበሉ ፡ ናቸው ፡፡

(፪) ከወደ፡ታች፡ የሚገኘው ፡ የመሬት፡ ባለሀብት፡ እንደዚህ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ የሚፈሰውን ፡ ውሃ ፡ የሚያግድ ፡ ግድብ ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ፡፡

(፫) ከወደ፡ ላይ፡ የሚገኘው፡ የመሬት፡ ባለሀብት ፡ ከወደ፡ ታች ፡ የሚገኘውን ፡ የመሬት ፡ ግዴታ ፡ የሚያከብድ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፪፻፵፪ ፡፡ የውሃ ፡ መውረጃውን ፡ የመጥረግ ፡ (የመሠንጠቅ)፡ ሥራዎች ፡፡**

(፩) ከወደ፡ ላይ፡ የሚገኘው፡ የመሬት፡ ባለሀብት ፡ በመሬቱ፡ ላይ፡ የውሃ፡ መውረጃ፡ የመጥረግ፡ (የመሠንጠቅ) ፡ ሥራዎችን ፡ የፈጸመ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ከወደ፡ ታች ፡ የሚገኙት ፡ የመሬቶች ፡ ባለሀብቶች ፡ ከተባለው ፡ መጥረግ ፡ የተነሣ ፡ በመሬታቸው ፡ ላይ ፡ የሚወርደውን ፡ ውሃ ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፈላቸው ፡ መቀበል ፡ አለባቸው ፡፡

(፪) ከወደ፡ ታች፡ የሚገኙት፡ የመሬቶች ፡ ባለሀብቶች፡ በዚህ፡ ወደ፡ እነርሱ፡ በሚወርደው ፡ ውሃ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስባቸውን ፡ ጉዳት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ አነስተኛ ፡ እንዲሆን ፡ ከወደ ፡ ላይ፡ የሚገኘው ፡ የመሬት ፡ ባለሀብት፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ ማድረግና ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡፡

(፫) ከወደታች ፡ የሚገኙት፡ የመሬቶች፡ ባለሀብቶች ፡ ወራጅ፡ ውሃ፡ ቤቶች ፡ ባሉበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በቤቶች ፡ አጠገብ ፡ በሚገኝ ፡ ወለል ፡ ወይም ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አቋርጦ ፡ የሚያልፍ ፡ ሲሆን ፡ ውሃው ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ በሚደረግ ፡ ቦይ ፡ እንዲሄድ ፡ ሲሉ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የመሬቶች፡ ባለሀብቶች ፡ ማስገደድ ፡ ይችላሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፲፪፻፺፰ ። ስለ ፡ አዳዲስ ፡ ምንጮች ።**

መሬትን ፡ በመቈፈር ፡ ወይም ፡ የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሥራዎችን ፡ በመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብት ፡ ከመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ ውሃ ፡ ያመነጨ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፺፱ ። ውሃን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ፤ (፩) የባለሀብቱ ፡ መብት ።**

(፩) ባለሀብቱ ፡ መሬቱን፡ በውሃ፡ ለማጠጣት ፡ ወይም ፡ ለማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አገልግሎት ፡ በመሬቱ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ በሚሄደው ፡ ውሃ ፡ ለመጠቀም ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሃውን ፡ ለመውሰድ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ጎረቤት ፡ በሆነው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለማስደገፍ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እነዚህን፡ ሥራዎች፡ ለመፈጸምና ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ለመያዝ ፡ በዚህ ፡ በጎረቤቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለማሳለፍ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፫፻ ። ስለሚገባው ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ለዚህ፡ ለውሃ፡ መከተሪያ ፡ የተሠራው ፡ ግድብ ፡ ከጎረቤቱ ፡ መሬት ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ነዋሪነት ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳጣው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጎረቤቱ ፡ ኪሣራ ፡ የሚገባው ፡ ይሆናል ።

(፪) እንዲሁም፡ በግድቡ ፡ ሥራዎች፡ ወይም ፡ ሥራዎቹን ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ በመጠበቅ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ሥራዎቹ ፡ ተሠርተው ፡ የሚቈዩበት ፡ ጊዜ ፡ በመርዘሙ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ትልቅነት ፡ ምክንያት ፡ ጎረቤቱ ፡ በመሬቱ ፡ በሚያገኘው ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ሁከት ፡ ከደንበኛው ፡ የጉርብትና ፡ ሁከት ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራ ፡ የሚገባው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፩ ። በግድቡ ፡ ስለ፡ መጠቀም ።**

(፩) በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ግድብን ፡ ለማስደገፍ ፡ የተጠየቀው ፡ አዋሳኙ፡ ጎረቤት ፡ ለሥራውና ፡ ሥራውን ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚወጣውን ፡ ኪሣራ ፡ አጋማሽ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ ግድቡ ፡ ለጋርዮሽ ፡ እንዲያገለግል ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ለጋርዮሹ ፡ እንዲያገለግል፡ የተጠየቀው ፡ ሥራዎቹ ፡ ከተጀመሩ፡ ወይም ፡ ከተፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከወንዙ ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ያሉትን ፡ መሬቶች ፡ ለማጠጣት ፡ ሲባል ፡ የግድቡ ፡ የመለዋወጥ ፡ ሥራዎች ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ትርፍ ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ጠያቂው ፡ ብቻውን ፡ መቻል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፪ ። ስለ ፡ መስኖ ፡ ቦይ ፡ (፩) የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ መብት ።**

ለቤቱ ፡ አስፈላጊነት፡ ወይም ፡ መሬቱን፡ ለማጠጣት ፡ ወይም ፡ ለማናቸውም፡ ለሌላ ፡ አገልግሎት ፡ በመሬቱ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ በማይሄድ ፡ ወይም ፡ በመሬቱ ፡

ላይ ፡ አቋርጦ፡ በማያልፍ ፡ ውሃ፡ ለመገልገል ፡ የፈለገ ፡ ባለሀብት ፡ ለባለርስት ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈል ፡ ትክክለኛ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተደርጎ ፡ ይህን ፡ የተባለውን ፡ ውሃ ፤ አማካይነት ፡ ባላቸው ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ መሬቱ ፡ ለማሳለፍ ፡ መብቱን ፡ ከዳኞች ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፵፫ ። (፪) የቦዮች ፡ ሥራ ፡ የሚሄድበት ፡ መሥመር ።**

(፩) ቦዮቹ ፡ የሚከተሉት ፡ መሥመር ፡ አቋቋማቸውና ፡ ዐይነታቸው ፡ የሚወሰ ነው ፡ ለጕዳዩ ፡ አካባቢ ፡ የሆኑትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በማየት ፡ ነው ።

(፪) የቦዮቹ፡ ሥራ፡ ቦዮቹ ፡ የሚያልፉባቸው ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብቶች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ፡ የሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ከሁሉ ፡ አነስተኛ ፡ እንዲሆን፡ በማድረግ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፫) የቦዮችም፡ አመራር፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ቤቶች ፡ በቆሙበት ፡ ቦታ ፡ እንዲሁም፡ በቤቶች ፡ አጠገብ ፡ በሚገኘው ፡ ወለል ፡ ወይም ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እን ዳይሄድ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፵፬ ። (፫) የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ቦዩ ፡ በመሬታቸው፡ ላይ ፡ ለሚያልፍባቸው፡ ባለርስቶች ፡ አንድ ፡ ኪሣራ ፡ ይከፈላቸዋል ።

(፪) የዚህንም ፡ የኪሣራ፡ ልክ ፡ ለመወሰን፡ ባለመሬቶቹ ፡ ለዘወትር ፡ እንዳይጠቀ ሙበት ፡ የተደረገው ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ ይገመታል ።

(፫) ከዚህም፡ በቀር፡ ቦዩን ፡ በመሥራት ፡ ሥራውን ፡ በመጠበቅ ፡ ምክንያት ፡ ባለ መሬቶች፡ ከመሬታቸው ፡ በሚያገኙት ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ሁውከት ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፵፭ ። በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኝ ፡ ውሃ ።**

(፩) በመሬት፡ ውስጥ፡ የታፈነና ፡ ወንዝነት ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ውሃ ፡ የመንግሥት ፡ (የሕዝብ) ፡ ንብረት ፡ ነው ።

(፪) ማንም ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ከመቶ ፡ ሜትር ፡ አብልጦ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ጕድጓድ ፡ ለመቈፈር ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፵፮ ። ስለ ፡ ዓሣ ፡ ማጥመድና ፡ በጀልባ ፡ ስለ ፡ መሄድ ።**

(፩) ዓሣን፡ የማጥመድ፡ መብቶች ፡ በልዩ፡ ሕግ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው።

(፪) በፈሳሽ፡ ውሆችና፡ በሐይቆች ፡ ላይ ፡ በጀልባ ፡ የመሄድ ፡ መብቶችም ፡ እን ደዚሁ ፡ የተወሰኑ፡ ናቸው ።

## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፤ በአላባ ፡ ስለ ፡ መጠቀምና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የጋራ ፡ ባለሀብትነት ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፯ ። መሠረቱ ።**

(፩) የአንድ ፡ ንብረት ፡ ሀብትነት ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ፤ እነዚህም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ናቸው ።

(፪) የእርሻ ፡ ኅብረቶችንና ፡ በዐዋጅ ፡ የታወቁትን ፡ የባለርስቶች ፡ ማኅበር ፡ ስለ ሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ በንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፰ ። የጋራ ፡ ሀብት ፡ ደንብ ፡ አመራር ።**

(፩) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚወሰኑት ፡ የጋራ ፡ ሀብቱ ፡ በተቋቋመበት ፡ ውል ፡ መሠረትና ፤ የሕጉ ፡ ግልጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ስምምነት ፡ ያልኖረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ስምምነቶቹ ፡ ያልተሟሉና ፡ የማይበቁ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፶፱ ። የእኩልነት ፡ አገማመት ።**

የያንዳንዶቹ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ድርሻ ፡ ሀብት ፡ እኩል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷ ። በድርሻው ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ መብት ።**

(፩) እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ የራሱን ፡ ድርሻ ፡ ለመሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ከያንዳንዶቹ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የባለዕዳውን ፡ ድርሻ ፡ ለመያዝ ፡ ይችላሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ፲፪፻፷፩ ። ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ።**

(፩) የጋራ ፡ ባለሀብቶች፣ የሆኑ ፡ ሰዎች፣ ያልተከፈለውን ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ከማንኛውም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በፊት ፡ ቀዳሚ ፡ ሆነው ፡ በግዥ ፡ የማስቀረት ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) ይህ፣ በቀዳሚነት፣ የማስቀረት ፡ መብት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለሚውልበት ፡ አኳኋን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ጸንቶ ፡ ይሠራበታል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፪ ። ድርሻ ፡ ሀብትን ፡ ስለ ፡ መተው ።**

(፩) ከጋራ፣ ባለንብረቶቹ፣ አንዱ ፡ የአንድነት ፡ ከሆነው ፡ ሀብት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን፣ ድርሻ ፡ በፈቃዱ ፡ የለቀቀ ፡ መሆኑን ፡ የገለጸ ፡ እንደ፣ ሆነ ፡ ይህ ፡ የተለቀቀው ፡ ድርሻ ፡ የቀሩትን ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶች ፡ ድርሻ ፡ ያሳድጋል ።

(፪) ድርሻውን፣ የለቀቀው፣ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ሀብቱን ፡ ከመልቀቁ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ነበረበት ፡ ዕዳ ፡ ኀላፊነት ፡ አይቀርለትም ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፫ ። የአንድነት ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መገልገል ።**

እያንዳንዱ ፡ የጋራ፣ ባለሀብት ፤ ሀብቱ ፡ እንዲያገለግል፣ በተመደበበት ፡ ነገር፣ መሠረትና ፡ ከሌሎቹ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ጋራ ፡ ተስማሚ ፡ በሚሆንበት ፡ መንገድ ፡ የአንድነት ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ሊገለገል ፡ (ሊጠቀም) ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፬ ። የንብረቱ ፡ ፍሬ ።**

(፩) ካልተከፈለው፣ ንብረት፣ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ ጥቅም ፡ እንዲሁም ፡ ያልተከፋፈለ ፡ ነው ።

(፪) ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ክፍያ ፡ እንዲደረግ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፭ ። የንብረቱ ፡ አስተዳደር ። (፩) በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ስለ ፡ መሠራቱ ።**

(፩) የጋራ፣ ባለሀብቶቹ፣ የሀብታቸውን ፡ አስተዳደር ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚመሩት ፡ በአንድነት ፡ ነው ።

(፪) የጋራ፣ የሆነ፣ ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ፡ በሚመለከተው ፡ ጒዳይ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ወ ሳኔ ፡ የሚያደርጉት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ከሀብቱ ፡ አጋማሽ ፡ የበለጠ ፡ ቍጥር ፡ ድርሻ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፮ ። (፪) የሁሉን ፡ ስምምነት ፡ የሚጠይቁ ፡ ጒዳዮች ።**

የጋራ፣ የሆነውን ፡ ንብረት፣ ለመሸጥ ፤ ለማስተላለፍ፣ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ለማስያዝ ፡ ወይም ፡ የተመደበበትን ፡ አገልግሎት ፡ ለመለወጥ ፡ ሲሆን ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ስምምነት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፯ ። (፫) ወጪ ።**

ለንብረቱ ፡ ማስተዳደሪያ፤ ለግብርና ፡ ለሌሎችም ፡ ጕዳዮች ፡ የሚደረገውን፡ ወጪ ፡ ወይም ፡ ከአንድነቱ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ የሚ ችሉት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶች ፡ በየድርሻቸው ፡ መጠን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፰ ። ለንብረቱ ፡ መጠገኛ ፡ አስፈላጊ ፡ ወጪ ።**

(፩) ከጋራ፡ ባለሀብቶቹ፡ አንዱ ፡ ንብረቱ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ወይም ፡ እንዳይጠፋ ፤ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ወጪ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ ወጪ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲከፍሉት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ፡ ሆነም፡ ወጪው ፡ ለማይጠቅም ፡ ጕዳይ ፡ የወጣ ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ወይም ፡ ወጪ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈለገው ፡ ገንዘቡን ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ወይም፡ራሱ፡ አላፊ ፡ የሚሆንበት ፡ ሰው ፡ ካደረሱት ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማንኛውንም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይቻልም።

(፫) ማንኛውም፡ የጋራ፡ ባለሀብት ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ መሠ ረት ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ድርሻውን ፡ ለቀሩት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ በመልቀቅ፡ ለንብረቱ፡ መጠገኛ፡ ወጪ፡ የሆነውን፡ ገንዘብ፡ አልከፍልም፡ ለማለት ፡ ይችላል።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፱ ። ለንብረቱ ፡ መጠገኛ ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ ፡ ወጪ ። (፩) ጠቅላላ ፡ ደንብ።**

(፩) ከጋራ፡ ባለሀብቶቹ፡ አንዱ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ለንብረቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆኑ ትንና ፡ የንብረቱን ፡ ዋጋ ፡ ለማሳደግ ፡ ጠቃሚ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ለማሳመር ፡ ወጪ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ማንኛውንም ፡ ወጪ ፡ የመጠ የቅ ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ከዚህ፡ ንብረት፡ ጋራ ፡ የተያያዘውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ለይቶ ፡ ለመውሰድና ፡ ዋነ ኛውን ፡ ንብረት ፡ ቀድሞ ፡ በነበረበት ፡ ሁኔታ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፸ ። (፪) ፍሬዎችን ፡ ስለ ፡ ማራባት ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ፍሬን ፡ ለማራባት ፡ ወይም ፡ የተገኘውን ፡ ፍሬ ፡ ወይም ፡ ሰብልን ፡ ለመ ሰብሰብ ፡ ስለ ፡ ተደረጉ ፡ ወጪዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፪) ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ፡ አንዱ ፡ ሳይፈቀድለትም፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ንብረቱን ፡ ለማ ልማት ፤ ወይም ፡ ፍሬውንና ፡ ሰብሉን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ወጪ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍሬው ፡ ወይም ፡ ሰብሉ ፡ ከመከፋፈሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ከዚሁ ፡ ከፍሬውና ፡ ከሰብሉ ፡ ላይ ፡ ለመከፈል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፸፩ ። ያልተከፈለ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ በሐራጅ ፡ የሚሸጥበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ይህን፡ ተቃራኒ፡ የሚሆን ፡ስምምነትም ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ሀብቱ ፡ የሚንቀ ሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ያልተከፋፈለው ፡ ሀብት ፡ በግልጽ ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ፡ ጥያቄ፡ የቀረበው፡ ተስማሚ፡ ባልሆነ፡ ጊዜ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ዳኞች፡ ንብረቱ፡ ከስድስት፡ ወር፡ ለማያልፍ፡ ጊዜ፡ ሳይከፋፈል፡ እንዲቈይ፡ ለማዘዝ፡ ይችላሉ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፸፪ ። ያልተከፋፈለ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ክፍያ ። (፩) መሠረቱ።**

(፩) ሀብቱ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ሀብቱ ፡ እንዲከፋፈል ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፡

(፪) ክፍያው፡ ለሀብቱ፡ ተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ለተመደበበት ፡ ጉዳይ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያስከትል ፡ ተቃዋሚ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የሀብቱን ፡ ባለዋጋነት ፡ በግልጽ ፡ የሚቀንሰው ፤ ወይም ፡ የሀብቱን ፡ ፍሬ ፡ አሰጣጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የሚጎዳው ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ክፍያውን ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ይታዘዛል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፸፫ ። (፪) የዳኞች ፡ ሥልጣን ።**

(፩) የሀብቱ፡ ክፍያ፡ ወይም ፡ በሐራጅ ፡ የመሸጡ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበው ፡ ተስማሚ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ ዳኞች ፡ የተረዱት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ለማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ንብረቱ ፡ ሳይከፋፈል ፡ እንዲቈይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው፡ አጋጣሚ፡ ሁኔታ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለሀብቱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ የሚሆን ፡ ሰው፡ ዳኞች ፡ ይመርጣሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፸፬ ። (፫) ንብረቱ ፡ እንዳይከፋፈል ፡ የማድረግ ፡ ስምምነት ።**

(፩) ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ፡ አንዱ ፡ ንብረቱ ፡ ይከፋፈል፡ ብሎ ፡ የሚጠይቅበት ፡ መብቱ ፤ ይህ ፡ ንብረት ፡ አይከፋፈልም ፡ ተብሎ ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት፡ ወይም፡ በባለሀብቶቹ፡ ሁሉ፡ ስምምነት፡ መሠረት፡ ሊወገድ፡ ይችላል።

(፪) ቢሆንም፡ ከዚህ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ላነሰ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡— ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ አይጸናም ።

(፫) ስምምነቱ ፡ የተደረገው ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የስምምነቱ ፡ ጊዜ ፡ ያልቃል ።

**ቍ ፡ ሺ፪፻፸፭ ። የግልግል ፡ ስምምነት ።**

(፩) የጋራ ፡ ንብረቱ ፡ በተቋቋመበት፡ ውል ፡ ወይም ፡ በጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ስምምነት ፤ በጋራ ፡ ባለንብረቶቹ ፡ መካከል ፡ የሚነሣው ፡ ክርክር ፡ ሁሉ፡ በአንድ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ሊቈረጥ ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነቱ ፡ ሥራ ፡ የሚ ፈጸመው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ግልግልና ፡ ስለ ፡ ስምምነት ፡ በተመለከተው ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፸፮ ። ንብረቱ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የማይከፋፈል ፡ ስለ፡መሆኑ ። (፩) ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻልበት ፡ ሁኔታ ።

ለሀብቱ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም፡ ሀብቱ፡ ለተመደበበት ፡ አገልግሎት ፡ አለመከፋፈሉ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የሀብቱ ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ መከ ፋፈል ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ ለደኅና ፡ አእምሮ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ የሀብቱ፡ ያለ ፡ መከፈል ፡ ጕዳይ ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ለማ ድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፸፯ ። (፪) ንብረቱ ፡ የማይከፋፈልበት ፡ ሥርዐት ።

(፩) ሀብቱ ፡ ለመከፋፈል፡ የማይችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ የያንዳንዱን ፡ የጋራ ፡ ባለን ብረት ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚወሰንና ፡ የአንድነት ፡ ሀብት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ የሚተዳደርበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ ያለመከፋፈል ፡ ደንብ ፡ ይደ ራጃል ።

(፪) ስለዚህ፡ ጕዳይ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ስምምነት ፡ ለማግኘት ፡ ያልተ ቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ደንብ ፡ ለማቆም ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ዳኞች፡ ስም ምነቱን ፡ ተቀብለው ፡ እንዲያጸድቁት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ክፍል ፡ ፪ ።

## ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

## የአማካይ፡ ወሰን፡ አጥሮች ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፸፰ ። የባለሀብት ፡ ነፃነት ።

ማንም፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ጎረቤቱን ፡ አንድ ፡ የአማካይ ወሰን ፡ አጥር ፡ እንዲያጥር ፡ ወይም ፡ አጥሩን ፡ እንዲያድስ ፡ ሊያስገድድ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፸፱ ። የወሰን ፡ መሐል ፡ ግንብ ፡ አጥርን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

(፩) አንድ፡በአማካይ፡ ወሰን፡ ላይ፡ ያለ፡ አጥር፡ ፈርሶ፡ከባለርስቶቹ፡ አንደኛው፡ እንደ፡ ገና ፡ የመገንባትን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንደኛው ፡ ባለርስት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሊገነባው ፡ ይችላል ።

BACK



(፪) ከግንቡ፡ አንደኛው፡ ክፍል ፡ በጎረቤቱ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የተሠራም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተገነባው ፡ አጥር ፡ የሡራው ፡ ንብረት ፡ ይሆናል ።

(፫) ቢሆንም፡ አጥሩን፡ ያልሠራው ፡ ባለሀብት ፡ አጥሩን ፡ የሠራው ፡ ጎረቤቱ ፡ ያወጣውን ፡ ኪሣራ ፡ አጋማሽ ፡ መልሶ ፡ በመክፈል ፡ አጥሩን ፡ የጋራ ፡ የወሰን ፡ አማካይነት ፡ አጥር ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹ ። በአማካይ ፡ ወሰን ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ ስላለ ፡ መብት ።

ማንኛውም፡ የጋራ፡ ባለሀብት፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ አዋሳኙ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ የወሰን፡ አማካይ ፡ የግንብ ፡ አጥር ፡ ከፍ፡ ለማድረግም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ሕንጻ ፡ አስገድፎ ፡ ለመሥራት ፤ በር ፡ ለመቅደድ ፡ በጠቅላላውም ፡ በአጥሩ ፡ ላይ ፡ የባለሀብትነት ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## የአንድ ፡ ቤት ፡ ፎቅ ፡ ወይም ፡ ለመኖሪያ ፡ የተመደቡ ፡ ክፍሎች ፡ ባለሀብትነት ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፩ ። የአንድነት ፡ ሀብት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚቈጠር ፡ ክፍል ።

(፩) ያንድ፡ ቤት፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ ፎቆች፡ ወይም፡ ለመኖሪያ፡ የተመደቡ፡ ክፍሎች፡ (አፓርተማን)፡የልዩ፡ ልዩ ፡ ባለሀብቶች፡ ንብረት፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሰነድ፡ ከሌለ ፡ ከነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ለአንደኛው ፡ ባለንብረት ፡ የግል ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅም ፡ እንዲሆን ፡ ከተደረገው ፡ በቀር ፤ የመሬቱና ፡ የሌላውም ፡ የቤቱ ፡ ክፍሎች ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) የቤቱን ፡ ለመኖሪያ ፡ የተመደቡትን ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች፡ አፓርተማን፡ የሚለያዩ፡ ግድግዳዎች፡ የነዚሁ፡ የቤት፡ ክፍሎች፡ ባለሀብቶች፡ የጋራ፡ ግድግዳዎች፡ ናቸው።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፪ ። የጋራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳደር ፡ ደንብ ።

(፩) የያንዳንዱ፡ የጋራ፡ ባለንብረት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ የጋራ ፡ ንብረታቸው ፡ የአስተዳደር ፡ ሥርዐት ፤ ስለማይንቀሳቀስ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ጕዳይ ፡ በወጣው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ይመራል ።

(፪) ይህም ፡ ደንብ ፡ በማንቀሳቀሰው ፡ የጋራ ፡ ንብረት፡ ላይ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ያላቸውን ፡ ድርሻ ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፫ ። የደንቡ ፡ ፎርም ።

የጋራ ፡ ንብረት፡ የሚመራበት፡ ደንብ፡ በጽሑፍ፡ ካልሆነ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፬ ። ደንቡን ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

(፩) የጋራ፡ ንብረት፡ ማስተዳደሪያ ፡ የሆነው ፡ የጽሑፍ ፡ ደንብ ፡ አንዱ ፡ ግልባጭ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ሀብት ፡ በሚገኝበት ፡ አገር ፡ ባለ ፡ ባንድ ፡ ውል ፡ አዋዋይ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል ።

(፪) ይህንንም ፡ ደንብ ፡ ባለጥቅም ፡ የሆኑት ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ሊመለከቱትና ፡ አንዳንድ ፡ ግልባጭም ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፭ ። ደንቡ ፡ የሚቋቋምበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የጋራ፡ ባለሀብቶች፡ ማስተዳደሪያ ፡ የሚሆነውን ፡ ደንብ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ሕንጻ ፡ ከመሠራቱም ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ ለወደ፡ ፊት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ የሚሆኑት ፡ በሚያደርጉት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ የሚሆነውን ፡ ሕንጻ ፡ ሥራ ፡ በወጠነው ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ሊዘጋጅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህ፡ ባልሆነ፡ ጊዜ ፤ ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ፡ አንዱ ፡ እንደ፡ ጠየቀ ፡ ወዲያውኑ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ሁሉም ፡ ተስማምተው ፡ ያዘጋጁታል ።

(፫) በጋራ ፡ ንብረቱ፡ አስተዳደር፡ ደንብ ፡ ጕዳይ፡ ደንቡን ፡ ስለ፡ማዘጋጀት ፡ ወይም፡ ስለ ፡ ማሻሻል ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ የሁሉም ፡ ስምምነት ፡ የማይገኝ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ደንቡን ፡ እንዲያጸድቁት ፡ ወይም ፡ እንዲያሻሽሉት ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፮ ። ደንቡን ፡ መቃወሚያ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፤ ደንቡን ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

ለጋራ ፡ ንብረቱ ፡ ማስተዳደሪያ ፡ የሆነው ፡ ደንብ ፤ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለን ፡ የሚሉትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ሰዎች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ የሚችለው ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ያገኙት ፤ ደንቡ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ሕግ፡ በሚያዝበት ፡ ስፍራ ፡ ተቀማጭ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፯ ። በመዝገብ ፡ ቤት ፡ ያልተቀመጠ ፡ ደንብ።

(፩) የጋራ ፡ ንብረት፡ ማስተዳደሪያ ፡ ደንብ፡ በሚገባ ፡ ተቀማጭ ፡ ያልሆነ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የፈረሙትን ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ደንብ ፡ በሚመለከት ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የፈረሙትን ፡ ያስገድዳቸዋል ።

(፪) እንዲሁም፡ በዚሁ ፡ ሥርዐት፡ መሠረት ፡ የነዚህን ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶችና ፡ ወራሾቻቸውን ፡ ከነዚሁ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ መብትና ፡ መያዣ ፡ የሌላቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ያስገድዳል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፹፰ ። ያልተሟላ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ስምምነት ።

የጋራ ፡ ንብረት ፡ ማስተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ምንም ፡ የማያመለክት ፡ ወይም፡ ከመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ባሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተመለከተው ፡ ይሟላሉ ፤ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በምትክ ፡ ይገቡባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፷፱ ። የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የአንድነት ፡ ያልሆኑት ፡ ክፍሎች ።**

**(፩) መሠረቱ ።**

(፩) እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለንብረት ፡ የአንድነት ፡ ሀብት ፡ ባልሆነው ፡ ክፍል ፡ ንብረቱ ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ ለባለሀብት ፡ የሚሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ ይኖሩታል ።

(፪) በተለየም ፡ የግሉ ፡ የሆነውን ፡ ለመኖሪያ ፡ የተመደቡትን ፡ ክፍሎች ፡ (አፓርተማን) ፡ ወይም ፡ ፎቅ ፡ ለመሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ለማከራየት ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፸ ። (፪) የተጠበቀ ፡ ሁናቴ ።**

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የተመደበበትን ፡ አገልግሎት ፡ አክብሮ ፡ መጠበቅ ፡ ይገባዋል ፤ እንዲሁም ፡ የተከፈለ ፡ ድርሻው ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡ እንዲያገለግል ፡ የተመደበበትን ፡ ጒዳይም ፡ ሆነ ፡ የመጠቀሚያውን ፡ ዐይነተኛ ፡ ነገር ፡ ሌሎቹን ፡ ባለሀብቶች ፡ በሚጎዳ ፡ ሁኔታ ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፸፩ ። የአንድነት ፡ የሆነው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ክፍሎች ። (፩) አገልግሎት ።**

እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ተካፍሎ ፡ የራሱ ፡ ድርሻ ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ የአንድነት ፡ ንብረት ፡ በተመደበበት ፡ አገልግሎት ፡ መሠረት ፡ በሌሎች ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ መሰናከል ፡ በማያመጣ ፡ መንገድ ፡ በድርሻ ፡ ሀብቱ ፡ ለመጠቀም ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፸፪ ። (፪) ወጪ ።**

(፩) እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ የአንድነት ፡ ለሆነው ፡ ንብረት ፡ አያያዝ ፤ አጠባበቅና ፡ አስተዳደር ፡ ወጪ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ከሌሎቹ ፡ ባለንብረቶች ፡ ጋራ ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ።

(፪) የአንድነት ፡ ለሆነው ፡ ንብረት ፡ ወጪ ፡ የሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የሚደለደለው ፤ ከማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ክፍያ ፡ ድርሻ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆን ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፸፫ ። የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ። (፩) ሥራው ።**

(፩) የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፤ ሁሉም ፡ የጋራ ፡ ንብረታቸውን ፡ ለመምራት ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴ ፡ በመሆን ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ በአንድ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡ ፡ ናቸው ።

(፪) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ የጋራ ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ፡ ጒዳይ ፡ በጋራው ፡ ንብረት ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፬ ። (፪) የሥራው ፡ አካሄድ ።

(፩) እያንዳንዱ፡ የጋራ፡ ባለንብረት ፡ የአንድነት ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ካለው፡ ድርሻ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሆነ ፡ መጠን ፡ በሥራ ፡ መሪው ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ቍጥሩ ፡ ተስተካካይ ፡ የሆነ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር፡ ለሚያደርገው ፡ ስብሰባና ፡ ድምፅ፡ የመስጠት ፡ ጕዳይ ፡ ባለሀብቱ ፡ እንደራሴውን ፡ ለመላክ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፭ ። (፫) ስብሰባ ።

(፩) የጋራ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር፡ ስብሰባ ፡ የሚያደርገው ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መሪ፡ አሳሳቢነት ፡ የጋራ ፡ የሆነው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ፡ ነው ።

(፪) አጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ አምስቱ ፡ ሥራ ፡ መምሪያ፡ ማኅበሩ ፡ ስብሰባ ፡ እንዲያደርግ ፡ ከጠየቁ ፡ ማኅበሩ ፡ በግድ ፡ መሰብሰብ ፡ ይገባዋል ።

(፫) የማኅበሩን፡ ስብሰባ ፡ ሥርዐቱንና ፡ ጊዜውን ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ለሕሊና፡ በሚስማማ ፡ ዐይነት ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፮ ። (፬) ውሳኔ ።

(፩) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚጸኑት ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው ።

(፪) በስብሰባው፡ ላልተገኙትና፡ ወኪሎቻቸውን ፡ ላልላኩት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች፡ የማኅበሩ ፡ ውሳኔ ፡ የሚገለጽላቸው ፡ በሥራ ፡ መሪው ፡ አማካይነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፯ ። (፭) ስለ ፡ አቤቱታ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም፡ እንኳ ፡ ማንኛውም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት፡ እርሱ ፡ በሌለበት ፡ ማኅበሩ ፡ የሰጠውን ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ሥራ ፡ መምሪያ ፡ የሆነውን ፡ ደንብንና ፡ ሕግን ፡ የሚጥሰውን ፡ ውሳኔ፡ በዳኞች፡ ፊት ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም፡ የመቃወም፡ ክስ ፡ የማኅበሩ ፡ ውሳኔ ፡ ለባለቤቱ ፡ በተገለጸለት ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀባይነትን፡ አያገኝም ።

(፫) የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ የማኅበሩ ፡ ውሳኔ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚወሰን ነው ፡ ፍርድ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፰ ። (፮) ስለ ፡ ሥራ ፡ መሪጡ ፡ (ሰንዲክ) ። (፩) ሹመት ።

(፩) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የንብረት ፡ ሥራ ፡ የሚመራው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ከመካከላቸው ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ በመረጡት ፡ ባንድ ፡ የማኅበር ፡ ንብረት ፡ ሥራ ሹም ፡ (ሰንዲክ) ፡ ነው ።

(፪) ሥራ ፡ መሪው ም፡ (ሰንዲኩም) ፡ የሚሾመው ፡ በጋራ ፡ ባለንብረቶች ፡ ማኅበር ፡ መራጭነት ፡ ነው ።

(፫) አስፈላጊ፡ በሆነ ፡ ጊዜ፡ ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ባንደኛው ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢነት ፡ ለጊዜው ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ዳኞች ፡ መርጠው ፡ ሊሾሙ፡ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፱ ። (፬) የሥልጣኑ ፡ ማስረጃ ።**

(፩) የጋራ ፡ ንብረት ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ የሥልጣኑንና ፡ የችሎታውን ፡ ማስረጃ ፡ ሰነድ ፡ ከጋራ ፡ ንብረት ፡ ሥራ ፡ መምሪያ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ላይ ፡ ጠይቆ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፪) አስፈላጊ ፡ ሆኖም፡ ሲገኝ ፡ ይህ ፡ የሥልጣን ፡ ማስረጃ ፡ ሥራው ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ይገልጻል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻ ። (፭) የአገልግሎት ፡ ዋጋ ።**

(፩) በተለይ፡ የተወሰነ ፡ ካልሆነ፡ በቀር ፡ በመሠረቱ ፡ የንብረት ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ ማንኛውንም ፡ አበል ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ሥራ ፡ መሪው ፡ ለማኅበሩ፡ ሲል ፡ ወጪ፡ ያደረገውን ፡ ሒሳብ ፡ ብቻ ፡ እንዲመለስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፩ ፡ (፮) የሥራ ፡ መሪው ፡ መሻር ፡ (መለወጥ) ።**

(፩) የጋራ፡ ባለሀብቶቹ፡ የንብረት ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ ማኅበር ፡ (ሰንዲክ) ፡ በስምምነታቸው ፡ ላይ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡ ለሥራ ፡ መሪው ፡ የሚከፈለው ፡ የአበል ፡ አከፋፈል ፡ ጕዳይ ፡ እንደ፡ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የንብረት፡ሥራ ፡ መሪውን ፡ (ሰንዲክ)፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ሊሽሩት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሥራ፡ መሪው፡ የተጣለበትን፡ አደራ፡ በግልጽ፡ እንደ፡ መጣስ፡ ያለ፡ ወይም፡ የተሰጠውን ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ ችሎታ ፡ እንደ፡ማጣት ፡ ያለ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሲገኝበት ፡ ይህን ፡ የሥራ ፡ መሪውን ፡ የመሻር ፡ መብት ፡ የሚወስን ፡ ወይም ፡ የሚያግድ ፡ ተግባር ፡ አይፈቀድም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፪ ። (፯) የሥራ ፡ መሪው ፡ ሥራዎች ።**

(፩) ሥራ ፡ መሪው ፡ የአንድነት ፡ የሆነውን፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረትን ፡ አያያዝ ፤ የአጠባበቅና ፡ ንብረቱም ፡ በሚገባ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲኖር ፤ የማደስ ፡ ሥራዎችን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) አስፈላጊ፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ መሪው ፤ የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ እንዲሰበሰቡና ፡ የሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ይጠባበቃል ።

(፫) በፍርድ ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ውጭ ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ የማኅበሩ ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ይሠራል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፷፫ ። (፮) የሥራ ፡ መሪው ፡ አላፊነት ።

(፩) ሥራ፡ መሪው፡ በተሰጠው፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣኑ ፡ መሠረት ፡ ለማኅበሩ፡ ( ለሰንዲካው ) ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) የጋራ፡ ንብረት ፡ ማኅበር፤ ሥራ ፡ መሪው ፡ ያቀረበውን ፡ ሒሳብ ፡ በማጽደቅ ፡ ወይም ፡ አላፊነት ፡ የሚያመጣበት ፡ ሥራ ፡ አድርጓል ፡ የሚል፡አንድ፡ውሳኔ፡ቢያደርግ ፡ ይህን ፡ የሚቃወም ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ በራሱ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ፡ ወይም፡ የእርሱ ፡ እንደራሴ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ ከሆነ ፡ የሥራ ፡ መሪው ፡ ማኅበር ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በዳኞች ፡ ፊት ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፷፬ ። የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መጥፋት ።

የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ፡በሙሉ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት፤ ቦታውና ፡ ከጠፋው ፡ ንብረት ፡ የተረፈው ፡ ዕቃ ፡ በግልጽ ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፷፭ ። የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በከፊል ፡ መጥፋት ። (፩) የጋራ ፡ ንብረት ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ማኅበር ፡ ሥልጣን ።

ንብረቱ ፡ በከፊል ፡ የፈረሰ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የጋራ፡ ንብረቱ ፡ ማኅበር ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መሥራት ፡ ወይም ፡ አለመሥራት ፡ ወይም ፡ ማደስ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወይም ፡ የማያስፈልገው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፷፮ ። (፪) እንደ ፡ ገና ፡ የመሥራት ፡ ውሳኔ ።

(፩) የጋራ፡ የሆነው፡ ንብረት ፡ ማኅበር ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ሕንጻው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲሠራ ፡ ወይም ፡ እንዲታደስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሕንጻው፡ክፍል፡ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መሥራት ፡ ወይም ፡ መታደስ ፡ ለሚያስፈልገው ፡ ክፍል ፡ የሚሆነውን ፡ ወጪ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ በሀብቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ማዋጣት ፡ አለበት ።

(፪) የጋራ፡ ሀብት፡ የሆነው፤ ሕንጻ ፡ የፈረሰው ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ አንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላው ፡ አንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ አልፈረሰም ፡ የሚያሰኘው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ መነሣት ፡ አይገባውም ።

(፫) በሕንጻው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት፡ ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ አንዱ፡ በአደረገው፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ውስጥ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡

አላፊው፡ በሆነው ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ኪሣራው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሊጣል፡ ይገባል ፡ የሚባል ፡ ጕዳይ ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፯ ። (፫) እንደ ፡ ገና ፡ እንዳይሠራ ፡ የሚደረግ ፡ ውሳኔ ።**

(፩) የጋራ፡ ንብረቱ፡ ማኅበር ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በከፊል ፡ የፈረሰው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዳይሠራ ፡ ወይም ፡ እንዳይታደስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ ያልፈረሰውም ፡ ክፍል ፡ ጭምር ፡ በግልጽ ፡ ሐራጅ ፡ ይሸጣል ።

(፪) የኅብረት፡ ንብረቱን፡ የሽያጭ ፡ ዋጋም ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶቹ ፡ እንደየድርሻቸው ፡ ይከፋፈሉታል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአለው ፡ ቍጥር ፡ የተነገሩት ፡ የሁለተኛውና ፡ የሦስተኛው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፰ ። የንብረት ፡ ማኅበር ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መያዣ ።**

የጋራ ፡ ባለንብረቶች ፡ ወይም ፡ የንብረት ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ የተበደሩትን ፡ ዕዳ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነ ፡ ከሌላ ፡ ሀብታችን ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ እንከፍላለን ፡ ብለው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ባደረጉት ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ለተደረጉት ፡ የብድር ፡ ወሎች ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሚሆነው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ የጋራ ፡ ንብረቱና ፡ የተከፋፈለውም ፡ ድርሻ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በአላባ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ፡ መብት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፱ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የአላባ ፡ መብት ፡ ማለት ፡ የሚጠቀሙበትን ፡ ነገር ፡ ከመጠበቅ ፡ ግዴታ ፡ ጋራ ፡ ከዚሁ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ነገሮች ፡(ፍሬዎች)፡ ወይም ፡ መብቶች፡ ለመጠቀምና ፡ ለመገልገል ፡ የሚሰጥ ፡ መብት ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ መብት ፡ በሚንቀሳቀሱና ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በመብቶች ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፲፫፻፲ ። ስለ ፡ መምራት ፡ (ስለ ፡ መጥቀስ) ።**

(፩) አላባ፡ ማግኘትን ፡ ማስተላለፍን ፡ ማጣትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፤ የአላባው ፡ መብት፡ግዙፍነት፡ባለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ግዙፍ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎች ፡ ሀብትነት ፡ ማግኘት ፡ ማስተላለፍና ፡ ማጣት ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም፡ማግኘትን ፡ ማስተላለፍን፡ማጣትን፡የሚመለከቱ፡ደንቦች፡በገንዘብ ፡ ወይም ፡ ግዙፍነት ፡ በሌላቸው ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ጠቅላላ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ገንዘብና ፡ ግዙፍነት ፡ ስለሌላቸው ፡ ሌሎች ፡ መብቶች ፡ ማግኘት ፤ ማስተላለፍና፡ ማጣት ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቊ ፡ ፲፫፻፲፩ ። የአላባ ፡ ለጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ መብቶች ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ ፡ በአላባነት ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ መብት ፡ እጅ ፡ ለማድረግ፤በዚሁም፡ ለመገልገልና ፡ ንብረቱ ፡ በሚያስገኘው ፡ ፍሬም ፡ ለመጠቀም ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የማስተዳደሩም ፡ መብት ፡ የእርሱ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፲፫፻፲፪ ። የንብረቱ ፡ አስተዳደር ።**

የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በመብቱ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የመልካም ፡ አስተዳደርን ፡ ሥርዐቶች ፡ አክብሮ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፲፫፻፲፫ ። የንብረቱ ፡ አያያዝ ።**

የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ አያያዝና ፡ ከዚሁም ፡ ላይ ፡ ስለሚገኘው፡ ጥቅም፡ የሚደረገውን ፡ የወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ኪሣራና ፡ እንዲሁም ፡ ከንብረቱ ፡ ላይ ፡ የማይለየውን ፡ የዕዳ ፡ ወለድ ፡ መቻል ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፲፫፻፲፬ ። ደንበኛ ፡ ወጪ ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባነት ፡ በያዘው ፡ ንብረት ፡ ደንበኛ ፡ ከሆኑት ፡ ገቢዎች ፡ ላይ ፡ የሚጠየቁትን ፡ የዓመት ፡ ግብሮችና ፡ ሌሎቹንም ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚከፈሉበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ በባለርስቱ ፡ ስም ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባነት ፡ በያዘው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ግብር ፡ በመክፈል ፡ ይረጋልኛል ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመብት ፡ ማስረጃ ፡ ይሆነኛል ፡ ብሎ ፡ ርስቱን ፡ ሊከራከርበት ፡ አይችልም ።

BACK



**ቍ ፡ ፲፻፶፲፩ ። የተለዩ ፡ ወጪዎች ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በዚህ ፡ ሀብት ፡ በሚጠቀምበት ፡ ጊዜ ፡ ከባለ ንብረቱ ፡ ላይ ፡ የሚጠየቁ ፡ አዲስ ፡ ልዩ ፡ ወጪዎች ፡ የተወሰኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህንን ፡ ወጪ ፡ የሚከፍለው ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ነው ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ይህን ፡ በተለይ ፡ እንዲከፍል ፡ የተጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ የአባላ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ ያለ ፡ ወለድ ፡ እንዲያበድረው ፡ ጠይቆት ፡ ያለ አበደረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የተጠየቀው ፡ ልዩ ፡ ወጪ ፡ ከዚያው ፡ በአላባነት ፡ ከተሰጠው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ነገሮች ፡ በመሸጥ ፡ ለመከፈል ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፲፪ ። የዕቃው ፡ መዝገብ ፡ ዝርዝር ።**

የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ና ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በአላባው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ንዋዮች ፡ ዝርዝራቸውን ፡ የሚናገር ፡ መዝገብ ፡ በሁለቱም ፡ ኪሣራ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፲፫ ። የዕቃው ፡ መመለስ ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የመጠቀም ፡ ዘመን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በአላባ፡ የተሰጠውን ፡ ንብረት ፡ ለአላባ ፡ ሰጪው ፡ መልሶ ፡ ማስረከብ፡ አለበት ።

(፪) በዕቃው ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ መጥፋትና ፡ መበላሸት ፡ ከዐቅሙና ፡ ከችሎታው ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ለዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፲፬ ። ግዙፍ ፡ መብቶች ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባነት ፡ በሚጠቀምበት ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪውን ፡ መብቶች ፡ ለመጉዳት ፡ የሚችል ፡ አንዳች ፡ ግዙፍ ፡ መብት ፡ ሊያቋቁምበት ፡ (ሊያደርግበት) ፡ አይችልም ።

(፪) በተለይም ፡ በአላባ ፡ ጥትም ፡ ሰጪው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያመጣ ፡ ዐይነት ፡ በአላባነት ፡ የተሰጠውን ፡ ንብረት ፡ ለዕዳ ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ መስጠት ፡ አይችልም ።

(፫) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ሳይፈቅድለት ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ጥሶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአላባነት ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ መብቱ፡ መቅረት ፡ አንዳችም፡ ኪሣራ ፡ ሳይሰጠው ፡ ወዲያውኑ ፡ ከአላባነት ፡ ጥቅሙ ፡ ይወገዳል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፲፭ ። የዕቃው ፡ መጥፋት ።**

(፩) በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ የጠፋ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአላባው ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) በአላባነት ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ ለጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተነቀለ ፡ ወይም ፡ የተወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በምትክነት ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የአላባው ፡ ጥቅም ፡ ይተላለፋል ።

ቍ ፡ ፲፫፻፶ ። ኢንሹራንስ ።

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ና ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ መል ካም ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እየራሳቸው ፡ መብታቸው ን ፡ የሚጠ ብቅ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ይገባሉ ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌላቸው ፡ በቀር ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ የገባው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ው ል ፤ ለአላባ ፡ ጥቅ ም ፡ ተቀባዩ ፡ አይጠቅመው ም ።

(፫) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌላቸው ፡ በቀር ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ የገባው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ው ል ፡ ለአባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ አይጠቅመ ው ም ።

ቍ ፡ ፲፫፻፶፩ ። የሀብቶቹ ፡ ግምት ።

(፩) በዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ በአላባነት ፡ በተሰጡት ፡ ንዋዮች ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ግምት ፡ ሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ የተስማሙበት ፡ ተቃ ራኒ ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንዋዮችን ፡ ሀብትነት ፡ ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ አያስተላልፍም ።

(፪) ስለዚህ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የመጠቀሙ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ የሚመልሰው ፡ ሀብቶቹ ፡ የተገመቱበትን ፡ ዋጋ ፡ ሳይሆን ፡ ያኑ ፡ በአላባነት ፡ ተሰጥተው ት ፡ የነበሩትን ፡ ሀብቶች ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፫፻፶፪ ። በአላባ ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ መቅረት ።

(፩) የአላባ ፡ ጥትም ፡ ተቀባዩ ፡ ሲሞት ፡ ወይም ፡ ስለዚሁ ፡ ማለቂያ ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ ሲደርስ ፡ የአላባው ፡ መብት ፡ ይቀራል ።

(፪) በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ በአላባ ፡ ተጠቃሚነት ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ መቈየት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፫፻፶፫ ። የአላባ ፡ ሰጪው ፡ በአላባነት ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ የሚያዝበት ፡ ተግባር ።

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ በአላባ ፡ የሰጠው ን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ አላባው ፡ በሚመለከተው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ቢያደርግ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገ ረው ፡ በልዩ ፡ ግዴታም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩን ፡ መብት ፡ ሊለውጠው ፡ አይችልም ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የተሰጠው ን ፡ ሀብት ፡ ለመተው ፡ መፍቀ ዱን ፡ በግልጽ ፡ ካላረጋገጠ ፡ በቀር ፡ በአላባው ፡ መጠቀሙን ፡ ይቀጥላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፴፩ ። ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ የሚሰጥ ፡ ዋስትና።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፤ ሰጪው ፡ መብቶቹ፡ አደጋ ፡ (ጥፋት )፡ የሚያገኛቸው ፡ መሆኑን ፡ ካስረዳ ፡ ለመብቱ ፡ ማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጠው ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) የአላባ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ በሚያልቁ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ዕቃዎቹን ፡ ከማስረከብ ፡ በፊትና ፡ ማስረጃም ፡ ሳይ ሰጥ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጠው ፡ የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በሚታሰብና፡ በወሰነለት፡ ቀን ፡ የአላባ፡ጥቅም፡ተቀባዩ ፡ ማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ ያልሰጠ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ እየተቃወመ ፡ ሳለ ፤ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በያዘው ፡ ነገር ፡ላይ ፡ ሕግ ፡ ያልፈቀደው ን ፡ ሁኔታ ፡ በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ መገልገሉን ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ይዞታውን ፡ አስለቅቀው ፡ ለሌላ ፡ ጠባቂ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ግዙፍ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሀብቶች ፡ የሚጸና ፡ (የሚፈጸም) ፡ ልዩ ፡ ደንብ ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፴፪ ። የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ግዴታ ፡ የሌለበት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የሚሰጠውን ፡ ነገር ፡ በአላባ ፡ በሚቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ መወሰድ፡ አለበት ።

(፪) ዕቃውን ፡ አድስልኝ ፡ በማለት ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪውን ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፴፫ ። በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መገልገል ።**

(፩) የግዙፍ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ በአላባ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነ፡ሰው ፡ የተሰጠው ፡ ነገር፡ ሊያገለግል፡በተመደበበት ፡ ጉዳይ ፡ መሠረት ፡ ሊገለገልበት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ሀብት ፡ በሚገለገልበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ በደንበኛ ፡ አገልግሎቱ ፡ ምክንያት ፡ ዋጋው ፡ ቢቀነስ ፡ አላባ ፡ ተቀባዩ ፡ አንዳችም ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፴፬ ። የሚያልቁ ፡ ነገሮች ።**

(፩) አላባው ፡ በሚያልቁ ፡ ነገሮች፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲያልቁ ፡ ሳይደረግ ፡ በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ ለመገልገል ፡ የማይቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በአላባ ፡ ተጠቃሚው ፡ የነዚህ ፡ የሚያልቁ ፡ ነገሮች ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነቱ ፡ ሲቀር ፡ አላባው ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያልቁት ፡ ነገሮች ፡ የነበራቸውን ፡ ግምት ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፹፰ ። በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ አላባ ።

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ በነገሩ ፡ ዓላማና ፡ ነገሩ ፡ በሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ መሠረት ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍሬዎች ፡ ካፈሯቸው ፡ ነገሮች ፡ በተለያየበት ፡ ጊዜ ፡ ከተገኙ ፤ የፍሬዎቹ ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ።

(፪) ያለ ፡ አገባብ ፡ የተወሰዱ ፡ አላባዎች ፡ አላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ይመለሳሉ ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፹፱ ። የተቀበረ ፡ ገንዘብ ።

የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ በያዘው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለሚገኘው ፡ የተቀበረ ፡ ገንዘብ ፡ አንድም ፡ መብት ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፺ ። የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ መብቶች ፡ ወሰን ።

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በያዘው ፡ ነገር ፡ መገልገሉ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንዳይሆን ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ ዐይነተኛ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ የሚገኝበትን ፡ ቦታ ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ።

(፫) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ የአላባው ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ቈየበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የተባሉት ፡ ግዴታዎቹ ፡ መፈጸማቸውን ፡ በሚገባ ፡ ሁኔታ ፡ ሊመረምር ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፺፩ ። በአላባነት ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ማከራየት ።

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባነት ፡ የሚጠቀምበትን ፡ ነገር ፡ ለማከራየት ፡ ይችላል ።

(፪) በአከራየው ፡ ነገር ፡ በየቀኑ ፡ የሚገኘው ፡ ኪራይ ፡ የርሱ ፡ ሀብት ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፺፪ ። ስለ ፡ ኪራዩ ፡ መቅረት ።

(፩) ያንድ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ኪራይ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀይባነቱ ፡ ሲቀር ፡ ይቀራል ።

(፪) ላንድ ፡ ገበሬ ፡ ወይም ፡ ተከራይ ፡ ባንድ ፡ ርስት ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ የሰጣቸው ፡ ውሎች ፡ የአላባው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀበት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪውንና ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ የሚያስገድዷቸው ፡ ይሆናሉ ።

(፫) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ በአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በገበሬው ፡ ወይም ፡ በተከራዩ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ በመብቶቹ ፡ ላይ ፡ በማይገባና ፡

በተንኰል፡ የተደረገ ፡ መሆኑን ፡ ያፀረጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ በሚቀርበት ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ውሉን ፡ ለማቋረጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፫ ። የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ፕላን ፡ (፩) መደራጀት ፡ የሚገባበት ፡ ጊዜ ።

የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ የአላባ ፤ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ የተሰጠውን ፡ ንብረት ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ጥቅም ፡ ፕላን ፡ እንዲደራጅ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉት ።

(ሀ) በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደን ፡ የመሰለ ፡ ሆኖ ፡ የሥራው ፡ ጥቅም ፡ በያመቱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አላባዎችን ፡ የሚሰጥ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ የድንጋይ፡ መፍለጫ፡ ቦታን ፡ የመሰለ፡ ሀብትን፡ የሚመለከት ፡ ሆኖ ፡ የሥራው ፡ ጥቅም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ የሚጨርሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፬ ። (፪) የአቋቋሙ ፡ ዐይነት ።

(፩) የሥራው ፡ ድርጅት፡ ፕላን፡ በባለጕዳዮቹ ፡ ስምምነት ፡ የሚቋቋም ፡ ይሆናል ።

(፪) በባለጕዳዮቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ያልተደረገ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ በመረጡቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሥራው ፡ ድርጅት ፡ ፕላን ፡ የሚሰናዳ ፡ ሆኖ ፡ ዳኞቹ ፡ የሚያጸድቁት ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፭ ። (፫) መለዋወጥ ።

ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ የሥራውን ፡ ዐቅድ ፡ እንዳይፈጸም ፡ የከለከሉ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ መለዋወጡን ፡ መልካም ፡ አድርገው ፡ ያሳዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ባንዱ ፡ ጥያቄ ፡ ዐቅዱ ፡ ሊለወጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፮ ። በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተደረገ፡ መሻሻል ።

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለሚያደርገው ፡ ማሻሻል ፡ አንድም ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ እንደዚሁ ፡ ለሚሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፫) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ የአላባው ፡ ጥቅም ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ አፍርሶና ፡ ሀብቱን ፡ በተረከበ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለመመለስ ፡ ብቻ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፯ ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ (፩) ትርጓሜ ።

ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ የሚባለው ፡ በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ መጠነኛ ፡ ከሆነ ፡ ገቢ ፡ ሀብት ፡ በላይ ፡ ወጪን ፡ የሚያስገድድ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፫ ። (፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ በማንኛዎቹም ፡ ሁኔታዎች ፡ በአላባ ፡የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ ለመጠበቅ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ የሚያስፈልግ፡ ሲሆን ፡ በአላባ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ ይህን፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ ለማድረግ ፡ የሚገደደው፡ ይህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ በራሱ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በተለይም ፡ በአላባ፡የተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ከተጀመረ፡ ወዲህ ፡ ባለማደስና ፡ ባለመጠገን ፡ የደረሰ ፡ ጕድለት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፬ ። (፫) ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ አፈጻጸም ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በአላባ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ ለማድረግ ፡ አይገደድም ።

(፪) ባለሀብቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደስ ፡ ለማድረግ ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በዚህ ፡ በመታደሻው ፡ ጊዜ ፡ የተነሣ፡ የሚደርስበትን ፡ በአላባ፡ ያለ ፡ መጠቀምና ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጉዳትን ፡ መታገሥ ፡ አለበት ።

(፫) የአላባ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ለዚህ ፡ አስተያየት ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ በተቻለ፡ መጠን ፡ የአላባ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩን ፡ ጥቅሞች ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፭ ። በመያዣ ፡ የተሰጡ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ዕዳ ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ ባንድ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በልዩ ፡ ስም ፡ በማያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ርስት ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ አይገደድም ።

(፪) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ እንዲከፍል ፡ የተገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲመለስለት ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፮ ። የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ ክስ ።**

(፩) የአላባ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ በአላባነት፡ በተሰጠው፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሚመለከቱ ፡ የይዞታ ፡ (የጅ ፡ ማድ ረግ) ፡ ክሶችን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፯ ። የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) አላባው ፡ በሚቈይበት፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ከርስቱ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ፡ የንጥቂያ ፡ ተግባር፡ ያደረገ፡ ወይም፡ የአላባ፡ ጥቅም ፡ ሰጪውን፡ መብቶች፡ ከጉዳት ፡ ላይ፡ የጣለ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የአላባ ፡ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ ለአላባ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) የአላባ፡ጥቅም፡ ተቀባዩ ፡ ይህን ፡ ባያደርግ፡እርሱ ፡ ባደረገው፡ማበላሸት ፡ ኀላፊ፡ እንደሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቁ ፡ ፲፫፻፵፫ ። በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ መጥፋት ።**

የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ የአላባ፡ጥትም፡ተቀባዩ ፡ በማርጀት ፡ የወደ ቀወ ን፡ ወይም ፡ በድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ የፈረሰውን ፡ ለማደስ ፡ አይገደድም ።

**ቁ ፡ ፲፫፻፵፬ ። በከፊል ፡ ስለ ፡ መጥፋት ።**

በአላባ፡የተሰጠው ፡ነገር፡ በከፊል፡ ብቻ ፡ የጠፋ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የአላባው፡መብት፡ በቀሪው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይቈያል ።

**ቁ ፡ ፲፫፻፵፭ ። የከብት ፡ መንጋ ፡ በአላባነት ።**

(፩) በአላባ፡ ጥቅም፤ ተቀባዩ፡ ጥፋት፡ ሳይሆን ፡ በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ መንጋ ፡ በድን ገተኛ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ በበሽታ፡ በሙሉ፡ ያለቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ ፡ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ ቆዳዎችን ፡ ለመመለስ ፡ ወይም ፡ የቆዳዎ ቹን ፡ ዋጋቸው ን፡ ለመስጠት ፡ ብቻ፡ ይገደዳል ።

(፪) መንጋው ፡ በሙሉ ፡ ያላለቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ ፡ በተወለ ዱት ፡ ከብቶች ፡መጠን ፡ ያለቁትን ፡ መተካት ፡ አለበት ።

**ቁ ፡ ፲፫፻፵፮ ። ይርጋ ።**

(፩) በአላባ ፡ የተሰጠው ን፡ ነገር ፡ በመለወጥ ፡ ወይም ፡ ዋጋው ን ፡ በመቀነስ ፡ ምክ ንያት ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ሰጪው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ በአላባ ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ ከተመለሰበት ፡ ቀን ፡ አሥንቶ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ ራሱ ፡ የሠራቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ለማንሣት ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እንደዚሁ ፡ በ፩ ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የገንዘብና ፡ ሌሎች ፡ ግዙፎች ፡ ያልሆኑ ፡ ነገሮች ፡ የአላባ ፡ መብት ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ።

**ቁ ፡ ፲፫፻፵፯ ። ገቢ ።**

የገንዘብ ፡ ወይም ፡ ግዙፍነት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ካገኘበት ፡ ነገር ፡ የሚገኙት ፡ ግዙፍ ፡ ወይም ፡ ድርሻ ፡ ገንዘቦች ፡ የመከፈያ ፡ ቀናቸው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እኒሁኑ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

**ቁ ፡ ፲፫፻፵፰ ። ያልታሰቡ ፡ ልዩ ፡ ትርፎች ።**

(፩) የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባይ ፡ ከሆነበት፡ መብት ፡ ሊገኙ፡ የሚችሉ ፡ ያልታሰቡ ፡ ልዩ ፡ ትርፎች ፡ ቢገኙ ፡ ለነዚህ ፡ ትርፎች ፡ ባለሀብት ፡ አይሆንም ።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነት ፡ መብት ፡ በነዚህም ፡ ትርፎች ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።

**ቊ ፡ ሺ፫፻፴፱ ። በአዲስ ፡ አክሲዮኖች ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።**

(፩) በአላባነት፡ ለተሰጠ፡አክሲዮን፡እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ ወጡት ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖች ፡ በቀደምትነት ፡ የመጻፍ ፡ መብት ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርጦ ፡ የመጻፉ ፡ መብት ፡ አክሲዮኑን ፡ በአላባነት ፡ ለሰጠው ፡ ባለሀብት ፡ ነው።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቃራኒ፡ መብት፡የአላባ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ በገባባቸው ፡ አዲስ፡ አክሲዮኖች ፡ ወይም፡ የቀዳሚነት ፡ ፈራሚነትን ፡ መብት ፡ በመሸጥ ፡ ባገኘው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።

**ቊ ፡ ሺ፫፻፵ ። የገንዘብ ፤ ወይም ፡ የመብቱ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ።**

(፩) የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ መብት ፡ የተሰጠበት ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ መብት ፡ አላባው ፡ ጸንቶ ፡ በሚቈይበት፡ጊዜ ፡ ተከፍሎ ፡ ወይም ፡ ተተክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ በአከፋፈሉ ፡ ረገድ ፡ ተስማምቶበት ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር፡ ገንዘቡ ፡ ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ፡ መስጠት ፡ የለበትም ።

(፪) የአላባ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ፡እንዲሰጥ ፡ ያልፈቀደ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ባለዕዳው ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ለሚገባው ፡ በማስረከብ፡ ከዕዳው ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

(፫) የአላባ ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ ዕዳው ፡ የሚከፈልበት፡ ጊዜ፡ ሲደርስ፡ ገንዘቡን ፡ መረከብ ፡ በሚገባው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ሺ፫፻፵፩ ። እስከ ፡ ዕድሜ፡ ልክ ፡ የሚሰጠው፡ጡረታ ፡ በአላባነት ፡ ስለ ፡ መስጠት።**

እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በተሰጠ ፡ ጡረታ ፡ ላይ ፡ የሚሰጥ፡ አላባ፤ አላባው ፡ ጸንቶ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ ለመመለስ ፡ ተገዳጅ ፡ ሳይሆን ፡ የአላባ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ፡ የተባለውን ፡ ለጡረታ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ መብት፡ አለው ።

**ቊ ፡ ሺ፫፻፵፪ ። ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

(፩) የአላባ፡ ጥቅም፡ ሰጪው ፡ ወይም፡ የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ ከባለዕዳው፡ ወይም ፡ አላባው ፡ የተሰጠበትን ፡ ሰነድ ፡ ካወጣው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሁለቱም ፡ ባለ ጕዳዮች ፡ ኪሣራ ፡ አንዱ ፡ የአላባ፡ ጥቅም ፡ ሰጭነት ፡ መብት ፡ አንደኛው ፡ የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባይነት ፡ መብት፡ የሚያረጋግጡ ፡ ሁለቱ ፡ልዩ ፡ ሰነዶች ፡ይሰጡን ፡ ሲሉ ፡ ባለዕዳውን፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በባንክኖቶች ፡ (ወረቀቶች) ላይ ፡ አይፈጸምም ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## በቤት ፡ ው ስጥ ፡ የመኖር ፡ መብት ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፫ ። ትርጓሜ ።**

በቤት ፡ ው ስጥ ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ ማለት ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ው ስጥ፡የመቀመጥ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፬ ። የመብቱ ፡ ባለጥቅሞች ።**

በቤት ፡ ው ስጥ ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ማናቸው ም ፡ ሰው ፡ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በያዘው ፡ ቤት ፡ ከሚስቱ ፤ በቀጥታ ፡ መሥመር፡ዘመዶቹ ፡ ከሆኑና ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ ለመኖር ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፭ ። ባንድ ፡ ቤት ፡ በከፊል ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መብት ።**

ባንድ ፡ ቤት ፡ ከፊል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ለጋራ ፡ አገልግሎት ፡ በተቋቋሙት ፡ ነገሮች ፡ ለመጠቀም ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፮ ። የመጠገኛ ፡ ወጪ ፡ (ኪሣራ) ።**

(፩) ባለመብት ፡ የሆነው ፡ ቤቱን ፡ ወይም ፡ ክፍሉን ፡ ብቻውን ፡ የሚገለገልበት ፡ ከሆነ ፡ ለመጠገን ፡ ደንበኛ ፡ ወጪዎችን ፡ (ኪሣራ) መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) በቤቱ፡ ው ስጥ፡ የመኖሩ ፡ መብት ፡ ከባለሀብቱ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጠገኛውን ፡ ወጪዎች ፡ የሚከፍለው ፡ ባለሀብቱ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፯ ። የማይተላለፍ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ባንድ ፡ ቤት ፡ የመኖሩ ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ የማይተላለፍ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለወራሾች ፡ የማይተላለፍ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፰ ። ወደ ፡ አላባ ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መምራት ።**

ለሌሎቹ ፡ ጕዳዮች ፡ የአላባ ፡ ደንቦች ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፶፱ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የንብረት፡ አገልግሎት፡ ማለት ፡ ስለ፡ሌላው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ጥቅም፡ በአንዱ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ግዴታ፡ አገልጋይ፡ በሆነ ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ ፈንታ ፡ አገልግሎት ፡ የሚቀበለው ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ አንዳንድ ፡ የልማድ ፡ ተግባሮች ፡ እንዲሠራ፡ወይም ፡ ከሀብቱ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙትን ፡ አንዳንድ ፡ መብቶች ፡ ከማከናወን ፡ ራሱ ፡ እንዲታገድ ፡ ያስገድደዋል ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፷ ። የማድረግ ፡ ግዴታ ።**

አንድ ፡ የማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ከአንድ ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ጋራ ፡ በተጨማሪ ፡ የተያያዘ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፷፩ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ሀብትነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) የንብረት፡ አገልግሎት፡ የተቋቋመላቸው ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ የነበራቸው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሀብትነት ፡ መለወጥ ፡ የንብረቱን ፡ አገልግሎት ፡ የሚለዋውጠው ፡ አይደለም ።

(፪) በሕግ፡ የሚጠየቀው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገለት ፡ የንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ እነዚህን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ወደ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በሚተላለፉበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከተል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፷፪ ። ስለ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ፡ መቋቋም ። (፩) ውል ፡ ወይም ፡ ኑዛዜ ።**

(፩) የንብረት፡ አገልግሎት፡ አገልጋይ ፡ በሆነ ፡ ርስት ፡ ባለቤትና ፡ አገልግሎት ፡ በሚቀበለው ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ መካከል ፡ ከሚደረገው ፡ ውል ፡ የመነጨ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚሁም፡ የንብረት፡ አገልግሎትን ፡ ያንድ ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ ይህን፡ርስት ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ ከሚያከፋፍልበት ፡ ኑዛዜ ፡ የመነጨ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፷፫ ። (፪) የጽሑፍ ፡ አስፈላጊነት ።**

አንድ ፡ የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ ለማቋቋም ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፤ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፷፬ ። (፫) ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።**

አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ መሬት ፡ ይህ ፡ ግዴታ፡ ያለበት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መዝገብ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፲፫፻፷፭ ። ለንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ትርጓሜ ፡ መሠረት ።**

ባንድ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የውል፡ ቃል፡ የንብረት፡አገልግሎትን፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ በንብረቱ ፡ ባለሀብት ፡ ላይ ፡ የግል ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ ለመወ

ሰን፡ የተደረገ ፡ መሆኑ ፡ የሚያጠራጥር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ ተራ፡ (ሰነፍ) ፡ የሆነ ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ ለማቋቋም ፡ እንደ ፡ ተስማሙ ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፮ ። በቀን ፡ ብዛት ፡ ምክንያት ፡ ለመገልገል ፡ መብት ፡ ማግኘት ፤ (፩) የሚታይ ፡ የንረብት ፡ አገልግሎት ።

(፩) ዐሥር ፡ ዓመት፡ በመያዝ ፤ የሚታይ፡ (የታወቀ) ፡ የአገልግሎት ፡ መብት ፡ ይገኛል ።

(፪) የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ የሚታይ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ መኖሩን ፡ የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ምልክት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፯ ። (፪) የማይታይ ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ።

የማይታይ ፡ (ያልታወቀ) ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ መብት ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ምክንያት ፡ መብት ፡ ሊያስገኝ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፰ ። (፫) ሦስተኛ ፡ ወገኖችን፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) በቀን ፡ ብዛት፡ በንብረት ፡ መገልገል፡ ምክንያት ፡ የሚታይ ፡ የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ መብት ፡ ያገኘና ፡ ይህንንም ፡ አገልግሎት ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መዝገብ ፡ ያስመዘገበ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ መኖርና ፡ መሠረቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ሰነድ ፡ እንዲሰናዳለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) በቀን ፡ ብዛት ፡ መገልገል ፡ ምክንያት ፡ የሚገኘው ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ መብት ፤ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፷፱ ። የፈቃድ ፡ ተግባር ።

(፩) ባንድ፡ መሬት፡ ላይ ፡ ለመገልገል ፡ ወይም ፡ ለመጠቀም ፡ የተሰጠ ፡ ፈቃድ ፡ ለተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ።

(፪) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፈቃዱ ፡ ሊሻር ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፫፻፸ ።የንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ መሠረት ።

(፩) ከአገልግሎት ፡ የሚመነጩ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ በርስት ፡ መዝገብ ፡ በሚደረገው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደነገጉ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የንብረቱ፡ አገልግሎት፡ ወሰን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ በተደረገው ፡ ወሰን ፡ መሠረት ፡ በአመጣጡ ፡ ወይም ፡ በሰላምና ፡ በቅን ፡ ልቡና፡ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ በተደረገበት ፡ ሁኔታ ፡ ሊጠናቀቅ ፡ ይችላል ።

(፫) የሚያጠራጥር፡ ሲሆን፡ ከአገልግሎት፡ የሚመነጩ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች፡ በሚከተሉት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሚወሰኑ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፹፩ ። የገጠር ፡ የመተላለፍ ፡ መብትና ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ።**

(፩) የመተላለፍ፡ መብት፡ በእግር ፡ ወይም ፡ ከከብት ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ሰብል ፡ በሌለበት ፡ ወቅት ፡ ወይም ፡ በእርሻ ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ ከደን ፡ ለመውጣት ፡ መተላለፍን ፡ የመሰሉ ፡ ሁሉ ፤ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የመተላለፉ ፡ መብት ፡ መጠን ፡ በቦታው ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ እንዳለው ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ ይሆናል ።

(፪) ስለ፡ ግጦሽ ፡ ወይም፡ ደን ፡ ስለ ፡ መግባት ፡ ውሃ ፡ ስለ ፡ ማጣጣት ፡ ስለ፡መሰና፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ የገጠር ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ መብት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳለው ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፹፪። ስለ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ፡ አከናወን ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑ ፡ ዘዴዎች ፡ (ሁኔታዎች) ።**

(፩) የንብረት፡ አገልግሎት፡ መኖር ፡ ለአከናወኑ ፡ አስፈላጊ ፡ ዘዴዎችን ፡ ያስከትላል ።

(፪) እንደዚሁ፡ ካንድ ፡ ምንጭ፡ ውሃ ፡ የመቅዳት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እስከ፡ ምንጩ ፡ ለመድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ የመተላለፍ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፹፫ ። አስፈላጊ ፡ ሥራዎች ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የንብረት፡ አገልግሎት፡ መስጠት ፡ (መቀበል) ፡ የሚገባው ፡ መሬት፡ባለሀብት፡ በንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ ለመጠቀምና ፡ አገልግሎቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ ለማድረግና ፡ ሥራዎችን ፡ ሁሉ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላል ።

(፪) የንብረቱን፡ አገልግሎት፡ የሚያቋቁመው ፡ ሰነድ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ነገር፡ካልተናገረ ፡ በቀር ፡ የነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ ወጪ ፡ በራሱ ፡ እንጂ ፡ የንብረቱን ፡ አገልግሎት ፡ ሰጪ ፡ የሚሆነው ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ ኪሣራ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፹፬ ። (፪) የመተው ፡ መብት ።**

የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ሰጪ ፡ የሆነው ፡ ርስት ፡ ባለሀብት ፡ በአገልግሎቱ ፡ ለመጠቀም ፡ ወይም ፡ በደኅና ፡ ለመኖር ፡ በኪሣራው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመሥራት ፤ ሰነዱ ፡ የሚያስገድደው ፡ ቢሆንም ፡ በአገልግሎቱ ፡ ለሚጠቀመው ፡ ባለሀብት ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጠውን ፡ ርስት ፡ ወይም ፡ ለአገልግሎቱ ፡ አከናወን ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ድርሻውን ፡ በመተው ፡ ዘወትር ፡ ከግዴታው ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፹፭ ። በአገልግሎቱ ፡ የሚጠቀመው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ግዴታ ።**

(፩) በአገልግሎቱ፡ የሚጠቀመው ፡ መሬት፡ ባለሀብት ፤ አገልግሎት ፡ የሚበጠው፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ጉዳት ፡ እንዳያገኘው ፡ አድርጎ፡ በመብቱ፡ ሊሠራበት ፡ ይገባዋል ።

(፪) በአገልግሎቱ፡ የሚጠቀመው፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ በአገልግሎት ፡ የሚጠቀመው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ በሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጠውን ፡ መሬት ፡ ሁኔታ ፡ የሚያከብድ ፡ ማለዋወጥ ፡ ሳያደርግ ፡ (ለማድረግ ፡ ሳይችል)፡ በሰነዱ ፡ መሠረት ፡ በንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ ሊገለገልበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፸፬ ። በአገልግሎቱ ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆነ ፡ መሬት ፡ የሚያስፈልጉ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ።**

በንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆነው ፡ መሬት ፡ የሚያስፈልጉት ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ ምንም ፡ የአገልግሎትን ፡ ማክበድ ፡ አያስከትሉም ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፸፭ ። በንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ ስለሚጠቀመው ፡ መሬት ፡ መከፋፈል ።**

(፩) በንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀመው ፡ መሬት ፡ የተከፋፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ሁኔታ ፡ የከበደ ፡ ሳይሆን ፤ አገልግሎቱ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ድርሻ ፡ የተገባ ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።

(፪) እንዲሁም፡ ለምሳሌ ፡ ስለ፡ መተላለፍ ፡ መብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማንኛዎቹም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ በዚያው ፡ በተለመደው ፡ ቦታ ፡ ለመተላለፍ ፡ የተገደዱ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በንብረቱ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀመው፡ ከድርሻዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገልግሎቱን ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ የሌሎቹ ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ መብት ፡ እንዲሠረዝ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፸፮ ። የንብረቱን ፡ አገልግሎት ፡ ስለሚሰጠው ፡ መሬት ፡ መከፋፈል ።**

(፩) የንብረቱን፡ አገልግሎት፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ የተከፋፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ አገልግሎቱን ፡ ይቀጥላል ።

(፪) አገልግሎቱ ፡ ባንዳንድ ፡ ክፍሎች፡ ላይ ፡ በርግጥ ፡ የማይከናወንና ፡ ለመከናወን ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የነዚሁ ፡ ክፍሎች ፡ ባለሀብት ፡ በክፍሎች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፸፯ ። የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ግዴታ ።**

የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ አገልግሎትን ፡ የሚቀንስ ፡ ወይም ፡ የማይመች ፡ ዘዴ፡ የማድረግ፡ ዝንባሌን ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፸፰ ። የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ በሚሰጠው ፡ መሬት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ብቻ፡ የሚደረግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገልግሎት ፡ ተቀባይ ፡ የሆነው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ጥቅም ፡ ያለውና ፡ ወጪውን ፡ (ኪሣራውን) ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፤ ሥራው ፡ በአ

ገልግሎት ፡ ለሚጠቀመው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ምቹነትን ፡ ሳያሳጣ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እንዲዛወር ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፷፩ ። የንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ መቅረት ።**

(፩) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መዝገብ ፡ ላይ፡ የተጻፈው ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት፡ በጽሑፉ ፡ መሠረዝ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) በአገልግሎቱ ፡ የሚጠቀመው፡ መሬት ፡ ባለሀብት፡ ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቱ፡ የሚገባውን ፡ አገልግሎት ፡ ትቻለሁ ፡ ሲል ፡ በጽሑፍ ፡ በማረጋገጥ ፡ እሳቡን ፡ ፀግልጽ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ በመዝገብ ፡ የተጻፈው፡ጽሑፍ፡ እንዲሠረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፫) እንዲሁም፡ የሚታይ፡ አገልግሎት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አገልግሎት፡ መኖሩን፡ የሚገልጹት ፡ ሥራዎች ፡ በጠፉ ፡ ወይም ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ የማያገለግሉ ፡ ሆነው ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ በመዝገብ ፡ የገባው፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፷፪ ። የንብረቱ ፡ አገልግሎት ፡ በከፊል ፡ መቅረት ።**

የንብረቱ፡ አገልግሎት፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ንብረቱ፡ አገልግሎት ፡ መኖርና፡እሱን ፡ በሚመለከተው ፡ ዐይነት ፡ በይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፷፫ ። የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መግዛት ። (፩) የሚቻልበት ፡ ሁኔታ ።**

የንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ የሚቻለው ።

(ሀ) ለአገር፡ ኤኮኖሚ ፡ ጥቅም፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ አንዳንድ ፡ የሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በአገልግሎት፡ ለሚጠቀመው፡ መሬት ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም፡ አገልግሎትን ፡ በሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ማወክና፡የዋጋ፡ መቀነስ ፡ የማይመዛዘን ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፷፬ ። (፪) አሠራር ።**

(፩) በባለጉዳዮቹ፡ መካከል፡ ስምምነት ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገልግሎትን ፡ በሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ጥያቄ ፡ የአገልግሎቱን ፡ መልሶ ፡ መግዛት ፡ ዳኞች፡ ያዝዛሉ ።

(፪) የንብረቱን፡ አገልግሎት፡መልሶ ፡ በመግዛት ፡ የሚደርሰውን ፡ ኪሣራ ፡ ዳኞች፡ ይወስናሉ ።

BACK



(፫) ዳኞች ፡ ይህን ፡ ኪሣራ ፡ ለመወሰን ፡ በአገልግሎት ፡ ለሚጠቀመው ፡ መሬት ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ አገልግሎትን ፡ ለሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ጉዳት ፡ አገልግሎቱ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ምክንያትና ፡ በተለይም ፡ አገልግሎቱ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ ያመዛዝናሉ ፡ (በግምት ፡ ውስጥ ፡ ያገባሉ) ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፺፭ ። መልሶ ፡ መግዛትን ፡ የሚያስቀር ፡ የውል ፡ ቃል ።**

ባለጕዳዮቹ ፡ አገልግሎትን ፡ በሚያቋቁመው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ በተጻፈ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለማብለጥ ፡ በማይችል ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አገልግሎትን ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ ዳኞችን ፡ የመጠየቅ ፡ ሥልጣንን ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## በቀዳሚነት ፡ ግኘ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፺፮ ። ትርጓሜ ።**

በቀዳሚነት ፡ ግኘ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ዋጋን ፡ በመክፈል ፡ የአንድ፡ ንብረት፡ ሀብትነት፡ ወይም ፡ የአላባ፡ጥቅም፡ ተቀባይነትን ፡ ባንዳንድ፡ ምክንያቶች፡ የሚገዛውን፡ ሦስተኛ፡ ወገን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ላንዱ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ፡ መብት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፺፯ ። በአገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ ማናቸውም ፡ መብት ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በቈየ፡ አገልግሎት ፡ ቢሆንም ፡ በአገልግሎቱ ፡ ብቻ ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፺፰ ። የጋራ፡ ባለሀብቶች ፡ በቀዳሚነት ፡ ግኘ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ።**

(፩) በቀዳሚነት ፡ ግኘ፡ ይገባኛል፡ የማለት ፡ መብት፡ ከጋራው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ፡ ለሚሸጠው፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ለጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ አላቸው ።
(፪) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የሆኑት፡ ባልተከፋፈለው፡ ሀብት፡ ላይ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ፡ መጠን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በቀዳሚነት ፡ ግኘ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብታቸውን፡ ይሠሩበታል ።

(፫) ከመካከላቸው ፡ አንዱ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹ፡ የተዉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌሎቹ ፡ በተተዉ ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ በማለት ፡ መብታቸው ፡ ይሠሩበታል ።

**ቍ ፡ ፲፻፪፻፺፱ ። የዘመዶች ፡ በቅድሚያ ፡ የመግዛት ፡ መብት ፤ (፩) መሠረቱ ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ ከዘመዶቹ ፡ ከአንደኛው ፡ በውርስ ፡ ያገኘውን ፡ ርስት ፡ የሸጠ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሻጩ ፡ ዘመዶች ፡ በቅድሚያ ፡ የመግዛት ፡ መብት ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፹፻፵፺ ። (፪) የዝምድና ፡ ደረጃ ፡ አገማመት ።

(፩) ሻጩ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ያገኘው ፡ በአባቱ፡ የዝምድና፡ መሥመር፡ ከሆነው ፡ ከአንዱ ፡ ዘመዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀደምትነት፡ ለመግዛት ፡ በተሰጠው፡ መብት ፡ ሊጠቀሙ፡ የሚችሉት ፡ በሻጩ፡ የአባት ፡ ወገን ፡ የዝምድና፡ መሥመር፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ዘመዶቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሻጩ ፡ የማይንቀሳቀሰውን፡ ንብረት ፡ ያገኘው ፡ በእናቱ ፡ የዝምድና ፡ መሥመር፡ ከሆነ ፡ ከአንዱ ፡ ዘመዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት፡ በተሰጠው ፡ መብት ፡ ሊጠቀሙ፡ የሚችሉት ፡ በሻጩ ፡ የእናት ፡ መሥመር፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ዘመዶቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፹፻፵፺፩ ። (፫) የቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራ ።

የቤት ፡ ዘመድ ፡ የይገባኛል ፡ ቀዳሚነት ፡ ተራ ፡ የሚወሰነው ፡ ኑዛዜ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ የውርስ ፡ ንብረት ፡ የሚከፋፈልበትን ፡ አኳኋን ፡ በሚመለከተው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ በተጻፈው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፹፻፵፺፪ ። (፬) ለአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ምርጫ ።

በእነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ በይገባኛል ፡ መብታቸው ፡ ሊጠቀሙ ፡ የሚችሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀዳሚነቱ ፡ ምርጫ ፡ የሚሰጠው ፡ በሚሸጠው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩት ፡ ወይም ፡ ራሳቸው ፡ እየሠሩ ፡ በዚሁ ፡ መሬት፡ ለሚጠቀሙት ፡ ቤት ፡ ዘመዶች ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፹፻፵፺፫ ። ስለ ፡ ብዙ ፡ ባለመብቶች ።

(፩) በአንድ፡ የተራ ፡ ደረጃ፡ ውስጥ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባናል ፡ በማለት፡እኩልነት ፡ ያላቸው ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መብቱን ፡ በኅብረት ፡ ይሠሩበታል ፡ በመሬቱም ፡ ትክክል ፡ በሆነ ፡ ድርሻ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) በቀዳሚነት፡ ይገባኛል፡ በማለት ፡ የማይገለገሉ ፡ ሰዎች ፡ ድርሻ ፡ የዝምድና ፡ ተራ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የሌሎቹን ፡ ዘመዶች ፡ ድርሻ ፡ የሚያበዛው ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፹፻፵፺፬ ። በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ አመዳደብ ።

በሕግ ፡ የተደነገገው ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብቶች ፡ በሚከተለው ፡ ተራ ፡ ተመድበዋል ።

(፩) የጋራ፡ ባለሀብት፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፤

(፪) የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባናል ፡ የማለት ፡ መብት ፤

**ቊ ፡ ፪ሺ፫፻፺፫ ። የአንዳንዶች ፡ ሰዎችን ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

ዝቅተኛ ፡ ደረጃ፡ ያለው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በቀዳሚነት፡ ይገባኛል ፡ የማለት፡ መብት፡ ያለውን፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ መብት፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊቃወመው ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፫፻፺፬ ። በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

የተሸጠው ፡ ርስት፡ በከተማ ፡ ቀበሌ፡ ውስጥ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ፡ወይም፡ የተሸጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ፡ሕንጻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ የተደ ነገገው ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ አይቻልም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፫፻፺፭ ። በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የማይተላለፍ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) በሕግ ፡ የተደነገገው ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ በሕግ ፡ መብቱ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ።

(፪) መብቱንም ፡ ባለጥቅሞቹ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሊያስተላልፉ ፡ አይችሉም ።

(፫) ከባለጥቅሞቹም፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ መብት ፡ ተተ ክተው ፡ ሊሠሩበት ፡ አይቻልም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፫፻፺፮ ። በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብትን ፡ እንዲሠሩበት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) በቀዳሚነት፡ ይገባኛል፡ የማለት ፡ መብት ፡ ባለጥቅም ፡ የሆነ ፡ ሰው፡ባለሀብቱ ፡ በፈቃዱ ፡ ሀብቱን ፡ ወይም ፡ የሀብቱን ፡ አላባ ፡ በዋጋ ፡ በሚሸጥበት ፡ በመናቸው ም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ በማለት ፡ በመብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡ ከባለሀብቱ፡ ላይ ፡ የዕዳ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ሀብቱ ፡ በሚያዝበት ፡ ጊዜ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ በመብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፫፻፺፯ ። የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ልል ፡ ማስለቀቅ ።**

የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በሚያስፈልግ ፡ ምክን ያት ፡ እንዲለቀቅ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ባለጥቅም ፡ በዚሁ ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፪ ። በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ በማለት ፡ መብቱ ፡ እንዲገለገልበት ፡ ለመጠየቅ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ (፩) የማስተላለፍ ፡ ማስታወቅ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል፡ በማለት፡ መብት ፡ ሊገለገልበት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱ ፡ በሀብትነት ፡ ወይም ፡ በአላባነት ፡ ለገዢ ፡ ወይም ፡ በሐራጅ ፡ ለሚገዛው ፡ ሰው ፡ የተላለፈ ፡ መሆኑ ፡ ለይገባኛል ፡ ባዩ፡ ከተነገረበት፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በመብቱ ፡ ሊገለገልበት ፡ የፈለገ ፡ መሆኑን ፡ ካላስታወቀ ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፫ ። (፪) ስላለማስታወቅ ።**

(፩) ይህ ፡ እንደዚህ፡ ያለው ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይነገር ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ ንብረቱ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የተላለፈ ፡ መሆኑን ፡ ካወቁበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚቈጠር ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል ፡ በማለት ፡ መብታቸው ፡ ሊገለገሉበት ፡ የፈለጉ ፡ መሆናቸውን ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

(፪) የሥጋ፡ ዘመዶች ፤ ፡ አዲሱ ፡ ባለሀብት ፡ (ገዢው) ወይም ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዩ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እጅ ፡ ካደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚቈጠር ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በቀዳሚነት ፡ ይገባናል ፡ በማለት ፡ መብታቸው ፡ሊገለገሉበት ፡ የፈለጉ ፡ መሆናቸውን ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፬ ። በቀደምትነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ለማን ፡ እንደሚነገር ።**

በቀደምትነት፡ ይገባኛል፡ በማለት ፡ መብት፡ ለመጠቀም ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተመለከቱት ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ለሚመለከተው ፡ ንብረት ፡ አዲስ ፡ ባለሀብት ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፭ ። ዋስትና ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ።**

በቀደምትነት ፡ ይገባኛል፡ በማለት፡ መብት፡ ለመገልገል፡ እንደሚፈልግ ፡ የሚሰጠው ፡ መግለጫ ፡ የንብረቱን ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ የሚያረጋግጡና ፡ ዳኞቹም ፡ በቂ ፡ አድርገው ፡ የሚቀበሏቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ መግለጫው ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፮ ። በተሰጠው ፡ መግለጫ ፡ የሚጠቀሙት ።**

(፩) ከባለመብቶቹ ፡ አንዱ፡ የሚያደርገው ፡ መግለጫ ፡ የሚጠቅመው ፡ በተለይ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያደረገውን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ ስለ ፡ ተባለ፡ ማስታወቂያው ፡ የቀድሞው፡ ባለሀብት ፡ ዘመዶች ፡ ከሆኑት ፡ በዝምድና ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ሥራውን ፡ በሚፈጽም ፡ ባንድ ፡ ዘመድ፡ ተደርጎ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በዝምድናው ፡ መደብ ፡ እኩል ፡ የሆኑት ፡ ዘመዶች ፡ በማስታቂያው ፡ ለመጠቀም ፡ አሳባቸውን ፡ የገለጹ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉም ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ይችላሉ ።

(፫) ይህም፡ አሳብ፡ ማስታወቂያው ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚቈጠር ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካልተገለጸና ፡ ለዚህም ፡ በአመልካቹ ፡ ላይ ፡ የሚታሰብ ፡ ከዋጋው ፡ ድርሻውን ፡ ለመክፈል ፡ የሚያረጋግጡ ፡ በቂዎች ፡ የሆኑ ፡ ዋሶችን ፡ በመጥራት ፡ ወይም ፡ ማረጋገጫዎችን ፡ በመስጠት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

<u>ቍ ፡ ሺ፬፻፺፫ ። በቀደምትነት ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ውጤት ።</u>

(፩) በቀደምትነት፡ ይገባኛል፡ የማለት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በመብቱ ፡ ለመገልገል ፡ መፈለጉን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ለይገባኛል ፡ ባዩ ፡ እንዲያስተላልፍለት ፡ ይገደዳል ።

(፪) የሚገባው ፡ ዋጋ፡ እንደ ፡ ተከፈለው ፡ ይህን ፡ ግዴታውን ፡ ወዲያውኑ ፡ ራሱ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ሺ፬፻፺፬ ። ንብረቱን ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገው ፡ ሰው ፡ መብቶች ። (፩) ዋጋ ።</u>

(፩) ንብረቱን፡ እንዲለቅ፡ የተደረገው ፡ ሰው ፡ የከፈለው ፡ ዋጋ ፡ እንዲመለስለት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ንብረቱን ፡ ገዝቶ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በሽያጩ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ዋጋ ፡ በውነት ፡ ከከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ዝቅተኛ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ አይፈቀድለትም ።

(፫) በቀደምትነት፡ ይገባኛል፡ በማለት ፡ መብት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚፈልገው ፡ ሰውግን ፡ በሽያጩ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ዋጋ ፡ በማስመሰል ፡ የተነገረ ፡ ዋጋ ፡ ለመሆኑ ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፬፻፺፭ ። (፪) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ግምት ።</u>

(፩) በቀደምትነት ፡ መግዛት ፡ ይገባኛል ፡ የማለትን ፡ መብት ፡ ያስከተለው ፡ የንብረት ፡ ማግኘት ፡ ያለ፡ዋጋ ፡ የተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገው ፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ የንብረት ፡ ግምት ፡ የሚተካከል ፡ ዋጋ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ክርክርም፣ በተነሣበት፣ ጊዜ ፡ ዋጋው ፡ የሚወሰነው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በተመለከተው ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፰ ። (፫) ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ።**

(፩) ንብረቱን ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገው ፡ ሰው ፡ ከሚገባው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ንብረቱ ፡ ሲተላለፍለት ፡ ያወጣቸውን ፡ የውልና ፡ የማዘዋወር፣ ወጪዎች ፡ እንዲከፈለው ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ከዚህም ፡ ሌላ፣ የዚህን ፡ ንብረት፣ ዋጋ፣ ከከፈለበት፣ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፣ ተመለሰለት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለከፈለው ፡ ዋጋና ፡ ወጪዎች ፡ ሕጋዊ ፡ ወለድ ፡ እንዲከፈለው ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል፣ በማለት ፡ መብት፣ ለመጠቀም ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው፣ ንብረቱን ፡ እጅ ፡ ካደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚቈጠር ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ ያፈራውን ፡ ሀብት ፡ ለባለይዞታው ፡ በመተው ፡ ወለዱን ፡ ከመክፈል ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፱ ። (፬) ወጪ ።**

ንብረቱን፣ እንዲለቅ፣ የተደረገው ፡ ሰው፣ በለቀቀው ፡ ንብረት ፡ ላይ፣ ያወጣውን፣ ገንዘብና ፡ ንብረቱ፣ በእጁ፣ ሆኖ ፡ በቈየበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በተባለው ፡ ንብረት፣ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ መበላሸት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## ባለሀብቱ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ንብረቶች ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ እንዳያደርግ ፡ መብቱን ፡ ስለ ፡ ማጥበብ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የግገርን ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ የመግዛትን ፡ መብት ፡ ስለሚመለከት ፡ የውል ፡ ስምምነት ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የሽያጭ ፡ ተስፋ ፡ መስጠት ፡ ማለት ፡ የአንድ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ ሀብቱን ፡ ለመግዛት ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ወዲያው ፡ አሳቡን ፡ እንደ፣

ገለጸለት ፡ እሸጥልሃለሁ ፡ ሲል ፡ ለዚያው ፡ ሰው ፡ የሚገባለት ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ ነው ።

(፪) በቀደምትነት ፡ የመግዛት ፡ መብት ፡ ማለት ፡ የአንድ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ ሀብቱን ፡ ለመሸጥ ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ አንዱን፡ ሰው፡ በመምረጥ ፡ ሀብቱን ፡ እሸጥልሃለሁ ፡ ሲል ፡ ለዚሀ ፡ ለመረጠው ፡ ሰው ፡ ከሚገባለት ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ የሚመነጭ ፡ መብት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፲፩ ። የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ዓላማ ፡ ወሰን ።

(፩) ለሽያጭ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ስምምነት፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረትን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሚመለከት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለተስፋ ፡ ሰጪው ፡ የባለሀብትነቱን ፡ መብት ፡ የሚያጠብና ፡ በነዚህም ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ለተስፋ ፡ ተቀባዩ ፡ መብትን ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ።

(፪) በሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ የግዴታዎች ፡ ግንኙነቶች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአራተኛውና ፡ በአምስተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ተወስኗል ።

(፫) ከዚህ፡ በታች፡ የሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እነዚህ ፡ ስምምነቶች ፡ ከሚያስከትሉት ፡ ከእውነተኛው ፡ ውጤት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አያመለክቱም ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፲፪ ። ስምምነቱ ፡ የሚጸናበት ፡ ሁኔታ ።

ለሽያጭ ፡ የተስፋ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ ወይም፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ስምምነት ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገና ፡ ባለጥቅሙ ፡ የሚጠቀምበት ፡ ጊዜና ፡ ዋጋ ፡ ተለይቶ ፡ ካልታወቀ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፲፫ ። ከፍተኛ ፡ ጊዜ ።

(፩) ለሽያጭ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ በውል ፡ የሚሰጠው ፡ መብት ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ።

(፪) በውሉ፡ ቃል፡ ጊዜው ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ እንዲቈይ ፡ ተነግሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ጊዜ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፲፬ ። ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ርስትን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ።

(፩) ለሽያጭ፡ የተስፋ፡ ቃል፡ መስጠትና ፡ ስለ ፡ ግዢ ፡ ቀደምትነት ፡ መብት ፡ መስጠት ፡ የሚያደረጉት ፡ ስምምነቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅም፡ የተወሰደ፡ ወይም፡ ለጊዜው፡ የተያዘ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ፈራሾች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



(፪) በዚሁ፡ ምክንያት፡ የነዚህ ፡ መብቶች ፡ ባለጥቅሞች ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አን ዳች ፡ ኪሣራ ፡ አይሰጣቸውም ።

ቍ ፡ ፳፩፻፲፩። መብቶቹ ፡ የማይተላለፉ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

(፩) ለሽያጭ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ መስጠትና ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ በውል ፡ የሚሰጠው ፡ መብት ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር፡ የነዚህ፡ መብቶች ፡ ባለጥቅም ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የተሰጡ ፡ ናቸው ።

(፪) ባለጥቅሞቹ ፡ መብቶቻቸውን ፡ ሊያስተላልፏቸው ፡ አይችሉም ፤ እንዲሁም ፡ ለወራሾቻቸው ፡ አያልፍም ።

(፫) ከባለጥቅሙ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በባለጥቅሙ ፡ ስም ፡ በሻጭነት ፡ ምርጫ ፡ ወይም ፡ በግዢ ፡ ቀደምትነትም ፡ መብት ፡ ለመሥራት ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፳፩፻፲፪ ። ለሽያጭ ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ (፩) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ዋስትናን ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለመሸጥ ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለጥቅሙ ፡ ለመግዛት ፡ መፈለጉን ፡ እንዲያስታውቅ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ተስፋ ፡ ሰጪው ፡ ንብረቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፤ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ማንኛውንም ፡ ዋስትና ፡ ሊያቋቁም ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ለመሸጥ ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ በተሰጠው ፡ ውስጥ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ላልሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆን ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ በመያዣ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፳፩፻፲፫ ። (፪) ስለ ፡ ንብረቱ ፡ መያዝ ።

(፩) ለሽያጭ ፡ የተሰፋ፡ ቃል ፡ የተሰጠበት፡ ንብረት ፡ የተያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለዕዳው ፡ የንብረቱን ፡ መያዝ ፡ ቃል ፡ ለተገባለት ፡ ባለጥቅም ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ባለጥቅሙም ፡ ውሉ ፡ እንዳይፈርስበት ፡ (እንዳይቀርበት) ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ በሐራጅ ፡ ከመሸጡ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ግዢ ፡ በተሰጠው ፡ የምርጫ ፡ መብቱ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፳፩፻፲፬። በቀደምትነት ፡ የመግዛት ፡ መብት ፤ በንብረት ፡ ላይ ፡ ዋስትናን ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ።

(፩) ለሌላ ፡ ሰው ፡ የግዥ ፡ ቀደምትነትን፡ መብት፡ የሰጠ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የግዢ ፡ ቀደምትነት ፡ በሚመለከተው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ዋስትናን ፡ ሊያቋቁምበት ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ የተባለውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፡ ለመለወጥ ፡ ያሰበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚህ ፡ መብት ፡ ባለጥቅም ፡ ማስታወቅ ፡ ብቻ ፡ አለበት ።

BACK



(፫) እንደዚሁም፡ የማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት ፡ የተያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለባለጥቅሙ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፩፻፲፱ ። በግገር ፡ ቀደምትነት ፡ መብት ፡ ለመሥራት ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ።

(፩) የማይንቀሳቀሰውን፡ ንብረት፡ የመሸጥ ፡ የመለወጥ ፡ አሳብ ፡ መኖሩን ፡ የገዥ፡ ቀደምትነት ፡ መብት ፡ ለተሰጠው ፡ ባለጥቅም ፡ ከተነገረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በሚቈጠር ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠራበት ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ በውል ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) ጊዜው፡ ከአንድ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያለክር ክር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ እንዲወርድ ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ሺ፩፻፳ ። በገዥ ፡ ቀደምትነት ፡ መብት ፡ ስላለመሥራት ።

(፩) የገዥ፡ ቀደምትነት፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ባለጥቅም ፡ በመብቱ ፡ ሳይጠቀም በት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

(፪) ባለሀብቱም ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረቱን ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ በነፃ ፡ ለመ ሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላል ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ንብረቱን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፩፻፳፩ ። የንብረት ፡ መያዝ ።

(፩) ንብረት፡ በሚያዝበት፡ ጊዜ፡ ንብረቱ፡ በሐራጅ፡ ከመሸጡ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ግገር፡ ቀደምትነት ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ ካልተሠራበት ፡ በቀር ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) ማናቸውም ፡ ለዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ሺ፩፻፳፪ ። ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፤ (፩) ሁኔታዎች ።

ለሻያጭ ፡ የተሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ በውል ፡ የሚሰጠው ፡ መብት ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ርስት ፡ መዝገብ ፡ በሚገባ ፡ ካል ተጻፈ ፡ በቀር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፩፻፳፫ ። (፪) ስለ ፡ ሌሎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።

(፩) የማይንቀሳቀሱ፡ ንብረቶች፡ ጕዳይ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፤ እነዚህ ፡ ከዚህ፡ በላይ ፡ የተባሉት ፡ መብቶች ፡ ይህ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለበት ፡ ቦታ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ካልተጻፈ፡ በቀር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገ ኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ አመዘጋገብ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ መኖሩን ፡ ያወቁ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የነበረባቸው ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ሻያጭ ፡ የሚሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ስለ፡ ገዥ ፡ ቅድሚያነት ፡ የሚደረገው ፡

የስምምነት ፡ መብት ፡ በነዚሁ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ አይሆንባቸውም ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፳፬ ። (፫) ስለ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ንብረቶች ።**

ለሻያጭ ፡ የተሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ በውል ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ የሚመለከተው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ የሚችለው ፡ ፫ኛ ፡ ወገኖች ፡ የመብቶቹን ፡ መኖር ፡ ዐውቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የነበረባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፳፭ ። (፩) መቃወሙ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

(፩) ለሻያጭ ፡ የተሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንበት ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለራሱ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገው ፤ መብታቸውን ፡ ባለማክበር ፡ በመጣስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለጥቅም ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ መብቱ ፡ በተቋቋመበት ፡ ጽሑፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ የተባለውን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የንብረቱን ፡ ሀብትነት ፡ እንዲለቅለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ለሻያጭ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ባለጥቅም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ የንብረቱ ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እጅ ፡ ካደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በመብቱ ፡ ካልሠራበት ፡ መብቱ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፫) ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ በሸጠለት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይያዝ ፡ የማድረግ ፡ ስምምነት ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፳፮ ። ተንቀሳቃሽ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ የሚመለከት ፡ ስምምነት ።**

(፩) ግዙፍ ፡ የሆነ፡ ተንቀሳቃሽ፡ ንብረት ፡ የሠራ ፡ ያወጣ ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ የዚህ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ መያዝ ፡ ወሰን ፡ አደርጋለሁ ፡ ሲል ፡ የሚገባባቸው ፡ የውል ፡ ስምምነቶች ፡ በግልጽ ፡ በተቀበሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ።

(፪) እነዚሁ፡ የውል ፡ ስምምነቶች፡ በሕግ ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ ካልተፈቀዱ ፡ በቀር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ አይጸኑባቸውም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፳፯ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት፡ የሆነ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ በግልጽ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ የተባለውን ፡ ንብረት ፡ የማይሸጥ ፡ ወይም፡ የማይያዝ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፳፰ ። ተንቀሳቃሽ ፡ ያልሆነውን ፡ ንብረት ፡ የሚሸጥ ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ሰው ፡ መብት ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ሀብትነትን፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ የተላለፈለትን ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ እንዳይሸጥ ፡—እንዳያስተላልፍ ፡ ለመከልከል ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን፡ ለመቀነስ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የተባለው ፡ ንብረት፡ ከተላለፈለት፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ንብረቱ ፡ የማይያዝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመስማማት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፳፱ ፡ የውል ፡ ቃሎችን ፡ ስለ ፡ መተርጐም ።**

(፩) ከዚህ፡ በላይ፡ ባለው፡ ቍጥር ፡ እንደ፡ ተመለከተው ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይያዝ፡ ተብሎ ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ በማጥበብ ፡ መተርጐም ፡ አለባቸው ።

(፪) እንደዚሁም፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ እንዳይሸጥ፡ እንዳይተላለፍ ፡ የሚነገረው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ መሬት ፡ የማይያዝ ፡ አያደርገውም ።

(፫) ደግሞ፡ ንብረቱ፡ እንዳይሸጥ፡ እንዳይያዝ ፡ የተነገሩት ፡ ስምምነቶች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ፡ ያሉት፡ ድንጋጌዎች፡ በሰጧቸው ፡ ሁኔታዎችና፡ በወሰኑዋቸው ፡ ወሰኖች፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፴ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ፎርም ።**

አንድ ፡ ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይያዝ ፡ የሚነገሩት፡ ስምምነቶች ፡ ፈራሽነትን ፡ እንዳያስከትሉ ፡ በጽሑፍ ፡ መደረግና ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የማይሸጥ ፡ የማይለወጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ መለየት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፴፩ ። ከፍተኛ ፡ ጊዜ ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይያዝ ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነቱ ፡ ከኻያ ፡ ዓመት፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም፡ ንብረቱን፡ ሀብቱ ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ በላይ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ስምምነት ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ የውሉ ፡ ስምምነት ፡ ውጤት ፡ የሚያገኘው ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

BACK



(፫) ጊዜው ፡ የሚቈጠርበት፡ መነሻ፡ የማይንቀሳቀሰው ን፡ ንብረት ፡ ሀብትነት፡ ለአ ገኘው ፡ ሰው ፡ ከተላለፈበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፩፻፴፪ ። በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ ስላለመቻሉ ።

(፩) የውሉ ፡ ስምምነት ፡ የሚመለከተው፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በርስት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ በመዝገብ ፡ ተጽፎ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይች ልም ።

(፪) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ስምምነቱ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ተጽፎ ፡ ካልተገኘ፡ በቀር ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም።

ቍ ፡ ፲፩፻፴፫ ። ስለ፡ ዳኞች ፡ ሥልጣን። (፩) ንብረቱ ፡ እንዳይያዝ ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት።

ማናቸው ም፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ የማይንቀሳቀ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ ለመፍቀድ ፡ የሚችሉት ፡—

(ሀ) ንብረቱ ፡ እንዲያዝለት ፡ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብ፡ጠያቂ ፡ ለማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ ላለበት ፡ ሰው ፡ ላቀረበው ፡ ምግብ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈለው ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ዕዳው ፡ የመነጨው ፡ ባለሀብቱ ፡ ከሠራው ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፩፻፴፬ ። (፪) ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።

(፩) ዳኞች ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የተባለው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ እንዲሸጥ ፡ እንዲለወጥ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያሰጥ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለውን ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ፡ እንዲለወጥ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሁለቱ ፡ ወገን፡ ተዋዋዮች፡ የተለየ ፡ ስምምነት ፡ በማድረግ ፡ የተባለውን ፡ ሥል ጣን ፡ ሊያስቀሩባቸው ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ፡ የተባለውን፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ በመጣስ ፡ የማይን ቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ እንዲለወጥ ፡ ተብሎ ፡ የሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ የዚህን ፡ የንብረት ፡ ባለሀብትነት ፡ ያስተላለፈው ፡ (ያዛወረው)፡ ሰው ፡ በሕይ ወት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እና ፡ እርሱም ፡ ፈቃዱን ፡ ለመግለጽ ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ የሚገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ።

ቊ ፡ ሺ፩፻፴፭ ። ንብረት ፡ እንዳይያዝ ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ።

፩ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብትነት ።

(፩) እንዳይያዝ፡ ስምምነት ፡ የተነገረበት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ ተይዞ ፡ በፍርድ ፡ እስከ ፡ ተሸጠ ፡ ድረስ ፡ ንብረቱ ፡ እንዳይያዝ ፡ የተነገረ ፡ ስምምነት ፡ አለኝ ፡ ሲል ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ስምምነት፡ አልጠቀምም፡ በማለት ፡ አስቀድሞ፡ የተነገረው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) ባለሀብቱ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ይህ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚያዝ ፡ አለመሆኑን ፡ በሚገባው ፡ ጊዜ ፡ ሳያስታውቀው ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ንብረት ፡ መያዝ ፡ ምክንያት ፡ ለሚወጣው ፡ ኪሣራ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቊ ፡ ሺ፩፻፴፮ ። (፪) ሌሎች ፡ ሰዎች ።

(፩) ንብረቱ ፡ እንዳይያዝ፡ የተነገረውን፡ ስምምነት ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ እንዲያስከብር ፡ እርሱ ፡ የላከው ፡ ሰው ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

(፪) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ እንዳይያዝ ፡ በተነገረው ፡ ስምምነት ፡ ሊጠቀምበት ፡ ያልፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንብረቱ ፡ መያዝ ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ እንዲያስከብር ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) ንብረቱን ፡ ለሚያስይዘው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂም ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ሺ፩፻፴፯ ። (፫) የውሉን ፡ ቃል ፡ የማስታወቂያ ፡ ጊዜ ።

(፩) የንብረቱ ፡ መያዝ ፡ ተነግሮት ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ ለመጠቀም ፡ የሚፈልግ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ በሐራጅ ፡ ለሌላ ፡ ከመሸጡ ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ የውል፡ ቃል ፡ ለመጠቀም ፡ መፈለጉን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) የዚህ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዝ ፡ ያልተነገረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በሐራጅ ፡ ከተሰጠበት ፡ እንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ ለመጠቀም ፡ መፈለጉን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) የተባለው ፡ ንብረት ፡ እንዳይያዝ ፡ የተነገረው፡ ስምምነት፡ እነዚህን ፡ ጊዜዎች ፡ ለማስረዘም ፡ አይችልም ።

ቊ ፡ ሺ፩፻፴፰ ። (፬) ንብረቱን፡ በሐራጅ፡ ከሚሸጠው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ስላሉት፡ ግንኙነቶች።

(፩) በውሉ ፡ ቃል ፡ ለመጠቀም ፡ የሚፈልገው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የተወሰነውን ፡ ዋጋ ፡ በማስከፈል ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ፡

ሆነ ፡ በሐራጅ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ የከፈለወን ፡ ዋጋ ፡ በመክፈል ፡ ንብረቱ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ እንዲያስተላልፍለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ስለ፡ተደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ወይም ፡ በሐራጅ ፡ ንብረቱ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ስላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በተነገረው ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፱ ። (፭) በሐራጅ ፡ ካገኘው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ንብረቱን ፡ የራሱ ፡ ካደረገ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ስላለ ፡ ግንኙነት ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ በሐራጅ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ ለሌላ ፡ የሸጠ ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአካባቢ ፡ ነገሮች ፡ ይህን ፡ ለማወቁ ፡ ማስረጃ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያገኘ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ንብረቱን፡ የራሱ፡ ያደረገውን፡ የኋለኛውን፡ (አዲሱን)፡ሰው፡ ለመጉዳት፡ አይቻልም።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚፈልግ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ በሐራጅ ፡ በተላለፈበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ ንብረቱን ፡ ገንዘብ ፡ ባደረገው ፡ በኋለኛው ፡ (በአዲሱ) ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይኖረዋል ።

(፫) እንዲህ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ውጤት ፡ መስጠቱ ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲ ። ንብረቱ ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የሚነገር ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የሚሰጣቸው ፡ ውጤቶች ። (፩) የውሉን ፡ ቃል ፡ ለመጥቀስ ፡ ማን ፡ እንደሚችል ።**

(፩) አንድ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የተነገረውን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በመጣስ ፡ ይህን ፡ የተባለውን ፡ ንብረት ፡ የሸጠ ፡ ባለሀብት ፡ ንብረቱን ፡ በገዛው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ።

(፪) አንድ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የተነገረውን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለመጥቀስ ፡ የሚችለው ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ የተስማማው ፡ ወይም፡ ይህን ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ ለማስከበር ፡ እርሱ ፡ የላከው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፩ ። (፪) ጊዜ ።**

አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ በተነገረው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለመጠቀም ፡ ሲባል ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ ከተሸጠበት ፡ ከተለወጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥና ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የተወሰነው፡ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ካልቀረበ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

BACK



ቍ ፡ ፲፻፱፻፵፱ ። ንብረቱን ፡ የራሱ ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ስላሉት ፡ ግንኙነቶች ።

(፩) የማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ያደረገና ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ እንዳይያዝ ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ በስምምነቱ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ የመግዛት ፡ ተቀዳሚነት ፡ መብታቸውን ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ንብረቱን፡ እንዲለቅ፡ የተደረገው ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ ሽጦለት ፡ በነበረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በዋስነቱ ፡ የሚያቀርብበት ፡ አቤቱታ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፶ ። ስለ ፡ አደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ።

የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪን ፡ ስለሚመለከተው፡ጉዳይ፡በዚህ፡ሕግ ፤ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ሀብቶች ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## አንቀጽ ፡ ዘጠኝ ።

## በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

## ምዕራፍ ፡ አንድ ።

## የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ( የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ) ፡ እና ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፶፩ ። የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አስተዳደር ፡ ሁኔታ ።

(፩) የመንግሥት፡ ንብረት፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ክፍል ፡ ንብረቶች ፡ በጠቅላላው ፡ የባለግል ፡ ንብረት ፡ ለሆኑት ፡ ሀብቶች ፡ በተደነገጉት ፡ ሕጎች ፡ የሚተዳደሩ ፡ ናቸው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም፡ እነዚህ ፡ ንብረቶች ፡ ለጠቅላላ፡ አገልግሎት ፡ ጥቅም፡የተመደቡ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚተዳደሩ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፵፬ ። የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ፡ (፩) መሠረቱ ።**

የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው፡የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅት ፡ ንብረቶች ፡ የሆኑ ፡ ሀብቶች ፡ ተብለው ፡ የሚቈጠሩት ፤

(ሀ) ሕዝብ፡ እንዲጠቀምባቸው፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ እንዲገለገልባቸው ፡ የተመደቡ ፡ ሲሆኑ ፤

(ለ) ለአንድ ፡ የሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ለሚሆን ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ለተመደቡ ፡ ሲሆኑና ፡ በዐይነታቸው ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አሠራሮች ፡ ለዚሁ ፡ የአገልግሎት ፡ ድርጅት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ይበልጥ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ የተመደቡ ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፵፭ ። (፪) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅት ፡ ንብረቶች ፡ የሆኑት፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረቶች ።

(ሀ) ጎዳናዎችና ፡ መንገዶች ፡ የውሃ ፡ ቦዮችና ፡ የምድር ፡ ባቡሮች ፤

(ለ) የባሕር ፡ ዳርቻዎች ፤ በወደብ፡ ላይ፡ የተቋቋሙ ፡ ነገሮችና ፡ የወደብ ፡ መብራቶች ።

(ሐ) በተለይ፡ ለሕዝብ፡ አገልግሎት ፡ የተቋቋሙ ፡ ሕንጻዎች ፡ እንደ ፡ ምሽግና፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሉ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፤ የሕዝብ ፡ አገልግሎት፡ ንብረቶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፵፮ ። (፫) ውሃዎች ።**

(፩) እንደዚሁም ፡ ወራጅ ፡ ውሃዎች ፡ ሐይቆችና ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የውሃ ፡ ንጣፎች ፡ በተለይ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ፡ ተብለው ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) የውሃዎችን፡ ባለሀብትነትና፡ አገልግሎት ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተጻፉት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይፈጸማሉ ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፵፯ ። (፬) ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ።**

ከዚህም ፡ በቀር ፡ አቀማመጣቸው ፡ ወይም፡ የተመደቡት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሆኑና ፡ ለሕዝብ ፡ ትርኢይት ፡ የተቀመጡ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረቶች ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፵፰ ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ፡ ወሰን ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

(፩) የአስተዳደር፡ ክፍል፡ ባለሥልጣኖች ፡ የወራጅ ፡ ውሃዎችንና ፡ የባሕር ፡ ጠረፎችን ፡ የተፈጥሮ ፡ ወሰን ፡ ክልል ፡ ይመድባሉ ።

BACK



(፪) የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሰጠው፡ ውሳኔ ፡ ያለ፡ አገባብ ፡ መሆኑን ፡ ዳኞች ፡ የገመቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጎዱት ፡ የግል ፡ ባለሀብቶች ፡ ስለ ፡ ንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ በተደነገጉት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኙ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፫) በእንደዚህ፡ ያለው፡ ጉዳይ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ዳኞች፡ ሊሽሩት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፶፱ ። ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅና ፡ መሥመር ፡ ስለ ፡ ማግባት ።**

(፩) የአስተዳደር፡ ክፍል፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረትን ፡ ለማስለቀቅ፡ በተሰጠው ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት፡ ለአውራ ፡ ጐዳናዎችና ፡ ለመንገዶች፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መሬቶች ፡ ከባለግሎች ፡ ላይ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ መሥመር፡ ስለ፡ ማግባት፡ በተደነገገው ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ የሕዝብ ፡ ጐዳናዎችንና ፡ መንገዶችን ፡ ለማስፋትና ፡ ለማስተካከል ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷ ። መሥመር ፡ ስለ ፡ ማግባት ። (፩) ሕንጻ ፡ ያልተሠራባቸው ፡ መሬቶች ።**

በከተማው ፡ ፕላን ፡ አቀያየስ ፡ መሠረት ፡ በሕዝብ ፡ ጎዳናዎች ፡ ክልል፡ውስጥ፡ የሚገኙት ፡ መሬቶች ፡ ሕንጻ ፡ ያልተሠራባቸው ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ በዚሁ ፡ በመንገድ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ይመደባሉ ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፩ ። (፪) ሕንጻ ፡ የተሠራባቸው ፡ መሬቶች ።**

(፩) በከተማው፡ ቅያስ፡ መሠረት ፡ ለሕዝብ ፡ ጎዳና ፡ በተከለለ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ሕንጻዎች ፡ የማፈግፈግ ፡ ግዴታ ፡ ይኖርባቸዋል ።

(፪) የነዚህ ፡ ሕንጻዎች ፡ ባለሀብት ፡ የነዚህን፡ ሕንጻዎች ፡ ጥንካሬ ፡ የሚያሳድግ ፡ ወይም ፡ የሚቈዩበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚያራዝም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፪ ። (፫) ስለ ፡ ኪሣራ ።**

የንብረቶቹ ፡ ባለቤቶች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ባለመብቶች ፡ ሀብታቸው ፡ በከተማው ፡ ቅያስ ፡ ፕላን ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ መወሰዱ ፡ ወይም ፡ ለዚህ ፡ ዐይነት ፡ አገልግሎት ፡ በመመደቡ ፡ ለሚደርስባቸው ፡ ጉዳት ፡ የሚጠይቁት ፡ ኪሣራ ፡ የሚወሰነው፡በዚሁ፡ አንቀጽ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ጥቅም ፡ ስለሚለቀቁ ፡ ሀብቶች ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ በተደነገገው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፫ ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ሀብቶች ፡ የማይሸጡ ፡ የማይተላለፉ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ሀብቶች ፡ ከዚሁ ፡ አገልግሎት፡ውጭ፡መሆናቸው ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ መመደባቸው ፡ መቅረቱ ፡ በሚገባ ፡ ካልተወሰነ፡ በቀር ፡ ሊሸጡ ፡ ሊተላለፉ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፶፭ ። በቅን ፡ ልቡና ፡ የተደረገ ፡ ይዞታና ፡ በንብረቱ ፡ በመጠቀም ፡ ስለ ሚገኙ ፡ ሀብቶች ።**

በቅን ፡ ልቡና፡ በሆነ፡ ይዞታ፡ ወይም ፡ በንብረቱ ፡ በመጠቀም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በተመደበው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ለመሆን ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፶፮ ። ስለ ፡ ኪራይ ።**

ውሎቹ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበውን ፡ ንብረት ፡ ለአገልግሎቱ ፡ እንዳይውል ፡ ለማድረግ ፡ ሲባል ፡ ካልተደረጉ ፡ በቀር ፡ ንብረቶቹን ፡ በኮንሴሲዮን ፡ ለግል ፡ ሰዎች ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፶፯ ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በተመደበው ፡ ሀብት ፡ የመጠቀም ፡ ፈቃድ ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ከተመደበው ፡ ንብረት ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ በባለግልነት ፡ ለመያዝ ፡ አይችልም ።

(፪) ይህም፡ የአስተዳደር፡ ክፍል ፡ የሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ የተፈቀደለት ፡ ባለጥቅም፡ በዚህ ፡ በቦታ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ማቋቋም ፡ የሚችል ፡ መሆኑንና ፡ የሚቋቋመውን ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ ለይቶ ፡ ይገልጻል ።

(፫) ከዚህም፡ በቀር፡ ይህ ፡ ፈቃድ ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተሰጠና ፡ ተጠቃሚውም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዋጋ ፡ እንደሚከፍል ፡ ለይቶ ፡ ይገልጻል ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፶፰ ። ግዴታን ፡ ስላለመፈጸም ።**

ፈቃድ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ የገባባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሰጠውን ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሰጠውን ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰርዘው ፡ ወይም ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፶፱ ። የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ስላለው ፡ የመሻር ፡ መብት ።**

(፩) ተቃራኒ፡ የሆነ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበውን ፡ ንብረት ፡ አጠባበቅን ፡ የሚጎዳ ፡ ወይም ፡ የንብረቱን ፡ አገልግሎት ፡ ግብ ፡ የሚቃወመውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም፡ አሠራር ፡ እንዲቀር ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚሁ ፡ አኳኋን፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ የተስማማባቸውን ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሰጣቸውን ፡ ፈቃዶች ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ድርጅት ፡ ውሎች ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ወይም፡ ባለይዞታው ፡ ያላቸው ፡ የኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

BACK



## ክፍል ፡ ፪ ።

## ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀሙትን ፡ ሀብቶች ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷ ። ትርጓሜ ።**

ንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ማለት ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ አገልግሎት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት፡ እንዲለቅ ፡ የሚያስገድድበት ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፩ ። ይህ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የንብረት፡ ማስለቀቂ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ የሪም ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ግዙፍ ፡ መብት ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ ተብሎ ፡ ሊሠራበት ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲሁም፡ የአስተዳደሩ፡ ክፍል ፡ በወሰደው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ፡ የነበረው ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ዘመኑ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ እንዲቋረጥ ፡ በማድረግ ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቁ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሊሠራበት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፪ ። ባለኮንሴሲዮን ።**

የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ በኮንሴሲዮን ፡ የተሰጠው ፡ ሰውና ፡ አድሚኒስትራሲዮኑ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ የሰጣቸውን ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ መብት ፡ ሊኖራቸው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፫ ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ጠቃሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ የሚደረግ ፡ መግለጫ ።**

አንድ ፡ ሀብት ፡ እንዲለቀቅ ፡ የታቀደ ፡ ሲሆን ፡ ሀብቱ ፡ ከመወሰዱ ፡ በፊት ፡ ተገቢ ፡ የሆኑት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አስቀድሞ ፡ ይህ ፡ ሀብት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ መወሰንና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በቍጥር፡ ፵፬ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ግልጽ ፡ ሁኖ ፡ እንዲወጣ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፬ ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ጥቅም ፡ የሚሆን ፡ ሀብት ።**

(፩) የንብረት፡ ማስለቀቅ ፡ ግቡ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረትን ፡ ለማስለቀቅ ፡ አይቻልም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም፡ ለሕዝብ፡ አገልግሎት ፡ በተሠሩት፡ ሥራዎች ፡ ምክንያት ፡ መሬቶቹ ፡ ያገኙትን ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ ለኅብረት ፡ ጥቅም ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ከሆነ ፡ ንብረቱን ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚቻል ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፩፻፷፭ ። ምርመራ ።**

(፩) አንድ፡ ንብረት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ይጠቅማል ፡ መባሉ ፡ ከመገለጹ ፡ በፊት ፡ ምርመራ ፡ ማድረግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለበት ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ምርመራው ፡ በግልጽ ፡ የሚፈጸም ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ የጥናት፡ ምርመራ፡ በሚደረግበት፡ ጊዜ ፡ ባለጉዳዮች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች፡ ሁሉ ፡ በታቀደው፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ነቀፌታና ፡ አስተያየት ፡ ለማቅረብ፡ ይችላሉ ።

(፫) ባለጉዳይ፡ የሆነው፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል፡ የምርመራውን ፡ አሠራርና ፡ ጊዜ ፡ በደንቦቹ ፡ መሠረት ፡ ይወስናል ።

## ቍ ፡ ፲፬፻፷፮ ። የማስለቀቅ ፡ ትእዛዝ ።

(፩) አንድ ፡ ዐቅድ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ ባለሥልጣኖች፡ ይህነኑ ፡ ዐቅድ ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲለቀቁ ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚባሉትን ፡ የግል ፡ ሰዎች ፡ ሕንጻዎች ፡ ያመለክታሉ ።

(፪) የነዚህ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች፡ ባለሀብቶች ፡ ሌጣ ፡ ባለርስቶችና ፡ ባለሪዎች ፡ የታቀደውን ፡ የኅብረት ፡ መልቀቅ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በሚላከላቸው ፡ ማስታወቂያ ፡ ይገለጽላቸዋል ።

(፫) እንዲሁም ፡ የአስተዳደሩ፡ ክፍል ፡ በአእምሮ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ንብረታቸውን ፡ በሚለቁበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ጥያቄ ፡ ይደረግላቸዋል ።

## ቍ ፡ ፲፬፻፷፯ ። የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ትእዛዝ ።

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ እንዲለቀቁ ፡ የሚደረገው ፡ በንብረት ፡ ማስለቀቂያ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ የንብረት፡ ማስለቀቂያ፡ ትእዛዝ ፡ የሚለቀቀውን ፡ ንብረት ፡ ከማንኛውም ፡ መብት ፡ ነጻ ፡ አድርጎ ፡ ለአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ እንዲተላለፍ ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ።

(፫) ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች፡ ከአስተዳደሩ፡ ክፍል ፡ ጋራ ፡ በቀጥታ ፡ ያሏቸው ፡ መብቶችና ፡ እንዲሁም ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ንብረቱን ፡ እንዲለቅ ፡ ለተደረገው ፡ ባለሀብት ፡ በሚከፍለው ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ፲፬፻፷፰ ። ትእዛዙን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) ንብረት፡ የማስለቀቁ፡ ትእዛዝ ፡ የተለቀቀው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ለሆነው ፡ ሰውና ፡ በዚሁ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብቶች ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ላስመዘገቡት ፡ሰዎች፡ሁሉ ፡ እንዲያውቁት ፡ ይደረጋል ።

(፪) እንዲሁም፡ ባለሀብቱ፡ በዚሁ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አላቸው ፡ ብሎ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ላመለከተው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዙ ፡ ይነገራቸዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፸፱ ። አንድ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረትን፡ በከፊል ፡ እንዲለቀቅ፡ ስለ ፡ ማድረግ።**

(፩) አንድ ፡ ሕንጻ፡ በከፊል ፡ እንዲለቀቅ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሀብቱ፡ይህን፡ ሕንጻ ፡ በሙሉ ፡ አድሚኒስትራሲዮኑ ፡ እንዲወስደው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡ አንድ ፡ መሬት፡ በከፊል ፡ እንዲለቀቅ ፡ ሲደረግ ፡ ቀሪው ፡ የማይጠቅም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመሬቱ ፡ ባለሀብት ፡ አድሚኒስትራሲዮኑ፡በሙሉ፡ እንዲወሰድ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ፡ በላይ፡ የተባሉት፡ መብቶች ፡እንዲለቀቅ፡ በተደረገው፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ላይ፡ ካላቸው ፡ መብቶች፡ ሌላ ፤ ባለርስቱና ፡ የአላባ፡ ጥቅም፡ ተቀባዩ፡ ከዚህ ፡በላይ ፡ ባሉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ የተጻፉት ፡ መብቶች ፡ ይኖራቸዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፹ ። የኪሣራ ፡ ግምት/፡ አወሳሰን ።**

ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ አገልግሎት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የተወሰደባቸው ፡ ባለሀብቶች ፡ወይም፡ ሌጣ፡ ባለርስቶች፡ ወይም ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባዮችና፡ በዚሁ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የንብረቱን ፡ ማስለቀቂያ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያውቁት ፡ ከተነገራቸው ፡ ቀን፡ አንሥቶ ፡ በሚከተለው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የሚጠይቁትን ፡ ኪሣራ ፡ ልክ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፹፩ ። ግምቱ ፡ እንዳይከፈል ፡ ስለ ፡ መቃወም ።**

ባለጒዳዮች ፡ የሆኑ ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች፡በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ከአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ የሚከፈለው ፡ የኪሣራ ፡ ዋጋ ፡ ከአንድ ፡ ከተወሰነ ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ እንዳይሆን ፡ ወይም ፡ መብታቸውን ፡ በመጒዳት ፡ የኪሣራው ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይከፈል ፡ ላስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፹፪ ። በመብቱ ፡ አገማመት ፡ ላይ ፡ ስለሚነሣ ፡ ክርክር ።**

ባለጒዳዩ ፡ የጠየቀውን ፡ ዋጋ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ አልቀበልም፡ ያለ፡እንደ፡ ሆነ ፡ የመብቱን ፡ አገማመት ፡ ክርክር ፡ የሚወስነው ፡ የግምት ፡ የሽምግልና ፡ ኮሚሲዮን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፩፻፹፫ ። የመገመት ፡ የሽምግልና ፡ ኮሚሲዮን ።**

(፩) የአገማመቱ፡ የሽምግልና፡ ኮሚሲዮን ፡ በተሰጡት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የሚቋቋም ፡ የሚሠራና ፡ የሚወሰን ፡ ይሆናል ።

(፪) የኮሚሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ መክፈል ፡ ያለበትን ፡ የግምት ፡ ልክ ፡ መገመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ክርክር፡ በተነሣባቸው፡ መብቶች ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ አይ ችልም ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፸፬ ። የንብረቱ ፡ አገማመት ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ስለ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅ፡ የሚከፈለው ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ መሰል ፡ ምትኩ ፡ መሬቱን ፡ ከማስለቀቁ ፡ የተነሣ ፡ በደረሰውና ፡ በተረጋገጠው ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ይሆናል ።

(፪ ይህ፡ትክክል፡የሆነ ፡ ግምቱ ፡ ወይም፡መሰል፡ምትኩ ፡ የሚገመተው ፡ የአገማመት፡ የሽምግልና ፡ ኮሚሲዮን ፡ በገመተበት ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፸፭ ። በግምት ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡት ፡ ነገሮች ።**

(፩) ኮሚሲዮኑ፡ በሚያደርገው፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ባለጕዳዮቹን፡በማስለቀቅ ፡ የአስ ተዳደር ፡ ክፍል ፡ ስለሚወስዳቸው ፡ ንብረቶች ፡ ወይም ፡ መብቶች፡በሚመለከት፡ ጕዳይ ፡ ባለጕዳዮች ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ያቀረቡዋቸውን ፡ መግለጫዎች ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ያገባል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ በተሠሩት፡ ሥራዎች ፡ ምክንያት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ያልተደረገው ፡ የመሬቱ ፡ ክፍል ፡ ያገኘውን ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ እን ዲሁም ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ያገባል ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፸፮ ። (፫)በግምት ፡ ውስጥ ፡ የማይገቡ ፡ ነገሮች ።**

(፩) የበለጠ፡ግምት ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል፡ በሚለቀቀው፡ ንብረት፡ ላይ ፡ የንብረት፡ ማስለቀቂያ ፡ ትእዛዝ፡ ከደረሰው፡ በኋላ፡የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ማሻሻ ያዎች ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ አያገባቸውም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት፡ ሥራዎች ፡ ሊፈጸሙ ፡ ነው ፡ በመባሉ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሰውን ፡ የዋጋ ፡ መንሣሣት ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ አያገባም ።

**ቍ ፡ ፲፬፻፸፯ ። ለዳኞች ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።**

(፩) የግምት ፡ ክፍል ፡ የሽምግልና፡ የአገማመት፡ ኮሚሲዮን ፡ በሰጣቸው ፡ ውሳኔ ዎች ፡ ላይ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

(፪) ይህም ፡ አቤቱታ ፡ የግምቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ስለ ፡ ግምቱ ፡ ያደረገውን ፡ የመጨ ረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ለባለጥቅሞቹ ፡ ካስታወቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፰ ። የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እጅ ፡ ስለማድረግ ።

(፩) የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሚያስለቅቀውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍል ፡ እጅ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

(፪) የግምት ፡ የሽምግልና ፡ ኮሚሲዮን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ ግምት ፡ አነሰኝ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚከራከረው ፡ ባለሀብቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ወዲያው ፡ ዋጋውን ፡ ከፍሎ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እጅ ፡ ያደርጋል ።
ዳኞችም ፡ ዋጋውን ፡ ቢጨምሩለት ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ይከፍለዋል ። ዳኞች ፡ ግን ፡ ዋጋውን ፡ ሊቀንሱበት ፡ አይችሉም ።

(፫) ስለ ፡ ተወሰደው ፡ መሬት ፡ የሚሰጠው ፡ ምትክ ፡ መሬት ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ እንደ ፡ ወሰነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለተወሰደበት ፡ ሰው ፡ ይሰጠዋል ፡ ዳኞችም ፡ የተሰጠው ፡ መሬት ፡ አይበቃም ፡ ብለው ፡ ቢወስኑ ፡ ትርፉን ፡ ገንዘብ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ይከፍለዋል ።

(፬) ለሚወሰደው ፡ መሬት ፡ ዋጋውን ፡ የግምት ፡ የሽምግልና ፡ ኮሚሲዮን ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ ግምት ፡ በዛብኝ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚከራከርረው ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ፍርዳቸውን ፡ እስኪሰጡ ፡ ባለመሬቱን ፡ መሬቱን ፡ ማስለቀቅ ፡ አችልም ፡ ። ክሱ ፡ ለዳኞች ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት፡ ዳኞቹ ፡ የሚከፍለውን ፡ ግምት ፡ ሳይወስኑ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቂያው ፡ ትእዛዝ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ የባለርስቱ፡ መሬት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይሆናል ።

(፭) ለማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ የተነሣበት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ባለ፡ ጥቅም፡ የሆነ፡ አይከፈል፡ ብሎ ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆነ ፡ ክር ፡ ክር ፡ የተነሣበትን ፡ ገንዘብ ፡ አስይዞ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፱ ፡ ዳኞች ፡ የሚያደርጉት ፡ የዋጋ ፡ ተጨማሪ ።

(፩) በቍጥር፡ ሺ፬፻፸፰ ። በን ፡ ቍ ፡፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡መሬት፡ ለተወሰደበት ፡ ሰው ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ ዳኞች ፡ የጨመሩለት ፡ እንደሆነ ፡ የዳኞቹ ፡ ውሳኔ ፡ መጨረሻ ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ የተጨመረውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፍል ፡ አለበት ።

(፪) የመሬቱ፡ ምትክ፡ ለተሰጠውም ፡ ሰው ፡ ተጨማሪ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ ቢወሰን ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፹ ። በገደብ ፡ የሚደረግ ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ።

(፩) የአስተዳደር፡ ክፍል፡ ያቀዳቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቅዶች ፡ የሚጠይቁትን ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ለማወቅ ፡ ሲል ፡ ለባለጕዳዮቹ ፡ መብታቸውን ፡ በሙሉታ ፡ ሊያስለቅቃቸው ፡ መፈለጉን ፡ ሊያስታውቃቸው ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህም፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ የኪሣራ ፡ አገማመት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ንብረቱ ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚያደርገው ፡ ትእዛዝ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ተጀምሮ ፡ የሚፈጸም ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፩። ስለ ፡ አላፊነት ። (፩) ንብረት ፡ የማስለቀቅ ፡ ነገር ፡ ይደረጋል ፡ ስለማለት ።

ንብረት ፡ የማስለቀቅ ፡ ነገር ፡ ይደረጋል ፡ በመባሉ ፡ ብቻ፡ለሚደርስበት፡ጉዳት፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፪ ። (፪) የኪሣራው ፡ አገማመት ።

(፩) የአስተዳደሩ ፡ ክፍል፡ የተቃወመው፡ የአገማመቱ ፡ ኪሣራ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአገማመቱን ፡ ኪሣራ ፡ የሚችለው ፡ ይህ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

(፪) ለመቃወሚያ ፡ የቀረበው፡ ጥያቄ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘው ፡ መጠን ፡ ግን ፡ የአገማመቱን ፡ ኪሣራ ፡ የሚችለው ፡ ጥያቄ ፡ የአቀረበው ፡ ሰው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፫ ። የታሰበውን ፡ ዐቅድ ፡ ስለ ፡ መተው ፡ (፩) መሠረቱ ።

ይሠራሉ ፡ ተብለው ፡ ለንብረት ፡ ማስለቀቂያ ፡ የሆኑት ፡ ሥራዎች ፡ ሳይፈጸሙ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ባለሀብቶች ፡ የቀድሞ ፡ ሀብታቸውን ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፬ ። የቀዳሚነት ፡ መብት ።

(፩) ከዚህ፡ በላይ ፡ በተጻፈው፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተነገረው ፡ የቀዳሚነት፡መብት፡ በመዝገብ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ የተመዘገበ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ፡ ንብረቱን ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ መልሶ ፡ ከሸጠበት ፡ ወይም ፡ ከሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ መብት ፡ በዚህ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ፡ዓመት፡ድረስ፡ በሦስተኛ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ፡ በቀር፡ የዚህ ፡ የተባለው ፡ መብት ፡ የሚሠራበት ፡ ሁኔታና ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭ ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ሀብት ፤ ስለ ፡ ስለ ፡ አላባ ፡ ጥቅምና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ተወስኗል ።

(፫) የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው፡ በዚሁ ፡ በመብቱ፡ መሠረት ፡ የቀድሞ ፡ ንብረቱን ፡ የሚገዛው ፡ ቀድሞ ፡ ንብረቱን ፡ በማስለቀቅ ፡ በተወሰደበት ፡ ጊዜ ፡ ከአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ በተቀበለው ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፸፭ ። ቀጥተኛ ፡ ያልሆነ ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ። (፩) መሠረቱ ።

የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ በባለግል ፡ ባለቤቶች ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ በሀብቱ ፡ ጥቅም ፡ አሰጣጥ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሰናክል ፡ የማያደርስበት ፡

ከሆነና ፡ የንብረቱንም ፡ ጥቅም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ የሚቀንስ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ ሳይከተል ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ሥራዎች ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ ቀዋሚ ፡ የሆኑ ፡ ድርጅቶች ፡ ለማቋቋም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፬፻፹፮ ። (፪) አፈጻጸም ።

ቀጥተኛ ፡ ባልሆነ ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ በተለይ ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚችሉም ፡ ሥራዎች ።

(ሀ) ተቋቁመው ፡ የሚቈዩበት ፡ ጊዜ፡ ከአንድ፡ ወር ፡ በታች ፡ የሆነና ፡ የማይንቀሳቀሰውን፡ ሀብት፡ ደንበኛ፡ ፍሬ፡ አሰጣጥ፡ የማያሰናክሉ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ፡—

(ለ) በመሬት፡ ውስጥ፡ ለውስጥ፡ የሚያልፉ፡ የውሃ ፡ መሥመሮች ፡ በአየር ፡ላይ፡ የሚያልፉ፡ መሥመሮች ፡ የስልክ ፡ ወይም ፡ የኤሌትሪክ ፡ ምሰሶዎች ፡ ናቸው።

ቍ ፡ ፲፬፻፹፯ ። (፫) የተጠበቀ ፡ መብት ።

ቀጥተኛ ፡ ያልሆነ ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ አሠራር ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ የመብት ፡ መንካት ፡ የሚያደርስ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፲፬፻፹፰ ። (፬) ኪሣራ ።

(፩) የግል ፡ ባለንብረቶች ፡ ከዚህ፡ በላይ፡ በተነገረው፡ ቍጥር፡ በተሠራው ፡ ሥራ፡ ምክንያት ፡ ጉዳት ፡ የደረሰባቸው፡ ሲሆን፡ በደረሰባቸው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ ብቻ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) በኪሣራ፡ አከፋፈሉ፡ ረገድ፡ ከአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ጋራ ፡ በሰላማዊ፡መንገድ ፡ ለመስማማት ፡ ያልተቻለ ፡ ሲሆን ፤ በንብረታቸው ፡ ላይ ፡ ሥራዎቹ ፡ ከተፈጸሙበት፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ በሚቈጠር ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ኪሣራቸው ፡ አከፋፈል ፡ ጕዳይ ፡ አቤቱታቸውን ፡ ካላቀረቡ ፡ ጥያቄያቸው ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የኅብረት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ።

ቍ ፡ ፲፬፻፹፱ ። መሠረቱ ።

ሀብትነታቸው፡ የኅብረት ፡ የሆኑ፡ (የደሽ)፡ እንደ ፡ የጐሣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ በኅብረት ፡ መሠራታቸው ፡ የኅብረቱን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የተከተሉ ፡ መስሎ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረት ፡ የሚሠሩ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፲፬፻፺ ። ልማዶችን ፡ በጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

ለእነዚህ ፡ ኅብረቶች ፡ ለያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ የልማዶቻቸውና ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ልማዶቻቸውን ፡ የሚያሟላ ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲያገኙ ፡ ለማድረግ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስብበታል ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፶፮ ። በመተዳደሪያጡ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፈጡ ፡ ቃል ።

የኅብረት ፡ መተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ጕዳዮች ፡ በተለይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(ሀ) በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፤

(ለ) የኅብረቱ፡ መብት ፡ የሚዘረጋባቸውን ፡ መሬቶች ፤

(ሐ) ኅብረቱ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ አኳኋንና ፡ ለኅብረቱም፡ ወኪል ፡ ለመሆን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፤

(መ) የኅብረቱ፡ መሬቶች ፡ ወይም፡ ሌሎች ፡ ሀብቶች ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እን፣ ሚሠሩና ፡ እንደ ፡ ተከፋፈሉ ፤

(ሠ) የኅብረቱ፡ መተዳደሪያ፡ ደንብ ፡ በመሻሻል ፡ የሚለዋወጥበትን ፡ አኳኋን ፤

ቍ ፡ ሺ፬፻፶፯ ። ልዩነት ፡ ማድረግ ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በኅብረቱ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ በዘራቸው ፤ በሃይማኖታቸው፡ ወይም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃቸው ፡ ልዩነትን ፡ የሚያቋቁም ፡ ውሳኔ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፶፰ ። የኅብረቱ ፡ መሬቶች ፡ የማይሸጡ ፡ የማይተላለፉ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

(፩) በባለይዞታነት ፡ ምክንያት ፡ የኅብረቱ ፡ የሆኑትን ፡ መሬቶች ፡ ሀብትነት ፡ ለማግኘት ፡ አይቻልም ።

(፪) ማንኛውም ፡ ተቃራኒ ፡ ልማድ፡ ቢኖር፡ እንኳ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ካላስፈቀደ ፡ በቀር ፡ ኅብረቱ፡ መሬቶቹን፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላለፍ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፶፱ ። የኅብረቱ ፡ ግዴታዎችና ፡ እንደራሴነት ።

(፩) ኅብረቱ ፡ በድርጅቶቹ ፡ አማካይነት ፡ ውሎቹን ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡ በዚሁ፡ ዐይነት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ለመከሰስ ፡ ይችላል ።

(፫) ከውል ፡ ውጭ፡ ስለሚደርሱ፡ አላፊነቶችና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የተመለከቱት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ በሌሎቹ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ፡ተፈጻሚዎች እንደሚሆኑ ፡ ሁሉ ፡ በእርሻ ፡ ኅብረቶችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፷ ። የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።

(፩) ከእርሻ ፡ ኅብረቱ፡ ላይ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለ ብረቱ ፡ መሬት ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ለኅብረቱ ፡ አባሎች ፡ መተዳደሪያ

ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆኑትን ፡ የኅብረቱን ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ ሌሎቹን ፡ ንብረቶች ፡ ለማስያዝ ፡ አይችሉም ።

(፫) ከኅብረቱ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በኅብረቱ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ እንዳችም ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፶፯ ። የመሬቶች ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፤ (፩) መሠረቱ ።**

የእርሻ ፡ ኅብረት ፡ መሬቶች ፡ የሚለሙበት ፡ አሠራር ፡ ሁኔታ ፡ በኅብረቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ (ቻርት) ፡ ይህም ፡ ባይኖር ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፶፰ ። አፈጻጸም ።**

(፩) የኅብረት ፡ ሀብት ፡ የሆኑት ፡ መሬቶች ፡ ለአባሎቹ ፡ በድርሻ ፡ የሚደለደሉ ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ የሚውሉ ፡ መሆናቸው ፡ የሚወሰነው ፡ በልማድ ፡ ነው ።

(፪) በዚህም ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ የኅብረቱና ፡ የኅብረቱ ፡ አባሎች ፡ በእነዚህ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ያሉባቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ ያሉዋቸው ፡ መብቶች ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በልማድ ፡ ይወሰናሉ ።

(፫) እንዲሁም ፡ ቀድሞ ፡ የተደረጉትን ፡ የመሬት ፡ ክፍያ ፡ ድልድሎች ፡ እንደገና ፡ የማሻሻል ፡ ጉዳይ ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ በምን ፡ ጊዜና ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልማዶች ፡ ይወሰናሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፶፱ ። ልማዶችን ፡ ስለ ፡ ማሻሻል ።**

(፩) የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የኅብረቱን ፡ የኤኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ለማሻሻል ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተመሠረተበትን ፡ የፍትሕንና ፡ የሞራልን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳቦች ፡ ለመከተል ፡ ከነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ጋራ ፡ ተስማሚ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ የኅብረቱ ፡ ልማዶች ፡ በየጊዜው ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ለማድረግ ፡ ያስብበታል ።

(፪) ልማዶች ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንዳይለዋወጡ ፡ ወይም ፡ የእነዚህን ፡ አለዋወጥ ፡ ለአእምሮ ፡ ግምት ፡ በማይስማማ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሆን ፡ የሚያደርግ ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፷ ። ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

የኅብረቱ ፡ ድርጅቶች ፡ በሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፤

(፩) ውሳኔዎቹ ፡ ከኢትዮጵያ፡ ሕገ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ሊታለፉ ፡ ከማይቻሉት፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(፪) ድርጅቶቹ ፡ ውሳኔውን ፡ የሰጡት ፡ ከሥልጣናቸው ፡ በላይ ፡ ወይም ፡ የሥነ ፡ ሥርዐትንና፡ የፍትሕን፡ መሠረታዊ፡ ነገር፡ በመተላለፍ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው።

ቍ ፡ ፲፪፻፸ ። ጸጥታን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብን ፡ መብት ፡ የሚያስቀሩ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የሚሠራበትን ፡ አኳኋን ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ የሚገባ ፡ ባልሆነ ፡ ግዴታ ፡ ውስጥ ፡ የሚያገባ ፡ ማናቸውም፡ ገደብ ፡ ያለበት ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ መቋቋም ።

ቍ ፡ ፲፪፻፸፩ ። የኅብረት ፡ ሥራዎቹ ፡ የሚፈጸሙባቸው ፡ መንደሮች ።

ባንድ ፡ በተለየ ፡ መንደር ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩ፡ሆነው፡በነዚህም፡ ሥራዎች ፡ ምክንያት ፡ በዚሁ ፡ መንደር ፡ የሚገኙትን ፡ መሬቶች ፡ ዋጋ ፡ እጅግ ፡ የሚለዋውጠው ፡ ሲሆን፡ ይህን ፡ መንደር ፡ በኅብረት ፡ ሥራዎች ፡ የሚፈጸምበት ፡ መንደር ፡ ብሎ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐዋጅ ፡ ሊያስታውቅና ፡ በዚሁ ፡ መንደር ፡ በሚገኙት ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብቶች ፡ መካከል ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ እንዲቋቋም ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፸፪ ። የግል ፡ ሙከራ ።

ባንድ፡ መንደር፡ ውስጥ፡ የሚገኙት ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብቶች ፡ በኅብረት፡ ይህን፡ መንደር ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ለማድረግ ፡ የጋራ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመሥራት ፡ በፈቃዳቸው ፡ በመካከላቸው ፡ የባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፪፻፸፫ ። መንግሥት ፡ እንዲያጸድቀው ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።

አንድ ፡ የባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ግማሽ ፡ የሚሆኑ ፡ ባለሀብቶች ፡ ያሉበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ዓላማውን ፡ እንዲፈቅድለትና ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀ ፡ ማኅበር ፡ እንዲሆን ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጠው ፡ የርሻ፡ ሚኒስቴርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፭፻፬ ። ምርመራ ።**

የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለጕዳይ ፡ በሆኑ ፡ ባለሀብቶች ፡ መካከል ፡ በኤኮኖሚና ፡ በማኅበራዊ ፡ ጥቅም ፡ ረገድ ፡ ከማኅበሩ ፡ ይገኛል ፡ የተባለው ፡ ጥቅም ፡ በሀብትነት ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ሊያስከትል ፡ ከሚችለው ፡ ጉዳት ፡ ይልቅ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ምርመራ ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ሺ፭፻፭ ። የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ዐቅድ ፡ (ፕሮዤ) ።**

(፩) የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚያደርገው ፡ ምርመራ ፡ መንግሥት ፡ እንዲያውቀው ፡ ለማድረግ ፡ በሚደግፍ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማኅበሩ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ የደንብ ፡ ረቂቅ ፡ ያደራጃል ።

(፪) ባለጕዳዮቹም፡ በዚሁ ፡ የደንብ፡ ረቂቅ ፡ ላይ ፡ ሐሳባቸውን ፡ እንዲያስታውቁ፡ ይጠየቃሉ ።

(፫) የመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ለባለጕዳዮቹ ፡ እንዲገለጽ ፡ ወይም ፡ እንዲላክ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ በ፮ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መጨረሻውን ፡ የደንብ ፡ ረቂቅ ፡ የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያደራጃል ።

**ቍ ፡ ሺ፭፻፮ ። የማኅበሩ ፡ መታወቂያ ።**

ማኅበሩን ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀ ፡ (አፌሲየል) ፡ የሚያደርገው ፡ መብቱ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ሚኒስትር ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚያወጣው ፡ ማስታወቂያ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፭፻፯ ። አንድ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ ለመፍቀድ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣው ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚጻፈው ።**

(፩) በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀ ፡ የባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ከማቋቋሙ ፡ ወይም ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ማኅበር፡ በመንግሥት ፡ እንዲታወቅ ፡ ከማድረጉም ፡ በላይ ፡ ማኅበሩ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውንበትን ፡ አጥቢያ ፡ ትክክለኛ ፡ ክልል ፡ ይወስናል ።
(፪) እንዲሁም ፡ የማኅበሩን ፡ ደንብ ፡ ያጸድቃል ።

**ቍ ፡ ሺ፭፻፰ ። ማኅበሩን ፡ ስለ ፡ መጠባበቅ ።**

በመንግሥት ፡ የታወቀው ፡ የባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ሥራውን ፡ በተፈቀደለት ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ አለመፈጸሙን ፡ መሬቶቹ ፡ ወይም ፡ አብዛኛዎቹ ፡ መሬቶች ፡ በሚገኙበት ፡ መንግሥት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚያመጣው ፡ ማስታወቂያ ፡ በተከለለው ፡ አጥቢያ ፡ የሚገኙት፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይጠባበቁታል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ።

**ቍ ፡ ፬፻፱ ። የማኅበሩ ፡ ጉባኤ ። (፩) አቋቋሙ ።**

(፩) በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የሚወጣ ፡ ማስታወቃያ ፡ በሚወስነው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብት ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በድንጋጌው ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ በተመለከተው ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ አባልነታቸው ፡ በደንብ ፡ የታወቀላቸው ፡ ነው ።

(፪) እነርሱም ፡ የዚሁ ፡ ማኅበር ፡ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፲ ። ስብሰባዎች ።**

(፩) በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የመሬት፡ ባለሀብቶች፡ ማኅበር ፡ ጉባኤ ፡ በማኅበሩ ፡ አስተዳደር ፡ ደንብ ፡ (በቻርቱ) ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀንና ፡ ስፍራ ፡ በየዓመቱ ፡ ይሰበሰባል ።

(፪) ከዚህ፡ ከተወሰነው፡ ጊዜ ፡ ውጭ ፡ ደግሞ፡ አስቸኳይ ፡ የሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ሲያጋጥሙ ፡ ወይም ፡ ከማኅበሩ ፡ አባሎች፡ አንድ ፡ አምስተኛው ፡ ሲጠይቅ ፡ ጉባኤው፡ ይሰበሰባል ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፩ ። የጉባኤው ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ።**

(፩) የጉባኤው ፡ ውሳኔ ፡ የሚጸፈው ፡ በስብሰባው ፡ ላይ፡ የተገኙት ፡ ወይም ፡ እንደ ራሴዎቻቸውን ፡ የላኩት ፡ አባሎች ፡ በሰጡት ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው ።

(፪) በመንግሥት፡ የታወቁ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ፡ ይህንን ፡ ሥርዐት ፡ ለመለወጥና ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ባላቸው ፡ ጥቅም ፡ ከፍተኛነት ፡ መጠን ፡ አባሎቹ ፡ ያላቸውን ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ በተለይ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) በሌላ ፡ በኩልም፡ ደግሞ ፡ ለአንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ውሳኔዎች ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ስለሚችለው ፡ ጉባኤ ፡ ቍጥር ፡ (ስለ ፡ ኮሩምና) ፡ ስለ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ልዩ ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ደንቡ ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፪ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ።**

(፩) ጉባኤው፡ በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ ማኅበሮችን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ መሾምና ፡ መሻር ፡ እንዲሁም ፡ ሥራቸውን ፡ መቈጣጠር ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፤ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ድርጅቶችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ሀብቶች ፡ በተጻፈው ፡ አንቀጽ ፡ የማኅበሮችን ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ፡ (ዲሬክተሮች) ፡ የሚመለከቱት ፡ በነዚሀ ፡ ሕጎች ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

(፫) እንዲሁም፡ በመንግሥት፡ የታወቁ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶችን ፡ ሥራ ፡ መሪዎች፡ ሥልጣንና፡ አላፊነት፡ ለመወሰን፡ ስለ፡ ማኅበሮች፡ ሥራ፡ መሪዎች ፡ ሥልጣንና ፡ አላፊነት ፡ የተነገሩት ፡ የዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ሕጎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፲፫ ። የመተዳደሪያውን ፡ ደንብ ፡ (ቻርቱን) ፡ ስለ ፡ማሻሻል ፡ (ስለ ፡ መለወጥ)።

(፩) በመተዳደሪያው ፡ ደንብ፡ (በቻርቱ)፡ ውስጥ፡ ደንቡን ፡ ለማሻሻል ፡ ሥልጣን፡ መስጠቱ ፡ በግልጽ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ የማኅበሩን ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀው ፡ ማኅበር ፡ ጉባኤ ፡ ሊያሻሽለው ፡ አይችልም ።

(፪) ማናቸውንም፡ የደንቡን፡ ሌላ ፡ ድንጋጌ ፡ ሁሉ ፡ ለማሻሻል ፡ የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ፈቃድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፲፬ ። ጉባኤው ፡ በሰጠው ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) ማናቸውም፡ በመንግሥት፡ የታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ አባል፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፤ ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ጉባኤው ፡ የሰጠውን ፡ አባሉ ፡ ያልገባበትንና ፡ ከሕግ ፡ ወይም ፡ ከመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተቃራኒ ፡ በሆኑ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ለዳኞች ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ የመቃወም፡ ክስ ፤ አባሉ፡ ውሳኔውን፡ ካወቀበት፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ደግሞ ፡ ውሳኔው ፡ ተፈጻሚነቱን ፡ ካገኘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ የመክሰስ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበበት ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ሊያግድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፲፭ ። የማኅበሩ ፡ ግዴታዎችና ፡ የማኅበሩ ፡ እንደራሴነት ።

(፩) በመንግሥት ፡ የታወቁ፡ የመሬት፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ በሥራ ፡ መሪዎቹ ፡ (በድርጅቶቹ) ፡ አማካይነት ፡ የውል ፡ ስምምነቶችን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚሁም ፡ ዐይነት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመክሰስ ፡ ለመከሰስም ፡ ይችላል ።

(፫) ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርሱ ፡ አላፊነቶችንና ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የተሠሩት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ በተራ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ በሚሆኑበት ፡ ሁኔታ ፡ በመንግሥት ፡ በታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች፡ ማኅበሮችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፲፮ ። የርስት ፡ ባለሀብትነት ።

በማኅበረተኛነት ፡ የተሰበሰቡት ፡ የርስት ፡ ባለሀብቶች ፡ የርስታቸውን ፡ ባለሀብትነት ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ የሚቈዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ለታወቀው ፡ ማኅበር ፡ ሀብትነቱን ፡ የሚለቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማኅበሩ ፡ ደንብ፡

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

## የግል ፡ ርስት ፡ እንዳለ ፡ የሚጠበቅበት ፡ ሁኔታ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፲፯ ። መሠረቱ ።**

(፩) የማኅበሩ ፡ ደንብ፡ ተቃራኒ፡ የሚሆን ፡ ውሳኔ ፡ ያላመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ገንዘባቸው ፡ የነበረውን ፡ የግል ፡ መሬት ፡ ባለሀብትነት ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይቈያሉ ።

(፪) ከዚህ፡ በታች፡ የሚከተሉት ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የግል ፡ ርስት ባለሀብቶች ፡ ከርስቱ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ መብታቸው ፡ ይሠሩበታል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፲፰ ። የርስት ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ መቀነስ ።**

በመንግሥት ፡ የታወቀው፡ የባለሀብቶች፡ ማኅበር፡ ለሱ ፡ በተመደበው ፡ ክልል፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ በኅብረት ፡ እነዚሁኑ ፡ መሬቶች ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ማኅበሩን ፡ እንዲታወቅ ፡ ባደረገው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተፈቀዱትን ፡ ሥራዎች ፡ ለመፈጸም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ሀብትነት ፡ መብት ፡ መቀነስ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፲፱ ። የጉዳትን ፡ ኪሣራ ፡ የማግኘት ፡ መብት ።**

በርስት ፡ ባለሀብቶች ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ የመብት ፡ መቀነስና ፡ በአንዳንድ ፡ የርስት ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ የሚቋቋመው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ፡ በዚህ፡ ምክንያት ፡ መብታቸው ፡ ለተቀነሰባቸው ፡ ወይም ፡ በመሬቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ግዴታ ፡ ለተጣለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ኪሣራ ፡ የሚያሰጡ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፳ ። የጉዳት ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ከዚህ፡ በላይ ፡ ባለው፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራዎች፡በማኅበሩ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በያንዳንዱ ፡ የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ ሊጣሉ ፡ ይችላሉ ።

(፪) አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ የርስት ፡ ባለሀብቶች ፡ ወይም ፡ ጠቅላላው ፡ ማኅበር ፡ የሚከፍላቸውን ፡ የጕዳት ፡ ኪሣራዎች ፡ ልክና ፡ የሚከፍሉበትን ፡ የድርሻ፡ መጠን ፡ የሚወስነው ፡ የማኅበሩ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

(፫) ባለጕዳዮቹ፡ ውሳኔው፡ ከተነገራቸው ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፳፩ ። የርስትን ፡ ባለሀብትነት ፡ የመልቀቅ ፡ መብት ።**

(፩) ማንም፡ የርስት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የርስቱን ፡ ባለሀብትነት ፡ ለማኅበሩ ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ ለመረጠው ፡ ሰው ፡ በመልቀቅ ፡ ከሚጠየቅበት ፡ የገንዘብ ፡ መዋጮ ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

(፪) በእንደዚህ፡ ያለው፡ ጊዜ ፡ ለለቃቂው ፡ ማኅበሩ ፡ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ የርስ ቱን ፡ ዋጋ ፡ (ግምት) ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) የርስቱ፡ ባለሀብት ፡ ለጉዳቱ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፈለውን ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የሚደረጉትን ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፳፪ ። የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ ግምት ።**

(፩) ከዚህ፡ በላይ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተባለው ፡ ጉዳይ ፡ የመሬቱን ፡ ዋጋ ፡ ለመ ገመት ፡ የማኅበሩን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መከተል ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያሉት፡ ድንጋጌዎች፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በም ዕራፍ ፡ ፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ዋጋውን ፡ አስታራቂ ፡ የዘ መድ ፡ ዳኞች ፡ ይወስናሉ ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## መሬቶቹ ፡ የኅብረት ፡ ሀብት ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፳፫ ። የመሬቱ ፡ ሀብትነት ፡ የሚዛወርበት ፡ ጊዜ ።**

የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ፡ ደንብ፡ ማኅበሩ፡ በሚሠራበት፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚ ገኙት ፡ መሬቶች ፡ የማኅበሩ ፡ እንዲሆኑ ፡ ወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የነዚህ ፡ ንብረ ቶች ፡ ሀብትነት ፡ የሚዛወረው ፡ ማኅበሩን ፡ እንዲታወቅ ፡ ያደረገው ፡ ማስታወ ቂያ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፳፬ ። የመዛወር ፡ ውጤቶች ።**

(፩) መሬቶቹ ፡ ከተዛወሩበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የተዛወሩት ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብ ቶች ፡ ወይም ፡ የአላባ ፡ ጥቅም፡ ተቀባዮች ፡ በነዚህ ፡ መሬቶቻቸው ፡ ላይ ፡ በነበ ራቸው ፡ መብት፡ ፈንታ፡ ለማኅበሩ ፡ ከተዛወሩት፡ ንብረቶች፡ ላይ፡ በባለሀብትነት ወይም ፡ በአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነት ፡ ድርሻ ፡ የማግኘት ፡ መብት፡ አላቸው ።

(፪) ለማኅበሩ ፡ በተዛወሩት፡ መሬቶችና፡ በአጠገባቸው ፡ በሚገኙት ፡ መሬቶች ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ አገልግሎቶች ፡ እንዳሉ ፡ ይቈ ያሉ ።

(፫) ለባለጉዳዮቹ፡ መብት፡ መድን ፡ የሚሆኑ ፡ የደንቡ ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ለማኅበሩ ፡ በተላለፉት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የተሰጡት ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መያዣ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ ንብረቶችን ፡ መልሶ ፡ የመውሰድ ፡ ወይም፡ የመግዛት ፡ መብቶች ፡ ውድቅ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፳፭ ። የየአንዳንዱ ፡ ድርሻ ።**

የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሬቶቹ ፡ ደንቡ ፡ በተደነገገበት ፡ ጊዜ ፡ ያላ ቸውን ፡ ዋጋ ፡ በመገመት ፡ የያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ ድርሻ ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ሺ፭፻፳፯ ፡፡ የመሬቶቹ ፡ ግምት ፡፡ (፩) መሠረቱ ፡፡**

የመሬቶቹ ፡ ግምት ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በሆነ ፡ መሠረት ፡ የሚፈጸመው ፡ በዚሁ ፡ የገጠር፡ ክልል፡ ውስጥ፡ የያንዳንዱን ፡ ሄክታር ፡ መካከለኛ ፡ ግምት ፡ በማሰብ፡ነው፡፡

**ቍ ፡ ሺ፭፻፳፯ ፡፡ (፪) ማረሚያ ፡፡**

(፩) የመሬቶቹን፡ ተፈጥሮና፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በግል፡ ያለ፡ችግር ፡ የሚያገኝባቸውን ፡ ጥቅም ፡ በማመዛዘንና ፡ እንዲሁም ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚሆኑትን ፡ የመሬቶቹ ፡ ባለሀብቶች ፡ ያደረጓቸውን ፡ የሥራዎችና ፡ የሕንጻዎች ፡ ዋጋ፡ በማመዛዘን ፡ ግምቱ ፡ የሚታረም ፡ ይሆናል ፡፡

(፪) መሬቱ፡ እስከዚያን፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በተሠራበት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ መሬት ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ አሠራሩን ፡ የቀና ፡ ለማድረግ ፡ በተፈጸሙት ፡ ሥራዎች ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከአንድ ፡ መሬት ፡ የሚገኙት ፡ ልዩ ፡ የሆኑት ፡ ጥቅሞች ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፭፻፳፰ ፡፡ የማኅበሩ ፡ ደንብ ፡፡**

(፩) በመንግሥት፡ የታወቀ ፡ የመሬት፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ሀብቶች ፡ በሆኑት ፡ መሬቶቹና ፡ በሌሎቹ ፡ ሀብቶቹ ፡ ላይ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ የግል ፡ ባለሀብት ፡ ያለው ፡ መብቶች ፡ አሉት ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ግዴታዎች ፡ አሉበት ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፭፻፳፱ ፡፡ የመሬቱ ፡ አሠራር ፡ ደንብ ፤ ሥርዐት ፡፡**

(፩) የማኅበሩ፡ ጉባኤ፡ የማኅበሩ ፡ ሀብቶች ፡ የሆኑትን ፡ መሬቶች ፡ የአሠራር ፡ ዐይነት ፡ ይወስናል ፡፡

(፪) እንዲሁም፡ ከመተዳደሪያው፡ ደንብ ፡ (ከቻርቱ) ፡ ጋራ ፡ በሚስማማ ፡ ዐይነት ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀውን፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ መብታቸውንና ፡ ግዴታቸውን፡ ለይቶ ፡ ያመለክታል ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፭፻፴ ፡፡ ድርሻን ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ፡፡**

(፩) የማኅበሩ ፡ አባሎች፡ በማኅበሩ፡ ንብረቶች፡ ውስጥ ፡ ያላቸውን ፡ ድርሻ ፡ በዋጋ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላሉ ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ ሲሞቱ ፡ ድርሻቸውን፡ ለወራሾቻቸው፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ፡ ለሚያደርጉላቸው ፡ ሰዎች ፡ ያስተላልፋሉ ፡፡

(፫) ከነሱ ፡ ላይ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎቻቸው ፡ የነዚህን ፡ አባሎች ፡ ድርሻ ፡ ለማስያዝ፡ ይችላሉ ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፭፻፴፩ ፡፡ የድርሻ ፡ መከፋፈል ፡፡**

የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ድርሻ ፡ የማይከፋፈል ፡ እንዲሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለማግባት ፡ ወይም ፡ ለድርሻው ፡ መከፋፈል ፡ ወሰን ፡ እንዲኖረው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፲፭፻፴፪ ፡፡ የማኅበሩ ፡ ፈቃድ ፡፡**

(፩) ድርሻው ፡ የተላለፈለት ፡ ወይም ፡ ወራሽ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ድርሻውን ፡ በሐራጅ ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ድሮውንም ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ወራሽ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠር ፡ ተወላጅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማኅበሩን ፡ ፈቃድ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ፡፡

(፪) ባለጕዳዩ ፡ ጥያቄውን ፡ ካላቀረበ ፡ ወይም ፡ በአባልነቱ ፡ ስም ፡ በማኅበሩ ፡ ጉባኤ ፡ ተካፋይ ፡ ሁኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ ያልተቀበለው ፡ መሆኑን ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ወር ፡ ካላስታወቀው ፡ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ አስረጂ ፡ እንኳ ፡ ቢኖር ፡ የማኅበሩን ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ፡፡

**ቍ ፡ ፲፭፻፴፫ ፡፡ ፈቃድን ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡፡**

(፩) ማኅበሩ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥያቄ ፡ ከተደረገለት ፡ ለባለ መብቱ ፡ ድርሻውን ፡ ማኅበሩ ፡ ራሱ ፡ ለመግዛት ፡ ያሰበ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ የሚፈቅድለትን ፡ ይህንኑ ፡ ድርሻ ፡ ገዝቶ ፡ ለመክፈል ፡ የሚ ችል ፡ ሌላ ፡ ገዥ ፡ ለባለመብቱ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ፡፡

(፪) በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማኅበሩ ፡ ለባለመብቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ያላስታወቀ ፡ ወይም ፡ ያልተናገረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመብቱ ፡ የገዛውን ፡ ድርሻ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቀራል ፡፡

**ቍ ፡ ፲፭፻፴፬ ፡፡ የማስተላለፍ ፡ ሁኔታዎች ፡፡**

(፩) ማኅበሩ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱትን ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፡ ያደረጉለት ፡ ባለመብት ፡ ይህን ፡ ድርሻውን ፡ እንዲያስተላልፍ ፡ ይገደዳል ፡፡

(፪) የማስተላለፉ ፡ ዋጋ ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በተነገሩት ፡ ውሳኔ ዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ፡፡

(፫) እነዚሁ ፡ የደንቡ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በም ዕራፍ ፡ ፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ዋጋውን ፡ አስታራቂ ፡ የዘ መድ ፡ ዳኞች ፡ ይወስኑታል ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፬ ፡፡

## የከተማ ፡ ክልል ፡ የሆኑ ፡ ስፍራዎች ፡፡

**ቍ ፡ ፲፭፻፴፭ ፡፡ የክልሉ ፡ አቋቋም ፡፡**

(፩) በበለጠ ፡ ቁጠባና ፡ ጤናማ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ከተማዎች ፡ እንዲስፋፉ ፡ ከማድ ረግ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚያወጡት ፡ ድንጋጌ ፡ የከተማ ፡ ክልል ፡ የሚሆኑ ፡ ስፍራዎች ፡ ሊወሰን ፡ ይቻላል ፡፡

(፪) ድንጋጌው ፡ ይህን ፡ ለከተማ ፡ የተከለለውን ፡ ክልል ፡ በዐዋጅ ፡ ይወስናል ፡፡

## ቍ ፡ ፲፭፻፷፯ ። የከተማ ፡ ቅያስ ፡ (ፕላን) ።

(፩) የከተማ ፡ ቅያስ ፡ በያንዳንዱ ፡ የከተማ፡ ክልል ፡ ለሆነው ፡ ሰፍራ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ የከተማ ፡ ቅያስ ፡ ያደራጃል ።

(፪) የከተማውን ፡ ቅያስና ፡ በዚህም ፡ ላይ፡ የሚደረጉትን ፡ ማሻሻያዎች ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ካላጸደቃቸው ፡ አይጸኑም ።

## ቍ ፡ ፲፭፻፷፰ ። የቅያሱ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የከተማው ፡ ቅያስ ፡ በከተማው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ምክትል ፡ ክልሎች ፡ እንዲኖሩበት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ቅያሱ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ፡ አኳኋን፡ በተቋቋሙት ፡ ምክትል ፡ ክልሎች ፡ ውስጥ፡ ባሉት ፡ የቦታ ፡ ባለሀብቶች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ሊጣሉ ፡ የሚችሉ ፡ የመብት ፡ መቀነስና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ መሬት ፡ አገልግሎትን ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ይወስናል ።

## ቍ ፡ ፲፭፻፷፱ ። የቅያስ ፡ መፈጸም ።

(፩) የከተማውን፡ ቅያስ፡ ለማስፈጸም ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ በቦታዎቹ ፡ ባለሀብቶች ፡ ላይ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የቦታ ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ መቀነስ ፡ ሊያደርግ ባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) በተለየም፡ ቤትን፡ ለመሥራት ፡ ግዴታዎች ፡ መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ የመስ ጠትን ፡ ግዴታዎች ፡ ወይም ፡ በከተማው ፡ ለሚሄደው ፡ ውሃ ፡ መውረጃዎችና ፡ ቦዮች ፡ የሚመለከቱት ፡ ግዴታዎች ፡ ሊጣልባቸው ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲሁም፡ አስፈላጊ፡ ሲሆን ፡ አንዳንድ ፡ የቦታ ፡ ክፍል ፡ እንዲለቁ ፡ ሊጠይ ቃቸው ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፲፭፻፸ ። ግምት ፡ የመቀበል ፡ መብት ።

(፩) በቦታዎቹ ፡ ባለሀብቶች ፡ ላይ ፡ የሚጣለው ፡ የመብት ፡ መቀነስና ፡ ቦታዎ ቹን ፡ የመልቀቅ ፡ ግዴታዎች ፡ መብታቸው ፡ ለተቀነሰባቸው ፡ ወይም ፡ ቦታዎቻ ቸው ፡ ለተወሰደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ግምት ፡ የሚያሰጣቸው ፡ ይሆናል ።

(፪) ለተወሰደባቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚከፈለው ፡ ግምት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በመጀ መሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገረው ፤ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

## ቍ ፡ ፲፭፻፸፩ ። ቤትን ፡ የመሥራት ፡ ፈቃድ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ አሳቡን ፡ ሳይገልጽና ፡ በደንቦቹም ፡ መሠረት፡ቤትን ፡ የመሥራት ፡ ፈቃድ ፡ ሳይቀበል ፡ በከተማው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ።

**ቁ ፡ ፲፮፻፵፩ ። የፈቃድ ፡ ጥያቄ ።**

ፈቃድን ፡ ለማግኘት ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ፡ የታሰበውን ፡ የሕንጻ ፡ ወይም ፡ የቤቶችን ፡ ዐይነት ፡ መዘርዘር ፡ አለበት ።

**ቁ ፡ ፲፮፻፵፪ ። ስለ ፡ ሕንጻ ።**

(፩) የሚሠራው ፡ ሕንጻ ፡ ቤት፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህም፡ ቤት ፡ ለመኖሪያ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ አገልግሎት ፡ ማለት ፡ ለንግድ ፡ ወይም ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ የሚያገለግል ፡ መሆኑን ፡ በጥያቄው ፡ መዘርዘር ፡ አለበት ።

(፪) ሕንጻው ፡ ፋብሪካ፡ ወይም፡ ማጋዘን ፡ ወይም ፡ የኢንዱስትሪና ፡ የንግድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመሥራት፡ የተፈለገውን ፡ የኢንዱስትሪውን ፡ ወይም፡ የንግዱን ፡ ዐይነት ፡ መዘርዘር ፡ ያስፈልጋል ።

**ቁ ፡ ፲፮፻፵፫ ። ሌሎች ፡ ማስታወቂያዎች ።**

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ፈቃድን ፡ ለማግኘት ፡ የሚቀርበው፡ ጥያቄ ፡ የሕንጻው ፡ የቤቶች ፡ ሥራዎች ፡ የሚጀመሩበትን ፡ ጊዜና ፡ የታሰበው፡ ሕንጻ፡ ወይም ፡ የቤቶቹ፡ ሥራ ፡ የሚፈጀውን ፡ ገንዘብ ፡ መለየት ፡ አለበት ።

**ቁ ፡ ፲፮፻፵፬ ። የፈቃዱ ፡ መሰጠት ።**

ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አለመቀበሉን ፡ የሚያመለክት ፡ ወይም ፡ ጥያቄው ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ የተወሰኑትን ፡ ውለታዎች ፡ ጥያቄው ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በ፫ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለባለጉዳዩ ፡ ካላስታወቀው ፤ ፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ይቈጠራል ።

**ቁ ፡ ፲፮፻፵፭ ። የሚፈቀዱ ፡ ውለታዎች ።**

(፩ ሕንጻውን ፡ ለመሥራት ፡ የሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ለታሰበው ፡ ሕንጻ ፡ አገልግሎት ፡ ጠቃሚ፡ የሚሆኑትን ፡ የመንገድ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ቦዮች፡ ጠያቂው ፡ እንዲሠራቸው ፡ የሚያደርግ ፡ ውለታ ፡ ሊኖርበት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም፡ ሊሠራ፡ የታሰበውን ፡ ሕንጻ ፡ ስፋት ፡ ሕንጻው ፡ የሚሠራባቸውን፡ መሥሪያ ፡ ነገሮችን ፡ ወይም ፡ ዐይነትን ፡ (ሞዴል) ፡ ከሚመለከቱ ፡ ውለታዎች፡ ጋራ ፡ የተሰጠ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

**ቁ ፡ ፲፮፻፵፮ ። የማይፈቀዱ ፡ ውለታዎች ።**

ሕንጻን ፡ ወይም ፡ ቤቶችን ፡ ለመሥራት ፡ የሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራውን ፡ ተቋራጭ ፡ ለይቶ ፡ የሚያስታውቅ ፡ ወይም ፡ የቦታው ፡ ባለሀብት ፡ የአንድ ፡ ወይም ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ አገልግሎት ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እንዲያውል ፡ የሚል ፡ ውለታ ፡ ሊቀርብበት ፡ አይችልም ።

BACK



ቍ ፡ ፲፩፻፴፮ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎትን ፡ ስለ፡ ማግኘት ።

(፩) ሕንጻን፡ ወይም፡ቤቶችን፡ለመሥራት፡የሚሰጠው፡ ፈቃድ፤ የጠየቀው፡ሰው፡ ሕንጻው ፡ ወይም፡ ቤቱ፡በሚሠራበት ፡ አጠገብ፡ ከሚገኙት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ እንዲሠሩ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት፡መብት ፡ ያገኘ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ የሚል፡ ውለታ ፡ ሊኖርበት ፡ ይችላል።

(፪) በዚህ፡ ጊዜ ፡ ሕንጻን፡ ወይም፡ቤቶችን፡ ለመሥራት፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው፡ በውዴታ ፡ ያልተስማሙ ፡ ሲሆን ፡ የነዚህን ፡ ባለሀብቶች ፡ ሕንጻ ፡ቤት፡ ወይም፡ እንዳይሠሩ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቶቻቸው ፡ ላይ ፡ የአገልግሎት ፡ መብት ፡ እንዲሰጡት ፡ ሊያስገድዳቸው ፡ ይችላል ።

(፫) በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ላይ ፡ በግድ ፡ የሚሰጠውን ፡ የአገልግሎት ፡ መብት፡ የሚወስኑትና ፡ እንዲሁም ፡ ከማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የአገልግሎት ፡ መብት ፡ ለተደረገበት ፡ ቦታ ፡ ባለሀብት ፡ የሚገባውን ፡ ኪሣራ ፡ የሚወስኑት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፩፻፴፯ ። የፈቃድ ፡ አለመኖር ።

ሕንጻን፡ ወይም፡ቤቶችን፡ ለመሥራት፡ ፈቃድ፡ ሳይሰጥ፡ ሕንጻ ፡ ወይም፡ ቤት ፡ መሠራት ፡ የተጀመረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የሕንጻው ፡ ወይም ፡ የቤቶቹ ፡ ሥራዎች ፡ ወዲያው ፡ እንዲታገዱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፩፻፴፰ ። ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ቦታ ፡ ባለሀብትነት ፡ የተነገሩትን ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መጥቀስ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ሕጎች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በአንድ ፡ የከተማ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የቦታዎች ፡ ባለሀብቶች ፡ በቦታዎቻቸው ፡ ላይ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ሀብት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከቱት ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ አሏቸው ።

ቍ ፡ ፲፩፻፴፱ ። በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የቦታ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ (፩) አቋቋሙ ።

በየአንዳንዱ ፡ ምክትል ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የቦታዎች ፡ ባለሀብቶች ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ሌላ ፡ ፎርማሊቴ፡ በመንግሥት ፡ ከታወቀው ፡ ማኅበር ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ይቀላቀላሉ ።

ቍ ፡ ፲፩፻፵፩ (፪) ። የድርጅቱ ፡ አባሎች ፡ ሥራ ።

(፩) በመንግሥት፡ ለታወቁት፡ የቦታ ፡ ባለሀብት ፡ ማኅበሮች ፡ የወጡት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ፡ ድርጅቱ ፡ አባሎችና ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ የተጻፉት፡ ሕጎች ፡ በከተማ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ የቦታ ፡ ባለሀብቶች፡ መካከል ፡ ለተቋቋሙት ፡ ማኅበሮች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የአንዳንድ፡ ማኅበር ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ በማዘጋጃ፡ ቤት ፡ የተረጋገጠ ፡ ይሆናል።

ቍ ፡ ፲፭፻፶፪ ። ማኅበሩ ፡ የምክር ፡ ድርጅት ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በመንግሥት ፡ የታወቀ ፡ የባለቤታ ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ ሥራው ፡ ምክር ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ማኅበሩ ፤ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ያቀረበለትን፡ የከተማ ፡ ቅያሶች ፡ መርምሮ ፡ ስለ ፡ ቅያሶቹ ፡ ጠቃሚዎች ፡ መስለው ፡ የታዩትን ፡ አስተያየቶችና፡ነቀፌታዎች፡ ያስታውቃል ።

አንቀጽ ፡ ፲ ።

ስለ ፡ ማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ መዝገቦቹ ፡ አያያዝና ፡ ግልጽ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ቍ ፡ ፲፭፻፶፫ ። መሠረቱ ።

በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡ በያንዳንዱ፡ አውራጃ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ተቋቁሞ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዐቃብያነ ፡ መዝገብ ፡ በተባሉት ፡ እጅ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፭፻፶፬ ። የመዛግብቱ ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ ጥበቃ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ ዐቃቤ ፡ መዝገብ፡ ሹሞችና ፡ ረዳቶቻቸው ፡ የሚሾሙበትንና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የሚሆናቸውን ፡ የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይወስናል ።

(፪) ይህም ፡ ሚኒስቴር፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ዐቃቤ ፡ መዝገብ ፡ ሠራተኞችን፡ የሥራ ፡ ድልድልና ፡ ሥራቸውንም ፡ በትክክል ፡ መካሄዱን ፡ ይጠብቃል ።

(፫) ስለ ፡ ማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መዝገብ፡ አጠባበቅ ፡ አያያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፲፭፻፶፭ ። የርስት ፡ ክልል ፡ አገር ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ የሚቋቋመው ፡ በያንዳንዱ ፡ የርስት ፡ ክልል ፡ አገር ፡ ነው ።

(፪) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች፡ የአገር፡ ክልል ፡ የሚወስነው ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፫ ። ዋና ፡ ዋና ፡ መዝገቦች ።

በያንዳንዱ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ቤተ ፡ መዛግብትና፡ ለያንዳዱም ፡ የማ ይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ክልል ፡ አገር ፡ ወሰን ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ሀብትነትን ፡ የሚመለከት ፡ መዝገብና ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ የሚመለከት ፡ መዝገብን፡ የሚያቋቁም ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፬ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ።

የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መዝገብ፡ ክፍል ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ የዚህን፡ ዐይነት፡ ሥራ ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያስችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ መዝገቦችም ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መጻፊያ ፡ መዝገብ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የርስት ፡ ክልል ፡ አገር ፡ ይቋቋማል ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፭ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብቶች ፡ መዝገብ ።

የርስት፡ መዝገብ፡ ክፍል ፡ ሥራ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብን፡ ለማቋ ቋም ፡ የማይፈቅድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ መዝገብ ፡ ፈንታ፡ በያንዳንዱ፡ ቀበሌ ፡ የርስት ፡ ባለሀብቶችን ፡ የሚመለከት ፡ መዝገብ ፡ ይቋቋማል ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፮ ። ሌሎች ፡ መዝገቦች ።

የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚሰጠው ፡ በጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ በልዩ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ቤተ ፡ መዛ ግብት ፡ ተጨማሪ ፡ የሚሆኑ ፡ ሌሎች ፡ መዝገቦች ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፯ ። መዝገቦችን ፡ ከስፍራቸው ፡ ማዘዋወር ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በማናቸውም፡ ምክንያት ፡ ቢሆን፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መዝገቦችን ፡ ከተ ቋቋሙበት ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ለማዛወር ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፰ ። መዛግብቱ ፡ ግልጽ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ፤ (፩) መሠረቱ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ ለሕዝብ ፡ ግልጽ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ሺ፭፻፶፱ ። (፪) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችና ፡ የባለርስቶች ፡ መዛግብት ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዐቃብያነ ፡ መዛግብት ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበላቸው ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ መስጠት ፡ ይገባቸዋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በባለርስቶች ፡ መዝገብ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ የመዝገብ ፡ ግል ባጭ ፡ እንዲሰጡ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ የመዝገቡን ፡ ገጽ ፡ ወይም ፡ የገጾቹን ፡ ትክ ክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ ለጠያቂው ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

(፫) አስፈላጊም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፤ ስለ ፡ አንዱ ፡ ባለርስት ፡ ጒዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ አለመኖሩን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ መስጠት፡ አለባቸው ።

## ቍ ፡ ፲፮፻፳፫ ። (፫) ዋና ፡ ዋና ፡ መዝገቦች ፡ ወይም ፡ የማስረጃ ፡ ጽሑፎች።

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ዐቃብያን፡ መዝገቦች ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበላቸው ፡ ጊዜ፡ በርስቶች ፡ ወይም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መጻፊያ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘውን ፡ ጽሑፍ ፡ ቅጂ፡ ስለ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭነቱ ፡ በፊርማቸው ፡ አረጋግጠው ፡ ለጠያቂው ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

(፪) እንዲሁም፡ ጥያቄ ፡ በቀረበላቸው ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚገኘውን ፡ የማስረጃ ፡ ጽሑፍ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፤ ስለ፡ ትክክለኛነቱ ፡ ፈርመውና፡ አረጋግጠው ፡ ለጠያቂው ፡ ይሰጣሉ ።

## ቍ ፡ ፲፮፻፳፬ ። የግልባጮቹና ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶቹ ፡ ፎርም ።

ዐቃብያን ፡ መዝገብ ፡ የሚሰጡት ፡ ግልባጮችና ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ሁሉ ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ የዐቃቤ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ግልባጮቹንና ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶችን ፡ ለመስጠት ፡ በሚገባ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፤ የመዝገቡ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ የምስክር ፡ ወረቀቱ ፡ የተሰጠበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ካልተደረገባቸው ፡ በቀር ፡ ፍርስ ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ፲፮፻፳፭ ። የሚከፈል ፡ ገንዘብ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መዝገብ ፡ ለማስገባት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በሕግ ፡ ይወሰናል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የመዝገብ ፡ ወይም ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ግልባጭ ፡ ዐቃብያን ፡ መዛግብት ፡ ፈርመው ፡ ሲሰጡ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ይወስናል ።

## ቍ ፡ ፲፮፻፳፮ ። ስለ ፡ አላፊነት ፤ (፭) ዐቃቤ ፡ መዝገብ ።

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ዐቃብያን ፡ መዛግብት ፡ (መዝገብ ፡ ) ያዥዎች ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ ባለመፈጸማቸው ፤ ወይም ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ በመፈጸማቸው ፤ ወይም ፡ ዘግይቶ ፡ በመፈጸማቸው ፡ ምክንያት ፡ በሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ላይ፡ ጉዳት ፡ ቢያደርሱ ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ሕግ፡ ላይ ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ስለሚደርሱ፡ አላፊነቶች ። በተጻፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ለዚህ ፡ ጉዳት ፡ መንግሥትም ፡ በአላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

(፫) የዐቃብያን ፡ መዛግብት ፡ የወንጀል ፡ ወይም ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አላፊነት ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተጠቀሱት ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በልዩ ፡ ልዩ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚጻፉ ፡ ነገሮች ።

**ቍ ፡ ፩ሺ፭፻፶፫ ። የሀብትነት ፡ መዝገብ ፡ (የርስት ፡ መዝገብ) ። (፩) መሠረቱ ።**

የአንድ ፡ ወይም ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የባለሀብትነት ፡ መብት ፡ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ወይም ፡ በሞት ፡ ምክንያት ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በግል ፡ የተደረጉት ፡ ማንኛዎቹም ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ በባለሀብቶች ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይጻፋሉ ።

**ቍ ፡ ፩ሺ፭፻፶፬ ። (፪) ሀብትነትን ፡ (ርስትን) ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ በባለሀብትነት ፡ (በባለርስትነት) ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

(ሀ) የሽያጭ ፡ ወይም ፡ የስጦታ ፡ ወይም ፡ በማኅበር ፡ ውስጥ ፡ መዋጮ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ የመካፈል ፡ ወይም ፡ የግልግል ፡ ጽሑፎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ጕዳይ ፡ ሲሆን ፡ ሀብትነትን ፡ የሚያቋቁሙ ፡ ውሎች ።

(ለ) አንድ ፡ ወራሽ ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ውርሱን ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታ ፡ የተደረገለትን ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ ውርሱን ፡ ወይም ፡ የኑዛዜ ፡ ስጦታውን ፡ የተቀበሉባቸው ፡ ጽሑፎች ፤

(ሐ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ጽሑፎች ፡ የሚሰርዙ ፡ ወይም ፡ የሚሽሩ ፡ ወይም ፡ የሚያስቀሩ ፡ ፍርዶች ፤

(መ) የመፋለም ፡ ክስ ፡ ቀርቦ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሀብትነቱ ፡ ላይ ፡ የተፈረዱት ፡ ፍርዶች ፤

(ሠ) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ባስያዙት ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ላይ ፡ የተሰጡት ፡ ፍርዶች ፤

**ቍ ፡ ፩ሺ፭፻፶፭ ። (፫) ሌላ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መብትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሥራዎች ።**

እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩት ፡ በባለሀብትነት ፡ (በርስት) ፡ መዝገብ ፡ የሚጻፉ ፡ ናቸው ።

(ሀ) በአንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሌጣ ፡ ሀብትነትን ፡ ወይም ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነትን ፡ ወይም ፡ የመኖርያነትን ፡ መብት ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ ለማሳወቅ ፡ ለማስተላለፍ ፤ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ የተደረጉት ፡ ጽሑፎች ፤

(ለ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የአገልግሎት ፡ መብት ፡ ለማቋቋም ፤ ለማሳወቅ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ የተደረጉት ፡ ጽሑፎች ፤

BACK



(ሐ) ባንድ፡ በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የባለሀብትነትን፡ወይም ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይነትን ፡ መብት፡ የሚቀንስ ፡ ውል ፡ ለማቋቋም ፡ ለማ ስለተላለፍ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ የተደረጉ ፡ ጽሑፎች ።

**ቍ ፡ ፺፻፴፰ ። (፩) ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የ ሚቀርቡ ፡ ክሶች ።**

እንዲሁም ፡ በአንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የባለሀብትነትን ፡ ወይም፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሌላ ፡ መብትን ፡ እንዲታወቁለት፡ የሚያስተላልፍለት፡ የሚሽርለት፡የ ሚያስቀርለት፡ ፍርድ፡ ለማግኘት፡ እፍርድ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ በባለሀብትነት ፡ (በርስት) ፡ መዝገብ ፡ ይጻፋሉ ።

**ቍ ፡ ፺፻፴፩ ። (፪) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ኪራይ ።**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሎች ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ መዝገብ ፡ የሚጻፉ ፡ ናቸው ።

(ሀ) ከአምስት፡ ዓመት፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የተደረገባቸው ፡ የማ ይንቀሳቀሱ ፡ ሀብቶች ፡ ኪራይ ፤

(ለ) ከሦስት፡ ዓመት፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የተደረገባቸውና ፡ ገና ፡ ያላለፈ ፡ የኪራይ ፡ ሒሳብ ፡ የሚከፈልባቸው ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ወይም ፡ የእርሻ ኮንሴሲዮኖች ፤

(ሐ) ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የተደረገባቸው ፡ ገና ፡ ያላለፈ ፡ የኪራይ ፡ ሒሳብ ፡ የሚከፈልባቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የተከፈለባቸው ፡ የኪራዩ ፡ ደረሰኝ ፡ ለአንድ ፡ ተከራይ ፡ ወይም ፡ ለአንድ ፡ ገበሬ ፡ የተሰጡ ፡ የቤት ፡ ኪራዮች ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ ኮንሴሲዮኖች ።

**ቍ ፡ ፺፻፴፪ ። (፫) ኮንሴሲዮን ።**

እንዲሁም ፡ ወረዳ ፤ አውራጃ ፡ ወይም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የሰጡአቸው ፡ የውሆች ፡ ወይም ፡ የማዕድኖች ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ውል ፡ በባለሀብትነት ፡ (በርስት) ፡ መዝገብ ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፺፻፴፫ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መዝገብ፤ (፩) መሠረቱ ።**

በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመያዣ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፉ ፡ ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

(ሀ) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣን ፡ ወይም ፡ የወለድ ፡ አግድን ፡ መብት ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ የተደረጉ ፡ ጽሑፎች፡ ሁሉ ።

(ለ) በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ዋስትና ፡ የተረጋገጠውን ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ መብት ፡

በሕግ ፡ የታወቀውንና ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ መብት ፡ ለማስተላለፍ ፡ የተደረጉት ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ።

ቍ ፡ ፲፭፻፷፬ ። (፪) ስለ ፡ ማስያዝ ።

እንዲሁም ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ባለው ፡ ወይም ፡ በሌለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ክስ ፡ አቅራቢነት ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝና ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማድረግ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ በመያዣ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፍ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፭፻፷፭ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ (የርስት) ፡ ክልል ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ እያንዳንዱ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለዚሁ ፡ በተቋቋመው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ተሰጥቶት ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ገጽ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) መዝገቡም፡ በያንዳንዱ ፡ ገጾች ፡ ላይ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ተለይቶ ፡ በሚታወቅበት ፡ ሁኔታ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነቱን ፡ አጭር ፡ ዝርዝር ፡ ጽፎ ፡ ያመለክታል ።

(፫) የማይንቀሳቀሰውን፡ ሀብት፡ የሚመለከቱት ፡ ከመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይግቡ ፡ የተባሉት ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ ከሌሎቹ ፡ መዝገቦች ፡ ጋራ ፡ የሚጠቀሱበትን ፡ ቍጥሮችና ፡ የተመዘገቡበትን ፡ ቀንና ፡ ዓ. ም. በማመልከት ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ይጠቀሳሉ ።

ቍ ፡ ፲፭፻፷፮ ። (፪) ከከተማ ፡ ቅያስ ፡ ጋራ ፡ የሚኖራቸው ፡ ግንኙነት ።

(፩) በማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፈው ፡ የያንዳንዱ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ አመዘጋገብና ፡ ዝርዝር ፡ በከተማ ፡ ቅያስ ፡ በተመለከተው ፡ መለካትና ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መዝገብ፡ የሚጻፈው ፡ ከዚሁ ፡ ፕላን ፡ ጋራ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የተስማማ ፡ በመሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፭፻፷፯ ። (፫) በብዙ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።

(፩) በብዙ ፡ ክልል፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ የሚመዘገበው ፡ በእያንዳንዱ ፡ ክልል ፡ መዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ መዝገብ ፡ ጋራ ፡ እየተጣቀሰ ፡ ነው ።

(፪) የማይንቀሳቀሰውን፡ ንብረት፡ የሚመለከቱት ፡ ጥያቄዎችና ፡ ጽሑፎች ፡ የሚመዘገቡት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ በሚገኝበት ፡ ክልል ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፹፰ ። (፩) የሕዝብ ፡ የሆኑ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

የግል ፡ ሀብት ፡ ያልሆኑና ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያገለግሉ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መመዝገብ ፡ ያለባቸው ፡ እነሱን ፡ የሚመለከቱ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ ከሌሉባቸው ፡ በቀር ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መመዝገብ ፡ የለባቸውም ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፹፱ ። (፪) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ መለየት ።**

(፩) አንድ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ የተከፋፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐቃቤ ፡ መዝገቡ ፡ የዱሮውን ፡ ቍጥር ፡ እየጠቀሰ ፡ እያንዳንዱን ፡ አዲስ ፡ ክፍል ፡ በመዝገቡ ፡ ይመዘግባል ።

(፪) በአዲሶቹም ፡ ገጾች ፡ ላይ ፡ ንብረቱ፡ ከመከፋፈሉ፡ በፊት ፡ ተመዝግቦበት ፡ የነበረውን ፡ የቀድሞውን ፡ ገጽ ፡ ይጠቅስበታል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፺ ። (፫) ከመሬቱ ፡ አንዱን ፡ ቍራጭ ፡ ስለ ፡ መለየት ።**

(፩) ከአንድ፡ ከማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ አንድ ፡ ቍራጭ ፡ ለተይቶ፡ ከሌላ ፡ ንብረት ፡ ጋራ ፡ እንዲያያዝ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጀመሪያ ፡ የተመዘገበበት ፡ የመዝገብ ፡ ገጽ ፡ እንዳለ ፡ ይቈያል ።

(፪) በመዝገቡ፡ ውስጥ ፡ የማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት ፡ ስፋት ፡ በሚለው ፡ ማውጫ፡ ውስጥ ፡ ከሀብቱ ፡ ላይ ፡ የተለወጠውን ፡ ነገር ፡ ማመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፫) ይህን ፡ መለዋወጥ፡ ያስከተለው፡ ጽሑፍና ፡ የተደረገበትም ፡ ቀን ፡ በመዝገብ ፡ ይጻፋል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፺፩ ። (፬) የማይንቀሳቀሱ ፡ የብዙ ፡ ንብረቶች ፡ መቀላቀል ።**

(፩) ያንድ ፡ ሰው፡ ሀብት፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በአንድነት ፡ ተጠቃለው ፡ በአንድ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ንብረት ፡ እንዲሆኑ ፡ በነዚህ ፡ በብዙዎቹ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ የመያዣ ፡ ወይም ፡ የወለድ ፡ አግድ ፡ መብት ፡ ካለ ፡ ወይም ፡ ከነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሆኑት ፡ ባለመያዣዎች ፡ እንዲቀላቀል ፡ ካልፈቀዱ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ ሊፈጸም ፡ አይቻልም ።

(፪) እነዚህ፡ የማይንቀሳቀሱ፡ ንብረቶች ፡ ለሌላ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመብቶቹ ፡ ሳይፈቅዱ ፡ በአንድነት ፡ ተጠቃልለው፡ ሊመዘገቡ ፡ አይቻልም ።

(፫) ለእነዚህ፡ ንብረቶች፡ ጥቅም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአገልግሎት ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ ርስቶች ፡ ባለሀብቶች ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ ተጠቃልለው ፡ ለመመዝገብ ፡ አይቻሉም ።

BACK



ቍ ፡ ፲፭፻፷፱ ። (፰) የተዘጉ ፡ የመዝገብ ፡ ገጾች ።

(፩) አንድ ፡ ሀብት ፡ በመከፋፈሉ ፡ ወይም ፡ በአንድነት ፡ በመደረቡ ፡ ምክንያት ፡ ተጽፎበት ፡ የነበረው ፡ ገጽ ፡ የማያገለግል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ የተደረገበትን ፡ ምክንያት ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ መግለጫ ፡ በመዘርዘር ፡ ገጹ ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ በቀሩስ ፡ (በአግዳሚ) ፡ መሥመር ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ተሰርዞ ፡ ይዘጋል ።

(፪) እንዲሁም፡ መዝገብ፡ ገብቶ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመዝገብ ፡ ወደማይጻፍ ፡ ንብረት ፡ መደብ ፡ ውስጥ ፡ የተዛወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) የተዘጉት፡ የመዝገብ፡ ገጾች ፡ በማንኛቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ እንዲጠፉ፡ አይደረግም ።

ቍ ፡ ፲፭፻፸ ። የባለሀብቶች ፡ መዝገብ ፡ (የባለርስቶች ፡ መዝገብ) ፡ (፩) መሠረቱ ።

በፊደል ፡ ተራ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ሆነው ፡ ከዋናዎቹ ፡ መዝገቦች ፡ በአንዱ ፡ ውስጥ ፡ በተመዘገበ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ በክልሉ ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብቶች ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የተገለጹት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ በባለሀብቶች ፡ መዝገብ ፡ የሚጻፍ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፭፻፸፩ ። (፪) የጋራ ፡ የሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ።

(፩) አንድ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ በስሙ ፡ አንዳንድ ፡ ገጽ ፡ ይኖረዋል ።

(፪) የያንዳንዱ ፡ የድርሻ ፡ ልክ ፡ ባለሀብቱን ፡ በሚመለከተው ፡ የመዝገብ ፡ ገጽ ፡ ውስጥ ፡ ይጻፋል ።

ቍ ፡ ፲፭፻፸፪ ። (፫) የብዙ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ባለሀብትነት ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ የርስት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የብዙ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ንብረቶቹ ፡ ቍጥር ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ በስሙ ፡ አንዳንድ ፡ ገጽ ፡ ይኖረዋል ።

ቍ ፡ ፲፭፻፸፫ ። በየገጹ ፡ ላይ ፡ የሚጻፉ ፡ ጽሑፎች ።

በመዝገብ ፡ መመዝገብ ፡ ያለባቸው ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ሀብትን ፡ የሚመለከቱ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ በሌላ ፡ መዝገብ ፡ ያለውን ፡ ቍጥራቸውንና፡ የተጻፈበትን፡ቀን፡ ከሚያመለክት ፡ መግለጫ ፡ ጋራ ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ በሚመለከተው ፡ የመዝገብ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በመዝገቦቹ ፡ ላይ ፡

## ስለ ፡ ጽሑፎች ፡ አመዘጋገብ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ አመዘጋገቡ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፷፯ ። የመዝገቦቹ ፡ አቀራረብ ፡ ዐይነት ።**

የባለሀብትነትና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ የሚመለከቱ ፡ መዝገቦች፡የታተሙ ፡ ቃሎች ፡ የሚገኙባቸው ፡ ገጾች ፡ የያዙ ፡ ሆነው ፡ ባለጕዳዮቹ፡የማያስፈልጓቸውን ፡ ቃሎች ፡ እየሰረዙ ፡ ባዶ ፡ የሆኑትን ፡ ቦታዎች ፡ እንዲሞሉ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲችሉ ፡ ለነሱ ፡ የተዘጋጁ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፷፰ ። የታተሙት ፡ ቃሎች ፡ ዐይነት ።**

የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገቦች ፡ ላይ ፡ የሚታተሙትን ፡ ቃሎች ፡ ዐይነትና ፡ የመዝገቡንም ፡ መጠን ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፷፱ ። ስለ ፡ ታተሙት ፡ ቃሎች ፡ አሰጣጥ ።**

(፩) ስለ ፡ መዝገቦቹ ፡ አያያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የታተሙ ፡ ቃሎች ፡ ያሉባቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ከርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተቀብሎ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ አገረ ፡ ገዥ፡ ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዐቃብያነ ፡ መዝገብ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ይሰጣቸዋል ።

(፪) የማይንቀሳስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦችን ፡ ዐቃብያነ ፡ መዝገብ፡ የሆኑ፡ ሰዎች ፡ በእጃቸው ፡ ያሉትን ፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ በየስድስት ፡ ወር ፡ እያወጡ ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነ ፡ ለአገልግሎታቸው ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ተጨማሪ ፡ መጠባበቂያ ፡ ጽሑፎች ፡ እንዲሰጧቸው ፡ ይጠይቃሉ ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፸ ። የአመዘጋገቡ ፡ ዐይነት ።**

(፩) በደንቦቹ፡ በግልጽ ፡ ከታዘዙት ፡ አጫጭር፡ ቃላት ፡ በቀር ፤ አንድም ፡ ማሳጠር፡ ሳይደረግ ፡ አመዘጋገቡ ፡ ከመዝገቦቹ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ እንደሚነበብ ፡ ዐይነት ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

(፪) በማቸውም፡ ሁኔታዎች፡ ሁሉ ፡ አመዘጋገቡ ፡ የተፈጸሙበትን ፡ ቀንና፡ (ጊዜና)፡ በተጻፉበት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ለአመዘጋገቡ ፡ የተሰጠውን ፡ ቍጥር ፡ ያመለክታል ።

**ቍ ፡ ፲፭፻፸፩ ። ገንዘቦችን ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ ማመልከት ።**

አንድ ፡ አመዘጋገብ ፡ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ የሆነ ፡ ነገርን፡ የሚያመለክት፡

የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ በአኀዝና ፡ በፊደል ፡ መመልከት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፺፪ ። ቀንን ፡ ስለ ፡ ማመልከት ።**

(፩) ቀንን ፡ ስለ ፡ መመዝገብ፡ በአኀዝ፡ የሚጻፈው ፡ በጣም ፡ በሚነበብ ፡ አኳኋን ፡ ሆኖ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ወርንና ፡ የወሩን፡ ክፍል ፡ ቀኖች ፡ ግን ፡ በፊደል ፡ ብቻ ፡ መጻፍ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፺፫ ። ስለ ፡ አመዘጋገብ ፡ ጥያቄ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊነት ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዐቃቤ ፡ መዝገብ ፡ በሥልጣኑ ፡ ብቻ ፡ (ጠያቂ ፡ ሳይኖር) ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይመዘግብም ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፺፬ ። በመዝገብ ፡ ለማጻፍ ፡ መጠየቅ ፡ የሚችል ።**

(፩) ማንኛውም፡ ባለጕዳይ፡ ሁሉ ፡ በመዝገብ ፡ ለማጻፍ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ጠያቂው፡ ጥያቄውን፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ ይኸንኑ ፡ ጥያቄ ፡ ለማግባት ፡ በግልጽ ፡ በተወሰነው ፡ ታሪፍ ፡ የተመለከተውን ፡ ቍርጠኛ ፡ ዋጋ ፡ ይከፍላል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፺፭ ። የተጠበቁ ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ አለመኖር ።**

በመዝገብ ፡ ለማጻፍ ፡ በሚቀርቡ ፡ ጥያቄዎች ፡ ውስጥ፡ አንዳችም፡የመጠበቂያ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ውለታ ፡ ሊኖርበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፺፮ ። የጥያቄጡ ፡ አደራረግ ።**

(፩) በመዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ እንዲመዘገብ ፡ ለማድረግ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሰው ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚሰጠውን ፡ የታተመ ፡ ጽሑፍ ፡ ሁለት ፡ ቅጂዎች ፡ ይሞላል ።

(፪) ጠያቂው ፡ በሥራት ፡ እንዲነበብ ፡ በመኪና ፡ ወይም ፡ በጥቍር ፡ ቀለም ፡ በታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ባዶ ፡ ቦታዎች ፡ እየሞላ ፡ ይጽፋል ።

(፫) ጠያቂው፡ ከታተሙት ፡ ጽሑፎች፡ ውስጥ ፡ ጠቃሚ ፡ ያልሆኑትን ፡ ጽሑፎች፡ ይሰርዛል ፤ ወይም ፡ እነዚህን ፡ ጽሑፎች ፡ በሚመሳሰለው ፡ ባዶ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አግድም ፡ የሆነ ፡ መሥመር ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ሺ፫፻፺፯ ። የተከለከሉ ፡ ጽሑፎች ።**

(፩) ለሕዝብ፡ አገልግሎት፡ በተሰጡ ፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ በቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ተጨማሪ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ።

BACK



(፪) አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ተመለከቱት ፡ ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ አስረጂ ፡ ጽሑፎች ፡ በመምራት ፡ የተ ጓደሉትን ፡ ቃሎች ፡ ለማሟላት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፮፻፷፰ ። የዐቃቤ ፡ መዝገብ ፡ ተግባር ።

(፩) ዐቃቤ ፡ መዝገቡ ፡ ለሚቀርብለት ፡ እያንዳንዱ ፡ ጥያቄ ፤ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የሚ ሆን ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ከመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) መዝገብ፡ ያገርው ፡ በተሰጡት፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ ፊርማውን ፡ እያደረገ ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱን ፡ ማኅተም ፡ በያንዳንዱ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ያትምባቸዋል ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፱ ። ለጠያቂው ፡ አንዱን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

ዐቃቤ ፡ መዝገቡ ፡ ጥያቄ ፡ ለአቀረበው ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ በሚገባ ፡ የፈረመበት ንና ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ ያለበትን ፡ አንዱን ፡ ጽሑፍ ፡ ጥያቄ ፡ ለአቀረ በው ፡ ሰው ፡ ይሰጠዋል ።

ቍ ፡ ፲፯፻ ። ሌላው ፡ የታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ሁኔታ ።

(፩) ሌላው ፡ የታተመ ፡ ጽሑፍ ፡ ወዲያውኑ ፡ እርሱን ፡ በሚመለከተው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ይሆናል ።

(፪) የታተመው ፡ ጽሑፍ፡ አመዘጋገብ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ባቀረቡበት ፡ ቅደም ፡ ተከተል፡ ተራ ፡ መሠረት ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፩ ። የተጨማሪ ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍ ።

አዲስ ፡ የተመዘገበው ፡ ሰነድ ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ክፍል ፡ በክልሉ ፡ ተንቀሳ ቃሽ ፡ ባልሆኑ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በባለሀብቶች ፡ መዝገብ ፡ ወዲያ ውኑ ፡ ይጻፋል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ለአመዘጋገብ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ፎርሙሎች ።

ቍ ፡ ፲፯፻፪ ። ለታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ።

ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ የተሰናዱት ፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ ያመለክታሉ ።

(ሀ) ለማስመዝገብ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበበትን ፡ ቀን ፤

(ለ) የሚመዘገበውን፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረትና ፡ ይህኑ ፡ ንብረት ፡ ለመለየት፡ የሚያገለግሉትን ፡ ሁሉ ፡ መግለጫዎች ፡ የሚለዩ ፡ ጽሑፎችን ፡ ጭምር ፤

(ሐ) አመዘጋገቡ ፡ የሚያመለክተውን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ የራሱን ፡ ስምና ፡ ያባቱን ፡ ስም ፤

(መ) እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ ባሉበት ፡ ከተማ ፤ ውስጥ ፡ ጠያቂው ፡ የመረጠውን ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታና ፡ የጠያቂውን ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የራሱንና ፡ የአባቱን ፡ ስም ፤

(ሠ) ከጥያቄው ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ አስረጂ ፡ ሰነዶችን ፡ ብዛት ፡ ዐይነት ፡ የመጠቀሻ ፡ ቍጥራቸውን ፤

(ረ) ሊጠቀሱ ፡ የሚቻሉትን ፡ አስቀድሞ ፡ የተመዘገቡትን ፡ ጽሑፎች ፡ ከነመጠቀሻ ፡ ቍጥራቸው ፤

**ቍ ፡ ሺ፮፻፫ ። ለባለሀብትነት ፡ (ለርስት) ፡ የሚያገለግል ፡ የታተመ ፡ ጽሑፍ ፡ መዝገብ ፡ (ፎርሙል) ። (፩) ጠቅላላ ፡ ጥቅሶች ።**

ለባለሀብትነት ፡ መዝገብ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ በውስጣቸው ፤

(ሀ) ለመመዝገብያው ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ የጽሑፍ ፡ ዐይነት ፤

(ለ) ይህ ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ጽሑፍ ፡ የሚመለከተውን ፡ የመብት ፡ ዐይነት ፤

(ሐ) በጽሑፉ ፡ ጊዜ ፡ ተከራይ ፡ መብት ፡ የተላለፈለትን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የራሱን ፡ ስም ፤ ያባቱን ፡ ስምና ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታውን ፡ ወይም ፡ የመረጠውን ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታውን ፤

(መ) መመዝገብ ፡ ስለሚያስፈልጋቸው ፡ ሌሎች ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ ሁኔታዎች ፡ የተደረጉት ፡ ልዩ ፡ ስምምነቶች ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፬ ። (፪) ልዩ ፡ የውል ፡ ቃሎች ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሱት ፡ ልዩ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ የሚመለከቱት ፤

(ሀ) የሽያጭ ፤ የማኅበር ፤ መዋጮ ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፤ የመሸጥ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፤ የስጦታና ፡ ሌሎች ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ነገሮች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ የተላለፈውን ፡ መብት ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ግምት ፤

(ለ) መከፋፈል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ከድርሻው ፡ በላይ ፡ የደረሰው ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባውን ፤

(ሐ) ኪራይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ኪራዩ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ ልክና ፡ የዓመት ፡ ኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፤

(መ) የመከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሰውን ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ማስተላለፍ ፡ ወይም ፡

BACK



ደረሰኝ ፡ በመስጠት ፡ ሲሆን ፡ ከራዮቹ ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደ፡ ተላለፉ፡ ወይም ፡ ደረሰኝ ፡ እንደ ፡ ተሰጠባቸው ፡ የሚያመለክተውን ፡ ጊዜ ፤

(ሠ) የሽያጭ ፡ ተስፋ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሽያጩ ፡ ቢፈጸም ፡ የሚከፈለውን ፡ ዋጋ ፡ ልክና ፡ የተስፋ ፡ ሽያጩ ፡ ቃል ፡ የሚጸናበትን ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፤

(ረ) የባለሀብትን፡ መብት፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ለመቀነስ ፡ ሲሆን ፡ እነዚሁ ፡ የመ ብት ፡ መቀነስ ፡ የሚቀሩበትን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፲፻፶፭ ። ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ።

ለማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣዎች፡ መዝገብ፡ እንዲያገለግል፡ የታተመው፡ ጽሑፍ ፡ የሚያመለክተው ፦

(ሀ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ፡ የተሰጠውን፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፤ የራሱን ፡ ስም ፤ ያባቱን ፡ ስም ፤ የመኖሪያ ፡ ቦታውን ፤

(ለ) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፤

(ሐ) ዕዳው ፡ የሚከፈልበትን ፡ ቀን ፤

(መ) ገንዘቡ ፡ በዓመት ፡ የሚሰጠውን ፡ ወለድ ፡ ልክ ፤

(ሠ) በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመጻፍ ፡ መብቱ፡ ለሌላ፡ የሚተላለፍ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ለአምጪው ፡ የሚከፈል ፡ መሆኑን ፤

(ረ) መብቱ፡ የተመዘገበው፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የተመዘገበውን ፡ መብት ፡ ለማደስ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፲፻፶፮ ። ተንቀሳቃሽ ፡ ያልሆነውን ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መለየት ፤ (፩) መሠረቱ ።

(፩) በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመለየት ፡ ዐይነቱን፡የሚገኝበትን፡ቀበሌና፡በመዝገብ፡ውስጥ፡የተሰጠውን፡ የቅያስ ፡ ቍጥር ፤

(፪) ንብረቱ ፡ ቅያስ ፡ ባልተጣለበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተቻለ፡ መጠን ፡ ዐይነቱን ፡ ሁኔታውን ፡ በበላዩ ፡ ያለውን ፡ እና ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ የአዋሳኞቹን ፡ ስም ፡ በማመልከት ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፲፻፶፯ ። (፪) ዝርዝር ፡ የሆነ ፡ ፕላን ።

(፩) በጽሑፉ ፡ ውስጥ፡ ለተመለከተው፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ምልክት ፡ የሆ ኑትን ፡ ነገሮች ፡ አስረጂ ፡ ከሆኑት ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ ዝርዝር ፡ የሆነ ፡ ፕላን ፡ በማ ቅረብ ፡ የበለጠ ፡ ለመግለጽ ፡ ይቻላል ።

(፪) በተለይ፡ እንደዚሁ ፡ የሚደረገው ፡ ለመመዝገብ ፡ የሚገባው፡ ጽሑፍ ፡ የሚ መለከተው ፡ የቅያስ ፡ ቍጥር ፡ ከተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አንዱን፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፫) ይህ ፡ ሲሆን፡ የተደረገው፡ አመዘጋገብ ፤ ከአመዘጋገቡ ፡ ጥያቄ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ፕላን ፡ ላይ ፡ የተጻፉትን ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ቍጥር ፡ ይጠቅሳል ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፰ ። በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ አመዘጋገብ ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ያንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ማኅበር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ በጠያቂው ፡ ስምና ፡ በአባቱ ፡ ስም ፡ ፈንታ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠውን ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የድርጅቱን ፡ የመጠሪያ ፡ ስም ፡ የሚገልጽ ፡ ይሆናል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በተመዘገበው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚጨቀመው ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ ይፈጸማል ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፱ ። የሞተ ፡ ሰው ፡ ሀብት ።**

በአንድ ፡ በሞተ ፡ ሰው ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ አመዘጋገብ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ እየተባለ ፡ አመዘጋገቡ ፡ በሟቹ ፡ ስም ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፲ ። የጋራ ፡ የሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባላሀብቶች ፡ የሆኑ ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ባለጕዳዩ ፡ አንዱ ፡ ባለሀብት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህኑ ፡ ባለጕዳይ ፡ ድርሻ ፡ ብቻ ፡ በመጥቀስ ፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ የዚሁ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ይጠቀሳል ።

(፪) ጽሑፉ ፡ የሚመለከተው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶችን ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ አብዛኛዎቹን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ተብሎ ፡ ተጨማሪ ፡ አስረጂ ፡ በሆኑት ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ሀብትነት ፡ ወደሚመለከተው ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ መምሪያ ፡ ይደረግባቸዋል ።

(፫) በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ለያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ በተመደበው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ በባለሀብቶች ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፉ ፡ የሚጠቀስ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፲፩ ። በሰነዱ ፡ የሚጠቀሙት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ።**

መመዝገብ ፡ ባለበት ፡ ጽሑፍ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በአንድነት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፲፪ ። የጠያቂው ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ምርጫ ።**

(፩) ጠያቂው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ ባሉበት ፡ ከተማ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ መምረጥ ፡ አለበት ።

(፪) መመዝገብን፡ የሚመለከቱ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ሁሉ ፡ እዚህ ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከተላኩ ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፮፻፲፫ ። አስረጂ ፡ ሰነዶች ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) ጠያቂው፡ የሚጠቅሙ፡ መስለው ፡ የታዩትን ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፡ ከጥያቄው ፡ ጋራ ፡ ማያያዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ዐቃቤ ፡ መዝገቡ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑት፡ ሰነዶች፡ ከዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ጋራ ፡ አልተያያዙም ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ ጥያቄውን ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፫) ዐቃቤ፡ መዝገቡ ፡ እንደዚህ፡ ያለው ፡ ሰነድ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑንና ፡ የዚህም፡ ሰነድ ፡ መቅረት ፡ ለማስከተል ፡ የሚችለውን ፡ ምክንያት ፡ ለጠያቂው ፡ ሊያስጠነቅቀው ፡ ብቻ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፮፻፲፬ ። (፪) የተለመዱ ፡ ሰነዶች ።

ከጥያቄው፡ ጋራ፡ የተያያዙ ፡ ተጨማሪ፡ ወይም ፡ አስረጂ ፡ ሰነዶች ፡ በተለይ ፡ የሚከተሉት ፡ ሊኖርባቸው ፡ ይችላል ።

(ሀ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ፕላን ፤

(ለ) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ባለዕብት ፡ ወይም ፡ በሰነዱ ፡ በሚጠቀመው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ እንዲሠራ ፡ ጠያቂውን ፡ የሚፈቅድለት ፡ ውክልና ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፤

(ሐ) የሚመዘገበውን ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፤

(መ) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ መሞቱን ፡ ወይም ፡ ከአገር ፡ የጠፋ ፡ መሆኑን ፡ የሚመሰክር ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ግልባጭ ፤

(ሠ) ጠያቂው፡ ስለማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረቡን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጽሑፍ ፤

(ረ) በማይንቀሳቀሰው፡ ንብረት፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ የሚያመለክት ፡ ዝርዝር ፤

ቍ ፡ ፲፮፻፲፭ ። (፫) አስረጂ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ አቀማመጥ ።

(፩) የመመዝገብን ፡ ጥያቄዎች፡ ለመደገፍ፡ ወይም ፡ መመዝገብን ፡ ለማቃናት ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሰረዝ ፡ የሚሰጡ ፡ ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ አስረጂ ፡ ሰነዶች ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ አያያዝ ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚቀመጡ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ ሰነድ ፡ የመጣቀሻ ፡ ልዩ ፡ ቍጥር ፡ ይሰጠዋል ።

BACK



(፫) ሊያንፀባርቁ፡ ሰነድ፡ አያያዝና ፡ አቀማመጥ ፡ በታሪፉ ፡ የተመለከተው ፡ ልዩ ፡ ቀረጥ ፡ ይከፈላል ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፲፮ ። የሰነዱ ፡ ዐይነት ።**

(፩) «የሰነዱ፡ ዐይነት»፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ፡ የታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ቀጥሎ፡ ያሉት ፡ ምርጫዎች ፡ ጉዳዮች ፡ የተዘረዘሩበት ፡ ይሆናል ። ሽያጭ ፡ የማኅበር ፡ መዋጮ ፡ ስጦታ ፡ መከፋፈል ፡ ግልግል ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ፍርድ ፡ የመብት፡ መተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ሰነድ ፡ መሰረዝ ፡ መብት ፡ ማስታወቅ ፡ መብት ፡ ማቋቋም ፡ መብት ፡ መለወጥ ፡ መብት ፡ ማስቀቀረት ፡ የሽያጭ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ ያኮንሴሲዮን ፡ ውል ፡ የማስቀረት ፡ መብት ፡ መከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሱትን ፡ ኪራዮች ፡ የማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ የሚሰጥ ፡ ደረሰኝ ፡ የወርስ ፡ መብቶችን ፡ መቀበል ፡ የማይሸጥ ፡ የማይተላለፍ ፡ የማይያዝ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቍ. . . . . .የሆነውን ፡ የተያያዘውን ፡ ሰነድ፡ ተመልከት ።

(፪) ጠያቂው ፡ ከነዚሁ፡ ጉዳዮች፡ ውስጥ ፡ ለሥራው ፡ ዐይነት ፡ ይበልጥ ፡ የተሻሉትን ፡ ነገሮች ፡ ይመርጣል ።

(፫) ጠያቂው ፡ እንዳስፈላጊው፡ ቍ . . . . የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ ተመልከት ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ይሰርዛል ፡ ወይም ፡ ይሞላል ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፲፯ ። የሚሰጠው ፡ መብት ፡ ዐይነት ።**

"የመብት ፡ ዐይነት፡ " በሚለው ፡ አርእስት፡ ሥር ፡ ጥያቄ፡ አቅራቢው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የባለሀብትነት ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት፡ ድርሻ፡ ወይም፡ የሌላ፡ ርስት፡ መብት ፡ ወይም፡የአላባ፡ ጥቅም ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አገልግሎት ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የባለሀብትነትን ፡ መብት ፡ መቀነስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያመለክታል ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፲፰ ። የገንዘብ ፡ መጠየቂያው ፡ መብት ፡ ልክ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ የወለድ ፡ አግድ ፡ መብትን ፡ ማረጋገጫ ፡ የተሰጠ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ የሚጻፈው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

(፪) የገንዘብ ፡ መጠየቂያው፡ መብት፡ ልክ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መድን ፡ ሊሆን ፡ ለሚችለው ፡ ለከፍተኛው ፡ ገንዘብ ፡ የሚመዘገብ ፡ ይሆናል ።

(፫) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መያዣ፡ ከተሰጠበት ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ጋራ ፡ ለመስማማት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የገንዘቡን ፡ ልክ ፡ ይወስናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፲፱ ። በትእዛዝ ፡ የሚከፈል ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣው ፡ የሚያረጋግጠው ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ፡ በመጻፍ ፡ ብቻ ፡ የሚተላለፍ፡የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብትን፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመዘጋገቡ ፡ በሰነዱ ፡ ያዥ ፡ ስም ፡ ይፈጸማል ።

(፪) የዚህ ፡ የመመዝገቡ፡ ጥቅም፡ ሌላ ፡ ፎርማሊቴ ፡ ሳያስፈልግ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በኋላ ፡ ለሚፈርሙትም ፡ ሰዎች ፡ የሚጠቅም ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፳ ። ለአምጪው ፡ የሚከፈል ፡ የገንዘብ ፡ መጠይቂይ ፡ መብት ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣው ፡ የሚያረጋግጠው ፡ ለአምጪው ፡ የሚከፈል ፡ በተባለ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰነዱን ፡ ያወጣውን ፡ ሰው ፡ ስም ፤ ሰነዱ ፡ የወጣበትን ፡ ጊዜ ፤ ሴሪውን ፤ ቍጥሩንና ፡ የወጡትን ፡ ሰነዶች ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ የሚያመለክት ፡ አንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ሰነድ ፡ ይኖራል ።

(፪) አስፈላጊም፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ተጨማሪው ፡ ሰነድ ፡ ለሰነዶቹ ፡ አምጪዎች ፡ ሊወከል ፡ የሚችለውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ጨምሮ ፡ ያመለክታል ።

## ክፍል ፡ ፫ኛ ።

## የተመዘገቡትን ፡ ጽሑፎች ፡ ስለ ፡ ማቃናትና ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፳፩ ። ማቃናት ፤ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ለማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ዐቃቤ ፡ መዝገብ ፡ ተሰጥቶ ፡ ከመዝገብ ፡ ጋራ ፡ በተያያዘው ፡ የታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የጐደለ ፡ ወይም ፡ ያልተተካከለ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመዘጋገቡን ፡ ማቃናት ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) አመዘጋገቡ፡ ፈራሽ፡ የሚሆነው ፡ በሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ብቻ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፳፪ ። (፪) ማቃናትን ፡ የሚመስል፡ መለዋወጥ ።**

እንዲሁም ፡ ማቃናት ፡ የሚያስፈልገው ፡—

(ሀ) በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሰዎች፡ አንዱ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታውን ፡ ወይም ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ የታወቀውን ፡ የመረጠውን ፡ የመኖሪያ ፡ ቤት ፡ ለመለወጥ ፡ ሲፈለግ ፤

(ለ) በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መያዣ፡ ወይም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ መብት ፡ የተረጋገጠው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሩቡ ፡ የተከፈለ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ የተሰጠበትን ፡ የገንዘብ ፡ ጠመየቂያ ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የተላለፈ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠ ፡ ሲሆን ፤

(መ) የተመዘገበው፡ ጽሑፍ፡ እንዲለዋወጥ ፡ በባለጉዳዮቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ የፈረዱ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡፡

ቍ ፡ ሺ፮፻፹፫ ፡፡ (፫) የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡፡

(፩) ዳኞቹ ፡ ለዐቃቤ፡ መዝገብ ፡ በሚሰጡት፡ ትዛዝ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የተመዘገበውን ፡ ቃል ፡ ለማቃናት ፡ አይቻልም ፡፡

(፪) ማናቸውም፡ ባለጉዳይ፡ የተመዘገበው ፡ ቃል ፡ እንዲቃና ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጡ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ፡፡

ቍ ፡ ሺ፮፻፹፬ ፡፡ (፬) ስለ ፡ ማቃናት ፡ ሥራ ፡ አደራረግ ፡፡

(፩) የቃሉ፡ ማቃናት፡ የሚፈጸመው ፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚያቃኑትን ፡ ቃሎች ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ በመሰረዝ ፡ ነው ፡፡

(፪) ዐቃቤ፡ መዝገቡ፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የተቃናበትን ፡ ቀንና ፡ እንዲቃናም ፡ ዳኞች ፡ የሰጡትን ፡ ፍርድ ፡ ከሚጠቅስ ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ "ተቃንቷል ፡" የሚል ፡ ቃል ፡ ይጽፍበታል ፡፡

(፫) ስለዚህ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠውም፡ ፍርድ ፡ ከአስረጂ ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ በቤተ ፡ መዛግብት ፡ ይቀመጣል ፡፡

ቍ ፡ ሺ፮፻፹፭ ፡፡ (፭) በተጨማሪ ፡ መዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መጥቀስ ፡፡

እንዲሁም ፡ "ተቃንቷል ፡" የተባለው ፡ ቃል ፡ ከተመዘገበ፡ በኋላ ፡ በማይንቀሳቀሱ፡ ንብረቶች ፡ ወይም ፡ በባለሀብቶቹ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ከተቃናበት ፡ ቀን ፡ ጋራ ፡ ይጻፋል ፡፡

ቍ ፡ ሺ፮፻፹፮ ፡፡ (፮) የተቃናው ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡፡

(፩) ለባለጉዳዮቹ፡ የሚሰጡት፡ የታተሙት ፡ ጽሑፎች ፡ ግልባጮች ፡ ከዋናው፡ ጋራ፡ በሙሉ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ፡፡

(፪) ግልባጮቹ ፡ መጀመሪያ፡ በታተሙ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ የተጻፈውንና ፡ በኋላም፡ የተደረገውን ፡ ማቃናት ፡ ያመለክታሉ ፡፡

ቍ ፡ ሺ፮፻፹፯ ፡፡ (፯) የመቃናቱ ፡ ውጤቶች ፡፡

የተመዘገበውን፡ ጽሑፍ ፡ የማቃናት፡ ሥራ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፡ የመቃናቱ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፡፡

BACK



<u>ቍ ፡ ፲፭፻፹፰ ። የጽሑፉ ፡ መመዝገብ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አለማሆን ።</u>

በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መዝገብ፡ ውስጥ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ መመዝገብ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ ውጤት ፡ የሌለው ፡ የሚሆነው ፡—

(ሀ) የተመዘገበበትን ፡ ቀን ፡ የማያመለክት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) መመዝገቡ፡ የሚመለከተውን፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመለየት ፡ የማያስችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ የሚመዘገበውን ፡ መብት ፡ ያስተላለፈዉን ፡ ሰው ፡ ለመለየት ፡ የማያስችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የገዛውን ፡ ወይም ፡ ያገኘውን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ወይም ፡ በተመዘገበው ፡ መብት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ለመለየት ፡ የማያስችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ልክ ፡ የማያመለክት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ረ) ዋጋ፡ በሌለው፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ በመመሥረት ፡ ተመዝግቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሰ) ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ዘግይቶ ፡ ተመዝግቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፲፭፻፹፱ ። ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ስለሚመዘገብ ፡ ሰነድ ።</u>

ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የተመዘገበ ፡ ጽሑፍ፡ ነው፡ የሚባለው፡ ከእርሱ፡ በፊት ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረገ ፡ ሌላ ፡ አመዘጋገብ ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፲፭፻፺ ። ስለ ፡ መሰረዝ ። (፩) የዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ አስፈላጊነት ።</u>

ሕጉ፤የተመዘገበው፡ ጽሑፍ፡ ዋጋ፡ የሌለው፡(ፈራሽ)ነው፡ በሚልበት፡ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ አመዘጋገቡ ፡ እንዲሰረዝ ፡ በማለት ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፲፭፻፺፩ ። (፪) የባለጕዳዮቹ ፡ ስምምነት ።</u>

(፩) አመዘጋገቡ፤ የሚመለከተው፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በተመዘገበው ፡ መብት ፡ የሚጠቀመው ፡ ሰው ፡ አመዘጋገቡ ፡ እንዲሰረዝ ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመዘጋገቡ ፡ እንዲሰረዝ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጡ ፡ በማለት ፡ ለዳኞች ፤ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) የተመዘገበው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ፡ አልቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የተመዘገበው ፡ ጽሑፍ ፡ መኖሩ ፡ ጥቅም ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመብቱ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፵፪ ። (፫) በሥልጣን ፡ የሚደረግ ፡ መሰረዝ ።**

(፩) በመዝገብ፡ በገባው፡ ጽሑፍ ፡ ቃል ፡ የተመዘገበው ፡ መብት ፡ የተደረገው ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሆነና ፡ የተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመዘጋገቡን ፡ ዐቃቤ ፡ መዝገቡ ፡ በሥልጣኑ ፡ (ጠያቂ ፡ ባይኖርም)፡ ይሰርዘዋል ።

(፪) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የቱደረገ ፡ መያዣ ፡ ከተመዘገበ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሆኖት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ እንዲታደስ ፡ አልተጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተመዘገበውን ፡ ዐቃቤ ፡ መዝገቡ ፡ በሥልጣኑ ፡ ይሰርዘዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፵፫ ። (፬) የመሰረዙ ፡ ሥራ ፡ አደራረግ ።**

(፩) የተመዘገበው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚሰረዘው፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የተመሳቀሉ ፡ ሁለት ፡ መሥመሮች ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) ዐቃቤ ፡ መዝገቡ፡ በታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ፊት ፡ ላይ ፤ የተሰረዘበትን ፡ ቀን ፡ በመጥቀስ ፡ "ተሰርዟል ፡" የሚል ፡ ቃል ፡ ይጽፍበታል ። ያለም ፡ እንደሆነም ፡ እንዲሰረዝ ፡ ያዘዘውን ፡ ፍርዱን ፡ የሚጠቅስ ፡ ቃል ፡ ያደርግበታል ።

(፫) ስለዚህ፡ ጉዳይ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ከአስረጂ ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ በቤተ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፵፬ ። (፭) የተሰረዘጥ ፡ ጽሑፍ ፡ ግልባጭ ።**

(፩) የተሰረዘው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚነበብ፡ ሆኖ ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለበት ።

(፪) ባለጉዳዮቹ ፡ ከተሰረዘም ፡ በኋላ ፡ ግልባጭ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፵፭። (፮) ጽሑፉን ፡ በተጨማሪ ፡ መዝገቦች ፡ ስለ፡ ማግባት።**

(፩) እንደዚሁም ፡ "ተሰርዟል ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፤ የተሰረዘበትንም ፡ ቀን ፡ ጭምር ፤ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በባለሀብቶች ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

(፪) ለባለጉዳዮቹ ፡ የሚሰጡት ፡ የነዚህ ፡ መዝገቦች፡ ወረቀቶች ፡ የተሰረዙትን ፡ ጽሑፎች ፡ መጥቀስ ፡ የለባቸውም ።

**ቍ ፡ ሺ፮፻፵፮ ። ጽሑፍ ፡ በሚቃናበት ፡ ወይም ፡ በሚሰረዝበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚከፈለጥ፡ ታክስ ።**

(፩) ማንም፡ ሰው ፡ የተመዘገበ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲቃና ፡ ወይም ፡ እንዲሰረዝ ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥያቄውን ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ቀረጥ ፡ ይከፍላል ።

(፪) ጽሑፉን፡ ለማቃናት ፡ የሚወጣውን፡ ኪሣራ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚከፍል ፡ የሚቃናውን ፡ ስሕተት ፡ ያደረገው ፡ ወይም ፡ አንዳችም ፡ የተደረገ ፡ ስሕተት ፡ ባይኖር ፡ ጽሑፉ ፡ እንዲቃና ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፫) ስለ፡ ጽሑፉ ፡ መሰረዝ፡ የሚወጣውን ፡ ኪሣራ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚከፍለው ፡ ጽሑፉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበው ፡ ሰው ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ማስመዝገብ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

### ቍ ፡ ፲፮፻፵፯ ። ሰነዶችን ፡ የማስመዝገብ ፡ ግዴታ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ ዐቃብያን፡ መዛግብት ፡ እንዲመዘገቡ ፡ የቀረበላቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ባለዋጋነት ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ፈራጆች ፡ አይደሉም ።

(፪) ሕጉ፡ ያዘዛቸውን፡ ፎርማሊቴዎች ፡ ባለጉዳዮች ፡ ፈጽመዋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዐቃብያን ፡ መዛግብት ፡ ሰነዶቹን ፡ ሳይዘገዩ ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ።

(፫) በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መዝገብ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰነድ ፡ መመዝገብ ፤ ስለ ሰነዱ ፡ ዋጋ ፡ መኖር ፡ ጉዳይ ፤ የሚያስከትለው ፡ ጉዳይ ፡ የለም ።

### ቍ ፡ ፲፮፻፵፰ ። እርግጠኛ ፡ ጊዜ ።

በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ ማስመዝገብ ፡ በነዚሁ፡ መዝገቦች፡ለተመዘገቡት ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ እንዳስረጂ ፡ ሰነዶች ፡ ሆነው ፡ ለተቀመጡት ፡ ጽሑፎች ፡ እርግጠኛ ፡ ቀን ፡ ይሰጣቸዋል ።

### ቍ ፡ ፲፮፻፵፱ ። ስለ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፤ ወይም ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ስለሚረጋ ፡ መብት ።

በአንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የአንድ ፡ ጽሑፍ ፡ መመዝገብ ፡ በመመዝገቡ ፡ ብቻ ፡ መብት ፡ ስለሚያሳጣ ፡ ወይም ፡ መብት ፡ ስለሚያስገኝ ፡ የይርጋ ፡ መብት ፡ ጉዳይ ፡ አንድም ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

### ቍ ፡ ፲፮፻፶ ። የተመዘገበውን ፡ ጽሑፍ ፡ ስላለማወቅ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ሰው፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መዝገብ ፡ የገባውን ፡ ጽሑፍ ፡ መኖሩን ፡ አላውቅም ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ አይችልም ።

(፪) ይህ ፡ የተባለው፡ አለማወቅ፡ የደረሰው ፡ ከሠራተኞች ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዐቃቤ ፡ መዝገቡና ፡ የመንግሥት ፡ ኀላፊነት ፡ ጉዳይ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፲፮፻፶፩ ። በተመዘገቡት ፡ ሁለት ፡ ጽሑፎች ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣው ፡ ክርክር ።

(፩) ካንድ፡ ሰው፡ ተላልፎ ፡ ሊመዘገብ ፡ የሚገባውን ፡ መብት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ከዚሁ ፡ ባለመብት ፡ አግኝተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ መብቱን ፡ መጀመሪያ ፡ ላስመዘገበው ፡ ሰው ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) በመጀመሪያ ፡ ያጸፈውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ተቃዋሚ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ የሁለተኛው ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

(፫) መብቱን ፡ በሰጠው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሁለተኛው ፡ ሰው ፡ ያሉት ፡ መብቶች ፡ የጠበቁ ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ሺ ፮፻፵፪ ። በአንድ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ተመዘገቡ ፡ መብቶች ።</u>

(፩) ሁለት ፡ መብቶች ፡ በአንዱ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሁለቱ ፡ በፊት ፡ የተጸፈው ፡ ሰነድ ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) ሁለቱ ፡ ሰነዶች ፡ የተጻፉበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አንዱ ካንደኛው ፡ በፊት ፡ ለማጸፉ ፡ ማስረጃ ፡ የታጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ የቅድሚያ ፡ መመዝገቢያ ፡ ቍጥር ፡ የተሰጠው ፡ ቅድሚያ ፡ አለው ።

<u>ቍ ፡ ሺ ፮፻፵፫ ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።</u>

የሀብትነትን ፤ ወይም ፡ ሌላ ፤ የማይንቀሳቀስ ፤ ግዙፍ ፡ መብትን ፡ የሚያረጋግጡ ፤ ወይም ፤ የሚያስተላልፉ ፡ ወይም ፡ የሚለውጡ ፤ ወይም ፡ የሚያስቀሩ ፡ ፍርዶች ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉት ፡ ይህንኑ ፡ ፍርድ ፡ ለማግኘት ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ከተጻፈበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ሺ፮፻፵፬ ። መጥፎ ፡ ልቡና ።</u>

(፩) መመዝገቡ ፡ የሚመለከተውን ፡ መብት ፡ ጥያቄውን ፡ ያቀረበው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ መብቱን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ መጥፎ ፡ ልቡና ፡ መሆኑ ፡ የመመዝገቡን ፡ ዋጋ ፡ የሚያስቀር ፡ አይሆንም ።

(፪) እንደዚሁ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በመመዝገቡ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ እርግጠኛ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የተከሳሹን ፡ መጥፎ ፡ ልቡና ፡ አረጋግጦ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፮፻፵፭ ። መዝገብ፡ስላልገባ ፡ መብት ።</u>

(፩) የአንድ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ባለመግባቱ ፡ ምክንያት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆን ፡ መብት ፡ መብቱን ፡ ካላስመዘገበው ፡ ሰው ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ አንድ ፡ መብት ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ያገኘበትን ፡ ሰነድ ፡ ከማስመዝገቡ ፡ በፊት ፡ መብቱን ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ መብት ፡ ያገኘበትን ፡ ጽሑፍ ፡ ማስመዝገብ ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፲፮፻፵፮ ። መዝገቡን ፡ ለባለሀብቱ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ አንድ ፡ መብት ፡ ያስመዘገበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መብቱ ፡ ለሚመለከተው ፡ ለማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ የገባውን ፡ ጽሑፍ ፡ ዐቃቤ ፡ መዝገብ ፡ የመሰከረበት ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለባለሀብቱ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

(፪) ይህንን ፡ አሠራር ፡ ባለመፈጸሙ ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ለሚደርስ ፡ ጕዳይ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

## አንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ።

## ስለ ፡ ድርሰትና ፡ ስለ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ባለሀብትነት ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፵፯ ። የመብቱ ፡ አሰጣጥ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በአእምሮው ፡ አስቦ ፡ አንድ ፡ ቀዋሚ ፡ ነገር ፡ ፈጥሮ ፡ ያወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈጥሮ ፡ በማውጣቱ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ለዚያ ፡ ፈጥሮ ፡ ላወጣው ፡ ግዙፍነት ፡ የሌለውን ፡ የባለሀብትነትን ፡ መብት ፡ ያገኛል ።

(፪) ሥራው ፡ ማናቸውም ፡ የአገላለጽ ፡ ዐይነት ፡ መልክ ፡ ፎርም ፡ ማንኛውም ፡ ምስጋና ፡ ወይም ፡ ግብ ፡ ቢኖረው ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ይኖራል ።

(፫) ሠሪው ፡ የሠራው ፡ ነገር ፡ በሥራ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ማከናወን ፡ ውል ፡ (በአንትሬፕሪዝ) ፡ ምክንያት ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ለሠራው ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ ይህ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፵፰ ። በአእምሮ ፡ ታስቦ ፡ የሚወጣ ፡ ሥራ ።**

የአእምሮ ፡ ሥራዎች ፡ናቸው ፡ የሚባሉት ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) እንደ ፡ መጻሕፍት ፡ በጥራዝ ፡ እየሆኑ ፡ እንደሚወጡት ፡ ጽሑፎች ፡ እንደ ፡ መጽሔት ፡ ጽሑፎች ፡ (ረቪዮ) ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጋዜጦች ፡ በጉባኤ ፡ እንደሚሰጡት ፡ ንግግሮች ፡ እንደ ፡ አጭር ፡ ንግግሮች ፡ እንደ ፡ ስብከቶች ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ቲያትሮችና ፡ ቲያትርን ፡ እንደ ፡ መሳሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ ያሉት ፡ የዕውቀት ፡ ድርሰቶች ፤

(ለ) በቃል ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ በሙዚቃ ፡ እንዲሰሙ ፡ የተዘጋጁ ፡ ሥራዎች ፡ በሙዚቃ ፡ እንዲሰሙ ፤ የተዘጋጁ ፡ የቲያትር ፡ ሥራዎች ፡ በራዲዮ ፡ ድምፅ ፡ እንዲሰሙ ፡ ወይም ፡ በራዲዮቢዙየል ፡ እንዲታዩ ፡ የተዘጋጁ ፡ ሥራዎች ፡ ለቲያትር ፡ የተዘጋጁ ፡ የዳንስ ፡ ወይም ፡ የዜማ ፡ ስልቶች ፡ ሆነው ፡ አፈጻጸማቸውም ፡ በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አደራረግ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) እንደ ፡ ሥዕል ፤ እንደ ፡ ንድፍ ፡ ሥዕል ፤ እንደ ፡ ቅርጽ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ማነጥ ፡ ያሉ ፡ ሥራዎች ፤ እንዲሁም ፡ እንደ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሲኒማ ፡ ያሉት ፡ የሚታዩ ፡ ሥራዎች ፤

(መ) የሥዕል ፡ መጽሔቶች፣ የጂኦግራፊ ፡ ካርታዎች፣ ፕላኖች ፡ የመጀመሪያ ፡ ንድፍ ፡ ሥራዎች ፡ ጂኦግራፊን ፡ የአገር ፡ መልክን ፡ (ቶፖግራፊ) ፡ የሕንጻ ፡ አሠራርን ፡ አርኪቴክቱር ፡ ኪነ ፡ ጥበብን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዕውቀትን ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከቱ ፡ እንደ ፡ እጅ ፡ ጥበብ ፡ ማንሻ ፡ ያሉ ፡ የሥዕል ፡ ሥራዎች ፤

(ሠ) በሠሪያቸው፣ አእምሮ፣ የተፈጠሩና ፡ የዚሁኑ ፡ አሠራር ፡ ልዩነት ፡ የሚያሳዩ ፡ ሌሎችም ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ሺ፮፻፵፱ ። ትርጕምና ፡ ማስማማት ።

የመጀመሪያው ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ አውጪ ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፡ የመጽሐፉን ፡ ትርጕም ፡ የሥራውን ፡ ማስማማት ፡ (ማሻሻል) ፡ የሙዚቃ ፡ ማስማማቱን ፡ እና ፡ የድርሰትን ፡ ወይም ፡ የኪነ ፡ ጥበብን ፡ ዐይነት ፡ መለወጥ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያ ፡ ሥራ ፡ ሆነው ፡ ይጠበቃሉ ።

## ቍ ፡ ሺ፮፻፶ ። እንሲክሎፔዲና ፡ የቅኔ ፡ ጥርቅም ።

ነገሮቹን ፡ በማማረጥ ፡ ወይም ፡ በማዘጋጀት ፡ ከድርሰቶችና ፡ ከኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ ተለቅመው ፡ የአእምሮ ፡ ሥራ ፡ ፈጠራ ፡ እንደሚወጣቸው ፡ እንደ ፡ እንሲክሎፔዲና ፡ እንደ ፡ ቅኔ ፡ ያሉት ፡ የጥርቅም ፡ አስተዋጽኦችም ፡ በነዚህ ፡ በተዋጽኦ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ በያንዳንድ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ የመጀመሪያ ፡ አውጪዎች ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያ ፡ ሥራ ፡ ሆነው ፡ የሚጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ሺ፮፻፶፩ ። ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ የመንግሥት ፡ ጽሑፎች ።

(፩) የሕግ፣ የአስተዳደር፣ ወይም ፡ የዳኝነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ከመንግሥት ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ የሚነገሩት ፡ ጽሑፎች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተነገረውን ፡ ጥበቃ ፡ አያገኙም ።

(፪) እንድ ፡ ተሰብስበው ፡ በነጻ ፡ ሊታተሙ ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ሺ፮፻፶፪ ። የወጣወን ፡ ሥራ ፡ የማስታወቅ ፡ መብት ።

(፩) ያወጣውን፣ ሥራ፣ የማስታወቅ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በተባለው ፡ መብት ፡ የሚሠራ ፡ እርሱ ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ የመረጠው ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥራው ፡ አውጪ ፡ ወራሾች ፡ ናቸው ።

(፫) የሥራ ፡ አውጪው፡ ወራሾች ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አወጣጥ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስታወቁ ፡ ሁኔታዎች ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞቹ ፡ ወራሾቹ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ያቀረቡትን ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፡ ያመዛዝናሉ ።

ቍ ፡ ፲፮፻፶፱ ። የወጣውን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማሳየትና ፡ ማባዛት ።

(፩) ያወጣውን፡ ሥራ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ለማሳየት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ ያወጣውን ፡ ሥራ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ለባማዛት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ያው ፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷ ። ሥራውን፡ ስለ፡ ማስማማት ።

(፩) ለቲያትር ፡ ለሲኒማ ፡ ለራዲዮ ፡ ቢዚዮን ፡ ወይም ፡ ለማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ እንዲስማማ ፡ ለመፍቀድ ፡ መብቱ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የሌላ ፡ ሰው ፡ ሥራ፡ ሆኖ ፡ አሠራሩን፡ በማስማማት ፡ ወጣ ፡ የሚባለው፡አዲስ ፡ ሥራ ፡ የአሠራሩን ፡ ሁኔታዎች ፡ በማየት ፡ በፊት ፡ ከወጣው ፡ ሥራ፡ጋራ፡ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መስልነት ፡ ሲኖረው ፡ ወይም ፡ በጥብቅ ፡ በመያያዝ ፡ ከተፃለው ፡ ሥራ ፡ የመነጨ ፡ ለመሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ሲታይ ፡ ነው ።

(፫) በሌላው ፡ ሰው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ሐተታ ፡ መግለጽ ፡ ወይም ፡ በገጥም ፡ ላይ ፡ መግጠም ፡ ወይም ፡ በሚያሥቅ ፡ ዐይነት ፡ ሥዕሎችን ፡ ነድፎ ፡ የማውጣት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ሥራ ፡ አስማምቶ ፡ እንደ ፡ ማውጣት ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፩ ። ትርጒም ።

(፩) ያውጣው፡ ሥራ፡ (መጽሐፍ) ፡ እንዳይተረጐም ፡ ደራሲው ፡ ለመቃወም ፡ አይችልም ።

(፪) ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ የተደረገው ፡ ትርጒም ፤የዚህን፡ ሁኔታ ፡ በተተረጐመው ፡ መጽሐፍ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) ይህን፡ ሳይገልጽ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የደራሲውን ፡ መብቱ ፡ እንደ ፡ ነካ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፪ ። በግልና ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የሚደረግ ፡ ማሳየት ።

በተለይ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለብቻና ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የሚፈጽመውን ፡ የሥራውን ፡ ማሳየት ፡ ተግባር ፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ለመከልከል ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፫ ። የዘመኑ ፡ ሁኔታ ፡ ጽሑፎችና ፡ ወሬዎች ።

(፩) የዘመኑን፡ ጠባይ፡ የሚገልጹ ፡ ጋዜጣዎች ፡ ወይም ፡ በማኅተም፡መሳዛታቸው ፡ በግልጽ ፡ ያልተጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማኅተም ፡ ወጥተው ፡ ወይም ፡ በራዲዮ ፡ ተገልጸው ፡ ለመታየት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ቢሆንም ፡ የተገኙበት ፡ ምንጭ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ መነገር ፡ አለበት ።
(፫) የተራ ፡ ነገር ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ የለዕት ፡ ወሬዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ በነጻ ፡ ታትመው ፡ ሊመውጣት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፮፻፶፰ ። በአደባባይ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ።

በፖሊቲካ ፡ ጉባኤ ፡ በሕዝብ ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ውስጥ ፡ የተደረጉትን ፡ ንግግሮች ፡ ክተነገሩበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እየታተሙ ፡ ሊወጡና ፡ በራዲዮ ፡ ሊነገሩ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፮፻፶፱ ። የንግግሮቹ ፡ ወይም ፡ የጋዜጦቹ ፡ መድበል ።

የራሱን ፡ ንግግሮችና ፡ ጽሑፎች ፡ በመጽሐፍ ፡ ዐይነት ፡ አድርጎ ፡ ለማውጣትና ፡ በአንድ ፡ ለማጠቃለል ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ራሱ ፡ ደራሲው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷ ። ሥራውን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳያባዛ ፡ የመከልከል ፡ መብት ፡ ወሰን ።

(፩) ጸሐፊው ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ጻፈው ፡ ጉዳይ ፡ የሚደረገውን ፡ ማፍታታትና ፡ በጋዜጣ ፡ የሚወጡትን ፡ የመግለጫ ፡ (ጽሑፎች) ፡ ለመከልከል ፡ አይችልም ።
(፪) እንደዚሁም ፡ ለግል ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ የሚሆን ፡ ከመጽሐፉ ፡ አንድ ፡ ቅጂ ፡ ወይም ፡ ግልባጭ ፡ ብቻ ፡ ለመውሰድ ፡ ይፈቀዳል ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፩ ። ጥቅሶች ።

የሚጠቀሱ ፡ ነገሮች ፡ ከአንድ ፡ የቅኔ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲሆን ፡ ከአርባ ፡ መሥመሮች ፡ ከሌላ ፡ ዐይነት ፡ መጽሐፍ ፡ ሲሆን ፡ ከዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ፊደላት ፡ የማያልፉ ፡ (ማይበልጡ) ፡ ከሆኑ ፡ ከወጣው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይጠቀሱ ፡ ደራሲው ፡ ለመከልከል ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፪ ። የፎቶግራፍ ፡ ሥራዎች ።

(፩) የፎቶግራፍ ፡ ሥራዎች ፡ የሚጠበቁት ፡ በአንድ ፡ የፎቶግራፍ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ውስጥ ፡ ተያይዘው ፡ የሚገኙ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ታትመው ፡ የወጡ ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ።
(፪) በሌላ ፡ ሁኔታዎች ፡ የፎቶግራፍ ፡ አንሺውን ፡ ወይም ፡ የወኪሉን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ የያዙ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ እንዳይባዙ ፡ የተጠበቁ ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፲፮፻፷፫ ። የወጣውን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ ያወጣውን ፡ (ግዙፍነት) ፡ የሌለው ፡ ሥራ ፡ ባለሀብትነት ፡ መጠበቅ ፡ ከሚገባው ፡ ከግዙፍ ፡ ዕቃ ፡ ባለሀብቶችነት ፡ የተለየ ፡ ነው ።

(፪) ይህን፡ ዕቃ ፡ በመግዛት፡ እጅ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ እጅ ፡ በማድረጉ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከቍጥሩት ፡ መብቶች ፡ አንዱም ፡ አይሰጠውም ፡
(፫) ስለ፡ ሆነም፡ ሥራውን ፡ አስቦ ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ በለቀቀው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ በመብቱ ፡ እንድሠራበት ፡ አድርግልኝ ፡ ሲል ፡ የተባለው ፡ ግዙፍ ፡ ዕቃ ፡ ባለቤት ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፮፻፷፬ ፡፡ አሳትሞ ፡ ለማስወጣት ፡ ወደ ፡ ተጻፈው ፡ የውል ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መምራት ፡፡**

ድርሰትን፡ ወይም ፡ ኪነ ፡ ጥበብን ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ የዚህን ፡ ያወጣውን ፡ ሥራ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚለቅባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ የአሳትሞ ፡ ማስወጣት ፡ ውል፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ተወስነዋል ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፮፻፷፭ ፡፡ የወጣውን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ፡፡**

ማንኛቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ያወጣውን ፡ ሥራ ፡ ዐይነቱን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የለወጠበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ ሥራ ፡ የዚያ ፡ የለወጠው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በመባል ፡ እንዳይቀጥል ፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፮፻፷፮ ፡፡ ሥራ ፡ አውጪው ፡ ማን ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ መወሰን ፡፡**

(፩) ተቃራኒ፡ የሚሆን፡ አስረጂ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የሥራው ፡ አውጪ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ሥራው ፡ በስሙ ፡ መውጣቱ ፡ የታወቀለት ፡ ሰው ፡ ነው ፡፡
(፪) ሥራ ፡ አውጪው ፡ ያወጣው ፡ ሥራ ፡ የፈጠራ ፡ ስምን ፡ በመስጠት ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ ትክክለኛነት ፡ አንዳች ፡ ጥርጥር ፡ ከሌለ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተወሰኑት ፡ መብቶች ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፮፻፷፯ ፡፡ የአውጪው ፡ ስም ፡ የሌለባቸው ፡ ሥራዎች ፡፡**

የአውጪው ፡ (የደራሲው) ፡ ስም ፡ የሌለባቸው ፡ ሥራዎችና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ ከተጠቀሱት፡ በቀር ፡ በፈጠራ ፡ ስም ፡ የተጻፉ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ ሲገኙ ፡ በወጣው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስሙ ፡ የተመለከተው ፡ አሳትሞ ፡ ጽሑፍ ፡ አውጪው ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ሳያስፈልግ ፡ የሥራ ፡ አውጪው ፡ ወኪል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ፡፡

**ቍ ፡ ሺ፮፻፷፰ ፡፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ የወጣው ፡ ሥራ ፤ (፩) የጋራ ፡ ሥራዎች ፡ መብት ፡፡**

(፩) በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሠሪነት ፡ ታስቦ ፡ የወጣው ፡ ሥራ ፡ የአውጪዎቹ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ይሆናል ፡፡
(፪) የሥራው፡ አውጪነት፡ መብት ፡ በመካከላቸው ፡ በሚደረግ ፡ በጋራ ፡ ስምምነት ፡ ሊሠራበት ፡ ይገባል ፡፡

(፫) የጋራ፡ ሠሪዎቹ፡ የያንዳንዱ ፡ ድርሻ ፡ መሳተፍም ፡ የወጣበት ፡ ከልዩ፡ልዩ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የጋራው ፡ ሥራ ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ሳይነካ ፡ እያንዳንዱ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ባደረገው ፡ በራሱ ፡ ድርሻ ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ለብቻው ፡ መጠቀም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፮፻፷፱ ። (፪) ሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) አንድ፡ የወጣ፡ ሥራ ፡ በአንዱ ፡ አውጪ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌሎቹ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ይህ ፡ በሥራው ፡ አውጪነት ፡ ስሙ ፡ የተጠራው ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ የሥራው ፡ አውጪ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናቸዋል ።

(፪) የጋራ ፡ ሥራ፡ አውጪዎቹ፡ መብት ፡ እነዚህን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፮፻፸ ። የሥራ ፡ አውጪው ፡ ወራሾች ፤ (፩) የገንዘብ ፡ መብት ።

(፩) አስቦ ፡ ሥራ ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ያወጣውን ፡ ሥራ ፡ የማሳየት ፡ የማባዛት ፡ ወይም ፡ የሥራውን ፡ ማስማማት ፡ የመፍቀድ ፡ መብቱ ፡ እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ወራሾቹ ፡ ሥራው ፡ በአደባባይ ፡ ወጥቶ ፡ ከታወቀበት ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አምሳ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ወራሾቹ፡ በነገሩ ፡ ሳይስማሙ፡ በሚቀሩበት ፡ ጊዜ ፡ ዳኞቹ ፡ እያንዳንዱ፡ወራሽ ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ለማመዛዘን ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ሺ፮፻፸፩ ። (፪) የሕሊና ፡ መብት ።

የወጣውን ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ፫ኛ ፡ ወገን ፡ ዐይነቱን ፡ ሲለውጥ ፡ ይህ ፡ ዐይነቱ ፡ የተለወጠው ፡ ሥራ ፡ የአውጪው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እንዲቀጥል ፡ የማስደረጉ፡ መብት ፡ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ እንዳቸው ፡ የሥራ ፡ አውጪው ፡ ወላጆች ፡ ልጆቹና ፡ የልጅ ፡ ልጆቹ ፡ በየራሳቸው ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ሺ፮፻፸፪ ። ከሞት ፡ በኋላ ፡ የሚታወቅ ፡ ሥራ ።

ሥራውን ፡ ያወጣ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ሥራ ፡ ከታወቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የተጠበቀ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፮፻፸፫ ። የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መብት ።

(፩) የወጣው፡ ሥራ፡ አውጪው ፡ ባለቤቱ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ በግልጽ ፡ አስታውቀውት ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ ሠሪው ፡ ቢቃወምም ፡ ቅሉ ፡ ለጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ አስቦ ፡ ያወጣው ፡ ሥራ ፡ እንዲታይ ፡ ወይም ፡ መሰሉ ፡ እንዲባዛ ፡ ወይም ፡ ዐይነቱ ፡ የተስማማ ፡ በመሆን ፡ እንዲሻሻል ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የዚህ፡ የአፈቃቀድ፡ ምክንያቶችና ፡ ፎርሞች ፡ ለሥራ ፡ አውጪው ፡ የሚገባ ፡ ትክክለኛ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጠው ፡ በሚናገረው ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ይወሰናሉ ።

(፫) የሕዝብ፡ ባለሥልጣኖች፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ የሥራው ፡ ዐይነት ፡ እንዲለዋወጥ ፡ ለመፍቀድ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፲፮፻፸፬ ። የድርሰት ፡ ወይም ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ባለሀብትነት ።

(፩) የድርሰት፡ ወይም፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ባለ ፡ ሀብትነት ፡ መብቱ ፡ የተነካበት፡ሥራ ፡ አውጪ ፡ የተባለው ፡ መነካት ፡ እንዲቆም ፡ እና ፡ ሕግን ፡ በመተላለፍ ፡ (በመጣስ) ፡ የተደረጉት ፡ የሥራው ፡ ቅጂዎች ፡ ወይም ፡ የሥራው ፡ ማሻሻያዎች ፡ እንዲጠፉ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህም፡ በላይ ፡ በሕሊናም፡ ሆነ ፡ በግዙፉ ፡ ረገድ ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ የገንዘብ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችልባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኀላፊነት ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ተወስነዋል ።

# አራተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ግዴታዎች ።

## አንቀጽ ፡ ፲፪ ።

## ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ።

ቍ ፡ ፲፮፻፸፭ ። የውል ፡ ትርጓሜ።

ውል ፡ ማለት ፡ ንብረታቸውን ፡ የሚመለከቱ ፡ ግዴታዎችን ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፤ ባላቸው ፡ ተዋዋይ ፡ ግንኙነት ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ስምምነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፮፻፸፮ ። ውሎች ፡ የሚመሩባቸው ፡ ደንቦች ።

(፩) ውሎች ፡ ዐይነታቸው ፡ ምክንያታቸውም ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በተጻፉት ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ ይመራሉ ።

(፪) እነዚህን ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ የሚለውጡ ፡ ወይም ፡ የሚያሟሉ ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ውሎች ፡ የተጻፉ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በ፭ኛው ፡ መጽሐፍና ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተዋል ።

ቍ ፡ ፲፮፻፸፯ ። የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ አፈጻጸም ።

(፩) ግዴታዎቹ ፡ ከውል ፡ የተገኙ ፡ ባይሆኑም ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ደንቦች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

BACK



(፪) የአንዳንድ ፡ ግዴታዎችን ፡ ከስር ፡ አመጣጣቸውን ፡ ወይም ፡ ዐይነታቸውን ፡ በመመልከት ፡ ከዚህ ፡ ደንብ ፡ የተለዩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ውል ፡ አመሠራረት ።

**ቍ ፡ ፲፻፯፻፸፰ ። የውል ፡ አቋሞች ።**

የሚጸና ፡ ውል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ሦስት ፡ ሁኔታዎች ፡ ያስፈልጉታል ።

(ሀ) ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ችሎታ ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጕድለት ፡ የሌለው ፡ ስምምነት ፡ መኖር ፤

(ለ) በቂ ፡ የሆነ ፡ እርግጠኛነት ፡ ያለው ፡ የሚቻልና ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ጕዳይ ፤

(ሐ) ይኸውም ፡ የውሉ ፡ አጻጻፍ ፡ ፎርም ፡ (ዐይነት) ፡ በሕግ ፡ የታዘዘ ፡ ሆኖ ፤ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ባይፈጸም ፡ ፈራሽነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ፎርም ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ፈቃዶ ፡ ስለ ፡ መዋዋል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

## ውለታን ፡ የመቀበል ፡ አቋሞች ።

**ቍ ፡ ፲፻፯፻፸፱ ። ውልን ፡ ፈቃዶ ፡ መዋዋል ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ውል ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በገቡባቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ እነዚሁም ፡ አስገዳች ፡ እንዲሆኑ ፡ የተስማሙበትን ፡ በሚገልጸው ፡ የፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፯፻፹ ። የተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ።**

(፩) ውሉ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በተስማማ ፡ አኳኋን ፡ መፍቀዳቸውን ፡ ገልጸው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

(፪) ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሳያውቀው ፡ ከውሉ ፡ ውስጥ ፡ የማስቀረትና ፡ የማገድ ፡ ቃላት ፡ ተጨምረውበት ፡ ቢገኙ ፤ በአጻጻፉ ፡ በግልጽ ፡ ተነግሮ ፡ የሚገኘው ፡ የመፍቀድን ፡ ዋናውን ፡ ሁኔታ ፡ ሊያቃውሱትና ፡ ሊቀንሱት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፲፻፯፻፹፩ ። የውል ፡ አቀራረብና ፡ አቀባበል ።**

(፩) ፈቃድን ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በተለመዱ ፡ ጠቅላላ ፡ ምልክቶች ፡ ወይም ፡ ለውሉ ፡ መነሻ ፡ ከሆነው ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ግዴታ ፡ ለመግባት ፡ መፍቀዱን ፡ በማያጠራጥር ፡ አሠራር ፡ ለማስታወቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) ቢሆንም ፡ ለውሉ ፡ አቀባበል ፡ አቅራቢው ፡ የተለየ ፡ አሠራር ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፹፩ ። ዝምታ ። (፩) መሠረቱ ።**

የውል ፡ አቀራረብ ፡ ሲቀርብለት ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ የቀረበለትን ፡ የውል ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ አያስቈጥርም ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፹፪ ። (፪) የመቀበል ፡ ግዴታ ።**

(፩) በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ውል ፡ (ኰንሰሲዮን) ፡ ምክንያት ፡ የተወሰነ ፡ የውል ፡ አፈጻጸም ፡ ሲኖርና ፡ አስቀድሞ ፡ በተሠራው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የተለዩ ፡ ሰዎች ፡ የሚገደዱበት ፡ ሲሆን ፤ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ውሉን ፡ ስለ ፡ መቀበላቸው ፡ ማረጋገጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሲሆን ፡ ውል ፡ ተቋቋመ ፡ (ተፈጸመ) ፡ የሚባለው ፡ የውሉን ፡ ድርድር ፡ አቀራረብ ፡ በተቀበለበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፹፫ ። (፫) አስቀድመው ፡ ስላሉ ፡ የውለታ ፡ ግንኙነቶች ።**

(፩) ቀድሞ ፡ የነበረውን ፡ የውል ፡ ዘመን ፡ ለማስረዘም ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ ማስታወቂያ ፡ በዝምታ ፡ ብቻ ፡ ለመቀበል ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በተለይ ፡ የማሆነው ፡ ጽሑፍ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በተሰናዳ ፡ አቀራረብ ፡ ድርድሩ ፡ ቀርቦ ፤ በዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ተቈርጦለት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ቢቀር ፡ የቀረበለትን ፡ ድርድር ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፹፬ ። (፬) ፋክቱር ።**

ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ በፋክቱር ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ማስታወሻ ፡ ጽፎበት ፡ ቢገኝ ፡ በዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመስማማቱ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ አስቀድሞ ፡ ከሰጠው ፡ ስምምነት ፡ ጋራ ፡ የሚገጣጠም ፡ ስምምነት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ይህንኑ ፡ ግዴታ ፡ በግልጽ ፡ ካልተቀበለ ፡ አያስገድደውም ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፹፭ ። (፭) ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታዎች ።**

ባለውል ፡ የፈጸማቸው ፡ ጠቅላላ ፡ የጕዳይ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሌላውን ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ ሊያስገድዱት ፡ የሚችሉት ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ እነዚህን ፡ ጕዳዮች ፡ አስቀድሞ ፡ ዐውቋቸውና ፡ ወዶ ፡ ተቀብሏቸው ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የደነገጓቸው ፡ ወይም ፡ ያጸደቋቸው ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፮፻፹፮ ። አሳብን ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።**

(ሀ) ለተጠቃሚው ፡ ሳያስታውቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፤ አንድ ፡ ጕዳይ ፡ የማድረግ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ማድረግ ፡ አሳቡን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) እንዲሁም ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ተመን ፡ (ታሪፍ) ፡ ወይም ፡ የዕለት ፡ ገበያ፡ ዋጋ ፡ መግለጫ ፤ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ የሚያሳይ ፡ ጽሑፍ ፡ ለሌላ ፡ ሰው፡ የላከ ፤ ወይም ፡ በአደባባይ ፡ በሚለጠፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ የገለጸ ፡ ወይም ፡ የን ግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ለሕዝብ ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ ያሳየ ፡ የደረደረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አድራጎት ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ አያስቈጥረውም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፲፫ ። ለሕዝብ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሐራጅ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ሀብቱን ፡ በሐራጅ ፡ የሚሸጥ ፡ መሆኑን ፡ ሲያስታውቅ ፤ አሳ ቡን ፡ መግለጹ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ውል ፡ እንዳቀረበ ፡ አይቈጠርም ።

(፪) እንዲሁ፡በሆነ፡ጊዜ፡ውል፡ተፈጸመ፡ለማለት፡የሚቻለው፡በመጨረሻው፡ሐራጅ፡ ለጨረታ ፤ የቀረበው ፡ ሀብት ፡ ለዋጋ ፡ አቅራቢው ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፲፬ ። ሽልማት ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ በግልጽ ፡ የተሰጠ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ።**

(፩) የጠፋ ፡ ዕቃ ፡ ላገኘ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለፈጸመ ፡ ሰው ፡ ሽልማት ፡ ይሰ ጠዋል ፡ ተብሎ ፡ በተለጠፈ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ በአደባባይ ፡ ሊታወቅ ፡ በሚቻል ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ወጥቶ ፡ ቃል ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ የጠፋ ውን ፡ ዕቃ ፡ አግኝቶ ፡ ቢያመጣ ፡ ወይም ፡ እንዲፈጸም ፡ የተባለውን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ፡ ቢገኝ፡ ይህን ፡ ያደረገው፡ ሰው ፡ የወጣውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳያውቅ፡ ቢቀርም ፡ የተሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቃል ፡ ሰጪውም ፡ በበኩሉ ፡ የሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፲፭ ። ጊዜ ፡ ተወስኖ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ውል ።**

(፩) የመቀበያውን ፡ ጊዜ ፡ ወስኖ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ እንዲደረግ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚ ያቀርብ ፡ ሁሉ ፡ ለዚሁ ፡ የወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ በዚሁ ፡ አቀ ራረብ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ይጸናበታል ።

(፪) ከዚህ ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ሊድን ፡ የሚችለው ፡ ጊዜው ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ ያቀ ረበውን ፡ ውል ፤ የቀረበለት ፡ ሰው ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፲፮ ። ጊዜ ፡ ሳይወሰን ፡ የሚቀርብ ፡ ውል ።**

(፩) ለቀረበው ፡ ውል ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሳይደረግለት ፡ ቢቀር ፡ ውሉን ፡ ያቀረበው፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ ተገዳጅ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ የቀረበለት ፡ ሰው ፡ መቀ በል ፡ ያለ ፡ መቀበሉን ፡ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችል ፡ የነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በአእምሮ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ይሆናል ፡ እስከሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

(፪) መቀበሉን ፡ ዘግይቶ ፡ ቢያስታውቅና ፡ ውል ፡ አቅራቢው ፡ በዚህ ፡ ባቀረበው፡ የውል፡ ቃል፡ መገደድ፡ ባይፈልግ፡ ወዲያውኑ፡ ለተቀባዩ፡ ማስታወቅ፡ አለበት።

**ቍ ፡ ፲፯፻፲፯ ። ተዋዋዮቹ ፡ ሳይገናኙ ፡ ስለሚደረግ ፡ ውለታ ።**

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ሳይገናኙ፡ የተደረገ ፡ ውለታ ፡ ተዋውለውበታል ፡ ተብሎ ፡ የሚታወ ቀው፡ ውል፡ ተቀባዩ ፡ መቀበሉን ፡ ያስታወቀበት ፡ ስፍራና ፡ የላከበት ፡ጊዜ፡ነው።

BACK



(፪) በቴሌፎን ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ተዋዋዩ ፡ በቴሌፎን ፡ በተጠራበት ፡ ስፍራ ፡ የተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) ይህን፡ተቃራኒ፡ የሆኑት፡ የተዋዋዮቹ፡ ወገኖች፡ ስምምነቶች፡ የተጠበቁ፡ናቸው።

ቍ ፡ ፲፯፻፫ ። የውል ፡ ማቅረብን ፡ ወይም ፡ መቀበልን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።

(፩) ውል ፡ ተቀባዩ ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ መኖሩን ፡ ከማወቁ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ይህ፡ መኖሩን ፡ እንዳወቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ድርድሩ ፡ መሻሩን ፡ ያወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የውሉ ፡ ድርድር ፡ እንዳልተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ይኸው ፡ ደንብ ፡ የውሉን ፡ ድርድር ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ትቻለሁ ፡ ለሚለ ውም ፡ ወገን ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፬ ። ፍጹም ፡ ያልሆነ ፡ የውል ፡ አቀባበል ።

የተጠበቀ ፡ ሁኔታ ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ ከቀረበው ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ በትክክል ፡ የማይስማማ ፡ የውል ፡ አቀባበል ፡ ድርድሩን ፡ እንደ ፡ አለመቀ በልና ፡ አዲስ ፡ ድርድር ፡ እንደ ፡ ማቅረብ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ፡ ፲፯፻፭ ። የውል፡ፍጹምነት ።

(፩) ከውሉ ፡ ባንዱ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮች ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ ከተዋ ዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ አለመስማማቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ነገር ፡ ካለ ፡ ውሉ ፡ ተፈጸመ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

(፪) ተዋዋዮቹ ፡ በውላቸው ፡ የተስማሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ከገለጹና ፡ ካመኑ ፡ ስም ምነቱ ፡ ያልተሟላ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ ውሉ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ የጐደለው ፡ ስምምነት ፡ የሚሟላው፡ በሕግ ፡ ተደንግጎ ፡ በሚገኘው ፡ ነው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

የተዋዋዮቹ ፡ ፈቃድ ፡ ጕድለት ።

ቍ ፡ ፲፯፻፮። ውልን ፡ የሚያፈርሱ ፡ ምክንያቶች ።

(፩) ውል ፡ የሚፈርሰው ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ የአንደኛው ፡ መፍቀድ ፤ በስሕተት ፡ በድ ንገተኛ ፡ ተንኰል ፤ ወይም ፡ በኀይል ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፯ ። ውልን፡ ከመቀበል፡ ስለሚያደርስ፡ ስሕተት ።

መሳሳቱ ፡ ይታወቅልኝ ፡ ሲል ፡ የሚከራከረው ፡ ወገን ፡ ስሕተቱ ፡ ለመዋዋል ፡ ያደረሰው ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ፤ እንዲህ ፡ መባሉ ፤ እውነቱን ፡ ዐውቆ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ፈቅዶ ፡ የማይሠራው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ነው ።

ቍ ፲፯፻፰ ። ለውል ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መሳሳት ።

ለመዋዋል ፡ ያደረሰው ፡ ስሕተት ፡ ውል ፡ ማፍረሻ ፡ የሚሆነው ፤ ተዋዋዮቹ ፡ አስፈላጊ ፡ አቋም ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በሚቀበሉት ፡ አኳኋን ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ ስሕ ተት ፡ ሲሆንና ፡ ወይም ፤ ውሉ ፡ ሲፈጸም ፡ በአኳኋኑና ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ አስፈ ላጊ ፡ አቋም ፡ በሆነው ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ሲገመት ፡ ነው ።

BACK



ቍ ፡ ፲፮፻፺፱ ። በውሉ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ጒዳይ ፡ ላይ ፡ ስለሚሆን ፡ ስሕተት ።

ለመዋዋል ፡ ያደረሰው ፡ ስሕተት ፡ በተለይ ፡ ውሉን ፡ የሚያፈርሰው ፤

(ሀ) በውሉ ፡ ዐይነት ፡ ላይ ፡ ስሕተቱ ፡ የደረሰ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) አንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ መሳሳቱ ፡ የሚያቀርበው ፡ መከራከሪያ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እስረጅነት ፡ የሚያገኝ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ ውል ፡ ተቀ ባይ ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ በእውነት ፡ ከፈቀደው ፡ እጅግ ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻ ። በተዋዋዩ ፡ ስለ ፡ ማሳሳት ።

ተዋዋዩ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሥራው ፡ ሞያው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማሳሳት ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ የሚቀረው ፡ በተለመደው ፡ የነገር ፡ አግባብ ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ተዋዋዩን ፡ ወይም ፡ ሞያውን ፡ ማወቅ ፡ ለውሉ ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ጒዳይ ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፩ ። በቂ ፡ ምክንያት ፡ የማይሆን ፡ ስሕተት ።

(፩) ለመዋዋል ፡ ባደረሱት ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ ስሕተት ፡ ውሉን ፡ አያ ስቀረውም ።

(፪) በውሉ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የሒሳብ ፡ ስሕተት ፡ ብቻ ፡ የተሳሳተው ፡ ሒሳብ ፡ እንዲተካከል ፡ ያደርገዋል ፡ እንጂ ፤ ውሉን ፡ በሙሉ ፡ አያፈርሰውም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፪ ። ለቅን ፡ ልቡና ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ አሠራር ።

(፩) በስሕተቱ ፡ ተጎጂ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ የቅን ፡ ልቡና ፡ አሠራርን ፡ ተቃዋሚ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ይታይልኝ ፡ ሊል ፡ አይችልም ።

(፪) ሌላው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ የሚፈቅድ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጠ ፡ ተዋውሎበት ፡ በነበረው ፡ ውል ፡ መገደድ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፯፻፫ ። ኪሣራ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ።

ውሉ ፡ ከሚያደርስበት ፡ ግዴታ ፡ ለመዳን ፡ ሲል ፡ በስሕተቱ ፡ የሚያመካኘው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፤ ሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ ስሕተቱን ፡ ካላወቀ ለት ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ ካልገለጸ ፡ በቀር ፡ በውሉ ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ።

ቍ ፡ ፲፯፬ ። ተንኰል ።

(፩) በተንኰል ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ የሚሆነው ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ውሉ ፡ እንዲደረግ ፡ ያደረገው ፡ በሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ላይ ፡ ተን ኰል ፡ ባይደርስበት ፡ ኖሮ ፡ ውል ፡ የማያደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሲገለጽ ፡ ነው ።

(፪) ከተዋዋዮቹ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ ተንኰል ፡ ያለ ፡ ውዴታ ፡ ባደረ ገው ፡ ውል ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ወገን ፤ ሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ይህ ፡ ተን ኰል ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑን ፡ ካላወቀለት ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ ካልተገለጸ ፡ ወይም ፡ ከውሉም ፡ ጥቅም ፡ ካገኘ ፡ በውሉ ፡ ተገዳጅ ፡ ይሆናል ።

BACK



ቍ ፡ ሺ፯፻፭ ። እርግጠኛ ፡ ባልሆነ ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ መዋዋል።

(፩) በክፉ ፡ ልቡና ፡ ወይም፡ በቸልተኛነት ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን፡ ይልቁንም ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ የተለየ ፡ የታወቀ ፡ መተማመን ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ በግንኙነታቸውም ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ የተለየ ፡ ታማኝነት ፡ እንዲኖረው ፡ ሲገደድ ፤ እርግጠኛ ፡ ባልሆነ፡ ጕዳይ፡ የሰጠው፡ ውል፡ ለማፍረስ ፡ የሚፈቅድ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል።

(፪) እንዲሁም፡ ዝም ፡ በማለት ፤ የተዋዋለው ፡ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ያልተካከለውን፡ ነገር ፡ አሳምኖት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይኸው ፡ ሥርዐት ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፮ ። በመገደድ ፡ የተደረገ ፡ ውለታ ።

(፩) የኀይል ፡ ሥራ ፡ ለውሉ ፡ ማፍረሻ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆነው ፡ አንደኛውን ፡ ወገን፡ እሱን ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ወላጆቹን ፡ ወይም ፡ ተወላጆቹን ፡ ወይም ፡ ባልን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ከባድና ፡ የማይቀር ፡ አደጋ ፡ በሕይወቱ ፡ በአካሉ ፤ በክብሩ ፡ ወይም ፡ በንብረቱ ፡ እንደሚመጣበት ፡ ያሳመነው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ይኸውም ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ አእምሮው ፡ የተደላደለውን ፡ ሰው ፡ ለማሥጋት፡ የሚችል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ የማስገደድ ፡ ሥራ ፡ የደረሰበትን ፡ ሰው ፤ ዕድሜውን ፡ ጾታውን ፡ አኳኋኑን ፡ ማመዛዘን ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ፡ ሺ፯፻፯ ። ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ስለሚያደርገው ፡ የኀይል ፡ ሥራ ።

(፩) በተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ሲፈጸም ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ሠሪው፡ በስምምነቱ ፡ ተጠቃሚ ፡ ያልሆነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የውል ፡ ማፍረሻ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።

(፪) የኀይል፡ ሥራውን፡ የፈጸመው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ያላወቀውና፡ ሊያውቀውም፡ የማይገባው፡ ያልሆነ፡ እንደ፡ሆነ፤ ከተዋዋዮቹ፡ አንዱ፡ በመገደዱ ፡ ምክንያት ፡ ከውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ እድናለሁ ፡ ባዩ ፤ ውሉ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ላገኘው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፰ ። በመብት ፡ ስለ ፡ ማስፈራራት ።

በመብት ፡ ማስፈራራት ፡ ውሉን ፡ ማፍረሻ ፡ የሚሆነው ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አገልግሎ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

ቍ፡ ሺ፯፻፱ ። በአክብሮት ፡ ስለሚደረግ፡ ውለታ ።

(፩) ሳይገደድ ፡ ወላጅን ፡ ወይም ፡ የበላይን ፡ በማክበር ፡ ብቻ ፡ በሆነ ፡ ሥጋት ፡ የተፈጸመ ፡ ጕዳይ ፡ ውልን ፡ ለማፍረስ ፡ በቂ ፡ አይደለም ።

(፪) ቢሆንም ፤ ውሉን ፡ ያደረገው ፡ ከሚፈራውና ፡ ከሚያከብረው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ይኸውም ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ውል ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጥቅም ፡ አግኝቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ የሚፈርስ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፲ ። ስለ ፡ መጐዳት ።

(፩) ላንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

(፪) ቢሆንም ፡ የተጎጂው ፡ ፈቃድ ፡ የተገኘው ፤ ችግሩን ፡ የመንፈስ ፡ ቀላልነቱን ፡ መጃጃቱን ፡ በዕድሜ ፡ መግፋቱን ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የልማድ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመደገፍ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በሕሊናም ፡ ግፍ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ውለታው ፡ ጕዳይ ።

### ቍ ፡ ፲፯፻፲፩ ። የውል ፡ ጕዳይ ፡ አወሳሰን ።

ሕግ ፡ ከወሰናቸውና ፡ ከከለከላቸው ፡ ነገሮች ፡ በቀር ፡ ተዋዋዮች ፡ ሁሉ ፡ የሚዋዋሉበትን ፡ ጕዳይ ፡ እንደ ፡ መሰላቸው ፡ የመወሰን ፡ መብት ፡ አላቸው ።

### ቍ ፡ ፲፯፻፲፪ ። የመስጠት ፡ የማድረግ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ለሚዋዋሉት ፡ ሰው ፤ በአንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ስላለማድረግ ፡ ሊዋዋሉ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እናደርግልሃለን ፡ በማለት ፡ በተዋዋሉ ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የተወሰነ ፡ አድራጎት ፡ ለመፈጸም ፡ ሊዋዋሉና ፡ ወይም ፡ የሚዋዋሉት ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ እንዲያገኝ ፡ የተቻላቸውን ፡ የሚያደርጉ ፡ መሆናቸውን ፡ ብቻ ፡ ሊዋዋሉ ፡ ይችላሉ ።

### ቍ ፡ ፲፯፻፲፫ ። ለውለታው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ።

ውሎች ፡ አስገዳጅነታቸው ፡ በውሉ ፡ በተነገረው ፡ ጕዳይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ልማድ ፤ ፍትሕ ፤ ቅን ፡ ልቡና ፡ የውለታው ፡ ዐይነት ፡ የሚያስከትሉዋቸውን ፡ ነገሮች ፡ ጭምር ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፲፯፻፲፬ ። በማይበቃ ፡ አወሳሰን ፡ የተመለከተ ፡ የውል ፡ ጕዳይ ።

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወይም ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የገቡት ፡ ግዴታዎች ፡ በትክክልና ፡ በሚበቃ ፡ ሁኔታ ፡ ካልተገለጹ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) ውል ፡ መተርጐምን ፡ ሰበብ ፡ በማድረግ ፡ ለተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ዳኞች ፡ ሊፈጥሩ ፡ አይችሉም ።

### ቍ ፡ ፲፯፻፲፭ ። የሚዋዋሉበት ፡ ጕዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የውል ፡ ጕዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚቻል ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

(፪) ተዋዋዮቹ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ሊፈጸም ፡ በማይቻል ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የተዋዋሉበትም ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ የማይቻልና ፡ የማይሞከር ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፲፯፻፲፮ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ጕዳይ ።

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ የገቡበት ፡ ግዴታ ፡ ሕግን ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ለገባለት ፡ ግዴታ ፡ ሲል ፤ አንዱ ፡ ወገን ፡ የገባበት ፡ ግዴታ ፡ ለሕግ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፲፯። (ሀ) ምክንያት ። (፩) መሠረቱ ።

ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ የገባበት ፡ ምክንያት ፤ ውሉ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ መሆኑን ፡ ለማመዛዘን ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፲፰። (ለ)(፪) የተጠበቀ ፡ ሁኔታ።

ስለ ፡ ሆነም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ የቀረበላቸውን ፡ ጥያቄ ፡ አንቀበልም ፡ ለማለት ፡ ይችላሉ ።

(ሀ) ተዋዋዮቹ ፡ ወይም ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ የሚፈልጉት ፡ የውል ፡ ዓላማ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ ያልሆነ ፡ መሆኑ ፡ ከውሉ ፡ ቃል ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህ ፡ ዓላማ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ ከሚጠይቀው ፡ ተዋዋይ ፡ ጽሑፍ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ውል ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ።

ቍ ፡ ፲፯፻፲፱። ስለ ፡ ውል ፡ አጻጻፍ ፡ ነጻነት።

(፩) በጠቅላላው ፡ ሥርዐት ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፪) ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ የሚያስገድድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የሚጠበቅ ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) እንዲሁም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የውላቸውን ፡ አፈጻጸም ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ አጻጻፍ ፡ ሥርዐት ፡ ሊወስኑት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳። ስለ ፡ ውል ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ የተሰጠ ፡ ደንብ ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያስከትለው።

(፩) ሕግ ፡ የተለየ ፡ ጽሑፍ ፡ (ፎርም) ፡ እንዲኖር ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አኳኋን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ረቂቅ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

(፪) እንደ ፡ ቴምብር ፡ መክፈል ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ መመዝገብ ፡ ግዴታ ፡ ያሉት ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰኑት ፡ የቀረጥና ፡ የግብር ፡ ድንጋጌዎች ፡ አለመፈጸም ፡ ውሉን ፡ ፈራሽ ፡ አያደርገውም ።

(፫) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰኑ ፡ የማስታወቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አለመፈጸም ፡ ውሉን ፡ ፈራሽ ፡ አያደርገውም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፳፩። ተቀዳሚ ፡ ውሎች ።

ተቀዳሚ ፡ ውሎች ፡ ለመጨረሻ ፡ ውል ፡ በተወሰነው ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ ዐይነት ፡ መሠራት ፡ አለባቸው ።

**ቊ ፣ ፲፯፻፳፪ ። ውልን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።**

ዋናውን ፡ ውል ፡ የመለወጥ ፡ ጕዳይ ፡ ለዚሁ ፡ ውል ፡ በተደነገገው ፡ አጻጻፍ። (ፎርም) ፡ መሠራት ፡ አለበት ።

**ቊ ፣ ፲፯፻፳፫ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ።**

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ባለቤትነት ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የመያዣ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ አገልግሎት ፡ መብት ፡ ለማቋቋም ፤ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚደረጉት ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ በጽሑፍና ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ውል ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ፊት ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሚመለከቱ ፡ የክፍያ ፡ ወይም ፡ የማዛወር ፡ ስምምነቶች ፡ ሁሉ ፡ በጽሑፍና ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ውል ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ፊት ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

**ቊ ፣ ፲፯፻፳፬ ። ካስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ።**

መንግሥት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የቆሙ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ግዴታ ፡ የሚዋዋሉባቸው ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ በጽሑፍና ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ባስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ውል ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ መሠራት ፡ አለባቸው ።

**ቊ ፣ ፲፯፻፳፭ ። ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የሚቈዩ ፡ ውሎች ።**

እንዲሁም ፡—

(ሀ) የዋስትና ፡ ውሎች ፡

(ለ) የኢንሹራንስ ፡ ውሎች ፡—

(ሐ) ይህ ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ በሕግ ፡ ያስፈልጋቸዋል ፡ የተባሉት ፡ ሌሎች ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፤ በጽሑፍ ፡ መሠራት ፡ አለባቸው ።

**ቊ ፣ ፲፯፻፳፮ ። በስምምነት ፡ ስለሚሆን ፡ ያጻጻፍ ፡ ዐይነት ፡ (ፎርም) ።**

ተዋዋዮቹ ፡ ለሚዋዋሉት ፡ ውል ፡ ሕግ ፡ የማያስገድደውን ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ (ፎርም) ፡ ለመፈጸም ፡ የተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስምሳሌ ፤ ሕግ ፡ ሳያስገድድ ፡ በጽሑፍ ፡ ለመዋዋል ፡ የተስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ውሉ ፡ ፍጹም ፡ የሚሆነው ፡ የተስማሙበትን ፡ የውላቸውን ፡ አፈጻጸም ፡ ሞልተው ፡ በተዋዋሉ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቊ ፣ ፲፯፻፳፯ ። የውል ፡ ጽሑፍ ፡ አኳኋን ፡ (ፎርም) ።**

(፩) ውል ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲደረግ ፡ ግዴታ ፡ ሲኖር ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ተገልጾ ፡ በውሉ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መፈረም ፡ አለባቸው ።

BACK



(፪) በሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ካልተረጋገጠ ፡ አይጸናም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፳፯። ፊርማ ።**

(፩) ፊርማ ፡ በውሉ ፡ ተገዳጅ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ መጻፍ ፡ ይገባዋል ።
(፪) ለመፈረም ፡ የማይችል ፡ ሰው ፡ በጽሕፈት ፡ ፊርማው ፡ ፋንታ ፡ የጣት ፡ ምልክት ፡ መተካት ፡ ይችላል ።
(፫) የዕውራን፡ ወይም ፡ የመሐይምናን፡ ፊርማ ፡ የጣት ፡ ምልክት ፡ ፊርማ ፡ የነሱ፡ ፊርማ ፡ መሆኑን ፡ ውል ፡ አዋዋይ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ጸሐፊ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ያረጋገጧቸው ፡ ካልሆነ ፡ አያስገድዳቸውም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፳፰ ። ምስክሮች ፡ (፩) ችሎታ ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ተዋዋዮች ፡ በተዋዋሉት ፡ ውል ፡ ምስክሮች ፡ እንዲኖሩ ፡ የተባለ ፡ ሲሆን ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ምስክሮቹ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሱና ፡ ያልተከለከሉ ፡ እንዲሆኑ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።
(፪) የሰዎቹ ፡ ጾታ ፡ ወይም ፡ ዜግነት ፡ ምስክር ፡ የመሆንን ፡ ችሎታ ፡ አያስቀርም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፳፱ ። (፪) የምስክሮቹ ፡ አግባብ ።**

(፩) የአንድ ፡ ውል ፡ ምስክሮች ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲመሰክሩ ፡ የሚፈለጉት ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ውሉን ፡ ተስማምተው ፡ የፈጸሙ ፡ መሆናቸውንና ፡ የውሉ ፡ ቃል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
(፪) ከተዋዋዮቹ ፡ ለአንዱ ፡ ዋስ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ገልጸው ፡ ውል ፡ የገቡ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ምስክሮቹ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ግዴታቸውን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ የዋስትና ፡ አላፊነት ፡ የለባቸውም ።

## ምዕራፍ ፪ ።

## የውሎች ፡ ውጤት ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፴፩ ። መሠረቱ ።**

(፩) በሕጉ ፡ አግባብ ፡ የተቋቋሙ ፡ ውሎች ፡ ባቋቋሟቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ ናቸው ።
(፪) በውል ፡ የማይለወጡና ፡ አዛዥ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ቃሎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የተስማሙበት ፡ ነው ።
(፫) ተዋዋዮቹ ፡ እንዳይፈጸምባቸው ፡ በማድረግ ፡ ያስቀሯቸው ፡ ባልሆነበት ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ በውል ፡ እንዳይለወጥ ፡ የሚያዝ ፡ ሕግ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ውል ፡ ትርጉም ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፴፪ ። በቅን ፡ ልቡና ፡ ውሎችን ፡ ስለ ፡ መተርጐም ።**

በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ ሊኖር ፡ የሚገባውን ፡ የቅንነትንና ፡ የመተማመንን ፡ ግንኙነት ፡ መሠረት ፡ በማድረግና ፡ በጕዳዮቹ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዐት ፡ በመከተል ፡ ውሎች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ሊተረጐሙ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፴፫ ። የትርጕሙ ፡ ወሰን ።**

ውለታዎች ፡ ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ከሚሰማው ፡ በመራቅ ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ፈቃድ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዳኞች ፡ ለመተርጐም ፡ አይችሉም ።

**ቍ. ሺ፯፻፴፬ ። የተዋዋዮቹ ፡ ሐሳብ ፡ አንድነት ።**

(፩) የውሉ ፡ ቃል ፡ የሚያሻማ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ሐሳብ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለማወቅ ፡ መፈለግ ፡ ይገባል ።

(፪) ስለዚህም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ውላቸውን ፡ ከመዋዋላቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ወይም ፡ ከተዋዋሉ ፡ በኋላ ፡ የነበሩበትን ፡ ሁኔታ ፡ ማመዛዘን ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፴፭ ። ጠቅላላ ፡ አነጋገር ።**

በውሉ ፡ የተገለጠው ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ ጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ቢሆን ፡ ውሉ ፡ የሚጸናው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ሊዋዋሉበት ፡ የፈለጉ ፡ መስሎ ፡ በሚታየው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፴፮ ። የውል ፡ ቃሎችን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ስለ ፡ መተርጐም ።**

(፩) በውሉ ፡ መሠረት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የሚገባውን ፡ ትርጕም ፡ በመስጠት ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ በአንደኛው ፡ አነጋገር ፡ ይተረጐማሉ ።

(፪) ሁለት ፡ ፍቺ ፡ ለሚያሳዩት ፡ ውለታዎች ፡ ትር ፡ ም ፡ የሚሰጠው ፡ ለውሉ ፡ ጕዳይ ፡ ይበልጥ ፡ በሚስማማው ፡ አኳኋን ፡ [illegible] ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፴፯ ። ውጤት ፡ ያለው ፡ ትርጕም ።**

አንድ ፡ ስምምነት ፡ ሁለት ፡ ፍቺ ፡ የሚያመጣ ፡ ነ ሆን ፡ መቀበል ፡ የሚገባው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሊሰጥ ፡ ከማይችለው ፡ አኳኋን ፡ ይልቅ ፡ ተጨባጭ ፡ ውጤት ፡ ሊሰጥ ፡ በሚችለው ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፴፰ ። ለባለዕዳው ፡ ምቹ ፡ የሆነ ፡ ትርጕም ።**

(፩) የውሉ ፡ አኳኋን ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሲሆን ፡ የሚተረጐመው ፡ በውሉ ፡ አስገዳጅ ፡ የሆነው ፡ በሚጠቀምበት ፡ ሁኔታ ፡ ሳይሆን ፡ በውሉ ፡ ተገዳጅ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ምቹ ፡ በሚሆንበት ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፡ በጠቅላላው ፡ ስምምነት ፤ በውል ፡ ዐይነት ፤ ወይም ፡ ለውል ፡ ፎርም፡ ተመልክተው ፡ የሚገኙት ፡ ውለታዎች ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ብቻ ፡ የተሠሩ ፡ ሲሆኑ ፡ የሚተረጐሙት ፡ እንዲቀበልና ፡ እንዲፈቅድ ፡ ለተ ጠየቀው ፡ ለውል ፡ ተቀባዩ ፡ ጥቅም ፡ ምቹ ፡ በሚሆንበት ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፸፱ ። ያለ ፡ ዋጋ ፡ ስለሚደረግ ፡ ውል ።

ተዋዋይ ፡ የተቀበለው ፡ ግዴታ ፡ በቀላል ፡ አኳኋን ፡ የሚተረጐምለት ፡ የተቀበ ለው ፡ ውል ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ያልተደረገ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ውሎች ፡ አፈጻጸም ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፹ ። የውሉን ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ማን፡እንደ ፡ ሆነ ፡ስለ ፡ ማወቅ ።

(፩) ከውሉ ፡ ዐይነት ፡ የተነሣ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ጥቅም ፤ ግዴታውን ፡ ባለ ዕዳው ፡ እንዲፈጽመው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ እን ዲደረግ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ እንዳለ ፤ ባለዕዳው ፡ የዚህን ፡ ግዴታ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) በሌላው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ግዴታውን ፡ እንዲፈጽምለት፡ ከባለዕዳው ፡ ሥልጣን ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ባለዕዳው ፡ ሆኖ ፡ ግዴታዎችን ፡ እንዲፈጽም ፡ በፍ ርድ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የተባለውን ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፹፩ ። የገንዘቡ ፡ መከፈል ፡ ለማን ፡ እንደሚገባው ።

የሚከፈለው ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ከባለገንዘቡ ፡ ሥልጣን ፡ ለተቀበለ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀበልለት ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ለተፈቀደ ለት ፡ ሰው ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፹፪ ። ስለ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።

ባለገንዘቡ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመቀበል ፡ ችሎታ ፡ ያልነበረው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ባለዕ ዳው ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፤ ለባለገንዘቡ ፡ ጥቅም ፡ መዋሉን ፡ ካላስረዳ ፡ የባለዕዳው ፡ መከፈል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፯፻፹፫ ። የመቀበል ፡ መብት ፤ ለሌለው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መከፈል ።

(፩) ስለ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ሆኖ ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ለሌለው ፡ ሰው ፡ የተደረገ ፡ አከፋፈል ፡ የሚጸናው ፡ ባለገንዘቡ ፡ አከፋፈሉን ፡ ሲያጸድቀው ፡ ወይም ፡ የመ ከፈሉ ፡ ጥቅም ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የዋለ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ ባለገንዘቡን ፡ መስሎ ፡ ለተገኘ ፡ ሰው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ መክፈል ፡ የሚጸና ፡ አከፋፈል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፶፬ ። ባለገንዘቡ ፡ መሆኑ ፡ አጠራጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ።

(፩) ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባጠራጠረ ፡ ጊዜ ፡ ባለ ዕዳው ፡ ለጠያቂው ፡ አልከፍልም ፡ በማለት ፡ የሚከፈለውን ፡ ሀብት ፡ ለፍ ርድ ፡ ቤት ፡ በማስረከብ ፡ ከዕዳው ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

(፪) ያለውን ፡ ክርክር ፡ እያወቀ ፡ ባለገንዘቦች ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ከሚሉት ፡ እርግጠኞች ፡ ካልሆኑ ፡ ላንደኛው ፡ ቢከፍል ፡ ግን ፡ አላፊነቱ ፡ የራሱ ፡ ነው ።

(፫) የተጀመረ ፡ ሙግት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ገንዘቡም ፡ ሊጠየቅ ፡ የሚገባው ፡ ከሆነ ፤ ባለገንዘቦች ፡ ነን ፡ ከሚሉት ፡ አንደኛው ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ልክ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲያስረክብ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፶፭ ። የዕቃው ፡ ዐይነት ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

ባለገንዘቡ ፡ ሊሰጠው ፡ ከሚገባው ፡ ዕቃ ፡ በቀር ፡ የቀረበለትን ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ ከሚቀበለው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ወይም ፡ የበለጠ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ያንኑ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንዲቀበል ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፶፮ ። በከፊል ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ዕዳው ፡ በሙሉና ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በከ ፊል ፡ መከፈልን ፡ እንቢ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) አንድ ፡ ዕዳ ፡ በከፊል ፡ ክርክር ፡ በተነሣበት ፡ ጊዜ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ባለዕዳው ፡ ያመነለትን ፡ ከዕዳው ፡ በከፊል ፡ መቀበልን ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለዕዳው ፡ ይህንኑ ፡ ያመነውን ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፶፯ ። በዕዳው ፡ ዐይነት ፡ መገደድ ፡ (፩) ተገቢውን ፡ ዐይነት ፡ መክፈል ።

(፩) ዕዳው ፡ ከራሱ ፡ ተፈጥሮ ፡ ዐይነት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መጠሪያ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ተቃራኒ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የመመለሱ ፡ ምርጫ ፡ የሚሰጠው ፡ ለባለዕ ዳው ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፡ ባለዕዳው ፡ ተመሳሳይ ፡ ከሆነው ፡ ከመጠነኛው ፡ ዐይነት ፡ ዝቅ ተኛ ፡ የሆነውን ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፶፰ ። (፪) በቂ ፡ ያልሆነ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ብዛት ።

(፩) ግዴታው ፡ የሚመለከተው ፡ የዕቃውን ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥቅም ፡ ከሌ ለው ፡ ወይም ፡ ይኸው ፡ መብት ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ካልተዋዋለ ፡ በቀር ፡ ባለ ገንዘቡ ፡ የዕቃው ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ ዐይነቱ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከ ተው ፡ በፍጹም ፡ ትክክለኛ ፡ ተመሳሳይ ፡ ዐይነት ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ሊከ ፈለው ፡ የቀረበለትን ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፪) የተሰጠው ፡ ነገር ፡ በትክክል ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ተመሳሳይ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የራሱን ፡ ፋንታ ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ( በሒሳቡ ፡ ) ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ይህንኑ ፡ ግዴታውን ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ፡ ፲፯፻፵፱ ። የገንዘብ ፡ ዕዳ ።**

(፩) ገንዘብን ፡ የሚመለከት ፡ ዕዳ ፡ ሲሆን ፡ ዕዳው ፡ የሚከፈለው ፡ በአገሩ ፡ መገበያያ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

(፪) ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባው ፡ የገንዘብ ፡ ሒሳብ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፡ የሚችለው ፡ የዋነኛ ፡ ጠባያቱን ፡ ዋጋዎች ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ያገልግሎት ፡ ዋጋ ፤ ወይም ፡ ዋጋው ፡ ሊወሰን ፡ የሚችል ፡ የማንኛውንም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

**ቍ፡ ፲፯፻፶ ። ሕጋዊ ፡ መገበያያ ፡ ያልሆነ ፡ ገንዘብ ።**

ዕዳው ፡ በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፤ ውሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ እውነተኛ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ ከሌለበት ፡ በቀር ፡ ዕዳው ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ በአገሩ ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፈል ፡ ይቻላል ።

**ቍ፡ ፲፯፻፶፩ ። ሕጋዊ ፡ ወለድ ።**

በውል ፡ ያልተወሰነ ፡ ወለድ ፡ (ጥቅም) ፡ ከፋይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በዓመት ፡ በመቶ ፡ ዘጠኝ ፡ ሒሳብ ፡ ይከፍላል ።

**ቍ፡ ፲፯፻፶፪ ። ስለ ፡ ተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ አቀናነስ ። (፩) ወጪ ። ገንዘብ ፤ ወለድ ፤ ዋና ፡ ገንዘብ ።**

አንድ ፡ ተበዳሪ ፡ ከዋናው ፡ ዕዳ ፡ በቀር ፡ ወጪና ፡ ወለድ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚገባው ፡ ሲሆን ፡ በከፊል ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚቀነሰው ፡ መጀመሪያ ፡ ከወጪ ፡ ገንዘቡ ፤ ቀጥሎ ፡ ከወለዱ ፤ በመጨረሻ ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

**ቍ፡ ፲፯፻፶፫ ። (፪) በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የሚደረግ ፡ ምርጫ ።**

(፩) ለአንዱ ፡ ባለሀብት ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ የሚከፍል ፡ ባለዕዳ ፡ ዕዳውን ፡ በሚከፍልበት ፡ ጊዜ ፡ ከዕዳዎቹ ፡ ውስጥ ፡ የትኛውን ፡ አስቀድሞ ፡ ለመክፈል ፡ እንደሚፈልግ ፡ የመግለጽ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የትኛውን ፡ አስቀድሞ ፡ ለመክፈል ፡ መግለጫ ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለዕዳው ፡ ወዲያውኑ ፡ ያልተቃወመ ፡ ሲሆን ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለየትኛው ፡ ዕዳ ፡ ደረሰኝ ፡ ለመስጠት ፡ እንደሚፈቅድ ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

**ቍ፡ ፲፯፻፶፬ ። (፫) ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ አቀናነስ ።**

(፩) በደረሰኙ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ያልተመለከተበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ከዕዳው ፡ የሚቀነሰው ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ከደረሰው ፡ ዕዳ ፡ ላይ ፡ ነው ። ወይም ፡ የመክፈያው ፡ ቀን ፡ ያልደረሰ ፡ ዕዳ ፡ እንዳለ ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ የተቃረበ ፡ ከሆነው ፡ ዕዳ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ባለፈበት ፡ ዕዳ ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ ጊዜው ፡ ለማለፍ ፡ በተቃረበ ፡ ዕዳ ፡ መካከል ፡ ክፍያው ፡ የሚታሰበው ፡ ባለዕዳው ፡ አስቀድሞ ፡ ለመክፈል ፡ ይበልጥ ፡ ከሚጠቅመው ፡ ዕዳ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፫) ዕዳዎቹ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንደ የመጠናቸው ፡ ይቀነሳል ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፶፭ ። የመክፈያ ፡ ስፍራ ።

(፩) ክፍያው ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

(፪) የመክፈያው ፡ ስፍራ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ያልተመለከተ ፡ ሲሆን ፤ ክፍያው ፡ የሚፈጸመው ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ባለዕዳው ፡ ይገኝበት ፡ በነበረው ፡ በመደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ነው ።

(፫) ቢሆንም ፡ የሚከፈለው ፡ ነገር ፡ የተረጋገጠ ፡ ግዙፍነት ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ አካል ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፤ በውሉ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ነገር ፡ ካልተመለከተበት ፡ በቀር ፡ ክፍያው ፡ የሚፈጸመው ፡ ውሉ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ በጕዳዩ ፡ የተመለከተው ፡ ዕቃ ፡ ይገኝ ፡ በነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፶፮ ፡ የመክፈያ ፡ ዘመን ።

(፩) ክፍያው ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዘመን ፡ ነው ።

(፪) የመክፈያው ፡ ዘመን ፡ ያልተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክፍያው ፡ ወዲያውኑ ፡ መፈጸም ፡ ይችላል ።

(፫) ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ እንዳስገደደው ፡ ክፍያው ፡ ወዲያውኑ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፶፯ ። ተዋዋዮቹ ፡ ባንድነት ፡ ስለሚፈጽሙት ፡ ግዴታ ።

ተዋዋዩ ፡ የተዋዋለበትን ፡ ግዴታ ፡ በውሉ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ እንዲፈጽምለት ፡ የሚጠይቀው ፡ ወገን ፡ ከውሉ ፡ ስምምነት ፡ የተነሣ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ እሱም ፡ በበኩሉ ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ፡ ወዲያውኑ ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ ለመፈጸም ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ ይገባዋል ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፶፰ ። የጉዳት ፡ አላፊነትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) አንድ ፡ ዕቃ ፡ የማስረከብ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ባለዕዳ ፡ በውላቸው ፡ መሠረት ፡ ለተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ከአስረከበበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰውን ፡ የመበላሸትን ፡ ወይም ፡ የመጥፋትን ፡ ጉዳት ፡ የሚችለው ፡ እሱ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ዕቃውን ፡ እንዲረከብ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከተደረገለት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ የሚደርሰውን ፡ ጉዳት ፡ የሚችለው ፡ ተዋዋዩ ፡ ነው ።

(፫) አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ በአንድ ፡ ውል ፡ ያለበትን ፡ ግዴታውን ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ በማያሻማ ፡ አኳኋን ፡ ውሉን ፡ አልፈጽምም ፡ ብሎ ፡ ያስታወቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይኸው ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡

ሁኗል ፡ ብሎ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተዋዋዩም ፡ በበኩሉ ፡ ግዴታውን ፡ አልፈጽምም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ሺ፯፻፶፱ ። የዚህ ፡ መብት ፡ ወሰን ።

አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆኑን ፡ በማረጋገጥ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ዋስትና ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ አሳብ ፡ ውሉ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ሺ፯፻፷ ። ስለ ፡ አከፋፈሉ ፡ የሚሆን ፡ ወጪ ።

ስለ ፡ ዕዳው ፡ አከፋፈል ፡ የሚደረገው ፡ ሌላ ፡ ወጪ ፡ የሚታሰበው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ሺ፯፻፷፩ ። ደረሰኝ ።

(፩) ዕዳውን ፡ የሚከፍል ፡ ባለዕዳ ፡ ስለ ፡ መክፈሉ ፡ የደረሰኝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ዕዳውም ፡ በሙሉ ፡ ተከፍሎ ፡ እንደሆን ፡ የውሉ ፡ ሰነድ ፡ እንዲመለስለት ፡ ወይም ፡ እንዲሰረዝለት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ክፍያው ፡ በሙሉ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የውሉ ፡ ሰነድ ፡ ለባለ ሀብቱ ፡ ሌላ ፡ መብት ፡ የሚያስገኝለት ፡ ሲሆን ፡ ባለዕዳው ፡ አንድ ፡ ደረሰኝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ወይም ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ እንዲጻፍለት ፡ የማስገደድ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቊ ፡ ሺ፯፻፷፪ ። ስለ ፡ ሰነድ ፡ ማጥፋት ።

ባለገንዘቡ ፡ ሰነዱ ፡ ጠፍቶብኛል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰነዱ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ስለ ፡ መሆኑና ፡ ዕዳውም ፡ ያለቀለት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሰጠው ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ክፍል ፡ ፫ ።

ስለ ፡ ውል ፡ መሻሻል ።

ቊ ፡ ሺ፯፻፷፫ ። ውሎች ፡ በዳኞች ፡ የማይሻሻሉ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ የተመለከተ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዳኞች ፡ ርትዕን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ውሉን ፡ ለማሻሻልም ፡ ሆነ ፡ ለመለወጥ ፡ አይችሉም ።

ቊ ፡ ሺ፯፻፷፬ ። የውሉ ፡ ሚዛናዊነት ፡ ስለ ፡ መቅረቱ ።

(፩) የአፈጻጸሙ ፡ ሁኔታ ፡ ቢለወጥና ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የገባበት ፡ ግዴታ ፡ አስቦት ፡ ከነበረው ፡ የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ቢሆንበትም ፡ እንኳ ፡ ውሉ ፡ እንዳለ ፡ ጸንቶ ፡ ይቈያል ።

(፪) በመሠረታዊው ፡ ስምምነታቸው ፡ ወይም ፡ በአዲስ ፡ ስምምነት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ የሚያስከትለውን ፡ ሁኔታ ፡ የማሻሻሉ ፡ ጒዳይ ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዳኞች ፡ ሥልጣን ፡ አይደለም ።

<u>ቍ፡፲፯፻፷፫፡፡የዘመድ፡ ዳኛ፡ ስለ ፡ መምረጥ ፡፡</u>

የውሉ ፡ ስምምነት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ የውሉን ፡ የዋጋ ፡ ሆኔታ ፡ የለወጠውን ፡ ነገር ፡ በስምምነት ፡ ለማሻሻል ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ለመፈለግ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ነገራቸውን ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ እንዲቀርብ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ፡፡

<u>ቍ፡፲፯፻፷፬፡፡በተዋዋዮቹ፡ ወገኖች፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ልዩ ፡ የመተማመን ፡ ግንኙነት ፡፡</u>

በተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ የታጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ በሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ የተሳሰረ ፡ ግንኙነት ፡ ወይም ፡ በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ የመተማመን ፡ ልዩ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለተዋዋያቸው ፡ በተለይ ፡ በርትዕ ፡ አስተያየት ፡ እንዲያደርጉለት ፡ በሚገደዱበት ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ውሉን ፡ ለማሻሻል ፡ ይችላሉ ፡፡

<u>ቍ፡፲፯፻፷፭፡፡ ከመንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ጋራ፡ ስለሚደረግ ፡ ውል ፡፡</u>

(፩) ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ ሊሻሻሉ ፡ የሚችሉት ፤ የውሉ ፡ ስምምነቶች ፡ የተፈጸሙበት ፡ የዋነኛው ፡ ስምምነት ፡ ሁኔታ ፡ በሕዝባዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተለወጠ ፡ሲሆንና ፡ ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ የከበደ ፡ የገንዘብ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣበት ፡ ወይም ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡፡

(፪) ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ስለ ፡ ተፈጸሙ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ፡፡

<u>ቍ፡፲፯፻፷፮፡፡ እንደ፡ ውሉ፡ ለመፈጸም፡ በከፊል ፡ የሚያጋጥም ፡ ችግር ፡፡</u>

ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ በከፊሉ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆንበትና ፡ ቢሆንም ፡ የውሉ ፡ ስምምነት ፡ ውሳኔ ፡ እንዲቀር ፡ ለመፍረድ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ሳይታይ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የሚፈጸመውን ፡ ግዴታ ፡ ለመቀነስ ፡ ይችላሉ ፡፡

<u>ቍ፡፲፯፻፷፯፡፡ የውሉ፡ ሚዛናዊነት፡፡</u>

ከላይ ፡ የተመለከቱት ፡ የሁለቱ ፡ ቍጥሮች ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጡ ፡ የውሉ ፡ ሚዛናዊነት ፡ አፈጻጸም ፡ እንዳይጓደል ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ፡፡

<u>ቍ፡፲፯፻፷፰፡፡ስለ፡ችሮታ፡የሚሰጥ፡ጊዜ ፡፡</u>

(፩) ዳኞች ፡ የባለዕዳውን ፡ ሁኔታና ፡ የነገሩን ፡ አግባብ ፡ በመረዳት ፡ (በመመልከት) ፡ ይህንንም ፡ ሥልጣናቸውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲያውሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ በማድረግ ፡ ለባለዕዳው ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸሚያ ፡ አስፈላጊ ፡ ጊዜ ፡ የሚያሻው ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ የችሮታ ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ፡፡

BACK



(፪) ይህም ፡ ጊዜ ፡ በማንኛቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ከስድስት ፡ ወር፡ የበለጠ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፫) ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ዳኞች ፡ የምሕረት ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጡ ፡ አይችሉም፡ የሚል፡ ቃል ፡ በውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ሊያገቡ ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ውልን ፡ ስላለመፈጸም ።

**ቍ፡ ፲፯፻፸፩።የውል ፡ አለመፈጸም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ነገር ።**

(፩) ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ነገሩ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ውሉን ፡ እንዲፈጽምለት ፡ ሊጠይቅ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ ባይሆን ፡ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ ራሱ ፡ ሊጠይቅ ፡ ወይም ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል ።

(፪) በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ጉዳይ ፤ ጉዳት ፡ ስላደረሰበት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፸፪።የማስጠንቀቅ ፡ አስፈላጊነት ።**

እንደ ፡ ውሉ ፡ ሳይፈጸምልኝ ፡ ቀርቷል ፡ በማለት ፡ ክርክር ፡ ለማቅረብ ፡ የሚፈልገው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፤ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ግዴታውን ፡ እንዲፈጽምለት፡ ለማድረግ፡ አስቀድሞ፡ ማስጠንቀቂያ፡ ሊሰጠው ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ፡ ፲፯፻፸፫።ማስጠንቀቂያ፡ የሚደረግበት፡ ሥርዐትና፡ ( ፎርም ) ፡ ዘመን ።**

(፩) የማስጠንቀቂያ ፡ መስጠት ፡ ጉዳይ ፡ የሚደረገው ፡ ይህን ፡ እንድትፈጽም ፡ የሚል፡ እንደ፡ መጨረሻ፡ ትእዛዝ፡ በሆነ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አድራጎት ፡ የባለገንዘቡን ፡ አሳብ ፡ መግለጫ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የሚቀርብ ፡ የውሉን ፡ ፍጻሜ ፡ ለማግኘት ፡ የሚደረግ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

(፪) ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ግዴታው ፡ ተጠያቂ ፡ ከሆነበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

**ቍ፡ ፲፯፻፸፬። ጊዜ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) ባለ ፡ ገንዘቡ ፡ ለባዕዳው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሲሰጥ ፡ ለግዴታው ፡ መፈጸሚያ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ፡ ሊወስንለት፡ ይችላል ፤ ይህ ፡ የተወሰነው፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ውሉ ፡ በዐይነታው ፡ እንዲፈጸም ፡ የማይቀበለው፡ መሆኑን ፡ ያስታውቃል ።

(፪) ይህ ፡ ጊዜ ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ በጉዳዩ ፡ ዐይነትና ፡ በአካባቢው ፡ ሁኔታ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ መጠን ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፲፯፻፸፭ ። ማስጠንቀቂያ ፡ መስጠት ፡ ጠቃሚ ፡ የማይሆንበት ፡ ጕዳይ ።**

ማስጠንቀቂያ ፡ መስጠት ፡ ጠቃሚ ፡ የማይሆነው ፤

(ሀ) ያለ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፤

(ለ) ባለዕዳው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ የሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህ ፡ የተወሰነው ፡ የግዴታ ፡ መፈጸሚያ ፡ ዘመን ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ባለዕዳው ፡ ግዴታውን ፡ የማይፈጽም ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ በጽሑፍ ፡ ያስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ተግባር ፡ ሳያስፈልግ ፡ በውሉ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እንዳለፈ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለባለዕዳው ፡ የመጨረሻ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ይቈጠራል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ተመልክቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፲፯፻፸፮ ። ውልን ፡ በግድ ፡ ስለ ፡ ማስፈጸም ።**

(፩) ውሉ ፡ በግዴታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሊታዘዝ ፡ የሚቻለው ፤ እንደ ፡ ውሉ ፡ ይፈጸምልኝ ፡ ብሎ ፡ ለሚጠይቀው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ የተለየ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጠው ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ አፈጻጸሙም ፡ በባለዕዳው ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ መስናከል ፡ ሳያደርስበት ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፲፯፻፸፯ ። የማድረግና ፡ ያለ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ባለዕዳው ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ የማድረግ ፡ ግዴታ ፤ ባለገንዘቡ ፡ በባለዕዳው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ባለዕዳው ፡ በውል ፡ ተገድዶበት ፡ የነበረውን ፡ ያለማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ተላልፎ ፡ የሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በባለዕዳው ፡ ኪሣራ ፡ ሊያፈርስ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ሊያስፈርስ ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፲፯፻፸፰ ። ዐይነቱ ፡ በታወቀ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መዋዋል ።**

በውሉ ፡ የተገባው ፡ ግዴታ ፡ ዐይነቱ ፡ በታወቀ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ወገን ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲያስረክበው ፡ የተገደደበትን ፡ ዐይነቱ ፡ የታወቀውን ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ችግርና ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ወጪ ፡ ለማድረግ ፡ ሳይገደድ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ ውሉ ፡ በግዴታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፲፯፻፸፱ ። የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ አልቀበልም ፡ ስለ ፡ ማለት ።**

ባለገንዘቡ ፡ ሊመለስለት ፡ የቀረበለትን ፡ ነገር ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለዕዳው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በባለገንዘቡ ፡ ኪሣራ ፡ ሕዝባዊ ፡ በሆነ ፡ የዕቃ ፡ ማስቀመጫ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሣጥን ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ ሊከፈልበት ፡ ይገባው ፡ በነበረበትና ፡ ዳኞች ፡ ባዘዙበት ፡ በማንኛውም ፡ ስፍራ ፡ ለማስረከብ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፣ ፩ሺ፯፻፹ ። ተገቢውን ፣ ነገር ፣ ለማድረግ ፣ ስላለመቻል ።

ባለገንዘቡ ፣ ማን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ለማወቅ ፣ ያልተቻለ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ ራሱ ፣ ስለ ፣ መሆኑ ፣ የሚያጠራጥር ፣ ሲሆን ፤ ወይም ፣ በባለገንዘቡ ፣ የግል ፣ ጕዳይ፣ ምክንያት ፣ ለባለገንዘቡ ፣ ተገቢ ፣ የሆነው ፣ ነገር ፣ ሊቀርብ ፣ ( ሊሰጥ ) ፣ የማይ ቻል ፣ ሲሆንም ፣ እንደዚሁ ፤ ለባለዕዳው ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ የተመለከተው ፣ መብት ፣ አለው ።

ቍ ፣ ፩ሺ፯፻፹፩ ። ዕቃውን ፣ ስለ ፣ መሸጥ ።

(፩) የተዋዋሉበት ፣ ነገር ፣ ዕቃ ፣ ለመበላሸት ፣ የሚችል ፣ ይበላሻል ፣ ተብሎ ፣ የሚያሠጋ ፣ ሲሆን ፣ ወይም ፣ ከራሱ ፣ ዋጋ ፣ ያልተመዛዘነ ፣ የጥበቃ ፣ ወይም፣ የማስቀመጫ ፣ ዋጋ ፣ የሚጠይቅ ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ባለዕዳው ፣ ፍርድ ፣ ቤትን ፣ አስፈቅዶ ፣ ይህን ፣ ዕቃ ፣ በሐራጅ ፣ ሊሸጠው ፣ ይችላል ።

(፪) እንደዚሁም ፣ ዕቃው ፣ በዕለት ፣ ገበያ ፣ ተወስኖ ፣ የታወቀ ፣ ዋጋ ፣ ያለው ፣ ሲሆን፣ ወይም ፣ በነዋሪ ፣ ዋጋ ፣ ተወስኖ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፤ ወይም ፣ ደግሞ ፣ በሐ ራጅ፣ ለመሸጥ፣ ከሚጠየቀው፣ ዋጋ ፣ የሚበልጥ ፣ ተመዛዛኝ ፣ ያልሆነ ፣ ወጪ፣ የሚያስፈልገው ፣ ዝቅተኛ ፣ ዋጋ ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ባለዕዳው ፣ የፍርድ ፣ ቤትን፣ፈቃድ ፣ ጠይቆ ፣ ዕቃውን ፣ አስማምቶ ፣ ለመሸጥ ፣ ይችላል ።

(፫) እንዲህም፣ ሲሆን ፣ የዕቃውን ፣ ሽያጭ ፣ ዋጋ ፣ ለመንግሥት ፣ መሥሪያ ፣ ቤት፣ ማጥን ፣ ማስረከብ ፣ ይገባዋል ።

ቍ ፣ ፩ሺ፯፻፹፪ ። ማስረከብ ፣ የሚጸናበት ።

ያስረከበው ፣ ዕቃ ፣ ወይም ፣ ዋጋ ፣ ትክክለኛ ፣ መሆኑ ፣ በዳኞች ፣ ከተረጋገጠለ ትና ፣ ባለዕዳውም ፣ ይህንኑ ፣ በደንብ ፣ ካስረከበ ፣ ከግዴታ ፣ ነጻ ፣ ይሆናል ።

ቍ ፣ ፩ሺ፯፻፹፫ ። ያስረከበውን ፣ ዕቃ ፣ መልሶ ፣ ስለ ፣ መውሰድ ።

(፩) ያስረከበውን፣ ነገር፣ ተገቢ፣ ባለዋጋ ፣ መሆኑ ፣ ከታወቀለት ፣ በኋላም ፣ ቢሆን፣ ይህን ፣ ያስረከበውን ፣ ነገር ፣ ባለገንዘቡ ፣ የሚቀበለው ፣ መሆኑን ፣ ካላስታ ወቀ ፣ ባለዕዳው፣ አስረክቦት፣ የነበረውን ፣ ነገር ፣ ወይም ፣ ዋጋውን ፣ መልሶ፣ ሊወስድ ፣ ይችላል ።

(፪) ይህ ፣ በሆነ ፣ ጊዜ ፣ ዕዳው ፣ እንደ ፣ ገና ፣ በባለዕዳው ፣ ላይ ፣ ይመለስበታል ።

(፫) ባለዕዳው ፣ አስረክቦት ፣ የነበረው ፣ ነገር ፣ ወይም ፣ ዋጋው ፣ ትክክል ፣ መሆኑ፣ በዳኞች ፣ ከታወቀ ፣ በኋላ ፤ ቀድሞ ፣ በዋስትና ፣ አላፊነት ፣ ውስጥ ፣ ገብ ተው ፣ የነበሩትን ፣ ዋሶች ፣ አላፊነት ፣ እንደ ፣ ገና ፣ አያገኛቸውም ።

ቍ ፣ ፩ሺ፯፻፹፬ ። ውሉን ፣ በፍርድ ፣ ስለ ፣ መሰረዝ ።

በተወሰነው ፣ ጊዜ ፣ ግዴታዎቹን ፣ ያልፈጸመ ፣ እንደ ፣ ሆነና ፣ ወይም ፣ የፈጸ ማቸው ፣ ሙሉ ፣ ወይም ፣ ፍጹም ፣ ባልሆነ ፣ አኳኋን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ዳኞቹ ፣ በአን ደኛው ፣ ወገን ፣ ጠያቂነት ፣ ውሉን ፣ ሊያስቀሩት ፣ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ሺ፯፻፸፭ ። ቅን ፡ ልቡና ።</u>

(፩) ዳኞቹ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የተዋዋዮችን ፡ ጥቅምና ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ መሠረት ፡ ማድረግ ፡ ይገባቸዋል ።

(፪) በውሉ ፡ ላይ ፡ ዐይነተኛ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ መጣስ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ዳኞች ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ አይበይኑም ።

(፫) እንዲሁም ፡ የውሉ ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ ካልተነኩና ፡ በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ ጠያቂው ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ነገር ፡ ይሆናል ፡ ቢል ፡ ኖሮ ፡ ተዋዋዩ ፡ ካለመፈጸሙ ፡ የተነሣ ፡ ውሉ ፡ በሚገኝበት ፡ ሁኔታ ፡ ውሉን ፡ የማይዋዋል ፡ መሆኑ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ ሊገለጽ ፡ የሚቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አፈጻጸሙ ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ሺ፯፻፸፮ ። በአንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ የሚደረግ ፡ የውል ፡ ማፍረስ ። (፩)</u>የውል ፡ <u>ማፍረሻ ፡ የሚሆኑ ፡ የውል ፡ ቃሎች ።</u>

በአንድ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ውልን ፡ የሚያፈርሱ ፡ የስምምነቶች ፡ ቃል ፡ ተገልጾ ፡ ከተጻፈበትና ፡ የዚሁም ፡ ስምምነት ፡ አፈጻጸም ፡ ጕዳይ ፡ ተሟልቶ ፡ ከተገኘ ፡ አንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ሲል ፡ ለመግለጽ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፯፻፸፯ ። (፪) ቍርጠኛ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ መፈጸሚያ ፡ ጊዜ ።</u>

በውሉ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ግዴታ ፡ መፈጸሚያ ፡ ሆኖ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ ይበቃል ፡ ተብሎ ፡ በተሰጠው ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በዳኛ ፡ በተሰጠው ፡ የችሮታ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከተዋዋዩ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ይፍረስልኝ ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ የማፍረስ ፡ መብት ፡ አለው ።

<u>ቍ ፡ ሺ፯፻፸፰ ። (፫) መፈጸም ፡ ስላለመቻል ።</u>

ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻለው ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ወይም ፡ የመፈጸሚያውን ፡ ጊዜ ፡ ካዘገየ ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የውሉ ፡ መሠረታዊ ፡ ስምምነት ፡ የተነካ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ያንደኛው ፡ ወገን ፡ የውል ፡ አፈጻጸም ፡ ግዴታ ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱም ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ውሉ ፡ ይፈጸምልኝ ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ፈረሰ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፯፻፸፱ ። (፬) መፈጸምን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ።</u>

(፩) እንዲሁም ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ውሉን ፡ የማይፈጽም ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ያስታወቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከላይ ፡ የተመለከተው ፡ የማፍረስ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህ ፡ ሲሆን ፡ አስቀድሞ ፡ አንደኛውን ፡ ወገን ፡ ከማስጠንቀቅ ፡ በፊት ፡ የው

ሉን ፡ መሻር ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ፤ ይህ ፡ መብት ፡ ተሠርቶ በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውሉ ፡ ተገዳጅ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከደ ረሰለት ፡ በኋላ ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ለመፈጸም ፡ ስለ ፡ መቻሉ፡ በቂ፡ ዋስትና፡ ያቀረበ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የውል ፡ ማፍረስ ፡ መብት፡ ይቀራል ።

(፫) አንደኛው፡ ወገን፡ ግዴታውን፡ የማይፈጽም ፡ መሆኑን ፡ በጽሑፍ ፡ ካስታወቀ፤ የማስጠንቀቂያ ፡ መስጠቱ ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺ ። ውልን ፡ ባለመፈጸም ፡ የተደረገ ፡ ጉዳት ።

(፩) ተዋዋዩ ፡ ግዴታውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ውሉን ፡ በግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ እንዲፈርስ ፡ ከማስደረጉም ፡ በቀር ፡ ከነዚሁ ፡ ማሻሻያዎች ፡ ጋራ ፡ አጣምሮ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ኪሣ ራውና ፡ ልኩ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡ በሚ ለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፩ ። ኪሣራ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ጥፋት ፡ ባያደርግ ፡ እንኳ ፡ ያለ በትን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ግዴታውን ፡ ባለ መፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ተዋዋይ ፡ የውል ፡ ግዴታውን ፡ ያልፈጸመበትን ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካላስረዳና፤ ይህም ፡ ምክንያት ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠለት ፤ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ከሚያመጣው ፡ አላፊነት ፡ ሊድን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፪ ። ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ።

(፩) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ሊመልሱት ፡ የማይቻል ፡ ኀይል ፡ ደርሷል ፡ የሚባ ለው ፡ አንድ ፡ ባለዕዳ ፡ ባላሰበው ፡ ነገር ፡ ድንገት ፡ ደራሽ ፡ ሆኖበት ፡ ግዴታ ውን ፡ እንዳይፈጽም ፡ ፍጹም ፡ መሰናከል ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የሚያግደው ፡ ነገር ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) በአእምሮ፡ ግምት፡ ባለዕዳው፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሊያስብበት ፡ የሚቻል ፡ መሆኑ፡ የታወቀ ፡ አንድ ፡ ድንገተኛ ፡ ደራሽ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ለውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ወጪ ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ የሚደርስበት ፡ ቢሆን ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይገመትም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፫ ። ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ የሚያሰኙ ፡ ምክንያቶች ።

እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ ሊያሰኙ ፡ የሚ ችሉ ፡ ምክንያቶች ፤

BACK



(ሀ) ባለዕዳው ፡ አላፊ ፡ የማይሆንበት ፤ ያልታሰቡና ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚ መጡ ፡ ድንገት ፡ ደራሽ ፡ ነገሮች ፤

(ለ) ውሉ ፡ እንዳይፈጸም ፡ በመንግሥት ፡ የሚደረግ ፡ ክልከላ ፤

(ሐ) እንደ ፡ መሬት ፡ መናወጽ ፡ መብረቅ ፤ ማዕበል ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ፍጥረ ታዊ ፡ መቅሠፍት ፤

(መ) የጠላት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጦርነትና ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ጦርነት ፤

(ሠ) የባለዕዳው ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ ባልታሰበ ፡ ሁኔታ ፡ የሚደርስበት ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ጽኑ ፡ ሕመም ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፬ ። ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ አለመኖር ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር፤

(ሀ) በተዋዋዩ ፡ ፋብሪካ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ ከሚያከናውንበት ፡ ባንደ ኛው ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ውስጥ ፡ የተደረገ ፡ የሠራተኞች ፡ አድማ ፡ ወይም ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ መዘጋት ፡ ጉዳት ፤

(ለ) ለውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ዋነኛ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ መወደድ ፡ ወይም ፡ መርከስ ፤

(ሐ) ባለዕዳው ፡ ያለበትን ፡ የግዴታ ፡ አፈጻጸም ፡ ወጪ ፡ የሚያከብድበት ፡ የአ ዲስ ፡ ሕግ ፡ መውጣት ፤

ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ አያሰኝም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፭ ። ጥፋት ፡ መደረጉን ፡ ስለ ፡ ማስረዳት ።

አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሁለተኛውን ፡ ወገን ፡ ግዴታውን ፡ አልፈጸመልኝም ፡ ብሎ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ የሚችለውና ፡ የተዋዋዩን ፡ ጥፋት ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚያስፈልገው ፤

(ሀ) ባለዕዳው ፡ ለተዋዋዩ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያስገኝለት ፡ ለዚሁም ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ሳይል ፡ የሚችለውን ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ለማድረግ ፡ ውል ፡ የገባ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሕግ ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ የውል ፡ ልዩነት ፡ ለይቶ ፡ ይህን ፡ ደንብ ፡ የጠቀሰ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፮ ። ከባድ ፡ ጥፋት ።

ውሉ ፡ ለአንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ባልተ ፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ የሚገባው ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ጥፋት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፯ ። ለተዋዋዩ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) ባለዕዳው ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚከለክለውን ፡ ምክንያት ፡ ለተዋዋዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

BACK



(፪) ተዋዋዩ ፡ በጊዜው ፡ ማስታወቂያ ፡ ደርሶት ፡ ኖሮ ፡ ቢሆን ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስበት ፡ አስፈላጊውን ፡ ለማድረግ ፡ ይችል ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ግዴታውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ በተዋዋዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ባለዕዳው ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፰ ። የማስጠንቀቂያ ፡ ውጤት ።

ለባለዕዳው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከደረሰው ፤ ውሉ ፡ ያልተፈጸመበት ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ ኪሣራ ፡ መታሰቡ ፡ አይቀርም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፱ ። ደንበኛው ፡ የኪሣራ ፡ አቈራረጥ ።

(፩) የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ የሚታሰበው ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ይደርሳል ፡ ብሎ ፡ በሚገምተው ፡ አስተያየት ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የውሉ ፡ መሠረቶች ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚያዙት ፡ የውሉን ፡ ዐይነት ፡ መመልከት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የተዋዋዮቹን ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነበራቸውን ፡ ግንኙነት ፤ ባለዕዳው ፡ የሚያውቃቸውን ፡ ሁኔታዎችና ፡ ማንኛዎቹንም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻ ። ዝቅተኛ ፡ ጉዳት ።

ባለገንዘቡ ፡ ከጠየቀው ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ያገኘው ፡ መሆኑን ፡ ባለዕዳው ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊነቱ ፡ በዚሁ ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፩ ። ከፍተኛ ፡ ጉዳት ።

(፩) ባለገንዘቡ ፡ ውል ፡ ሲያደርግ ፡ ጉዳቱን ፡ ይበልጥ ፡ የሚያከብዱትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ለባለዕዳው ፡ አስቀድሞ ፡ ያስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራው ፡ ባለገንዘቡ ፡ በደረሰበት ፡ እርግጠኛ ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ይሆናል ።

(፪) የአፈጻጸሙ ፡ ጕድለት ፡ ባለዕዳው ፡ ለመጕዳት ፡ ሲል ፡ ባደረገው ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ጕልህ ፡ በሆነ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያቶች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የሚገባው ፡ ኪሣራ ፡ በደረሰበት ፡ እርግጠኛ ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፪ ። የጉዳት ፡ ኪሣራን ፡ የመቀነስ ፡ ግዴታ ።

(፩) ውል ፡ አልተፈጸመልኝም ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ውሉ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ ያነሰ ፡ እንዲሆን ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፤ ይኸውም ፡ ይህ ፡ የሚያደርገው ፡ ጥንቃቄ ፡ አስቸጋሪና ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ እንዲያደርግ ፡ የማያስገድደው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ጥንቃቄ ፡ በቸልተኛነት ፡ ሳይደረግ ፡ ቢቀር ፡ ውሉን ፡ ያልፈጸመው ፡ ሰው ፡ የሌላውን ፡ ወገን ፡ ቸልታ ፡ መከራከሪያ ፡ አድርጎ ፡ ኪሣራው ፡ እንዲቀነስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ፡ ሺ፰፻፭ ። የገንዘብ ፡ ዕዳ ። (፩) ጊዜ ፡ በማሳለፍ ፡ ስለሚከፈል ፡ ወለድ ።</u>

(፩) የገንዘብ፡ ዕዳ ፤ እንዲከፍል ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የደረሰው ፡ ባለዕዳ ፡ አነስተኛ ፡ ወለድ ፡ እንዲከፍል ፡ በስምምነቱ ፡ ቢወሰንም ፡ እንኳ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ውን ፡ ወለድ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) በውለታው ፡ ውስጥ ፡ የበለጠ ፡ ወለድ ፡ የታሰበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚሁ ፡ በከ ፍተኛው ፡ ወለድ ፡ መታሰቡ ፡ ይቀጥላል ።

(፫) ባለገንዘቡ ፡ ምንም ፡ ኪሣራ ፡ ባይደርስበትም ፡ ወለድ ፡ ይገባዋል ።

<u>ቍ፡ ሺ፰፻፮ ። (፪) የወለድ ፡ ወለድ ።</u>

(፩) ከባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ሆኖ ፡ ለባለገ ንዘቡ ፡ በየጊዜው ፡ የሚገኘው ፡ ገቢ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ለምሳሌ ፡ ኪራይ፤ የርስት፡ አሳብ ፤ የዘወትር ፡ ጡረታ ፡ ወይም ፡ ለሕይወቱ ፡ የተወሰነ ፡ ጡረታ ፡ የአንድ ፡ ካፒታል፡ ወለድ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ከሆነ ፡ ደንበኛው ፡ ወለድ ፡ የሚ ታሰበው ፡ ክስ ፡ ለአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበበት፡ ቀን ፡ ጀምሮና ፡ ይኸውም፡ ባለዕዳው ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ሒሳብ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ተመላላሽ ፡ ሒሳቡን ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

<u>ቍ፡ ሺ፰፻፯ ። የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ማቻቻያ ።</u>

ባለገንዘቡን ፡ ያገኘው ፡ ጉዳት ፡ ጊዜ ፡ በማሳለፍ ፡ ምክንያት ፡ ከሚከፈለው ፡ ወለድ ፡ የበለጠ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ በተዋዋሉ ፡ ጊዜ ፡ ባለዕዳው ፡ ማስ ጠንቀቂያ ፡ ተደርጎለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ውለታው ፡ ያልተፈጸመበት ፤ ባለ ገንዘቡን ፡ ለመጉዳት ፡ በመፈለጉና ፡ በከባድ ፡ ቸልታና ፡ ወይም፡ በከባድ ፡ ጥፋት፡ ሲሆን ፡ ኪሣራውን ፡ ባለዕዳው ፡ በሙሉ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## <u>የግዴታዎች ፡ መቅረት ።</u>

<u>ቍ፡ ሺ፰፻፰ ። (ሀ) ግዴታን ፡ የሚያስቀሩ ፡ መደበኛ ፡ ምክንያቶች ።</u>

ውለታው ፤ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግዴ ታው ፡ ይቀራል ።

<u>ቍ፡ ሺ፰፻፱ ። (ለ) ሌሎች ፡ ምክንያቶች ።</u>

እንደዚሁም ፡ ግዴታው ፡ የሚቀረው ።

(ሀ) ግዴታው ፡ የተፈጸመበት ፡ ውል ፡ የተሰረዘ ፡ ወይም ፡ የፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ተዋዋዮቹ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ውለታው ፡ እንደሚፈቀድለት ፡ እንዲ ያልቅ ፡ ያደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ተዋዋዮቹ ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ፡ በሌላ ፡ ግዴታ ፡ በመተካት ፡ ለማደስ ፡(ኖባሲ ዮን)፡ የተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(መ) ባለገንዘቡ ፡ ለባለዕዳው ፡ ያለበት ፡ ሌላ ፡ ግዴታና ፡ ዋናው ፡ ግዴታ ፡ የተ ቻቻሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
(ሠ) የባለገንዘቡና ፡ የባለዕዳው ፡ መብት ፡ የተቀላቀለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
(ረ) የግዴታውን ፡ አፈጻጸም ፡ ሳይጠይቅ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ውሎችን ፡ ስለ ፡ መሰረዝና ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

ቍ ፡ ፲፰፻፰ ። የውልን ፡ ማፍረስ ፡ ማን፡ስለሚጠየቅ ።

(፩) ከውል ፡ ፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ጉድለት ፡ ወይም ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ በአ ንደኛው ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ የተነሣ ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚ ችለው ፡ በስምምነት ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ ውሉን ፡ ለመሰረዝ ፡ እንዲጠ ይቅ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ውሉ ፡ የተደረገበት ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ ምክንያት ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ለውሉ ፡ አጻጻፍ ፡ የተደነገገው ፡ ፎርም ፡ አልተጠበቀም ፡ ብሎ ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፱ ። ውልን ፡ ለመፈጸም፡እንቢ ፡ ማለት ።

ውሉን ፡ ለመፈጸም ፡ እንቢ ፡ ለማለት ፡ የሚፈልገው ፡ ወገን ፤ ውሉ ፡ የማይ ረጋ ፡ መሆኑን ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲ ። የውል ፡መሰረዝ ፡ ክስ ።

(፩) ውል፡ የማይረጋበት፡ ምክንያት ፡ ከቀረበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት፡ በኋላ ፡ የማሰረዝ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።
ጉዳቱ ፡ የደረሰበት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ የማሰረዝ ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ውሉ ፡ በተደረገ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፩ ። ውልን ፡ ለማጽናት፡መቻል ።

(፩) ስምምነቱ ፡ የጐደለበት ፡ ተዋዋይ ፤ ፈቃዱ ፡ ሳይሆን ፡ የተዋዋለባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ከቀሩ ፡ በኋላ ፡ ውሉን ፡ ለማሰረዝ ፡ እንዲጠይቅ ፡ የተሰጠውን ፡ መብት ፡ ለመተው ፡ ይችላል ።

(፪) የማጽናቱም፡ አሠራር ፡ መፍረስ ፡ እንዲቀርለት፡ የተባለው ፡ ውል ፡ ስለዚሁ፡ ውል ፡ አሠራር ፡ ፎርም ፡ በተደነገገው ፡ አኳኋን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፪ ። ጥያቄን ፡ ስላለመቀበል ።

በጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ የተጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውሉ ፡ የሚጠቀመው ፡ ተዋዋይ ፡ ጉድለቱን ፡ ለመሙያ ፡ በሚበቃ ፡ ያኸል ፡ ተጨ

ማሪውን ፡ ከፍሎ ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ለማቆም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፫ ። (ሀ) ውለታን፡በከፊል ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

ውሉ፡ በመሠረቱ ፡ የማይረጋ ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ የተሳሳተው ፡ በአንዳንድ ፡ ክፍል ፡ ቃላት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የሚሰረዙት ፡ እነዚህ ፡ የተሳሳቱት ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፬።(ለ)የማስታወቅ፡ግዴታ ።

(፩) ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ወይም ፡ አልፈረሰም ፡ የሚል፡ መሆኑን፡ ሌላው፡ ወገን ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ ገልጾ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ይህኛውም፡ ተዋዋይ ፡ በበኩሉ፡ በአጭር ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ቢኖርም ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ መርጧል ፡ ያሰኘዋል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፭ ። የመሰረዙ፡ወይም፡የመፍረሱ ፡ ውጤት ።

(፩) አንድ ፡ ውለታ ፡ ሲሰረዝ ፡ ወይም ፡ ሲፈርስ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ውለታ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለሱ ፡ ማድረግ ፡ ይገባቸዋል ።

(፪) ውለታውን ፡ ለመፈጸም ፡ የተሠራ ፡ ሁሉ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ውጤት ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፮ ። የሮኛውን ፡ ወገን፡መብት፡ስለ ፡ መጠበቅ ።

በቅን ፡ ልቡና ፡ ለሆነ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ ጠቃሚ ፡ ከሆነ ፡ እንደ ፡ ረጋ ፡ እንዲቀር ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፯ ። እንደ ፡ ነበር፡ለማድረግ፡ስለ ፡ አለመቻል ።

(፩) ውለታውን ፡ ለመፈጸም ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ለማፍረስ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሰናከል ፡ የሚያመጣ ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ ፡ የተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ ረጉ ፡ እንዲቀሩ ፡ ይደረጋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ እንደ ፡ ታያቸው ፡ ኪሣራ ፡ በማስከፈል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ በማድረግ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ተዋዋዮቹን ፡ ውሉ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ሁኔታ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፰፻፲፰ ። ስለ፡ወጪ ።

ውሉ ፡ ከመፍረሱ ፡ ወይም ፡ ከመሰረዙ ፡ የተነሣ ፡ ንብረትን ፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፤ ንብረቱን ፡ ለውጦ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ወጪ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ መለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ወጪ ፡ የተነሣ ፡ ያሉት ፡

መብቶች ፡ ወይም ፡ ግዴታዎች ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ያላገባብ ፡ መበልጸግን ፡ በሚመለከተው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይመራሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ውሎችን ፡ ስለ ፡ ማስቀረትና ፡ ዕዳን ፡ ስለ ፡ መተው ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፲፱ ። የሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መስማማት ።**

(፩) ውልን ፡ የተዋዋሉት ፡ ወገኖች ፡ ተስማምተው ፡ ሊያስቀሩት ፡ (ሊያፈርሱት) ፡ ይችላሉ ።

(፪) ውሉ ፡ ቀሪ ፡ ሲሆን ፡ ወደፊት ፡ የውልን ፡ መፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ያስቀራል ።

(፫) የውሉ ፡ መፍረስ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ አይነካም ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፳ ። በአንድ ፡ ወገን ፡ በኩል ፡ ውልን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

(፩) ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ በማስታወቅ ፡ ብቻ ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ይፈቀዳል ፡ ብለው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

(፪) ውሉ ፡ ከሁለት ፡ በበለጡ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ቢወጣ ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ፊቱ ፡ በቀሩት ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ረጋ ፡ ይቀራል ፡ ብለው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፳፩ ። ጊዜ ፡ ያልተወሰነላቸው ፡ ውሎች ።**

ውሉ ፡ የተደረገው ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአንዱ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ማስታወቅ ፡ ውሉን ፡ የማስቀረት ፡ መብት ፡ ለሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ይኖራቸዋል ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፳፪ ፡ የሚከበር ፡ ጊዜ ።**

(፩) በማስታወቅ ፡ ብቻ ፡ ውሉን ፡ ለማስቀረት ፡ የሚፈልገው ፡ ወገን ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ማክበር ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ባይኖር ፡ እንደ ፡ ሁኔታው ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ የሚበቃው ፡ ጊዜ ፡ መከበር ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፳፫ ። ልዩ ፡ የእምነት ፡ ግንኙነት ።**

በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ ለውሉ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ እምነት ፡ መረዳዳት ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ አስተያየት ፡ ሲቀርና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማገናኘት ፡ የማይቻል ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ውሉታውን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላሉ ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፳፬ ። ያለ ፡ ጥቅም ፡ የተደረገ ፡ ውል ።**

አንድ ፡ ውል ፡ ለአንድ ፡ ተዋዋይ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ተደርጎ ፡ ሌላው ፡ ተዋዋይ ፡ በቂ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ምክንያት ፡ አቅርቦ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ እንደዚሁ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላሉ ።

**ቊ ፡ ፲፰፻፳፭ ። ዕዳን ፡ ስለ ፡ መተው ።**

ባለገንዘብ ፡ ለባለዕዳው ፡ የምፈልግብህ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ባስታወቀው ፡

ጊዜ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ወዲያውኑ ፡ ዕዳ ፡ እንዲቀርልኝ ፡ አልፈቅድም ፡ ብሎ ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር ፡ ዕዳው ፡ ይቀራል ።

ክፍል ፡ ፫ ።

ስለ ፡ መተካት ፡ (ኖባሲዮን) ።

ቍ ፡ ፲፰፻፳፮ ። መሠረቱ ።

ግዴታው ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖቹ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ግዴታ ፡ በጕዳዩ ፡ ወይም ፡ በምክንያቱ ፡ በተለይ ፡ አዲስ ፡ ግዴታ ፡ ሊተኩበት ፡ የተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፳፯ ። የመተካቱ ፡ ውጤት ።

(፩) ከመጀመሪያው ፡ ግዴታ ፡ ጋራ ፡ የሚገኙት ፡ ዋስትናዎች ፤ ቅድሚያዎች ፡ መያዣዎች ፡ እንዳሉ ፡ እንዲኖሩ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በግልጽ ፡ የተጠበቀ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ምትክ ፡ ወደሚሆነው ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ አይተላለፉም ።

(፪) እንዲሁም ፡ በግልጽ ፡ እንዲጠበቁ ፡ የተደረገ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ግዴታን ፡ ከመተካቱ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ ወለዶች ፡ ሊጠየቁ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፲፰፻፳፰ ። ግዴታውን ፡ የማስቀረት ፡ ፍላጎት ።

አዲሱን ፡ ግዴታ ፡ ለመተካት ፡ እንዲቻል ፡ የመጀመሪያውን ፡ ግዴታ ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ የሚያስቀር ፡ ፈቃድ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፳፱ ። የምትክ ፡ አለመኖር ።

ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ምትክ ፡ ሊደረግ ፡ የማይቻለው ።

(ሀ) ዕዳውን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ አዲስ ፡ ሰነድ ፡ የተደራጀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ባለዕዳው ፡ ላለበት ፡ ዕዳ ፡ አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ ቃል ፡ የተሰጠበት ፡ ወረቀት ፡ (ፕሮሚሶሪ ፡ ኖት) ፡ የፈረመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ግዴታውን ፡ ለመክፈል ፡ አዲስ ፡ ዋስትናዎች ፡ የተደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፴ ። ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ።

(፩) በያይነቱ ፡ የሆኑትን ፡ ጕዳዮች ፡ በተቀመጠው ፡ ሒሳብ ፡ በማጻፍ ፡ ምትክ ፡ አይሆኑም ።

(፪) ሆኖም ፡ ሒሳቡ ፡ ከቆመና ፡ ከታወቀ ፡ ምትክ ፡ ተደረገ ፡ ይባላል ።

(፫) ከጕዳዮቹ ፡ አንዱ ፡ ልዩ ፡ ዋስትና ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለገንዘቡ ፡ ሒሳቡ ፡ ከቆመና ፡ ከታወቀ ፡ በኋላም ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ እነዚህን ፡ ዋስትናዎች ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቀራል ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ማቻቻል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፴፩ ፡ የማቻቻሉ ፡ መሠረት ።

ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ ባለዕዳ ፡ ሆኖ ፡ሲገኝ ፤ ከዚህ ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ደንብ ፡ የሁለቱን ፡ ዕዳዎች ፡ የሚያስቀር ፡ ማቻቻል ፡ ይደረጋል ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፩። መቻቻያ ፡ የሚያስደርጉ ፡ ሁኔታዎች ።**

ማቻቻል ፡ የሚደረገው ፡ ለገንዘብ ፡ ዕዳዎች ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆኑትና ፡ የመከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ በደረሰ ፡ ዕዳዎች ፡ መካከል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፪። መቻቻያን ፡ የማያስደርጉ ፡ ሁኔታዎች ።**

ቀጥሎ ፡ ከተዘረዘረው ፡ በቀር ፡ የዕዳው ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ ማቻቻያ ፡ ይደረጋል ።

(ሀ) የዕዳው ፡ ዐይነት ፡ ልዩ ፡ በመሆኑ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ በእጁ ፡ የሚከፈል ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ ለባለዕዳውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከደመወዙና ፡ አስፈላጊውን ፡ ወይም ፡ ለቀለቡ ፡ የሚሆነውን ፡ ዐይነት ፡ የመሳሰለ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ለመንግሥትና ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ባለቤቱ ፡ በማይገባ ፡ የተወሰደበት ፡ እንዲመለስለት ፡ ጥያቄ ፡ ሲያቀርብ ፤

(መ) በአደራ ፡ የሰጠውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመለስለት ፡ ሲጠይቅ ፡ መቻቻያ ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፫። በችሮታ፡ የሚሰጥ፡ ጊዜ ።**

በችሮታ ፡ የተሰጠ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ለማቻቻያ ፡ ዕንቅፋት ፡ አይሆንም ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፬። የአከፋፈል ፡ አቀናነስ ።**

በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የሚቻቻሉ ፡ ዕዳዎች ፡ ሲኖሩበት ፡ ስለ ፡ ማቻቻሉ ፡ አሠራር ፡ የአከፋፈል ፡ አቀናነስ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ይጸናበታል ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፭። የማቻቻያው ፡ ውጤት ።**

ሁለት ፡ ዕዳዎች ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲኖሩ ፤ በአንድነት ፡ የሚቻቻሉት ፡ ባነስተኛው ፡ ዕዳ ፡ ልክ ፡ ነው ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፮። የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መብት ።**

ከዕዳዎች ፡ መካከል ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የሦስተኛውን ፡ ወገን ፡ መብት ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ ማቻቻል ፡ አይደረግም ።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፯። መቻቻያ፡ እንዲደረግ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ማቻቻያ፡ የሚደረገው፡ ባለዕዳው፡ እንዲቻቻልለት ፡ መፈለጉን ፡ ለባለገንዘቡ፡ ሲያስታውቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ዳኛው ፡ የማቻቻሉን ፡ ጉዳይ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ሊያዝ ፡ አይችልም።

**ቍ፡ሺ፰፻፴፰። መቻቻያን ፡ አልፈልግም ፡ ስለ ፡ ማለት ።**

ባለዕዳ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ መቻቻልን ፡ አልፈልግም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺ ። በውል ፡ የሚደረግ፡መቻቻል ።**

(፩) በሕግ ፡ ከተወሰነውም ፡ በቀር ፡ መቻቻል ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ፈቃድ ፡ ሊደ ረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ተዋዋዮቹ ፡ አስቀድመው ፡ መቻቻል ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደሚፈጸም ፡ መወሰን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፩ ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚደረግ፡ማቻቻል ።**

(፩) አንደኛው ፡ ዕዳ ፡ የበሰለ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞቹ ፡ ለጊዜው ፡ ክርክር ፡ በሌለበት ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ዕዳው ፡ እምን ፡ ድረስ ፡ እንዲቻቻል ፡ ሊገ ልጹ ፡ ይችላሉ ።

(፪) አንደኛው ፡ ዕዳ ፡ የበሰለ ፡ ባይሆንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሊከፈል ፡ የማያስቸግር ፡ ከሆነ ፤ ዳኞች ፡ የበሰለውን ፡ ገንዘብ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዳይከ ፍል ፡ አድርገው ፡ የአንደኛው ፡ ዕዳ ፡ የሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ እስኪደርስ ፤ ከማ ስገደድ ፡ ሊያቈዩ ፡ ይችላሉ ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

## ስለ ፡ መብት ፡ መቀላቀል ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፪ ። የመቀላቀል ፡ መሠረት ።**

የባለዕዳውና ፡ የባለገንዘቡ ፡ መብት ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሲጠቀለሉ ፤ በሕግ ፡ ሁለቱን ፡ ዕዳዎች ፡ የሚያስቀር ፡ መቀላቀል ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፫ ። የሦስተኛ፡ወገን፡መብት ።**

ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቅበትን ፡ መብቱን ፡ በመጉዳት ፤ የዕዳ ፡ ማቀላቀል ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፬ ። የዕዳ፡መቀላቀል፡መቅረት ።**

የዕዳው ፡ መቀላቀል ፡ ሲቀር ፡ ግዴታው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይጀመራል ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ ይርጋ ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፭ ። የይርጋ፡ጊዜ ።**

ሕግ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ካልወሰነ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ ወይም ፡ ካለመፈ ጸሙ ፡ የተነሣ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፮ ። የይርጋው፡መነሻ፡ጊዜ ።**

የይርጋ ፡ ቀን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ግዴታውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ተገቢ ፡ ከሆ ነው ፤ ወይም ፡ ውሉ ፡ የሚሰጠው ፡ መብት ፡ ከተሠራበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፵፮ ። በየጊዜው ፡ የሚሰጥ ፡ ገንዘብ ።

በየጊዜው ፡ የሚሰጥ ፡ ገንዘብን ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ይርጋ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፤ መከፈሉ ፡ ከተቋረጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፵፯ ። የጊዜው ፡ አቈጣጠር ።

(፩) የይርጋው ፡ መጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ከይርጋው ፡ ዘመን ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ አይታሰብም ።

(፪) የይርጋው ፡ ቀን ፡ የሚሞላው ፡ ለይርጋው ፡ የተወሰነ ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፫) ምናልባት ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ ገንዘቡ ፡ በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይርጋው ፡ የሚሞላው ፡ ከበዓሉ ፡ ተከታይ ፡ በሆነው ፡ በዓል ፡ ባልሆነው ፡ ቀን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፵፰ ። ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ።

የዋነኛው ፡ ገንዘብ ፡ ይርጋ ፡ በወለዱና ፡ በሌሎቹም ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘቦች ፡ ይጸናል ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፶ ። መያዣ ።

ባለገንዘቡ ፡ ለገንዘቡ ፡ መያዣ ፡ በእጁ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በይርጋ ፡ ገንዘቡ ፡ ቀርቷል ፡ ተብሎ ፡ መቃወሚያ ፡ ሳይሆንበት ፡ በመያዣው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፶፩ ። ይርጋ ፡ የሚቋረጥባቸው ፡ ምክንያቶች ።

ይርጋ ፡ የሚቋረጠው ፡—

(ሀ) ባለዕዳ ፡ ዕዳውን ፡ ሲያምን ፤ ይልቁንም ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ከዕዳው ፡ ላይ ፡ በከፊል ፡ ሰጥቶ ፡ ሲገኝ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤

(ለ) ባለገንዘቡ ፡ መብቱ ፡ እንዲታወቅለት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ለባለዕዳው ፡ አስታውቆ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፶፪ ፡ የይርጋው ፡ ማቋረጥ ፡ ውጤት ።

(፩) ይርጋው ፡ ከተቋረጠበት ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ ይጀምራል ።

(፪) ዕዳው ፡ በአንድ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አዲሱ ፡ የይርጋ ፡ አቈጣጠር ፡ ዘመን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፰፻፶፫ ። የመታዘዝ ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ግንኙነት ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይርጋን ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ የሚችለው ፡ ባለገንዘቡ ፡ የሚፈልገውን ፡ ያልጠየቀበት ፡ ምክንያት ፡ ባለዕዳውን ፡ የመፍራትና ፡ የማክበር ፡ ስሜት ፡ ኑሮት ፡ ለሱም ፡ የተቀራረበ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ ታዛዥነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ ሲሆንም ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ዋስ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ከኀላፊነታቸው ፡ ነጻ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ፡ሺ፰፻፶፪።ክፉ ፡ ልቡና ።**

ይርጋ ፡ እንዳይቈጠርበት ፡ ክፉ ፡ ልቡናን ፡ መቃወሚያ ፡ አድርጎ ፡ ለመከራከር ፡ አይቻልም ።

**ቍ፡ሺ፰፻፶፫። ተቃራኒ ፡ ስምምነቶች ።**

ሕግ ፡ የወሰነው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ እንዲቀር ፡ ወይም ፡ እንዲለወጥ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመስማማት ፡ ወይም ፡ ለመዋዋል ፡ አይቻልም ።

**ቍ፡ሺ፰፻፶፬።የሞላውን ፡ ይርጋ ፡ ስለ ፡ መተው ።**

(፩) በይርጋ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የሞላውን ፡ ይርጋ ፡ ለመተው ፡ ይችላል ።
(፪) ዳኞች ፡ በገዛ ፡ ሥልጣናቸው ፡ የይርጋውን ፡ ደንብ ፡ መከላከያ ፡ ለመጥቀስ ፡ አይችሉም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የአንዳንድ ፡ ግዴታዎች ፡ ወይም ፡ የአንዳንድ ፡ ውሎች ፡ አኳኋን ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጊ ዜ ።

**ቍ፡ሺ፰፻፶፭።የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

ውል ፡ ከተደረገ ፡ ጀምሮ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አንድ ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ የሚረጋ ፡ ነገር ፡ መፈጸም ፡ ሲያስፈልግ ፡ የጊዜው ፡ አወሳሰን ፡ ቀጥለው ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

**ቍ፡ሺ፰፻፶፮። በቀኖች፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

ጊዜው ፡ በቀኖች ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውል ፡ የተደረገበት ፡ ቀን ፡ ሳይታሰብ ፡ ዕዳ ፡ ለመፈክል ፡ የሚገባው ፡ በተወሰነው፡ ጊዜ ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ፡ሺ፰፻፶፯።በሳምንቶች ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

ጊዜው ፡ በሳምንቶች ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ውል ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ ስም ፡ በመጨረሻ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ በዋለው ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ፡ ሺ፰፻፶፰። በወሮች ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ጊዜው ፡ በወር ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ወሮች ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ የሚገባው ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ በመጨረሻው ፡ ወር ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው ።

BACK



(፪) ጊዜውም ፡ የተወሰነው ፡ እንደ ፡ ኤሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ ከሆነና ፡ በመጨረሻው ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ ሳይኖር ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የሚገባው ፡ በተባለው ፡ ወር ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው ።

(፫) ጳጉሜ ፡ እንደ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስተኛ ፡ ወር ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፲፰፻፷፩ ። ለወሮች ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) ለመፈጸሚያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በወሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ወይም ፡ የወሩ ፡ መጨረሻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በወሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ወይም ፡ በወሩ ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ጊዜው ፡ በወር ፡ መካከል ፡ ከሆነ ፡ የወሩ ፡ ፲፭ኛ ፡ ቀን ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፷፪ ። የበዓላት ፡ ቀኖች ።

በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ የመክፈያው ፡ ቀን ፡ ከአንድ ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ ጋራ ፡ የገጠመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዓል ፡ ባልሆነበት ፡ በማግሥቱ ፡ በዋለው ፡ ቀን ፡ በደንብ ፡ ይተላለፋል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፷፫ ። የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) አንድ ፡ ግዴታ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲፈጸም ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለዕዳው ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሳያልቅ ፡ አስቀድሞ ፡ ግዴታውን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) ግዴታው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ቀን ፡ ለመወሰን ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ለመሆኑ ፡ ሁኔታው ፡ የሚያስረዳ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የግዴታውን ፡ መፈጸሚያ ፡ ቀን ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ ባለዕዳው ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፷፬ ። የተወሰነን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማርዘም ።

ላፈጻጸሙ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እንዲረዝም ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አዲሱ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ በመጀመሪያ ፡ የተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀበት ፡ ከመጨረሻው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፰፻፷፭ ። የጊዜው ፡ ጠቃሚነት ።

በስምምነቱ ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ሁኔታው ፡ ለባለገንዘቡም ፡ እንዲጠቅም ፡ ተብሎ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፤ የጊዜው ፡ መስጠት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ለባለዕዳው ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፲፰፻፷፮ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜን ፡ መጠበቅ ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) በውሉ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ አኳኋን ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ሐሳብ ፡ ተቃራኒ ፡ ሆኖ ፡ ካልተገኘ ፤ ባለዕዳው ፡ የተዋዋለበት ፡ ቀን ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

(፪) ለዕዳ ፡ መክፈያ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አይመለስም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፶፰ ። የባለገንዘቡ ፡ መብት ።**

(፩) ፍጸሚው ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሳይደርስ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ግዴታው ፡ እንዲፈጸም ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለባለዕዳው ፡ ግዴታውን ፡ እንዲፈጽም ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ የሚበቃ ፡ ጊዜ ፡ ይሰጠዋል ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፶፱ ። የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቀር ፡ ምክንያት ።**

ባለዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ በፍርድ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የሰጣቸውን ፡ ዋስትናዎች ፡ በእሱ ፡ ምክንያት ፡ ያጐደላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተወሰነው ፡ የጊዜው ፡ ጥቅም ፡ ይቀርበታል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ሁኔታ ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፷ ። የሁኔታ ፡ መሠረት ።**

ለውሉ ፡ ጉዳይ ፡ የሆነው ፡ ግዴታ ፡ መኖር ፡ ካጠራጣሪ ፡ ሁኔታ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ሲሆን ፡ ውሉ ፡ በሁኔታ ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፷፩ ። ቅን ፡ ልቡና ።**

አንደኛው ፡ ወገን ፡ የቅን ፡ ልቡናን ፡ አሠራር ፡ በመጣስ ፡ ውሉ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ሁኔታው ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ለመቁጠር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፷፪ ። ውሉን ፡ የማቈያ ፡ ሁኔታ ።**

ተዋዋዮቹ ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ሐሳብ ፡ ካልገለጹ ፡ ውሉ ፡ ውጤት ፡ ማግኘት ፡ የሚጀምረው ፡ ሁኔታው ፡ ከሚፈጸምበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፷፫ ። የሚያስቀር ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ውሉ ፡ የሚቀረው ፤ ያልተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲፈጸም ፡ ብቻ ፡ ከሆነ ፡ የውሉ ፡ ውጤት ፡ ወዲያውኑ ፡ ይጀመራል ።

(፪) ሁኔታው ፡ ሲፈጸም ፡ ግን ፡ ውሉ ፡ ውጤት ፡ መስጠቱ ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፷፬ ። ተዋዋዮች ፡ ስለሚከለከሉት ፡ ነገር ።**

ውሉ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የውሉን ፡ ደንበኛ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚከለክለውን ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ አለማድረግ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፷፭ ። የማስተዳደር ፡ ሥራዎች ።**

ሁኔታው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ያስተዳደር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ ሁሉ ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ሠርቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሁኔታው ፡ ከተፈጸመ ፡

በኋላ ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ፡ እንጂ ፤ በአስተዳዳሪነት ፡ መብት ፡ የሠራቸው ፡ ተግባሮች ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ።

<u>ቍ ፡ ሺ፰፻፷፭ ። የማዘዝ ፡ ሥራዎች ።</u>

(፩) ሁኔታ ፡ ያለበት ፡ ውል ፡ ሲኖር ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በማዘዝ ፡ ያስፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ በሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ጥያቄ ፡ ይሰረዛሉ ።

(፪) ባለጥቅሞቹ ፡ በሚበቃ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ እንዲሰረዝ ፡ የሚፈልግ ፡ መሆኑን ፡ እንዲገልጽ ፡ ይህን ፡ ሁለተኛውን ፡ ወገን ፡ ሊጠይቁት ፡ ይችላሉ ።

(፫) የመሰረዙም ፡ ጉዳይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የሚወሰነው ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የውሎችን ፡ መሰረዝ ፡ ወይም ፡ መፍረስ ፡ በሚመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ሺ፰፻፷፮ ። ፍሬና ፡ ትርፍ ።</u>

ሁኔታው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያገኘው ፡ ፍሬና ፡ ትርፍ ፡ ሁኔታው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላም ፡ ይረጋለታል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፰፻፷፯ ። የመጠበቂያ ፡ እርምጃ ።</u>

በሁኔታ ፡ የተሰጡት ፡ መብቶች ፡ አደጋ ፡ የሚደርስባቸው ፡ ሆኖ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ሲታየው ፡ ለሌላ ፡ ያለሁኔታ ፡ ለተሰጡ ፡ መብቶች ፡ የሚደረገውን ፡ መጠበቂያ ፡ ለእነዚህም ፡ ሊያደርግላቸው ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፰፻፷፰ ። ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሁኔታ ።</u>

የውሉን ፡ መኖር ፡ የሚያረጋግጠው ፡ ሁኔታ ፡ የማይቻል ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለውል ፡ ጉዳይ ፡ አለመቻል ፡ ለውል ፡ ጉዳይ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ የሕሊና ፡ ተቃራኒነት ፡ ስለሚሆነው ፡ ጉዳይ ፡ የሚጸኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለዚህም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ይፈጸማሉ ።

<u>ቍ ፡ ሺ፰፻፷፱ ። ብችል ፡ እሠራለሁ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) የሚሠራው ፡ ግዴታ ፡ በባለዕዳው ፡ ፈቃድ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ እንዲፈጸም ፡ ተዋውለው ፡ ሲገኝ ፡ ግዴታው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) ውሉ ፡ የተደረገው ፡ ተገዳጁን ፡ ውሉ ፡ ባይፈጸምም ፡ ማናቸውም ፡ ኀላፊነት ፡ እንዳያገኘው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ ብችል ፡ እሠራለሁ ፡ ለማለት ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ውል ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## <u>ማማረጫ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ።</u>

<u>ቍ ፡ ሺ፰፻፸ ። ማማረጫ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ መሠራት ።</u>

ባለዕዳው ፡ በውለታው ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁለት ፡ ዐይነቶች ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱን ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግዴታውን ፡ ፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፩ ። ጕዳዩን ፡ መምረጥ ።

(፩) የመምረጥ ፡ መብት ፡ ተገልጾ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ለአንድ ፡ ሌላ ፡ ፫ኛ ፡ ወገን ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ መርጦ ፡ መፈጸም ፡ የባለዕዳው ፡ ነው ።

(፪) አንደኛው ፡ ወገን ፡ ግዴታውን ፡ ለመምረጥ ፡ ውሉ ፡ ሲፈቅድለት ፡ ያልመረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲ ፡ ውሉ ፡ እንዲመርጥ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ደርሶት ፡ ሳይመርጥ ፡ ቢቀር ፡ ወዲያውኑ ፡ የመምረጡ ፡ መብት ፡ ለ፪ኛው ፡ ወገን ፡ ይሰጣል ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፪ ። መፈጸም ፡ ስላለመቻሉ ።

(፩) በውሉ ፡ ከተመለከቱት ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ባለዕዳው ፡ ቀሪውን ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) የግዴታው ፡ አፈጻጸም ፡ ያልተቻለው ፡ ምርጫ ፡ ባልተሰጠው ፡ ወገን ፡ ጥፋት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ቃ ብ ድ ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፫ ። የቃብድ ፡ ትርጒም ።

አንዱ ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ ወገን ፡ ቃብድ ፡ መስጠቱ ፡ በማያከራክር ፡ ሁኔታ ፡ ውል ፡ መደረጉን ፡ ያረጋግጣል ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፬ ። የውሉ ፡ አፈጻጸም ።

ቃብድ ፡ የተቀበለው ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ መመለስ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ሲፈጸም ፡ ከሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፭ ። የውል ፡ አለመፈጸም ።

(፩) ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ቃብድ ፡ የሰጠው ፡ ወገን ፡ የሰጠውን ፡ ቃብድ ፡ በመልቀቅ ፡ ውሉታውን ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ቃብድ ፡ የተቀበለው ፡ ወገን ፡ የተቀበለውን ፡ ቃብድ ፡ አጠፌታ ፡ በመክፈል ፡ ውሉታውን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

ክፍል ፡ ፭ ።

ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ የተጻፈ ፡ የውል ፡ ቃል ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፮ ። ኀላፊነትን ፡ ስለ ፡ ማስፋፋት ።

ተዋዋዮቹ ፡ በውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ ቢሆን ፡ ኀይል ፡ ሳይፈጸም ፡ ቢቀርም ፡ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ለሚያመጣው ፡ ጕዳት ፡ ኀላፊ ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ አላፊነታቸውን ፡ አስፋፍተው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

ቍ፡ ፲፰፻፹፯ ። አላፊነትን ፡ በጥፋት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

ተዋዋዮቹ ፡ በውሉ ፡ የሚደርስባቸውን ፡ አላፊነት ፡ ለመቀነስና ፡ አላፊነታቸውም ፡ ጥፋት ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፺፰ ። ስለ ፡ ሠራተኞች ፡ አድራጎት ።**

(፩) ውሉ ፡ በሠራተኞቻቸው ፡ ወይም ፡ በረዳቶቻቸው ፡ ጥፋት ፡ ያልተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ አላፊ ፡ አንሆንም ፡ ብለው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ የተደረገው ፤ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ሥልጣን ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራው ፡ ሰው ፡ እንዲጎዳ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፯፻፺፱ ። ስለ፡ መቀጫ ፡ ስምምነት ፡ (ስለ ፡ ገደብ) ።**

አንደኛው ፡ ወገን ፡ ግዴታውን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አጓድሎ ፡ ወይም ፡ አዘግይቶ ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚከፈለውን ፡ መቀጮ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ አስቀድመው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፰፻ ። የባለገንዘቡ ፡ መብት ።**

(፩) (የገደብ) ፡ የመቀጫ ፡ ስምምነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ የውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ኪሣራው ፡ የተወሰነው ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ መዘግየት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ለተጨማሪ ፡ ግዴታዎች ፡ አለመፈጸም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለገንዘቡ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸምና ፡ (ገደቡን) ፡ መቀጫውንም ፡ እንዲቀበል ፡ ሁለቱንም ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፰፻፩ ። የሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ።**

ባለገንዘቡ ፡ መቀጫ ፡ ( ገደብ ) ፡ ሊቀበል ፡ የሚገባው ፡ ውሉ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፰፻፪ ። የተረጋገጠ ፡ ጉዳት ።**

(፩) ባለገንዘቡ ፡ ኪሣራ ፡ ባይደርስበትም ፡ የተዋዋለው ፡ መቀጫ ፡ (ገደብ) ፡ ሊከፈለው ፡ ይገባዋል ።

(፪) ባለገንዘቡ ፡ ከተወሰነው ፡ መቀጫ ፡ (ገደብ) ፡ የበለጠ ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ውሉ ፡ ያልተፈጸመው ፡ ባለዕዳው ፡ ባለገንዘቡን ፡ ለመጉዳት ፡ አስቦ ፤ ጕልህ ፡ በሆነ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ በከባድ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፰፻፫ ። የተወሰነውን ፡ ስምምነት ፡ ስለ፡ ማሻሻል ።**

ግዴታው ፡ ባለመፈጸሙ ፡ እንዲከፈል ፡ የተወሰነውን ፡ መቀጫ ፡ (ገደብ) ፡ ዳኞች ፡ ሊቀንስ ፡ የሚችሉት ፡ ግዴታው ፡ በከፊል ፡ የተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፰፻፬ ። የማፍረስ ፡ ውጤት ።**

(፩) የውለታ ፡ መፍረስ ፡ የመቀጫውን ፡ (የገደቡን) ፡ ስምምነት ፡ ያስቀረዋል ።

(፪) የመቀጫው ፡ (የገደቡ) ፡ ስምምነት ፡ መፍረስ ፤ ውሉን ፡ አያፈርሰውም ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፭ ። በውሉ ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ።**

አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ ባጓደለ ፡ ጊዜ ፡ ፪ኛው ፡ ወገን ፡ የተለዩ ፡ ቅጣቶችን ፡ ያስፈጽምበታል ፡ ተብሎ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ የተባሉትን ፡ ቅጣቶች ፡ የሚ ያስከትሉ ፡ ነገሮች ፡ ተደርገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚችሉት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## በባለዕዳዎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ የማይከፋፈል ፡ አንድነት ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፮ ። አንድነት ፡ ስለሚገኝበት ፡ ጊዜ ።**

ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ከሌለና ፡ በሕግም ፡ ላይ ፡ የተገለጹ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳዎች ፡ በማይከፋፈል ፡ አላፊነት ፡ ዕዳውን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፯ ። ስለማይከፋፈል ፡ አላፊነት ።**

(፩) ባለገንዘቡ ፡ ስለ ፡ ግዴታው ፡ አፈጻጸም ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊሉ ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ አላፊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከነዚህ ፡ አንዱን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ዕዳው ፡ በሙሉ ፡ ተከፍሎ ፡ እስካለቀ ፡ ድረስ ፡ ባለዕዳዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፰ ። ፍርድ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ነገር ።**

ከባለዕዳዎቹ ፡ መካከል ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበው ፡ የገንዘብ ፡ ክስ ፡ ነገር ፡ ጠያቂውን ፡ በቀሩት ፡ ላይ ፡ ክስን ፡ እንዳያቀርብ ፡ አያግደውም ።

**ቍ ፡ ፲፰፻፺፱ ። ዕዳዎቹ ፡ እንዲከፈሉ ፡ ስለሚደረገው ፡ ማስጠንቀቂያ ።**

ለአንዱ ፡ ባለዕዳ ፡ የተደረገው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ (ማስታወቂያ) ፡ በሌሎቹ ፡ ባለ ዕዳዎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ውጤት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፲፱፻ ። ስለማይረጋ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ግዴታው ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ዓላማ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ እንዲሁም ፡ ግዴታውን ፡ የሚያፈርሱትን ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ በመጥቀስ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ሁሉ ፡ ባለገንዘቡን ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የመስማማት ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ባለዕዳ ፡ የተዋዋለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ግዴታን ፡ ለማፍረስ ፡ በሚደረ

ገው ፡ ክርክር ፡ ምክንያት ፡ ለመከራከር ፡ የሚችለው ፡ አንድነት ፡ ከተበደ ሩት ፡ ባለዕዳዎች ፡ በስምምነቱ ፡ ጉድለት ፡ ተደርጎብኛል ፡ የሚለው ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ባለዕዳ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፩ ። ስለ ፡ መክፈልና ፡ ስለ ፡ ይርጋ ።

ባለዕዳ ፡ የሆኑት ፡ ሁሉ ፡ ዕዳው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በክፊል ፡ ተከፍሏል ፡ ወይም ፡ በይርጋ ፡ ታግዷዋል ፡ በማለት ፡ ባለገንዘቡን ፡ ለመከራከር ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፪ ። ዕዳን ፡ ስለ ፡ መማር ።

(፩) ባለገንዘቡ ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ከሆኑት ፡ መካከል ፡ አንዱን ፡ ዕዳውን ፡ የማረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ለሆኑት ፡ ሁሉ ፡ ለአንዱ ፡ የተደረገ ፡ ምሕረት ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናቸዋል ።

(፪) ቢሆንም ፡ ባለገንዘቡ ፡ ዕዳውን ፡ የማረው ፡ ከጋራ ፡ ባለዕዳዎቹ ፡ መካከል ፡ ለብቻው ፡ ለተለይ ፡ አንዱን ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለሌሎች ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳዎች ፡ የዕዳው ፡ መማር ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆናቸው ፡ ዕዳውን ፡ የተማረው ፡ ባለዕዳ ፡ በመጨረሻው ፡ ይከፍለው ፡ በነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፫ ። ስለ ፡ መተካት ።

(፩) እንደዚሁም ፡ ባለገንዘቡ ፡ ከጋራ ፡ ባለዕዳዎቹ ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ በፊተኛው ፡ ዕዳው ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ዕዳ ፡ ለውጦ ፡ እንዲተካ ፡ የተስማማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተደነገጉት ፡ ለዚህም ፡ ይጸናሉ ።

(፪) ባለገንዘቡ ፡ በተለይ ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ መዋዋሉን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዕዳው ፡ መተካት ፡ የሚጸናው ፡ በዚሁ ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳ ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፬ ። ስለ ፡ ማቻቻል ።

ከባለዕዳዎቹ ፡ አንዱ ፡ ከዋናው ፡ ባለገንዘብ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ዕዳው ፡ ይቻቻልልናል ፡ ለማለት ፡ የሚችሉት ፡ ዕዳው ፡ የሚቻቻልለት ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳቸው ፡ በመጨረሻው ፡ ይከፍለው ፡ በነበረው ፡ ዕዳ ፡ ልክ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፭ ። መቀላቀል ።

ከጋራ ፡ ባለዕዳዎቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኀላፊ ፡ ለሆኑት ፡ ለሌሎች ፡ ባለዕዳዎች ፡ ዕዳው ፡ የሚቀርላቸው ፤ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነው ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳ ፡ በመጨረሻው ፡ ዕዳውን ፡ የሚከፍል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚከፍለው ፡ ልክ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፮ ። ስለ ፡ አላፊነት ።

(፩) የአንድነት ፡ ባለዕዳ ፡ ከሆኑት ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በራሱ ፡ አድራጎት ፡ የሌሎችን ፡ ሁኔታ ፡ ሊያከብድ ፡ አይችልም ።

(፪) የአንድነት ፡ ባለዕዳ ፡ ለሆኑት ፡ ሁሉ ፡ መከራከሪያ ፡ የሚሆናቸውን ፡ ነገር፡ያል ሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጋራ ፡ ተገዳጆቹ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፯። የመጨረሻ ፡ አከፋፈል ።**

በውሉ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአንድነት ፡ ባለዕዳ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ የሚከፍሉትን ፡ ዕዳ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ትክክል ፡ ድርሻቸውን ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፰ ። ስለ ፡ ጥያቄ ።**

(፩) ሊከፍለው ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ አብልጦ ፡ የከፈለ ፡ የአንድነት ፡ ባለዕዳ ፤ አብልጦ ፡ ስለ ፡ ከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ሌሎችን ፡ የያንዳንዳቸውን ፡ ድርሻ ፡ እንዲከፍሉት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከአንድነት ፡ ባለዕዳዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕዳው ፡ በየአንዳንዳቸው ፡ ላይ ፡ ሊደርስባቸው ፡ በሚገባው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ይከፋፈላል ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፱ ። ስለ ፡ መዳረግ ፡ (ድርጎ) ።**

(፩) ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ የአንድነት ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ለባለገንዘቡ ፡ በከፈለው ፡ ልክ ፡ በባለገንዘቡ ፡ መብት ፡ ተዳራጊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ገንዘቡን ፡ ለከፈለው ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳ ፡ ማስረጃዎቹንና ፡ ወደፊትም ፡ ለሚያደርገው ፡ ጥያቄ ፡ የሚጠቅሙትን ፡ አሠራር ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲችል ፡ ባለገንዘቡ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፫) ከባለገንዘቡ ፡ ተግባር ፡ የቀነሣ ፤ በባለገንዘቡ ፡ ስም ፡ የአንድነት ፡ ባለዕዳው ፡ ለመዳረግ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በባለገንዘቦቹ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ አንድነት ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፲። አንድነት ፡ ስለሚገኝበት ፡ ጊዜ ።**

ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለና ፡ እንደዚሁም ፡ በሕጉ ፡ የተወሰነ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ በባለገንዘቦቹ ፡ መካከል ፡ አንድነት ፡ የለም ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፲፩ ። የአንድነት ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ።**

(፩) አንድነት ፡ ካላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ የአንዳንዱ ፡ ባለዕዳው ፡ ዕዳውን ፡ በሙሉ ፡ እንዲከፍለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) አንድነት ፡ ካላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ ለአንዱ ፡ የተከፈለ ፡ ዕዳ ፡ ባለዕዳውን ፡ ነጻ ፡ ያደርገዋል ።

(፫) አንድነት ፡ ካላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ መካከል ፡ ከአንዱ፡ማስጠንቀቂያ ፡ ካልደረሰው ፡ ባለዕዳው ፡ እንደ፡ፈቀደ፡ለአንዱ፡ወይም ፡ ለሌላው ፡ ለመክፈል ፡ ምርጫ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፪ ። ስለ ፡ ይርጋ ።**

አንድነት ፡ ካላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ መካከል ፡ ለአንዱ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠሩን ፡ የሚያቋርጥ ፡ ተግባር ፤ ለሌሎችም ፡ ባለገንዘቦች ፡ የይርጋውን ፡ ዘመን ፡ ያቋርጥላቸዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፫ ። ዕዳን ፡ ስለ ፡ መማር ።**

አንድነት ፡ ካላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ባለዕዳውን ፡ የማረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የተደረገው ፡ ምሕረት ፡ ባለዕዳውን ፡ ለዚሁ ፡ ባለገንዘብ ፡ ከሚደርሰው ፡ ድርሻ ፡ እንጂ ፤ ከሌሎቹ ፡ ዕዳ ፡ ነጻ ፡ አያወጣውም ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፬ ። ስለ ፡ መተካት ።**

እንዲሁም ፡ በአንድ ፡ ባለገንዘብና ፡ በባለዕዳው ፡ መካከል ፡ ስለሚደረገው ፡ የመተካት ፡ ስምምነት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተደነገገው ፡ ይጸናል ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፭ ። ስለ ፡ ማቻቻል ።**

ባለዕዳው ፡ አንድነት ፡ ካላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ መካከል ፡ ከአንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለሌሎች ፡ አንድነት ፡ ለአላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ የተቻቻለውን ፡ ገንዘብ ፡ መከራከሪያ ፡ ማድረግ ፡ የሚችለው ፡ የተቻቻለው ፡ ገንዘብ ፡ በመጨረሻው ፡ ላቻቻለው ፡ ባለገንዘብ ፡ የሚጠቅም ፡ ሲሆንና ፤ በዚያውም ፡ ልክ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፮ ። የመጨረሻ ፡ አከፋፈል ።**

(፩) በውሉ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ አንድነት ፡ ያላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ ባለዕዳው ፡ ከከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ትክክል ፡ ድርሻ ፡ መቀበል ፡ አለባቸው ።

(፪) ከድርሻው ፡ በላይ ፡ የወሰደ ፡ ባለገንዘብ ፡ በብልጫ ፡ ስለ ፡ ወሰደው ፡ ነገር ፡ ለሌሎቹ ፡ ባለገንዘቦች ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለማይከፋፈሉ ፡ ግዴታዎች ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፯ ። (ሀ)አለመከፋፈል ።**

አንድነት ፡ ለአላቸው ፡ ግዴታዎች ፡ የተወሰኑት ፡ ደንቦች ፡ ከጕዳዩ ፡ የተነሣ ፡ የማይከፋፈል ፡ በሆነው ፡ ግዴታ ፡ ላይም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፬፻፲፰ ። (ለ) የባለዕዳዎች ፡ ብዙ ፡ መሆን ።**

(፩) ግዴታዎቹ ፡ በሙሉ ፡ የአንድነት ፡ አላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ያልሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆንና ፡ የማይከፋፈሉ ፡ ያልሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግዴታው ፡ በዕዳው ፡ ተጠያቂ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ።

(፪) እያንዳንድ ፡ ባለዕዳዎች ፡ በሚደርስባቸው ፡ ልክና ፡ በውሉ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፤ ለተወሰነባቸው ፡ ሌላ ፡ የዕዳ ፡ ድርሻ ፡ ይጠየቃሉ ፡ (ይያዛሉ) ።

(፫) ከባለዕዳዎቹ ፡ አንደኛው ፡ ለዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ ለመክፈል ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በዋስትናው ፡ የሚገደድበት ፡ ደንብ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፱፻፲፱ ። (ሐ) የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ብዙ ፡ መሆን ።

(፩) ግዴታው ፡ የአንድነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ ያልሆነና ፡ በዐይነቱም ፡ ሁኔታ ፡ የማይከፋፈል ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሚደርሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ብቻና ፡ በውል ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተወሰነለትን ፡ ድርሻ ፡ ብቻ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፩ ። ዋስትና ።

ቍ ፡ ፲፱፻፳ ። የዋስትና ፡ መሠረት ።

ለግዴታው ፡ አፈጻጸም ፡ ዋስ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ባለዕዳው ፡ ግዴታውን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለባለገንዘቡ ፡ ይህን ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጽም ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፲፱፻፳፩ ። ስለ ፡ ባለዕዳው ፡ ፈቃድ ።

ባለዕዳው ፡ ሳይጠይቅ ፤ ወይም ፡ ሳያውቅም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ለሱ ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፲፱፻፳፪ ። ስለ ፡ ዋስትና ፡ ፎርም ።

(፩) በሕሊና ፡ ግምት ፡ ብቻ ፡ ዋስትና ፡ እንዳለ ፡ አይቈጠርም ።

(፪) ዋስትና ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ እንደዚሁም ፡ ከተደረገው ፡ ውል ፡ ወሰን ፡ ለማለፍ ፡ አይችልም ።

(፫) ለግዴታው ፡ ዋስ ፡ የሆነበት ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ ካልተገለጸ ፡ ዋስትናው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፱፻፳፫ ። የዋናው ፡ ግዴታ ፡ ፈራሽ ፡ መሆን ።

(፩) ዋስትና ፡ በማይጸና ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ።

(፪) በተዋዋዩ ፡ የፈቃድ ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ በውሉ ፡ የመጣው ፡ ዕዳ ፡ ባለዕዳውን ፡ የማያስገድደው ፡ ቢሆንም ፡ ዋሱ ፡ ባለዕዳው ፡ ውል ፡ ለመግባት ፡ የማይችልበትን ፡ ጕድለት ፡ እያወቀ ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋስትናው ፡ ሊጸናበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፱፻፳፬ ። የዋስትና ፡ ወሰን ።

(፩) ዋስነት ፡ ባለዕዳው ፡ ሊከፍለው ፡ ከሚገባው ፡ ነገር ፡ በላይ ፡ ወይም ፡ የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ወጪ ፡ በሚያመጣ ፡ ሁኔታ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

BACK



(፪) ዋስነት ፡ ከዕዳው ፡ በከፊል ፡ ብቻና ፡ ያነሰ ፡ ወጪ ፡ በሚያመጣ ፡ ሁኔታ ፡ ለመ ስማማት ፡ ይቻላል ።

(፫) ከዕዳው ፡ በላይ ፡ ወይም ፡ በበለጠ ፡ ከባድ ፡ ወጪ ፡ ሁኔታ ፡ የተደረገ ፡ ዋስ ነት ፤ በዋናው ፡ ግዴታ ፡ መጠን ፡ ይቀነሳል ፡ እንጂ ፤ ፈራሽ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፳፭። ለወደፊት ፡ ስለሚሆን ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚመጣ፡ ግዴታ ።

(፩) ወደፊት ፡ ለሚሆን ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ለሚመጣ ፡ ግዴታ ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ።

(፪) ዋስነቱ ፡ ለስንት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚረጋ ፡ በስምምነቱ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ የዋናው ፡ ዕዳ ፡ ተጠያቂነት ፡ ካልደረሰ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዋሱ ፡ ዋስትናውን ፡ ሊያስቀር ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፳፮ ። ስለ ፡ ዕዳ ፡ መቅረት ።

(፩) ዋናው ፡ ዕዳ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቀሪ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋሱ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

(፪) ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ መቃወሚያ ፡ አያደርጋቸውም ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ሳይቻል ፡ ባለዕዳው ፡ ባለገንዘቡን ፡ በሚቃወምባቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ዋሱ ፡ ሊከራከ ርባቸው ፡ ይችላል ።

(፫) ነገሩን ፡ እያወቀ ፡ ውል ፡ የገባ ፡ ዋስ ፡ ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ግዴታ ፡ የገባው ፡ የፈቃድ ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ውሉ ፡ ፍርስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፳፯ ። ዕዳን ፡ በተለዋጭ ፡ ስጦታ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

ባለገንዘቡ ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ወዶ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተቀበለው ፡ ዕቃ ፡ በክርክር ፡ ቢወ ሰድበትም ፡ ዋሱ ፡ ነጻ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ይቀራል ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፳፰ ። በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) ውሉ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በባለገንዘቡና ፡ በባለዕዳው ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ሌላ ፡ ውል ፡ የዋሱን ፡ ግዴታ ፡ ሊያብስበት ፡ አይችልም ።

(፪) ለዕዳ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ አራዝሞ ፡ የመስጠትን ፡ ጕዳይ ፡ በተለይ ፡ ዋሱን ፡ ሳያስፈቅድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለባለዕዳው ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜ ፡ አራዝሞ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋሱ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፳፱ ፡ ስለ ፡ ይርጋ ።

በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ላይ ፡ የተጀመሩ፡ክሶች ፡ ለዋሱ ፡ መቈጠር ፡ የተጀመረለትን ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ያቋርጡበታል ።

**ቊ ፡ ፲፱፻፳፭ ። ስለ ፡ ወለድ ።**

ዕዳን ፡ ለመክፈል ፡ ዋስ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ዕዳው ፡ ወለድ ፡ የሚያስከፍል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ለወለዱም ፡ እንደ ፡ ተዋስ ፡ ይቈጠራል ።

**ቊ ፡ ፲፱፻፳፮ ። ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ወጪ ።**

በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ደርሶት ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ዕዳውን ፡ ካልከፈለ ፤ ዋሱ ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ከተወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ በዋሱም ፡ ላይ ፡ ለቀረበው ፡ ክስ ፡ የዳኝነት ፡ ወጪ ፡ ተገዳጅ ፡ ይሆናል ።

**ቊ ፡ ፲፱፻፳፯ ። ዕዳ ፡ ስለሚከፈልበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) ከባለዕዳው ፡ መክሠር ፡ የተነሣ ፤ ዕዳው ፡ በቶሎ ፡ እንዲከፈል ፡ ቢጠየቅም ፡ እንኳ ፡ ዋናው ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፈል ፡ ከተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ዋሱን ፡ ዕዳውን ፡ እንዲከፍል ፡ ማስገደድ ፡ አይቻልም ።

(፪) የዋናው ፡ ዕዳ ፡ አከፋፈል ፡ በአንዱ ፡ በተቀዳሚ ፡ ማስታወቂያ ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ተቀዳሚ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለዋሱም ሊሰጠው ፡ ይገባዋል ።

(፫) ዕዳው ፡ በሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ ማስታወቂያ ፡ በዋሱ ፡ ላይ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ማስታወቂያው ፡ ከደረሰው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፲፱፻፳፰ ። አንድነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዋስትና ።**

(፩) ዋሱ ፤ አንድነት ፡ በሆነ ፡ ዋስትና ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ተመሳሳይነት ፡ ስም ፡ በመሆን ፤ ከዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ጋራ ፡ የሚገደድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለገንዘቡ ፡ ለዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ በዋሱ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ማቅረብና ፡ በእጁ ፡ ያለውንም ፡ መያዣ ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንድነት ፡ በሆነ ፡ ዋስትና ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቊ ፡ ፲፱፻፳፱ ። ስለ ፡ ተራ ፡ ዋስትና ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ቊጥር ፡ ውጭ ፡ ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ግዴታውን ፡ የማይፈጽም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋሱ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ እንዲከፍለው ፡ አይገደድም ።

(፪) ዋሱ ፤ በዋስትና ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ እንዲከፍል ፡ በባለገንዘቡ ፡ ከመገደዱ ፡ በፊት ፡ ባለገንዘቡ ፡ በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ እንዲከራከርና ፡ በተለይም ፡ ከባለዕዳው ፡ ሀብቶች ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለውን ፡ ሸጦ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

ቍ፡ሺ፱፻፹፭።ከዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ተከራክር ፡ የማለት ፡ መብት ።

(፩) ዋሱ ፡ እንደ ፡ ተከሰሰ ፡ ወዲያውኑ ፡ ባለገንዘቡን ፡ ከባለዕዳው ፡ ጋራ ፡ ተከራከር ፡ ካላለ ፡ በቀር ፡ ባለገንዘቡ ፡ ከዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ጋራ ፡ ለመከራከር ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ።

(፪) የባለዕዳው ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፡ ባለገንዘቡ ፡ ከባለዕዳው ፡ ጋራ ፡ እንዲከራከር ፡ ዋሱ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ፡ሺ፱፻፹፮። መከራከር ፡ የሚቻልባቸው ፡ ንብረቶች ።

(፩) ክርክሩን ፡ የሚጠይቀው ፡ ዋስ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የዋናውን ፡ ባለዕዳ ፡ ንብረ ቶች ፡ መምራትና ፡ ለዚሁም ፡ ክርክር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ በቂ ፡ ወጪ ፡ አስ ቀድሞ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሲሆን ፡ ዋሱ ፡ ዕዳው ፡ ከሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ውጭ ፡ ያሉትን ፤ ወይም ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ ተሰጥተው ፡ በእጁ ፤ የማይገኙትን ፡ የዋናውን ፡ ባለዕዳ ፡ ንብረቶች ፡ መምራት ፡ አይገባውም።

ቍ፡ሺ፱፻፹፯፡ ክስን ፡ ስላለማቅረብ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ እንደተባለው ፡ የተፈቀዱትን ፡ ንብረ ቶች ፡ ዋሱ ፡ ካሳየና ፡ ለክርክሩም ፡ አስፈላጊውን ፡ ወጪ ፡ ከከፈለ ፡ ዋናው ፡ ባለ ዕዳ ፡ ሳይከሰስ ፡ በመቈየቱ ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለገንዘቡ ፡ በተመለከቱት ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ለዋሱ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቍ፡ሺ፱፻፹፰።በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ።

(፩) ዋናው ፡ ግዴታ ፡ ተጠያቂ ፡ ሲሆን ፤ ባለገንዘቡ ፡ በስድስት ፡ ሳምንቶች ፡ ውስጥ ፡ ከባለዕዳው ፡ ላይ ፡ የመብቶቹን ፡ አፈጻጸም ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ክስ ፡ እንዲ ያቀርብ ፡ ዋሱ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ዋሱ ፡ የነገረውን ፡ ባለገንዘቡ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ ወይም ፡ ክሱን ፡ በሚገባ ፡ ትጋት ፡ ያልቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋሱ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ፡ሺ፱፻፹፱። ዕዳን ፡ ልክፈል ፡ ስለ ፡ ማለት ።

(፩) ዋናው ፡ ግዴታ ፡ ተጠያቂ ፡ ሲሆን ፤ ዋሱ ፡ የሚከፍለውን ፡ ዕዳ ፡ እንዲቀበለው ፡ ባለገንዘቡን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ባለገንዘቡ ፡ የሚከፍለውን ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በዋስትና ፡ የተሰጡትን ፡ መያዣዎች ፡ አልመልስም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋሱ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ፡ ሺ፱፻፺። ዋሱ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ።

(፩) ባለዕዳው ፡ ዐውቆት ፡ ወይም ፡ ሳያውቀው ፡ በተደረገው ፡ ዋስትና ፤ ዕዳን ፡ የከፈለ ፡ ዋስ ፡ በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ላይ ፡ ክስን ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ አለው ።

BACK



(፪) ይህ ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፤ ስለ ፡ ወለዱና ፡ ስለ ፡ ወጪውም ፡ ጭምር ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፫) ስለ፡ሆነም ፡ ዋሱ ፡ የቀረበበትን ፡ ክስ ፡ ለዋናው ፡ ባለዕዳ፡ካስታወቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ባለው ፡ ኪሣራ ፡ ብቻ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ወጪ ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፺፩ ። ስለ ፡ ኪሣራ ።

(፩) ዋሱ ፡ ዕዳውን ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የከፈለው ፡ በባለዕዳው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፤ ቸልተኛነት ። የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የኪሣራውም ፡ ልክ ፡ የሚወሰነው ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፪ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፺፪ ። የጥያቄ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማጣት ።

(፩) ከግዴታው ፡ ዐይነት ፡ የተነሣ ፡ እንዲቀሩ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለገንዘቡን ፡ መከራከሪያ ፡ እንዲሆኑት ፡ ለባለዕዳው ፡ የተሰጡት ፡ ሁሉ ፡ ዋሱ ፡ እንዲሠራባቸው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ አለው ።

(፪) እነዚህን ፡ መከራከሪያዎች ፡ ሳይሠራባቸው ፡ የቀረ ፡ ዋስ ፡ እንዳይከፍል ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉትን ፡ የተሰጡትን ፡ የጥያቄ ፡ መብቶች ፡ ያጣል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ ጥፋት ፡ ሳይኖር ፡ መከራከሪያዎች ፡ መኖራቸውን ፡ ላለማወቁ ፡ ማስረጃ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የማጣቱ ፡ ደንብ ፡ አይጸናበትም ።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፺፫ ። ሁለተኛ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ዋሱ ፡ መክፈሉን ፡ ሳይነግረው ፡ ቀርቶ ፡ ባለዕዳው ፡ ሁለተኛ ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋሱ ፡ የከፈለውን ፡ ከባለዕዳው ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) ባለገንዘቡን ፡ በማይገባ ፡ የተቀበለውን ፡ መልስ ፡ ብሎ ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፺፬ ። ስለ ፡ መዳረግ ፡ (ዳረጎት) ።

(፩) ዋሱ ፡ በከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በባለገንዘቡ ፡ መብት ፡ ተዳራጊ ፡ ሆኖ ፡ ይገባል ።

(፪) የዚህን ፡ ጥቅም ፡ መብት ፡ ለመተው ፡ አስቀድሞ ፡ መዋዋል ፡ አይፈቀድም ።

ቍ ፡ ፲፻፱፻፺፭ ። የባለገንዘቡ ፡ ግዴታዎች ።

ባለገንዘቡ ፡ የማስረጃ ፡ ሰነዶችን ፡ እንዲያስረክብ ፤ እንደዚሁም ፡ አቤቱታን ፡ ለማቅረብ ፡ ሊረዱት ፡ የሚችሉትን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥርዐት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ደንቦች ፡ እንዲሞላና ፡ ስለ ፡ ገንዘቡም ፡ የተያዙት ፡ መያዣዎች ፡ እንዲሸጡ ፡ ዕዳውን ፡ ለከፈለው ፡ ዋስ ፡ አስፈላጊውን ፡ እንዲያደርግለት ፡ ይገደዳል ።

BACK



**ቍ፡ ፲፻፸፮ ። የማይቻል ፡ ዳረጎት ።**

ከባለገንዘቡ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ዋሱ ፡ በባለገንዘቡ ፡ መብቶች ፤ መያዣ ዎች ፤ ልዩ ፡ መብቶች ፡ በተዳራጊነት ፡ ሊገባ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በባለገንዘቡ ፡ ዘንድ ፡ ካለበት ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

**ቍ፡ ፲፻፸፯ ። የባለዕዳው ፡ መክሠር ።**

(፩) ባለዕዳው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቡ ፡ የኪሣራውን ፡ ሥራ ፡ ለተቀ በለው ፡ ሰው ፡ የገንዘቡን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ ባለገንዘቡ ፡ የባለዕዳውን ፡ መክሠር ፡ እንዳወቀ ፤ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ ለዋሱ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሳይከበሩ ፡ ቢቀሩ ፡ ባለገንዘቡ ፡ የዚሁኑ ፡ አሠራር ፡ ካለመፈጸሙ ፡ የተነሣ ፡ ስለሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ በዋሱ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብ ቶች ፡ በደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ያጣል ።

**ቍ፡ ፲፻፸፰ ። ለዋሱ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማረጋገጫ ።**

ዋሱ ፡ ከመክፈሉ ፡ በፊት ፡ ቢሆንም ፤ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ክስን ፡ ለማቅረብና ፡ ከባለዕዳውም ፡ የማረጋገጫ ፡ ዋስትናዎችን ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ሦስት ፡ ነገሮች ፡ ባጋጠሙት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(ሀ) ባለዕዳው ፡ ዕዳውን ፡ እንዲከፍል ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ደርሶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የባለዕዳው ፡ መክሠር ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ባለዕዳው ፡ በደረሰበት ፡ ኪሣራ ፡ ወይም ፡ ከኪሣራው ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ዋሱ ፡ በዋስትና ፡ ከገባበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚደር ስበት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ፡ ፲፻፸፱ ። የጠለፋ ፡ ዋስ ።**

ስለ ፡ ዋናው ፡ ዋስ ፡ የሚደረገው ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፤ በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርቡት ፡ አቤቱታዎች ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፹ ። የዋስ ፡ አረጋጋጭ ።**

(፩) ለዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ዋስም ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ።

(፪) ለዋስ ፡ አረጋጋጩ ፡ ከዋሱ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፤ የተራው ፡ ዋስ ፡ ግን ኙነት ፡ ከባለዕዳው ፡ ጋራ ፡ እንዳለው ፡ ግንኙነት ፡ ነው ።

(፫) በዋናው ፡ ባለዕዳና ፡ በዋሱ ፡ መካከል ፡ የሚሆነው ፡ የመብት ፡ መቀላቀል ፡ ባለገንዘቡን ፡ ባረጋጋጭ ፡ ዋስ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የክስ ፡ መብት ፡ አያስቀር በትም ።

ቍ፡ ሺ፱፻፶፩። ብዙ፡ ሰዎች፡ ዋስ፡ ስለ፡ መሆናቸው።

(፩) ለአንድ፡ ባለዕዳ፡ ለአንድ፡ ዕዳ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ በአንድ፡ ጊዜ፡ ዋስ፡ የሆኑ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ለየድርሻቸው፡ እንደ፡ ተራ፡ ዋሶች ፤ ለሌሎቹ፡ ዋሶች፡ እንደ፡ አረጋጋጭ፡ ዋስ፡ ሆነው፡ ይገደዳሉ።

(፪) ዋሶቹ፡ ተከታታይ፡ በሆኑ፡ ስምምነቶች፡ ዋስ፡ ሆነው፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በሁለተኛው፡ ጊዜ፡ ዋስ፡ የሆነው፡ ሰው፡ ከሱ፡ አስቀድሞ፡ ዋስ፡ ለሆነው፡ ሰው፡ እንደ፡ አረጋጋጭ፡ ዋስ፡ ተቈጥሮ፡ ይገደዳል።

(፫) ከዋና፡ ባለዕዳ፡ ጋራ፡ በመሆንም፡ ሆነ ፤ እርስ፡ በርሳቸው፡ በመሆንም፡ ሆነ ፤ ዋሶቹ፡ በአንድነት፡ ዋስ፡ የሆኑ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ስለ፡ ሌሎቹ፡ ድርሻ፡ የመጠየቁ፡ መብት፡ ሳይነካ፡ እያንዳንዳቸው፡ ስለ፡ መላው፡ ዕዳ፡ ተገዳጆች፡ ይሆናሉ።

## ምዕራፍ፡ ፮።

### ከውሉ፡ ጋራ፡ ግንኙነት፡ ስላላቸው፡ ሦስተኛ፡ ወገኖች።

ቍ፡ ሺ፱፻፶፪። ውሎችን፡ የሚመለከት፡ ጉዳይ፡ ስለሚያስከትለው፡ ውጤት።

(፩) በዚህ፡ ሕግ፡ ተለይቶ፡ የተመለከተ፡ ካልሆነ፡ በቀር፡ ውሎች፡ ውጤት፡ ያላቸው፡ በተዋዋሏቸው፡ ወገኖች፡ መካከል፡ ነው።

(፪) ከውሉ፡ ውጭ፡ ስለሚደርስ፡ አላፊነት፡ የተነገሩት፡ የዚህ፡ ሕግ፡ ድንጋጌዎች፡ የተጠበቁ፡ ናቸው።

(፫) እንደዚሁም፡ ስለ፡ እንደራሴነት፡ የተነገሩት፡ ድንጋጌዎች፡ የተጠበቁ፡ ናቸው።

### ክፍል፡ ፩።

### ስለ፡ ሌላ፡ ሰው፡ ሆኖ፡ የሚሰጥ፡ ተስፋና፡ የሚደረግ፡ ውል።

ቍ፡ ሺ፱፻፶፫። የትእዛዝ፡ ቃል፡ አሰጣጥ።

አንድ፡ ውል፡ በሚፈጸምበት፡ ጊዜ፡ ከተዋዋዮቹ፡ አንደኛው፡ ወገን ፤ በራሱ፡ ምትክ፡ ሌላ፡ ሰው፡ ተተክቶ፡ በውሉ፡ ላይ፡ የተመለከተውን፡ መብት፡ እንዲሠራበት፡ ከውሉም፡ የሚመጣውን፡ ግዴታ፡ እንዲፈጽም፡ የማድረግ፡ ችሎታ፡ እንዲኖረው፡ ሊስማማ፡ ይችላል።

ቍ፡ ሺ፱፻፶፬። ውጤት።

(፩) በዚህ፡ ዐይነት፡ የታሰበው፡ የሌላ፡ ሰው፡ በውሉ፡ የመጠቀስ፡ ጉዳይ፡ በሦስት፡ ቀን፡ ውስጥ፡ ተደርጎ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የውሉ፡ ውጤት፡ በእንደራሴነት፡ ሥልጣን፡ እንደ፡ ተፈጸመ፡ ሆኖ፡ ይቈጠራል።

(፪) ሰውዬውን፡ በውሉ፡ ላይ፡ የመጥቀሱ፡ ጉዳይ፡ በተወሰነው፡ ሦስት፡ ቀን፡ ውስጥ፡ ሳይፈጸም፡ የቀረ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ውሉ፡ ውጤቱን፡ የሚያገኘው፡ በሁለቱ፡ ወገን፡ ዋና፡ ተዋዋዮች፡ መካከል፡ ነው።

ቍ፡ ሺ፱፻፶፭። መጪውን፡ እመልሳለሁ፡(አጠናለሁ)፡ ስለ፡ ማለት።

ሦስተኛው፡ ሰው፡ ተግባሩን፡ የሚፈጽም፡ ለመሆኑ ፤ መጪውን፡ እመልሳለሁ፡ ብሎ፡ ግዴታ፡ ለመግባት፡ ይችላል።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፶፮ ። እመልሳለሁ ፡ ማለት ፡ የሚያስከትለው ፡ ነገር ።**

(፩) እመልሰዋለሁ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ስለ፡እርሱ ፡ የገባለትን ፡ ግዴታ ፡ ያጸደቀው፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እመልሳለሁ ፡ ባዩ ፡ ነጻ ፡ ይወጣል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እመልሳለሁ ፡ ባዩ ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ ዋስ ፡ አይደለም ።

(፫) እመልሰዋለሁ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ያላጸደቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ ውል ፡ አለመፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ላይ ፡ ስለሚያ ደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ተጠያቂ ፡ የሚሆነው ፡ እመልሳለሁ ፡ ባዩ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፶፯ ። ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መዋዋል ።**

በአንድ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ልፈጽም ፡ እችላለሁ ፡ ብሎ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፶፰ ፡ የተዋዋዩ ፡ መብት ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፤ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሆኖ ፡ የተዋዋለው፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ለተመለከቱት ፡ ውል ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ የመምረጥ፡ መብት ፡ ያልተሰጠው ፡ ከሆነ ፡ ወይም ፡ ይኸው ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ከውሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ የማይፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጠ ፤ ከውሉ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ለራሱ ፡ ለማስቀረት ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ውል ፡ ስም ምነት ፡ በሚያስገኘው ፡ ትርፍ ፡ የሚጠቀም ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ሰው ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ይህንን ፡ ጥቅም ፡ ፈቅዶ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተስፋ ፡ ሰጪው ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ የማይፈጽም ፡ ሲሆን ፡ ተዋዋዩ ፡ በውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ ሊያገኝ ፡ የሚገባው ፡ ጥቅም ፡ እንዲከፈለው ፡ ክርክር ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፶፱ ። የባለጥቅሙ ፡ ምርጫ ።**

ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ በውል ፡ ስምምነት ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፤ በውሉ ፡ ስምምነት፡ መሠረት ፡ የመራጭነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህን ፡ ስምምነት ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ፈለገው ፡ የመቀበል ፡ ወይም ፡ ያለመቀበል ፡ ምርጫ ፡ ለማድረግ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፷ ። የተዋዋዩ ፡ ወራሾች ።**

(፩) ተስፋ ፡ ሰጪው ፤ በውሉ ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባው ፤ ተዋዋዩ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተዋዋይ ፡ በውሉ ፡ እንዲጠቀም ፡ ያመለ ከተው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ለመጠቀም ፡ መፍቀዱን ፡ ከገለጸ ፡ ተዋዋዩ ፡ በሞ ተበት ፡ ጊዜ ፡ የተሰጡት ፡ መብቶች ፡ በተስፋ ፡ ሰጪው ፡ ላይ ፡ ይኖሩታል ።

(፪) የተዋዋይ ፡ ወራሾች ፡ ተዋዋዩ ፡ በውሉ ፡ ትርፍ ፡ ሊጠቀም ፡ ይችላል ፡ ሲል፡ ሟቹ ፡ ተጠቃሚውን ፡ በማመልከት ፡ ቃል ፡ የሰጠለትን ፡ ሰው ፡ ለመለወጥ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፹፩ ። የተጠቃሚው ፡ መብቶች ።

(፩) ተጠቃሚው ፡ የውሉን ፡ ስምምነት ፡ የተቀበለው ፡ ሲሆን ፤ በተስፋ ፡ ሰጪው ፡ ላይ ፡ ውሉ ፡ የሚያስገኛቸውን ፡ መብቶች ፡ በማይመለስ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቀራል ።

(፪) ተስፋ ፡ ሰጪው ፡ በተዋዋዩ ፡ ላይ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ በተለይ ፡ የራሱ ፡ የሆኑትን ፡ መከራከሪያዎች ፡ ሰበብ ፡ በማድረግ ፡ በተጠቃሚው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርግበት ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የገንዘብ ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ስለ ፡ መዳረግ ፡ (ዳረጎት) ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፹፪ ። የገንዘብን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

የገንዘብ ፡ መብትን ፡ ማስተላለፍ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ካልተከለከለ ፡ ወይም ፡ የጒዳዩ ፡ ተፈጥሮ ፡ ካላገደው ፡ በቀር ፤ የባለዕዳው ፡ ፈቃጅነት ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ባለገንዘቡ ፡ መብቱን ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፹፫ ። የማስተላለፉ ፡ መጠን ።

ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩ ፡ የወለድ ፡ ገንዘቦችም ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተላለፉ ፡ ይቈጠራሉ ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፹፬ ። ዋቢነት ።

(፩) የገንዘቡ ፡ መብት ፡ መተላለፍ ፡ የተደረገው ፡ በዋጋ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አስተላላፊው ፡ በሚያስተላልፍበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ መኖር ፡ ዋቢ ፡ ይሆናል ።

(፪) በግልጽ ፡ ግዴታ ፡ ካልገባ ፡ በቀር ፡ አስተላላፊው ፡ ለባለዕዳው ፡ መክፈል ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

(፫) የገንዘቡ ፡ መብት ፡ መተላለፍ ፡ ያለዋጋ ፡ ሲሆን ፡ አስተላላፊው ፡ ለገንዘቡ ፡ መኖር ፡ እንኳ ፡ ዋቢ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ሺ፬፻፹፭ ። የዋቢነት ፡ ወሰን ።

(፩) መብቱን ፡ አስተላላፊው ፡ በዋቢነት ፡ ተገዳጅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በመብት ፡ ተቀባዩ ፡ በኩል ፡ የሚገደደው ፡ በተቀበለው ፡ በዋናው ፡ ገንዘብና ፡ በወለዱ ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ በቀር ፡ የመብት ፡ ማስተላለፊያውን ፡ ወጪና ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ ሳያገኝ ፡ የቀረውን ፡ ለክሱ ፡ ኪሣራም ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፷፮ ። መቃወሚያ ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ።

(፩) ባለዕዳው ፤ የገንዘቡ ፡ ማስከፈል ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተላልፎ ፡ መስጠቱን ፡ ባወቀበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረውና ፡ ሊያቀርባቸው ፡ በሚችለው ፡ የመቃወሚያ ፡ ነገሮች ፡ መብት ፡ አስተላላፊውን ፡ ሊቃወም ፡ ይችል ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ሁሉ ፡ መብት ፡ ተቀባዩን ፡ ሊቃወምባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) መብቱን ፡ ከሚያስተላልፈው ፡ ባለገንዘብ ፡ ላይ ፡ ባለዕዳው ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሰ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መብቱ ፡ ከተላለፈለት ፡ ሰው ፡ እንዲቻቻልለት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ የገንዘቡ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ መብቱ ፡ ከተላለፈ ፡ ወዲህ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፷፯ ። ባለዕዳው ፡ የሚያቀርበው ፡ መቃወሚያ ።

(፩) የዕዳ ፡ ማስከፈሉን ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የመተላለፉ ፡ ጉዳይ ፡ በመብት ፡ አስተላላፊው ፡ ወይም ፡ በመብት ፡ ተቀባዩ ፡ በኩል ፡ ለባለዕዳው ፡ ከመገለጹ ፡ በፊት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ዕዳውን ፡ ለመብት ፡ ሰጪው ፡ አስቀድሞ ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለዕዳው ፡ በሚገባ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

(፪) የዚያው ፡ የአንዱ ፡ ዐይነት ፡ ዕዳ ፡ ማስከፈል ፡ መብት ፡ ተከታትሎ ፡ ለብዙ ፡ መብት ፡ ተቀባዮች ፡ ተላልፎ ፡ የተሰጣቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መብቱ ፡ ተላልፎ ፡ መሰጠቱን ፡ ለባለዕዳው ፡ መጀመሪያ ፡ ላስታወቀት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ ባለበት ፡ ጽሑፍ ፡ እከፍላለሁ ፡ ብሎ ፡ ባለዕዳው ፡ ለተቀበለው ፡ ሰው ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ባለዕዳው ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ መብቱ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ መብቱ ፡ የተላለፈልኝ ፡ ከሁሉ ፡ ቀደምትነት ፡ ባለው ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለሚከራከረው ፡ ወገን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፷፰ ። ባለገንዘቡ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ዳረጎት ፡ (ድርጎ) ።

(፩) ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ባለገንዘቡ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በራሱ ፡ መብቶች ፡ ተዳራጊ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

(፪) የዳረጎቱ ፡ ጉዳይ ፡ ግልጽ ፡ መሆንና ፡ የገንዘቡ ፡ መክፈል ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ወዲያውኑ ፡ መፈጸም ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፷፱ ። ባለዕዳው ፡ የሚሰጠው ፡ ዳረጎት ፡ (ድርጎ) ።

ባለዕዳው ፤ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ ለመክፈል ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ ተበድሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመጀመሪያ ፡ አበዳሪ ፡ የነበረው ፡ ባይፈቅድም ፡ እንኳ ፡ ለዚሁ ፡ ለመጀመሪያው ፡ አበ

ዳሪ ፡ ሰጥቶት ፡ በነበረው ፡ መብት ፡ ይህን ፡ በመጨረሻ ፡ የተመለከተውን ፡ አበዳሪ ፡ ለመዳረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፸ ። የዳረጎት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) በባለዕዳው ፡ ፈቃጅነት ፡ የሚደረገው ፡ የዳረጎት ፡ ጉዳይ ፡ የሚጸናው ፡ የብድሩ ፡ ውል ፡ የተደረገበት ፡ ዘመን ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ ያለው ፡ ሲሆንና ፡ በብድር ፡ የተወሰደው ፡ ገንዘብ ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ተመደበ ፡ የተመለከተ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የገንዘቡ ፡ ደረሰኝ ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ እንዲኖረውና ፡ የተከፈለውም ፡ በመጨረሻ ፡ ከተበደረው ፡ ገንዘብ ፡ ለመሆኑ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ሊመለከትበት ፡ ይገባል ።

(፫) ባለዕዳው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እንዲጠቅስለት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ባለገንዘብ ፡ ከጠየቀው ፤ በሚሰጠው ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ጠቅሶ ፡ ለመጻፍ ፡ እንቢተኛ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፸፩ ። ሕጋዊ ፡ መዳረግ ፡ (ዳረጎት) ።**

በባለገንዘቡ ፡ መብቶች ፡ በተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በሕግ ፡ የሚተላለፈው ፡ ድርጎ ።

(ሀ) ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ሆኖ ፡ አንድ ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፍል ፡ በመገደድ ፡ ይህን ፡ ዕዳ ፡ ከፍሎ ፡ የጋራ ፡ ባለዕዳዎችን ፡ ድርሻ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የአንድ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ቀዳሚነት ፡ ባለው ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በልዩ ፡ መብት ፤ ወይም ፡ በመያዣ ፡ መብት ፡ (ሞርጌጅ) ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ላለው ፡ ባለገንዘብ ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በሌላዎችም ፡ በሕግ ፡ በተወሰኑ ፡ ጉዳዮች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፸፪ ። በከፊል ፡ የሚደረግ ፡ ክፍያ ።**

(፩) ድርጎ ፡ መዳረግ ፡ ገንዘቡ ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ የተመለሰለትን ፡ ባለገንዘብ ፡ ሊጎዳው ፡ አይችልም ።

(፪) ባለገንዘቡ ፡ ከተዳራጊው ፡ የተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ በከፊል ፡ ከሆነ ፡ ላልተከፈለው ፡ ለቀሪው ፡ ገንዘብ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በመብቶቹ ፡ ከተዳራጊው ፡ በቀዳሚነት ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፸፫ ። የማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ የዳረጎት ፡ ውጤት ።**

(፩) የተዳረገው ፡ ባለገንዘብ ፡ ወይም ፡ የባለገንዘብነት ፡ መብት ፡ የተላለፈለት ፡

BACK



ሰው ፡ በዕዳው ፡ ላይ ፡ በተሰጡት ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ በዋስትናዎች ፡ በሌሎችም ፡ ተጨማሪ ፡ መብቶች ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ መያዣውን ፡ ሰጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ ባለገንዘቡ ፡ በመያዣ ፡ ስም ፡ ተቀብሎት ፡ የነበረውን ፡ ሀብት ፡ የተዳረገው ፡ ሰው ፡ ከእጁ ፡ ሊያገባው ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፷፱ ። የዋነኛው፡ባለገንዘብ፡ግዴታዎች ።**

(፩) የዕዳ ፡ ማስከፈሉን ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ ወይም ፡ የገንዘቡን ፡ ክፍያ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የተቀበለ ፡ ባለገንዘብ ፡ የብድሩን ፡ ሰነድ ፡ ለተላለፈለት ፡ ወይም ፡ ለተዳራጊው ፡ ሊያስረክበውና ፡ ያሉትንም ፡ የማስረጃ ፡ ሰነዶች ፡ ሊያቀርብለት ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የሚጠይቃቸው ፡ መብቶቹ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ እንዲኖራቸው ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰጠው ፡ ይገደዳል ።

(፪) የዕዳው ፡ ማስከፈል ፡ መብት ፡ የተላለፈው ፡ ወይም ፡ ገንዘቡ ፡ የተመለሰለት፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ዕዳ ፡ መኖሩን ፡ የሚያረጋግጡትን ፡ በሁለት ፡ ምስክሮች ፡ የተፈረሙ ፡ ሰነዶች ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፸ ። የማይነኩ ፡ ጉዳዮች ።**

(፩) አንዳንድ ፡ መብቶችን ፡ የማስተላለፍ ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ በታዘዘው ፡ ዐይነት ፡ እንዲፈጸም ፡ ያስፈልጋል ፡ ተብሎ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተጠያቂው ፡ ሀብት ፡ በስሙ ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ላምጪው ፡ የሚከፈል ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራ ፡ ሰነድ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ሲሆን ፡ እንደዚህ ፡ ላለው ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠው ፡ ድንጋጌም ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የምትክ ፡ ውክልናና ፡ የዕዳ ፡ ማስተላለፍ ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፸፩ ። የምትክ ፡ ውክልና ፤ መሠረቱ ።**

በሕጉ ፡ ወይም ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ በባለገንዘቡ ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ ባለዕዳው ፡ ራሱ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽምለት ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሊወክል ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ሺ፱፻፸፪ ። የባለገንዘቡ ፡ መፍቀድ ፡ እቀበላለሁ ፡ ማለት ።**

(፩) በምትክ ፡ የተወከለውን ፡ ፈቅዶ ፡ የተቀበለ ፡ ባለገንዘብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ በዋነኛው ፡ ባለዕዳ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

BACK



(፪) ስለ፡ሆነም፡የምትክ ፡ ውክልና ፡ ሥልጣን ፡ የተቀበለውን ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ከመጠየቁ ፡ በፊት ፡ ዋነኛውን ፡ ባለዕዳ ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲከፍለው ፡ ሊጠይቀው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፱፻፸፫ ። የተወካዩ ፡ መፍቀድ ፡ (እቀበላለሁ ፡ ማለት) ።

ለሚወክለው ፡ ሰው ፡ ባለዕዳም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የልማድ ፡ አሠራር ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ተወካዩ ፡ የወኪልነቱን ፡ ሥልጣን ፡ እንዲቀበል ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፲፱፻፸፬ ። የውክልናውን ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መሻር ።

(፩) በምትክ ፡ የተወከለው ፡ ሰው ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ የምትክነቱን ፡ ሥልጣን ፡ ፈቅዶ ፡ ከተቀበለ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ዕዳ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ምትክ ፡ አድራጊው ፡ ከምትክነት ፡ ሥልጣኑ ፡ ሊሽረው ፡ አይችልም ።

(፪) ምትክ ፡ አድራጊው ፡ ከሞተ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ ተተኪው ፡ የምትክ ፡ አድራጊውን ፡ ግዴታ ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ የመክፈሉን ፡ ጉዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፱፻፸፭ ። የተተኪው ፡ መብቶች ።

(፩) ተተኪው ፡ ከምትክ ፡ አድራጊው ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ የግል ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በባለገንዘቡንና ፡ በምትክ ፡ አድራጊው ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ የግል ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ የሚኖራቸውን ፡ ልዩነት ፡ ያላቸውን ፡ መከራከሪያዎች ፡ በመጥቀስ ፡ ባለገንዘቡን ፡ ሊከራከረው ፡ አይችልም ።

(፪) ተተኪው ፡ በባለገንዘቡና ፡ በሱ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የግል ፡ ግንኙነት ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ሊኖር ፡ በሚችለው ፡ መቃወሚያ ፡ ሊከራከር ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፱፻፸፮ ። የተተኪው ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።

(፩) ባለዕዳው ፡ የዕዳውን ፡ መክፈል ፡ ሥልጣን ፡ ለተተኪው ፡ በማሳለፉ ፡ የተተኪውን ፡ መተካት ፡ ፈቅዶ ፡ ባለዕዳውን ፡ ነጻ ፡ ያወጣ ፡ ባለገንዘብ ፡ በስምምነታቸው ፡ ላይ ፡ የተገለጸ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተተኪው ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋነኛውን ፡ ባለዕዳ ፡ ሊጠይቀው ፡ አይችልም ።

(፪) ተተኪው ፡ የምትክነቱን ፡ ሥልጣን ፡ በተቀበለበት ፡ ጊዜ ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ባለገንዘቡ ፡ ዋነኛውን ፡ ባለዕዳ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችልበት ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀለት ፡ ይቈያል ።

ቍ ፡ ፲፱፻፸፯ ። ማረጋገጫዎች ።

ዋስ ፡ የሆኑና ፡ ለዕዳው ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆን ፡ ንብረታቸውን ፡ አሳፈ ፡ ያደረጉ ፡

ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የምትከነቱን ፡ ጕዳይ ፡ ፈቅደው ፡ የተቀበሉ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ተገዳጆች ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፲፻፺፫ ። ንብረትንና ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) አንድ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ካለው ፡ መብትና ፡ ከሚጠየቅበት ፡ ዕዳ ፡ ጋራ ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ግዢውን ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ እንዳስታወቀ ፡ ወይም ፡ በጋዜጣ ፡ እንደ ፡ ገለጸ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለባለገንዘቦቹ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) የቀድሞው ፡ ባለዕዳ ፡ ከአዲሱ ፡ ባለዕዳ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይቈያል ።

(፫) ይህም ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ መታሰቡን ፡ የሚጀምረው ፡ የመክፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ ለደረሰ ፡ ዕዳዎች ፡ የግዢው ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፤ ለሌሎች ፡ ዕዳዎች ፡ ደግሞ ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ከደረሰበት ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፺፬ ። የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መቀላቀል ።

ሁለት ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ (እንትረፕሪዞች) ፡ ያላቸውን ፡ መብትና ፡ የሚጠየቅባቸውን ፡ ዕዳ ፡ አንዱ ፡ ለአንደኛው ፡ በማስተላለፍ ፡ ተደራርበው ፡ በአንድነት ፡ በተቀላቀሉ ፡ ጊዜ ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ላይ ፡ ለሚጠየቀው ፡ ዕዳ ፡ አለፊ ፡ የሚሆነው ፡ አዲሱ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ (እንትረፕሪዝ) ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፺፭ ። የአንድ ፡ ማኅበር ፡ መቋቋም ።

(፩) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ የግል ፡ የነበረ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ (እንትረፕሪዝ) ፡ ወደ ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ኀላፊነቱ ፡ ወደ ፡ ተለየ ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፡ አፈጻጸሙ ፡ በላይኛው ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፪) አዲሱ ፡ ማኅበር ፤ ወደ ፡ ራሱ ፡ አጠቃሎ ፡ ለደረበው ፡ ማኅበር ፡ ዕዳ ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ወራሾች ፤ (የወገኖቹ ፡ ወራሾች) ።

ቍ ፡ ፲፻፺፮ ። መሠረቱ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገና ፡ ወይም ፡ የውሉ ፡ ተፈጥሮ ፡ ዐይነት ፡ የሚከለክል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የተዋዋዩ ፡ ወራሾች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በአውራሾቻቸው ፡ ስፍራ ፡ ከውሉ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፺፯ ። ስለ ፡ ሌላ ፡ ሆኖ ፡ መዋዋል ።

ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ በስምምነቱ ፡ ተጠቃሚው ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡

BACK



ከተቀበለ ፡ በኋላና ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወራሾቹ ፡ ተተክተው ፡ ይህ ፡ ውል ፡ በሚሰጠው ፡ ትርፍ ፡ ይጠቀማሉ ።

## ክፍል ፡ ፰ ።

## ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፹፰ ። መያዝ ።**

(፩) ለባለዕዳው ፡ ግዴታ ፡ አፈጻጸም ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚሆነው ፤ ሊያዝበት ፡ አይገባም ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ በቀር ፡ የሚገኘው ፡ ንብረቱ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

(፪) የመያዝን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ይልቁንም ፡ የባለዕዳው ፡ ሀብት ፡ በዕዳ ፡ ማስከፈል ፡ ስም ፡ የመያዝን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ደንብ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ውስጥ ፡ ይገለጻል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፹፱ ። ባለዕዳው ፡ ያደረገው ፡ የውል ፡ ስምምነት ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የፈጸማቸው ፡ ውሎች ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ መመለሻ ፡ ይሆናል ።

(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ በተወሰነ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ ካገኘበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲገለጽ ፡ ማድረግ ፡ የታዘዘ ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ ሥርዐት ፡ ከተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ የሚያገኙትን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺ ። (፪) ልዩ ፡ መብት ፡ ስላለው ፡ ባለገንዘብ ።**

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረትና ፡ በተለይም ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የውሉ ፡ ስምምነት ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ ባለዕዳው ፡ የሀብቱን ፡ ሥራ ፡ የማካሄዱን ፡ ጉዳይ ፡ ራሱ ፡ እንዳያከናውን ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የታገደ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ የአፈጻጸም ፡ ልዩነት ፡ አላቸው ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፩ ። (፫) መሰል ።**

(፩) እንዲሁም ፡ ውሉ ፡ የተደረገው ፡ ለይምሰል ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ልዩ ፡ አፈጻጸም ፡ ይሰጣቸዋል ።

(፪) ድብቅ ፡ የሆነ ፡ የስምምነት ፡ ጽሑፍ ፡ ዋጋ ፡ የሚያገኘው ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ከአንደኛው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ ይህንኑ ፡ በማመን ፡ በተዋዋለበት ፡ ለይምሰል ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ መብቱን ፡ ለማዋል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፪ ። የመጠበቅ ፡ ተግባሮች ።**

አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የባለዕዳው ፡ መብቶች ፡ እንዳይጠፉ ፡ ሲል ፡ ማናቸውንም ፡ የመጠበቂያ ፡ ተግባሮች ፡ በባለዕዳው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ለማከናወን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፫ ። በባለዕዳው ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ መሥራት ።**

(፩) አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የባለዕዳው ፡ መደኸየት ፡ ገንዘቡን ፡ የማያስከፍል ፡ ምክንያት ፡ እንዳይሆንበት ፡ ሲል ፤ ዳኞችን ፡ አስፈቅዶ ፡ እንደ ፡ ባለዕዳው ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ የባለዕዳውን ፡ መብቶች ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚጠይቅበት ፡ መብት ፡ በመብቱ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ለባለዕዳው ፡ ብቻ ፡ የሚሆን ፡ መብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገሩን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመከታተል ፡ እንዲፈቀድለት ፡ የሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ሊከለከል ፡ ይገባል ።

(፫) እንዲሁም ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ ሁኗል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ ባለ ዕዳ ፡ ክስ ፡ ባለማቅረቡ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ መብቶቹ ፡ ጉዳት ፡ የሚደርስባቸው ፡ ካልሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ለመክሰስ ፡ እንዲፈቅድለት ፡ የሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ሊከለከል ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፬ ። ስለ ፡ ማስመሰል ።**

አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ባለዕዳው ፡ ያደረገው ፡ ውል ፡ የማስመሰል ፡ እንጂ ፤ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገ ፡ ያለመሆኑን ፡ በፍርድ ፡ እንዲታወቅለት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፭ ። የባለዕዳው ፡ አጭበርባሪነት ።**

ባለዕዳው ፡ በአጭበርባሪነት ፡ ተግባሩ ፡ መብቱን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ግዴታ ፡ የመፈጸም ፡ ስምምነት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቡ ፡ እነዚህን ፡ ተግባሮች ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፮ ። ስለ ፡ አጭበርባሪነት ፡ ሥራ ።**

(፩) አንድ ፡ ሥራ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ በአጭበርባሪነት ፡ የተፈጸመ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፤ ባለዕዳው ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ እንዳይችል ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ ችሎታው ፡ ይበልጥ ፡ እንዲቀነስ ፡ ሲል ፤ እያወቀ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ደርሶ ፡ የተከፈሉትን ፡ ዕዳዎች ፡ ሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ሊቃወሙዋቸው ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፲፱፻፺፯ ። ቅን ፡ ልቡና ፡ ስላላቸው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ።**

ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣበት ፡ እንደ ፡ ሆነና፣ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ የተቃወመው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ መብቶቹን ፡ ያገኘባቸው ፡ ሥራ

ዎች ፡ በዋጋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ አልቀበልም ፡ ሲል ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፺፰ ። የጊዜ ፡ ልክ ።**

ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችሉት ፤ የተነቀፈው ፡ ሥራ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፱፻፺፱ ። ውጤቱ ።**

(፩) ባለዕዳው ፡ የፈጸመው ፡ ሥራ ፡ በማጭበርበር ፡ መሆኑ ፡ ከተገለጸ ፡ ክስ ፡ ያቀረበውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።
(፪) በተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ግንኙነትና ፡ በሌሎቹ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ዘንድ ፡ በሚኖረው ፡ ጕዳይ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ይጸናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ ። መክሠር ።**

ባለዕዳው ፡ በከሠረ ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የባለዕዳውን ፡ የሥራ ፡ መብት ፡ ማከናወን ፡ ወይም ፡ ባለዕዳው ፡ ባደረገው ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የክስ ፡ ማቅረብን ፡ መብት ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ይኖራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

## የውልን ፡ ጕዳይ ፡ ስለሚመለከት ፡ ማስረጃ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታና ፡ አቀባበሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩ ። ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ።**

(፩) አንድ ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ የሚጠይቅ ፡ ሰው ፡ ለግዴታው ፡ መኖር ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።
(፪) እንዲሁም ፡ ግዴታው ፡ ፍርስ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ተለውጧል ፡ ወይም ፡ ቀርቷል ፡ የሚለው ፡ ወገን ፤ ይኸንኑ ፡ ግዴታ ፡ ያፈረሰውን ፡ የለወጠውን ፡ ወይም ፡ ያስቀረውን ፡ ተግባር ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪ ። የማስረጃ ፡ ዐይነቶች ።**

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ መሠረትና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ ድንጋጌ ፡ ዐይነት ፤ በጽሑፍ ፡ በምስክር ፤ በሕሊና ፡ ግምት ፡ በተከራካሪው ፡ ወገን ፡ እምነት ፤ ወይም ፡ በመሐላ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫ ። ጽሑፍ ፡ በሆነ ፡ ሥርዐት ፡ ( ፎርም ) ፡ ይደረጉ ፡ የተባሉ ፡ ውሎች ።**

ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሆን ፡ ሕግ ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የተቀደደ ፡ የተ

ለረቀ ፡ የጠፋ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ውሉን ፡ በምስክሮች ፡ ወይም ፡ በሕሊና ፡ ግምት ፡ ለማስረዳት ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩ ። በማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ መዋዋል ።**

እንዳንድ ፡ ማስረጃዎችን ፡ የሚያስቀሩትን ፡ ወይም ፡ አቀራረቡን ፡ የሚቀንሱትን ፡ ደንቦች ፡ ጥሰው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ እንዲዋዋሉ ፡ አይፈቀድላቸውም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪ ። የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በቂነት ።**

(፩) የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፤ በላዩ ፡ ስለሚገኘው ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ እንዲሁም ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተጻፈው ፡ ቀን ፡ በተፈራራሚዎቹ ፡ መካከል ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ በእንደራሴ ፡ በተፈጸመላቸው ፡ ሰዎች ፡ በኩልና ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ወራሾች ፡ በሆኑት ፡ ዘንድም ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ በቂ ፡ ማስረጃነት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫ ። መቃወሚያ ፡ ማስረጃ ።**

(፩) በጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ቃሎች ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ለመቃወም ፡ የሚችሉት ፤ ቃሉ ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ወገን ፡ በማስማል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ተጻፉት ፡ ቃላቶች ፤ የሰው ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ግምት ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬ ። ጽሕፈትን ፡ ለመካድ ።**

(፩) የግል ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈ ፡ ሰነድ ፡ የቀረበለት ፡ ሰው ፡ የኔ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጽሕፈቱን ፡ ወይም ፡ ፊርማውን ፡ ግልጥ ፡ አድርጎ ፡ መካድ ፡ አለበት ።

(፪) ወራሽ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የአውራሾችን ፡ ፊርማ ፡ ወይም ፡ ጽሕፈት ፡ መሆኑን ፡ አናውቅም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ይበቃቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭ ። የጽሕፈት ፡ ምርመራ ።**

አንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ፊርማውን ፡ ወይም ፡ ጽሕፈቱን ፡ በካደ ፡ ጊዜ ፡ ወራሾቹም ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ፈረመውና ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ አናውቅም ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፊርማው ፡ ወይም ፡ ጽሕፈቱ ፡ እንዲመረመር ፡ ዳኞች ፡ ሊያዙ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮ ። ሦስተኛ ፡ ወገኖች ።**

(፩) ሰነዱን ፡ የጻፈው ፡ ወይም ፡ የተቀበለው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡

ባለሥልጣን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉትን ፡ ቃሎች ፡ ሐሰተኛነት ፡ በማነኛውም ፡ ዐይነት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ በቀረበው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ቀን ፡ የተረጋገጠ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በተለይ ፡ ይህ ፡ የተጻፈው ፡ ቀን ፡ ሐሰተኛ ፡ መሆኑን ፡ በማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፲ ። በባለሥልጣን ፡ የተረጋገጠ ፡ ሰነድ ።

(፩) ሰነዱን ፡ ያዘጋጀው ፡ ወይም ፡ የተቀበለው ፡ ይህንኑ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ራሱ ፡ ለመመርመር ፡ ያልቻላቸውን ፡ የውሉን ፡ ቃላት ፡ ሁሉ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንደ ፡ ፈቀዱ ፡ ሊቃወሟቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ራሱ ፡ የመረመራቸውን ፡ የውል ፡ ቃላት ፡ ለመቃወም ፡ የሚቻለው ፡ ዳኞች ፡ ይህ ፡ እንዲፈጸም ፡ በተለይ ፡ የፈቀዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፲፩ ። በባለሥልጣን ፡ የተረጋገጠ ፡ የሰነድ ፡ ግልባጭ ።

(፩) በባለሥልጣን ፡ ከተረጋገጠ ፡ ዋነኛ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተቀዱ ፡ ግልባጮች ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተነሡ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ኮፒዎች ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ለመሥራት ፡ በተመደበ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነ ፡ ሹም ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ መሆናቸው ፡ ከተመሰከረ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) ይኸውም ፡ ደንብ ፡ ከዋናው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ለተነሡ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ኮፒዎችም ፡ ይጸናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፲፪ ። የመንግሥት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ።

በመንግሥት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ የሚቀመጡ ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ሰነዶች ፡ ከዋናው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተገለበጡት ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነው ፡ ሰነድ ፡ አስቀማጭ ፡ ሠራተኛ ፡ ከሆነ ፡ እንደ ፡ ዋናዎቹ ፡ ሰነዶች ፡ ተቈጥረው ፡ ይታመናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፲፫ ። ማስተያያ ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ፎቶግራፎች ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ ነገር ፡ በሚያጋጥምበት ፡ ጊዜ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ዋናው ፡ ሰነድ ፡ ይቅረብልን ፡ ብለው ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የያዙት ፡ ግልባጭ ፡ ከዋናው ፡ ሰነድ ፡ ጋራ ፡ ይህም ፡ ባይኖር ፡ ከቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ ከተቀመጠው ፡ ግልባጭ ፡ ጋራ ፡ በራሳቸው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲመሳከርላቸው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ዋናው ፡ ሰነድ ፡ በራሳቸው ፡ ኪሣራ ፡ በፎቶግራፍ ፡ እን ዲገለበጥላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፩ ፡ የዋናው ፡ ሰነድ ፡ መጥፋት ።**

ዋናው ፡ ሰነድ ፤ ወይም ፡ በቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ የተቀመጠው ፡ ትክክል ፡ ግል ባጭ ፡ በጠፋ ፡ (በሌለ) ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ቍጥሮች ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በሚገባ ፡ የተገለበጡት ፡ የሰነድ ፡ ቅጂዎች ፡ ስርዝም ፡ ሆነ ፡ የቃል ፡ መለወጥ ፡ ድልዝ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማናቸውም ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነገር ፡ የሌለባቸው ፡ ከሆነ ፡ የሚታመኑ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፪ ። የተረጋገጠ ፡ ቀን ።**

ሰነዱ ፡ የተጻፈበት ፡ እርግጠኛ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ የሚባለው ።

(ሀ) ሰነዱን ፡ የጻፈው ፡ ወይም ፡ የተቀበለው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሲሆን ፡ የጻፈበት ፡ ወይም ፡ የተቀበለበት ፡ ቀን ፤

(ለ) ሰነዱ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ በጻፈው ፡ ወይም ፡ በተቀበለው ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሌላው ፡ ሰነድ ፡ የተጻፈበት ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የተቀበለበት ፡ ቀን ፤

(ሐ) ይህን ፡ ሰነድ ፡ ከፈረሙት ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለመፈረም ፡ የአካል ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰውዬው ፡ የሞተ በት ፡ ወይም ፡ የመፈረም ፡ ዐቅም ፡ ያጣበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፫ ። የነጋዴዎች ፡ መዝገብ ።**

(፩) የነጋዴዎች ፡ መዛግብት ፤ ለጻፉቸው ፡ ሰው ፡ አስረጅ ፡ ሊሆኑት ፡ አይችሉም።

(፪) እነዚህ ፡ መዛግብት ፡ በጻፉቸው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆኑበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ በነዚህ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚፈልገው ፡ ወገን ፡ የሚጠቅመውን ፡ ቃል ፡ ከሚቃወመው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለይቶ ፡ ጠቃሚውን ፡ ብቻ ፡ ያስረዳልኝ ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፬ ። የቤት ፡ መዛግብትና ፡ የቤት ፡ ደብዳቤዎች ።**

የቤት ፡ መዛግብት ፡ የቤት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ለጻፉቸው ፡ ሰው ፡ አስረጅ ፡ ሰነድ ፡ ሊሆኑት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፭ ። በጻፉዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አስረጅ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

የቤት ፡ መዛግብትና ፡ የቤት ፡ ደብዳቤዎች ፡ በጻፉቸው ፡ ላይ ፡ ተቃዋሚ ፡ ማስ ረጃ ፡ መሆናቸው ፡ የሚታመነው ።

(ሀ) አንድ ፡ ገንዘብ ፡ የተከፈለ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ተመልክቶባቸው ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፤

BACK



(ለ) ግዴታው ፡ ለሚጠቅመው ፡ ሰው ፡ የሚያስረዳው ፡ ሰነድ ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ለዚሁ ፡ ሰነድ ፡ ምትኩ ፡ እንዲሆን ፡ ተብሎ ፡ በግልጽ ፡ የተጻፈባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፲፱ ። የምክንያቱ ፡ ማስረጃ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ቃል ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኑን ፡ ያመነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እከፍልሃለሁ ፡ የተባለው ፡ ወይም ፡ ዕዳው ፡ የታመነለት ፡ ሰው ፡ የነዚህን ፡ ምክንያት ፡ ማረጋገጥ ፡ የለበትም ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በሚገባ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ እንዳለ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) የግዴታው ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መደበቁ ፡ ማስረጃ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ለግዴታው ፡ ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ የሚያስቈጥሩ ፡ የሕሊና ፡ ግምቶች ።

ቍ ፡ ፪ሺ፳ ። ዕዳው ፡ የተከፈለ ፡ ያህል ፡ የሚያስቈጥሩ ፡ የሕሊና ፡ ግምቶች ።

ሰነድ ፡ ለባለዕዳው ፡ መመለሱ ፡ ዕዳውን ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ ያስቈጥራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፳፩ ። የባለገንዘቡ ፡ ጽሕፈት ።

በእጁ ፡ ቈይቶ ፡ በሚገኘው ፡ በዕዳው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በግርጌው ፤ በጐኑ ፡ ወይም ፡ በጀርባው ፡ ጽፎበት ፡ የተገኘው ፡ ቃል ፡ የባለዕዳውን ፡ ነጻነት ፡ ወደ ፡ ማረጋገጥ ፡ የሚያዘነብል ፡ ጽሑፍ ፡ ከሆነ ፤ ሳይፈረምበት ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ ሳይ ሞላበት ፡ ቢቀርም ፡ እንኳ ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ የሚችል ፡ አስረጅ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፳፪ ። ስለ ፡ ውዝፍ ፡ ዕዳ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ።

(፩) የተከፈለው ፡ ዕዳ ፤ ወለዶችን ፡ ወይም ፡ በየተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈሉትን ፡ ሌሎች ፡ የክፍያ ፡ ድርሻዎች ፡ የሚመለከት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተከፋዩን ፡ ዐይነት ፡ ለይቶ ፡ ሳይገልጽ ፡ ለአንዱ ፡ የክፍያ ፡ ደረሰኝ ፡ የሰጠ ፡ ባለገንዘብ ፡ ያለፈው ንም ፡ ድርሻ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ባለገንዘቡ ፡ ለዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ደረሰኝ ፡ ከሰጠ ፡ ባለዕዳው ፡ ወለዱንም ፡ ጭምር ፡ እንደ ፡ ከፈለ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፳፫ ። በስድስት ፡ ወር ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ መጠየቅ ፡ ከሚገባው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ሳይከፈል ፡ የቈየ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ የሚቈጠረው ፤

BACK



(ሀ) ለንግድ ፡ ቤት ፡ ወኪሎች ፡ ለቢሮ ፡ ሠራተኞች ፡ በቀን ፡ ሒሳብ ፡ ለተቀጠሩ ፡ አሽከሮችና ፡ የቀን ፡ ሒሳብ ፡ ለሚከፈሉ ፡ የዕለት ፡ ኩሊዎች ፤ የሚከፈል ፡ የደመወዝ ፡ ዕዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለአስተማሪዎችና ፡ ለአሠልጣኞች ፡ ለሚሰጡት ፡ ትምህርት ፡ በየወሩ ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ለባለሆቴሎች ፤ ለመጋቢዎችና ፡ ለማደሪያ ፡ ሆቴል ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ለሚሰጡት ፡ ምግብና ፡ ለመኝታ ፡ ቤቱ ፡ ኪራይ ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ለዕለት ፡ ምግብ ፡ ወይም ፡ ለዘወትር ፡ አገልግሎት ፡ ነጋዴዎች ፡ ለባለግል ፡ ሰዎች ፡ ለሸጡት ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ለምግብ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪ሺ፳፬ ። በሁለት ፡ ዓመት ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ መጠየቅ ፡ ከሚገባበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሳይከፈል ፡ የቀረ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ የሚቈጠረው ፤

(ሀ) ለሐኪሞች ፤ ለቀዳጅ ፡ ሐኪሞች ፤ ለጥርስ ፡ ሐኪሞች ፤ ለአዋላጅ ፡ ሴቶች ፤ ለመድኀኒት ፡ ቀማሚዎችና ፡ ሻጮች ፤ ለከብት ፡ ሐኪሞች ፤ በልዩ ፡ ሞያቸው ፡ ስላደረጉት ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሰጡት ፡ ሕክምና ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፤

(ለ) ለጠበቆች ፤ ለውል ፡ አዋዋዮች ፡ ለሌሎችም ፡ የሕግ ፡ አማካሪዎች ፡ በሞያ ፡ ሥራቸው ፡ ወይም ፡ በሹመት ፡ ሥራቸው ፡ ላደረጉት ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፤

(ሐ) ለጥበበኞች ፡ ለአንጥረኞች ፡ በልዩ ፡ ሞያቸው ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ሥራ ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፤

(መ) ለቤቶች ፡ ኪራይና ፡ ለእርሻ ፡ ሀብት ፡ ለሆነ ፡ የሚከፈል ፡ ዕዳ ፤

(ሠ) ለመጦሪያ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፤

(ረ) በብድር ፡ ለተሰጠ ፡ የገንዘብ ፡ ወለድና ፡ በጠቅላላውም ፡ የዓመት ፡ ጊዜ ፡ ተወስኖለት ፡ በየዓመቱ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ባነሰ ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባው ፡ ዕዳ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪ሺ፳፭ ። ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ።

(ሀ) ባለዕዳው ፡ በጽሑፍ ፡ ዕዳውን ፡ ያመነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በሕግ ፡ የተደነገገው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሳይደርስ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲከፍለው ፡ ባለዕዳውን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ አስጠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕዳው ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ መቈጠሩ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፳፮ ። መሐላ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ላይ ፡ ለተገለጠው ፡ የሕሊና ፡ ግምት ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆን ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡ ማስረጃ ፡ ለመቀበል ፡ አይቻልም ።

(፪) ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ግን ፤ ዕዳው ፡ በእርግጠኛ ፡ መከፈሉን ፡ ወይም ፡ ያለመከፈሉን ፡ ለማስረዳት ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለባለዕዳው ፡ ወይም ፡ ባለዕዳው ፡ ለባለገንዘቡ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ ሊያወርድለት ፡ ይችላል ።

(፫) የባለገንዘቡ ፡ ወይም ፡ የባለዕዳው ፡ ወራሾች ፡ ገንዘቡ ፡ የተከፈለ ፡ ወይም ፡ ያልተከፈለ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

## አንቀጽ ፡ ፲፫ ።

## ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፳፯ ። ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ የአላፊነት ፡ ምንጮች ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ የገባው ፡ ግዴታ ፡ ባይኖር ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ ካደረሰ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ ከሠራ ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ የያዘው ፡ ነገር ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ካደረሰ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፫) በመጨረሻውም ፡ በጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ አላፊነት ፡ ሲኖር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለፈጸመው ፡ አድራጎት ፡ በሕጉ ፡ አላፊነት ፡ አለበት ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ አላፊ ፡ ነው ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### በጥፋት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተመሠረተ ፡ አላፊነት ።

#### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

#### ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፳፰ ። ጠቅላላ ፡ መሠረት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ከራሱ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ካደረሰ ፡ ላደረገው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፳፱ ። የጥፋት ፡ ልዩ ፡ ልዩነት ።**

(፩) አስቦ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ በሚሠራ ፡ ተግባር ፡ ጥፋት ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ተግባርን ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ ተግባርን ፡ አለመፈጸም ፤ ጥፋት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፪ሺ፴ ። መልካም ፡ ጠባይ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ሕሊናን ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ ተቃዋሚ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የማይገባውን ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ሳይሠራ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋት ፡ ማድረጉ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚህ ፡ ስላለውም ፡ ጉዳይ ፡ ትክክለኛ ፡ አእምሮ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ አስተያየት ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።

(፫) በሕግ ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ የጥፋት ፡ አድራጊውን ፡ ዕድሜም ፡ ሆነ ፡ የአእምሮውን ፡ ትክክለኛነት ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ባለመያዝ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፴፩ ። በሞያ ፡ ሥራ ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥፋት ።

(፩) በልዩ ፡ ሞያው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ በሞያው ፡ የሥራ ፡ ተግባሩን ፡ የሚያካሂድ ፡ ሰው ፡ የዚሁ ፡ የሞያ ፡ ሥራው ፡ የሚመራበትን ፡ ደንብ ፡ መጠበቅ ፡ ይገባዋል ።

(፪) በሥነ ፡ ጥበብ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ በሚሠራው ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ አለመከተሉ ፡ ሲገለጽ ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፴፪ ። የመጉዳት ፡ አሳብ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ጥቅሙን ፡ ለመፈለግ ፡ ሳይሆን ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ለመጉዳት ፡ በማሰብ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ከተደረገው ፡ ጉዳት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የሌለውን ፡ የራሱን ፡ ጥቅም ፡ ሲፈልግ ፡ እያወቀ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳትን ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፴፫ ። በሥልጣን ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ የሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊ ፡ ነው ።

(፪) የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ እንዲያገለግልበት ፡ በሥራው ፡ (በሹመቱ) ፡ ያገኘውን ፡ ሥልጣን ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ወይም ፡ ለተለየ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ያዋለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፴፬ ። ስለ ፡ መብቶች ፡ ግብ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሳይነኩ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ የተሰጠውን ፡ መብቱን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋለበት ፡ ሁኔታ ፡ ከኤኮኖሚክና ፡ (የቁጠባ ፡ ዘዴ) ፡ ከማኅበራዊ ፡ አስተዳደር ፡ ጋራ ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ መንቀፍ ፡ አይቻልም ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፴፭ ። ሕግን ፡ ስለ ፡ መጣስ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ በትክክል ፡ ተገልጾ ፡ የተመለከተውን ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፤ ልዩ ፡ ደንብና ፡ ሥርዐት ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፪) ሕግን ፡ አለማወቅ ፡ ይቅርታ ፡ ሊያስገኝ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፴፮ ። የበላይ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) በበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ትእዛዝ ፡ የተፈጸመ ፡ ተግባር ፤ ትእዛዙ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ የሥራውን ፡ ጥፋትነት ፡ ግድ ፡ አያስቀረውም ።

(፪) የተባለውን፡ ሥራ ፡ ሠርቶ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፤ የዚህን ፡ ሥራ ፡ ሕገ፡ ወጥነት ፡ እያወቀ ፤ በተለይም ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጪው ፡ ሥልጣን ፡ (ችሎታ)፡ እንደ ፡ ሌለውና ፡ የሥራውን ፡ የዐመፅ ፡ ጠባይ ፤ ወይም ፡ አስወቃሽነቱን ፡ እያወቀ ፡ ሠርቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፫) በነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ዐይነት ፤ በተለይም ፡ አጥፊው ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ በመንግሥታዊ ፡ ወይም ፡ በወታደራዊ ፡ ዲሲፕሊን ፡ ምክንያት ፤ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ለመከራከር ፡ ወይም ፡ ያንን ፡ የታዘዘውን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ በማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ከመገኘት ፡ የተነሣ ፡ የተባለውን ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋት ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፴፯ ። የውል ፡ አለመፈጸም ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የመጣበትን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ከውሉ ፡ ውጭ ፡ ለሆነ ፡ ነገር ፡ አላፊነትን ፡ የሚያስከትልበትን፡ ጥፋት ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ አያስቈጥረውም ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የውል ፡ አለመፈጸም ፡ ደንብ ፡ ብቻ፡ ተፈጻሚ፡ ይሆናል።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

<u>ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።</u>

**ቍ ፡ ፪ሺ፴፰ ። ሰውነትን፡ ስለ ፡ መጉዳት ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ሳይፈቅድ ፡ በሚያደርገው ፡ መንካት ፡ በዚህ ፡ በመንካቱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዬውን ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሕይወት፡ ባለው፡ ወይም፡ በሌለው፡ ነገር፡ አማካይነት፡ ቢነካውም፡ ጥፋተኛ ፡ ነው።

(፫) በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረግ ፡ የተደረገ ፡ የመዛት ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ በጠቅላላው ፡ ጥፋት ፡ አይባልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፴፱ ። (፪) በቂ ፡ ምክንያት ።**

ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ የማይባለው ፤

(ሀ) ከሳሹ ፡ ሥራውን ፡ የሚቃወም ፡ መሆኑን ፡ ተከሳሹ ፡ በአእምሮው ፡ ግምት ፡ ሊያስበው ፡ የማይችል ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) ሥራው ፡ የተፈጸመው ፤ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለመከላከል ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ የያዘውን ፡ ንብረት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ሥራው ፡ የተፈጸመው ፡ ተከሳሹ ፡ ልጁን ፡ የአደራ ፡ ልጁን ፡ ተማሪውን ፡ ወይም ፡ አሽከሩን ፡ በሚገባ ፡ ለመቅጣት ፡ ሲል ፡ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ አቀጣጥ ፡ ፈጽሞበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ከሳሹ ፡ አደገኛ ፡ እብድ ፡ በመሆኑ ፤ ጉዳት ፡ እንዳያደርስ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ለመከልከል ፡ ስላልተቻለውና ፡ ተከሳሹ ፡ ሥራውን ፡ የፈጸመው ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) የተከሳሹ ፡ ሥራ ፡ አእምሮ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ግምት ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፷ ። የሌላውን ፡ ሰው ፡ ነፃነት ፡ ስለ ፡ መንካት ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆንም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ነፃነት ፡ የነካና ፡ እንደ፡ተፈቀደለት ፡ መጠን ፡ ካንዱ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ቦታ ፡ እንዳይዘዋወር ፡ ሰውዬውን ፡ የከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በከሳሹ ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያላደረሰም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ጥፋቱ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ መቈጠሩ ፡ አይቀርም ።

(፫) ከሳሹ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ በተከሳሹ ፡ ዛቻ ፡ ተገድዶ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህም ፡ ዛቻ ፡ ሊያስከትልበት ፡ የሚችለውን ፡ አደጋ ፡ ለመገመት ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ እንደ ፡ ጥፋት ፡ ለመቈጠር ፡ በቂ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፷፩ ። (፪) ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ።

ቢሆንም ፡ ተከሳሹ ፡ ይህን ፡ የማስገደድ ፡ ሥራ ፡ የፈጸመው ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፤ ሕግ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ሥልጣኑ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በሥልጣኑ ፡ ሥር ፡ በሚገኝ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ጥፋት ፡ አይቈጠርበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፷፪ ። (፫) ወንጀል ፡ መሰል ፡ እልፊት ።

(፩) የሌላውን ፡ ሰው ፡ ነጻነት ፡ የነካ ፡ ሰው ፤ ይህን ፡ ነጻነቱ ፡ የተነካበትን ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶዋል ፡ ብሎ ፡ ለማሰብ ፡ የሚያስችለው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካገኘ ፡ ጥፋተኛ ፡ አያሰኘውም ።

(፪) ቢሆንም ፡ አስገድዶ ፡ ነጻነቱን ፡ የነካበትን ፡ ሰው ፡ ወዲያውኑ ፡ ለከፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ወስዶ ፡ ካላስረከበው ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ነጻነት ፡ በመንካት ፡ አላፊነት ፡ ያገኝዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፷፫ ። (፬) ዋስ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ እንዲኖር ፡ ለመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በዋስትና ፡ አላፊነትን ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ በአንድ፡ስፍራ ፡ ታግዶ ፡ እንዲቀመጥ፡

BACK



የተደረገው ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ለማምለጥ ፡ መሰናዳቱን ፡ የሚያሳምን ፡ በቂ ፡ ምክን ያት ፡ ካለው ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ ነጻነት ፡ ቢነካበት ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፵፬ ። ስምን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ፤ (፩) መሠረቱ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በንግግሮቹ ፡ በጽሑፎቹ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎቶቹ ፡ በሕይወት ፡ ያለውን ፡ የአንደኛውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በማጥፋት ፡ ይህ ፡ ስሙ ፡ የጠ ፋው ፡ ሰው ፡ እንዲጠላ ፤ ወይም ፡ እንዲዋረድ ፡ ወይም ፡ እንዲሣቅበትና ፡ በእሱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እምነትና ፡ መልካም ፡ ዝናው ፡ ወይም ፡ የወደፊት ፡ ዕድሉ ፡ እንዲ በላሽ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፵፭ ። (፪) የመጉዳት ፡ አሳብ ፡ የሌለው ፡ አድራጎት ።

(፩) ስም ፡ አጥፊ ፡ ለመባል ፡ የመጉዳት ፡ አሳብ ፡ መኖር ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

(፪) በስም ፡ ማጥፋት ፡ ነገር ፡ ስም ፡ ያጠፋል ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ በንግግርና ፡ በጽ ሑፍ ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በንግግሩ ፡ የማንንም ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በተለይ ፡ ካልገለጸ ፡ በቀር ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ አያስቈጥረውም ።

(፫) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ የስም ፡ ማጥፋትን ፡ አድራጎት ፡ በንግግር ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ የገለጸው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ አድራጎቱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንደሚጎዳ፡ አስቀድሞ ፡ ለመረዳት ፡ መቻሉ ፡ ካተልገለጸ ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ጒዳይ ፡ አላፊ ነት ፡ አይኖርበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፵፮ ። (፫) የሕዝብን ፡ ጥቅም ፡ የሚነኩ ፡ ጒዳዮች ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ በሚሆን ፡ ጒዳይ ፡ ላይ ፡ አሳቡን ፡ በመግለጽ፡ ብቻ ፡ ከተወሰነ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ አሳቡ ፡ በሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ የሚያስወቅሰው ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ።

(፪) ተከሳሹ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ የገለጸው ፡ አሳብ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ በእርግጥ ፡ ያወቀው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስም ፡ እንዳጠፋ ፡ አያስቈጥረውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፵፯ ። (፬) የተነገረው ፡ ጒዳይ ፡ እውነትነት ።

(፩) ተከሳሹ ፡ ያወራው ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ ጒዳይ ፡ እርግጠኛ ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ፡ ካገኘ ፡ ስም ፡ አጠፋ ፡ አያሰኘውም ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፤ ያደረገው ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ ጒዳይ ፡ በተለይ ፡ ሰውዬውን ፡ ለመጉዳት ፡ ብቻ ፡ ያደረገው ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፵፰ ። (፭) የማይደፈር ፡ መብት ።

(፩) በምክር ፡ ቤት ፡ (በፓርላማ) ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ በፍርድ፡ ቤት ፡ ክርክር ፡ ላይ፡ በተደረገው ፡ ንግግር ፡ ተናጋሪው ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

(፪) የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ንግግር ፡ በትክክለኛ ፡ እርግጥነቱን ፡ የገለጠው ፡ ሰው ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቀው ፤ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ ሰውዬውን ፡ ለመጉ ዳት ፡ ብቻ ፡ አስቦ ፡ ያደረገው ፡ መሆኑ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪ሺ፹፱ ። ፯) በቂ ፡ ምክንያት ።

(፩) በጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ የተወራ ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ ነገር ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ተከሳሹም ፡ በጋዜጣ ፡ አማካይነት ፡ የሰውን ፡ ስም ፡ ያጠፋው ፡ በተለይ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ለመጉዳት ፡ አስቦ ፡ ሳይሆንና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቸልተኛነትም ፡ ያላደረገ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በከሳሹም ፡ ጠያቂነት ፡ የስም ፡ ማጥፋቱን ፡ ጒዳይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ቃሉን ፡ መልሶ ፡ ይቅርታ ፡ ከጠየቀ ፡ አላፊነቱ ፡ ይወገድለታል ።

(፪) የስም ፡ ማጥፋቱ ፡ ነገር ፡ የተደረገው ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ በበለጠ ፡ ጊዜ ፡ በሚወጣ ፡ (በሚታተም) ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የስም ፡ ማጥፋቱ ፡ ነገር ፡ የሚለውጥበትን ፡ የይቅርታ ፡ መጠየቂያው ፡ ጽሑፍ ፡ ጠያቂው ፡ ራሱ ፡ በመረጠው ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲታተምለት ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለለው ።

(፫) የስም ፡ ማጥፋቱ ፡ ነገር ፡ የሚለወጥበትን ፡ ጋዜጣ ፤ ጠያቂው ፡ ባልመረጠ ፡ ጊዜ ፤ የስም ፡ ማጥፋቱ ፡ ነገርና ፡ የይቅርታ ፡ መጠየቁ ፡ ነገር ፡ የሚታተመው ፡ በዚያው ፡ ቀድሞ ፡ በወጣው ፡ ጋዜጣ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪ሺ፺ ። የባልና ፡ የሚስትን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መንካት ፤ (፩) መሠረቱ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፤ ሴትዮዋ ፡ ባለባል ፡ መሆኑዋን ፡ እያወቀ ፡ ያለባልዋ ፡ ፈቃድ ፡ ባልዋን ፡ ትታው ፡ እንድትሄድ ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ እንዲኖራት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ ባለሚስት ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፤ ሚስት ፡ እንዳለችው ፡ እያወቀ ፤ ሚስቲቱ ፡ ሳትፈቅድ ፡ ትቷት ፡ እንዲሄድ ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ባሉዋ ፡ ነገሩን ፡ እንደሚቃወም ፡ ሲያውቀው ፡ የሰው ፡ ሚስት ፡ ተቀብሎ ፡ እቤቱ ፡ ያስቀመጠ ፡ ወይም ፡ ያስተናገደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ፡ነው ።

ቊ ፡ ፪ሺ፺፩ ። (፪) የሚበቃ ፡ ምክንያት ።

በላይኛው ፡ ቊጥር ፡ በ፫ኛው ፡ ንኡስ ፡ ቊጥር ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጥፋት ፡ የማይቈጠሩት ፤

(ሀ) ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ተለያይተው ፡ ለመኖር ፡ ተስማምተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ባልየው ፡ በሚስቱ ፡ ላይ ፡ የማሠቅየት ፡ ተግባር ፡ በመፈጸሙ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ባልየው ፡ በሚስቱ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ መሥራቱን ፡ ተከሳሹ ፡ በሕሊና ፡ መንገድ ፡ በእርግጥ ፡ በመገመቱ ፡ ሴትዮዋን ፡ ተቀብሎ ፡ ያኖራት ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄን ፡ በሚመለከት ፡ አድራጎት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪ሺ፺፪ ። የማስተማርና ፡ የመጠበቅ ፡ ግዴታ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ አገባብ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በራሱ ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ጠባቂነት ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደር ፡ በአደራ ፡ የተሰጠውን ፡

ሌላውን ፡ ሰው ፡ በአስተዳዳሪነቱ ፡ ምክንያት ፡ ሊፈጽምለት ፡ የሚገባውን ፡ በሕሊና ፡ አገማመት ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚጠበቀውን ፡ ተግባር ፡ በጊዜው ፡ አጋጣሚና ፡ በልማድ ፡ አሠራር ፡ ሁኔታ ፡ ባለው ፡ ምቾት ፡ መጠን ፡ በትምህርት ፡ የማሳደግንና ፡ በሚገባ ፡ የመጠበቅን ፡ ጉዳይ ፡ ሳይፈጽምለት ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

በዚሁ ፡ ባደረገው ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት፡ በሥልጣኑ ፡ ሥር ፡ የሚተዳደረው ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ከዚሁ ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ በሥልጣኑ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚጠብቀው ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ባደረሰው ፡ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፶፫ ። በሌላው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መሬት ፡ ስለ ፡ መግባት ።

አንድ ፡ ሰው ፤ በሕግ ፡ ሳይፈቀድለትና ፡ ቤቱን ፡ ወይም፡መሬቱን ፡ በደንብ ፡ ባለ እጅ ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ የያዘው ፡ ሳይፈቀድለትና ፡ የማይፈቅድ ፡ መሆኑንም ፡ በግልጽ ፡ እየተናገረ ፤ የሌላ ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ በሆነ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፶፬ ። ንብረትን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ባለንብረቱ ፡ ሳይፈቅድለትና ፡ አለመፍቀዱንም ፡ በመግለጽ ፡ ሲናገር ፡ በደንብ ፡ በእጁ ፡ የሆነውን ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ የወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፶፭ ። ውል ፡ ከማድረግ ፡ በፊት ፡ የተደረገ ፡ ድርድር ።

አንድ ፡ ሰው ፤ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ውል ፡ እንዲያደርጉ ፡ አሳቡን ፡ ከገለጸላቸው ፡ በኋላና ፡ እነዚሁንም ፡ ሰዎች ፡ ወጪ ፡ እንዲያደርጉ ፡ አግባብቷቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፶፮ ። በውል ፡ የገባውን ፡ የግዴታ ፡ ቃል ፡ ስላለማክበር ፡ (ስለ ፡ መጣስ) ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ እያወቀ ፡ ውል፡ ካደረጉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ካንደኛው ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ሌላ ፡ ውል ፡ አድርጎ ፡ ቀድሞ ፡ የነበረውን ፡ ውል ፡ ለመፈጸም ፡ እንደማይቻል ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፡ የመጀመሪያው ፡ ውል ፡ ተጣሰብኝ ፡ ብሎ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ የሚያቀርበው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፤ ውሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ በቸልተኛነት ፡ ሳያደርግ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የኋለኛው ፡ ተዋዋይ ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፶፯ ። የማይገባ ፡ ውድድር ።

አንድ ፡ ሰው ፤ ሐሰተኛ ፡ በሆነ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ቅን ፡ ልቡናን ፡ ተቃራኒ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ አድራጎት ፡ የአንዱን ፡ ፋብሪካ ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡

BACK



(ዕቃ) ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ መልካም ፡ ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ስብከት ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፰ ። የሌለውን ፡ አስመስሎ ፡ ማሳየት ።**

አንድ ፡ ሰው ፤ በሚሰጠው ፡ የማረጋገጫ ፡ ቃል ፤ በጠባዩ ፤ በአካሄዱ ፡ ወይም ፡ ባለ ማድረጉ ፡ የአንድ ፡ ያልተወሰነ ፡ ነገር ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ባዕዶች ፡ ሰዎች ፡ እንዲያምኑ ፡ ያግባባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚሁንም ፡ ነገር ፡ እርግጠኛውን ፡ ሀልዎት ፡ በተቃራኒ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያምኑ ፡ ቅን ፡ ሕሊናን ፡ ተቃዋሚ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ሌሎቹን ፡ ሰዎች ፡ ያግባባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፱ ፡ ያልተካከለ ፡ ወሬ ። (፩) መሠረቱ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ያልተካከለ ፡ ወሬ ፡ የማስተላለፍ ፡ ጥፋት ፡ እንዳደረገ ፡ የሚቈጠረው ፡—

(ሀ) ከእርሱ ፡ ወሬውን ፡ የሰማው ፤ ወይም ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ በማመን ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ጉዳት ፡ የሚያገኘው ፡ መሆኑን ፡ ያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በልዩ ፡ ሞያ ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ ትክክለኛ ፡ ወሬ ፡ (መረጃ) ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚገባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻ ። (፪) ልዩነት ።**

(፩) ይህን ፡ ያልተካከለ ፡ ወሬ ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፤ በሰጠው ፡ ወሬ ፡ ላይ ፡ ያስረዳው ፡ የአንዱን ፡ ሰው ፡ ሁኔታዎቹን ፤ ዐመሉን ፡ ለመክፈል ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፤ ችሎታውን ፡ በመናገር ፡ ለዚሁ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ እንዲያገኝ ፡ በማሰብ ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አላፊነት ፡ የለበትም ።

(፪) ይህንንም ፡ የመግለጫ ፡ ቃሉን ፡ በጽሑፍ ፡ አድርጎ ፡ ራሱ ፡ ካልፈረመ ፡ በቀር ፡ አላፊነት ፡ ሊመለከተው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፩ ። (፫) ምስክሮች ።**

(፩) አንድ ፡ ነገር ፡ መፈጸሙን ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ መፈጸሙን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አድራጎት ፡ መኖሩን ፡ ወይም ፡ ያለመኖሩን ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ምስክሮች ፡ የሰጡት ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እርግጠኛ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) አላፊነታቸውም ፡ የአረጋገጡትን ፡ እውነት ፡ ያልሆነ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ እውነተኛ ፡ በማመን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ነው ።

(፫) ምስክሮቹ ፡ ይህን ፡ ያደረጉት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስሕተት ፡ እንዲገቡ ፡ ባደረጓቸው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብታቸው ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፷፪ ። ምክር ፡ ወይም ፡ የአደራ ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ምክር ፡ ቢሰጥ ፡ ወይም ፡ አደራ ፡ ቢለው ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፷፫ ። ስለ ፡ መያዝ ።**

እንድ ፡ አበዳሪ ፡ ባለዕዳው ፡ ሊከፍለው ፡ የሚገባውን ፡ ዕዳ ፡ ለማስከፈል ፡ ሲል ፡ ሊቀበል ፡ ከሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ ያልሆነ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አስ ፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፷፬ ። የፍርድን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ።**

(፩) አንድ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፤ ዳኛው ፡ የሰጠው ፡ የፍድር ፡ ውሳኔ ፡ ትክክለኛ ፡ አሠራሩን ፡ የያዘ ፡ ( ፎርም ) ፡ ከሆነ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ቢፈጽም ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ትእዛዙ ፡ ከደንበኛው ፡ አሠራር ፡ ፎርም ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ከተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ያለፈ ፤ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡ ሕግን ፡ ባለማክበር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋተኛ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፷፭ ። ስለ ፡ ይርጋ ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ በባለይዞታነቴ ፡ ወይም ፡ በይርጋ ፡ ደንብ ፡ መከሰስ ፡ ቀርቶልኛል ፡ ብሎ ፡ ቢከራከር ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## አጥፊ ፡ ሳይሆን ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፷፮ ። አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ሀብቱን ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ በርግጥ ፡ ሊደርስበት ፡ ከሚችል ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፡ ሲከላከል ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ጉዳቱ ፡ በደረሰበት ፡ ሰው ፡ ጥፋትና ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላፊነት ፡ አያመጣም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፷፯ ። በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።(፩)መሠረቱ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፤ ይህን ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ ሥራ ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደ ፡ የታዘዘ ፡

BACK



እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሥራው ፡ የተፈጸመው ፡ ራስን ፡ ለማዳን ፡ በሚገባ ፡ ሲከላከል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አደጋው ፡ ሊደርስ ፡ የቻለው ፡ በተበዳዩ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአድራጊው ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ኣላፊነት ፡ አይደርስበትም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፷፰ ። (፪) የስፖርት ፡ ሥራ ። (ጨዋታ) ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የስፖርት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ በዚሁ ፡ እስፖርት ፡ ተካፋይ ፡ የሆነውን ፡ ወይም ፡ ተመልካቹን ፡ ቢያቈስለው ፤ በስፖርት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚመለከተውን ፡ ደንብ ፡ በግልጽ ፡ ካልጣሰ ፡ ወይም ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ ካልፈጸመ ፡ በቀር ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፷፱ ። አደገኛ ፡ ሥራ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የሚፈነዱ ፡ ወይም ፡ መርዝ ፡ የሚሆኑ ፡ ቅመማት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ወይም ፡ በማከማቸት ፤ ወይም ፡ ከፍተኛ ፡ ጕልበት ፡ ያለው ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መሥመር ፡ በመዘርጋት ፤ ወይም ፡ የመሬትን ፡ የተፈጥሮ ፡ መልክ፡ በመለወጥ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ በማካሄድ ፡ ይህ ፡ ሥራው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኣላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ መንግሥትም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ በባለሥልጣን ፡ የተፈቀደለት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ይጸናል ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፸ ። (፪) ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ አደጋ ።**

ጥፋት ፡ ያለበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ጎረቤት ፡ በሆኑት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ መበላሸት ፡ ኣላፊነትን ፡ አያመጣም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፸፩ ። እንስሳዎች ፡ ባደረጉት ፡ ጉዳት ፡ የሚመጣ ፡ አላፊነት ፡ (፩) የእንሳስው ፡ ባለቤት ።**

የአንድ ፡ እንስሳ ፡ ባለሀብት ፡ ከብቱ ፡ ጉዳቱን ፡ ያደረሰው ፡ በድንገት ፡ በማምለጥም ፡ ቢሆን ፡ ያደርጋል ፡ ተብሎ ፡ ያልታሰበውንም ፡ ጉዳት ፡ አድርሶ ፡ ቢገኝ ፤ ይህ ፡ እንስሳው ፡ ባደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኣላፊ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፸፪ ። (፪) የእንስሳው ፡ ጠባቂ ።**

(፩) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ እንዲያውለው ፡ በራሱ ፡ ጠባቂነት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ከብት ፡ በእርሱ ፡ እጅ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኣላፊ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ እንስሳውን ፡ በኪራይ ፡ ወይም ፡ በተውሶ ፡ ወይም ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ለመቀለብ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ የተረከበ ፤ በራሱ ፡ ጠባቂነት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ እንስሳ ፡ ጉዳት ፡ ባደ

BACK



ረሰ ፡ ጊዜ ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ይኸው ፡ እንስሳ ፡ በእጁ ፡ የሚገኘው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፫) አንድ ፡ እንስሳ ፡ በታዛዥነት ፡ የተረከበ ፤ ወይም ፡ ለባለከብቱ ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ የሚሠራበት ፡ ሰው ፤ እንስሳው ፡ ያደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በርሱ ፡ ጥፋት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፸፫ ። (፫) የአላፊነቶች ፡ ግንኙነት ።**

(፩) የእንስሳው ፡ ባለመብት ፡ እንስሳው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰበትን ፡ ተበዳይ ፡ ከካሰ ፡ በኋላ ፤ የእንስሳው ፡ ጠባቂ ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

(፪) እንስሳው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ በባለሀብቱ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ አላፊነት ፡ ውስጥ ፡ በሚተዳደረው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ያደረሰበትን ፡ ኪሣራ ፡ በሙሉ ፡ እንዲመልስለት ፡ ጠባቂ ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ፡፪ሺ፸፬ ። (፬) ጌታው፡ የለቀቀው ፡ እንስሳ ።**

(፩) የሰው ፡ አገልጋይ ፡ የሆነ ፡ የቤት ፡ እንስሳ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ እንስሳ ፡ ባለቤት ፡ የሆነው፡ ሰው ፡ እንስሳውን ፡ ጉዳት ፡ ላደረሰበት ፡ ሰው ፡ የለቀቀ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ከአላፊነቱ ፡ ለመዳን፡ ይችላል ።

(፪) ቢሆንም ፤ እንስሳው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ በሚተዳደረው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

(፫) የቤት ፡ እንስሶችና ፡ የቤት ፡ አራዊት ፡ ተብለው ፡ የሚቈጠሩት ፡ ለመደሰት ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ ጥቅምን ፡ ለማግኘት ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ሰው ፡ የሚያኖራቸው ፡ ናቸው ።

**ቍ፡፪ሺ፸፭። (፭) ጠባቂው፡ የለቀቀው ፡ እንስሳ ።**

(፩) የእንስሳው ፡ ጠባቂ ፡ (እረኛ ) ፡ የሚገደደው ፡ ጉዳቱ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፤ እንስሳው ፡ በነበረው ፡ ግምት ፡ ልክ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ሆኖም ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በቤት ፡ እንስሳና ፡ በቤት ፡ አራዊት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ጉዳቱ ፡ በራሱ ፡ ወይም፡ በርሱ ፡ አላፊነት ፡ ሥር ፡ በሚገኘው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለእንስሳው ፡ ጠባቂ ፡ ተገዳጅነት ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፸፮። ለተበዳዩ ፡ ለስሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ የሚሆን ፡ መያዣ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ እንስሶች ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ገብተው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሱበት፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባውን ፡ ኪሣራ ፡ ከባለከብቱ ፡ ላይ ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ እንስሶችን ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ በእጁ ፡ ሊያቈይ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ከእንስሳው ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ጉዳት ፡ ለማስ

BACK



ቀረት ፡ እንስሳውን ፡ ለመግደል ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፤ እንስሶቹን ፡ ለመግደል፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) በሁለቱ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሳይዘገይ ፡ ለእንስሶቹ ፡ ባለቤት ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባዋል ። ባለቤቱንም ፡ ባያውቀው ፡ ለማግኘት ፡ የሚችልበትን ፡ አስፈላጊውን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቊ፡፪ሺ፹፯ ። ሕንጻ፡ (ቤት)። (፩) መሠረቱ።

(፩) ያንድ ፡ ሕንጻ ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ ባለይዞታ ፡ ሕንጻው ፡ ሊያደርስ ፡ ይችላል፡ ተብሎ፡ ያልታሰበ፡ ድንገተኛ ፡ ነገር ፡ ቢያደርስም ፡ ይህ ፡ ሕንጻ ፡ በሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ሕንጻውን ፡ የሠራውን ፤ ወይም ፡ በዚህ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፤ ወይም፡ ይህ፡ ሕንጻ፡ ባደረሰው፡ ጉዳት፡ አጥፊ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፤ ለባለቤቱ፡ ያለው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቊ፡፪ሺ፹፰ ። (፪) ሕንጻን ፡ ስለ፡መልቀቅ ።

(፩) የሕንጻው ፡ ባለቤት ፡ ይህን ፡ ቤቱን ፡ ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ሰው ፡ የለቀቀለት፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአላፊነቱ ፡ ውጭ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፪) ቢሆንም ፤ ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ባደረገው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ እርሱ፡ በሥልጣኑ፡ሥር ፡ በሚያሳድረው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

ቊ፡፪ሺ፹፱ ። (፫) የሚያሠጋ፡ ጉዳት ።

ከሌላ፡ ሰው፡ ቤት፡ ላይ፡ ጉዳት፡ ይደርስብኛል ፡ ብሎ ፡ የሚሠጋ ፡ ሰው ፤ የዚህ፡ አሥጊ ፡ የሆነው ፡ ሕንጻ ፡ ባለቤት ፡ ይህ ፡ ጉዳት ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ አሥጊው ፡ ነገር ፡ እንዲወገድለት ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲያደርግ ፡ ሊጠይቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቊ፡፪ሺ፺ ፡ (፬) ከሕንጻ ፡ ላይ ፡ የሚወድቁ ፡ ነገሮች ።

በአንድ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፤ ከዚህ ፡ ሕንጻ ፡ እየወደቁ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በሚያደርሱት ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገሮች ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቊ፡፪ሺ፺፩ ። መኪናዎችና ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪዎች ፤ (፩) ባለቤቱ ።

(፩) የአንድ ፡ መኪና ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪ ፡ ባለቤት፡ የሆነ፡ ሰው ፡ አደጋውን ፡ ያደረሰው ፡ ይህን ፡ መኪና ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪ ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ ወይም ፡ ለመንዳት ፡ ባልተፈቀደለትም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፤ እንኳ ፡ መኪናው ፡ ወይም ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪው ፡ ባደረሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ባለሀብቱ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም፡ አደጋው፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መኪናው ፡ ወይም ፡ ተሽከርካሪው፡ የተሰረቀበት ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሀብቱ ፡ አላፊነት፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፹፩ ። (፪) ጠባቂ ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ።

(፩) እንዲሁም ፡ መኪናውን ፡ ወይም ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪውን ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ሊገለገልበትና ፡ ሊጠቀምበት ፡ የወሰደው ፡ ሰው ፤ ይህ ፡ መኪና ፡ ወይም ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪው ፡ በእጁ ፡ በሚገኙበት ፡ ጊዜ ፡ ላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ከመኪናው ፡ ወይም ፡ ከባለሞተር ፡ ተሽከርካሪው ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ታዛዥ ፡ ስለ ፡ ባለቤቱ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ በመኪናው ፡ ወይም ፡ በባለሞተር ፡ ተሽከርካሪው ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ መኪና ፡ ወይም ፡ ባለ ሞተር ፡ ተሽከርካሪው ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰው ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፹፪ ። (፫) የአላፊነቶች ፡ ግንኙነት ።

(፩) የመኪናው ፡ የባለሞተር ፡ ተሽከርካሪው ፡ ባለቤት ፡ ተበዳዩን ፡ ተገድዶ ፡ ከካሠ ፡ በኋላ ፡ ጠባቂ ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ በኪሣራው ፡ አከፋፈል ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

(፪) እሱ ፡ ራሱ ፡ ባደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ጥፋት ፡ ካልሠራ ፡ ወይም ፡ ጕዳቱ ፡ የደረሰው ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ በሚተዳደረው ፡ ሰው ፡ በተደረገ ፡ ጕድለት ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ የከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ በሙሉ ፡ እንዲመለስለት ፡ ጠባቂውን ፡ ለመ ጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፹፫ ። የተሽከርካሪዎች ፡ መጋጨት ።

(፩) ሁለት ፡ ባለሞተር ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ ሲጋጩ ፡ እያንዳንዱ ፡ ተሽከርካሪ ፡ በየ ራሱ ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ እንዳደረሰ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ለየአንዳንዱ ፡ ተሽከርካሪ ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ ለአደጋው ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በአደጋው ፡ ምክንያት ፡ ከደረሰው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉዳት ፡ ግሚሱን ፡ መክ ፈል ፡ አለበት ።

(፫) ይህ ፡ አደጋ ፡ የደረሰው ፡ በተለይ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በአንደኛው ፡ መኪና ፡ ነጂ ፡ ስሕተት ፡ መሆኑ ፡ በማስረጃ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ አይጸናም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፹፬ ። የተሠሩ ፡ ዕቃዎች ።

(፩) ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ዕቃዎችን ፡ የሚሠራና ፡ እነዚህኑ ፡ ዕቃዎች ፡ ለሕ ዝብ ፡ የሚያቀርብ ፡ ሰው ፡ በዕቃዎቹ ፡ በሚገባ ፡ ሲጠቀምባቸው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፤ ይህ ፡ ዕቃ ፡ በልማድ ፡ እንደሚደረገው ፡ ተመርምሮ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፤ ጉዳቱን ፡ ያመጣው ፡ ጕድለት ፡ ተገልጾ ፡ ሊታወቅ ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፤ ምንም ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ።

**ቍ፡፪ሺ፹፮። ከአላፊነት ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መሆን ።**

(፩) በእንስሳት ፤ በሕንጻዎች ፤ (በቤቶች) ፡ በመኪናዎች ፡ ወይም ፡ በባለሞተር ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ ወይም ፡ በፋብሪካ ፡ ተሠርተው ፡ በወጡት ፡ ነገሮች ፡ ምክንያት ፤ አደጋ ፡ በሚፈጠርበት ፡ ወይም ፡ በሚደርስበት ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ አላፊዎች ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዳች ፡ ጥፋት ፡ ያላደረጉ ፡ መሆናቸውን ፡ በማስረዳት ፡ ወይም ፡ የጉዳቱ ፡ ምክንያት ፡ ሳይታወቅ ፡ በመቅረት ፤ ወይም ፡ ጉዳቱን ፡ ለመከልከል ፡ አንችልም ፡ ነበር ። ወይም ፡ ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ በሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በማስረዳት ፡ ጉዳቱ ፡ በደረሰበት ፡ ሰው ፡ በኩል ፡ ከአላፊነት ፡ ለማምለጥ ፡ አይችሉም ።

(፪) ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ከተበዳዩ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፤ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ከአላፊነቱ ፡ ለመዳን ፡ አይችሉም ።

**ቍ፡፪ሺ፹፯። ሌሎች ፡ ነገሮች ።**

የአንድ ፡ ነገር ፡ ባለቤት ፡ ወይም ፡ ጠባቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ አላፊነት ፡ ውስጥ ፡ የሚተዳደር ፡ ሰው ፡ ካላጠፋ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ከተመለከተው ፡ አስተያየት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ጉዳይ ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

**ቍ፡፪ሺ፹፰። የውል ፡ ግንኙነቶች ።**

(፩) ጉዳቱን ፡ ካደረሰው ፡ አደገኛ ፡ እንዱስትሪ ፤ ወይም ፡ እንስሳ ፤ ወይም ፡ ሕንጻ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ግንኙነት ፡ ያለውና ፡ በሕግ ፡ በኩልም ፡ ለነዚሁም ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ ከተባለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ተዋውያለሁ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ አሥጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ በመፍጠር ፡ ወይም ፡ በእንስሳዎች ፡ ወይም ፡ በሕንጻዎች ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ነገሮች ፡ ለሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ፡ የአላፊነትን ፡ ደንቦች ፡ በመጥቀስ ፡ ከአላፊነት ፡ ለመዳን ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳቱ ፡ የሚያደርሰው ፡ ነገር ፡ የሚመራው ፡ በተደረገው ፡ የውል ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ፡፪ሺ፹፱። ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ግንኙነት ።**

(፩) እንዲሁም ፡ ውል ፡ ባይኖርም ፡ እንኳ ፡ ጉዳቱ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ ጠባቂው ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ሳያገኝ ፡ በእንስሳው ፡ በሕንጻው ፤ ወይም ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ይገለገል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ እንስሳው ፡ ሕንጻው ፤ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ የአላፊነትን ፡ ደንቦች ፡ ጠቅሶ ፡ ለመከራከር ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረጉ ፤ ባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ ጠባቂው ፡ አላፊነት ፡ የለባቸውም ።

BACK



## ክፍል ፡ ፫ ።

## የካሣ ፡ አከፋፈልና ፡ ልክ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ።

### (ሀ) ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ጉዳቶች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺ ። የኪሣራ ፡ አከፋፈል ።**

(፩) በመደቡ ፡ በጉዳቱ ፡ ምክንያት ፡ ተበዳዩ ፡ የሚካሠው ፡ ለጉዳቱ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ኪሣራ ፡ በመክፈል ፡ ነው ።

(፪) የሰዎች ፡ ነጻነትና ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ ፋንታ ፡ ወይም ፡ ከኪሣራው ፡ በላይ ፡ ለጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሆን ፡ ወይም ፡ ለጉዳቱ ፡ ወሰን ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ ሁሉ ፡ ዳኞች ፡ ለመበየን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፩ ። የኪሣራው ፡ ልክ ።**

ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ የታወቀው ፡ ሰው ፡ የሚከፍለው ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፤ አላፊነቱን ፡ ያመጣው ፡ ጉዳይ ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ከደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ መመዛዘን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፪ ። ለወደፊት ፡ ሊደርስ ፡ ስለሚችል ፡ ጉዳት ።**

ለወደፊት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ ጉዳት ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፤ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ሳይጠበቅ ፡ ካሣ ፡ ሊከፈለው ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፫ ። አሹራንስ ፡ የገባ ፡ ተበዳይ ።**

(፩) ተበዳዩ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ አሹራንስ ፡ ቢገባም ፡ አሹራንስ ፡ እንዳልገባ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) አሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ እከፍላለሁ ፡ ብሎ ፡ በገባው ፡ የአሹራንሱ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የከፈለውን ፡ የአሹራንስ ፡ ኪሣራ ፡ ይህን ፡ ጉዳት ፡ ካደረሰው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ማናቸውንም ፡ ኪሣራ ፡ ሊጠይቅ ፡ አይችልም ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ የአሹራንስ ፡ ውል ፡ አድራጊው ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ከሚሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በተበዳዩ ፡ ስም ፡ ተዳራጊ ፡ ሆኖ ፡ የተበዳዩን ፡ መብቶች ፡ የመጠየቅ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖረው ፡ አስቀድሞ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፬ ። ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ጡረተኛ ።**

(፩) ተበዳዩ ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ መጦሪያ ፡ የሚቀበል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጦሪያ ፡ እንደማይቀበል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ጡረታ ፡ የሚከፍል ፡ ሰው ፡ በተጠዋሪ ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ለተጎጂው ፡ ጡረታ ፡ በመክፈሉ ፤ ጡረታውን ፡ ለመክፈል ፡ ያደረሰውን ፡ የጉዳት ፡ ሥራ ፡ የፈጸመውን ፡ ሰው ፡ ማናቸውንም ፡ ኪሣራ ፡ ይክፈለኝ ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ሊጠይቀው ፡ አይችልም ።

(፫) ከተበዳዩ ፡ ጋራ ፡ በሚያስተሳስረው ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ በተበዳዩ ፡ ስም ፡ ተዳራጊ ፡ ሆኖ ፡ የተበዳዩን ፡ መብት ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመስማማት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፺፭ ። ስለ ፡ ሞት ፡ አደጋ ፡ (፩) አንዳንድ ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶች ፡ ስለ ፡ አላቸው ፡ መብቶች ።

(፩) የተጎጂው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፤ ወይም ፡ ወላጆቹና ፡ ልጆቹ ፡ በተጎጂው ፡ ላይ ፡ ከደረሰው ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ የተነሣ ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ በመተዳደሪያ ፡ ረገድ ፡ ለሚደርስባቸው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስለዚህ ፡ ጉዳት ፡ የሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ ምግብን ፡ (መተዳደርን) ፡ በመስጠት ፡ እንደሚደረገው ፡ ጡረታ ፤ መልክና ፡ ዐይነት ፡ ይሆናል ።

(፫) ከሳሾቹ ፡ ቀለብ ፡ እንዲሰጧቸው ፡ የሚጠይቋቸው ፡ ዘመዶች ፡ ቢኖሯቸው ፡ እንኳ ፤ ይህ ፡ በምግብ ፡ ረገድ ፡ ለመጦሪያ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ካሣ ፡ ይገባቸዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፺፮ ። ሌሎች ፡ ሰዎች ።

ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ይረዳቸው ፡ ወይም ፡ ያስተዳድራቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ቢያረጋግጡ ፡ እንኳ ፤ በተበዳይ ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ ማናቸውንም ፡ ኪሣራ ፡ ሊጠይቁ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፺፯ ። ቅን ፡ ልቡና ።

(፩) ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነው ፡ አኳኋን ፡ ሊጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) ተበዳዩ ፡ በማስተዋል ፡ ቢሠራ ፡ ኖሮ ፡ የደረሰበትን ፡ ጉዳት ፡ ሊያግደው ፡ ወይም ፡ ሊያቀለው ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፤ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ በሙሉ ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፺፰ ። ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ ጥፋት ።

(፩) በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በከፊሉ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ጥፋት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚከፈለው ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ በከፊሉ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የጉዳቱ ፡ ካሣ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ መከፈል ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ መጠኑን ፡ ለመወሰን ፡ ያካባቢዎችን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፤ በተለይም ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ጥፋቶቹ ፡ የተባበሩበት ፡ መጠን ፡ እንደዚሁም ፡ የነዚህን ፡ ጥፋቶች ፡ የየአንዳንዳቸውን ፡ ከባድነት ፡ በመገመት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፺፱ ። በርትዕ ፡ የመወሰን ፡ ችሎታ ። (፭) ጥፋት ፡ መሆኑን ፡ ስላለማወቅ ።**

(፩) የሥራውን ፡ ጥፋት ፡ ለመገመት ፡ የማይችል ፡ ሰው ፤ አላፊነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ አስተያየት ፡ እንዲደረግበት ፡ ርትዕ ፡ ሲያስገድድ ፡ ዳኞች ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ የካሣውን ፡ ልክ ፡ መወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስለዚህ ፡ ዳኞች ፡ የነገረተኞችን ፡ ንብረት ፡ ሁኔታንም ፤ እንደዚሁም ፡ በዳዩን ፡ ካሣ ፡ በመክፈሉ ፡ የሚደርስበትን ፡ ጉዳት ፡ ማመዛዘን ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻ ። (፮) የበላይ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) በዲሲፕሊን ፡ ወይም ፡ በታዛዥነት ፡ የተግባር ፡ ተገቢነት ፡ ስሜት ፡ ምክንያት ፡ ጥፋተኛው ፡ ጥፋቱን ፡ እንዲፈጽም ፡ አድርጎት ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በርትዕ ፡ (በአገባብ) ፡ በኩል ፡ አስገዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ዳኞቹ ፡ የካሣውን ፡ ልክ ፤ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ለዚሁም ፡ ነገር ፡ ዳኞች ፡ የመታዘዙን ፡ ተገቢነት ፡ ማነስ ፡ ማደጉን ፡ መገመት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፩ ። (፯) ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ሊታሰብ ፡ የማይችል ፡ ጉዳት ።**

(፩) ሊታሰቡ ፡ በማይቻሉ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ ጕዳት ፡ እስከዚህ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ያስከትላል ፡ ተብሎ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ ሊታሰብ ፡ የማይችል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፤ የርትዕ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስገድድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ዳኞች ፡ ለዚህ ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ የካሣ ፡ ልክ ፡ አሻሽለው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) አላፊነቱ ፡ የደረሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ከተደረገ ፡ ጥፋት ፡ የመነጨ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ሊሠሩበት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፪ ። (፰) ስለ ፡ ግምት ፡ አስቸጋሪነት ።**

(፩) ስለ ፡ ጉዳቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ኪሣራ ፡ እንደሚከፍል ፡ በትክክል ፡ ለመወሰን ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞቹ ፡ የነገሮቹን ፡ ተራ ፡ ሁኔታዎችንና ፡ ተጐጂውም ፡ ያደረገውን ፡ ጥንቃቄ ፡ አመዛዝነው ፡ በመገመት ፡ የኪሣራውን ፡ ልክ ፡ በርትዕ ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፤ የሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የጉዳቱም ፡ መፈጸም ፡ የሚያጠራጥር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ማንኛቸውንም ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ እንዲከፈል ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፫ ። (፱) አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ሳያደርግ ፡ ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ወይም ፡ ሌሎችን ፡ ከጉዳት ፡ ወይም ፡ ከድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳ

BACK



ትን ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ አድራጊው ፡ የሚከፍለውን ፡ የካሣ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በርትዕ ፡ ይወስናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፩ ። ለደንቡ ፡ ብቻ ፡ ስለሚወሰኑት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራዎች ።**

የከሳሹ ፡ መብት ፡ በመደፈሩ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የመጣው ፡ አላፊነት ፡ በተከሳሹ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ብቻ ፡ የክስ ፡ ተግባር ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ለደንቡ ፡ ብቻ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራዎች ፡ ሊወሰኑ ፡ ይችላሉ ።

## (ለ) የሕሊና ፡ ጉዳት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፭ ፡ መሠረቱ ።**

(፩) ለደረሰው ፡ ጉዳት ፤ ካሣ ፡ ለመክፈል ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሆነ ፡ አድራጎት ፡ ሊፈጸም ፡ በሚቻልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋተኛው ፡ በደሉ ፡ ለሚያስከትለው ፡ የሕሊና ፡ ጉዳት ፡ ካሣን ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ።

(፪) የሕሊና ፡ ጉዳት ፡ በሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ የገንዘብ ፡ ኪሣራ ፡ አያስከፍልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፮ ። ታስቦ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ጥፋት ።**

በከሳሹ ፡ ላይ ፡ ታስቦ ፡ የሕሊና ፡ ጉዳት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ዳኞቹ ፡ በዚሁ ፡ በደል ፡ ካሣ ፡ ስም ፡ ተከሳሹ ፡ ለከሳሹ ፡ በርትዕ ፡ አንድ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍል ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ ላመለከተው ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ እንዲከፈል ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፯ ። በተበዳዩ ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሰው ፡ ጉዳት ።**

ተከሳሹ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ አስቀያሚ ፡ ወይም ፡ የሚያስጠላ ፡ መጥፎ ፡ መንካት ፡ አድርጎ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፤ ለከሳሹ ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ ላመለከተው ፡ በጎ ፡ ድርጅት ፡ ለዚሁ ፡ በደል ፡ በካሣ ፡ ስም ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍል ፡ ዳኞች ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፰ ። ያለ ፡ አገባብ ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መያዝና ፡ ስለ ፡ ማገድ ።**

እንዲሁም ፡ ተከሳሹ ፡ ሕግን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የከሳሹን ፡ ነፃነት ፡ አግዶ ፤ በተገኘ ፡ ጊዜ ፤ ለከሳሹ ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ ላመለከተው ፡ በጎ ፡ ድርጅት ፡ ለዚሁ ፡ በደል ፡ ካሣ ፡ ስም ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ ሊቈረጥለት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፱ ። ስምን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።**

ከሳሹ ፡ ተሰድቦ ፡ ወይም ፡ ስሙ ፡ ጠፍቶ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ለከሳሹ ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ ላመለከተው ፡ በጎ ፡ ድርጅት ፡ ለዚሁ ፡ በደል ፡ በካሣ ፡ ስም ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊደረግ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) ከሳሹ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቷል ፡ በማለት ፡ ስሙን ፡ በማጥፋት ፡ የበደለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) የስም ፡ ማጥፋት ፡ ሥራዎች ፡ ከሳሹን ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ እውነተኛነት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ለማሳመን ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) ነጋዴ ፡ ሆኖ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳመን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ አድሮበታል ፡ በማለት ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳመን ፡ የሚጥር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ረ) አስነዋሪ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ አለው ፡ በማለት ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳመን ፡ የሚጥር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፲ ። የባልና ፡ ሚስትን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መድፈር ።**

ተከሳሹ ፡ የባልነትን ፡ ወይም ፡ የሚስትነትን ፡ መብቶች ፡ ነክቶ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ለከሳሹ ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ ላመለከተው ፡ በጎ ፡ ድርጅት ፡ ለዚሁ ፡ በደል ፡ በካሣ ፡ ስም ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ ሊቈረጥ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፲፩ ። ልጅን ፡ ነጥቆ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።**

የልጁ ፡ ጠባቂነት ፤ የከሳሹ ፡ ሆኖ ፡ ተከሳሹ ፡ ልጁን ፡ ነጥቆ ፡ በመውሰዱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በወንጀል ፡ በሚቀጣበት ፡ ጊዜ ፡ ለከሳሹ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ ላመለከተው ፡ በጎ ፡ ድርጅት ፡ ለዚሁ ፡ በደል ፡ በካሣ ፡ ስም ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ ሊቈረጥ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፲፪ ። ንብረቶችን ፡ ስለ ፡ መድፈር ።**

ከሳሹ ፡ እንዳይደርስበት ፡ በግልጽ ፡ ያስታወቀውን ፡ በመቃወም ፡ ተከሳሹ ፡ በደንብ ፡ በእጁ ፡ ወይም ፡ በይዞታው ፡ የሚገኘውን ፡ ንብረት ፡ የወሰደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በርስቱና ፡ በቤቱ ፡ የገባበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ለዚሁ ፡ በደል ፡ ካሣ ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፲፫ ። የአካል ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ ሞት ።**

አካሉ ፡ በመጕደል ፡ ለተበደለው ፡ ሰው ፤ ወይም ፡ ሰውዬው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዘመዱ ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ዳኞች ፡ በአስተያየት ፡ ተገቢ ፡ ኪሣራ ፡ ሊቈርጡ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፲፬ ። የንጽሕናን ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ መድፈር ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በመድፈር ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ለክብረ ፡ ንጽሕና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ተግባር ፡ በወንጀል ፡ የተቀጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞቹ ፡ ለተደፈረችው ፡ ሴት ፡ በሕሊና ፡ በደል ፡ ካሣ ፡ ስም ፡ ተከሳሹ ፡ የሚሰጠውን ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ ለመቍረጥ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለሴቲቱ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ ለተገሠሠችው ፡ ልጃ ፡ ገረድ ፡ ቤት ፡ ዘመዶች ፡ ካሣ ፡ ሊቈረጥ ፡ ይቻላል ።

BACK



ቍ ፡ ፪ሺ፻፲፭ ። በሚስት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ጉዳት ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ላይ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ በማድረሱ ፡ በት ዳር ፡ በኩል ፡ ለባሏ ፡ የምትሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ደስታ ፡ እንዲቀነስ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ በደል ፡ ካሣ ፡ ዳኞች ፡ በበዳዩ ፡ ላይ ፡ ለባለቤቷ ፡ በርትዕ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ኪሣራ ፡ ሊቈርጡለት ፡ ይችላሉ ።

(፪) በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሚስቱ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ባል ፡ የሚያቀርበው፡ ክስ ፡ ሚስቱ ፡ ለደረሰባት ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ ጥቅም ፡ ከምታቀርበው ፡ ክስ፡ የተለየ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፲፮ ። ስለ ፡ አገር ፡ ልማድ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የካሣውን ፡ ልክ ፡ ምን፡ ያህል ፡ መሆኑን ፡ በርትዕ ፡ በአስተያየት ፡ ለመወሰንና ፡ እንዲሁም ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ለመነጋገር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማ ወቅ ፡ ዳኞች ፡ የአገር ፡ ልማድን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ይይዛሉ ።

(፪) ዳኞች ፡ እነዚህን ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ ጊዜያቸው ፡ ያለፈና ፡ ከሕሊና ፤ ከሰብ አዊ ፡ አእምሮ ፡ ተቃራንያን ፡ መሆናቸውን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባቸውም ።

(፫) የጉዳት ፡ ካሣውም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ከአንድ ፡ ሺሕ ፡ የኢት/ብር ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ፡፪ሺ፻፲፯ ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ።

(፩) በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደ ፡ ራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ የሚቈጠሩት ፡—

(ሀ) የተበደለው ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፤

(ለ) እነዚህ ፡ በሌሉበት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዕድሜ ፡ ታላቅ ፡ የሆነና ፡ ለመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፤

(ሐ) ልጆቹ ፡ ባይኖሩ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አባት ፤

(መ) አባት ፡ ባይኖር ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናት ፤

(ሠ) እናት ፡ ባትኖር ፤ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌላት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከወንድሞቹ ፡ ወይም ፡ ከእኅቶቹ ፡ ታላቅ ፡ የሆነና ፡ ለመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ስለ ፡ መካሥ ።

ቍ፡፪ሺ፻፲፰ ። ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

(፩) ዳኞች ፡ ከከሳሹ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የተወሰዱበት ፡ ዕቃዎችና ፡ እንዚሁም ፡ ዕቃ ዎች ፡ ከተወሰዱበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያፈሯቸውን ፡ ጥቅሞች ፡ ለከሳሹ ፡ እን ዲመለስለት ፡ ያዛሉ ።

(፪) ዕቃዎቹ ፡ ጠፍተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ተከሳሹ ፡ ግምታቸውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ተከሳሹ ፡ ሊመልሳቸው ፡ ለሚገባው ፡ ዕቃዎች ፡ ወጪ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደዚህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መክበር ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይጸናሉ ።

ቍ፡ ፪ሺ፻፲፱ ። በዐይነቱ ፡ ስለ ፡ መተካት ።

(፩) የተበላሹ ፡ ወይም ፡ የተጎዱ ፡ ዕቃዎችን ፡ የማበላሸቱ ፡ ወይም ፡ የጉዳቱ ፡ አላፊ ፡ ከሆነው ፡ ሰው ፡ እንዲተኩ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሠሩ ፡(እንዲታደሱ ) ፡ የሚስማማ ፡ ውጤት ፡ የሚሰጥ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ተከሳሹ ፡ ዐይነቱን ፡ እንዲተካ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሠራ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደዚህም ፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ያተካኩን ፡ ወይም ፡ ያሠራሩን ፡ ዐይነት ፡ ይወስናሉ ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ እንዲከፍል ፡ የተወሰነው ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግምቱን ፡ ይከፍላል ፡ እንጂ ፡ ዐይነቱን ፡ ይተካ ፡ ተብሎ ፡ ሊወሰንበት ፡ አይቻልም ።

ቍ፡ ፪ሺ፻፳ ። ስለ ፡ ክብርና ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ዝና ።

በሰዎች ፡ ክብር ፡ ወይም ፡ በመልካም ፡ ዝና ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ የተፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ እነዚህ ፡ የንቀፌታ ፡ ተግባሮች ፡ ያደረሱትን ፡ ውጤት ፡ ለመሻር ፡ በተከሳሹ ፡ ኪሣራ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ የስም ፡ ማደሻ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲገለጽና ፡ እንዲጻፍ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

ቍ፡ ፪ሺ፻፳፩ ። ማስጠንቀቂያዎች ።

(፩) ዳኞች ፡ ተከሳሹ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያመጣ ፡ ነገር ፡ እንዳይሠራ ፡ በመሥራትም ፡ ላይ ፡ ቢገኝ ፡ እንዳይቀጥል ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዳይጀምር ፡ የሚያግድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

(፪) የጉዳት ፡ ተግባር ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ ጉዳቱን ፡ የሚያመጣ ፡ መሆኑን ፡ ለማመን ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደዚሁም ፡ ከሳሹን ፡ የሚያስፈራው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራውን ፡ በመክፈል ፡ የማይካሥ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

ቍ፡ ፪ሺ፻፳፪ ። ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ውድድር ።

ተከሳሹ ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የሚያደርገውን ፡ የተንኰል ፡ ውድድር ፡ እንዲተው ፡ ዳኞች ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ፡፪ሺ፻፳፫ ። በይመስላል ፡ ስለሚፈጸም ፡ ተግባር ።**

ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በይመስላል ፡ እምነት ፡ አድርገው ፡ የፈጸሙት ፡ ተግባር ፡ በአድራጎቱ ፡ ወይም ፡ ባለመናገሩ ፡ ለዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ አላፊ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆናቸው ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

## ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተግባር ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

**ቍ፡፪ሺ፻፳፬።ስለ፡ አባት ፡ አላፊነት ።**

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አላፊነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ለተሠራው ፡ ሥራ ፡ አላፊ ፡ የሚሆን ፡ አባት ፡ ነው ።

**ቍ፡፪ሺ፻፳፭።የልጁ ፡ ሌሎች ፡ ጠባቂዎች ።**

**በአባት ፡ አላፊነት ፡ ምትክ ፡ ሆነው ፡ የሚጠየቁት ።**

(ሀ) በልጅዋ ፡ ላይ ፡ ባባትነት ፡ ሥልጣን ፡ በምትሠራበት ፡ ጊዜ ፡ እናት ።

(ለ) አካለመጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ከአባቱ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ሲኖር ፡ በእምነት ፡ የተሰጠው ፡ የልጁ ፡ ጠባቂ ።

(ሐ) ልጅ ፡ እተማሪ ፡ ቤት ፡ ሳለ ፤ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ በሚማርበት ፡ ጊዜ ፡ የቀለም ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ አስተማሪው ፤

(መ) ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ ለልጁ ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ በሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ አሠሪው ፡ ናቸው ።

**ቍ፡፪ሺ፻፳፮።ስለ ፡ መንግሥት ፡ አላፊነት ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ኪሣራውን ፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳል ።

(፪) የተደረገው ፡ ጥፋት ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ የደረሰ ፡ የሥራ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተጎዳው ፡ ሰው ፡ ኪሣራ ፡ ከመንግሥት ፡ ላይ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፤ ሆኖም ፡ ስለ ፡ ከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ መንግሥት ፡ የተባለውን ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ሹም ፡ መልሶ ፡ እንዲከፍለው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ሠራተኛው ፡ ያደረገው ፡ ጥፋት ፡ የግል ፡ ጥፋቱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንግሥት ፡ አላፊነት ፡ አይኖርበትም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፳፯ ። (፪) የሥራ ፡ ጥፋት ።**

(፩) ጥፋቱ ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ጥፋት ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ጥፋት ፡ አድራጊው ፡ በዚህ ፡ ጥፋት ፡ ላይ ፡ የወደቀው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ በሥልጣኑና ፡ ለሥራው ፡ ክፍል ፡ መልካም ፡ ያደረገ ፡ መስሎት ፡ የፈጸመው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ ውጭ ፡ በሆነው ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ግል ፡ ጥፋት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) በቅን ፡ ልቡና ፡ ያልተሠራ ፡ ለመሆኑ ፡ ተቃዋሚ ፡ ማስረጃ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሹሙ ፡ ወይም ፡ የሠራተኛው ፡ አሠራር ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ይገመታል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፰ ። (፫) ተመሳሳይነት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ሁለት ፡ ቍጥሮች ፡ የተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ ብንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ክፍለ ፡ አገሮችና ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ብተቋቋሙ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሠራተኞችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፱ ። የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ አላፊነት ።</u>

የማኅበሩ ፡ እንደራሴዎች ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ደመወዝተኞች ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ጊዜ ፡ አላፊነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቁ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረት ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፪፻ ። ስለ ፡ አሠሪ ፡ አላፊነት ።</u>

አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ሥራውን ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ አላፊነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ጥፋት ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቀው ፡ አሠሪው ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፩ ። ሥራዎችን ፡ ስለ ፡ ማካሄድ ።</u>

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ሁለት ፡ ቍጥሮች ፡ ለተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አፈጻጸም ፡ አላፊነት ፡ የደረሰው ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ ባለመሥራት ፡ የደረሰውን ፡ ጥፋት ፡ ሥራን ፡ በማከናወን ፡ ሐሳብ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በመሥራት ፡ ወይም ፡ ባለመሥራት ፡ የደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ሥልጣንን ፡ በመተላለፍ ፡ ሆኖ ፡ ሠሪው ፡ እንዳይሠራ ፡ በግልጽ ፡ ተከልክሎ ፡ ቢገኝ ፡ እንኳ ፤ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ምክንያቱን ፡ ካላወቀ ፡ ወይም ፡ ሊያውቀው ፡ ይገባው ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ኀላፊነት ፡ የሚጠየቀውን ፡ ከልከላው ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ከኀላፊነት ፡ አያድነውም ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፻፴፪ ። የሕሊና ፡ ግምት ።**

(፩) የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የማኅበር ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ደመወዘኛ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ በሚሠራበት ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፡ የስሕተት ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጉዳቱን ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በዚህ ፡ ግምት ፡ ላይ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ይፈቀዳል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፴፫ ። በሥልጣኑ ፡ ስላለመሥራት ።**

የጥፋቱን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ላለመፈጸም ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ሆኖት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቢሥልጣኑ ፡ ያከናወነው ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፴፬ ። በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ስለሚሠራ ፡ ሠራተኛ ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የተጠየቀውን ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ለሠራው ፡ ጥፋት ፡ ጥፋተኛው ፡ በሥራ ፡ ሰጪው ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነፃነቱንም ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ አሠሪው ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፴፭ ። ስምን ፡ ስለ ፡ ማጥፋት ።**

የጋዜጣ ፡ መሪ ፤ የአንድ ፡ ተባራሪ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ (ፓንፍሌት) ፡ አሳታሚ ፡ መጽሐፍ ፡ አውጪ ፡ ደራሲው ፡ ለጻፈው ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ አላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፴፮ ። የአላፊነቶች ፡ መደራረብ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ለአንድ ፡ ጉዳት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ የተረጋገጠ ፡ መሆኑ ፤ ጉዳት ፡ አድራጊው ፡ ላደረገው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ መክፈልን ፡ አያስቀርለትም ።

(፪) ጉዳትን ፡ ያደረሰውና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ለካሣው ፡ አከፋፈል ፡ የአንድነት ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ።

(፫) በሕጉ ፡ አስተያየት ፡ ረገድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በበኩሉ ፤ ጉዳት ፡ ያደረሰውን ፡ ዋነኛውን ፡ አላፊ ፡ በቀረበበት ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ካሣ ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ክስ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፴፯ ። የማይደፈሩ ፡ ሕጋዊ ፡ መብቶች ፡ (፩) ነጋሢ ።**

ጥፋትን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምንም ፡ የኀላፊነት ፡ ክስ ፡ አይቀርብም ።

BACK



ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፴፫ ። (፪) ስለ ፡ ሚኒስትሮች ፤ ስለ ፡ ፓርለማ ፡ አባሎችና ፡ ስለ ፡ ዳኞች ።

(ሀ) በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አባሎች ፡ ላይ ፤
(ለ) በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በፓርለማ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፤
(ሐ) በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳኞች ፡ ላይ ፤
የሥራቸው ፡ ነክ ፡ በሆነው ፡ ተግባር ፡ የኀላፊነት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብባቸው ፡ አይቻልም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፴፱ ። ልዩነት ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ ቊጥር ፡ ደንብ ፡ የተከበሩት ፡ ሰዎች ፡ በሥራቸው፡ ምክንያት ፡ ባደረጉት ፡ ተግባር ፤ በወንጀል ፡ ተቀጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ከሳሹ ፡ ጠቅሶ ባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ አይጸናባቸውም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፵ ። የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ስለሚወስናቸው ፡ ተግባሮች ።

መንግሥት ፡ በአላፊነት ፡ በሚጠየቅበት ፡ ጊዜ ፡ ክስ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ለመሆኑና ፡ እንደዚሁም ፡ የትኛው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ክፍል፡ በመጨረሻው ፡ ዐይነት ፡ አከፋፈል ፡ ወይም ፡ በእንዴት ፡ አኳኋን ፡ ዕዳውን ፡ መክ ፈል ፡ የሚገባው ፡ ለመሆኑ ፡ ያስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ ይወስናሉ ።

ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፵፩ ። አስረጅ ፡ ለማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ።

የደረሰበትን ፡ ጉዳት ፡ ልክና ፡ እንዲሁም ፡ የአካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ተከሳሹን ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍለው ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፵፪ ። ጉዳት ፡ አድራጊውን ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።

(፩) ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጉዳቱን ፡ የፈጸመው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በርግጥ፡ ለማወቅ ፡ ባልተቻለ ፡ ጊዜ ፡ በርትዕ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ አድርጓል፡ ለማለት ፡ የሚቻለውን ፡ ስብሰባና ፡ በዚሁ ፡ መካከል ፡ አጥፊው ፡ በርግጥ ፡ እንደሚገኝ፡ የታወቀውን ፡ ዳኞች ፡ ለጉዳቱ ፡ እንዲከስ ፡ ሊፈርዱበት ፡ ይችላሉ።
(፪) ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ለአድራጊው፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ለጉዳት፡ እንዲከስ፡ ለመፍረድ፡ ይችላሉ።

ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፵፫ ። ክስ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ተበዳዩ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ካሣ ፡ የሚጠይቅበት ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ።
(፪) ስለ፡ ሆነም ፡ ጉዳቱ ፡ በወንጀል ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሆኖ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ ርዝመት፡ የበለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የካሣው ፡ ጉዳይ ፡ ክስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ልክ ፡ በዚሁ፡ መሠረት ፡ ይሆናል ።
(፫) ተበዳዩ ፡ የራሱ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ የሚጠይቅበትና ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ፡ መበልጸግ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሚከራከርበት ፡ መብቱ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፵፩ ። ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ ወራሾች ።**

(፩) በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ የገንዘብ ፡ ጉዳት ፡ ወራሾች ፡ ካሣን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ። ስለ ፡ ሆነም ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤

(፪) የተበዳዩ ፡ ወራሾች ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ለሕሊና ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉት ፡ ተበዳዩ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ክስ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) የጉዳቱ ፡ አላፊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወራሾች ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ኀላፊው ፡ ተቈጥረው ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፵፪ ። ከተበዳዩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ።**

(፩) ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ባለዕዳቸው ፡ ጉዳት ፡ ደርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጉዳቱም ፡ ሰውነቱን ፡ ሙሉ ፡ አካሉን ፡ ወይም ፡ ክብሩን ፡ የሚነካ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሱ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ሊጠይቁ ፡ አይችሉም ።

(፪) ባለገንዘቦቹ ፡ ካበደሩበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅምን ፡ ብቻ ፡ የሚነካ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባሉት ፡ ባለገንዘቦች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ፡ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የተወሰኑትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመከተል ፡ የባለዕዳውን ፡ የክስ ፡ መብት ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፵፫ ። የገንዘብ ፡ መብት ፡ የማይተላለፍ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ለተበዳዩ ፡ የሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ መኖሩና ፤ ልኩም ፡ በፍርድ ፡ እስኪታወቅና ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፡ ተበዳዩ ፡ ለጉዳቱ ፡ አላፊ ፡ በሚሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ሊያስተላልፍ ፡ አይችልም ።

(፪) በፍርድ ፡ ከታወቀለትና ፡ ልኩም ፡ ከተወሰነለት ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ሊያስተላልፍ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፻፵፬ ። አላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ፡ የሚደረግ ፡ የውል ፡ ስምምነት ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ የሠራው ፡ ጥፋት ፡ የሚያስከትለውን ፡ አላፊነት ፡ ለማስወረድ ፡ ለማስወገድ ፡ መዋዋል ፡ አይፈቀድለትም ።

(፪) ሌላው ፡ ለሚሠራው ፡ ጥፋት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ በአላፊነት ፡ ሊጠየቅ ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ለሚሠራው ፡ ጥፋት ፡ አላፊ ፡ እንዳይሆን ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

(፫) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ጥፋትም ፡ ባይኖር ፡ በሚደርሰው ፡ አደጋ ፡ ሁሉ ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ የሚገባም ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ጥፋት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ካሣ ፡ አይከፈልም ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ።

BACK



ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፰ ። ግልግል ።

አንድ ፡ አደጋ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ለዚሁ ፡ አደጋ ፡ መሻሻያ ፡ ካሣ ፡ የማይከፈልበት ፡ መሆኑን ፡ ሊስማሙበት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ እንደሚካሥ ፡ በስምምነት ፡ ሊገላገሉ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፱ ። የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ጥፋት ፡ ተደርጓል ፡ ብሎ ፡ ለመወሰን ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ተከሳሹ ፡ ነፃ ፡ መለቀቁ ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ አያስከስሰውም ፡ ተብሎ ፡ መበየኑ ፤ ዳኞቹን ፡ አያግዳቸውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻ ። የኪሣራው ፡ መገመቻ ፡ ጊዜ ።

(፩) ዳኞች ፡ በተበዳዩ ፡ ላይ ፡ የደረሰበትን ፡ ጉዳት ፡ ለማመዛዘን ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጡበትን ፡ ቀን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ መያዝ ፡ አለባቸው ።

(፪) ሊደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ፍርድ ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ለመገመት ፡ የማይቻል ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሚጸና ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ሰጥተው ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲታይ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅ ረብ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ይችላሉ ።

(፫) ይህ ፡ ፍርድ ፡ እንደገና ፡ ይታይልን ፡ የማለት ፡ ጥያቄ ፡ ለጊዜው ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ከተወሰነበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከዘ ገየ ፡ ለመቅረብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፩ ። በፍርድ ፡ ያለቀ ፡ ነገር ፡ መጽናት ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በዳኞች ፡ የተደረገ ፡ የጉዳት ፡ ግምት ፡ የመጨረሻ ፡ ነው ።

(፪) ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ የተባለው ፡ ጉዳት ፡ በአመጣጡ ፡ ምክንያት ፡ አስ ቀድሞ ፡ ካሣ ፡ ከጠየቀበት ፡ ጉዳት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የሌለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለዚሁ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ በአዲስ ፡ ክስ ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፪ ። የይግባኝ ፡ አለመኖር ።

ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ጥቅም ፡ አከፋፈል ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ የተወሰነ ፡ ፍርድ ፡ ለበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለይግባኝ ፡ ለመቅረብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፫ ። የተጠበቁ ፡ ሁኔታዎች ።

ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ልዩ ፡ አስታ ያየት ፡ የሚሰጠው ፤

(ሀ) ዳኞች ፡ ሊገምቱት ፡ የሚገባቸውን ፡ የነገሩን ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ያላገባብ ፡ በመያዝ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥተው ፡ እንደ ፡ ሆ[illegible] ወይም ፡ ሊገምቱ ፡ የሚገባቸውን ፡

BACK



ትክክለኛውን ፡ መንገድ ፡ ትተው ፡ ያላገባብ ፡ የሆነውን ፡ ያገማመት ፡ መን ገድ ፡ ይዘው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በዳኞች ፡ የተወሰነው፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በግልጽ ፡ ከአእምሮ ፡ ግምት ፡ ውጭ ፡ የሆነና ፡ የተወሰነውም ፡ በማድላት ፡ ወይም ፡ በዝንባሌ ፡ መሆኑ ፡ እርግጥ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በዳኞቹ ፡ የተወሰነው ፡ የጉዳቱ ፡ ካሣ ፡ በሒሳብ ፡ ማሳሳት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ፡፪ሺ፻፶፩ ። በየጊዜው ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ።

(፩) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ አከፋፈል ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ተስማሚ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳስብ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ፡ ዳኞች ፡ የካሣው ፡ ሒሳብ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲከፈል ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህ፡ ሲሆን ፡ ባለዕዳው ፡ ኪሣራውን ፡ በየጊዜው ፡ ሊከፍል ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፶፪ ። ያንድነት ፡ ኀላፊነት ።

(፩) ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ በሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣን ፡ እንዲ ከፍሉ ፡ የተገደዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአንድነት፡እያንዳንዳቸው ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ለበደሉ ፡ ተግባር ፡ አነሣሽ ፡ በሆነውና ፡ በዋናው ፡ አድራጊ ፤ በበደሉ ፡ ተግባር ፡ ተባባሪዎች ፤ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግም ።

(፫) እንዲሁም ፡ የግዴታው ፡ መነሻ ፡ ለየአንዳንዶቹ ፡ ከውል ፡ ውስጥ ፡ ለየአንዳ ንዳቸው ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ አላፊነት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ልዩነት ፡ ሳይደ ረግ ፡ አንድ ፡ ለሆነ ፡ ጉዳት ፡ እንዲከሡ ፡ ግዴታ ፡ ባለባቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ አላፊነት ፡ የአንድነት ፡ አላፊነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፶፫ ። የማይከፋፈል ፡ ጥፋት ። (፩) መሠረቱ ።

አላፊዎች ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ጥፋት ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በመጨረሻው ፡ የተወሰነውን ፡ ዕዳ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ መቻል ፡ አለ በት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፶፬ ። (፪) በርትዕ ፡ ልዩነት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፤ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የአንድ ፡ ማኅበር ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ ደመወዘኛ ፡ ጥፋቱን ፡ የፈጸመው ፡ ሥራውን ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ዕዳውን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ አሠሪው ፡ ይከፍላሉ ፡ ብለው ፡ ዳኞች ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ዳኞቹ ፡ ውሳኔያቸውን ፡ በሚሰጡበት ፡ ጊዜ ፤ የተሠራውን ፡ ጥፋት ፡ ከባድ ነትና ፡ አድራጊው ፡ ጥፋቱን ፡ ሲሠራ ፡ የተሰጡትን ፡ ሥራዎች ፡ አብልጦ ፡ ለመፈጸም ፡ ሲል ፡ የነበረውን ፡ ፈቃድ ፡ መገመት ፡ አለባቸው ።

**ቍ፡፪ሺ፻፺፰ ። ማመዛዘንን ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ነገሮች ።**

(፩) ዳኞች ፡ ጥፋት ፡ አድራጊው ፡ ጥፋት ፡ በአደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ፈቃዱ ፡ ሥራውን ፡ በመልካም ፡ ለማከናወን ፡ መሆኑንና ፡ ያደረገውንም ፡ ጥፋት ፡ ከባድነት ፡ ያመዛዝናሉ ።

(፪) ዳኞቹ ፡ ኀላፊ ፡ ናቸው ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ያላቸውን ፡ የየአንዳንዳቸውን ፡ ሀብት ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ መያዝ ፡ የለባቸውም ።

**ቍ፡፪ሺ፻፺፱ ። የዚህ ፡ ልዩነት ፡ ወሰን ።**

በዳኞቹ ፡ በኩል ፡ አንዳች ፡ የኀላፊነት ፡ ክፍያ ፡ የማይፈቀደው ፤

(ሀ) ኀላፊነቱን ፡ ያመጣው ፡ ሥራ ፡ ታስቦ ፡ ለመጉዳት ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ወይም ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ አድራጊው ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻ ። የሚከፋፈል ፡ ጥፋት ።**

(፩) ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ በሆነ ፡ ጉዳይ ፡ የጥፋት ፡ ተግባርን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ የተባበሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ በመጨረሻ ፡ በየአንዳንዳቸው ፡ መካከል ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ዕዳ ፡ በርትዕ ፡ ይወስኑባቸዋል ።

(፪) ዳኞች ፡ በሚሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ የነበሩትን ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ በተለይም ፡ የየአንዳንዱን ፡ በደለኛ ፡ ጥፋት ፡ ያደረሰውን ፡ የጉዳት ፡ ተግባር ፡ መጠንና ፡ የጥፋቱንም ፡ ከባድነት ፡ መገመት ፡ አለባቸው ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፩ ። ስለ ፡ መዳረግ ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ከሚወሰነው ፡ ዕዳ ፡ የክፍያውን ፡ ድርሻውን ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ሲሆን ፤ ዕዳውን ፡ በሙሉ ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ዕዳውን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ግዴታ ፡ ባለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ጥያቄውን ፡ ለማቅረብ ፡ በተበደለው ፡ ሰው ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ይቈጠራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ኍ፡፪ሺ፪፻፪ ። ጠቅላላ ፡ መሠረት ።**

በሌላ ፡ ሰው ፡ የሥራ ፡ ድካም ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ በመገልገል ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ጥቅም ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፤ አላገባብ ፡ ጥቅም ፡ ባገኘበት ፡ መጠንና ፡ ለባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ ጉልበቱ ፡ ለደከመው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡

BACK



አድራጎት ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ ለባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ ጉልበቱ ፡ ለደ ከመው ፡ ሰው ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፫ ። ያላገባብ ፡ የተገኘ ፡ መበልጸግ ፡ ስለ ፡ መቅረቱ ።

(፩) መልስ ፡ በሚባልበት፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ ላለመበልጸጉ ፡ ማስረጃ ፡ ባቀረበበት፡ መጠን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ተከሳሹ ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ዕቃውን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አስተላልፎ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ መመለስ ፡ እንዳለበት ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ አስተላ ልፎ ፡እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ያለ ፡ አገባብ ፡ የበለጸገበትን ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የወሰደውን ፡ እንዲመልስ ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የማይገባውን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፬ ። የማይገባውን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ሊከፍል ፡ የማይገባውን ፡ ነገር ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ እንዲመለስለት ፡ የመጠ የቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የሚከፈለው ፡ ነገር ፡ የተቀበለው ፡ እምነትን ፡ በሚያጐድል ፡ ሁኔታ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የማይገባውን ፡ ነገር ፡ የከፈለው ፡ ሰው ፡ ከከፈለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ይህ ፡ የከፈለው ፡ ነገር ፡ የሰጠውን ፡ ፍሬ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊውን ፡ ወለድ ፡ ጭምር ፡ እንዲመልስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፭ ፡ ስሕተት ፡ ስላለመኖሩ ።

ሊከፍለው ፡ የማይገባው ፡ ዕዳ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀና ፡ የሚያስከፍለውም ፡ ምክ ንያት ፡ ያለመኖሩን ፡ እየተረዳው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ ይመለስልኝ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፮ ። በቂ ፡ ምክንያት ።

(፩) የመክፈሉ ፡ ጉዳይ፡ የተፈጸመው ፡ በይርጋ ፡ ለታገደ ፡ ዕዳ ፡ (ወይም) ፡ የሕሊና ፡ ግዴታ ፡ የበጎ ፡ አድራጎትን ፡ መንፈስ ፡ በመከተል ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለከፋዩ ፡ አይመለስለትም ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የከፈለው ፡ ሰው ፡ የሚከፍለውን ፡ ነገር ፡ ያለ ዋጋ ፡ የመስጠት ፡ ችሎታ ፡ ያልነበረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያላገባብ ፡ የከፈለው ፡ ሊመለስለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፯ ። የማይመለስ ፡ ዕዳ ።

(፩) የማይገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ያላገባብ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ የተቀበለውን ፡ ገን

BACK



ዘብ ፡ ያላገባብ ፡ ለከፈለው ፡ ሰው ፡ የማይመልስለት ፡ ይህ ፡ ባለገንዘብ ፡ የብ ድሩ ፡ ሒሳብ ፡ ስለ፡ተከፈለው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያበደረበትን ፡ ሰነድ ፡ ቀዶ ፡ ወይም ፡ ሰርዞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዋሶቹን ፡ ከዕዳው ፡ ነፃ ፡ አውጥቶዋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከእውነተኛው ፡ ባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ሊቀበል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ በይርጋ ፡ አሳልፎ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ያላግባብ ፡ የከፈለው ፡ ሰው ፡ ሒሳቡን ፡ ለመጠ የቅ ፡ የሚችለው ፡ ከዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፻፷፰ ። የዚህ ፡ ክፍሉ ፡ ተፈጻሚነት ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በእጁ ፡ የቈየውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ የተገ ደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሕግ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የተባለውን ፡ ዕቃ ፡ ከመለዋወጥ ፡ የተነሣ ፡ ያሉት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚከተሉት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናሉ ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፻፷፱ ። የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ወጪ ።**

የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ ዕቃው ፡ እንዳይጠፋ ፡ ወይም ፡ እንዳይበላሽ ፡ ያደረገው ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ጠቃሚ ፡ ሳይሆን ፡ ከቀረ ፡ ወይም ፡ የወጪው ፡ ግዴታ ፡ ዕቃውን ፡ ሊመልስ ፡ በተገደደው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ተገዳጁ ፡ ኀላፊ ፡ በሚሆንበት ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ካልተ ገኘ ፡ በቀር ፡ ተገዳጁ ፡ ለተባለው ፡ ጉዳይ ፡ ያወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ሊመለስለት ፡ ይገባል ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፻፸ ። ስለ፡ዕቃው ፡ አጠባበቅ ፡ የተደረገ ፡ ወጪ ።**

የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለመመለስ ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ ለዕቃው ፡ አጠባበቅ ፡ ስለ ፡ ተደረ ገው ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በይዞታው ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ከፈለው ፡ ግብር ፡ እንዳች ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፻፸፩ ። የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ስላደረገው ፡ ወጪ ።**

(፩) እንደዚሁም ፡ ለዕቃው ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ፡ የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ ከፍ ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕቃውን ፡ ለመመለስ ፡ የተገደደው ፡ ሰው ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ያወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ሊመለስለት ፡ ይገባል ።

(፪) ቢሆንም ፡ ለዕቃው ፡ መጀመሪያ ፡ ከነበረው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ብልጫ ፡ እንጂ ፤ ዕቃውን ፡ በሚመልስበት ፡ ጊዜ ፡ ከሚገኘው ፡ የዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ በላይ ፡ ባደረገው ፡ ወጪ ፡ ልክ ፡ ሊጠይቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፪ ። ክፉ ፡ ልቡና ።

(፩) ወጪ፡ ገንዘብ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ ዕቃውን ፡ ለመመለስ ፡ ግዴታ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ያውቅ፡እንደ፡ነበረ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ይገባው ፡ እንደ ፡ ነበረ፡ ርትዕም ፡ ሲያስገድድ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን፡ ኪሣራ ፡ ዳኞች ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ በጭራሽ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ደግሞ ፡ ርትዕ ፡ ሲያስገድድ ፡ ለከሳሹ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፍልበት ፡ ቢበዛ ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፫ ። የማለያየት ፡ መብት ።

የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለመመለስ ፡ የተገደደው ፡ ሰው ፡ ዕቃውን ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ አገጣጥሞት ፡ የቈየውን ፡ ነገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሳይደርስ ፡ ለማላቀቅ ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለይቶ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፬ ። የመያዝ ፡ መብት ።

(፩) የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት፡ ቍጥሮች ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሊመለስለት ፡ የሚገባውን ፡ የኪሣራ ፡ ወጪ፡ ገንዘብ ፡ ካልተቀበለ ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ ኪሣራው ፡ በሚከፈልበት፡ ቀን ፡ መከፈሉን ፡ የሚያረጋግጥለት ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ካልተቀበለ ፡ አልመልስም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ዕቃውን ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ ለሌባ ፡ ወይም ፡ ዕቃውን ፡ እጅ፡ ሲያደርግ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የሚሰጠው፡ አንዳች ፡ መብት ፡ እንደሌለው ፡ እያወቀ ፡ እጅ ፡ ባደረገ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ አይጸናለትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፭ ። ስለ ፡ ዕቃው ፡ መበላሸት ።

(፩) የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ ዕቃውን ፡ አበላሽቶ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ለባለመብቱ ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) የዕቃው ፡ መበላሸት ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ የደረሰ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፤ ዕቃው ፡ በተበላሸበት ፡ ጊዜ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ወይም፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የሚሰጠው ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ያውቅ ፡ ኖሮ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ መበላሸት ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፡ ፪ሺ፱፻፸፮ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መጥፋት ።

(፩) ዕቃው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በሚጠፋበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



(፪) በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ለባለመብቱ ፡ ዕቃው ፡ በዐይነቱ ፡ ሊከ ፈለው ፡ በማይቻልበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆ ናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸፯ ፡ የኪሣራው ፡ ልክ ።

(፩) የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ ዕቃውን ፡ ለመመለስ ፡ ባልተቻለበት ፡ ቀን ፡ ከነበ ረው ፡ ዋጋ ፡ እኩል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የሚሰጠው ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ እንደሌለው ፡ ያውቅ ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ ሁኖ ፡ ስለ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፫) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ እንዲመለስለት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በእጁ ፡ ይዞት ፡ እንደ ፡ ኖረ ፡ ሆኖ ፡ ኪሣራው ፡ ይታሰብለታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸፰ ፡ ዕቃው ፡ ያስገኘው ፡ ፍሬ ።

(፩) የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ የተገደደ ፡ ሰው ፡ የተቀበለው ፡ ዕቃ ፡ ያፈ ራውን ፡ ነገር ፡ ያስቀራል ።

(፪) ዕቃውን ፡ እጅ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ የሚጸና ፡ ውል ፡ የሚሰጠው ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ እንደሌለው ፡ እያወቀ ፡ እጅ ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለከሳሹ ፡ ዕቃው ፡ ያፈራውን ፡ ግምት ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

## አንቀጽ ፡ ፲፬ ።
## ስለ ፡ እንደራሴነት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸፱ ፡ የእንደራሴነት ፡ ምንጭ ።

የሌላ ፡ ሰው ፡ እንደራሴ ፡ በመሆን ፡ ሥራዎችን ፡ የመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ የሚገ ኘው ፡ ከሕግ ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹ ፡ ስለ ፡ ሥልጣን ፡ ፎርም ።

ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፤ ሕጉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ፎርም ፡ እንዲደረግ ፡ ያስገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወሉን ፡ የሚፈጽምበት ፡ ሥልጣን ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ፎርም ፡ ለወ ኪሉ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፩ ፡ ስለ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ።

(፩) የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ የተገኘው ፡ በውል ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥልጣኑ ፡ የሚወሰነው ፡ በተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

(፪) እንደራሴው ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ አስታውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሦስተኛው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑ ፡ የሚጸናው ፤ ባስታወቀው ፡ ማስታወቂያ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡፡

(፫) የእንዳራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚተረጐመው ፡ ሳይስፋፋ ፡ በጠባቡ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፪ ፡፡ ስለ ፡ ሥልጣኑ ፡ መቅረት ፡፡**

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ እንደራሴው ፡ ወይም ፡ ሿሚው ፡ መሞቱ ፡ ወይም ፡ የሌለ ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ መክሠሩ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአንድ ፡ ጽሑፍ ፡ የተገኘው ፡ ሥልጣን ፡ ይቀራል ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ መኖሩ ፡ ሲቀር ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ ይቀራል ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፫ ፡፡ ሥልጣንን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ፡፡**

(፩) እንደራሴ ፡ ሿሚው ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ በእሱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ለእንደራሴው ፡ የሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ሊቀንስበት ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ ሊያስቀርበት ፡ ይችላል ፡፡

(፪) ይህን ፡ መብት ፡ የሚያስቀር ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ማንኛውም ፡ ጽሑፍ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፬ ፡፡ እንደራሴነትን ፡ ስለ ፡ መመለስ ፡፡**

(፩) ሥልጣኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጽሑፍ ፡ የተሰጠው ፡ እንደራሴ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፤ ይህን ፡ የተሰጠውን ፡ የሥልጣን ፡ ጽሑፍ ፡ ለሿሚው ፡ መመለስ ፡ አለበት ፡፡

(፪) እንደራሴው ፡ ሒሳቡ ፡ ሳይጣራና ፡ የሚገባኝን ፡ ሿሚው ፡ ሳይሰጠኝ ፡ የተሰጠኝን ፡ ሥልጣን ፡ ይዤ ፡ እቈያለሁ ፡ ለማለት ፡ አይፈቀድለትም ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፭ ፡፡ የእንደራሴነቱ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መጥፋት ፡፡**

እንደራሴው ፡ የሹመቱ ፡ ወረቀት ፡ መጥፋቱን ፡ ያስታውቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሿሚው ፡ በእንደራሴው ፡ ኪሣራ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የእንደራሴነቱን ፡ መሰረዝ ፡ የሚገልጽ ፡ ውሳኔ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፮ ፡፡ ሥልጣንን ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ፡፡**

ከአንድ ፡ እንደራሴ ፡ ጋራ ፡ ሕጋዊ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሁል ጊዜ ፡ እንደራሴው ፡ ሥልጣኑን ፡ እንዲያረጋግጥለት ፡ ሊያስገድድና ፡ እንደዚሁም ፡ የእንደራሴነቱ ፡ ተግባር ፡ በጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደራሴው ፡ ስለ ዚሁ ፡ ተግባር ፡ በሚገባ ፡ የፈረመበትን ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ፡፡

ቍ፡፪ሺ፪፻፳፯።ተቃዋሚ ፡ ጥቅሞች ።

(፩) እንደራሴው ፡ በፈጸመው ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የሿሚውና ፡ የእንደራሴው ፡ ጥቅሞች ፡ የሚቃወሙ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ውል ፡ የፈረመው ፡ ፫ኛ ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ያወቀና ፡ ሊያውቀውም ፡ የሚገባ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሿሚው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ የተፈጸመው ፡ ውል ፡ ሊፈርስ፡ ይችላል ።

(፪) ሿሚው ፡ የዚሁኑ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ካወቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለት፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አሳቡን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ይህን ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተቀበለ ፡ ወዲህ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሉን ፡ የመቀጠል ፡ አሳቡን ፡ ያልገለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ይፈርሳል ።

ቍ፡፪ሺ፪፻፳፰።ከገዛ፡ ራስ ፡ ጋራ ፡ ስለሚደረግ ፡ ውል ።

(፩) እንደራሴው ፡ ለራሱ ፡ ጉዳይ ፡ በመሥራትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ በመሥራት ፡ ውሉን ፡ ከራሱ ፡ ጋራ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሿሚው ፡ ይህ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ በ፪ና ፡ በ፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተሰጡ ፡ ውሳኔዎች ፡ ለዚህም ፡ ተፈጻሚነት ፡ አላቸው ።

(፫) ስለ ፡ ኮሚሲዮኔሮች ፡ የተሠሩት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ። (ቍ) ፡

ቍ፡፪ሺ፪፻፳፱።ፍጹም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደራሴነት ።

(፩) እንደራሴው ፡ ከወኪልነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ሳያልፍ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የመዋዋል ፡ ተግባሮችን ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ በርሱ ፡ የተፈጸሙት ፡ ተግባሮች ፡ በቀጥታ ፡ በሿሚው ፡ እንደ ፡ ተፈጸሙ ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በእንደራሴው ፡ ፈቃድ ፡ ላይ ፡ የተፈጸሙትን ፡ ጕድለቶች ፡ ሿሚው ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ጠቅሶ ፡ ሊከራከርባቸው ፡ ይችላል ።

(፫) ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ እንደራሴው ፡ ባደረሰበት ፡ የማሳሳት ፡ ጉዳት ፡ ሿሚውን ፡ ሊከራከረው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴ ። የሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ስለ ፡ ማለፍ ፤ ወይም ፡ ቀሪ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥልጣን ።

(፩) እንደራሴው ፡ የሥልጣኑን ፡ ወሰን ፡ በመተላለፍ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በስሙ ፡ የተሠራለት ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ እንደራሴው ፡ የፈጸመውን ፡ ተግባር ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ እንደራሴው ፡ ቀሪ ፡ በሆነው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ በስሙ ፡ የተሠራለት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ በስሙ ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

<u>ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺፩ ። ለሿሚ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ምርጫ ።</u>

(፩) ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ የተዋዋሉ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ሿሚው ፡ በስሙ ፡ የተሠራለትን ፡ ሥራ ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ ለማፍረስ ፡ የቈረጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በፍጥነት ፡እንዲያስታውቃቸው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሿሚው ፡ የመቀበሉን ፡ ውሳኔ ፡ በፍጥነት ፡ ሳያስታውቃቸው ፡ የቀረ ፡እንደ፡ ሆነ ፤ እንደራሴው ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ እንዳልተቀበለው ፡ ይቈጠራል ።

<u>ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺፪ ። የመቀበሉ ፡ ውጤት ።</u>

ሿሚው ፡ እንደራሴው ፡ የፈጸመውን ፡ ተግባር ፡ ያጸደቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ ራሴው ፡ የፈጸመውን ፡ ተግባር ፡ ከውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ ሳያልፍ፡ እንደ ፡ ፈጸ መው ፡ ይቈጠራል ።

<u>ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺፫ ። ያለመቀበል ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።</u>

(፩) እንደራሴው ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሿሚው ፡ ባልተቀበለው ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከተው ፡ መሠ ረት ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ መሰረዝና ፡ መፍረስ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻ ሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ የስምምነቱን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን፡ የእንደራሴነትን ፡ ሥልጣን ፡ መኖሩን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ በማመኑ ፡ ስለ ፡ ደረ ሰበት ፡ ጉዳት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ካሣ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺፬ ። ስለሚደርሱት ፡ አላፊነቶች ።</u>

(፩) ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ መጠየቅ ፡ የሚገባው ፡ እንደራ ሴው ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፤ የእንደራሴነቱን ፡ ሥልጣን ፡ የሚያስቀረውን ፡ ምክንያት ፡ ባለ ማወቅ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ሠርቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

(፫) እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚ ጠየቀው ፡ ሿሚው ፡ ነው ።

<u>ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺፭ ። (፩) ስለ ፡ ሿሚው ፡ አላፊነት ።</u>

በሌላም ፡ በኩል ፡ በሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ ሿሚው ፡ ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ በሙሉ ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፤

(ሀ) ሿሚው ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥልጣን ፡ አስታውቆ፡ ሳለ ፤ የሰጠውን ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊሉ ፡ መሰ ረዙን ፡ ለዚያው ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ያላስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሿሚው ፡ ለእንደራሴው ፡ የሰጠውን ፡ የእንደራሴነት፡ ሥልጣን ፡ ጽሑፍ ፡ እን ዲመልስለት ፡ እንደራሴውን ፡ ከማስገደድ ፡ ችላ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆንና ፡ እንዲ

ሁም ፡ ይህ ፡ ሿሚው ፡ የሰጠው ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ጽሑፍ ፡ በፍ ርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ያላደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አኳኋን ፡ ሿሚው ፡ በሚሰጣቸው ፡ መግለጫዎች ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ወይም ፡ በአመራሩ ፡ ወይም ፡ ሊያደርግ ፡ የሚገባውን ፡ ባለማድረጉ ፡ ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ የሚያደርጉት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገ ኖች ፡ እንደራሴው ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መስሎዋቸው ፡ ስሕተት ፡ ያደረ ሰባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፯ ። ከአላፊነት ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለው ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከመዋዋሉ ፡ በፊት ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥልጣን ፡ ጽሑፍ ፡ ዐውቆ ፡ የተዋዋለ ፡ ከሆነ ፤ በነገሩ ፡ የማታ ለል ፡ ሥራ ፡ ከሌለበት ፡ በቀር ፡ ከሥልጣኑ ፡ አልፎ ፡ የሠራውን ፡ እንደራሴ ፡ ማንኛውንም ፡ ኪሣራ ፡ ሊጠይቀው ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ የሚዋዋለው ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ ግድ ፡ የሌለው ፡ ከሆነና ፡ እንደራሴውም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የተፈጸመውን ፡ ውል ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ለማድረግ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ማንኛውንም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፰ ። እንደራሴው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ስለሚፈጽመው ፡ ተግባር ።

(፩) እንደራሴው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገ ኖች ፡ ከእንደራሴው ፡ ጋራ ፡ መዋዋላቸውን ፡ ቢያውቁትም ፡ እንኳ ፤ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ የፈጸማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ለሚያስከትሉዋቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ መብ ቶች ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ባለቤት ፡ ይሆናል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተባሉ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ከሿሚው ፡ ጋራ ፡ አንዳ ችም ፡ ቀጥታ ፡ ግንኙነት ፡ የላቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእንደራሴው ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ የእንደራሴውን ፡ መብት ፡ ከሿሚው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፻፺፱ ። ስለ ፡ ሿሚው ፡ መብቶች ።

(፩) ሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያገኙዋቸው ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ እንደራሴው ፡ ለሿሚው ፡ ሲል ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ያፈራቸ ውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፤ ሿሚው ፡ ገንዘቦቼ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ለመጠ የቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ እንደራሴው ፡ ለሿሚው ፡ ሲል ፡ ያገኛቸውን ፡ የገንዘብ ፡ መብ ቶች ፡ ሿሚው ፡ በእንደራሴው ፡ ተተክቶ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ስለሆነም ፤ ሿሚው ፡ በበኩሉ ፡ በእንደራሴው ፡ ዘንድ ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ ፈጽሞ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ እነዚህን ፡ መብቶች ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ወኪልነት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፸፱ ፡ ትርጓሜ ።**

ውክልና ፡ ማለት ፡ ተወካይ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወካይ ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሕጋዊ ፡ ሥራዎች ፡ በወካዩ ፡ ስም ፡ ለማከናወን ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ነው ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የወኪልነት ፡ ሥልጣን ፡ አቋቋምና ፡ የሥራው ፡ ግብ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፹ ። የውክልና ፡ ፎርም ።**

(፩) ውክልና ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ቢሆንም ፡ ተወካዩ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባው ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፤ ስለ ፡ አፈ ጻጸሙ ፡ በአንዳንድ ፡ ሕጋዊ ፡ ፎርም ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲሆን ፡ ውክልናው ፡ ለተወካዩ ፡ ሊሰጠው ፡ የሚገባው ፡ ይኸው ፡ ሕግ ፡ በሚያዝዘው ፡ ፎርም ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፹፩ ። ውክልናን ፡ ስለ ፡ መቀበል ።**

(፩) ውክልናን ፡ የመቀበል ፡ ጉዳይ ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ ሊፈጸም ፡ ይች ላል ።

(፪) ተወካዩ ፡ ወኪል ፡ የሚሆንበት ፡ ነገር ፡ ከሚያካሂደው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ከሆነ ፤ ወይም ፡ ከሞያ ፡ ሥራው ፡ አመራር ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ጉዳይ ፡ ከሆነ ፤ ወይም ፡ ይህንን ፡ የመሰለውን ፡ ጉዳይ ፡ ለመሥራት ፡ ፈቃደኛ ፡ ለመሆኑ ፡ በአደባባይ ፡ ገልጾ ፡ አሳብ ፡ በማ ቅረብ ፡ አስታውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውክልናውን ፡ የማይቀበል ፡ ለመሆኑ ፡ ወዲ ያውኑ ፡ ካልገለጸ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፹፪ ። የውክልናው ፡ ወሰን ።**

(፩) የውክልናው ፡ ወሰን ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ ተጠቅሶ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ ለውክልናው ፡ የሚሰጠው ፡ ወሰን ፡ እንደ ፡ ጉዳዩ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፪) ውክልናው ፡ ለአንድ ፡ ልዩ ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ጉዳዮች ፡ ወይም ፡ ለወካዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ጠቅላላ ፡ ውክልና ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፹፫ ። ጠቅላላ ፡ ውክልና ።**

በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የተደረገ ፡ ውክልና ፡ ለተወካዩ ፡ የአስተዳደርን ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ ከሚያደርገው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጠውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፹፬ ። የአስተዳደር ፡ ሥራ ።**

(፩) የወካዩን ፡ ሀብት ፡ የማስቀመጥ ፡ የመጠበቅ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ለማያልፍ ፡ ዘመን ፡ የማከራየት ፤ በብድር ፡ የተሰጠውን ፡ ሀብት ፡ የመሰብሰብ ፤ ከሀብቱ ፡

BACK



የሚመጣውን ፡ ገቢ ፡ ተቀብሎ ፡ የማስቀመጥና ፡ ለተከፈሉ ፡ ዕዳዎች ፡ ደረሰኝ ፡ የመስጠት ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ የሰብልን ፡ መሸጥ ፤ ለሽያጭ ፡ የተመደቡ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወይም ፡ ይበላሻሉ ፡ ተብለው ፡ የሚታሰቡ ፡ ነገሮችን ፡ የመሸጥ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ አስተዳደር ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፭ ። ልዩ ፡ ውክልና ።

(፩) ተወካዩ ፡ ከአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ ልዩ ፡ ውክልና ፡ እንዲኖረው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) ተወካዩ ፡ ልዩ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ ከሌለው ፡ በቀር ፤ ይልቁንም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ አሲዞ ፡ መበደር ፡ ካፒታሎችን ፡ በአንድ፡ማኅበር ፡ ዘንድ ፡ ለማግባት ፡ የለውጥ ፡ ግዴታን ፡ ውል ፡ መፈራረም ፡ መታረቅ ፡ ለመታረቅ ፡ ውል ፡ መግባት ፡ ስጦታ ፡ ማድረግና ፡ በአንድ፡ጉዳይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ መከራከር ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፮ ። ልዩ ፡ ውክልና ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ።

(፩) ልዩ ፡ ውክልናው ፡ በላዩ ፡ ተዘርዝረው ፡ የተመለከቱትን ፡ ጉዳዮችና ፡ የነዚሁ ፡ ተከታታይና ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነውን ፡ እንደ ፡ ጉዳዩ ፡ ዐይነትና ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ አሠራር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ከማከናወን ፡ በቀር ፡ ለተወካዩ ፡ ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጠውም ።

(፪) ተወካዩ ፡ ከተሰጠው ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ አልፎ ፡ የፈጸመውን ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፡ ወካዩ ፡ ካላጸደቀው ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ አመራር ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወካዩን ፡ አያስገድደውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፯ ። የማጽደቅ ፡ ግዴታ ።

(፩) ተወካዩ ፡ በውክልናው ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣንና ፡ ወካዩ ፡ ከሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውጭ ፡ በማለፍ ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተወካዩ ፡ የሠራው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሥራውን ፡ ወካዩ ፡ እንዲያጸድቅለት ፡ ይገደዳል ።

(፪) ወካዩ ፡ የሥራውን ፡ አረማመድና ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ ሁኔታ ፡ ቢረዳው ፡ ኖሮ ፡ ለተወካዩ ፡ የሥራውን ፡ የሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ማስፋት ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ መገመት ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ የሚታመን ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝም ፡ አፈጻጸሙ ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፫) ተወካዩ ፡ ያልተፈቀደለትን ፡ ሥራ ፡ በገዛ ፡ አሳቡ ፡ ከመፈጸሙ ፡ አስቀድሞ ፡ የሥልጣኑን ፡ ወሰን ፡ እንዲያሰፋለት ፡ ወካዩን ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚያስችለው ፡ ምቹ ፡ መንገድ ፡ እያለው ፡ ፈቃድ ፡ ሳይጠይቅ ፡ ቸል ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ተግባሩን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ለወካዩ ፡ ሳያስታውቀው ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ የፈጸምኩትን ፡ አጽናልኝ ፡ ብሎ ፡ ወካዩን ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

BACK



## ክፍል ፡ ፪ ።

## የተወካዩ ፡ ግዴታዎች ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፰ ። ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ ቅን ፡ ልቡና ።**

(፩) ተወካዩ ፡ ከወካዩ ፡ ጋራ ፡ በሚያስተሳስረው ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

(፪) የውክልናውን ፡ ሥልጣን ፡ የሚያስቀሩትን ፡ ምክንያቶችና ፡ ወይም ፡ የቃላቸውን ፡ አነጋገር ፡ ማሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንበትን ፡ ምክንያት ፡ ለወካዩ ፡ አሳብ ፡ ማቅረብና ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፱ ። አፈጻጸሙ ።**

(፩) ተወካዩ ፡ ሥራውን ፡ የሚፈጽመው ፡ በተለይ ፡ ለወካዩ ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ በሚችልበት ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ስለዚሁም ፡ በወኪልነቱ ፡ ምክንያት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወካዩ ፡ ሳያውቅ ፡ እንዳችም ፡ ጥቅም ፡ ለግሉ ፡ መውሰድ ፡ አይችልም ።

(፪) ተወካዩ ፡ በውክልናው ፡ ምክንያት ፡ ያገኛቸውን ፡ መረጃዎች ፤ የወካዩን ፡ ጥቅም ፡ በሚጎዳ ፡ ሁኔታ ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፲ ። የውክልናው ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ ።**

(፩) ተወካዩ ፡ በውክልና ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ ገቢ ፡ ላደረገው ፡ ገንዘብና ፡ በሥራውም ፡ ላገኘው ፡ ትርፍ ፡ ሁሉ ፡ ያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ለወካዩ ፡ የማይገባው ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ሥራ ፡ ለወካዩ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ተወካዩ ፡ ለወካዩ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ አውሎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገንዘቡን ፡ ከወሰደበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ አንድም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳያስፈልግ ፡ እስከ ፡ ወለዱ ፡ ለወካዩ ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባል ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፪፻፲፩ ። አስፈላጊ ፡ ትጋት ።**

(፩) ተወካዩ ፡ በውክልና ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ በሚገኝባቸው ፡ ጊዜዎች ፡ ሁሉ ፡ በውክልናው ፡ የተሰጠውን ፡ አደራ ፤ አንድ ፡ መልካም ፡ የቤት ፡ ሰብ ፡ አባት ፡ ቤቱ ፡ ሰቡን ፡ ለመጠበቅ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ በትጋትና ፡ በጥንቃቄ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) በአላፊነት ፡ የሚጠየቀው ፡ በማታለል ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሥራው ፡ አመራር ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ጥፋቶችም ፡ ጭምር ፡ ነው ።

(፫) የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ በነፃ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የወካዩን ፡ ጉዳዮች ፡ እንደራሱ ፡ ጉዳይ ፡ አድርጎ ፡ ተጠንቅቆ ፡ ከሠራ ፡ በአላፊነት ፡ ሊያስጠይቀው ፡ አይችልም ።

**ቍ፡ ፪ሺ፩፻፲፪ ። ዋቢነት ፡ የሌለው ፡ ጒዳይ ።**

(፩) በውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ የሚገኝበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ተወካዩ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ቢሠራም ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ ላደረገው ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ጒዳይ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ አላፊነት ፡ ሊጠየቅ ፡ አይገባውም ።

(፪) ውሉን ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችልና ፡ በገባበት ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ ገንዘቡን ፡ የማይከፍል ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ የሆነ ፡ እን ፡ ደሆነ ፡ አፈጻጸሙ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጻፈው ፡ የተለየ ፡ ይሆናል ።

**ቍ፡ ፪ሺ፩፻፲፫ ። የሒሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ተወካዩ ፡ ወካዩ ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ የሥራውን ፡ አካሄድ ፡ መግለጫና ፡ ሒሳብ ፡ በየጊዜው ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) የተሰጠውን ፡ የውክልና ፡ ሥራ ፡ መፈጸሙን ፡ ያለመዘግየት ፡ ለወካዩ ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባል ።

**ቍ፡ ፪ሺ፩፻፲፬ ። የሥራውን ፡ አመራር ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ።**

(፩) ተወካዩ ፡ ያቀረበው ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ መግለጫ ፡ ለወካዩ ፡ ደርሶት ፡ የጒዳዩ ዐይነትና ፡ ልማዳዊው ፡ ደንብ ፡ ለመልስ ፡ መስጫ ፡ የሚበቃ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ሚፈቅድለት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፤ (በቀረበለት ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ የሚፈቅድ ፡ ወይም ፡ የማይፈቅድ ፡ መሆኑን) ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠው ፡ ከተወሰነው ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ በዝምታ ፡ ያሳለፈው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተወካዩ ፡ የያዘውን ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ ዘዴ ፡ ወካዩ ፡ ፈቅዶ ፡ እንደ ፡ ተቀበለው ፡ ያስቈጥረዋል ።

(፪) ተወካዩ ፡ ወካይ ፡ ከሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ አልፎ ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በውክልናው ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ በላይም ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለወካዩ ፡ ላቀረበው ፡ መግለጫ ፡ ተቃዋሚ ፡ ወይም ፡ አጽዳቂ ፡ መልስ ፡ ካልተሰጠው ፡ አፈጻጸሙ ፡ ከላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ይሆናል ።

**ቍ፡ ፪ሺ፩፻፲፭ ። በተወካይ ፡ ስለ ፡ መተካት ። (፩) የሚቻልበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ከውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ የሆነውን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ምትክ ፡ አድርጎ ፡ እንዲያሠራ ፡ ወካዩ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፤ ተወካዩ ፡ የተወከለበትን ፡ ሥራ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) የተወካዩ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መተካቱ ፡ እንደ ፡ ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ ለወካዩ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ ከሆነ ፡ ተወካዩ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ተተክቶ ፡ ሥራውን ፡ እንዲያሠራ ፡ እንደ ፡ ተፈቀደለት ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

(፫) ተወካዩ ፡ በውክልናው ፡ የተሰጠውን ፡ የሥራ ፡ ጒዳይ ፡ ራሱ ፡ እንዳያካሂደው ፡ ድንገተኛ ፡ መሰናክል ፡ የገጠመው ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የወካዩም ፡ ሥራ ፡

መልካም ፡ አመራር ፡ ጉዳይ ፡ የሚያስገድደው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ንም ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ ለወካዩ ፡ ለማስታወቅና ፡ ለማስፈቀድ ፡ ጊዜ ፡ የሚያጥ ረው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ተክቶ ፡ ሥራውን ፡ ማሠራት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፲፮ ። (፪) የተወካዩ ፡ አላፊነት ።**

(፩) ተወካዩ ፡ በማይገባ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ተክቶ ፡ ያሠራው ፡ ሰው ፡ በሚያደር ገው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፤ እሱ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ያህል ፡ ተቈጥሮ ፡ በአላፊ ነት ፡ ይጠየቃል ።

(፪) በሥራው ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲተካና ፡ እንዲያሠራ ፡ በሚገባ ፡ ተፈቅዶ ለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፤ በአላፊነት ፡ የሚጠየቀው ፡ ተተኪውን ፡ በመምረጥ ፡ ላይ ፡ ጥንቃቄ ፡ ባላደረገበት ፡ ጉዳይና ፡ ለተተኪውም ፡ የሰጠው ፡ የሥራ ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ጕድለት ፡ በሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፲፯ ። (፫) በወካዩና ፡ በተተኪው ፡ ተወካይ ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ግንኙነቶች ።**

(፩) በወካዩና ፡ በተተኪው ፡ ተወካይ ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚወሰ ኑት ፡ ተተኪው ፡ ወኪል ፡ ዋናው ፡ ወኪል ፡ በሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ለመተካት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያህል ፡ በሚገባ ፡ ያመነ ፡ ሲሆን ፡ ተተኪው ፡ ወኪል ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ያገኘው ፡ በቀጥታ ፡ ከወካዩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያህል ፡ በመቍጠር ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ጕዳዩ ፡ የሚወሰነው ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፲፰ ። ስለ ፡ ብዙ ፡ ወኪሎች ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተወክለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ መቀበላቸው ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ውክልናው ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ አይቈጠርም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በአንድ ፡ ውል ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተወክለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሠሩዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ወካዩን ፡ ሊያስገ ድዱት ፡ የሚችሉት ፡ ተወካዮቹ ፡ ሁሉ ፡ አብረው ፡ ሠርተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ወካዩ ፡ ግዴታዎች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፲፱ ። በውል ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ስለሚከፈል ፡ የድካም ፡ ዋጋ ።**

(፩) ተወካዩ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ታስቦ ፡ የተመለከተውን ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

BACK



(፪) በውሉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ሆኖ ፡ ያገኙት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ተወካዩም ፡ ከሰጠው ፡ የአገልግሎት ፡ ፍሬ ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ የገመቱት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ በመጠኑ ፡ ሊቀንሱ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፳፰። በውል ፡ ያልተወሰነ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ።**

(፩) ስለ ፡ ድካሙ ፡ ዋጋ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ በውል ፡ ላይ ፡ ያልተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሥራውን ፡ ተግባር ፡ በውክልናው ፡ የፈጸመው ፡ በሞያ ፡ ሥራው ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተ ፡ በግል ፡ ሥራው ፡ ካልሆነና ፡ እንደ ፡ ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ማግኘት ፡ የሚገባው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወኪሉ ፡ ዋጋ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

(፪) በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ስምምነት ፡ የሌለ ፡ ሲሆንና ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ለሞያ ፡ ሥራ ፡ ሊከፈል ፡ በሚገባው ፡ በታወቀው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ማስታወቂያ ፡ ታሪፍና ፡ በልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለወኪሉ ፡ የሚከፈለውን ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ዳኞች ፡ ይወስናሉ ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፳፱።ተቀዳሚ ፡ ተከፋይና ፡ ወጪ ።**

(፩) ለተወካዩ ፡ ስለ ፡ ውክልናው ፡ ሥራ ፡ ማስኬጃና ፡ ማከናወኛ ፡ የሚሆን ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከፋይ ፡ ወጪ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተወካዩ ፡ ስለ ፡ ውክልና ፡ ሥራው ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ወካዩ ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባል ።

(፫) የዚህም ፡ የተቀዳሚ ፡ ተከፋይና ፡ የወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ወጪ ፡ ከሆነበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ አንዳችም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳያስፈልግ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፴።ግዴታና ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ተወካዩ ፡ ለወካዩ ፡ ጥቅምና ፡ ለውክልናው ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ ሲል ፡ በወኪልነቱ ፡ ከገባው ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ወካይ ፡ ነፃ ፡ ሊያወጣው ፡ ይገባል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተወካዩ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ያመጣው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የውክልና ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ አደጋ ፡ ወካዩ ፡ ኪሣራ ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፩ ። ለመቃወም ፡ የሚቻልበት ፡ ነገር ።**

(፩) ወካዩ ፡ የሥራው ፡ ጉዳይ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አላገኘም ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፤ ለወኪሉ ፡ ሊከፍለው ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ አልከፍልም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፪) ተወካዩ ፡ ሊከፍለው ፡ ከሚገባው ፡ በተለይም ፡ የውክልና ፡ ሥራውን ፡ ሲፈጽም ፡ ስላደረገው ፡ ጥፋት ፡ ከሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ ወካዩ ፡ ለተወካዩ ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማቻቻል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፩ ። የመያዣ ፡ መብት ።**

ወካዩ ፡ ሊከፍለው ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ጨርሶ ፡ እስኪከፍለው ፡ ድረስ ፡ ተወካዩ ፡ በውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ እንዲሠራበትና ፡ እንዲገለገልበት ፡ ከተረከበው ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ ሊከፈለው ፡ በሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ በእጁ ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፪ ። ስለ ፡ ብዙ ፡ ወካዮች ።**

ብዙ ፡ ወካዮች ፡ ሆነው ፡ ለአንድ ፡ ዐይነት ፡ የጋራ ፡ ጒዳይ ፡ የወከሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወካዮቹ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ውክልናው ፡ ውል ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ ጒዳይ ፡ እየአንዳንዳቸው ፡ ለተወካዩ ፡ በሙሉ ፡ አላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፭ ።
## ስለ ፡ ውክልና ፡ መቅረት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፫ ። ውክልናውን ፡ ስለ ፡ መሻር ።**

(፩) ወካዩ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ የውክልናውን ፡ ሥልጣን ፡ ለመሻርና ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖም ፡ ቢገኝ ፡ ተወካዩ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣኑን ፡ የተቀበለበትን ፡ የውል ፡ ጽሑፍ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ እንዲመልስለት ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህንንም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፬ ። የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ መሻር ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

(፩) በውክልናው ፡ የተሰጠው ፡ የሥልጣን ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ወካዩ ፡ ወኪሉን ፡ ከሥልጣኑ ፡ ሽሮት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የሽረቱ ፡ ጒዳይ ፡ በተወካዩ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወካዩ ፡ ተወካዩን ፡ ከሥልጣኑ ፡ በሻረው ፡ ጊዜ ፡ በሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) የውሉ ፡ መጽኛ ፡ ዘመን ፡ የተወሰነው ፡ ለራሱ ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ወይም ፡ ተወካዩን ፡ ለመሻር ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ካለው ፡ ወካዩ ፡ ማናቸውም ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፭ ። ስለ ፡ ብዙ ፡ ወካዮች ።**

(፩) ብዙ ፡ ወካዮች ፡ ሁነው ፡ ለጋራ ፡ ጒዳያቸው ፡ የወከሉትን ፡ ተወካይ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ሊሽረው ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ ፡ ተወካዩ ፡ መሻር ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ወካዮቹ ፡ በመላው ፡ ሳይስማሙበት ፡ አንዱ ፡ ወካይ ፡ ብቻውን ፡ ተወካዩን ፡ ሊሽረው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፱ ። ወኪሉ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣኑን ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) ተወካዩ ፡ የውክልናውን ፡ ሥራ ፡ የሚተው ፡ መሆኑን ፡ ለወካዩ ፡ አስታውቆ፡ ውክልናውን ፡ ለመተው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የተወካዩ ፡ ሥራ ፡ መተው ፡ በወካዩ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ ከሆነ፤ ተወካዩ ፡ በወካዩ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ሆኖም ፡ ተወካዩ ፡ የውክልናውን ፡ ሥራ ፡ መቀጠሉ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀና ፡ ሥራውንም ፡ ለመቀጠል ፡ በፍጹም ፡ የማያስችለው ፡ ምክንያት ፡ መኖሩ ፡ ከተረጋገጠለት ፡ ማንኛውንም ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴ ። የተወካዩ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ያለ ፡ መቻል ።

(፩) ተወካዩ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በስፍራው ፡ ያለመኖሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ደርሶበት ፡ በንግድ ፡ ኪሣራ ፡ ላይ ፡ መውደቁ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለዚሀ ፡ ጒዳይ ፡ ታስቦ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ውል ፡ ተመልክቶ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ ወዲያውኑ ፡ ይቀራል ።

(፪) የተወካዩ ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ መኖሩን ፡ ካወቁ ፤ በተወካዩ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰበት ፡ ወዲያውኑ ፡ ለወካዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

(፫) እንዲሁም ፡ ዋናው ፡ ተወካይ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ከደረሰበት ፡ በኋላ ፡ ወካዩ ፡ ነገሩን ፡ ዐውቆ ፡ አስፈላጊውን ፡ ድርጅት ፡ እስኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ ለወካዩ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፩ ። ስለ ፡ ብዙ ፡ ተወካዮች ።

(፩) ብዙዎች ፡ ተወካዮች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ጒዳይ ፡ ለማከናወን ፡ ተወክለው ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ከመካከላቸው ፡ አንደኛው ፡ በአንድ ፡ ምክንያት ፡ ሥራውን ፡ ለመቀጠል ፡ የማያስችለው ፡ ነገር ፡ ገጥሞት ፡ የውክልናውን ፡ ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡ የተገደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጒዳይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ በውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቶ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ የአንዱ ፡ ሥራ ፡ ማቆም ፡ የሁሉንም ፡ ተወካዮች ፡ ሥራ ፡ ለማቆም ፡ ይችላል ።

(፪) ሌሎቹ ፡ ተወካዮች ፡ የውክልና ፡ ሥልጣናቸው ፡ የቆመበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዳወቁ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለወካዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ። ወካዩም ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ እስኪያዘጋጅ ፡ ድረስ ፡ የሥራው ፡ ሁኔታና ፡ የጊዜው ፡ አጋጣሚ ፡ የሚያስገድደውን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጒዳይ ፡ እያከናወኑ ፡ መቈየት ፡ ይገባቸዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፪ ። የወካዩ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ያለ ፡ መቻል ።

(፩) ወካዩ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በስፍራው ፡ አለመኖሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ የመውደቅ ፡

ኪሣራ ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለጉዳዩ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ውል ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ ወዲያውኑ ፡ ይቀራል ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ተወካዩ ፡ ሥራውን ፡ ቢያቋርጥ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የሚደርስበት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በውክልናው ፡ ሥልጣንም ፡ መሠረት ፡ ሥራውን ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዋናው ፡ ወካይ ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴዎች ፡ አስፈላጊውን ፡ ጉዳይ ፡ እስኪያደርጉና ፡ ራሳቸውም ፡ ሊያስቡበት ፡ እስኪችሉ ፡ ድረስ ፡ ሥራውን ፡ መቀጠል ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፫ ። ወደ ፡ እንደራሴነት ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መምራት ።**

በወካዩ ፡ በተወካዩና ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በሆኑ ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደገረው ፡ የግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ በተደነገገው ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይከናወናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ኮሚሲዮን ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ግዥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ኮሚሲዮን ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፬ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የግዥ ፡ ወይም ፡ የሽያጭ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሲባል ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፤ ተወካይ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሰጭ ፡ ተብሎ ፡ ለሚጠራው ፡ ወካይ ፡ ተወካዩ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለወካዩ ፡ ጥቅም ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ወረቀቶችን ፤ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሌላ ፡ ነገሮች ፤ ለመግዛት ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውክልና ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከተው ፡ ግልጽ ፡ ድንጋጌና ፡ የማሻሻል ፡ ደንብ ፡ በመሠረቱ ፡ ልዩነት ፡ ከሚኖረው ፡ በቀር ፡ የውክልና ፡ ደንብ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ ይጸናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፭ ። የአጠባበቅ ፡ ጥንቃቄዎች ።**

(፩) ኮሚሲዮኔሩ ፤ በኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ስም ፡ የተላኩለትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ መፈጸምና ፡ ዕቃዎችም ፡ የተበላሹ ፡ መስለው ፡ የታዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በመዘግየት ፡ ደርሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕቃ ፡ ጫኚው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ባለንብረት ፡ ሆኖ ፡ የኮሚሲዮን ፡ ሰጪውን ፡ መብት ፡ ይዞ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

(፪) ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ጉዳይ ፡ ዕቃዎቹ ፡ እንዳልደረሱ ፡ ያህል ፡ በሚያስቈጥር ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፤ ኰሚሲዮኔሩ ፡ ለኰሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ወዲያውኑ ፡ አሳቡን ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ።

(፫) አንድ ፡ ሰው ፡ የኰሚሲዮኑን ፡ አደራ ፡ ያልተቀበለም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የኰሚሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ ጉዳይ ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ የሞያና ፡ የግል ፡ ሥራውን ፡ የሚመለከት ፡ ከሆነ ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ግዴታዎችን ፡ መፈጸም ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፮ ። የንግድ፡ዕቃዎች፡መሸጥ ።

በኰሚሲዮን ፡ የተላኩትን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በቶሎ ፡ ይበላሻሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ ነገር ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኰሚሲዮኔሩ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በሚገኙበት ፡ አገር ፡ ባሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ እንዲሸጣቸው ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ፤ እንዲያውም ፡ የኰሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገድደው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ይህንኑ ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፯ ። አስቀድሞ ፡ ዋጋ፡ስለ፡መክፈል ።

ሻጭ ፡ ዕቃውን ፡ ከማስረከቡ ፡ በፊት ፡ ኰሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ኰሚሲዮኔሩ ፡ ላልተረከበው ፡ ዕቃ ፡ አስቀድሞ ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሚመጣው ፡ ኪሣራና ፡ ጥፋት ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ራሱ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፰ ። በዱቤ፡የመሸጥ፡ጉዳይ ።

(፩) የሽያጩ ፡ ጉዳይ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ስፍራ ፡ ያለው ፡ የንግድ ፡ ልማድ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ኰሚሲዮን ፡ ሰጪውም ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠው ፡ በቀር ፡ ኰሚሲዮኔሩ ፡ ለዕቃ ፡ ገዢው ፡ ዕቃውን ፡ በዱቤ ፡ ሸጦ ፡ የዋጋውን ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ሊወስንለት ፡ ይችላል ።

(፪) ለዕቃ ፡ ገዢው ፡ የመክፈያ ፡ ቀን ፡ የፈቀደለት ፡ ኰሚሲዮኔር ፡ ገዢው ፡ ማን ፡ መሆኑንና ፡ ለዋጋ ፡ መክፈያ ፡ የፈቀደለት ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኰሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) ኰሚሲዮኔሩ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ለኰሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዕቃው ፡ ዋጋ ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ ከመቈጠሩም ፡ ይልቅ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፴፱ ። ያለ ፡ ፈቃድ፡የተደረገ፡ዱቤ ።

(፩) ኰሚሲዮኔሩ ፡ ኰሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወምና፡የአገሩንም ፡ ልማድ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የንግድ ፡ ዕቃውን ፡ በዱቤ ፡ ሸጦ ፡ ለዋጋው ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለንብረቱ ፡ የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲከፍለው ፡ ኰሚሲዮኔሩን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ኰሚሲዮኔሩ ፡ ለዕቃው ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ ያገኘውን ፡ ትርፍ ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶ ። ኮሚሲዮኔሩ፡መስጠት ፡ ስለሚገባው ፡ዋቢነት ።**

(፩) ኮሚሲዮኔሩ ፤ በኮሚሲዮን ፡ ሥራው ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ራሱ ፡ በሚያምነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንዲሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ ለተዋዋለው ፡ ግዴታ ፡ መልካም ፡ አፈጻጸምና ፡ ስለ ፡ ዕቃውም ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ለኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ወረቀቶችን ፡ የመግዛትና፡ የመሸጥ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ኮሚሲዮኔር፤ ተቃራኒ፡የሆነ፡ስምምነት፡ከሌለ ፡ በቀር ፤ በራሱ ፡ እምነት ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ነው ።

(፫) የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ለመግዛት ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ኮሚሲዮኔር ፤ የኮሚሲዮኑ ፡ውል፡በተደረገበት ፡ አገር ፡ ያለው፡የንግድ፡ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ለተዋዋላቸው ፡ ሰዎች ፡ አላፊ ፡ ዋስ ፡ ሆኗቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በራሱ ፡ እምነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራ ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፩ ። በራሱ፡እምነት ፡ ስለሚሠራ ፡ ኮሚሲዮኔር ።**

(፩) በራሱ ፡ እምነት ፡ የሚሠራ ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ በኮሚሲዮኑ ፡ ጉዳይ ፡ ለሚዋዋለው ፡ ሰው ፡ ሙሉ ፡ አላፊ ፡ የሆነ ፡ ዋስ ፡ ነው ።

(፪) የውሉን ፡ ስምምነት ፡ ያለመፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ያስከተለው ፡ በኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ጕድለት ፡ በተነሣ ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ኮሚሲዮኔሩ ፡ ላደረገው ፡ ውል ፡ አፈጻጸምና ፡ ለማናቸውም ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡አላፊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፪ ። የአደጋ ፡ መጠባበቂያ ፡ ውል ፡ ( ኢንሹራንስ ) ።**

ኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠው ፡ በቀር፡ኮሚሲዮኔሩ፡የአደጋ፡መጠባበቂያ ፡ ውል ፡ ( ኢንሹራንስ ) ፡ እንዲያደርግ ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፫ ። ለኮሚሲዮኔሩ ፡ የሚከፈል ፡ የድካም ፡ዋጋ ።**

(፩) ለኮሚሲዮኔሩ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኮሚሲዮኔሩ ፡ የኮሚሲዮኑን ፡ ውል ፡ በተዋዋለበት ፡ አገር ፡ ባለው ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ እንዲከፈለው ፡ ይደረጋል ።

(፪) ልማድ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኮሚሲዮኔሩ ፡ የፈጸመውን ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመያዝና ፡ ሥራውንም ፡ ለማከናወን ፡ ያደረገውን ፡ ወጪና፡ የደረሰበትን ፡ ኪሣራና ፡ ድካም ፡ በመገመት ፡ ዳኞች ፡ በትክክለኛ ፡ ፍትሐዊ ፡ መንገድ ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ኮሚሲዮኔሩ ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ የሚሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በኮሚሲዮኑ ፡ ውል፡ መሠረት ፡ የተወሰነለትን ፤ በልማድ ፡ ወይም ፡ በትክክለኛ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፩ ። የድካሙ ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ኮሚሲዮኔሩ ፡ እንዲፈጽም ፡ ለታዘዘው ፡ ሥራ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ የሚኖረው ፡ የታዘዘውን ፡ ጉዳይ ፡ እግቡ ፡ በማድረስ ፤ በሚገባ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ በኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አፈጻጸሙ ፡ እግቡ ፡ ሊደርስ ፡ ሲችል ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሰናክሎ ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ሥራውን ፡ በሚያካሂድበት ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ልማድ ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ እንዲፈጽም ፡ የተሰጠው ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ እግቡ ፡ ደርሶ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ከሆነ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፪ ። የድካም ፡ ዋጋ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማጣት ።

(፩) ኮሚሲዮኔሩ ፡ በኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ፊት ፡ እምነቱን ፡ በማጕደል ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማንኛውንም ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ይቀርበታል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የገዛውን ፡ ዕቃ ፡ በእርግጥ ፡ ከገዛበት ፡ ዋጋ ፡ አብልጦ ፡ የገዛው ፡ ያስመሰለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሚሸጠውን ፡ ከሸጠበት ፡ ከእውነተኛው ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ አሳንሶ ፡ የሸጠ ፡ ያስመሰለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ መብት ፡ የማጣቱ ፡ ጉዳይ ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፫ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወጪና ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከፋይ ።

(፩) ኮሚሲዮኔሩ ፤ ኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ያዘዘውን ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያደረገውን ፡ ወጪና ፡ በተቀዳሚነት ፡ የከፈለውን ፡ ሒሳብ ፡ ሁሉ ፡ ከነወለዱ ፡ እንዲከፍለው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ወጪ ፡ ያደረገበት ፡ ጉዳይ ፡ ፍጻሜ ፡ ያላገኘም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወኛ ፡ የከፈለው ፡ ወጪ ፡ ሊመለስለት ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፬ ። የመያዝ ፡ መብት ።

(፩) ኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ለኮሚሲዮኔሩ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ እስኪከፍለው ፡ ድረስ ፡ ኮሚሲዮኔሩ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በመያዣ ፡ ስም ፡ የማስቀረት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህንንም ፡ መብት ፡ ለኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ሊገዛ ፡ ወይም ፡ ሊሸጥ ፡ ከመደባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ውስጥ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲሁም ፡ በኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ስም ፡ ከተቀበለው ፡ ከአንድ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ይዞ ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፰ ፡፡ የኮሚሲዮኔሩ ፡ የመግዛት ፡ መብት ፡፡**

(፩) እንዲገዛ ፡ ወይም ፡ እንዲሸጥ ፡ ትእዛዝ ፡ የተቀበለበት ፡ ዕቃ ፡ የንግድ ፡ ታሪፍ ፡ ተወስኖለት ፡ ወይም ፡ በገበያ ፡ ተወስኖ ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ኮሚሲዮኔሩ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ከራሱ ፡ ጋራ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ፡፡

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፤ በስምምነቱ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባውን ፡ መብት ፡ አይከለከልበትም ፡፡

(፫) ከራሱ ፡ ጋራ ፡ የሚስማማበት ፡ ዋጋ ፤ ኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ከወሰነው ፡ ዋጋ ፡ በንግድ ፡ ታሪፍ ፡ ወይም ፡ በዕለት ፡ የገበያ ፡ ዋጋ ፡ ከተወሰነው ፡ በታች ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፱ ፡፡ የይመስላል ፡ ግምት ፡፡**

ኮሚሲዮኔሩ ፡ ራሱ ፡ ገዥ ፡ ወይም ፡ ሻጭ ፡ ሆኖ ፡ በገዥው ፡ ወይም ፡ በሽያጩ ፡ ጕዳይ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋዋለ ፡ ለኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ሳይገልጽለት ፡ በውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ አደራ ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ለኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ያስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገዥነቱን ፡ ወይም ፡ የሻጭነቱን ፡ አላፊነት ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ወሰደ ፡ ይቈጠራል ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻ ፡፡ ስለ ፡ ኮሚሲዮን ፡ መቅረት ፡፡**

ኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፤ ወይም ፡ ኮሚሲዮኔሩ ፡ ቢሞቱ ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ቢያጡ ፤ ወይም ፡ በአገር ፡ አለመኖራቸው ፡ ቢረጋገጥም ፡ እንኳ ፤ የኮሚሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ የኮሚሲዮኔሩ ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ የነዚሁ ፡ ምትክ ፡ ሆነው ፡ የንግድ ፡ ሥራውን ፡ በማካሄድ ፡ ከቀጠሉ ፡ የኮሚሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ቀረ ፡ አይቈጠርም ፡፡

## ክፍል ፡ ፪ ፡፡

## ስለ ፡ ማመላለሻ ፡ ኮሚሲዮን ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፩ ፡፡ የማመላለሻ ፡ ኮሚሲዮን ፡፡**

(፩) የማመላለሻ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሲባል ፡ ላኪ ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ ወይም ፡ የትራንስፖርት ፡ መልክተኛ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ተወካይ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሰጪ ፡ ተብሎ ፡ ለተጠራው ፡ ወካይ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የማመላለሻ ፡ ስምምነት ፡ ከትራንስፖርት ፡ ኮሚሲዮኔሮች ፡ ጋራ ፡ የመዋዋል ፡ ውክልና ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡

(፪) የገዥው ፡ ወይም ፡ የሽያጭ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ደንቦች ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውልም ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፪ ። የአደጋ ፡ መጠባበቂያ፡ ውልና፡ኢንሹራንስ ፡ የዚሁ ፡ ለውጥ ፡ መብት ።**

(፩) ዕቃ ፡ ላኪው ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለሚል ካቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ መጠባበቂያ ፡ ኢንሹራንስ ፡ እንዲያደርግ ፡ አይገ ደድም ።

(፪) የማመላለሱን ፡(የትራንስፖርን)፡ ጕዳይ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ሊጠባበቀው ፡ ይችላል።

(፫) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ዕቃ ፡ ጫኙ ፡ የሚገባውን ፡ መብት ፡ ያገኛል ። የሚደርስበትንም ፡ ግዴታ ፡ ይፈጽማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።
## ዳኞች ፡ ስለሚሰጡት ፡ ውክልና ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፫ ። መሠረቱ ።**

አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ሥራን ፡ ወይም ፡ የተመደቡ ፡ ሥራዎችን ፡ በሌላው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ እንዲያከናውን ፡ ዳኞች ፡ ጠባቂ ፡ ባላደራ ፡ ለተባለው ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ውክ ልና ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፬ ። እንዲሾም ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።**

(፩) እንደራሴ ፡ እንዲደረግበት ፡ ለሚያስፈልገው ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ዘመዶች ፡ የሆኑ ፡ ወኪል ፡ እንዲሾሙለት ፡ ለዳኞች ፡ ጥያቄ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሌላ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፭ ። የዳኞች ፡ ውሳኔ ።**

(፩) እንደራሴ ፡ ይደረግለት ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በመራቅ ፡ ወይም ፡ በሕመም ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ወኪል ፡ ከማጣት፡ሁኔታ ፡ ውጭ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዳኞች ፡ ወኪል ፡ እንዲሾሙለት ፡ የቀረበላቸውን ፡ ጥያቄ ፡ አይቀበሉትም ።

(፪) እነርሱም ፡ የሚሾሙት ፡ ጠባቂ ፡ ባላደራ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆኑትን ፡ ጕዳዮች ፡ ብቻ ፡ እንዲያከናውን ፡ ይፈቅዱለታል ።

(፫) እንደራሴ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ መብቶች፡ በሙሉ ፡ የሚጠበቁበትንና ፡ እን ደራሴ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ፡ ባላደራ ፡ በጥበቃ ፡ ሥራው ፡ ምክንያት ፡ በአላፊነት ፡ የሚፈረድበት ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ትእዛዞች ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፮ ። ውጤቶች ።**

(፩) ዳኞች ፡ የመረጡት ፡ ጠባቂ ፡ ባለአደራ ፡ እንደራሴው ፡ እንዲሆን ፡ ለተሾ መለት ፡ ሰው ፡ የርሱ፡ወኪል ፡ ሆኖ ፡ መሾሙን ፡እንደ ፡ ተቻለ ፡ ወዲያው ፡ ያስታውቀዋል ።

(፪) ወኪልነቱን ፡ የሰጡት ፡ ዳኞች፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡እንደራሴ፡ የተደረገለት ፡ ሰውና፡ የጠባቂው ፡ ( ባለአደራው ) ፡የየራሳቸው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በሁለተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሥራ ፡ አመራር ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፯ ። የአፈጻጸሙ ፡ ሥልጣን ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ እየተገነዘበ ፡ ይህን ፡ እንዲፈጽም ፡ ሳይገደድ ፡ የወኪልነትም ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጠው ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ በመምራት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ጉዳዩን ፡ ያካሄደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ አመራር ፡ እንዳለ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፰ ። ባለቤቱ ፡ ያልፈቀደውን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መምራት ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የባለቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የሥራውን ፡ ጉዳይ ፡ መምራት ፡ ያከናወነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ፤ እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሚመጣ ፡ አላፊነትን ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነውን ፡ ድንጋጌ ፡ መፈጸም ፡ ይቻላል ።

(፪) ባለንብረቱ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ተግባር ፡ ያጸደቀለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ አይኖራቸውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፱ ። ለባለንብረቱ ፡ ጥቅም ፡ በማይሰጥ ፡ ሁኔታ ፡ የተፈጸሙ ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ አመራሮች ።**

(፩) የሥራው ፡ አመራር ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነው ፡ ለባለንብረቱ ፡ ጥቅም ፡ ሳይሆን ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሥራውን ፡ ለመምራት ፡ ወጥኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ያለአገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ።
እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሚመጣን ፡ አላፊነት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ የሚጸና ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ያካሄደው ፡ የሌላው ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ ከራሱ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ አንዱ ፡ ሥራ ፡ ካንደኛው ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ ሊካሄድ ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ከራሱ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ደርቦ ፡ መርቶት ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መጽናታቸው ፡ አይቀርም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷ ። የሥራ ፡ መሪው ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) የሌላውን ፡ ሰው ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ለመምራት ፡ የወጠነው ፡ የሥራ ፡ መሪ ፤

BACK



የወጠነውን ፡ የሥራ ፡ ጕዳይ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለባለንብረቱ ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) የጕዳዩ ፡ ባለቤት ፡ የሥራውን ፡ ጕዳይ ፡ ራሱ ፡ ለማካሄድ ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፤ ሥራ ፡ መሪው ፡ የወጠነውን ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ መቀጠል ፡ አለበት ።

(፫) የሥራውን ፡ ሁኔታ ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ ጕዳይ ፡ አንድ ፡ ተወካይ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባውን ፡ ጕዳይ ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፩ ። ትጋትና፡አላፊነት ።

(፩) ሥራ ፡ መሪው ፡ ለማከናወን ፡ የወጠነውን ፡ ሥራ ፤ እንደ ፡ መልካም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባት ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ፡እንደሚያስብና ፡ እንደሚጠነቀቅ ፡ ያህል ፡ በጥን ቃቄና ፡ በትጋት ፡ ማከናወን ፡ ይገባዋል ።

(፪) ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፤ ዳኞች ፡ ከሥራ ፡ መሪው ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ለሚደርስ ሰው ፡ ካሣና ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ጕዳይ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሲያስቡ ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ለማካሄድ ፡ ያነሣሡትን ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያቶች ፡ ገምቶ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የኪሣራውን ፡ ውሳኔ ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ማመዛዘን ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፪ ። የመሪው፡ችሎታ ፡ ማጣት ።

ሥራ ፡ መሪው ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለመምራት ፡ በውል ፡ ግዴታ ፡ ለመግባት ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በመራው ፡ ሥራ ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ በጥቅሙ ፡ በከበረበት ፡ መጠን ፡ ተመዛዛኝ ፡ ሊሆን ፡ በሚቻል ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ በሥራው ፡ ካገኘው ፡ ትርፍ ፡ ባስቀረው ፡ ጥቅም ፡ ልክ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፫ ። ቅን፡ልቡና ።

(፩) የሥራ ፡ መሪው ፤ ከባለንብረቱ ፡ ጋራ ፡ በሚያደርገው ፡ የሥራ ፡ ግንኙነት ፡ ጕዳይ ፡ ሁሉ ፡ የቅን ፡ ልቡናን ፡ ደንብ ፡ መከተል ፡ አለበት ።

(፪) እንደዚህ ፡ ላለው ፡ ነገር ፡ የውክልናን ፡ ሥልጣን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጕዳ ዮች ፡ የተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ ይጸናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፳፬ ። የባለንብረቱ፡ ግዴታዎች ።

(፩) የሥራው ፡ አመራር ፡ እንዲወጠንና ፡ በሥራ ፡ መሪው ፡ እንዲካሄድ ፡ የባለቤቱ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገድድ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራ ፡ መሪው ፡ በስሙ ፡ የወጠነውን ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፡ ባለንብረቱ ፡ ሊያጸድቅለት ፡ ይገባዋል ።

(፪) ሥራ ፡ መሪውም ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መራለት ፡ ሥራውን ፡ ለማካሄድ ፡ ያወ ጣውን ፡ ወጪ ፡ መክፈል ፡ ለድካሙም ፡ የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ መስጠትና ፡ ለሥራውም ፡ መምራት ፡ ጕዳይ ፡ ያወጣውን ፡ ወጪ ፡ መተካት ፤ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ በሥራው ፡ ጕዳይ ፡ ለደረሰበት ፡ አደጋ ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ለሥራው ፡ ማካሄጃ ፡ በሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሒሳብ ፡ ወጪ ፡ የሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ አንዳችም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ወጪ ፡ ከሆነበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ወለድ ፡ ይታሰብለታል ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፷፭።የሥራውን ፡ ማጽደቅ ፡ ጒዳይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ የጒዳዩ ፡ ባለቤት ፡ የሥራውን ፡ አመራር ፡ ተግባር ፡ ለሥራ ፡ መሪው ፡ የማያጸድቅለት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ውክልና ፡ ጒዳይ ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ ይጸናበታል ።

# አምስተኛ ፡ መጽሐፍ

## ስለ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ።

## አንቀጽ ፡ ፲፫ ።
## መብቶች ፡ ማስተላለፍን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ሽያጭ ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፷፮። ትርጓሜ ።**

ሽያጭ ፡ ማለት ፡ ሻጭ ፡ የሆነው ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ገዥ ፡ ለሆነው ፡ ሌላ ፡ ወገን ዋጋው ፡ በገንዘብ ፡ የተወሰነውን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ገዢው ፡ ሊከፍለው ፡ ግዴታ ፡ በገባበት ፡ መሠረት ፡ ሊያስረክብና ፡ ሀብትነቱን ፡ ሊያስተላልፍ ፡ የሚገደድበት ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፷፯።የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ተፈጻሚነት ። (፩) ግዙፍነት ፡ ያለው ፡ ተንቀሳቃሽ ።**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ግዙፍነት ፡ ባላቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ግዙፍነት ፡ ያላቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ስለሚመለከት ፡ የመሸጥ ፡ ውል ፤ የተወሰኑ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ፡፪ሺ፪፻፷፰። (፪) ከማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የማይለይ ፡ አካል ፡ የሆነ ፡ ክፍል ።**

(፩) ከማይንቀሳቀሱ ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ ክፍሎች ፡ መሸጥ ፡ እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ ከማይንቀሳቀሰው ፡ ነገር ፡ ተለይተው ፡ ግዙፍነት ፡ እንዳላቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ በመሆን ፡ ለገዢው ፡ መተላለፍ ፡ የሚገባቸው ፡ ሲሆን ፡ የተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ መሸጥ ፡ ይባላል ።

(፪) ይልቁንም ፡ እንደዚህ ፡ የሚሆንበት ፤ ሰብልን ፡ ወይም ፡ የሚፈርስ ፡ ሕንጻ ፡ የተሠራባቸው ፡ ነገሮችን ፡ ወይም ፡ ድንጋይን ፡ እብነ ፡ በረድን ፤ እነዚህን ፡ የመ

BACK



ሳሰሉትን ፡ ከመሬት ፡ የሚወጡትን ፡ ነገሮች ፡ የመሸጥ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፱ ። የማስረከብ ፡ ስምምነት ።

ስለዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ተፈጻሚነት ፤ የሚሠሩትን ፡ ወይም ፡ የሚወጡትን ፡ ግዙፍነት ፡ ያላቸውን ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ የሚደረገው ፡ ውል ፡ እነዚህን ፡ የተባሉትን ፡ ነገሮች ፡ ለማስረከብ ፡ ግዴታ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ለሚሠራው ፡ ወይም ፡ ለሚወጣው ፡ ነገር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ዐይነተኞች ፡ ነገሮች ፡ መስጠት ፡ ያለ በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ ይቈጠራል ።

## ክፍል ፡ ፩ ።
## የውሉ ፡ አደራረግ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸ ። የሚሸጠው ፡ ነገር ።

(፩) የሚሸጠው ፡ ነገር ፤ የሻጩ ፡ ገንዘብ ፡ ሆኖ ፡ ሀልዎት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ለመ ሆን ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የሽያጩ ፡ ጕዳይ ፡ ሻጩ ፡ ወደፊት ፡ ለገዢው ፡ የሚያስረክበውና ፡ ሠርቶ ፡ ለማውጣት ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ነገር ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፤ የሌላ ፡ ገንዘብ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸፩ ። ዋጋውን ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ እንዲገምተው ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) ዋጋውን ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ እንዲገምተው ፡ ለመተው ፡ ይቻላል ።

(፪) የተባለው ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ ዋጋውን ፡ ለመገመት ፡ ያልፈለገ ፡ ወይም ፡ ያል ቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሽያጩ ፡ ይቀራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸፪ ። የውሉ ፡ ዐይነት ።

(፩) የሽያጩ ፡ ውል ፡ ያለአንዳች ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ ያለበት ፡ መሆን ፡ ይች ላል ።

(፪) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ የገቡባቸው ፡ ግዴታዎች ፡ የውሉን ፡ መኖር ፡ የሚነኩ ፡ ምክንያቶች ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።
## ስለ ፡ ውሉ ፡ መፈጸም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፸፫ ። ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

(፩) ሻጩ ፤ በውሉና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ ማስረከብ ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

(፪) ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ ባለሀብትነት ፡ ለገዢው ፡ ለማዛወርና ፡ ለዚህም ፡ ለሸጠው ፡ አንዳንድ ፡ ጕድለቶች ፡ ዋቢ ፡ መሆን ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፤ በሽያጭ ፡ ውል ፡ የተጣሉበትን ፡ ሌሎች ፡ ግዴታዎች ፡ ለመ ፈጸም ፡ ይገደዳል ።

## (ሀ) የማስረከብ ፡ ግዴታ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፩ ። በግዴታው ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ነገር ።**

ማስረከብ ፡ ማለት ፡ በውሉና ፡ በተጨማሪው ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ ነገር ፡ ለገዢው ፡ በውሉ ፡ ልክ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፪ ። በግምት ፡ የሚወሰን ፡ ብዛት ።**

(፩) ሻጩ ፤ ብዛቱ ፡ በግልጽ ፡ የተወሰነ ፡ ነገር ፡ ለማስረከብ ፡ ግዴታ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለገዢው ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ብቻ ፡ የተደረገ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጹ ፡ ምክ ንያቶች ፡ ካልተገኙበት ፡ በቀር ፡ የሚሰጠውን ፡ ነገር ፡ የብዛት ፡ ልክ ፡ መወ ሰን ፡ የሻጩ ፡ ነው ።

(፪) በተደረገው ፡ ውል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ይሁን ፡ በተባለው ፡ የግምት ፡ ብዛትና ፡ በውነተኛው ፡ ባስረከበው ፡ ብዛት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ የተገዛው ፡ ነገር ፡ የአንድ ፡ መርከብ ፡ ሙሉ ፡ ጭነት ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሲሆን ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከመቶ ፡ አምስት ፡ በላይ ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፫ ። የማስረከቢያው ፡ ጊዜ ።**

የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ የማስረከቢያው ፡ ጊዜ ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ቃል ፡ ያልተገለጸ ፡ ሲሆን ፤ ገዢው ፡ አስረክበኝ ፡ ብሎ ፡ ሲጠይቅ ፤ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ ወዲያውኑ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፬ ። በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚደረግ ፡ ማስረከብ ።**

የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ማስረከብ ፡ የሚፈጸምበት ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይሁን ፡ በመባባል ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ የተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዥው ፡ የሚረከብበትን ፡ ቀን ፡ የሚወስንበት ፡ ምክንያት ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፤ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ የማስረከቢያውን ፡ ቀን ፡ መወሰን ፡ የሻጩ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፭ ። የማስረከቢያውና ፡ የዋጋው ፡ መክፈል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መሆን ።**

(፩) በውሉ ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የተሸጠውን ፡ ማስረከብ ፡ ከዋጋው ፡ መክፈል ፡ ጋራ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ ፡ ዋጋው ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ለመቆየት ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፮ ። የማስረከቢያው ፡ ቦታ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

የተሸጠው ፡ ነገር ፡ መረከቢያ ፡ ቦታ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ያልተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ ማስረከብ ፡ ያለበት ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት

ጊዜ ፡ በነበረው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባይኖረው ፡ ዘወትር፡ በሚቀመጥበት ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹።(፪)ልዩነት ።

(፩) የተሸጠው ፡ አንድ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ሲሆንና ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች፡ ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ ያወቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ ማስረከብ ፡ ያለበት ፡ በዚሁ ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የተሸጡት ፡ ነገሮች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሆነው ፡ ከአንድ፡የንግድ፡ ዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ውስጥ ፡ የሚወሰዱ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጠቅላላ ፡ ነገር ፡ ሲሆኑ ፤ ወይም ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋ ዮች ፡ በታወቀ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሚሠሩ ፡ ወይም ፡ የሚወጡ ፡ ሲሆኑም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ይሆናል ።

## (ለ) ባለሀብትነቱን ፡ ለገዢው ፡ የማስተላለፍ ፡ ግዴታ ።

ቍ ፡፪ሺ፪፻፹፩።ባለሀብትነቱን፡ለገዢው፡ለማስተላለፍ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ግዴታዎች ።

ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ የማያስነካ ፡ መብት ፡ ለገዢው ፡ ለማስተላለፍ ፡ አስ ፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፪ ። የኔ፡ነው ፡ ባይ ፡ ሲመጣ ፡ መድን ፡ ስለ፡መሆን ።(፩)መሠረቱ ።

በተሸጠው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በውሉ ፡ ጊዜ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በነበረው ፡ መብት ፡ ምክ ንያት ፡ ሻጩ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ይለቀቅልኝ ፡ የሚ ለውን ፡ መጪ ፡ ለመመለስ ፡ ለገዢው ፡ መድን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፫ ። (፪) ስለ፡መድኑ ፡ የተሰጠ፡ሕጋዊ ፡ ወሰን ።

(፩) ገዢው ፡ በገዛው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ይለቀቅልኝ ፡ ባይ ፡ መኖሩን ፡ በውሉ ፡ ጊዜ ፡ ዐውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ መጪውን ፡ ለመመለስ ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ ካል ተገኘ ፡ በቀር ፡ መድንነት ፡ የለበትም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ይለቀቅልኝ ፡ ባይነቱ ፡ ሻጩ፡ በሰጠው ፡ የዋስትና ፡ መያዣ፡ምክንያት ፡ የተፈጠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለሸጠው ፡ ነገር ፡ መድንነቱ ፡ የርሱ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፬።መድን፡ላለመሆን፡የሚደረግ፡ውለታ ።

(፩) ይለቀቅልኝ ፡ ባይ ፡ (መጪን ) ፡ ለመመለስ ፡ የሻጩን ፡ መድንነት ፡ የሚያስ ቀሩ ፡ ወይም ፡ የሚቀንሱ ፡ ውለታዎች ፡ በጠባቡ ፡ መተርጐም ፡ አለባቸው ።

(፪) የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ለይለቀቅልኝ ፡ ባይ ፡ በሚለቀቅበት ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ የገባ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እነዚህ ፡ ውለታ

ዎች ፡ በሺያጩ ፡ ላይ ፡ የተቀበለውን ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለገ ዢው ፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡ እንዲኖር ፡ ያደርጋሉ ።

(፫) ሻጩ ፤ በሸጠው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ያለውን ፡ የይለቀቅልኝ ፡ ባይ ነት ፡ መብት ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሰውሮት ፡ ቢገኝ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ይለቀቅልኝ ፡ ባይነት ፡ ሻጩ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሲሆን ፤ አላፊነትን፡ የሚያስቀር ፡ ወይም ፡ የሚቀንስ ፡ ማንኛቸውም ፡ ውለታ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፩ሺ፪፻፹፭ ። ሻጩን፡በዋቢነት፡ስለ፡ማሳለፍ ።

(፩) የኔ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ የተነሣበት ፡ ገዥ ፡ በርሱ ፡ ላይ፡ ለተነሣው ፡ ሙግት ፡ ሻጩን ፡ በዋቢነት ፡ ማሳለፍ ፡ አለበት ።

(፪) ሻጩ ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ለነገሩ ፡ እንዲያልፍ ፡ ሲጠየቅ ፤ ይለቀቅልኝ ፡ ባይ ፡ የመጣው ፡ በገዢው ፡ በሚመካኝ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፤ ዋቢ ፡ የመሆን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፫) ሻጩ ፡ ለነገሩ ፡ እንዲያልፍ ፡ ያልተጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአስፈላጊው ፡ ጊዜ፡ ለነገሩ ፡ ቢያልፍ ፡ ኖሮ ፡ ሙግቱ ፡ ለርሱ ፡ ይቀናው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በሚያስ ረዳበት ፡ መጠን ፡ ለነገሩ ፡ ያለ ፡ ማለፉ ፡ ምክንያት ፡ ሳይነካው ፡ ከአላፊነት ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፩ሺ፪፻፹፮።ግልግል።

ግዥው ፡ በዳኛ ፡ ፊት ፡ ከሚደረገው ፡ ክርክር ፡ ውጭ ፡ ለሌላ ው፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ መብቱን ፡ ዐውቆለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ከተባለው ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ወዶ ፡ ተገላግሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ የኔ ፡ ነውና ፡ ይለቀቅልኝ ፡ ባይ ፡ መጪን ፡ ለመመ ለስ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ ሻጩ፡ እንዲያልፍለት ፡ መድ ንነቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(ሐ) በተሸጠው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለሚገኝ ፡ ጒድለት ፡ ዋቢ ፡ መሆን ።

ቍ፡፩ሺ፪፻፹፯።መሠረቱ።

ሻጩ ፡ ያስረከበው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ለመሆኑና ፡ ጒድለትም ፡ የሌ ለበት ፡ ለመሆኑ ፡ ለገዢው ፡ መድን ፡ (አላፊ ) ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፩ሺ፪፻፹፰ ። እንደ ፡ ውሉ፡ትክክል፡ስለ፡መሆኑ ።

ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ፡ የሚባለው ፡—

(ሀ) ሻጩ ፡ ከተሸጠው ፡ ነገር ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሻጩ ፡ ሊሰጥ ፡ በውል ፡ ቃል ፡ ከገባበት ፡ ልክ ፡ አብልጦ ፡ ወይም ፡ *አሳንሶ የሰጠ እንደሆነ፤*

*(ለ) በውሉ የተመለከተው ሳይሆን ሌላ ነገር ወይም ዐይነቱ ሌላ የሆነውን ነገር የሰጠ እንደሆነ ነው።*

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፱ ። ዋቢ ፡ ያላቸው ፡ ጕድለቶች ።**

ዋቢ ፡ ሊሰጥበት ፡ የሚገባው ፡—

(ሀ) የሸጠው ፡ ነገር ፡ ለደንበኛው ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ረገድ ፡ ለመ ጠቀሚያ ፡ ጥሩነት ፡ የሌላቸው ፡ ሲሆን ፤

(ለ) የሸጠው ፡ ነገር ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በውስጣዊ ፡ አሳብ ፡ ለተነገረው ፡ ልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሆኑ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆኑት ፡ ጥሩነት ፡ የሌሉት ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ዕቃዎቹ ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ወይም፡ በዝምታ ፡ የተመለከ ተው ፡ ዐይነታቸው ፡ ወይም ፡ ልዩነታቸው ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺ ። የማመዛዘን ፡ ግምት ፡ ስለሚደረግበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ መሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ ጕድለቶች ፡ የሌሉበት ፡ መሆኑ ፡ የሚወሰነው ፤ የአደጋ ፡ አላፊነት ፡ በሚዛወርበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ በነ በረው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ወይም ፡ ለጐደለው ፡ ነገር ፡ ምትክ ፡ ይሰጥ ፡ ብሎ ፡ መግለጫ ፡ በመስጠት ፡ ምክንያት ፡ የአደጋ ፡ ኪሣራ ፡ አላፊነት ፡ አልተዛወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ኑሮ ፡ ቢሆን ፡ የአደጋ ፡ ኪሣራ ፡ ይዛ ወር ፡ ነበር ፡ የሚባልበትን ፡ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፫) በዕቃው ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ የዕቃው ፡ ትክክል ፡ ያለመሆን ፡ የደረሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነው ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ የደረሰበት ፡ በሻጩ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ አላፊ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ አድራጎት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ሳይሆን ፡ ለመቅረቱ ፡ ወይም ፡ ጕድ ለት ፡ ያለበት ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘቱ ፡ ሻጩ ፡ መድን ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፩ ። ገዢው ፡ የሚያደርገው ፡ ምርመራ ።**

(፩) ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ለመመርመር ፡ እንደ፡ተቻለው ፡ ወዲያው ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነገሩን ፡ መመርመር ፡ አለበት ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የዚህ ፡ ምርመራ ፡ አሠ ራር ፡ ፎርም ፡ ምርመራው ፡ በሚፈጸምበት ፡ ስፍራ ፡ ባሉት ፡ ልማዶች ፡ መሠ ረት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) ገዢው ፡ በምርመራው ፡ ውጤት ፡ እጠቀማለሁ ፡ የሚል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃ ውን ፡ የጥፋት ፡ አደጋ ፡ የሚያገኘው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ሻጩን ፡ ወይም ፡ ወኪሉን ፡ በምርመራው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መጥራት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፪ ። ገዢው ፡ የሚያደርገው ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) የተደረገው ፡ ምርመራ ፡ ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ አለመሆኑን ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ የገለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ይህንኑ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለሻጩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

BACK



(፪) ጒድለቱን ፡ ሲያስታውቅ ፡ ገዢው ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ አሠራርና ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የጒድለቱን ፡ ዐይነት ፡ መለየት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፫ ። አለማስታወቅ ።**

(፩) ገዢው ፡ የነገሩን ፡ ጒድለት ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ ጒድለት ፡ መኖሩን ፡ ካላመነ ፡ በቀር ፤ ገዢው ፡ ዕቃው ፡ ከውሉ ፡ ስምምነት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ አይደለም ፡ ወይም ፡—

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ እንደ ፡ አሠራሩ ፡ ልማድ ፡ በተደረገው ፡ ምርመራ ፡ ሊገለጽ ፡ ያልቻለው ፡ ጒድለት ፡ በኋላ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተባለው ፡ ጒድለት ፡ እንደ ፡ ተገለጸ ፡ ገዢው ፡ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ የተገለጸውን ፡ ጒድለት ፡ ለሻጩ ፡ ካስታወቀ ፡ ስለ ፡ ጒድለቱ ፡ ሻጩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) አስቦ ፡ ገዢውን ፡ እንዲታለል ፡ ያግባባ ፡ ሻጭ ፡ ጒድለቱ ፡ እንደሚገባ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ አልተለየልኝም ፡ ወይም ፡ በአስፈላጊ ፡ ጊዜ ፡ አላስታወቅኸኝም ፡ በማለት ፡ ከአላፊነት ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፬ ። የስምምነት ፡ አላፊነት ።**

ሻጩ ፡ የገባበት ፡ አላፊነት ፤ ለነገሩ ፡ አንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ለነገሩ ፡ መልካም ፡ አገልግሎት ፤ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ በመወሰን ፡ ዋቢ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ የነገሩን ፡ ጒድለት ፡ በዚያው ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለሻጩ ፡ ማስታወቅ ፡ በቂው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፭ ። የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ጒድለቶች ፡ ገዢው ፡ ስለ ፡ ማወቁ ።**

(፩) ሻጩ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ጒድለቶች ፡ ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ ዐውቆዋቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዋቢነት ፡ አይያዝም ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ ፡ የገባበት ፡ አላፊነት ፡ ግልጽ ፡ ቢሆንም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፮ ። የገዢው ፡ ከባድ ፡ ቸልተኛነት ።**

(፩) የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ጒድለቶች ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ የሚታዩ ፡ እንደ ፡ ሆኑና ፡ ገዢው ፡ ያላወቃቸውም ፡ ከራሱ ፡ ከባድ ፡ ቸልተኛነት ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ ሲሆን ፡ ሻጩ ፡ ለነዚሁ ፡ ጒድለቶች ፡ ዋቢ ፡ አይሆንም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፤ ሻጩ ፡ ለተሸጠው ፡ ነገር ፡ ጒድለት ፡ የለበትም ፡ ሲል ፡ በግልጽ ፡ አስታውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለዕቃው ፡ አንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ዋቢ ፡ በመሆን ፡ ተዋውሎ ፡ ሲገኝ ፡ አላፊነት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፯ ። ከዋቢነት ፡ የሚያድን ፡ የውል ፡ ቃል ።**

የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ጒድለቶች ፡ ገዢው ፡ እንዳያውቃቸው ፡ ሻጩ ፡ በተንኰል ፡ ደብቋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አላፊነትን ፡ የሚሰርዙ ፡ ወይም ፡ የሚቀንሱ ፡ ውለታዎች ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፰ ። የዋቢነት፡ክስ፡የሚቀርብበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) ክስ ፡ ማቅረቡን ፡ የከለከለው ፡ የሻጩ ፡ አጭበርባሪነት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ አለመሆኑን ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ካስታወቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ክስ ፡ ያላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የመክሰስ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

(፪) ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ይህን ፡ የተባለውን ፡ ጊዜ ፡ ለማሳጠር ፡ አይችሉም ።

(፫) ስለ ፡ ተባለው ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ መልካም ፡ አገልግሎት ፡ ሻጩ፡ የሰጠው ፡ ዋቢነት ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ መነሻ ፡ የሚያደርገው ፡ ይቱባለው ፡ ጊዜ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፱ ። የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ፡የገዢው፡ሁኔታ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ከውሉ ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ ያለመሆኑን ፡ ወይም ፡ ጉድለቱን ፡ ለማንሣት ፡ አይችልም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ዋጋውን ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የነገሩን ፡ ከውሉ ፡ ጋራ ፡ ያለ መስማማት ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አስታውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ስለ ፡ አከፋፈል ፡ ለሚደረግለት ፡ ጥያቄ ፡ የዋጋውን ፡ መቀነስ ፡ ወይም ፡ በተገኘው ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈልን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻ ። ጉድለትን ፡ ለማደስ ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ሺያጩ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ባላቸው ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፤ በውሉ ፡ የተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ ጉድለት ፡ በተገኘባቸው ፡ ነገሮች ፡ ፋንታ ፤ አዲስ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ለማስረከብ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ሺያጩ ፡ በገዢው ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሻጩ ፡ በሚሠራቸው ፡ ወይም ፡ በሚያወጣቸው ፡ ነገሮች ፡ ሲሆን ፤ የነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የመረከባቸው ፡ መዘግየት ፡ ለገዢው ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ የሚያመጣበት ፡ አይሁን ፡ እንጂ ፤ ነገሮቹን ፡ ለማስረከብ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፤ በነገሮቹ ፡ የተገኙ ትን ፡ ጉድለቶች ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለማደስ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

(፫) ስለ ፡ ጉዳት ፡ የተወሰነው ፡ ኪሣራ ፡ መቀበል ፡ መብት ፡ ለገዢው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

## (መ) የሻጩ ፡ ሌሎች ፡ ግዴታዎች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፩ ። አስረጅ ፡ ጽሑፎችን ፡ስለ፡ማስተላለፍ ።**

(፩) ሻጭ ፤ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ የሚመለከቱ ፡ አስረጅ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለገዢው ፡ እንዲያስተላልፍ ፡ ልማድ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጭ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ ከማ

BACK



ስረከብ ፡ ሌላ ፡ የተባሉትን ፡ አስረጅ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለገዢው ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ይኸውም ፡ አስረጅ ፡ ጽሑፎቹ ፡ የመስጠት ፡ ሥራ ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ወይም ፡ ለልማድ ፡ ትክክል ፡ በሆነው ፡ ስፍራ ፡ በሙሉ ፡ ትጋትና ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፫) አስረጅ ፡ ጽሑፎቹ ፡ ከውሉ ፡ ጋራ ፡ የተስማሙ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ ሊቀበላቸው ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፪ ። ኢንሹራንስ ።

አካባቢ፡ ሁኔታዎችን፡ በመመልከት፡ የማመላለስ ፡ኢንሹራንስ ፡ ማድረግ ፡ ልማድ፡ እንደ ፡ ሆነና፡ ሻጩም፡ ራሱ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለማድረግና ፡ ለመፈረም ፡ ግዴታ ፡ የሌለበት ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም፡ ኢንሹራንስ፡ እንዲያደርግ ፡ ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ አላስታወቀው፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም፡ እንደዚሁ ፡ ያለውን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለመዋዋል ፡ ገዢው ፡ የጠየቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጭ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ መግለጫዎች ፡ ሁሉ ፡ ለገዢው ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## የገዢው ፡ ግዴታዎች ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፫ ። ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ።

(፩) ገዢው ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈልና ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ለመረከብ ፡ ይገደዳል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ በሽያጩ ፡ ውል ፡ የገባባቸውን ፡ ሌሎች ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፬ ። ዋጋውን ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ።

(፩) ዋጋን ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ ዋጋውን ፡ ለመክፈል ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ፡ ወይም፡ በአላፊነት ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ባለው ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ የመፈጸምን ፡ ግዴታ ፡ ይጠቀልላል ።

(፪) ገዢው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሐዋላ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያሰጥ ፡ ሰነድ ፡ (ክሬዲ ፡ ደኩማንቴር) ፡ እንዲከፍት ፡ ወይም ፡ የባንክ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዋስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሊገደድ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፭ ። በክብደት ፡ የተወሰነ ፡ ዋጋ ።

ዋጋው ፡ የተወሰነው ፡ በዕቃው ፡ ክብደት ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥርጣሬ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ መገመት ፡ ያለበት ፡ የዕቃው ፡ የራሱ ፡ ብቻ ፡ ጥሩ ፡ ክብደቱ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፮ ። የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ዕቃ ።**

የተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ በገበያ ፡ የተወሰነ ፡ ወይም ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፤ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ስለ ፡ ተሸጠው ፡ ነገር ፡ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ በሚያስረ ክብበት ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ በሚገበይበት ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ተዋዋሉ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፯ ። ሻጭ ፡ ዘወትር ፡ የሚሸጣቸው ፡ ነገሮች ።**

(፩) ሽያጩ ፡ ዘወትር ፡ ሻጩ ፡ በሚሸጠው ፡ ነገሬ ፡ ሲሆን ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ ተዋ ዋዮች ፡ ሽያጩ ፡ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ በሚያስረክብበት ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ ዘወ ትር ፡ በሚሸጥበት ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ተዋዋሉ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ሻጩ ፡ ባቀረበው ፡ ፋክቱር ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ዋጋ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጻ ፈው ፡ ዋጋ ፡ ጋራ ፡ ትክክለኛ ፡ ዋጋ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፰ ። የዕቃው ፡ ብዛት ፡ በውሉ ፡ ከተመለከተው ፡ ብዛት፡በላይ ፡ ስለ ፡ መሆኑ።**

(፩) ሻጩ ፡ በውሉ ፡ ከተመለከተው ፡ ብዛት ፡ በላይ ፡ ዕቃ ፡ ለገዢው ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ በውሉ ፡ ከተመለከተው ፡ ብዛት ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ላለመቀበል ፡ ወይም ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፪) ገዢው ፡ የቀረበለትን ፡ በሙሉ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተጨመረው ፡ ዕቃ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፱ ። ዋጋው ፡ የሚከፈልበት ፡ ቦታ።**

(፩) ገዢው ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ ያለበት፡ በሻጩ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፫) ውሉ ፡ የዋጋው ፡ መከፈል ፡ የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ሰነዶቹ ፡ በገዢው ፡ እጅ ፡ ሲገቡ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ዋጋው ፡ እነዚህ ፡ በሚሰጡበት ፡ ቦታ ፡ ዋጋው ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲ ። ዋጋው ፡ የሚከፈልበት፡ጊዜ ። ፩ ፡ የጅ ፡ በጅ ፡ ሽያጭ ።**

የዋጋው ፡ መከፈል ፡ ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ በሚረከብበት ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ሳይመረምር ፡ ዋጋውን ፡ ለመክፈል ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፩ ። (፪) የዱቤ፡ሽያጭ ።**

በዱቤ ፡ በተደረገው ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋው ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ ያልተወ ሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ከተረከበ ፡ በኋላ ፡ ሻጩ ፡ እንደ ፡ ጠየ ቀው ፡ ወዲያውኑ ፡ ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፪ ። ከማስረከብ ፡ ጋራ ፡ የሚደረጉ ፡ ተግባሮች።**

ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ የማስረከብ ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲችል ፡

BACK



አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ገዢው ፡ በበኩሉ ፡ የሚደረጉትን ፡ አስፈላጊ ፡ ተግባሮች ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፫ ። ዕቃውን ፡ መረከብ ።

ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ከተረከበ ፡ በኋላ ፡ ዕቃውን ፡ እጁ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ተግባሮች ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

በሻጩና ፡ በገዢው ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ።

(ሀ) ወጪ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፬ ። የውሉ ፡ ወጪ ።

ለሽያጩ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ውል ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ገዢው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፭ ። ስለ ፡ መክፈል ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ።

(፩) ለገዛው ፡ ነገር ፡ ዋጋውን ፡ ስለ ፡ መክፈል ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ የሚችለው ፡ ገዢው ፡ ነው ።

(፪) ውሉ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ሻጩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ወይም ፡ መኖሪያውን ፡ በመለወጡ ፡ ምክንያት ፡ ወጪው ፡ በዝቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ ተጨማሪ ፡ የሆነውን ፡ ወጪ ፡ መቻል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፮ ። ስለ ፡ ማስረከብ ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ።

(፩) የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ሻጩ ፡ ነው ።

(፪) ይኸውም ፡ ወጪ ፡ በተለይ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ለመቍጠር ፡ ለመለካትና ፡ ለመመዘን ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ ያጠቃልላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፯ ። ከመረከብ ፡ በኋላ ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ።

የገዛውን ፡ ነገር ፡ ከተረከበ ፡ በኋላ ፡ የሚወጣውን ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ገዢው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፰ ። የማመላለስ ፡ (የትራንስፖርት) ፡ ወጪ ።

(፩) የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ መረከቢያው ፡ ቦታ ፡ መላኩ ፡ ቀርቶ ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ የሚላክ ፡ ሲሆን ፤ (የትራንስፖሩን) ፡ የማመላለሱን ፡ ወጪ ፡ የሚችለው ፡ ገዢው ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ መረከብ ፡ ያለ ፡ ኪራ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማመላለሱን ፡ (የትራንስፖርን) ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ሻጩ ፡ ነው ።

(፫) ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ማንኛቸውም ፡ አላፊ ፡ በማይሆኑበት ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ (ትራንስፖር) ፡ ማመላለሻው ፡ የተቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ልዩ ፡ የሆ

BACK



ነውን ፡ የማመላለሻ ፡ (የትራንስፖርን) ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ድንገተኛውን ፡ የሚችለው ፡ ወገን ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፲፱ ፡፡ የጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡፡**

(፩) ስለ ፡ ዕቃው ፡ ማምጣት ፡ የሚከፈለውን ፡ የጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ ወይም ፡ የመጣውን ፡ ዕቃ ፡ ስለሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ የሚከፈለውን ፡ ሌላ ፡ ተከፋይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚችለው ፡ ሻጩ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ውሉ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ በሚከፈለው ፡ ቀረጥ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ተከፋይ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ተጨማሪ ፡ ሒሳብ ፡ ከዋጋው ፡ ጋራ ፡ ይደመራል ፡፡

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህን ፡ ቀረጥ ፡ የደረሰበትን ፡ ዕቃ ፡ ተቀባዩ ፡ ሳይረከብ ፡ የቈየው ፡ በሻጩ ፡ ወይም ፡ ሻጩ ፡ በአላፊነት ፡ በሚጠየቅበት ፡ ሰው ፡ አድራጎት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ ዕቃ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ ተረክቦ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ቀረጥ ፡ ወይም ፡ ሒሳብ ፡ መክፈል ፡ ሊደርስ ፡ አይችልም ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ሻጩ ፡ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ በተጨማሪነት ፡ የሚጠየቀውን ፡ ሒሳብ ፡ የሚከፍል ፡ ሻጩ ፡ ነው ፡፡

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ የጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ በሚቀነስበት ፡ መጠን ፡ ዋጋም ፡ ይቀነሳል ፡፡

## (ለ) የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ መጠበቅ ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳ ፡፡ የሻጩ ፡ ግዴታ ፡፡**

(፩) ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ሳይረከብ ፡ ወይም ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍል ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ በገዢው ፡ ኪሣራ ፡ ማስጠበቅ ፡ አለበት ፡፡

(፪) ሻጩ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ በመጠበቅ ፡ ያወጣው ፡ ወጪ ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ በጁ ፡ ለማቈየት ፡ መብት ፡ አለው ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳፩ ፡፡ የገዢው ፡ ግዴታ ፡፡**

(፩) ገዢው ፡ የተሸጠውን ፡ ገንዘብ ፡ የተቀበለ ፡ ሲሆን ፤ የማይፈልገው ፡ መሆኑን ፡ በሚያስብበት ፡ ጊዜ ፡ የተቀበለውን ፡ ነገር ፡ በሻጩ ፡ ኪሣራ ፡ ማስጠበቅ ፡ አለበት ፡፡

(፪) የተቀበለውን ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡ ምክንያት ፡ ሳይሰጥ ፡ እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሻጩ ፡ ለመመለስ ፡ መብት ፡ የለውም ፡፡

(፫) የተቀበለውን ፡ ነገር ፡ በመጠበቅ ፡ ያወጣው ፡ ወጪ ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ የተቀበለውን ፡ ነገር ፡ በጁ ፡ ይዞ ፡ ለማቈየት ፡ መብት ፡ አለው ፡፡

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳፪ ። የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ማስረከብ ፡ ወይም፡መሸጥ ።

ሻጩ ፡ ወይም ፡ ገዢው ፡ ጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ውሉች ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ በተሰጡት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፤ ዕቃውን ፡ በማስረከብ ፡ ወይም፡ በመሸጥ ፡ ዕቃውን ፡ ከመጠበቅ ፡ ግዴታ ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

(ሐ) ሊደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ አደጋዎች ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳፫ ። መሠረቱ ።

የአደጋ ፡ አላፊነት ፡ ለገዢው ፡ ተዛውሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ ቢደርስ ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ ቢለዋወጥ ፡ እንኳ ፡ ገዢው ፡ ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳፬ ። የተሸጠውን ፡ ዕቃ፡ስለ፡ማስረከብ ።

(፩) በውሉና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ዕቃው ፡ ለገዢው ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ፡ጀምሮ ፡ የአደጋ ፡ አላፊነትም ፡ ለገዢው ፡ ይዛወራል ።

(፪) ለገዢው ፡ የተሰጠው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ ዕቃ ፡ ቢሆንም ፤ ገዢው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ያላስታወቀ ፡ ወይም ፡ ያልጠየቀ ፤ ወይም ፡ ዕቃው ፡ እንዲለወጥና ፡ እንዲተካለት ፡ ያልጠየቀ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተጻፈው ፡ ደንብ ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳፭ ። የገዢው፡መዘግየት ።

(፩) እንዲሁም ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ የአደጋ ፡ አላፊነቶች ፡ ገዢው ፡ የዕቃ ፡ ማስረከቢያ ፡ ዋጋውን ፡ ለመክፈል ፡ ከሚዘገይበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ለገዢው ፡ ይዛወራሉ ።

(፪) ሽያጩ ፡ የተደረገው ፡ የተወሰነ ፡ ዐይነት ፡ በአላቸው ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ በግልጽ ፡ የተጠበቁትን ፡ ነገሮች ፡ ለብቻ ፡ አስቀድሞ ፡ ለይቶ ፡ ማኖሩን ፡ ለገዢው ፡ ካላስታወቀው ፡ ገዢው ፡ ሳይቀበል ፡ በመዘግየቱ ፡ በነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉት ፡ የአደጋ ፡ አላፊነቶች ፡ ወደርሱ ፡ አይዛወሩበትም ።

(፫) ዐይነታቸው ፡ ተለይቶ ፡ የታወቁት ፡ ነገሮች ፡ ከዐይነታቸው ፡ የተነሣ ፡ የማይለያዩ ፡ በመሆናቸው ፡ ምክንያት ፡ ገዢው ፡ እስኪረከባቸው ፡ ድረስ ፡ ሻጩ ፡ ለይቶ ፡ ለማስቀመጥ ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ እነዚህን ፡ ዕቃዎች ፡ ሊረከብ ፡ የሚችልበትን ፡ ማናቸውንም ፡ የተቻለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ቢያደርግ ፡ በቂ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፳፮ ፡ በጕዞ ፡ ላይ፡ስላለ፡ነገር ።

(፩) ሽያጩ ፡ የተፈጸመው ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፤ የተሸጠው፡ነገር፡ ለጫኙ ፡ በመሰጠቱ ፡ የማስረከቡ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉት ፡ የአደጋዎች ፡ አላፊነቶች ፡ በገዢው ፡ ላይ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ፡ የተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ ጠፍቶ ፡ ወይም፡ ተበላሽቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሻጩም፡ የሚያውቅ፡ ወይም፡ ማወቅ፡ የሚገባው፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፸፬ ፡ ወጪዎችን ፡ የሚመለከት ፡ የውል ፡ ቃል ።**

(፩) ስለ ፡ ወጪ ፡ የተደረገው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ይልቁንም ፡ ወጪውን ፡ የሚ ችለው፡ ሻጩ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገ ፡ ቢሆንም፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ሊደርሱ፡ የሚ ችሉትን ፡ የአደጋ ፡ አላፊነቶች ፡ ለማዛወር ፡ በቂ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፸፭። በክፍል ፡ በክፍል ፡ ተደርገው ፡ በአንድነት ፡ የሚጫኑ፡ሸቀጦች ።**

ሸቀጦቹ፡ በክፍል፡ በክፍል፡ ተደርገው፡ በአንድነት፡ በተጫኑ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ፡ለገ ዢው ፡ ዕቃው ፡ የተጫነበትን ፡ ማስረጃ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ መጫኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ሌላ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከላከለት ፤ ሻጩ ፡ ዕቃውን ፡ ለጫኙ ፡ በመስ ጠት ፡ የማስረከቡን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ፈጸመ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ አላፊነት ፡ ለገ ዢዎች ፡ ለየአንዳንዱ ፡ በየድርሻቸው ፡ መጠን ፡ ይዛወራል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ውልን ፡ ስላለመፈጸም ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ውልን ፡ በግድ ፡ ስለ ፡ ማስፈጸም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፸፮ ።የመረካከብን ፡ ግዴታ፡ ስላለመፈጸም ።(፩) መሠረቱ ።**

ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ ያላስረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተዋዋለበት ፡ ውል ፡ በግድ ፡ ሲፈጸም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝለት ፡ ሆኖ ፡ ሲታየው ፡ ገዢው ፡ ውሉ ፡ በግድ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፸፯ ።(፪)ምትክ ፡ ለመስጠት ፡ ስለ፡ መቻሉ።**

የሽያጭ ፡ ስምምነት ፡ የተደረገበት ፡ ዕቃ ፡ በልማድ ፡ ምትክ ፡ ሊገዛበት ፡ የሚ ቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የተባለው ፡ ምትክ ፡ በገዢው ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ችግርና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪ ፡ ሳይደረግበት ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻል ፡ እንደ ፡ሆነ ፤ ገዢው ፡ ውሉ፡ በግድ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለማስገደድ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፯፻፸፰ ።(፫) የማስገደጃ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ገዢው ፡ ውሉ ፡ ሳይፈጸም ፡ መዘግየቱን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ በግዴታ፡ እን ዲፈጸምለት ፡ የማስገደድ፡ አሳቡን ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ለሻጩ ፡ ያልገለጸለት ፡ እን ደሆነ ፤ ውሉ ፡ በግድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማስገደድ ፡ የሚፈቀድለት ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

(፪) የውሉ ፡ መፈጸሚያ ፡ ጊዜ ፡ በጥብቅ ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ የማስታወቂያው ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ጥብቅ ፡ አኳኋን ፡ የተገመተ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፪ ። ዕቃው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ትክክል ፡ ስለ ፡ አለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ገዢው ፡ የተሸጠውን ፡ ዕቃ ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ትክክል ፡ ያለመሆኑን ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ በሚገባ ፡ ያስታወቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉን ፡ በግዴታ ፡ ለማስፈጸም ፡ በሚቻልበት ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ ፡ አዲስ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ከዕቃው ፡ የጐደለውን ፡ እንዲያስረክበው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የሽያጩ ፡ ስምምነት ፡ በገዢው ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሻጩ ፡ በሚሠራው ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ሥራ ፡ በሚያወጣው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሲሆንና ፡ የተሠራው ፤ ወይም ፡ የወጣው ፡ ነገር ፡ ጉድለት ፡ ሲገኝበት ፡ ሻጩ ፡ ጉድለቱን ፡ በማጥፋት ፡ ሊያድሰው ፡ የሚችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያድስለት ፡ ገዢው ፡ ሻጩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፫ ። ዋጋን ፡ አለመክፈል ።

ገዢው ፡ ዋጋውን ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለዕቃው ፡ የተደረገው ፡ የሽያጩ ፡ ስምምነት ፡ በንግድ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ሁለቱን ፡ ባለጉዳዮች ፡ በሚያቻችል ፡ ሽያጭ ፡ ለመሆን ፡ የሚችል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሻጩ ፡ ዋጋው ፡ እንዲከፈለው ፡ ለማስገደድ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፬ ። ዐይነቱ ፡ ወደፊት ፡ የሚገለጽ ፡ ሽያጭ ።

(፩) ፡ የሻጩ ፡ መብት ።

በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ገዢው ፡ ከስምምነቱ ፡ በኋላ ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ፎርም ፤ መለካትን ፡ ወይም ፡ ለነገሩ ፡ ሌላውን ፡ ዐይነት ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ የመወሰን ፡ መብት ፡ የርሱ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የሚለየውን ፡ ዐይነት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለርሱ ፡ በሚበቃ ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይለይ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ ራሱ ፡ ለገዢው ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነውን ፡ በሚያውቀው ፡ መሠረት ፡ ዐይነቱን ፡ ሊለይለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፭ ። (፪) ለነገሩ ፡ አሠራር ፡ የተሰጠው ፡ ዐይነትና ፡ ውሳኔ ።

(፩) ሻጩ ፡ ለነገሩ ፡ የሰጠውን ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ለይቶ ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ተለየው ፡ ለገዢው ፡ ያስታውቃል ። ደግሞ ፡ የተለየ ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ የሚፈልግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚበቃ ፡ ጊዜ ፡ ይወስንለታል ።

(፪) ገዢው ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈልገውን ፡ የአሠራር ፡ ልዩነት ፡ ዐይነት ፡ ሳይለይ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ የፈጸመው ፡ ዐይነት ፡ አስገዳጅ ፡ ይሆናል ። (ገዢውን ፡ እንዲቀበል ፡ ያስገድደዋል ) ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፮ ።

## የውል ፡ መፍረስ ።

### (ሀ) ገዢው ፡ ውሉን ፡ የሚያፈርስበት ፡ ምክንያት ።

ቍ ፡ ፩ሺ፯፻፸፩ ። መሠረቱ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ገዢው ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብለው ፡ እንዲበይኑ ፡ ለዳኞች ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፉት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፩ሺ፯፻፸፪ ። ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ የውሳኔ ፡ ጊዜ ።

(፩) ዕቃዎች ፡ በገበያ ፡ ላይ ፡ ዋጋቸው ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆንና ፡ ገዢውም ፡ እነዚህኑ ፡ በገበያ ፡ ላይ ፡ ሊያገኛቸው ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ የሚወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ዘወትርም ፡ የጠበቀ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚህም ፡ በውሉ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሻጩ ፡ ወይም ፡ ገዢው ፡ ቀኑን ፡ ለመወሰን ፡ የሚችሉ ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ በጥብቅ ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፩ሺ፯፻፸፫ ። ተጨማሪ ፡ ጊዜ ። (፩) ስለ ፡ መቻሉ ።

(፩) የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ የተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ በጥብቅ ፡ ያልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ ዳኞቹ ፡ ለሻጩ ፡ ግዴታውን ፡ የሚፈጽሙበት ፡ የችሮታ ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ወስኖ ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ ዕቃውን ፡ የማይቀበል ፡ መሆኑን ፡ ለሻጩ ፡ ሊያስታውቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ሻጩ ፡ የተወሰነው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ያላስረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፩ሺ፯፻፸፬ ። የማይበቃ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ገዢው ፡ የወሰነው ፡ የመረከብ ፡ ጊዜ ፤ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ያልሆነ ፡ ሲሆን ፤ ሻጩ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ የማ

BACK



ረካከቡን ፡ ተግባር ፡ እንደማይፈጽም ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለገዢው ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፤ ገዢው ፡ የወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵ ። የመረከቢያ ፡ ስፍራ ።

(፩) ሻጩ ፡ ሊያስረክብ ፡ ይገባው ፡ የነበረበትን ፡ ስፍራ ፡ ትቶ ፡ ዕቃውን ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ያስረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ መንገድ ፡ የውሉን ፡ ስምምነት ፡ የመጣስ ፡ ዐይነተኛ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ አይበይኑም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ከውሉ ፡ ግዴታ ፡ የጐደለውን ፡ ነገር ፡ ውሉ ፡ ወይም ፡ በሚፈቅደው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሻጩ ፡ ሊያሻሽል ፡ የማይችል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዳኞች ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ አይፈርዱም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፩ ። በሙሉ ፡ ለገዢው ፡ ያልተላለፈ ፡ ሀብትነት ።

(፩) መብቱን ፡ በሚነካ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ሻጩ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ከሚሉ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ለገዢው ፡ ሳያስረክብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ገዢው ፡ ዕቃውን ፡ ሲገዛ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ገዝቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ፍርስ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፫) እንደዚሁም ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ያለበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ የተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ እጅግም ፡ የማያጎዳ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ገዢው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ የተባለው ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ ቢያውቅም ፡ ኖሮ ፡ ሳይገዛው ፡ የማይቀር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ውሉ ፡ ፍርስ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፪ ። እንዲለቅ ፡ ስለ ፡ መደረጉ ።

(፩) ሻጩ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ተፋላሚ ፡ ሲመጣ ፡ ለገዢው ፡ መድን ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢ ፡ የገዛውን ፡ ዕቃ ፡ በሙሉ ፡ ሲለቅ ፡ ውሉ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ገዢው ፡ ከገዛው ፡ ነገር ፡ በከፊል ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፫ ። በከፊል ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

(፩) ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ዕቃ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ያስረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ካስረከበው ፡ ዕቃ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ትክ

ክል ፡ ሆኖ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ውሉ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚፈጸም ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቦት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ውሉን ፡ አያደርግም ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ ካልተገመተ ፡ በቀር ፡ ገዥ ፡ በሞላው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ በከፊል ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገው ፡ ዕቃ ፡ እጅግም ፡ የማያጎዳ ፡ የነገሩ ፡ ክፍል ፡ ሲሆንና ፤ ገዢው ፡ የዚህን ፡ በጣም ፡ የማያጎዳ ፡ ያልሆነውን ፡ ነገር ፡ መልቀቅ ፡ የሚደርስበት ፡ መሆኑን ፡ ዐውቆ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮም ፡ ሳይገዛው ፡ የማይቀር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፩ ።የተሸጠው፡ነገር፡ጉድለት።</u>

(፩) የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ሻጩ ፡ ለገዢው ፡ ዋቢ ፡ ሊሆንበት ፡ የሚገባው ፡ ጉድለት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጉድለቱ ፡ እጅግም ፡ የማያጎዳ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ገዢው ፡ ጉድለቱን ፡ ዐውቆ ፡ ኖሮም ፡ ቢሆን ፡ ጉድለት ፡ የተገኘበትን ፡ ነገር ፡ ሳይገዛው ፡ የማይቀር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሲታይ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፪ ። ከተሸጡት ፡ ነገሮች ፡ በአንዱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ጉድለት ።</u>

<u>(፩) መሠረቱ ።</u>

(፩) የተሸጡት ፡ ነገሮች ፡ ብዙዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ነገር ፡ ዕቃዎች ፡ ሲሆንና ፡ የተገኘው ፡ ጉድለት ፡ ከነገሮቹ ፡ መካከል ፡ በአንዳንዶቹ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚቻለው ፡ ጉድለት ፡ በተገኘባቸው ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ ጉድለት ፡ የሌለባቸው ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ተረከባቸው ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ግምታቸው ፡ መጠን ፡ ዋጋቸውን ፡ ይከፍላል።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፫።(፪)ልዩነት።</u>

(፩) ጉድለት ፡ የተገኘበት ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፤ በገዢው ፡ ወይም ፡ በሻጩ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሳያደርስ ፡ ጉድለት ፡ ከሌለባቸው ፡ ነገሮች ፡ ሊነጠል ፡ የማይቻል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ በሙሉ ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።

(፪) ተጨማሪ ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዋጋ ፡ የተሸጡ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ በዋናው ፡ ነገር ፡ የተደረገው ፡ የውል ፡ መፍረስ ፡ በተጨማሪዎቹም ፡ ላይ ፡ ይደርሳል።

(ለ) <u>ሻጩ ፡ ውሉን ፡ የሚያፈርስበት ፡ ምክንያት ።</u>

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፬።መሠረቱ።</u>

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ <u>ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው</u> ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከ

ቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፤ ሻጩ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብለው ፡ እንዲፈርዱ ለት ፡ ዳኞቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፩ ። የዋጋ ፡ አለመክፈል ።

(፩) ዋጋውን ፡ የመክፈል ፡ መብት ፡ በውሉ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ለሻጩ ፡ የተሰጠው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ፡ ዋጋው ፡ ያልተከፈለው ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ውሉ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል።

(፪) ሽያጩ ፡ የተደረገው ፡ ዋጋቸው ፡ በተወሰነ ፡ ወይም ፡ የዕለት ፡ ዋጋቸው ፡ በታ ወቀ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መብት፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ለሻጩ ፡ በግልጽ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ የሚበቃ ፡ ቀን ፡ ሰጥቶ፡ በማስጠንቀቂያ ፡ ቃል፡ ለገዢው ፡ የወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ ፡ ሻጩ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ዳኞች ፡ ለገዢው ፡ የችሮታ ፡ ጊዜ ፡ ሰጥተውት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ ፡ ሻጩ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታ ወቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፪ ። ዕቃውን ፡ ስላለመረከብ ።

ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ በውሉ ፡ በተነገሩት ፡ ውለታዎች ፡ አደራረግ ፡ ያልተረ ከበ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህ ፡ ገዥ ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ አለመረከብ ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከ ፍል ፡ ይቀራል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ የነገሩ ፡ ሁኔታዎች፡ ሲታዩ፡ ከውሉ ፡ ዋነኛው ፡ አንዱ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ መረከብ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፫ ። ለይቶ ፡ የማስታወቅ ፡ ጕድለት ።

በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ገዢው ፡ ከስምምነቱ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ፎርም ፡ (ቅጡን) ፡ ለመለካት ፡ ወይም ፡ ለነገሩ ፡ ሌላውን ፡ ዐይነት ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መስጠት፡ የመወሰን ፡ መብት ፡ ለርሱ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የሚለየውን ፡ ዐይ ነት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለርሱ ፡ በሚበቃ ፡ ሻጩ ፡ በወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይለይ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታ ወቅ ፡ ይችላል ።

## (ሐ) ሁለቱም ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ውሉን ፡ የሚያፈርሱባቸው ፡ ምክንያቶች ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፬ ። የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ በማከታተል ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ የተደረገ ፡ ውል ።

(፩) በማከታተል ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋ ዋዮች ፡ አንዱ ፡ ግዴታ ፡ የገባበትን ፡ ነገር ፡ ሳይፈጽም ፡ በመቅረቱ ፡ ወይም ፡

የሚሰጠው ፡ ነገር ፡ የተበላሸ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ወደፊት ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚገባቸውም ፡ የመስጠት ፡ ተግባሮች ፡ ሳይፈጸሙ ፡ ይቀራሉ ፡ ወይም ፡ የተበላሹ ፡ ይሆናሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ሥጋት ፡ ያደረበት ፡ ወገን ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህም፡ በቀር፤ ገዢው ፡ የሚረከባቸው ፡ ነገሮች ፡ ሳይፈጸሙለት ፡ ከቀሩት ፡ ወይም፡ ከተበላሹ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ በመሆናቸው ፡ ምክንያት ፡ ለርሱ፡ ጠቃሚነት ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወደፊት ፡ ለሚረከባቸው ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ለተረከባቸው ፡ ወይም ፡ ለሁለቱም ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፪ ። ውልን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ለውሉ ፡ መፈጸም ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ የተዋዋለውን ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የውሉ፡ መሠረት፡ የሚነካ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ መፈጸሙ ፡ የሚዘገይ ፡ ሲሆን ፤ ሌላው፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፫ ። አስቀድሞ ፡ የሚደረግ ፡ የውል ፡ ማፍረስ ።

ለውሉ ፡ መፈጸም ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ አንዱ ፡ ውሉን ፡ የማይፈጽም ፡ መሆኑን ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ያስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(መ) የውሉ ፡ መፍረስ ፡ ሁኔታዎችና ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፬ ። በመዘግየት ፡ ምክንያት ፡ የሚደረግ ፡ የሚገባ ፡ የውል ፡ መፍረስ ።

አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ከውሉ ፡ አንዱን ፡ ዋነኛ ፡ የሆነውን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ውሉን ፡ እንዲፈጽምለት ፡ መፈለጉን፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ምላሽ ፡ ሳይሰጠው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ በሚገባ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፭ ። የውሉ ፡ መፍረስ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ።

(፩) ውሉ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ተገቢ ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉት ፡ ኪሣራዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ባደረጉት ፡ ውል ፡ ከገቡባቸው ፡ ግዴታዎች ፡ ነጻ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) አንዱ ፡ ወገን ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ያወጣውን ፡ ኪሣራ ፡ ጭምር ፡ የሰጠው ፡ ነገር ፡ እንዲመለስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በየበኩላቸው ፡ የፈጸሙት ፡ ግዴታ ፡ እንዳለ ፡ የተቀበሉትን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መመለስ ፡ በያንየንዳንቸው ፡ ላይ ፡ ስለሚወድቀው ፡ ግዴታ ፡

አንዱ ፡ ወገን ፡ ለሌላው ፡ ያለበትን ፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡ እስኪፈጽምለት ፡ ድረስ ፡ ሌላውም ፡ አልመልስም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፮ ። የዋጋው ፡ ወለድና ፡ ሌላ ፡ ጥቅም ።**

(፩) ሻጩ ፡ የተቀበለውን ፡ ዋጋ ፡ በሚመለስበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋውን ፡ ከተቀ ለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ከነወለዱ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ገዢውም ፤ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ሲመልስ ፤ ከዚያው ፡ ነገር ፡ ያገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ጭምር ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፯ ። የተገዛውን ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ለመመለስ ፡ አለመቻል ።**

(፩) በርሱ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ አላፊ ፡ በሚሆንለት ፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ የገዛው ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ጠፍቶ ፡ ወይም ፡ ተበላሽቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ የመጠየቅ ፡ ወይም ፡ የማስታወቅ ፡ ወይም ፡ ፈርሷል ፡ የተባለውን ፡ ውል ፡ የመጥቀስ ፡ መብቱን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በልማድ ፡ እንደሚደረገው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ለምርመራ ፡ ሰጥቶት ፡ በምርመራው ፡ ምክንያት ፡ የተበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ የተባለ ውን ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሸጠው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ለዋወ ጠው ፡ ወይም ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ በርሱ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበላሸ ፡ ለመመለስ ፡ የማይቻለው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ውሉ ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፰ ። በተሸጠው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ መለዋወጥ ።**

የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ዐይነት ፡ ተለዋውጦ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ለማስታወቅ ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ የሚቈየው ፡—

(ሀ) ውሉ ፡ እንዲፈርስለት ፡ የሚጠይቅበትን ፡ ወይም ፡ የሚያስታውቅበትን ፡ ጕድለት ፡ ለማግኘት ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ ገዢው ፡ የገዛው ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ከለዋወጠው ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ ጕድለቱ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በነገሩ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ መለዋወጥ ፡ ግን ፡ የማይጎዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፱ ። ወጪ ፡ ገንዘብ ።**

(፩) ገዢው ፡ ስለ ፡ ገዛው ፡ ነገር ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ያለአገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በሚል ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገረው ፡ ሕግ ፡ የተጻፉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ እንዲለቅ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚያው ፡ ከሚያስለቅቀው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ኪሣራውን ፡ ለመቀበል ፡ የማይችል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለገዛው ፡ ነገር ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ ከሻጩ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## የጉዳት ፡ ኪሣራ ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፪ ። ጠቅላላ ፡ ውሳኔ ።

(፩) አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ለአንደኛው ፡ ወገን ፡ ከገባበት ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱን ፡ ሳይፈጽምለት ፡ በመቅረቱ ፡ ምክንያት ፡ ጉዳት ፡ አድርሶበት ፡ ሲገኝ ፤ ሻጩ ፡ ወይም ፡ ገዢው ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ውሉ ፡ በትክክልና ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይፈጸም ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ ቢፈርስም ፡ ጸንቶ ፡ ቢቀርም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

## (ሀ) ውሉ ፡ ባልፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ኪሣራ ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፫ ። የኪሣራው ፡ ልክ ።

(፩) ውሉ ፡ ያልፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

(፪) ገዢው ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍል ፡ በሚዘገይበት ፡ ጊዜ ፤ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ወለድ ፡ መሠረት ፡ የመዘግየት ፡ ወለድ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) በገዢውና ፡ በሻጩ ፡ መካከል ፡ ሁለቱን ፡ የሚያገናኝ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በየዓመቱ ፡ በዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ የወለድ ፡ ወለድ ፡ አይከፈልም ።

## (ለ) ውሉ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ኪሣራ ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፬ ። ነገሩ ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) ውሉ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ የተሸጠው ፡ ነገር ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፤ የጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ የውሉን ፡ ፈራሽነት ፡ የማስታወቅ ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ በተቻለበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ በዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ መብት ፡ ፈራሽ ፡ በሆነበት ፡ ቀን ፡ ማግሥት ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ የዋጋ ፡ ልዩነት ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ይሆናል ።

(፪) ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በምትክ ፡ በሚሆን ፡ ግዥ ፤ ወይም ፡ በማቻቻያ ፡ በሚደረግ ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሰውም ፡ ደንበኛ ፡ ወጪ ፡ አብሮ ፡ ይታሰባል ።

BACK



(፫) ለኪሣራው ፡ ማመዛዘኛ ፡ የሚሆነው ፡ ዋጋ ፤ ገዢው ፡ ወድም ፡ ሻጩ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎቻቸው ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ደንበኛ ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ የተነገሩትን ፡ ሸቀጦች ፡ ለመግዛት ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ የሚሄዱበት ፡ ገበያ ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፺፫ ። (፪) በምትክ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግዥ ፡ ወይም ፡ በመቻቻያ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ሽያጭ ።

(፩) ገዢው ፡ በምትክ ፡ የተደረገውን ፡ ግዥ ፡ ወይም ፡ ሻጩ ፡ የማቻቻያውን ፡ ሽያጭ ፡ በውነት ፡ ፈጽመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጉዳትን ፡ ኪሣራ ፡ ለማስብ ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፤ ስለ ፡ ግዥው ፡ የተከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ በሽያጩ ፡ የተገኘው ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

(፪) አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ በምትክ ፡ የሆነው ፡ ግዥ ፡ ወይም ፡ በመቻቻያ ፡ የተረገው ፡ ሽያጭ ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ወይም ፡ ለንግድ ፡ አሠራር ፡ ደንበኛ ፡ ባልሆነ ፡ አኳኋን ፡ መፈጸሙን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኪሣራው ፡ ሊቀነስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፬ ። የበለጠ ፡ ጉዳት ።

(፩) ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ከልዩ ፡ አካባቢዎች ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፤ የጉዳቱ ፡ ልክ ፡ የበለጠ ፡ ለመሆን ፡ እንደሚችል ፡ ለሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ማስጠንቀቁን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ በውነት ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ግዴታው ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረበት ፡ ተዋዋዩን ፡ በመጉዳት ፡ ፍላጎት ፡ በከባድ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ይፈጸማል ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፺፭ ። ነገሩ ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ዕቃው ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ የሚከፈለው ፡ የጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ ዕውቀት ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ግምት ፡ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ባለገንዘቡ ፡ ይደርስበታል ፡ ተብሎ ፡ በሚገመተው ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ባለፈው ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ ስለ ፡ ኪሣራው ፡ የሚከፈለው ፡ የካሣ ፡ ልክ ፡ በእውነት ፡ ከደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ጋራ ፡ እኩልነት ፡ ያለው ፡ በሚሆን ፡ መጠን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፮ ። ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ።

(፩) ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ውሉ ፡ በሚፈርስበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ የታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ኪሣራ ፡ የሚገመተው ፤ ስለ ፡ ግዴታው ፡ መፈጸም ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ማለቂያ ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ዕቃው ፡ ባለው ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) በውሉ ፡ ማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራው ፡ የሚገመ

ተው ፡ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ የማስታወቅ ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ በቻለ ፡ ቀን ፡ የነበረውን ፡ የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ የጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ አስቀድሞ ፡ ለተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ ምትክ ፡ በተገዛበት ፡ ጊዜ ፡ እርግጥ ፡ ከተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፤ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ለተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ የማቻቻያ ፡ ሽያጭ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ ከተከፈለው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፪ ። የገዛውን፡ዕቃ፡እንዲለቅ ፡ ስለ፡መደረጉ ።

ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ነገር ፡ እንዲለቅ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፤ ሻጩ ፡ ሌላውን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈሉ ፡ ሳይቀር ፡ ክስ ፡ የሚያቀርብ ፡ መሆኑን ፡ ለሻጭ ፡ ገዥ ፡ ነግሮት ፡ ቢሆን ፡ ሊያስቀረው ፡ ይችል ፡ የነበረ ፡ ወጪ ፤ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ ለዳኝነትና ፡ ከዳኝነት ፡ ውጭ ፡ ያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሽያጭ ፡ አሠራር ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ከብቶችና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ በሕይወት ፡ ስላሉ ፡ እንስሶች ፡ ሽያጭ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፫።(፩)፡መሠረቱ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ከብቶችና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ በሕይወት ፡ ስላሉ ፡ እንስሶች ፡ ሽያጭ ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ተወስኖዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፬ ። ተላላፊ ፡ በሽታዎች፤መድን፡የመሆን፡ሕጋዊ ፡ ግዴታ ።

ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ እንስሳ ፡ በሚያስረክብበት ፡ ጊዜ ፡ እንስሳው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ካሉት ፡ በሽታዎች ፡ በአንዱ ፡ ያልተያዘ ፡ ለመሆኑ ፡ መድን ፡ ነው ። በሽታዎች፡የተባሉትም ፤ ከአበደ ፡ ውሻ ፡ በሽታ ፡ ከማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ እንስሶች ፡ ሁሉ ፤

ከደስታ ፡ በሽታ ፡ በቀንድ ፡ ከብቶችና ፡ እነሱንም ፡ ለመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፤

ከሳምባ ፡ በሽታ ፡ በቀንድ ፡ ከብቶች ፤

ከዕባጭና ፡ ከንድፍት ፡ በጋማ ፡ ከብቶችና ፡ እነሱንም ፡ በመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፤

ከአባ ፡ ሠንጋና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ መዥገር ፡ አመጣሽ ፡ በሽታዎች ፡ በጋማ ፡ ከብት ፤ በቀንድ ፡ ከብቶች ፤ በፍየልና ፡ በበጎች ፡ ላይ ፤

ከአፍታ ፡ ( አፈማዝ ) ፡ በቀንድ ፡ ከብቶች ፤ በበግ ፤ በፍየሎችና ፡ በላሞች ፡ እንዲሁም ፡ በአሳማና ፡ በግመል ፡ ላይ ፤

ከአባ ፡ ጐርባና ፡ ነቀርሳ ፡ በሽታ ፡ በቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ላይ ፤

ከበጎች ፡ ፈንጣጣ ፡ በበጎችና ፡ በአሳሞች ፡ ላይ ፤
ከልዩ ፡ ዐይነቶች ፡ የአሳሞች ፡ በሽታና ፡ ፈንጣጣ ፤
ከእከክ ፡ ( የቆዳ ፡ በሽታ ) ፡ በጋማ ፡ ከብትና ፡ እነሱን ፡ በመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፤
ከአሳማ ፡ ነቀርሳ ።
ከንድፍት ፡ ( ቲሪፓኖ ፡ ዞማዚስ ) ፡ ከዝንብ ፡ የሚተላለፍ ፡ በሽታ ፡ በጋማ ፡ ከብቶችና ፡ በግመል ፡ ላይ ፤
ከኤፕ ፡ ቶስፖይሮሲስ ፡ ( የጉበት ፡ በሽታ ) ፡ በጋማ ፡ ከብቶች ፡ ላይ ፤
ከኩልኩልት ፡ አስፋ ፡ (ጐስቶ ፡ ማቶሲስ) ፡ ( ትል ፡ በሽታ ) ፡ በበጎች ፡ ላይ ፤
ከውርጃ ፡ በሽታ ፡ በቀንድ ፡ ከብቶች ፡ በበግና ፡ በፍየሎች ፡ ላይ ፤
ከመኽገር ፡ አመጣሽ ፡ በሽታ ፤
ከተላላፊ ፡ የጋማ ፡ ከብት ፡ የመስከ ፡ በሽታ ፤
ከልዩ ፡ ዐይነት ፡ የአዕዋፍ ፡ በሽታ ፤
ተላላፊ ፡ ከሆነና ፡ የተጋብአ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የቆዳ ፡ በሽታና ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የንብ ፡ በሽታ ፡ ሁሉ ፤

## ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፸ ። (፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ ለተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማናቸውም ፡ ውል ፡ ፍርስ ፡ ነው ። ( አይረጋም ) ፡

## ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፸፩ ። ስለ ፡ ጕድለቶች ፡ (፩) መድን ፡ የመሆን፡ሕጋዊ፡ግዴታ ።

የተሸጠው ፡ እንስሳ ፡ ለተፈጥሮው ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ለተነገረው ፡ አገልግሎት፡ እንዳይሆን ፡ የሚያደርገው ፡ ጕድለት ፡ ያደረበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሻጩ ፡ መድን ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፸፪ ። (፪) በስምምነት፡የሚደረግ፡የውል ፡ ቃል ።

(፩) ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ለእንስሳው ፡ አለበት ፡ የተባለውን ፡ ጕድለት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፤ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፤ ለማስወገድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ደግሞ ፡ በሻጩ ፡ በኩል ፡ እንስሳው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ አለው ፡ ስለ ሚባለው ፡ ነገር ፡ የመድንነቱን ፡ ወሰን ፡ ለማስፋትና ፡ ስለ ፡ ዋቢነቱም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

## ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፸፫ ። የውሉ፡መፍረስ ።

እንደ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ስለ ፡ እንስሳው ፡ መድን ፡ መሆን ፡ የሚገባ ፡ ሲሆን ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ የያዘው ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፤ የሺያጩ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፬ ። የእንስሳው ፡ መሞት ።

መድን ፡ መሆን ፡ ባለበት ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ጕድለት ፡ በደረሰው ፡ ድንገተኛ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ እንስሳው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእንስሳው ፡ መሞት ፡ የሻጩ ፡ ኪሣራ ፡ ሆኖ ፡ ዋጋውን ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፭ ። የጉዳት ፡ ኪሣራ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሻጩ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ በገዢው ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፤

(ሀ) ለሽያጩ ፡ ውል ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ እንስሳ ፡ በሽታ ፡ ያልያዘው ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ የሌለበት ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ አረጋግጦ ፡ መድን ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለሽያጩ ፡ ውል ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ እንስሳ ፡ ሻጩ ፡ ባስረከበበት ፡ ጊዜ ፡ እንስሳው ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ሻጩ ፡ ማወቁን ፡ ለማስረዳት ፡ የተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፮ ። የውሉ ፡ አለመፍረስ ።

(፩) ገዢው ፡ የእንስሳውን ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፤ በሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ በጽሑፍ ፡ በተነገረው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ በልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ አሳይቶ ፡ እንስሳው ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ለሻጩ ፡ ካላስታወቀው ፡ ገዢው ፡ በሻጩ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

(፪) በውል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ እንስሳውን ፡ ካስረከበበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የእንስሳውን ፡ በሽታ ፡ ወይም ፡ ያለበትን ፡ ጕድለት ፡ በልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ አሳይቶ ፡ ለሻጩ ፡ ካላስታወቀው ፡ እንደዚሁ ፡ ገዢው ፡ በሻጩ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## በዐይነት ፡ ስለሚደረግ ፡ ሽያጭ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፯ ። ሻጩ ፡ ኀላፊ ፡ መድን ፡ የሚሆንባቸው ፡ ዐይነቶች ።

(፩) ዐይነትን ፡ ወይም ፡ ሞዴልን ፡ (ናሙናን) ፡ በማሳየት ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ ዐይነት ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ታየው ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ታየው ፡ ሞዴል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) በተሰጠው ፡ ዐይነትና ፡ ( በናሙናው ) ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ አጻጻፍ ፡ መካከል ፡ የሚያጣላ ፡ ነገር ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተሰጠው ፡ ዐይነት ፡ ብልጫ ፡ ይኖረዋል ።

(፫) የሚያጣላ ፡ ነገር ፡ ሳይኖር ፤ ልዩነት ፡ ብቻ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተባለው ፡ ዕቃ ፡ የዐይነቱንና ፡ (ናሙናውን) ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉትን ፡ ዐይነቶች ፡ ሁለቱም ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፯ ። የዕቃውን ፡ ዐይነት ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

ዐይነቱ ፡ የተሰጠው ፡ ወገን ፡ ለማሳየት ፡ የሚያቀርበው ፡ ዐይነቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ከተቀበለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፹፰ ። የነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚነት ።**

(፩) ሽያጩ ፤ (ናሙናውን) ፡ ዐይነቱን ፡ (ኤቫንቲዮውን) ፡ ወይም ፡ ሞዴሉን ፡ ለገዢው ፡ ለማሳየት ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤ የዕቃውን ፡ ዐይነት ፡ ለመስጠት ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ መገደድ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐይነትን ፡ (ኤቫንቲዮን) ፡ ወይም ፡ ሞዴልን ፡ በማሳየት ፡ የተደረገ ፡ ሽያጭ ፡ አለ ፡ አይባልም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## በፈተና ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺ ። ወዶ ፡ ለመቀበል ፡ የሚሰጥ ፡ ጊዜ ።**

(፩) የሽያጩ ፡ ውል ፡ በፈተና ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ ወዶ ፡ መቀበሉን ፡ ወይም ፡ አለመቀበሉን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በውሉ ፡ ማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ለመፈተን ፡ የወሰደውን ፡ ነገር ፡ ወዶ ፡ መቀበሉን ፡ አለመቀበሉን ፡ የሚያስታውቅበትን ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ ፡ ሊወስንለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፩ ። የገዢው ፡ ዝምታ ።**

(፩) ገዢው ፡ የወሰደውን ፡ ነገር ፡ ወዶ ፡ መቀበሉን ፡ ወይም ፡ አለመቀበሉን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያላስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተባለውንም ፡ ነገር ፡ እንዲፈትን ፡ ተሰጥቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሽያጩ ፡ ውል ፡ ደንበኛ ፡ ይሆናል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገዢው ፡ ዕቃውን ፡ እንዳልፈለገው ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፪ ፡ የዝምታ ፡ መቀበል ።**

እንደዚሁም ፡ ገዢው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሳይለይ ፡ ለወሰደው ፡ ነገር ፡ ዋጋውን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ለመፈተን ፡ አስፈላጊ ፡

BACK



ከነበረው ፡ ሥራ ፡ አልፎ ፡ በወሰደው ፡ ነገር ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አደራረግ ፡ የሠራ
በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሽያጩ ፡ ደንበኛ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፫ ። በነገሩ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ መበላሸት ።

የሚፈተነውን ፡ ነገር ፡ ገዢው ፡ የተረከበውም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፤ ገዢው ፡ ለመ
ፈተን ፡ የወሰደውን ፡ ነገር ፡ መውደዱን ፡ ሳያስታውቅ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ በተ
ባለው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ መበላሸት ፡ በሻጩ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

ዋጋው ፡ በየጊዜው ፡ ስለሚከፈልለት ፡ ሽያጭ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፬ ። ለሻጩ ፡ ያለው ፡ የመምረጥ ፡ መብት ።

በየጊዜው ፡ ዋጋው ፡ እንዲከፈል ፡ ውለታ ፡ በማድረግ ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ ተሸጦ ፤
ለገዢው ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ ገዢው ፡ በየጊዜው ፡ እንዲከፍለው ፡ ከተመ
ደበው ፡ ገንዘብ ፡ አንዱን ፡ መደብ ፡ እንዲከፍለው ፡ ሻጩ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥ
ቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ያልተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያገባለት ፡ ገዢውን ፡ ለመክ
ሰስ ፡ ይችላል ፤ ወይም ፡ የውሉን ፡ ፈራሽነት ፡ የማስታወቅ ፡ መብት ፡ የራሱ ፡ እን
ዲሆን ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፭ ። የውሉ ፡ መፍረስ ።

(፩) ውሉ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፤ ሻጩና ፡ ገዢው ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ የተሰጣጡትን ፡
ነገር ፡ መመለስ ፡ አለባቸው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፤ ሻጩ ፡ በገዢው ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ቈየው ፡ ነገር ፡ አገልግሎት ፡ የሚ
ገባ ፡ ኪራይና ፡ በማገልገሉ ፤ ስለ ፡ ተበላሸበትም ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡
ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በገዢው ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ የሆኑትን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመጣል ፡ የሚና
ገረው ፡ ማንኛውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፮ ። ቀሪው ፡ ዕዳ ፡ ስለሚከፈል ፡ የአስገዳጅነት ፡ ውል ።

(፩) ዋጋው ፡ በየጊዜው ፡ እንዲሰጥ ፡ የተደረገው ፡ አከፋፈል ፡ በሚቀርበት ፡ ጊዜ ፡
ቀሪውን ፡ ዕዳ ፡ የማስከፈል ፡ አስገዳጅነት ፡ በውሉ ፡ ተነግሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
ባለዕዳው ፡ በማከታተል ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያልከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እጅግ ፡ ቢያ
ንስ ፡ ከሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ዐሥረኛው ፡ እጅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሻጩ ፡ በተደ
ረገው ፡ ስምምነት ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ።

(፪) በገዢው ፡ ላይ ፡ የበለጠና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪን ፡ የሚያስከትል ፡ ተቃራኒ ፡
ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ አይጸናም ።

BACK



## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፭ ።

## ባለሀብትነቱን ፡ ለራሱ ፡ በማስጠበቅ ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፯ ። በሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን፡ላይ፡መቃወሚያ፡ስለሚሆን ፡ ውል ።**

(፩) ይዞታው ፡ ለገዥው ፡ ተላልፎ ፡ ባለሀብትነቱ ፡ ግን ፡ ዋጋው ፡ እስኪከፈልለት፡ ድረስ ፡ የሻጩ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቈይ ፡ የተደረገ ፡ የውል ፡ ቃል ፤ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተዘጋጀ ፡ የሕዝብ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ በገዢው ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ የተባለው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ነገሩን ፡ በገዙት ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) በንግድ ፡ ሕግ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ነገሩን ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ በከሠረ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ከገዢው ፡ ገንዘብ ፡ በሚፈልጉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፰ ። በዕቃው ፡ ላይ፡ሊደርሱ፡የሚችሉ፡አደጋዎች ።**

የማስረከቡ ፡ ተግባር ፡ ከተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሊደርሱ፡ የሚችሉ ፡ አደጋዎች ፡ የገዢው ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፶፱ ። የሽያጭ፡መፍረስ ።**

(፩) ሽያጩ ፡ በሚፈርስበት ፡ ጊዜ ፡ ሻጩ ፡ በየጊዜው ፡ በተደረገው ፡ አከፋፈል ፡ የተቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለገዢው ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) ደግሞም ፡ በገዢው ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ቈየው ፡ ነገር ፡ አገልግሎት ፡ የሚገባ ፡ ኪራይና ፡ በማገልገሉ ፡ ስለ ፡ ተበላሹትም ፡ ኪሣራን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በገዢው ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ የሆኑትን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመጣል ፡ የሚናገረው ፡ ማንኛውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፮ ።

## የተሸጠውን ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ የሚደረግ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷ ። መልሶ ፡ የመግዛት፡ችሎታ ።**

ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መልሶ ፡ ከገዥው ፡ ለመግዛት ፡ የሚፈቅድለትን ፡ መብት ፡ አስጠብቆ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፩ ። የሚወሰነው፡ጊዜ።**

(፩) ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ነገር ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ ባለው ፡ ችሎታ ፡የሚሠራበት ፡ ጊዜ ፤ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ከዚህ ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ ፡ በመወሰን ፡ ስምምነት ፡ አልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ የተወሰነ ፡ ይሆናል ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፪ ። ቅጣት ፡ (ኪሣራ) ።**

(፩) መልሶ ፡ በመግዛት ፡ ውል ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፤ ገዢው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሊሸጠው ፡ አይችልም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ሻጩ ፡ የሸጠውን፡ነገር ፡ መልሶ ፡ እንዲገዛ ፡ የሚፈቅደው ፡ ውል ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በተዘጋጀው ፡ የሕዝብ ፡ መገዝብ ፡ ላይ ፡ በገዢው ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ የተባለው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለመሸጥ ፡ አለመቻል ፡ ለሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፫ ። (ሀ) የሻጩ ፡ ግዴታ ።**

(፩) የሸጠውን ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሻጭ ፡ የተቀበለውን ፡ ዋጋ ፡ ለባለውሉ ፡ መመለስና ፡ ተዋዋዩ ፡ ስለ ፡ ሽያጩ ፡ ውል ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ገዢው ፡ ለገዛው ፡ ነገር ፡ ያደረገው ፡ ወጪ ፡ እንዳለም ፤ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ያላገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚፈጸሙ ፡ ይሆናሉ ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፯ ።

## ዕቃውን ፡ ከመላክ ፡ ግዴታ ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ ሺያጭ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፬ ። ዕቃውን ፡ የማመላለስ ፡ ጥንቃቄ ።**

ውሉ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ ሻጩ ፡ እንዲልክ ፡ የሚያስገድደው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ በሺያጩ ፡ ውል ፡ እስከ ፡ ተመለከተው ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ እንዲደርስ ፡ ሻጩ ፡ በተለመዱት ፡ ዘዴዎች ፡ ለመላክ ፡ አስፈላጊዎችን ፡ የማመላለስ ፡ ውሎች ፡ ከዕቃ ፡ ጫኙ ፡ ጋራ ፡ መዋዋል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፺፭ ። ማስረከብ ፤ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የሽያጩ ፡ ውል ፡ የዕቃውን ፡ ማጓጓዝ ፡ ግዴታ ፡ የሚጨምር ፡ ሲሆን ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የዕቃው ፡ ማስረከብ ፡ ጕዳይ ፡ የሚፈጸመው ፡ ዕቃውን ፡ ለዕቃ ፡ አመላላሹ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

(፪) ይህን ፡ የዕቃ ፡ ማመላስ ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውነው ፡ ሻጩ ፡ በራሱ ፡ የማመላለሻ ፡ ዘዴዎች ፡ ወይም ፡ በሻጩ ፡ ስም ፡ በሚሠሩና ፡ እሱ ፡ በቀጠራቸው ፡ ዕቃ ፡ አመላለሾች ፡ አማካይነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የዕቃው ፡ ማስረከብ ፡ ሥራ ፡ የሚፈጸመው ፡ በገዢው ፡ ስም ፡ የተደረገ ፡ የዕቃ ፡ ማመላለስ ፡ ውል ፡ ተሠርቶ ፡ ለዕቃ ፡ አመላላሹ ፡ ዕቃው ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፫) የዕቃው ፡ ማጓጓዝ ፡ ሥራ ፡ በብዙ ፡ ዕቃ ፡ አመላላሾችና ፡ በተከታታይ ፡ ሁኔታ ፡ የሚፈጸም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የሽያጩም ፡ ውል ፡ ሻጩ ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ማጓጓዝ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ውል ፡ በማድረግ ፡ ጠቅላላውን ፡ የዕቃ ፡

መጫን ፡ ውል ፡ ራሱ ፡ እንዲፈጽም ፡ የሚያስገድደው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዕቃው ፡ ማስረከብ ፡ ጉዳይ ፡ የሚፈጸመው ፡ ዕቃውን ፡ ለመጀመሪያው ፡ ዕቃ ፡ አመላላሽ ፡ በመስጠት ፡ (በማስረከብ) ፡ ነው ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፩። (፪) ውልን ፡ ለመፈጸም ፡ የተላከ ፡ መሆኑ ፡ ያልተገለጸበት ፡ ዕቃ ።

አድራሻ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ለጫኙ ፡ የተሰጠው ፡ ዕቃ ፡ የተላከው ፡ ውልን ፡ ለመፈጸም ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ነገር ፡ ያልተደረገበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ ለገዢው ፡ ዕቃው ፡ መላኩን ፡ ማስታወቂያ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ የዕቃውን ፡ ዝርዝር ፡ የሚያስታውቅ ፡ ወረቀት ፡ ካላከለት ፡ በቀር ፡ የማስረከቡ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ አይቈጠርም ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፪። በውሃ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ማጓጓዝ ።

(፩) ከዚሀ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዕቃውን ፡ እንዲጭን ፡ የሚሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ጫኝነቱ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ የማመላለስ ፡ ሥራ ፡ ለሚሠራ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማስረከቡ ፡ ሥራ ፡ የሚፈጸመው ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ አኳኋን ፡ ዕቃውን ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ አጠገብ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

(፪) ሻጩ ፡ ለገዢው ፡ ዕቃው ፡ በመርከብ ፡ የተሳፈረበትን ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፫። ሻጩ ፡ ዕቃውን ፡ ለመያዝ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ዕቃው ፡ የሚጫንበት ፡ ውል ፡ ሻጩ ፡ ዕቃው ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ሊያዝበት ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሻጩ ፡ ዋጋው ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ ዕቃ ፡ መላኩን ፡ ለማዘግየት ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ውላቸው ፡ ዕቃውን ፡ ሻጩ ፡ ለገዢው ፡ የሚያስረክበው ፡ በተላከበት ፡ ስፍራ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ የሚከፈለው ፡ ዕቃውን ፡ ካስረከበ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ሻጩ ፡ ዕቃውን ፡ መያዝና ፡ ማቈየት ፡ አይችልም ።

(፫) ሻጩ ፡ ዕቃው ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ የሚያዝበት ፡ በመሆኑ ፡ ዕቃውን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃው ፡ በተላከበት ፡ ስፍራ ፡ ዋጋው ፡ ሳይከፈለው ፡ ለገዢው ፡ እንዳይሰጥ ፡ መቃወም ፡ ይችላል ።

ቍ፡፪ሺ፫፻፶፬። ጽሑፍ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ስለሚደረግ ፡ የዋጋ ፡ አከፋፈል ።

(፩) ዕቃውን ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስችል ፡ ዕቃው ፡ የተጫነበት ፡ ማስረጃ ፡ ወረቀት ፡ (ኰኔስማ) ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ተደርጎለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁም ፡ ዕቃ ፡ ለማዘዝ ፡ ይህነኑ ፡ ጽሑፍ ፡ መያዝ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ በውሉ ፡ የተመለከቱት ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ የታወቁት ፡ ጽሑፎች ፡ ሳይሰጡ ፡ የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ መጠየቅ ፡ አይቻልም ።

(፪) ዕቃውን ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስችለው ፡ ጽሑፍ ፡ ለገዢው ፡ ከተሰጠው ፡ ዕቃውን ፡ ለመመርመር ፡ አልቻልሁም ፡ በማለት ፡ ዋጋውን ፡ አልከፍልም ፡ ለማለት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፫) ጽሑፉ ፡ ዕቃው ፡ የተጫነበት ፡ ማስረጃ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ሲሆንና ፡ ዕቃውን ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስችለው ፡ ይኸው ፡ ጽሑፍ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በዕቃው ፡ ለማዘዝ ፡ ይህንኑ ፡ ጽሑፍ ፡ መያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ጽሑፎቹን ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ፡ የውሉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺ ። ዕቃውን ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማቆም ።

(፩) ሻጩ ፡ ዕቃውን ፡ ከላከ ፡ በኋላ ፡ ገዢው ፡ መክፈል ፡ አለመቻሉን ፡ በፍርድ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ የሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ ዕቃ ፡ የተጫነበትን ፡ የደረሰኝ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ የገዛውን ፡ እንዲረከብ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ማንኛቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ በጁ ፡ ቢገኝም ፡ ለገዢው ፡ ዕቃው ፡ እንዳይሰጠው ፡ ሲል ፡ ሻጩ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) ሻጩ ፡ ዕቃው ፡ የተጫነበት ፡ የማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ሰነድ ፡ በደንብ ፡ ይዞ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ አምጪ ፡ ዕቃውን ፡ እንዳይረከብ ፡ ለመቃወም ፡ አይችልም ።

(፫) በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ዕቃው ፡ የተጫነበትን ፡ የማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ሰነዱ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ያሉበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ወይም ፡ የደረሰኙ ፡ ወይም ፡ የሰነዱ ፡ አምጪ ፡ ያመጣውን ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ሰነድ ፡ ለማግኘት ፡ ዐውቆ ፡ ሻጩን ፡ ለመጉዳት ፡ ሲል ፡ ያደረገው ፡ መሆኑን ፡ ሻጩ ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ዕቃው ፡ እንዳይሰጥ ፡ የመቃወም ፡ መብት ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፩ ። የተገዛውን ፡ ነገር ፡ የመረከብ ፡ ግዴታ ።

(፩) የተሸጠው ፡ ነገር ፡ ለገዢው ፡ ተልኮለት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በመረከቢያው ፡ ቦታ ፡ ዝግጁ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝለት ፡ ገዢው ፡ ዕቃውን ፡ ለመቀበል ፤ የማይፈቅድ ፡ ሲሆን ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍልና ፡ ያለ ፡ ችግርም ፡ ሌላ ፡ ወጪ ፡ ሳያደርግ ፡ ለመቀበል ፡ ከቻለ ፡ የተላከውን ፡ ነገር ፡ በሻጩ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

(፪) ሻጩ ፡ በሸጠው ፡ ነገር ፡ መድረሻ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ሆኖ ፡ የተላከውን ፡ ነገር ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀበልለት ፡ የተደረገ ፡ ሰው ፡ ሲኖር ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ መሥመር ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፺፪ ። በነገሩ ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ ጉድለት ፡ መታየት ።

(፩) የተሸጠው ፡ ነገር ፡ በሚላክበት ፡ ጊዜ ፤ ገዢው ፡ በተባለው ፡ ነገር ፡ መድረሻ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የተላከለትን ፡ ነገር ፡ መመርመር ፡ አለበት ።

(፪) ገገርው ፡ የገዛውን ፡ ዕቃ ፡ መልሶ ፡ የላከው ፡ ከጭነቱ ፡ ሳይራገፍ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነና ፡ ሻጩም ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ ተመልሶ ፡ መላክ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተሸጠው ፡ ዕቃ ፡ ምርመራ ፡ የሚደረገው ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ መድረሻ ፡ ቦታው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፯ ።

## በሐራጅ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሽያጭ ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፫ ። የውሉ ፡ አደራረግ ።

(፩) በሐራጅ ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ፡ ተፈጸመ ፡ የሚባለው ፡ ሻጩ ፡ ወይም ፡ ለሐራጁ ፡ አሻሻጭ ፡ የተመረጠው ፡ ሰው ፡ ዕቃውን ፡ ለገዢው ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ሻጩ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ አሳቡን ፡ ካልገለጸ ፡ በተቀር ፡ ሐራጁን ፡ የሚያካሂደው ፡ ዋጋ ፡ ላበለጠ ፡ ለመሸጥ ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ይቈጠራል ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፬ ። በሐራጅ ፡ ገዥ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ግዴታ ።

(፩) በሐራጅ ፡ ላይ ፡ እገዛለሁ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ለሽያጩ ፡ ሁኔታ ፡ በተመለከቱት ፡ ቃሎች ፡ መሠረት ፡ በሚያደርገው ፡ የዋጋ ፡ አቀራረብ ፡ ይገደዳል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቀረበው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ዋጋ ፡ ካልተነገረ ፡ ወይም ፡ ያቀረበውን ፡ ዋጋ ፡ ከተለመደው ፡ ከሐራጅ ፡ ድምፅ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ካልተቀበሉት ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፭ ። እጅ ፡ በጅ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) በሽያጩ ፡ ስምምነት ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በሐራጅ ፡ ገዢው ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ ዋጋውን ፡ ለመክፈል ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) ሻጩ ፡ ገንዘቡ ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ ወይም ፡ በሽያጩ ፡ ስምምነት ፡ እንደ ፡ ተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ያልተከፈለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፮ ። ሻጩ ፡ ዋቢ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ሻጩ ፡ በተለመደው ፡ የሽያጭ ፡ ስምምነት ፡ ለሚሸጠው ፡ ነገር ፡ ዋቢ ፡ በመሆን ፡ እንደሚገደድ ፡ ሁሉ ፡ በአደባባይና ፡ በፈቃድ ፡ ለሚደረገው ፡ የሐራጅ ፡ ስምምነት ፡ ዋቢ ፡ ነው ።

(፪) እርሱ ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሻጩ ፡ በግድ ፡ ለሚደረግ ፡ ሐራጅ ፡ ዋቢ ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፪ ። በሐራጅ ፡ ይሸጥልኛ ፡ ባዩ ፡ ዋቢ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ምክንያት ፡ ሐራጅ ፡ ሲባል ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢው ፡ በሐራጅ ፡ ስለሚሸጠው ፡ ነገር ፡ ለሰጠው ፡ ዝርዝር ፡ ዋቢ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ነገር ፡ ለሥራው ፡ አታላይነትም ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የመሸጥ ፡ ውል ፡ መሰልነት ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የለውጥ ፡ ውል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፫ ። ከሽያጭ ፡ ውል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ።

(፩) እያንዳንዱ ፡ ለዋጭ ፡ ለመለዋወጥ ፡ የተነገሩትን ፡ ነገሮች ፡ ስለሚመለከት ፡ ጉዳይ ፤ የአንድ ፡ ሻጭ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ አሉት ።

(፪) በለውጡ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ለዋጭ ፡ ተጨማሪውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚነካው ፡ ጉዳይ ፡ ገዥ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሚገደድበት ፡ ግዴታ ፡ ይገደዳል ።

(፫) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ለውጥ ፡ ውል ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ ሁለቱ ፡ የለውጥ ፡ ተዋዋዮች ፡ እኩል ፡ በኩል ፡ ይችላሉ ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፬ ። ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ ወደ ፡ ተሰጡት ፡ ደንቦች ፡ መምራት ።

የሽያጩን ፡ ስምምነት ፡ ውል ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ ለውጥ ፡ ውል ፡ ለቀረበውም ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

### የባለሀብትነትን ፡ መብት ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎችን ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፭ ። ሪምን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የሪም ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በዋጋ ፡ ባስተላለፈ ፡ ጊዜ ፡ የሽያጭን ፡ ውል ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የዕቃውን ፡ ሀብትነት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ ሻጩ ፡ ግዴታ ፡ እንዳለበት ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሪም ፡ ሰጪው ፡ ሪሙን ፡ የማስተላለፍ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፮ ። ግዙፍነት ፡ የሌላቸውን ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፤ ግዙፍነት ፡ የሌላቸውን ፡ መብቶች ፡ በዋጋ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ሲሆን ፡ ልዩ ፡ የሆኑት ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የሽያጭ ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ስለ ፡ ገንዘብ ፡ መብት ፡ ማስተላለፍ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ ተገልጸው ፡ ይገኛሉ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።
## ስለ ፡ ኪራይ ፡ ሽያጭ ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፪ ። ሽያጭን ፡ ስለ፡መምሰሉ ።

ተዋዋዮቹ ፡ የሚያደርጉት ፡ ውል ፡ የዕቃ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ነው ። በየጊዜውም ፡ የተወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ተከራዩ ፡ ለተከራዩ ፡ የዕቃው ፡ ባለ ሀብት ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ የተዋዋሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ የተወሰኑት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፫ ። ሊደርሱ ፡የሚችሉ፡አደጋዎች ።

የተከራየው ፡ ነገር ፡ ከተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ አደጋ ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ የሚታሰብ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፬ ። ውልን ፡ ስላለመቀጠል፡የሚደረግ፡ማስታወቅ ።

ተከራይ ፡ የተከራየውን ፡ ነገር ፡ ለአከራዩ ፡ በመመለስ ፤ በማንኛቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፭ ። የውል ፡መፍረስ ።

(፩) ውሉ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፤ አከራዩ ፡ በኪራይ ፡ የተቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለተከራዩ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ አከራዩ ፡ የሚገባውን ፡ ኪራይና ፡ ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ነገር፡ በመገልገል ፡ ስለ ፡ ጐዳበት ፡ ኪሣራን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በተከራዩ ፡ ላይ ፡ ይበልጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪን ፡ የሚያስከትል ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፬ ።
## የዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ ውል ።

### ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፮።ትርጓሜ።

የዕቃዎች ፡ ማቅረብ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ለሌላው ፡ ተዋዋይ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ በየጊዜው ፡ ወይም ፡ ባለማቋረጥ ፡ በዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ ውለታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፯ ። የውሉ ፡ ዓላማ ።

(፩) የሚቀርበው ፡ ዕቃ ፡ ልክ ፡ ያልተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ አቅራቢው ፡ ውሉ ፡ የተደረገበትን ፡ ጊዜ ፡ በማመዛዘን ፡ ለተዋዋዩ ፡ ደንበኛ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘውን ፡ ያህል ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳል ።

(፪) ተዋዋዮቹ ፡ የሚቀርበውን ፡ ዕቃ ፡ በጠቅላላው ፡ ወይም ፡ በየአንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀርበውን ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ ያነሰውን ፡ ወሰን ፡ ብቻ ፡ ቈርጠው ፡ የተዋዋሉ ፡ ሲሆኑ ፤ የአቅራቢው ፡ ተዋዋይ ፡ ሊቀበለው ፡ የሚገባውን ፡ ልክ ፤ በነዚህ ፡ በተሰጡት ፡ ወሰኖች ፡ ውስጥ ፡ ለመወሰን ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ሊቀርብ ፡ የሚገባው ፡ ዕቃ ፡ ልክ ፡ ለተዋዋዩ ፡ አስፈላጊነት ፡ እንደሚበቃ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሰጥ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፤ የቀረበው ፡ ልክ ፡ አነስተኛ ፡ ተብሎ ፡ ከተወሰነው ፡ ልክ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ እንኳን ፡ ተቀባዩ ፡ አስፈላጊውን ፡ በሙሉ ፡ ለመውሰድ ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፰ ። ዋጋ ።

የሚቀርቡት ፡ ዕቃዎች ፡ በየተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የሚቀርቡ ፡ ሲሆኑ ፤ በውሉ ፡ የተነገረ ፡ የውለታ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ የነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ የየአንዳንዱ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፲፱ ። የዋጋው ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ።

(፩) ዕቃዎቹ ፡ በየጊዜው ፡ የሚቀርቡ ፡ ሲሆኑ ፤ ዋጋቸው ፡ በየቀረቡበት ፡ ጊዜ ፡ ተከፋይ ፡ ነው ።

(፪) ባለማቋረጥ ፡ ሊቀርቡ ፡ የሚገባቸው ፡ ሲሆኑ ፤ ዋጋው ፡ በልማድ ፡ በሚወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ይከፈላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳ ። የጊዜው ፡ ወሰን ።

(፩) ለሚቀርቡት ፡ ዕቃዎች ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲኖር ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

(፪) በሚቀርቡት ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሆነው ፡ ስለሚቀርቡት ፡ ዕቃዎች ፡ ጊዜ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ጊዜውን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፩ ። ውልን ፡ አለመፈጸም ።

(፩) ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ስለ ፡ ተነገረው ፡ የዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ የገባባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አለመፈጸሙም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ያሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይኸውም ፡ ነገር ፡ ለወደፊት ፡ በሚፈጸሙ ፡ ግዴታዎች ፡ የደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ውስጥ ፡ እምነት ፡ የሚያጠፋ ፡ ጠባይ ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፤ ውሉ ፡ ለመፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) ዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ለተዋዋለው ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፤ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ወይም ፡ አፈጻጸሙን ፡ ማቆም ፡ አይችልም ።

(፫) ማንኛቸውም ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የተነገረው ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፪ ። የምርጫ ፡ ስምምነት ፡ (፩) የሚቆይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ የተለየ ፡ ዐይነት ፡ ያላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ባስፈለጉት ፡ ጊዜ ፡ በምርጫ ፡ ከአንድ ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢ ፡ ብቻ ፡ ለመውሰድ ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ሊጸና ፡ አይችልም ።

(፪) ይበልጥ ፡ እንዲቈይ ፡ ተደርጎም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ሊጸና ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፫ ። (፪) ተፈጻሚነት ።

(፩) እንደዚሁ ፡ ባለ ፡ ቃል ፡ ውል ፡ የሚገባ ፡ ተዋዋይ ፡ ሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያቀረቡለትን ፡ ውለታዎች ፡ ለዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ለምርጫ ፡ ባለው ፡ መብት ፡ እጠቀማለሁ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ካላስታወቀ ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፬ ። ከተመረጠው ፡ አቅራቢ ፡ ብቻ ፡ በደንበኛው ፡ ያለበት ፡ የመቀበል ፡ ግዴታ ።

(፩) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንዳንድ ፡ የዕቃ ፡ ዐይነት ፡ ከአንድ ፡ የታወቀ ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢ ፡ ብቻ ፡ ለመውሰድ ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተባለው ፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ የተነገረውን ፡ የዕቃ ፡ ዐይነት ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለመውሰድ ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ የተነገሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ለማውጣት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፭ ። ለተመረጠው ፡ ደንበኛ ፡ ብቻ ፡ ለማቅረብ ፤ በዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ።

(፩) ዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ለአንድ ፡ የታወቀ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ለማቅረብ ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ በውሉ ፡ በተነገረው ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥና ፡ ውሉ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፤ በውሉ ፡ የተነገሩትን ፡ የዕቃ ፡ ዐይነቶች ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በጅ ፡ አዙር ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጥቅም ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

(፪) ተዋዋዩ ፡ የግል ፡ ሆነው ፡ የተጠበቁለትን ፡ ነገሮች ፡ በመሸጥ ፡ በተወሰነለት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ ለማስፋፋት ፡ ተዋውሎ ፡ ሳለ ፤ ይህን ፡ ግዴታ ፡ ያልፈ

ጾመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በውሉ ፡ የተነገረውን ፡ አነስተውኛን ፡ መጠን ፡ ሽጦ ፡ ቢገኝ ፡ እንኳን ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፮ ። ውሉን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

የዕቃው ፡ አቀራረብ ፡ የተወሰነ ፡ የውል ፡ ጊዜ ፤ በውሉ ፡ አልተጻፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አስቀድሞ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ በውሉ ፡ የተጻፈውን ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ፡ በመስጠት ፤ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ የተጻፈ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ ተዋዋዮቹ ፡ እየአንዳንዳቸው ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ስጦታ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፯ ። ትርጓሜ ።**

ስጦታ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ማለት ፡ ሰጪው ፡ ተቀባይ ፡ ተብሎ ፡ ለሚጠራው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ችሮታ ፡ በማድረግ ፡ አሳብ ፡ ከንብረቶቹ ፡ አንዱን ፡ የሚለቅበት ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፰ ። በሞት ፡ ምክንያት ፡ የሚደረጉ ፡ ስጦታዎች ።**

ሰጪው ፡ ሲሞት ፡ ይፈጸማሉ ፡ ተብለው ፡ በተወሰኑት ፡ ስጦታዎች ፤ ላይ ፡ ስለ ፡ ኑዛዜ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፱ ። ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ርዳታ ፡ የሚደረጉ ፡ ስጦታዎች ።**

(፩) በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ በሚደረጉት ፡ ስጦታዎች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሌሎቹ ፡ ስጦታዎች ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እነዚህ፡ ስጦታዎች ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ በዋጋ ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ ሆነው ፡ አይቈጠሩም ።

(፫) ስለዚህ ፡ ስጦታዎች ፡ በተለይ ፡ የተነገሩት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴ ። ያለዋጋ ፡ የሚሆን ፡ አገልግሎት ።**

ያለዋጋ ፡ የሚደረግ ፡ የአገልግሎት ፡ ሥራ ፤ ወይም ፡ የራሱን ፡ ዕቃ ፡ ያለዋጋ ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ዝግጁ ፡ ማድረግ ፡ ስጦታ ፡ አይባልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፩ ። አለመቀበል ።**

እንደዚሁም ፤ ወራሽነትን ፡ አልፈልግም ፡ ብሎ ፡ መተው ፡ ወይም ፡ በኑዛዜ ፡ የተደረገለትን ፡ ስጦታ ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መብትን ፡ የሚ

ያስገኘውን ፡ ወይም ፡ መብትን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ለመቅረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ መቅረት ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፪ ። የተፈጥሮ ፡ ግዴታ ።

መንፈሳዊ ፡ ተግባርን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚደረገው ፡ የገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ሥራ ፡ ስጦታ ፡ አይባልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፫ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሚደረግ ፡ ስጦታ ።

እንደዚሁም ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ለሰጪው ፡ ወይም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ስላደረገው ፡ አገልግሎት ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ ስጦታ ፡ አይባልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፬ ። ስጦታ ፡ ማድረግ ፡ የሰጭ ፡ የራሱ ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ስጦታ ፡ የሰጭ ፡ የራሱ ፡ የተለየ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

(፪) ስጦታ ፡ የሚደረገው ፡ በወኪሉ ፡ ሲሆን ፡ የሚሰጡት ፡ ንብረቶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆኑና ፡ ለማን ፡ እንደሚሰጡ ፡ ገልጾ ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፭ ። ስለ ፡ ስጦታ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ መስጠት ።

(፩) ስጦታ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ መስጠት ፡ አንዳች ፡ ግዴታ ፡ አያስከትልም ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አለመፈጸም ፤ ቃል ፡ የተሰጠው ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡ በተሰጠው ፡ ቃል ፡ ምክንያት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያወጣው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስ ፡ ብቻ ፡ ያስገድዳል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፮ ። ስጦታን ፡ ተቀባዩ ፡ እቀበላለሁ ፡ ማለት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የስጦታ ፡ ውል ፡ ፍጹም ፡ የሚሆነው ፤ ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ለእርሱ ፡ የተደረገውን ፡ ልግስና ፡ እቀበላለሁ ፡ ብሎ ፡ አሳቡን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ሰጪው ፡ ከሞተ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ከአጣ ፡ በኋላ ፡ ስጦታውን ፡ እቀበላለሁ ፡ የማለት ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፫) ስጦታን ፡ የስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴ ፡ ስለሱ ፡ ሆኖ ፡ ሊቀበል ፡ ይችላል ። የስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ወራሾች ፡ ግን ፡ ስለሱ ፡ ሆነው ፡ መቀበል ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፴፯ ። የሰጪው ፡ አእምሮ ፡ ትክክል ፡ አለመሆን ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የሰጪው ፡ አእምሮው ፡ ትክክል ፡ አልነበረም ፡ የማለት ፡ ምክንያት ፡ ስጦታን ፡ አያፈርስም ፤ ስጦታው ፤ ፈራሽ ፡ የሚሆነው ፤

BACK



(ሀ) ሰጪው ፡ ስጦታውን ፡ ባደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ተከልክሎ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ እንደ ፤ ሆነና ፡ ስጦታው ፡ በሞግዚቱ ፡ በኩል ፡ በደንብ ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ሰጪው ፡ በፍርድ ፡ እንዲከለከል ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነና ፡ ዳኞች ፡ ለቀረበላቸው ፡ ጥያቄ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ከመቻላ ቸው ፡ በፊት ፡ ሰጪው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የሰጪው ፡ አእምሮ ፡ ትክክል ፡ አለመሆን ፡ ስለ ፡ ስጦታው ፡ በተደረገው፡ የውል ፡ አጻጻፍ ፡ የሚታወቅ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቊ፡፪ሺ፬፻፵፰ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ።

(፩) ስጦታው ፤ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ሕገ፡ ወጥ፡ ከሆነ ፡ መንፈስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ምክን ያት ፡ ያለበት ፡ ስጦታ ፡ ከዚያው ፡ ከስጦታው ፡ አደራረግ ፡ ወይም ፡ ከሰጪው ፡ የጽሑፍ ፡ አስረጅ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፤ ስጦታው ፡ ፍርስ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ አይቻልም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፵፱ ። የመንፈስ ፡ መጫን ። (፩) በውርስ ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ።

(፩) ዳኞች ፤ የኑዛዜን ፡ ቃል ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅዳ ቸው ፡ ሁኔታ ፤ ስጦታን ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ የሰጪው ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ (ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት) ፡ ቢሆንም ፡ ስጦ ታው ፡ እንዲቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዲሻር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ለአስተዳዳሪ ፡ (ላሳዳጊ) ፡ ወይም ፡ ለሞግዚት ፡ የተደረገ ፡ ስጦታ ፡ ሲሆን ፡ የሰጪውን ፡ ዕድሜ ፡ መገመት ፡ አያስፈልግም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፬፻፶ ። (፪) ከርክር ፡ ያለበት ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ስጦታ ።

ስጦታው ፡ የተደረገው ፡ የሰጪውን ፡ ወይም ፡ ከባልና ፡ ሚስት ፡ ያንደኛውን ፡ ወይም ፡ የዘመዱን ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ ክርክር ፡ በተነሣበት ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሆኖ፡ ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የተነሣው ፡ ክርክር ፡ እንዲወገድ ፡ የመንፈስ ፡ መጫን ፡ መብቱን ፡ (የሥልጣን ፡ መብ ቱን) ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ እንዲያውል ፡ ወይም ፡ እንዲረዳው ፡ ለማድረግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተደረገው ፡ ስጦታ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቊ፡፪ሺ፬፻፶፩ ። (፫) ስጦታን ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።

(፩) ስጦታ ፡ እንዲቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዲሻር ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ስጦታው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ለዳኞች ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፪) ሟች ፡ ያደረገውን ፡ ኑዛዜ ፡ በመጫን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ኑዛዜው ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ሕግ ፡ የሚፈቅድላቸው ፡ ሰዎች ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ሰጭ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በቁም ፡ ያደረገው ፡ ስጦታ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፪ ። ስሕተት ፡ ወይም ፡ ተንኰል ።

(፩) በመሳሳት ፡ የተደረገ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ እንዲሻር ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሰጭ ፡ ወራሾች ፡ በሰጭ ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ስጦታው ፡ እንዲሻር ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችሉም ።

(፪) የሰጪው ፡ ወራሾች ፡ በተደረገው ፡ ስጦታ ፡ ተንኰል ፡ አለበት ፡ በማለት ፡ ስጦታው ፡ እንዲሻር ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ።

(፫) ስጦታው ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ ተንኰል ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሰጪው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ስጦታው ፡ እንዲሻር ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ወራሾቹ ፡ ክሱን ፡ ለመቀጠል ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፫ ። የስጦታው ፡ ሥርዐት ፡ ፎርም ፡ (፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።

በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብትን ፡ የሚሰጥ ፡ ስጦታ ፡ በግልጽ ፡ በሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ ካልተደረገ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፬ ። (፪) የሚንቀሳቀሱ ፡ ግዙፎች ፡ ንብረቶችና ፡ ለአምጪው ፡ የሚከፈሉ ፡ ሰነዶች ።

(፩) ግዙፎች ፡ የሆኑ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶችና ፡ ለአምጪው ፡ የሚከፈሉ ፡ ሰነዶች ፡ እጅ ፡ ብጅ ፡ በሚደረግ ፡ ማስተላለፍ ፡ ብቻ ፡ ሊሰጡ ፡ ይቻላል ።

(፪) ወይም ፡ ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስጦታ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ሥርዐት ፡ ሞልቶ ፡ ሊሰጡ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፭ ። (፫) ሌሎች ፡ መብቶችና ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ።

(፩) ሌሎች ፡ መብቶችን ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶችን ፡ በዋጋ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ በታዘዘው ፡ ሥርዐት ፡ ፎርም ፡ መሠረት ፡ ሊሰጡ ፡ ይቻላል ።

(፪) ተቀባዩ ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ በመተው ፡ ስጦታ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) ሰጭ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጥ ፡ የተዋዋለበትን ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ለስጦታ ፡ ተቀባይ ፡ በመስጠት ፡ ስጦታ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፮ ። የተሰወረ ፡ ስጦታ ።

(፩) ስጦታን ፡ ዋጋ ፡ የተቀበሉበት ፡ ዐይነት ፡ አድርጎ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

(፪) ስለ ፡ ስጦታዎች ፡ የተወሰኑት ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦች ፡ በስውር ፡ በተደረጉ ፡ ስጦታዎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፯ ። ማስረጃ ።**

(፩) ስጦታ ፡ አለ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ስጦታ ፡ መኖሩን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

(፪) ግዙፍ ፡ የሆኑ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶችን ፡ ወይም ፡ ለአምጪው ፡ የሚሰጡ ፡ ሰነዶችን ፡ ይዞ ፡ መገኘት ፡ የነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ይዞታ ፡ የሚያሻማ ፡ ምክንያት ፡ የሌለበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይዞታው ፡ ስጦታ ፡ መኖሩን ፡ አያረጋግጥም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፰ ። በውለታ ፡ ቢስነት ፡ ምክንያት ፡ ስጦታን ፡ ስለ ፡ መሻር ።**

**፩ ፡ ሰጪው ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ።**

(፩) ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ሚችን ፡ ለመውረስ ፡ የማይገባ ፡ የሚያደርግ ፡ ወንጀል ፡ በሰጭ ፡ ላይ ፡ በመሥራት ፡ ውለታ ፡ ቢስ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ስጦታው ፡ ሊሻር ፡ ይቻላል ።

(፪) ተቀባዩ ፡ ያደረገውን ፡ ውለታ ፡ ቢስነት ፡ ሰጪው ፡ ምሕረት ፡ አድርጎለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታውን ፡ ለመሻር ፡ አይቻልም ።

(፫) ሰጪው ፡ ያደረገውን ፡ ስጦታ ፡ ለመሻር ፤ የሚችልበትን ፡ ምክንያት ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፤ ያደረገለትን ፡ ስጦታ ፡ የመሻር ፡ አሳቡን ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለተቀባዩ ፡ ያላስታወቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ አስረጅ ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ ይቅርታ ፡ እንደ ፡ አደረገለት ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፱ ። የስጦታ ፡ አድራጊው ፡ ወራሾች ፡ ስለሚያቀርቡት ፡ ክስ ።**

የሰጪው ፡ ወራሾች ፤ አውራሻቸው ፡ ያደረገውን ፡ ስጦታ ፡ እንዲሻር ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉት ፤

(ሀ) ሰጪው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ለተቀባዩ ፡ ያደረገለትን ፡ ስጦታ ፡ የመሻር ፡ አሳቡን ፡ በማያሻማ ፡ አነጋገር ፡ አስታውቆት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ተቀባዩ ፡ ሰጪውን ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እንዲሞት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የውለታ ፡ ቢስነት ፡ ሥራ ፤ ሰጪው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ተሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ሰጪው ፡ በስጦታ ፡ መሻር ፡ መብቱ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ከልክሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷ ። የልጅ ፡ መወለድ ።**

በተደረገው ፡ የስጦታ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ስጦታ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ በመወለዱ ፡ ምክንያት ፡ ስጦታውን ፡ ለመሻር ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፩ ። የሚሰጠው ፡ ነገር ።**

(፩) ስጦታ ፡ የሚደረገው ፤ ስጦታው ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ የሰጪው ፡ ገንዘብ ፡ ከሆነ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ስጦታው ፡ ገና ፡ ወደፊት ፡ የሚገኙትን ፡ ንብረቶች ፡ የሚመለከት ፡ በሚሆን
በት ፡ መጠን ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፪ ። ክርክር፡ ያለበት ፡ ሀብት ።**

ስጦታው ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት ፡ ክርክር ፡ ያለበት ፡ የሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ስጦታ ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፫ ። አላባን ፡ ለራስ፡ጠብቆ፡ ስለሚደረግ ፡ ስጦታ ።**

ሰጪው ፡ የሰጣቸውን ፡ ንብረቶች ፡ አላባውን ፡ ለራሱ ፡ የተጠበቀ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፬ ። በየጊዜው፡ስለሚደረጉ፡ስጦታዎች ።**

በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ስጦታ ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰጥ ፡ ነገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሰጪው ፡ ሲሞት ፡ ይቋረጣል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፭ ። ገደብ ፡ ወይም፡ግዴታ ።**

(፩) ስጦታው ፡ ገደብ ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል።

(፪) በኑዛዜ ፡ ለሚሰጡ ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ ገደብ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ግዴታ ፡ በውርስ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ የተሠራው ፡ ደንብ ፡ በቁም ፡ ስጦታዎችም ፡ ላይ ፡ ለተደ ረገ ፡ ገደብ ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፮ ። የማይቻል ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ፡ገደብ፡ወይም ፡ ግዴታ ።**

(፩) ሰጪው ፡ ስጦታውን ፡ ገደብ ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ አድርጎት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ገደቡ ፡ ወይም ፡ ግዴታው ፡ የማይቻል ፡ ወይም፡ ለሕግ፡ ወይም፡ ለመ ልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ገደቡ ፡ ወይም ፡ ግዴታው ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ሲሆን ፡ ስጦ ታውን ፡ ያደረገበት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ገደቡ ፡ ወይም ፡ ግዴታው ፡ ቢሆንም፡ እንኳ ፡ ስጦታው ፡ አይፈርስም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፯ ። በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ የሚደረጉ፡ስጦታዎች ።**

(፩) በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ ወደፊት ፡ ለሚጋቡ ፡ ዕጮኞች ፡ የሚደረጉ ፡ ስጦታዎች፡ ጋብቻው ፡ እስቲፈጸም ፡ ድረስ ፡ ታግዶ ፡ የሚቈይ ፡ ውለታ ፡ ያሉባቸው ፡ ስጦታዎች ፡ ሆነው ፡ ይቈያሉ ።

(፪) በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ ለዕጮኞቹ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ለሌሎቹ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ የተደረጉትም ፡ ስጦታዎች ፡ ጋብቻው ፡ እስቲፈጸም ፡ ድረስ ፡ ታግዶ ፡ የሚቈይ ፡ ውለታ ፡ ያለባቸው ፡ ስጦታዎች ፡ ሆነው ፡ ይቈያሉ ።

(፫) የጋብቻው ፡ መሰረዝ ፡ ወይም ፡ መፍረስ ፡ ውጤት ፡ ስጦታዎችን ፡ ስለሚመለከ ተው ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ስጦታዎችን፡

BACK



ስለሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡(ዝምድና)፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፰ ። ለሰጭ ፡ ቀለብ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ።</u>

(፩) በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ባይኖርም ፡ ሰጪው ፡ በድኅነት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሲገኝ ፡ ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ለሰጭ ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) ሰጭ ፡ እንደ ፡ መረጠ ፡ ቀለቡን ፤ እርሱ ፡ ስጦታ ፡ ካደረገለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ ለርሱ ፡ ቀለብ ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ፡ ከሚላቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ለሰጭ ፡ ቀለቡን ፡ የሰጡ ፡ ሰዎች ፡ የሰጡትን ፡ ቀለብ ፤ ስጦታ ፡ የተደረገለት፡ ሰው ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፱ ፡ ዕዳ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ።</u>

ስጦታ ፡ ተቀባይ ፡ የሰጪውን ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፍል ፡ ውል ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ስለ ፡ ሰጭው ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ የዕዳው ፡ ልክ ፡ ተወስኖ፡ የታወቀ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷ ። ስጦታው ፡ ለሰጭ ፡ እንዲመለስ ፡ ስለሚደረግ ፡ ውል ።</u>

(፩) ከሰጭ ፡ አስቀድሞ ፡ ስጦታ ፡ ተቀባይ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰጭ ፡ የሰጣቸው ፡ ነገሮች ፡ እንዲመለሱለት ፡ በስጦታው ፡ ውስጥ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለማግባት ፡ ይችላል ።

(፪) በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተቀባዩ ፡ ወደታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ትቶ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታዎቹ ፡ እንዲመለሱ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ አይቻልም ።

(፫) ስጦታ ፡ የተደረገው ፡ ስጦታዎቹ ፡ ለሰጭ ፡ እንዲመለሱ ፡ ውል ፡ ከማድረግ ፡ ጋራ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተሰጡት ፡ ንብረቶች ፡ እንዳይሸጡ ፡ እንዳይለወጡ ፡ የሚያደርግ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ውጤት ፡ አለው ፤ የዚህም ፡ ዐይነት ፡ ውል ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ደንብ ፡ የሚከተል ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፩ ። ምትክነት ።</u>

(፩) ተቀባይ ፡ የተሰጡትን ፡ ንብረቶች ፡ ጠብቆ ፡ አቈይቶ ፡ እሱ ፡ ሲሞት ፡ ወይም፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጸም ፡ በስጦታ፡የተቀበላቸውን ፡ ንብረቶች ፡ ለሚተኩ ፡ ለአንድ ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች፡ ማስተላለፍ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰጭ ፡ በስጦታው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ማግባትና ፡ በስጦታ ፡ ተቀባይ ፡ የሚተኩ ፡ ሰዎች ፡ እንዲቀሩ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በኑዛዜ ፡ የተነገረውን ፡ ምትክነት ፡ ስለ ሚመለከት ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተጻፉት ፡ ሥርዐቶች ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ መንገድና ፡ ግዴታዎች ፡ መሠረት ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፪ ። ግዴታ ፡ ስለ ፡ መፈጸም ።

(፩) ሰጭ ፡ በስጦታ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ውል ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ውል ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ግዴታውን ፡ እንዲያስፈጽምለት ፡ ሰጭ ፡ የመረጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሰጪው ፡ ወራሾች ፡ ይህ ፡ የማስገደድ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፫) ተቀባዩ ፡ ግዴታውን ፡ መፈጸም ፡ ያለበት ፡ ስጦታው ፡ በተደረገለት ፡ ቀን ፡ በነበረው ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፫ ። ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ድርጅት ፡ ስለሚ ደረግ ፡ ስጦታና ፡ ስለ ፡ አደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ (ፌዴዩኮሚ) ።

በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ድርጅቶችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠ ረት ፡ ሰጪው ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ድርጅት ፡ የሚደረጉ ፡ ስጦታዎችንና ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጥበቃን ፡ ለማቋቋም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፬ ። ግዴታን ፡ ባለመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ የስጦታው ፡ መሻር ።

(፩) ተቀባይ ፤ ግዴታዎቹን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ቍጥር ፡ በተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ ጥያቄ ፤ ስጦታው ፡ ሊሻር ፡ ይችላል ።

(፪) ተቀባይ ፡ ግዴታውን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታው ፡ ይሻራል ፡ ብሎ ፡ ሰጭ ፡ በስጦታው ፡ ውል ፡ በግልጽ ፡ ያላመለከተና ፡ የስጦታውም ፡ መሻር ፡ የሚያመጣውን ፡ ነገር ፡ የወሰነ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሰጪው ፡ ወራሾች ፡ ጠያ ቂነት ፡ ስጦታው ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።

(፫) የተደረገውን ፡ ስጦታ ፡ ለመሻር ፡ ይቻላል ፡ ተብሎ ፡ ፍርድን ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ የሚነገሩ ፡ ምክንያቶችና ፡ የስጦታው ፡ መሻር ፡ ውጤቶች ፤ ውሎችን ፡ ስለ መሻርና ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚ ለው ፡ አንቀጽ ፡ በተነገሩት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፭ ። መድን ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) ሰጭ ፡ ያደረገውን ፡ ስጦታ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ሲመጣ ፡ መድን ፡ ለመሆን ፡ በግ ልጽ ፡ ውል ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የተሰጠው ፡ ነገር ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ የመጣው ፡ በሰጭ ፡ ተንኰል ፡ ወይም ፡ በሰጭ ፡ የግል ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስጦታ ፡ ላደረጉለት ፡ ሰው ፡ መድን ፡ ይሆናል ።

BACK



(፪) ስጦታውን ፡ አስለቃቂ ፡ ሲመጣ ፡ የስጭ ፡ መድንነት ፡ ነገር ፡ በሺያጭ ፡ ጊዜ፡ ስለ ፡ መድን ፡ በተሠራው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የተደረገለትን ፡ ስጦታ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ያስለቀቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተሰጠው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ አላባ ፡ አግኝቶ ፡ በአላባው ፡ የተቻቻለ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በስጦታው ፡ ምክንያት ፡ ያደረገው ፡ ወጪ፡ በነዚህ ፡ ደንቦች ፡ እንዲመለስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፮ ። ስለ ፡ ጕድለት፡ የሚሰጥ፡የመድንነት፡ቃል ።</u>

(፩) ሰጭ ፡ በተሰጠው ፡ ነገር ፡ ጕድለት ፡ አላፊ ፡ መድን ፡ ሊሆን ፡ በግልጽ ፡ ቃል፡ ካልገባ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ ካልሠራ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ጕድለት ፡ አላፊ ፡ መድን ፡ አይሆንም ።

(፪) እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የጕድለቱ ፡ መድንነት ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ውል፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተነገረው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። (ከቍ. ፪ሺ፪፻፺፮ ፡ እስከ ፡ ፪ሺ፫፻፱ ) ።

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ በስጦታ ፡ የወሰደው ፡ ሀብት ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ያደረሰበትን ፡ ጉዳት ፡ ከዚሁ፡ሀብት ፡ላይ ፡ ያገኘው ፡ አበል ፡ ያልተካለት ፡ ሲሆን ፡ በነዚሁ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በስጦታ ፡ የወሰደው ፡ ነገር ፡ ያደረሰበት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፯ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂ፡ስለሚያቀርበው፡ክስ ።</u>

(፩) ከሰጪው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መብታቸውን ፡ ለመጉዳት ፡ ሰጪው ፡ በተንኰል ፡ ያደረገውን ፡ ስጦታ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህን ፡ ስለሚመለከተው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ ይፈጸማሉ ።

<u>ቍ፡ ፪ሺ፬፻፷፰ ። የመጦሪያ ፡ መብት ፡ ስላላቸው፡ሰዎች ፡ (፩) መሠረቱ ።</u>

ከሰጪው ፡ ውርስ ፡ ላይ ፡ የመጦሪያ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ የውርስ ፡ ሀብት ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሰጪው ፡ ከመሞቱ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የሚቹን ፡ ስጦታ ፡ ከተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የመጦሪያ ፡ መብታቸውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፱ ፡ (፪) የሚገመተው፡ዋጋ ።</u>

(፩) ስጦታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የሚገደደው ፡ በተቀበላቸው ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ግምቱም ፡ የሚደረገው ፡ ስጦታ ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

(፫) አስፈላጊ ፡ ሲሆንም ፡ በስጦታ ፡ ተቀባዩ ፡ ላይ ፡ የተጣሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ዋጋ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፸ ። ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተደረጉ ፡ ስጦታዎች ።**

(፩) ሟቹ ፡ ከመሞቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ዓመቶች ፡ ውስጥ ፤ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስጦታዎች ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስጦታ ፡ የተደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ እየአንዳንዱ ፤ በየተሰጧቸው ፡ ንብረቶች ፡ መጠን ፤ የጡረታ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ማውጣት ፡ አለባቸው ።

(፪) በልዩ ፡ ልዩ ፡ የተደረጉት ፡ ስጦታዎች ፡ እየአንዳንዳቸው ፡ የተሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገባም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።
## የሚያልቅ ፡ ነገር ፡ ብድር ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፸፩ ። (፩) ፡ ትርጓሜ ።**

የሚያልቅ ፡ ነገር ፡ ብድር ፡ ማለት ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ አበዳሪው ፤ ሌላውን ፡ ተበዳሪ ፡ ሰው ፡ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ በዐይነቱ ፡ ለመመለስ ፡ ተገዳጅ ፡ በማድረግ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በማገልገል ፡ የሚያልቅ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለተበዳሪው ፡ ለመስጠትና ፡ ሀብትነቱን ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚገደድበት ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፸፪ ። (፪) የብድር ፡ ማስረጃ ።**

(፩) በብድር ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ $500 የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ የብድሩን ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በተደረገ ፡ የእምነት ቃል ፡ ወይም ፡ መሐላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማስረዳት ፡ አይቻልም ።

(፪) ለብድር ፡ ውል ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ከ$500 የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ የመከፈል ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ይፈጸማል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፸፫ ። (፫) በባለባንኮችና ፡ በደንበኞቻቸው ፡ መካከል ፡ ስላሉ ፡ ግንኙነቶች ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ዋነኛው ፡ ሥራቸው ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ በሆነ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ማኅበሮችና ፡ በደንበኞቻቸው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፪) በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ የብድርን ፡ ውል ፡ ወይም ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ መልሶ ፡ መክፈልን ፡ በምስክሮች ፡ ወይም ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ ማስረጃ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፸፬ ። የአበዳሪው ፡ ግዴታ ።**

(፩) በሽያጭ ፡ ውል ፡ ምዕራፍ ፡ የተነገሩት ፤ የሻጭን ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ በአበዳሪ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ብድሩ ፡ እንዲያው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአበዳሪው ፡ ግዴታዎች ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመቱ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በዚህ፡ጊዜ፤ባበደረው፡ነገር፡ላይ፡ለሚገኘው፡እርሱ፡ለሚያውቀው፡ጕድለት፡ብቻ፡ካልሆነ፡ዋቢ፡መሆን፡የለበትም።

**ቍ፡፪ሺ፬፻፸፭።ተበዳሪው፡ዕዳውን፡ለመክፈል፡ስላለመቻሉ።**

(፩) ውሉ፡ከተደረገ፡በኋላ፡ተበዳሪው፡የመክፈል፡ችሎታ፡ማጣት፡የደረሰበት፡እንደ፡ሆነ፤አበዳሪው፡በብድር፡ሊሰጠው፡ቃል፡የገባለትን፡ነገር፡ለመከልከል፡ይችላል።

(፪) ይህ፡ለመክፈል፡አለመቻሉ፡ውሉ፡ከመደረጉ፡በፊት፡ደርሶ፡እንደ፡ሆነና፡አበዳሪው፡ውሉ፡ከተደረገ፡በኋላ፡ነገሩን፡ቢያውቀውም፡እንኳን፡አልሰጥም፡የማለት፡መብት፡አለው።

**ቍ፡፪ሺ፬፻፸፮።ስለ፡ወጪና፡የዕቃው፡ጥበቃ።**

(፩) ስለ፡ወጪና፡ስለ፡ዕቃው፡አጠባበቅ፡ተዋዋዮቹ፡ያሉባቸውን፡ግዴታዎች፡የሚመለከቱት፤በሽያጭ፡ውል፡ምዕራፍ፡የተጻፉት፡ደንቦች፡በሚያልቅ፡ነገር፡ብድርም፡ላይ፡ተፈጻሚ፡ይሆናሉ።

(፪) በዚህ፡ነገር፡ባበዳሪው፡ላይ፡የሻጭ፡ግዴታዎች፡በተበዳሪው፡ላይ፡የገዢው፡ግዴታዎች፡ይፈጸማሉ።

**ቍ፡፪ሺ፬፻፸፯።ሊደርስ፡የሚችል፡አደጋ።**

(፩) ተበዳሪው፡ለተበደረው፡ነገር፡ባለሀብት፡ይሆናል።

(፪) የተበደረው፡ነገር፡የጠፋ፡ወይም፡የተበላሸ፡እንደ፡ሆነ፡ከተቀበለበት፡ጊዜ፡አንሥቶ፡በነገሩ፡የሚደርሰውን፡የጥፋት፡ወይም፡የመበላሸት፡አደጋ፡የሚችል፡እርሱ፡ይሆናል።

**ቍ፡፪ሺ፬፻፸፰።ወለድ።(፩) የሚከፈልበት፡ጊዜ።**

ተበዳሪው፡ወለድ፡እንዲከፍል፡የውል፡ቃል፡ከሌለ፡በቀር፡ላበዳሪው፡ወለድ፡መክፈል፡የለበትም።

**ቍ፡፪ሺ፬፻፸፱።(፪) የወለዱ፡ልክ።**

(፩) ተዋዋዮቹ፡በወለድ፡የሚከፈለውን፡ገንዘብ፡በዓመት፡በመቶ፡ከዐሥራ፡ሁለት፡በላይ፡እንዲሆን፡ለመዋዋል፡አይችሉም።

(፪) ብድሩ፡በወለድ፡እንዲሆን፡ውል፡ቢኖር፡በወለድ፡የሚከፈለው፡ገንዘብ፡ግን፡ከፍተኛ፡እንዲሆን፡በጽሑፍ፡የተደረገ፡ውል፡የሌለ፡እንደ፡ሆን፡ተበዳሪው፡ዘጠኝ፡በመቶ፡በዓመት፡ወለድ፡መክፈል፡ይገባዋል።

(፫) በወለድ፡የሚከፈለው፡ገንዘብ፡በመቶ፡ከአሥራ፡ሁለት፡በላይ፡በዓመት፡እንዲሆን፡በጽሑፍ፡የተደረገ፡ውል፡ቢኖር፡እንኳ፡ተበዳሪው፤በመቶ፡ዘጠኝ፡ብቻ፡በዓመት፡ወለድ፡መክፈል፡አለበት።

**ቍ፡፪ሺ፬፻፹።(፫) የመክፈል፡አስገዳጅነት።**

ተቃራኒ፡የሚሆን፡የውል፡ቃል፡ከሌለ፡በቀር፤ወለዱ፡ውሉ፡ከተደረገበት፡አንሥቶ፡በሚቈጠር፡በየዓመቱ፡መጨረሻ፡መክፈል፡አለበት።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፩ ። የወለድ ፡ ወለድ ።

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወለዱ ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ ወለድ ፡ ይወልዳል ፡ ብለው ፡ አስቀድመው ፡ ለመዋዋል ፡ አይችሉም ።

(፪) ስለ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ የወለድ ፡ ወለድ ፡ አስተሳሰብ ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፪ ። የብድር ፡ መመለሻ ፡ ጊዜ ። (፩) በውል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) ተበዳሪው ፤ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ በብዛቱና ፡ በዐይነቱ ፡ ልክ ፤ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ለመመለስ ፡ ይገደዳል ።

(፪) ብድሩ ፡ በወለድ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ለመመለስ ፡ ማሰቡን ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ላበዳሪው ፡ አስታውቆ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሊመልስለት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዘጠኝ ፡ በመቶ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ወለድ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ይፈጸማል።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፫ ። (፪) የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አለመኖር ።

(፩) ብድሩ ፡ የሚመለስበት ፡ አንዳችም ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አበዳሪው ፡ መልስልኝ ፡ ሲል ፡ ከጠየቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ ላበዳሪው ፡ ለመመለስ ፡ አሳቡን ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ካስታወቀ ፡ በኋላ ፡ ሊመልስለት ፡ ይችላል።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፬ ። ልዩ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ።

ተበዳሪው ፡ እንደ ፡ ተቻለው ፤ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ እንዳገኘ ፡ ሊመልስ ፡ ውል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞቹ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ በማመዛዘን ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ የማያልፍ ፡ የሚከፍልበትን ፡ ጊዜ ፡ ሊወስኑለት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፭ ። የሚመለሰው ፡ ነገር ፤ (፩) በኢትዮጵያ ፡ ብር ።

(፩) በብድር ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የሚታሰብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ በሚከፍልበት ፡ ቀን ፡ የሕግ ፡ መገባያያ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘውን ፡ ኖትም ፡ ሆነ ፡ ዝርዝር ፡ በተበደረው ፡ መጠን ፡ በመክፈል ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

(፪) ተበዳሪው ፡ ገንዘቡ ፡ በብድር ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ግዥ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የዋጋ ፡ መለዋወጥ ፡ ማሰብ ፡ የለበትም ።

(፫) እንዲሁም ፡ ገንዘቡ ፡ በብድር ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የተሰጠውን ፡ ትርጓሜ ፡ መለወጥ ፡ ማሰብ ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፮ ። (፪) ብድሩ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በብድር ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ የተጻፈ ፡ ሲሆን ፤ ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ በሚከፍልበት ፡ ቀን ፤ በተባለው ፡ ገንዘብ ፡

አገር፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ መገበያያ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘውን ፡ ያንኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ በተበደረው ፡ ቍጥር ፡ ልክ ፡ ኖት ፡ ዝርዝር ፡ በመስጠት ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

(፪) የሚፈቅድም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚከፍልበት ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ከተበደረው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ የሚቈጠር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በመክፈል ፡ ነፃ ፡ ይሆናል።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፯ ። (፫) የንግድ፡ዕቃዎች፡ወይም ፡ እንከብል፡ገንዘቦች ።

(፩) በብድር ፡ የተሰጡ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ እንከብሎች ፡ ወይም ፡ ለምግብ ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ሸቀጦች ፡ ሲሆኑ ፡ ተበዳሪው ፡ በተበደረው ፡ ልክ ፡ ብዛቱንና ፡ ዐይነቱን ፡ በመክፈል ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

(፪) ከብድሩ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የሆነው ፡ የነዚህ ፡ የእንከብሎች ፡ ለምግብ ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሮችና ፡ የሸቀጦች ፡ ዋጋ ፡ መለዋወጥ ፡ ከግምት ፡ አይገባም ።

(፫) ተበዳሪው ፤ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ ለመመለስ ፡ የማይቻለው ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ በርሱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ መመለሱ ፡ እጅግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሲሆንበት ፤ ዕዳው ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ (የተገመተ) ፡ የብድሩን ፡ ግምት ፡ ላበዳሪው ፡ በመስጠት ፡ ከዕዳው ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፹፰ ። የተበዳሪው ፡ መዘግየት ፡ (፩)ውሉን፡ማፍረስ።

(፩) ተበዳሪው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሲታሰብ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በማከታተል ፡ የተዘለለው፡ ወለድ ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ዐሥረኛ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አበዳሪው ፡ ወለድ ፡ ሳይከፈለኝ ፡ ቀረ ፡ በማለት ፡ በብድር ፡ የሰጠው ፡ ነገር ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ በብድር ፡ የተሰጠው ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ በየጊዜው ፡ በክፊል ፡ እንዲመለስ ፡ ስምምነት ፡ ሲኖር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) ለዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማንኛቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ፡፪ሺ፬፻፹፱።ኪሣራ።

(፩) ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ ከመመለስ ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ወለድ ፡ ከመክፈል ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚል ፡ አንቀጽ፡ በተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ጊዜ ፡ በማስተላለፍ ፡ የሚከፈለውን ፡ ወለድ ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ።

(፪) ይህን ፡ ግዴታ ፡ የሚያከብድ ፡ ማንኛቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## መጠሪያን ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፺ ። ትርጓሜ ።

(፩) መጠሪያን ፡ የማቋቋም ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ንብረትን ፡ በለውጥ ፡ በማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በመተው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚባል ፡ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ ብዛታቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚሆኑ ፡ የሚያልቁ ፡ ዕቃዎ

ችን ፡ በየጊዜው ፡ ለማስከፈል ፤ የማስገደድ ፡ መብትን ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ የሚሰጥበት ፡ ውል ፡ ነው ።

(፪) የመጦሪያ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በስጦታ ፡ ላይ ፡ እንደሚደረግ ፡ ግዴታ ፡ ሆኖ ፡ ስምምነት ፡ ሊደረግበት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፩ ። ዕዳውን ፡ ስለሚያመለክት ፡ ሰነድ ።**

(፩) ሰነዱን ፡ በእጁ ፡ ከያዘ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕዳ ፡ አስከፋዩ ፡ አዲስ ፡ ሰነድ ፡ እንዲሰጠው ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ሊያስገድድ ፡ ይችላል ።

(፪) አዲሱ ፡ ሰነድ ፡ የሚዘጋጀው ፡ በዕዳ ፡ አስከፋይ ፡ ኪሣራ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፪ ። ዘለዓለም ፡ ስለሚኖር ፡ መጦሪያና ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ስለሚቈይ ፡ መጦሪያ ።**

መጦሪያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሆኖ ፡ መቋቋም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፫ ። መከፈል ፡ ያለበትን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መከፈል ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ የመጦሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ውሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ አንሥቶ ፡ በየዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ይከፈላል ።

(፪) ተዋዋዮቹ ፡ ያልተከፈለ ፡ የመጦሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ይሰጣል ፡ ብለው ፡ አስቀድመው ፡ መስማማት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፬ ። ወደ ፡ ብድር ፡ ደንቦች ፡ ስለ ፡ መምራት ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ በመጦሪያ ፡ ማቋቋም ፡ ውል ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፭ ። የተጠበቁ ፡ ደንቦች ።**

በመንግሥት ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፤ ስለ ፡ መጦሪያዎች ፡ የተመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ለዘለዓለም ፡ ስለሚኖር ፡ መጦሪያ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፮ ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ ችሎታ (፩) መሠረቱ ።**

ምንም ፡ እንኳ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖር ፡ ለዘለዓለም ፡ የተቋቋመውን ፡ መጦሪያ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሊገዛው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፯ ። (፪) የሚቻሉ ፡ ውሳኔዎች ።**

(፩) ሆኖም ፡ ዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ከማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ መልሶ ፡ መግዛት ፡ አይቻልም ፡ ብለው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ለዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ መልሶ ፡ መግዛት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

(፫) ከዚህ ፡ የበለጡ ፡ ጊዜዎች ፡ በውሉ ፡ ተጽፈው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ( ኀይለ ፡ ቃሎች ) ፡ የተመለከቱት ፡ ከፍተኞች ፡ የሆኑ ፡ ጊዜዎች ፡ ይተኩባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፰ ። መልሶ ፡ የመግዛት፡ግዴታ ።**

ለዘለዓለም፡የተቋቋመን ፡ መጦሪያ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ መልሶ ፡ እንዲገዛ ፡ የሚገደደው፤

(ሀ) ሁለት ፡ ዓመት ፡ ግዴታዎቹን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ለዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ በውሉ ፡ ተስፋ ፡ የተሰጡትን ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ወይም ፡ እነዚህ ፡ ከሌሉ ፡ የሚገዳደሩ ፡ አዲስ ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ያልሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤

(ሐ) ባለዕዳው ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ማጣቱ ፡ በፍርድ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፶፱ ። መልሶ፡ሲገዛ፡የሚሰጠው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ።**

(፩) መጦሪያውን ፡ መልሶ ፡ በገዛ ፡ ጊዜ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ (ስለ፡ወለድ) ፡ በሕግ ፡ በተ ወሰነው ፡ ወለድ ፡ መሠረት ፡ የመጦሪያውን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ የሚገዳደር ፡ ገን ዘብ ፡ ለዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ የዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያከብድ ፡ የውል ፡ ቃል፡ ሁሉ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ስለሚቈይ ፡ መጦሪያ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷ ። መጦሪያው ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ። (፩) የአንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ።**

(፩) እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚቈይ ፡ መጦሪያ ፡ በዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ ዕድሜ ፡ በዕዳ፡ ከፋዩ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ስሦተኛ ፡ ወገን ፡ ዕድሜ፡ ልክ ፡ መቋቋም፡ይችላል።

(፪) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ ዕድሜ ፡ ልክ፡ እንደ፡ተቋ ቋመ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፩ ፡ (፪) የብዙ ፡ ሰዎች፡ዕድሜ ።**

(፩) ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚቈይ ፡ መጦሪያ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ለመቋ ቋም ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይተላ ለፋል ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ማግባት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፷፪ ፡ የሚፈርስበት፡ሁኔታ ።**

(፩) ጡረታው ፡ የተቋቋመባቸው ፡ ሰዎች ፡ የመጦሪያ፡ ውል ፡ በተቋቋመበት ፡ ቀን፡ አንዳቸውም ፡ በሕይወት ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጦሪያውን ፡ የሚያቋቁ መው ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) መጠሪያው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ይተላለፋል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጠሪያው ፡ ውል ፡ በሚቋቋምበት ፡ ቀን ፡ ይተላለፍለታል ፡ የተባለው ፡ ሰው ዬው ፡ በሕይወት ፡ ከሌለ ፡ መጠሪያውን ፡ የሚያስተላልፈው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።}

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፫ ። ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ የተቋቋመ ፡ መጠሪያ ፡ ለዕዳ ፡ ጠያቂዎች ፡ ወራሾች ፡ ይተላለፋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፬ ። ለመጠሪያ ፡ ለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ ወለድ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ አራጣ ።**

(፩) እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚቈይ ፡ መጠሪያ ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ገንዘብን ፡ በመክፈል ፡ ለውጥ ፡ የተቋቋመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ገንዘቦች ፡ ከዚህ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከመቶ ፡ ሓያ ፡ የሚበልጡ ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ።

(፪) አንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወለድ ፡ በጽሑፍ ፡ ውል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከመቶ ፡ ኻያ ፡ የሚበልጥ ፡ ወለድ ፡ በስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወለዶቹ ፡ የሚከፈሉት ፡ በመቶ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፭ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ መፍረስ ።**

አቋቋሚው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ በውል ፡ ቃል ፡ የተነገሩትን ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ያልሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚቈየው ፡ መጠሪያ ፡ የተቋቋመለት ፡ ሰው ፤ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፮ ። ገንዘቦችን ፡ ስለአለመክፈል ።**

(፩) የመጠሪያ ፡ ገንዘቦችን ፡ ያለመክፈል ፤ መጠሪያው ፡ የተቋቋመለት ፡ ሰው ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስለት ፡ ወይም ፡ ያስተላለፋቸው ፡ ሀብቶች ፡ በእጁ ፡ እንዲገቡ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይፈቅድለትም ።

(፪) የዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ሀብቶች ፡ ማስያዝና ፡ ማሸጥ ፡ ከሽያጩም ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ እንዲታዘዝለት ፡ ወይም ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ማድረግ ፤ ለገንዘቦች ፡ ሥራም ፡ በቂ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ የመውሰድ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፯ ። መልሶ ፡ የመግዛት ፡ ችሎታ ፡ አለመኖር ።**

(፩) ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ እመልሳለሁ ፡ በማለትና ፡ የከፈላቸውንም ፡ ገንዘቦች ፡ በመተው ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ መጠሪያውን ፡ ከመክፈሉ ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ አይችልም ።

(፪) የተጠዋሪ ፡ ወይም ፡ መጠሪያው ፡ የተቋቋመባቸው ፡ ሰዎች ፡ ዕድሜ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የመጠሪያው ፡ አከፋፈል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ቢሆን ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ መጠሪያውን ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፯ ። ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ ጉዳት ።**

(፩) እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚሆነው ፡ መጦሪያ ፡ ለዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ የሚከፈለው ፡ መጦሪያ ፡ በተቋቋመበት ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፪) ሆኖም ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈል ፡ ለመሆኑ ፡ ስምምነት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከፋፈሉ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ገንዘቦች ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፰ ። መብትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ ስለ ፡ መያዝ ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ ዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ መብቶቹን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላል ።

(፪) ለአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ መጦሪያው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የሚያቋቁም ፡ ሰው ፡ መጦሪያውን ፡ በሚአቋቁምበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚሁ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ የመጦሪያውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመያዝ ፡ አይችሉም ፡ ሲል ፡ በውል ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ለመጻፍ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፱ ። ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂነት ፡ መብት ፡ ማስረጃ ።**

እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚቈይ ፡ የመጦሪያ ፡ ዕዳ ፡ ጠያቂው ፡ በሕይወቱ ፡ መኖሩን ፡ ወይም ፡ መጦሪያ ፡ የተቋቋመበት ፡ ሰው ፡ መኖሩን ፡ ማስረጃ ፡ ካላቀረበ ፡ ገንዘቦችን ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲፩ ። በአሹራንስ ፡ መሠረት ፡ የሚከፈል ፡ መጦሪያ ።**

እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ የሚቈይ ፡ መጦሪያ ፡ በአሹራንስ ፡ መሠረት ፡ የሚከፈል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአሹራንስን ፡ ውል ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## አንቀጽ ፡ ፲፮ ።

## የሥራዎች ፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲፪ ። (፩) ትርጓሜ ።**

የሥራ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ ወገን ፡ አንዱ ፤ ሠራተኛው ፤ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ለአሠሪው ፤ አንድ ፡ ግዙፍነት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ሥራ ፡ በተወሰነ ፡ ወይም ፡ ባልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አሠሪው ፡ ሊከፍለው ፡ በተገደደበት ፡ አንድ ፡ ደመወዝ ፡ በርሱ ፡ አገልግሎትና ፡ በርሱ ፡ መሪነት ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ ግዴታ ፡ የገባበት ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲፫ ። (፪) የመንግሥት ፡ ሹማምቶችና ፡ ሠራተኞች ።**

(፩) የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከሹማምቶች ፡ ጋራ ፡ ባሏቸው ፡ ግንኙነቶች ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አይፈጸሙባቸውም ።

(፪) በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ ከኢንዱስትሪኤል ፡ ወይም ፡ ከንግድ ፡ ሥራ ፡ ማካሄጃዎች ፡ ጋራ ፡ በመንግሥት ፡ ወይም ፡ በአስተ ዳደር ፡ (በአድሚኒስትራቲብ) ፡ ወይም ፡ በቴክኒክ ፡ ክፍሎቹ ፡ መሪነት ፡ በሚደ ረጉ ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲፱ ። (፫) የማይነኩ ፡ ልዩ ፡ ሠራተኞች ።

የሠራተኞችን ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳ ። የውል ፡ አፈጻጸም ።

ለሥራ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ማናቸውም ፡ የተለየ ፡ ፎርም ፡ አያስፈልገውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳፩ ። የኅብረት ፡ ስምምነቶች(፩)መሠረቱ ።

አሠሪዎች ፡ ወይም ፡ የአሠሪዎች ፡ ስብሰባ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፤ የሠራተኞች ፡ ስብ ሰባ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፤ ከኅብረት ፡ ስምምነቶች ፡ ውስጥ ፡ እነዚሁኑ ፡ የሚመሩ ፡ የእ ያንዳንዳቸው ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ የሚደረጉበትን ፡ ሁኔታዎች ፡ መወሰን ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳፪ ። (፪) ውሉ ፡ የሚጸናበትና ፡ የሚቈይባቸው ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ የጋራ ፡ ስምምነቶች ፡ በጽ ሑፍ ፡ ካልሆኑና ፡ ደንበኛ ፡ በሆኑ ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ካልጸደቁ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ።

(፪) ቢሆንም ፡ ማንኛውም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፤ ውሉ ፡ ከተ ደረገ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የ፮ ፡ ወር ፡ ማስታ ወቂያ ፡ ተሰጥቶ ፡ የኅብረቱ ፡ ስምምነት ፡ ቀርቷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይቻ ላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳፫ ። (፫) ውጤቶች ።

(፩) ለሠራተኛው ፡ የበለጠ ፡ የሚጠቅሙ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ የእያንዳንዳቸው ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ቃል ፡ ከኅብረት ፡ ስምምነት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆን ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

(፪) ፈራሾች ፡ የሆኑት ፡ የየአንዳንድ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ቃል ፡ በኅብረት ፡ ስምምነት ፡ በተመለከቱት ፡ ቃል ፡ የሚተኩ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳፬ ። ለዐይነት ፡ የሚሆኑ ፡ ውሎች ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሆኑ ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ዐይነት ፡ የሚ ሆኑ ፡ ውሎች ፡ ማዘጋጀት ፡ ይችላሉ ።

(፪) የተዘጋጁትም ፡ የውል ፡ ዐይነቶች ፡ ውሎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የሚሆኑት ፡ በሚገባ ፡ ታትመው ፡ በግልጽ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴ ። (፪) ውጤቶች ።

(፩) የእያንዳንዳቸው ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ በዐይነት ፡ ውሎች ፡ ሁኔታዎች ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ ይገመታሉ ።

(፪) ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ በዐይነት ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በጽሑፍ ፡ መለወጥ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፩ ። የሥራ፡ማካሄጃው፡የውስጥ ፡ ደንብ ።

(፩) በሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ውስጥ ፡ አሠሪው ፡ ያዘጋጀው ፡ የውስጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ደንብ ፡ በጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ ሆኖ ፡ ከመቀጠሩ ፡ በፊት ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ሠራተኛውን ፡ አያስገድደውም ።

(፪) በዚህ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ አሠሪው ፡ በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ ያደረጋቸው፡ቅጣቶች ፡ ለሕግ ፡ ወይም ፡ ለሚገባ ፡ ፍርድ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ፡እንደ፡ሆነ፡እንደ ፡ ገና ፡ በዳኞች ፡ ለመሻሻል ፡ (መታየት) ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፪ ። ሠራተኛውን ፡ የሚጎዳ፡የውል፡ቃል ።

(፩) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከተጻፈው ፡ በአነሰ ፡ አኳኋን ፡ ለሠራተኛው ፡ የሚጠቅም ፡ የሥራ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በሕግ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር፡ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) ይህም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሠራተኛው ፡ ሥራ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፫ ። ግዴታው ፡ የራሱ፡ስለ፡መሆኑ ።

በውሉ ፡ ወይም ፡ በሁኔታዎቹ ፡ ተቃራኒ ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ሠራተኛው ፡ ሊሠራው ፡ ቃል ፡ የሰጠበትን ፡ ሥራ ፡ ራሱ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፬ ። የትጉህነት፡አሠራር፡ግዴታ ።

(፩) ሠራተኛው ፡ ሥራውን ፡ በጥንቃቄ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

(፪) አስቦ ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ በአሠሪው ፡ ላይ ፡ ለሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፫) አላፊነት ፡ አለበት ፡ ወይም ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ ለመገመት ፡ የሚቻለው ፡ አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ ቃል ፡ የሰጠበትን ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ እንዲሁም ፡ የሠራተ

ኛውን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ችሎታዎችና ፡ የሥራ ፡ ደረጃውን ፡ አሠሪው ፡ የሚያውቀው ፡ ወይም ፡ ይገባው ፡ የነበረውን ፡ ማወቅ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፭ ። የሥራው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ (ዲሲፕሊን) ።

የሥራውን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመለከቱ ፡ የአሠሪው ፡ ትእዛዞች ፤ ለውሉ ፡ ለሕጉና ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ አንዳችም ፡ ተቃራኒነት ፡ ከሌላቸውና ፡ እነዚህንም ፡ መፈጸም ፡ አደጋ ፡ የማያመጣ ፡ ከሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ መታዘዝ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፮ ። መሠራት ፡ የሚገባው ፡ ሥራ ። (፩) መሠረቱ ።

ሠራተኛው ፡ ሊሠራው ፡ ግዴታ ፡ የገባበትን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፯ ። (፪) ስለ ፡ ሥራ ፡ መለወጥ ።

(፩) ቢሆንም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አሠሪው ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ማካሄጃ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የሠራተኛውን ፡ ደመወዝ ፡ የሚቀንስ ፡ ወይም ፡ ከሁኔታው ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ የሚለዋወጥ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) አዲሱ ፡ ሥራ ፡ ሠራተኛው ፡ ከተቀጠረበት ፡ ሥራ ፡ ይበልጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደመወዝ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሠራተኛው ፡ ይህን ፡ ደመወዝ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፰ ። (፫) ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ።

(፩) አሠሪው ፡ በውሉ ፡ ከተመለከተው ፡ በላይ ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሠራተኛውን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ሠራተኛው ፡ ይህን ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ከቻለና ፡ አልሠራም ፡ ማለቱም ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ አሠራር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሠራተኛው ፡ ይህን ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

(፫) ሠራተኛውም ፡ አስቀድሞ ፡ በተሰማሙበት ፡ ደመወዝ ፡ አንጻር ፡ በተወሰነውና ፡ በሁኔታዎቹ ፡ ዐይነት ፡ ለዚህ ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ ተጨማሪ ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፱ ። (፬) በቍጥር ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ መሥራት ።

(፩) በቍጥር ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ሥራው ፡ ደመወዝ ፡ የሚከፈለው ፡ ሠራተኛ ፡ አሠሪው ፡ ከሆነው ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ በሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ብዛት ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በቍጥር ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፤ ለመስጠት ፡ ካልቻለ ፡ አሠሪው ፡ በሰዓት ፡ ወይም ፡ በቀን ፡ ሠራተኛውን ፡ ሊያሠራው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴ ። መሣሪያዎችን፡መሥሪያዎችን ፤ (፩) ስለ፡ማቅረብ ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለሥራው ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆኑትን ፡ መሥሪያዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ለሠራተኛው ፡ የሚያቀርበው ፡ አሠሪው ፡ ነው ።

(፪) ሠራተኛው ፡ ግዴታ ፡ ሳይኖርበት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ያቀረባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አሠሪው ፡ ኪሣራውን ፡ ይከፍለዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፩ ። (፪) በጥበቃ ፡ ስለ ፡ ማኖር።**

ሠራተኛው ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ የተሰጡትን ፡ ነገሮች ፡ በጥንቃቄ ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፪ ። ሠራተኛው፡ስለሚፈጥረው፡ነገር ።**

(፩) ለአሠሪው ፡ ሥራ ፡ ሲል ፡ ሥራውን ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ፤ ሠራተኛው ፡ ፈጥሮ ፡ ያወጣው ፡ ነገር ፡ የራሱ ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ሠራተኛው ፡ ፈጥሮ ፡ ወይም ፡ ፈልጎ ፡ እንዲያወጣ ፡ በተለይ ፡ ተቀጥሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአሠሪው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፫ ። የሥራ ፡ ማካሄጃን፡ስለሚመለከቱ፡መግለጫዎች ።**

(፩) ሠራተኛው ፡ የሥራው ፡ ውል ፡ ካለቀ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ በሥራው ፡ ጊዜ ፡ ያወቃቸውን ፡ የአሠሪውን ፡ ምስጢሮች ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) በአሠሪው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረግ ፡ ዐይነት ፡ በሥራው ፡ ጊዜ ፡ ያገኛቸውን ፡ መግለጫዎች ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይገባውም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ለሠራተኛው ፡ ስለሚገባው ፡ ደመወዝ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፬ ። ስለ ፡ ደመወዝ፡መብት።**

ይህ ፡ ሥራ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሠራ ፡ ልምድ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ በሚሠራ ፡ ሰው ፡ ሞያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ከሆነ ፤ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በደመወዝ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፭ ።የደመወዙ፡ልክ።**

(፩) በተስማሙበት ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ ስምምነቶች ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ ለአሠሪው ፡ አስገዳጅ ፡ በሆኑ ፡ ዐይነት ፡ ውሎች ፡ መሠረት ፡ ሠራተኛው ፡ ደመወዝ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እነዚህ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ከሌሉ ፡ የደመወዝ ፡ ውል ፡ በልማድ ፡ ሞያዎች ፡ ወይም ፡ ሥራው ፡ በሚሠራበት ፡ በታ ፡ ልምዶች ፡ የተወሰነ ፡ ይሆናል ።

(፫) ልምዶች ፡ ከሌሉ ፡ ግን ፡ በርትዕ ፡ መሠረት ፡ ዳኞች ፡ ይወስኑታል ።

ቍ፡፪ሺ፭፻፴፭።ስለ፡ደመወዝ ፡ አወሳሰን ።

(፩) ደመወዝ ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፤ በሰዓት ፤ በቀን ፤ በሳምንት ፤ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፤ በወር ፡ ወይም ፡ በዓመት ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ሠራተኛው ፡ ለአሠሪው ፡ በሚሰጠው ፡ ሥራ ፡ መጠን ፡ ለመ ሆን ፡ ይችላል ።

ቍ፡፪ሺ፭፻፴፮።ከትርፍ፡ ተከፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) ደመወዙ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፤ አሠሪው ፡ ካገኛቸው ፡ ትርፎች ፡ ካንድ ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ የንግድ ፡ ከንውን ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ማካሄጃው ፡ ውስጥ ፡ ከተገኘው ፡ የቁጠባ ፡ ገንዘብ ፡ ካንድ ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ከመሰለ ፡ ከሌላ ፡ ከሥራ ፡ ዋጋ ፡ ውስጥ ፡ በመቶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተብሎ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ (ኢንቫን ቴር ) ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ ሊከፍለው ፡ የሚገባውን ፡ ሒሳብ ፡ ያስረክበዋል ።

(፫) ሠራተኛውም ፡ በተዋዋሉት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ የተመረጠው ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ ባይኖር ፡ ዳኞች ፡ የመረጡት ፡ ሰው ፡ የተሠራውን ፡ ሒሳብ ፡ እንዲመረመርለት ፡ ለማስደረግ ፡ ይችላል ።

ቍ፡፪ሺ፭፻፴፯።ጕርሻዎች።

ደመወዝም ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ደንበኞች ፡ ለሠራተኛው ፡ ከከፈሉት ፡ ጕርሻዎች ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሠራተኞቹ ፡ አሠሪው ፡ ከተቀበላቸው ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

ቍ፡፪ሺ፭፻፴፰።የመክፈያው ፡ ጊዜ ።

(፩) ግዙፍነት ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የተገደዱ ፡ ሠራተኞች ፡ ደመወዝ ፡ የሚከፈለው ፤ በቀን ፡ መቍጠሪያው ፡ በየዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ መጨ ረሻ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ አጭር ፡ ሆኖ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መጨረሻ ፡ ነው ።

(፪) ለጸሓፊዎችና ፡ ለቢሮ ፡ ወይም ፡ ለማጋዘን ፡ ሠራተኞች ፡ የሚከፈለው ፡ በየ ወሩ ፡ መጨረሻ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ አጭር ፡ ሆኖ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መጨ ረሻ፡ ነው ።

(፫) የሥራው ፡ ውል ፡ ሲያልቅ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ደመወዝ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆ ናል ።

ቍ፡፪ሺ፭፻፴፱። ሥራ ፡ ስለ ፡ ማቆም ።

የሚከተሉት ፡ ሁለቱ ፡ ቍጥሮች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ሥራውን ፡ ላልሠ ራባቸው ፡ ቀኖች ፡ ሠራተኛው ፡ ደመወዝ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፩። የሥራ፡አለመኖር።**

(፩) ሠራተኛው ፡ አንድም ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ባይሰጥም ፡ እንኳ ፡ ይኸውም፡ ሁኔታ ፡ አሠሪው ፡ ሥራ ፡ ሳይሰጠው ፡ በመቅረቱ ፡ ወይም ፡ አሠሪው ፡ እንዳ ይሠራ ፡ ከመከልከሉ ፡ የተነሣም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ደመወዙን ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ሳይሰጥ ፡ በመቆጠብና ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ በመፈጸም ፡ ያገኛቸውን ፡ ጥቅሞች ፡ አሠሪው ፡ ከደመወዙ ፡ ለመቀነስ፡ይችላል።

(፫) የሥራው ፡ አለመኖር ፡ በአሠሪው ፡ ጥፋት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሠራተኛው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ በመፈጸም ፡ ሊያገኝ ፡ ይችል፡ የነበረውን፡ ጥቅሞች ፡ አሠሪው ፡ እንደዚሁ ፡ ከደመወዙ ፡ ለመቀነስ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፪ ። ስለ፡ሠራተኛው ፡ መታመም ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ሠራተኛው ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ሰጥቶ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሳይሆን ፡ በበሽታ ፡ ምክንያት ፡ አገልግሎት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የታወከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የደመወዙን ፡ ግማሽ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ሠራተኛው ፡ ለአሠሪው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ወይም፡ ይበልጥ ፡ ሥራውን፡ ከመተዉ ፡ በፊት ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የደመወዙ ፡ መብት ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ፡ ይቀራል ። እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፫) አሠሪው ፡ አስገዳጅ ፡ በሆነው ፡ ሕጋዊ ፡ አቈራንስ ፡ መሠረት ፡ ለሠራተኛው፡ ሥራውን ፡ በመተው ፡ ምክንያት ፡ የተከፈሉትን ፡ ገንዘቦች ፡ ከዕዳው ፡ ለመቀነስ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፫ ።(፪)ለያንዳንድ ፡ ሥራ ፡ በቍጥር፡የሚከፈል ፡ ደመወዝ ፡ ወይም ፡ ጕርሻ ።**

(፩) ደመወዝ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሥራ ፡ በቍጥር ፡ ወይም ፡ በመላው ፡ ሥራ ፡ የሚከፈል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ቍጥር ፡ እንዲሠራበት ፡ ለማድረግ ፡ በበሽታ ፡ ምክንያት ፡ የታወከው ፡ ሠራተኛ ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ የሚፈጽሙ ፡ በሥራው ፡ ማካሄጃ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ሠራተኞች ፡ በሚከፈለው ፡ መካከለኛ ፡ ደመወዝ ፡ ግምት ፡ ይወሰናል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሥራውን ፡ ከመተው ፡ አስቀድሞ ፡ በነበረው ፡ ወር ፡ ውስጥ፡ ታሞ ፡ የነበረው ፡ ሠራተኛ ፡ ይቀበለው ፡ የነበረው ፡ ደመወዝ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

(፫) የሚከፈለውም ፡ ደመወዝ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በክፊል ፡ በጕርሻዎች ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ለመቈጣጠር ፡ በሚቻል ፡ አኳኋን ፡ አሠሪው ፡ የሚቀበላቸው ፡ ጕርሻዎች ፡ ብቻ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፩ ። ደመወዝን ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በተወሰነው ፡ አደራረግ ፡ ካልሆነ፡ በቀር ፡ የሠራተኛ ፡ ደመወዝ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በኩል ፡ ለመያዝ ፡ አይችልም ።

(፪) እንደዚህ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሠራተኛው ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፪ ። ከደመወዝ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።

(፩) ከሠራተኛው ፡ ችግር ፡ የተነሣና ፡ ለአሠሪውም ፡ ምንም ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣበት ፡ ካልሆነ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ለሠራተኛው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ አሠሪው ፡ አስቀድሞ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ሠራተኛው ፡ ደመወዙን ፡ ለሌላ ፡ ለማስተላለፍ ፡ በሚችልበት ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ገና ፡ ባልተፈጸመ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ለሠራተኛው ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ መከፈል ፡ ሊፈቀድ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፫ ። ስለ ፡ ማቻቻል ።

(፩) ሠራተኛው ፡ ደመወዙን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ማስተላለፍ ፡ በሚችልበት ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አሠሪው ፡ በሠራተኛው ፡ ስም ፡ ለሌላ ፡ የከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ማቻቻያ ፡ አድርጎ ፡ ሠራተኛውን ፡ ለመቃወም ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ፡ነሆም ፡ ሠራተኛው ፡ አስቦ ፡ በአሠሪው ፡ ላይ ፡ ላደረገው ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ሊከፍለው ፡ የሚገባውን ፡ ኪሣራ ፡ መቻቻያ ፡ አድርጎ ፡ ያላንዳች ፡ ወሰን ፡ ሠራተኛውን ፡ ሊቃወመው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፬ ። ከደመወዝ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መያዝ ።

(፩) ከደመወዝ ፡ ላይ ፡ ይያዛል ፡ ተብሎ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ሠራተኛው ፡ በአጋጣሚ ፡ አሠሪውን ፡ ሊያደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ለመካስ ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

(፪) ደመወዙን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስተላለፍ ፡ በሚቻልበት ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ የደመወዝ ፡ መያዝ ፡ አይፈቀድም ።

(፫) ደመወዙም ፡ ከተያዘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ወለድ ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ስለ ፡ አሠሪው ፡ የጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፡ ግዴታ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፭ ። መሠረቱ ።

(፩) የሠራተኛውን ፡ ሕይወት ፤ ሙሉ ፡ ሰውነቱን ፡ ጤንነቱንና ፡ የሕሊና ፡ (የሞ

ራል ) ፡ ክብሩን ፡ በመጠበቅ ፡ ረገድ ፡ አሠሪው ፡ ለሥራው ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ዎች ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡፡

(፪) በልማድና ፡ በቴክኒክ ፡ ሥራዎች ፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ግብ ፡ ለሥራው ፡ ማካ ሄጃ ፡ ቦታዎችን ፡ ማቋቋምና ፡ አስፈላጊ ፡ መሣሪያን ፡ በተለይ ፡ ማደራጀት ፡ አለበት ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፵፱ ፡፡ በሥራ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሱ ፡ አደጋዎች ፡፡**

በሥራው ፡ ምክንያት ፡ በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ ለሚደርሱ ፡ አደጋዎች ፡ አሠሪው ፡ አላፊ ፡ ነው ፡፡

**ቍ፡ ፪ሺ፭፻፶ ፡፡ ለሥራው ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለሚሆን ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡፡**

ይህ ፡ ሥራ ፡ በአሠሪው ፡ የታዘዘም ፡ ባይሆን ፡ ለሥራ ፡ ማካሄጃው ፡ ጥቅም ፡ ሠራተኛው ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ማካሄድ ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሱበት ፡ አደጋዎች ፡ አሠሪው ፡ አላፊ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፩ ፡፡ በሥራው ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ስለሚሆኑ ፡ አደጋዎች ፡፡**

(፩) ሠራተኛው ፡ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነለት ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ የሥራውን ፡ አገልግሎት ፡ ሲፈጽም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሥራው ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ በሠራተኛው ፡ ለሚደርሱበት ፡ አደጋዎች ፡ አሠሪው ፡ አላፊ ፡ ነው ፡፡

(፪) በሥራው ፡ ሰዓት ፡ የሚፈቀደው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ፡፡

(፫) በነዚሁ ፡ ዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ለሠራተኞች ፡ ማረፊያ ፡ የተዘጋጁት ፡ ቦታዎች ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ቦታ ፡ ክፍል ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፪ ፡፡ በሞያ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሱ ፡ በሽታዎች ፡፡**

(፩) በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሱበት ፡ በሽታዎች ፡ አሠሪው ፡ አላፊ ፡ ነው ፡፡

(፪) ምንም ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ ያስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ የሚደርሱትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የሚ ቈጠሩትን ፡ በሽታዎች ፡ ይወስናሉ ፡፡

(፫) ከነዚህ ፡ በሽታዎች ፡ ዝርዝር ፡ ውጭ ፡ ለሆነው ፡ ወይም ፡ የእነዚህ ፡ ዝርዝር ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኛው ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ በሽታው ፡ የደረሰበት ፡ ለመሆኑ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፫ ፡፡ ስለ ፡ አሠሪው ፡ ከአላፊነት ፡ መዳን ፡፡**

**(፩) ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡፡**

(፩) አደጋው ፡ ወይም ፡ በሽታው ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ አስቦ ፡ ባደረገው ፡ ጥፋት ፡ መሆኑን ፡ አሠሪው ፡ ካስረዳ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ከተወሰነው ፡ አላፊነት ፡ አሠሪው ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ አደጋው ፡ ወይም ፡ በሽታው ፡ የደረሰበት ፡ ሠራተኛው ፡ በግልጽ ፡ በጽሑፍ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፍ ፡ መሆኑን ፡ ካስረዳ ፡ አሠሪው ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፬ ። (፪) ከሥራው ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ አለመኖር ።

አደጋው ፡ ከሠራተኛው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ግንኙነት ፡ ካለው ፡ ከሥራው ፡ ውል ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ካስረዳ ፡ አሠሪው ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፭ ። (፫) ሌሎች ፡ ምክንቶያች ።

አሠሪው ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ከአላፊነት ፡ አይድንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፮ ። የአላፊነት ፡ መጠን ።

፩ ፡ የሕክምናና ፡ የሌሎች ፡ ወጪዎች ።

(፩) አሠሪው ፡ ስለ ፡ ሕክምና ፡ መድኀኒቶች ፡ ሆስፒታልና ፡ ሌሎችም ፡ አደጋው ፡ ወይም ፡ በሽታው ፡ ሠራተኛውን ፡ የሚያስገድዱትና ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ የተደረጉትን ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) በአደጋው ፡ ወይም ፡ በበሽታው ፡ ጠንቅ ፡ ሠራተኛው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ ለመቃብር ፡ ሥርዐቶች ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ወጪዎች ፡ አሠሪው ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፯ ። (፪) የደመወዝ ፡ ክፍል ።

(፩) በአደጋው ፡ ወይም ፡ በበሽታው ፡ ምክንያት ፡ ሠራተኛው ፡ ለመሥራት ፡ የታወከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሠራተኛው ፡ ሥራውን ፡ ከተወበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከደመወዙ ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ አሠሪው ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ከሠራተኛው ፡ ደመወዝ ፡ የበለጠ ፡ ሳይሆን ፡ አሠሪው ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ሠራተኛው ፡ በአሠሪው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለቈየበት ፡ ለያንዳንድ ፡ ዓመት ፡ በመቶ ፡ አምስት ፡ ይጨመራል ።

(፫) ሆኖም ፡ በወር ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የሚበልጥ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፶፰ ። (፫) ስለ ፡ ቀለብ ፡ ግዴታ ።

(፩) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላና ፡ ሠራተኛው ፡ ከአደጋው ፡ ወይም ፡ ከበሽታው ፡ የተነሣ ፡ ግማሹን ፡ ወይም ፡ በሚበልጥ ፡ የሥራ ፡ ችሎታውን ፡ በጭራሽ ፡ ያጣ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ አሠሪው ፡ ለሠራተኛውና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ ልጆቹ ፡ የቀለብ ፡ መክፈል ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

BACK



(፪) አሠሪው ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ የሚደርስበት ፡ በምትክነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ከቤተ ፡ ዘመዱ ፡ አባሎች ፡ ይህን ፡ የቀለብ ፡ ርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ይህ ፡ ግዴታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ በተነገረው ፡ መጽሐፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ይወሰናል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፭፻፶፱ ። (፬) ስለ ፡ አሠሪው ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ አታላይነት ።

(፩) በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ በሽታ ፡ በአሠሪው ፡ አታላይነት ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያሉት ፡ የሁለቱ ፡ ቍጥሮች ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆኑም ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡ በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ሠራተኛው ፡ ቤተ ፡ ዘመዱና ፡ ወራሾቹ ፡ የደረሰባቸውን ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ አሠሪውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፫) አሠሪው ፡ ስሕተት ፤ አለመጠንቀቅ ፤ ወይም ፡ ችላ ፡ ባይነት ፤ ሲያደርግና ፡ ይኸውም ፡ በነዝኅላልነት ፡ በድፍረት ፡ ወይም ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ጤንነት ፡ ግድ ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ሲተረጐም ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ይሆናል ።

ክፍል ፡ ፭ ።

## ለሠራተኞች ፡ የሚገባ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ።

ቊ ፡ ፪ሺ፭፻፷። የተለመዱ ፡ ሰዓቶችና ፡ ቀኖች ።

አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ የተለመዱትን ፡ የዕረፍት ፡ ሰዓቶችና ፡ ቀኖች ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፪ሺ፭፻፷፩ ። የዓመት ፡ የዕረፍት ፡ ፈቃድ ።

ሥራ ፡ አሠሪው ፡ የሠራተኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከጊዜው ፡ ዋነኛውን ፡ ክፍል ፡ የተገለገለበት ፡ ሲሆን ፡ ለሠራተኛው ፡ የዓመት ፡ የዕረፍት ፡ ፈቃድ ፡ መስጠትና ፡ ለዕረፍት ፡ በሚሰጠውም ፡ ጊዜ ፡ ደመወዙን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፪ሺ፭፻፷፪ ። ዕረፍቱ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ሠራተኛው ፡ በአሠሪው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ክፍል ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ መደዳውን ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።

(፪) ሠራተኛው ፡ በአሠሪው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ክፍል ፡ ሲሠራ ፡ ከአምስት ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ መደዳውን ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።

(፫) ሠራተኛው ፡ በአሠሪው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡

ክፍል ፡ ሲሠራ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ይበልጥ ፡ ሆኖት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈየው ፡ መደዳውን ፡ ኻያ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፫ ። ስለ፡ ውሉ፡ማለቅ ።**

የሥራው ፡ ውል ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኛው ፡ ለአሠሪው ፡ በዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ የሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ተገምቶ ፡ የሚገባውን ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፬ ። ስለሚቀነሱ፡ ቀኖች።**

(፩) በሠራተኛው ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ከዕረፍቱ ፡ ላይ ፡ የተሰጡትን ፡ የዕረፍት ፡ ቀኖች ፡ አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ ከሚገባው ፡ ከዓመት ፡ የዕረፍት ፡ ቀኖች ፡ ላይ ፡ ይቀንሳል ።

(፪) ሠራተኛው ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ያልሠራባቸውን ፡ ቀኖች ፡ አሠሪው ፡ ለመቀነስ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፭ ። የዕረፍት፡ጊዜ።**

(፩) የዕረፍቱም ፡ ጊዜ ፡ ከዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ ምቹ ፡ በሆነ ፡ ወራት ፡ ይፈቀዳል ።

(፪) ይኸውም ፡ የሥራውን ፡ ዐይነት ፡ (አሠሪውንና ፡ የሠራተኛውን ፡ ጥቅሞች ፡ እንደ ፡ ተቻለ ፡ በማስማማት ፡ ነው ።

(፫) ዕረፍቱን ፡ የሚያገኝበት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ለሠራተኛው ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ይነገረዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፮። ለመውለድ፡ስለሚሰጥ፡ዕረፍት።**

(፩) ልጅ ፡ ለመውለድ ፡ የምትጠባበቅ ፡ ሠራተኛ ፡ በመውለጃዋ ፡ ጊዜ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ ዕረፍት ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አላት ።

(፪) በዚሁ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ አሠሪው ፡ ግማሽ ፡ ደመወዝዋን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## ውልን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፯። ጊዜው፡የተወሰነ፡ውል ።**

(፩) የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፡ ያለቀ ፡ ይሆናል ።

(፪) የተወሰነ ፡ ሥራን ፡ ለመፈጸም ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ በስምምነት ፡ የሆነው ፡ ሥራ ፡ ሲፈጸም ፡ ያለቀ ፡ ይሆናል ።

(፫) የተፈጸመውን ፡ ውል ፡ አልቋል ፡ ለማለት ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ ማስታወቂያ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳፰ ። ውሉ ፡ የሚቈይበት ፡ ከፍተኛ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የአገልግሎትን ፡ ሥራ ፡ ለመዋዋል ፡ አይቻልም ።

(፪) ከተዋዋዮቹ ፡ ባንዱ ፡ ወገን ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ወይም ፡ ከ፩ ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ተዋዋዮቹን ፡ ሊያስገድዳቸው ፡ አይችልም ።

(፫) ይህ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ውሉን ፡ ቀሪ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፳፱ ። ስለ ፡ ውል ፡ ማደስ ።**

ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ አሠሪው ፡ ሳይቃወመው ፡ ሠራተኛው ፡ ሥራውን ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ታደሰ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴ ። የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ ውል ።**

(፩) ውሉ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የተጠየቀው ፡ የሥራው ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ውሉ ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚያመለክቱ ፡ ያልሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ተዋዋዮች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ፡ ቀሪ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ውሉን ፡ ቀሪ ፡ ለማድረግ ፡ አሠሪው ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አስቀድሞ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፩ ። ማስጠንቀቂያ ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ጊዜ ።**

(፩) ማስጠንቀቂያው ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሰባት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ መሰጠት ፡ አለበት ። ውጤትም ፡ የሚያገኘው ፡ ከሚከተለው ፡ የደመወዝ ፡ መክፈያ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) የሥራው ፡ ውል ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ቈይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለወሩ ፡ መጨረሻ ፡ ሆኖ ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ አስቀድሞ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

(፫) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ ለተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ለሠራተኛው ፡ ደመወዙን ፡ ወዲያውኑ ፡ የሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መስጠቱ ፡ ይቀርለታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፴፪ ። ውሉ ፡ የሚቀርበት ፡ ምክንያት ።**

የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነውን ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ ያደረገበትን ፡ ወይም ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነለትን ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ የሚያድስበትን ፡ ምክንያት ፡ ሠራተኛው ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ በጽሑፍ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፫ ። ከሥራ፡በማሰናበት፡ስለሚሰጥ፡ኪሣራ ።**

አሠሪው ፡ ውሉን ፡ ቀሪ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ አላድስም ፡ በማለት ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፬ ። የኪሣራው፡ልክ።**

(፩) የዚህን ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ ለመወሰን ፡ የሠራተኛውን ፡ የአገልግሎት ፡ ጊዜና ፡ የሥራውን ፡ ዐይነት ፡ የሚያስወቅሱትንም ፡ ጥፋቶች፡ ከባድነት ፤ የሥራ ፡ ማካሄጃውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁኔታና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ማና ቸውንም ፡ ግልጽ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ ዳኞች ፡ ይመረምራሉ ።

(፪) ኪሣራውም ፡ ሠራተኛው ፡ ባለፈው ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ከተቀበለው ፡ ደመወዝ ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፭ ።በቂ፡ምክንያቶች ።**

(፩) ከውሉ ፡ ዐይነት ፡ የተነሣ ፡ ውሉ ፡ እንዲታደስ ፡ ወይም ፡ እንዲራዘም ፡ ባሉት፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ለአእምሮ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ፡ አሠሪው ፡ የወሰነው ፡ ውሳኔ ፤ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል።

(፪) እንዲሁም ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ የሚፈለገውን ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀቶቹን ፡ ቅን ፡ ሕሊና ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፤ ትክክለኛነቱን ፤ ወይም ፡ ፈጣንነቱን ፤ በሥራው ፡ ያላሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ የወሰ ነው ፡ ውሳኔ ፤ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዳለው ፡ ይገመታል ።

(፫) ሠራተኛው ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ቀሪ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ የወሰነው ፡ ውሳኔ ፤ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዳለው ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፮ ። ውሉን፡ያስቀረው፡ሠራተኛው፡ስለ፡መሆኑ ።**

(፩) ውሉን ፡ ያስቀረው ፡ አሠሪው ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ ሠራተኛው ፡ ውሉን ፡ እን ዲያፈርስ ፡ አሠሪው ፡ በአድራጎት ፡ ገፋፍቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሥራ ፡ በማሰና በቱ ፡ የሚወሰንለትን ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) በተለይም ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ በማይገባ ፡ ሁኔታ ፡ ያጕላላው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የውሉን ፡ ዋና ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመንካት ፡ ወይም ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ በመደጋገም ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ተፈ ጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፯።ስለ፡እምነት፡ሥራዎች።**

(፩) የሥራው ፡ ውል ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ችሎታዎችን ፡ የሚጠይቁ ፡ የእምነት ፡ ሥራ ዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ ውሉን ፡ ቀሪ ፡ የሚያደርግበትን ፡ ወይም ፡ የማያድስበትን ፡ ምክንያት ፡ ለማስታወቅ ፡ አይገደድም ።

(፪) እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ የተደረገው ፡ በማይገባ ፡ ጊዜና ፡ አን ደኛውን ፡ ወገን ፡ ለመጉዳት ፡ ወይም ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ባለማሰብ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ የውሉ ፡ መቅረት ፡ ኪሣራ ፡ መክ ፈልን ፡ አያስከትልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፰ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽነት ። (፩) መሠረቱ ።

ለመፍረስ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ የኖረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ የሥራውን ፡ ውል ፡ ወዲያውኑ ፡ ቀሪ ፡ ለማ ድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፱ ። (፪) ግዴታዎችን ፡ ስላለመፈጸም ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የግዴታዎች ፡ አለመፈጸም ፡ በሁኔታዎ ችና ፡ በልምዶች ፡ አንጻር ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ከባድ ፡ ጠባይ ፡ ካላሳየ ፡ በቀር ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፹ ። (፫) ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ መተው ።

ሁኔታው ፡ በሠራተኛው ፡ ጥፋት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በበሽታ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሠራተኛው ፡ እንዳይሠራ ፡ የተከለከለበት ፡ ሁኔታ ፡ ለአሠሪው ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፹፩ ። (፬) የሥራ ፡ አድማ ።

(፩) ላንድ ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ የሠራተኛው ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ የተደረገው ፡ አሠሪውን ፡ ለመጉዳት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተከለከለ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ለአሠሪው ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።

(፪) ከነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፹፪ ። (፭) የአሠሪው ፡ መክሠር ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ።

አሠሪው ፡ የከሠረ ፡ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ስለ ፡ ደመወዙ ፡ ዋስትና ፡ የጠየቃቸው ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ዋሶች ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልተሰጡት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፹፫ ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ግዴታ ። (፩) አላገባብ ፡ ውልን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ በማይገባ ፡ ሁኔታ ፡ ውሉን ፡ ያፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማይገባ ፡ ውሉን ፡ ስላቋረጠ ፡ ውል ፡ አፍራሹ ፡ በተዋዋዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፱ ። (፪) በሚገባ ፡ ውልን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

አንዱ ፡ ወገን ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚያደርሰው ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ውልን ፡ በመጣስ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡ መጣስ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ያልፈጸመው ፡ ወገን ፡ ውሉን ፡ በመተው ፡ በተዋዋዩ ፡ ላደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸ ። ስለ ፡ ሠራተኛው ፡ መሞት ።**

(፩) የሠራተኛው ፡ መሞት ፡ የሥራውን ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ ያደርገዋል ።

(፪) የሠራተኛው ፡ ወራሾች ፡ በውሉ ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ የግል ፡ ግዴታ ፡ አይደርስባቸውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፩ ፡ ስለ ፡ አሠሪው ፡ መሞት ።**

(፩) ስምምነቱ ፡ የተደረገው ፡ አሠሪውን ፡ በመመልከት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በአሠሪው ፡ መሞት ፡ የሥራው ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ አይሆንም ።

(፪) በአሠሪው ፡ መሞት ፡ የሥራው ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ጊዜው ፡ ላልተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ማስታወቂያ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ያህል ፡ ተቈጥሮ ፡ አሠሪው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሠራተኛው ፡ ደመወዙን ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፪ ። የሥራ ፡ ማካሄጃን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

(፩) አሠሪው ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃውን ፡ ለሌላ ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እሱ ፡ ያደረጋቸው ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ በሠራተኞቹና ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃውን ፡ በገዛው ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ይቀጥላሉ ።

(፪) ሠራተኞቹ ፡ የሥራው ፡ ማካሄጃ ፡ ከመተላለፉ ፡ በፊት ፡ ያገኙዋቸውን ፡ የነባርነት ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) የሥራው ፡ ማካሄጃ ፡ በተላለፈለት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ለሠራው ፡ ሥራ ፡ ሊከፈል ፡ ለሚገባው ፡ ገንዘብና ፡ እንዲሁም ፡ አስተላላፊው ፡ ውሉን ፡ በማፍረሱ ፡ ሊከፍል ፡ ለሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ጭምር ፡ እነዚህ ፡ ገንዘቦች ፡ ሊከፈሉ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለሠራተኛው ፤ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ በተላለፈው ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ ደብተር ፡ ተጽፎ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ ካስተላለፈው ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ይገደዳል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፫ ። ስለ ፡ ተሠራው ፡ ሥራ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ።**

(፩) ሠራተኛው ፡ የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ የሥራውን ፡ ዐይነትና ፡ ሥራዎቹ ፡ የቈዩበትን ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲሁም ፡ የአሠሪው ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ ያለበት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጠው ፡ አሠሪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ለጠባዩና ፡ ለፈጸመው ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ ያስተያየት ፡ ግምት ፡ በምስክር ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሠራተኛው ፡ አሠሪውን ፡ በግልጽ ፡ ካልጠየቀው ፡ በቀር ፡ የምስክሩ ፡ ወረቀት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ አስተያየት ፡ አይገኝበትም ።

ሎ ፡ ፪ሺ፭፻፶፱ ። መወዳደር ፡ እንዳይደረግ ፡ የሚደረግ ፡ የውል ፡ ቃል ።

፩ ፡ መሠረቱ ።

(፩) ለሠራተኛው ፡ የተሰጠው ፡ ሥራ ፡ የአሠሪውን ፡ ደንበኞች ፡ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ በጉዳዮቹ ፡ ምስጢር ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ የፈቀደለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ውሉ ፡ ቀሪ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ አሠሪውን ፡ ለመወዳደር ፡ እንዳይችል ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ አሠሪውን ፡ በሚወዳደር ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃው ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ እንዳይሆን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ መዋዋል ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በግልጽና ፡ በጽሑፍ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

ሎ ፡ ፪ሺ፭፻፷ ። (፪) ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ ወሰን ።

(፩) መወዳደርን ፡ የሚከልክለው ፡ ስምምነት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የሚሆነው ፡ ለአሠሪው ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትን ፡ ጥቅሞች ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ መጠንና ፡ ለሠራተኛው ፡ የወደፊት ፡ አኗኗር ፡ ዕድል ፡ በርትዕ ፡ መሠረት ፡ ተቃራኒ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በተለይም ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ የሚጸናው ፡ ለሠራተኛው ፡ የተከለከለው ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ ስፍራውና ፡ ጊዜው ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪ሺ፭፻፷፩ ። (፫) ፡ ስለ ፡ ቅጣት ።

(፩) የተከለከለውን ፡ የመወዳደር ፡ ስምምነት ፡ የጣሰ ፡ ሰው ፡ ስምምነቱን ፡ በመጣሱ ፡ ለሚደርሰው ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ክልከላውን ፡ የጣሰ ፡ ይቀጣል ፡ ብለው ፡ ተዋውለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ሠራተኛው ፡ ለአሠሪው ፡ የተወሰነውን ፡ መቀጫ ፡ በመክፈል ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

(፫) ይህ ፡ መብት ፡ ለራሱ ፡ እንዲጠበቅ ፡ በጽሑፍ ፡ በግልጽ ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ በቀር ፡ አደጋ ፡ በደረሰባቸው ፡ ወይም ፡ ያደርስባቸዋል ፡ ተብለው ፡ በሚያሠጉት ፡ ጥቅሞች ፡ ትልቅነት ፡ መጠንና ፡ ከሠራተኛው ፡ አሠራር ፡ የተነሣ ፡ ውሳኔው ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ይህ ፡ ሠራተኛው ፡ ያደረገው ፡ የውል ፡ መተላለፍ ፡ ሥራ ፡ እንዲቀር ፡ አሠሪው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፭፻፷፪ ። (፬) ስለ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ፈራሽነት ።

(፩) የመወዳደር ፡ ክልከላ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለማድረግ ፡ አሠሪው ፡ እርግጠኛ ፡ ጥቅም ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ የመወዳደሩ ፡ ክልከላ ፡ ስምምነት ፡ ቀሪ ፡ ሆይናል ።

(፪) በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ሳያገኝበት ፡ አሠሪው ፡ የሥራውን ፡ ውል ፡ ያፈረሰ ፡ ወይም ፡ ለማደስ ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው፡ ውድድርን ፡ በሚከለክለው ፡ ውለታ ፡ ለመጠቀም ፡ አይችልም ።

(፫) እንዲሁም ፡ ሠራተኛው ፡ ውሉን ፡ እንዲያፈርስ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ የሰጠው ፡ አሠሪው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውድድሩን ፡ በሚከለክለው ፡ ውለታ ፡ አሠሪው ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፫ ፡ የቀሪ ፡ ሒሳብ ፡ የመጨረሻ ፡ ደረሰኝ ።**

(፩) ሠራተኛው ፡ የፈረመበት ፡ የቀሪ ፡ ሒሳብ ፡ የመጨረሻ ፡ ደረሰኝ ፡ አሠሪው ፡ ለሚሰጠው ፡ ደመወዝ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ሠራተኛው ፡ ከአሠሪው ፡ ላይ ፡ ሊያገኛቸው ፡ የሚችለው ፡ ሌሎች ፡ ገንዘቦች፡ የተከፈሉ ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱት ፡ አሠሪውን ፡ ነጻ ፡ የሚያደርጉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ ደረሰኞች ፡ ሆነው ፡ አከፋፈላቸውን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ወይም ፡ የሠራተኛውን ፡ አልፈልግም ፡ ማለትን ፡ የሚያስረዱ ፡ ሰነዶች ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ውሎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ሞያ ፡ ሥራ ፡ መልመጃ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፬ ። አሠሪው ፡ ለሥራ ፡ ለማጁ ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ።**

(፩) በሥራ ፡ መልመጃ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አሠሪው ፡ ለሥራ ፡ ለማጁ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ትምህርትን ፡ በሚያስፈልገው ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ።

(፪) በውሉ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ባላቸው፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አሠሪው ፡ ሥራ ፡ ለማጁን ፡ ያውለዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፭ ። ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ ማዘውተር ።**

(፩) ሥራ ፡ ለማጁ ፡ የግዴታ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ እንዲያዘወትር ፡ አሠሪው ፡ ይጠባበቃል ።

(፪) አሠሪውም ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችንና ፡ የሞያ ፡ ሥራዎችን ፡ ትምህርት ፡ እንዲሁም ፡ በሥራ ፡ ለማጆች ፡ ፈተና ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ እንዲችል ፡ ለሥራ ፡ ለማጁ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጊዜ ፡ ይፈቅድለታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፺፮ ። የተከለከሉ ፡ ሥራዎች ።**

ከሁኔታዎች ፡ የተነሣ ፡ የሚገባ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ አሠሪው ፡ ሥራ ፡ ለማጁ ፡ በሌሊት ፡ ወይም ፡ በእሑድ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፯ ። ወደ፡ሥራ ፡ ውል ፡ ደንቦች፡ስለ፡መመራት ።**

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ደንቦች ፡ በሥራ ፡ መልመጃ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ይጸናሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሥራ ፡ ሙከራ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፰ ። በሙከራ፡ስለ፡መቅጠር ።**

(፩) ሠራተኛውን ፡ በሙከራ ፡ ለመቅጠር ፡ ይቻላል ።

(፪) ይህንን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጽሑፍ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሙከራ ፡ የተቀጠረው ፡ ሠራተኛ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተቀጠረ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፱ ። የሕሊና፡ግምት ።**

ከአሽከሮች ፡ ጋራ ፡ የተደረገ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ሳምንቶች ፡ እንደ ፡ ሙከራ ፡ ጊዜ ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸ ። ለሙከራ ፡ የተደረገን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

(፩) በሙከራው ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ለመስጠት ፡ ሳይገደድ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፍል ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሙከራው ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆነ ፡ አነስተኛ ፡ ጊዜ ፡ የተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አነስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በቤተ ፡ ሰብ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ስለሚኖር ፡ አሽከር ፡ የሥራ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፩ ። ስለ ፡ ሠራተኛው ፡ ጤናና ፡ ግብረ ፡ ገብነቱ ።**

ሠራተኛው ፡ ከአሠሪው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ የምግብን ፡ የሥራና ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜዎችን ፡ የሚመለከቱትን ፡ የሠራተኛውን ፡ ጤና ፡ ግብረ ፡ ገብነቱን ፡ የሚጠብቁትን ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ዝግጅቶች ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸፪ ። ሠራተኛውን ፡ የማስታመም ፡ ግዴታ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) በአሠሪው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረውና ፡ እርሱም ፡ የሚጠብቀው ፡ አሽከር ፡ የታመመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ለታመመው ፡ ሠራተኛ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሕክምናዎች ፡ በቤቱም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ሆስፒታል ፡ ለማስታመም ፡ አሠሪው ፡ አስፈላጊውን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ውሉ ፡ ከተጀመረ ፡ ቢያንስ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በሽታው ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአንድ ፡ ወር ፡ በሚቈይ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ውሉ ፡ ከተጀመረ ፡

ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በሚቈይ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ የማስታመም ፡ ግዴታ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

(፫) በበሽታው ፡ ጊዜ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ወጪዎች ፡ አሠሪው ፡ ከሠራተኛው ፡ ደመወዝ ፡ ላይ ፡ ለመቀነስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፫ ። (፪) ነጻ ፡ ስለሚያደርጉ ፡ ምክንያቶች ።

(፩) ሠራተኛው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ አስቦ ፡ በሽታው ፡ እንዲይዘው ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ከተመለከቱት ፡ ግዴታዎች ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

(፪) በሽታውን ፡ ተቃዋሚ ፡ ከሚሆን ፡ ካንድ ፡ አስገዳጅ ፡ አሹራንስ ፡ የመነጨን ፡ አንድ ፡ መብት ፡ በመፈጸም ፡ ባንድ ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ሠራተኛው ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአሠሪው ፡ ግዴታ ፡ እንዲሁ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፫) በሠራተኛው ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ ውሉን ፡ በማፍረስ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ከተመለከቱት ፡ ግዴታዎች ፡ አሠሪው ፡ ነጻ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፬ ። ስለ ፡ ደመወዝ ፡ አከፋፈል ።

(፩) የሥራው ፡ ውል ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ ፡ ካልወሰነ ፡ በቀር ፡ ከአሠሪው ፡ ቤት ፡ ሰብ ፡ ጋራ ፡ በአሽከርነት ፡ የሚኖሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ደመወዝ ፡ የሚከፈላቸው ፡ በየሦስት ፡ ወር ፡ መጨረሻ ፡ ነው ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ውሉ ፡ ቀሪ ፡ ሲሆን ፡ ደመወዝ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

ክፍል ፡ ፬ ።

ስለ ፡ እርሻ ፡ ሥራ ፡ ውል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ስለ ፡ እርሻ ፡ ውል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፭ ። መሠረቱ።

(፩) የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ በተለይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ንኡስ ፡ ክፍሎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚፈጸሙበት ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፮ ። ጊዜው፡ያልተወሰነ፡ ውል ።

(፩) ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ባልተወሰነ ፡ ውል ፡ መሬቱን ፡ ያከራየ ፡ ባለመሬት ፡ ውሉን ፡ የሚያፈርስ ፡ መሆኑን ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ገበሬው ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ በኖረበት ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ዓመት ፡ የአንድ ፡ ወር ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ይኖረዋል ።

(፫) ስለ ፡ ገበሬው ፡ መሰናበት ፡ የተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ ከመጋቢት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ካለው ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ማናቸውንም ፡ ውጤት ፡ አያስከትልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፯ ። ባለመሬቱ ፡ ገበሬውን ፡ ለመመገብ ፡ ስላለበት ፡ ግዴታ ።

(፩) የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ገበሬ ፡ በተወሰነ ፡ የእርሻ ፡ ስፍራ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመሬቱ ፡ ለዚህ ፡ ገበሬ ፡ ምግብ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ በዚህ ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በተመለከተው ፡ አንቀጽ ፡ የተባሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይጸኑበታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፰ ። ይህ ፡ ግዴታ ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ግዴታ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ባለመሬቱ ፡ ሊመግባቸው ፡ የሚገደድበት ፡ ሌሎች ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶችና ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነሱን ፡ በመጉዳት ፡ ገበሬው ፡ አሠሪውን ፡ ባለመሬት ፡ ቀለብ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ገበሬው ፡ ምግብ ፡ ሊሰጡት ፡ የሚችሉ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለመሬቱን ፡ ምግብ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፱ ። የጊዜው ፡ ወሰን ።

ባለመሬቱ ፡ ገበሬውን ፡ ለመመገብ ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ፡ የእርሻ ፡ ሥራው ፡ ውል ፡ ከተፈጸመ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የሚቀር ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲ ። ትርጓሜ ።

የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አሠሪው ፡ በገባው ፡ ውለታ ፡ ለ፩ኛው ፡ ወገን ፡ የሥራውን ፡ ዋጋ ፡ ሊከፍለው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩም ፡ በኀላፊነት ፡ የተሰጠውን ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ በገባበት ፡ ውለታ ፡ ሊፈጽም ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲፩ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሥራ ፡ ማከናወኛዎች ።

(፩) የሥራ ፡ ማከናወኛው ፡ ዓላማ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማከናወኛውን ፡ ውል ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የማይንቀሳቀሱትን ፡ ንብረቶች ፡ በሚመለከተው ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተዋል ።

(፪) የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ጠቅላላ ፡ ዋጋ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፲፪ ። በዝምታ ፡ መቀበል ።

(፩) አንድ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በግልጽ ፡ ያስታወቀ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ በሙያ ፡ ሥራው ፡ ክንውን ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የሥ

ራውን ፡ ማቅረብ ፡ ተቀብሎ ፡ የታዘዘለትን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ወዲያውኑ ፡ እንቢታውን ፡ ካላስታወቀ ፡ የማከናወኛው ፡ ውል ፡ የተፈጸመ ፡ ይሆናል ።

(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በባለሥልጣኖች ፡ የተመረጠ ፡ ሲሆንና ፡ ለመፈጸም ፡ አለመፈለጉን ፡ ወዲያውኑ ፡ ካላስታወቀ ፡ እንደዚሁ ፡ ውሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፫ ። መሣሪያዎችና፡መሥሪያዎች ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራን ፡ ለመፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ መሣሪያዎችንና ፡ መሥሪያዎችን ፡ የሚያቀርበው ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ መሣሪያዎችንና ፡ መሥሪያዎችን ፡ አሠሪው ፡ እንዲሰጥ ፡ ሆኖ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ ብቻ ፡ እንዲሠራ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፬ ። ሥራ፡ተቋራጩ፡የሚያቀርባቸው ፡ መሥሪያዎች ።

(፩) ሥራ፡ተቋራጩ፡ለሚያቀርባቸው፡መሥሪያዎች፡መልካምነት፡ኣላፊ፡ነው።

(፪) ስለ ፡ መሥሪያዎቹ ፡ መልካምነት ፡ ሻጩ ፡ ኣላፊ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩም ፡ ኣላፊ ፡ ነው ።

(፫) አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ የገባበት ፡ የዕውቀት ፡ የሥራ ፡ ውለታ ፡ ተዋዋይ ፡ የተዋዋለበት ፡ ነገር ፡ በሚሰጣቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ ሥራው ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ እንጂ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ውል ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፭ ። አሠሪው፡ያቀረባቸው፡መሥሪያዎች።

(፩) መሥሪያዎቹን ፡ ያቀረባቸው ፡ አሠሪው ፡ ሲሆን ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በጥንቃቄ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይገባል ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ፡የሠራባቸውን፡መሥሪያዎች፡ለአሠሪው፡ገልጾ ፡ ሥራው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የተረፈውን ፡ ይመልስለታል ።

(፫) አሠሪው ፡ ያቀረባቸው ፡ መሥሪያዎች ፡ የተበላሹ ፡ ሲሆኑ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ፡ ወዲያውኑ ፡ ለአሠሪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፮ ። የሥራ፡ተቋራጭ፡ነጻነት።

(፩) የኪነ ፡ ጥበብን ፡ ደንቦች ፡ በማክበር ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ እንደሚመስለው ፡ ሥራውን ፡ ይፈጽማል ።

(፪) ውሉን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተስማማበት ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በአሠሪው ፡ ትእዛዞች ፡ ለመሄድ ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፯ ። ራሱ፡ባለቤቱ፡ስለሚፈጽመው፡ሥራ ።

ከታዘዘው ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ የተነሣ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩ፡ ችሎታ ፡ ለአሠሪው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሌላቸው ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ራሱ ፡ ሥራውን፡መፈጸም ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፰ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ መዘግየት ።**

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ ሳይጀምር ፡ በመቈየቱ ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው፡ የቀጠሮ ፡ ጊዜ ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሲሆን ፡ ሥራውን ፡ የሚጀምርበትን ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ጊዜ ፡ አሠሪው ፡ ሊወስንለት ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የቀጠሮ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ ያልጀመረ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ያቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ሳይጠብቅ ፡ አሠሪው ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አሠሪው ፡ ከሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ላይ ፡ ኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፲፱ ። ጊዜ ፡ ስላልተወሰነበት ፡ ጕዳይ ።**

(፩) በውሉ ፡ ማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ያልተመለከተበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሥራውን ፡ ጀምሮ ፡ በአሠራር ፡ ልምድ ፡ መሠረት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ ወዲያውኑ ፡ ያልጀመረ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ አፈጻጸም ፡ ያቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳ ። ሥራን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ስላለመሥራት ።**

(፩) ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥራው ፡ በመጥፎ ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ለውሉ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የሚፈጸም ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ አሠሪው ፡ ለተመለከተው ፡ ጕድለት ፡ ማሻሻል ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጩ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) በውሉና ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ ያላደሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሠሪው ፡ መብቶቹን ፡ ለማስከበር ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ የተመለከተውን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሳይጠብቅ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል ፡ ብሎ ፡ ማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አሠሪው ፡ ከሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፩ ። ሥራን ፡ ለአሠሪው ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።**

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ በተመለከተው ፡ ቦታ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ባይገኝ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ በአለበት ፡ ቦታ ፡ ለአሠሪው ፡ ያስረክባል ።

(፪) ለጕዳዮቹ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ አሠሪው ፡ ሥራውን ፡ በፍጥነት ፡ ይቀበላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፪ ። የጕድለት፡ዋስትና ።**

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራው ፡ የተከናወነው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በትክክል ፡ ስለ ፡ መሆኑና ፡ ጕድለትም ፡ የሌለበት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ለአሠሪው ፡ አላፊ ፡ መድን ፡ የመሆን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) በአንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ጕድለትን ፡ አላፊ ፡ መድንነት ፡ የሚመለከተው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ በተነገረው ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ በሥራ ፡ ተቋራጩና ፡ በአሠሪው ፡ መካከል ፡ ስላሉት ፡ ግንኙነቶች፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፫ ። የመክፈያ፡ጊዜ ።**

(፩) ሥራው ፡ የተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ አሠሪው ፡ ከተረከበ ፡ (ከተቀበለ) ፤ ለሥራ ፡ ተቋራጩ፡ ዋጋው ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

(፪) ሥራዎቹን ፡ በከፊል ፡ ለማስረከብና ፡ ክፍያዎቹም ፡ በከፊል ፡ እንዲሆኑ ፡ ስምምነቶች ፡ ተደርገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ አሠሪው ፡ ሲረከብ ፡ (ሲቀበል) ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የተመደበው ፡ ዋጋ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፬ ። በቍርጥ ፡ የተወሰነ፡ዋጋ ።**

(፩) ዋጋው ፡ በቍርጥ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ አሠሪው ፡ ይህን ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የበለጠ ፡ ሥራ ፡ አስፈለገው ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ከተመለከተው ፡ በላይ ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ አወጣ ፡ በማለት ፤ ከተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ለሥራው ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፫) አሠሪው ፡ ያነሰ ፡ ሥራ ፡ አስፈለገው ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ከተመለከተው ፡ በታች ፡ ያነሰ ፡ ዋጋ ፡ አወጣ ፡ በማለት ፡ ከተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ ይቀንስልኝ ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፭ ። ስምምነት ፡ የተደረገበትን ፡ ሥራ፡ስለ፡መለወጥ ።**

(፩) ስለ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታ ፡ በፊት ፡ የተስማሙትን ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በአዲስ ፡ ስምምነት ፡ ቢለውጡት ፡ እንኳ ፡ ለሥራው ፡ የተወሰነ ፡ ቍርጥ ፡ ዋጋ ፡ ያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቀራል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ መለወጥ ፤ ዋጋ ፡ ለመጨመር ፡ ወይም ፡ ለመቀነስ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፮ ። አስቀድሞ ፡ ያልተወሰነ ፡ ዋጋ ።

(፩) ዋጋው ፡ በውሉ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሙያ ፡ ሥራዎች ፡ ታሪፍና ፡ (የዋጋ ፡ ልክ) ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ይወስናል ።

(፪) የሙያ ፡ ሥራዎች ፡ ታሪፍና ፡ ልማድ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለሥራ ፡ ያዋለውን ፡ መሥሪያዎች ፡ ዋጋ ፤ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ደንበኛ ፡ ሥራና ፡ የተቋራጩን ፡ ወጪዎች ፡ በመገመት ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፯ ። በተቃረበ ፡ ግምት ፡ ዋጋን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

ውሉ ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ በተቃረበ ፡ ግምት ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተደረገው ፡ ግምት ፡ ዋጋው ፡ ከመቶ ፡ ሐያ ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፰ ። የመያዝ ፡ መብት ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሠራቸው ፡ ወይም ፡ ያደሳቸውና ፡ በጁ ፡ የሚገኙትን ፡ የአሠሪው ፡ የሆኑትን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎች ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ በአሠሪው ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ገንዘብ ፡ ዋስትና ፡ ለመያዝ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) አሠሪው ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሰጣቸው ፡ ዕቃዎች ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተሰጡት ፡ ዕቃዎች ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ሳያውቀው ፡ ወይም ፡ ከፈቃዱ ፡ ውጭ ፡ መሆኑን ፡ ያወቀ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ የሚገባው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡ መብቱ ፡ ይህንን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፷፱ ። ሊደርስ ፡ ስለሚችል ፡ አደጋ ።

(፩) ሥራው ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊዎች ፡ መሥሪያዎች ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ የጠፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራው ፡ መሥሪያዎቹን ፡ ባቀረበው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ የአደጋን ፡ አላፊነት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ሽያጭ ፡ በተነገረው ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ መያዝ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፭፻፸ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ መሞት ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ የተደረገው ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ የግል ፡ ችሎታዎች ፡ በመገመት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) ሊሠራባቸው ፡ ከቻለ ፡ አሠሪው ፡ በከፊል ፡ የተፈጸሙትን ፡ ሥራዎች ፡ እንዲረከብና ፡ (እንዲቀበልና) ፡ የነዚህንም ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ።

BACK



(፫) ትክክል ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ከፍሎ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የተሰናዱት ፡ መሥሪያዎችና ፡ ፕላን ፡ እንዲሰጡት ፡ አሠሪው ፡ ማስገደድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፩ ። አንዱ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ውልን ፡ ስለ ፡ ማፍረሱ ።

(፩) አሠሪው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በስምምነት ፡ የተደረገውን ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ቢሆንም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ውሉ ፡ ከመፍረሱ ፡ የተነሣ ፡ የቀረለትን ፡ ወጪና ፡ በሌላ ፡ ሥራ ፡ ያገኘውን ፡ ወይም ፡ ለማግኘት ፡ ይችል ፡ የነበረውን ፡ በክፉ ፡ ልቡናና ፡ በቸልተኛነት ፡ ሳያገኝ ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ዕውቀት ፡ ሥራ ፡ ማከራየት ፡ ውል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፪ ። የሚፈጸሙ ፡ ድንጋጌዎች ።

(፩) የዕውቀት ፡ ጠባይ ፡ ሥራዎች ፡ አገልግሎት ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ በሚከተሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተወስኗል ።

(፪) ከነዚሁ ፡ ውሳኔዎች ፡ ጋራና ፡ ከተመለከተው ፡ ግንኙነት ፡ ዐይነት ፡ ጋራ ፡ ለመስማማት ፡ በሚችሉበት ፡ መጠን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደዚሁ ፡ ይፈጸማሉ ።

(፫) የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያዎችን ፡ ተግባር ፡ የሚመለከቱ ፡ የልዩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፫ ። ግዴታው ፡ የግል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የዕውቀት ፡ ሥራውን ፡ የተዋዋለ ፡ ሰው ፡ ግዴታዎቹን ፡ ራሱ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ በውሉ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ የተፈቀደ ፡ ሲሆንና ፡ ከሥራ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠት ፡ ዓላማ ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ከሆነ ፡ በሱ ፡ መሪነትና ፡ አላፊነት ፡ ረዳቶችን ፡ ማሠራት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፬ ። አሠሪው ፡ አስቀድሞ ፡ ስለሚከፍለው ፡ ገንዘብ ።

(፩) ስለ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ አስፈላጊ ፡ ወጪዎችን ፡ አሠሪው ፡ ለተዋዋዩ ፡ አስቀድሞ ፡ ይከፍላል ።

(፪) እንደዚሁ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ከሥራ ፡ ዋጋ ፡ በከፊል ፡ አስቀድሞ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፭ ። ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ።

በሁለት ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ የተደረገበት ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የዕውቀት ፡ ሥራውን ፡ ለሚያዋውለው ፡ ሰው ፡

የሞያ ፡ ሥራ ፡ ተግባር ፡ ክብር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ሊቀንሱት፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፮ ። ስለሚጠየቅበት ፡ ጥንቃቄና ፡ አላፊነት ።**

(፩) በውቀት ፡ ሥራው ፡ የሚዋዋል ፡ ሰው ፡ በልማድና ፡ በሙያ ፡ ሥራ ፡ ድንጋጌ ዎች ፡ መሠረት ፡ ከልብ ፡ በመሥራት ፡ ለአሠሪው ፡ ጥቅሞች ፡ በሚሻል ፡ አኳኋን ፡ ሥራን ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የኪነ ፡ ጥበብን ፡ ደንቦች ፡ በማፍረስ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ በአሠሪው ፡ በኩል ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ አላፊነት ፡ አይነካውም ።

(፫) ሳይሠራ ፡ ከመቅረቱ ፡ የተነሣ ፡ እንዲሁም ፡ በአሠሪው ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ የሚ ያመጣ ፡ ሥራ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊ ፡ ነው ፡ ለመባል ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፯ ። ስለ ፡ ውል፡መፍረስ ። (፩) የአሠሪው ፡ ውል ፡ ማፍረስ ።**

(፩) አሠሪው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ፡ ማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ስለ ፡ ወጪዎቹ ፡ ኪሣራን ፡ እንዲሰጥና ፡ ለፈጸመው ፡ ሥራ ፡ በርትዕ ፡ የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፍል ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፰ ። (፪) የሠሪው፡ውል ፡ ማፍረስ ።**

(፩) የዕውቀት ፡ ሥራውን ፡ ያዋዋለ ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ፡ ማፍ ረስ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከሥራው ፡ ዋጋና ፡ ወጪዎች ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ የተቀበላቸ ውን ፡ ለአሠሪው ፡ ይመልሳል ።

(፫) ውሉ ፡ ሲፈርስ ፡ አሠሪውን ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የሚያገኘው ፡ ጉዳት ፡ ከሁሉ ፡ ያነሰ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ኪሣራ ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሕክምና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሆስፒታል ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፱ ። የሕክምና ፡ ውል ፡ ትርጓሜ ።**

የሕክምና ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሐኪም ፡ ውለታ ፡ ገብቶ ፡ የሚገባውን ፡ ገን ዘብ ፡ በመቀበል ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ የሕክምና ፡ ሥራዎችን ፡ እንዲያደርግለትና ፡ በተ ቻለውም ፡ በመልካም ፡ ጤና ፡ እንዲቈይ ፡ ወይም ፡ ሊያድነው ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵ ። የሕክምና፡ሞያ ።**

የሕክምና ፡ ውልን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ለቀዳጆች ፤ ለጥርስ ፡ ሐኪሞች ፤ ለአእምሮ ፡ በሽታ ፡ ሐኪሞች ፤(ለራዲአሎን)፤ ለአዋላጅ ፡ ሴቶች ፡ ለአስታማሚዎ

ችና ፡ ሰዎችን ፡ ከማከም ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ጋራ ፡ ተያይዘው ፡ የሞያዎች ፡ ተግባርን ፡ የመሳሰሉን ፡ በሚሠሩ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ ይፈጸምባቸዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፩ ። የሆስፒታል ፡ ውል ፡ ትርጓሜ ።

የሆስፒታል ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ የሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ የታወቀ ፡ በሽታ ፡ ብዙ ፡ ሐኪሞች ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ የሕክምና ፡ ሥራዎች ፡ ሊያደርግለት ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፪ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ መፈጸም ።

(፩) ውሉ ፡ በቀጥታ ፡ በሚታከመው ፡ ሰውና ፡ በሐኪሙ ፡ ወይም ፡ በሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሚታከመው ፡ ሰው ፡ ፋንታ ፡ ከሐኪሙ ፡ ወይም ፡ ከሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፫ ። ስለ ፡ ታከመው ፡ ሰው ፡ ግዴታ ።

በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ያደረገለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የታከመው ፡ ሰው ፡ ለሐኪሙ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ለሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ዋጋውን ፡ የሚከፍለው ፤

(ሀ) በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ውሉን ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ አባቱ ፡ እናቱ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ስለ ፡ ጤናው ፡ አጠባበቅ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ውሉም ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃደኛነቱን ፡ ለማስታወቅ ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ሕክምና ፡ ሊደረግለት ፡ አስቸኳይ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፬ ። ሐኪሙን ፡ ስለ ፡ ጠራው ፡ ሰው ፡ ግዴታ ።

ለሌላው ፡ ሰው ፡ ብሎ ፡ ከሐኪሙ ፡ ወይም ፡ ከሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ውል ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፤ ለሐኪሙ ፡ ስለሚገባው ፡ ገንዘብና ፡ ስለ ፡ ሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ የሚገደደው ፤

(ሀ) ሕክምና ፡ ለተደረገለት ፡ ሰው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጤናው ፡ አጠባበቅ ፡ ውል ፡ ያደረገ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ለሐኪሙ ፡ ወይም ፡ ለሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ራሱ ፡ ኣላፊ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ የተስማማ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፪ሺ፮፻፵፭ ። ክስ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

ለሐኪሙ ፡ ወይም ፡ ለሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ሕክምና ፡ በተደረገለት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ አለው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፮ ። የሚከፈል ፡ ዋጋ ።</u>

(፩) ለሐኪሙ ፡ የሚገባው ፡ ገንዘብና ፡ ለሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ይወሰናል ።

(፪) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

(፫) ይህ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመሆኑ ፡ የሕክምናን ፡ ሞያ ፡ ክብር ፡ ተቃራኒ ፡ ሲሆን ፡ ዳኞች ፡ ሊያሻሽሉት ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፯ ። ስለ ፡ ሐኪም ፡ አላፊነት ።</u>

(፩) በኪን ፡ ጥበብ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ሐኪሙ ፡ ለመታከም ፡ ለተዋዋለው ፡ ሰው ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ።

(፪) ሳይሠራ ፡ ከመቅረቱ ፡ ወይም ፡ ከመሥራቱ ፡ የተነሣ ፡ በአከመው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ሥራ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አጥፊ ፡ ነው ፡ ለመባል ፡ ይቻላል ።

(፫) እንዲሁም ፡ ሕክምና ፡ ሊያደርግለት ፡ የተቀበለውን ፡ ሰው ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ የተወ ፤ በልማድ ፡ መሠረትም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ የሚተካውን ፡ ሰው ፡ ያልሰጠ ፡ ሐኪም ፡ አላፊ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፰ ። የማዳን ፡ ዋስትና ።</u>

ሐኪሙ ፡ ላደረጋቸው ፡ ሕክምና ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ለመስጠት ፡ በግልጽ ፡ በጽሑፍ ፡ ያላፊነትን ፡ ግዴታ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ አይጠየቅም ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፱ ። ግዴታው ፡ የግል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።</u>

(፩) ለአንድ ፡ ሰው ፡ ሕክምናን ፡ ለማድረግ ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ሐኪም ፡ ራሱ ፡ ግዴታዎቹን ፡ መፈጸም ፡ ይገባዋል ።

(፪) ይሁን ፡ እንጂ ፤ በሱ ፡ መሪነትና ፡ ሙሉ ፡ አላፊነት ፡ በረዳቶች ፡ ማሠራት ፡ ይችላል ።

(፫) ከረዳቶቹ ፡ በአንዱ ፡ ጥፋት ፡ ሕክምና ፡ በተደረገለት ፡ ሰው ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡ በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፶ ። በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ኀላፊ ፡ ስለ ፡ መሆን ።</u>

(፩) የበሽተኛዋ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ የበሽተኛው ፡ ሚስት ፡ ወላጆቻቸውና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ብቻ ፡ በታመመው ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርስባቸው ፡ ጉዳት ፡ ሐኪሙን ፡ ካሣ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የበሽተኛው ፡ ሞት ፡ የደረሰው ፡ በሐኪሙ ፡ አስቦ ፡ ጥፋት ፡ ማድረግ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ በነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ በደረሰው ፡ የሕሊና ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ካሣ ፡ አይሰጥም ።

(፫) ምንም ፡ ሟቹ ፡ ለሕይወታቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ነገርን ፡ ይሰጣቸው ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ነበሩ፡ ቢያስረዱም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በበሽተኛው ፡ መሞት ፡ ምክንያት ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ ምንም ፡ የጉ ዳት ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ።

<u>ቁ ፡ ፪ሺ፮፻፶፩ ። ስለ ፡ ሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አላፊነት ። (፩) ስለ ፡ ሕክምናው ፡ አፈጻጸም ።</u>

በሐኪሞች ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ ባሠራቸው ፡ ረዳት ፡ ሠራተኞች ፡ ጥፋት ፡ በበሽተ ኛው ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ፡ ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር፡ ረገድ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

<u>ቁ ፡ ፪ሺ፮፻፶፪ ። (፪) ስለ ፡ ሆቴሉ ፡ ሥራ፡አፈጻጸም፡ጥንቃቄ ።</u>

በሽተኛው ፡ ስለ ፡ ሕክምናው ፡ ጥቅም ፡ በማለት ፡ በሆስፒታሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተመገበና ፡ የተቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለዚሁ ፡ መቀመጥና ፡ ስለዚሁ ፡ መመገብ ፡ አላፊነቱንና ፡ ግዴታዎቹን ፡ የሚመለከት ፡ የሆቴል ፡ ሥራን ፡ ውል ፡ በሚመሩት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

<u>ስለ ፡ ሆቴል ፡ ሥራ ፡ ውል ።</u>

<u>ቁ ፡ ፪ሺ፮፻፶፫።ትርጓሜ።</u>

(፩) የሆቴል ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሆቴልን ፡ ሥራ ፡ የሞያ ፡ ተግባሩ ፡ በማድረግ ፡ ሰውን ፡ ለአንድ ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ሌሊት ፡ ለማ ኖር ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ቤቱ ፡ ላንድ ፡ ወር ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ በውል ፡ የተ ሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ እንጂ ፤ የሆ ቴል ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ አይባልም ።

<u>ቁ ፡ ፪ሺ፮፻፶፬ ። ውሉ ፡ የሚቈይበት፡ጊዜ ።</u>

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የሆቴሎች ፡ ክፍል ፡ ቤቶች ፡ የሚከ ራዩት ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ነው ።

(፪) ሰውዬው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያልተከራየውን ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ባለሆቴሉ ፡ በእ ኩለ ፡ ቀን ፡ እንዲለቅለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፫ ፡ ስለ፡ውል፡ማደስ ።**

ተከራዩ ፡ ወይም ፡ ባለሆቴሉ ፡ ውሉን ፡ ላለመቀጠል ፡ (ላለማርዘም)፡ ሐሳባቸውን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ያላስታወቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባንድ ፡ ደንበኛ ፡ የተያዘ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ላንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተከራየ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፬ ። ተጨማሪ ፡ አገልግሎቶችን፡ስለ፡መስጠት ።**

ቤትን ፡ ከማከራየት ፡ በላይ ፡ ለቤቱ ፡ ተጨማሪ፡ ነገሮችን ፡ በመስጠትና ፡ የቤት፡ ዕቃን፡ በሆቴሉ ፡ ደረጃና ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ መብራትን ፡ የመሳሰለ ፡ ባለሆቴሉ፡ ለተከራየው ፡ ሰው ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፭ ። ስለ ፡ መንገደኛው ፡ ዕቃዎች፡ አጠባበቅ ።**

ተጨማሪ ፡ ዋጋ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ ክፍለ ፡ ቤቱ ፡ ከተከራየበት ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ ጀምሮ ፡ የኪራዩ ፡ ጊዜ ፡ እስካለቀበት ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ባለሆቴሉ ፡ ተከራዩን ፡ ተቀብሎና ፡ ዕቃዎቹንም ፡ ሊጠብቅ ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፮ ። ባለሆቴሉ ፡ስለሚሰጠው፡ዋስትና ።**

(፩) ባለሆቴሉ ፡ ያከራያቸውን ፡ ቤቶችና ፡ ለሁሉ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ክፍሎችን ፡ ለመቀመጫ ፡ ተገቢ ፡ ጤናማና ፡ ጉዳት ፡ የማያመጡ ፡ ለመሆናቸው ፡ ለተከራዩ ፡ ዋስትናውን ፡ ያረጋግጣል ።

(፪) ለተከራዩ ፡ መብል ፡ ወይም ፡ መጠጥ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ጤናማ ፡ ጠባያቸውና ፡ መርዛም ፡ ላለመሆናቸውም ፡ እንዲሁ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፫) አደጋው ፡ የደረሰው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ በማይታለፍ ፡ ኀይል ፡ ወይም፡ በተጎጂው ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ አላፊነቱ ፡ ለመዳን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፯ ። ስለ ፡ ባለመብል ፡ ቤቶችና ፡ ስለ ፡ቡና፡ቤቶች ።**

ባለመብል ፡ ቤቶችና ፡ ባለቡና ፡ ቤቶች ፡ ለሚሰጡት ፡ መብልና ፡ መጠጥ፡ ጤናማ ፡ ለመሆናቸውና ፡ መርዛም ፡ ላለመሆናቸው ፡ ለደንበኞቻቸው ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፰ ። ክፍለ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡ መያዝ ።**

(፩) ለታወቀ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ክፍለ ፡ ቤት ፡ የያዘ ፡ ተከራይ ፡ በባለሆቴሉ ፡ ክፍለ ፡ ቤቱ ፡ የተያዘለት ፡ ለመሆኑ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ባይገባበት ፡ እንኳ ፡ ለዚሁ ፡ ክፍለ ፡ ቤት ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ የሚሆነው ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመኝታ ፡ ክፍሉን ፡ መልቀቁን ፡ ለባለሆቴሉ ፡ አስታውቆና ፡ ባለሆቴሉም ፡ ይህን ፡ ማስታወቂያ፡ ተቀብሎ ፡ የተያዘውን ፡ ክፍለ ፡ ቤት ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ማከራየት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ክፍለ ፡ ቤቱ ፡ የተያዘው ፡ ለብዙ ፡ ቀን ፡ ቢሆንና ፡ የገንዘቡም ፡ አከፋፈል ፡ በሳምንት ፡ ወይም ፡ በወር ፡ ሆኖ ፡ ቢመለከትም ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፈለው ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፩ ። የውል ፡ መፍረስ ።

(፩) ክፍለ ፡ ቤቱን ፡ ለብዙ ፡ ቀን ፡ የተከራየ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ተከራዩ ፡ እሱ ፡ ባለው ፡ ቀን ፡ ያልያዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ይፈርሳል ።

(፪) ከተከራዩ ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ ከሆነው ፡ ሰው ፡ ተከራዩ ፡ መከራየቱን ፡ አልተውም ፡ የሚል ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልደረሰው ፡ በቀር ፡ ባለሆቴሉ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ክፍለ ፡ ቤቱን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ቢያከራይ ፡ አንድም ፡ አላፊነት ፡ አይነካውም ።

(፫) ባለሆቴሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ ለኪራዩ ፡ ዋጋ ፡ በቂ ፡ እስከሚሆንበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለተከራዩ ፡ ክፍለ ፡ ቤቱን ፡ ጠብቆ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፪ ፡ የመያዝ ፡ መብት ።

(፩) ተከራዩ ፡ በሆቴል ፡ ውስጥ ፡ የቈየበትን ፡ ጊዜ ፡ በመገመት ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ እስከ ፡ ከፈለ ፡ ድረስ ፡ ያመጣቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ባለሆቴሉ ፡ መያዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ለነዚሁ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ባለሆቴሉ ፡ ዕቃ ፡ ይዞ ፡ የሚያበድር ፡ ሰው ፡ መብትና ፡ ቀደምትነት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፫ ። የአላፊነት ፡ መሠረት ።

(፩) ደንበኞቹ ፡ በሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ ላስቀመጧቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ባለሆቴሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ደመወዘኛ ፡ አደራ ፡ አስቀማጭ ፡ ይገደዳል ።

(፪) አንድ ፡ ደንበኛ ፤ ዕቃዎቹን ፡ ወደ ፡ ሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ ለማምጣቱ ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ማስረጃ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፬ ። ቍርጥ ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

የባለሆቴሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ፭፻ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በሆነ ፡ ገንዘብ ፡ የተወሰነ ፡ ሆኗል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፭ ። ስላልተወሰነ ፡ አላፊነት ። (፩) በአደራ ፡ ዕቃ ፡ ሲቀመጥ ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ሲገኝ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የባለሆቴሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ የሚሆነው ፤

(ሀ) የተደረገው ፡ ጉዳት ፡ በባለሆቴሉ ፡ ወይም ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ወይም ፡ ከሠራተኞቹ ፡ በአንዱ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ ደንበኛው ፡ ለባለሆቴሉ ፡ በተለይ ፡ በአደራ ፡ በሰጣቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፶፮። (፪) አደራ ፡ ማስቀመጥን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ።

(፩) ባለሆቴሉ ፡ ትክክል ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ በአደራ ፡ ለማስቀመጥ ፡ አልቀበልም ፡ ያላቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ጉዳት ፡ ያገኛቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ የባለሆቴሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ ነው ።

(፪) እንደ ፡ ሆቴሉ ፡ ማዕርግና ፡ እንዳሉት ፡ ክፍሎች ፡ መጠን ፡ ዕቃው ፡ ያለ ፡ መጠን ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ለማኖር ፡ የማይመች ፡ ሁኔታ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለእንቢታው ፡ ትክክል ፡ ምክንያት ፡ ይሆነዋል ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፶፯ ። ኀላፊነት ፡ የሚቀርበት ።

(፩) ኀላፊነቱ ፡ የሚቀረው ፡ ዕቃው ፡ የተሠረቀው ፡ የጠፋው ፡ ወይም ፡ የተበላሸው ፡ በደንበኛው ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ደንበኛውን ፡ በሚጠይቁት ፡ በሚከተሉት ፡ ወይም ፡ እሱን ፡ በሚያገለግሉ ፡ ሰዎች ፡ ጥፋት ፡ መሆኑን ፡ ባለሆቴሉ ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ በዕቃው ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከኀላፊነት ፡ ነጻ ፡ ነው ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፶፰ ። ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታ ።

ደንበኛው ፤ ጉዳቱን ፡ እንዳወቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር ፡ ባለሆቴሉ ፡ ከኀላፊነት ፡ ነጻ ፡ ነው ።

ቍ ፡፪ሺ፮፻፶፱ ። ኀላፊነትን ፡ የሚያስቀር ፡ ስምምነት ።

የባለሆቴሉን ፡ ኀላፊነት ፡ ለማስቀረት ፡ ወይም ፡ ለመቀነስ ፡ የሚደረግ ፡ የውል፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ አይጸናም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፷፡ ሕጉ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ወሰን ።

(፩) ደንበኛው ፡ ዕቃዎቹን ፡ አስቀድሞ ፡ ልኮ ፡ እርሱ ፡ ካልቀረ ፡ በቀር ፡ ዕቃዎቹ፡ በሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ ከገቡ ፡ ወዲህ ፡ የዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆቴሉ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በሆቴሉ ፡ ለደንበኞች ፡ በሆኑ ፡ ቦታዎች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ እንደ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ አቶሞቢሎች ፡ በሕይወት ፡ ያሉ ፡ እንስሳዎች ፡ ዕቃዎችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፷፩። እንደ ፡ ሆቴሎች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ቤቶች ።

የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ደንቦች ፡ በሆስፒታል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በዕረፍት ፡ ቤቶች ፡ በሕዝብ ፡ መደሰቻዎች ፡ በመታጠቢያ ፡ ቤቶች ፡ በኪራይ ፡ በሚመገቡ ፡ ሰዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ በምግብ ፡ ቤቶች ፡ አልጋ ፡ ባለባቸው ፡ የማደሪያ ፡ (የባር) ፡ ክፍል ፡ ቤቶች ፡ ለሕዝብ ፡ በተሠሩ ፡ በረቶችና ፡ ሌሎች ፡ እነዚሁን ፡ በመሳሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ በሚካሄዱ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

BACK



## ምዕራፍ ፡ ፯ ።
## አትሞ ፡ የማውጣት ፡ (ፐብሊሺንግ) ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፪ ። ትርጓሜ ።**

አትሞ ፡ የማውጣት ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ደራሲ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ባንድ ፡ የድርሰት ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ግዙፍነት፡ የሌለውን ፡ የባለሀብትነት ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ መብቶች ፡ በከፊል ፡ አትሞ ፡ አውጪ ፡ (ፐብሊሺር) ፡ ተብሎ ፡ ለሚጠራው ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ የሚሰጥበት ፡ አትሞ ፡ አውጪውም ፡ ድርሰቱን ፡ ለማተም ፡ ለማሳየት ፡ ወይም ፡ ለማባዛት ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ለመንዛት ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፫ ። የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

ሥራው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ላንድ ፡ ሌላ ፡ አትሞ ፡ አውጪ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ድርሰቱን ፡ ደራሲው ፡ ዐውቆት ፡ ለሕዝብ ፡ ታትሞ ፡ ተገልጾ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ደራሲ ፡ ውሉን ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ አትሞ፡ ለሚያወጣው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፬ ። የውሉ ፡ ዐይነት ፡ (ፎርም)።**

ሥራውን ፡ ለማባዛት ፡ ወይም ፡ ለማሳየት ፡ ደራሲው ፡ አትሞ፡ ለሚያወጣው ፡ የሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፭ ። ወደፊት ፡ በሚወጡት ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

### ፩ ፡ ወሰን ።

(፩) አእምሮ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ በመመልከት ፡ ተግባር ፡ ከሁለት ፡ ዓመት፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በደራሲው ፡ ለመፈጸም ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸው፡ ከታወቁ ፡ ደራሲው ፡ ገና ፡ ያላለቀ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የተለየ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚዋዋለው ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ ወሰን ፡ አልፎ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡት ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ደራሲው፡ መብቶቹን ፡ ለማስተላለፍ ፡ የተዋዋለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምንም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል፡ ቃል ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ አትሞ ፡ ከሚያወጣው ፡ የተቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ አስቀርቶ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ፡ ማፍረስ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፮ ። (፪) አትሞ ፡ አውጪው ፡ ያለው ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ።**

(፩) ይፍረስ ፡ ያለው ፡ ደራሲ ፡ ውሉ ፡ ከፈረሰበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አትሞ ፡ ማውጣትን ፡ ተዋውሎት ፡ ለነበ

BACK



ረው ፡ ሰው ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በፊት ፡ የቀደምትነት ፡ መብቱን ፡ ሊሰጠው ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) እነዚህንም ፡ መብቶች ፡ ለማግኘት ፡ ሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ ያቀረቡለትን ፡ የውለታ ፡ ሁኔታዎች ፡ ለአታሚው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) በቀደምትነት ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ መፈለጉን ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካላስታወቀ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ይቀርበታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፯።የውሉ፡ውጤት።

(፩) በዚህ፡አንቀጽ ፡ በተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ የውሉ ፡ አፈጻጸም፡ እንደሚያስገድደው ፡ መጠን ፡ ደራሲው ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብ ቶች ፡ ለአትሞ ፡ አውጪው ፡ ያስተላልፍለታል ።

(፪) እነዚህን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃልን ፡ በግልጽ ፡ ለመጻፍ ሕጉ ፡ ያልከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ እነዚህን ፡ ውሳኔዎች ፡ ለመለ ወጥ ፡ ይችላሉ ።

(፫) የሚያጠራጥር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማተም ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ለደራሲው ፡ ጥቅም ፡ እንደሚሆኑ ፡ የሚተረጐሙ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፰ ። በጠባቡ፡ስለ፡መተርጐም ።

(፩) ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሥራውን ፡ እንዲሠራ ፡ ለአትሞ ፡ አውጪው ፡ የተ ሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ በጠባቡ ፡ መተርጐም ፡ አለበት ።

(፪) አትሞ ፡ አውጪው ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከተው ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ ውጭ ፡ በሌላ ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፸፱ ። በሥራው፡ለመጠቀም፡የተፈቀደ፡የአሠራር፡ዐይነት ።

(፩) የውሉ ፡ ቃሎች ፡ ምንም ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ቢነገሩም ፡ እንኳ ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ አስበውት ፡ በነበረ ፡ ወይም ፡ ሊያስቡት ፡ ይገባቸው ፡ በነበረ ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ አሠራር ፡ ለመጠቀም ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በሚገምተው ፡ ዐይነት ፡ ማመዛዘን ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፹።መለዋወጥና፡መተርጐም።

አንድ ፡ ሥራን ፡ ለማባዛት ፡ ወይም ፡ ለማሳየት ፡ የተሰጠ ፡ ፈቃድ ፡ መለዋወጥን፡ ወይም ፡ እንዲተረጐም ፡ መፍቀድን ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ ማስማማትን ፡ አይ ፈቅድም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፺፩ ። በራዲዮ፡የተነገሩትን፡ሥራዎች፡ስለ፡መመዝገብ ።**

አንድ ፡ ሥራ ፡ በራዲዮ ፡ እንዲነገር ፡ የተሰጠ ፡ ፈቃድ ፤ በራዲዮ ፡ የተነገረውን ፡ ሥራ ፡ ድምፅን ፡ ወይም ፡ ሥዕልን ፡ ተቀብለው ፡ ለማስቀረት ፡ በሚችሉ ፡ መሣሪያ ዎች ፡ እንዲመዘገብ ፡ መፍቀድን ፡ አይጨምርም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፺፪ ። የተለያዩ፡ሥራዎችና፡ሙሉ፡የሆኑ፡ሥራዎች ።**

(፩) ያንድ ፡ ደራሲ ፡ ሥራዎችን ፡ ለየብቻ ፡ አትሞ ፡ የማውጣት ፡ መብት ፡ ሁሉ ንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ የማውጣትን ፡ መብት ፡ አይጨምርም ።

(፪) ያንድ ፡ ደራሲን ፡ ሙሉ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ከሥራዎች ፡ አንዱን ፡ ዐይነት፡ ክፍል ፡ አትሞ ፡ የማውጣት ፡ መብት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ የያዙትን ፡ ለየ ብቻ ፡ የማውጣትን ፡ መብት ፡ አትሞ ፡ ለሚያወጣው ፡ አይሰጠውም ።

**ቍ፡፪ሺ፮፻፺፫።የደራሲው፡መድንነት።**

አትሞ ፡ ከማውጣት ፡ ውል ፡ የተነሣ ፡ ደራሲው ፡ አትሞ ፡ ለሚያወጣው ፡ ሰው፡ የሚያስተላልፋቸው ፡ የድርሰት ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ መብቶች ፡ እንዳሉትና ፡ እነዚህ ንም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ባለመብት ፡ ለመሆኑ ፡ አትሞ ፡ ለሚያወጣው ፡ ሰው ፡ መድን፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፺፬ ። አትሞ ፡ ለሚያወጣው፡ሰው፡የተላለፈ፡መብት ።**

(፩) አትሞ ፡ የሚያወጣው ፡ ሰው ፡ አትሞ ፡ ያወጣቸው ፡ ድርሰቶች ፡ እስካለቁ ፡ ድረስ ፡ ደራሲው ፡ ሥራውን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ አትሞ ፡ የሚያወጣውን ፡ ሰው ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ ሊያዝበት ፡ አይችልም ።

(፪) በኅብረት ፡ ከተደረሰ ፡ ድርሰት ፡ ወይም ፡ ከተጻፈ ፡ ቃል ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ የማውጣቱ ፡ ተግባር ፡ ከተፈጸመ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ካላለፈ ፡ በቀር ፡ ደራሲው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማውጣት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፺፭ ። በሁለት ፡ አትሞ፡አውጪዎች፡መካከል፡ስለሚነሣ ፡ ክርክር ።**

(፩) አንድ ፡ ደራሲ ፡ መብቶቹን ፡ ላንድ ፡ አትሞ ፡ አውጪ ፡ ካስተላለፈ ፡ በኋላ ፡ እነዚሁኑ ፡ መብቶች ፡ ለሌላ ፡ አትሞ ፡ አውጪ ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለ ተኛው ፡ ባለውል ፡ የመጀመሪያውን ፡ ውል ፡ ካላወቀ ፡ በቀር ፡ የሚያደርገው ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

(፪) ደራሲው ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ተዋዋዮች ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፺፮።ድርሰቱን፡አትሞ፡ስለ፡ማውጣት።**

(፩) አትሞ ፡ አውጪው ፡ ድርሰቱን ፡ ሳያሳጥር ፡ ሳይጨምር ፡ እንዲሁም ፡ ሳይለዋ ውጥ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ፎርም ፡ ማውጣት ፡ አለበት ።

(፪) ድርሰቱንም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያውቀውና ፡ የተለመዱትንም ፡ የማስታወቂያ ፡ አሠራር ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፫) የመሸጫውንም ፡ ዋጋ ፡ ይወስናል ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፹፯ ። ደራሲው ፡ ስለሚያደርገው ፡ እርማት ፡ (ማረም) ።

(፩) ያትሞ ፡ አውጪውን ፡ ጥቅሞች ፡ ካላበላሹ ፡ ወይም ፡ ኀላፊነትን ፡ የሚጨምርበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ደራሲው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ድረስቱን ፡ ለማረምና ፡ ለማሻሻል ፡ ይችላል ።

(፪) በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ ያደረጋቸውን ፡ ወጪዎች ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፹፰ ። እንደ ፡ ገና ፡ አትሞ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

አትሞ ፡ አውጪው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አትሞ ፡ ከማውጣቱ ፡ በፊት ፡ ደራሲው ፡ ድርሰቱን ፡ ለማሻሻል ፡ እንዲችል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፹፱ ። እንዲታተሙና ፡ እንዲወጡ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ድርሰቶች ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ ለማውጣት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ በመጀመሪያው ፡ አትሞ ፡ ያወጣቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) አትሞ ፡ ለማውጣት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቅጂዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ውሉ ፡ ለይቶ ፡ ያላመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብዛቱን ፡ የሚወስነው ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ ነው ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺ ። ታትሞ ፡ የወጣው ፡ ስለ ፡ ማለቁ ።

(፩) በብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያተመ ፡ ወይም ፡ የሚታተመውን ፡ ሁሉ ፡ ድርሰት ፡ ለማውጣት ፡ ላትሞ ፡ አውጪው ፡ ውሉ ፡ የፈቀደለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደራሲው ፡ ስለ ፡ ድርሰቱ ፡ በመጨረሻው ፡ ታትሞ ፡ የወጣው ፡ ካለቀ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አትሞ ፡ እንዲያወጣ ፡ ያንድ ፡ ዓመት ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

(፪) በዚሁ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡ ካልፈጸመ ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ መብቶቹን ፡ ያጣል ።

(፫) ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ፡ ፪ሺ፮፻፺፩ ። ተከታትለው ፡ ታትመው ፡ ስለሚወጡ ፡ ድርሰቶች ፡ የሚደረግ ፡ የውል ፡ ስምምነት ።

(፩) አትሞ ፡ አውጪው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አትሞ ፡ ለማውጣት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚከተሉት ፡ አንዳንድ ፡ ታትመው ፡ በሚወጡት ፡ ላይ ፡ የመጀመሪያው ፡ አትሞ ፡ ማውጣት ፡ ስምምነቶች ፡ ቃል ፡ እንዲሠራባቸው ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በተለይም ፡ የደራሲውን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሚመለከቱ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ በዚሁ ፡ ይፈጸማሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፶፪ ። የደራሲው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ።

(፩) መሠረቱ ።

(፩) የሥራውን ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ ለመተው ፡ ስምምነት ፡ አድርጓል ፡ ለማለት ፡ አካባቢው ፡ ሁኔታዎቹ ፡ በሚፈቅዱበት ፡ ጊዜ ፡ ታትሞ ፡ የሚወጣን ፡ ድርሰት ፡ የሰጠ ፡ ደራሲ ፡ ለሥራ ፡ ዋጋ ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ተዋዋዮቹ ፡ ያልተስማሙበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለደራሲው ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ በርትዕ ፡ ዳኞች ፡ ይወስናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፶፫። (፪) ያለ ፡ ዋጋ ፡ የሆኑ ፡ ቅጂዎች ።

(፩) ደራሲው ፡ የተወሰነ ፡ ብዛት ፡ ያለውን ፡ የድርሰቱን ፡ ቅጂዎች ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ የነዚሁኑ ፡ ቅጂዎች ፡ ብዛት ፡ ዳኞች ፡ በርትዕ ፡ ይወስናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፶፬ ። (፫) ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ድርሰቱ ፡ ለመሸጥ ፡ ዝግጁ ፡ ሲሆን ፡ የደራሲው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

(፪) ከሽያጩ ፡ ውጤት ፡ በሙሉው ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የደራሲውን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አትሞ ፡ አውጪው ፡ በተስማሙባቸው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሽያጩን ፡ ውጤቶች ፡ ለደራሲው ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

(፫) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ ያትሞ ፡ አውጪው ፡ ሒሳብ ፡ በያመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ወር ፡ ለደራሲው ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፶፭ ። ስለ ፡ ድርሰቱ ፡ መጥፋት ፤ (፩) ታትሞ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ።

(፩) ድርሰቱ ፡ ለአሳትሞ ፡ አውጪው ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ታትሞ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በድንገተኛ ፡ ነገር ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ ለደራሲው ፡ የሥራ ፡ ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ደራሲው ፡ የጠፋው ፡ ድርሰት ፡ ቅጂው ፡ በጁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአትሞ ፡ አውጪው ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፫) እንዲህ ፡ ካልሆነም ፡ ድርሰቱ ፡ የማያስቸግር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አትሞ ፡ አውጪውም ፡ ሲጠይቀው ፡ ደራሲው ፡ የሚገባ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ድርሰቱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፶፮ ። (፪) ታትሞ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ።

(፩) አትሞ ፡ አውጪው ፡ ያሰናዳው ፡ ከታተመ ፡ በኋላ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በድንገተኛ ፡ ነገር ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ የጠፉትን ፡ ቅጂዎች ፡ በኪሣራው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማሠራት ፡ መብት ፡ አለው ።

BACK



(፪) ኪ.ሣራው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሳይሆን ፡ ለማድረግ ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትሞ ፡ አውጪው ፡ እነዚሁኑ ፡ ቅጂዎች ፡ መተካት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፰ ። ስለ፡ውሉ፡ቀሪነት ።

(፩) ሥራው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ደራሲው ፡ የሞተ ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ሳይኖርበት ፡ ለመጨረስ ፡ ያልተቻለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማተሙ ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) ያትሞ ፡ አውጪው ፡ መሞት ፡ ወይም፡ የደረሰበት ፡ የችሎታ ፡ ማጣት ፡ ውሉን ፡ ቀሪ ፡ አያደርገውም ።

(፫) አትሞ ፡ አውጪው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መክሠሩ ፡ በሚገለጽበት ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ያልደረሰባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመፈጸም ፡ ዋስትና ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ደራሲው ፡ ሥራውን ፡ ለሌላ ፡ አትሞ ፡ አውጪ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

## አንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ።

## የዕቃ ፡ ጥበቃን ፡ በዕቃ ፡ መገልገልን ፡ ወይም ፡ በዕቃ ፡ መጠቀመን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፱ ። የዚህ ፡ አንቀጽ፡ደንብ፡አፈጻጸም ።

(፩) አንድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ እንዲጠቀምበት፡ ከተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ በውል ፡ ተስማምቶ ፡ በመረከቡ ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ በእጁ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ከተዋዋዩ ፡ ጋራ ፡ በሚኖረው ፡ ግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከቱት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ አሉት ።

(፪) በተንቀሳቃሹ ፡ ዕቃ ፡ ባለቤትና ፡ ዕቃው ፡ በእጁ ፡ በሚገኘው ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፤ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፤ ከማነኛውም ፡ ውል ፡ በሆነውም ፡ ነገር ፡ እንዲሁ ፡ እነዚሁ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፱ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ።**

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ኪራይ ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ በተጻፈው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጸዋል ።

(፪) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መገልገልና ፡ መጠቀም ፡ ለሌላ፡ሰው ፡ የተሰጠው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ያገልግሎት ፡ ትውስትን ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳ ። ባለቤት ።**

(፩) ባለሀብት ፡ (ባለቤት) ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ዕቃውን ፡ አሳልፎ ፡ በባለይዞታው ፡ እጅ ፡ እንዲገኝ ፡ አድራጊውን ፡ ሰው ፡ ለማመልከት ፡ ነው ።

(፪) ባለይዞታው ፡ በዚህ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ አለኝ ፡ የሚለው ፡ መብት ፡ ከባለሀብትነት ፡ መብት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፩ ። የማስረከብ ፡ ግዴታ ።**

ባለሀብቱ ፡ ዕቃውን ፡ ለባለይዞታው ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ የዕቃው ፡ ተፈጥሮ ፡ ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ ሊሰጥ ፡ በሚችልበት ፡ ዐይነት ፡ እንዲያገለግል ፡ ከተጨማሪው ፡ ጋራ ፡ አድርጎ ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፪ ። ወደ ፡ ሽያጭ ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መምራት ።**

የዕቃው ፡ ማስረከቢያ ፡ ስፍራና ፡ ዘመን ፡ እንዲሁም ፡ የዕቃው ፡ መለዋወጫ ፡ የሆኑትን ፡ ተጨማሪ ፡ ነገሮች ፡ የመጥቀስ ፡ ጉዳዮች ፡ የሚከናወኑት ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ደንብ ፡ በወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፫ ። በዕቃው ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ጉድለት ። (፩) ስለ ፡ ውል ፡ መፍረስ ።**

(፩) ዕቃው ፡ ተላልፎ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፤ ለባለይዞታው ፡ ሊያገለግል ፡ የነበረውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ሊያሳጣው ፡ የሚችል ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ለማኖር ፡ ወይም ፡ ለመጠበቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ የሚያመጣበት ፤ ወይም ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ወጪ ፡ የሚያደርስበት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ባለይዞታው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ዕቃው ፡ ጉድለት ፡ የተገኘበት ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ የተገለጸበት ፡ ተላልፎ ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ ለባለይዞታው ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፫) የውሉ ፡ ስምምነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ባለሀብቱ ፡ ይህ ፡ ጉድለት ፡ መኖሩን ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ይገባው ፡ የነበረ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለይዞታው ፡ በዕቃው ፡ አገልግሎት ፡ ማግኘት ፡ ይገባው ፡ የነበረው ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ በግምት ፤ ውስጥ ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፬ ። (፪) ኪሣራ ።

(፩) ባለሀብቱ ፡ ዕቃውን ፡ ባስረከበበት ፡ ጊዜ ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ የሚገባው ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ ይህ ፡ ጕድለት ፡ መኖሩንም ፡ ለባለይዞታው ፡ ሳያስታውቅ ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጕድለቱ ፡ በባለይዞታው ፡ ላይ ፡ ላደረሰበቸ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ጕድለቱ ፡ የደረሰው ፡ ውሉ ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ የደረሰውም ፡ ከባለሀብቱ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ አፈጻጸሙ ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፭ ። (፫) የውሉ ፡ ስምምነት ፡ መድን ።

ባለሀብቱ ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ እንዳረጋገጠው ፡ ሳይሆን ፤ አለው ፡ የተባለው ፡ ጠባያዊ ፡ ዐይነት ፡ ያልነበረው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ የዕቃው ፡ ጕድለትም ፡ ላደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ባለይዞታው ፡ ኪሣራ ፡ ሊጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፮ ። (፬) ባለይዞታው ፡ ያወቃቸው ፡ ጕድለቶች ።

(፩) የውሉ ፡ ስምምነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፤ ባለይዞታው ፤ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ጕድለት ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ የሚያውቅ ፡ መሆኑን ፡ ባለሀብቱ ፡ ካስረዳ ፤ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተገኘው ፡ ጕድለት ፡ አላፊ ፡ መድን ፡ አይሆንም ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ባለሀብቱ ፡ የሰጠው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ዋስትና ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፯ ። (፭) አደገኛ ፡ ጕድለት ።

(፩) ዕቃው ፡ በባለይዞታው ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ በጤንነቱ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ በጤንነታቸው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ ጕድለት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕቃው ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ያወቀው ፡ የውሉን ፡ ስምምነት ፡ ባደረገበት ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ ቀሪ ፡ ነው ፡ (ዋጋ ፡ የለውም ) ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፰ ። (፮) አላፊነት ፡ የለብኝም ፡ ተብሎ ፡ ስለሚደረግ ፡ የውል ፡ ቃል ።

ባለሀብቱ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጕድለት ፡ ሳይገልጽ ፡ የደበቀው ፡ በማታለል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የዕቃው ፡ ጕድለቶች ፡ ለባለይዞታው ፡ የሚሰጡትን ፡

ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያጠፉበት ፡ (የሚያፈርሱበት) ፡ ሆነው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለሀብቱ ፡ በዕቃው ፡ ጉድለቶች ፡ ምክንያት ፡ ከሚደርስበት ፡ አላፊነት ፡ ለመዳን ፡ አላፊነቱን ፡ የተወሰነ ፡ ለማድረግ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የጠቀሰው ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ (ዋጋ ፡ የለውም) ፡ ቀሪ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፱ ። ሰላማዊ ፡ መጠቀም ።**

ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ በሚቈይበት ፡ ዘመን ፤ ባለይዞታው ፡ በዕቃው ፡ ሰላማዊ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ ባለሀብቱ ፡ አላፊ ፡ መድን ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፲ ። በዕቃው ፡ ላይ፡ስለሚደርሰው ፡ መለወጥ ።**

ባለሀብቱ ፡ የዕቃውን ፡ የአገልግሎት ፡ ጥቅም ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ በባለይዞታው ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪ ፡ ሊያመጣ ፡ የሚችል ፡ ማንኛውም ፡ የመለወጥ ፡ ጠባይ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ እንዲደርስ ፡ ማድረግ ፡ አይገባውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፲፩ ። ድንገተኛ፡ሁከት ።**

(፩) በዕቃው ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለን ፡ የማይሉ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ ዕቃ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚያደርሱት ፡ ሁከት ፡ ባለሀብቱ ፡ አላፊ ፡ መድን ፡ እንዲሆን ፡ አይገደድም ።

(፪) ባለይዞታው ፡ በእነዚህ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፲፪ ። ግዴታና፡ግብር ።**

በዕቃው ፡ ላይ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ግዴታና ፡ የሚከፈለውን ፡ ግብር ፡ የሚችል ፡ ባለሀብቱ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፲፫ ። ዕቃውን ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ስለ፡ማኖር ።**

(፩) ባለይዞታው ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ጥበቃና ፡ ስለ ፡ ማኖሩ ፡ ጕዳይ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ባለሀብቱ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፡ የዕቃውን ፡ አገልግሎት ፡ ለሌላ ፡ ጕዳይ ፡ ሊያውለው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፲፬ ። ለባለሀብቱ ፡የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

ለዕቃው ፡ መልካም ፡ አያያዝና ፡ ጥበቃ ፡ ባለሀብቱ ፡ እንዲደርስ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆኑበትን ፡ ጕዳዮች ፡ እንደ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆኑ ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች ፡ ያሉትን ፡ ነገሮችና ፡ ድንገት ፡ የሚገኙበትን ፡ ጕድለቶች ፡ በሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በኩል ፡ የሚደርስበትን ፡ የመውሰድ ፡ የሁከት ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ወዲያውኑ ፡ የዕቃው ፡ ባለይዞታ ፡ ለባለሀብቱ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፫ ። ዕቃውን ፡ ለማኖርና ፡ በመልካም ፡ አያያዝ ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ወጪ ።**

(፩) ዕቃውን ፡ ለማኖርና ፡ ለመጠበቅ ፡ ላያያዙ ፡ ወጪ ፡ ማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ወጪ ፡ መቻል ፡ ያለበት ፡ ባለይዞታው ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ወጪ ፡ ማስፈለጉን ፡ ለባለሀብቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባዋል ።

(፪) ለዚሁ ፡ ጒዳይ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ ወጪ ፡ አስፈልጎ ፡ ባለይዞታው ፡ ይህን ፡ አስፈላጊ ፡ ወጪ ፡ እንዳደረገ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለባለሀብቱ ፡ አስታውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያወጣው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፬ ።የባለሀብቱ፡ተቈጣጣሪነት ።**

(፩) ባለይዞታው ፡ እሱን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ በሚገባ ፡ የሚፈጽምና ፡ የማይፈጽም ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ባለሀብቱ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህ ፡ ምርመራ ፡ ግን ፡ በባለይዞታው ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሁከትና ፡ የማበሳጨት ፡ ስሜት ፡ በማያደርስበት ፡ ሁኔታ ፡ ትክክለኛነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፭ ። በዕቃው ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ስለሚል ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ።**

(፩) ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ዕቃው ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለይዞታው ፡ ይህን ፡ ጒዳይ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለባለሀብቱ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ፤ ሳያስታውቅ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ።

(፪) ይህም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ክርክሩ ፡ በከሳሹና ፡ በባለሀብቱ ፡ መካከል ፡ እንዲፈጸምና ፡ ባለይዞታው ፡ ከነገሩ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ዕቃውን ፡ ዳኞች ፡ ባዘዙት ፡ ሁኔታ ፡ ባመለከቱት ፡ ስፍራ ፡ በባለሀብቱ ፡ ኪሣራ ፡ መልሶ ፡ በማስረከብና ፡ በማስቀመጥ ፡ በውሉ ፡ ከገባበት ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፮ ። መልሶ፡የመስጠት፡ግዴታ ።**

(፩) ባለይዞታው ፡ ዕቃውን ፡ መልሶ ፡ መስጠት ፡ የሚገባው ፡ በተረከበበት ፡ ጊዜ፡ በነበረበት ፡ ሁኔታና ፡ በተረከበበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

(፪) በተረከበበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ ይገኝ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሚታወቀው ፡ ተዋዋዮች ፡ ወገኖች ፡ ስምምነቱን ፡ ሲያደርጉ ፡ በሰጡት ፡ ዝርዝር፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለይዞታው ፡ ዕቃውን ፡ በተረከበ ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሆኖ ፡ ይታሰባል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፱ ። ከባለይዞታው ፡ የተወሰደበት ፡ ዕቃ ።**

(፩) ራሱን ፡ ተጠያቂ ፡ በማያደርገው ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያት ፡ ዕቃው ፡ ከባለይዞታው ፡ ላይ ፡ ተወስዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከመመለስ ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ ይወጣል ።

(፪) ይህ ፡ ዕቃ ፡ ከእጁ ፡ የወጣበትን ፡ ምክንያትና ፡ ባለይዞታ ፡ መሆኑ ፡ የቀረበትን ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ወዲያውኑ ፡ በፍጥነት ፡ ለባለሀብቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባዋል ።
ሳያስታውቅ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ይህ ፡ ዕቃ ፡ ከባለይዞታው ፡ ስለ ፡ ተወሰደበት ፡ በምትኩ ፡ የሚሰጠውን ፡ ልዋጭ ፡ ዕቃ ፡ የመቀበል ፡ መብትና ፡ በባለይዞታው ፡ መብት ፡ ተተክቶ ፡ ባለገንዘቡ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹ ። የዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ። (፩) ጥቅም ፡ ያለው ፡ ጥበቃ ።**

(፩) ባለይዞታው ፡ ዕቃውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ዋጋ ፡ ይከፈለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም፡ እንዲገለገልበት ፡ ተፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ዕቃ ፡ በመገልገል ፡ እርግጠኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚያገኝበት ፡ ሲሆን ፡ ዕቃውን ፡ ከተረከበ ፡ በኋላ፡ ቢጠፋ ፡ ወይም ፡ ቢበላሽ ፡ ባለይዞታው ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) ዕቃው ፡ የጠፋው ፡ ወይም ፡ የተበላሸው ፡ በዕቃው ፡ እንዲገለገልበት ፡ አሳልፎ ፡ በሰጠው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በተለይ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ለጠፋው ፡ ወይም ፡ ለተበላሸው፡ ዕቃ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፩ ። (፪) የአላፊነቱ ፡ ወሰን ።**

(፩) ባለይዞታው ፡ አላፊነቱ ፡ የሚቀርለት ፡ የዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ የደረሰው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ለዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ ለመበላሸቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ከእርጅና ፡ ወይም ፡ ከዕቃው ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ባስረዳ ፡ ጊዜ ፡ ከአላፊነት ፡ ለመዳን ፡ ይችላል ።

(፫) ዕቃው ፡ በሚሰጠው ፡ መጠነኛ ፡ አገልግሎት ፡ በመጠቀም ፡ ወይም ፡ ለዕቃው ፡ መገልገያ ፡ በተፈቀደው ፡ ተገቢ ፡ ሁኔታ ፡ ሲገለገልበት ፡ ቢበላሽ ፡ ባለይዞታው ፡ አላፊነት ፡ አያገኘውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፪ ። (፫) ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ጥበቃ ።**

(፩) ባለይዞታው ፡ በዕቃው ፡ ምንም ፡ የማይጠቀምበት ፡ ሲሆንና ፡ ጥበቃውንም ፡ የሚያከናውነው ፡ በፍጹም ፡ ለባለሀብቱ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕቃው ፡ የጠፋው ፡ ወይም ፡ የተበላሸው ፡ ራሱ ፡ ባደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ካልሆነና ፡ ወይም ፡ ለባለሀብቱ ፡ እንዲመለስ ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላ ፡

ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ በአላፊነት ፡ አያስጠይቀውም ።

(፪) የዕቃውን ፡ አጠባበቅና ፡ አያያዝ ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ ዕቃ ፡ አጠባበቅና ፡ አያያዝ ፡ አድርጎ ፡ ከመጠበቅ ፡ የተቀነሰ ፡ ጥንቃቄ ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ባለይዞታው ፡ ማንኛውም ፡ አላፊነት ፡ አይደርስበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፳፫ ። ማስጠንቀቂያ ፡ የደረሰው ፡ ባለይዞታ ።

(፩) ባለይዞታው ፡ ዕቃውን ፡ እንዲመልስ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ቢደርሰውም ፡ እንኳ ፡ ዕቃውን ፡ ቢመልስም ፡ ባይመልስም ፡ ከመጥፋት ፡ ወይም ፡ ከመበላሸት ፡ ለማዳን ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ካስረዳ ፤ እንዲያውም ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለባለሀብቱ ፡ እንደ ፡ መለሰ ፡ ያህል ፡ የሚገመት ፡ ከሆነ ፡ በአላፊነት ፡ መጠየቁ ፡ ይቀርለታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፳፬ ። ለዕቃው ፡ የተደረገለት ፡ ማሻሻል ፡(፩)ኪሣራ ፡ የመቀበል ፡ መብት ።

(፩) ባለይዞታው ፡ ለዕቃው ፡ ስላደረገው ፡ የማሻሻል ፡ ሥራ ፡ ማንኛውንም ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ቢሆንም ፡ ለዕቃው ፡ መሻሻል ፡ የተደረገው ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመው ፡ በባለሀብቱ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለይዞታው ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ወጪ ፡ ያደረገውን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ለባለሀብቱ ፡ በሚያስረክብበት ፡ ጊዜ ፡ የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ ከፍተኛ ፡ ለማድረግ ፡ የቻለው ፡ በመታደሱ ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ የዚህኑ ፡ ግምት ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ዝቅተኛ ፡ ሒሳብ ፡ ድረስ ፡ መልሶ ፡ ገቢ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ባለሀብቱን ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፳፭ ። (፪) መቻቻልና ፡ አንሥቶ ፡ የመውሰድ ፡ መብት ።

(፩) ባለይዞታው ፡ ማንኛውም ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ባይኖረውም ፡ እንኳ ፡ የራሱን ፡ አላፊነት ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ በሱ ፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ያጐደለውን ፡ የዕቃ ፡ ዋጋና ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ሊያድስ ፡ ከሚገድብት ፡ ወጪ ፡ በቀር ፡ ያለውን ፡ የሒሳብ ፡ ግምት ፡ ሊያቻችል ፡ ይችላል ።

(፪) በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ ባለይዞታው ፡ ለዕቃው ፡ ማሻሻያ ፡ ያደረገው ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ከላዩ ፡ ተለይቶ ፡ ቢወሰድ ፡ በዋናው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የማያደርስበት ፡ ከሆነ ፡ የጨመረውን ፡ አንሥቶ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፳፮ ። በመያዣ ፡ የማቈየት ፡ መብት ።

(፩) ባለይዞታው ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፤ ለመጠየቅ ፡ የተሰጠውንና ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባውን ፡ ሒሳብ ፡ ባለሀብቱ ፡ አጠናቆ ፡ እስኪከፍለው ፡ ድረስ ፡ ዕቃውን ፡ ሳይመልስ ፡ ለዚሁ ፡ መብቱ ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ለሱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡ በመጠየቅ ፡ እስኪከፈለኝ ፡ ድረስ ፡ ዕቃውን ፡ አልመልስም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፫) ለባለይዞታው ፡ የምከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የለብኝም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚበቃ ፡ ዋስ ፡ ሰጥቶ ፡ ዕቃው ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ዕቃ ፡ ማከራየት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፮ ። ትርጓሜ ።**

ያንድ ፡ ዕቃ ፡ ኪራይ ፡ ሲባል ፡ አከራይ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተከራይ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ሁለተኛ ፡ ወገን ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ እየተጠቀመ ፡ ለዚሁ ፡ ልውጫ ፡ ኪራይ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚስማሙበት ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፯ ። ኪራይና ፡ ሽያጭ ።**

(፩) የተከራየው ፡ ነገር ፡ ባለሀብትነት ፡ የአከራዩ ፡ ሆኖ ፡ ቈይቶ ፡ የውሉ ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሲፈጸም ፡ ላከራዩ ፡ ይመለስለታል ።

(፪) ተከራዩ ፡ ለተከራየው ፡ ዕቃ ፡ ለተወሰኑ ፡ የመከፈያ ፡ ጊዜያቶች ፡ ኪራዩን ፡ ሲከፍል ፡ ቈይቶ ፡ የዕቃው ፡ ባለቤት ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ተጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተዋዋዮቹ ፡ ውሉን ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ነው ፡ ቢሉትም ፡ እንኳ ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፰ ። ክራይና ፡ ትውስት ።**

በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ የኪራይ ፡ ገንዘብ ፡ አልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተውሶ ፡ ዕቃ ፡ ጕዳይን ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፱ ። ከመጠን ፡ አሳልፎ ፡ ስለ ፡ መጠቀም ።**

(፩) ተከራዩ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በተከራየው ፡ ዕቃ ፡ ያላገባብ ፡ በመገልገሉ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሊታደስ ፡ የማይችል ፡ ጉዳት ፡ ይደርስበታል ፡ ተብሎ ፡ የሚ

ያሠጋ ፡ ሆኖ ፡ የታየ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ ፡ ውሉ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲ ፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከመጠየቁም ፡ በፊት ፡ ጉዳት ፡ ደርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የውሉ ፡ መፍ ረስ ፡ የሚያጎዳው ፡ ሲሆን ፡ አከራዩ ፡ ኪሣራም ፡ ጭምር ፡ የመጠየቅ ፡ መብት፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፩ ። የዕቃው ፡ ጠበቃ ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ዕቃውን ፡ በመልካም ፡ አያያዝ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) የዚህንም ፡ የጠበቃ ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ራሱ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፪ ። የኪራይ ፡ አከፋፈል ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ለኪራይ ፡ መክፈያ ፡ በየተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነው ፡ ዐይነት ፡ ኪራዩን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) ስለ፡ ኪራዩ ፡ አከፋፈል ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ስምምነት ፡ የሌለ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ተቃራኒ ፡ ልማድ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኪራዩ ፡ ሒሳብ ፡ የሚከፈለው ፡ በየተ ወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፫ ። ክፍያውን ፡ ስለ ፡ ማዘግየት ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ሊከራይ ፡ መክፈያ ፡ የተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ክፍያ ውን ፡ ያዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ ያሥር ቀን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቶት፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ ውሉ ፡ ቀሪ ፡ ይሆ ናል ፡ ብሎ ፡ ለተከራዩ ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ቀኑም ፡ የሚቈጠረው ፡ ለተከራዩ ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ ከደረሰለት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፬ ። ተከራይቶ ፡ ማከራየት ።**

ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተከራዩ ፡ አከራዩን ፡ ሳያስፈ ቅድ ፡ የተከራየውን ፡ ዕቃ ፡ አሳልፎ ፡ ለማከራየት ፡ ወይም ፡ ውሉን ፡ አሳልፎ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፭ ። የውሉ ፡ ማለቂያ ፡ ጊዜ ።**

(፩) ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ጊዜው ፡ የሚያልቀው ። ተዋዋዮች ፡ ወገኖች ፡ የተስማሙበት የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሲደርስ ፡ ነው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተዋዋዮች ፡ ቢሞቱ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ቢያጡም፡ እንኳ ፡ የተወሰነው ፡ ዘመን ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ አያልቅም።

(፫) ቢሆንም፡ ተከራዩ፡ የከሠረ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ላለፈውም፡ ሒሳብ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ፊት፡ ለሚመጣው ፡ የኪራይ ፡ መክፈያ ፡ ዘመን ፡ ሒሳቡን በሚስማማ ፡ ጊዜ ፡

ውስጥ ፡ የሚከፍል ፡ ለመሆኑ ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚሆን ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ካል ሰጠው ፡ በቀር ፡ አከራዩ ፤ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፰ ። ጊዜ ፡ ያልተወሰነላቸው ፡ ውሎች ።**

(፩) የኪራዩ ፡ ዘመን ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ሳይመለከት ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ አንዱ ፤ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ውሉ ፡ እንዲያልቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፩ኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ የተከራየውን ፡ ዕቃ ፡ ስለ፡መመለስ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ የቀረበውን ፡ ለማስረከብ ፡ (ለመረከብ) ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ ጊዜ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፱ ። መልሶ ፡ በማስረከብ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ መዘግየት ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ዕቃውን ፡ እንዲመልስ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ሳይመልስ ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕቃውን ፡ እስከ ፡ መለሰበት ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ የኪራይ ፡ ሒሳብ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ የመዘግየቱ ፡ ጕዳይ ፡ በአከራዩ ፡ ላይ ፡ ላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺ ። የውሉ ፡ ዘመን ፡ መቀጠል ፡ (መርዘም) ።**

(፩) ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ዘመን ፡ እንዲጸና ፡ በተደረገ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ስምምነት ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ የተከራየውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስለት ፡ ሳይጠይቀው ፡ የጊዜው ፡ ውሳኔ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ዕቃው ፡ በተከራዩ ፡ ባለይዞታነት ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በመጀመሪያው ፡ (በዋነኛው) ፡ ውል ፡ በተስማሙበት ፡ ሁኔታና ፡ መሠረት ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ጸንቶ ፡ እንዲቈይ ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ እንደ ፡ ተስማሙበት ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ቢሆንም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ (ስለ ፡ ዋነኛው) ፡ ውል ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ ዋሶች ፡ የነበሩት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## እንስሳን ፡ ስለ ፡ መከራየት ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ባንድ ፡ የርሻ ፡ መሬት ፡ ሥራ ፡ ኪራይ ፡ ውስጥ ፡ ከብትን ፡ ጭምር ፡ ስለ ፡ መከራየት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፩ ። የነዚህ ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ።**

ገበሬው ፡ የተጋዛው ፡ (የተከራየው) ፡ የርሻ ፡ መሬት ፡ ሥራ ፡ ከብቶች ፡ ያሉበት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፯፻፵ ። የከብት ፡ ሽያጭ ። (፩) የገበሬው ፡ መብት ።**

(፩) ተጋዡ ፡ ገበሬ ፡ የርሻ ፡ መሬት ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ ከብቶች ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ገበሬው ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በብዛትና ፡ በዐይነት ፡ የሚተካከል ፡ ዘር ፡ ያለው ፡ የርቢ ፡ ከብት ፡ ማኖር ፡ አለበት ።

(፫) አከራዩ ፡ የርቢው ፡ ከብት ፡ የበረከተ ፡ (የበዛ) ፡ ቢሆንም ፤ ከብቶቹን ፡ እንዲሸጥ ፡ ተጋዡን ፡ ገበሬ ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፯፻፵፩ ። (፪) ያከራዩ ፡ መብት ።**

(፩) አከራዩ ፡ የርሻው ፡ መሬት ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ ከብቶች ፡ ለመሸጥ ፡ አይችልም ።

(፪) አከራዩ ፡ በየዓመቱ ፡ ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ የርቢ ፡ ከብት ፡ ዝርዝር ፡ እንዲሰጠው ፡ ገበሬውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) አከራዩ ፡ በገበሬው ፡ አሠራር ፡ ምክንያት ፡ የርቢው ፡ ከብት ፡ ካንድ ፡ እሩብ ፡ በሚበልጥ ፡ የተቀነሰ ፡ መሆኑን ፡ የተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፯፻፵፪ ። የከብቶች ፡ ጥቅም ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ከዚህ ፡(የሚቀጥሉት)፡ ቍጥሮች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ ገበሬው ፡ ከከብቶቹ ፡ በሚገኙት ፡ ነገሮች ፡ (በቁርበቶቻቸው) ፡ በቆዳዎቻቸውና ፡ በብዛታቸው ፡ በመርባታቸው ፡ በነጻ ፡ ሊገለገልባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ገበሬው ፡ የሚከፍለው ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ከነዚሁ ፡ ጥቅሞች ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ እነዚሁኑ ፡ ጥቅሞች ፡ በመገመት ፡ የተወሰነ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥራውን ፡ አካሄድ ፡ ለአከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፯፻፵፫ ። (፪) የበግ ፡ ጠጕር ።**

(፩) ገበሬው ፡ የሥራውን ፡ ክንውን ፡ መሪነት ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ መንጋው ፡ ከአምሳ ፡ ያነሰ ፡ ከሆነ ፡ የበጎቹን ፡ ጠጕር ፡ ብቻ ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ሥራውን ፡ የሚመራ ፡ አከራዩ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የበጎቹም ፡ መንጋ ፡ ከአምሳ ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ የበጎቹን ፡ ጠጕር ፡ ለመሸጥ ፡ የሚችለው ፡ አከራዩ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፯፻፵፬ ። (፫) ፍግ ።**

የከብቶቹ ፡ ፍግ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በተለይ ፡ ስለ ፡ መሬቱ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ መዋል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፲፯፻፵፭ ። (፬) ርቢ ።**

በሚሞቱ ፡ ወይም ፡ በታረዱ ፡ ከብቶች ፡ ልክ ፡ የርቢ ፡ ከብቶች ፡ መተካት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፵፮ ። መልሶ፡የመስጠት፡ግዴታ ።**

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ሲያልቅ ፡ ገበሬው ፡ እመሬቱ ፡ ላይ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በዘር ፡ በብዛትና ፡ በዐይነት ፡ የሚተካከል ፡ የርቢ ፡ ከብት ፡ መተው ፡ አለበት ።

(፪) የርቢው ፡ ከብት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በግምት ፡ የገባ ፡ ቢሆንም ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ ይኖርበታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፵፯ ። ጒድለት ።(፩)የአከራዩ ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ጒድለት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የሚከፈለውም ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ካንድ ፡ ከተወሰነ ፡ ጥቅም ፡ ድርሻ፡ ወይም ፡ ከተወሰነ ፡ ከከብቶች ፡ ጥቅም ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራው ፡ የአከራዩ ፡ ነው ።

(፪) የከብቶቹ ፡ ኪሣራ ፡ በገበሬው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ አላፊ ፡ በሆነለት ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ጒድለት ፡ ገበሬው ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፵፰ ።(፪)የገበሬው ፡ ኪሣራ ።**

ለኪራዩ ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ በተለይ ፡ ከከብቶቹ ፡ ጥቅም ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ በሌለው ፡ አኳኋን ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገበሬው ፡ ላላቀረባቸው ፡ ከብቶች ፡ ዋጋ ፡ (ግምት) ፡ አላፊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፵፱ ። (፫)የአላፊነቱ ፡ መጠን ።**

(፩) ገበሬው ፡ ያላቀረባቸው ፡ ከብቶች ፡ ዋጋ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በሚደረገው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህን ፡ የመሰለ ፡ ግምት ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኪራዩን ፡ ውል ፡ የሚቀርቡት ፡ ከብቶቹ ፡ በሚያወጡት ፡ ግምት ፡ ልክ ፡ ገበሬው ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
## የከብቶቹ ፡ ኪራይ ፡ ዋና ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፶ ። የነዚህ ፡ ደንቦች፡አፈጻጸም ።**

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ለእርሻ ፡ ወይም ፡ ለንግድ ፡ ጥቅም ፡ ለመስጠት ፡ በሚችሉ ፡ ከብቶች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ እንስሳዎች ፡ የተቋቋመ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ልማደ ፡ ሀገር ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፶፩ ። ለዐይነት ፡ የሆኑ፡ውሎች ።**

(፩) ለዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ውሎች ፡ አንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ (ዘር) ፡ ከብቶችን ፡ በሚመለከት ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ አውራጃዎች ፡ ውስጥ ፡

መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ ለዐይነት ፡ የሚሆኑ ፡ ውሎችን ፡ የርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሊያደራጃቸው ፡ ይችላል ።

(፪) የከብት ፡ ዐይነቶችን ፡ ወይም ፡ ለዐይነት ፡ የተደራጁት ፡ ውሎች ፡ ከሚመለከቷቸው ፡ መሬቶች ፡ ከአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ ለዐይነት ፡ በተሠሩት ፡ ውሎች ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በሚያደርጉት ፡ ግልጽ ፡ ስምምነት ፡ ለዐይነት ፡ የተሠሩትን ፡ ውሎች ፡ ሁኔታ ፡ ሊለውጡት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፪ ። ውሉ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ (ዘመን) ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ቃል ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ ለአራት ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይገመታል ።

(፪) የአራቱ ፡ ዓመት ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ውሉ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፫ ። ለመሬቱ ፡ ባለቤት ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) የርቢው ፡ ከብት ፡ በኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ገበሬ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገበሬው ፡ ለሚሠራበት ፡ መሬት ፡ ባለሀብት ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያልደረሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተቃራኒ ፡ ልማድ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ አከራዩ ፡ ከተጋገፉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ የርቢውን ፡ ከብት ፡ በማስያዝ ፡ ወይም ፡ በማቈየት ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

(፫) ከብቶቹ ፡ የገበሬው ፡ ሀብት ፡ አለመሆናቸውን ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ነበረበት ፡ ብሎ ፡ ማመካኘት ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፬ ። የርቢው ፡ ከብት ፡ ግምት ።

(፩) በኪራዩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ለርቢው ፡ ከብት ፡ የተደረገው ፡ ግምት ፡ ለተከራዩ ፡ ሀብትነቱን ፡ አያስተላልፍም ።

(፪) የግምቱ ፡ መገለጽ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በሚቀርበት ፡ ጊዜ ፡ ኪሣራውን ፡ ወይም ፡ ጥቅሙን ፡ የመውሰድ ፡ ዓላማ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፭ ። ስለ ፡ ርቢው ፡ ከብት ፡ አጠባበቅ ።

(፩) ተከራዩ ፡ ስለ ፡ ርቢው ፡ ከብት ፡ አያያዝና ፡ አጠባበቅ ፡ የተለመደውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ተከራዩም ፡ ለዚህ ፡ አጠባበቅ ፡ ራሱ ፡ ወጪውን ፡ መቻል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፮ ። የርቢ ፡ ከብቶች ፡ ውላጆች ።

በርቢ ፡ የተሰጡ ፡ ከብቶች ፡ ልጆች ፡ የአከራዩና ፡ የተከራዩ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፯ ። የከብቶቹ ፡ ጥቅም ።

ተከራዩ ፡ ለርቢ ፡ በተሰጡት ፡ ከብቶች ፡ ወተት ፡ ፍግና ፡ ሥራ ፡ ብቻውን ፡ ይጠቀማል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፰ ። የበግ ፡ ጠጕር ።

(፩) ለርቢ ፡ የተሰጡ ፡ በጎች ፡ ጠጕር ፡ በአከራዩና ፡ በተከራዩ ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ ይከፋፈላል ።

(፪) ተከራዩ ፡ የሚሸልትበትን ፡ ቀን ፡ ለአከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፱ ። ስለ ፡ ከብቶች ፡ መሸጥ ።

(፩) ተከራዩ ፡ ያለ ፡ አከራዩ ፡ ፈቃድ ፡ በተሰጡት ፡ ከብቶች ፡ ሆነ ፡ በርቢ ፡ ከተገኙት ፡ ልጆች ፡ ሆነ ፤ ከመንጋው ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ ከብት ፡ ለመሸጥ ፡ አይችልም ።

(፪) አከራዩም ፡ ያለ ፡ ተከራዩ ፡ ፈቃድ ፡ ለመሸጥ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፻ ። ስለ ፡ ከብቶች ፡ መጥፋት ።

(፩) ተከራዩ ፡ ስለ ፡ ከብቶቹ ፡ መሞት ፡ መጥፋት ፡ ኣላፊ ፡ የሚሆነው ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ይህን ፡ ጥፋት ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ አከራዩ ፡ ነው ።

(፫) ተከራዩ ፡ የሞቱትን ፡ ከብቶች ፡ ቆዳ ፡ ዘወትር ፡ ለአከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፻፩ ። ሒሳብ ፡ ስለ ፡ መተሳሰብ ።

(፩) አከራዩ ፤ ገበሬው ፡ የርቢ ፡ ከብቶቹን ፡ ዝርዝር ፡ ቍጥር ፡ በያመቱ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ የዓመቱንም ፡ ሒሳብ ፡ እንተሳሰብ ፡ ሊለው ፡ ይችላል ።

(፪) የገበሬው ፡ ነው ፡ በሚባል ፡ ምክንያት ፡ የርቢዎቹ ፡ ከብቶች ፡ ከሩብ ፡ በላይ ፡ የቀነሱ ፡ የመሰለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አከራዩ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፻፪ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ ማለቅ ።

(፩) ውሉ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ በስምምነት ፡ እንዲያልቅ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ የሚቀር ፡ ይሆናል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ የሚፈልገው ፡ ወገን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ አስቀድሞ ፡ የማስቀረት ፡ ሐሳቡን ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፻፫ ። ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መሞት ።

(፩) ውሉ ፡ በአከራዩ ፡ ወይም ፡ በተከራዩ ፡ መሞት ፡ የሚቀር ፡ አይሆንም ።

(፪) ተከራዩ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱ ፡ በሞተ ፡ በ፮ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ለአከራዩ ፡ በመግለጽ ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ የሚያልቀው ፡ አከራዩ ፡ የተከራዩ ፡ ወራሾች ፡ ሐሳብ ፡ በደረሰው ፡ ቢያንስ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ካለው ፡ መጋቢት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፴፱ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ ሒሳብ ፡ መጣራት ።

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ሲያልቅ ፡ ወይም ፡ በሚፈርስበት ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ የርቢው ፡ ከብት ፡ ግምት ፡ ይደረጋል ።

(፪) አከራዩ ፡ የመጀመሪያው ፡ ግምት ፡ እስከሚስተካከል ፡ ድረስ ፡ ከያንዳንዱ ፡ ዐይነት ፡ ከብቶች ፡ መውሰድ ፡ ይችላል ።

(፫) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ትርፍ ፡ የሆነው ፡ በአከራዩና ፡ በተከራዩ ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ ይከፋፈላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፵ ። የማይበቃ ፡ የርቢ ፡ ከብት ።

(፩) የመጀመሪያውን ፡ ግምት ፡ ለመሙላት ፡ በቂ ፡ ከብቶች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አከራዩ ፡ የተረፉትን ፡ ወስዶ ፡ በጠፋው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ውሳኔ ፡ ያደርጋሉ ።

(፪) የከብቶቹ ፡ መጕደል ፡ በተጋዥ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ አላፊ ፡ በሚሆነው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ካልሆነ ፡ በተጋዥ ፡ አይታሰቡበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፵፩ ። ፈራሽ ፡ የሆኑ ፡ የውል ፡ ቃሎች ።

(፩) ተከራዩ ፡ ባልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ ጥፋቱ ፡ የደረሰበትን ፡ የርቢ ፡ ከብት ፡ መጥፋት ፡ በሙሉ ፡ ይከፍላል ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተከራዩ ፡ ከሚያገኘው ፡ ትርፍ ፡ የበለጠ ፡ ኪራይ ፡ ይከፍላል ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) እንዲሁም ፡ አከራዩ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ሲቀር ፡ ከሰጠው ፡ የርቢ ፡ ከብት ፡ በላይ ፡ ይወስዳል ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።
## ስለ ፡ መገልገያ ፡ ብድር ፡ ወይም ፡ ትውስት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፵፪ ። ትርጓሜ ።

ለመገልገያ ፡ መዋስ ፡ ሲባል ፡ አዋሽ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋሹ ፡ የሚባለው ፡ ሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ወስዶ ፡ በነጻ ፡ እንዲገለገልበት ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፵፫ ። ውሉ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ውሰት ፡ በፍጹም ፡ ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ በነጻ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ።

BACK



(፪) አዋሹ ፡ ላዋሰው ፡ ዕቃ ፡ አበል ፡ ይከፈለዋል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ዕቃ ፡ ኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፷፱ ። የዕቃው ፡ ባለሀብትነት ።

(፩) አዋሹ ፡ ላዋሰው ፡ ዕቃ ፡ ባለሀብት ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።
(፪) የውሉ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ተዋሹ ፡ ዕቃውን ፡ ሊመልስለት ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸ ። የዕቃው ፡ አያያዝ ።

(፩) ተዋሹ ፡ ዕቃውን ፡ በሚገባ ፡ ጥበቃ ፡ መያዝ ፡ አለበት ።
(፪) የዚህንም ፡ የአያያዝ ፡ ወጪ ፡ የሚችል ፡ ራሱ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፩ ። የዕቃው ፡ አገልግሎት ።

(፩) ተዋሹ ፡ በዕቃው ፡ እንዲገለገልበት ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሊገለገል ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ የተለየ ፡ ስምምነትም ፡ ባይኖር ፡ የዕቃው ፡ ተፈጥሮ ፡ ዐይነት ፡ ከሚፈቅድለት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ ሊገለገልበት ፡ አይችልም ።
(፪) አዋሹ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፡ በተዋሰው ፡ ዕቃ ፡ ሌሎች ፡ እንዲገለገሉበት፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ አይፈቀድለትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፪ ። ዕቃውን ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

(፩) ተዋሹ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ዕቃውን ፡ መመለስ ፡ አለበት ።
(፪) ለዕቃው ፡ መመለሻ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ተዋሹ ፡ ዕቃውን ፡ መመለስ ፡ ስለሚገባው ፡ ጕዳይ ፡ ልማዳዊ ፡ አሠራር ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፤ አዋሹ ፡ እንዲመልስለት ፡ ሲጠይቀው ፡ ወዲያውኑ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፫ ። ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ መመለስ ። (፩) የተዋሹ ፡ መብት ።

በውሉ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ዕቃው ፡ ቢመለስለት ፡ ባዋሹ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የማያደርስበት ፡ ከሆነ ፡ ተዋሹ ፡ የውሉ ፡ ዘመን ፡ ከመድረሱ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ ዕቃውን ፡ ለመመለስ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፬ ። (፪) ያዋሹ ፡ መብት ።

ተዋሹ ፡ በውሉ ፡ ከተፈቀደለት ፡ አገልግሎት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በዕቃው ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ዕቃውን ፡ ያበላሸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲገለገልበት ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አዋሹ ፡ በቃው ፡ ራሱ፡ እንዲገለገል ፡ የሚያስፈልግ ፡ አስቸኳይና ፡ ድንገተኛ ፡ ያልታሰበ ፡ ጕዳይ ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በውሉ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ዘመን ፡ ከመድረሱ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ አዋሹ ፡ ዕቃው ፡ እንዲመለስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፭ ። የተዋሹ ፡ መሞት ።

ተዋሹ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለተዋሹ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የፈቀደለትም ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ የተዋሹ ፡ ወራሾች ፡ ዕቃውን ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲመልሱለት ፡ አዋሹ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፮ ። ያለመጠን ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

(፩) ተዋሹ ፡ በዕቃው ፡ ያለመጠን ፡ በመገልገሉ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ያላገባብ፡ እንዲገለገልበት ፡ አሳልፎ ፡ በማይገባ ፡ በመስጠቱ ፡ ዕቃው ፡ የተበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዕቃው ፡ መበላሸት ፡ ያስከተለው ፡ ሊታለፍ ፡ በማይቻል ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ተዋሹ ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መበላሸት ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ቢያፈርስም ፡ እንኳ ፡ ዕቃው ፡ ከመጥፋት ፡ ወይም ፡ ከመበላሸት ፡ የማይድን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ አላፊነት ፡ ለመዳን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፯ ። ሊቀር ፡ የሚቻል ፡ ጥፋት ።

ሊታለፍ ፡ በማይችል ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክንያትም ፡ ቢጠፋ ፡ እንኳ ፤ ከተዋሰው ፡ ዕቃ ፡ ይልቅ ፡ የራሱ ፡ ዕቃ ፡ እንደሚሻል ፡ ገምቶ ፡ የራሱን ፡ ዕቃ ፡ አሳልፎ ፡ ለጥፋት ፡ ባለመስጠት ፤ ከሁለቱ ፡ አንደኛውን ፡ ብቻ ፡ ከጥፋት ፡ ለማዳን ፡ ሲችል ፡ የራሱን ፡ ዕቃ ፡ ለማዳን ፡ መርጦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለጠፋው ፡ ዕቃ ፡ ተዋሹ ፡ አላፊ ፡ መሆኑ ፡ አይቀርለትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፰ ። በውሉ ፡ ላይ ፡ የተገመተ ፡ ዕቃ ።

የውሉ ፡ ጽሑፍ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ የዕቃውን ፡ ግምት ፡ አመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢጠፋ ፡ ተዋሹ ፡ በአላፊነት ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## አ ደ ራ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ አደራ ፡ በጠቅላላው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፱ ። ትርጓሜ ።

አደራ ፡ ማለት ፡ አደራ ፡ ተቀባይ ፡ የተባለው ፡ አደራ ፡ አስቀማጭ ፡ የተባለውን ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ዕቃ ፡ ተቀብሎ ፡ በአደራ ፡ ጠባቂነት ፡ እንዲያስቀምጥለት ፡ የሚገባበት ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹ ። አደራ ፤ በሁኔታ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሽያጭ ፡ ስለ ፡ ሥራ ።

(፩) አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ስምምነት ፡ ለዕቃው ፡ ማስቀመጥ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈልበት ፡ ተፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ የአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ደንብ ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ሁኔታ ፡ ሽያጭ ፡ በተወሰነው ፡ ድጋጌ ፡ ነው ።

(፪) አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ዕቃውን ፡ እንዲያድስ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ እንዲለውጠው ፡ የሚገደድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ድንጋጌ ፡ ያደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ደንብ ፡ ሳይሆን ፡ የውልና ፡ የሥራ ፡ ደንብ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፩ ። የዕቃው፡ባለቤትነት ።

(፩) አደራ ፡ ሰጪው ፡ የዕቃው ፡ ባለቤት ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።

(፪) አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ለአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ የተወሰነው ፡ የውሉ ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሲደርስ ፡ ዕቃውን ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ሊመልስለት ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፪ ። በአደራ፡የተቀመጠ፡አላቂ፡ዕቃ ።

(፩) ለአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ የተሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በማገልገል ፡ የሚያልቅ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ብዛት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አደራ ፡ ተቀባዩም ፡ እንዲገለገልበት ፡ ተፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጕዳይ ፡ የአላቂ ፡ ነገርን ፡ ብድር ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ለአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ የተሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የተረከበውም ፡ ሳይታሸግና ፡ ሳይዘጋበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲጠቀምበት ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፫ ። አደራ ፡ በተቀመጠው፡ዕቃ፡ስለ፡መገልገል ።

(፩) አደራ ፡ የተቀመጠው ፡ ዕቃ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አደራ ፡ ሰጭ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፡ አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ሊገለገልበት ፡ አይችልም ።

(፪) ይህን ፡ ደንብ ፡ የጣሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ዕቃ ፡ ኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ ደንብ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ይጸናበታል ።

(፫) አደራ ፡ ሰጭ ፡ የዕቃው ፡ ኪራይ ፡ እንዲከፈለው ፡ አደራ ፡ ተቀባዩን ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። ኪራዩም ፡ የሚወሰንለት ፡ በትክክለኛ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፬ ። ያለ ፡ ዋጋ፡ወይም ፡ በደመወዝ፡የሚሰጥ፡አደራ ።

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ለአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ አንድ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈለው ፡ በውላቸው ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ በአደራ ፡ የሚቀመጥ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጕዳይ ፡ የአደራ ፡ ተቀባዩን ፡ ልዩ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ዐይነተኛ ፡ ነገርና ፡ ሌሎቹንም ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ መገመት ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፹፭ ። የአደራ ፡ ማስቀመጥን ፡ አጋጣሚ፡ጕዳይ ፡ ስለ፡መለወጥ ።

(፩) አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ ድንገተኛ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ የሚያስገድደው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ አቀማመጥ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ከተመለከ

BACK



ተው ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ ሊጠብቅ ፡ ወይም ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ እርግ ጠኛ ፡ የሆነ ፡ የማይቀር ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ የመበላሸት ፡ አደጋ ፡ የሚደርስ በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተለይ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ በአደራ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ። (ይገባዋልም) ።

(፪) ይህንንም ፡ እንዳደረገ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፮ ። የአደራ ፡ ማስቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ ማለቅ ።(፩)የአደራ ፡ ሰጪው ፡ መብት ።**

(፩) ለአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ አደራ ፡ የተቀመጠውን ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መመለስ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ እንደ ፡ ጠየቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ዕቃው ፡ ሊመለስለት ፡ ይገባል ።

(፪) በተስማሙበት ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ዕቃውን ፡ ለመ ጠበቅና ፡ ላያያዙ ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደ ዳል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፯ ። (፪)የአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ መብት ።**

(፩) ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ አደራ ፡ የተቀመጠውን ፡ ዕቃ ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ዕቃውን ፡ መልሶ ፡ እንዲወስድ ፡ በማንኛ ውም ፡ ጊዜ ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

(፪) ማንኛውም ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በስምምነታቸው ፡ ላይ ፡ ያልተመለከተ ፡ ቢሆ ንም ፡ እንኳ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ዕቃውን ፡ መልሶ ፡ ለመውሰጃ ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እን ዲኖረው ፡ ዳኞች ፡ በአስተያየት ፡ ጊዜውን ፡ ሊወስኑለት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፰ ። ስለ ፡ ብዙ ፡ አደራ ፡ ሰጪዎች ።**

(፩) ዕቃውን ፡ ለአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ የሰጡት ፡ ብዙ ፡ አደራ ፡ ሰጪዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑና ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ተመልሶ ፡ ሊወሰድ ፡ እንደሚገባ ፡ ያል ተስማሙበት ፡ ሲሆን ፤ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ የመስጠቱ ፡ መብት ፡ የዳኞች ፡ ነው ።

(፪) አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ብዙ ፡ ወራሾች ፡ ትቶ ፡ በሞተ ፡ ጊዜና ፡ ዕቃውም ፡ የማይከ ፋፈል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መልሶ ፡ የመውሰዱን ፡ ደንብ ፡ የሚወስኑት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፸፱ ። ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ የተቀመጠ ፡ አደራ ።**

(፩) በአደራ ፡ የተቀመጠው ፡ ዕቃ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ ሆኖ ፡ ይህም ፡ ሦስ ተኛ ፡ ወገን ፡ ላደራ ፡ ሰጪውና ፡ ለተቀባዩ ፡ ስምምነቱን ፡ አስታውቋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሳይፈቅድ ፡ አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ዕቃውን ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ መልሶ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺ ፡፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መመለስ ፡፡**

(፩) አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቦታ ፡ እንዲያስቀምጥና ፡ እንዲጠብቅ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ የተመለከተ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፤ ዕቃው ፡ ተመልሶ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባው ፡ በዚሁ ፡ በተወሰነው ፡ ስፍራ ፡ ነው ፡፡

(፪) በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መመለስ ፡ የሚደርሰው ፡ ወጪና ፡ ጉዳት ፡ የአደራ ፡ ሰጪው ፡ ነው ፡፡

**ቍ፡፪ሺ፯፻፺፩ ፡፡ ፍሬውን ፡ ስለ ፡ መመለስ ፡፡**

አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ በአደራ ፡ ካስቀመጠው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ያገኘው ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ለባለቤቱ ፡ መመለስ ፡ አለበት ፡፡

**ቍ፡፪ሺ፯፻፺፪፡፡ ዕቃው ፡ ለማን ፡ መመለስ ፡ እንደሚገባው ፡፡**

(፩) አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ በአደራ ፡ ያስቀመጠውን ፡ ዕቃ ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ ይቀበልልኝ ፡ ብሎ ፡ ላመለከተው ፡ ሰው ፡ መመለስ ፡ አለበት ፡፡

(፪) አደራ ፡ ሰጪው ፡ ላስቀመጠው ፡ ዕቃ ፡ ባለቤት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብለት ፡ አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ሊጠይቀው ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፫ ፡፡ የአደራ ፡ ሰጪው ፡ ግዴታዎች ፡፡**

(፩) አደራ ፡ ሰጪው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ የተስማሙበትን ፡ የአደራ ፡ ጠባቂነት ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ለአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡፡

(፪) ዕቃውንም ፡ በመልካም ፡ አያያዝ ፡ ለማኖር ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባል ፡፡

(፫) ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ በአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ አላፊ ፡ በሚሆንበት ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ (ጉድለት) ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የአደራ ፡ ማስቀመጡ ፡ ጉዳይ ፡ ላደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ ግዴታ ፡ አለበት ፡፡

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፬ ፡፡ በመያዣ ፡ የማቈየት ፡ መብት ፡፡**

አደራ ፡ ተቀባዩ ፡ በአደራ ፡ ስላስቀመጠው ፡ ዕቃ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ሒሳብ ፡ በሙሉ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ በአደራ ፡ የተቀመጠውን ፡ ዕቃ ፡ በእጁ ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ፡፪ሺ፯፻፺፭ ፡፡ የአደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ወራሽ ፡፡**

(፩) ያደራ ፡ ተቀባዩ ፡ ወራሽ ፡ ዕቃው ፡ በአደራ ፡ የተቀመጠ ፡ መሆኑን ፡ ሳያውቅ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ሸጦት ፡ ወይም ፡ ለውጦት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲመልስ ፡ የሚገደደው ፡ ዋጋውን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡

(፪) የዕቃውም ፡ ዋጋ ፡ ገና ፡ አልተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ በሻጩ ፡ ወራሽ ፡ መብት ፡ ተተክቶ ፡ ገዢውን ፡ በቀጥታ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፡፡

## ክፍል ፡ ፪ ።
## በትእዛዝ ፡ የተቀመጠ ፡ አደራ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፮ ። ትርጓሜ ።**

አንድ ፡ ዕቃ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታው ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ የሚያጠራጥር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃው ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ተሰጥቶ ፡ ይህ ፡ በትእዛዝ ፡ አስቀማጭ ፡ የሚባለው ፡ ባለአደራ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ጥርጣሬ ፡ ከተገለጸ ፡ በኋላ ፡ ባለመብት ፡ ነው ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ እንዲመልስ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በትእዛዝ ፡ የተቀመጠ ፡ አደራ ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፯ ። የትእዛዝ ፡ ባለአደራን ፡ ስለ ፡ መምረጥና ፡ አላፊነቱን ፡ ስለ ፡ ማስወረድ ።**

(፩) የትእዛዝ ፡ ባለአደራ ፡ የሚመረጠው ፡ በሁለቱ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

(፪) ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ይመርጡታል ።

(፫) ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በጉዳዩ ፡ ካልተስማሙበትና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የትእዛዝ ፡ በለአደራው ፡ የተሰጠውን ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ጊዜው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ አላፊነቱን ፡ ሊያስወርድ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፰ ። ስለ ፡ ዕቃው ፡ መመለስ ።**

የትእዛዝ ፡ ባለአደራው ፡ በጉዳዩ ፡ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ ካልተስማሙበት ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ካላዘዙት ፡ በቀር ፡ ዕቃውን ፡ ለመመለስ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፯፻፺፱ ። ወደ ፡ አደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መመራት ።**

ከዚህ ፡ የተረፈው ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ አደራ ፡ ዕቃ ፡ አቀማመጥ ፡ በተወሰነው ፡ ደንብ ፡ ይፈጸማል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።
## አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ አደራ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻ ። ትርጓሜ ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የራሱ ፡ ንብረት ፡ በሆኑት ፡ ዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ የማይታገድ ፡ እርግጠኛ ፡ አደጋ ፡ የሚደርስባቸው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ ዕቃዎች ፡ ከቀረበው ፡ አደጋ ፡ ለማሸሽ ፡ ሲል ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በአደራ ፡ ተቀብሎ ፡ እንዲያስቀምጥለት ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ አድራጎት ፡ አስፈላጊ ፡ የአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፩ ። አስፈላጊ ፡ የአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ።**

(፩) የዚህን ፡ ዐይነት ፡ አስፈላጊ ፡ አደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲፈጽም ፤ የአደራው ፡ ዕቃ ፡ የቀረበለት ፡ ሰው ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ካልኖረው ፡ በቀር ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ አይችልም ።

(፪) የአደራ ፡ ማስቀመጡ ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ የበለጠ ፡ ተራዝሞ ፡ የሚቈይ ፡ ሲሆን ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) የአደራ ፡ ማስቀመጡ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ በስምምነት ፡ የተወሰነው ፡ አደራው ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ገንዘቡን ፡ ሊቀንሱ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፪ ። የአሠራሩ ፡ ፎርምና ፡ ማስረጃ ።**

(፩) አስፈላጊ ፡ የአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ጕዳይ ፡ ከማናቸውም ፡ ያሠራር ፡ ሥርዐት ፡ ነጻ ፡ ነው ።

(፪) በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፫ ። ስለ ፡ አደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ የተሰጠውን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ማጽናት ።**

ከዚህ ፡ ለሚተርፈው ፡ ጕዳይ ፡ ያስፈላጊ ፡ አደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ሥርዐት ፤ ስለ ፡ አደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ደንብ ፡ በተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይመራል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ባለቤቱ ፡ ሳያውቅ ፡ የተገኙ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የተቀመጡ ፡ ዕቃዎች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፬ ። ያገኘው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ።**

(፩) አንድ ፡ ዕቃ ፡ አግኝቶ ፡ የዚሁ ፡ ዕቃ ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፤ ልክ ፡ እንደ ፡ አደራ ፡ ተቀባይ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ የግል ፡ ባለሀብትነት ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ ለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፭ ። ሰውዬው ፡ ሳያውቅ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ በአደራ ፡ የተቀመጠ ፡ ዕቃ ።**

(፩) ሰውዬው ፡ ሳያውቅ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ አንድ ፡ ዕቃ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ተቀምጦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ ደንብ ፡ ላስቀማጩ ፡ አይረጋለትም ።

(፪) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ዕቃ ፡ አስቀማጭ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ አላፊነት ፡ ተጠያቂ ፡ አይሆንም ። (ማንኛውም ፡ ግዴታ ፡ አይደርስበትም) ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ቦታ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፮ ። ትርጓሜ ።**

የዕቃ ፡ ማከማቸት ፡ ማለት ፡ ሸቀጦችን ፡ እየተቀበለ ፡ በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ከሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለዚህ ፡ ዐይነት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠው ፡ ዕቃ ፡ አከማች ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡

ዕቃ ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለው ፡ የማከማቻ ፡ ዕቃ ፡ ሰጭ ፡ ተብሎ ፡ ለሚጠራው ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፤ ዕቃውን ፡ ተቀብሎ ፡ በማከማቻው ፡ ስፍራ ፡ እንዲያ ስቀምጥለት ፡ በውል ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፯ ። የሸቀጡ ፡ መጥፋትና ፡ መበላሸት ።

(፩) ዕቃውን ፡ በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ የተረከበው ፡ አስቀማጭ ፡ ስለ ፡ ሸቀጡ ፡ መጥፋትና ፡ መበላሸት ፡ ኣላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ሸቀጡን ፡ ከመጥፋት ፡ ወይም ፡ ከመበላሸት ፡ ያደረሰው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ በሸቀጡ ፡ ተፈጥሮ ፡ ዐይነትና ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ካጠቃለሉ ፡ መጥፎነት ፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ በአ ላፊነት ፡ ከመጠየቅ ፡ አይድንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፰ ። ለዕቃ፡ሰጪው፡የማስታወቅ፡ ግዴታ ።

የሸቀጡ ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ የመለወጥ ፡ ነገር ፡ በታየበት ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ዐይ ነት ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግበት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በዕቃ ፡ መከማቻ ፡ ስፍራ ፡ አስቀማጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ለሸቀጥ ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፱ ። ዕቃውን ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ለሸቀጡ ፡ ማስቀመጥ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ተረካቢው ፡ በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ ሸቀጡን ፡ ማኖር ፡ አለበት ።

(፪) አስቀማጭ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ያልታሰበ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ከደረሰበት ፡ ለሸ ቀጡ ፡ ማስቀመጥ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ባለአደራው ፡ ዕቃውን ፡ ለባለቤቱ ፡ መመለስ ፡ ይችላል ፡ በሚለው ፡ ሰበብ ፡ ለመከራከር ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲ ። ሸቀጡን ፡ ከሌላ ፡ ሸቀጥ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ማደባለቅ ።

(፩) ይህ ፡ መብት ፡ ተለይቶና ፡ ተገልጾ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፤ በሸቀጥ ፡ ማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ አስቀማጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የተረከባ ቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ተፈጥሮዋቸውና ፡ ዐይነታቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ ቢሆንም ፡ ካላቂ ፡ ዕቃዎች ፡ ጋራ ፡ አደባልቆ ፡ ለማስቀመጥ ፡ አይችልም ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ሸቀጦች ፡ ተቀላቅለው ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትን ፡ ከፊል ፡ ድርሻዎች ፡ እንዲሰጡት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሸቀጡን ፡ አከማች ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ድር ሻውን ፡ ሌሎችን ፡ ሳይጠይቅ ፡ ሊመልስለት ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፩ ። የሸቀጥ ፡ ሽያጭ ።

(፩) በስምምነታቸው ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ካለፈ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ሸቀጡን ፡ ሳይወስድ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሸቀጥ ፡ አስቀማጩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ሸቀጦቹን ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፪) በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሳይወሰን ፡ ቀርቶ ፡ ሸቀጡ ፡ በአደራ፡ ከተቀመጠ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ባለፈውም ፡ ጊዜ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሸቀጦቹ ፡ የመበላሸት ፡ አደጋ ፡ ይደርስባቸዋል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጉ ፡ ሆነው ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊሸጣቸው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፪ ። የዋጋው ፡ አወሳሰድ ።

ሸቀጡን ፡ ለመሸጥ ፡ የተደረገው ፡ ወጪና ፡ ለአስቀማጩ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ሌላው ፡ ሒሳብ ፡ ተቀናሽ ፡ ሆኖ ፡ ዕቃው ፡ የተሸጠበት ፡ ዋጋ ፡ ለባለመብቶቹ ፡ ተቀማጭ ፡ ሆኖ ፡ መቈየት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፫ ። ደረሰኝና ፡ የመያዣ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ።

(፩) አደራ ፡ ሰጪው ፡ በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ ላስቀመጠው ፡ ሸቀጥ ፡ ደረሰኝ ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀባዩ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) በደረሰኙ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ያለበት ፡ የመያዣ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከደረሰኙ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

(፫) ደረሰኙና ፡ ይህ ፡ የመያዣ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፤ ከሸቀጥ ፡ ተረካቢው ፡ እጅ ፡ ተቀማጭ ፡ ሊሆን ፡ ከሚገባው ፡ አንድ ፡ ቀሪና ፡ ሂያጅ ፡ ካለው ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ተኀርዶ ፡ ላስረካቢው ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፬ ። በደረሰኙና ፡ በመያዣ ፡ ማስቀመጫውም ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ የሚጻፍ ፡ ዝርዝር ።

በደረሰኙና ፡ በመያዣ ፡ ማስቀመጫው ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ ሊመለከትባቸው ፡ የሚገባው ፡ —

(ሀ) የአስቀማጩ ፡ ስምና ፡ የአባት ፡ ስም ፤ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ስም ፡ ዋና ፡ መኖሪያው ፤

(ለ) የማከማቻው ፡ ቤት ፡ ያለበት ፡ ስፍራ ፤

(ሐ) በተከማችነት ፡ የተሰጡት ፡ ሸቀጦች ፡ ዐይነትና ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ እንዲሁም፡ተለይተው፡ሊገለጹ ፡ የሚቻልበት ፡ ዝርዝር፡ ማመልከቻ፡ሁሉ ፤

(መ) ስለ ፡ ንግድ ፡ ዕቃ ፡ የጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ ተከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ዕቃዎቹም ፡ አሹራንስ ፡ የተከፈሉባቸው ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፭ ። በነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ ተጠቃሚዎች ።**

(፩) የደረሰኝና ፡ የመያዣ ፡ ማስቀመጫው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በአስረካቢው ፡ ወይም ፡ ይኸው ፡ አስረካቢው ፡ ለእገሌ ፡ ይሰጥልኝ ፡ ብሎ ፡ ባመለከተው ፡ በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ስም ፡ ተጽፈው ፡ ሊሰጡ ፡ ይቻላል ።

(፪) አባሪ ፡ በመሆንም ፡ ሆነ ፡ በመነጣጠል ፡ በነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ተፈርሞባቸው ፡ ለሌላ ፡ እንዲተላለፉ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፮ ። የሁለቱ ፡ ሰነዶች ፡ ባለይዞታ ፡ መብት ።**

(፩) የደረሰኝና ፡ የማያዣውን ፡ ማስቀመጫ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሰነዶች ፡ ሁለቱንም ፡ ባንድነት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፤ በሸቀጥ ፡ ማከማቻ ፡ ቦታ ፡ የተቀመጡት ፡ ዕቃዎች ፡ እንዲሰጡት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ እነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ቡብዙ ፡ ክፍል ፡ እንዲመደቡና ፡ ለእነዚህም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ብዙ ፡ መደቦች ፡ ዕቃ ፡ ተቀባዩ ፡ በመጀመሪያው ፡ ደረሰኝና ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሰነድ ፡ ምትክ ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ደረሰኝና ፡ አንዳንድ ፡ የመያዣ ፡ ማስቀመጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፯ ። የመያዣ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ባለይዞታ ፡ መብት ።**

የመያዣ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቱ ፡ ሰነድ ፡ ብቻ ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ዕቃ ፡ አስቀማጩ ፡ ዘንድ ፡ በተቀመጡት ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፰ ። የመያዣውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

(፩) በመያዣው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሰነድ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በመጀመሪያ ፡ የማስተላለፍ ፡ ጽሑፍ ፡ በሚመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ የዕዳውን ፡ ልክና ፡ ወለዱን ፡ እንዲሁም ፡ የሚከፈልበትን ፡ ቀን ፡ ለይቶ ፡ ማመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) በመያዣው ፡ ወረቀት ፡ በጀርባው ፡ የመጻፍ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫና ፡ የዚሁኑ ፡ ዝርዝር ፡ የማመልከቱ ፡ ጽሑፍ ፡ በደረሰኙ ፡ ላይ ፡ ተደርጎ ፡ የዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ እንዲፈርምበት ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፲፱ ። ተገቢውን ፡ መግለጫ ፡ ስላለማመልከት ።**

(፩) በመያዣ ፡ መስጫው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ጽሑፍ ፡ በዕዳ ፡ ተጠይቆ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚገባውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ወስኖ ፡ ያላመለከተ ፡ሲሆን ፡ በማከማቻው ፡ ስፍራ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆኑት ፡ ዕቃዎች ፡ በሙሉ ፡ ግምታቸውና ፡ ሙሉ ፡ ዋጋቸው ፡ ለተጠያቂው ፡ ዕዳ ፡ ዋስትና ፡ እንደ ፡ ተሰጡ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራሉ ።

(፪) ደረሰኙ ፡ በስሙ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ ደረሰኝ ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ሊከፈል ፡ የማይገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ክፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመ

ጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በደረሰኙ ፡ ጀርባ ፡ በጻፈው ፡ ሰውና ፡ በከፋ ፡ ልቡና ፡ የመ
ያዣ ፡ ዕቃውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ባለይዞታ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡
ክሱን ፡ አቅርቦ ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺ ። የደረሰኙ ፡ ሰነድ ፡ ባለይዞታ ፡ መብት ።

(፩) የዕቃው ፡ ደረሰኝ ፡ ሰነድ ፡ ብቻ ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ በዕቃ ፡ ማከ
ማቻ ፡ ስፍራ ፡ የተቀመጡትን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የመመርመር ፡ መብት ፡
አለው ።

(፪) ለዕቃ ፡ ማስቀመጡ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፡ ዕቃውን ፡ በመያዣ ፡
ስም ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ለዕቃ ፡ ተረካቢው ፡ ወይም ፡
ለትእዛዝ ፡ ባለአደራው ፡ በመስጠት ፡ በማከማቻው ፡ ስፍራ ፡ የተቀመጡ
ትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፩ ። መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ዕቃውን ፡ ስለ ፡ መሸጡ ።

(፩) የመያዣው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሊከፈለው ፡
የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሳይከፈለው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡
ሆነና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡
ያለመከፈሉን ፡ መግለጫ ፡ (ፕሮቴ) ፡ አቅርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመክፈያው ፡
የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ባለፈ ፡ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ በማከማቻው ፡ ስፍራ ፡
የተቀመጡትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፪) የመያዣው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ የሚጠይቀውን ፡
ሒሳብ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ የከፈለ ፡ በዚሁ ፡ በምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጀርባ ፡ ፈራሚ ፡
በዚህኛው ፡ መብት ፡ ተተክቶ ፡ የከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ የተወሰነው ፡ ዘመን ፡ ካለፈ ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡
የሸቀጦችን ፡ ሽያጭ ፡ ለማከናውን ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፪ ። በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ የተቀመጡት ፡ ሸቀጦች ፡ መሸጥ ።

ሸቀጦችን ፡ ተረካቢ ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ የመያዣው ፡ የምስክር ፡ ሰነድ ፡ ባለ
ይዞታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ተይዘው ፡ በማከማቻው ፡ ስፍራ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሸቀ
ጦች ፡ በሚያሸጥበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጕዳይ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡
ውስጥ ፡ ስለ ፡ መያዣ ፡ ዕቃ ፡ ደንብ ፡ በተመለከተው ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ በተሰጠው ፡
ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ያሻሻጡ ፡ ሥርዐት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፫ ። በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረሙትን ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።

(፩) የመያዣው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የያዛቸውን ፡ ሸቀ
ጦች ፡ ሽያጭ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ በምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጀርባ ፡ የፈረሙ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) በምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጀርባ ፡ ተከታታይ ፡ ፈራሚዎች ፡ በሆኑት ፡ ላይ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቻልበት ፡ የጊዜ ፡ አወሳሰን ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ወረቀት ፡ በተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

(፫) ጊዜውም ፡ መታሰብ ፡ የሚጀምረው ፡ ሽቀጦቹ ፡ ከተሸጡበት ፡ ቀን ፡ አን ሥቶ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩ሺ፱፻፲፱ ። በደንብ ፡ የታዘዘውን ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርማሊቴ) ፡ ስለ ፡ ለመፈጸም ።**

(፩) የመያዣው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ የሚጠይቀው ፤ ሒሳብ ፡ እንዲከፈለው ፡ የተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ መከፈሉን ፡ መግለጫ ፡ (ፕሮቴ) ፡ ካላቀረበ ፡ ወይም ፡ ባቀረበ ፡ ባሥራ ፡ አምስቱ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሽቀጦቹ ፡ እንዲሸጡ ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሥርዐት ፡ ካልጀመረ ፡ በቀር ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ሊያቀርብ ፡ የሚችለውን ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያጣል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በደረሰኙ ፡ ሰነድ ፡ ጀርባ ፡ የፈረሙትንና ፡ ባለዕዳውን ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

(፫) ይህን ፡ ጥያቄ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ የተወሰነው ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ የሚጸናው ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።
## ስለ ፡ መያዣ ፡ ውል ።

### ክፍል ፡ ፩ ።
### ስለ ፡ መያዣ ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ።

#### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
#### የሚጸናባቸው ፡ ሁኔታዎች ።

**ቍ ፡ ፩ሺ፱፻፳ ። የመያዣ ፡ ውል ፡ ትርጓሜ ።**

(፩) የመያዣ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ባለዕዳ ፤ በባለገንዘቡ ፡ በኩል ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ መቻሉን ፡ በማረጋገጥ ፡ መያዣ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ ዕቃ ፡ ለመስጠት ፡ የሚገደድበት ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩ሺ፱፻፳፩ ። መያዣ ፡ ሰጪው ።**

ለሌላው ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ ዋስ ፡ እንዲሆን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከባለገንዘቡ ፡ ጋራ ፡ የመያዣውን ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፰፻፷፯ ። ዋስትና ፡ የተሰጠበት ፡ ዕዳ ።

ወደፊት ፡ ስለሚፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ ስላለበት ፡ ግዴታ ፡ በመያዣ ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፰፻፷፰ ። የአሠራሩ ፡ ሁኔታ ፡ ፎርም ።

(፩) ዋስትና ፡ የተሰጠበት ፡ ግዴታ ፡ ከፍተኛው ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማንኛቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ በግልጽ ፡ ተጠንቅቆ ፡ በመያዣው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ መመልከት ፡ ይገባዋል ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ውሉ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) የመያዣው ፡ ውል ፡ ከ፭፻ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገና ፡ ይኸውም ፡ ጽሑፍ ፡ እርግጠኛ ፡ ቀን ፡ ካገኘበት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይጸናም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፰፻፷፱ ። በመያዣ ፡ የተሰጠ ፡ ነገር ።

(፩) በመያዣነት ፡ የሚሰጠው ፡ አንድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፤ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ዕቃ ፡ ተብለው ፡ ከሚጠሩ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የመብት ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነድ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፪) ተለያይቶ ፡ በአደባባይ ፡ በሐራጅ ፡ ለመሸጥ ፡ የሚቻል ፡ ነገር ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፪ሺ፰፻፸ ። መያዣው ፡ በባለገንዘቡ ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በዕቃው ፡ ለማዘዝ ፡ የሚያስችሉት ፡ ሰነዶች ፡ ከተሰጡት ፤ ባለገንዘቡ ፡ መያዣውን ፡ እጅ ፡ እንዳደረገ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በማከማቻው ፡ ስፍራ ፡ የተቀመጠው ፡ የሸቀጥ ፡ መያዣ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ የሸቀጡ ፡ መላኪያ ፡ ሸኚ ፡ ደብዳቤ ፤ ወይም ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የተጫኑ ፡ ሸቀጦች ፡ የሚያመለክተው ፡ መሸኛ ፡ ወረቀት ፡ በስተጀርባው ፡ በባለገንዘቡ ፡ ስም ፡ ተጽፎ ፡ ከተሰጠው ፡ መያዣው ፡ በእጁ ፡ እንዳለ ፡ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፰፻፸፩ ። በተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ፡ መያዣው ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ መቀመጡ ።

(፩) መያዣው ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ስለ ፡ አደራ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ በወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይከናወናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፴፪ ። መያዣው ፡ በባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ በመያዣ ፡ ተሰጥቶ ፡ ተይዞዋል ፡ የተባለው ፡ ዕቃ ፡ ከባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ሳይወጣ ፡ በመያዣ ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ሆኖ ፡ ሊቈጠር ፡ አይችልም ።

(፪) በሕግ ፡ ከተፈቀደው ፡ በቀር ፡ መያዣው ፡ በባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ቢዋዋሉ ፡ ውሉ ፡ አይጸናም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፴፫ ። የመያዣ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ።

(፩) የመያዣ ፡ አሰጣጥን ፡ ውል ፡ የሚመለከቱ ፡ የውል ፡ አፈጻጸም ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ከተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ አጻጻፍና ፡ አፈጻጸም ፡ በሚሰጥ ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ መያገር ፡ እየ ተቀበሉ ፡ እንዲያበድሩ ፡ ተፈቅዶላቸው ፡ ስለሚቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ፡ በሚ ወጣ ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሚደነገግ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

(፪) በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ በተቀመጡት ፡ ሸቀጦች ፡ ስለ ፡ መዋዋል ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ በማከማቻ ፡ ስፍራ ፡ ስለሚቀመጥ ፡ ዕቃ ፡ በሚለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ተነግሮአል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ (፪) ።
## የመያዣ ፡ ሰጪው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፴፬ ። የመያዣው ፡ ዕቃ ፡ ባለሀብት ።

(፩) በመያዣው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ባለመብት ፡ የሚሆነውን ፡ ለይተው ፡ ካልተዋዋሉ ፡ በቀር ፡ አስያዡ ፡ በመያዣነት ፡ ለሰጠው ፡ ዕቃ ፡ ባለቤት ፡ ሆኖ ፡ የመቈየት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በዚህም ፡ መብቱ ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ ሊያዝበት ፡ በተለየም ፡ መያዣውን ፡ ሊሸጠው ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተተኪ ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ አሳልፎ ፡ ሊያ ሲዘው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፴፭ ። መያዣውን ፡ ለመጠበቅና ፡ በመልካም ፡ ለመያዝ ፡ የሚደረግ ፡ ወጪ ።

ዕቃውን ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለመጠበቅና ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ለመያዝ ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ አሲያዡ ፡ መክፈል ፡ አለ በት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፴፮ ። ባለገንዘቡ ፡ የሚያደርገው ፡ ኪሣራን ፡ ማለፍ ።

ዕቃውን ፡ በመያዣ ፡ ስም ፡ የተረከበው ፡ ባለገንዘብ ፡ በመያዣው ፡ ላይ ፡ መብቱ ፡ ከሚፈቅድለት ፡ በማለፍ ፡ አላገባብ ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለ ዕዳው ፡ የመያዣው ፡ ዕቃ ፡ ከባለገንዘቡ ፡ እጅ ፡ ወጥቶ ፡ የትእዛዝ ፡ ባላደራ ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ተዛውሮ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፴፯ ። ዕዳውን ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

(፩) ዕቃ ፡ አስያዥ ፡ የሆነው ፡ ባለዕዳው ፡ ዕቃው ፡ የተያዘበትን ፡ ገንዘብ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በመክፈል ፡ የተያዘው ፡ ዕቃ ፡ እንዲመለስለት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህን ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ አይጸናም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፴፰ ። ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሰጠው ፡ መያዣ ።**

(፩) መያዣውን ፡ የሰጠው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የማስያዙ ፡ ጕዳይ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በባለገንዘቡና ፡ በባለዕዳው ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ የዚህን ፡ የዕቃ ፡ አስያዡን ፡ ሁኔታ ፡ ሊያብስበት ፡ (ሊጎዳው )፡ አይችልም ።

(፪) ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ በዚህ ፡ አልከራከርም ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ለመቃወም ፡ ሳይቻል ፡ ባለዕዳው ፡ ሊከራከርበት ፡ የሚገባውን ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ መያዣ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ሊከራከርበት ፡ ይችላል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

ዕቃውን ፡ የያዘ ፡ የባለገንዘብ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፴፱ ። ጠቅላላ ፡ መሠረቱ ።**

(፩) መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ በባለዕዳው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ለሌሎቹ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ ለሱም ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ የመያዣውን ፡ ዕቃ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵ ። የመያዣው ፡ ዕቃ ፡ አገልግሎት ።**

መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ሰጪው ፡ ባለዕዳ ፡ ካልፈቀደለት ፡ ወይም ፡ ለተያዘው ፡ ዕቃ ፡ አጠባበቅ ፡ አገልግሎት ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ በተያዘው ፡ ዕቃ ፡ ለመገልገል ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፩ ። የመያዣው ፡ ፍሬ ።**

(፩) መያዣው ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍሬውን ፡ መሰብሰብ ፡ የሚገባቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ወይም ፡ ጠባቂው ፡ ናቸው ።

(፪) መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ከመያዣው ፡ ለተገኘ ፡ ፍሬ ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ።

(፫) መያዣው ፡ የሚሰጠው ፡ ፍሬ ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ለጥበቃውና ፡ ለአያያዙ ፡ ለተደረገው ፡ ወጪ ፡ መያዣው ፡ ለተያዘበት ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ለዋናውም ፡ ገንዘብ ፡ እየታሰበ ፡ ይቀነሳል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፪ ። የእጅ ፡ ክስ ።

(፩) መያዣውን ፡ የተቀበለ ፡ ባለገንዘብ ፡ ስለ ፡ መያዣው ፡ የእጅ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) መያዣውን ፡ የሚጠብቀው ፡ ሰው ፡ ይህንን ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ለባለገንዘቡና ፡ መያዣውን ፡ ለሰጠው ፡ ሰው ፡ ሳይዘገይ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፫ ። መያዣው ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ።

መያዣ ፡ የተቀበለ ፡ ባለገንዘብ ፡ ይህን ፡ መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ ከሌለው ፡ ሰው ፡ ላይም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፤ የመያዣው ፡ ውል ፡ በሚሰጠው ፡ መብት ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፬ ። ልዩነት ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የመያዣው ፡ ባለቤት ፤ የመያዣው ፡ ውል ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ መያዣውን ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፤ መያዣ ፡ ሰጪው ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ የሌለውና ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ሲገባው ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ ካስረዳ ፡ የተያዘውን ፡ ዕቃ ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ዕቃው ፡ በዋስትና ፡ የተያዘበትን ፡ ዕዳ ፡ በመክፈል ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፭ ። መያዣውን ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

(፩) ገንዘቡ ፡ በመከፈሉ ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የመያዣው ፡ ውል ፡ ሲያልቅ ፡ መያዣውን ፡ የተቀበለ ፡ ባለገንዘብ ፡ ለዕቃ ፡ አስያዡ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ይቀበልልኝ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ዕቃውን ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) መያዣውን ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ መያዣ ፡ የሆነውን ፡ ዕቃ ፡ እስኪመልስ ፡ ድረስ ፡ በአንድ ፡ ዕቃ ፡ ጥቅም ፡ በሚያገኝ ፡ ባለይዞታ ፡ ላይ ፡ በሚፈጸመው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ስለዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፮ ። ይዞ ፡ የማቈየት ፡ መብት ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ መያዣውን ፡ የተቀበለ ፡ ባለገንዘብ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ የመያዣውን ፡ ዕቃ ፡ በእጁ ፡ የማቈየት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፯ ። የመያዣው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ።

መያዣውን ፡ ተረክቦ ፡ የሚጠብቀው ፡ ባለገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፤ ስለ ፡ መያዣው ፡ መጥፋትና ፡ በመበላሸት ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ራሱ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፰ ። ስለ ፡ ዕቃ ፡ መተካት ።

መያዣው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢጠፋ ፡ ወይም ፡ ቢበላሽ ፤ መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ መብት ፡ የሚተካው ፤ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ሊከፍል ፡ በሚገባው ፡ ኪሣራ ፤ ወይም ፡ የዕቃውን ፡ አሱራንስ ፡ ያደረገው ፡ በሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ዕቃውን ፡ የወሰደው ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊከፍለው ፡ በሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

የመያዣ ፡ ውል ፡ የሚቀርበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፵፱ ። ውሉ ፡ በተጨማሪ ፡ ዐይነት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

ዕቃው ፡ የተያዘበት ፡ የዋስትና ፡ ዕዳ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመያዣው ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ የተያዘውም ፡ ዕቃ ፡ ላስያዡ ፡ ይመለሳል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶ ። መያዣው ፡ የማይከፋፈል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

የብድሩ ፡ ገንዘብና ፡ የመያዣው ፡ ዕቃ ፡ ለመከፋፈል ፡ የሚችል ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ካልተከፈለው ፡ በቀር ፡ መያዣውን ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ እንዲመልስ ፡ አይገደድም ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፭ ።

የመያዣ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፩ ። መያዣን ፡ ይዞ ፡ ለመቅረት ፡ ስለሚደረግ ፡ ስምምነት ።

(፩) ዕዳው ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ ባለዕዳው ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለገንዘቡ ፡ በሕጉ ፡ የተደነገገውን ፡ ሥርዐት ፡ ፎርማሊቴ ፡ ሳይፈጽም ፡ መያዣውን ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ ለራሱ ፡ ማስቀረት ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ ቢስማሙ ፤ ስምምነቱ ፡ መያዣው ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ አይጸናም ።

(፪) ለዕዳው ፡ መክፈያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ባለዕዳው ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ምትክ ፡ መያዣውን ፡ እንዲለቅ ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፪ ። የመያዣው ፡ ውል ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የመያዣው ፡ ውል ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ እንዲችል ፡ ባለገንዘቡ ፡ በመያዣው ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ መያዣው ፡ በባለገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በመረጡት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲገኝ ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፤ የዕዳ ፡ ዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሆነው ፡ ዕቃ ፡ ከባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ካልወጣ ፤ ወይም ፡ በባለገንዘቡ ፡ ፈቃድ ፡ ከባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ተመልሶ ፡ ከገባ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ባለገንዘቡ ፡ አምጣ ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡

BACK



መብት ፡ በሌለው ፡ በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ከሆነ ፡ የመያዣው ፡ ውል ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

ቍ፡ ፪ሺ፰፻፶፫ ። ስለ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አሰጣጥ ።

(፩) መያዣውን ፡ የያዘው ፡ ባለገንዘብ ፡ የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ከመሸጡ ፡ በፊት ፡ አስያዡ ፡ ባለዕዳ ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ሳይፈጽም ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ዕቃውን ፡ የሚያሸጥበት ፡ መሆኑን ፡ አስቀድሞ ፡ በማስጠንቀቅ ፡ ማስታ ወቂያ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) የዚህም ፡ ዐይነት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መያዣውን ፡ ሰጭ ፡ ለሆነው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፬ ። የመያዣው ፡ መሸጥ ።

(፩) ማስጠንቀቂያው ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ተከታዩ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ማንኛውም ፡ መቃወሚያ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የቀረበው ፡ መቃወሚያ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቡ ፡ መያዣውን ፡ በአደባባይ ፡ በሐራጅ ፡ ለማሸጥ ፡ ይችላል።

(፪) መያዣ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በዕለት ፡ ገበያ ፡ የተወሰነ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲሸጥ ፡ በተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ዕቃው ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፭ ። ዳኞች ፡ የሚያደርጉት ፡ አወሳሰን ።

መያዣ ፡ ሰጪው ፡ መቃወሚያ ፡ አቅርቦላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የመያ ዣው ፡ ዋጋ ፡ የባለገንዘቡን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የሚበቃውን ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ዕቃ ፡ እንዲሸጥና ፡ ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ የባለገንዘቡን ፡ መብት ፡ በዚሁ ፡ ብቻ ፡ ሊወስኑበት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፮ ። መያዣው ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ (ለባለገንዘቡ) ፡ የሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ።

ባለገንዘቡ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ መያዣ ፡ በዋስትና ፡ የተቀበለውን ፡ ዕቃ ፤ በልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ በተሰጠው ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ በዕለት ፡ ገበያ ፡ በተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ተገምቶ ፡ ሊከፈለው ፡ ከሚገባው ፡ ሒሳብ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆነውን ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ዕዳው ፡ ለራሱ ፡ እንዲያስቀረው ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፯ ። የቀዳሚነት ፡ መብት ።

(፩) መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ከመያዣው ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ከሌሎቹ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ቀድሞ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የመያዣው ፡ ዋስነት ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ለዋናው ፡ ዕዳና ፡ ለወለዱ ፤ ጊዜው ፡ በማለፍ ፡ ለሚከፈለው ፡ ወለድ ፤ መያዣውን ፡ ለመጠበ

ቅና ፡ በመልካም ፡ አያያዝ ፡ ለማኖር ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ለሚደረገው ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፰ ። የባለገንዘቡ ፡ መብቶች ፡ ወሰን ።

(፩) ባለገንዘቡ ፡ በመያዣው ፡ ውል ፡ ከተወሰነው ፡ ከፍተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ሊከራከርበት ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የመያዣው ፡ ውል ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የተገኘ ፤ ከባለዕዳው ፡ ወይም ፡ ከዕቃ ፡ አስያዡ ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀው ፡ ሌላ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖረውም ፡ በመያዣው ፡ ላይ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ሊከራከር ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፶፱ ። የዋጋው ፡ አሰጣጥ ።

(፩) የመያዣው ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ሊከፈለው ፡ እስከሚገባው ፡ ተመዛዛኝ ፡ ሒሳብ ፡ ድረስ ፡ ተሰጥቶ ፡ ዕቃ ፡ አስያዡ ፡ ዕዳውን ፡ እንደ ፡ ከፈለ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ከዕዳው ፡ ሒሳብ ፡ የተረፈው ፡ የሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ለዕቃ ፡ አስያዡ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፷ ። መያዣ ፡ ስለ ፡ ተቀበሉ ፡ ብዙ ፡ ባለገንዘቦች ።

(፩) ዕቃው ፡ ብዙ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ጠያቂ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቦቹ ፡ ሒሳባቸው ፡ የሚከፈላቸው ፡ እንደ ፡ ቅድሚያ ፡ ደረጃቸው ፡ ነው ።

(፪) የቅድሚያ ፡ ደረጃቸውም ፡ የሚመደበው ፡ መያዣውን ፡ ባደረጉበት ፡ ቀን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፷፩ ። የገዥው ፡ መብቶች ።

(፩) መያዣውን ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ ለዕቃው ፡ ባለቤትነቱ ፡ ከማናቸውም ፡ ዕዳ ፡ ነጻ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፷፪ ። የባለገንዘቡ ፡ አላፊነት ።

የመያዣው ፡ ውል ፡ በተጻፈበት ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለውን ፡ የሌላውን ፡ ዕቃ ፡ የሚሸጥ ፡ ባለገንዘብ ፡ ዕቃውን ፡ በመሸጡ ፡ ማንኛውም ፡ አላፊነት ፡ አይደርስበትም ።

ክፍል ፡ ፪ ።

የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነዶችን ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ ያልሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሀብቶችን ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፷፫ ። በመያዣ ፡ ሰጪውና ፡ በባለዕዳው ፡ መካከል ፡ ስላሉ ፡ ግንኙነቶች ።

በዋሱና ፡ በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ደንብ ፡ የተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ ዕቃውን ፡ ባስያዘው ፡ በሦስተኛው ፡ ወገንና ፡

በዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ማንኙት ፡ በሚመለከተውም ፡ ጉዳይ ፡ ተፈ ጻሚ ፡ ሆኖ ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፬ ። የሰነድ ፡ ማስረጃ ፡ የሌለው፡ገንዘብ ።</u>

(፩) በሰነድ ፡ ላይ ፡ ያልተገለጸ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ሰነድ ፡ በመያዣ፡ ሲሰጥ ፡ ዋስትና ፡ የሚሰጥበት ፡ ገንዘብ ፡ ማንኛውም ፡ ብዛት ፡ ቢኖረው ፤ በመ ያዣው ፡ የተሰጠው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብት ፡ ማስረጃ ፡ የምን ፡ ያህል፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ዋስትና ፡ የሚሰጥበት ፡ ገንዘብ ፡ ስንት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አብዛኛውን ፡ ልክ ፡ በግልጽ ፡ የሚያመለክት ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) በመያዣ ፡ የተሰጠው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ የመያዣው ፡ ገንዘብ፡ ባለዕዳ ፡ እንዲያውቀው ፡ ካልተደረገ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ በተመ ለከተበት ፡ ጽሑፍ ፡ ውሉን ፡ ካልተቀበለ ፡ የተሰጠው ፡ መያዣ ፡ አይጸናም ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፭ ። በሰነድ ፡ ላይ፡ያልተገለጸ ፡ መብት ።</u>

(፩) የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ያልሆነና ፡ በሰነድ ፡ ያልተገለጸ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ በመያዣ ፡ ሲሰጥ ፤ የመያዣው ፡ ውል ፡ የሚከናወነው ፡ ለነዚህ ፡ መብቶች ፡ ማስተላለፍ ፡ በተደነገገው ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም) ፡ ነው ።

(፪) በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ የመብት ፡ ዐይነትና ፡ ዋስትና ፡ የሚሰጥበትን ፡ የገ ንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነድ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ በመዘርዘር ፡ የሚገልጽ ፡ ቀኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲኖር ፤ በማንኛውም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሳይፈጸም ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) አንዳንዶቹ ፡ መብቶች ፡ በመያዣነት ፡ ሲሰጡ ፤ የሚሠራባቸው ፡ ድንጋጌዎች፡ የተጠበቁ ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፮ ። በሰነድ ፡ የተገለጸ ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ።</u>

(፩) በመያዣነት ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ መብት ፡ በዕዳ ፡ መተማመኛ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ መለዋወጫ ፡ ባልሆነ ፡ በሌላ ፡ ሰነድ ፡ የተጻፈ ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ ሰነድ ፡ መያዣ ፡ በተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ወይም ፡ በመያ ዣው ፡ ውል ፡ በተስማሙበት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ሊቀመጥ ፡ ይገባል ።

(፪) የንግድ ፡ መለዋወጫ ፡ መሆናቸው ፡ በጽሑፍ ፡ የተገለጹትን ፡ የገንዘብ ፡ መጠ የቂያ ፡ መብት ፡ የሆኑትንና ፡ ሰነዶች ፡ በመያዣ ፡ የመስጠቱ ፡ ሥርዐት ፡ የሚ ፈጸመው ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፯ ። በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የገቢ፡ጥቅም ፡ የሚሰጡ፡የገንዘብ ፡ መብት ፡ ሰነዶች ። (፩) የመያዣው ፡ ወሰን ።**

(፩) እንደ ፡ ጥቅም ፡ ድርሻ ፡ (ዲቢዳንድ) ፡ የሆኑ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኙ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነዶች ፡ በመያዣ ፡ በተሰጡ ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ መያዣነታቸው ፡ የሚጸናው ፡ ወደፊት ፡ በሚያስገኙት ፡ ትርፎች ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የመከፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ ባለፉት ፡ ትርፎች ፡ ላይ ፡ አይደለም ።

(፪) እነዚህ ፡ ተጨማሪ ፡ ትርፎች ፡ በልዩ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ ተለይተው ፡ በመዘርዘር ፡ የተመለከቱ ፡ ከሆኑ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተፈቀደው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ራሳቸው ፡ መያዣ ፡ ሆነው ፡ ካልተሰጡ ፡ በቀር ፡ በመያዣው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ አይቈጠሩም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፰ ።(፪)መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ።**

(፩) መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ የተቀበለው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነድ ፡ የሚያስገኘውን ፡ ወለድና ፡ እንደዚሁም ፡ የዚሁ ፡ የገንዘብ ፡ መቀበያ ፡ ሰነድ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በየጊዜው ፡ መከፈል ፡ የሚገባቸውን ፡ ሌሎቹን ፡ ገቢዎች ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

(፪) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ያገኘውንም ፡ ለእሱ ፡ ራሱ ፡ ከሚከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፡ ሊቀነስ ፡ የሚገባው ፡ አስቀድሞ ፡ ስላደረጋቸው ፡ ወጪዎች ፡ ቀጥሎ ፡ ስለሚቀበላቸው ፡ ወለዶች ፡ በመጨረሻም ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፫) አስያዡ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ አከፋፈል ፡ ለመቃወም ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፷፱ ። መጠበቂያ፡የሚሆኑ፡ተግባሮች ።**

መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ በመያዣ ፡ የተረከባቸውን ፡ መብቶች ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፸ ። በመያዣ፡የተሰጡ፡አክሲዮኖች ።**

አክሲዮኖች ፡ በመያዣ ፡ በተሰጡ ፡ ጊዜ ፡ በአክሲዮኔሮች ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠው ፡ አክሲዮኔሩ ፡ ራሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አክሲዮን ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፸፩ ። በመያዣ ፡ ስለ፡ተሰጠው ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ፡የባለዕዳው ፡ መብቶች ።**

(፩) በመያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነድ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ከእሱ ፡ ገንዘብ ፡ ፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ የሚከራከርበትን ፡ መብት ፡ መያዣ ፡ የተቀበለውን ፡ ሌላውንም ፡ ባለገንዘብ ፡ ሊከራከርበት ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የመያዣ ፡ መስጫውን ፡ ውል ፡ ያቋቋመውን ፡ ስምምነት ፡ ያላንዳች ፡ ክርክር ፡ ባለዕዳ ፡ ፈቅዶ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእሱና ፡ ከእሱ፡ላይ ፡

ገንዘብ ፡ በሚፈልገው ፡ መካከል ፡ በነበረው ፡ ግንኙነት ፡ የሆነውን ፡ የዕዳ ፡ መቻቻል ፡ ሊከራከርበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፪ ። በመያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ሰነድ ፡ የሚያመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ የሚጠይቀው ፡ መብት ፡ እንዲከፈለው ፡ የተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፤ በመያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ሰነድ ፡ የሚያመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ዕዳው ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ እንዳይከፈል ፡ መያዣ ፡ ሰጪው ፡ የተቃወመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለዕዳው ፡ የሚጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ገቢ ፡ ካላደረገ ፡ ወይም ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ካላስረከበ ፡ በቀር ፡ ከዕዳው ፡ ነጻ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፫) ስለ ፡ ዕዳው ፡ ክፍያ ፡ የተሰጡት ፡ ገቢ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ አላቂ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ የሚቀመጡበት ፡ ስፍራ ፡ የሚመረጠው ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፤ ይህ ፡ ስምምነት ፡ ባይኖር ፤ በዳኞች ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፫ ። የገንዘብ ፡ መጠየቂያውን ፡ መብት ፡ ሰነድ ፤ ወይም ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

ዋስትና ፡ የተሰጠበት ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፈል ፡ የመጠየቂያው ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ በመያዣ ፡ የተቀበለውን ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ መብት ፡ ወይም ፤ ባለዕዳው ፡ ስለ ፡ ዕዳው ፡ ክፍያ ፡ ያስረከባቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክፍል ፡ የተመለከተውን ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ለማሸጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፬ ። በላይኛው ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ስለ ፡ መመራት ።

የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ሰነዶችን ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ ያልሆኑ ፡ ሀብቶችን ፡ በመያዣ ፡ የመስጠትን ፡ ሥርዐት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ላልተመለከተው ፡ ደንብ ፡ ሁሉ ፤ በጠቅላላው ፡ የመያዣን ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ስለሚመለከተው ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ ይጸናል ።

## አንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ።

## የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ስለ ፡ ሚመለከቱ ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሽያጭ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፭ ። መሠረቱ ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሽያጭ ፡ የሚመራው ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ያንድ ፡ ነገ

ርን ፡ ባለሀብትነት ፡ ማስተላለፍን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ በተደነገገው ፡ አንቀጽ ፡ በተመለከተው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፮ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መሥራትና ፡ መሸጥ ።

አንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ አንድ ፡ ቤት ፤ አንድ ፡ የቤት ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ገና ፡ የሌለ ፡ አንድ ፡ የሚሠራ ፡ ሕንጻ ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፤ የአንድ ፡ ሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፤ የሽያጭ ፡ ውል ፡ ሊባል ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፯ ። የውሉ ፡ ፎርም ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ ሳይደረግ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፰ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ ማጻፍ ።

ያንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ ንብረቱ ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ በሚገኘው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ መዝገብ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ ውጤትን ፡ ሊያስገኝ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፸፱ ። የንብረቱ ፡ ሻጭ ፡ የነገሩ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ገዢው ፡ የገዛውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሀብትነት ፡ በስሙ ፡ ለማዛወርና ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ለማጻፍ ፡ እንዲችል ፡ ሻጩ ፡ የንብረቱን ፡ ሰነድና ፡ ማንኛውንም ፡ ማስረጃ ፡ ሁሉ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ።

(፪) ይህ ፡ ግዴታም ፡ ለሽያጩ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ስምምነት ፡ ሆኖ ፡ የሚገመት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹ ። ሻጩ ፡ አንዳንድ ፡ መብቶችን ፡ መግለጽ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ሳይጻፉ ፡ በገዥ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑበት ፡ የሚችሉትን ፡ የተሸጠውን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የሚመለከቱትን ፡ የ፫ኛ ፡ ወገኖች ፡ መብቶች ፡ ሻጩ ፡ ለገዥ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጥቅም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ የተጻፉትን ፡ መብቶች ፡ ሻጩ ፡ ለገዢው ፡ ገልጾ ፡ እንዲያስታውቀው ፡ ውሉ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፩ ። የተመዘገቡ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። (፩) መሠረቱ ።

ገዢው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ባለው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፤ የተጻፉትን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የሚመለከቱትን ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያውቅ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፪ ። (፪)የሻጩ ፡ ግልጽ ፡ ዋስትና ።**

(፩) በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከቱትን ፡ መብቶች ፡ በሚመለከት ፡ ምክንያት ፡ በሸጥኩት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመነቀል ፡ ነገር ፡ ሊደርስ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ሻጩ ፡ መድን ፡ ሊሆን ፡ ቃል ፡ ካልገባ ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ የማስለቀቅን ፡ ዋስትና ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሊከራከርባቸው ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) ይህም ፡ የአላፊነት ፡ ዋስትና ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡ በሽያጩ ፡ ውል ፡ ላይ ፤ በግልጽ ፡ የተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ፡ ፪ሺ፰፻፹፫ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣና ፡ የወለድ ፡ አግድ ።**

የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፤ መያዣ ፡ ባለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ (በዕዳ ፡ ገንዘብ) ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ በያዘው ፡ ሰው ፡ ጠያቂነት ፡ በፍርድ ፡ ተይዞ ፡ እንዲሸጥ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ ስለ ፡ መነቀሉ ፡ ሻጩ ፡ በመድንነቱ ፡ እንዲያልፍ ፡ ለመጠየቅና ፡ በዚሁም ፡ መብቱ ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፬ ። የሌላውን ፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀስ፡ንብረት፡ስለ፡መሸጥ ።**

(፩) የተሸጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሻጩ ፡ ሀብት ፡ ሳይሆን ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመነቀልን ፡ የአላፊነት ፡ ዋስትናን ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ገዢው ፡ የገዛውን ፡ ንብረት ፡ እንዲለቅ ፡ መደረጉን ፡ ሳይጠብቅ ፡ በዚህ ፡ የመነቀል ፡ የአላፊነት ፡ ዋስትና ፡ ደንብ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊጠቀምበት ፡ ይችላል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ የገዥነት ፡ መብቱን ፡ እንዳያጣ ፡ ዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጡ ፡ በደረሱበት ፡ ጊዜ ፡ የመነቀሉም ፡ ጉዳይ ፡ የማያስፈራው ፡ ከሆነ ፡ በነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፭ ። በቀዳሚነት ፡ ይገባኛል፡የማለት፡መብት ።**

በውሉ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የተሸጠውን፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ገዢው ፡ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ለሚል ፡ ሰው ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሻጩ ፡ ለገዢው ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፮።የሻጩ፡አላፊነት ።**

ገዢው ፡ የገዛውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዋጋውና ፡ በውሉ ፡ ካደረገው ፡ ወጪ ፡ በላይ ፡

BACK



ገዢው ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ ለማልሚያ ፡ ያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመልስለት ፡ ሻጩን ፡ በአላፊነት ፡ ይጠይቃል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፯ ። ጉዳት ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ የንብረትን ፡ ሽያጭ ፡ ገዢው ፡ ወይም ፡ ሻጩ ፡ ተጎዳሁ ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ ሊያፈርሱት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፰ ። በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ሀብት ፡ የሚሰጥ ፡ ዋስትና ። (፩) መሠረቱ ።**

የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ስፋት ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተ ፡ ከሆነ ፡ ሻጩ ፡ በዚህ ፡ በንብረት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ዋስ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፹፱ ። (፪) የገዢው ፡ መብት ።**

(፩) በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ የተገኘው ፡ ሀብት ፡ ይገኛል ፡ ተብሎ ፡ ከተረጋገጠው ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ በዚሁ ፡ በጐደለው ፡ ሀብት ፡ መጠን ፡ የዋጋ ፡ ቅናሽ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ዋጋ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ሻጩ ፡ እንደ ፡ ገለጸው ፡ ንብረቱ ፡ ለተመደበበት ፡ ጕዳይ ፡ የማያገለግል ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺ ። (፫) ሁኔታና ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ።**

በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ሀብት ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ የገዢው ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ በጕድለቱ ፡ ማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ ላይ ፡ በተመሠረተው ፡ ሁኔታና ፡ ለዚያው ፡ በሚጸናው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፩ ። (፬) የሻጩ ፡ መብት ።**

(፩) የተሸጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ልክ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ እንኳ ፡ ሻጩ ፡ ዋጋ ፡ እንዲጨመርለት ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) ሻጩ ፡ ስሕተት ፡ የደረሰበት ፡ በገዢው ፡ ወይም ፡ በእንደራሴው ፡ አታላይነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ (ሻጩ) ፡ መብቱን ፡ የሚጠይቅበት ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀለት ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፪ ። ውሉ ፡ በግዴታ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ቃሉ ፡ ዐይነት ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለማድረግ ፡ የተለየ ፡ ጥቅም ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

BACK



(፪) ስለዚህ ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ቃሉ ፡ ዐይነት ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ ሻጩ ፡ ውሉን ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ከመፈጸም ፡ መዘግየቱን ፡ ከተረዳበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ካልጠየቀ ፡ በቀር ፡ ገዢው ፡ ውሉ ፡ በግዴታ ፡ እንዲፈጸም ፡ የማድረግ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፫ ። መልሶ ፡ የመግዛትን ፡ መብት ፡ አስጠብቆ ፡ ስለ፡ሚደረግ፡ሽያጭ ።</u>

(፩) ሻጩ፡የሸጠውን፡የማይንቀሳቀስ፡ንብረት ፡ ከገዢው ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ የሚችልበትን ፡ መብቱን ፡ በሽያጩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ አስጠብቆ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

(፪) የጋራ ፡ ሀብትነትን ፡ የአላባ ፡ ተቀባይነትንና ፡ የሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶችን ፡ በሚመለከቱት ፡ አንቀጾች ፡ ለመሸጥ ፡ የተሰፋ ፡ ቃል ፡ መስጠትን ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በዚህም ፡ ስምምነት ፡ ተፈጻሚችን ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፬ ። ከሽያጭ ፡ ጋራ ፡ የተዛመዱ ፡ ውሎች ።</u>

የልዋጭን ፡ ውል ፤ ከሀብትነት ፡ በቀር ፡ መብቶችን ፡ ማስተላለፍንና ፡ የኪራይ ፡ ሽያጭን ፡ መብት ፡ ስለሚያስተላልፉ ፡ ውሎች ፡ ጕዳይ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ በሚመለከቱት ፡ ጕዳዮችም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፭ ። የኪራይ ፡ ሽያጭ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ፡መዝገብ ፡ ስለ ፡ ማጻፍ ።</u>

የኪራይ ፡ ሽያጭ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ተከራዩ ፡ ገዥ ፡ በውሉ ፡ የተሰጠውን ፡ የቀደምትነት ፡ መግዛት ፡ መብቱን ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ አገር ፡ ባለው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መጻፊያ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ለማጻፍ ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## <u>ስለ ፡ ኪራይ ።</u>

### ክፍል ፡ ፩ ።

### <u>ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይ ፡ በጠቅላላው ።</u>

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፮።ትርጓሜ።</u>

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ኪራይ፡ማለት፡አከራይ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራይ ፡ ተብሎ ፡ ለሚጠራው ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፤ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተከራይ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ኪራይ ፡ እየከፈለ ፡ ባንድ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ እንዲጠቀም ፡ ወይም ፡ እንዲገለገል ፡ የሚረጋገጥበት ፡ የውል፡ ስምምነት ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) የንግድ ፡ ወይም ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንባቸውን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ኪራይ ፡ የሚመለከቱትና ፡ በንግድ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፯ ። ኪራይና ፡ ሽያጭ ።**

ተከራዩ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ኪራይ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ለተከራየው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነታቸውን ፡ እንደ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ብለው ፡ ቢሰይሙትም ፡ እንኳ ፡ ውላቸው ፡ እንደ ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፰ ። የውሉ ፡ ማስረጃ ።**

(፩) አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ተከራይቶ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ የመከራየቱ ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በማቅረብ ፤ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ችሎት ፡ ፊት ፡ በተሰጠ ፡ የቃል ፡ መተማመን ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ በተሰጠ ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ አስረጅነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውል ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ለማስረዳት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ማስረጃዎች ፡ ሌላ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፫) ቢሆንም ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ የመከናወኑን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ ምስክሮች ፡ በማቅረብ ፡ ወይም ፡ በግምት ፡ አስተያየት ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፰፻፺፱ ። በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።**

(፩) ካ፲ ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የኪራይ ፡ ውሎች ፡ ንብረቶቹ ፡ በሚገኙበት ፡ አገር ፡ ባለው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ካልተጻፉ ፡ በቀር ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

(፪) ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ያልተጻፈ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ያጻፉትን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብታቸውን ፡ ካጻፉበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፫) እንደዚህ ፡ ያልሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።**

(፩) አከራዩ ፡ ያከራየውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ከተጨማሪ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ጋራና ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሀብቱ ፡ ተፈጥሮ ፡ መሠረት ፡ ለተመደበበት ፡ ጕዳይ ፡ ሊያገለግል ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ አሟልቶ ፡ ለተከራዩ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

(፪) የማስረከቢያው ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ የሚወሰነው ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌና ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፩ ። የሥራዎች ፡ ሁኔታና ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) አንደኛው ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ለተከራዩ ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፡ የተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚገኝበት ፡ ሁኔታና ፡ እንዲሁም ፡ ከተከራየው ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ የሚገኘው ፡ የተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ ዝርዝርና ፡ የዋጋውም ፡ ግምት ፡ ጭምር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ጥያቄው ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለተከራዩ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፪ ። (፪) ወጪ ።**

(፩) ለተከራየው ፡ ሀብት ፡ የስፍራ ፡ ሁኔታና ፡ ለዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ መጻፊያ ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ የሚችሉት ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ናቸው ።

(፪) ተከራዩ ፡ ለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ ወጪ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለአከራዩ ፡ ከሚከፍለው ፡ የኪራይ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሒሳቡ ፡ ቀንሶ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፫ ። (፫) ቅጣት ።**

(፩) ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ የስፍራውን ፡ ሁኔታና ፡ የዕቃውን ፡ ዝርዝር ፡ የሚያመለክተውን ፡ ሰነድ ፡ በአድነት ፡ ሁኖ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ በራሱ ፡ ሠርቶ ፡ ወይም ፡ አሠርቶ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህኛውም ፡ ወገን ፡ የሚያደርጋቸውን ፡ መቃወሚያዎችና ፡ ይጠበቅልኝ ፡ የሚለውን ፡ መብቱን ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ላንደኛው ፡ ተዋዋዩ ፡ ካላስታወቀ ፡ ይህን፡የቦታ ፡ ሁኔታ ፡ መግለጫና ፡ ዝርዝሩን ፡ ፈቅዶ ፡ እንደ ፡ ተቀበላቸው ፡ ይቈጠራል ።

(፫) አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ የሚያቀርባቸው ፡ መቃወሚያዎችና ፡ ይጠበቁልኝ ፡ የሚላቸው ፡ መብቶች ፡ ዋጋ ፡ የሚኖራቸው ፡ ማስታወቂያው ፡ ከደረሰው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በ፮ ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ሁኔታና ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ያዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፩ ። የዕቃው ፡ ጕድለት ፡ (፩) የውሉ ፡ መፍረስ ።**

(፩) የመረካከቡ ፡ ጕዳይ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፤ የተከራየው ፡ ሀብት ፡ የተመደበበትን ፡ አገልግሎት ፡ እንደሚቀንስ ፡ ዐይነት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ጕድለት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ከተረከበ ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ጕድለት ፡ የደረሰ ፡ ወይም ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝልኝ ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፫) ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ አከራዩ ፡ ይህን ፡ ጕዳይ ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተከራዩ ፡ በተከራየው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገባም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፪ ። (፪) የጉዳት ፡ ኪሣራ ።**

(፩) አከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ሀብት ፡ ለተከራዩ ፡ ባስረከበበት ፡ ጊዜ ፡ የተከራየው ፡ ሀብት ፡ ጕድለት ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ ሲያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ሲሆን ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጕድለት ፡ ለተከራዩ ፡ ሳያስታውቅ ፡ በቸልታ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አስረክቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፤ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ የውሉ ፡ ዘመን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጕድለት ፡ በአከራዩ ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፫ ። (፫) ከውሉ ፡ መፍረስ ፡ ጋራ ፡ ስላለ ፡ ግንኙነት ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ከውሉ ፡ መፍረስ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለውም ።

(፪) ውሉን ፡ ማፍረስ ፡ አስፈላጊ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ ኪሣራው ፡ እንዲከፈል ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) የውሉ ፡ መፍረስ ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቁንም ፡ በውሉ ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ለመካሥ ፡ ሲባል ፡ የጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈል ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፬ ። (፬) የሚታይ ፡ ጕድለት ።**

ተከራዩ ፡ የሚከራከርበት ፡ ጕድለት ፡ የሚታይ ፡ ጕድለት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህንንም ፡ ጕድለት ፡ ውሉን ፡ በፈረመበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያውቀው ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ የመከራከሪያ ፡ መብቱን ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፰ ። (፰) አደገኛ ፡ ጕድለት ።

(፩) ስለ ፡ ሆነም ፡ የተከራየው ፡ ሀብት ፡ በተከራዩ ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ በጤንነቱ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ አብረው ፡ በሚኖሩት ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ፡ ሕይወትና ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ የሚገመት ፡ አደጋ ፡ የሚያደርስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ጕድለት ፡ የሚታይ ፡ ጕድለት ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጕድለት ፡ መኖሩን ፡ ውሉን ፡ በተዋዋለበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያውቅ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ተከራዩ ፡ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ስምምነት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፱ ። (፱) አላፊነትን ፡ የሚያስወግድ ፡ ስምምነት ።

በተከራየው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጕድለት ፡ አከራዩ ፡ በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ ደብቆ ፡ ሳይገልጽ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እነዚህ ፡ ጕድለቶች ፡ ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ሀብት ፡ ጠቃሚነት ፡ የሚያስቀሩ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በንብረቱ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስበትን ፡ አላፊነት ፡ የሚያስወግዱ ፡ ወይም ፡ አላፊነቱን ፡ የተወሰነ ፡ የሚያደርጉ ፡ ማንኛቸውም ፡ ስምምነቶች ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲ ። (፲) በውሉ ፡ ስምምነት ፡ የተሰጠ ፡ ዋስትና ።

(፩) የተከራየው ፡ ሀብት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ አከራዩ ፡ በግልጽ ፡ ያረጋገጠው ፡ ዐይነተኛ ፡ ነገር ፡ በሀብቱ ፡ ላይ ፡ የሌለ ፡ ወይም ፡ ሳይኖር ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከራዩ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስለት ፡ ለመጠየቅና ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህን ፡ መብት ፡ በመቀነስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ አከራዩ ፡ ሊከራከርባቸው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፩ ። በተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሰላም ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

ተከራዩ ፡ በተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የኪራዩ ፡ ዘመን ፡ ጸንቶ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በሰላም ፡ ሊጠቀምበት ፡ እንዲችል ፡ አከራዩ ፡ ዋስትና ፡ ይሰጠዋል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፪ ። የተከራየውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

አከራዩ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ጸንቶ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሁኔታ ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፫ ። በተከራየው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ በማለት ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ የሚያቀርበው ፡ ክርክር ።**

(፩) የተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ንብ ረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ክርክር ፡ ያነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ላከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ክርክሩን ፡ በፍርድ ፡ ፊት ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተ ነሣው ፡ ክርክር ፡ በሦስተኛው ፡ ሰውና ፡ ባከራዩ ፡ መካከል ፡ እንዲፈጸምና ፡ ተከራዩ ፡ ከነገሩ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በዚሁ ፡ በተነሣው ፡ ክርክር ፡ ምክንያት ፡ በተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብ ረት ፡ የሚገለገልበት ፡ ጥቅሙ ፡ ተቋርጦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ሁከትና ፡ ችግር ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑን ፡ ለአከራዩ ፡ ካስታወቀ ፡ ጥቅሙ ፡ ለተቋረጠበት ፡ ጊዜ ፡ ካለው ፡ ሒሳብ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆን ፡ መጠን ፡ ከኪራዩ ፡ ላይ ፡ ቀንሶ ፡ ማስቀረት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፬ ። ቀላል ፡ የሆነ ፡ አድራጎት ፡ ሁከት ።**

(፩) በተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መብት ፡ አለን ፡ በማይሉ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ አድራጎት ፡ ለሚነሣው ፡ ሁከት ፡ አከራዩ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ አይገደድም ።

(፪) ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሁከት ፡ ለማስወገድ ፡ ተከራዩ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ለመ ከራከር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፭ ። ቀረጥና ፡ ግብር ።**

ከተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ የሚከፍል ፡ አከራዩ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፮ ። ስለ ፡ ማሳደስ ፡ (፩) ያከራዩ ፡ ግዴታዎች ።**

አከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሚገባ ፡ መጠበቅና ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ዘመን ፡ ጸንቶ ፡ እስከሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለንብረቱ ፡ ማደሻ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውንና ፡ በኪራዩ ፡ ውስጥ ፡ የማይታሰበውን ፡ የማደሻ ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ መቻል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፯ ። (፪) ለአከሪ ፉ ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

የተከራየው ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ጥበቃውና ፡ ስለ ፡ አያያዙ ፡ የማደሻ ፡ ወጪ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሁኖ ፡ ይህንንም ፡ ወጪ ፡ የሚችለው ፡ ተከራዩ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተከራዩ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ላከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፰ ። (፫) የማደሱ ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትለውን ፡ የመቻል ፡ ግዴታ ።**

የተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የማደስ ፡ ሥራ ፡ የሚያሻው ፡ ሲሆንና ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ለመጠበቅ ፡ የማይቻል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትለው ፡ መሰናክል ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆንና ፡ የማደሱ ፡ ሥራ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ከተከራየው ፡ ንብረት ፡ በከፊሉ ፡ አገልግሎቱን ፡ የሚያቋርጥበት ፡ ቢሆንም ፡ ተከራዩ ፡ ሥራው ፡ እስኪሠራ ፡ መታገሥ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፲፱ ። (፬) የአከራዩ ፡ ግዴታ ፡ ወሰን ።**

አከራዩ ፡ ላከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ማደሻ ፡ የሚያወጣው ፡ ገንዘብ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ከሚያገኘው ፡ ኪራይ ፡ የበለጠ ፡ ሒሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህን ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች ፡ እንዲፈጽም ፡ ሊገደድ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳ ። የአከራዩ ፡ ግዴታዎችን ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያስከትለው ።**

(፩) አከራዩ ፡ ሊፈጽማቸው ፡ የሚገባውንና ፡ ለተከራዩ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆኑት ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች ፡ ጊዜ ፡ ሳይፈጅ ፡ ሳይፈጽማቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከራዩ ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ለማሠራትና ፡ ያወጣውን ፡ ወጪ ፡ ከሕጋዊ ፡ ወለዱ ፡ ጋራ ፡ ከኪራዩ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ቀንሶ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

(፪) ከፈቀደም ፡ እንደ ፡ ጊዜውም ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ተከራዩ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅና ፡ አስፈላጊም ፡ ከሆነ ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝለት ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፩ ። ተከራዩ ፡ በተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚጠቀምበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ተከራዩ ፡ በተከራየው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚጠቀመው ፡ አስፈላጊውን ፡ የጥበቃ ፡ ጥንቃቄ ፡ በማድረግና ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ንብረቱ ፡ የተመደበበትን ፡ አገልግሎት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ውሉ ፡ ካለቀ ፡ በላይ ፡ ውጤቱን ፡ የሚቀጥል ፡ መለዋወጥ ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ሁኔታና ፡ ንብረቱ ፡ በተመደበበት ፡ የፍሬ ፡ አሰጣጥ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፪ ። የአከራዩ ፡ መቈጣጠር ።**

(፩) አከራዩ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ ተከራዩ ፡ አክብሮ ፡ የሚጠብቅ ፡ መሆኑን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ይችላል ።

BACK



(፪) ይህም ፡ የመቈጣጠር ፡ ጕዳይ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባው ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ እንዳችም ፡ ችግር ፡ በማያመጣና ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ በሚባል ፡ ሁኔታ ፡ ተከራዩንም ፡ በማያበሳጭ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፫ ። የኪራዩ ፡ አከፋፈል ።

(፩) ተከራዩ ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ በተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ የንብረቱን ፡ ኪራይ ፡ ወይም ፡ የርሻ ፡ አበል ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) የኪራይ ፡ መክፈያውና ፡ ዘመን ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ያልተመለከተ ፡ ሲሆን ፡ በሕግ ፡ በተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፬ ። የአከራዩ ፡ ይዞ ፡ የማቈየት ፡ መብት ። (፩) መሠረቱ ።

ያንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ አከራይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ላልተከፈለው ፡ ኪራይና ፡ ላለበትም ፡ ዓመት ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊከፈለው ፡ ለሚገባው ፡ ኪራይ ፡ ዋስትና ፡ ለቤቱ ፡ ማጌጫ ፡ ከሚያገለግሉት ፡ ዕቃዎችም ፡ ሆነ ፡ ለስፍራው ፡ ማልሚያ ፡ ከሚጠቅሙት ፡ መሣሪያዎች ፡ ውስጥ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፭ ። (፪) መብቱ ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ።

(፩) አከራዩ ፡ የዕቃዎቹ ፡ ባለሀብትነት ፡ የተከራዩ ፡ አለመሆኑን ፡ ዐውቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ይገባው ፡ ኑሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብቱ ፡ ሊፈጸም ፡ አይቻልም ።

(፪) አከራዩ ፤ ተከራዩ ፡ ወደ ፡ ተከራየው ፡ ስፍራ ፡ ያመጣቸው ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ሀብቶች ፡ የራሱ ፡ አለመሆናቸውን ፡ ያወቀው ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲፈርስ ፡ ካላመለከተ ፡ በቀር ፡ በእነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ይዞ ፡ የማቈየት ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፮ ።(፫) ውጤቱ ።

(፩) ይዞ ፡ የማቈየት ፡ መብት ፡ ባለው ፡ መሠረት ፤ በዳኞቹ ፡ ፈቃድ ፤ ተከራዩን ፡ በተከራየው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፤ ኪራዩን ፡ ወይም ፡ የርሻውን ፡ አበል ፡ ለመክፈል ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆኑት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች ፡ እንዲተው ፡ አከራዩ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) በስውር ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ የተወሰዱትን ፡ ዕቃዎች ፡ ከነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ ከተዛወሩ ፡ በኋላ ፡ አከራዩ ፡ በዐሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በፍርድ ፡ ያሲያዛቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአከራዩን ፡ መብቶች ፡ በቀደምትነት ፡ መክፈያ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፯ ። ውሉ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይ ፤ ለተወሰነ ፡ ወይም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ። ስለሆነም ።

BACK



(፪) ከሃምሳ ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ሊደረግ ፡ አይችልም ።

(፫) ከሃምሳ ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ለሚቈይ ፡ ዘመን ፡ የተደረገ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ለአምሳ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፰ ። ያከራይ፡ወይም ፡ የተከራይ ፡ መሞት ።

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፤ በአከራይ ፡ ወይም ፡ በተከራይ ፡ መሞት ፤ ወይም ፡ በአከራዩ ፡ ወይም ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ በሚደርሰው ፡ የችሎታ ፡ ማጣት ፡ ምክንያት ፡ አይፈርስም ።

(፪) ስለ ፡ መሬት ፡ ኪራይ ፡ የተጻፉት ፡ ልዩ ፡ ደንቦችና ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ተከራዩ ፡ መክሠር ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ የኪሣራን ፡ ደንብ ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፳፱ ። በኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መጥፋት ።

(፩) በኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባልታሰበ ፡ ምክንያት ፡ በሙሉ ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ያላ ፡ አንዳች ፡ ፎርማሊቴ) ፡ ይፈርሳል ።

(፪) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የጠፋው ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፤ ተከራዩ ፡ እንደ ፡ አካባቢዎቹ ፡ ምክንያቶች ፡ ዋጋው ፡ እንዲቀነስለት፡ወይም፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በነዚህ ፡ በሚጠይቃቸው ፡ ነገሮች ፡ በሁለቱም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ አንዳች ፡ ኪሣራ ፡ ሊጠይቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፴ ። አከራዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ስለ፡ አለመፈጸሙ ።

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ጠቃሚነት ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ በሚያጐድል ፡ አኳኋን ፡ አከራዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፤ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ ከውሉ ፡ መፍረስ ፡ ሌላ ፤ አከራዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ተከራዩ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፴፩ ። ተከራዩ ፡ ግዴታዎችን፡ስለ ፡ አለመፈጸሙ ።

(፩) የአከራዩን ፡ መብት ፡ አደጋ ፡ በሚደርስበት ፡ አኳኋን ፡ ተከራዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አከራዩ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፤ ወይም ፡ ከውሉ ፡ መፍረስ ፡ ሌላ ፡ ተከራዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ በሚያደርስበት ፡ ጉዳት ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆን ፡ የጉዳቱን ፡ ኪሣራ ፡ አከራዩ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፪ ። የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ በሚሆን ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ መቃወሚያ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) በአከራዩና ፡ በተከራዩ ፡ መካከል ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዐይነት ፡ የተነገረ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ተከራዩ ፡ ከተረከበው ፡ በኋላ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ አላባ ፡ ተቀባይ ፡ ለሚሆነው ፡ ሰው ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፪) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ተብሎ ፡ የሚለቀቅበት ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፫ ። (፪) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚጻፍበት ፡ መዝገብ ፡ ያልተጻፈ ፡ የኪራይ ፡ ውል ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ የርስት ፡ መዝገብ ፡ ያልተጻፈ ፡ ሲሆን ፤ ንብረቱን ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ውል ፡ አድርጎ ፡ ለመገመት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ የተረጋገጠ ፡ ቀን ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ ውሉን ፡ በርስት ፡ መዝገብ ፡ ካጻፈበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ተከራዩ ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለገዢው ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፬ ፡ ይህን ፡ ግምት ፡ ስለሚመለከተው ፡ የውል ፡ ቃል ። (፩) ውጤቱ ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ያገኘው ፡ ወይም ፡ የገዛው ፡ ሰው ፤ የኪራይ ፡ ውል ፡ እንዳይቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፤ በአከራዩና ፡ በተከራዩ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉን ፡ እንዳይቀጥል ፡ የሚፈልግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ንብረቱን ፡ ለገዛው ፡ ወይም ፡ ላገኘው ፡ ሰው ፡ ጥያቄ ፡ ካቀረበለት ፡ በኋላ ፤ የገዛው ፡ ወይም ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ የመሥራት ፡ ፈቃድ ፡ እንዳለው ፡ ወይም ፡ እንደሌለው ፡ ለተባለው ፡ ተከራይ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በዚህ ፡ በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በተሰጠው ፡ መብት ፡ ያልሠራበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱን ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፭ ። (፪) መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ ውለታ ፡ አድርጎ ፡ ስለሚደረገው ፡ ሽያጭ ።**

የሸጠውን ፡ ንብረት ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ ውል ፡ አድርጎ ፡ ንብረቱን ፡ የሸጠ ፡ ሰው ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አልቆ ፡ ፍጹም ፡ ባለሀብት ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፤ ባለይዞታውን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ባለው ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

BACK



ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፮ ። ንብረቱን ፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) የኪራዩ ፡ የውል ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፤ ተከራዩ ፡ በኪራይ ፡ የያዘውን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለአከራዩ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) እንደዚሁም ፡ ከማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ጋራ ፡ የተቀበላቸውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዐይነታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ የሚገኙትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የተፈጥሮ ፡ ዐይነታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ለአከራዩ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፯ ። (፪) ለኪራይ ፡ ከተሰጠው ፡ ንብረት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ከዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ ጋራ ፡ ትክክለኛ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በአከራይና ፡ በተከራይ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ እንዳለ ፤ ተከራዩ ፤ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ሁኔታና ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ በተነገረው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ የተቀበለውን ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፰ ። (፫) ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ አለመኖር ።

(፩) ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ሁኔታ ፡ በአከራይና ፡ በተከራይ ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ የመተማመኛ ፡ ጽሑፍ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከራዩ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተቀበለው ፡ ይገመታል ።

(፪) ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ የመተማመኛ ፡ ጽሑፍ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፤ ተጨማሪ ፡ ነገሮች ፡ እንዳልነበሩበት ፡ ሁኖ ፡ ይገመታል ።

(፫) በነዚህ ፡ ግምቶች ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፱ ። (፬) የዳኞች ፡ አመዛዘን ።

ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር ፤ የተሰናዳው ፡ ጽሑፍ ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ አካባቢዎቹን ፡ ምክንያቶች ፡ በመመልከት ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ ለሚሆነው ፡ ስምምነት ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ የሚታያቸውን ፡ ግምት ፡ ይሰጡታል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺ ። የተከራየው ፡ ነገር ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ።

(፩) ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ነገር ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፤ ነገሩ ፡ የጠፋ ፡ ወይም ፡ የተበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) በተለየም ፤ የተባለውን ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ ያደረሰው ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ወይም ፡ ወደማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ባስገባው ፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፩ ። የኀላፊነቱ ፡ ወሰን ።**

(፩) ተከራዩ ፤ የተከራየው ፡ ነገር ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ በአከራዩ ፡ ወይም ፡ በድንገተኛ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊነቱ ፡ ይቀርለታል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የጠፋው ፡ ወይም ፡ የተባላሸው ፡ ነገር ፡ ከማርጀቱ ፡ ወይም ፡ ከማናቸውም ፡ በነገሩ ፡ ከተገኘው ፡ ጕድለት ፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊነት ፡ ይቀርለታል ።

(፫) የነገሩ ፡ መበላሸት ፡ ነገሩን ፡ በደንበኛ ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ በማዋልና ፡ በተፈቀደው ፡ አደራረግ ፡ ሲሆን ፤ ተከራዩ ፡ ኀላፊነት ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፪ ። ማስጠንቀቂያ ፡ የተሰጠው ፡ ተከራይ ።**

የተቀበለውን ፡ ነገር ፡ እንዲመልስ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የተሰጠው ፡ ተከራይ ፤ የተባለው ፡ ነገር ፡ የጠፋው ፡ ወይም ፡ የተበላሸው ፡ ይህንኑ ፡ ነገር ፡ በአስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ ለአከራዩ ፡ መልሶለት ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ ከመጥፋቱ ፡ ወይም ፡ ከመበላሸቱ ፡ ሁኔታ ፡ የማይድን ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀላፊነቱ ፡ ይቀርለታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፫ ። የጕዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ መጠን ።**

(፩) ለመመለስ ፡ ያልቀረቡት ፡ ነገሮች ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ቀድሞውኑ ፡ ተገምተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከራዩ ፡ ለነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የተሰጠውን ፡ ግምት ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳል ።

(፪) አከራዩ ፤ ተከራዩ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ከተሰጣቸው ፡ ግምት ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ መሸጥ ፡ መለወጡን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጨማሪዎች ፡ የሆኑትን ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራዎች ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፤ በተከራዩ ፡ በኩል ፡ የተደረገው ፡ የነገሩ ፡ መሸጥ ፡ መለወጥ ፤ አከራዩና ፡ ተከራዩ ፤ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ በተስማሙበት ፡ አሳብ ፤ መሠረት ፡ ለሥራው ፡ ደንበኛ ፡ የአስተዳደር ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተነገረው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፬ ። በተከራዩ ፡ ጥፋት ፡ ስለሚደርስ ፡ የውል ፡ መፍረስ ።**

በተከራዩ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ውሉ ፡ የፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተደረገው፡ ጥፋት፡ ሊያስከትለው ፡ የሚችል ፡ ኪሣራን ፡ መክፈሉ ፡ ሳይቀርለት ፡ በኪራዩ፡ ውል ፡ ላይ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ ቀን ፡ እስኪደርስ ፡ ንብረቱን ፡ እንደ፡ገና ፡ ለማከራየት ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የቤቱን ፡ ኪራይ ፡ ወይም ፡ የርሻ ፡ አበል፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፪ ።
## የቤትን ፡ ኪራይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፵፭ ። የዚህ ፡ ክፍል ፡ ተፈጻሚነት ።**

(፩) የአከራይና ፡ የተከራይ ፡ ውል ፤ ቤትን ፡ ከነዕቃው ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ባለክፍሎች ፡ ቤት ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ አንድ ፡ ሌላ፡ ሕንጻ፡ ወይም ፡ የሕንጻ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ለመከራየት ፡ ሲሆን ፤ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ የተነገሩት ፡ ስለ ፡ ሆቴል ፡ ውል ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፵፮ ። ለዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ውሎች ።**

(፩) በታወቀ ፡ ቀበሌ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ክፍለ ፡ ቤቶች ፡ ኪራይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲሆኑ ፤ ለዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ውሎችን ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሊያደራጁ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እነዚህን ፡ ቤቶችና ፡ ክፍለ ፡ ቤቶች ፡ የሚመለከቱ ፡ በያንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገሩት ፡ ለዐይነት፡ በተደራጁት ፡ ውሎች ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ ሆነው ፡ ይገመታሉ ።

(፫) ተዋዋዮቹ ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ግልጽ ፡ ስምምነቶች ፡ ለዐይነት ፡ ከተደራጁት፡ ውሎች ፡ የተለዩ ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፵፯ ። በከፊል ፡ ስለሚደረግ ፡ የሕንጻ ፡ ኪራይ ። (፩) የአከራዩ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ለአንድ ፡ ተከራይ ፡ በኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ ሕንጻ ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ አከራዩ ፡ የዚህን ፡ ሕንጻ ፡ ሌሎች ፡ ክፍሎች ፡ በሚያከራይበት ፡ ጊዜ ፡ ልማድን፡ በመከተልና ፡ የቦታዎቹን ፡ ተፈጥሮ ፡ በመመልከት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ተከራይ ፡ ጥቅም ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) ሌሎቹን ፡ ተከራዮች ፡ ሲመርጥ ፡ እንዲሁም ፡ ከነዚህ ፡ ተከራዮች ፡ ጋራ ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ ለሚያገባቸው ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ አከራዩ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባለው ፡ ግዴታ ፡ ይኖርበታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፵፰ ። (፪) የተከራይ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ተከራዩ ፤ በከፊል ፡ ከተከራየው ፡ ቤት ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ ለሚኖሩት ፡ ሌሎች፡ ሰዎች ፡ የሚገባው ፡ አክብሮት ፡ እንዲኖረው ፡ ይገደዳል ።

(፪) ተከራዩ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፤ ወይም ፡ በተከራየው ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ እርሱ ፡ የሚያስገባቸው ፡ ሰዎች ፡ በሁኔታቸው ፡ (በአካሄዳቸው ፡ ወይም ፡ በኑሮዋቸው ፡ ዐይነት ፡ ሕንጻውን ፡ የተከራዩትን ፡ የሌሎች ፡

ሰዎች ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ ያወኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫ በአዋኪዎቹ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ደረሰባቸው ፡ ጉዳት ፡ እነዚህ ፡ ሌሎች ፡ ተከራዮች ፡ የጉዳትን ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፵፱ ። ተከራዩ ፡ በተከራየው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ዕቃ ፡ ለማስገባት ፡ ስለ ፡ አለበት ፡ ግዴታ ።

(፩) ተከራዩ ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ አገልግሎትና ፡ እንደ ፡ ቦታው ፡ ልማድ ፡ በተከራየው ፡ (በማይንቀሳቀስ) ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ዕቃ ፡ ማግባት ፡ አለበት ።

(፪) ተከራዩ ፤ ዕቃዎች ፡ ያሏቸውን ፡ ቤቶች ፡ ተከራይቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ኪራዩን ፡ አስቀድሞ ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለኪራዩ ፡ ዋስ ፡ ጠርቶ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ግዴታ ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ አይፈጸምበትም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፶ ። የኪራዩ ፡ ልክ ።

(፩) የኪራዩ ፡ ልክ ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነት ፡ ይወሰናል ።

(፪) በሚያጠራጥር ፡ ጊዜ ፤ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በወሰኑት ፡ ታሪፍ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ታሪፍ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቦታዎቹን ፡ ልማድ ፡ በመከተል ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፶፩ ። ኪራዩ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ።

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ለአንድ ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ ኪራዩ ፡ በየሦስት ፡ ወር ፡ መጨረሻ ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።

(፪) ውሉ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በየወሩ ፡ መጨረሻ ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ኪራዩ ፡ የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ (ሲያቆም) ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፶፪ ። የተከራዩ ፡ ሳይከፍል ፡ መቈየት ።

(፩) የኪራዩ ፡ መከፈያ ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ተከራዩ ፡ በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ከመክፈል ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ የሠላሳ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ ውሉ ፡ ለአነስተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ የሚፈርስ ፡ መሆኑን ፡ ለተከራዩ ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይችላል ።

(፪) የጊዜው ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ተከራዩ ፡ የአከራዩን ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተቀበለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) እነዚህን ፡ ጊዜዎች ፡ የሚያሳጥሩ ፡ ወይም ፡ ኪራዩ ፡ ባለመከፈሉ ፡ ምክንያት፡ ወዲያው ፡ ውሉን ፡ የማፍረስ ፡ መብት ፡ ለአከራዩ ፡ የሚሰጡ፡የውል፡ቃሎች፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ፤ (ዋጋ ፡ የላቸውም) ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፫ ። ቤቶቹን ፡ ስለ ፡ ማደስ ። (፩) የተከራዩ ፡ ግዴታዎች ።**

ተከራዩ ፡ ሊያድሳቸው ፡ የሚገባውን ፡ የተከራያቸውን ፡ ቤቶች ፡ በራሱ፡ ኪሣራ፡ ለማደስ ፡ ይገደዳል ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፬ ። (፪) የማደስ ፡ ትርጉም ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ቤቶችን ፡ ማደስ ፡ ይገባዋል ፡ የተባሉት ፡ (የሚባለው) ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ ተከራዩ ፡ ይፈጽማቸዋል ፡ ተብሎ ፡ የተወሰኑት ፡ ናቸው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ቤቶችን ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች፡ ተብለው ፡ የሚቈጠሩት ፡ መዝጊያዎችን ፡ ወይም ፡ መስኮቶችን ፡ የቤት ፡ ወለ ሎችን ፡ ወይም ፡ ንጣፎቹን ፡ የውሃ ፡ መቅጃ ፡ መዘውሮችንና ፡ የውሃ ፡ መስደ ጃዎችን ፡ ለማደስ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑት ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ።

(፫) እንደዚሁም ፡ በተከራየው ፡ ቤት ፡ ለመጠቀም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ቤቶ ችን፡ የማጥዳትና ፡ በደንብ ፡ የመያዝ ፡ ሥራዎች ፡ ቤትን ፡ እንደ ፡ ማደስ ፡ ያሉ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፭ ። (፫) በማርጀት ፡ ወይም ፡ ካቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ መበላሸት ።**

(፩) ቤቶቹ ፡ በማርጀት ፡ ወይም ፡ ካቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ የተበላሹ፡ ሲሆኑ ፡ ተከራዩ ፡ ማናቸውንም ፡ ቤቶችን ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች ፡ መፈጸም ፡ የለበትም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በኪራይ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በገባ ፡ የውል ፡ ቃል፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ ደንብ ፡ ሊለውጥ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፮ ። በማደስ ፡ ምክንያት ፡ በቤቱ ፡ ሳይገለገሉ ፡ ስለ ፡ መቈየት ።**

(፩) በኪራዩ ፡ ውል ፡ ጊዜ ፤ አከራዩ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ባልሆነው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ቤትን ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ የበ ለጠ ፡ ጊዜ ፡ የቈዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ለዚህ ፡ ለተወሰነው ፡ ቀንና ፡ ሳይገ ለገልበት ፡ ለቈየው ፡ ክፍል ፡ የኪራዩን ፡ ዋጋ ፡ ይቀንሳል ።

(፪) የማደሱ ፡ ሥራዎች ፡ ዐይነት ፡ ለተከራዩና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ውን ፡ መኖሪያ ፡ ሊቀመጡበት ፡ የማይቻል ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከራዩ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፶፯ ። የተከራዩትን ፡ ስለ፡ ማከራየት ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) ተከራዩ ፡ እርሱ ፡ የተከራየውን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለማከራየት ፡ ይችላል ።

(፪) የተከራየውን ፡ ለማከራየት ፡ ከመፍቀዱ ፡ በፊት ፡ ተከራዩ ፡ አሳቡን ፡ ለአከራዩ ፡ ማስታወቅና ፡ አከራዩ ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለውን ፡ ተቃዋሚነት ፡ ማወቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፶፰ ። (፪) የአከራይ ፡ ተቃዋሚነት ።**

(፩) በተከራዩ ፡ በኩል ፡ የሚደረገው ፡ ማከራየት ፡ አከራዩ ፡ ይህንኑ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለሌሎች ፡ ተከራዮች ፡ ሲያከራይ ፡ ለገባው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ተቃራኒ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ወይም ፡ የተባለው ፡ ማከራየት ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ እርግጠኛ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያመጣበት ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ይህን ፡ ተከራዩ ፡ የሚያደርገውን ፡ ማከራየት ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) ተከራዩ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፫) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ስምምነት ፡ በተፈረመ ፡ ጊዜ ፡ ተቃዋሚነትን ፡ ያስከተለውን ፡ ነገር፡ ተከራዩ ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱ ፡ ለአከራዩ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፶፱ ። (፫) የተከራዩን ፡ አከራይነት ፡ የሚያጠብ ፡ የውል ፡ ቃል ።**

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ቤት ፡ እንዳያከራይ ፤ ወይም ፡ ተከራዩ ፡ ከማከራየቱ ፡ በፊት ፡ የአከራዩን ፡ ፈቃድ ፡ መቀበል ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲል ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ቤት ፡ ከማከራየቱ ፡ በፊት ፡ ሌላውን ፡ ተከራይ ፡ ሲያከራይ ፡ አከራይ ፡ ወዶ ፡ እንዲቀበለው ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚል ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አከራዩ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ፈቃዱን ፡ የከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፷ ። (፬) የተከራይ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) የተከራየውን ፡ ቤት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ያከራየ ፡ ሰው ፡ በኪራይ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ ለአከራዩ ፡ ለገባቸው ፡ ግዴታዎች ፡ ተገዳጅ ፡ ይሆናል ።

(፪) አከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ አከራይነት ፡ ፈቅዶም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንኳ ፡ ተከራዩ ፡ ያሉበት ፡ ግዴታዎች ፡ አይቀሩለትም ።

(፫) ተከራዩ ፡ ካሉበት ፡ ግዴታዎች ፡ ነጻ ፡ የሚሆነው ፡ በርሱና ፡ በአከራዩ ፡ መካከል ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

BACK



ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፩ ። (፳) ከተከራይ ፡ የተከራየ ፡ ሰው ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ከተከራይ ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ በኪራይ ፡ የተሰጡትን ፡ ቦታዎች ፡ ጥቅም ፡ በሚመለከት ፡ ሁሉ ፡ የዋናውን ፡ የኪራይ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ በሙሉ ፡ ማክበር ፡ አለበት ።

(፪) እነዚህን ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ እንዲያከብር ፡ ከተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ሰው ፡ አከራዩ ፡ በቀጥታ ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

(፫) ከተከራይ ፡ ላይ ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ እነዚህን ፡ ውሎች ፡ ሳያውቅ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንዳይጠብቃቸው ፡ ተከራይ ፡ ፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ከተከራይ ፡ ላይ ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ በአከራየው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፪ ። (፮) አከራዩ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ቀጥታ ፡ ክስ ።

(፩) ከተከራይ ፡ ላይ ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ከተስማማበት ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ላለው ፡ ተጠያቂ ፡ አይሆንም ።

(፪) ዋናው ፡ አከራይ ፡ ከተከራይ ፡ ላይ ፡ የተከራየውን ፡ ሰው ፡ የተከራየበትን ፡ ዋጋ ፡ በቀጥታ ፡ በእጁ ፡ ለርሱ ፡ እንዲከፍለው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) ከተከራይ ፡ ላይ ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ ለዋናው ፡ ኪራይ ፡ ላለበት ፡ ጊዜ ፡ ከሚከፍለው ፡ ዋጋ ፡ በቀር ፡ አስቀድሞ ፡ ለአከራየኝ ፡ ከፍያለሁ ፡ በማለት ፡ ዋናውን ፡ አከራይ ፡ ለመቃወም ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፫ ። (፯) ይዞ ፡ የማቈየት ፡ መብት ።

ከተከራይ ፡ ላይ ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ተከራየው ፡ ቦታ ፡ ባመጣቸው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ አከራይና ፡ ተከራይ ፡ ይዞ ፡ በማቈየት ፡ መብታቸው ፡ ለመሥራት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፬ ። (፰) የኪራይ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ መፍረስ ።

(፩) ዋናው ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ ሲሆን ፡ ተከራይ ፡ ያደረገው ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ አከራዩ ፡ በግልጽ ፡ ተከራዩ ፡ እንዲያከራይ ፡ ፈቅዶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋናውን ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ለመፈጸም ፡ ሁለተኛ ፡ ተከራይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በዋናው ፡ ተከራይ ፡ ፋንታ ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፭ ። ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማለቅ ።

ስለ ፡ ኪራይ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ልዩ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ሳሆን ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ፎርማሊቲ ፡ ውሉ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፬፻፳፮ ። ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማለቅ ።

(፩) የኪራይ ፡ ውል ፡ የተደረገው ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ ተከራዩን ፡ ለማስታወቅ ፡ ወይም ፡ ተከራዩ ፡ አከራዩን ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ አለቀ ፡ የሚባለው ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ተከታዩ ፡ የኪራይ ፡ ዘመን ፡ ዋጋ ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማለቅ ፡ ማስታወቁን ፡ ባይሰጥ ፡ ኑሮ ፡ ኪራዩ ፡ ሊከፈልበት ፡ ይገባው ፡ በነበረበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፷፯ ። ቤቱን ፡ የሚያገኝ ፡ ወይም፡የሚገዛ ፡ ሰው ።

(፩) ቤቱን ፡ የሚገዛ ፡ ወይም ፡ የሚያገኝ ፡ ሰው ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለማቋረጥ ፡ እንዲችል ፡ መብት ፡ ተሰጥቶት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲቋረጥ ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) ለዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፷፰ ። ስለ ፡ ኪራይ ፡ ውል፡መራዘም ።

(፩) የኪራይ ፡ ውል ፡ ሲያልቅ ፡ ተከራዩ ፡ የተከራየውን ፡ ነገር ፡ አከራዩ ፡ ዐውቆና ፡ ፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ የተቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ታደሰ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ስለ ፡ ሌላው ፡ ነገር ፡ የሁለት ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ አስቀድሞ ፡ በተነገረው ፡ ውል ፡ በተነገሩት ፡ ውለታዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ ስለ ፡ መጀመሪያ ፡ ውል ፡ የተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፷፱ ። አከራዩ ፡ ቤቱን ፡ መልሶ፡ስለ ፡ መውሰድ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አከራዩ ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ እቀመጥበታለሁ ፡ ቢል ፡ እንኳ ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለማፍረስ ፡ አይችልም ።

(፪) በኪራዩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ አከራዩ ፡ ቤቱን ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ሊቀመጥበት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ የሚናገር ፡ ስምምነት ፡ እንዳለ ፡ የተባለው ፡ አከራይ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉትን ፡ የኪራይ ፡ ውሎች ፡ ለማቋረጥ ፡ የተወሰኑትን ፡ ጊዜዎች ፡ መጠበቅና ፡ ለተከራዩም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ለመስጠት ፡ አከራይ ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸ ። ስለ ፡ ቤቱ ፡ መቃጠል ፡ (፩) መሠረቱ ።

ተከራዩ ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ቃጠሎ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ በቤቱ ፡ ሥራ ፡ ጕድሎነት ፡ ወይም ፡ ቃጠሎው ፡ ከጎረቤቱ ፡ ቤት ፡ መያያዝ ፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ተከራዩ ፡ ለአከራዩ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፩ ። (፪) ስለ ፡ ብዙ፡ተከራዮች ።

(፩) ተከራዮቹ ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተከራይነት ፡ በያዙዋቸው ፡ ቤቶች ፡ ክፍል ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ ሁሉም ፡ ለቃጠሎው ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃሉ ።

(፪) ቃጠሎው ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንደኛ ፡ ተከራይ ፡ ባለበት ፡ ቤት ፡ የጀመረ ፡ ለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ ተከራይ ፡ ብቻ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፫) ከተከራዮቹ ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ ቃጠሎው ፡ እነርሱ ፡ ባሉበት ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ መጀመሩን ፡ ያስረዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህ ፡ ተከራዮች ፡ ኀላፊዎች ፡ አይሆኑም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፪ ። አከራዩ ፡ በከፊል ፡ ስለሚኖርበት፡ቤት ።**

(፩) አከራዩ ፡ የሚኖርበት ፡ ከተቃጠለው ፡ ቤት ፡ በአንዱ ፡ ክፍል ፡ በሆነም ፡ ጊዜ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ አከራዩ ፡ የሚቀመጥበትን ፡ ክፍል ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ቤቱን ፡ እንደ ፡ ተከራየው ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፫ ። በቤቱ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ማሻሻል ።**

**(፩) የወጪ ፡ መካፈል ፡ መብት ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ያላከራዩ ፡ ፈቃድ ፡ በተከራየው ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ስላደረገው ፡ ማሻሻያ ፡ አንዳች ፡ ወጪ ፡ እንዲከፍለው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ማሻሻያውን ፡ ያደረገው ፡ በአከራዩ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ያደረጋ ጋቸውን ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲከፈለው ፡ አከራዩን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፬ ። ማቻቻልና፡አንሥቶ፡የመውሰድ፡መብት ።**

(፩) ምንም ፡ እንኳ ፡ ተከራዩ ፡ አንዳች ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ባይኖራቸው ፡ የቤቱን ፡ ባለዋጋነት ፡ ከፍ ፡ ያደረጉትን ፡ ሥራዎችና ፡ በርሱ ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ ኀላፊ ፡ ለሆነባቸው ፡ የቤቱን ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ያደረጉትን ፡ መበላሸቶች ፡ ለማቻቻል ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ አሠራሩ ፡ ቤቱን ፡ ሳይጎዳ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተከራዩ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ማሻሻያዎች ፡ አንሥቶ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መሬት ፡ የተሰጡት ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፭ ። የዚህ ፡ ክፍል፡ተፈጻሚነት ።**

(፩) የኪራይ ፡ ውል ፡ የሚመለከተው ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ አንድ ፡ መሬትን ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ተከራዩም ፡ መሬቱን ፡ የሚያለማው ፡ ሲሆን ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፮ ። ለዐይነት ፡ የሚሆኑ ፡ ውሎች ።

(፩) ለዐይነት ፡ የሚሆኑትን ፡ ውሎች ፤ ለአንዳንድ ፡ የግብርና ፡ አገልግሎት ፡ የሚውሉ ፡ መሬቶች ፡ ወይም ፡ በአንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አውራጃዎች ፡ የሚገኙትን ፡ መሬቶች ፡ የሚመለከቱትን ፡ ለዐይነት ፡ የሚሆኑትን ፡ ውሎች ፡ የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሊደነግጋቸው ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚህን ፡ መሬቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ በያንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉት ፡ ውሎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገሩት ፡ ዐይነት ፡ በተደራጁት ፡ ውሎች፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ ሆነው ፡ ይገመታሉ ።

(፫) ተዋዋዮቹ ፡ በሚያደርጉዋቸው ፡ ግልጽ ፡ ስምምነቶች ፡ ለዐይነት ፡ ከተደራጁት ፡ ውሎች ፡ የተለዩ ፡ ስምምነቶች ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፯ ። መሬት ፡ ስለሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ የሚደረግ ፡ አመራር ። (፩) መብቱ ።

(፩) የመሬቱ ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ የሚመራው ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የመሬቱ ፡ ኪራይ ፡ የሚከፈለው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ አብዛኛው ፡ ከመሬቱ ፡ ሰብሎች ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ መጠን ፡ ልክ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ መሬቱ፡ ከሚያፈራቸው ፡ በአንዳንድ ፡ ሰብሎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የመሬቱ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የአከራዩ ፡ ነው ።

(፫) የመሬቱ ፡ ኪራይ ፡ የሚከፈለው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ አብዛኛው ፡ ለአከራዩ ፡ በእጁ ፡ በገንዘብ ፡ የሚከፈለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የመሬቱ ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የገበሬው ፡ ነው።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፰ ። (፪) የአንደኛው ፡ ወገን ፡ (ተዋዋይ)፡ መብት ።

(፩) የታሰቡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ውጤቶቻቸው ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የሚቀጥል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሥራው ፡ መሪ ፡ ለአንደኛው ፡ ወገን ፡ ማማከር ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ የተባለው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔውን ፡ ሳያስታውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነና፡ መጠበቁም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚያስከትል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ (የሥራ ፡ መሪው)፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ውሳኔውን ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፸፱ ። መሬቱን ፡ የማልማት ፡ ግዴታ ።

(፩) ገበሬው ፡ (ተጋገዡ) ፡ መሬቱ ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጥ ፡ ለማድረግና ፡ በፍሬያማነት ፡ መልካም ፡ ሁኔታ ፡ እንዲገኝ ፡ አድርጎ ፡ ለመያዝ ፡ ይገደዳል ።

BACK



(፪) ተከራዩ ፡ ይህን ፡ ግዴታ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራይ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺ ። የተክሉ ፡ ዐይነትና ፡ አደራረግ ።

በውሉ ፡ መሠረት ፡ የመሬቱ ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ መሪነት ፡ የተሰጠው ፡ ወገን ፡ የሚደረገውን ፡ የግብርና ፡ ዐይነት ፡ አሠራር ፡ ይወስናል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፩ ። የሥራዎች ፡ ወቅት ።

(፩) በማናቸውም ፡ ሁኔታዎች ፡ የግብርናውን ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ተግባሮች ፡ የሚፈጸሙበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ገበሬው ፡ (ተከራዩ) ፡ ነው ።
(፪) በዚህ ፡ ጕዳይ ፡ አከራዩ ፡ ገበሬውን ፡ ከማስጠንቀቅ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ አይችልም ።

ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፪ ። መሬቱን ፡ ለማልማት ፡ ስለሚደረገው ፡ ወጪ ።

(፩) መሬቱን ፡ ለማልማት ፡ የሚደረገው ፡ ተራ ፡ የሆነ ፡ ወጪ ፡ በገበሬው ፡ ላይ ፡ የሚታሰብ ፡ ነው ።
(፪) ስለ ፡ መሬቱ ፡ የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ መሬቱ ፡ ከሚያፈራቸው ፡ ነገሮች ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ መሬቱ ፡ የሚያፈራቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ሰብሎች ፡ በመስጠት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገበሬው ፡ (ተጋዡ) ፡ ለዘር ፡ የሚሆን ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ለማድረግ ፡ በማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ሲገኝ ፡ አከራዩ ፡ ይህን ፡ ለዘር ፡ የሚሆነውን ፡ ወጪ ፡ ያለ ፡ ወለድ ፡ አስቀድሞ ፡ በብድር ፡ መስጠት ፡ አለበት ።
(፫) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ በብድር ፡ የተሰጠው ፡ ሒሳብ ፡ በመጪው ፡ ጊዜ ፡ ከሚገኘው ፡ ሰብል ፡ ላይ ፡ ለአከራዩ ፡ ይከፈላል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፫ ። ስለ ፡ ማደስና ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ አያያዝ ።

(፩) ተከራዩ ፡ በኪራይ ፡ ተሰጥተውት ፡ የሚገለገልባቸውን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የእህልና ፡ የገለባ ፡ ቤቶች ፡ በረቶች ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ቦታዎች ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ አስቀድሞ ፡ በተጻፈው ፡ ክፍል ፡ የተነገሩትን ፡ የቤት ፡ ማደስ ፡ ሥራዎች ፡ ለመፈጸም ፡ ይገደዳል ።
(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ በቦታዎቹ ፡ (በአገሬዎቹ) ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ በኪራይ ፡ የተሰጠ ፡ መሬት ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ መንገዶች ፡ የውሃ ፡ ጕድጓዶች ፡ አጥሮች ፡ የውሃ ፡ መንገዶች ፡ የውሃ ፡ ቦዮችና ፡ ግድቦች ፡ በቦታዎቹ ፡ ልማድ ፡ (በአገሬዎቹ) ፡ መሠረት ፡ በደንብ ፡ ለመያዝ ፡ (ለመጠገን) ፡ ይገደዳል ።

ቊ ፡ ፪ሺ፱፻፺፬ ። ማርጀት ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ የማደሱ ፡ ሥራ ፡ በማርጀት ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ በገበሬው ፡ (በጢሰኛው) ፡ ኪሣራ ፡ ይሆናል ።

(፪) እንደዚሁ ፡ ገበሬው ፡ ( ጢሰኛው ) ፡ በማርጀት ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ የጠፉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ መሣሪያዎች ፡ መተካት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፫ ። ልዩ ፡ የሆነ ፡ ወጪ ።

ገበሬው ፡ (ጢሰኛው) ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ በደረሰ ፡ አደጋ ፡ መሬቱን ፡ ለማደስ ፡ (ለማ ቋቋም) ፡ የሚደረገውን ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያወጣ ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፬ ። የመሬት ፡ ቍራጭ ፡ (ክፍል) ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የመሬቱን ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፡ መሪነት ፡ የያዘው ፡ ወገን ፡ የሥራውን ፡ ክንውን ፡ ለማካሄድ ፡ ቀና ፡ እንዲሆን ፡ ከሌሎች ፡ ባለሀብቶች ፡ ( ባለርስቶች ) ፡ ወይም ፡ ገበሬዎች ፡ (ጢሰኞች ) ፡ ጋራ ፡ የመሬት ፡ ክፍልን ፡ (ቍራጭን) ፡ ልውጫ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ ልውጫ ፡ የገበሬው ፡ ተግባር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከነዚህ ፡ የመሬት ፡ ክፍል ፡ ቍራጭ ፡ አገልግሎት ፡ በቀር ፡ የርስትነትን ፡ መብት ፡ ሊነካ ፡ አይችሉም ።

(፫) ልውጫውን ፡ አከራዩ ፡ ካልወሰነው ፡ ወይም ፡ አከራዩ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፤ ውሉ ፡ ሲያልቅ ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ አሠራር ፡ ውጤት ፡ መስጠታቸው ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፭ ። መሬቱን ፡ ስለ ፡ ማደራጀት ።

ገበሬው ፡ (ጢሰኛው) ፡ በኪራይ ፡ የተሰጠውን ፡ መሬት ፡ አእምሮ፡ በሚቀበለው፡ ዐይነት ፡ ለሚደረገው ፡ ክንውን ፡ እንቅፋት ፡ የሚሆኑትን ፡ ዳገቶች ፡ (አረሆች ) ፡ ጕብታዎች ፡ በዮች ፡ ወይም ፡ አጥሮችን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፮ ። የሚከፈለው ፡ የኪራይ ፡ ዐይነት ።

(፩) የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ከግብርና ፡ በሚገኘው ፡ ሰብል ፡ ወይም ፡ በተወሰኑ ፡ ሰብሎች ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ ሽመታ ፡ ዋጋ ፡ በሚወሰን ፡ ገንዘብ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ በኪራይ ፡ ከተሰጠው ፡ መሬት ፡ ከሚገ ኘው ፡ ከተወሰነ ፡ ሰብል ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍሬዎች ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፯ ። የሚከፈለው ፡ የኪራይ ፡ ልክ ።

የሚከፈለው ፡ የኪራይ ፡ ልክ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፹፰ ። ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የሕሊና ፡ ግምት ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ በኪራይ ፡ ከተሰጠው ፡ መሬት ፡ ከሚገኘው ፡ ሰብል ፡ ግማሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ሰብል ፡ ባከራዩና ፡ በገበሬው፡ (በጢሰኛው) ፡ መካከል ፡ በዐይነት ፡ የሚከፋፈል ፡ ይሆናል ።

(፫) ገበሬው ፡ (ጢሰኛው) ፡ ማናቸውም ፡ ክፍያ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት፡ለሚመጣው ፡ ሰብል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ዘር ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

ቍ፡ ፪ሺ፱፻፺፩ ። ሕጋዊ ፡ ከፍተኛ ፡ ድርሻ ።

(፩) ለአከራዩ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰብል ፡ መጠን ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ከሦስት ፡ ሩብ ፡ ለመብለጥ ፡ አይችልም ።

(፪) በውል ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ድርሻ ፡ የተመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ሆኖና ፡ ሰብሉ ፡ ባከራዩና ፡ በገበሬው ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ የሚከፋፈል ፡ ይሆናል ።

ቍ፡ ፪ሺ፱፻፺፪ ። ለቀለብ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ሰብል ፡ (፩) መሠረቱ ።

(፩) ገበሬው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ለቀለቡና ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ለሚኖሩት ፡ ቀለብ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የሰብል ፡ ድርሻ ፡ ማስቀረት ፡ (መያዝ) ፡ ይችላል ።

(፪) ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ሰብሉ ፡ ለአከራዩ ፡ ቀለብና ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ለሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ቀለብ ፡ እንዲሁ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አይፈጸምም ።

(፫) እንደዚህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሰብሉን ፡ አከራዩና ፡ ገበሬው ፡ እኩል ፡ ይካፈሏሉ ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፫ ። የአከራዩ ፡ የተጠበቁ ፡ መብቶች ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ አከራዩ ፡ የሚገባውን ፡ ሙሉ ፡ የሰብል ፡ ድርሻውን ፡ ሳያገኝ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተከታዩ ፡ ዓመት ፡ ሰብል ፡ ላይ ፡ ድርሻውን ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፬ ። ሰብል ።

(፩) የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ ከዚሁ ፡ ሰብል ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ይኸንኑ ፡ ሰብል ፡ በመመልከት ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገበሬው ፡ ሰብሉን ፡ ከመሰብሰቡ ፡ በፊት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለአከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በውሉ ፡ መሠረት ፡ ለአከራዩ ፡ የሚደርሰው ፡ የሰብል ፡ ድርሻ ፡ እስከሚሰጠው፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ገበሬው ፡ ይህን ፡ ሰብል ፡ መጠበቅና ፡ ማስቀመጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፭ ። ኪራይ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) የሚከፈለው ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ ከግብርናው ፡ በሚገኘው ፡ በተወሰነ ፡ ሰብል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪራዩ ፡ በያንዳንዱ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።

BACK



(፪) የኪራዩ ፡ ውል ፡ አከራዩ ፡ የማይንቀሳቀሰውን፡ንብረት ፡ ለገበሬው ፡ ካስረከበ በት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፪ ። የገበሬው ፡ ሳይከፍል ፡ መዘግየት ።

(፩) ገበሬው ፡ ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ኪራይ ፡ ሳይከፍል ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከ ራዩ ፡ የስሳ ፡ ቀን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ሳይከፍል ፡ ቢቀር ፡ ውሉ ፡ የሚፈርስ ፡ መሆኑን ፡ (ያስታውቀዋል) ፡ ሊያስገነዝበው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ጊዜ ፡ የሚጀመረው ፡ ገበሬው ፡ የአከራዩ ፡ ማስታ ወቂያ ፡ ከደረሰው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) ይህን ፡ የማስታወቂያ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀንሱ ፡ ወይም ፡ የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ ባለመከፈሉ ፡ ምክንያት ፡ ወዲያውኑ ፡ ለአከራዩ ፡ የማፍረስ ፡ መብትን ፡ የሚሰጡ ፡ ማንኛዎቹም ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ወይም ፡ ልማዶች ፡ ሁሉ ፡ ፈራ ሾች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፫ ። ስለ ፡ መሬቱ ፡ አበል ፡ ሁኔታ ።

(፩) የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ በኪራይ ፡ ከተሰጠው ፡ መሬት ፡ ሰብል ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከተወሰነ ፡ ሰብል ፡ ውስጥ ፡ በመጠን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሰብል ፡ ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ለአከራዩ ፡ የሚገባው ፡ ድርሻ ፡ ወዲ ያው ፡ ጥያቄ ፡ እንዳደረገ ፡ የሚሰጠው ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ልማዶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፬ ። (የሚከፈለውን ፡ የኪራዩን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) የሚከፈለው ፡ የመሬት ፡ ኪራይ ፡ ዋጋ ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ በተ ወሰነ ፡ ሰብል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገበሬው ፡ በአንበጣ ፡ ወረራ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ድርቅ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ይኸንኑ ፡ በመሰለ ፡ ልዩ ፡ መዓት ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ የተመደበው ፡ የሰብል ፡ (የሀብት) ፡ ገቢ ፡ ከደንበኛው ፡ መጠን ፡ ግማሽ ፡ ሆኖ ፡ የተቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕዳውን ፡ በከፊል ፡ ይቅርልኝ ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ የዕዳው ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ሲል ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ውሎችና ፡ ልማዶች ፡ ሁሉ ፡ ፈራ ሾች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፺፭ ። (፪) ለመጠየቅ ፡ ስላለመቻል ።

(፩) የሰብሉ ፡ መጥፋት ፡ የደረሰው ፡ ከመሬቱ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገበሬው ፡ ዕዳው ፡ ይቅርልኝ ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርሰው ፡ ምክንያት ፡ ያለና ፡ በዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ የታወቀ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገበሬው ፡ እንደዚሁ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይ ችልም ።

፫) እንደዚሁም ፡ ገበሬው ፡ በራሱ ፡ የደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ በአንዱ ፡ አሹራንስ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ የተጠበቀ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዘገየ ፡ ጊዜ ፡ ለመ ጠየቅ ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ ። (፫) ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ የዕዳ ፡ ልክ ።</u>

(፩) ገበሬው ፡ ሊቀነስልኝ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ የሚጠይቀውን ፡ የዕዳ ፡ ልክ ፡ ለመ ገመት ፡ የተለመደውን ፡ (የሰብል) ፡ የሀብት) ፡ ገቢና ፡ የደረሰበትን ፡ ጉዳት ፡ ትልቅነት ፡ በማመዛዘን ፡ ይደረጋል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ገበሬው ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ሰብል ፡ ሊያገኝ ፡ ያልቻለውን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ ውሉ ፡ እስከሚያልቅ ፡ ድረስ ፡ በቀሩት ፡ ዓመ ታት ፡ ውስጥ ፡ አገኛለሁ ፡ የሚለውን ፡ የሰብል ፡ ትርፍ ፡ በመገመት ፡ ነው ።

(፫) ርትዕ ፡ ካላስገደደና ፡ የውሉ ፡ መለዋወጥ ፤ ገበሬውን ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋራ ፡ ለማኖር ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ የውሉን ፡ ግዴታዎች ፡ መለወጥ ፡ አይችሉም ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩ ። የተከራይ ፡ አከራይ ። (፩) መሠረቱ ።</u>

(፩) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ገበሬው ፡ የተከራየውን ፡ መሬት ፡ ያለ ፡ አከራዩ ፡ ፈቃድ ፡ ለማከራየት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ተከራዩ ፡ መሬቱን ፡ አሳልፎ ፡ ለሌላ ፡ ለማከራየት ፡ አከራዩ ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ምክንያት ፡ የከለከለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገበሬው ፡ ውሉ ፡ እንዲሻር ፡ ለመጠ የቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፪ ። (፪) ልዩነት ።</u>

(፩) ስለ ፡ ሆነም ፡ በአከራዩ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የማያስከትል ፡ ከሆነ ፡ ገበሬው ፡ በውል ፡ በተቀበለው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ቤቶች ፡ ለሌላ ፡ ለማከራየት ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ የተከራይ ፡ አከራዩን ፤ የሚመለከቱ ፡ ደን ቦች ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ላይ ፡ የጸኑ ፡ ይሆናሉ ፤ እንዲሁም ፡ አሳልፎ ፡ ማከ ራየቱን ፡ አከራዩ ፡ በፈቀደም ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፫ ። የውሉ ፡ ማለቅ ፡ (፩) መሠረቱ ።</u>

(፩) ለኪራዩ ፡ ውል ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ለሌ ላው ፡ ወገን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ሰጥቶ ፡ ስንብቱን ፡ ካስ ታወቀ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ውሉ ፡ የሚያልቅ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ልማዶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፬ ። (፪) ስለ ፡ ውሉ ፡ መታደስ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ስንብት ፡ ያልተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ስንብት ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ገበሬውን ፡ አከራዩ ፡ እያወቀ ፡ ሳይቃወመው ፡ በመሬቱ ፡ መጠቀሙን ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በተጨማሪ ፡ ለአራት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ የታደሰ ፡ ይሆናል ።

(፪) ለቀረበው ፡ ጕዳይ ፡ ሁሉ ፡ የሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ አስቀድመው ፡ ባደረጉት ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የሚፈጸሙ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ አስቀድሞ ፡ ለነበረው ፡ ውል ፡ የተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፭ ። (፫) ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ።**

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ወይም ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሬቱን ፡ ከተረከበ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡ ሲሆን ፡ ገበሬው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ የውሉን ፡ ዘመን ፡ ለመለዋወጥ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ የሚያልቀው ፡ ገበሬው ፡ ውሉን ፡ ለመሰረዝ ፡ የመፍቀዱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለአከራዩ ፡ ከደረሰው ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በመጋቢት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያልቃል ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተጻፈውን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፮ ። (፬) ጊዜው ፡ ያልተወሰነ ፡ ኪራይ ።**

(፩) ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ባልተወሰነ ፡ ውል ፡ የተደረገ ፡ ኪራይ ፤ የመሬቱ ፡ ይዞታ ፡ በገበሬው ፡ እጅ ፡ ከገባበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ለሚጸና ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ልማዶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፯ ። (፭) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ መተው ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሚገዛ ፡ ወይም ፡ የሚያገኝ ፡ ሰው ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲቋረጥ ፡ የፈለገ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ለርሱ ፡ ተሰጥቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱን ፡ ከገዛበት ፡ ወይም ፡ ካገኘበት ፡ አንሥቶ ፡ በሚከተለው ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለገበሬው ፡ ስንብት ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ይህ ፡ ስንብት ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በመጋቢት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፫) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ወይም ፡ ልማዶች ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፰ ። (፯) የተከራዩ ፡ መብት ።

(፩) የስንብት ፡ ማስታወቂያ ፡ የተሰጠው ፡ (የተነገረው) ፡ ገበሬ ፡ ለአከራዩ ፤ ንብረቱን ፡ ለገዛው ፤ ወይም ፡ ለአገኘው ፡ ሰው ፡ ሐሳቡን ፡ በማስታወቅ ፡ ውሉ ፡ የሚያልቅበትን ፡ ቀን ፡ ለማሳጠር ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አከራዩ ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ የገበሬው ፡ ሐሳብ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰው ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ገበሬው ፡ በወሰነው ፡ ቀን ፡ ውሉ ፡ የሚቋረጥ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፱ ። ስለ ፡ ገበሬው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አከራዩ ፡ መሞት ።

(፩) ገበሬው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የርሱ ፡ ወራሾች ፡ መብቱን ፡ ያቈየላቸው ፡ ሰው ፡ ከሞተበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሚከተሉት ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለአከራዩ ፡ ስንብት ፡ በመስጠት ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲቋረጥ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪) አከራዩ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥራው ፡ ክንውን ፡ መሪነት ፡ በኪራዩ ፡ ውል ፡ ለአከራዩ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ ከሞተበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሚከተሉት ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለአከራዩ ፡ ወራሾች ፡ ስንብት ፡ በመስጠት ፡ ገበሬው ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲቋረጥ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በፊት ፡ በተመለከቱት ፡ ሁለት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ ውሉ ፡ በሚከተለው ፡ መጋቢት ፡ አንድ ፡ ቀንና ፡ አከራዩ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹ ፡ የገበሬውን ፡ ወይም ፡ የገበሬውን ፡ ወራሾች ፡ ስንብት ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፲ ። ስለ ፡ ገበሬው ፡ መታመም ። (፩) የገበሬው ፡ መብት ።

(፩) ገበሬውን ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ አንዱን ፡ ሥራውን ፡ በደንበኛው ፡ ሁኔታ ፡ ለመቀጠል ፡ የማያስችለው ፡ በሽታ ፡ የያዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውሉ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፪) ገበሬው ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአከራዩ ፡ አንዳችም ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

(፫) ውሉም ፡ የሚያልቀው ፡ የገበሬው ፡ ማስታወቂያ ፡ ለአከራዩ ፡ ከደረሰው ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፲፩ ። (፪) የአከራዩ ፡ መብት ።

(፩) ገበሬውን ፡ ወይም ፡ ከገበሬው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አንዱን ፡ ሥራውን ፡ በደንበኛ ፡ ሁኔታ ፡ ለመቀጠል ፡ የማያስችለው ፡ በሽታ ፡ የያዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚከፈለው ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ከተወሰነ ፡ የሰብል ፡ ድርሻ ፡ ወይም ፡ ከትወሰነ ፡ ከመሬቱ ፡ አበል ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ በውሉ ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፪) አከራዩ ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ የተገለገለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለገበሬው ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ መጠነኛ ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ውስጥ ፡ ግማሹን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ውሉም ፡ የሚያልቀው ፡ ለገበሬው ፡ የአከራዩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰው ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፪ ። ቃጠሎ ።**

የተከራየው ፡ ነገር ፡ በእሳት ፡ መጥፋቱን ፡ ወይም ፡ መበላሸቱን ፡ የሚያመለክተው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለገበሬው ፡ በኪራይ ፡ በተሰጠው ፡የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ክፍል ፡ በሆኑ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤትና ፡ ሌሎች ፡ ሕንጻዎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፫ ። ውሉ ፡ ሲቋረጥ ፡ የሚደረግ ፡ ሥርዐት ፡ (፩) ጕዝጓዝ ፡ ሣርና ፡ ፍግ ።**

(፩) መሬቱን ፡ ለቆ ፡ የሚወጣው ፡ ገበሬ ፡ ስለ ፡ መሬቱ ፡ ደንበኛ ፡ አሠራር ፡ በሚያስገድደው ፡ ጥንቃቄ ፡ መሠረት ፡ የመጨረሻውን ፡ ዓመት ፡ ገለባ ፡ ሣሩንና ፡ ፍጉን ፡ መተው ፡ አለበት ።

(፪) ገበሬው ፡ መሬቱን ፡ ሲረከብ ፡ አነስተኛ ፡ መጠን ፡ የተቀበለም ፡ ቢሆን ፡ ትርፍ ፡ ሆኖ ፡ ለሚገኘው ፡ መጠን ፡ ኪሣራ ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ገበሬው ፡ ይበልጥ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለጐደለው ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፬ ። (፪) ዘር ።**

ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ልማድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ መሬቱን ፡ ለቆ ፡ የሚወጣ ፡ ገበሬ ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ሰብል ፡ ዘር ፡ እንዲተው ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፭ ። (፫) የግብርና ፡ ሥራ ፡ ወጪ ፡ (ኪሣራ) ።**

(፩) ገበሬው ፡ ውሉን ፡ በሚተውበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተለቀሙ ፡ ፍሬዎችን ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ርትዕ ፡ የሚያስገድድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፤ ላደረጋቸው ፡ የተክል ፡ ሥራዎች ፡ ወጪ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲቀበል ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ይኸውም ፡ ኪሣራ ፡ አከራዩ ፡ ከሚያገኛቸው ፡ ፍሬዎች ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፮ ። በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ማሻሻል ። —(፩) መሠረቱ ።**

(፩) የኪራዩ ፡ ውል ፡ የተቋረጠው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ በራሱ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ ባደረጋቸው ፡ ወጪዎች ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የማሻሻል ፡ ሥራ ፡ የፈጸመ ፡ ገበሬ ፡ ውሉ ፡ በሚያልቅበት ፡ ጊዜ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እንደዚሁ ፡ በተከራየው ፡ መሬት ፡ ላይ፡ውሉ፡በሚፈቅድለት፡መሠረት፡ቤቶች፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገበሬው፡ ኪሣራ ፡ (ግምት) ፡ ለማግኘት፡መብት፡አለው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፯ ። (፪) የኪሣራው ፡ (የግምቱ) ፡ ክፍል ።**

(፩) የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ ልክ ፡ ከተደረጉት ፡ ማሻሻያዎች ፡ ወይም ፡ ከተሠሩት ፡ ቤቶች ፤ የተነሣ ፡ መሬቱ ፡ ያገኘው ፡ ብልጫ ፡ ለ፱ ፡ ዓመት ፡ ከሚታሰበው ፡ ጋራ ፡ የሚተካከል ፡ ነው ።

(፪) ለዚህ ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ዳኞች ፡ ለአከራዩ ፡ ጊዜ ፡ መስጠት ፡ (መፍቀድ) ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፰ ። (፫) አንሥቶ ፡ የመሄድ ፡ (የመውሰድ) ፡ መብት ።**

ገበሬው ፡ ከመረጠ ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሳያደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የተቻለ ፡ ከሆነ ፡ ያደረጋቸውን ፡ የማሻሻል ፡ ሥራዎች ፡ አንሥቶ ፡ ለመውሰድ ፡ ወይም ፡ ቤቶችን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሥራ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፲፱ ። ተፈጻሚነት ፡ ያላቸው ፡ ደንቦች ።**

(፩) የሥራ ፡ ተቋራጭነቱ ፡ ውል ፡ የተደረገው ፡ የሕንጻን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የተሠራውን ፡ ለማደስ ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ ለማደራጀት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚመራ ፡ ይሆናል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን፡ስለሚመለከቱ፡ ውሎች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጭነትን ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ በተባሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተወገዱ ፡ ሆኖ ፡ በማይገኙበት ፡ መጠን ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፳ ። የውሉ ፡ መፈጸም ፡ አስረጅነት ።**

(፩) ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ስለሚፈጽሙት ፡ ሥራዎችና ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ካል ተስማሙ ፡ በቀር ፡ የተቋራጭነት ፡ ውል ፡ አለ ፡ አይባልም ።

(፪) የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ አሠሪው ፡ እያወቀ ፡ ሥራዎቹን ፡ ለመሥራት፡ ጀምሮ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከዋጋው ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውል ፡ ለመኖሩ ፡ በቂ ፡ ማረጋገጫ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፳፩ ። የሚፈጸሙ ፡ ሥራዎች ። (፩) በቂ ፡ የሆነ ፡ የሥራዎች ፡ ዝርዝር ።**

(፩) የሚሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ዐይነት ፡ በፕላን ፡ በንድፍ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አስረጂዎች ፡ ሊለይ ፡ ይችላል ።

(፪) የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ አስረጂዎች ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ አጥብቆ ፡ መከተል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፪ ። (፪) በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) የሚሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ የተነገሩት ፡ በጠቅላላው ፡ አኳኋን ፡ ብቻ፡ እንደ፡ሆነ፤ የነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ ብዛት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ውሉ ፡ በጠባብ፡ ዐይነት ፡ መተርጐም ፡ አለበት ።

(፪) ደግሞም ፡ የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ለአእምሮ ፡ ግምት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ በሚታየው ፡ መጠን ፡ ያሠሪውን ፡ ፈቃድ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፫ ። የዋጋው ፡ አወሳሰን ፡ ዐይነት ።**

(፩) የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ ለመፈጸም ፡ የተዋዋላቸው ፡ ሥራዎች ፡ ዋጋ፡በጅምላ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) የሥራዎቹ ፡ ዋጋ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ ግምትም ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፫) ዋጋው ፡ በጅምላ ፤ ወይም ፡ በአቅራቢያ ፡ ግምት ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሥራው ፡ ዋጋ፡የሚገመተው፡ለሥራ ፡ በዋሉት ፡ ነገሮችና ፡ ግምት ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ ሥራ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፬ ። በአቅራቢያ ፡ ግምት ፡ የሚደረግ ፡ ዋጋ ።**

(፩) የሥራው ፡ ዋጋ ፡ በአቅራቢያ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥራው ፡ ተቋራጭ፡ በጅምላ ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ተዋዋለ ፡ ታስቦ ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ ይገደዳል ።

(፪) የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ በደረሰበት ፡ ወጪና ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ ምክንያት፡ የሚወሰነው ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ አቅራቢያ ፡ ግምት ፡ ተብሎ፡ ከተስማማበት፡ዋጋ፡ ሐያ ፡ በመቶ ፡ ካልበለጠ ፡ በቀር ፡ የመጨረሻውን ፡ ዋጋ ፡ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፫) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ዋጋ ፡ ባደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አሠሪው ፡ አንዳች ፡ አስረጅ ፡ ሊጠይቀው ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፭ ። በጅምላ ፡ ወይም ፡ በአቅራቢያ ፡ ግምት ፡ የተወሰነ ፡ ዋጋ ።**

**(፩) የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።**

(፩) የሥራው ፡ ዋጋ ፡ ለሥራ ፡ የሚውሉትን ፡ ነገሮችና ፡ ሥራ ፡ በመመልከት ፡ የሚወሰን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖር ፡ የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ ሥራዎቹ ፡ የደረሱበትን ፡ ሁኔታና ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ ላሠሪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በውሉ ፡ የተነገረ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በየወሩ ፡ መጨረሻ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፮ ። (፪) የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሥራው ፡ ዋጋ ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ፪ቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ የተስማሙበትን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ከአሠሪው ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የተነገረ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለአሠሪው ፡ በሰጠው ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ለሥራው ፡ የሚሆን ፡ ደመወዝ ፡ ሊያገባበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፯ ። (፫) ላሠሪው ፡ ያለው ፡ መብት ።

አሠሪው ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ሒሳብ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ዎች ፡ እንዲመረምሩት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፰ ። የሥራ ፡ ምርመራ ።

አሠሪው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ሥራዎቹ ፡ የደረሱበትን ፡ ሁኔታ ፡ በሥ ራው ፡ ላይ ፡ የዋሉትን ፡ መሥሪያዎች ፡ ዐይነትና ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ በልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ለማስመርመር ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፱ ። ሥራውን ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ዋጋውን ፡ መክፈል ፤ ሥራው ፡ እንደ ፡ ተመረመረና ፡ አሠሪው ፡ እንደ ፡ ተቀ በለው ፡ የሚያስገምት ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የተከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፡ ከዋጋው ፡ ላይ ፡ በቅድሚያ ፡ እንደ፡ተከ ፈሉ ፡ የሚገመት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተሰጠው ፡ አገማመት ፡ የሚጸና ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴ ። በከፊል ፡ ሥራውን ፡ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ዋጋውን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ውሉ ፡ በደረጃ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ደረጃ ፡ ሥራ ፡ በተፈጸመ ፡ ቍጥር ፡ ምርመራውና ፡ የአቀባበሉ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዐት ፡ ይፈጸማል ።

(፪) የያንዳንዱ ፡ የሥራ ፡ ደረጃ ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በተፈ ጸሙት ፡ ሥራዎች ፡ መጠን ፡ ከሥራው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ እንዲከ ፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፩ ። አሠሪው ፡ የሚጠይቃቸው ፡ የሥራ ፡ መለዋወጥ ። (፩) የአሠሪው ፡ መብት ።

የተጠየቁት ፡ የሥራ ፡ መለዋወጥ ፡ በቴክኒክ ፡ ረገድ ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚቻልና ፡ የሥራውንም ፡ ጥንካሬ ፡ የማይጎዱ ፡ ከሆኑ ፡ አሠሪው ፡ አስቀድሞ ፡ ከተስማማበት ፡ የሥራ ፡ ዐቅድ ፡ አንዳንድ ፡ መለዋወጥ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፴፪ ። (፪) የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲቀነስ ፡ ሥራ ፡ አሠሪው ፡ የጠየቀው ፡ የሥራ ፡ መለዋወጥ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ወጪ ፡ በቀነሰለት ፡ መጠን ፡ በውል ፡ ተወስኖ ፡ ከነበረው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ እንዲቀነስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ አሠሪው ፡ በጠየቀው ፡ የሥራ ፡ መለዋወጥ ፡ ምክንያት ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ወጪ ፡ የሚያበዛ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ የሚያ ስከትል ፡ ወይም ፡ አላፊነቱን ፡ የሚያከብድበት ፡ በመሆኑ ፡ መጠን ፡ ለዚሁ ፡ ለተጨማሪው ፡ ሥራ ፡ ዋጋውና ፡ የሚከፈለው ፡ አበል ፡ ተጨምሮ ፡ እንዲከፈ ለው ፡ አሠሪውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በሚቀነሰው ፡ ወይም ፡ በሚጨመረው ፡ የዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተጨማሪ ፡ ወይም ፡ ተቀናሽ ፡ ሥራ ፡ የሚከፈለውን ፡ ሒሳብ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የሚመርጡዋ ቸው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ ዳኞች ፡ ይወስኑታል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፴፫ ። (፫) የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ እንቢታ ።

(፩) አሠሪው ፡ የጠየቃቸው ፡ የሥራ ፡ መለዋወጥ ፡ ስምምነት ፡ የተደረገባቸውን ፡ ፕላኖች ፡ ንድፎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰነዶች ፡ የሚነኩ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አሠሪው ፡ የጠየቃቸው ፡ መለዋወጥ ፡ በብዛታ ቸውም ፡ ወይም ፡ በዐይነታቸው ፡ ስምምነት ፡ ከተደረገበት ፡ ሥራ ፡ በአፈ ጻጸማቸው ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትሉ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አልቀ በልም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፫) ሥራው ፡ በተለይ ፡ በፍጹም ፡ እንደ ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ የሚገመተው ፡ አስቀድሞ ፡ ከታሰበው ፡ ሥራ ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ ሊገመት ፡ ከሚቻለው ፡ ከመቶ ፡ ሐያ ፡ በላይ ፡ መለዋወጥን ፡ የሚያስከትል ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፴፬ ። ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሚያቀርባቸው ፡ መለዋወጥ ።

(፩) በቴክኒክ ፡ ምክንያት ፡ ስምምነት ፡ የተደረገበት ፡ ዕቅዱ ፡ እንዲለዋወጥ ፡ አስ ፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አስቸኳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሥራ ፡ ተቋ ራጩ ፡ ለአሠሪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) የታሰበው ፡ መለዋወጥ ፡ አሠሪውን ፡ አንድም ፡ ተጨማሪ ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ የሚያስገድደው ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፴፭ ። ውሉን ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።

አሠሪው ፤ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አንዳችም ፡ ጥፋት ፡ ባያደርግም ፡ እንኳ ፡ የፈረ መውን ፡ ውል ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፴፮ ። የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ መብት ። (፩) ዋጋው ፡ በጅምላ ፡ ወይም ፡ በአቅራ ቢያ ፡ ግምት ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ።

(፩) አሠሪው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ውሉን ፡ ያፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ስምምነት ፡ የተደረገበትን ፡ የጅምላ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ የአቅራቢያ ፡ ግምት ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በውሉ ፡ መሻር ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከማውጣት ፡ የቀረለት ፡ ወጪ ፡ ከዚህ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ ግምት ፡ ዋጋው ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ሁለት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ መሠረት ፡ አሠሪው ፡ መክፈል ፡ ያለበትን ፡ ገንዘብ ፡ እስከ ፡ ሐያ ፡ በመቶ ፡ ድረስ ፡ በማብዛት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፳፮፻፳፯ ። (፪) ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ዋጋዎች ።

(፩) የሥራው ፡ ዋጋ ፡ በመሥሪያዎቹና ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ በሚሆነው ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ የተወሰነ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለሱ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ለተሠራባቸው ፡ መሥሪያዎችና ፡ ለተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ተቋራጩ ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እንዲሁም ፡ አሠሪው ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ላደረጋቸው ፡ ውሎች ፡ በራሱ ፡ ሒሳብ ፡ ማሰብ ፡ አለበት ። ወይም ፡ በነዚሁ ፡ ውሎች ፡ መሻር ፡ ምክንያት ፡ ለሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ የሚደርስበትን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) በመጨረሻም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አሠሪው ፡ ሊከፍለው ፡ ግዴታ ፡ የገባበትን ፡ ጠቅላላ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፳፮፻፳፰ ። የውሉ ፡ መፍረስ ።

(፩) የውሉ ፡ መፍረስ ፡ በሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ አሠሪው ፡ በሚገባ ፡ የጠየቀውን ፡ መለዋወጥ ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቀበል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስቀድመው ፡ በተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ስምምነት ፡ ከተደረገበት ፡ የሥራ ፡ ዋጋና ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ የአሠሪው ፡ የኪሣራ ፡ መጠየቁ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፳፮፻፳፱ ። ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሚሰጠው ፡ መድን ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራ ጩ ፡ ሥራውን ፡ ካስረከበበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ አሠራሩና ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ስለ ፡ ጠንካራነቱ ፡ ለዐሥር ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ መድን ፡ ነው ።

(፪) በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ በተሠራበት ፡ መሬት ፡ ዐይነት ፡ ምክንያት ፡ በተሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፫) ማናቸውም ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ የሚያሳጥር ፡ ወይም ፡ መድንነቱን ፡ የሚሽር ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ አይጸናም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፵ ። የምክትል ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮችና ፡ ሠራተኞች ፡ በቀጥታ ፡ ያላቸው ፡ የክስ ፡ መብት ።

በአንድ ፡ የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭነት ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮች ፡ ወይም ፡ ሠራተኞች ፡ የሠሩበትን ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለመከፈል ፡ ክሳቸውን ፡ ባቀረቡበት ፡ ጊዜ ፡ አሠሪው ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ሊከፍል ፡ በሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ባሠሪው ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ገንዘባቸውን ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣና ፡ ስለ ፡ ወለድ ፡ አግድ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ አቋቋም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፵፩ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ የማቋቋሚያው ፡ ሰነድ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ በቀጥታ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በኑዛዜ ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፵፪ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሻጭ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠው ፡ መያዣ ።

አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሸጠ ፤ ያስተላለፈ ፡ ሰው ፡ ለተዋዋለበት ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ ዋስትናና ፡ በሽያጩ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ሌሎች ፡ ግዴታዎች ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆነው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በዚህ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፵፫ ። ለማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠው ፡ መያዣ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፤ በክፍያው ፡ መሠረት ፡ በሌሎቹ ፡ የጋራ ፡ ተካፋዮች ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠው ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህም ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ከክፍያው ፡ ውስጥ ፡ ለሚጐልበት ፡ ድርሻውና ፡ ምናልባትም ፡ በክፍያ ፡ ያገኛቸውን ፡ ሀብቶች ፡ እንዲለቅ ፡ ቢፈረድበት ፤ የጋራ ፡ ተካፋዮቹ ፡ ሊከፍሉት ፡ ለሚገባው ፡ ኪሣራ ፡ ዋስትና ፡ ነው።

BACK



ቍ ፡ ፫ሺ፶፬ ። በፍርድ ፡ የሚሰጥ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ።

(፩) ዳኞች ፡ በዳኝነት ፡ የሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ሽማግሎች ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ የሰጡት ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ የሰጡት ፡ ትእዛዝ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማረጋገጥ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ይህም ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ብይን ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ የዕዳ ፡ ልክና ፡ ስለዚህም ፡ ዕዳ ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ንብረቶች ፡ ለይቶ ፡ ያመለክታል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፶፭ ። የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የሚቋቋምበት ፡ ሰነድ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ የሚያቋቁም ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ ሰነድ ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) መያዣ ፡ የተሰጠበት ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገንዘብ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፶፮ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠው ፡ ዕዳ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፤ አሁን ፡ ለተደረገ ፡ ለወደፊቱ ፡ ለሚደረግ ፡ በውለ ፡ ገብነት ፡ ለሚደርስ ፡ ወይም ፡ ይደርሳል ፡ ለሚባል ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ዋስትና ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ለአምጪው ፡ በሚከፈል ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ገንዘብ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ ውል ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፶፯ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉ ፡ ንብረቶች ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ሊቋቋም ፡ የሚቻለው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ እንደማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፶፰ ። መያዣ ፡ የሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ።

(፩) በመያዣነት ፡ መስጠቱ ፡ የተመዘገበ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣውን ፡ በሚያቋቁመው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ መጠቀስ ፡ አለበት ።

(፪) ሰነዱም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የሚገኝበትን ፡ ወረዳ ፡ የንብረቱን ፡ ዐይነት ፡ የሚቻልም ፡ ቢሆን ፡ በርስት ፡ መዝገብ ፡ የተጻፈበትን ፡ የካርታ ፡ ቍጥር ፡ በቶለይ ፡ ማመልከት ፡ ይገባዋል ።

(፫) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የሚገኘው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ባልተቋቋመበት ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሰነዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሁለቱን ፡ አዋሳኞቹን ፡ ገልጾ ፡ ማመልከት ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፵፱ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ችሎታ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ በባለዕዳው ፤ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ መያዣ ፡ ሰጥቶ ፡ በሚዋዋል ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፤ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

(፪) ለራሱ ፡ ዕዳ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆን ፡ አንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለዕዳ ፡ በመያዣነት ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻለው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ለሌላ ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሆን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለመያዣ ፡ መስጠት ፡ የሚቻለው ፡ ይህንኑ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ሳይቀበል ፡ በችሮታ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ሊያዝበት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፶ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቅጣት ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው የሰጠው ፡ የመያዣ ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ (አይጸናም) ።

(፪) ይህ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ሀብቱን ፡ በመያዣ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ የማይን ቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሊያዝበት ፡ ችሎታ ፡ ቢያገኝም ፡ እንኳ ፡ አስቀድሞ ሰጥቶት ፡ የነበረው ፡ መያዣ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይሆንም ። ፡

(፫) እንዲሁም ፡ ወደፊት ፡ ይሠራሉ ፡ የሚባሉትን ፡ ሕንጻዎች ፡ መያዣ ፡ መስጠት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፶፩ ። (፪) በባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የታወቀ ፡ ንብረት ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ ክፍል ፤ የአንድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ መሆኑን ፡ ዐውቆለት ፡ የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከሰጠው ፡ ሰው፡ ጋራ፡ የተደረገ ፡ የንብረት ፡ መያዣ ፡ ውል ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

(፪) የባለሀብትነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተሰጠበት ፡ ማስረጃ ፡ ፍርስ ፡ ሆኖ ፡ የተሰረዘ ፡ ቢሆንም ፡ በመያዣው ፡ የሚከራከረው ፡ ሰው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ አለመሆኑ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ የርስት ፡ መያዣው ፡ ውል ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

(፫) የርስት ፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ከምስክር ፡ ወረቀት ፡ መስጫው ፡ ታክስ ፡ ጋራ ፡ ከሚከፈለው፡ ለመጠባበቂያ ፡ ዋስትና ፡ ከተመደበው ፡ ገንዘብ ፡ በዕዳ ፡ የተያዘውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቱን ፡ ዕዳ ፡ ከፍሎ ፡ ንብረቱን ፡ ላስለቀቀው ፡ ባለሀብት ፡ ይከፈለዋል ።

BACK



### ቍ ፡ ፫ሺ፶፪ ። የማጻፍ ፡ አስፈላጊነት ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ቢሆን ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ርስት ፡ መዝገብ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡ ውጤት ፡ አያስገኝም ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፶፫ ። የአጻጻፉ ፡ ሥርዐት ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ መያዣ ፡ እንዲመዘግብ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበለት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ሠራተኛ ፤ የውሉን ፡ አመዘጋገብ ፡ ሥርዐት ፡ የሚፈጽመው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ አመዘጋገብ ፡ ሥርዐት ፡ በሚመለከተው ፡ አንቀጽ ፡ በተደነገገው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የዚሁም ፡ አንቀጽ ፡ ደንብ ፡ አመዘጋገብ ፡ የሚሻሻልበትንና ፡ የሚለወጥበትን ፡ ሥርዐት ፡ ወስኗል ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፶፬ ። የማስመዝገቢያው ፡ ወጪ ።

(፩) የማስመዝገቢያውን ፡ ወጪ ፡ የሚችለው ፡ በመጨረሻው ፡ ባለዕዳው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ ያስመዘገበና ፡ ለዚህም ፡ ወጪውን ፡ አስቀድሞ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ የከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲከፍለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፶፭ ። የገንዘብ ፡ መብት ፡ መቀነስ ።

(፩) ባለዕዳው ፡ ከዕዳው ፡ ጠቅላላ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ሩቡን ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ከመዝገቡ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ እንዲተካከልለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ገንዘብ ፡ ጠያቂውም ፡ ይህን ፡ የመዝገብ ፡ መተካከል ፡ ጉዳይ ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

(፫) ባለዕዳው ፡ ከተበደረው ፡ ገንዘብ ፡ በከፊሉ ፡ በመክፈል ፤ በመያዣ ፡ ካስያዛቸው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ በከፊል ፡ እንዲለቀቅለት ፡ ለመጠየቅ ፡ አይፈቀድለትም ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፶፮ ። የገንዘብ ፡ መብት ፡ መጨመር ።

(፩) በመጀመሪያ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በማስተካከል ፡ ብቻ ፡ የገንዘቡን ፡ ልክ ፡ ለመጨመር ፡ አይቻልም ።

(፪) በመጀመሪያ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ከተጻፈው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲኖረው ፡ ከተፈለገ ፡ ይህንኑ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማስመዝገብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፶፯ ። ለማስመዝገብ ፡ የተወሰነ፡ ጊዜ ።**

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የተያዘበትን ፡ ዕዳ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ የሌለበት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በዕዳ ፡ ተይዟል ፡ የተባለውን ፡ ይህንኑ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ገዝቶ ፡ ግዥውን ፡ በማይንቀሳቀስ፡ ንብረት ፡ መጻፊያ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ካጻፈ ፡ በኋላ፡ የተመዘገበውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመያዣ ፡ ማጻፍ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ በፍርድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መወሰኑ ፡ በመዝገብ ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ባለዕዳው ፡ መክሠሩ ፡ ከተገለጸ ፡ በኋላ ፡ የሚደረግ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመያዣ ፡ መጻፍ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፶፰ ። የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ ፡ መብት ፡ የሚቀርበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፤ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለፋ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ውል ፡ እንዲታደስ ፡ አዲስ ፡ የመዝገብ ፡ ማጻፍ ፡ ጕዳይ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ዘመን ፡ ይራዘማል ።

(፫) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ የተመዘገበው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ውል ፡ አዲሱ ፡ የመዝገብ ፡ ማስጻፍ ፡ ጕዳይ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ወደፊት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ውጤቶች ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፶፱ ። መሠረቱ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፤ መያዣው ፡ የሚመለከተውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ያስያዙት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ ከሌሎቹ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በፊት ፡ ለርሱ ፡ በቀዳሚነት ፡ እንዲከፈለው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የመጀመሪያው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ፤ መብቱን፡ ላስመዘገበ፡ ለሌላ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን፡ ባለዕዳው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ቢሸጥ ፡ ቢያስተላልፍም ፡ እንኳ ፡ የመያዣ ፡ መብቱን ፡ ያስመዘገበው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ባለመያዣ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ለማንኛቸውም ፡ ሌሎች ፡ ተራ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ ይኖረዋል ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፹ ። ንብረትን ፡ የማስቀረት ፡ ስምምነት ።

(፩) ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይከፈል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያገኘበትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ይወስዳል ። ወይም ፡ በሕጉ ፡ የተመለከተውን ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርማሊቴ) ፡ ሳይ ጠብቅ ፡ ሊሸጠው ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ለዕዳው ፡ መክፈያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያገኘበትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፤ የዕ ዳው ፡ መክፈያ ፡ አድርጎ ፡ ባለዕዳው ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ለመስጠት ፡ (ይችላል ፡ ብሎ) ፡ መስማማት ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፹፩ ። ክስ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ (፩) ሥልጣን ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ አመዘጋገብ ፤ ወይም ፡ መያዣ ፡ የተሰጠ በትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፤ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ይኸው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ የሚገ ኙት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፹፪ ። (፪) መኖሪያ ፡ ቦታን ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) በማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢነት ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠውና ። ንብረቱንም ፡ በመያዣ ፡ ሰጭ ፡ የሆነ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታቸውን ፡ እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሚገኙበት ፡ ክፍል ፡ ለይቶ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

(፪) ሕጋዊ ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታቸውን ፡ እንዲመርጡ ፡ ከተጠየቁበት ፡ ጊዜ ፡ አን ሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ሳይመርጡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ በሚገባ ፡ ከቀረቡላቸው ፡ በኋላ ፡ የባለጉዳዮቹን ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ መርጠው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፹፫ ። (፫) (ወኪል) ፡ የንብረት ፡ ጠባቂ ።

እንዲሁም ፡ በማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢነት ፡ ስሙና ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ላልታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በክርክሩ ፡ ላይ ፡ ራሱ ፡ እንዲኖር ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አንድ ፡ አስቸኳይ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ ዳኞች ፡ ለዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ አንድ ፡ ንብ ረት ፡ ጠባቂ ፡ ለመሾም ፡ ይችላሉ ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡
ቀደምትነት ፡ የብልጫ ፡ መብት ።

(ሀ) ይህ ፡ መብት ፡ የሚመለከታቸው ፡ ንብረቶች ።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፬ ። ከንብረቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሆነና ፡ ተጨማሪ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይና ፡ ከንብረቱ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ባላቸው ፡ ክፍሎች ፡ እንዲሁም ፡ ተጨማሪ ፡ ክፍሎችንም ፡ ጭምር ፡ የሚጠቀልል ፡ ነው ።

(፪) በመያዣው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ንብረቱ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆነው ፡ በግልጽ ፡ የተመለከቱት ፡ ዕቃዎች ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፭ ። የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ ከሚመለከተው ፡ ከማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በተለዩትና ፡ ባለሀብትነታቸውም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በተዛወሩት ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የባለመያዣነት ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ በአጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ መያዣ ፡ የሆነው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ቢቀነስ ፡ ቢጠፋ ፡ ወይም ፡ ቢበላሽ ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ በታወቁለት ፡ መብቶቹ ፡ ብቻ ፡ ሊገለገልባቸው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፮ ። የማይንቀሳቀሰውን፡ ንብረት ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መሥራትና ፡ ስለ ፡ ማሻሻል ። (፩) መሠረቱ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዝ ፡ መብት ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ በሚመለከተው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትና ፡ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚሠሩትን ፡ አዳዲስ ፡ ሥራዎች ፤ ተክሎችና ፡ ሰብሎች ፡ የሚጠቀልል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፯ ። (፪) የሥራ ፡ ተቋራጮችና ፡ የዕቃ ፡ አቅራቢዎች ፡ ልዩ ፡ መብት ።

(፩) ስለ ፡ ሆነም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሰውን ፡ በማደስ ፡ የማሻሻል ፡ ሥራና ፡ የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮችና ፡ ለሥራው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የማደሻውን ፡ ዕቃ ፡ የሸጡ ፡ አትክልት ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ የሰብል ፡ ፍሬ ፡ ያቀረቡ ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢዎች ፤ ለፈጸሙት ፡ ሥራና ፡ ላቀረቡት ፡ ዕቃ ፡ ስለሚከፈላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጉዳይ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ካላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ (ብልጫ) ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጣቸዋል ።

BACK



(፪) በዚህም ፡ በክፍያ ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ የድርሻውን ፡ ልክ፡ ይወስናሉ ።

(፫) እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በልዩ ፡ ልዩዎች ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮችና ፡ በዕቃ ፡ አቅራቢዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረገውን ፡ የክፍያ ፡ ጉዳይ ፡ ይወስናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፫ ። የቤትና ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ኪራይ ።

(፩) በኪራይ ፡ የተሰጠውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚመለከተው ፡ የመ ያዣ ፡ መብት ፡ ንብረቱ ፡ በፍርድ ፡ ከተያዘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የሚታሰ በውን ፡ የቤትና ፡ የርሻ ፡ ኪራይን ፡ ይጠቀልላል ።

(፪) ቤት ፡ ተከራዮችና ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ተከራዮች ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ መያዙ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተሰጣቸው ፡ በኋላ ፡ የቤቱን ፡ ወይም ፡ የመሬቱን ፡ ኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ለማይንቀሳቀሰው ፡ ንብ ረት ፡ ባለሀብት ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ሊከፍሉ ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፬ ። ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የተመደበ ፡ ኪሣራ ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፤ ንብረቱ ፡ በጠፋ ፡ ወይም ፡ በተ በላሸ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ አሹራንስ ፡ ወይም ፡ በአላፊ ነት ፡ የሚከፈል ፡ የኪሣራን ፡ ሒሳብ ፡ የሚጠቀልል ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ንብረቱ ፡ በሚወሰድበት ፡ ጊዜ ፡ ለባለዕዳው፡(ለባለሀብቱ)፡ የሚከፈለውን ፡ ግምት ፡ የሚጠቀልል ፡ ነው።

ቍ ፡ ፫ሺ፳፭ ። (፪) ስለ ፡ አከፋፈሉ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ፈቃድ ።

(፩) በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብታቸውን ፡ ያስመዘገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፤ በአሹራንስ ፡ በኀላፊነት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ በመልቀቅ ፡ ምክንያት ፡ መያዣውን ፡ ለሰጠው ፡ ባለዕዳ ፡ የሚከፈሉት ፡ ኪሣራዎች ፡ ሊሰጡት ፡ አይቻልም ።

(፪) ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኪሣራ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት፡ መያዣ ፡ የሰጠ ፡ ባለዕዳ ፡ ለተመዘገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች፡ የኪሣራውን፡ ልክና ፡ ምክንያት ፡ እንዲሁም ፡ የሚከፍለውን ፡ ሰው ፡ ስምና ፡ አድርሻ ፡ ያስ ታውቃል ።

(፫) ለዚህ ፡ አከፋፈል ፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሠ ላሳ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ ባለመብት ፡ የሆኑ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መቃወማቸውን ፡ ያልገለጹ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣ ራው ፡ ለባለዕዳዎች ፡ እንዲከፈል ፡ እንደ ፡ ተስማሙ ፡ ያህል ፡ ይገመታሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፭፩ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ መያዣ ፡ የሰጠ ፡ ባለዕዳ ፡ መብት ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ለሰጠ ፡ ባለዕዳ ፡ የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ያልበለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሱው ፡ እንዲከፈለው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የሰጠ ፡ ባለዕዳ ፡ በኪሣራው ፡ ገንዘብ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመሥራት ፡ ወይም ፡ ለማ ደስ ፡ የሚያውለው ፡ ለመሆኑ ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ተስፋ ፡ የሰጠበት ንም ፡ ነገር ፡ ለመፈጸም ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሆን ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱ ፡ ዋስትናዎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ መያዣዎች ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኪሣራ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆንም ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የሰጠ ፡ ባለዕዳ ፡ ለሱ ፡ የሚከፈለውን ፡ ኪሣራ ፡ ዳኞች ፡ በመረጡት ፡ በትእዛዝ ፡ ባለአደራ ፡ ተይዞ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፭፪ ። በስመ ፡ ርስቱ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

በስመ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ አላባው ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ የሚጠቀለል ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፭፫ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ ማጓድል ። (፩) የባለዕዳው ፡ አድራጎት ።**

(፩) ባለዕዳው ፡ በራሱ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብ ረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ እንዲቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዲ ጎዳ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ አዲስ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰ ጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) ለገንዘቡ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ እነዚህን ፡ መያዣዎች ፡ ያላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዕዳ ፡ መከፈያው ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለዋስትናው ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ መልሶ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፭፬ ። ንብረቱን ፡ የሚገዛ ፡ የሦስተኛ ፡ ሰው ፡ አድራጎት ።**

ከባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ንብረቱን ፡ በገዛ ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበት ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ የተቀነሰ ፡ ወይም ፡ የተጎዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ፡ጠያቂ ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ባለፈው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ መብቶች ፡ ይኖሩታል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፸፩ ። ሌሎች ፡ ምክንያቶች ።**

ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ያለበት ፡ የዋጋ ፡ መቀነስ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያስቀንሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያስፈራ ፡ ጉዳይ ፡ ከባለዕዳው ፡ አዲስ ፡ ዋስትናዎችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ ዕዳ ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ለባለ ገንዘቡ ፡ መብት ፡ አይሰጠውም ።

## (ለ) ቀደምትነት ፡ ያላቸው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፸፪ ። የተመዘገበ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ዋና ፡ ገንዘብ፡ (ካፒታል)።**

በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገበውን ፡ ገንዘ ቡን ፡ ከሌሎች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በፊት ፡ በቀደምትነት ፡ እንዲከፈለው ፡ የማ ይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ መድን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፸፫ ። የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ።**

(፩) እንዲሁም ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ በተመዘገበው ፡ የወለድ ፡ መጠን ፡ የዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ከሌሎች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አስቀድሞ ፡ ለመክፈል ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ መድን ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያገ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ መሠረት ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ወለዱ ፡ በቀደምትነት ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፫) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ በሚመዘገብበት ፡ ጊዜ ፡ ወለዱ ፡ በቀደምትነት ፡ የሚከፈልበት ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ሊጻፍ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፸፬ ። አስፈላጊ ፡ ወጪዎችና ፡ ለአሹራንስ ፡ የሚከፈል ፡ ዋጋ ።**

እንዲሁም ፡ ባለዕዳው ፡ ሊከፍላቸው ፡ የሚገባ ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ለማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ጥበቃ ፡ ያደረጋቸውን ፡ አስፈላጊ ፡ ወጪዎችና ፡ ለንብረቱ ፡ አሹራንስ ፡ የከፈላቸውን ፡ ዋጋዎች ፡ ከሌሎቹ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በፊት ፡ በቀደምትነት ፡ ለመክፈል ፡ ያው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መድኑ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፸፭ ። በፍርድ ፡ ለማሲያዝ ፡ የሚደረጉ ፡ የተለመዱ ፡ ወጪዎች ።**

እንዲሁም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ በፍ ርድ ፡ ለማሲያዝ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ወጪዎች ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ በፊት ፡ በቀ ደምትነት ፡ ለመክፈል ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መድኑ ፡ ነው ።

BACK



ቍ ፡ ፫ሺ፹ ። ሕጋዊ ፡ ወለድ ።

(፩) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ አራት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ገንዘቦች ፤ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ከተያዘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ወለድን ፡ ይሰጣሉ ።

(፪) በመያዣ ፡ የተሰጠ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ተይዞ ፡ ሐራጅ ፡ እስከ ፡ ተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ለሚታሰበው ፡ የወለድ ፡ ገንዘብ ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መድኑ ፡ ነው ።

(ሐ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ያስመዘገቡ ፡ ብዙዎች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፩ ። መሠረቱ ።

(፩) ባንድ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ አስመዝግበው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀደምትነት ፡ መብታቸውን ፡ የሚሠሩበት ፡ ተራ ፡ የሚወሰነው ፡ መብታቸውን ፡ ያስመዘገቡበትን ፡ ቀን ፡ በመከተል ፡ ነው ።

(፪) የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብታቸው ፡ እርግጠኛ ፡ የሆነበት ፡ ወይም ፡ እንዲከፈል ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚቻልበት ፡ ቀን ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፪ ። ባንድ ፡ ቀን ፡ የተመዘገቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

ባንድ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በየመጠናቸው ፡ ይከፋፈላሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፫ ። ስለ ፡ መተካት ።

(፩) ማናቸውም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ቀደምትነት ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ አስፈቅዶ ፡ የቀደምትነቱን ፡ ተራ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ። በተራ ፡ ተከታይ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ባደረገው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ እንዲያዝ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ተራ ፡ የነበረውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ማስፈቀድ ፡ አስፈላጊው ፡ አይደለም ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በቀደምትነት ፡ ተራ ፡ የሚተካው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የቀደምትነት ፡ ተራ ፡ ይኖረዋል ።

## ፪ ፡ የመከታተል ፡ መብት ።

### (ሀ) ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፬ ። የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ የመሸጥ ፡ የመለወጥ ፡ መብት ።

(፩) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፡ ይኸንኑ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፡ ለመለወጥ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፭ ። በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ስላለመሆኑ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ባለገንዘብ ፡ የንብረቱ ፡ የመሸጥ ፡ መለወጡ ፡ ጽሑፍ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገቦች ፡ ከመጻፉ ፡ በፊት ፡ የመያዣ ፡ መብቱን ፡ አስመዝግቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱን ፡ ከገዢው ፡ እጅ ፡ በፍርድ ፡ ሊያስዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፮ ። በፊተኛው ፡ ባለዕዳ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ውጤት ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበት ፡ ንብረት ፡ መሸጥ ፡ መለወጥ ፡ በጠቅላላው ፡ በፊተኛው ፡ ባለዕዳ ፡ ግዴታ ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ መለዋወጥ ፡ አያመጣም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ገዢው ፡ ዕዳውን ፡ እከፍላለሁ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለገንዘቡ፡ በፊተኛው ፡ ባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ የማይተው ፡ መሆኑን ፡ በጽሑፍ ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር ፡ የቀድሞው ፡ ባለዕዳ ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

(፫) የተደረገው ፡ የመሸጥ ፡ የመለወጥ ፡ ስምምነት ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ እንዲያውቀው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ መግለጫው ፡ ካልተላከ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፯ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የማይከፋፈል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የማይከፋፈል ፡ ነው ።

(፪) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ከተሰጠበት ፡ ንብረት ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ የተሸጠ ፡ የተለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ የተከፋፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የንብረቱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ መያዣ ፡ ለተሰጠበት ፡ ሙሉ ፡ ዕዳ ፡ መክፈያ ፡ መሆኑ ፡ አይቀርለትም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፰ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ግዙፍ ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ።

(፩) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የሰጠ ፡ በዚሁ ፡ ንብረቱ ፡ ላይ ፡ በአላባ ፡ የመጠቀም ፤ የንብረት ፡ አገልግሎት ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣዎች ፡ ወይም፡ሌሎች ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ ሊያቋቁም ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፹፱ ። በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ስለ ፡ አለመሆኑ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መብቱን ፡ ካስመዘገበበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ የተመዘገቡ ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑበት ፡ አይችሉም ።

(፪) እነዚህን ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ እንዳልተቋቋሙ ፡ አድርጎ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ሊያሸጥ ፡ ይችላል ።

(፫) ባለግዙፍ ፡ መብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ እንዲያዝ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሱ ፡ በኋላ ፡ መብታቸውን ፡ ካስመዘገቡት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ካላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በፊት ፡ በቀደምትነት ፡ የመብቱ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፡፡

## (ለ) ገዥ ፡ የሆነ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሁኔታ ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፺ ፡፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ስለ ፡ መያዝ ፡፡ (፩) እንደ ፡ ዋስ ፡ ስለ ፡ መቈጠር ፡፡**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ ከተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ጋራ ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ዋስ ፡ በተሰጡት ፡ መብቶች ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፺፩ ፡፡ (፪) ቤቶችን ፡ ስለ ፡ ማሻሻል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡፡**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ በማሻሻል ፡ ተክል ፡ ወይም ፡ ሰብል ፡ በማድረግ ፡ የዚህን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ እንዲጨመር ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሽያጩን ፡ ጽሑፍ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ካስመዘገበበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደረገውን ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ ከንብረቱ ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ እንዲቀንስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፡፡

(፪) ገዢው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ከመግዛቱ ፡ በፊት ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ የንብረት ፡ አገልግሎትና ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሊሠራባቸው ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደርጉለታል ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፺፪ ፡፡ (፫) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡፡**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ፡፡

(፪) ለዚህ ፡ መጥፋትና ፡ ለዚህ ፡ መበላሸት ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ በሱ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይኸውም ፡ የሆነው ፡ ንብረቱን ፡ በፍርድ ፡ የማስያዝ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የተጀመረና ፡ ማስታወቂያ ፡ የተላከበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፺፫ ፡፡ (፬) አላባ ፡፡**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ በፍርድ ፡ ከመያዙ ፡ በፊት ፡ ከንብረቱ ፡ ላገኘው ፡ አላባ ፡ መጠየቅ ፡ የለበትም ፡፡

BACK



(፪) ገዢው ፡ ንብረቱ ፡ ከእጁ ፡ እንዳለ ፡ በፍርድ ፡ ከተያዘበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የአ ላባው ፡ ባለሀብት ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፺፬ ። (፭) በመድኑ ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ የገዛ፡ (ያገኘ ፡ ) ሰው ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ ከእጁ ፡ ባለ፡ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ የተያዘበት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ንብረቱን ፡ ባስተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በመድንነቱ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ሊያ ቀርብበት ፡ ይችላል ።

(፪) ንብረቱን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ቢሆንም ፤ እንኳ ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ የማቅ ረብ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፫) በመሸጥ ፡ በመለወጥ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በጽሑፍ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ክሱ ፡ ሊወገድ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፺፭ ። (፮) መተካት ።

(፩) ከእጁ ፡ ንብረቱ ፡ የተያዘበት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መብቶች ፡ የሚተካ ፡ ይሆናል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ከባለዕዳው ፡ ወይም ፡ ከባለዕዳው ፡ ዋስ ፡ ላይ ፡ ለዕዳው ፡ መድን፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በገዙት ፡ በ፫ኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ፡ በተ ባለው ፡ መተካት ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፺፮ ። (፯) የትእዛዝ ፡ ባለአደራ ፡ ስለ ፡ መምረጥ ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት፡ የገዛ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ የመያዣ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠባቸውን ፡ ዕዳዎች ፡ እሱ ፡ ከራሱ ፡ ለመክፈል ፡ በማይገደድበት ፡ ጊዜ ፡ ንብረቱን ፡ በፍርድ ፡ ለማስያዝ ፡ ከሚደ ረገው ፡ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመያዙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚፈጸምበት ፡ አንድ ፡ ባለ አደራ ፡ ይመርጣል ፡ ወይም ፡ ዳኞቹ ፡ እንዲመርጡ ፡ ይጠይቃል ።

(፫) የትእዛዝ ፡ ባለአደራው ፤ የመያዙን ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ነዋሪ ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ መኖሪ ያውን ፡ መሰየም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፺፯ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ዎች ፡ ፈቅዶ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) የማይቀሳቀንስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበት ፡ ንብረትን ፡ ሀብትነት ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ተስማምቶ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ በዚሁ ፡ ባለገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡

በፍርድ ፡ እንዲያዝ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ባይስማማም ፡ ገንዘቡን ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ሊከፍለው ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መብትህ ፡ ተቀላቅሏል ፡ የማለት ፡ መቃወሚያ ፡ ሊቀርብበት ፡ ሳይቻል ፡ ገንዘቡ ፡ በተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ምትክ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፸፰ ። ከመያዣነት ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ። (፩) የሚቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ መያዣ ፡ የተሰጠባቸውን ፡ ዕዳዎች ፡ ለመክፈል ፡ የሚገደድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መያዣ ፡ የተሰጠባቸውን ፡ ዕዳዎች ፡ ከፍሎ ፡ ንብረቱን ፡ ነጻ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፸፱ ። (፪) ከመያዣነት ፡ ነጻ ፡ ለማድረግ ፡ ሐሳብ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ መያዣነቱን ፡ ነፃ ፡ ለማድረግ ፡ የሚፈልግ ፡ ንብረቱን ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ የመያዣ ፡ መብታቸውን ፡ ላስመዘገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችና ፡ እንዲሁም ፡ መብቱን ፡ ላስተላለፈለት ፡ ባለሀብት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ የተዘረዘረበትን ፡ ጽሑፍ ፡ ያስታውቃቸዋል ።

(ሀ) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ያገኘበትን ፡ የማስረጃ ፡ ጽሑፍ ፤ የማስረጃውን ፡ ጽሑፍ ፡ ያገኘበትን ፡ ቀንና ፡ ይህንኑም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ ያስመዘገበበትን ፡ ቀን ፤

(ለ) እርሱ ፡ ያገኘውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ትክክለኛነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ መግለጫ ፡ ቃል ፡ በተለይም ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ የሚገኝበት ፡ ቦታና ፡ በርስት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ቍጥር ፡ የሚያመለክት ፡ ( መግለጫ ) ፡ ቃል ፤

(ሐ) ንብረቱ ፡ የተገዛበትን ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ያገኘው ፡ በችሮታ ፡ ስም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዚህ ፡ ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚሰጠውን ፡ ግምት ፤

(መ) ይህንኑ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ግምት ፡ ለመክፈል ፡ የሚያቀርበውን ፡ ጥያቄ ፤

(ሠ) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ተሰጥተው ፡ የተመዘገቡትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብቶች ፡ ዝርዝር ፡ እንዲሁም ፡ የተመዘገቡትን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስም ፤ የገንዘባቸውን ፡ ልክና ፡ የተመዘገቡበትን ፡ ቀን ፤

(ረ) ይህ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ በሚያዝበት ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚቀመጥበት ፡ ስፍራ ፡ ይህን ፡ የተባለውን ፡ ንብረት ፡ ያገኘውን ፡ ሰው ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታ ።

BACK



**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻ ። (፫) ለመክፈል ፡ የሚቀርበው ፡ (ጥያቄ) ፡ ቃል ፡ የማይመለስ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ከመያዣነት ፡ ነጻ ፡ ለማድረግ ፡ ለመክፈል ፡ ቃል ፡ የሰጠውን ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ስሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ተገዳጅ ፡ ያደርገዋል ።

(፪) ጥያቄውን ፡ ካቀረበላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ለመመለስ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፩ ። (፬) የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ስለ ፡ መቀበል ።**

(፩) መያዣን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ በስሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ አንቀበለውም ፡ ሲሉ ፡ ያልመለሱት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥያቄው ፡ የቀረበላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ ይገመታሉ ፡ (ይቈጠራሉ) ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ንብረቱን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ለመክፈል ፡ ያቀረበውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ እንደ ፡ ተራቸው ፡ ይካፈሉታል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፪ ፡ (፭) መያዣን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ አለመቀበል ።**

(፩) አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፤ ባለሀብቱ ፡ መያዣን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ ያቀረበለትን ፡ ጥያቄ ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ይደረጋል ።

(፪) መያዣን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አንቀበልም ፡ የሚሉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሐራጅ ፡ ለማሸጥ ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ አስቀድመው ፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፫ ። (፮) በሐራጅ ፡ የመሸጥ ፡ ወጪ ።**

(፩) ይህን ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ለመክፈል ፡ ካቀረበው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በልጠ ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ በላይ ፡ ብልጫ ፡ በማድረግ ፡ ወሳጅ ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለሐራጅ ፡ የወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ንብረቱን ፡ ባገኘው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይታሰብበታል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፤ ኪሣራው ፡ መያዣውን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አንቀበልም ፡ ባሉት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይታሰባል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፱፻፬ ። (፯) መያዣን ፡ የማስለቀቅ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መቅረት ።**

የተባለው ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ የመያዣ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በተጀመረና ፡ ይኸውም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ መያዣ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተመዝግቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንብረቱን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ መያዣ ፡ የነበረውን ፡ መብት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ያለው ፡ መብቱ ፡ ይቀርበታል ።

**(ሐ) የንብረት ፡ ዋስትናን ፡ የሰጠ ፡ ሰውን ፡ ውል ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።**

**ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፭ ። የሕሊና ፡ ግምት ።**

ማንም ፡ ሰው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለሚከፍለው ፡ ዕዳ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሌሎቹ ፡ ንብረቶቹ ፡ ላይ ፡ ግዴታ ፡ ገብቷል ፡ ተብሎ ፡ አይገመትም ።

**ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፮ ። ንብረቱን ፡ አሲዞ ፡ ዋስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ ሁኔታ ።**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ የሁለቱ ፡ ቊጥሮች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ንብረት ፡ አሲዞ ፡ ዋስ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ይቈጠራል ።

**ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፯ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ።**

(፩) ግዙፍ ፡ ዋስትና ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበትን ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ እንዲቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዲጎዳ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ አዲስ ፡ ዋትስና ፡ እንዲሰጠው ፡ ግዙፍ ፡ ዋስትና ፡ ሰጥቶት ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበት ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ንብረቱን ፡ ግዙፍ ፡ ዋስትና ፡ አድርጎ ፡ ከሰጠው ፡ ሰው ፡ በገዛ ፡ ፫ኛ ፡ ወገን ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ የተቀነሰ ፡ ወይም ፡ የተጎዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ይኸውም ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

**ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፰ ። ሌሎች ፡ ልዩነቶች ።**

(፩) ንብረቱን ፡ አሲዞ ፡ ዋስ ፡ የሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ከእጁ ፡ የተያዘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቀድሞ ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ ባስተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ጥያቄ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

(፪) የመያዙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበትም ፡ ጊዜ ፡ ከነገሩ ፡ ውጭ ፡ ልሁን ፡ ብሎ ፡ ሊጠይቅ ፡ አይችልም ።

(፫) እንዲሁም ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ዕዳ ፡ ከፍሎ ፡ መያዣውን ፡ ለማስቀረት ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ መቅረት ።

**ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፱ ። መሠረቱ ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተመዘገበበት ፡ ጽሑፍ ፡ በተሰረዘ ፡ ጊዜ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) ያሰራረዙ ፡ አኳኋን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ርስት ፡ መዝገብ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ተደንግጓል ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፪፲ ። የመሰረዝ ፡ ምክንያቶች ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሰረዝ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) መያዣው ፡ የሚመለከተው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የመያዣውን ፡ መብት ፡ ይቅርብኝ ፡ ብሎ ፡ ሲተው ፤

(ሐ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ የተሰጠበት ፡ ንብረት ፡ በፍትሕ ፡ በሐራጅ ፡ ተሸጦ ፡ ዋጋው ፡ ለባለመብቶቹ ፡ የተከፈለ ፡ ሲሆን ፤

(መ) መያዣው ፡ እንዲለቀቅ ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ የቀረበውን ፡ ገንዘብ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ተቀብለው ፡ በባለመብቶቹ ፡ መካከል ፡ ገንዘቡን ፡ የተከፋፈሉ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፪፲፩ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣነት ፡ ስለሚሰጥ ፡ የአላባ ፡ መብት ።**

(፩) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የአላባው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ተቋቁሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አላባው ፡ በሚቀርበት ፡ ጊዜ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ባለጉዳይ ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በመጉዳት ፡ የአላባ ፡ ጥቅም / ተቀባዩ ፡ የአላባውን ፡ መብት ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ለመተው ፡ አይችልም ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፪፲፪ ። የመያዣውን ፡ መብት ፡ ይቅርብኝ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ መተው ።**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብትን ፡ የባለገንዘቡ ፡ ይቅርብኝ ፡ ብሎ ፡ መተው ፤ በተገለጸ ፡ ዐይነትና ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የመያዣውን ፡ መብት ፡ የባለገንዘቡ ፡ ይቅርብኝ ፡ ማለት ፡ የሚጠይቀውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ተወ ፡ አያስቈጥረውም ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፪፲፫ ። በባለመያዣ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ አጥፊነት ፡ ምክንያት ፡ መተካት ፡ ስለ ፡ ማይችል ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የሚመለከተው ፡ የባለዕዳው ፡ ያልሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሆኖ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ጥፋት ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ በዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መብቶች ፡ ለመተካት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፲፬ ፡፡ የመሰረዝ ፡ ምክንያት ፡፡**

(፩) በዳኞች ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ሊሰረዝ ፡ አይችልም ፡፡

(፪) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መብቱ ፡ እንዲሰረዝ ፡ መፍቀዱን ፡ በጽሑፍ ፡ ሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ መሰረዙን ፡ ማዘዝ ፡ አለባቸው ፡፡

(፫) ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፤ በማይገባ ፡ መሰረዝን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በአላፊነት ፡ የሚያስጠይቀው ፡ ይሆናል ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፲፭ ፡፡ የመሰረዙ ፡ ውጤቶች ፡፡**

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ መሰረዝ ፡ ከዚህ ፡ መብት ፡ በኋላ ፡ በተራ ፡ ለተመዘገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚጠቅም ፡ ይሆናል ፡፡

(፪) ባለሀብቱ ፡ በተሰረዘው ፡ መያዣ ፡ ቦታና ፡ ስፍራ ፡ አዲስ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ለማቋቋም ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፲፮ ፡፡ ያለ ፡ መብት ፡ የተደረገው ፡ መሰረዝ ፡፡**

(፩) በማይገባ ፡ የተደረገም ፡ ቢሆን ፤ የመያዣ ፡ መብት ፡ መሰረዝ ፤ በማናቸውም ፡ አንዳች ፡ ሁኔታ ፡ ሊሻር ፡ አይችልም ፡፡

(፪) በማይገባ ፡ የተሰረዘው ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ይጸፍና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተመዝግቦ ፡ የሚጸናውም ፡ ከዚሁ ፡ ከተመዘገበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ፡፡

(፫) በማይገባ ፡ በተፈጸመው ፡ መሰረዝ ፡ አላፊዎች ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ክስን ፡ የማቅረቡ ፡ መብቶች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ፡፡

## ክፍል ፡ ፬ ፡፡
## ስለ ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ « አንቲክሬዝ ፡፡ »

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፲፯ ፡፡ ትርጓሜ ፡፡**

ወለድ ፡ አግድ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ባለዕዳ ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ማረጋገጫ ፡ በማድረግ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ለማስረከብ ፡ የሚገደድበት ፡ ውል ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፲፰ ፡፡ የወለድ ፡ አግድ ፡ መቋቋም ፡፡ (፩) መሠረቱ ፡፡**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣን ፡ መቋቋም ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ ያሁኑ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚከተለው ፡ ቍጥር ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ፡፡

ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፲፱ ። (፪) ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ደንቦች ።

(፩) ወለድ ፡ አግድ ፡ በውል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊቋቋም ፡ አይችልም ።

(፪) ለአምጪው ፡ ወይም ፡ በትእዛዝ ፡ ለሚተላለፍ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ የወለድ ፡ አግድ ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ።

(፫) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሌጣ ፡ ርስት ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ ሊያቋቁም ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፳ ። በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ አከራይንና ፡ ተከራይን ፡ ወይም ፡ ገበሬን ፡ የሚያገናኙትን ፡ ነገሮች ፡ በሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተዋዋሉት ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ለአንደኛው ፡ ባላቸው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚመሩ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፳፩ ። የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

(፩) (የተባለውን) ፡ ወለድ ፡ አግዱን ፡ ያቋቋመው ፡ (የተዋዋለው) ፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ከተጨማሪዎቹ ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለሚይዘው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ለተመለከተው ፡ ሰው ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

(፪) የተባለው ፡ ማስረከብ ፤ ሳይፈጸም ፡ እስከ ፡ ቈየበት ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ወደ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወለድ ፡ አግዱ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፳፪ ። የንብረቱ ፡ ጕድለቶች ፡ መድንነት ።

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ ፡ የሚሰጥ ፡ ይሆናል ።

(፪) ንብረቱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ በንብረት ፡ በሚገኙት ፡ ጕድለቶች ፡ ምክንያት ፡ መድን ፡ እንዲሆን ፡ አይገደድም ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ ኀላፊነት ፡ የሚያገኘው ፡ ውሉ ፡ ሲደረግ ፡ እነዚህ ፡ ጕድለቶች ፡ መኖራቸውን ፡ እያወቀ ፡ ሳይገልጻቸው ፡ ቀርቶ ፡ እነዚህ ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ ጕድለቶች ፡ ይህን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እጅ ፡ ላደረገው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አብረውት ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ጤና ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአደጋ ፡ አሥጊነት ፡ ያላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፳፫ ። ስለ ፡ ማደስ ፡ ሥራ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ የማደስን ፡ ሥራ ፡ ለማድረግ ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፳፬ ። ስለ ፡ ዕዳው ፡ ወለድ ።

(፩) በወለድ ፡ አግድ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የያዘ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ንብረቱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለሰጠው ፡ ሰው ፡ አንዳች ፡ ኪራይ ፡ ወይም ፡ የርሻ ፡ ኪራይ ፡ አይከፍልም ።

(፪) በተባለው ፡ ንብረት ፡ መገልገሉና ፡ ከዚህ ፡ ንብረት ፡ የሚያገኛቸው ፡ ፍሬዎችና ፡ ጥቅሞች ፡ ለሚጠየቀው ፡ ለገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ናቸው ።

(፫) ከዚህ ፡ ከሚገለገልበትና ፡ ከሚጠቀምበት ፡ ነገር ፡ በላይ ፡ ወለድን ፡ የሚፈቅድለት ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፳፭ ። በኪራይ ፡ የተሰጡትን ፡ ቦታዎች ፡ ስለ ፡ ማደርጀት ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በኪራይ ፡ የተሰጡትን ፡ ቦታዎች ፡ ለማዘጋጀት ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፳፮ ። በወለድ ፡ አግድ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መሬት ።**

ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተሰጠው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መሬት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ መሬት ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጥ ፡ የማድረግ ፡ መሪነት ፡ ንብረቱ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፳፯ ። የመብት ፡ ማስተላለፍ ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ሳይፈቅድ ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ መብቱን ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፳፰ ። አንደኛው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ወለድ ፡ አግዱን ፡ ስለ ፡ መሰረዙ ።**

(፩) ወለድ ፡ አግድ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የወለድ ፡ አግድ ፡ መብቱን ፡ ለመተው ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የተባለው ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ የተ[illegible]በትን ፡ ግዴታ ፡ በመፈጸም ፡ ባለዕዳው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወለድ ፡ አግዱ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፳፱ ። ወለድ ፡ አግድ ፡ በተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂውና ፡ በሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነቶች ።**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ አመዘጋገብና ፡ የመያዣውንም ፡ ውጤቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ደንቦች ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ውልም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፴ ። የወለድ ፡ አግድ ፡ (የአንቲክሬዝ) ፡ መሰረዝ ።**

እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ መቅረትንና ፡ መሰረዝን ፡ የሚመለከቱት ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ደንቦች ፡ በወለድ ፡ አግድም ፡ ላይ ፤ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ።

## የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ (አድሚኒስትራሲዮኖች) ፡ የሚያደርጓቸው ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፩ ። የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ደንቦች ።**

(፩) መንግሥት ፤ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚዋዋሏቸው ፡ ውሎች ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላውና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ፡ የተሰጡት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ይጸኑባቸዋል ።

(፪) ውሉ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፤ የተባሉትን ፡ ደንቦች ፡ የሚያሟሉ ፡ ወይም ፡ በነሱ ፡ ፈንታ ፡ የሚተኩ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፪ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ።**

አንድ ፡ ውል ፡ እንዳስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፤

(ሀ) ሕግ ፡ ወይም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ቃል ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ውሉ ፡ ከሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘና ፡ ለሥራውም ፡ አፈጻጸም ፡ የተዋዋዩን ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ሥራ ፡ ተካፋይነት ፡ ሳይቋረጥ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ለጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ አስቸኳይ ፡ በመሆናቸው ፡ ብቻና ፡ የግል ፡ ሰዎች ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ የማይገኙ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ውለታዎች ፡ ያሉበት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፫ ። ደንቡ ፡ ባንዳንድ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ከሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ጥሪ ፡ የሚያደርጉ ፡ ወይም ፡ አክሲዮናቸውን ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ወረቀታቸውን ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሸጡ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ ውል ፡ በሚፈራረሙበት ፡ ጊዜ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ የተመደቡትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ፎርሞች ፡ እንዲከተሉ ፡ የአስተዳደረር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፩ ።
## ስለ ፡ ውሎች ፡ ሥርዐት ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።
### ፈቃድን ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፩ ። የመቀበሉ ፡ ፎርም ።**

(፩) በአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ደንብ ፡ የተመለከተ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ፡ በቀር ፤ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉን ፡ ተቀብሎታል ፡ የሚባለው ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ መቀበሉን ፡ ሲያስታውቅ ፡ ነው ።

(፪) የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ማጽደቅ ፡ ጕዳይ ፡ ዝም ፡ ማለቱ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ ውሉን ፡ እንደ ፡ አጸደቀው ፡ የሚያስገምት ፡ አይደለም ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች፡ አንድ፡ ውል ፡ ለማራዘም ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ውል ፡ ቃል ፡ ለመለወጥ ፡ በሚመለከቱት ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፪ ። ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ (፩) የውሎቹ ፡ አጻጻፍ ።**

ሥራዎች ፡ የሚፈጸሙባቸውን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ለዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ደብ ተሮችን ፡ (ከዬደሻርዥቲፕ) ፡ ጠቅላላ ፡ ውለታዎችንና ፡ ደንቦችን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ደብተሮችን ፤ አጠቃላይ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ ያሉባቸውን ፡ ደብተሮች ፤ ሥራው ፡ የሆነው ፡ እያንዳንዱ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሊያዘጋጃቸውና ፡ በሚኒስ ቴሩ ፡ ትእዛዝ ፡ ሥራዎቹ ፡ የሚፈጸሙት ፡ በነዚህ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ተብሎ ፡ ሊወሰን ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፫ ። (፪) ትርጓሜ ።**

(፩) ሥራዎቹ ፡ የሚፈጸሙባቸውን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለክት ፡ ለዐይነት ፡ የሆነው፡ ደብተር ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ መሪ ፡ እንዲሆን ፡ አስቀድሞና ፡ በጠቅላላ ፡ አኳኋን ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያዘጋጀው ፡ ነው ።

(፪) ጠቅላላ ፡ ውለታዎችን ፡ ደንቦችን ፡ የሚያመለክቱት ፡ ደብተሮች ፤ የአስተዳ ዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሚሰጣቸው ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ በአንዳንድ፡ ዐይነት ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑትን ፡ ደንቦች ፡ የሚወስኑ ፡ ናቸው ።

(፫) አጠቃላይ ፡ የሆኑትን ፡ ውሳኔዎች ፡ የያዙት ፡ ደብተሮች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ማቅረብን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጕዳዮች ፡ ላይ ፡ በቴክኒክ ፡ በኩል ፡ በውሎቹ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ደንቦች ፡ የሚ ወስኑ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፯ ። የደብተሮቹ ፡ ውጤት ። (፩) ውሉን ፡ ስለ ፡ መፈረም ።

(፩) ለውሉ ፡ አፈራረም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መከተል ፡ ስለ፡ አለበት ፡ ጕዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፤ ለሥራዎቹ ፡ ዕጩ ፡ የሆኑት ፡ የግል ፡ ሰዎችና ፡ በተለየም ፡ ሥራው ፡ በጨረታ ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ በጨረታው ፡ ተካፋይ ፡ የሆ ኑት ፡ ሰዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ውለታዎችንና ፡ ደንቦችን ፡ በሚመለከተው ፡ ደብ ተር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ደንብ ፡ ሊጠቅሱ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፰ ። (፪) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቃል ።

(፩) ሥራዎች ፡ የሚፈጸሙባቸውን ፡ አኳኋን፡ የሚያመለከተው ፡ ደብተር ፤ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ ውለታዎችና ፡ ደንቦች ፡ ያሉበት ፡ ደብተር ፡ አጠቃላይ ፡ የሆኑት ፡ ውሳኔዎች ፡ ያሉበት ፡ ደብተር ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሲደረግ ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡ የሚ መራ ፡ በግልጽ ፡ የተጻፈ ፡ ቃል ፡ ከሌለበት ፡ በቀር ፡ ስለ፡ውሉ ፡ አተረጓጐም ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ቃልና ፡ ስለ፡ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ በነዚህ ፡ ደብ ተሮች ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፪) ስለ ፡ አንድ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ሥራ ፡ ሥራዎቹ ፡ የሚፈጸሙባቸውን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለክተው ፡ ልዩ ፡ ደብተር ፡ የሌሎቹን ፡ ደብተሮች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ላይከተል ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፱ ። በደብተሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) የተዋዋዮቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የተወሰኑት ፡ ሥራ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚመለከተውን ፡ አንድ ፡ ደብተር ፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ ውለታዎ ችንና ፡ ደንቦችን ፡ ወይም ፡ አጠቃላይ ፡ ውሳኔዎች ፡ ያሉበትን ፡ ደብተር ፡ በመጥ ቀስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ በተፈረመበት ፡ ጊዜ ፡ ደብተሩ ፡ ተጽፎ ፡ የነበረበትን ፡ አኳኋን ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) የውሉ ፡ ስምምነት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የደብተሩ ፡ ቃል ፡ ቢለዋወጥ ፡ የተዋ ዋዮቹን ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚነካ ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፸ ። ለአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚፈቀድ ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ።

(፩) ለአንድ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የባጀት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚፈ ቅዱለት ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ በመፈቀዱ ፡ ብቻ ፡ ገንዘቡ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲ ውል ፡ ለማስደረግ ፡ ለግል ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ አይሰጣቸውም ።

(፪) ውሉን ፡ ለመፈራረም ፡ ፈቃድ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንዲያሠራ ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ውሉን ፡ እንዲፈራረም ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ሆኖ ፡ አይቈጠርም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፩ ። የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ ስላለው ፡ ነጻነት ።

(፩) አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ እንዲዋዋል ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ውሉን ፡ እንዲፈራረም ፡ አያስገድደውም ።

(፪) ውል ፡ እንዲዋዋል ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ የአስተዳደሩን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ እንዲችል ፡ ብቻ ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፪ ። ገንዘብ ፡ አለመኖር ።

ሥራዎቹን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ገንዘቦች ፡ ያልተሰጡት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የአስተተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተዋዋለው ፡ ውል ፡ የጸና ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፫ ። ለመዋዋል ፡ ያልተፈቀደለት ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ።

(፩) በአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ሳይቀበል ፡ ውሉን ፡ የፈረመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) የውሉ ፡ ዓላማ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በመሆኑ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ፈራሽነት ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ በሚመለከተው ፡ የውል ፡ መፍረስ ፡ ጕዳይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፬ ። ውሉን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ።

(፩) ውሉ ፡ እንዲረጋ ፡ ከተፈረመ ፡ በኋላ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዲያጸድቀው ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የማጽደቅ ፡ ተግባር ፡ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ድረስ ፡ ውሉ ፡ የመጨረሻ ፡ አስገዳጅነት ፡ ሊያገኝም ።

(፪) ውሉን ፡ የተዋዋለው ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ አሠራሮች ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፫) ይህን ፡ የውል ፡ ማጽደቂያ ፡ ፈቃድ ፡ የሚያሰናክል ፡ ወይም ፡ የሚያውክ ፡ አሠራር ፡ መፈጸም ፡ አይገባውም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፭ ። የዘገየ ፡ የውል ፡ ማጽደቅ ።

ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ የተዋዋለ ፡ ሰው ፡ ያደረገው ፡ ውል ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ በሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የማጽደቁ ፡ ነገር ፡ ያልተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለተ

ዋዋዩ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ማሲታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ ከውሉ ፡ ግዴታዎች ፡ ውጭ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፮ ። ውሉ ፡ ፍጸሜ ፡ ሳያገኝ ፡ ሲቀር ፡ የሚደርስ ፡ አላፊነት ።**

(፩) የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉን ፡ ሳይፈራረም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ በተደረገው ፡ ንግግር ፡ ባሳየው ፡ ሁኔታ ፡ ምክን ያት ፡ በአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጥፋት ፡ ተዋዋዩ ፡ ውሉ ፡ ይፈጸማል ፡ በማለት ፡ ላደረጋቸው ፡ ወጪዎች ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዳች ፡ ጥፋት ፡ ባያደርግም ፡ እንኳ ፡ ከተዋ ዋዩ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ድርድር፡ መሠረት ፡ ተዋዋዩ ፡ ለሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ ጥናት ፡ አድርጎ ፤ ፕላን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሥራ ውን ፡ ጀምሮ ፡ ወይም ፡ ወጪ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ሆነና ፡ ይኸንንም ፡ ኪሣራና ፡ ወጪ ፡ ያደረገው ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ በዚህም ፡ ወጪ ፡ የአ ስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተጠቅሞበት ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ በመክፈል ፡ ኪሣራውን ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
## የጨረታ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፯ ። ይህን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ማዋል ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ውሎች ፡ በጨረታ ፡ ሥርዐት ፡ ሊፈጸሙ ፡ ይቻላል ።

(፪) ሕጉ ፡ በእንደዚህ ያለ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያዝ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውሎቹ ፡ በጨረታ ፡ ካልተሰጡ ፡ ፈራሽ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፰ ። የጨረታ ፡ ማስታወቂያ ። (፩) መሠረቱ ።**

በጨረታ ፡ የሚፈጸመው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የውስጥ፡ ደንብ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ ባይኖርም ፡ ተገቢ ፡ ነው፡ ተብሎ ፡ በሚገመተው ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ ለሕዝብ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፱ ። (፪) በጨረታው ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚገለጸው ፡ ቃል ።**

የጨረታው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ነገሮች ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(ሀ) ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለክተውን ፡ ደብተር ፡ ለማ የት ፡ የሚቻልበትን ፡ ቦታ ፤

(ለ) ጨረታ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ባለሥልጣኖች ፤

(ሐ) ስለ ፡ ጨረታው ፡ መልስ ፡ የሚቀርብበትን ፡ ጊዜ ፤

(መ) ለጨረታው ፡ የተወሰነውን ፡ ስፍራ ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፤
(ሠ) ተጫራቾቹ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የዋስትና ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የዋስትና ፡ ማረጋገጫዎች ።

ቍ ። ፫ሺ፱፻፺ ። (፫) የጊዜ ፡ ውሳኔ ።

የሚያስቸኵል ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለጨረታው ፡ መልስ ፡ መስጫ ፡ ከተ ወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ የጨረታው ፡ ማስታወ ቂያ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲገለጽ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

ቍ ። ፫ሺ፱፻፺፩ ። የጨረታው ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

እንደ፡ገና ፡ በአዲስ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ የመጀመሪያው ፡ የጨረታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፤ ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለ ክተውን ፡ ደብተር ፡ መለዋወጥ ፡ አይቻልም ።

ቍ ። ፫ሺ፱፻፺፪ ። ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለክት ፡ ደብተር ።

(፩) ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚያመለክተው ፡ ደብተር ፡ ተጫራ ቾቹ ፡ ያለባቸውን ፡ የግዴታ ፡ ዝርዝር ፡ ገልጾ ፡ ያመለክታል ።
(፪) በዚህም ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የሚታየውን ፡ የተጫራቾቹን ፡ የቴክኒክና፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ችሎታ ፡ ይወስናል ።
(፫) አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ባንድ ፡ ጨረታ ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ማቅ ረብ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የማስረጃ ፡ ዐይነትና ፡ እንዲሁም ፡ የቀረቡት ፡ የሥራ ፡ ዐቅድ ፡ (ፕላኖች) ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ዐይነቶች ፡ ተገቢ ፡ አይደሉም ፡ ተብለው ፡ አቅራቢያዎቹ ፡ ከውድድሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚወገዱበትን ፡ ሁኔታ ፡ ገልጾ ፡ ይወስናል ።

ቍ ። ፫ሺ፱፻፺፫ ። መቅረብ ፡ የሚገባቸው ፡ አስረጅ ፡ ጽሑፎች ።

በጨረታው ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ የሚፈቅዱት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮች ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢዎች ፡ አስቀድሞ ፡ በተዘጋጀው ፡ ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ በሚገልጸው ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ስፍራና ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ በጨረታው ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆናቸውንና ፡ የሚሰጡትን ፡ መልስ ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ።

ቍ ። ፫ሺ፱፻፺፬ ። የጨረታ ፡ ዋጋ ፡ ለማቅረብ ፡ አሳብ ፡ አለኝ ፡ ሲባል ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታ ወቂያ ።

(፩) በጨረታው ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ሐሳብ ፡ መኖሩን ፡ የሚያመለክተው ፡ ማስ ታወቂያ ፡ የዕጩውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ የግል ፡ ስም ፡ ሥራውንና ፡ መኖ ሪያ ፡ ቦታውን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

BACK



(፪) ይህ ፡ መግለጫ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ማስረጃዎችና ፡ ሥራው ፡ የሚፈጸምበ ትን ፡ አኳኋን ፡ በሚያመለክተው ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ መቅረብ ፡ አስፈላጊው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ደንበኛ ፡ ከሆነ ፡ የዋስትና ፡ ጽሑፍ ፡ ጋራ ፡ መቅ ረብ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፶፭ ። የጨረታው ፡ አቀራረብ ።</u>

(፩) <u>በጨረታ ፡ ማቅረቢያው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚመለከተው ፡ ነገርና ፡ ፎርም ።</u>

(፩) የጨረታው ፡ ማቅረቢያ ፡ ጽሑፍ ፡ ዕጩው ፡ ያቀረበውን ፡ ዋጋና ፡ የሚገባ በትን ፡ ግዴታ ፡ ገልጸ ፡ ያመለክታል ።

(፪) የሚቀርበውም ፡ ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋን ፡ በሚያመለክተው ፡ ደብ ተር ፡ ላይ ፡ ተገልጸ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ በተዘጋና ፡ በታሸገ ፡ አምቦሎፕ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፶፮ ። የቀረበውን ፡ ጨረታ ፡ የመፈጸም ፡ ግዴታ ።</u>

(፩) የጨረታው ፡ ውጤት ፡ እስከ ፡ ተነገረ ፡ ድረስ ፡ ለጨረታ ፡ የቀረበው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ያቀረበውን ፡ የጨረታ ፡ ውድድር ፡ ትቻለሁ ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ ለመለዋወጥ ፡ አይችልም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ለጨረታ ፡ ባቀረበው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሚገደድበትን ፡ የጊዜ ፡ ልክ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፶፯ ። የጨረታ ፡ ክፍል ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።</u>

የጨረታ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚቋቋመው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የአስተዳዳር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በተሰጠው ፡ የውስጥ ፡ ደንብና ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፶፰ ። ጨረታውን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።</u>

የጨረታው ፡ ሥራ ፡ የሚፈጸመው ፡ በግልጽ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፶፱ ። ተጫራቾችን ፡ ስለ ፡ መቀበል ። (፩) የጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ።</u>

(፩) የጨረታው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ተጫራቾቹ ፡ የሥራው ፡ ተካ ፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚሰጡትን ፡ መግለጫ ፡ ይመለከታል ።

(፪) የጨረታው ፡ መግለጫ ፡ በሚገባ ፡ የቀረበ ፡ መሆኑንና ፡ ተጫራቾቹም ፡ ለጨረታው ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚያበቃቸው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ሁኔታ ዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ ሁሉ ፡ ያሏቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ይመረምራል ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፷ ። የመምረጥ ፡ ሥልጣን ።</u>

(፩) ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ከተጫራቾቹ ፡ ወይም ፡ ከዕቃ ፡ አቅራቢዎቹ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ ወይም ፡ በሞያ ፡ ሥራቸውም ፡ ረገድ ፡ የሚፈለጉት ፡ መድኖች ፡ ያሏቸ ውን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይቀበላቸውም ።

(፪) ሥራዎቹ ፡ የሚፈጸሙባቸውን ፡ አኳኋን ፡ በሚያመለክተው ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የማይቀበላቸውን ፡ ተጫራቾች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ሊሰማቸው ፡ አይገደድም ።

(፫) ውሳኔውንም ፡ የሰጠበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዲገልጽ ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፩ ። የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመለወጥ ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

የጨረታውን ፡ መልስ ፡ የያዙ ፡ አምቦሎፖች ፡ ከተከፈቱ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በጨረታው ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ የተፈቀደበትን ፡ ውሳኔ ፡ ለመለወጥ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፪ ። የጨረታ ፡ ማቅረቢያ ፡ ወረቀት ፡ ንባብ ።**

(፩) የጨረታውን ፡ መልስ ፡ የያዙት ፡ አምቦሎፖች ፡ የሚከፈቱት ፡ ሕዝብ ፡ ባለበት ፡ ነው ።

(፪) የሚነበበውም ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፫ ። የጨረታ ፡ ፕሮሴቬርባል ።**

የጨረታው ፡ ውጤት ፡ የዚሁኑ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ጠቅላላ ፡ ሥርዐት ፡ በሚገልጽ ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ (ፕሮሴቬርባል) ፡ ይጻፋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፬ ። ለጊዜው ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ተጫራች ፡ ስለ ፡ መምረጥ ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) የጨረታ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከተጫራቾቹ ፡ መካከል ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ይበልጥ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ ያቀረበውን ፡ ለጊዜው ፡ የጨረታው ፡ አሸናፊ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያስታውቃል ።

(፪) ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ ዋጋና ፡ ሥራው ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሁኔታ ፡ በሚገልጸው ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ መፈጸሙን ፡ ይመለከታል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፭ ። (፪) ማስታወቁን ፡ ስለ ፡ ማዘግየት ።**

(፩) በጨረታው ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከአንድ ፡ ከተወሰነ ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ ሊዋዋል ፡ አይፈልግም ፡ ተብሎ ፡ ተነግሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ለጊዜው ፡ የጨረታው ፡ አሸናፊ ፡ ነው ፡ የሚባለውን ፡ ሰው ፡ ላያስታውቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ የተወሰነ ፡ ዋጋም ፡ ተጫራቾቹ ፡ እንዲያውቁት ፡ አይደረግም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፮ ። (፫) የብዙ ፡ ዋጋ ፡ አቀራረብ ፡ እኩልነት ።**

(፩) ከተጫራቾቹ ፡ መካከል ፡ ብዙዎቹ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ አቅርበው ፡ እንደሆነና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱም ፡ ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ ለመምረጥ ፡ የማይቻለው ፡

የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጨረታው ፡ ደንብ ፡ ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ በዕጣ ፡ የደረሰው ፡ የሥራውን ፡ ውል ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሊኖርበት ፡ ይችላል ።

(፪) በደንቡ ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ድንጋጌ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ ጨረታ ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፯ ። (፬) ውጤቱ ።

(፩) አሸናፊ ፡ የሆነውን ፡ ተጫራች ፡ ለጊዜው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ቢመርጥ ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ አያስቈጥረውም ።

(፪) አሸናፊውን ፡ ተጫራች ፡ ለጊዜው ፡ መምረጥ ፡ ውሉን ፡ ለመፈራረም ፡ የሚችለውን ፡ ተጫራች ፡ የማመልከት ፡ ውጤት ፡ ብቻ ፡ ይኖረዋል ።

(፫) እንዲሁም ፡ ያንዱ ፡ ተጫራች ፡ መመረጥ ፡ የጨረታ ፡ ዋጋ ፡ አቅርበው ፡ የነበሩትን ፡ ሌሎቹን ፡ ተጫራቾች ፡ ከግዴታቸው ፡ ውጭ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፰ ። ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚያደርገው ፡ ማጽደቅ ።

(፩) የጨረታውን ፡ ሥርዐት ፡ ያስፈጸመው ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የጨረታውን ፡ ውጤት ፡ ለማጽናት ፡ ወይም ፡ ላለማጽናት ፡ ሙሉ ፡ ነጻነት ፡ አለው ።

(፪) ውሉም ፡ ተፈጸመ ፡ የሚባለው ፡ ይህ ፡ ማጽደቅ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፱ ። ስምምነት ።

(፩) በጨረታ ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየተስማሙ ፡ በጨረታው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ስምምነት ፡ ሊያደርጉበት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ የውሉ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ በማድረግ ፡ ስምምነት ፡ በየጊዜው ፡ ለመታደስ ፡ ወይም ፡ ቀኑን ፡ ለማራዘም ፡ ይቻላል ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## የውል ፡ ምክንያት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹ ። ምክንያት ፡ የሌለው ፡ ውል ።

የውሉ ፡ ስምምነት ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ለውል ፡ ሰጪው ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ወደ ፡ ታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ የሚያስችለው ፡ ምክንያት ፡ ሊያገኝ ፡ የማይችል ፡ መሆኑንና ፡ አድሚኒስትራሲዮኑ ፡ ያሰበውን ፡ ውጤት ፡ ለማስገኘት ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ይህንኑም ፡ ተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ የሚያውቀው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የተገለጸ ፡ ሲሆን ፡ ውሉ ፡ አንዳችም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፩ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ ምክንያት ።

፩) ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የውሉን ፡ ስምምነት ፡ ያደረገው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ለሆነ ፡ ግብ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ለሆነው ፡ ምክንያት ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

BACK



(፪) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ውል ፡ ያደረገው ፡ ለጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ ሳይሆን ፡ ለተዋዋዩ ፡ የግል ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅምን ፡ ለማስገኘት ፡ ታቅዶ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ውል ፡ ስለሚያስከትሰው ፡ ውጤት ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ውሎች ፡ ደንበኛ ፡ አፈጻጸም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፸፪ ። በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ሊመለከት ፡ የሚገባው ፡ ነገር ።**

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አድርገው ፡ ግዴታቸውን ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

(፪) በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የተመለከተውንም ፡ ነገር ፡ ትክክል ፡ አድርጎ ፡ በዘመኑ ፡ በሚሠራበት ፡ የጥበባዊ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ መሠረት ፡ አስደሳች ፡ በሆነ ፡ ዐይነትና ፡ ጥቅም ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ በተመደበው ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ መፈጸም ፡ ይገባቸዋል ።

(፫) እንዲሁም ፡ በትጋት ፡ በጥንቃቄ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፸፫ ። ግዴታዎች ፡ የሚፈጸሙበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ በስምምነቱ ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲችል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎችና ፡ መሥሪያዎች ፡ ለመግዛት ፡ ራሱ ፡ የፈለጋቸውን ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢዎች ፡ ለማምጣት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ግዴታዎቹን ፡ ለመፈጸም ፡ በራሱ ፡ አላፊነት ፡ ለሥራው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የዕለት ፡ ሠራተኞች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞችንም ፡ መርጦ ፡ ለመቅጠር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፸፬ ። ስለ ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ። (፩) መሠረቱ ።**

(፩) እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ግዴታዎቹን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) በውሉ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ በግልጽ ፡ የተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፻፸፭ ። (፪) ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መብት ።**

በውሉ ፡ ውስጥ ፡ በግዴታዎቹ ፡ አፈጻጸም ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ በሥራ ፡ ትእዛዝ ፡ ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሊወስን ፡ መብት ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ ካል

ተመለከተ ፡ በቀር ፡ ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በስምምነት ፡ ከተመለከተው ፡ የሥራ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ተዋዋዩን ፡ ሊያስገድደው ፡ አይችልም ።

**ቍ፡፫ሺ፩፻፸፯ ።የዋጋ ፡ አከፋፈል ።**

ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ በፊናንስ ፡ ሕግ ፡ በመንግሥት ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

**ቍ፡፫ሺ፩፻፸፰ ። ግዴታ ፡ አልተፈጸመም ፡ ማለትን ፡ መከራከሪያ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ አለመፈጸሙ ፡ ይህ፡ አድራጎት ፡ ውሉን ፡ ለመፈጸም ፡ እንዳይችል ፡ ካላደረገው ፡ በቀር ፡ ተዋዋዩ ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ አልፈጽምም ፡ ለማለት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆነው ፡ አይችልም ።

(፪) የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያስችለው ፡ ከሆነ ፡ ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያደረገውን ፡ የውለታ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ተዋዋዩ ፡ የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ ሊያቋርጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፸፱ ። ስለ ፡ ማቻቻል ።**

ተዋዋዩ ፡ ዕዳ ፡ ይቻቻልልኝ ፡ ብሎ ፡ ያስተዳደሩን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ይቻቻልልኝ ፡ የሚለው ፡ ዕዳ ፡ የቀረጥ ፡ ዕዳን ፡ የሚመለከት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ውሎች ፡ ምርመራ ።

### (ሀ) ላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በተለይ ፡ የተፈቀዱለት ፡ መጠቀሚያዎች ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፹። መሠረቱ ።**

ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውሉ ፡ በዝምታ ፡ የታለፈውንም ፡ ቢሆን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በሆነ ፡ አፈጻጸም ፡ በውሉ ፡ አንዳንድ ፡ መሻሻያዎች ፡ አድርጎ ፡ ተዋዋዩን ፡ ለማስገደድ ፡ ይቻለዋል ፤ ይህም ፡ አንድ ፡ አጋጣሚ ፡ የሆነ ፡ መለዋወጥ ፡ እኒሁ ፡ መሻሻያዎች ፡ ለሕዝባዊ ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸውን ፡ ባስረዳው ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፹፩ ። ውልን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

ተዋዋዩ ፡ ጥፋት ፡ ባይኖርበትም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉን ፡ ሊያፈርስ ፡ ይቻለዋል ። ይህም ፡ ውሉ ፡ ለሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅም ፡ ሳይሆን ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ ለፍላጎቱ ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፷፩ ። ስለ ፡ ኪሣራ ።**

(፩) ካስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ መሻ ሻል ፡ ወይም ፡ መሰረዝ ፡ ምክንያት ፡ በሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ኪሣራው ፡ ሲታሰብ ፡ ተዋዋዩ ፡ በውሉ ፡ ለማግኘት ፡ ያሰባቸውን ፡ ትርፎች ፡ ሁሉ ፡ መገመት ፡ ይገባል ።

(፫) ዳኞች ፡ ግን ፡ ለተዋዋዩ ፡ ስለ፡ቀሩበት ፡ ትርፎች ፡ የኪሣራውን ፡ ገንዘብ ፡ በማ ሳነስ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላሉ ። እንደዚህም ፡ የሚሆነው ፡ ውሉ ፡ እንዲሻሻል ፡ ወይም ፡ እንዲሰረዝ ፡ የተደረገው ፡ ውሉን ፡ በተዋዋለው ፡ ያስተዳደር ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤት ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ምክንያቶች ፡ መሆኑ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፷፪ ። በተዋዋዩ ፡ ጥያቄ ፡ ውልን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

(፩) ተዋዋዩ ፡ ባስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ የውሉን ፡ ጠቅ ላላ ፡ ገንዘብ ፡ ቁጠባ ፡ የሚለውጠው ፡ ወይም ፡ የሚገለባብጠው ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በውሉ ፡ ያደረገው ፡ ማሻሻል ፡ ብዛቱ ፡ ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ከታሰበው ፡ መብለጥ ፡ አለመብለጡን ፡ ማመዛዘን ፡ የሚችሉት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

(፫) ተዋዋዩ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚፈቅድለት ፡ አንቀጽ ፡ ካልኖረው ፡ በቀር ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይችልም ።

## (ለ) አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ ስለ ፡ መቅረት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፷፫ ። መሠረቱ ።**

(፩) ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይታሰቡ ፡ የቀሩት ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ዎች ፡ የውሉን ፡ ሚዛን ፡ ምናልባት ፡ ገለባብጠውት ፡ ቢገኙ ፡ ካስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ግዴታዎቹን ፡ የኒህም ፡ አፈጻ ጸም ፡ በመሣሪያ ፡ ረገድ ፡ የሚቻል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ግድ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነው ፡ ከወደቀበት ፡ ጉዳት ፡ የተ ዋዋለው ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በከፊል ፡ ችሎ ፡ እንዲረዳው ፡ ለመ ጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፯፻፷፬ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ መናወጥ ።**

የውሉ ፡ ሚዛን ፡ የሚናወጠው ፡ አዲስ ፡ የተፈጠሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ከአ ስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለውን ፡ ሰው ፡ ግዴታዎች ፡ ከፍ ፡ ሲያደርጉ

BACK



ትና ፡ ይኸም ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ሲዋዋሉ ፡ ከሰጡት ፡ አገማመት ፡ የመጨረሻ ፡ ወሰኑን ፡ ተላልፎ ፡ የበለጠ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፮ ። አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ ስለ፡መቅረት ።

(፩) አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ የቀረ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ ውሉን ፡ ሲዋዋሉ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ ለመገንዘብ ፡ ሳይቻላቸው ፡ የቀረው ፡ ነው ።

(፪) አንድ ፡ ሁኔታ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ የቀረ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊቈጠር ፡ የማይቻለው ፡ ለጥቅሙ ፡ ባደረገው ፡ ሰው ፡ አሠራር ፡ የሆነው ፡ ነው ።

(፫) አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ መቅረትን ፡ ለመጥቀስ፡ የሚቻለውም ፡ ባልታሰቡ ፡ ምክንያቶች ፡ ስለሚደርሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ ባልታሰበ ፡ የልክ ፡ መተላለፍና ፡ በውሉም ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ በተፈጸሙት ፡ ጕዳዮች ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፯ ። ዋጋዎችን ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማሻሻል ፡ የተደረጉ ፡ የውል ፡ ቃሎች ።

በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ዋጋዎችን ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ እንደ፡ገና ፡ ለመመርመርና፡ ለማሻሻል ፡ የሚፈቅድ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ሲኖሩ ፡ ኪሣራ ፡ ማግኘት ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ አያስቀርም ።

(ሀ) በጕዳዩ ፡ የተመለከተውን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሳይቻል ፡ ሲቀር ፤

(ለ) በውሉም ፡ ቃል ፡ አፈጻጸም ፡ ለምሳሌ ፤ በዋጋ ፡ መለዋወጥ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ፡ ከተመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ ውጭ ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ምክንያት ፡ በሚደርሰው ፡ የዋጋ ፡ መለዋወጥ ፡ የውሉን ፡ የቁጠባ ፡ ኤኮኖሚ ፡ መናወጥን ፡ ለማቃናት ፡ የማይበቃ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፰ ። የወጪ ፡ ብልጫ ፡ መኖር ፡ የሚያሻ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በጊዜው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምክንያት ፡ በተዋዋዩ ፡ ላይ ፡ የወጪ ፡ ብልጫ፡ ኪሣራ ፡ ሳይደርስበት ፡ ትርፎቹ ፡ በመቀነሳቸው ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ በማጣት ፡ ብቻ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፲፯፻፺፱ ። ስለ ፡ ኪሣራ፡ገንዘብ ።

(፩) የሚከፈለውም ፡ ኪሣራ ፡ በጊዜው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምክንያት ፡ ከደረሰው ፡ ጉዳት ፡ አንደኛውን ፡ ክፍል ፡ ተዋዋዩ ፡ ራሱ ፡ እንዲችል ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) በዚሁም ፡ ረገድ ፡ መገንዘብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ተዋዋዩ ፡ ችግሩን ፡ ለመወጣት ፡ ያደረገውን ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የሥራውን ፡ ድርጅት ፡ ጠቅላላ ፡ አኳኋኑን ፡ እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ ማናቸውንም ፡ ርትዕ ፡ የሆኑ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፹፱ ። አስቀድሞ ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ የሚቀርበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) አስቀድሞ ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ መቅረት ፡ የሚገባው ፡ የውሉ ፡ ሚዛን ፡ በተቃና ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) የውሉ ፡ ሚዛን ፡ መቃወስ ፡ ፍጹም ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ እያንዳንዱ ፡ ተዋዋይ ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያውቁለት ፡ ለዳኞች ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

(፫) ውሉ ፡ በስምምነት ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ ካልተቻለ ፡ ዳኞች ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ያደርጋሉ ።

## (ሐ) የመንግሥት ፡ ሥርዐት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፺ ። ጠቅላላ ፡ ጥንቃቄዎች ።

### (፩) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ ስለ ፡ መንካት ።

(፩) መንግሥት ፡ ያወጣቸው ፡ ሕጎች ፡ ደንቦች ፤ ትእዛዞችና ፡ እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ ጠቅላይ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ እነዚሁም ፡ ውሳኔዎች ፡ የውሉን ፡ ቃሎች ፡ በቀጥታ ፡ የሚለውጡ ፡ ወይም ፡ የውሉን ፡ አንዳንድ ፡ ቃሎች ፡ ለመፈጸም ፡ እክል ፡ የሚሆኑ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ እንዲቆም ፡ የሚያደርጉ ፡ ሲሆኑ ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደርጉለታል ።

(፪) በዚሁም ፡ ረገድ ፡ ጣልቃ ፡ የገባው ፡ ጠቅላይ ፡ የሆነው ፡ ውሳኔ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ አለመቻሉን ፡ ካልጠቀሰ ፡ በቀር ፡ ኪሣራውን ፡ ለመከልከል ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፩ ። (፪) የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ የሚያደርጉ ፡ ውሳኔዎች ።

(፩) መንግሥት ፡ በሚያወጣቸው ፡ ጠቅላይ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ የውሉ ፡ ቃሎች ፡ ሳይነኩ ፡ ያፈጻጸሙን ፡ አኳኋን ፡ ብቻ ፡ ቢለውጡ ፡ አፈጻጸሙንም ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪና ፡ ውድ ፡ ቢያደርጉትም ፡ ኪሣራ ፡ ሊገኝባቸው ፡ አይቻልም ።

(፪) ጣልቃ ፡ በገባው ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ለዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ኪሣራ ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራ ፡ ማግኘት ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፪ ። በተለይ ፡ የሆኑ ፡ ጥንቃቄዎች ። (፩) ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ ተዋዋይ ፡ ያደረጋቸው ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ።

(፩) ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ ተዋዋይ ፡ ያደረጋቸው ፡ በተለይ ፡ የሆኑ ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ፡ የውሉን ፡ ቃሎች ፡ የሚነኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አፈጻጸሙን ፡

BACK



ብቻ ፡ የሚያዳግቱ ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የሚያስወድዱ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ከአስተዳደር፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነውን ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ የሚገባው ፡ ያደርጉታል ።

(፪) የተደረጉት ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ግን ፡ ከወገኖቹ ፡ ውጭ ፡ የሆነውን ፡ ለማምለጥ ፡ የማይቻለውን ፡ የቁጠባ ፡ (የኤኮኖሚ) ፡ ሁኔታ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሲሆን ፤ እንዳ ችም ፡ ኪሣራ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይቻልም ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፫ ። (፪) በሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተደረጉ ፡ የጥንቃቄ ፡ ውሳኔዎች ።</u>

(፩) ጉዳት ፡ ያመጣውን ፡ ሥራ ፡ ፈጻሚው ፡ ተዋዋይ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ሳይሆን ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሲሆን ፤ እንዳችም ፡ ኪሣራ ፡ ሊከፈል ፡ አይገባም ።

(፪) ይህን ፡ የመሰለው ፡ ጕዳይም ፡ የሚፈጸመው ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ባለሥልጣን ፡ ኀላፊነት ፡ በተሠሩት ፡ ደንቦች፡ መሠረት ፡ ነው ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ውሎች ፡ ያለመፈጸም ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፬ ። ውልን ፡ በግድ ፡ ስለ ፡ ማስፈጸም ።</u>

(፩) ዳኞች ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግዴታውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ሊያ ስገድዱት ፡ አይችሉም ።

(፪) የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሳይወድ ፡ ቢቀር፡ ዳኞች ፡ ኪሣራ ፡ ለማስከፈል ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

(፫) ዳኞች ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያወጣቸውን ፡ መጠንቀቂያ ፡ ውሳኔ ዎች ፡ ራሱ ፡ ከተዋዋላቸው ፡ ግዴታዎች ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ ሲሆኑ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለመሰረዝ ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፭ ። በትእዛዝ ፡ የመውሰድ ፡ «ሬኪዚሲዮን» ፡ መብቶች ።</u>

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ራሱ ፡ ያደረገውን ፡ ውል ፡ «በሬኪዚሲዮን»፡ በትእዛዝ ፡ መብት ፡ ወስዶ ፡ ለማስፈጸም ፡ አይችልም ።

(፪) የሠራተኞችን ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ ለማስወገድ ፡ የመንግሥት ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ሠራተኞች ፡«በሬኪዚሲዮን»፡ ለመውሰድ ፡ ግን ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፮ ። ሳይከፈሉ፥ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ገንዘቦች ፡ ወለድ ።</u>

ሳይከፈል ፡ ለቀረው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገባው ፡ ወለድ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የመስጠት፡ አስፈላጊነት ፡ ሳይኖረው ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ መብት፡ ተፈላጊ ፡ የሚሆነው ፤

(ሀ) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውሉ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ከዐሥራ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ አከፋፈል ፡ የሚያስፈልገ ውን ፡ የማረጋገጥ ፡ ሥራ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፤

(ለ) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ የማረጋገጡ ፡ ሥራ ፡ በተፈጸመ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፺፯ ፡፡ ኀላፊነት ፡ እንዳይኖር ፡ የተደረገ ፡ የውል ፡ ቃል ፡፡**

ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሳይከፍለው ፡ ላቈየበት ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) ሳይከፈል ፡ የቈየበት ፡ ጊዜ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ውሉን ፡ ያደረገው ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለመጉዳት ፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ቸልተኛነትና ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ያደረገው ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፺፰ ፡፡ ስለ ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ ውድቅነት ፡፡**

(፩) አንድ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከተዋዋዩ ፡ ጋራ ፡ በመገናኘት ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ በሌላ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ መሠረት ፡ ንግግር ፡ ለማድረግ ፡ ቢጀምር ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ ውድቅ ፡ ስለሚሆን ፡ ማስጠንቀቂያውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማደስ ፡ ያስፈልገዋል ፡፡

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ሳያደርግ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቢያሳልፍ ፡ ወይም ፡ ከተዋዋዩ ፡ ጋራ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነትን ፡ ቢቀጥል ፡ በተዋዋዩ ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ መፈለጉን ፡ ትቷል ፡ የሚያሰኘውና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚያስገድደው ፡ አይሆንም ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፮፻፺፱ ፡፡ ስለ ፡ አቅራቢዎች ፡ መዘግየትና ፡ ጕድለት ፡፡**

(፩) አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነ ፡ በገዛ ፡ አቅራቢዎቹ ፡ መዘግየትና ፡ ጕድለት ፡ በሚደርሰው ፡ ጥፋት ፡ ሊከለከሉት ፡ በማይቻል ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለመከራከር ፡ አይችልም ፡፡

(፪) አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነ ፡ የገዛ ፡ አቅራቢዎቹ ፡ መዘግየትና ፡ ጕድለት ፡ ሊከለከሉት ፡ የማይቻል ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኀይል ፡ ተቈጥሮ ፡ ውሉን ፡ ባለመፈጸም ፡ ከሚደርስበት ፡ ኣላፊነት ፡ ሊያድነው ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፯፻ ፡፡ የቅድሚያ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ስላለመኖር ፡፡**

(፩) መሠረቱ ፡፡

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ተዋዋዩ ፡ ውሉን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ጥፋት ፡ አድርጓል ፡ በማለት ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ተዋዋዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ባለመ

BACK



ፈጸሙ ፡ ወይም ፡ ለመፈጸም ፡ በመዘግየቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈለግበትን ፡ ኪሣራ ፡ ልክ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ለመወሰን ፡ አይችልም ።

(፫) ዳኞች ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከመብቱ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ በተዋዋይ ፡ ላይ ፡ ባደረገው ፡ ውሳኔ ፡ (ቅጣት) ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፤ ይከፍለው ፡ ዘንድ ፡ ሊፈርዱበት ፡ ይችላሉ ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

## ውሎችን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መልቀቅና ፡ ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ስለ ፡ ተስማማ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፩ ። ትርጓሜ ።

(፩) ውሎችን ፡ ለሌላ ፡ መልቀቅ ፡ ማለት ፡ ተዋዋዩ ፡ ውሉን ፡ በሙሉ ፡ እንዲፈጽ ምለት ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለሆነ ፡ ሲያስተላልፍ ፡ ነው ።

(፪) ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ የተስማማ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ የሚባለውም ፡ ከተዋዋዩ ፡ ውሉን ፡ በከፊል ፡ ለማስፈጸም ፡ ካንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፪ ። የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ አስፈላጊነት ።

(፩) ተዋዋዩ ፡ ያደረጋቸው ፡ ውሎችን ፡ ለሌላ ፡ ለመልቀቅና ፡ ከሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ ጋራ ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ አስቀድሞ ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እንዲ ፈቀድ ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) ውልን ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ፡ ወይም ፡ ከሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ ጋራ ፡ የተ ደረገውን ፡ ውል ፡ ለመፍቀድ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ ውሉን ፡ ለመዋዋል ፡ የተፈቀደለት ፡ ባለሥል ጣን ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፫ ። የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ግዴታና ፡ ችሎታ ።

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ውልን ፡ ለሌላ ፡ ለመልቀቅ ፡ ወይም ፡ ለሁለ ተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ ለማድረግ ፡ ለሚቀርብለት ፡ የፈቃድ ፡ ጥያቄ ፡ መልሱን ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ውልን ፡ ለሌላ ፡ ለመልቀቅ ፡ ወይም ፡ የሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ ሆኖ ፡ የተዋዋ ለው ፡ የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የአ ስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ የታጨው ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ (በቴክኒካዊ ፡ ወይም) ፡ በገንዘብ ፡ ችሎታ ፡ ማነስ ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ ፈቃ ዱን ፡ ለመከልከል ፡ አይችልም ።

(፫) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በሌላ ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ ለሌላ ፡ ማሳለፍ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ ረገድ ፡ የመከልከል ፡ ወይም ፡ የመፍቀድ ፡ በተለይ ፡ የሆነ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፬ ። ቅጣት ።**

(፩) ሳይፈቀድለት ፡ የተደረገው ፡ ውልን ፡ ለሌላ ፡ መለቀቅ ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ የተስማማ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ አስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፪) እነዚህም ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ጥፋት ፡ ተቈጥረው ፡ በተዋዋዩ ፡ ጕድለት ፡ ውልን ፡ የሚያፈርሱ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፭ ። ፈቃዱ ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ። (፩) ለሌላ ፡ ስለ ፡ መልቀቅ ።**

(፩) ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ውልን ፡ ለሌላ ፡ ለመልቀቅ ፡ የሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ ውል ፡ በተሰጠው ፡ በቀድሞ ፡ ተዋዋይ ፡ ምትክ ፡ ያደርገዋል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ የቀድሞው ፡ ተዋዋይ ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ኀላፊነት ፡ ነጻ ፡ ነው ።

(፫) የቀድሞው ፡ ተዋዋይ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ዋስትና ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እጅ ፡ የሚቈየው ፡ በመካከላቸው ፡ ባሉት ፡ ክርክሮች ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፮ ። (፪) ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ የተስማማ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ።**

(፩) ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ለተስማማው ፡ ለሁለተኛው ፡ ተቋራጭ ፡ የሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፤ በተዋዋዩና ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የውል ፡ ማሰሪያ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ይቀጠዋል ።

(፪) የቀድሞው ፡ ተዋዋይ ፤ ሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ለፈጸማቸው ፡ ሥራዎችና ፡ ዕቃዎች ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ፈጸማቸው ፡ ተቈጥረው ፡ ኀላፊነት ፡ ይኖርበታል ።

(፫) ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ በመዘግየት ፡ ምክንያት ፡ ከሚወድቀው ፡ ቅጣት ፡ የመዘግየቱ ፡ ነገር ፡ በሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ጥፋት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞውን ፡ ተዋዋይ ፡ አይነካውም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ኮንሴሲዮን ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፯ ። ትርጓሜ ።**

(፩) አንድ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ የሚባለው ፡ መንግሥት ፡ ይኸን ፡ ሥራ ፡ የግል ፡ የሆነ ፡ ድርጅት ፡ በሚገባ ፡ ለማካሄድ ፡ የማይችለው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወስኖ ፡ በጠቅላላ ፡ ለሕዝቡ ፡ አስፈላጊነት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ራሱ ፡ የሚያካሂደው ፡ ነው ።

(፪) የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ የሚባለውም ፡ አንድ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ የሚከፈለውን ፡ ከሚገለገሉበት ፡ ሰዎች ፡ በመቀበል ፡ ለማካሄድ ፡ ካንድ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ ውል ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፰ ። የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የመቈጣጠር ፡ መብት ። (፩) መሠረቱ ።

(፩) የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ በደኅና ፡ እንዲካሄድ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉ ፡ በሚፈጸምበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለመቈጣጠር ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ ለሰጠው ፡ የሥራውን ፡ ሁኔታ ፡ ገልጾ ፡ ማስረዳትና ፡ እንዲሁም ፡ መቈጣጠሩን ፡ እንዲፈጽም ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፱ ። (፪) በደንብ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

(፩) ባለኮንሴሲዮኑን ፡ ለመቈጣጠር ፡ የሚፈጸመው ፡ አሠራር ፡ በደንብ ፡ በተደነገጉትና ፡ ተዋዋዮቹም ፡ በተስማሙባቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በታች ፡ ባሉት ፡ ቊጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ተፈጻሚ ፡ ናቸው ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲ ። (፫) የመቈጣጠሩ ፡ ወሰን ።

(፩) የኮንሴሲዮኑ ፡ መቈጣጠር ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ አበላሽቶ ፡ ሥራው ፡ በአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በቀጥታ ፡ እንደሚመራ ፡ አድርጎ ፡ የሚለውጠው ፡ እንዳይሆን ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ አንዱን ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ በሙሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እያስፈቀደ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻለውም ።

(፫) በውል ፡ የተወሰነው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ውሉን ፡ የሚፈጽምበትን ፡ አኳኋን ፡ በነጻነት ፡ ራሱ ፡ ይመርጣል ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲፩ ። (፬) ስለ ፡ ውሉ ፡ አተረጓጐም ።

(፩) የውሉን ፡ ቃሎች ፡ ለኮንሴሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ መቈጣጠርም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሥርዐት ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃም ፡ ሆነ ፡ አዲስ ፡ ለሆኑት ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ፡ አሰናካይ ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርጎ ፡ በፍጹም ፡ ትርጕም ፡ ሊሰጣቸው ፡ አይቻልም ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የአስተዳደሩ ፡ ባለሥልጣን ፡ ከተዋዋዩ ፡ ጋራ ፡ በውል ፡ የተስማማባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመለወጥም ፡ ሆነ ፡ ለመቈጣጠር ፡ በፖሊስ ፡ ደንቦች ፡ ኀይል ፡ መሠረት ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲፪ ። ዋጋዎችንና ፡ የዋጋ፡ልክ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ በውል ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) መሠረቱ ።

በኮንሴሲዮኑ ፡ ውስጥ ፡ በውሉ ፡ የተመለከቱት ፡ ዋጋዎችና ፡ የዋጋ ፡ ልክ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በቁጠባ ፡ ረገድ ፡ መለዋወጥ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ሊለወጡ ፡ ይቻላል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በውል ፡ ውስጥ ፡ ሊገባ ፡ ይቻላል ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲፫ ። (፪) የመለዋወጥ ፡ የውል ፡ ቃሎች ።

(፩) በያንዳንድ ፡ ዕቃዎች ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ በሚደርስባቸው ፡ የዋጋ ፡ መለዋወጥ፡ መጠን ፡ ዋጋዎቹ ፡ ዐውቀው ፡ ወዲያውኑ ፡ ተለውጠው ፡ በሥራ ፡ ላይ፡ ይውላሉ ፡ ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ውስጥ ፡ ሊወሰን ፡ ይቻላል ።

(፪) ያዲሶች ፡ ዋጋዎች ፡ ወይም ፡ የዋጋ ፡ ልክ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ አወሳሰን ፡ ባንድ ፡ የመለዋወጥ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ዐውቆ ፡ ተለዋጭ ፡ ሲሆን ፡ ክርክርም፡ ቢነሣ ፡ በዚሁ ፡ በተጠቀሰው ፡ የመለዋወጥ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ዳኞች፡ አዲሶችን ፡ ዋጋዎችና ፡ የዋጋ ፡ ልክ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ይወስናሉ ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲፬ ። (፫) የማሻሻያ ፡ የውል ፡ ቃል ።

(፩) በውሉ ፡ በቁጠባው ፡ ሁኔታዎች ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መለዋወጥ ፡ በደረሰ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ዋጋዎችና ፡ የዋጋ ፡ ልክ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ማሻሻል ፡ መሠረቱን፡ ጉልህ ፡ አድርጎ ፡ ሳይገልጽ ፡ መሻሻል ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሊጻፍ፡ ይቻላል ።

(፪) እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ተከራክረው ፡ ለውሉ ፡ አንድ ፡ የስምምነት ፡ ተጨማሪ ፡ ማድረግ ፡ ግድ ፡ ይኖርባቸዋል ።

(፫) ተዋዋዮቹ ፡ ሳይስማሙ ፡ ቢቀሩ ፡ ግን ፡ ዳኞች ፡ ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ ርትዕ ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ መቀበያ ፡ የሚሆነው ፡ አንድ ፡ የዋጋ ፡ ልክ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወስነው ፡ ማውጣት ፡ አለባቸው ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲፭ ። (፬) ስለ ፡ ውል ፡ ቃሎቹ ፡ የጊዜ ፡ አፈጻጸም ።

(፩) በውሉ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ ተዋዋዩ ፡ ሥራውን ፡ ከተቀበለበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የዋጋዎችን ፡ መለዋወጥና ፡ የማሻሻያ ፡ የውሎችን ፡ ቃል ፡ ለመጥቀስ ፡ ይችላል ።

(፪) ተዋዋዩ ፡ እነዚህኑ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ በውሉ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ ከተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ከመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የተጨመረለት ፡ ጊዜ ፡ ካልኖረው ፡ በቀር ፡ ለመጥቀስ ፡ አይችልም ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፲፮ ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ስለሚደረግ ፡ የውል፡መለዋወጥ ።

(፩) መሠረቱ ።

(፩) ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ የሆነው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉ ፡ በሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ አገልግሎት ፡

BACK



ሥራ ፡ መሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማንኛዎችንም ፡ ግዴታዎች ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ ላይ ፡ ሊጥልበት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ የሥራውን ፡ አኳኋን ፡ በሚያመለክተው ፡ በግዴታዎቹ ፡ ደብተር ፡ የተመለከተውን ፡ ያገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ እንዲለውጥ ፡ ባለኮንሴሲዮኑን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) ማናቸውም ፡ ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

<u>ቍ፡ ፫ሺ፪፻፲፯ ። (፪) ለመለዋወጥ ፡ የሚቻሉ ፡ የስምምነት ፡ ቃሎች ።</u>

(፩) ለመለዋወጥ ፡ የሚቻሉት ፡ አገልግሎት ፡ ሥራንና ፡ አፈጻጸሙን ፡ የሚመለከቱ ፡ ቃሎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ማቅረብ ፡ የሚገባውን ፡ ሀብት ፡ ብዛት ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ያገልግሎት ፡ ሥራውን ፡ እንዲያስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፲፰ ። (፫) ስለ ፡ መለዋወጡ ፡ ወሰኖች ።</u>

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የአገልግሎት ፡ ሥራን ፡ ድርጅት ፡ ዐይነቱን ፡ ወይም ፡ ውሉን ፡ ፍጹም ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ የሚሰጥ ፡ መለዋወጥ ፡ እንዲደረግ ፡ ለማስገደድ ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ በመንግሥት ፡ መሪነት ፡ በሚሠራ ፡ ሥራ ፡ አስተዳደር ፡ ዐይነት ፡ ለማስተዳደር ፡ አይችልም ።

(፫) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ከተሰጠው ፡ ያገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ጭራሹን ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ከችሎታው ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ለማሠራት ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፲፱ ። (፬) ለመለወጥ ፡ የማይቻሉ ፡ የስምምነት ፡ ቃሎች ።</u>

(፩) የኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ የሚያስገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ሁሉ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በበኩሉ ፡ ለብቻ ፡ ለመለዋወጥ ፡ አይቻለውም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ የተሰጠውን ፡ የብቻነት ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ ለመንካትም ፡ አይችልም ።

(፫) የኮንሴሲዮኑ ፡ ሰጭ ፡ በበኩሉ ፡ ለብቻው ፡ የዋጋዎቹን ፡ ማስታወቂያ ፡ በመለወጥ ፡ ሊያስገድደው ፡ ይችላል ። ግን ፡ በዚሁ ፡ መለዋወጥ ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ መካሥ ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹ ። (፰) ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ካሣ ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በበኩሉ ፡ ለብቻው ፡ ያለውን ፡ የመለዋወጥ ፡ መብት ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ።

(፪) ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ የሚከፈለውም ፡ ካሣ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የበለጠ ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ባደረገው ፡ ሥራ ፡ በሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ ልክ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፩ ። ከደንበኞቹ ፡ ጋራ ፡ ስለሚደረገው ፡ ግንኙነት ፡ (፩) የዋጋ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።**

ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ ከደንበኞቹ ፡ ላይ ፡ የሚቀበለው ፡ ቀረጥ ፡ (ታክስ) ፡ ባንድ ፡ የዋጋ ፡ ማስታወቂያ ፡ መደብ ፡ (ታሪፍ) ፡ የብዛቱ ፡ ልክ ፡ ተወስኖ ፡ ተፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ከዚሁ ፡ ከተፈቀደለት ፡ ከፍተኛ ፡ ወሰን ፡ ሳያልፍ ፡ የዋጋ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ራሱ ፡ ዐውቆ ፡ ለማውጣት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፪ ። (፪) የዋጋ ፡ ማስታወቂያን ፡ (ታሪፍ) ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።**

ኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ የመደበው ፡ የዋጋ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ግዴታዎች ፡ የተለወጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያዲሱ ፡ የዋጋ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ግዴታዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላሉ ። ግን ፡ በባለኮንሴሲዮኑና ፡ በደንበኞቹ ፡ መካከል ፡ ባሉት ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ሊጸኑባቸው ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፫ ። (፫) ኮንሴሲዮኑ ፡ እንደ ፡ ሕዝባዊ ፡ ሥርዐት ፡ (ጸጥታ) ፡ ዐይነት ፡ ለመሆኑ ።**

ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ካንድ ፡ ደንበኛ ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ የግል ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በግዴታዎቹ ፡ ደብተር ፡ የተወሰኑትን ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ ለመለወጥ ፡ አይቻለውም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፬ ። ስለ ፡ ደንበኞቹ ፡ እኩልነት ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤትም ፡ ሆነ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ በደንበኞቹ ፡ መካከል ፡ የከፍተኛነትና ፡ የዝቅተኛነት ፡ ተግባር ፡ በመወሰን ፡ የነርሱን ፡ እኩልነት ፡ ለማጥፋት ፡ አይችሉም ።

(፪) የአገልግሎቱም ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ማስታወቂያ ፡ በደንበኞቹ ፡ ደረጃ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ እኒህም ፡ ልዩነቶች ፡ በሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ፊት ፡ ለደንበኞቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ከሆኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

(፫) የንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራዎች ፡ የሚተዳደሩት ፡ በግል ፡ መብት ፡ ደንቦች ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ የታወቀላቸውም ፡ ቢሆን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡ አደራረግን ፡ ማክበር ፡ አለባቸው ።

BACK



ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፭ ። (፭) የደንበኞችና ፡ የባለኮንሴሲዮኑ ፡ ግንኙነቶች ።

(፩) በዋጋ ፡ መደብ ፡ ወይም ፡ ግዴታዎች ፡ አፈጻጸም ፡ የሚደረጉት ፡ ስሕተቶች ፡ ሁሉ ፡ መቃናት ፡ አለባቸው ።

(፪) ደንበኛው ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ አላገባብ ፡ የተወሰደበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስመለስ፡ ክሱን ፡ አላገባብ ፡ ከተወሰደበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) እንዲሁም ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ የዋጋ ፡ ተጨማሪ፡ ለመቀበል ፡ አላገባብ፡ ከከፈለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፮ ። (፮) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የደንበኞች ፡ ወኪል ፡ ስላለመሆኑ ።

የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለኮንሴሲዮኑን ፡ የውሉን ፡ ግዴታዎች ፡ ጠንቅቆ ፡ ባለመጠበቁ ፡ ምክንያት ፡ በአገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ደንበኞች ፡ ላይ ፡ ላደረሰባቸው ፡ አንድ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፯ ። የኮንሴሲዮኑ ፡ ጊዜ፡ልክ ።

(፩) ኮንሴሲዮኑ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ልኩ ፡ በውሉ ፡ ይወሰናል ።

(፪) የኮንሴሲዮኑም ፡ ጊዜ ፡ ከስሳ ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፫) የውል ፡ ቃል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፰ ። ስለ ፡ ኮንሴሲዮኑ፡መታደስ ።

(፩) የኮንሴሲዮኑ ፡ ውል፡ መፈጸሚያው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሲቀረው ፡ ወይም ፡ ውሉ፡ እንደሚያዝዘው ፡ አድርጎ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በቀርና ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ለሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ ካላስጠነቀቀው ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ ዐውቆ ፡ የታደሰ ፡ ሆኖ ፡ ይቀጥላል ።

(፪) በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ ውሉ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ አስቀድሞ ፡ በወሰኑት ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ ታድሶ ፡ ይቀጥላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፱ ። የኮንሴሲዮኑን ፡ ሒሳብ ፡ ስለ፡ማጣራት ።

(፩) መሠረቱ ።

(፩) የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ማለቅ ፡ በባለኮንሴሲዮኑና ፡ በኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ሒሳቦች ፡ ተጣርተው ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ያደርጋል ።

(፪) የሒሳብ ፡ ማጣራቱም ፡ ተግባር ፡ የሚፈጸመው ፡ በግዴታዎች ፡ ደብተር ፡ በተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) የስምምነት ፡ ውል ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ የሒሳቡ ፡ ማጣራት ፡ ቀጥሎ ፡ በሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

BACK



ቁ ፡ ፫ሺ፪፻፴ ። (፪) የባለኮንሴሲዮኑ ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ስለ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ መቀጠል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ በነጻ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ተከፍሎባቸው ፡ ተመላሽ ፡ የሆኑትን ፡ የኮንሴሲዮኑን ፡ ሥራዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዳሉ ፡ በደኅና ፡ ሁኔታ ፡ ለኮንሴሲዮኑ ፡ ሰጭ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

ቁ ፡ ፫ሺ፪፻፴፩ ። (፫) ተመላሽ ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶች ።

(፩) ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፍልባቸው ፡ የኮንሴሲዮኑን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መልሶ ፡ ይረከባል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ በግዴታዎች ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፈልባቸው ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናሉ ፡ ተብሎ ፡ የተመለከቱትንም ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፈልባቸው ፡ ይረከባል ።

ቁ ፡ ፫ሺ፪፻፴፪። (፬) እንደ ፡ ገና ፡ ሥራ ፡ መቀጠያ ፡ የሆኑ፡ንብረቶች ።

(፩) ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ የቀሩትን ፡ ለኮንሴሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ንብረቶች ፡ ኪሣራ ፡ ከፍሎ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

(፪) ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ ለኮንሴሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ንብረቶች ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ ተገዳጅነት ፡ የሚኖረውም ፡ በግዴታዎች ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ ተገዳጅነቱ ፡ ተጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቁ ፡ ፫ሺ፪፻፴፫ ። (፭) ስለሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ ገንዘብ።

(፩) ቀደም ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ቍጥር፡የተጠቀሰው ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያከራክር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ልኩን ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የመረጧቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያለዚያም ፡ ዳኞች ፡ እንዲወስኑት ፡ ይደረጋል ።

(፪) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ወይም ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ ንብረቶቹ ፡ ባወጡት ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ እንዲሆን ፡ ከወሰኑ ፡ ኪሣራው ፡ በዚሁ ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ የመበላሸትና ፡ የእርጅና ፡ ተቀንሶለት ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

(፫) ለንብረቶቹ ፡ የወጡላቸው ፡ ዋጋዎች ፡ ልኩ ፡ ሊታወቅ ፡ ካልተቻለ ፡ ኪሣራው ፡ ለንብረቶቹ ፡ በመረከቢያው ፡ ጊዜ ፡ በሚሰጣቸው ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

ቁ ፡ ፫ሺ፪፻፴፬ ። (፮) ውሎች ።

(፩) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ለኮንሴሲዮኑ ፡ ጠቃሚነት ፡ ያላቸውንና ፡ በሥራም ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ለኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ በነዚሁ ፡ ውሎች ፡ የባለኮንሴሲዮኑን ፡ ቦታ ፡ የሚይዝ ፡ በመሆኑ ፡ ለመሻር ፡ የሚፈልገውን ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ በተረዳበት ፡

ወር ፡ ውስጥ ፡ ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ ወይም ፡ ለተዋዋዩ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ በውሉ ፡ ቀዋሚ ፡ የሆነ ፡ ግዴታ ፡ ካልኖረበት ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ ሽረት ፡ በተዋዋዩ ፡ ፊት ፡ አንዳችም ፡ ኀላፊነት ፡ ሊያገኘው ፡ አይችልም ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፴፰ ። (፯)ዋስትናዎች።

በኮንሴሲዮን ፡ ሰጪውና ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ሒሳቦች ፡ እንደ ፡ ተፈጸሙ ፡ ወዲያኑ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ያስያዘው ፡ መያዣ ፡ ተመላሽ ፡ ሆኖለት ፡ የዋሶቹም ፡ ዋስትናቸው ፡ እንዲወርድ ፡ ይደረግላቸዋል ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፴፱ ። ኮንሴሲዮኑን ፡ መልሶ፡ ስለ፡መግዛት ።

(፩) መሠረቱ ።

(፩) መልሶ ፡ መግዛት ፡ ማለት ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ ከመፈጸሚያው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ለማቆም ፡ ከባለኮንሴሲዮኑ ፡ ማናቸውም ፡ ጥፋት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ነው ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራን ፡ ለማቆም ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማደራጀት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል ።

(፫) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ግን ፡ ለሌላ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ ለመስጠት ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ ከባለኮንሴሲዮኑ ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ መብት ፡ የለውም ።

ቊ ፡ ፫ሺ፪፻፵ ። (፪) ውጤቶች ።

(፩) ኮንሴሲዮኑ ፡ መልሶ ፡ በተገዛ ፡ ጊዜ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ሒሳቦች ፡ መሠረት ፡ መጣራት ፡ አለበት ።

(፪) ባለኮንሴሲዮኑ ፡ መልሶ ፡ በመግዛት ፡ ለሚያገኘው ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ በተለይም ፡ ለኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ባስተላለፈባቸው ፡ በንዚያ ፡ ዋጋቸውን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አድርጎ ፡ ለመመለስ ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኝ ፡ በቀረባቸው ፡ ንብረቶች ፡ ረገድ ፡ በሚያገኘው ፡ ጉዳት ፡ መካስ ፡ ይገባዋል ።

(፫) ለባለኮንሴሲዮኑ ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ አስቦት ፡ የነበረውን ፡ ትርፍ ፡ በመገን ዘብ ፡ ይኸኑኑም ፡ መልሶ ፡ በመግዛቱ ፡ ምክንያት ፡ በማጣቱ ፡ ርትዕ ፡ የሆነ ፡ ካሣ ፡ ሊሰጠው ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፰ ። ስለ ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ መብት ፡ እጦት ፡ (፩) ስለ ፡ መበየን ።**

(፩) የባለኮንሴሲዮኑ ፡ መብት ፡ እጦት ፡ መበየን ፡ የሚቻለው ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ በተለይ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ጥፋት ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) የመብት ፡ እጦቱም ፡ መበየን ፡ የሚገባው ፡ የኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ የመበየኑ ፡ ሥልጣን ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ካልተፈቀደለት ፡ በቀር ፡ በዳኞች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፱ ፡ (፪) ውጤቶች ።**

(፩) የመብት ፡ ማጣት ፡ ውሉን ፡ በጭራሽ ፡ ያፈርሰዋል ።

(፪) የመብት ፡ ማጣት ፡ የደረሰበት ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ሳይቋረጥ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ በውድ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ራሱ ፡ መቻል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺ ። (፫) መብቱን ፡ ስላጣ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ መብቶች ።**

(፩) ኮንሴሲዮኑ ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ ኀላፊነት ፡ በሐራጅ ፡ ይሸጣል ።

(፪) መብቱን ፡ ያጣው ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ላይ ፡ ስላሉት ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ምትክ ፡ እንዲሆነው ፡ በሐረጅ ፡ የተወሰነውን ፡ ዋጋ ፡ ከአዲሱ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ ይቀበላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፩ ። ስለ ፡ ማስያዝ ። (፩) ግዴታዎች ።**

(፩) ኮንሴሲዮኑ ፡ እንዲያዝ ፡ መበየን ፡ የሚቻለው ፡ በባለኮንሲሲዮኑ ፡ ደካማነት ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ማነስ ፡ የአገልግሎት ፡ ሥራውን ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ መላውን ፡ ያቆመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ እንዲያዝ ፡ ለመበየን ፡ የሚቻለው ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ ማናቸውም ፡ ጥፋት ፡ ባይኖርም ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ያገልግሎት ፡ ሥራን ፡ ለማካሄድ ፡ የማይዘልቀው ፡ መስሎም ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፪ ። (፪) ውጤቶች ።**

(፩) እንዲያዝ ፡ መደረጉ ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ውል ፡ በነበሩት ፡ መብቶች ፡ ለጊዜው ፡ እንዳይሠራባቸው ፡ ባለኮንሴሲዮኑን ፡ ያግደዋል ።

(፪) እንዲያዝ ፡ የተደረገው ፡ ባለኮንሴሲዮኑን ፡ ስለ ፡ ደካማነት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጥፋቱ ፡ ለመቅጣት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያገልግሎቱ ፡ ሥራ ፡ በኮንሴሲዮን ፡ ሰጭ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ በመረጠው ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ አማካይነት ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ ኪሣራና ፡ ኀላፊነት ፡ እንዲካሄድ ፡ ይደረጋል ።

(፫) ኮንሴሲዮኑ ፡ እንዲያዝ ፡ የተደረገው ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማስያዙ ፡ ወጪ ፡ በኮንሴሲዮን ፡ ሰጪው ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፫ ። ስለ ፡ ዳኞች ፡ ተቈጣጣሪነት ።**

(፩) ዳኞች ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባንድ ፡ የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ በሆነው ፡ ላይ ፡ የፈጸመውን ፡ ማሲያዝ ፡ በሥራ ፡ መሪ፣ ውስጥ ፡ ማድረግን ፡ መብት ፡ ማስቀረትን ፡ መሰረዝን ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ግዴታን ፡ የማስፈጸሚያ ፡ ማስገደኛ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ማፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ (ቅጣት) ፡ በሚገባ ፡ የተደረገ ፡ መሆኑን ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ዳኞች ፡ ለመሻር ፡ ይችላሉ ።

(፪) ከዚህ ፡ በቀር ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በማይገባ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ አድርጎ ፡ በተዋዋዩ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ቢያደርስበት ፡ ለአደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍለው ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ላይ ፡ ዳኞች ፡ ሊፈርዱበት ፡ ይችላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የመንግሥት ፡ ሥራዎችን ፡ የመቋረጥ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፬ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ውል ፡ የሚባለው ፡ አንድ ፡ ተቋራጭ ፡ የሆነ ፡ ሰው፣ ካንድ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋራ ፡ በዋጋ ፡ ተስማምቶ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ የሆነ ፡ ሕንጻ ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ለማደስ ፡ የሚያደርገው ፡ ውል ፡ ነው ።

(፪) የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ውል ፡ መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ የአቅራቢነት ፡ ውል ፡ የሚባለው ፡ ውሉ ፡ ከሚሠራው ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተካፋይነት ፡ ሳይኖረው ፡ አቅራቢው ፡ ለሥራው ፡ አስፈላጊነት ፡ ያላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ የማቅረብ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፭ ። ስለ ፡ ጥበባዊ ፡ ሥራዎች ፡ ገበያዎች ።**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ለመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ውል ፡ የተሠሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ በሚደረጉትም ፡ የጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ።

(፪) የጥበባዊ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ በአሠራራቸውም ፡ ብዙ ፡ ዐይነትና ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱም ፡ የተለየ ፡ አስፈላጊነት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ የሆኑት ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ውልን ፡ ስለ ፡ ማዘጋጀት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፮ ። ውድድር ። (፩) መሠረቱ ።**

የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ፡ የሆኑትን ፤ ወይም ፡ የልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ተቋራጭ ፡ የሆኑትን ፡ ቤቶች ፡ ያንድ ፡ ሕንጻን ፡ ዐቅድ ፡ ለማሠራት ፡ ማወዳደር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፯ ። (፪) የግዴታዎች ፡ አወሳሰን ።**

(፩) የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ ዐቅዶቻቸውን ፡ የሚያቀርቡ በትን ፡ የጊዜ ፡ ልክ ፡ እነዚሁም ፡ ዐቅዶች ፡ በመልክና ፡ በውስጥ ፡ መሆን ፡ የሚገባቸውንና ፡ ሌላም ፡ ማናቸውንም ፡ የውድድር ፡ ግዴታዎችን ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ በማንና ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ እንደሚወሰኑ ፡ ወይም ፡ የደረጃ ፡ ተራ ፡ ማዕርግ ፡ እንደሚሰጣቸውም ፡ ይቈርጣል ።

(፫) መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በውድድሩ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ይመርጣል ፤ ለምርጫውም ፡ ምክንያት ፡ መስጠት ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፰ ። (፫) የውድድርን ፡ ደንብ ፡ የማክበር ፡ ግዴታ ።**

የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ራሱ ፡ ያወጣውን ፡ የውድድር ፡ ደንብ ፡ ለማክበር ፡ የጠበቀ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፱ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ።**

የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያገኘውን ፡ ተወዳዳሪ ፡ ለመምረጥ ፡ ቃል ፡ የገባ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መልካም ፡ ከመሰለው ፡ ጋራ ፡ ለመዋዋል ፡ ነጻ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ውል ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ አፈጻጸም ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ሥራዎች ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂነት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፶ ። የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ መብት ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሥራዎቹን ፡ አፈጻጸም ፡ ለመጠባበቅ ፡ (ለመቈጣጠር) ፡ ይችላል ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሥራው ፡ በሚፈቅደው ፡ ዐይነት ፡ እንዲፈጸም ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) በውሉ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ስምምነቶች ፡ ካልኖሩ ፡ በቀር ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ የተቈጣጣሪነትና ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይወስናሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፶፩ ። ስለ ፡ መጠባበቅ ፡ መብት ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወኪሎች ፡ በሥራ ፡ ቦታዎች ፡ ዘወትር ፡ ገብተው ፡ ከሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ቦታዎች ፡ መልካም ፡ ሥርዐትና ፡ ጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ያወጣቸውን ፡ ደንቦች ፡ በሚገባ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፫) ይህን ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፶፪ ። ስለ ፡ ሥራዎች ፡ የበላይ ፡ ተጠባባቂነት ።**

(፩) የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሥራ ፡ ትእዛዞች ፡ እየሰጠ ፡ የሥራዎቹን ፡ አካሄድ ፡ ይወስናል ። እኒሁም ፡ ሥራዎች ፡ በሚፈቅደው ፡ ዐይነት ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ያዛል ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በተሰጡት ፡ ፕላኖች ፡ ዐይነቶች ፡ የዋጋና ፡ ሥራ ፡ ማስታወቂያው ፡ መሠረት ፡ ጠንቅቆ ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፶፫ ። ስለ ፡ ሥራዎች ፡ አካሄድ ።**

(፩) በውል ፡ የተደረገው ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ ሳይነካ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላውን ፡ ጊዜና ፡ እያንዳንዱ ፡ የሥራው ፡ ክፍል ፡ የሚፈጸሙበትን ፡ ጊዜዎች ፡ ወይም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ በተለይ ፡ የሆኑትን ፡ ጊዜዎች ፡ ብቻ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) በውሉ ፤ ሥራዎቹ ፡ በሙሉ ፡ የሚፈጸሙበት ፡ ጠቅላላው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሥራዎች ፡ የሚጀመሩበትን ፡ ጊዜ ፡ ዘርዝሮ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሥራዎቹን ፡ አከታተልና ፡ አካሄድ ፡ በውሉ ፡ በተመለከተው ፡ ጠቅላላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፶፬ ። ስለ ፡ ጊዜዎች ፡ መነሻ ።**

(፩) የጊዜዎቹ ፡ መነሻ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ የሥራው ፡ ውል ፡ እንዲታወቅ ፡ የተደረገበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚጀምርበት ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሊያደርግ ፡ የሚገባውን ፡ አደራረግ ፡ መጠበቅ ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ ፡ ተግባሮች ፡ መፈጸም ፡ የተጀመሩበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፭ ። የተቋራጩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችና ፡ መሥሪያዎች ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለሥራው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሠራተኛና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውለውን ፡ መሥሪያ ፡ ብዛት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችን ፡ ይቈጣጠራል ። ሠራተኞች ፡ እንዲለወጡ ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ እንዲወጡ ፡ ያደርጋል ።

(፫) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውሉትን ፡ መሥሪያዎች ፡ ይቈጣጠራል ። እንዳይሠራባቸውም ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፮ ። ብልሹ፡ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ።**

የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውሉ ፡ መፈጸሚያ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ብልሹ ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በኪሣራው ፡ እንዲያፈርስና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲሠሩ ፡ ለማስደረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፯ ። በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በቃል ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ትእዛዞች ።**

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሥራ ፡ ትእዛዞችን ፡ መፈጸም ፡ ያለበት ፡ እነዚሁ ፡ ትእዛዞች ፡ በጽሑፍ ፡ ሆነው ፡ በተሰጡት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የቃል ፡ ትእዛዞች ፡ በሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ላይ ፡ ዋጋ ፡ የሚኖራቸው ፡ በሥራው ፡ ለውጥ ፡ ነገር ፡ ሳይገባ ፡ በሥራ ፡ ዝርዝር ፡ ማስታወቂየ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ብቻ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በውሉ ፡ ይህንኑ ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፰ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አቤቱታ ።**

ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ እንዲሠራ ፡ ታዞ ፡ ሳይፈርም ፡ በቀረው ፡ ወይም ፡ መብቱን ፡ ጠብቆ ፡ ለፈረመው ፡ ሥራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፵፱ ። የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የኪሣራ ፡ ማግኘት ፡ መብት ።**

(፩) በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ መጠን ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ደንበኛ ፡ የሆኑትን ፡ የተቈጣጣሪነት ፡ ችሎታዎችን ፡ ቢፈጽም ፡ ለተቋራጩ ፡ የኪሣራ ፡ መብት ፡ አይሰጠውም ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ጉዳት ፡ አድርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ከልክ ፡ በተላለፉ ፡ ነገሮች ፡ አጠያየቅ ፡ ጎድቶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ውሉን ፡ ለጊዜው ፡ እንዳይፈጽም ፡ አግዶት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አንድ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ከመብት ፡ መተላለፍ ፡ ባያደርግም ፡ አድራጎቱ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ሥራ ፡ ደንበኛ ፡ አፈጻጸም ፡ ከባድ ፡ ያደረገበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪሣራውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ከኀላፊነቱ ፡ ነጻ ፡ አያደርገውም ።

(፪) የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚቀረው ፡ በሥራ ፡ ማዘዣዎች ፡ ታዞ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ ባከናወናቸው ፡ ሥራዎች ፡ መጠን ፡ ኀላፊነት ፡ ይኖርበታል ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።
## ስለ ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፩ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ (፩)በቍርጥ ፡ ዋጋ ፡ ለማሠራት ፡ ስለ ፡ መዋዋል ።**

ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ በቍርጥ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፪ ። (፪) በዝርዝር ፡ ተራ ፡ ዋጋ ፡ ለማሠራት ፡ ስለ ፡ መዋዋል ።**

ውሉ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸመውን ፡ ሥራ ፡ ልክ ፡ ለይቶ ፡ ሳይወስን ፡ በሥራ ፡ መዋዋያው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሥራዎች ፡ ውሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑትን ፡ ዋጋዎች ፡ ብቻ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፫ ። (፫) በሥዕል ፡ ዝርዝር ፡ ማስረጃ ፤ ወይም ፡ በመለኪያ ፡ ልክ ፡ እየተላከ ፡ ለመክፈል ፡ ስለሚደረግ ፡ ውል ።**

የሚፈጸሙትን ፡ ሥራዎች ፡ ልክና ፡ ለየሥራውም ፡ ዐይነት ፡ የሚከፈለውን ፡ የዋጋ ፡ ዝርዝሮችን ፡ ውሉ ፡ ባንድነት ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፬ ። (፬) ወጪዎችን ፡ እየተቈጣጠሩ ፡ ለመክፈል ፡ ስለሚደረግ ፡ የሥራ ፡ ውል ።**

ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለሥራው ፡ ያወጣቸውን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ወጪዎቹን ፡ በሚገባ ፡ በመቈጣጠር ፡ እንዲከፈለውና ፡ ለቀረውም ፡ ወጪውና ፡ ለራሱም ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ ለማስገኘት ፡ በቍርጥ ፡ የሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲወሰንለት ፡ አድርጎ ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፭ ። (፭) በትእዛዝ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የሥራ ፡ ውል ።**

(፩) የጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ አስገዳጅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊነት ፡ ላላቸው ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ቴክኒካዊ ፡ መለዋወጥ ፡ ረገድ ፡ ውሉ ፡ ለጊዜው ፡ አንድ ፡ ዋጋ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለውሉ ፡ መፈጸሚያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ሩብ ፡ ጊዜው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ የመጨረሻውን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ አወሳሰን ፡ ትክክለኛ ፡ የሆኑትን ፡ ግዴታዎች ፡ የሚወስን ፡ ተጨማሪ ፡ ስምምነት ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

(፫) ተዋዋዮቹ ፡ ሳይስማሙ ፡ ቢቀሩ ፡ ግን ፡ የሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ለዳኞች ፡ የማመልከት ፡ መብት ፡ የተጠበቀለት ፡ ሆኖ ፡ የዋጋውን ፡ ልክ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ይወስናል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፮ ። (፮) ስለ ፡ ተጨማሪ፡ሥራዎች ።</u>

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ አስቀድሞ ፡ በሥራው ፡ ውል ፡ ያልተቋረጣቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ለመሥራት ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ቢታዘዝ ፡ መሥራት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

(፪) ተጨማሪ ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ዋጋ ፡ የሚወሰነው ፡ ተጨማሪ ፡ ስምምነት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።

(፫) ተዋዋዮቹ ፡ ሳይስማሙ ፡ ቢቀሩ ፡ ግን ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለዳኞች ፡ የማመልከት ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀለት ፡ ሆኖ ፡ ዋጋውን ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በተከታዩ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ይወስናል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፯ ። የዋጋው ፡ አከፋፈል ።</u>

የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባንድ ፡ የሥራውን ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታ ፡ በሚያመለክቱት ፡ የግዴታዎች ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ በተሰጠበት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በኀዋላ ፡ ወይም ፡ በየዓመቱ ፡ የሚከፈል ፡ ድርሻ ፡ አከፋፈል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ያከፋፈል ፡ ቃል ፡ እንዳያገባ ፡ ክልክል ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፰ ። ስለ፡መክፈያ ፡ ጊዜ ።</u>

(፩) የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ መመርመርና ፡ ማረጋገጥ ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ አፈጻጸም ፡ ቀዳሚ ፡ ጉዳይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ምርምርና ፡ ማረጋገጥ ፡ በሥራው ፡ ውል ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሥራውን ፡ መርምሮ ፡ የማረጋገጡ ፡ ሥራ ፡ ሳይደረግ ፡ ቢቀር ፡ ይህም ፡ የሆነበት ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ኀላፊነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ መክፈልን ፡ በማዘግየት ፡ የሚታሰበውን ፡ ወለድ ፡ እንዲያገኝ ፡ መብት ፡ ይሰጣል ።

<u>ቍ ፡ ፪ሺ፮፻፳፱ ። ከሒሳብ ፡ ላይ ፡ የሚታሰብ፡ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ የመቀበል ፡ መብት ።</u>

ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡—

(ሀ) የተቋረጣቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ለመሥራት ፡ በሥራው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አንጡራ ፡ ገንዘቡ ፡ የሆኑትን ፡ የመኪና ፡ መሥሪያ ፡ ወይም ፡ የፋብሪካ ፡ ቤትና ፡ ለሥራው ፡ የሚያገለግሉ ፡ ዕቃዎች ፡ አከማችቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



(ለ) የተቋረጣቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ለመሥራት ፡ በተለይ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ለቀጠራቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ቀለባቸውን ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሒሳቡ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍለው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፱፻፸ ። ከሒሳብ ፡ ስለሚታሰቡ ፡ ገንዘቦች ፡ አከፋፈል ።

(፩) በሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ጥያቄ ፡ ከሒሳብ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለሚሰጡ ፡ ገንዘቦች ፡ አከፋፈል ፡ መሠረት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በየወሩ ፡ መጨረሻ ፡ የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ ዝርዝርና ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩም ፡ ወጪ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ገንዘቦች ፡ ልክ ፡ የሚያመለክት ፡ ዝርዝር ፡ ማስታወቂያ ፡ ያዘጋጃል ።

(፪) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ የሚወስን ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ ከሒሳብ ፡ የሚታሰቡት ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፡ የሚሰጡት ፡ በየሦስት ፡ ወር ፡ ነው ።

(፫) ከሒሳብ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ለሥራው ፡ ከሚያገለግሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ከታወቁት ፡ ደመወዞች ፡ ዋጋ ፡ እኩል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፱፻፸፩ ። ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተዋዋለው ፡ ሥራ ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ የሚችለው ፡ ለዚሁ ፡ አስቀድሞ ፡ ለሚከፈለው፡ ገንዘብ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ግማሹን ፡ መልሶ ፡ ለመክፈል ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዋስትና ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) ይኸውም ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በሥራው ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ ወደፊት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከሚፈልጋቸው ፡ ቀሪ ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፱፻፸፪ ። መጨረሻ ፡ ሒሳብን ፡ በዝርዝር ፡ ስለ ፡ መተሳሰብ ።

(፩) የመጨረሻ ፡ ሒሳብን ፡ በዝርዝር ፡ መተሳሰብ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ዕዳዎች ፡ የሚወስንና ፡ ወገኖቹንም ፡ በማይሻር ፡ አኳኋን ፡ የሚያስገድድ ፡ የሒሳብ ፡ ውሳኔ ፡ ነው ።

(፪) ይህንም ፡ መጨረሻ ፡ ሒሳብ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

(፫) የመጨረሻ ፡ ሒሳብን ፡ በዝርዝር ፡ መተሳሰብ ፡ የሚቻለው ፡ በውሉ ፡ መሠረት፡ ሥራዎቹ፡ ተፈጽመው ፡ ከማለቃቸው ፡ በፊት ፡ የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፡ ካለፉና ፡ ከሥራዎቹም ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፱፻፸፫ ። የተስማሙበትን ፡ ሒሳቦች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ፡መመርመር ።

(፩) ወገኖቹ ፡ በስምምነት ፡ የተቀበሏቸውን ፡ ሒሳቦች ፡ የሒሳብ ፡ ስሕተት ፤ ዝንጋታ ፤ ሐሰት ፡(ሸፍጥ)፡ ወይም ፡ በአጠፌታ ፡ የመታሰብ ፡ ነገር ፡ ካልተገኘባቸው ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመመርመር ፡ አይቻልም ።

(፪) ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፤ የሒሳብ ፡ ዝንጋታ ምችን ፡ ስሕተቶችን ፡ ማስተካከል ፡ የሥራ ፡ ልክን ፡ ወይም ፡ የዋጋን ፡ ወይም፡ የውልን ፡ ክርክር ፡ የሚያስከትል ፡ አይደለም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሥራዎች ፡ ርክክብ ።

**ቍ፡፫ሺ፪፻፷፩ ። ለጊዜው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ርክክብ ። (፩) ለጊዜው ፡ የሆነ ፡ ርክክብ ፡ አኳኋን ።**

(፩) ለጊዜው ፡ የሆነ ፡ ርክክብ ፡ ማለት ፡ ሥራዎቹ ፡ ተሠርተው ፡ ካበቁ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የምርመራ ፡ ማረጋገጫ ፡ ነው ።

(፪) መብትን ፡ በመጠበቅ ፡ ተደርጎ ፡ ለጊዜው ፡ የሆነ ፡ ርክክብ ፡ በትክክል ፡ በእጅ ፡ አግብቶ ፡ መያዝን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፪ ። (፪) ስለ ፡ ውጤቶች ።**

(፩) ለጊዜው ፡ የሆነ ፡ ርክክብ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ለሚገለጹት ፡ የተበላሹ ፡ ሥራዎች ፡ የርክክቡ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ከአላፊነት ፡ ሊያድነው ፡ አይችልም ።

(፪) ለጊዜው ፡ የሆነ ፡ ርክክብ ፤ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለሥራው ፡ የታቀደውን ፡ ዐቅድ ፡ በመለወጥ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ቢኖር ፤ በዝምታ ፡ እንደ ፡ ተቀበሉት ፡ አድርጎ ፡ የሚያስቈጥር ፡ ነው ።

(፫) ለጊዜው ፡ የሆነ ፡ ርክክብ ፡ ለሥራው ፡ መድን ፡ ለመሆን ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መከፈቱን ፡ (መጀመሩን ) ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ። ለመድንነት ፡ የተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የመጨረሻው ፡ ርክክብ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፫ ። (፫) ስለ ፡ ጥፋትና ፡ ብልሽት ፡ የአደጋ ፡ ኪሣራን ፡ ስለ ፡ መቻል ።**

(፩) ከፍተኛ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ መፈራረስ ፡ ወይም ፡ ጉዳቶች ፡ ቢደርሱ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለጊዜው ፡ በሆነ ፡ ርክክብ ፡ ሥራዎቹን ፡ ካልተረከባቸው ፡ በቀር ፡ ኪሣራው ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ነው ።

(፪) የጠቅላላ ፡ ሁኔታዎችንና ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የሚፈጽማቸውን ፡ የሚያመለክቱ ፡ የግዴታዎች ፡ ደብተሮች ፡ ከዚህ ፡ ደንብ ፡ ሊነጠሉ ፡ ይችላሉ ።

(፫) እንደዚህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሚገባውን ፡ የኪሣራ ፡ ልክ ፡ የመጠየቂያውንም ፡ ጊዜና ፡ ሥርዐቱን ፡ ይወስኑታል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፮ ። የመድንነት ፡ ጊዜ ፡ (፩) የመድንነት ፡ ጊዜ ፡ አኳኋን ።

(፩) የመድንነት ፡ ጊዜ ፡ የተባለው ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራዎቹን ፡ በጊዜያዊ ፡ ከመረከቡ ፡ በፊት ፡ ሥራዎቹ ፡ በደኅና ፡ ስለ ፡ መሠራታቸው ፡ ለመመርመር ፡ የሚያስችለው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡—

(፪) የጊዜውም ፡ ልክ ፡ በውሉ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፯ ፡ (፪) ስለ፡ውጤቶች ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለሥራው ፡ መድንነት ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥራው ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለተበላሹ ፡ ሥራዎች ፡ መድን ፡ ነው ። ስለዚሁም ፡ ከአስተ ዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲያድሳቸው ፡ ትእዛዝ ፡ በደረሰው ፡ ጊዜ ፡ ማደስ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፰ ። ስለ፡መጨረሻ ፡ ርክክብ ። (፩) የሚፈጸምበት ፡ አኳኋን ።

(፩) የመጨረሻ ፡ ርክክብ ፡ ማለት ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ተቋ ራጩ ፡ ጠቅላላ ፡ ግዴታዎቹን ፡ በደኅና ፡ የፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳው ፡ በኋላ ፡ ሥራዎቹን ፡ በጭራሽ ፡ በእጁ ፡ የሚያደርግበት ፡ አፈጻጸም ፡ ነው ።

(፪) መጨረሻው ፡ ርክክብ ፡ የሚፈጸመው ፡ ወገኖቹ ፡ ባሉበትና ፡ በፕሮሴቬርባል ፡ ተጽፎ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፱ ። (፪) ስለ ፡ የአስተዳደር፡መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ አለመቅረብ ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራው ፡ ለመቀበል ፡ በሚቻል ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ታይቶ ፡ ዳኞች ፡ እን ዲያረጋግጡ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህም ፡ ሲሆን ፡ የመጨረሻው ፡ ርክክብ ፡ ስለ ፡ መድንነት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሚያ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መድንነት ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኞች ፡ በወሰኑት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፩ ። (፫) ስለ፡ ውጤቶች ።

(፩) የመጨራሻው ፡ ርክክብ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ መልካም ፡ አያያዝ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ያወርድለታል ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከዋጋው ፡ ቀሪ ፡ ሒሳቡ ፡ እንዲከፈለውና ፡ ለዋስትና ፡ መያዣ ፡ የተያዙበት ፡ ገንዘቦችም ፡ ይመለሱለት ፡ ዘንድ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፪ ። ስለ ፡ አሠራር ፡ ጒድለት፡መድንነት ።**

(፩) ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራዎቹን ፡ ከተረከባቸው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ወደፊት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አሠራር ፡ ጒድለት ፡ ለአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ኀላፊ ፡ መድን ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ መድንነቱ ፡ በሥራው ፡ የመጨረሻ ፡ ርክክብ ፡ ጊዜ ፡ ይታዩ ፡ ለነበሩት ፡ ጒድለቶች ፡ የተሰጠ ፡ አይደለም ።

(፫) መድንነት ፡ ያላቸው ፡ ጒድለቶች ፡ ሥራው ፡ ሊያገለግል ፡ የተሠራበትን ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱትን ፡ አገልግሎቶች ፡ ለመሥራት ፡ የሚያውኩ ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ አከሣሪ ፡ የሆኑ ፡ ወይም፡ጥቅም ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚያደርጉ ፡ ጒድለቶች ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።
## ውልን ፡ ስለ ፡ ማሻሻል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፫ ። ውሉን ፡ ለብቻ ፡ ስለ፡ማሻሻል ። (፩) የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መብት ።**

(፩) ለመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ውል ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ አስቀድሞ ፡ በግዴታዎች ፡ ደብተር ፡ የተመለከተውንና ፡ በመገበያያውም ፡ ውል ፡ የተወሰነውን ፡ ለማስለወጥ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ሊያዘው ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚህ ፡ የሚለወጡ ፡ ሥራዎች ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሥራዎች ፡ መልካም ፡ አቀማመጥ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፫) እነርሱም ፡ በውሉ ፡ የተስማሙበትን ፡ የገንዘብ ፡ ግዴታዎች ፡ ለመንካት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፬ ። (፪) ስለ፡አዳዲስ፡ሥራዎች ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመለከቱትን ፡ ሥራዎች ፡ በአንድ ፡ አዲስ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሠራው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ቢሆንም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በውሉ ፡ ከተመለከተው ፡ ሥራ ፡ ፍጹም ፡ ልዩ ፡ የሆነና ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የሌለውን ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ሊያዘው ፡ አይችልም ።

(፫) እንዲሁም ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ፍጹም ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ግዴታዎች ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩን ፡ ሊያዘው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፭ ። (፫) የሥራ፡ተቋራጩ፡መብቶች ።

(፩) ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የታዘዙት ፡ የሥራዎች ፡ መጨመር ፡ ወይም፡ መጕደል ፡ በውሉ ፡ ከታሰበው ፡ ሥራ ፡ ከስድስቱ ፡ እጅ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ነት ፡ ያስከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በቀር፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ጠቅላላ ፡ አቀናነስ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ በመለዋወጡ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳትና ፡ ሊያገኝ፡ ይገባው ፡ በነበረው ፡ ትርፍ ፡ ልክ ፡ የሆነ ፡ ኪሣራ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) የውሉን ፡ መለዋወጥ ፡ ያስከተለው ፡ ምክንያት ፡ ውሉን ፡ ባደረገው ፡ የአስ ተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት፡ መሆኑን ፡ ዳኞች ፡ የተረዱት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለቀረበት ፡ ሊያ ገኝ ፡ ለነበረው ፡ ትርፍ ፡ የሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ የተወሰነ ፡ እንዲሆን ፡ ሊቈ ርጡ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፮ ። ስለ፡ድንገተኛ፡እክሎች ። (፩) መሠረቱ።

(፩) ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ውሉን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ ውሉም ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ያልታሰበ ፡ እክል ፡ ያጋጠመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ እንዲሻሻልለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ከሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ውሉን ፡ የተዋዋለው ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ካልፈቀደ ፡ በዚሁ ፡ ባልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ እክል ፡ ከተ ፈጠረው ፡ ወጪ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ራሱ ፡ መቻል ፡ ይገባዋል ።

(፫) ይህም ፡ ጕዳይ ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ስላልታሰቡ ፡ ነገሮች ፡ በተወሰኑት ፡ ደን ቦች ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፯ ። (፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ምክር ፡ የመጠየቅ፡አስፈላጊነት ።

(፩) በውሉ ፡ ያልተመለከተውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ባጋጠመው ፡ እክል ፡ ምክን ያት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ተገዳጅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህነኑ ፡ለመሥራት ፡ የሚችለው ፡ ከመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ የተባለውን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም፡ ትእ ዛዝ ፡ እንዲተላለፍለት ፡ ካመለከተ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) የተባለውን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊነት ፡ ያለ ውና ፡ አስቸኳይነትም ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ባይኖርም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ መሥራት ፡ ይችላል።

(፫) እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሥራዎች ፡ አመራር ፡ ነገር ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ውል ፡ አለመፈጸም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፰።በሥራ ፡ መሪ ፡ ሥር ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ (፩)ግዴታዎች ፤ (ሁኔታዎች) ።**

(፩) በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ ሳይ ፈጽማቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራው ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ እን ዲሠራ ፡ ይደረጋል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ እንዲፈጽም ፡ ካስጠነቀቀው ፡ በኋላ፡ ባጭሩ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ካልሆነው ፡ በቀር ፡ ሥራውን ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ውስጥ፡ ለማድረግ ፡ አይቻለውም ።

(፫) ሥራው ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ሥር ፡ እንደሆን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ሲሆን ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ሥር ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለውም ፡ የሥራዎ ቹን ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፱ ። (፪) ስለ ፡ ውጤቶች ።**

(፩) ሥራው ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ሥር ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ለጊዜው ፡ ሥራ ፡ ከተቋረጠበት ፡ የተላቀቀ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

(፪) ሥራ ፡ አመራሩ ፡ የሚከናወነው ፡ በሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ወጪና ፡ ኪሣራ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺ ። (፫) ስለ ፡ ማቆም ።**

ሥራ፡ ተቋራጩ፡ ሥራዎቹ፡ በሥራ፡ መሪ፡ ሥር፡ መሆናቸው፡ ቀርቶ፡ በደኅና ፡ ከፍ ጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚያስችሉት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ እንዳለው ፡ ለማረ ጋገጥ ፡ ከቻለ ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ሥር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ እንዲለቀቅለት ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፩። እንደ ፡ ገና፡ ስለ ፡ ማጫረት ።**

(፩) የመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ሊሰረዝ ፡ መቻሉ ፡ በግልጽ ፡ በውሉ ፡ ታውቆ ለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በሐራጅ፡ ለማጫረት ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ በስምምነት ፡ ሥራውን ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ከሥራ ፡ ውጭ ፡ የተደረገው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አዲሱ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ክባድ ፡ የሆነውን ፡ ወጪ ፡ ራሱ ፡ መቻል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፪። ስለ ፡ ዳኞች ፡ ተቈጣጣሪነት ።**

(፩) የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የሚገባውን ፡ እንዲፈ ጽም ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያደረገውን ፡ የማስገደጃ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ማፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ (ቅጣት) ፡ ዳኞች ፡ ሊሽሩት ፡ አይችሉም ።

(፪) ዳኞች ፡ ማድረግ ፡ የሚችሉት ፡ ውሎቹን ፡ በመመርመር ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ (ቅጣት) ፡ አላገባብ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ኪሣራ ፡ የሚያገኝበት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ውልን ፡ ለዋስትና ፡ መያዣነት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፫ ። የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የተቋረጠበትን ፡ ውል ፡ በዋስትና ፡ ስለ፡ማስያዝ ።**

ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ያወቃቸው ፡ ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ውስጥ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጮች ፡ የሆኑት ፡ የመንግሥትን ፡ ሥራ ፡ የተቋረጡባቸውን ፡ ውሎች ፡ ለዕዳ ፡ መያዣ ፡ ሊሰጧቸው ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፬ ። የመንግሥትን ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ስለ፡ማስተላለፍ ።**

የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በደንብ ፡ መሠረት ፡ እንዲተላለፍ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋጋውን ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ ያለው ፡ አስተላላፊው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፭ ። ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ውስጥ ፡ ተቋራጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ መብቶች ።**

(፩) በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የታወቀ ፡ ከዋና ፡ ተቋራጭ ፡ ውስጥ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ ዋጋውን ፡ በቀጥታ ፡ ከመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ የፈቀደለት ፡ ሲሆንና ፡ በውሉም ፡ ሁለተኛው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሚሠራው ፡ የሥራ ፡ ዐይነትና ፡ የሥራውም ፡ ዋጋ ፡ በግልጽ ፡ የተመለከተ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ሁለተኛው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የፈጸማቸውን ፡ ሥራዎች ፡ የሚያስረዱ ፡ የዝርዝር ፡ ማስታወቂያዎቹን ፡ የውሉ ፡ ባለቤት፡ እንዲቀበላቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፫) ከሁለተኛው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ጋራ ፡ በቀጥታ ፡ ለመተሳሰብ ፡ የሚይቻል ፡ የሚሆነው ፡ ዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ውሉን ፡ በመያዣነት ፡ በሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፮ ። ከሒሳብ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብን፡መከልከል ።**

ሁለተኛ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የሆነው ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ ከሒሳብ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ማቅረብ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፯ ። ስለ ፡ ውል፡አፈጻጸም ።**

(፩) ዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ለማድረግ ፡ ምርጫና ፡ ቅድሚያ ፡ አለው ።

(፪) ዕቃ ፡ አቅራቢው ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን፡ ዕቃዎች ፡ ከሚፈቅዳቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፰ ። ስለ ፡ አደጋ ።**

(፩) ዕቃውን ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እስኪረከበው ፡ በመካከሉ ፡ ባንድ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ለሚደርስበት ፡ አደጋ ፡ ኪሣራውን ፡ የሚችለው ፡ ራሱ ፡ አቅራቢው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የቀረቡለትን ፡ ዕቃዎች ፡ ተቀብሎና ፡ በዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ቤቱ ፡ ካስቀመጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ለመረከብ ፡ ወይም ፡ ተመላሽ ፡ ለማድረግ ፡ አንድ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ እተሰጠበት፡ ቀን፡ ድረስ ፡ የዕቃ ፡ አደራ ፡ ከታኞች ፡ እንዳለባቸው ፡ ኀላፊነት ፡ ይኖርበታል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፱ ። ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ርክክብ ።**

የዕቃዎች ፡ ርክክብ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋንና ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻ ። የርክክቡን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የቀረቡለትን ፡ ዕቃዎች ፡ የተበላሹ ፡ ከሆኑ ፡ የርክክቡን ፡ ጊዜ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ላቅራቢው ፡ ስለ ፡ ተበላሹት ፡ ዕቃዎች ፡ የሚያሻሽልበትን ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ወስኖ ፡ ያስታውቀዋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፩ ። ዋጋ ፡ ስለሌላቸው ፡ ዕቃዎች ።**

የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በትክክል ፡ እንደ ፡ ተስማማበት ፡ ዐይነት ፡ ያልሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ የኒህም ፡ ጕድለታቸው ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ዕቃዎች ፡ ጥቅም ፡ የሚያጠፋና ፡ አቅራቢውም ፡ በተፈለገበት ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ጕድለት፡ ለማሻሻል ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ያልፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊቀበላቸው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፪ ። ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ምርምራ ፡ ኪሣራ ።**

(፩) በአቅራቢው ፡ ቤት ፡ የሚደረገው ፡ የዕቃዎች ፡ ምርመራ ፡ በአቅራቢው ፡ ኪሣራ ፡ ነው ። የቀረው ፡ ግን ፡ በአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ኪሣራ ፡ ነው ።

(፪) አቅራቢውም ፡ በምርመራዎቹ ፡ ጊዜ ፡ በቦታው ፡ ላይ ፡ የመገኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ስለ ፡ ምርመራው ፡ አፈጻጸም ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ለአቅራቢው ፡ እንዲነግረው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አሳቡንም ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ይፈቀድለታል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፫ ። ስለ ፡ አቅራቢው ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ያደረገው ፡ የመጠባበቅ ፡ ተግባር ፡ ያቅራቢውን ፡ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ አይቀንስለትም ።

BACK



(፪) እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ዕቃዎቹን ፡ በተረከበበት ፡ ጊዜ ። ተበላሽተው ፡ የተገኙትን ፡ ዕቃዎች ፡ ሳይቀበል ፡ ወይም ፡ በተወሰነው ፡ የመ ድንነት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተበላሹትን ፡ ለማሳደስ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ሊያስ ቀርበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፬ ። በሌለበት ፡ ማስፈጸም ።

(፩) በዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ ውል ፡ አቅራቢው ፡ በፍጥነት ፡ እንዲያቀርብ ፡ የታዘዘውን ፡ ሳያቀርብ ፡ በመቅረቱ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ ውል ፡ የተሰረዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሌለበት ፡ ለማስፈጸም ፡ ማስደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሳያቀርብ ፡ በቀረው ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢ ፡ ተተ ክቶ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ከሌላ ፡ አቅራቢ ፡ ዘንድ ፡ ገዝቶ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ፋብሪካ ፡ አሠርቶ ፡ ያቀርባል ።

(፫) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱም ፡ ውሉን ፡ ሳይፈጽም ፡ ከቀረው ፡ አቅራቢ ፡ ላይ ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፭ ። ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የዕቃ ፡ አቅራቢነት ፡ ውል ፡ ተዋዋይ ፡ የሆነው ፡ የሚገባውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ያደረገውን ፡ የማስገደጃ ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ማፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ ቅጣት ፡ ዳኞች ፡ ሊሽሩት ፡ አይችሉም ።

(፪) ዳኞች ፡ ማድረግ ፡ የሚችሉት ፡ ውሎቹን ፡ በመመርመር ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ (ቅጣት)፡ አላገባብ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አቅራቢው ፡ ኪሣራ ፡ የሚያገኝበት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፮ ። ለአስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አስቀድሞ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) ተዋዋዩ ፡ ይህን ፡ ተቀዳሚ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲከተል ፡ ውሉ ፡ በሚያስገ ደድው ፡ መጠን ፡ አስቀድሞ ፡ አቤቱታውን ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ይህን ፡ ግዴታ ፡ የሆነውን ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርበውን ፡ አቤቱታ ፡ ሳያ ስቀድም ፡ ለዳኛ ፡ የሚያቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ ተቀባይነት ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ።

(፫) ውሉ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ ጊዜ ፡ ወስኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተዋዋዩም ፡ ይኸንኑ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ አሳልፎ ፡ አቅርቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ጊዜው ፡ በመተላለፉ ፡ አቤቱታው ፡ የማይቀበሉት ፡ ይሆ ናል።ለዳኛም፡የሚቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ ተቀባይነትን ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ።

## አንቀጽ ፡ ኻያ ።

## ስለ ፡ ግልግልና ፡ ስለ ፡ ስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ ውል ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ግልግል ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### ስለ ፡ ግልግል ፡ በጠቅላላው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፯ ፡ ትርጓሜ ።**

ግልግል ፡ ማለት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፤ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡ ወይም ፡ ሰጥቶ ፡ የተጀመረውን ፡ ክርክር ፡ የሚያቆሙበት ፡ ወይም ፡ የሚፈጠረውን ፡ ክርክር ፡ አስቀድመው ፡ የሚያስቀሩበት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፰ ። (፪) የፎርሙ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ግልግል ፡ በመብት ፡ ምክንያት ፡ የሚያገኙዋቸውን ፡ ነገሮች ፡ የመፍጠር ፡ የመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ የማስቀረት ፡ ውጤት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፪) የነዚህንም ፡ ግንኙነቶች ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለመፍጠር ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ በሕግ ፡ የተደነገጉት ፡ የፎርም ፡ ግዴታዎች ፡ መጠበቅ ፡ አለ ባቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፱ ፡ አተረጓጐም ። (፩) መሠረቱ ።**

ስለ ፡ መብት ፡ መተው ፡ የሚደረጉ ፡ የግልግል ፡ ቃሎች ፡ በጠባብ ፡ አኳኋን ፡ መተርጐም ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲ ፡ (፪) አፈጻጸም ።**

(፩) ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ የክሱና ፡ የይገባኛል ፡ ባይነቱን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግልግሉ ፡ የሚያስቀራቸው ፡ ከግልግል ፡ ለመግባት ፡ ምክንያት ፡ የነበሩትን ፡ የክስ ፡ መብቶችና ፡ የይገባኛል ፡ ባይነቱን ፡ መብቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በራሱ ፡ በነበረው ፡ ባንድ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ መገላገሉ ፡ ከሌላ ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ መብት ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አዲስ ፡ የተገኘው ፡ መብት ፡ ካለፈው ፡ ግልግል ፡ ጋራ ፡ የተሳሰረ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፩ ። ግልግሉ ፡ የሚጸናበት ።**

ከባለጒዳዮቹ ፡ ባንዱ ፡ የተደረገ ፡ ግልግል ፡ ሌሎቹን ፡ ባለጒዳዮች ፡ አያስገድ ድም ፡ እነርሱም ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርጉት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፪ ። የመብት ፡ ስሕተት ።**

(፩) ግልግል ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ይግባኝ ፡ ሳይኖረው ፡ መጨረሻ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ተፈረደ ፡ ፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(፪) ግልግል ፡ ያደረጉበትን ፡ መብቶች ፡ በመመልከት ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንዱ ፡ በተደረገው ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ግልግል ፡ ሊነካ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፫ ። ዋነኛ ፡ ስሕተት ።**

(፩) ፍርስ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ።

(፩) ከስሕተት ፡ የተነሣ ፡ ግልግልን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚቻለው ፤ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ የገቡበት ፡ ሰነድ ፡ ራሱ ፡ ፍርስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ የተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ያንዱ ፡ ፈቃድ ፡ የተገኘው ፡ ሐሰተኛነቱ ፡ በታወቀ ፡ ባንድ ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግልግሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።

(፫) በውሉ ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ሰነዱ ፡ ፈራሽ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ ለመሆን ፡ መቻሉን ፡ አስበው ፡ የተገላገሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሁለቱም ፡ ጊዜ ፡ ግልግሉ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይቀራል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፬ ። (፪) ያልታወቀ ፡ ፍርድ ።**

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ሳያውቁት ፡ ከግልግሉ ፡ በፊት ፡ መጨረሻ ፡ በሆነ ፡ በፍርድ ፡ ጕዳዩ ፡ አልቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግልግሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።

(፪) በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንዱ ፡ ያልታወቀው ፡ ፍርድ ፡ በደንበኛው ፡ ይግባኝ ፡ መንገድ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ ግልግሉ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፭ ። (፫) ጠቅላላ ፡ ስምምነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ግልግል ።**

(፩) ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ አንድነት ፡ በሚኖሩዋቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በጠቅላላው ፡ የተገላገሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ላንዱ ፡ ግልግሉ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ያልታወቁ ፡ ሰነዶች ፡ በመጨረሻው ፡ የተገለጹ ፡ በመሆናቸው ፡ ምክንያት ፡ ግልግሉ ፡ ፍርስ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ውሉ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ የተባሉት ፡ ሰነዶች ፡ ከተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ባንዱ ፡ ወገን ፡ ሳይገለጹ ፡ ቀርተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግልግሉ ፡ ፍርስ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፮ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ግብ ።**

ግልግሉ ፡ ለሕግ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ተግባር ፡ ተቃራኒ ፡ ከሆነ ፤ ከአንድ ፡ ውል ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

BACK



**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፯ ። በሁለቱ ፡ ወገኖች፡ መስጠት ፡ የሚገባው ፡ መድን ።**

(፩) በግልግል ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሚያደርገው ፡ የመብት ፡ መተው ፤ ግልግሉ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ መግለጽ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የተተወውን ፡ መብት ፡ ለማስተላለፍ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የችሎታና ፡ የፎርም ፡ ግዴታዎች ፡ ሊጠበቁ ፡ ይገባቸዋል ።

(፫) ግልግሉን ፡ ያደረጉት ፡ ወገኖች ፡ ለራሳቸው ፡ ሥራና ፡ በግልጽ ፡ በውላቸው ፡ ለተጻፈው ፡ ጒዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለነዚሁ ፡ መብቶች ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ መድን ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ዕርቅ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፰ ። አስታራቂ ፡ ስለ ፡ መምረጥ ።**

(፩) ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እንዲያስታርቃቸውና ፡ ቢቻልም ፡ በመካከ ላቸው ፡ አንድ ፡ ግልግል ፡ እንዲያደርግላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጡት ፡ ይችላሉ ።

(፪) በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ጥያቄ ፡ አስታራቂው ፡ ባንድ ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሊመረጥ ፡ ይቻላል ።

(፫) አስታራቂ ፡ ሆኖ ፡ የተመረጠው ፡ ሰው ፡ ይኸንን ፡ ሥራ ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ላለመቀበል ፡ ነጻነት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፲፱ ። የተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ የሚሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ለአስታራቂው ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ።

(፪) የአስታራቂውን ፡ ሥራ ፡ የማይቻል ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ከሚያደርገው ፡ ሥራ ፡ መራቅ ፡( መወገድ) ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፳ ። የአስታራቂው ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) አስታራቂው ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔዎቹን ፡ ከመግለጹ ፡ በፊት ፡ ለተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ አስተያየታቸውን ፡ በሙሉ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

(፪) አስታራቂው ፡ የግልግል ፡ ቃሎችን ፡ ይጽፋል ፡ ወይም ፡ ለመገላገል ፡ ካልቻለ ፡ ዕርቅ ፡ ስላለመደረጉ ፡ አንድ ፡ ፕሮሲቬርባል ፡ ያዘጋጃል ።

(፫) እነዚህንም ፡ ጽሑፎች ፡ ለተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ይሰጣል ።

BACK



**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፳፩ ። የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) አስታራቂው ፡ በውል ፡ በተመለከተው ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ጊዜው ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተመረጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በስድ ስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ተግባሩን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ የመብቶቻቸውን ፡ የጥበቃ ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላሉ ።

(፫) አስታራቂው ፡ ዕርቅ ፡ ስላለመደረጉ ፡ አንድ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ካላዘጋጀ ፡ በቀር ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ክርክራቸው ፡ በዳኞች ፡ ፊት ፡ ለመቅረብ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፳፪ ። የአስታራቂው ፡ ሥልጣን ።**

(፩) የአስታራቂው ፡ ሥልጣን ፡ ጠባብ ፡ በመሆን ፡ መተርጐም ፡ አለበት ።

(፪) ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ አስታራቂው ፡ ያደረጋቸውን ፡ የግልግል ፡ ቃሎች ፡ ለማ ረጋገጥ ፡ በጽሑፍ ፡ በግልጽ ፡ ግዴታ ፡ ካልገቡ ፡ ሊገደዱ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፳፫ ። የአስታራቂው ፡ ወጪዎችና ፡ የድካም ፡ ዋጋዎች ።**

(፩) አስታራቂው ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ በሚገባ ፡ ሁኔታ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ወጪ ዎች ፡ ተመላሽ ፡ እንዲደረጉለት ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ግልጽ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አስታራቂው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፳፬ ። የግልግል ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

በአስታራቂው ፡ አማካይነት ፡ ግልግል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ለቀሪው ፡ አሠራር ፡ ሁሉ ፡ ባለፈው ፡ ክፍል ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይጸናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።
## በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ የመጨረስ ፡ ስምምነት ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፳፭ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የግልግል ፡ ስምምነት ፡ ማለት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ያንድ ፡ ክርክርን ፡ ውሳኔ ፡ ለአንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለሆነው ፡ ለአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ አቅር በው ፡ የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ውል ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ መሠረት ፡ ይኸንኑ ፡ ክር ክር ፡ ለመቍረጥ ፡ የሚያደርገው ፡ ውል ፡ ነው ።

(፪) የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ነገሩ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ሳይ ወስን ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ጕዳይ ፡ ብቻ ፡ እንዲያረጋግጥ ፡ ሊመረጥ ፡ ይችላል፣

**ቁ ፡ ፫ሺ፫፻፳፮ ። ችሎታና ፡ ፎርም ፡ (፩) መሠረቱ ።**

(፩) መብትን ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ ስለ ፡ መቻል ፡ የሚያስፈልገው ፡ ችሎታ ፡ በዚሁ ፡ መብት ፡ የተነሣውን ፡ ክርክር ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለመጨረስ ፡ ለሚደረገውም ፡ ውል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለመጨረስ ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ በሕግ ፡ ይህንኑ ፡ መብት ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ ፎርም ፡ ዐይነት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፫፻፳፯ ። (፪) የተጠበቀ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ቊጥር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንዲቀርብ ፡ በግልጽ ፡ ባዘዘው ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆኑም ።

(፪) ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ የመጨረሱን ፡ ስምምነት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ወይም ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሞግዚቱ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ።

(፫) በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ለመጨረስ ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ ማናቸውንም ፡ ፎርም ፡ መከተል ፡ የለበትም ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፫፻፳፰ ። የደረሰና ፡ ያልደረሰ ፡ ክርክር ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለመጨረስ ፡ ስለሚደረግ ፡ ስምምነት ።**

(፩) ለዘመድ ፡ ዳኛ ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ቀድሞውኑ ፡ የነበረ ፡ ክርክር ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ በአጋጣሚ ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ ለመነሣት ፡ የሚችለውን ፡ ክርክር ፡ ለዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ወደፊት ፡ የሚነሡትን ፡ ክርክሮች ፡ ለዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለማቅረብ ፡ ሲባል ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የሚሆነው ፡ ስምምነቱ ፡ በአንድ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በተለየ ፡ በመብት ፡ ገኙነት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፫፻፳፱ ። አተረጓጎም ።**

የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ሥልጣንን ፡ የሚመለከቱ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ፡ ቃሎች ፡ በጠባቡ ፡ መተርጐም ፡ አለባቸው ።

**ቁ ፡ ፫ሺ፫፻፴ ። የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ።**

(፩) የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ስምምነት ፡ የዚሁ ፡ ስምምነት ፡ አተረጓጎም ፡ ያነሣሣውን ፡ ችግር ፡ በሥልጣኑ ፡ እንዲወስን ፡ ለዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

(፪) በተለይም ፡ የራሱን ፡ ሥልጣን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ክርክሮች ፡ በሥልጣኑ ፡ እንዲወስን ፡ ለዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

(፫) የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ፡ ዋጋ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በሥልጣኑ ፡ ሊወስን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፬ ። የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስለ ፡ መምረጥ ። ፩/ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ስለ ፡ መመረጥ ።

(፩) የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ በዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ስምምነት ፡ በኋላ ፡ መመረጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ስምምነቱም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ የዘመድ ፡ ዳኞችን ፡ የሚኖሩ ፡ መሆናቸውን ፡ አስቀድሞ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፫) የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ስንት ፡ እንደሚሆኑ ፡ ወይም ፡ እንዴት ፡ እንደሚመረጡ ፡ ስምምነቱ ፡ ያላመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ይመርጣል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፭ ። (፪) በዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ በዳኞች ፡ ስለ ፡ መመረጥ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ብዛት ፡ በጥንድ ፡ የሚቈጠሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሥራው ፡ ከመግባት ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ይመርጣሉ ። ይኸውም ፡ የተመረጠው ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለዘመድ ፡ ዳኝነቱ ፡ ሰብሳቢ ፡ ይሆናል ።

(፪) ብዛታቸው ፡ በጥንድ ፡ የማይቈጠሩ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዘመድ ፡ ዳኞቹ ፡ ከመካከላቸው ፡ ለዘመድ ፡ ዳኝነቱ ፡ ሰብሳቢ ፡ የሚሆነውን ፡ ይመርጣሉ ።

(፫) በዘመድ ፡ ዳኞቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ እነዚህ ፡ ምርጫዎች ፡ በዳኞች ፡ የሚደረጉ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፮ ። (፫) የምርጫው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ ስምምነት ፡ የሚጠይቀው ፡ ወገን ፡ የሚያነሣውን ፡ ክርክር ፡ ገልጦ ፡ አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ይመርጣል ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ላንደኛው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ በዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ እንዲመርጥ ፡ ለተደረገው ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፯ ። (፬) የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) አንደኛው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ እንዲመርጥ ፡ የተጠየቀው ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልመረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዳኞች ፡ ይህን ፡ የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ ይመርጣሉ ።

BACK



(፪) ጊዜው ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰበት ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ለመለዋወጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፭ ። (፩) የተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ትክክለኛነት ።

የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ስምምነት ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ስለ ፡ መምረጥ ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ከተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ላንዱ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የበለጠ ፡ የመብት ፡ ሁኔታ ፡ የፈቀደለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፮ ። ስለ ፡ አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ መቅረት ፡ (፩) መተካት ።

(፩) አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ መመረጡን ፡ አልፈልግም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሞተ ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ ስንብት ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ተመረጠው ፡ ዐይነት ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ይመረጣል ።

(፪) የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ የተሻረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አዲሱን ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ዳኞች ፡ ይመርጣሉ ።

(፫) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውሳኔዎች ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ሊለዋወጡ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፯ ። (፪) የስምምነቱ ፡ ቀሪነት ።

(፩) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ስሙ ፡ ተጠርቶ ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ውስጥ ፡ የተመረጠ ፡ ሆኖና ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ ለማደረግ ፡ ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) ቢሆንም ፡ ወደፊት ፡ ለሚደርስ ፡ ክርክር ፡ ይኸውም ፡ ክርክር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ መሰናከል ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ስምምነት ፡ የሚረጋ ፡ ይሆናል ።

(፫) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውሳኔዎች ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ለመለዋወጥ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፰ ። ከተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ያንዱ ፡ መሞት ።

ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ካላገቡ ፡ በቀር ፡ ያንደኛው ፡ ወገን ፡ መሞት ፡ የመረጡትን ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ተግባር ፡ አያስቀረውም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፱ ። የገላጋዩ ፡ ተግባር ።

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ ለመመረጥ ፡ ይችላል ።

(፪) የዘመድ ፡ ዳኛው ፡ ዜግነት ፡ ለመመረጥ ፡ ከግምት ፡ አይገባም ።

BACK



(፫) ለዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ የተመረጠው ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ላለመቀበል ፡ ነጻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፺፫ ። የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ ስለ ፡ ማስወገድ ፡(፩)፡ምክንያቶች ።

(፩) አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ አካለ ፡ መጠን፡ያልደረሰ፡እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በደረሰበት ፡ በአንድ ፡ ቅጣት ፡ ምክንያትም ፡ ቢሆን ፤ ወይም ፡ ክፉና ፡ ደጉን ፡ መለየት ፡ ባለመቻሉ ፡ በበሽታ ፤ በመጥፋት ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ የተወሰነ ፡ ቀን ፡ ውስጥም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በሚያስደስት ፡ ሁኔታ ፡ ተግባሩን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ለማስወገድ ፡ ይቻላል ።

(፪) በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የተመረ ጠው ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ባለማዳላቱ ፡ ወይም ፡ በነጻነቱ ፡ ላይ ፡ ጥርጣሬን ፡ ለማ ስገባት ፡ የሚችል ፡ አንዳንድ ፡ አካባቢ ፡ ምክንያት ፡ ካለ ፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ።

(፫) በዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ ሰብሳቢ ፡ የሆነውም ፡ ሰው ፡ ይኸንኑ ፡ በመሰለ ፡ ምክንያት ፡ ሊወገድ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፺፬ ። (፪) ጥያቄን ፡ ስላለመቀበል ።

ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ራሱ ፡ የመረጠውን ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ከዚህ ፡ ምርጫ ፡ በኋላ ፡ ለደረሰው ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ምርጫ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ምክንያቱን ፡ ማወቁን ፡ ካላረጋገጠ ፡ ሊያስገድደው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፺፭ ። (፫) ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) የማስወገዱ ፡ ጥያቄ ፡ መቅረብ ፤ ለዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለሆኑት ፡ ውሳኔያቸውን ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊትና ፡ ጥያቄውንም ፡ የሚያቀርበው ፡ ወገን ፡ ምክንያቱን ፡ እንዳወቀው ፡ ወዲያውኑ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ የመወገዱ ፡ ጥያቄ ፡ ለሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ይቀርባል ፡ ብለው ፡ መስማማት ፡ ይችላሉ ።

(፫) የቀረበውን ፡ የመወገድ ፡ ጥያቄ ፡ አንቀበልም ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህኑ ፡ ውሳኔ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ በዳኞች ፡ ላይ ፡ ለመቃወም ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፫ ። የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ ስለ ፡ መሻር ።**

አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ሥራውን ፡ ተቀብሎ ፡ ከመፈጸም ፡ በማይገባ ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ፡ የተመረጠው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ስምምነት ፡ አላደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ዳኞች ፡ የዘመድ ፡ ዳኛውን ፡ ለመሻር ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፬ ። ባለመፈጸም ፡ ስለሚደረግ ፡ ቅጣት ።**

(፩) ለዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ ስምምነት ፡ ካደረጉት ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ በዚሁ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከተ ፡ ክርክር ፡ ወደ ፡ ዳኞች ፡ የሄደ ፤ ወይም ፡ የዘመድ ፡ ዳኝነን ፡ ለማደራጀት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ እንቢ ፡ ያለ ፤ ወይም ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ፡ የተያዘኩ ፡ አይደለሁም ፡ ባይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ መረጠው ፡ በዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማስገደድ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ለተነሣው ፡ ክርክር ፡ ስምምነቱ ፡ ቀሪ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመቍጠር ፡ ይችላል ።

(፪) አንዱ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት ፡ አንድ ፡ የአጠባበቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ዳኞችን ፡ ለመጠየቅ ፡ ያደረገው ፡ ተግባር ፡ የዚህን ፡ ስምምነት ፡ ቀሪነት ፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፭ ። ወደ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ መምራት ።**

(፩) የዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ የሚከተለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ተደንግጓል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ውሳኔ ፡ አፈጻጸምን ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ አቤቱታዎችን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ነገሮችም ፡ ይኸው ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፴፮ ። የዘመድ ፡ ዳኝነት ፡ አሠራር ።**

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ «የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ስምምነት» ፡ «ወይም» ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ስምምነት ፡ የተባሉት ፡ ቃሎች ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ለመጥቀስ ፡ የፈለጉትን ፡ የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ አሠራር ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ይጠቀልላሉ ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ፳፩ ።

## በቀድሞው ፡ ሕግና ፡ በዚህ ፡ በአሁኑ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ። የተሻሩት ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች ።**

(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ተተካ ፡ ተሽረዋል ።

(፪) በተለይም ።

ሀ) የካቲት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵ ዓ፡ ም ፡ የይርጋ ፡ ሕግ።

ለ) የ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ ም ፡ የብድር ፡ ሕግ ፤ ተሽረዋል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፰ ። በተሻሩት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ተገኝተው ፡ ለነበሩት ፡ መብቶች ።**

(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት፡ የነበሩትን ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ለማስገኘት ፡ አዲሱ ፡ ሕግ፡ የሚጠይቃቸው፡ አቋሞች ፡ ከዱሮው ፡ የተለዩ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፤ በተሻረው ፡ ሕግ፡ መሠረት ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩት ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

(፪) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጸናቱ ፡ በፊት ፡ በተሻረው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩት ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያስገኟቸውን ፡ ውጤቶች ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ አይለውጣቸውም ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፱ ። በከፊል ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ሕጋዊ ፡ ሁኔታን ፡ የሚያስገኙ ፡ አቋሞች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ለመገኘት ፡ የሚችሉ ፡ ወይም ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሲሆኑ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጸናቱ ፡ በፊት ፡ በከፊል ፡ ሳይፈጸም ፡ በቀረው ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሕጋዊ፡ ሁኔታ ፡ ለማስገኘት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ሊመራ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፶ ። የጊዜውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለማሻሻል ።**

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጸናቱ ፡ በፊት ፡ በሕግ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ ያለቀው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ የጊዜን ፡ ውሳኔ ፡ የሚያራዝም ፡ ሲሆን ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ፤ ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጸናቱ ፡ በፊት ፡ ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ መቀነስ ፡ ይገባዋል ።

(፫) ይህ ፡ ሕግ ፡ የጊዜን ፡ ውሳኔ ፡ የሚያሳጥር ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጸናቱ ፡ በፊት ፡ ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ እየተቈጠረ ፡ በድሮው ፡ ሕግ ፡ የተወሰነው ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፩ ። ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት።

(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ለሚወስነው ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ለሆነው ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ ለተገኙት ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ በጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ዘመኑ ፡ ያላለቀለት ፡ ውል ፡ በማታለል ፡ በኀይል፡ ዐይነት፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈርስ ፡ ካልተጠየቀ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ልዩ ፡ ድንጋጌ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፪ ። ችሎታን ፡ ስለ ፡ ማጥበብ ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ችሎታን ፡ የሚመለከቱ ፡ ስምምነቶች ፡ በቍ. ፪፻፳ ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፫ ። ችሎታ ፡ ስለሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጥበቃ ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ተመርጠው ፡ ሥራ ፡ የጀመሩ ፡ አሳዳሪዎች ፤ ሞግዚቶች ፤ ምትክ ፡ ሞግዚቶች ፡ ወይም ፡ ረዳት ፡ ሞግዚቶች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሕግ፡ መሠረት ፡ ለዚህ፡ ሥራ ፡ ለመመረጥ ፡ የማይችሉ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደ፡ ተመረጡ ፡ ተቈጥረው ፡ ሥራቸውን፡ መቀጠል ፡ ይችላሉ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተሰጣቸውንም ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፬ ። ስለ ፡ ውርስ ፡ (፩) ይህ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተጀመረ ፡ ውርስ ።

ይህ ፡ ሕግ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት፡ የተጀመረው፡ ውርስ ፡ የሚተላለፈውና ፡ ሒሳቡ፡ የሚጣራው ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፵፭ ። (፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ኑዛዜ ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ የሚጸናው ፡—

ሀ) በተሻረው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚጸና ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፤

ለ/ ይህ ፡ ሕግ ፡ በሚጠይቀው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፶፱ ። አትሞ ፡ የማውጣት ፡ ውል ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጸመውን ፡ አትሞ ፡ የማውጣት ፡ ውል ፡ ሕጉ ፡ ከጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላ ፡ ደራሲው ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷ ። የአገልግሎት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መቍጠር ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ሠራተኛው ፡ በአሠሪው ፡ ወይም ፡ በድርጅቱ ፡ ዘንድ ፡ የሠራበት ፡ ዘመን ፡ የሚቈጠርለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ከአሠሪው ፡ ወይም ፡ ከድርጅቱ ፡ ዘንድ ፡ የቈየበት ፡ የአገልግሎት ፡ ዘመን፡ ለዚህ ፡ ሕግ ፡ አፈጻጸም ፡ ይታሰብለታል ።

## አንቀጽ ፡ ፳፪ ።

## መሸጋገሪያ ፡ ሕግ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ሰወችንና ፡ ውርስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፩ ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ አሰጣጥ (፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተወለደ ፡ ሰው ።

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተወለደ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የቤተ ዘመድ ፡ ስም ፡ እንዲኖረው ፡ አይገደድም ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ እን ዲኖረው ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ የሚይዘው ፡ የአባቱን ፡ ስም ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ በሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ ዘመዶቹ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ትውልዶች ፡ በሕይወት ፡ ያሉ ፡ ሲሆን ፡ የቤተ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈልገው፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ አድርጎ፡ የሚይዘው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ በዕድሜ ፡ ታላቅ ፡ የሆነውን ፡ ወላጅ ፡ ስም ፡ ነው ።

(፫) አባቱ ፡ የተካደ ፡ ያልታወቀ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ የሚይ ዘው ፡ የእናቱን ፡ አባት ፡ ስም ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፪ ። (፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከጸና ፡ በኋላ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ።

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከጸና ፡ በኋላ ፡ የሚወለድ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ልጁ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ የሚይዘው ፡ የአባቱን ፡ ስም ፡ ነው ።

(፫) የተካደ ፡ ወይም ፡ አባቱ ፡ ያልታወቀ ፡ ልጅ ፡ ሲሆን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ የሚይዘው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ እንዳላት ፡ የእናቱን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ስም ፡ ወይም ፡ የእናቱን ፡ አባት ፡ ስም ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷ ። ውጤት ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁለት ፡ ቍጥሮች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለሚውሉበት፡ ጕዳይ ፡ በዚሁ፡ መሠረት ፡ የተሰጠ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ በቀጥታ ፡ መሥመር ፡ ለዚሁ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ተወላጅ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ መጠሪያ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፩ ። ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገቦች ።

(፩) በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበት ፡ ቀን ፡ ተወስኖ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታውጆ ፡ ካልወጣ ፡ በቀር፡ በቍ ፡ ፵፰ ፡ እስከ፡ ፶፭ ፤ በቍ ፤ ፶፯ ፡ እስከ ፡ ፷ ፤ በቍ ፡ ፷፪ ፡ እስከ ፷፯ ፤ በቍ ፤ ፷፱ ፡ እስከ ፡ ፩፻፴፩ ፡ እና ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ እስከ ፡ ፩፻፵፭ ፡ የተገለጹት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ፡ ባለው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፩) ፡ የተጠቀሱት፡ ቍጥሮች ፡ እስከሚጸኑበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ልደትን ፤ ጋብቻን ፤ ሞትን ፡ የሚገልጽ ፡ ማስረጃ ፡ የሚቀርበው ፡ በቍ ፤ ፩፻፵፯ ፡ እስከ ፡ ፩፻፶፫ ፡ በተመለከተው፡ መሠረት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፩፻፵፮ ፡ ን/ ቍ/ (፩) ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የመረጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ያዘጋጁትን ፡ የታወቀውን ፡ ጽሑፍ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩)፡ የተመለከተው ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍ/ ፩፻፳፩ ፡ እስከ፡ ፩፻፵፭ ፡ የተመለከቱት፡ ድንጋጌዎች፡ በተመሳሳይነት ፡ ለታወቁ ፡ ጽሑፎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፪ ። የማኅበሮች ፡ ጽ/ ቤት ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ለማኅበሮች፡ መመዝገቢያ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ እነዚሁ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ እስኪቋቋሙ ፡ ድረስ ፡ ሥራው ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይመራል ።

## ምዕራፍ ፱ ፡፡

## ስለ ፡ ንብረትና ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ማድረግን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፫ ፡፡ ስለ ፡ ማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡፡**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ዐሥር ፡ ስለ ፡ ማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ የተመለከተው ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበት ፡ ቀን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ድንጋጌ ፡ (ትእዛዝ) ፡ ተወስኖ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ እስኪታወጅ ፡ ድረስ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ፡፡

(፪) የአንቀጽ ፡ ዐሥር ፡ ድንጋጌ ፡ የሚጸናበት ፡ ቀን ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይሠራባቸዋል ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፬ ፡፡ ባለሀብትነትን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ፡፡**

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ባለሀብትነት ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፭ ፡፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ አገልግሎትና ፡ የባለሀብትነትን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መቀነስ ፡፡**

በመሬት ፡ ላይ ፡ ያገልግሎት ፡ መብትን ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ቃል ፡ መግባትን ፡ ወይም ፡ ለመግዛት ፡ የቀደምትነት ፡ መብትን ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ እንዳይያዝ ፤ እንዳይሸጥ ፤ እንዳይለወጥ ፤ የሚያደርጉት ፡ስምምነቶች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ እንዲሆኑ ፡ መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ ሥርዐቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልማዳዊያን ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፮ ፡፡ የሻጭ ፡ ግዴታዎች ፡፡**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገንን ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ እንዲችል ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ መመዝገብ ፡ የሚያስፈልገውንና ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ የሚቀንሰውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ሻጭ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ፡፡

(፪) በተሸጠው ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ የሚታየውን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የአገልግሎት ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ ሻጭ ፡ ለገዥ ፡ እንዲያስታውቅ ፡ አይገደድም ፡፡

(፫) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ያደረገው ፣ ስምምነት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ ፡ መመዝገብ ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ በዚህ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ሻጭ ፡ ማድረግ ፡ የሚገባውን ፡ እሱም፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ።

<u>ቍ ፡ ፫ሺ፫፻፷፯ ። ስለ ፡ ማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ።</u>

የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ እንዲሆን ፡ መፈጸም ፡ የሚገባቸው ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ ይሠራባቸዋል ።

BACK

## የግድፈት ፡ ማረሚያ ።

ገጽ ፡ ፪፻፶፫ ፡ ቍ ፡ ሺ፻፶፮ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፩) “ ከዚህ ፡ በታች ” ፡ የሚለው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፪፻፸ ፡ የክፍል ፡ ፫ ፡ አርእስት ፡ ስለ ፡ ውሃዎች ፡ ባለሀብት ፡ የሚለው ፡ ስለውሃዎች ፡ ባለሀብትነትና ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፪፻፺፱ ፡ ቍ ፡ ሺ፩፻፱ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፪) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የሚለው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ። ቀጥሎም ፡ “ አላገባብ ፡ ስለመበልጸግ ፡ “ የሚለው ፡ “ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ጥቅም ፡ ንብረትን ፡ ስለማስለቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ ስለዋጋ ፡ አወሳሰን ” . . . ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፫፻፵፰ ፡ ክፍል ፡ ፫ኛ ፡ “ የሚለው ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፬፻፷፱ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ ስለውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ “ ከሚለው ፡ ቀጥሎ ” ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ “እንዲሁም ፡ የቍ ፡ ፪ሺ፪፻፷፫ ፡ አርእስት ፡ “ መሠረቱ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፭፻፲ ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፯ ፡ የሚለው ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፰ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፭፻፹፱ ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ የሚለው ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፮፻፺፪ ፡ ፪ ፡ የመከታተል ፡ መብት ፡ የሚለው ፡ “ ክፍል ፡ ፪ ፡ ” የመከታተል ፡ መብት ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፯፻፷፪ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ . . . “ ስለሚያስከትሰው ፡ ” የሚለው ፡ ስለሚያስከትለው ’ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፫፻፺፱ ፡ ከቍጥር ፡ ሺ፰፻፺፭ ፡ በታች ፡ ምዕራፍ ፡ ፭ ። ስለብዙዎች ፡ ባለዕዳዎች ፡ ወይም ፡ ባለገንዘቦች ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጨምሯል ።

ገጽ ፡ ፫፻፷፭ ፡ የቍ ፡ ሺ፯፻፺፰ ፡ ን ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ የሺ፯፻፺፯ ፡ ን ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ሆኖ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፬፻፺ ፡ የቍ ፡ ፪ሺ፻፵፭ ፡ (፪) ጥቅስ ፡ ቍ ፡ ሺ፱፻፺፫ ።

ገጽ ፡ ፯፻፺፪ ፡ ከቍ ፡ ፫ሺ፹፩ ፡ በላይ ፡ “ ክፍል ፡ ” የተባለው ፡ “ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ” ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፬፻፺፩ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፪ ፡ የቍጥር ፡ ፪ሺ፫፻፵፫ ፡ ን፡ ቍ ፡ ፫ ፡ የቍጥር ፡ ፪ሺ፫፻፵፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ ሆኖ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፬፻፺፭ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፫፻፵፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ እና ፡ ፫ ፡ ይሠረዝና ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ይተካ ።

(፪) ከተሸጠው ፡ ነገር ፡ ገዢው ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ሳይረከብ ፡ በሚዘገይበት ፡ ጊዜ ፡ የጐደለውን ፡ ነገር ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ቢሰጠውም ፡ እንኳ ፡ የተሸጠውን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ስለ፡ መረከብ ፡ የተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ በጥብቅ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ገዢው፡ ውሉ ፡ በሙሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ገዢው፡ ውሉ፡በሙሉ፡ እንዲፈርስ፡ ለመጠየቅ፡ ወይም፡ ለማስታወቅ፡ መብቱ፡ የማይፈቅድለት፡ ሲሆን፡ ውሉ፡ በከፊል፡ እንዲፈርስ፡ ለመጠየቅ፡ ወይም፡ ለማስታወቅ፡ የሚገባው፡ ሆኖ፤ የተረከበውን፡ ነገር፡ የመጠኑን፡ ግምት፡ ዋጋውብቻ፡ ለመክፈል፡ ይችላል ።

BACK

## የማድፈት ፡ ማረሚያ ።

ገጽ ፡ ፻፹ ፡ ቍ ፡ ፳፻፷፬ ፡ (፫) ን ፡ ቍ ፡ (፩) በሁለተኛው ፡ መሥመር ፡ “ ታላቅ ፡ ወንድም ” ፡ ከሚለው ፡ ቀጥሎ ፡ “ ወይም ፡ ታላቅ ፡ እኅት ” ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ተሠርዞዋል ።

ገጽ ፡ ፻፹፩ ፡ ቍ ፡ ፳፻፹፫ ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ሊፈጽም ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቷል ። ( ቍ ፡ ፫፻፷፱ ) ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፵፭ ፡ ቍ ፡ ፯፻፲፱ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፪) “ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ” የተባለው ፡ “ ከዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፺፱ ፡ ቍ ፡ ፯፻፫ ፡ በ (ሀ) ፊደል ፡ ቍ ፡ ፻፺፰ ፡ የተባለው ፡ ቍ ፡ ፻፺፯ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፷፯ ፡ ቍ ፡ ፯፻፹፯ ፡ “ የተባለው ፡ ቍ ፡ ፯፻፺፩ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
በዚሁ ፡ ገጽ ፡ ቍ ፡ “ ፯፻፹፯ ” ፡ የተባለው ፡ ቍ ፡ “ ፯፻፹፯ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
» ቍ ፡ “፯፻፹፰” ፡ የተባለው ፡ ቍ ፡ “ ፯፻፹፯ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
» » ቍ ፡ “ ፯፻፹፱ ” ፡ የተባለው ፡ ቍ ፡ “ ፯፻፹፰ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
» » ቍ ፡ “ ፯፻፺ ” ፡ የተባለው ፡ ቍ ፡ “ ፯፻፹፱ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ “ ፯፻፺፩ ” ፡ የተባለው ፡ ቍ ፡ “ ፯፻፺ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፷፰ ፡ ቍ ፡ ፯፻፺፯ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፪) “ በጉዲፈቻው ፡ ልጅና ፡ በጉዲፈቻ ፡ አድራጊው ” ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ “ በጉዲፈቻ ፡ ተደራጊውም ” ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጨምሮ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፷፰ ፡ ቍ ፡ ፯፻፺፯ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፪) ከባልና ፡ ከሚስት ፡ አንዱ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ከሆነ ፡ ይበቃል ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፷፱ ፡ ቍ ፡ ፰፻፩ ፡ “ አንድ ፡ ሰው ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ አባትና ፡ እንደ ፡ እናት ፡ ተቈጥረው ፡ ለሁለቱ ፡ ብቻ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ” ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፸፩ ፡ ቍ ፡ ፰፻፲፯ ። ን ፡ ቍ ፡ (፫) “ ውዝፎችን ” ፡ የሚለው ፡ ገንዘቦችን ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፸፩ ፡ ቍ ፡ ፰፻፲፯ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፪) ቀለብ ፡ ተቀባዩ ፡ ከሚለው ፡ ቀጥሎ ፡ “ ውዝፉ ” የሚለው ፡ “ ገንዘቡ ” ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ። ቀጥሎም ፡ ማናቸውም ፡ “ ውዝፍ ” የሚለው ፡ ገንዘብ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፻፺፫ ፡ ቍ ፡ ፳፻፳፱ ፡ ተወስኗል ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ”የሚለው” ” የሚባለው ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ። ቀጥሎም ፡ « ለው » የሚል ፡ ቃል ፡ ተሠርዟል ።

ገጽ ፡ ፪፻፲፰ ፡ ከቍ ፡ ፲፼ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቍ ፡ “ ፲፼፩ ” ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ገጽ ፡ ፪፻፵፯ ፡ ቍ ፡ ፲፻፷፯ ፡ ን ፡ ቍ ፡ (፪) ተሠርዞዋል ።

BACK

ገጽ ፡ ፻፷፩ ፡ ቍ ፡ ፳፻፷፭ ፡ (፩) “ልጁ ፡ የተወለደው ፡ ጋብቻው ፡ ከፈረሰ ፡ ወይም ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ከ፪፻፲ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ቈይቶ. . . ” የሚለው ፡ ቀርቶ ፡ “ልጁ ፡ የተወለደው ፡ ጋብቻው ፡ ከተፈጸመ ፡ ወይም ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከተጀመረ ፡ አንሥቶ ፡ በ፪፻፲ ፡ ቀን ፡ ውስጥ . . . ” የሚል ፡ ቃል ፡ ተተክቶ ፡ የቀረው ፡ እንዳለ ፡ ይነበብ ።